ወወሀብኮሙ ፡ ትእምርተ ፡ ለእለ ፡ ይፈርሁከ ።

# መዝሙረ ፡ ዳዊት ።

ንባቡ ፡ ከነትርጓሜው ።

# መዝሙረ፡ዳዊት፡

ንባቡና ፡ ትርጓሜው ፡

ከጥንት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ እንደ ፡ መጣ ።




ተኀትመ ፡ በዐሥርቱ ፡ ወተስዐቱ ፡ ምእት ፡ ወኀምሳ ፡ ዓመት ፡
እምልደተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ዘአሕተሞ ፡ ዳግመ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ፓትርያርክ ፡ ዘኢትዮጵያ ።



የአዲስ አበባና የመላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን ፓትርያርክ።
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት።
የቅዱስ ሲኖዶሱ ሊቀ መንበር።

## መግቢያ ።

የዳዊት ፡ መቅድም ፡ ወይም ፡ ታሪክ ፡ ከጥንት ፡ በሊቃውንቱ ፡ የተዘ
ጋጀ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከሱ ፡ ሌላ ፡ መቅድም ፡ ለማዘጋጀት ፡ መድከም ፡ ደጊ
ሞተ ፡ ነገር ፡ ዘኢይትፈቅድ ፡ ውእቱ ፡ የሚያሰኝ ፡ ይሆናል ። ቢሆንም ፡
ባጭሩ ፡ ስለ ፡ ትርጓሜዎቹና ፡ ስለ ፡ መታተሙ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ለማስ
ታወስ ፡ እንሞክራለን ። እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዐት ፡
የመጻሕፍተ ፡ ብሉያትና ፡ የመጻሕፍተ ፡ ሐዲሳት ፡ ቍጥራቸው ፡ ፹፩ ፡
ሲሆን ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉያት ፡ ፵፮ ፡ ናቸው ። ካ፵፮ቱ ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉ
ያትም ፡ ፩ዱ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። መጻሕፍተ ፡
ብሉያትን ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ባንድ ፡ ትውልድ ፡ ሳይሆን ፡ በየጊዜው ፡ የተ
ነሡ ፡ ሊቃውንት ፡ በየዘመኑ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ከጽርእ ፡ (ግሪክ) ፡ ወደ ፡
ግእዝ ፡ ተርጕመውልናል ።

እንዲሁም፡ መጻሕፍተ፡ ሊቃውንትና፡ መጻሕፍተ፡ መነኮሳት፤ ዜና ፡ አበ
ው፡ ገድለ፡ ሰማዕታትን ፡ ስንክሳርን፡ የመሰሉትም፡ የጸሎትና ፡ የሥርዐት ፡
መጻሕፍት ፡ ከግሪክ ፡ ከግብጽም ፡ ከዐረብም ፡ በየጊዜው ፡ ተተርጕመዋል ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እነዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅን ፡ እነአትናቴዎስ ፡ ሐዋርያ
ዊውን ፡ የመሰሉ ፡ ታላላቆቹ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባቶች ፡ የተረጐሟ
ቸውን ፡ የብሉያትና ፡ የሐዲሳትን ፡ ትርጓሜ ፡ የሀገራችን ፡ ሊቃውንት ፡
እያቃኑ ፡ ለሰው ፡ እንደሚገባው ፡ እንደ ፡ ሀገሩ ፡ አነጋገርና ፡ ባህል ፡ እያ
ደረጉ ፡ በምስጢር ፡ በታሪክ ፡ በሐተታና ፡ በምሳሌ ፡ እየገላለጡ ፡ ተርጕ
መዋቸዋል ። ቢሆንም ፡ የመጻሕፍቱ ፡ ንባባቸውና ፡ ትርጓሜያቸው ፡
እጅግ ፡ ብዙ ፡ ስለ ፡ ነበረና ፡ እንደ ፡ ዛሬም ፡ ወረቀትና ፡ የጽሕፈት ፡ መ
ኪና ፡ ስላልነበረ ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ በቃል ፡ ማጥናትና ፡ በራስ ፡
መያዝ ፡ እንጂ ፡ በመጽሐፍ ፡ መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ ሊቅ ፡ የሚያሰኝ ፡ ስላ
ልነበረ ፡ የመጻሕፍቱን ፡ ትርጓሜ ፡ የሚያጠኑ ፡ እጅግ ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ፤
እነዚህም ፡ የምናኔ ፡ ያኸል ፡ ሕይወታቸውን ፡ ለዚሁ ፡ ብቻ ፡ አሳልፈው ፡
የሰጡ ፡ ነበሩ ። የሚገኙትም ፡ በታላላቁ ፡ ከተሞች ፡ አድባራትና ፡ ገዳማት ፡
ነበረ ።

የንባብ ፡ መጻሕፍትን ፡ እንኳ ፡ ማግኘት ፡ ችግር ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ፩ ፡
ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ትርጓሜ ፡ ማጥናት ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጓድ ፡ አበጅቶ ፡

ከባልንጀራው ፡ ጋራ ፡ አንዱን ፡ መጽሐፍ ፡ ለሁለት ፡ ለሦስትና ፡ ላራት ፡ እየተዋዋሱ ፡ ወይም ፡ ንባቡን ፡ በቃል ፡ እያጠኑ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መጽሐፍ ፡ ማግኘት ፡ ችግር ፡ ነበረ ።

ይህን ፡ በመሰለ ፡ ችግር ፡ አንድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ ትርጓሜ ፡ ለማግኘት ፡ ከሀገሩ ፡ ወጥቶ ፡ ከዘመዱ ፡ ተለይቶ ፡ በሞጣና ፡ በጐንደር ፡ እነዚህን ፡ በመሰሉ ፡ ከተሞች ፡ መላ ፡ ዘመኑን ፡ በትምህርት ፡ ይፈጅ ፡ ነበር ።

በ፲፱፻፲፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጽሕፈት ፡ መኪና ፡ መጥቶ ፡ መታተም ፡ እንደተጀመረ ፡ በመካከሉ ፡ የጠላት ፡ መግባት ፡ አቋረጠው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ በመታተምና ፡ በጥራዝ ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ መጻሕፍት ፡ በዘረፋው ፡ ምክንያት ፡ በየመንደሩና ፡ በየዱሩ ፡ ወድቀው ፡ ይታዩ ፡ ነበረ ። ይኸውም ፡ ሆኖ ፡ የተረፉት ፡ እስካሁን ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ ይታያሉ ።

ከጠላት ፡ መግባት ፡ በፊት ፡ የታተሙት ፡ መጻሕፍት
ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ።

፩ ፤ አራቱ ፡ ወንጌል ።
፪ ፤ ዐሥራ ፡ አራቱ ፡ ቅዳሴ ።
፫ ፤ የዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ድርሳንና ፡ ተግሣጽ ።
፬ ፤ ማር ፡ ይስሐቅ ።
፭ ፤ አረጋዊ ፡ መንፈሳዊና ፡ ፊልክስዩስ ።
፮ ፤ ሢራክና ፡ ሰሎሞን ።



፯ ፤ ሕዝቅኤል ።
፰ ፤ ውዳሴ ፡ ማርያም ።

እንዲሁም ፡ በነጠላ ፡ ትርጓሜ ፡ የታተሙት ።

አራቱ ፡ ወንጌላውያንና ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያት ፤ ዐሥራ ፡ አራቱ ፡ ቅዳሴ ፡ ናቸው ። «አሁንም ፡ በቅርቡ ፡ ግእዙና ፡ አማርኛው ፡ ተተካክሎ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ታትሟል» ።

መጻሕፍት ፡ ብሉያትና ፡ ሐዲሳት ፡ በፎቶ ፡ ተባዝተውና ፡ ተዘጋጅተው ፡ ስለነበረ ፡ በየአድባራቱና ፡ በየገዳማቱ ፡ እንዲሁም ፡ በየሰጪ ፡ እጅ ፡ ተገኝተው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጥቅም ፡ ሆነዋል ።

ይህም ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ መነኮሳት ፡ ካህናት ፡ መዘምራንም ፡ በዜማ ፡ በንባብ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ሳያቋርጡ ፡ እንዲጸልዩበት ፤ ምእመናንም ፡ ከሌላው ፡ ጸሎት ፡ ይልቅ ፡ እሱን ፡ መላልሰው ፡ እንዲጸልዩ ፡ የታዘዙ ፤ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ። መዝሙር ፡ ፻፫ ፡ ፩ ። በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ በዳዊት ፡ ቃል ፡ ይዘምራሉ ፡ ተብሎ ፡ የተነገረለት ፡ በመሆኑ ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ተፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ንባቡና ፡ ትርጓሜው ፡ እስካሁን ፡ ሳይታተም ፡ መዘግየቱ ፡ ተመልካቾቹን ፡ ሳያጸጽት ፡ አልቀረም ።

ይኸንንም ፡ መዝሙር ፡ በየጊዜው ፡ የተነሡ ፡ ሊቃውንት ፡ ለዜማ ፡ ለምስጋና ፡ ለጸሎት ፡ እንደሚሰማ ፡ እያደረጉ ፡ ክፍል ፡ ክፍል ፡ ሰጥተውት ፡ ይገኛል ።

ከሁሉም ፡ አስቀድሞ ፡ ሙሴ ፡ መጻሕፍተ ፡ ኦሪትን ፡ ካምስት ፡ እንደ ፡ ከፈለ ፤ እሊህም ፡ ዘፍጥረት ፡ ዘፀአት ፡ ዘሌዋውያን ፡ ዘኁልቍ ፡ ዘዳግም ፡ ናቸው ።

2014 04 17

መግቢያ ።

ትልቁ ፡ አትናቴዎስ ፡ ለመዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ትርጓሜ ፡ ምእዳን ፡ ትን ቢት ፡ ጸሎት ፡ እኩቴት ፡ ብሎ ፡ ጥቅሙን ፡ አስረድቶ ፡ ለይቶ ፡ አምስት ፡ ክፍል ፡ ሰጥቶ ፡ መቅድም ፡ አድርጎታል ።

የትርጓሜውም ፡ ዋና ፡ ጥቅሙ ፡ ምስጢሩን ፡ ሳያውቁ ፡ የሚጸልዩበት ፡ ምእመናን ፡ ምስጢሩን ፡ ዐውቀው ፡ እንዲጸልዩ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

የሚጠቅምና ፡ የሚያድን ፡ ሃይማኖት ፡ ቢሆንም ፡ ምስጢሩን ፡ ሳያ ውቅ ፡ የሚጸልየውን ፡ ሰው ፡ አበው ፡ በዐይነ ፡ ስውር ፡ መስለው ፡ «ዐይነ ፡ ስውር ፡ በሚሄድበት ፡ ጐዳና ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በበትሩ ፡ እየዳበሰ ፡ ሲሄድ ፡ በቅርብ ፡ የሚገኙ ፡ አራዊት ፡ በትር ፡ መያዙን ፡ እንጂ ፡ ዐይነ ፡ ስውርነ ቱን ፡ ባለማወቅ ፡ እንደሚሸሹና ፡ እንደሚርቁ ፤ አጋንንትና ፡ የክፉ ፡ ወ ገን ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቃሉ ፡ መናገሩን ፡ እንጂ ፡ የር ሱን ፡ አለማወቅ ፡ ስለማይፈልጉ ፡ ይርቃሉ ፡ ብለዋል» ፡ ሐዊ ።

ቢሆንም ፡ ምስጢሩን ፡ ሳያውቁ ፡ ከመጸለይና ፡ ከማንበብ ፡ ዐውቆ ፡ መጸለይና ፡ ማንበብ ፡ እንደሚበልጥ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ይኸ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ከጥንት ፡ አባቶች ፡ እንደ ፡ ተረ ጐሙትና ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ እንደ ፡ መጣው ፡ ንባቡና ፡ ትርጓሜው ፡ ተጽፎና ፡ ታርሞ ፡ በብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ፈቃድ ፡ በ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ታተመ ።

እንደገና ፡ በብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፈቃድ ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ በ፲፱፻፸፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ታተመ ።

ታሪክ ።

ፍካሬ ፡ ዘጻድቃን ፡ ወዘኃጥኣን ፡

ዳዊት ፡ ማለት ፡ ልበ ፡ አምላክ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ወእሠይም ፡ ኖሎተ ፡ ዘከመ ፡ ልብየ ፡ ወየኃሥሥ ፡ ኖሎተ ፡ ዘከመ ፡ ልቡ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ ዳዊት ፡ ማለት ፡ ኅሩይ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ወአል ዓልኩ ፡ ኅሩይየ ፡ እምሕዝብየ ፡ ብሎ ፡ እንዲያመጣው ፡ መዝ ፡ ፹፰-፲፱ ። አንድ ም ፡ ዳዊት ፡ ማለት ፡ መስተሳልም ፡ መስ ተፋቅር ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ እሥ ራ ፡ አንደኛ ፡ አርእስት ፡ ተብሎ ፡ አይ ቈጠርም ፤ ከልጁ ፡ ከሰሎሞን ፡ ገብቶ ፡ ይቈጠራል ። መዝ ፡ ፸፩-፩ ። ጥንተ ፡ ነገ ሩስ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ግብፃው ያንን ፡ በዘጠኝ ፡ መቅሠፍት ፡ በአሥ ረኛ ፡ ሞተ ፡ በኵር ፡ በአሥራ ፡ አን ደኛ ፡ ሥጥመት ፡ አጥፍቶ ፡ ዘፀ ፡ ፲፱- ፳፱-፲፱-፳፰ ። እስራኤልን ፡ ባሕር ፡ ሣ ህል ፡ ታድጎ ፡ መና ፡ ከደመና ፡ አው ርዶ ፡ ወሃ ፡ ከጭንጫ ፡ አፍልቆ ፡ ፵ ፡ ዘመን ፡ በገዳም ፡ ሲመግባቸው ፡ ኖረ ፡ ዘፀ ፡ ፲፯-፱-፭-፲፯-፯ ። ሙሴን ፡ መስፍን ፡ አሮንን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አድርጎ ፡ አሥንሥቶ ፡ መስፍን ፡ ሲ ሞት ፡ መስፍን ፤ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሲሞ ት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ፡ እየተካ ፡ በሙ ሴ ፡ እግር ፡ ኢያሱን ፡ በአሮን ፡ እግር ፡ አልአዛርን ፡ ተክቶ ፡ ፵ ፡ ዘመን ፡ ሲመግባቸው ፡ ኖረ ። ዘኍ ፡ ፳-፳፫-፳፱- ፳፯-፲፭-፳፫ ። ይህ ፡ ሲያያዝ ፡ ከኤሊ ፡ ደረሰ ። ኤሊም ፡ ከህነት ፡ ከምስፍ ና ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡ ፵ ፡ ዘ መን ፡ መግቢቸው ፡ አረጀ ። አፍኒ ፡ ፊንሐስ ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ ምሉና ፡ ዱግ ፡ አድርጎ ፡ ሹ ሟቸዋል ፤ አይነታና ፡ ተወራጅ ፡ ማለ ት ፡ ነው ። ወደቂቀ ፡ ኤሊስ ፡ እኩያን ፡ እሙንቱ ፡ ወኢያሠነዩ ፡ ማኅቶቶሙ ፡ ለአቤቶ ፡ እንዲል ፤ መላልሰው ፡ በ ደሉ ። ፩ሳሙ ፡ ፪-፲፪ ። በቀዳማይ ፡ ሰ ዓት ፡ ሴሊት ፡ በርቶ ፡ በቀዳማይ ፡ ሰዓት ፡ መዓልት ፡ የሚጠፋ ፡ ፋና ፡ ነበር ። ሙሴ ፡ አሮን ፡ የሠሩት ፡ ሥር ዓት ፡ ነው ። ዘፀ ፡ ፳፭-፴፯ ። ልማድ ፡ እንዳይሆንባቸው ፡ ከባዶ ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ ውስጥ ፡ ሲበራ ፡ ቢያድር ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ አስቀርተ ውታል ፤ አንድ ፡ በደል ።

ሁለተኛ ፡ የእስራኤል ፡ ሥርዓት ፡ ወያመጽእ ፡ መሆስስ ፡ ብርት ፡ ዘ፫ ፡ አስናኒሁ ፡ ወይወድዮ ፡ ውስተ ፡ ዓቢ ይ ፡ ጽሕርት ፡ ወዘይንእስ ፡ እምኔሁ ፡ ይላል ። ፩ሳሙ ፡ ፪-፲፫-፲፯ ። ሦስት ፡ ልሳ ን ፡ ያለው ፡ ጕጠት ፡ አምጥቶ ፡ ላም ፡ የተሠዋ ፡ እንደሆን ፡ ከላመ ፡ ፈጅ ። በግ ፡ የተሠዋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከበገ ፡ ፈጅ ፡ ይጥለዋል ። መጀመሪያ ፡ የወ ጣውን ፡ ለሊቀ ፡ ከህናቱ ፡ ይሰጠ ዋል ። የቀረውን ፡ ሌዋውያኑ ፡ ይ

2014 04 17

መገቡ ፡ ነበር ። አንድም ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ብልት ፡ ሥጋ ፡ እየወጣለት ፡ ይመገብ ፡ ነበር ። ሥርዓታቸው ፡ ይህ ፡ ነው ። ዘሌ ፡ ፯-፩-፲፰ ። እኒህ ፡ ግን ፡ ወይመጽእ ፡ ካህን ፡ ወልደ ፡ ካህን ፡ ኀበ ፡ ያበስሉ ፡ ሥጋ ፡ ወይብሎ ፡ ለበዓለ ፡ መሥዋዕት ፡ ሀበኒ ፡ ሥጋ ፡ ዘእጠብሶ ፡ ለካህን ፡ ይላል ። ለሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ጠብሼ ፡ የምሰጠው ፡ ሥጋ ፡ ስጠኝ ፡ ይለዋል ። ያም ፡ ቅድመ ፡ ይጢስ ፡ ሥብሑ ፡ ዘበሕጉ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ እንደ ፡ ወጉ ፡ ደሙ ፡ ይፍሰስ ፡ አጥንቱ ፡ ይከስከስ ፡ ሥቡ ፡ ይጢስ ፡ ወእምዝ ፡ ትነሥእ ፡ ዘፈተውት ፡ ነፍስከ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የወደድከውን ፡ ትወስዳለህ ፡ ይለዋል ። «ሐተታ» ፡ እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ የሚሰጠው ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ለማስቆም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያም ፡ ብትሰጠኝ ፡ ስጠኝ ፡ አይሆንም ፡ ካልክ ። እነሥእከ ፡ ወእሐይደከ ። የግድ ፡ እወስደዋለሁ ፡ ይለዋል ። ያም ፡ አይሆንም ፡ ካልክ ፡ ምን ፡ እላለሁ ፡ ብሎ ፡ የወደደውን ፡ ታላቅ ፡ ታናሽ ፡ ሥጋ ፡ ይሰጠዋል ፡ ሁለት ፡ በደል ፡ ፩ሳሙ ፡ ፪-፲፫-፲፯ ።

፫ኛ ፡ ወሰምዓ ፡ ኤሊ ፡ ከመ ፡ ይሰክቡ ፡ ደቂቁ ፡ ምስለ ፡ አንስትያ ፡ እስራኤል ፡ እለ ፡ ይቀውማ ፡ ውስተ ፡ ኆኅተ ፡ ደብተራ ፡ ዘስምዕ ፡ ይላል ። የእስራኤል ፡ ሴቶች ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ነስተን ፡ እንመጣለን ፡ ብለው ፡ ሲሄዱ ፡ እየተጫወቱ ፡ የሚሰዷቸው ፡ ሆነዋል ። እስከዚህስ ፡ አይደፍሩም ፡ ብሎ ፡ መቃጠሪያ ፡ አድርገውታል ። ሴቶችም ፡ ይህንማ ፡ ከቤታችንስ ፡ መቼ ፡ አጣን ፡ ብለው ፡ ቀርተዋል ። ወንዶቹም ፡ ሚስቶቻችንን ፡ ልንድርን ፡ ብለው ፡ አስቀርተዋቸዋል ፤ ሦስት ፡ በደል ። ፩ሳሙ ፡ ፪ ፡ ፳፪ ።

ይህን ፡ ሰምቶ ፡ እንቢክሙ ፡ ደቂቅየ ፡ እንቢክሙ ፡ ደቂቅየ ። አኮ ፡ ሠናይ ፡ ዘእሰምዕ ፡ ብክሙ ፡ ይላል ። ይህ ፡ በናንተ ፡ የምሰማው ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ አይደለም ፤ እንቢላችሁ ፡ ልጆቼ ፡ እንቢላችሁ ፡ አላቸው ። በሀገራቸው ፡ ቋንቋ ፡ የተመለሰ ፡ አማርኛ ። በሀገራችን ፡ አይሆንም ፡ አይሆንም ፡ ማለት ፡ ነው ። ለእመ ፡ አበሰ ፡ ሰብእ ፡ ላዕለ ፡ ቢፁ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጼልዩ ፡ ሎቱ ። ወለእመ ፡ አበሰ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምኀበ ፡ መኑ ፡ ይጼልዩ ፡ ሎቱ ። ሰው ፡ ከሰው ፡ ቢጣላ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያስታርቁታል ። ከእግዚአብሔር ፡ ቢጣላ ፡ በማን ፡ ያስታርቁታል ። ወሀ ፡ ቢያንቅ ፡ በምን ፡ ይውጡ ። ምላጭ ፡ ቢያብጥ ፡ በምን ፡ ይበጡ ፡ እንዲሉ ፡ ሁሉ ፡ ብሎ ፤ ከሹመታቸው ፡ ልሻራቸው ፡ ከመዓርጋቸው ፡ ላዋርዳቸው ፡ ሳይል ፡ ዝም ፡ አለ ። ፩ሳሙ ፡ ፪ ፡ ፳፫ ፡ ፳፭ ።

ያልታወቀ ፡ ነቢይ ፡ ነቢየ ፡ ሬማት ፡ ይለዋል ፡ መልአኩም ፡ ነው ፡ ይላሉ ።



መጥቶ ፡ ለምንት ፡ ነጸርከ ፡ ላዕለ ፡ ዕጣንየ ፡ ወመሥዋዕትየ ፡ በዓይን ፡ ሕዕፅት ፡ ወአፍቀርከ ፡ ደቂቀከ ፡ እምኔየ ፡ ሀየንተ ፡ በረከት ፡ ቀዳሚ ፡ መሥዋዕቶሙ ፡ ለ፳ኤል ። ሥራት ፡ ሲፈርስ ፡ ለምን ፡ ዝም ፡ አልክ ፤ ከኔስ ፡ ይልቅ ፡ ልጆችህን ፡ ለምን ፡ ወደድህ ። ሀየንተ ፡ በረከት ። አሥራቱን ፡ በኵራቱን ፡ ሰጥቼ ፡ ስላከበርኩህ ፡ ፈንታ ። ቀዳሚ ፡ መሥዋዕት ፡ ማለቱ ፡ እስራኤል ፡ አሥራቱን ፡ በኵራቱን ፡ ሳያወጡ ፡ መሥዋዕት ፡ አይሠዉም ፡ ነበረና ። ይህ ፡ ይቀርብኛል ፡ ስለማለት ፡ ፈንታ ፡ (ለሱ ፡ ሰጥተህ) ። አንድም ፡ ይህ ፡ ይቀርብቸዋል ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ ፈንታ ፡ (ለልጆቹ ፡ ሰጥተህ) ፡ ፩ሳሙ ፡ ፪ ፡ ፳፱ ። ሳሙኤል ፡ የሚባል ፡ የብዕዓት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ። ጦር ፡ ጠፍቶለታልን ፡ ቢሉ ፡ አወን ፡ ጠፍቶለታል ። አንድም ፡ እየገባ ፡ እየወጣ ። አንድም ፡ መነኰሴ ፡ ተማሪ ፡ ከቅዕረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጎጆ ፡ ሠርቶ ፡ ከመቃብር ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ እንዲኖር ፡ እንዲሁ ፡ ሆኖ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ፩ሳሙ ፡ ፪ ፡ ፳፮ ። ሴሊትን ፡ ነው ፡ መዓልት ፡ ቢሉ ፡ የመዓልት ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ተሠራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌሊት ፡ ነው ። በዚያ ፡ ሌሊት ፡ ሳሙኤል ፡ ሳሙኤል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ እርሱም ፡ ነየ ፡ ገብርከ ፡ እስመ ፡ ፀዋዕከኒ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ኤሊ ፡ ቀረበ ። ኤሊም ፡ ሑር ፡ ስከብ ፡ ኢፀዋዕኩከ ፡ አለው ። ፩ሳሙ ፡ ፫ ፡ ፩ ። ፪ኛ ፡ ሳሙኤል ፡ ሳሙኤል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ እርሱም ፡ ነየ ፡ ገብርከ ፡ እስመ ፡ ፀዋዕከኒ ፡ ብሎ ፡ ቀረበ ። ሑር ፡ ስክብ ፡ ኢፀዋዕኩከ ፡ አለው ። ፩ሳሙ ፡ ፯-፯ ።

በ፫ኛው ፡ ኤሊ ፡ ጠረጠረ ። ይህ ፡ ብላቴና ፡ ራዕይ ፡ ባይለምድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የተገለፀለት ፡ ነገር ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ስለተኛ ፡ የጠራህ ፡ እንደሆነ ፡ ተነሥተህ ፡ ታጥቀህ ፡ እጅ ፡ ነስተህ ፡ ቆመህ ፡ በል ፡ እግዚእየ ፡ እስመ ፡ እነ ፡ ገብርከ ፡ እሰምዓከ ፡ በል ። የነገረህንም ፡ እንድትነግረኝ ፡ አለው ። ወከነ ፡ ቃል ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ። ስለተኛ ፡ ሳሙኤል ፡ ሳሙኤል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ እርሱም ፡ ተነሥቶ ፡ ታጥቆ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ቆሞ ፡ በል ፡ እግዚእየ ፡ እስመ ፡ እነ ፡ ገብርከ ፡ እሰምዓከ ፡ አለ ። ፩ሳሙ ፡ ፲ ። እእኀዝኒ ፡ ወእሬጽም ፡ አለው ። ፩ሳሙ ፡ ፫ - ፲፪ ። እእኀዝኒ ፡ በእስራኤል ፡ ሞት ። ፩ሳሙ ፡ ፬ ፡ ፪ ። ወእሬጽም ፡ በታቦቱ ፡ ጽዮን ፡ መማረክ ። ፩ሳሙ ፡ ፬ ፡ ፲፱ ። አንድም ፡ እእኀዝኒ ፡ በታቦቱ ፡ ጽዮን ፡ መማረክ ። ወእሬጽም ፡ በአፍኒ ፡ በፊንሐስ ፡ ሞት ። አንድም ፡ እእኀዝኒ ፡ በአፍኒ ፡ በፊንሐስ ፡ ሞት ። ወእሬጽም ፡ በኤሊ ፡ ሞት ። አንድም ፡ እእኀዝኒ ፡ በኤሊ ፡ ሞት ። ወእሬጽም ፡ በሳዶቅ ፡ በአብያታር ፡ ሞት ፡ (ሐ) ፡ ሰሎሞን ፡ ሽሯቸው ፡ ነበርና ፡ ሽረቱን ፡ ከሞት ፡ ቈጥሮ ፡ አግብቶ ፡ ቈጠራቸው ። ፩ነገ ፡ ፪ ፡ ፳፮ ። ሳሙኤልም ፡ ምንስ ፡ ይህ ፡ ቢ

2014 04 17

ሆን፡አስቀድሜ፡አረዳዋለሁን፡ብሎ፡
ዝም፡ አለ ። ኤሊም ፡ በላ ፡ ንገረኝ ፡
አለው ። ያየሁትም ፡ የለ ፡ አለው ።
አልነግርሀም ፡ ካልከኝማ ፡ እንዲህ ፡
ይጣልህ ፡ ብየ ፡ እረግምሀ ፡ የለምን ፡
ብሎ፡ጭራውንም፡መቆሚያውንም፡
ቢሉ ፡ ቃጣ ። ፩ሳሙ፡ ፫ - ፲፮፡ ፲፰ ።

እንዲያውስ ፡ ሳትረግመኝ ፡ ታዝገር ፡
የለምን ፡ ብሎ ፡ የሱን ፡ ሞት ፡ ሠው
ሮ ፡ ሁሉን ፡ ነገረው ። ልጆቼስ ፡ ሲመ
ክሩት ፡ ይጠፋል ፡ ልጅ ፡ ሲታጠቡት ፡
ያድፋል ፡ እጅ ፡ እንዲሉ ፡ ብመክራ
ቸው ፡ እንቢ ፡ ብለውኛል ። ለይግበ
ር ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአደሞ ፡ የወደ
ደውን ፡ ያድርግ ። ነገር ፡ ግን ፡ አሥ
ራቱን ፡ በሎራቱን ፡ በልቼ ፡ ከብሬ ፡ ገ
ንኜ ፡ የምኖርበት ፡ ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ እን
ደ፡ምን ፡ ትማረክለች ፡ አለ ። ፩ሳሙ ፡
፫ ፡ ፲፰ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አሕዛብ ፡
ወደ ፡ ሽኤል ፡ ሽኤል ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡
ዘመቱ ። አልፈው ፡ ገጠሙ ። ሽኤል ፡
ሰነፉ ፡ ድል ፡ ሆኑ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ሰ
ዎች ፡ አለቁ ። ባጠገብ ፡ ሰፍረው ፡ አ
ድረዋል ። ፩ሳሙ ፡ ፬ ፡ ፪ ። ከሽኤል ፡
እኩሌቶቹ ፡ በይነ ፡ ምንት ፡ አውደ
ቀነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ እዴሆ
ሙ ፡ ለኢሎፍሊ ፡ በኢሎፍላውያን ፡
እጅ ፡ ለምን ፡ ጣለን ። ይሁዳ ፡ እዴከ ፡
ዲበ ፡ ዘባኖሙ ፡ ለፀርከ ፡ ተብሎ ፡ የ
ተገነረ ፡ ለኛ ፡ አልነበረምን ፡ አሉ ።
ዘፍ ፡ ፵፱ ፡ ፰ ። እኩሌቶቹ ፡ ቀድሞስ ፡
ለኛ ፡ ምን ፡ ኀይል ፡ አለን ። አባ
ቶቻችን ፡ እነ ፡ ሙሴ ፡ እለ ፡ ኢያሱ ፡
እለ ፡ ዓግ ፡ እለ ፡ ሲዖንን ፡ ድል ፡ ቢያ
ደርጉ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮንን ፡ ይዘው ፡ አ
ልነበረምን ፡ አሉ ። ዘኍ ፡ ፳፩ ፡ ፳፩-፴
፭ ። እግዚአብሔር ፡ የአፍኒ ፡ የፊን
ሐስ ፡ ሞት ፡ ፈቃዱ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡
እንዲመክሩ ፡ አደረጋቸው ። እሺ ፡
ስትሄድ ፡ እነርሱ ፡ አይቀሩምና ፡ በዚ
ያው ፡ ሥራውን ፡ ለመሥራት ። ከዚ
ህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኤሊ ፡ ይልኩበታል ።
በከተማ ፡ የቀረውን ፡ ጦር ፡ ሰብስበህ ፡
ታቦተ ፡ ጽዮንን ፡ አሲዘህ ፡ ላክልን ፡
ብለው ፡ አፍኒና ፡ ፊንሐስም ፡ ታቦተ ፡
ጽዮንን ፡ አጅበው ፡ ሄደዋል ። የል
ደት ፡ የጥምቀት ፡ ቀኝ ፡ ጌታ ፡ ግራ ፡
ጌታ ፡ ታቦት ፡ አጅበው ፡ እንዲወርዱ ።
፩ሳሙ ፡ ፬ ፡ ፬ ። በእስራኤል ፡ ከተማ ፡
ተድላ ፡ ደስታ ፡ ተደረገ ፡ ከዚህ ፡ በኋ
ላ ፡ አሕዛብ ፡ ይህን ፡ ሰምተው ፡ ምን
ት ፡ ውእቱ ፡ ዘንሰምዕ ፡ ውስተ ፡ ትዕ
ይንቶሙ ፡ ለእስራኤል ። በእስራኤ
ል ፡ ከተማ ፡ የምንሰማው ፡ ይህ ፡ ተ
ድላ ፡ ደስታ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ለል
ማዱ ፡ ድል ፡ ያደረገ ፡ ደስ ፡ ይለው ፡
ነበር ። ድል ፡ ያደረግን ፡ እኛ ፡ አሉ ።
ባጠገብ ፡ ያሉ ፡ አንድም ፡ ተማርከው ፡
አብረው ፡ ያሉ ፡ እስራኤል ። እንዲህ ፡
አይደለም ፡ ኀይል ፡ የምትሆናቸው ፡
እመቤት ፡ አለቻቸው ፡ እርሷ ፡ ብትመ
ጣላቸው ፡ ነው ፡ አሏቸው ። ወይ ፡ ለነ ፡
አሌ ፡ ለነ ፡ እስመ ፡ መጽኡ ፡ አማል
ክቲሆሙ ፡ ከመ ፡ ያጥፍዑነ ። ወመኑ ፡



ያድኅነነ ፡ እምእደዊሆሙ ፡ አሉ ። እን
ዲህ ፡ ማለታቸው ፡ ስለምን ፡ ነው ፡
ቢሉ ፡ ድንጋይ ፡ አለዝበው ፡ እንጨ
ት ፡ ጠርበው ፡ ጣዖት ፡ ያመልኩሉና ።
እንደነርሳቸው ፡ መስሎአቸው ። አን
ድም ፡ ኋላ ፡ ሥላሴ ፡ በነርሱ ፡ አድ
ረው ፡ ያጠፉናል ፡ ሲሉ ። ፊታቸው
ን ፡ ፀፍተው ፡ አፋቸውን ፡ ከፍተው ፡
አማልክቲሆሙ ፡ አሰኝተዋቸዋል ።
፩ሳሙ ፡ ፬ ፡ ፭—፰ ። ትላንት ፡ ድል ፡ አድ
ርገን ፡ ዛሬ ፡ ብንሸሽ ፡ ሴትን ፡ ይሉን ፡
ወንድ ፡ ብለው ፡ እየፈሩ ፡ ሄደው ፡
ገጠሙ ። አሕዛብ ፡ ድል ፡ አደረጉ ፡
ሽኤል ፡ ድል ፡ ሆኑ ። ከቄረበች ፡ አፈ
ረሰች ፡ ከመነኩሰች ፡ ባሰች ፡ እንዲ
ሉ ፡ ሶስት ፡ ዕልፍ ፡ ሰው ፡ አለቀ ፡ አፍ
ኒና ፡ ፊንሐስም ፡ በጦር ፡ ተነባብረው ፡
ወደቁ ። ታቦተ ፡ ጽዮንም ፡ ተማረከች ፡
ወእምሠጠ ፡ ፩ ፡ ብንያማዊ ፡ (ኢያሚ
ናዊ) ፡ እንዘ ፡ ስጡጥ ፡ አልባሲሁ ፡ ወ
ሐመድ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ እንዲል ። ከነ
ገደ ፡ ብንያም ፡ አንዱ ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፡
ትቢያ ፡ ነስንሶ ፡ ሔደ ፡ በሀገራቸው ፡
ትእምርት ፡ ኀዘን ፡ ነው ፡ አንድም ፡
ሲሮጥ ፡ ልብሱን ፡ ጋሬጣ ፡ ይይዘዋል ፡
ይቀድበታል ፡ ወድቆ ፡ ሲነሣ ፡ ትቢ
ያ ፡ ይመላበታልና ። እንዲህ ፡ ሆኖ ፡
እንዳማራ ፡ ከለ ፡ ሀገር ፡ ደረሰ ፡ ወጸ
ርሐት ፡ ሀገር ፡ ኵላ ፡ ይላል ፡ አባት ፡
ወንድም ፡ ልጅ ፡ ያልሔደበት ፡ የለ
ምና ፡ አንገት ፡ ላንገት ፡ ተያይዘው ፡
ያለቅሱ ፡ ጀመር ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ኤሊ ፡
ከደብተራ ፡ ፆሬት ፡ በር ፡ ወንበር ፡ አዘ
ርግቶ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፡ ወዔሊስ ፡
ይነብር ፡ ውስተ ፡ ኆኅተ ፡ ደብተራ ፡
ዘስምዕ ፡ እንዲል ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡
አሪት ፡ ኢይበዕ ፡ ሞዓባዊ ፡ ወአሞና
ዊ ፡ እስከ ፡ ሣልስ ፡ ወራብዕ ፡ ትውል
ድ ፡ ትላለችና ፡ ተሰስቶ ፡ እንዳይገባ ፡
ዘዳ ፡ ፳፫ ፡ ፭ ። አንድም ፡ መሥዋዕተ ፡
ሠርክ ፡ አለፈ ፡ መሥዋዕተ ፡ ነግህ ፡ አቅ
ርቡ ፡ መሥዋዕተ ፡ ነግህ ፡ አለፈ ፡ መ
ሥዋዕተ ፡ ሠርክ ፡ አቅርቡ ፡ ለማለት ፡
፩ነገ ፡ ፲፰—፳፱ ። ለዚህስ ፡ ባለወግ ፡
አለው ፡ ብሎ ፡ ቡራኬ ፡ የርሱ ፡ ነበ
ርና ፡ ለዚህም ፡ ባለወግ ፡ አለው ፡ ብሎ
ወይትሐዘዝ ፡ ልቡ ፡ ለኤሊ ፡ በእንተ
ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ እንዲል ፡ የታቦተ ፡
ጽዮንን ፡ ነገር ፡ ያወጣ ፡ ያወርድ ፡ ነበ
ርና ፡ ወሬ ፡ ለመጠየቅ ፡ እንደከተማ ፡
ሽማግሌ ፡ የከተማ ፡ ሽማግሌ ፡ ከመ
ንገድ ፡ ዳር ፡ ሆኖ ፡ የወጣ ፡ የወረደ
ውን ፡ ያለፈ ፡ ያገደመውን ፡ ወሬ ፡ እን
ዲጠይቅ ፡ ወተሐምጋ ፡ አእይንቲሁ
ለኤሊ ፡ እንዲል ፡ ዓይኑ ፡ ደፍርሶ ፡
ነበርና ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ አለው ፡ ትማ
ልም ፡ ዘእምሠጥኩ ፡ እምቀትል ።
ከጦርነት ፡ እምልጬ ፡ የመጣሁ ፡ ነኝ ፡
አለው ፡ ከዘመቻ ፡ እምልጬ ፡ የመ
ጣሁ ፡ ነኝ ፡ ትላለህሳ ፡ እስኪ ፡ ወሬ ፡
ንገረኝ ፡ አለው ፡ አበጥሮ ፡ አንጠር
ጥሮ ፡ ነገረው ። ልጆቼስ ፡ ብመክራቸ
ው ፡ ባስተምራቸው ፡ እንቢ ፡ ብለው
ኛል ፡ አሥራቱን ፡ በሎራቱን ፡ በልቼ ፡

2014 04 17

ከብሬ፡ገንዤ፡የምኖርበት፡ታቦት፡ጽ
ዮን፡እንደምን፡ተማረከች፡ትለኛለህ፡
ብሎ ፡ አዳንቄ ፡ አጋንኜ ፡ አለቅሳለ
ሁ ፡ ሲል ፡ የገልገላ ፡ ወደቀ ፡ የኋሊ
ት ፡ ማለት ፡ ነው ። ወሰበ ፡ ተዘከራ ፡
ኤሊ ፡ ለታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ወድቀ ፡ እመ
ንበሩ ፡ ወተሰብረ ፡ ዓፅመ ፡ ዘባኑ ፡
እስመ ፡ ልሂቅ ፡ ብእሲሁ ፡ ወልደ ፡ ተ
ስዓ ፡ ዓም ፡ እንዲል ፡ የዘጠና ፡ ዓመት ፡
ሽማግሌ ፡ ነበርና ፡ ወድቆ ፡ ተሰበረ ፡
እስመ ፡ ልሂቅ ፡ ባለው ፡ እስመ ፡ ግ
ዙፍ ፡ ይላል ፡ ቅርዐ ፡ ቀላል ፡ ሕፃን ፡
የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ወድቆ ፡ ይነሣል ፡
ቢሰበርም ፡ ይጠገናል ፡ እርሱ ፡ ግን ፡
አካሉ ፡ ግዙፍ ፡ ነበርና ፡ ወድቆ ፡ ተሰ
በረ ፡ ተሰብረ ፡ ባለው ፡ ተመይጠ ፡
ተዓፅፈ ፡ ይላል ፡ የጉድኑ ፡ አጥንት ፡
ተመልሶ ፡ ታጥፎ ፡ ሆዱን ፡ ወግቶ ፡
ገድሎታል ። ፩ሳሙ ፡ ፬ ፡ ፱ - ፲፰ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወንበር ፡ ያለሹም ፡
አይቀመጥምና ፡ ሳሙኤልን ፡ ሾሙ ፡
ሳሙኤልም ፡ ፳ ፡ ዘመን ፡ መግቧቸው ፡
አረጀ ፡ አሁን ፡ በኻያ ፡ ዘመን ፡ የሚ
ያረጅ ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ የመ
ሰልቸት ፡ የመበሳጨት ፡ የመሰቀቅ ፡
ይመስላል ። ፩ሳሙ ፡ ፯ ፡ ፩ ።

ኢዩኤል ፡ አብያ ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡
ልጆች ፡ ነበሩት ። እሊያን ፡ ምሉና ፡
ዱግ ፡ አድርጎ ፡ ሹሟቸዋል ፡ በደላቸ
ውም ፡ ምንም ፡ እንደአፍኒ ፡ እንደ
ፊንሐስ ፡ ባይሆን ፡ ማማለጃ ፡ በሉ ፡
ፍርድ ፡ አደሉ ፡ ሕዝቡም ፡ ተሰብስ
በው ፡ ሳሙኤልን ፡ አንተ ፡ እንዳት
መግበን ፡ አረጀህ ፡ ወደቂቅከኒ ፡ ኢ
ሖሩ ፡ በፍኖትከ ፡ ልጆችህም ፡ በሕ
ግህ ፡ ፀንተው ፡ አልኖሩም ፡ ነሥኡ ፡
ሕልያነ ፡ ወገመፁ ፡ ፍትሐ ፡ ማማለጃ ፡
በሉ ፡ ፍርድ ፡ አጉደሉ ፡ ይኸውም ፡
የቤት ፡ እንጉርጉሮ ፡ ነውና ፡ በቃል
ነው ፡ ነበር ፡ ይልቁንም ፡ በኢያቢስ ፡
ዘገለዓድ ፡ ባሉ ፡ ሁለት ፡ ነገድ ፡ ተኩ
ል ፡ (ከመንፈቅ) ፡ ወንድሞቻችን ፡
ናዖስ ፡ ዓሞናዊ ፡ ቀኝ ፡ ቀኝ ፡ ዓይና
ችሁን ፡ ገብሩኝ ፡ ብሎ ፡ በጠላትነት ፡
ተነሥቶባቸዋል ። ፩ሳሙ ፡ ፲፩ ፡ ፪ ።

ያን ፡ የሚያጠፋልን ፡ ንጉሥ ፡ አንግ
ሥልን ፡ አሉት ፡ አዘነ ፡ ማዘኑም ፡ መ
ንግሥት ፡ ከልጆቼ ፡ ሄደ ፡ ብሎ ፡ አይ
ደለም ። እግዚአብሔር ፡ በኔ ፡ አድሮ ፡
ይመግባቸው ፡ ነበረ ። ያነገሥኩላቸ
ው ፡ ንጉሥ ፡ የበደላቸው ፡ እንደሆነ ፡
ይከዱታል ፡ ጣኦት ፡ ከማምለክ ፡ ይደ
ርሳሉ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ወደእግ
ዚአብሔር ፡ ቢያመለክት ፡ ስምዖሙ ፡
ቃሎሙ ፡ ዘይቤሉክ ፡ የነገሩህን ፡ ስማ
ቸው ፡ አኮ ፡ ዘመነኑ ፡ ኪያከ ፡ አላ ፡
መነኑ ፡ ኪያየ ፡ ከመ ፡ ኢይንግሥ ፡
በሙ ፡ እንዲህ ፡ ማለታቸው ፡ አንተ
ን ፡ ንቀው ፡ አቃለው ፡ አይደለም ፡
እኔ ፡ ባንተ ፡ አድሬ ፡ ነግሼባቸው ፡ እን
ዳልኖር ፡ ንቀውኝ ፡ አቃለውኝ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ ወባሕቱ ፡ አስምዖ ፡ አስምዖሙ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ እስራኤልና ፡ ሴት ፡ ምክ



ንያት ፡ ይወዳሉና ፡ ሳናውቅ ፡ ተደረገ
ብን ፡ እንዳይሉ ፡ የንጉሡን ፡ ወግ ፡ ሥ
ርዓት ፡ ንገራቸው ፡ አለው ።

ሳሙኤልም ፡ ማንገሡን ፡ እነግሥላች
ኋለሁ ፡ ሳነግሥላችሁም ፡ ከናንተ ፡ አ
ንዱን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሌላ ፡ አይደለ
ም ። ነገር ፡ ግን ፡ ወግ ፡ ሥርዓቱን ፡
ልንገራችሁ ፡ ይነሥዕ ፡ ደቂቀክሙ ፡
ወአዋልደክሙ ፡ ወይሬስዮን ፡ መበ
ስላተ ፡ ወመዕዐጣተ ፡ ወንዶች ፡ ልጆ
ቻችሁን ፡ መልከ ፡ መልካሞቹን ፡ ም
ልምል ፡ መልከ ፡ ጥፉዎቹን ፡ ቋሚ ፡
ለጓሚ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችሁን ፡ መልከ
መልካሞቹን ፡ ገንቦ ፡ በጥባጭ ፡ ሸቱ ፡
አጣፋጭ ፡ መልከ ፡ ከፉዎቹን ፡ እን
ጀራ ፡ ጋጋሪ ፡ ወጠ ፡ ሠሪ ፡ ያደርግባች
ኋል ፡ ወይነሥዕ ፡ ዓፀደ ፡ ወፍርክሙ ፡
ከመስከችሁ ፡ ያዬ ፡ መስከ ፡ ከእርሻ
ችሁ ፡ ያዬ ፡ ሁዳድ ፡ ከዝመራችሁ ፡
ያዬ ፡ ቆሎ ፡ እህያችሁን ፡ ጎራዳ ፡ በቅ
ሏችሁን ፡ ወደል ፡ ጋዝ ፡ ከብታች
ሁን ፡ ተኰስ ፡ እያደረገ ፡ ይወስድባ
ችኋል ፡ አላቸው ፡ ይህም ፡ እስከ ፡
እዬ ፡ ፋሲል ፡ ደርሷል ፡ ከከፋትዎ ፡
ሁሉ ፡ ይህን ፡ አስቀርተዋል ። የሚ
ጠፋ ፡ ከተማ ፡ ነጋሪት ፡ ቢመቱበት ፡
አይሰማ ፡ እንዲሉ ፡ ሁሉ ፡ ጠላታች
ንን ፡ ያጥፋልን ፡ እንጂ ፡ ይሁንብን ፡
አሉ ። ያውስ ፡ ቢሆን ፡ ፀጅና ፡ ጉተና ፡
ዕለቱን ፡ አይፈላ ፡ እንዲሉ ፡ መንግ
ሥት ፡ ዕለቱን ፡ ይደርሳልን ፡ የዛሬ ፡
አርባ ፡ ቀን ፡ በመሴፋ ፡ እንገናኝ ፡
ብሎ ፡ ቀን ፡ ቀጥሮ ፡ ይሰዳቸዋል ፡
በዚህ ፡ መካከል ፡ ሥርዓተ ፡ መንግ
ሥት ፡ ይደረጋል ። ፩ሳሙ ፡ ፰ ፡ ፭-፳፪ ።

ከነገደ ፡ ብንያም ፡ ቂስ ፡ የሚባል ፡
ሰው ፡ ነበረ ፡ ወተገድፉ ፡ ፫ቱ ፡ አዕ
ዱጊሁ ፡ ለቂስ ፡ ይላል ፡ ሦስት ፡ አህ
ዮች ፡ ነበሩት ፡ ጠፉበት ፡ ልጁ ፡ ሳኦ
ል ፡ ይባላል ፡ ሂደህ ፡ አህዮቻችንን ፡
ፈልግ ፡ ገንዘቡስ ፡ ባልጉዳንም ፡ ነበረ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ ኦሪት ፡ ለገንዘባችሁ ፡
ሱስ ፡ ሳታወጡ ፡ አትቅሩ ፡ ትላለች ፡
እንጂ ፡ አለው ። ብላቴናው ፡ አበኔር ፡
ይባላል ፡ አስከትሎ ፡ ሄደ ፡ ወበጽሑ ፡
እስከ ፡ ደወለ ፡ ኤፍሬም ፡ ከኤፍሬም ፡
ዕፃ ፡ ሲደርሱ ። ዮጊ ፡ የጎድጎ ፡ ትከ
ዘ ፡ አዕዱግ ፡ ለአቡነ ፡ ወይቴክዝ ፡
በእንቲአነ ፡ አባታችን ፡ በኛ ፡ መጥ
ፋት ፡ ያዝናል ፡ እንጂ ፡ ባህዮቹ ፡ መጥ
ፋት ፡ አያዝንምና ፡ እንመለስ ፡ አለ
ው ፡ ብላቴናውም ፡ በዚህ ፡ ሀገር ፡
ነቢይ ፡ አለ ፡ እርሱ ፡ የአህዮቻችንን ፡
መጥፋት ፡ መገኘት ፡ ይነግረናልና ፡
ወደርሱ ፡ እንሂድ ፡ አለው ፡ ምንት ፡
ንሁብ ፡ ለነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሄ
ድስ ፡ በሄድን ። ነገር ፡ ግን ፡ ኦሪት ፡
ኢትቁም ፡ ዕራቀከ ፡ ቅድመ ፡ ነቢየ ፡
እግዚአብሔር ፡ ትላለችና ፡ ለነቢይ ፡
ምን ፡ እንሰጠዋለን ፡ መክፈልት ፡
ሲሹ ፡ መቅሠፍት ፡ እንዲሉ ፡ አለው ፡
ብላቴናውም ፡ ሀለወትኒ ፡ አሐቲ ፡ ራ
ብዕተ ፡ እዴሃ ፡ ለስቅለ ፡ ብሩር ፡ የብር ፡

2014 04 17

ሩብ፡ እለችኝ፡ ኪያየ፡ ትሁብ፡ እሷን፡ ትሰጠዋለህ፡ አለው፤ እንደምን፡ አድርጎ፡ ይዟት፡ ነበር፡ ቢሉ፡ ቀለበት፡ አሠርቶ፡ በጣቱ፡ እንድም፡ የወጣ፡ ሰው፡ አይታወቅምና፡ ብሎ፡ በድጉ፡ ቋጥሮ፡ ይዟት፡ ነበር። ፩ሳሙ፡ ፱-፰፡ ወረከቡ፡ ሐዋርያተ፡ ማይ፡ እንዘ፡ ይወፅኡ፡ ወሀ፡ የሚቀዱ፡ ሴቶችን፡ ከከተማ፡ በር፡ ሲወጡ፡ አገኙ፤ አይቴ፡ ቤቱ፡ ለረዓይ፡ የነቢየ፡ እግዚአብሔር፡ ቤቱ፡ ወዴት፡ ነው፡ አሏቸው፡ ደግ፡ እግር፡ ደርሳችኋል፤ እስራኤል፡ እንደ፡ ገዝከር፡ ያለ፡ ምሳ፡ አላቸው፡ አሁን፡ ለመበረክ፡ ሲወጣ፡ ታገኙታላችሁ፡ ብለዋቸዋል። ብዙም፡ ያልታወቀ፡ ነገር፡ ጠይቀዋቸዋል። ሴቶች፡ ነገር፡ አብገርዎች፡ ናቸውና፡ እንድም፡ የታወቀ፡ ነው። ሳኦል፡ ከራስ፡ ፀጉሩ፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ እግር፡ ጥፍሩ፡ ይህ፡ ቀረበት፡ የማይባል፡ መልከ፡ መልካም፡ ነበረና፡ መልኩን፡ ለመጥገብ፡ እንደ፡ ትናንት፡ ጌሠመ፡ ዘ፡ ጊዜ፡ እፌኑ፡ ለከ፡ ፩፡ ብእሴ፡ እምነገደ፡ ብንያም፡ ኪያሁ፡ ቅብዖ፡ ወእንግሦ፡ ብሎ፡ ለሳሙኤል፡ ነግሮት፡ ነበረና፡ ትማልም፡ ዘእቤለከ፡ ነዋ፡ ብእሲሁ፡ አለው፤ ሳኦልም፡ ሳሙኤልን፡ ተራ፡ ሰው፡ መስሎ፡ አገኘው፡ ዓይቴ፡ ቤቱ፡ ለረዓይ፤ የነቢየ፡ እግዚአብሔር፡ ቤቱ፡ ወዴት፡ ነው፡ አለው፤ ነቢየ፡ እግዚአብሔር፡ ይሉሃል፡ እኔ፡ ነኝ፡ አለው፤ ለምንት፡ ተኀዝን፡ በእንተ፡ ተገድፎቶሙ፡ ለ፫፡ አዕዱግ። አኮኑ፡ ደወሎሙ፡ ለ፳ኤል፡ ለከ፡ ወለቤተ፡ አቡከ፤ አሥራ፡ ሁለቱ፡ ነገደ፡ ፳ኤል፡ ላንተ፡ ላባትህ፡ ዘመዶች፡ በእጃችሁ፡ ጭብጥ፡ በእግራችሁ፡ እርግጥ፡ ሆነው፡ ሲገዙላችሁ፡ በሦስት፡ አህዮች፡ መጥፋት፡ ለምን፡ ታዝናለህ፡ አለው፤ ለከ፡ የተመቸ፡ ወለቤተ፡ አቡከ፤ እንደምን፡ ነው፡ ቢሉ፡ እሱ፡ ከነገሠ፡ ቀኛዝማች፡ ግራዝማች፡ እያለ፡ ይሾማቸዋልና፤ ነቢየ፡ እግዚአብሔር፡ ምነው፡ እንዲህ፡ ትቀፃፀበኛለህ፤ አኮኑ፡ እነ፡ እምእንተ፡ ትንዕስ፡ በትረ፡ ነገዱ፡ ለብንያም፡ ከአሥራ፡ ሁለቱ፡ ነገደ፡ ፳ኤል፡ ልሳሽ፡ መቆረጫ፡ ነገደ፡ ብንያም፡ ነው። ዘፍ፡ ፵፰፡ ፲፰። ከዚያ፡ የተወለድኩ፡ እኔን፡ ትነግሣለህ፡ ብለህ፡ ትቀፃፀበኛለህ፡ አለው፤ ይህን፡ እስከስረዳ፡ ነገር፡ ይወጣብኛል፤ ብሎ፡ ወደ፡ ባማ፡ ይዞት፡ ወጥቷል፤ አዳራሽ፡ ሰገነት፡ ማለት፡ ነው። ከሰባ፡ ሊቃናት፡ በላይ፡ አድርጎታል፤ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ነህ፡ ሲል፡ እንደሙሴ፡ ያለ፡ አስተንታኝ፡ ነበረው፤ ትላንትናውን፡ ታላቅም፡ ታናሽም፡ ሥጋ፡ ቢሉ፡ አስቀምጥ፡ ብሎት፡ ነበር፤ ትማልም፡ ዘእቤለከ፡ አንብር፡ ዝኩ፡ ክፍለ፡ እምጽእ፡ ሀቦ፡ ትላንት፡ አስቀምጥ፡ ያልኩህን፡ ሥጋ፡ አምጥተህ፡ ስጠው፡ አለው። አምጥቶ፡ ሰጠው፡ ብላዕ፡ እስከ፡ ትፀግብ፡ ወዘተር



ፈከ፡ አንብር፡ የበላኸውን፡ በልተህ፡ የተረፈህን፡ አኑር፡ ብሎታል፤ ምነው፡ ነቢይ፡ ንፍገት፡ ማስተማሩ፡ ነውን፡ ቢሉ፡ አይደለም፡ ሥርዓት፡ ማስተማሩ፡ ነው፡ እንጂ፤ ከሰው፡ ቤት፡ ማዘገዝ፡ አይገባም፡ ቢጠቅምም፡ ባይጠቅምም፡ ባለቤት፡ ያውቃል፡ እንጂ፡ እንግዳ፡ አያውቅምና፡ ለማለት፡ ከላዋቂ፡ ቤት፡ አዋቂ፡ እንግዳ፡ ናኘበት፡ እንዲሉ፤ እንድም፡ መንግሥቱ፡ በንተ፡ ብቻ፡ ይቀራል፡ እንጂ፡ ለልጅ፡ ልጅህ፡ አያልፍም፡ ሲል። ፩ሳሙ፡ ፴፮፡ ፩-፲፫።

እንድም፡ የቀድሞ፡ ነገሥታት፡ የበሉትን፡ በልተው፡ የተረፋቸውን፡ ከአዘቅት፡ ይጥሉ፡ ነበር፤ ይህም፡ እስከ፡ ዓፄ፡ ቴዎድሮስ፡ ሲያያዝ፡ መጥቶ፡ ነበር፤ በርሳቸው፡ ጊዜ፡ ቀርቷል፤ ከተበላበት፡ ከተጠጣበት፡ ደስቅ፡ የሚባል፡ የእንቅልፍ፡ ጋኔን፡ (ሰይጣን)፡ አለና፡ እንዳይጫነው፤ አንድም፡ ንጉሥ፡ ነህና፡ መጠበቅ፡ መጠንቀቅ፡ ይገባሃል፡ ሲል፡ ነው። ከዚህ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ሰገነት፡ ይዞት፡ ወጣ፤ ሲነጋ፡ ቀርን፡ ቅብዑን፡ በልብሱ፡ ሠውሮ፡ ይዞ፡ ነዓ፡ ወልድየ፡ እፈኑከ። ልጄ፡ ና፡ ልሸኝህ፡ አለው፤ ከሁለተኛው፡ በር፡ ሲደርሱ፡ በሎ፡ ለወልድከ፡ ይሑር፡ ቅድሜነ። አገዛ፡ ሲል፡ ነው፤ ብላቴናህ፡ ወደፊት፡ ይሔድ፡ ዘንድ፡ እዘዘው፡ አለው፤ ምነው፡ እርሱ፡ አያዘውምን፡ ቢሉ፡ ቆርሶ፡ ያላጉረሱትን፡ ቀዶ፡ ያላለበሱትን፡ ብላቴና፡ ማዘዝ፡ አይገባምና፤ ቅድሜነም፡ ማለቱ፡ ምሥጢር፡ እንዳይመረምር፡ ወደፊት፡ የሚሔድ፡ ብላቴና፡ ደረሱብኝ፡ እያለ፡ ወደፊቱ፡ ይሔዳል፡ እንጂ፡ ወደኋላው፡ አያይምና። ፩ሳሙ፡ ፱፡ ፳ - ፳፯። ከሦስተኛው፡ በር፡ ሲደርሱ፡ ከመገዘ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ቀባዕኩከ፡ ትንግሥ፡ ላዕለ፡ ሕዝብየ፡ ፳ኤል፡ ብሎ፡ ቅብዑን፡ በራሱ፡ ላይ፡ አፈሰሰበት፤ ወሣጠዲበ፡ ርእሱ፡ እንዲል። ፩ሳሙ፡ ፲፡ ፩። እግሩን፡ እጁን፡ አፉን፡ ይስመዋል፤ እግሩን፡ እጁን፡ መሳሙ፤ አሥራ፡ ሁለቱን፡ ነገደ፡ ፳ኤል፡ በእግርህ፡ እርግጥ፡ በእጅህ፡ ጭብጥ፡ አድርገህ፡ ትገዛለህ፡ ሲለው፡ ነው፤ አፉን፡ መሳሙ፡ ነገርህ፡ ይወደድልሃል፤ ሲለው፡ ነው፤ ይስዕመኒ፡ በስዕመተ፡ አፉሁ፡ እንዲል፤ ያፈቅረኒ፡ በፍቅረ፡ ልቡ፡ ሲል፤ መኃ፡ ፩፡ ፩። ከዚህ፡ በኋላ፡ ምልክት፡ ነግሮ፡ ይሰደዋል፤ እምዝ፡ ኅሊፈከ፡ ትረክብ፡ ፫ተ፡ ዕደወ፤ ፩ዱ፡ ይነድዕ፡ ፫ተ፡ አጣሌ፡ ወ፩ዱ፡ ይፀውር፡ ዝቀ፡ ወይን፤ ወ፩ዱ፡ ይፀውር፡ መስነቅተ፡ ኅብስት፤ ወይሁበከ፡ ቀዳምያተ፡ ኅብስት፤ ከዚህ፡ ስትሄድ፡ ፫ ሰዎች፡ ታገኛለህ፤ አንዱ፡ ፫ ፍየሎች፡ የሚነዳ፤ አንዱ፡ የወይን፡ ፊቀን፡ የያዘ፤ አንዱ፡ የስንቅ፡ አቁማዳ፡ የተሸከመ፤ እርሱም፡ መጀመሪያ፡ የወጣውን፡ ይሰጥሃል፤ ከምን፡

2014 04 17

የወጣውን፡ ቢሉ፡ ከአቴማዳ፤ አንድም፡ ከምጣድ፤ የግብር፡ ምልክት፡ ነው፡ ወእምዝ፡ ኅሊፈከ፡ ናሴብሃ፡ ኢሎፍላዊ፤ ከዚያ፡ አልፈህ፡ ናሴብ፡ ኢሎፍላዊን፡ ታገኛለህ፤ ይህም፡ ለምልክት፡ ያህል፡ ነው፡ እንጂ፡ ቁም፡ ነገር፡ የለውም፤ አማራና፡ ጋላ፡ ሴራ በቈረጡ፡ ጊዜ፡ ካማራ፡ ገበያ፡ አንድ፡ ጋላ፡ እንዳይታጣ፤ ወእምዝ፡ ትረክብ፡ መዘምረ፡ ነቢያት፤ ነቢያት፤ መዘምር፤ ደቂቀ፡ ነቢያት፡ ሲል፡ ነው፡ ከዚህ፡ አልፈህ፡ ደቂቀ፡ ነቢያትን፡ ታገኛለህ፤ እንዘ፡ ይትኔበዩ፤ ትትኔበይ፤ ወእንዘ፡ ይትናገሩ፡ ትትናገር፤ ትንቢት፡ ሲናገሩ፡ ትንቢት፡ ትናገራለህ፤ ምስጋና፡ ሲያመሰግኑ፡ ታመሰግናለህ፤ ሳኦልኑ፡ ምስለ፡ ነቢያት፡ ተኈለቈ፤ ተደመረ፡ ኅቡረ፡ ሲል፡ ነው፤ ዛሬስ፡ ሳኦል፡ ከደቂቀ፡ ነቢያት፡ ተቈጠረን፡ ይሉሃል፤ ከከተማ፡ አጠገብ፡ ስትደርስ፡ ሁለት፡ ሰዎች፡ ታገኛለህ፤ የቤተ፡ ሰብህን፡ ደህንነት፡ የአህዮችህን፡ መገኘት፡ ይነግሩሃል፤ የዛሬ፡ ሁለት፡ ዓመት፡ አሕዛብ፡ በጠላትነት፡ ይነሡብሃል፤ እኔ፡ እስከመጣ፡ ሰባት፡ ቀን፡ ያልፋል፤ ቀረ፡ ብለህ፡ መሥዋዕት፡ እንዳትሠዋ፡ መንግሥት፡ እንጂ፡ ክህነት፡ አልተሰጠህምና። ፩ሳሙ፡ ፲፡ ፩-፲፱። እንድም፡ ገልጾ፡ ነግሮታል፤ ወእምድኅረ፡ በጽሐከ፡ ዝ፡ ኵሉ፡ ግበር፡ ዘፈቀድከ፤ ይህ፡ ሁሉ፡ ምልክት፡ ከደረሰህ፡ በኋላ፡ መጽውት፡ ስጥ፤ ፍለጥ፡ ቁረጥ፡ የንጉሥ፡ ንፉግ፡ ፈሪ የለውምና፡ ብሎታል። ከዚያ፡ አልፎ፡ ሲሔዱ፡ ሦስቱን፡ ሰዎች፡ አገኘ፡ ናሴብን፡ አገኘው፤ ደቂቀ፡ ነቢያትንም፡ እያመሰገኑ፡ ሲሄዱ፡ አገኛቸው፤ ዛሬ፡ የሀገራችን፡ ደቀ፡ መዝሙር፤ ክብረ፡ በዓል፡ ኑሮ፡ ሲመለስ፡ መዝሙር፡ እስመ፡ ለዓለም፡ እየቃኘ፡ እንዲሄድ፡ ከከተማ፡ አጠገብ፡ ሲደርስ፡ ቤተ፡ ሰቦቹን፡ አገኘ፤ አህዮቻችንም፡ እከ፡ ወዲያው፡ እላንት፡ እልፍ፡ ስትሉ፡ ተገኙ፤ ወዴት፡ ሰነበታችሁ፡ አሏቸው፤ የአህዮቻችንንስ መገኘት፡ ነቢየ፡ እግዚአብሔር፡ ነገረን፤ ወነገረ፡ መንግሥትሰ፡ ኢዜነወነ፤ የመንግሥትን፡ ነገር፡ ግን፡ አልነገረንም፡ አለው፤ ያረገዘች፡ ታስታውቅ፡ ከደረቷ፡ ትታጠቅ፡ እንዲሉ። እንድም፡ የአህዮቻችንንስ፡ መገኘት፡ ነቢየ፡ እግዚአብሔር፡ ነገረን አላችሁ፤ የመንግሥትን፡ ነገርሳ፡ ቢለው፤ ወነገረ፡ መንግሥትሰ፡ ኢዜነወነ፤ የመንግሥትን፡ ነገር፡ ግን፡ አልነገረንም፡ አለ፡ የተመቸ፤ በዚያ፡ ወራት፡ የመንግሥት፡ ነገር፡ ይወራ ነበርና፡ እንድም፡ ወነገረ፡ መንግሥትሰ፡ ኢዜነዎ፡ ሳሙኤል፡ ለአበኔር፤ የመንግሥትን፡ ነገር፡ ግን፡ ሳሙኤል ለአበኔር፡ አልነገረውም፡ ይላል፡ ጸሐፊው፤ እንድም፡ ወነገረ፡ መንግሥትሰ፡ ኢዜነዎ፡ ሳሙኤል፡ ለሳኦል፤



የመንግሥትን፡ ነገር፡ ሳሙኤል፡ ለሳኦል፡ አልነገረውም፡ ይላል፤ አበኔር አላየምና።

አርባው፡ ቀን፡ ሲፈጸም፡ አሥራ፡ ሁለቱን፡ ነገደ፡ ሽኤል፡ ይዞ፡ ወደ፡ መሴፋ፡ ወጣ፤ በትራችሁን፡ ስጡኝ፡ ዕጣ፡ ላውጣላችሁ፡ አላቸው፤ ምነው፡ እንደቀባው፡ እንደሰጠው፡ ያውቅ፤ የለምን፡ ቢሉ፡ እግዚአብሔር፡ ከሰጠው፡ አይነሣውም፡ ብሎ፡ እንድም፡ ማማለጃ፡ በልቶ፡ ቃል፡ ለቃል፡ ተጨዋውቶ፡ ተዘምዶተ፡ ሥጋ፡ ኑሮት፡ አድልቶ፡ ይሉኛል፡ ብሎ፡ ዕፃ፡ ቢጥል፡ ለነገደ፡ ብንያም፡ ደረሰ፤ ከነገደ፡ ብንያም፡ ቢጥል፡ ለነገደ፤ ማጥር፡ ደረሰ፤ ከዚህ፡ በኋላ፡ ሰጡ፡ እያነሰ፡ ይሄዳል፡ ወአቀምሙ፤ በበብእሲሁ፤ ሰዎችን፤ እያቆመ፤ ቢጥል፤ ለነገደ፡ ቂስ፤ ደረሰ፡ ከነገደ፤ ቂስ፤ ቢጥል፤ ላልነበረ፡ ለሳኦል፡ ደረሰ፡ ወዴት፤ ሄዶ፡ ኖሯል፤ ቢሉ፤ ነገ፡ ታገቢያለሽ፤ ያሏት፡ ልጃገረድ፡ እንድታፍር፡ ትነግሣለህ፤ ያሉት፡ ንጉሥ፡ ያፍራልና፡ አፍሮ፡ ተሠውሮ፡ ውሎ፡ ነበር።

ሳሙኤልም፤ ወደ፡ እግዚአብሔር፤ እመለከተ፤ ምነው፤ ነቢይ፡ አይደለምን፡ ቢሉ፡ ነቢይነቱ፡ የጸጋ፡ ነው፤ እንጂ፤ የባሕርይ፤ ነውን፤ ይሏል። ወናሁ፤ ሀሎ፤ ይትኀባዕ፤ ማዕከለ፤ ንዋይ፡ ከዕቃው፤ መካከል፡ ተሠውሮአል፡ አለው፡ ባለቤቱ፡ ታጥቆ፡ እጅ፡ ነሥቶ፡ አመጣው፤ ብላቴናልክ፡ አያስመጣውም፡ ነበርን፡ ቢሉ፡ ለማስፈጠን፡ ለማስከበር፡ ነቢየ፡ እግዚአብሔር፡ እንጂ፡ ሂዶ፡ አመጣው፡ ብለው፡ እንዲያከብሩት። ነዋ፡ ንጉሥክሙ፡ ሽኤል፤ እስራኤል፡ ንጉሣችሁ፡ እነሆ፡ ብሎ፡ ሰጣቸው፤ ወከኑ፡ ሽኤል፡ ታሕተ፡ መትከፍቱ፡ ለሳኦል፡ ከትከሻው፡ በታች፡ ሆኑ፡ አሁን፤ ዕለቱን፡ ወርድ፡ ቁመት፡ የሚጨምር፡ ሆኖ፡ አይደለም፤ የሁሉ፡ ዓይን፡ የሚያርፍበት፡ ስለሆነ፡ ጥበበ፡ ለጸሐፊ፡ በመዋዕለ፡ ሢመቱ፡ እንዲል፤ ሲራ፡ ፴፰-፴፱። ደጋጎቹ፡ ሕየው፡ አበ፡ ነጋሢ፡ ብለው፡ ተቀብለውታል፤ ሕየው፡ አበ፡ ነጋሢ፡ ማለትም፡ ሺህ፡ ዓመት፡ ያንግሥህ፡ ወንድ፡ ልጅ፡ ወልደህ፡ ለፈረስ፤ ሴት፡ ልጅ፡ ወልደህ፡ ለበርኖስ፡ አድርስ፡ ማለት፡ ነው፡ ከፉዎች፡ ግን፡ እንግሥልን፡ ብንለው፡ ሲሆን፤ ከበነሶሩ፡ ከሮቤል፡ ባነገሠልን፡ ዘፍጥ፡ ፴፱-፵፰-፵፱-፫። ሳይሆንም፡ ኢይጠፍእ፡ ምስፍና፡ ወምልክና፡ እምአባሉ፡ ለይሁዳ፡ እስከ፡ አመ፡ ይረክብ፡ ዘጽኑሕ፡ ሎቱ፡ ተብሎ፡ ከተነገረለት፡ ከቤተ፡ ይሁዳ፡ ባነገሠልን፡ ነበር። ዘፍጥ፡ ፵፱-፲። ያለዚያ፡ ከአሥራ፡ ሁለቱ፡ ነገደ፡ ሽኤል፡ ልሳሽ፡ መቍረጫ፡ ብንያም፡ ነው፡ ከዚያ፡ የተወለደ፡ ያህያ፡ ጠ

2014 04 17

ባቂ ፣ የለማኝ ፣ የቂስ ፣ ልጅ ፣ ነግሦ ፣
ምን ፣ ጠላት ፣ ሊገፋልን ፣ ነው ፣ ብለ
ው ፣ ሄደዋል ። ፱፻፺፩-፲፻፰-፴፱-፷፯ ።
አሁን ፣ ናዖስ ፣ አሞናዊን ፣ ተዋግቶ ፣
ድል ፣ ነሥቶ ፣ እጅ ፣ አድርጎ ፣ እስኪ
ገዛቸው ፣ ድረስ ፣ ፩ሺ ፣ ፲፩፷፯ ፣
ወእምድኅረ ፣ ፩ወርኅ ፣ ዓርገ ፣ ናዖስ ፣
አሞናዊ ፣ ይላል ፣ ሳኦል ፣ ከነገሠ ፣
ከአንድ ፣ ወር ፣ በኋላ ፣ ናዖስ ፣ አሞ
ናዊ ፣ በኢያቢስ ፣ ዘገለዓድ ፣ ያሉ ፣
ሁለት ፣ ነገድ ፣ ተኩል ፣ (ተመንፈቅ) ፣
እስራኤልን ፣ ቀኝ ፣ ቀኝ ፣ ዓይናች
ሁን ፣ ገብሩልኝ ፣ ብሎ ፣ በጠላትነት ፣
ተነሣባቸው ፣ ምነው ፣ እንደወጉ ፣
እንደሥራቱ ፣ ፈረስ ፣ በቅሎ ፣ ግም
ጃ ፣ አውራጃ ፣ እንገብርልሀምን ፣
አሉት ፣ እኔ ፣ የፈረስ ፣ የበቅሎ ፣ የግ
ምጃ ፣ የአውራጃ ፣ ድሀ ፣ ነኝን ፣ ዳዕ
ሙ ፣ ከመ ፣ እግበር ፣ ዕዕለተ ፣ ላዕለ ፣
እስራኤል ፣ በእስራኤል ፣ ተረት ፣ ዘ
በት ፣ ላደርግ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ የኋላ ፣
ልጆች ፣ አባታችን ፣ ናዖስ ፣ ዓሞና
ዊ ፣ ሸኤልን ፣ ቀኝ ፣ ቀኝ ፣ ዓይቸውን ፣
አስገበራቸው ፣ ብለው ፣ እንዲናገሩ ፣
ለዝና ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ አላቸው ፣ አለ
ያም ፣ ብንችል ፣ እንዋጋለን ፣ ባንች
ል ፣ እንገብራለን ፣ አሉ ፣ አሁን ፣
እነርሱ ፣ ደፍረው ፣ እንደዚህ ፣ የሚሉ ፣
ሆነው ፣ አይደለም ፣ እሱ ፣ ትዕቢተኛ ፣
ነውና ፣ ይህንም ፣ ግድ ፣ የላችሁም ፣
ብትችሉ ፣ ትዋጋላችሁ ፣ ባትችሉ ፣ ግን
ትገብራላችሁ ፣ ብሏቸዋል ፣ ከከተማ ፣

ያሉ ፣ ወንድሞቻችን ፣ አዲስ ፣ ንጉሥ ፣
እንግሠዋል ፣ እሱ ፣ ቢችሉ ፣ ይረዱ
ናል ፣ ባይችሉ ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣
ያመለክቱልናል ፣ ብለው ፣ ላኩ ፣ እኒ
ያም ፣ አንገት ፣ ላንገት ፣ ተያይዘው ፣
ያለቅሱ ፣ ጀመር ፣ በሀገራቸው ፣ ዋዕ
የ ፣ ፀሐይ ፣ ይፀናል ፣ ቀን ፣ እያሠራ
ቸውም ፣ ከተራራ ፣ ላይ ፣ ዕንቀ ፣ እስቀ
ምጠው ፣ በዚያ ፣ ፀዳል ፣ ሌሊት ፣ ሲሠ
ሩ ፣ ያድራሉ ፣ በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ሳኦል ፣
አደን ፣ አድሮ ፣ ሲመለስ ፣ ወሳአልሰ ፣
የዓቱ ፣ ጊዜ ፣ ጽባሕ ፣ እንዲል ፣ ልቅሶ ፣
ሰምቶ ፣ ይህ ፣ የምሰማው ፣ ልቅሶ ፣
ምንድነው ፣ ብሎ ፣ ጠየቀ ። ነገሩት ፣
ጠላት ፣ ሴት ፣ ይመስል ፣ ቢያለቅሱ
ለት ፣ ይመለሳልን ። ባጭር ፣ ታጥቆ ፣
ዘገር ፣ ነጥቆ ፣ ቢሄዱበት ፣ ነው ፣ እንጂ ፣
ብሎ ፣ ሁለት ፣ ላም ፣ አምጡ ፣ አላቸ
ው ። አመጡለት ፣ እኒህን ፣ ከአሥራ ፣
ሁለት ፣ አባላ ፣ መትቶ ፣ አንዱን ፣ ከስ
ድስት ፣ አንዱን ፣ ከስድስት ፣ ቈርጦ ፣
ጌሠመ ፣ ዘ ፣ ጊዜ ፣ ዘኢተለዎሙ ፣ ለሳ
ኦል ፣ ወለሳሙኤል ፣ ከመዝ ፣ ይሬስ
ይዎሙ ፣ ለመራዕይሁ ፣ ንሬስዮሙ ፣
ሲል ፣ ነው ፣ ነገ ፣ ይህን ፣ ጊዜ ፣ ሳኦል
ንና ፣ ሳሙኤልን ፣ ያልተከተሏቸውን ፣
መንጋውን ፣ እንዲህ ፣ ያደርጉታል ፣
ማለት ፣ እናደርጋቸዋለን ፣ ብሎ ፣ ለ
አሥራ ፣ ሁለቱ ፣ ነገደ ፣ እስራኤል ፣
ይልከላቸዋል ። እናንተም ፣ እንገብራ
ለን ፣ ብላችሁ ፣ አትስነፉ ፣ አዘልላች
ሁ ፣ ቈዩኝ ። ጌሠመ ፣ ዘ ፣ ጊዜ ፣ ይከ



ውን ፣ ትፍሥሕትከሙ ፣ ድኅነትከ
ሙ ፣ ሲል ፣ ነው ፣ ነገ ፣ ይህን ፣ ጊዜ ፣
አድናችኋለሁ ፣ አላቸው ፣ በዚያ ፣ ወ
ራት ፣ የእስራኤል ፣ ድኅነት ፣ የጌታ ፣
ፈቃድ ፣ ነውና ፣ ሠላሳ ፣ ሦስት ፣ ዕል
ፍ ፣ አጋር ፣ ተሰበሰበ ። በሶስት ፣ ዘር
ፍ ፣ ያሠማራቸዋል ፣ ሲገሠግሥ ፣ አ
ድሮ ፣ ማለዳ ፣ ደርሶ ፣ ከነግህ ፣ እስከ ፣
ሰለስት ፣ ፈጸማቸው ፣ ሳኦል ፣ ድል ፣
አደረገ ፣ ብለው ፣ ለሳሙኤል ፣ ነገሩ
ት ፣ ንዑ ፣ ነሐድስ ፣ መንግሥቶ ፣ ለሳ
ኦል ፣ በገልገላ ፣ ብሎ ፣ የቃል ፣ ቅባ
ት ፣ ይቀባዋል ፤ የማትረባ ፣ ፍየል ፣
አራት ፣ መንታ ፣ ትወልድ ፣ እንዲሉ ፤
ወሖረ ፣ ውስተ ፣ ቀርሜሎስ ፣ ደጋ ፣ ደጋ
ውን ፣ በገልገላ ፣ በኩል ፣ መጣ ፣ አሉ
ት ፤ ወሜጠ ፣ ሠረገላሁ ፤ ሠረገላውን ፣
ወደ ፣ ገልገላ ፣ መለሰ ፤ እንድም ፣ ገል
ገላ ፣ ለፈረስ ፣ ለበቅሎ ፣ የማትመች ፣
ወጣ ፣ ገባ ፣ ነበረችና ፣ በእግሩ ፣ ለመ
ሄድ ፣ ሠረገላውን ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ መለ
ሰ ፤ ሁለት ፣ ዓመት ፣ ሙሉ ፣ ጠላት ፣
ጠፍቶለት ፣ ይኖራል ፤ ፩ሺ ፣ ፲፩ ፣
፩ - ፲፭ ። በሁለተኛው ፣ ዓመት ፣ አሕ
ዛብ ፣ በጠላትነት ፣ ተነሡበት ፣ ዘመተ ።
እስራኤል ፣ በደጋ ፤ አሕዛብ ፣ በቈላ
ሰፈሩ ፤ እስራኤል ፣ የአሕዛብን ፣ ብዛ
ት ፣ አይተው ፣ ከኒህ ፣ ጋር ፣ መዋጋት ፣
ማን ፣ ይችላል ፤ የደጋውም ፣ ውር
ጭ ፣ አልቻል ፣ አለን ፣ ከየቤታችን ፣
አሳልፈነው ፣ እንምጣ ፣ ብለው ፣ እየ
ተሠረቁ ፣ ሄደዋል ፤ ዕለቱንም ፣ ዮር

ዳኖስን ፣ ተሻግሮ ፣ ያደረ ፣ አለ ፤ ሳኦ
ል ፣ ግን ፣ አርበኛ ፣ ነውና ፣ ሁለት ፣ መቶ ፣
ራሱን ፣ ሆኖ ፣ ቀርቷል ፣ በ፯ኛው ፣ ቀን ፣
ሳሙኤል ፣ የቀረ ፣ መስሉት ፣ ከጠላ
ቶቹ ፣ ጋር ፣ ስዋጋ ፣ ወደ ፣ እግዚአብ
ሔር ፣ ሳላመለክት ፣ ይሆናልን ፣ ብሎ
መሥዋዕት ፣ ሠውቶ ፣ ሲወጣ ፣ ሳሙ
ኤል ፣ መጣ ፣ አሉት ። ሊቀበለው ፣
ቢወጣ ፣ ምን ፣ ስታደርግ ፣ ኑረሃል ፣
አለው ፤ በምን ፣ አውቆ ፣ ቢሉ ፣ ነቢይ ፣
ነውና ፣ በጸጋ ። አንድም ፣ ጢስ ፣ ሲወ
ጣ ፣ አይቶ ፤ አንድም ፣ መዓዛ ፣ መሥ
ዋዕት ፣ ሸቶት ፤ ዛሬ ፣ ድኅረ ፣ ቍር
ባን ፣ የዕጣን ፣ የኅብስት ፣ መዓዛ ፣
እንዲሸት ፣ አንድም ፣ ከእጁ ፣ ፈርስ ፣
ከልብሱ ፣ ደም ፣ አይቶ ፣ ሳአልም ፣
ተዓጊሥየ ፣ ሰቡዓ ፣ መዋዕለ ፣ ሦዕኩ ፣
ሰባት ፣ ቀን ፣ ጠብቄ ፣ ብትቀርብኝ ፣
ሠዋሁ ፣ አለው ። ኢይኄይስኑ ፣ ሰሚ
ዕ ፣ እምነ ፣ ሠዊዕ ፣ ወተአዝዞ ፣ እም
ስብሐ ፣ አባግዕ ፤ ያወለወለውን ፣ የ
ሰባውን ፣ ከመሠዋትማ ፣ የእግዚአ
ብሔርን ፣ ትእዛዝ ፣ መስማት ፣ አይ
ሻልም ፣ ነበርን ፤ ላሁን ፣ ድሉን ፣ ሰጥ
ቶሃል ፣ ያውም ፣ በልጅህ ፣ በዮናታን ፣
እጅ ፣ ነው ፣ በዚያው ፣ አልፈህ ፣ አማ
ሌቅን ፣ አጥፍተህ ፣ ሰውን ፣ ከብቱን ፣
ገድለህ ፣ እህሉን ፤ አቃጥለህ ፣ ተክ
ሉን ፣ ቈርጠህ ፤ ወሀውን ፣ ደፍነህ ፣
ና ፣ ብሎሃል ፣ አለው ፤ እኒህስ ፣ አማ
ሌቅ ፣ ምን ፣ አድርገዋል ፣ ቢሉ ፣ ፳
ኤል ፣ ከግብፅ ፣ ሲወጡ ፣ የደከመሙ

2014 04 17

ን ፡ አያሳርፉ ፡ የበረታውን ፡ አያሳል ፉም ፡ ነበርና ። ዘፀ ፡ ፲፯-፰-፲፱ ። ፩ሳሙ ፡ ፲፭-፪-፫ ። ለጊዜው ፡ ኢያሱ ፡ አጥፍቷቸዋል ፡ ፍጻሜው ፡ ግን ፡ ወእፀብዖሙ ፡ ለዘመደ ፡ ዘመድ ፡ በእድ ፡ ኅብዕት ፡ ተብሎ ፡ ተነግሮባቸዋል ፡ እድ ፡ ኅብዕት ፡ የተባለም ፡ ሳኦል ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዮናታን ፡ ብላቴናውን ፡ ጠርቶ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ከተማ ፡ እንሂድ ፡ ኑ ፡ ያሉን ፡ እንደሆነ ፡ ድሉን ፡ እንደሰጠን ፡ እናውቀዋለን ፤ ዝም ፡ ያሉን ፡ እንደሆነ ፡ ሰልለን ፡ እንመለሳለን ፡ ብሎት ፡ ሄዱ ፤ አሕዛብም ፡ አይተው ፡ አዮ ፡ ዛሬስ ፡ ሸኤል ፡ መዋጋት ፡ ቢሳናቸው ፡ አንዳንድ ፡ እያሉ ፡ ወባት ፡ ሊገቡ ፡ መጡን ፤ እላንት ፡ ሰዎች ፡ ኑ ፡ ኑ ፡ አልዋቸው ፤ ወሚጠ ፡ ገጸ ፡ ዮናታን ፡ ወደ ፡ ብላቴናው ፡ ፊቱን ፡ መለሰ ፡ ጋሻ ፡ ጦሩን ፡ ለመቀበል ፤ አንድም ፡ የወንድ ፡ ፊቱን ፡ አጠቄረ ፡ ብላቴናው ፡ ደንጋይ ፡ እያቀበለው ፡ ኻያ ፡ ሰው ፡ አጥፍቷል ፡ ወከነት ፡ ቀዳሚት ፡ ቀትሉ ፡ ፳ ፡ እንዲል ፤ ሳኦልም ፡ ሲያምከነክናቸው ፡ ሲያምታታቸው ፡ አይቶ ፡ እስኪ ፡ ከኛ ፡ የሄደ ፡ ሰው ፡ እንዳለ ፡ ፍቀዱ ፡ አለ ፡ ዮናታን ፡ ከነብላቴናው ፡ ታጣ ፤ የጦር ፡ ገበሬ ፡ ነውና ፡ ወርዶ ፡ ገጠመ ፡ ድል ፡ አደረጋቸው ።

በዚያው ፡ ኢሎፍሊ ፡ ሂዶ ፡ የኢሎፍላውያን ፡ አበጋዞቻቸው ፡ አጋግ ፡ ይባላል ፤ በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡ ሆኖ ፡ በፊት ፡ በኋላ ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡ ሲያጣልፍ ፡ አይቶት ፡ ይህንስ ፡ ተዉት ፡ ልጄን ፡ አጋብቼ ፡ አንድ ፡ በር ፡ ይይዝልኛል ፤ ወህውንም ፡ አትድፈኑት ፡ እህሉን ፡ ተክሉን ፡ ከብቱን ፡ አታጥፉት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ብናጠፋው ፡ ምን ፡ ይጠቅመናል ፤ ቢኖሩ ፡ ይህን ፡ እየበሉ ፡ ይገብሩልናል ፤ ባይኖሩስ ፡ ማን ፡ ይወስድብናል ፡ አላቸው ፤ ፩ሳሙ ፡ ፲፱-፲ ፡ ፳፫ ። ፲፭-፩-፱ ። ለሳሙኤል ፡ ሳኦል ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ መጣ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፡ ሊቀበለው ፡ ወጣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባንተ ፡ አድሮ ፡ ያዘዘኝን ፡ አድርጌ ፡ መጣሁ ፡ አለው ፤ ይህ ፡ ከሆነ ፡ የምሰማው ፡ ድምፅ ፡ ምንድነው ፡ አለው ፤ በምን ፡ አውቆ ፡ ቢሉ ፤ ከገሯ ፡ የወጣች ፡ ላም ፡ በድምጿ ፡ ትታወቃለችና ፤ አንድም ፡ በጸጋ ፡ አውቆ ፤ ሳኦልም ፡ መቸስ ፡ ሸኤል ፡ ለክፋት ፡ ያርፋሉን ፡ ለመሥዋዕት ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ አምጥተዋል ፡ አለው ፤ የራሷን ፡ አበሳ ፡ በሰው ፡ አብሳ ፡ እንዲሉ ፤ የአጋግንም ፡ መምጣት ፡ ከሴላ ፡ የሰማ ፡ እንደሆን ፡ ይጣላኛል ፡ ብሎ ፤ አጋግንም ፡ እንጂ ፡ መከረህ ፡ አስተምረህ ፡ ወደ ፡ አሪት ፡ ትመልሰዋለህ ፡ ብዬ ፡ አምጥቸዋለሁ ፡ አለሁ ፡ ከዚህም ፡ ደርሰህልን ፡ ብሎ ፡ ተቈጥቶ ፡ እሄዳለሁ ፡ ሲል ፡ ልብሱን ፡ ቢይዘው ፡ ተቀደደ ፤ በከመ ፡ ሠጠጥከ ፡ ለልብስየ ፡ ከማሁ ፡



ሰጠጣ ፡ ለመንግሥትከ ፡ ወወሀባ ፡ ለካልዕ ፡ ዘይኄይስ ፡ እምኔከ ፡ ልብሴን ፡ እንደቀደድከት ፡ መንግሥትህንም ፡ ከንተ ፡ ለሚበልጥ ፡ ሰጠብህ ፡ አለው ። እምኔከ ፡ ማለቱ ፡ ዳዊት ፡ ያልኹ ፡ እንደሆነ ፡ ይጣላዋል ፡ ብሎ ፡ ዘይኄይስም ፡ አለው ፡ በዓይን ፡ ጥቅሸ ፡ በከንፈር ፡ ንክሻ ፡ የሚያውቅ ፡ ሲል ፡ ነው ። ሳኦልም ፡ ስንኳን ፡ አንተ ፡ ተጣልተኸኝ ፡ እንዲያውም ፡ ሸኤል ፡ ሳይወዱ ፡ በግድ ፡ ነግሼባቸዋለሁ ፤ በእሳት ፡ ጠብሰው ፡ በድንጋይ ፡ ወግረው ፡ ይገሉኛልና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አስታርቀኝ ፡ አጋግን ፡ እንደ ወደድህ ፡ አድርገው ፡ አለው ፤ ሳሙኤልም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሄደ ፡ ሳኦል ፡ ከዚያው ፡ ቀርቶ ፡ የመንገድ ፡ ግብር ፡ አቀረበ ፤ ወአጋግሰ ፡ ይነብር ፡ በጸጋመ ፡ ንጉሥ ፡ አጋግ ፡ ከንጉሡ ፡ በስተግራ ፡ ተቀምጦ ፡ ይመገብ ፡ ነበረ ፤ ሳሙኤልም ፡ አጋግን ፡ ላክልኝ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ ላከ ፤ አጋግ ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ከመገዘኑ ፡ ሞት ፡ መሪር ፡ አለ ፤ አንድም ፡ በመቃብያን ፡ ያቀናዋል ፤ በሕፁዓንም ፡ ይላል ፤ ሳኦል ፡ አጋግን ፡ ለሳሙኤል ፡ ሊሰጠው ፡ ሳሙኤል ፡ ሳኦልን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሊያስታርቀው ፡ ተዋውለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሄደዋል ፤ ሳሙኤል ፡ ከቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀረ ፤ ሳኦል ፡ ተመለሰ ፡ ከድንኳኑ ፡ ገብቶ ፡ የመንገድ ፡ ግብር ፡ አቀረበ ፡ የደብተራ ፡ አሪት ፡ በርና ፡ የሳኦል ፡ ድንኳን ፡ በር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ነው ፡ ሳሙኤል ፡ ባጭር ፡ ታጥቆ ፡ ዘገር ፡ ነጥቆ ፡ ሲመጣ ፡ አጋግ ፡ አይቶ ፡ ከመገዘኑ ፡ ሞት ፡ መሪር ፡ ብሏል ፡ ሳሙኤልም ፡ በከመ ፡ አምከነቶን ፡ ኩናትከ ፡ ለአንስት ፡ ከማሁ ፡ ለትኩን ፡ እምከ ፡ ምክንተ ፡ እምኔከ ፡ ብሎ ፡ ፈከሮ ፡ ዘምሮ ፡ ገድሎታል ፤ እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ስለምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ባሎቻቸውን ፡ እየገደለ ፡ የሚደርስባቸው ፡ አጥተዋልና ። አንድም ፡ ልጆቻቸውን ፡ እየገደለች ፡ የወላድ ፡ መካን ፡ አድርጋቸዋለችና ፡ አንድም ፡ ሴትን ፡ ወንድን ፡ ገድዬ ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ ሆዳቸውን ፡ እየቀደደ ፡ ያየው ፡ ነበርና ፡ አንድም ፡ የእሥራኤል ፡ ሴቶች ፡ አጋግ ፡ መጣ ፡ ሲሏቸው ፡ ፅንሳቸው ፡ ይወርድ ፡ ነበርና ፡ የሳሙኤል ፡ አጋግን ፡ መግደል ፡ ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፴፫ ፡ የፊንሐስ ፡ ከስቢን ፡ ዘምሪን ፡ መግደል ፡ ዘኁ ፡ ፳፭ ፡ ፯-፲፭ ። ሸኤል ፡ ያጠመሙትን ፡ ከማቅናት ፡ ያጕደሉትን ፡ ከመምላት ፡ ተቈጥሮላቸዋል ፡ እንጂ ፡ ዕዳ ፡ አልሆነባቸውም ፡ ከዚህ በኋላ ፡ በእንዶራዊት ፡ ምክንያት ፡ እስኪነሣ ፡ አይገናኙም ። ፩ ፡ ነገ ፡ ፳፰ ፡ ፯ ፡ ፳፭ ። እንዲህ ፡ ግን ፡ ስለሆነ ፡ ይጸልይለታል ፤ መነኵሴ ፡ ላጭቶ ፡ ላመነኰሰው ፡ ነቢይ ፡ ቀብቶ ፡ ላነገሠው ፡ ማዘን ፡ ይገባልና ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፩ ፡ ፴፭ ። እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ትላህዎ ፡

2014 04 17

ሳሙኤል ፡ ለሳኦል ፡ እስመ ፡ አን ፡
መንንከዎ ፡ ወገደፍከዎ ፡ እኔ ፡ በረ
ድኤት ፡ ተለይቼዋለሁ ፤ እስከ ፡ መቼ ፡
ድረስ ፡ ስታዝንለት ፡ ትኖራለህ ፡ ብሎ ፡
ጌታ ፡ ለሳሙኤል ፡ ነገረው ፤ ለሸኤል ፡
ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ አለው ፤ ለሸ
ኤልስ ፡ ከልሀ ፡ ምላዕ ፡ ቀርነ ፡ ቅብዕ ፡
በሳኦል ፡ የጉደለውን ፡ ምላ ፡ መ
ልዕ ፡ ቀርን ፡ ቅብዑን ፡ ይዘህ ፡ ከ
ቤተ ፡ ልሔም ፡ ሒደህ ፡ የዕሤይን ፡
ልጅ ፡ ቀብተህ ፡ አንግሥልኝ ፡ አለው ፤
አንተ ፡ ጌታዬ ፡ መንንከዎ ፡ ገደፍ
ከዎ ፡ ትላለህ ፤ እርሱ ፡ አለሁ ፡ አለሁ ፡
ይላል ፡ በንጉሥ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡
አንግሼ ፡ ብገኝ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ አንገ
ቴን ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ባቴን ፡ ይቀጣኝ ፡
የለምን ፡ አለው ፤ ጌታም ፡ ማዳን ፡
መታደግ ፡ ሲቻለው ፡ ምልክት ፡
ነግሮ ፡ ይሰደዋል ፤ ሁለት ፡ ላም ፡ አስ
ነድተህ ፡ ሂድ ፤ ወዴት ፡ ትሄዳለህ ፡
ያሉህ ፡ እንደሆነ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ለቤተ ፡
ልሔም ፡ ሰዎች ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋ
ላቸው ፡ ብሎኛል ፡ በላቸው ፡ ብሎ ፡
ሳሙኤልም ፡ ጌታ ፡ ያዘዘውን ፡ አደ
ረገ ፡ ሰላምኑ ፡ ምጽአትከ ፡ አመጣ
ጥህ ፡ ደህና ፡ ነውን ፡ አሉት ፤ ነቢየ ፡
እግዚአብሔር ፡ የሚመጣ ፡ ወይም ፡
ለበጎ ፡ ወይም ፡ ለክፉ ፡ ነውና ፤ ደህና ፡
ነኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፈጣሪዬ ፡ ለቤተ ፡
ልሔም ፡ ሰዎች ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋ
ላቸው ፡ ብሎኛል ፡ አላቸው ፤ ከኔ ፡
ቤት ፡ እንሂድ ፡ ከኔ ፡ ቤት ፡ እንሂድ ፡
ብለው ፡ ተሻሙት ፡ እንዲህ ፡ አይደ
ለም ፡ ይህን ፡ ከየቤታችሁ ፡ ሠጪ ፡
እኔ ፡ ከዕሤይ ፡ ቤት ፡ ሂጀ ፡ እሠዋ
ለሁ ፡ አላቸው ፤ ወቀደሶሙ ፡ ለዕሤ
ይ ፡ ወለደቂቁ ፡ ዕሤይን ፡ ከልጆችህ ፡
የማነግሥ ፡ ነኝና ፡ ንጹሐን ፡ ሆናች
ሁ ፡ ሰንብቱ ፡ በላቸው ፡ አለው ፤ በር
ኛው ፡ ቀን ፡ መሥዋዕት ፡ ሠውቶ ፡
ለመንግሥት ፡ የሚገባውን ፡ አምጣ
ው ፡ አለው ፤ በኵሩ ፡ ኤልያብ ፡ ይ
ባላል ፡ አቀረበው ፤ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡
መሢሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፤ ለመንግ
ሥት ፡ የሚገባው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሳኦ
ልም ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ነበረ ፡ ይል
ቅስ ፡ ይህ ፡ ይበልጥ ፡ አለ ፤ ቀርነ ፡
ቅብዑ ፡ አልከፈትለት ፡ አለ ፤ ኢትር
አይ ፡ ግርማ ፡ ርእየቱ ፡ ለኤልያብ ፡
ሰብእሰ ፡ ገጸ ፡ ይሬኢ ፡ እግዚአብሔ
ርሰ ፡ ልበ ፡ ይሬኢ ፤ ሰው ፡ የመልክን ፡
ደም ፡ ግባት ፡ ያያል ፤ እግዚአብሔር ፡
ግን ፡ የልቡናን ፡ ቅንነት ፡ ያያል ፤
የኤልያብን ፡ መወደድ ፡ የመልኩን ፡
ቅንነት ፡ አትይ ፡ አለው ፤ ወዲያው ፡
ለዝ ፡ ኢኀረዮ ፡ ብሎታል ፡ ፩ሳሙ ፡ ፲፮-
፩-፯ ፡ ተከታዩ ፡ ሳባ ፡ ሳቢት ፡ ይባላል ፡
አመጣ ፤ ለዝኒ ፡ ኢኀረዮ ፡ ብሎታል ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለሱም ፡ ተገልያለት ፡
ለዝኒ ፡ ኢኀረዮ ፡ ለዝኒ ፡ ኢኀረዮ ፡
እያለ ፡ አሰናብቷቸዋል ፤ ወአምጽአ
ሙ ፡ እስከ ፡ ፯ቲሆሙ ፤ ለአመጣጥ ፡
፯ኛ ፡ ለልደት ፡ ፰ኛ ፡ አለ ፡ ያን ፡ አም
ጥቶ ፡ ዝም ፡ አለ ፤ ዳዕሙ ፡ እሉት ፡



ዕሤይ ፡ ደቂቅከ ። ዕሤይ ፡ ልጆችህ ፡
እኒህ ፡ ብቻ ፡ ናቸውን ፡ አለው ፡
አሁን ፡ ለተናገርከው ፡ አይሆንም ፡
እንጂ ፡ በጎች ፡ የሚጠብቅ ፡ ብላቴና ፡
አለ ፡ አለው ፤ ኢይመስሕ ፡ ዘእንበለ ፡
ይምጽእ ፡ እርሱ ፡ ሳይመጣ ፡ እህል ፡
ወሀ ፡ አልቀምስም ፡ አለው ። ስለምን ፡
ቢሉ ፡ ለማስፈጠን ፤ ዛሬ ፡ ከቤተ ፡
መንግሥት ፡ የተላከ ፡ ብላቴና ፡ መላ
ክቴን ፡ ሳልነግር ፡ እህል ፡ ወሀ ፡ አ
ልቀምስም ፤ እንዲል ፡ ዘፍ ፡ ፳፬-፴፫ ።
እሱም ፡ ልከ ፡ አስመጣው ፤ ገና ፡
አርባ ፡ ክንድ ፡ ሲቀር ፡ ቀርነ ፡ ቅብዑ ፡
ፀግ ፡ ብሎ ፡ ተከፈተ ፤ ፈላ ፡ ተፍለ
ቀለቀ ፡ በወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ ቀ
ብቶ ፡ አነገሠው ፤ ስለምን ፡ ቢሉ ፡
ከኛ ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ አደረገ
ለት ፡ ይሆን ፡ ብለው ፡ ምሥጢር ፡
እንዳይመረምሩ ፤ አንድም ፡ መከራ ፡
ያለበት ፡ ነውና ፡ በተስፋው ፡ እንዲ
ከተሉት ፤ አንድም ፡ በስደቱ ፡ ጊዜ ፡
መከራ ፡ አጥንተውበት ፡ በመንግሥ
ቱ ፡ ጊዜ ፡ መከራ ፡ እንዳያፀናባቸ
ው ፡ ፩ሳሙ ፡ ፲፮-፩-፲፫ ። በዚህም ፡ ቅባት ፡
ምክንያት ፡ ሰባቱ ፡ ሀብታት ፡ ተሰጥ
ተውታል ፤ ሰባቱ ፡ ሀብታትስ ፡ ምንና ፡
ምን ፡ ናቸው ፡ ቢሉ ፤ ሀብተ ፡ መን
ግሥት ፡ ፩ ። ሀብተ ፡ ክህነት ፡ ፪ ። ሀብ
ተ ፡ ኃይል ፡ ፫ ። ሀብተ ፡ መዊዕ ፡ ፬ ፡
ሀብተ ፡ በገና ፡ ፭ ። ሀብተ ፡ ፈውስ ፡
፮ ፡ ሀብተ ፡ ትንቢት ፡ ፯ ፡ ናቸው ።
ሀብተ ፡ መንግሥት ፡ የገደለውን ፡
ማስገደል ፡ ወንበደውን ፡ በአንድ ፡
አራት ፡ አምስት ፡ ማስከፈል ።
ሀብተ ፡ ክህነት ፡ መቶ ፡ አምሳውን ፡
መዝሙር ፡ ካራት ፡ አድርገው ፡ ተከ
ፍለው ፡ በሻያ ፡ አራቱ ፡ ጊዜ ፡ አሥ
ራ ፡ ሁለት ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ እየሆኑ ፡
ያደርሱት ፡ ነበር ፤ አለቆቻቸው ፡ ኤ
ማን ፤ ቆሬ ፤ አሳፍ ፡ ኤዶትም ፡ ይባ
ላሉ ፤ ከነዚያ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ተብሎ ፡
መቁጠር ፡ ፩ዜና ፡ መ ፡ ፲፭-፲፯ ። ሀብተ ፡
ኃይል ፡ አንበሳ ፡ በርግጫ ፡ ነብር ፡
በጡጫ ፡ መግደል ፡ ፩ሳሙ ፡ ፲፯-፴፬-
፴፯ ። ሀብተ ፡ መዊዕ ፡ ጦሩ ፡ በተደ
ረደረበት ፡ ኃያላኑ ፡ በተሰለፉበት ፡
የዳዊት ፡ ሎሌ ፡ የዳዊት ፡ ሎሌ ፡
መጣ ፡ መጣ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ይፈርስ ፡
ነበር ፤ ፩ሳሙ ፡ ፲፰ ፡ ፳፯ ። ሀብተ ፡ በገ
ና ፡ እንጨቱን ፡ ጠርቦ ፡ ቆርበቱን ፡
ጉልቦ ፡ ዥማቱን ፡ ወትሮ ፡ መደርደ
ር ፤ ሀብተ ፡ ፈውስ ፡ በገናውን ፡ እየ
ደረደሩ ፡ ድውይ ፡ መፈወስ ፡ ነው ፤
ይህስ ፡ ሀብተ ፡ በገና ፡ ካለው ፡ ይገባል ፡
ብሎ ፡ ሀብተ ፡ ፈውስ ፡ መንፈሳዊ ፡
አመጣጥ ፤ ፩ሳሙ ፡ ፲፮ ፡ ፳፫ ። ሀብተ ፡
ትንቢት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ መዝሙር ፡
መድረስ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ግን ፡ ስለ
ሆነ ፡ አርእስቱ ፡ አሥር ፡ ነው ፤ መጀ
መሪያ ፡ ተግሣፅ ፡ ለኵሉ ፤ መዝ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡
ሁለተኛ ፡ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ክር
ስቶስ ፡ መዝ ፡ ፪ ፡ ፩ ። ሦስተኛ ፡ ትን
ቢት ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ፡ መዝ ፡ ፫ ፡ ፩ ።
አራተኛ ፡ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ መነና

2014 04 17

ውያን ፡ መዝ ፡ ፱ ፡ ፩ ፡ አምስተኛ ፡ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ትሩፋን ፡ መዝ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ስድስተኛ ፡ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ሕዝቅያስ ፤ መዝ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ። ሰባተኛ ፡ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ኤርምያስ ። መዝ ፡ ፴፱ ፡ ፩ ። ስምንተኛ ፡ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ መቃብያን ፤ መዝ ፡ ፵፫ ፡ ፩ ። ዘጠነኛ ፡ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ዘለፋ ፡ ክህናት ፡ መዝ ፡ ፵፱ ፡ ፩ ። አሥረኛ ፡ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ሰሎሞን ፤ ወልዱ ፤ መዝ ፡ ፸፩ ፡ ፩ ። ተግሣፅ ፡ ለኵሉ ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢሖረ ፡ በምክረ ፡ ረሲዓን ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ለምንት ፡ አንገለጉ ፡ አሕዛብ ፤ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ፡ እግዚኦ ፡ ሚበዝኁ ፡ እለ ፡ ሣቅዩኒ ። ትንቢት ፡ በእንተ ፡ መነናውያን ፡ ሶበ ፡ ፀዋዕክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰምዓኒ ፡ ጽድቅየ ። ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ትሩፋን ፡ ቃልየ ፡ አጽምዕ ፡ እግዚኦ ፤ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ይብል ፡ ዓብድ ፡ በልቡ ፡ አልቦ ፡ እግዚአብሔር ፤ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ኤርምያስ ፡ ግፍዖሙ ፡ እግዚኦ ፡ ለዕለ ፡ ይገፍዑኒ ፤ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ መቃብያን ፡ እግዚኦ ፡ ሰማዕነ ፡ በዕዘኒነ ፡ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ዘለፋ ፡ ክህናት ፡ አምላከ ፡ አማልክት ፡ እግዚአብሔር ፡ ነበበ ፡ ወፀውዓ ፡ ለምድር ፤ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ሰሎሞን ፤ እግዚኦ ፡ ኰነኔከ ፡ ሀበ ፡ ለንጉሥ ፤ እሊህ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ ያሥሩ ፡ ቃላት ፡ የአሥሩ ፡ አውታረ ፡ በገና ፡ የአሥሩ ፡ ሕዋሳት ፤ የአሥሩ ፡ መዓርጋት ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ በዚህም ፡ በአሥሩ ፡ አርእስት ፡ አምስት ፡ ነገር ፡ አለበት ፤ የአምስቱ ፡ አዕማደ ፡ ምሥጢር ፤ ያምስቱ ፡ ሕዋሳት ፡ ተግሣፅ ፡ ለኵሉ ፡ ምዕዳን ፤ ጸሎት ። ትንቢት ፡ አኰቴት ፤ ተግሣፅ ፡ ለኵሉ ፡ አይለወጥም ፤ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢሖረ ፡ በምክረ ፡ ረሲዓን ፡ መዝ ፡ ፩ ፡ ምዕዳን ፡ እንደነ ፡ ኢትቅናዕ ፡ ፴፮ ፤ እንደነ ፡ ስምዑ ፡ ዘንተ ፡ ፵፰ ። እንደነ ፡ አዕምዑ ፡ ሕዝብየ ፡ ሕግየ ፡ ፸፯ ። ያለው ፡ ነው ፤ ጸሎት ፡ ስምዓኒ ፡ እግዚኦ ፡ ጸሎትየ ፡ ፻፩ ። ትንቢት ፡ ይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ለእግዚእየ ፡ ንበር ፡ በየማንየ ፡ ፻፱ ። አኰቴት ፡ አእኵተከ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ተወከፍከኒ ፡ ፳፱ ። ተአኵቶ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፻፵፭ ፡ ነው ፤ ይህን ፡ በረት ፡ ለይኩን ፤ በጅና ፡ ለይበሉ ፡ ከፍሎ ፡ ተናግሮታል ፤ መዝ ፡ ፶ ፡ ፫ ። ፸፩ ፡ ፲፱ ፡ ፹፰ ፡ ፶፪ ። ፻፭ ፡ ፵፰ ። ጻፊውም ፡ ብሎት ፡ ጽፎታል ። መጻፉም ፡ ለኛ ፡ ምክር ፡ ተግሣፅ ፡ ዕገሥት ፡ ሊሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለከንቱ ፡ አይደለም ። ወኵሉ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ ለተግሣፀ ፡ ዚአነ ፡ ተጽሕፈ ፡ ከመ ፡ በትዕግሥትነ ፡ ወበተወክሎ ፡ መጻሕፍት ፡ ንርከብ ፡ ተስፋነ ፡ እንዲል ፤ ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፬ ። ሲጽፍስ ፡ በማን ፡ ጀምሯል ፡ ቢሉ ፤ በጎልያድ ፡ ጊዜ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፤ ንዑስ ፡ አነ ፡ እምአኃውየ ፡ ብሎ ፡ መዝ ፡ ፻፶፩ ።



በሳኦል ፡ ጊዜ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ አድኅነኒ ፡ እግዚኦ ፡ ምብእሲ ፡ እኩይ ፡ ብሎ ፡ ጀምሯል ፤ መዝ ፡ ፻፴፱ ። ይህማ ፡ እንዳይሆን ፡ መጽሐፍ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ውስተ ፡ መዝሙር ፡ ዘ፪ ፡ ወልድየ ፡ አንተ ፡ ይላልሳ ፡ ቢሉ ፤ ግብ ፡ ሐ ፲፫ ፡ ፴፫ ።

ይህማ ፡ ምን ፡ ያውካል ፡ ለአድኅኖ ፡ ሂም ፡ ለንዑስም ፡ ሁለተኛ ፡ ቢያደርጉት ፡ ይሆናል ፤ እንግዲያ ፡ ዛሬ ፡ በጥራዝ ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲን ፡ እናስቀድማለንሳ ፡ ቢሉ ፤ ሊቃውንት ፡ በአስተጋብዖተ ፡ መጻሕፍት ፡ ጊዜ ፡ በጥራዝ ፡ አንድም ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ እያለ ፡ ሌላ ፡ እናስቀድማለንን ፡ ብለው ፡ በብያኔ ፡ አስቀድመውታል ፤ አንድም ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ በብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ጀምሯል ።

ይህም ፡ ሲነበብ ፡ ሲተረጎም ፡ እስከ ፡ ዘመነ ፡ ሐዋርያት ፡ ደርሷል ፤ ሐዋርያት ፡ ሰማንያ ፡ አንድ ፡ መጻሕፍት ፡ ለቀሌምንጦስ ፡ ሲያስረክቡ ፡ አንድ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ብለው ፡ ቈጥረው ፡ አስረክበዋል ፤ መቍጠራቸውም ፡ ስለአራት ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ለሕያዋን ፡ ዕቅበት ፡ ለሙታን ፡ ጸሎት ፡ ለሕፃናት ፡ ትምህርት ፡ ቅድመ ፡ መሐርዎሙ ፡ ለውሉድክሙ ፡ መጽሐፈ ፡ ሰሎሞን ፡ ወሲራክ ፡ ወመዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ እንዲል ፤ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስብከት ፡ ሊሆን ፡ ነው ፤ ከዚህም ፡ በአርእስቱ ፡ እስመ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊትስ ፡ ትመስል ፡ ገነተ ፡ ዘታቀርብ ፡ መላእክተ ፤ ወታርኅቅ ፡ (ትሰድድ) ፡ አጋንንተ ፡ ዘትጸጊ ፡ ጽጌያተ ፡ ወትፈሪ ፡ ፍሬያተ ፡ ይላል ፤ ዘይቤው ፡ ያልቀና ፡ ነው ፤ እስመ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊትስ ፡ ዘታቀርብ ፡ መላእክተ ፡ ወትሰድድ ፡ አጋንንተ ፡ ትመስል ፡ ገነተ ፡ ዘትጸጊ ፡ ጽጌያተ ፡ ወትፈሪ ፡ ፍሬያተ ፡ ቢል ፡ ይቀናል ፤ በዚህ ፡ በገነት ፡ አትክልት ፡ ሰባት ፡ ነገር ፡ አለበት ፤ ጣዕም ፡ ልምላሜ ፤ ጽጌ ፤ ስን ፤ ፍሬ ፤ መዓዛ ፡ ቈዕል ፡ ነው ፤ በዚህም ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ሰባት ፡ ነገር ፡ አለበት ፤ አፍቅሮ ፡ ፀላዕት ፤ ትህትና ፤ ሃይማኖት ፤ ተስፋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ተአምኖ ፡ ኃጣውዕ ፡ ሥርየት ፡ ምጽዋት ፤ አፍቅሮ ፡ ፀላዕት ፡ አነ ፡ ዓቀብኩ ፡ ፍናወ ፡ ዕፁባተ ፡ መዝ ፡ ፲፯ ፡ ፬ ። ትኅትና ፡ አንሰ ፡ ዕፄ ፡ ወአከ ፡ ሰብእ ፡ መዝ ፡ ፳፩ ፡ ፯ ። ሃይማኖት ፡ እምከርሠ ፡ እምየ ፡ አንተ ፡ አምላኪየ ፡ መዝ ፡ ፳፩ ፡ ፲ ። ተስፋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እትአመን ፡ ከመ ፡ እርአይ ፡ ሠናይቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በብሔረ ፡ ሕያዋን ። መዝ ፡ ፳፮ ፡ ፲፫ ። ተአምኖ ፡ ኃጣውእ ፤ እስመ ፡ ኖኅ ፡ እምስዕርተ ፡ ርእስየ ፡ ጌጋይየ ። መዝ ፡ ፴፯ ፡ ፬ ። ሥርየት ፡ ሕፅበኒ ፡ ወእንጽሐኒ ፡ እምኃጢአትየ ። መዝ ፡ ፶ ፡ ፪ ። ምጽዋት ፡ ዘረወ ፡ ወወሀበ ፡ ለነዳይ ። ፻፲፩ ፡ ፰፱ ፡ ነው ። (ፍካሬ ፡ ዘጻድቃን ፡ ወዘኃጥአን) ፡ የጻ

ድቃንንና ፡ የኃጥአንን ፡ ግብር ፡ የሚ ናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ይሕ ፡ ነው ፤ እን ድም ፡ ጻድቃንን ፡ በለውዝ ፡ በገውዝ ፡ ኃጥአንን ፡ በዕፅ ፡ ከንቱ ፡ መስሎ ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ቀ ፡ ፫ ፡ ። ጳላድዮስ ፡ ቅዱስ ፡ ቄር ሎስን ፡ የመለኮትና ፡ የትስብእትን ፡ ነገር ፡ ጠይቆት ፡ መለኮትን ፡ በእሳት ፡ ትስብእትን ፡ በብረት ፡ መስሎ ፡ ቢነግረ ው ፡ ሠናየ ፡ ትፈክር ፡ እንዳለ ። እንድ ም ፡ የጻድቃንንና ፡ የኃጥአንን ፡ ግብር ፡ ለይቶ ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ወፈከረ ፡ ላቲ ፡ ለድንግል ፡ እን ዲል ፡ ለየላት ፡ ሲል ። (መዝሙር ፡ ዘዳዊት) ፡ ይኸውም ፡ የዳዊት ፡ መጽ ሐፍ ፡ ነው ። እንድም ፡ ዳዊት ፡ በበገ ና ፡ በገና ፡ እየደረደረ ፡ የተናገረው ። እንድም ፡ ዳዊት ፡ በመዝሙር ፡ የተ ናገረው ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ወኢያፀምዕ ፡ መዝሙረ ፡ መሰንቆከ ሙ ፡ እንዲል ።

# መዝሙር ፡ ፩ ።

፩ ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢሖረ ፡ በምክረ ፡ ረሲዓን ።

ከሥሩ ፡ እርእስት ፡ እንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በረሲዓን ፡ ምክር ፡ ፀንቶ ፡ ያልኖረ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፤ ለምንት ፡ የሐውር ፡ ወልደ ፡ ብእሲት ፡ ምስለ ፡ ብሉየ ፡ መዋዕል ፤ ዳዕሙ ፡ እስ ፡ አም ሠጡ ፡ የሐውሩ ፡ ባቲ ፡ እንዲል ። ረሲዓን ፡ የሚላቸው ፡ እንጨት ፡ ጠር በው ፡ ደንጊያ ፡ አለዝበው ፡ የሚያመ ልኩ ፡ ናቸው ። ዘፀ ፡ ፴፪ ፡ ፩ ። ዳን ፡ ፫ ፡ ፩ ።

ወዘኢቆመ ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ኃጥአን ።

ሖረን ፡ ከዚህ ፡ መተርጉም ፡ ነው ፤ በኃጥአን ፡ ጐዳና ፡ ያልሔደ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፤ (ሐ) ፡ ምነው ፡ ነቢይ ፡ ጐዳናን ፡ ከለከለ ፡ እንስሳት ፡ በሔዱበት ፡ አራዊት ፡ ጻድቃን ፡ በሔ ዱበት ፡ ኃጥአን ፡ ይሔዱ ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ በግብር ፡ ያልመሰለ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እንድም ፡ ጐዳናውን ፡ ቅሉ ፡ ከለከለ ፤ አብረው ፡ ከሔዱ ፡ ዘንድ ፡ ወንድሜ ፡ ወዴት ፡ ትሔዳለህ ፡ ይለዋል ፤ ልሰ ርቅ ፡ ልቀማ ፡ ይለዋል ፤ መስሎ ፡ ይሠ ራዋልና ፡ ስለዚህ ፡ ከለከለ ፤ ምሳ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ። ፲፮ ፡ ፱ ፡ ፲፱ ። ኃጥአን ፡ የሚላ ቸው ፡ ሠርቀው ፡ ቀምተው ፡ አሥ ረው ፡ ፈትተው ፡ ቋንጃ ፡ ቈርጠው ፡ ነፍስ ፡ ገድለው ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ።

ወዘኢነበረ ፡ ውስተ ፡ መንበረ ፡ መስተሳልቃን ።

በመስተሳልቃን ፡ አደባባይ ፡ ያልተ ቀመጠ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። ምነው ፡ ነቢይ ፡ አደባባይን ፡ ከለከለ ፤ በአደባባይ ፡ ክሉውስ ፡ በጉውስ ፡ ይቀ መጥበት ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፤ በግብር ፡ ያልመሰለ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እንድም ፡ አደባባይን ፡ ቅሉ ፡ ከለከለ ፤ አብሮ ፡ ከተቀመጠ ፡ ዘንድ ፡ በሐሰት ፡ ሲተች ሲፈርድ ፡ ያየዋል ፤ ዕገሌ ፡ ምን ፡ ሲሆ ን ፡ አየሁት ፡ ብሎ ፡ መስሎ ፡ ይሠራ ዋልና ። ዘፀ ፡ ፳፱ ፡ ፩—፫ ፡ ፩ነገ ፡ ፫—፱ ፡ ዮሐ ፯ — ፳፱ ። መስተሳልቃን ፡ የሚላቸ ው ፡ ዓይኑ ፡ በፈረጠ ፡ እጁ ፡ እግሩ ፡ በተቈ ረጠ ፡ የሚዘብቱ ፡ ናቸው ፤ እንድም ፡ አ ልቦ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ብለው ፡ በራ ሳቸው ፡ በሚዘብቱ ፡ በሰዱቃውያን ፡ አደባባይ ፡ ያልተቀመጠ ፡ ሰው ፡ ንዑ ድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። ዘፀ ፡ ፳፩ ፡ ፭ ። ግብ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ። ግብ ፡ ፳፫ ፡ ፯ - ፰ ። እንዲህ ፡ ባለው ፡ ረሲዕ ፡ ዘይዔብስ ፡ ላዕለ ፡ ርእሱ ፡ ኃጥዕ ፡ ዘይኤብስ ፡ ላዕለ ፡ እ ምላኩ ፤ መስተሳልቅ ፡ ዘይሣለቅ ፡ ላ ዕለ ፡ ነውረ ፡ ቢፁ ፤ የሚል ፡ አብነት ፡ ይገኛል ፤ ትርጓሜው ፡ እንድ ፡ ነው ።

፪ ፡ ዘዳዕሙ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥምረቱ ።

ዳዕሙ ፡ ዋዌ ፡ ነው ፤ ፈቃዱም ፡ ሕገ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ የሆነለት ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። ገብ ፡ ፲ ፡ ፴፭ ። እንድ ም ፡ ፈቃዱ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ የሆነለት ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡ ር ፡ ነው ፤ ዳዕሙ ፡ እሉን ፡ ዕሤይ ፡ ደቂ ቅከ ፡ እንዲል ። ፩ሳሙ ፡ ፲፯ ፡ ፲፩ ።

2014 04 17

አንድም ፡ ፈቃዱ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ የሆነለት ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዘሖረ ፡ ዘቆመ ፡ ዘነበረ ፡ ኢ ፡ ብፁዕ ፡ ሮሜ ፡ ፱-፲፱ ። ፯-፳፯ ።

ወዘሕጎ ፡ ያነብብ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ።

ሕጉንም ፡ በመዓልት ፡ በሌሊት ፡ የሚ መለከት ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ በመዓልት ፡ በብርሃን ፡ ፀሐይ ፡ ዓይኑ ፡ ሥጋውን ፡ ዕገዛን ፡ ሥጋውን ፡ ከንባ ቡ ፡ ዓይኑ ፡ ሕሊናውን ፡ ዕገዛን ፡ ሕሊና ውን ፡ ከምሥጢሩ ፡ በሌሊት ፡ በብር ሃን ፡ ማኅቶት ፡ ዓይኑ ፡ ሥጋውን ፡ ዕገዛ ኑ ፡ ሥጋውን ፡ ከንባቡ ። ዓይኑ ፡ ሕሊ ናውን ፡ ዕገዛን ፡ ሕሊናውን ፡ ከምሥ ጢሩ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ የሚመለከ ት ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ አገዘ ልፍኬ ፡ ኅበ ፡ አንብቦተ ፡ መጻሕፍት ፡ አምላካውያት ፡ ወትረ ፡ በጽማዌ ፡ እስ መ ፡ እማንቱ ፡ ይመርሃሁ ፡ ለልብከ ፡ ኅበ ፡ አንክሮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ል ዑል ፡ ዑቅ ፡ በእንተ ፡ አንብቦ ፡ ወም ህሮ ፡ ወዘልፈ ፡ ሀሉ ፡ ባቲ ፡ እንዲል ፡ ፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፮ ። ይህማ ፡ ለፍጡር ፡ እን ዴት ፡ ይመቻል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተጨ ልጦ ፡ ተገርኝቶ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊ ትም ፡ መገዛት ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ብሎ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ቀን ፡ ሲማ ረው ፡ መምሕር ፡ ሲያስተምረው ፡ የሚውለውን ፡ ሌሊት ፡ ግብር ፡ ገብ ቶ ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ ሌሊተ ፡ ዘይዜክር ፡ ወመዓልተ

ዘያነብብ ፡ እንዲል ፡ አንድም ፡ ሌሊ ት ፡ ሥረቅ ፡ ቀማ ፡ የሚል ፡ ሕሊና ፡ ቢነሣበት ፡ መጽሐፍ ፡ እንጂ ፡ እንዲ ህ ፡ ብሎኛል ፡ ያዋቂ ፡ አጥፊ ፡ እሆና ለሁን ፡ ብሎ ፡ ሰውነቱን ፡ ገሥፆ ፡ የሚ ኖር ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

፫ ፡ ወይከውን ፡ ከመ ፡ ዕፅ ፡ እንተ ፡ ትክልት ፡ ኅበ ፡ ሙሐዘ ፡ ማይ ፡ ዘፍ ፡ ፵፱ ፡ ፳፪ ።

እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በፈሳሽ ፡ ወሀ ፡ እንደተተከለች ፡ ዕፅ ፡ ይሆናል ፡ አ ንድ ፡ በፈሳሽ ፡ ወሀ ፡ እንደተተከለች ፡ ዕፅ ፡ የሆን ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

እንተ ፡ ትሁብ ፡ ፍሬሃ ፡ በበጊዜሃ ።

ፍሬዋን ፡ በየጊዜዋ ፡ ለባለቤቷ ፡ እን ደምታቀርጽ ፡ ዕፅ ፡ የሆን ፡ ሰው ፡ ንዑ ድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

ወቈጽላኒ ፡ ኢይትነገፍ ።

ቅፀሏ ፡ እንደማይረግፍ ፡ ዕፅ ፡ የሆን ፡ ሰው ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። አንድም ፡ ፍሬ ዋን ፡ በየጊዜዋ ፡ ለባለቤቷ ፡ እንደም ታቀርጽ ፡ ቅፀሏ ፡ እንደማይረግፍ ፡ ዕፅ ይሆናል ፤ ይህችም ፡ ዕፅ ፡ በሀገራቸው ፡ ለውገዝ ፡ ገውዝ ። በሀገራችን ፡ ሎሚ ፡ ትርንጎ ፡ ናት ። ለጊዜው ፡ ሲተክሏ ት ፡ ሲያርሟት ፡ ሲኰተኵቷት ፡ ታፅ ራለች ፡ ታግራለች ፤ ዕሮ ፡ ግሮ ፡ ከረ ሟት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የለመደችውን ፡ ምሳምሷን ፡ ካላስቀሩባት ፡ በሥራ ፡ ሁለቱ ፡ አውራኅ ፤ ከልምላሜ ፡ ከጽ ጌ ፡ ከፍሬ ፡ አትለይም ። አንድም ፡ ሰው



ነቱ ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠብቆለት ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ ዕፅ ፡ ሰውነቱ ፡ ሙሐ ዘማይ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍሬ ፡ ልጁ ፡ ቈፅል ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ አንድም ፡ (አሽጋሽገው) ፡ ፍሬ ፡ ልጁ ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ ቈፅል ፡ ወገኑ ፡ በረድ ኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠብቆለት ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ ልጁ ፡ ወገኑ ፡ የማይሞትበት ፡ አለና ፡ እንዲህን ፡ አለ ፡ ቢሉ ፤ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠብቆ ፡ ከኖረ ፡ ልጁ ወገኑ ፡ ያለጊዜው ፡ አይሞትበትም ፤ ገንዘቡ ፡ ያለጊዜው ፡ አይጠፋበትም ። ዘፍ ፡ ፭ ፡ ፭—፴፪ ። ሚዜ ፡ ፱ ።

አንድም ፡ ፍሬ ፡ ደጋጉ ፡ ገንዘብ ፡ ወ ርቁ ፡ ዕንቁ ፡ ፈረስ ፡ በቅሎው ፡ ላሙ ፡ በሬው ፤ ቈፅል ፡ ጥቃቅኑ ፡ ገንዘብ ፡ የልብስ ፡ ወገን ፡ ብስጡ ፡ ብስያጡ ፡ ምንጣፉ ። አንድም ፡ ፍሬ ፡ አሥራት ፡ በኵራት ፤ ቈፅል ፡ አስተናጸሐከ ፡ ግ በር ፡ እንዲል ፡ አጽርቶ ፡ የሚሰጥ ፤ አንድም ፡ ፍሬ ፡ አጽርቶ ፡ የሚሰጥ ፡ ቈፅል ፡ ዘእምፈቃድየ ፡ እሠውዕ ፡ ለከ እንዲል ፡ ከ፱ ፡ አንዱን ፡ የሚሰጥ ፡ መዝ ፡ ፶፫ ፡ ፮ ። አንድም ፡ ፍሬ ፡ ምግባሩ ፡ ቈፅል ፡ ሃይማኖቱ ፡ የፀናለት ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ አሚንሰ ፡ መ ሠረት ፡ ይእቲ ፡ ወከልዓኒሃ ፡ ሕንፃ ፡ ወ ንድቅ ፡ እሙንቱ ፡ እንዲል ።

አሁን ፡ ከቅጠል ፡ ፍሬ ፡ እንዲበልጥ ፡ ከሃይማኖት ፡ ምግባር ፡ ይበልጣል ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ በቅጠል ፡ መሠ ረትነት ፡ ፍሬ ፡ እንዲገኝ ፤ በሃይማኖ ትም ፡ መሠረትነት ፡ ምግባር ፡ ይሠ ራልና ፡ ሃይማኖትን ፡ በቅጠል ፡ ምግ ባርን ፡ በፍሬ ፡ መስሎ ፡ ተናገረ ፡ እን ዲህ ፡ የሚል ፡ ሔት ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ በኤ ርምያስ ፡ አስተጋብዑ ፡ እለ ፡ ያስተጋ ብዑ ፡ አልቦ ፡ እስከል ፡ ውስተ ፡ ዓጸደ ፡ ወይን ፡ ወአልቦ ፡ እንከ ፡ በለ ስ ፡ ውስተ ፡ ሰግላ ፤ ወቈፅሎኒ ፡ ተነ ግፈ ፤ ካስራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ ቭኤል ፡ ስንኳን ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖትም ፡ ጠፋ ብኋልና ። ኤር ፡ ፰ ፡ ፲፫ ። አንድም ፡ ወ ይከውን ፡ ዕፀ ፡ ከመ ፡ ዕፅ ፡ እንተ ፡ ትክ ልት ፡ ኅበ ፡ ሙሐዘ ፡ ማይ ፡ ሕጉ ፡ በ ሙሴ ፡ ልቡና ፡ ተጠብቃ ፡ እንዳለች ፡ እንደ ፡ ሕገ ፡ አሪት ፡ የሆነለት ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ እንተ ፡ ትሁብ ፡ ፍሬሃ ፡ ለሕጊቱ ፡ ቅፅል ፡ ነው ፡ ደጋጉ ፡ ተአምራት ፡ የማይቀርበት ፤ በረድ ፡ እሳት ፡ ይገዘነም ፡ ብላ ፡ የምታደርግ ፡ ዘፀ ፡ ፱ ፡ ፳፬ ። ወቈፅላኒ ፡ ጥቃቅኑን ፡ ተአምራት ፡ የምታደርግ ፤ ወሀውን ፡ ደም ፤ ደሙን ፡ ወሀ ፡ የምታደርግ ፡ ዘፀ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ። ሙሴኒ ፡ ሜጠ ፡ ለማ ይ ፡ እምከዊኑ ፡ ማይ ፡ ኅበ ፡ ከዊነ ፡ ደም ፤ ወእምከዊነ ፡ ደም ፡ ኅበ ፡ ከዊነ ፡ ማይ ፤ እንበለ ፡ ይትናገር ፡ በአፉሁ ፡ ዳዕሙ ፡ በሕሊናሁ ፡ እንዲል ።

ወኵሎ ፡ ዘገብረ ፡ ይፈጽም ።

የጀመረውን ፡ የሚፈጽም ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ መፈጸም ፡

2014 04 17

እንጂ ፡ መጀመር ፡ አያስመሰግንም ና ፡ እንድም ፡ እሱ ፡ የጀመረውን ፡ እግ ዚአብሔር ፡ የሚፈጽምለት ፡ ሰው ፡ ንውድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። ዠላኬ ፡ ፍድፋ ዴ ፡ እንተ ፡ ይገብራ ፡ ብእሲ ፡ ኢትት ፈጸም ፡ ዘእንበለ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ወዘእንበሌየሰ ፡ ኢትክሉ ፡ ገቢረ ፡ ወኢምንተኒ ፡ እንዲል ። እንድ ም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ዘወጠ ነ ፡ ይፌጽም ፡ ዘኃሠሠ ፡ ይረክብ ፡ ዘተመነየ ፡ ይገብር ፡ የጀመረውን ፡ ይጨርሳል ፡ የፈለገውን ፡ ያገኛል ፡ የተመኘውን ፡ ያደርጋል ።

፬ ፡ አኮ ፡ ከመዝ ፡ ኃጥአንሰ ፡ አኮ ፡ ከመዝ ።

እኮና ፡ እከ ፡ ከመዝና ፡ ከመዝ ፡ አን ድ ፡ ወገን ፡ ኃጥአንስ ፡ እንዲህ ፡ አይ ደሉም ።

ኣላ ፡ ከመ ፡ መሬት ፡ ዘይግሕፎ ፡ ነፋስ ፡ እም ገጸ ፡ ምድር ፡ ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፳ ።

ነፋስ ፡ ከምድር ፡ እንደሚጠርገው ፡ ትቢያ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ኅን ፡ ፪ ፡ ፴፭ ። እንድም ፡ አከ ፡ ከመዝ ፡ ወአከ ፡ ከ ማሁ ፡ ይላል ፡ ኃጥአንስ ፡ እንዲህ ፡ አይደሉም ፡ ምሳሌያቸውም ፡ እንደ ፡ ለውዝ ፡ እንደ ፡ ገውዝ ፡ አይደለም ። (ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ መሬት ፡ ዘይግሕፎ ፡ ነፋስ ፡ እምገጸ ፡ ምድር) ፡ ነፋስ ፡ ከምድ ር ፡ ነቅሎ ፡ እንደሚጥለው ፡ እንደ ፡ ዕፅ ፡ ከንቱ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዕፅ ፡ ከንቱን ፡ መሬት ፡ አላት ፡ በኋላ ፡ ግብሯ ። በነግህ ፡ ትበቅላለች ፡ በሠ ለስት ፡ ታብባለች ፡ በቀትር ፡ ታፈ ራለች ፡ በተሰዓት ፡ ትደርቃለች ፡ በ ሠርክ ፡ ኳኩርኳ ፡ ብላ ፡ ትወድቃ ለች ፤ ከዚህ ፡ ደረሰች ፡ አትባልም ፤ መዝ ፡ ፹፱ ፡ ፮ ። ይህም ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ በነግህ ፡ መብቀሏ ፡ ሰው ፡ የመወለ ዱ ፡ በሠለስት ፡ ማበቧ ፡ የማደጉ ፡ በቀትር ፡ ማፍራቷ ፡ ሚሽት ፡ አግብ ቶ ፡ ሕፃናት ፡ ወልዶ ፡ ቤት ፡ ንብረ ት ፡ አበጅቶ ፡ የመኖሩ ፡ በተሰዓት ፡ መ ድረቋ ፡ የማርጀቱ ፡ በሠርክ ፡ ተነ ቃቅላ ፡ ወድቃ ፡ ከዚህ ፡ ደረሰች ፡ አለመባሏ ፡ ሰው ፡ ሙቶ ፡ መቃብር ፡ ከወረደ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ደረሰ ፡ አይባል ምና ፡ የዚህ ፡ ምሳሌ ፡ ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ። ፲፫ ፡ ፴ ።

፭ ፡ ወበእንተዝ ፡ ኢይትነሥኡ ፡ ረሲዓን ፡ እም ደይን ።

ስለዚህ ፡ ኃጥአን ፡ ከመቃብር ፡ አይ ነሡም ። ኢይትነሥኡ ፡ ማለቱ ፡ ምሳ ሌያቸው ፡ እንደ ፡ ጻድቃን ፡ ምሳሌ ፡ ስለአልመሰለ ፡ አይደለም ። በሥራ ፡ ስለአልመሰሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በድ ለው ፡ በድለው ፡ ቢቀሩማ ፡ እፍሻን ፡ እንጂ ፡ አይደለ ፡ ዲና ፡ ዳንኤል ፡ ማ ለት ፡ ፍርድ ፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፡ ከ ቍርጽ ፡ ፍርድ ፡ አይድኑም ፡ ሲል ፡ ነው ። እንድም ፡ ትንሣኤያቸው ፡ ዘለ ኃሣር ፡ ስለሆነ ፡ ኢይትነሥኡ ፡ አለ ፡

ወኢኃጥአን ፡ ውስተ ፡ ምክረ ፡ ጻድቃን ።

ኃጥአንም ፡ ጻድቃን ፡ በመከሯቸው ፡ ምክር ፡ ፀንተው ፡ አይኖሩም ፤ እንድ



ም ፡ ጻድቃን ፡ ለራሳቸው ፡ ብለው ፡ በመ ከሩት ፡ ምክር ፡ ኃጥአን ፡ ፀንተው ፡ አይ ኖሩም ። አሁንስ ፡ ምን ፡ ገጥሟቸው ፡ የጻድቃን ፡ ምክር ፡ ፍቅር ፡ ትህት ና ፡ ጾም ፡ ጸሎት ፡ ሰጊድ ፡ ምጽዋ ት ፡ የኃጥአን ፡ ምክር ፡ ሠሪቅ ፡ ቀቲ ል ፡ ቋንጃ ፡ መቍረጥ ፡ ዝሙት ።

፮ ፡ እስመ ፡ የአምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍኖቶሙ ፡ ለጻድቃን ።

እግዚአብሔር ፡ የጻድቃንን ፡ ግብር ፡ ይወዳልና ። ወይከውን ፡ ከመ ፡ ዕፅ ፡ ላለው ፡ እእመርኩከ ፡ ሙሴ ፡ ወል ደ ፡ እንበረም ፡ እንዲል ።

ወፍኖቶሙሰ ፡ ለኃጥአን ፡ ትጠፍዕ ።

የኃጥአንን ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ አይወድ ምና ፡ እከ ፡ ከመዝ ፡ ኃጥአንሰ ፡ ላ ለው ። እንድም ፡ እስመ ፡ የአምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍኖቶሙ ፡ ለጻድቃ ን ። እግዚአብሔር ፡ የጻድቃንን ፡ ሥራ ፡ ይወዳልና ፡ ትሄሉ ፡ ትነብር ፡ ያለበት ፡ ነው ፤ ዋጋ ፡ በማሰጠት ፡ እ ብነት ፡ በመሆን ፡ ፀንታ ፡ ትኖራለች ፤ ወፍኖቶሙሰ ፡ ለኃጥአን ፡ ትጠፍዕ ፡ የኃጥአንን ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ አይወድ ምና ፡ ኢትሄሉ ፡ ኢትነብር ፡ ዋጋ ፡ በማሰጠት ፡ አብነት ፡ በመሆን ፡ ፀንታ ፡ አትኖርም ፡ ትጠፍዕ ፡ ማለት ፡ ከተፈ ተለ ፡ ገመድ ፡ ከተተከለ ፡ ግንድ ፡ ከ ተቈፈረ ፡ ጉድጓድ ፡ አድርሳቸው ፡ በፍዳ ፡ አትያዝም ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እ ሳት ፡ ገለባን ፡ ይዞት ፡ እንዲጠፋ ፡ ይ ዛቸው ፡ ትጠፋለች ፤ ፍኖት ፡ እኪት ፡ ወእግረ ፡ ኃጥእ ፡ ኀቡረ ፡ ይትኀጐ ሉ ፡ በዕለት ፡ እኪት ፡ እንዲል ፡ ተግ ፩ ፡ ፱ ። እንድም ፡ ወኢኃጥአን ፡ ው ስተ ፡ ምክረ ፡ ጻድቃን ፡ ቅድመ ፡ ዓ ለም ፡ ለጻድቃን ፡ ተብሎ ፡ በልበ ፡ ሥላሴ ፡ በተዘጋጀ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ኃጥአን ፡ ኢይኄልዉ ፡ እ ይኖሩም ። መንግሥተ ፡ ሰማያትሰ ፡ ድ ሉት ፡ ይእቲ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ለጻድቃን ፡ እንዲል ።

(እስመ ፡ የአምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍኖቶሙ ፡ ለጻድቃን) ፤ እግዚአብ ሔር ፡ የጻድቃን ፡ ተድላ ፡ ምግባራ ቸውን ፡ ይወዳልና ፤ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ለጻድቃን ፡ ባዘጋጃት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ኃጥአን ፡ አይኖሩም ። ትጠ ፍዕ ፡ ማንሻ ፡ እግዚአብሔር ፡ የጻድ ቃን ፡ ተድላ ፡ ምግባራቸውን ፡ ይወ ዳልና ፤ ወፍኖቶሙሰ ፡ ለኃጥአን ፡ ትጠፍዕ ፤ የኀጥአን ፡ ተድላ ፡ ምግባ ራቸው ፡ ትጠፋለች ።

መዝሙር ፡ ፪ ።

፩ ፡ ለምንት ፡ አንገለጉ ፡ አሕዛብ ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ከአሥሩ ፡ አርእስት ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እንደዚህም ፡ ያለው ፡ ደረቅ ፡ ሐዲስ ፡ ይባላል ፤ አራት ፡ ቤት ፡ ጭ ፍራ ፡ ሮማውያን ፡ ኄሮድስ ፡ ጲላጦ

2014 04 17

ስ ፡ ሐና ፡ ቀያፋ ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ በጠላትንት ፡ እንደ ፡ ተነሡበት ፡ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ እንደደረሰ ፡ ሆኖ ፡ ተገልጦለት ፡ አስቀድሞ ፡ ተናግሮታል ፡ አራት ፡ ቤት ፡ ጭፍራ ፡ ሮማውያን ፡ የመጡበት ፡ ግብራቸውን ፡ ተገብረው ፡ ይሔዱ ፡ ይመስል ፡ እንደ መሔድ ፡ ሁሉ ፡ ከመሄድ ፡ ወጥተው ፡ ይሔዱ ፡ የነበረ ፡ ለምን ፡ ተሰበሰቡ ፡ አንድም ፡ በመኑ ፡ አንገለጉ ፡ የተሰበሰቡ ፡ በማን ፡ ነው ፡ ግብ ፡ ፬ ፡ ፳፭ ። ሉቃ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ።

ወሕዝብኒ ፡ ነበቡ ፡ ከንቶ ።

እኒያስ ፡ የተነገረውን ፡ ትንቢት ፡ የተቈጠረውን ፡ ሱባዔ ፡ ባያውቁ ፡ ነው ፡ ትንቢት ፡ እንደተነገረ ፡ ሱባዔ ፡ እንደ ተቈጠረ ፡ የሚያውቁ ፡ ሕዝቡ ፡ ስቅሎ ፡ ስቅሎ ፡ ብለው ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ስለምን ፡ ተናገሩ ፡ ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፳፫ ። ማር ፡ ፲፭ ፡ ፲፫ ። ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፳፫ ።

ምነው ፡ ከንቱ ፡ አለ ፡ ከንቱ ፡ ማለት ፡ አስበውት ፡ ሳይሠሩት ፡ የቀረ ፡ ነው ፡ እኒህማ ፡ አድርገውት ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ እነሱ ፡ ሰቅለን ፡ ከገድለነው ፡ በኋላ ፡ በመቃብር ፡ ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ ይቀራል ፡ መስሏቸው ፡ ነበር ፡ ተነሥቶ ፡ ነገራቸው ፡ ፈርሶበቸዋልና ፡ አንድም ፡ የጌታ ፡ ሞት ፡ ከሣነቱ ፡ ላመኑበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ላላመኑበት ፡ ከንቱ ፡ ነውና ።

፪ ፡ ወተንሥኡ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር ።

ሕዝቡ ፡ ቢያጠፉ ፡ ነገሥታቱ ፡ ይሠሩ ፡ ይቀጹ ፡ ይመስል ፡ ለምን ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡ ። ምነው ፡ ነገሥት ፡ ብሎ ፡ አበዛ ፡ ንጉሡ ፡ አንድ ፡ ኄሮድስ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ መጽሐፍ ፡ ስም ፡ ከልጠራ ፡ ማብዛት ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ በተአምኖ ፡ አመ ፡ ነገርዎ ፡ ለኖኅ ፡ በእንተ ፡ ዘኢያስተርኢ ፡ ግብር ፡ ዘኀቡዕ ፡ ፈርሀ ፡ ወገብረ ፡ ንፍቀ ፡ ታቦት ፡ በዘያድኅን ፡ ቤቶ ፡ አመ ፡ ተኰነነ ፡ ዓለም ፡ ወኮነ ፡ ወራሲሃ ፡ ለጽድቀ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲል ፡ የነገረው ፡ አንዱ ፡ ሱርያል ፡ መልአክ ፡ ሲሆን ፡ ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፯ ። ወፈጸሙ ፡ አፈ ፡ አናብስት ፡ እንዲል ፡ የዘጋው ፡ አንድ ፡ ዳንኤል ፡ ሲሆን ፡ ዕብ ፡ ፲፩-፴፫ ። እየ ፡ ገበ ፡ ረገዙ ፡ ሐራሁ ፡ ለጲላጦስ ፡ እንዲል ፡ የወጋው ፡ አንድ ፡ ሐራዊ ፡ ሲሆን ።

ወብዕሲት ፡ አንቲ ፡ እንተ ፡ ተአምኒ ፡ ከመ ፡ ይኩውን ፡ ቃል ፡ ዘነገሩኪ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ፡ የነገራት ፡ አንድ ፡ ቅ/ገብርኤል ፡ ሲሆን ፡ ሉቃ ፡ ፩-፵፭ ። አንድም ፡ ስምዖንን ፡ ከሌዊ ፡ አስጠግቶ ፡ ክህናት ፡ ኀሉፋን ፡ ፍኖት ፡ ከበቱ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአሙ ፡ አመ ፡ ቀተልዋ ፡ ለሰቂማ ፡ እስመ ፡ ገብሩ ፡ ዓመፃ ፡ በቤተ ፡ ሸኤል ፡ እንዲል ።

ጲላጦስን ፡ ከኄሮድስ ፡ ደርበ ፡ አስጠግቶ ፡ ነገሥት ፡ ብሎ ፡ አበዛ ፡ ዘፍ ፡ ፵፱-፭-፯ ። አንድም ፡ ደቂቀ ፡ መንግሥት ፡ አሉና ፡ አንድም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የሚነሡ ፡ ነገሥታትን ፡ ሁሉ ፡ ሉቃ ፡ ፳፱-፪ ። ዮሐ ፡ ፲፩ ፡ ፵፯ ።

ወመላእክትኒ ፡ ተጋብኡ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኅቡረ ።

ኅቡረ ፡ ምስለ ፡ ነገሥት ፡ ነው ፡ ሕዝቡ ፡ ነገሥታቱ ፡ ቢያጠፉ ፡ ካህናቱ ፡ ይመክሩ ፡ ያስተምሩ ፡ ይመስል ፡ ለምን ፡ ተሰበሰቡ ፡ ምነው ፡ ካህናት ፡ ብሎ ፡ አበዛ ፡ አንድ ፡ ቀያፋ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ ሐተታ ፡ እንዳለፈው ፡ (ብለህ ፡) ስምዖንን ፡ ከሌዊ ፡ አስጠግቶ ፡ እንደተናገረ ፡ ሐናን ፡ ከቀያፋ ፡ ደርበ ፡ ተናገረ ፡ ዮሐ ፡ ፲፰-፴፯

ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወላዕለ ፡ መሢሑ ።

በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ በኔ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወልድስ ፡ ይሁን ፡ ሰቅለው ፡ ገድለውታል ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ምን ብለው ፡ ተነሡ ፡ ቢሉ ፡ ወልድ ፡ ቢነከ ፡ አብ ፡ ይነከ ፡ እንዲሉ ፡ ወልድን ፡ መስቀል ፡ መግደል ፡ አብን ፡ መስቀል ፡ መግደል ፡ ሆኖባቸዋልና ፡ ባያገኙት ፡ ቀርቶባቸዋል ፡ እንጂ ። አንድም ፡ አብ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ብሎ ፡ የመሰከረለት ፡ ወልድን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ማለት ፡ አብን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ ዘዳ ፡ ፲፰ ፡ ፲፭-፲፱ ። ኢሳ ፡ ፵፪ ፡ ፩ ። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ። ፲፯ ፡ ፭ ። ፪ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ።

፫ ፡ ንበትክ ፡ እምኔነ ፡ ማዕሠሪሆሙ ።

የምዕመናን ፡ ሕጋቸውን ፡ ከኛ ፡ እናጥፋ ፡ ይላሉ ፡ አይሁድ ። አንድም ፡ ማዕሠሪነ ፡ ማዕሠር ፡ ሕጋችንን ፡ አይሁድ ፡ ከኛ ፡ እናርቅ ፡ ብለው ፡ ተሰበሰቡ ፡ ይላሉ ፡ ምዕመናን ።

ወንገድፍ ፡ እምላዕሌነ ፡ አርዑቶሙ ።

የምዕመናን ፡ ሕጋቸው ፡ አርዑትን ፡ ከኛ ፡ እናርቅ ፡ እናጥፋ ፡ ይላሉ ፡ አይሁድ ። አንድም ፡ አርዑቱን ፡ አርዑት ፡ ሕጋችንን ፡ ከኛ ፡ እናርቅ ፡ እናጥፋ ፡ ብለው ፡ አይሁድ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ይላሉ ፡ ምዕመናን ፡ ኤር ፡ ፭-፭ ። ሕግን ፡ ማዕሠር ፡ አላት ፡ የሺህ ፡ ፍልጥ ፡ ማሠሪያው ፡ ልጥ ፡ እንዲሉ ፡ ልጥ ፡ ብዙውን ፡ ፍልጥ ፡ አንድ ፡ እንዲያደርግ ፡ ሕግም ፡ ሕዝብንና ፡ አሕዛብን ፡ አንድ ፡ ታደርጋለችና ፡ አርዑትም ፡ አላት ፡ ቀንበር ፡ ሁለቱን ፡ በሮች ፡ አንድ ፡ እንድታደርግ ፡ ሕግም ፡ ሕዝብና ፡ አሕዛብን ፡ አንድ ፡ ታደርጋለችና ፡ አንድም ፡ ቀንበር ፡ ወይፈኑን ፡ ከባት ፡ በሬ ፡ ጋር ፡ እንድታስተካክል ፡ ሕግም ፡ ውሉድን ፡ ከአበው ፡ ጋራ ፡ ታስተካክላለችና ፡ ኤር ፡ ፭-፭ ። አንድም ፡ ተስእሎ ፡ እምነቢይ ፡ ወተሠጥዎ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይላል ፡ በአርእስቱ ፡ ነቢይ ፡ ይጠይቃል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመልሳል ፡ (ለምንት ፡ አንገለጉ ፡ አሕዛብ) ፡ አራት ፡ ቤት ፡ ጭፍራ ፡ ሮማውያን ፡ የመጡበት ፡ ግብራቸውን ፡ ተገብረው ፡ ይሄዱ ፡ ይመስል ፡ ለምን ፡ ተሰበሰቡ ፡ (ወሕዝብኒ ፡ ነበቡ ፡ ከንቶ) ፡ እኒያስ ፡ የተነገረውን ፡



2014 04 17

ትንቢት ፡ የተቈጠረውን ፡ ሱባዔ ፡ ባያ
ውቁ ፡ ነው ፤ ትንቢት ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡
ሱባዔ ፡ እንደተቈጠረ ፡ የሚያውቁ ፡
ሕዝቡ ፡ ስቅሎ ፡ ስቅሎ ፡ ብለው ፡ ከን
ቱ ፡ ነገርን ፡ ለምን ፡ ተናገሩ ፡ (፪ ፡
ወተንሥኡ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር) ፡ ሕዝ
ቡ ፡ አሕዛቡ ፡ ቢያጠፉ ፡ ነገሥታቱ ፡
ይሠሩ ፡ ይቀጡ ፡ ይመስል ፡ ለምን ፡
በጠላትነት ፡ ተነሡ ፤ (ወመላእክትኒ ፡
ተጋብኡ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኅቡረ) ፡ ነገ
ሥታቱ ፡ ሕዝቡ ፡ አሕዛቡ ፡ ቢያጠፉ ፡
ካህናቱ ፡ ይመክሩ ፡ ያስተምሩ ፡ ይመ
ስል ፡ ለምን ፡ ተሰበሰቡ ፡ ብሎ ፡ ነቢ
ይ ፡ ይጠይቃል ፡ ሉቃ ፡ ፳፡፲፱ ። ተሠጥ
ወ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወይቤ ፡ (ላዕለ ፡
እግዚአብሔር ፡ ወላዕለ ፡ መሢሑ) ፡
በኔ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅ
ዱስና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡
ነዋ ፡ ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመ
ልሳል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡
ተነሥተዋል ፡ እንጂ ፡ በእግዚአብሔ
ር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምን ፡ ብለው ፡
ተነሥተዋል ፡ ቢሉ ፡ ቃል ፡ ልብ ፡ የሌ
ለው ፡ እስትንፋስ ፡ የለም ፣ ቃሉ ፡ ወ
ልድን ፡ መግደል ፤ እስትንፋሱ ፡ መ
ፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መግደል ፡ ሆኖባቸ
ዋልና ፤ ባያገኙት ፡ ቀርቶባቸዋል ፡
እንጂ ፤ አንድም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ ወርዶ ፡ ለወልድ ፡
ከመሰከረለት ፡ በኋላ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡
ማለት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ የሩቅ ፡
ብእሲ ፡ ሕይወት ፡ ማለት ፡ ነውና ፤

ማቴ ፡ ፫፡፲፯ ። ማር ፡ ፩፡፲ ። ሉቃ ፡ ፫፡፳፪ ።
ዮሐ ፡ ፩፡፴፪ ።

(ንበትክ ፡ እምኔነ ፡ ማዕሠሪሆሙ) ፡
ማዕሠር ፡ ተዋሕዷችነን ፡ ከኛ ፡ እና
ርቅ ፡ ብለው ፤ (ወንገድፍ ፡ እምላዕሌነ ፡
አርዑቶሙ) ፡ አርዑተ ፡ ተዋህዷች
ነን ፡ ከኛ ፡ እናርቅ ፡ ብለው ፡ ተዋህ
ዶን ፡ አርዑት ፡ አላት ፡ ቀንበር ፡
ከበሬ ፡ ጫንቃ ፡ ላይ ፡ ሆና ፡ በሬውን ፡
ን ፡ ስታስጨንቀው ፡ እንድትውል ፡
የሥላሴም ፡ ባህርይ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
እንመርምር ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ስታስጨ
ንቀው ፡ ትኖራለችና ፤ ከዚህም ፡ የተ
ነሣ ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ንእመን ፡
ዘእንበለ ፡ ተኃሥሦ ፡ ብለዋል ፤ ንብ
ትክ ፡ ንግድፍ ፡ የሚል ፡ አብነት ፡
ይገኛል ፡ ትርጓሜው ፡ አንድ ፡ ነው ።

፬ ፤ ዘይነብር ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ይስሕቆሙ ።

በሰማይ ፡ ያለ ፡ መልአኩ ፡ ይስቅብ
ቸዋል ።

ወእግዚአብሔር ፡ ይሳለቅ ፡ ላዕሌሆሙ ።

እግዚአብሔርም ፡ ይዘብትባቸዋል ።
አሁን ፡ በመልአኩ ፡ በጌታ ፡ ሰሐት ፡
ሥላቅ ፡ ኑሮ ፡ አይደለም ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ይፈርድባቸዋል ፤ መልአ
ኩም ፡ ታዞ ፡ ያጠፋቸዋልና ፤ እንዲ
ህ ፡ አለ ፤ አንድም ፡ (ዘይነብር ፡) እግ
ዚአብሔር ፡ አብ ፤ (ወእግዚአብሔር ፡)
እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ነገራቸውን ፡
እንደ ፡ ዋዛ ፡ ያይባቸዋል ።



፭ ፤ ሶበ ፡ ይነብሎሙ ፡ በመዓቱ ፡ ወበመዓቱ ፡ የሀውኮሙ ።

ድኅረ ፡ ይነብሎሙ ፡ በመዓቱ ፤ በመዓቱ ፡
የሀውኮሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የገነፈለ ፡
ዋዌ ፡ ነው ። ባርባ ፡ ዘመን ፡ በጥጦስ ፡
ከፈረደባቸው ፡ በኋላ ፡ በምጽአት ፡
በነፍስ ፡ ይፈረድባቸዋል ፤ አንድም ፡
(ሶበ ፡ ይነብሎሙ) ፡ በአርባ ፡ ዘመን ፡ በጥ
ጦስ ፡ በፈረደባቸው ፡ ጊዜ ፤ (ወበመ
ዓቱ ፡ የሀውኮሙ) ፤ በምጽአትም ፡ በነ
ፍስ ፡ በፈረደባቸው ፡ ጊዜ ፤ (ዘይነብር ፡
ውስተ ፡ ሰማይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስ
ሕቆሙ ፡ ወይሳለቅ ፡ ላዕሌሆሙ) ፤ በል
ዕልና ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነገራቸ
ውን ፡ እንደዋዛ ፡ ያይባቸዋል ።

፮ ፤ አንስ ፡ ተሠየምኩ ፡ ንጉሠ ፡ በላዕሌሆሙ ፡
በጽዮን ፡ በደብረ ፡ መቅደሱ ።

እነሱ ፡ ባያውቁ ፡ ሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወልደ ፡
ዮሴፍ ፡ ይሉኛል ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ በ
ማኅፀነ ፡ ማርያም ፡ ነግሸለሁ ፤ ወእ
ሙንቱ ፡ ትምህርተ ፡ ሢመት ፡ ወመ
ንግሥት ፡ እንዲል ፡ ዳን ፡ ፱ ፡ ፳፭-፳፯ ።
ራዕ ፡ ፫-፲፱ ። በና ፡ በ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡
በጌኖን ፡ በቅሩብ ፡ ሳሌም ፡ እንዳለው ፡
ያለ ፡ ነው ። ጽዮን ፡ አላት ፡ እመቤ
ታችንን ፡ ፀወነ ፡ ሥጋ ፤ ፀወነ ፡ ነፍስ ፡
ፀወነ ፡ ጻድቃን ፡ ወኃጥአን ፡ ናትና ፤
ደብረ ፡ መቅደስም ፡ አላት ፡ ዘጠኝ ፡
ወር ፡ ከምስት ፡ ቀን ፡ ማኅፀኗን ፡ ዓለ
ም ፡ አድርጎ ፡ ተመስግኖባታልና ።
ድንግል ፡ አጽንነት ፡ ርእሳ ፡ መንገለ ፡
ከርሣ ፡ እንዲል ፡ መላእክት ፡ ሲያመ

ሰግኑ ፡ ትሰማ ፡ ነበር ፡ ዮሐ ፡ ፩፡፶፬ ።

፯ ፤ ከመ ፡ እንግር ፡ ትእዛዞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔር ፡ ሕጉ ፡ ወንጌልን ፡
አስተምር ፡ ዘንድ ፤ እግዚአብሔር ፡
የሦስቱ ፡ ስም ፡ ነው ፤ እንሰ ፡ ሶበ ፡ እቤ ፡
እግዚአብሔር ፡ እብል ፡ በኢንተ ፡ አብ ፡
ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡
በ፩ ፡ ስም ፡ ሥሉስ ፡ ያምልኩ ፡ እን
ዲል ፤ ሕጊቱም ፡ የ፫ቱ ፡ ናት ። የእግ
ዚአብሔር ፡ አብ ፡ እንደሆነች ፡ ሲያ
ጠይቅ ፡ ትምህርትየሰ ፡ ኢኮነት ፡ እን
ቲአየ ፡ አላ ፡ እንቲአሁ ፡ ለዘፈነወኒ ፡
አብ ፡ ይላል ፡ ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፲፮ ። የእግዚአ
ብሔር ፡ ወልድ ፡ እንደሆነች ፡ ሲያ
ጠይቅ ፡ እንሰ ፡ እብለከሙ ፡ ብሎ ፡
አስተምሯል ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፪-፵፰ ። የእግ
ዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ
ሆነች ፡ ሲያጠይቅ ፡ ወበገዙ ፡ ሕዝብ ፡
በትምህርተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይላ
ል ። አንድም ፡ (፮ ፡ አንሰ ፡ ተሠየምኩ ፡
ንጉሠ ፡ በላዕሌሆሙ) ፡ እነሱ ፡ ባያ
ውቁ ፡ አልብነ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእንበለ ፡
ቄሣር ፡ ይሉኛል ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ የአ
ብርሃም ፡ ዕፃ ፡ በምትሆን ፡ ደብረ ፡
መቅደሱ ፡ በተሠራችባት ፡ በኢየሩ
ሳሌም ፡ ነግሸለሁ ፡ ምነው ፡ የጌታ ፡
መንግሥቱ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ብቻ ፡
ነውና ፡ እንዲህን ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ የጌታ ፡
መንግሥቱ ፡ መታመኑ ፡ ነው ፡ ትም
ህርት ፡ ተአምራት ፡ ሠርቶ ፡ አስቀ
ድሞ ፡ በመቶ ፡ ኻያ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የታ

2014 04 17

መነበት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ነውና ፡
ማቴ ፡ ፩ ፡ ፳፭ ። ማር ፡ ፫ ፡ ፮-፲ ። ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ።
ኢሳ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።

፯ ፡ ከመ ፡ እንግር ፡ ትእዛዞ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ኢሳ ፡ ፳፭ ፡ ፩-፪ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፶ ።

እነ ፡ ወእብ ፡ ፩ ፡ ንሕነ ፡ ብየ ፡ የእግዚአብሔርነቱን ፡ ነገር ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፴ ። እንድም ፡ (እንተሥንጉ ፡ በላ ፡ በጽ ፡ በደ ፡ መቅ) ፡ እነሱ ፡ ባያውቁ ፡ ሰቅለን ፡ ገደልነው ፡ በኋላ ፡ ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ ይቀራል ፡ ይሉኛል ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ በመስቀል ፡ ነግሻለሁ ። መስቀልን ፡ መንግሥት ፡ አለው ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ስለተሠራበት ፡ መስቀል ፡ ኃይልነ ፡ መስቀል ፡ ፅንፅነ ፡ መስቀል ፡ ቤዛነ ፡ እንዲል ። ደብረ ፡ መቅደሱ ፡ አለው ፡ ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ መላእክት ፡ በቀትር ፡ እየመጡ ፡ ያመሰግኑ ፡ ነበር ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ቢመጡ ፡ ተሰቅሎ ፡ አግኝተውት ፡ በመስቀሉ ፡ ዙሪያ ፡ እንደ ፡ ሻሽ ፡ ተነጥፈው ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ረግፈው ፡ እንደ ፡ ግንድ ፡ ተረብርበው ፡ ለከ ፡ ኃይል ፡ ለከ ፡ ዕንዕ ፡ እያሉ ፡ አመስግነውታልና ። ወቀፈ.ፀ ፡ እምላዕሉ ፡ ምክዳነ ፡ ወርእየ ፡ ኃይላተ ፡ ሰማይ ፡ ድንጉፃነ ፡ በዓውደ ፡ መስቀሉ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲል ፡ መቅ ፡ ወን ፡ ፱ ፡ (ከመ ፡ እንግር ፡ ትእዛዞ ፡ ለእግዚአብሐር) ፡ የጌትነቱን ፡ ነገር ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ፡ ጽንዐ ፡ እስመ ፡ እነ ፡ ምዕከዎ ፡ ለዓለም ፡ ብየ ፡ ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፴፫ ።

እግዚአብሔር ፡ ይቤለኒ ፡ ወልድየ ፡ አንተ ።

አሁን ፡ አንተን ፡ አይሻም ፡ (ቃል ፡ ይቤ ፡ በል) ። ቅድመ ፡ ዓለም ፡ አካል ፡ ዘእምአካል ፡ ባሀርይ ፡ ዘእምባሀርይ ፡ የወለድኩህ ፡ ልጄ ፡ ነህ ፡ አለኝ ፡ ሉቃ ፡ ፰ ፡ ፲፬ ። ግብ ፡ ፲፫ ፡ ፴፫ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፭ ።

ወአነ ፡ ዮም ፡ ወለድኩከ ፡ መዝ ፡ ፹፯-፲፰ ።

አሁንም ፡ እነን ፡ አይሻም ፡ ዛሬም ፡ በተዋሀዶ ፡ የወለድኩህ ፡ ልጄ ፡ ነህ ፡ አለኝ ፡ ተውህበ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ስም ፡ በሥጋ ፡ ዘበሀላዌሁ ፡ ይሰመይ ፡ እንዲል ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ እንግድነት ።

እንድም ፡ ሥጋ ፡ ይቤ ፡ አንተ ፡ ሥጋ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ አካል ፡ ዘእምአካል ፡ ባሕርይ ፡ ዘእምባሀርይ ፡ የወለድኩህ ፡ ልጄ ፡ ነህ ፡ አለኝ ። አንተ ፡ ልጄ ፡ ነህ ፡ ዛሬም ፡ በተዋሀዶ ፡ ወለድኩህ ፡ ማለት ፡ በቃል ፡ ርስት ፡ አንድም ፡ አሁንም ፡ አንተንና ፡ እነን ፡ አይሻም ፡ (ሥግው ፡ ቃል ፡ ይቤ) ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ አካል ፡ ዘእምአካል ፡ ባሀርይ ፡ ዘእምባሀርይ ፡ የወለድኩህ ፡ ልጄ ፡ ነህ ፡ አለኝ ፡ ዛሬም ፡ አውፃእኩከ ፡ አንሣእኩከ ፡ ሲል ፡ ነው ። በትንሣኤ ፡ የወለድኩህ ፡ ልጄ ፡ ነህ ፡ አለኝ ፡ ሉቃ ፡ ፳፱ ፡ ፵፱ ። አሁን ፡ ሁለተኛ ፡ የሚወልደው ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ፡ በምሳሌ ፡ ተናገረው ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ዘምቶ ፡ ያረጃል ፡ በልቶ ፡ ያፈጃል ፡ ሕገ ፡ ብን ፡ ሰብስቦ ፡ ልጁን ፡ አስጠርቶ ፡



ልጄ ፡ ዘምቶ ፡ ያረጀ ፡ በልቶ ፡ ያፈጀ ፡ ይሉሃል ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ በርስቴ ፡ ውጣበት ፡ ውረድበት ፡ ብሎ ፡ ይሰጠዋል ፡ እሱም ፡ ወጣሁ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ፈላሁ ፡ ጠጅ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ እግሩን ፡ ለጠጠር ፡ ደረቱን ፡ ለጦር ፡ ሰጥቶ ፡ ይዘምታል ፡ በርስቱ ፡ ርስት ፡ በጉልቱ ፡ ጉልት ፡ ጨምሮበት ፡ ይመጣል ፡ አባቴ ፡ በሰጠኸኝ ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡ ጨምሬበት ፡ መጣሁ ፡ ይለዋል ፡ እርሱም ፡ ቀድሞም ፡ ልጄ ፡ ዛሬም ፡ ልጄ ፡ ይልቅስ ፡ የዛሬው ፡ ይብለጥ ፡ ይለዋል ፡ ጌታም ፡ ከአቤል ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ዓርብ ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ፃዑ ፡ ወእለ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ተከሥቱ ፡ ወርእዩ ፡ ብርሃነ ፡ ዐቢየ ፡ ብሎ ፡ በገነት ፡ አድርጎ ፡ ባረገ ፡ ጊዜ ፡ ልጄ ፡ ነህ ፡ አለው ፡ እንጂ ፡ መላ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ።

፰ ፡ ሰአል ፡ እምኔየ ፡ እሁበከ ፡ አሕዛበ ፡ ለርስትከ ፡ ራዕ ፡ ፪ ፡ ፳፰ ።

ለምነኝና ፡ አሕዛብን ፡ እሰጥሃለሁ ፡ አንድም ፡ እሰጥሃለሁና ፡ ለምነኝ ፡ (ለርስትከ) ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡ ሊሆኑህ ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡ ልትሆናቸው ፡ ማደሪያ ፡ ሊሆኑህ ፡ ማደሪያ ፡ ልትሆናቸው ፡ ሰአል ፡ ማለቱ ፡ ከተዋሀዶ ፡ በኋላ ፡ ልመና ፡ ኑሮበት ፡ አይደለም ፡ ልመና ፡ ይስማማው ፡ የነበረ ፡ ሥጋን ፡ እንደተዋሀደ ፡ ለማጠየቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ። እኮ ፡ ኢያእሚሮ ፡ ኀቡእተ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ መከነ ፡ ለጥንተ ፡ ትስብእቱ ፡ ዘኢየአምር ፡ ኀቡዓተ ፡ እንዲል ። ራዕ ፡ ፪ ፡ ፳፯ ።

ወምኵናኒከኒ ፡ እስከ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ።

ጌትነትህስ ፡ በአራት ፡ ማዕዘን ፡ ምሉ ፡ ነው ፡ ከዚህም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የእምላክነቱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሰውነቱን ፡ ነገር ፡ ይናገራል ፡ ሰአል ፡ ብሎ ፡ የሰውነቱን ፡ ወምኵናኒከኒ ፡ ብሎ ፡ የአምላክነቱን ፡ ነቢይ ፡ ባወቀ ፡ ከአድማስ ፡ እስከ ፡ አድማስ ፡ ነው ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ያለውን ፡ ግን ፡ ባለቤቱ ፡ ባወቀ ፡ ተናግሮታል ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፯ ። ዳን ፡ ፱ ፡ ፫ ። መዝ ፡ ፸፱ ፡ ፲፫ ።

፱ ፡ ወትርዕዮሙ ፡ በበትረ ፡ ሐጺን ።

ደጋጎቹን ፡ በጽኑ ፡ ሥልጣን ፡ ትጠብቃቸዋለህ ፡ ራዕ ፡ ፲፪ ፡ ፭ ። ፲፱ ፡ ፲፱-፳ ። ፲፱ ፡ ፲፭ ።

ወከመ ፡ ንዋየ ፡ ለብሐ ፡ ትቀጠቅጦሙ ።

ክፎችን ፡ ግን ፡ በጽኑ ፡ ሥልጣን ፡ ታጠፋቸዋለህ ፡ በግሥ ፡ ተናገረው ፡ ጠርሙዝ ፡ በሎታ ፡ የሚባል ፡ የብረት ፡ ዘንግ ፡ አለ ፡ ከንጉሥ ፡ ራስጌ ፡ ይሰቀላል ፡ በዚያ ፡ ጠላቱን ፡ ይበቀልበታል ፡ ወዳጁን ፡ ይጠብቅበታል ፡ ጌታም ፡ በሥልጣኑ ፡ ወዳጆቹን ፡ ይጠብቅበታል ፡ ጠላቶቹን ፡ ይበቀልበታልና ፡ አንድም ፡ ትሔድሶሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ሠሪ ፡ ያች ፡ ሠርታ ፡ ስትጨርስ ፡ ነቅዕ ፡ ያገኘችበት ፡ እንደሆነ ፡ እንደገና ፡ ከስክሳ ፡ አፍር

2014 04 17

ላ ፡ ታድሰዋለች ፡ ከራቱ ፡ ባህርያት ፡ የተፈጠረ ፡ ሰው ፡ ደካማ ፡ ነውና ፤ ደ ካሞ ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠራ ፡ በንስሓ ፡ ታድሰዋለህ ፡ ሲል ፡ ነው ።

፲ ፡ ወይእዜኒ ፡ ነገሥት ፡ ለብዉ ።

ወተንሥኡ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ቍ ፡ ፪ ። አሁንም ፡ ሄሮድስ ፡ ጲላጦስ ፡ እወቁ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ፤ አስ ተውሉ ፤ ክርስቶስን ፡ የባህርይ ፡ አም ላክ ፤ ወንጌልን ፡ ፍጽምት ፡ ሕግ ፡ በሉ ፤ ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌል ን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ አትበሉ ፤ አንድም ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የምትነሡ ፡ ነገሥታ ት ፡ ለብዉ ።

ወተገሠፁ ፡ ኵልክሙ ፡ እለ ፡ ትኴንንዋ ፡ ለምድር ።

ወመላእክትኒ ፡ ተጋብኡ ፡ ምስሌሆ ሙ ፡ ኅቡረ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፤ ቍ ፪ ። ዘምድረ ፡ ለብሰ ፡ እንዲል ፡ የሰውን ፡ ልቡና ፡ በትምሕርት ፡ እናንፃለን ፤ ሰ ውነቱን ፡ በሹመት ፡ እንገዛለን ፤ የም ትሉ ፡ ሐና ፡ ቀያፋ ፡ አንድም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የምትነሡ ፡ ካህናት ፡ እወቁ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ፤ አስተውሉ ።

፲፩ ፡ ተቀነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሃት ።

ወሕዝብኒ ፡ ነበቡ ፡ ከንቶ ፡ ብሎ ፡ ነበ ሩና ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመፍ ራት ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ ተገዙ ። ወተ ኃሠዩ ፡ ሎቱ ፡ በረዓድ ። ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ። አንድም ፡ በመገዛታችሁ ፡ ደስ ፡ ይበ ላችሁ ፤ ዋጋ ፡ ያለበት ፡ ነውና ፤ ደስ ሳይሰኙ ፡ መገዛት ፡ ዋጋ ፡ አያሰጥምና እንደ ፡ አፄ ፡ በከፋ ፡ ሰይፍ ፡ ጨንገሩ ፡ አንድም ፡ (ተቀነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ፡ እንዘ ፡ ትትኃ ሠዩ) ፡ ደስ ፡ እያላችሁ ፡ በፍርሃት ፡ በረዓድ ፡ ተገዙ ፤ ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፳፰ ። ፩ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ።

፲፪ ፡ አፅንዕዋ ፡ ለጥበብ ፡ ከመ ፡ ኢይትመዓዕ ፡ እግዚአብሔር ።

ጽፈት ፡ ድጉሰት ፡ እርሻ ፡ ቀፋሮን ፡ አዕንታችሁ ፡ ያዙ ፤ ጽፋችሁ ፡ ደጉሳ ችሁ ፤ አርሳችሁ ፡ ቈፍራችሁ ፡ ብሉ ፤ ብላቸው ፡ አይሆንም ፡ አሉ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረሀብ ፡ እንዳይፈር ድባችሁ ።

ወኢትትኃጐሉ ፡ እምፍኖተ ፡ ጽድቅ ።

ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከ ፡ ካለውም ፤ እንዳትወጡ ፡ ሁኑ ፤ ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ። አን ድም ፡ (አጽንዕዋ ፡ ለጥበብ ፡ ) ኢታ ምልክን ፡ ጠብቁ ፤ (ወኢትትኃጐሉ ፡ እምፍኖተ ፡ ጽድቅ) ፡ ከዘጠኙ ፡ ሕግ ጋትም ፡ እንዳትወጡ ፡ ሁኑ ። (ከመ ፡ ኢይትመዓዕ ፡ እግዚአብሔር) ፡ አሠ ርቱ ፡ ቃላትን ፡ ብሠራላቸው ፡ አንጠ ብቅም ፡ አሉ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳይፈርድባችሁ ። ዘፀ ፡ ፳ ፡ ፩ - ፲፯ ። አንድም ፡ (አጽንዕዋ ፡ ለጥበብ) ፡ ወን ጌልን ፡ ጠብቁ ፤ ወኢትትኃጐሉ) ፡ ከ አሪትም ፡ እንዳትወጡ ፡ ሁኑ ፤ (ከመ ፡ ኢይትመዓዕ) ፡ ወንጌልን ፡ አሪትን ፡ ብ ሠራላቸው ፡ አንጠብቅም ፡ አሉ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳይፈርድባችሁ ፤ አንድም ፡ (አጽንዕዋ ፡ ለጥበብ) ፡ ጥ



በብ ፡ ወልድን ፡ እመኑበት ። ጥበብ ፡ ሐነፀት ፡ ላቲ ፡ ቤተ ፡ ወዓቀመት ፡ ፯ ፡ አዕማደ ፡ ምሳ ፡ ፱ - ፩ ። ጥበብ ፡ ትዌ ድስ ፡ ርእሳ ፡ ሲራ ፡ ፳፱ ፡ ፩ ። እንዲል ፤ (ከመ ፡ ኢይትመዓዕ) ፡ ልጁን ፡ በሥ ጋ ፡ ብሰድላቸው ፡ አላመኑም ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳይፈርድባችሁ ፤ (ወኢትትኃጐሉ) ፡ ከዓለመ ፡ መንግ ሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንዳትወጡ ፡ ሁኑ ።

ሶበ ፡ ነደት ፡ ፍጡነ ፡ መዓቱ ፡ ዘላ ፡ ፩ ፡ ፳፱ ። ኢሳ ፡ ፴፫ ፡ ፲፱ ። ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፳፱ ።

መዓቱ ፡ ፈጥና ፡ በተደረገች ፡ ጊዜ ፡ ኢትትኃጐሉ ፡ በል ፤ ብፁዓን ፡ ማን ሻ ፡ አንድም ፡ ባርባ ፡ ዘመን ፡ መዓቱ ፡ ፈጥና ፡ በተደረገች ፡ ጊዜ ።

ብፁዓን ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ተወከሉ ፡ ቦቱ ።

ያመኑበት ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራ ን ፡ ናቸው ። ኢሳ ፡ ፴ ፡ ፲፰ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ያመነ ፡ አለና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፤ ሰብአ ፡ ረበዋትን ፡ ነው ፤ ኤጲ ስ ፡ ቆጶሳቸው ፡ ስምዖን ፡ ይባላል ፤ ጥጦስ ፡ መጣ ፡ በተባለ ፡ ጊዜ ፡ እነር ሱን ፡ ይዞ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻግሮ ፡ ሄዷ ል ፤ ኋላም ፡ ጥጦስ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ አፍርሶ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ እነሱን ፡ ይዞ ፡ ገብቷልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። አንድም ፡ መዓቱ ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ ፈጥና ፡ በ ተደረገች ፡ ጊዜ ፡ ያመኑበት ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ። ፈያታ ዊ ፡ ዘየማንን ፡ ሲያይ ። ተዘከረኒ ፡ እግ ዚኦ ፡ በውስተ ፡ መንግሥትከ ፡ ሲል ፡ ውሏልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፵፪ ። ነህ ፡ ፲፫ ፡ ፴፩ ።

አንድም ፡ ምጽአቱ ፡ ፈጥና ፡ በደረሰ ች ፡ ጊዜ ፡ ያመኑበት ፡ ሰዎች ፡ ንዑ ዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፤ ያን ፡ ጊዜስ ፡ ያመኑት ፡ እምነት ፡ አይረባም ፤ አይ ጠቅምም ፡ ብሎ ፡ አስቀድመው ፡ ሃይ ማኖት ፡ ምግባር ፡ ይዘው ፡ የተገኙት ን ፡ ሲያይ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፡ ስንኳን ፡ እሮ ፡ ከነ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ብ ለው ፡ ያምኑበታል ፤ አይረባቸውም ፡ አይጠቅማቸውም እንጂ ፡ እሮኑ ፡ ር እይ ፡ ታመጽእ ፡ አሚነ ፡ እንዲል ።

## መዝሙር ፡ ፫ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ ሚ ፡ በዝኁ ፡ እለ ፡ ይሣቅዩኒ ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ፡ ነው ፤ በአ ቤሴሎም ፡ ጊዜ ፡ ስለራሱ ፡ ተናግሮ ታል ፤ ከሥሩ ፡ አርእስት ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ይህስ ፡ እንደምን ፡ ነው ፤ ቢሉ ፤ ለዳዊት ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ነበ ሩት ፡ አምኖን ፤ አቤሴሎም ፤ ትዕማ ር ፡ የሚባሉ ፡ አምኖንን ፡ ከአኪናሆ ም ፡ ኢይዝራኤላዊት ፡ ወልዶታል ፤ ባባት ፡ እንጂ ፡ በእናት ፡ አይገናኙም ፤ ፪ሳሙ ፡ ፫ ፡ ፪ ። አቤሴሎምና ፡ ትዕማር ን ፡ ከመአክ ፡ ወለተ ፡ ቶልሜልም ፡

2014 04 17

ንጉሥ ፣ ጌድሶር ፣ ወልዶአቸዋል ፤ በ በትም ፣ በናትም ፣ ይገናኛሉ ። ፪ሳሙ ፣ ፫ ፣ ፫ ። ፩ዜና ፣ ፫ ፣ ፪ ።

ሰይጣን ፣ ከልጠፋ ፣ ነገር ፣ አምኖን ፣ በእኅቱ ፣ በትዕማር ፣ ፍቅር ፣ አሳድሮ በት ፣ ስትገባ ፣ ጡቷን ፣ ደረቷን ፣ ስት ወጣ ፣ ተረከዟን ፣ ባቷን ፣ እያየ ፣ በ ሐፀ ፣ ዝሙት ፣ ተነደፈ ። ፪ሳሙ ፣ ፲፫ ፣ ፩ ፣ ፪ ። ኢዮናዳብ ፣ የሚባል ፣ ፈላስ ፋ ፣ ሥጋዊ ፣ ጥበብ ፣ የተገለፀለት ፣ ለሱ ፣ አጐቱ ፣ ለዳዊት ፣ የወንድሙ ፣ ልጅ ፣ ነው ። ፪ሳሙ ፣ ፲፫ ፣ ፫ ። ፩ዜና ፣ ፪ ፣ ፲፫ ። ከሱ ፣ ዘንድ ፣ ዕለት ፣ ዕለት ፣ ይገሰግሳ ል ፣ ምንት ፣ ያደገድገከ ፣ እንዘ ፣ ወል ደ ፣ ንጉሥ ፣ አንተ ፣ ምን ፣ ያከሣሃል ፣ የነገሥታት ፣ ልጆች ፣ የሰባ ፣ አርደው የፀሩ ፣ አውርደው ፣ በልተው ፣ ጠጥ ተው ፣ ለስልሰው ፣ ቀልተው ፣ ይታ ያሉ ፣ አንተን ፣ ምን ፣ ያከሣሃል ፣ አለ ው ፣ ወያደገድጎ ፣ ከመ ፣ ላሕመ ፣ ሊባ ኖስ ፣ መዝ ፣ ፳፰ ፣ ፯ ። ለእመ ፣ ርእየክሙ ንጉሥ ፣ ድግዱጋኒክሙ ፣ ይኬንኒ ፣ ርእስየ ፣ እንዲል ፣ ዳን ፣ ፩ ፣ ፲ ። ዳግመኛ ፣ የነገሥታት ፣ ልጆች ፣ ደርበው ፣ ደራ ርበው ፣ ለብሰው ፣ ሞቅ ፣ ሲልላቸው ይወጣሉ ፣ አንተስ ፣ የንጉሥ ፣ ልጅ ፣ አይደለህምን ፣ ይህን ፣ ሁሉ ፣ ትተህ ፣ ለምን ፣ ትማልዳለህ ፣ አለው ፣ ዘበደ ገዲግ ፣ ይርሥቅ ፣ ክከብ ፣ እንዲል ፣ እንዲህ ፣ አይደለም ፣ ብፈራህ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ምክር ፣ ብትመፀውተኝ ፣ ብዬ ፣ ነው ፣ አለው ፤

ንገረኝ ፣ አለው ፤ አከኑ ፣ አፈቅራ ፣ ለ ትዕማር ፣ እኅተ ፣ አቤሴሎም ፣ የአቤ ሴሎምን ፣ እኅት ፣ ትዕማርን ፣ ወድጃ ት ፣ እንጂ ፣ ነው ፣ አለው ፣ የገዛ ፣ እኅ ቱን ፣ ያራቅሁ ፣ መስሎት ፣ እኅተ ፣ አ ቤሴሎም ፣ አለ ፣ እሱም ፣ ከፉ ፣ ነውና ፣ ልምከረው ፣ ልገሥፀው ፣ ሳይል ። ተደወይ ፣ ታመምኩ ፣ ብለህ ፣ ተኛ ፣ አባትህ ፣ ዳዊት ፣ ልጁን ፣ ወዳድ ፣ ነው ና ፣ ሊጠይቅህ ፣ መጥቶ ፣ እህል ፣ ቅመ ስ ፣ ሲልህ ፣ አይሆንም ፣ በለው ፣ ግድ ፣ ይልሃል ፣ ማን ፣ ያቀረበውን ፣ እበላለ ሁ ፣ በእኅቱ ፣ በትእማር ፣ እጅ ፣ ቢሆ ን ፣ አራት ፣ አምስት ፣ አምባሻም ፣ በበ ላሁ ፣ ነበር ፣ በለው ፣ ብሎታል ፤ ወጉ ጉዓ ፣ እስከ ፣ ይደዊ ፣ ታመምኩ ፣ ብሎ እስኪተኛ ፣ ቸኩለ ፣ ወተጠወቀ ፣ በፍ ቅረ ፣ ትዕማር ፣ እኅቱ ፣ በእኅቱ ፣ በት ዕማር ፣ ፍቅር ፣ ተጨንቋልና ፤ ፪ሳሙ ፣ ፲፫ ፣ ፩—፮ ።

ዳዊትም ፣ ሊጠይቀው ፣ መጥቶ ፣ እህ ል ፣ ቅመስ ፣ አለው ፣ ማን ፣ ያቀረበው ን ፣ እበላለሁ ፣ በእኅቴ ፣ በትዕማር ፣ እጅ ፣ ቢሆን ፣ አራት ፣ አምስት ፣ አም ባሻም ፣ በበላሁ ፣ (ነበር) ፣ ብሎታል ፣ እኅትህማ ፣ ለዚህ ፣ ከልሆንችህ ፣ ለም ን ፣ ትሆንሃለች ፣ ብሎ ፣ ሂዶ ፣ አንቺ ፣ ወንድምሽ ፣ ታሟልና ፣ እህል ፣ አቅ ምሺው ፣ አላት ፣ ከደናግለ ፣ ሺኤል ፣ መፃፃ ፣ አይታጣምና ፣ ወሎስቶ ፣ ይላ ል ፣ ከዶቂቱ ፣ አዋሃደችው ፣ ብረት ፣ ምጣድ ፣ እስክትጥድ ፣ ድረስ ፣ ኩፈፍ ፣



ፈካ ፣ አለ ፤ ወአብዓቶ ፣ ውስተ ፣ ጤ ገን ፤ ከኑብረት ፣ ምጣዱ ፤ እንድም ፣ ትኩሱን ፣ አብዓቶ ፣ ማለት ፣ አዳራሽ ፣ ነው ፣ ያሉ ፣ እንደሆነ ፤ ወደ ፣ እልፍኝ ፣ እልፍኝ ፣ ነው ፣ ያሉ ፣ እንደሆነ ፤ መጋ ረጃውን ፣ ገልጠሽ ፣ ዘፋኑን ፣ ተረግ ጠሽ ፣ አግቢው ፣ አላት ፣ አገባችው ፣ ምንስ ፣ ብታመም ፣ የንጉሥ ፣ ልጅ ፣ አይደለሁምን ፣ ሰው ፣ ይመለስልኝ ፣ አለ ፤ ከዚህ ፣ በኋላ ፣ አሁን ፣ እኔ ፣ አ ምኖን ፣ እህል ፣ የሚጋብዘኝ ፣ አጥቼ ፣ ነውን ፣ አንችን ፣ ብዬ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ብሎ ፣ እህሉን ፣ ትቶ ፣ ተራምዶ ፣ እ ሷን ፣ ያዛት ፤ እሷም ፣ አ ፣ እኁየ ፣ ኢ ትግበሮ ፣ ለዝ ፤ ወንድሜ ፣ ሆይ ፣ እን ዲህ ፣ ያለውን ፣ ሥራ ፣ አትሥራው ፣ እ ኔን ፣ ዕዕልት ፣ እምንዕሳ ፣ ታሰኘኛለህ ፤ አንተም ፣ የንጉሥ ፣ ልጅ ፣ መባልህ ፣ ቀርቶ ፣ ዓብድ ፣ እምወራዙት ፤ ከሰነ ፎች ፣ አንዱ ፣ ተብለህ ፣ ትቈጠራለህ ፣ ዘሌ ፣ ፳ ፣ ፲፯ ። ባይሆንም ፣ ላባታችን ፣ ንገረውና ፣ ያደርግልሃል ፣ አለችው ፤ አሁን ፣ ዳዊትን ፣ ያህል ፣ ሰው ፣ ሴት ፣ ልጁን ፣ ለወንድ ፣ ልጁ ፣ የሚድር ፣ ሆኖ አይደለም ፣ ለጊዜው ፣ እንዲህ ፣ ብዬ ፣ አመልጣለሁ ፤ ኋላ ፣ ግን ፣ የነገሥታ ት ፣ ልጆች ፣ ባዳራሽ ፣ ገብተው ፣ ዕል ፍኝ ፣ ተከትተው ፣ በዘበኛ ፣ ተጠብ ቀው ፣ ነውና ፣ የሚኖሩት ፣ እያገኘኝ ም ፣ ብላ ፣ ነው ፤ ምንም ፣ ቢሆን ፣ ሴት ፣ ናትና ፣ እድከማ ፣ ወእልሐማ ፤ ይላል ፣ ግድ ፣ ብሎ ፣ ከክብር ፣ አሳነሳት ፣ ዘሌ ፣ ፲፰

፲፭ ። ፪ሳሙ ፣ ፲፫ ፣ ፯—፲፬ ፣ ሰይጣን ፣ ያስጀ መረውን ፣ ነገር ፣ እያስፈጽምምና ፣ ወ ዐብየ ፣ ዕልዕ ፣ እንተ ፣ ፀልዓ ፣ ድኅረ ፣ እምቀዳሚ ፣ ፍቅር ፣ ዘአፍቀራ ፣ ቀድ ሞ ፣ ከወደዳት ፣ መውደድ ፣ ይልቅ ፣ ኋላ ፣ የጠላት ፣ መጥላት ፣ ፀና ። ው ጪልኝ ፣ አላት ፤ ዛቲ ፣ ድኅሪታ ፣ ተ እኪ ፣ እምቀዳሚታ ፣ ከቀድሞ ፣ ከፋ ትህ ፣ ይልቅ ፣ የአሁኑ ፣ ይብለጥ ፣ ፀ ሐይ ፣ ለፀሐይ ፣ ስሄድ ፣ በደም ፣ ሽታ ፣ አማቂት ፣ ይግደላት ፣ ብለኸኝ ፣ ነው ን ? አለችው ፣ በረኛውን ፣ ጠርቶ ፣ ይህችን ፣ የጠገበች ፣ ጋለሞታ ፣ አስ ወጣ ፣ አለው ፤ እያጋፋ ፣ እያዳፋ ፣ አስወጥቶ ፣ በሩን ፣ መለሰባት ፤ ደና ግለ ፣ ሺኤል ፣ ወይዛዝረ ፣ ሺኤል ፣ ከ ፍሬ ፣ አልደረሰንም ፣ ሲሉ ፤ ወርቅ ፣ እንደአበባ ፣ የፈነዳበት ፣ ነጭ ፣ ሐር ፣ ለብሰው ፣ ይታያሉ ፤ ከፍሬ ፣ ደርሰና ል ፣ ሲሉ ፤ ገልብጠው ፣ ለብሰው ፣ ይታ ያሉ ፤ በዚያ ፣ ልማድ ፣ ገልብጣ ፣ ለብ ሳ ፣ ትቢያ ፣ ነስንሳ ፣ ከንድና ፣ ከንዷ ን ፣ ከራሷ ፣ ላይ ፣ አድርጋ ፣ እያለቀ ሰች ፣ ስትሄድ ፣ አቤሴሎም ፣ አገኛት ፤ አምኖን ፣ እኅኪ ፣ ሰከበ ፣ ምስሌኪ ፤ ከንቺ ፣ ጋራ ፣ የተገናኘ ፣ ወንምድሽ ፣ አምኖን ፣ ነውን ፣ አላት ፤ እወ ፣ እግ ዚእየ ፣ ኢተስሕተከ ፣ ኢለየማን ፣ ወ ኢለፀጋም ፤ አዎን ፣ ጌታዬ ፣ ቀኝም ፣ ግራም ፣ አላልህም ፣ አለችው ። አከኑ ፣ እኅኪ ፣ ኢትክሥቲ ፣ ቦቱ ። ወንድ ምሽ ፣ አይደለምን ፣ አትግለጪበት ፤

በዚያውም ፡ ላይ ፡ ዛሬስ ፡ የዳዊት ፡ ልጆች ፡ ጠገቡና ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ይሠራሉ ፡ ሆን ፡ እንዳይሉን ፤ ሑሬ ፡ ቤተ ፡ አቡኪ ፡ ወንበሪ ፡ መበለተኪ ፤ ከባትሽ ፡ ቤት ፡ ሂደሽ ፡ ተቀመጪ ፡ አላት ፤ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አቡኪ ፡ ማለቱ ፤ ዳዊት ፡ ለልጆቹ ፡ ይሆናል ፡ እያለ ፡ በከተማው ፡ ሁሉ ፡ ቤት ፡ አሠርቶ ፡ ነበርና ። ፪ሳሙ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ፡ ፳ ።

ኢነበበ ፡ ኢሠናየ ፡ ወኢእኩየ ፤ ክፉም ፡ ሆነ ፡ በጎ ፡ ሳይነጋገሩ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ይኖራሉ ፤ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ በሱ ፡ ተጀምሮአል ፡ በሸኤልምቢሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ሲላጩ ፡ በግ ፡ ሲያሸልቱ ፡ ብዙ ፡ ድግስ ፡ ደግሰው ፡ ነው ፤ በዚያ ፡ ልማድ ፡ ድግስ ፡ ደግሶ ፤ አባቱ ፡ በጎቼን ፡ አስሸልታለሁና ፡ ከቤቴ ፡ ግባልኝ ፡ አለው ፤ አስቀድሞ ፡ ነግረኸኝ ፡ ቢሆን ፡ በዳጌው ፡ ዳጌ ፤ በፍሪዳው ፡ ፍሪዳ ፡ በተጨመረበት ፡ ነበር ፤ አሁንማ ፡ እኔ ፡ ስመጣ ፡ የወንድ ፡ መኳንንት ፤ የሴት ፡ ወይዛዝር ፡ ይከተሉኛል ፡ ማዕደ ፡ ጠባብ ፡ ተብለህ ፡ ትነቀፍ ፡ የለምን ፤ ኢዮአብ ፡ ይሂድልህ ፡ አለው ፤ ኢዮአብማ ፡ ምንስ ፡ የንጉሥ ፡ ቢትወደድ ፡ ንጉሥ ፡ ቢሆን ፡ ባዕድ ፡ አይደለምን ፡ ታላቅ ፡ ወንድም ፡ ያባት ፡ ያህል ፡ ነውና ፡ አምኖን ፡ ይሂድልኝ ፡ አለው ፤ የተዘነጋውን ፡ አስታውሰለሁን ፡ ብሎ ፡ ይሂድልህ ፡ አለው ፤ አቤሴሎምም ፡ ብላቴኖቹን ፡ ይመክራቸዋል ፤ እምከመ ፡ ሰክረ ፡ ልበ ፡ ለአምኖን ፡ በልዎ ፡ ወኢትምህክዎ ፡ ብሂለክሙ ፡ ወልደ ፡ ንጉሥ ። እስመ ፡ አነሂ ፡ ዘእኤዝዘክሙ ፡ ወልደ ፡ ንጉሥ ፡ አነ ፤ እምከመ ፡ ሰክረ ፡ ልቡ ፡ ለአምኖን ፡ ኩኑ ፡ ዕደወ ፡ ኃይል ፡ ይላል ። ተበልቶ ፡ ሲጠጣ ፡ ጋሻ ፡ ጓታ ፡ አንሡ ፤ አምኖን ፡ ልበ ፡ ቀላል ፡ ነውና ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፡ ይላልና ፤ በዘገር ፡ ልብ ራሱን ፡ በሉት ፤ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ አትፍሩ ፤ እማዝዛችሁ ፡ እኔም ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ነኝና ፡ አላቸው ፤ የሰባ ፡ አርዶ ፤ የፀሩ ፡ አውርዶ ፡ ተበልቶ ፡ ሲጠጣ ፡ ጋሻ ፡ ጓታ ፡ አንሡ ፡ አምኖን ፡ እኒያን ፡ ብላቴኖች ፡ ፈጅዋቸው ፡ መሰለኝ ፡ ብሎ ፡ እሄዳለሁ ፡ ሲል ፡ አንዱ ፡ ከመድረክ ፡ ተጠግቶ ፡ ቆይቶ ፡ ልብ ፡ ራሱን ፡ ብሎ ፡ ገድሎታል ፤ ፪ሳሙ ፡ ፲፫ ፡ ፳፰ - ፳፱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቤሴሎም ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ጌድሶር ፡ ኰበለለ ፤ ዳዊት ፡ ከሰገነት ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ይመለከት ፡ ነበረና ፤ ከዚያ ፡ ብላቴና ፡ ደጅ ፡ ፀብ ፡ ተነሣ ፡ አለ ። ኢዮናዳብ ፡ በነገሩ ፡ ያለ ፡ ነውና ፤ ነገር ፡ አዋቂ ፡ ገምጋሚ ፡ ይበሉኝ ፡ ብሎ ፡ ዛሬ ፡ ከአምኖን ፡ በቀር ፡ የሚጎዳ ፡ የለም ፡ አለ ፤ ይህን ፡ ሲነጋገሩ ፡ ልጅህ ፡ አምኖን ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፤ ልጄ ፡ አምኖን ፡ ልጄ ፡ አምኖን ፡ እያለ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመር ፡ ፪ሳሙ ፡ ፲፫ ፡ ፴-፴፮ ።



ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው ፡ ያለ ፡ እየተወሳ ፡ የሞተ ፡ እየተረሳ ፡ ይሄዳልና ፡ ዳዊት ፡ ያ ፡ ብላቴና ፡ ሥርዓተ ፡ መንግሥት ፡ ያውቅ ፡ ነበረ ፡ ሲወጣ ፡ ሲገባ ፡ ሲታጠቅ ፡ ሲፈታ ፡ ያምር ፡ ነበር ፡ እያለ ፡ አቤሴሎምን ፡ ያነሣሣው ፡ ጀመር ፡ ኢዮአብም ፡ ለካ ፡ ጌታዬ ፡ ሐፍረቱን ፡ የሚከላለት ፡ አጥቶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የልጁን ፡ ዕርቅ ፡ ወዷል ፡ ብሎ ፡ ቴቁሄ ፡ ሂዶ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ያስነሣል ፤ ቴቁሄ ፡ የፈረስ ፡ የበቅሎ ፡ የአዝማሪ ፡ የዘፋኝ ፡ ያልቃሽ ፡ አገር ፡ ናት ፤ እንዳሙስ ፡ ወንገሀ ፡ እንደ ፡ ዳውንት ፡ ራስሽን ፡ ተላጭተሽ ፡ ፊትሽን ፡ ነጭተሽ ፡ ልብስሽን ፡ ቀደሽ ፡ በደባባይ ፡ እየዞርሽ ፡ ግጥም ፡ እየገጠምሽ ፡ አልቅሺ ፡ ጩዋሂ ፡ ጠባቂው ፡ ንገሪኝ ፡ ልንገርልሽ ፡ ይልሻል ፡ እኔስ ፡ የምነግረው ፡ ለንጉሡ ፡ ነው ፡ በዪው ፤ ቀርበሽ ፡ ተናገሪ ፡ ይልሻል ፡ ቀርበሽ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ከሁለት ፡ ሰው ፡ የወለድኳቸው ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ነበሩኝ ፡ ቀን ፡ ጥሏቸው ፡ ሰይጣን ፡ አነሳስቷቸው ፡ ከመንገድ ፡ ተጣልተው ፡ ታናሹ ፡ ልጄ ፡ ታላቁ ፡ ልጄን ፡ ገደለው ፡ የታላቁ ፡ ዘመዶች ፡ የቂም ፡ ወራሺ ፡ የሙት ፡ አልቃሺ ፡ ያልሁትን ፡ እንጨርስብሽ ፡ አሉኝ ፡ በይው ፡ ያልተረዳልሽ ፡ እንደሆነ ፡ በደባባይ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ የምትናገረው ፡ ነገር ፡ የአምኖንንና ፡ የአቤሴሎምን ፡ ነገር ፡ ይመስላል ፡ ይላል ፡ በይው ፡ አላት ። እሷም ፡ እንደነገራት ፡ ራሷን ፡ ተላጭታ ፡ ፊቷን ፡ ነጭታ ፡ የኀዘን ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ በደባባይ ፡ እየዞረች ፡ ግጥም ፡ እየገጠመች ፡ ስታለቅስ ፡ ጪሂ ፡ ጠባቂው ፡ ንገሪኝ ፡ ልንገርልሽ ፡ አላት ፡ እኔስ ፡ የምነግረው ፡ ለንጉሡ ፡ ነው ፡ አለችው ፤ ቀርበሽ ፡ ተናገሪ ፡ አላት ፤ ቀርባ ፡ ንጉሥ ፡ ፍርድ ፡ ልበስ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ነበሩኝ ፡ ታናሹ ፡ ልጄ ፡ ታላቁ ፡ ልጄን ፡ ገደለው ፤ የታላቁ ፡ ልጄ ፡ ዘመዶች ፡ የቂም ፡ ወራሺ ፡ የሙት ፡ አልቃሺ ፡ ያልኩትን ፡ እንጨርስብሽ ፡ አሉኝ ፡ አለችው ፤ አምጽኢዮ ፡ ዝየ ፤ እንዳይገድሉብሽ ፡ ወደኔ ፡ አምጪው ፡ አላት ፤ አንድም ፡ አስገድላለሁ ፡ ያለውን ፡ ደመኛ ፡ ተማጥነሽ ፡ አምጪው ፡ አላት ፤ አንድም ፡ የቂጣ ፡ አነጋገር ፡ እንዲህ ፡ የሚአደርግ ፡ ዳኛ ፡ ማነው ፡ ተማጥነሽ ፡ ወደኔ ፡ አምጪው ፡ አላት ፤ ነገሯን ፡ ባይረዳላት ፡ ወደቀደመ ፡ ግብሯ ፡ ትመለሳለች ፡ በደባባይ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ የምትናገረው ፡ ነገር ፡ የአምኖንንና ፡ የአቤሴሎምን ፡ ነገር ፡ ይመስላል ፡ ይላል ፡ አለችው ፡ ለጊዜው ፡ ከዚህም ፡ ደርሳለችን ፡ ብሎ ፡ ተቈጣ ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ሀሎኑ ፡ እዴሁ ፡ ለኢዮአብ ፡ በኵ ፡ ነገርኪ ፤ በዚህ ፡ በነገርሽ ፡ ኢዮአብ ፡ ገብቶበታልን ፡ አላት ፤ አወን ፡ ጌታዬ ፡ አንተ ፡ እውነተኛ ፡ ንጉሥ ፡ ነህ ፡ እሱ ፡ ቢል

2014 04 17

ከኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያለዚያማ ፡ ለኔ ፡
ለሴቲቱ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጥበብ ፡ እን
ደምን ፡ ተገለጸልኝ ፡ አለችው ። ፪ ፡
ሳሙ ፡ ፲፱-፭-፰ ። ኢዮአብን ፡ አስጠር
ቶ ፡ የዚህን ፡ የብላቴና ፡ ዕርቅ ፡ ወደ
ሀልን ፡ አለው ፤ አወን ፡ ጌታዬ ፡ እን
ግዴህ ፡ ወዲህ ፡ እኛ ፡ እያነስን ፡ እየ
ደከምን ፡ እንሄዳለን ፡ እንጂ ፡ እየበ
ዛን ፡ እየበረታን ፡ እንሄዳለንን ፤ አለ
ው ። ምሬልሀለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አደ
ባባይ ፡ አይግባ ፡ ፍርድ ፡ አይስማ ፡
ፊቴን ፡ አይይ ፡ ብሎታል ። አስታር
ቂሀለሁና ፡ ከከተማ ፡ ግባ ፡ ብሎ ፡
ይልከበታል ፡ አቤሴሎም ፡ ኢዮአ
ብን ፡ መጥቶ ፡ ሳይጠይቀው ፡ ቀረ ፤
ምንስ ፡ የንጉሥ ፡ ቢትወደድ ፡ ንጉሥ ፡
ቢሆን ፡ እኔስ ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ንጉ
ሥ ፡ አይደለሁምን ፡ ብሎ ፡ ኢዮአ
ብም ፡ አቤሴሎምን ፡ ሄዶ ፡ ሳይጠይቀ
ው ፡ ቀረ ፤ ምንስ ፡ ንጉሥ ፡ የንጉሥ ፡
ልጅ ፡ ቢሆን ፡ እኔስ ፡ የንጉሥ ፡ ቢት
ወደድ ፡ ንጉሥ ፡ አይደለሁምን ፡
ብሎ ፡ አቤሴሎምም ፡ ብላቴናቹን ፡
ባጠገባችን ፡ ኢዮአብን ፡ የምንገዳ
በት ፡ ገንዘብ ፡ የለውምን ፡ አላቸው ፤
ሀለወቶ ፡ አሐቲ ፡ ገራህተ ፡ ሰገም ፡
በጥቃ ፡ ገራኅትነ ፤ በርሻችን ፡ አጠ
ገብ ፡ አንዲት ፡ የገብስ ፡ ሁዳድ ፡ አለ
ችው ፡ አሉት ። ሂዳችሁ ፡ አቃጥሏት ፡
አላቸው ፤ አቃጠሏት ፡ የገንዘብ ፡ ዓ
ይኑ ፡ ጥቁር ፡ ነውና ፤ እየተገለፈለፈ ፡
መጥቶ ፡ ምነው ፡ ጌታዬ ፡ ወርቅ ፡ ላበደ
ረ ፡ ጠጠር ፡ እህል ፡ ላበደረ ፡ አፈር ፡ እ
ንዲሉ ፡ የበጎ ፡ ወረታ ፡ ክፉት ፡ መለስ
ህልኝ ፡ አለው ፤ አቤሴሎምም ፡ ይህ
ስ ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፡ ነው ፤ በአንድ ፡
ሁለት ፡ በጥሬ ፡ ዱቄት ፡ በጊደር ፡ ጥ
ገት ፡ ይመለስልሃል ፡ ይልቅስ ፡ አንተ ፡
በኔ ፡ በብላቴኖቼ ፡ የቀን ፡ ሐሩር ፡
የሌሊት ፡ ቍር ፡ እየወረደብን ፡ ምነ
ው ፡ ዝም ፡ ማለትህ ፡ የዚያ ፡ የዚያማ ፡
በናቴ ፡ ሀገር ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ተብ
ዬ ፡ ከብሬ ፡ መኖር ፡ አይሻለኝም ፡
ኖሯልን ፡ አስታርቂሃለሁ ፡ ብለህ ፡ አ
ስመጥተህ ፡ ባደባባይ ፡ ላልቀመጥ ፡
ፍርድ ፡ ላልሰማ ፡ የአባቴን ፡ ፊት ፡
ላላይ ፡ ነውን ፡ አለው ፤ እውነትህ ፡
እንጂ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሄዶ ፤ ንጉሥ ፡
ከታጠቡ ፡ ከክንድ ፡ ከታረቁ ፡ ከሆ
ድ ፡ እንዲሉ ፤ ታርቀንሃል ፡ ብለን ፡
አስመጥተን ፡ ፍርድ ፡ አይስማ ፡ እን
ላለንን ፡ ፈጽመህ ፡ ታረቅልኝ ፡ አለ
ው ፡ ምሬልሀለሁ ፡ አለው ፤ ረከበ ፡
ሞገስ ፡ ገብርከ ፡ በቅድሜከ ፡ በቤትህ ፡
እንጀራ ፡ መቍረስ ፡ ከጀመርኩ ፡ እን
ደዛሬ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ አያውቅም ፡
አለው ፤ ዳዊት ፡ ልጅ ፡ ይወዳልና ፡
አቤሴሎም ፡ መጥቶ ፡ ጫማውን ፡ ሲ
ስም ፡ እሱም ፡ ራሱን ፡ ስሞታል ።
፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፱-፳፭-፴፫ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አ
ቤሴሎም ፡ አሥር ፡ ሠረገላ ፡ አምሳ ፡
ትርት ። አደረገ ፡ በከተማው ፡ ቆርባ ፡
ቆርባ ፡ ይል ፡ ጀመረ ፤ ላሥራ ፡ ሁ
ለቱ ፡ ነገደ ፡ ሺኤል ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡



በር ፡ አላቸው ። ሕዝ ፡ ፵፰-፴-፴፭ ። ራእ ፡
፳፩-፲-፳፩ ። አንድ ፡ ወር ፡ ካንዱ ፡ በር ፡
አንድ ፡ ወር ፡ ካንዱ ፡ በር ፡ እየሄደ ፡
አንተ ፡ አገርህ ፡ ወዴት ፡ ነገርህ ፡ እን
ዴት ፡ ይለዋል ፤ ያም ፡ አገሬም ፡ ከ
ዚህ ፡ ነገሬም ፡ እንዲህ ፡ ይለዋል ፤
አንተማ ፡ ነገርህም ፡ ጥቂት ፡ አገር
ህም ፡ ቅርብ ፡ ነው ፤ ዳኛ ፡ ግን ፡ ምን ፡
ይሆናል ፡ ነገሥታቱ ፡ መኳንንቱ ፡
ቀን ፡ በስካር ፡ ሌሊት ፡ በዝሙት ፡
ይኖራሉ ፤ ፍርድ ፡ ጐደለ ፡ ድሀ ፡ ተበ
ደለ ፡ የሚል ፡ የለ ፡ እኔማ ፡ ይህችን ፡
መንግሥት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አግኝቻት ፡
ቢሆን ፡ በጣይ ፡ በጉባይ ፡ እንዲሉ ፡
ሌሊት ፡ በብርሃን ፡ ማኅቶት ፡ ቀን ፡
በብርሃነ ፡ ፀሐይ ፡ እየፈረድኹ ፡ እየ
ተቸሁ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ አብርቻት ፡
እኖር ፡ አልነበረምን ፡ ይላቸዋል ፡
ተራ ፡ ሰው ፡ የመጣ ፡ እንደሆነ ፡
ይነሣለታል ፤ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ እንደ
ሆነ ፡ ሄዶ ፡ ጫማውን ፡ ይስመዋል ፡
የሚያውቅ ፡ ያውቀዋል ፡ የማያውቅ ፡
ይህ ፡ ማነው ፡ ይላል ፤ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡
አቤሴሎም ፡ ይሏችኋል ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡
ነው ፡ ይሏቸዋል ፤ ወሠረቀ ፡ አቤሴ
ሎም ፡ ልበ ፡ ኵሉ ፡ ሺኤል ። የሰውን ፡
ሁሉ ፡ ልብ ፡ እፍኝ ፡ ጭልጥ ፡ አድር
ጎ ፡ ወሰደው ፡ ሕዝቡም ፡ ይህነንስ ፡
ያነገሠው ፡ ይላሉ ። ያነገሠው ፡ ትላ
ላችሁ ፡ እንጂ ፡ እንግዲያ ፡ መንግሥ
ት ፡ በእጃችሁ ፡ ነው ፡ አታነግሡኝ
ንም ፡ ይላቸዋል ፤ ማንገሥስ ፡ በነገሥ
ንሀ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሥርዓተ ፡ መንግ
ሥት ፡ ማን ፡ ያወጣልሃል ፡ ይሉታል ፤
ይህስ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ነገር ፡ ላም
ጪው ፡ ይግደደው ፡ እኔ ፡ ባወቅሁ ፡
አወጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ሄዶ ፡ አባቴ ፡ ከ
ናቴ ፡ ሀገር ፡ ሄጄ ፡ ሳለሁ ፡ የአባቴን ፡
ፊት ፡ ብታሳየኝ ፡ በዓል ፡ አደርጋለ
ሁ ፡ ብዬ ፡ ተስዬ ፡ ነበርና ፡ ሥርዓ
ተ ፡ መንግሥት ፡ ይውጣልኝ ፡ አለው ፤
ባሕቱ ፡ ዑቅ ፡ ኢትግበር ፡ እኩየ ፡
ክፉ ፡ እንዳታደርግ ፡ ተጠንቀቅ ፡ እ
ንጂ ፡ ይውጣልህ ፡ አለው ፤ ወሖሩ ፡
በየውሃቱ ፡ ልበሙ ፡ ከነገር ፡ ያልገቡ ፡
ሁለት ፡ መቶ ፡ መኳንንት ፡ አብረው
ት ፡ ሄደዋል ፤ እምከመ ፡ ሰማዕከሙ ፡
ቃለ ፡ ቀርን ፡ በኬብሮን ፤ በሉ ፡ አቤ
ሴሎም ፡ ነግሠ ፡ በኬብሮን ፤ የነጋሪ
ት ፡ ድምጽ ፡ በኬብሮን ፡ የሰማችሁ ፡
እንደሆነ ፡ አቤሴሎም ፡ በኬብሮን ፡
ነገሠ ፡ እያላችሁ ፡ ዝፈኑ ፡ ብሏቸው ፡
ሄዶ ፡ የሰባ ፡ አርዶ ፡ የበሬ ፡ አውርዶ ፡
በኬብሮን ፡ ነገሠ ፡ በከተማ ፡ ያሉ ፡
የነጋሪት ፡ ድምፅ ፡ ሰምተው ፡ አቤሴ
ሎም ፡ ነገሠ ፡ በኬብሮን ፡ እያሉ ፡ ይ
ዘፍኑ ፡ ጀመር ። ፪ ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፩-፲፪ ።
ዳዊትም ፡ ሰምቶ ፡ የምሰማው ፡ ድምፅ ፡
ምንድነው ፡ አለ ። አቤሴሎም ፡ ነገ
ሠ ፡ በኬብሮን ፡ እያሉ ፡ ይዘፍናሉ ፡
አሉት ። ንዑ ፡ ንጉየይ ፡ እምኢየሩሳ
ሌም ፡ እስመ ፡ አልብነ ፡ ሐይው ፡ እ
ምእደ ፡ አቤሴሎም ፡ ከአቤሴሎም ፡
እጅ ፡ መዳን ፡ አይቻለንምና ፡ ኑ ፡

2014 04 17

ከኢየሩሳሌም ፣ እንሸሽ ፣ አለ ፤ ኢዮአብ ፣ አቢሳ ፣ ትናንት ፣ አገዘለን ፣ ያሳደግነው ፣ ብላቴና ፣ ነገሥ ፣ ብለን ፣ እንሸሸለን ፣ እንዋጋለን ፣ እንጂ ፣ አሉት ፤ አይሆንም ፣ በነፍስህ ፣ ምርሃል ፣ በሥጋህ ፣ ግን ፣ ከአብራክህ ፣ የተከፈለ ፣ ልጅህ ፣ መንግሥትህን ፣ እስከ ፣ ሦስት ፣ ወር ፣ ይወስድብሃል ፤ እዋጋለሁ ፣ አትበል ፣ ብሎኛል ፤ ከፈጣሪዬ ፣ ጋር ፣ እዋጋለሁን ፣ ብኋቸው ፣ ነጠላ ፣ ልብስ ፣ ለብሶ ፣ ተራ ፣ ጫማ ፣ ተጫምቶ ፣ ከከተማው ፣ ወጥቶ ፣ ሲሄድ ፣ ተናግሮታል ። ፪ ፣ ሳሙ ፣ ፲፭ - ፲፫ - ፲፯ ።

ሚ ፣ አይ ፣ በከልዓይ ፣ እንጂ ፣ በቀዳማይ ፣ አይወድቁም ። መቻያ ፣ የሚያመጡብኝ ፣ ሥቃይ ፣ የሚያፀኑብኝ ፣ እለ ፣ አቤሴሎም ፣ አቤቱ ፣ ምንኛ ፣ በዙ ፣ ምን ፣ ይበዙ ፣ (እፎ ፣ በዝኁ) ፣ እንደት ፣ በዙ ፣ (ለምንት ፣ በዝኁ) ፣ ለምን ፣ በዙ ።

ብዙኃን ፣ ቆሙ ፣ ላዕሌየ ።

ብዙ ፣ የሚሆኑ ፣ እለ ፣ አቤሴሎም ፣ በላዬ ፣ ቆሙ ፣ ሰውማ ፣ በሰው ፣ ላይ ፣ ይቆማልን ፣ ብሎ ፣ በፀላትነት ፣ ተነሡብኝ ፣ ሲል ፣ ነው ፤ ቁም ፣ ላዕሌየ ፣ ወቅትለኒ ፣ እንዲል ። ፪ ሳሙ ፣ ፳ - ፪ ።

፪ ፤ ብዙኃን ፣ ይቤልዋ ፣ ለነፍስየ ፣ ኢያድኅነኪ ፣ አምላክኪ ።

ብዙ ፣ የሚሆኑ ፣ እለ ፣ አቤሴሎም ፣ ሰውነቴን ፣ ፈጣሪሽ ፣ እግዚአብሔር ፣ አያድንሽም ፣ አሏት ፤ ምንው ፣ እለ ፣ አቤሴሎም ፣ ከደዋልና ፣ እንዲህ ፣ አለ ፣ ቢሉ ፣ መከድስ ፣ አልከዱም ፣ ጉልማሳ ፣ ገድሏል ፣ የጕልማሳ ፣ ሚስት ፣ (ነሥቷል) ፣ ቀምቷልና ፣ ልመናውን ፣ አይሰማውም ፣ ሲል ፣ ነው ። ፪ ፣ ሳሙ ፣ ፲፭ ፣ ፪ - ፲፯ ። እንድም ፣ ቃለ ፣ መርገም ፣ ኢያድኅንኪ ፣ ይላል ፤ ፈጣሪሽ ፣ እግዚአብሔር ፣ አያድንሽ ፣ እንዲህ ፣ ይጣልሽ ፣ እያሉ ፣ የያዙትን ፣ እየጣሉ ፣ ይረግሙኛል ። እንድም ፣ (እግዚአ ፣ ሚ ፣ በዝኁ ፣ እለ ፣ ይሣቅዩኒ) ፣ መቻያ ፣ የሚያመጡብኝ ፣ ሥቃይ ፣ የሚያፀኑብኝ ፣ አይሁድ ፣ ምንኛ ፣ በዙ ፣ (ብዙኃን ፣ ቆሙ ፣ ላዕሌየ) ፣ ብዙ ፣ የሚሆኑ ፣ አይሁድ ፣ በላዬ ፣ ቆሙ ፤ አሁን ፣ የተመቸ ፣ መቃብሩን ፣ በኖራ ፣ ለስነው ፣ ሦስት ፣ መዓልት ፣ ሶስት ፣ ሌሊት ፣ ከላዩ ፣ ሰፍረው ፣ ሰንብተዋልና ፣ ማቴ ፣ ፳፯ ፣ ፳፫ - ፳፯ ። ፪ ፣ (ብዙኃን ፣ ይቤልዋ ፣ ለነፍስየ ፣ ኢያድኅነኪ ፣ አምላክኪ) ፣ ብዙ ፣ የሚሆኑ ፣ አይሁድ ፣ ሰውነቴን ፣ ፈጣሪሽ ፣ እግዚአብሔር ፣ አያድንሽም ፣ አሏት ፤ መዝ ፣ ፳፩ - ፰ ። ምንው ፣ አይሁድ ፣ ከደዋልና ፣ እንዲህን ፣ አለ ፣ ቢሉ ፣ መከድስ ፣ አልከዱም ፤ ሰንበት ፣ ሻረ ፣ ሕግ ፣ ሙሴን ፣ አፈረሰ ፣ ብለውታልና ፣ ልመናውን ፣ አይሰማውም ፣ ሲሉ ፣ ነው ። ዘዐ ፣ ፳፱ ፣ ፲ ። ማቴ ፣ ፭ ፣ ፲፯ - ፲፰ ። ፲፱ ፣ ፭ - ፲፱ ። እምላክነትሽ ፣ አያድንሽም ፣ አሏት ።



፫ ፤ አንተሰ ፣ እግዚኦ ፣ ምስካይየ ፣ አንተ ።

አቤቱ ፣ አንተ ፣ ግን ፣ አምባ ፣ መጠጊያዬ ፣ ነህ ።

ክብርየ ፣ ወመልዕለ ፣ ርእስየ ።

ምልዓለ ፣ ርእስየ ፣ አልዓሌ ፣ ርእስየ ፣ ይላል ፤ የራሴ ፣ ከፍታ ፣ ራሴን ፣ ከፍ ፣ የምታደርግልኝ ፣ አንተ ፣ ነህ ፤ አንድም ፣ ክብርየ ፣ ዘመልዕልተ ፣ ርእስየ ፣ ከራሴ ፣ በላይ ፣ ያለህ ፣ ዘውዴ ፣ አንተ ፣ ነህ ፤ ያ ፣ እንዲያስከብር ፣ የምታስከብረኝ ፣ አንተ ፣ ነህ ።

፬ ፤ ቃልየ ፣ ኀበ ፣ እግዚአብሔር ፣ ዐራኀኩ ።

ልመናዬን ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ አቀረብኩ ፤ እከዕዋ ፣ ለነፍስየ ፣ እንዲል ፣ ፩ ፣ ሳሙ ፣ ፩ ፣ ፲፭ ። እንድም ፣ በቃሌ ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ መልሼ ፣ ለመንሁ ። መዝ ፣ ፻፵ ፣ ፩ ። ፻፵፩ ፣ ፩ ።

ወሰምዓኒ ፣ እምደብረ ፣ መቅደሱ ።

በሰማያዊት ፣ መቅደሱ ፣ ሆኖ ፣ ልመናዬን ፣ ሰማኝ ፤ አንድም ፣ በምድራዊት ፣ መቅደሱ ፣ ሆኜ ፣ የለመንኩትን ፣ ልመናዬን ፣ በሰማያዊት ፣ መቅደሱ ፣ ሆኖ ፣ ሰማኝ ። መዝ ፣ ፲፯ ፣ ፯ ።

፭ ፤ አንሰ ፣ ሰከብኩ ፣ ወኖምኩ ።

ኖምኩ ፣ ወሰከብኩ ፣ እኔስ ፣ ሞትሁ ፣ ተቀበርኩ ፣ ብዬ ፣ ነበር ፤

ወተንሣእኩ ፣ እስመ ፣ እግዚአብሔር ፣ አንሥአኒ ።

እግዚአብሔር ፣ እንዳልሞት ፣ እንዳልቀበር ፣ አድርጎኛልና ፣ ዳንሁ ፣ እንጂ ።

፮ ፣ ኢይፈርህ ፣ እምእእላፈ ፣ አሕዛብ ።

የብዙ ፣ ብዙ ፣ ከሚሆኑ ፣ ከነአቤሴሎም ፣ ብዛት ፣ አልፈራም ፤ እለ ፣ አቤሴሎምን ፣ አሕዛብ ፣ አላቸው ፣ ስለ ፣ ብዛታቸው ፣ በፀያፍ ፣ የገባ ፣ አንድም ፣ ግብረ ፣ አሕዛብ ፤ ይሠራሉና ፣ እንድም ፣ አቤሴሎም ፣ በናቱ ፣ ወገን ፣ ከአሕዛብ ፣ ይወለዳልና ፣ ፪ ፣ ሳሙ ፫ ፣ ፫ ።

እለ ፣ ዓገቱኒ ፣ ወቆሙ ፣ ላዕሌየ ።

ከከበቡኝ ፣ በፀላትነት ፣ ከተነሡብኝ ፣ ከነአቤሴሎም ፣ ብዛት ፣ የተነሣ ፣ አልፈራም ፤ አንድም ፣ የትናንት ፣ ብላቴኖች ፣ እለ ፣ አቤሴሎምስ ፣ ይቅሩና ፣ እንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ ከሚነሡብኝ ፣ የብዙ ፣ ብዙ ፣ ከሚሆኑ ፣ ከሌሎች ፣ ጠላቶቼ ፣ ብዛት ፣ የተነሣ ፣ አልፈራም ፤ እንድም ፣ (አንሰ ፣ ሰከብኩ ፣ ወኖምኩ) ፣ ሶስት ፣ መዓልት ፣ ሦስት ፣ ሌሊት ፣ በከርሰ ፣ መቃብር ፣ አደርሁ ፤ ማቴ ፳፯ ፣ ፳፫ - ፳፯ ።

(ወተንሣእኩ ፣ እስመ ፣ እግዚአብሔር ፣ አንሥአኒ) ፣ እግዚአብሔር ፣ አንሥቶኛልና ፣ ተነሣሁ ፣ እንጂ ፣ ሉቃ ፣ ፳፬ ፣ ፺፬ ። አብ ፣ አንሥአ ፣ መንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ አንሥአ ፣ ወተንሣእኩ ፣ በሥልጣኑ ፣ ባህቲትየ ፣ ቢል ፣ አንድ ፣ነው ፣ ዕሪናቸውን ፣ መናገር ፣ ነው ። ኢይፈርህ ፣ እምእዕላፈ ፣ አሕዛብ) ፣ እለ ፣ ዓገቱኒ ፣ ወቆሙ ፣ ላዕሌየ) ፣ ከዓቀብት ፣ መቃብር ፣ ብዛት ፣ የተነሣ ፣ አልፈራም ።

፯ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ ወአድኅንኒ ።

ብሎዩን ፡ ይዞ ፡ ይሄዳል ፡ አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሥተህ ፡ አድነኝ ።

እስመ ፡ አንተ ፡ ቀሠፍኮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይፃረሩኒ ፡ በከንቱ ።

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ እለ ፡ ሳኦልን ፡ አጥፍተህ ፡ አድነኸኛልና ፤ ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፳፱ ፡ ፩ - ፳፫ ። ፴፩ ፡ ፫ - ፭ ።

አሁንም ፡ እለ ፡ አቤሴሎምን ፡ አጥፍተህ ፡ አድነኝ ።

ስነኒሆሙ ፡ ለኃጥአን ፡ ሰበርከ ።

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ የሳኦልን ፡ ሥልጣን ፡ አጥፍተህ ፡ አድነኸኛልና ፡ አሁንም ፡ የአቤሴሎምን ፡ ሥልጣን ፡ አጥፍተህ ፡ አድነኝ ።

ዘእግዚአብሔር ፡ አድኅኖ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝብከ ፡ ወበረከትከ ፡ ዘፍ ፡ ፲፮ ፡ ፩ - ፰ ። የእግዚአብሔርነትህ ፡ ትድግና ፡ በረከትህም ፡ ለኔ ፡ ለልጅ ፡ ልጅህ ፡ ይደረግልኛል ፡ ይደረግልኝ ፡ አንድም ፡ (ላዕለ ፡ ሕዝብከ) ፡ ለኔ ፡ ለልጅህ ፡ (ወበረከትከ) ፡ ባርኮ ፡ እባርከከ ፡ ወአስተባዝኆ ፡ አስተባዝኀከ ፡ ብለህ ፡ ባርከህ ፡ ለሰጠኸኝ ፡ ለወገኖችህ ፡ ይደረግላዋቸል ፡ ይደረግላቸው ፤ ዘፍ ፡ ፲፪ ፡ ፯ ። ሕዝብ ፡ ብሎ ፡ ልጅ ፡ ይሆናል ፡ ፱ቱ ፡ አንጋድ ፡ ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ ማኅፀንኪ ፤ ወ፱ ፡ ሕዝብ ፡ ይወጽኡ ፡ እምከርሥኪ ፡ ዘየዓቢ ፡ ሕዝብ ፡ ይትቀነይ ፡ ለዘይንዕስ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲል ፡ ዘፍ ፡ ፳፭ ፡ ፳፫ ። አንድም ፡ (ላዕለ ፡ ሕዝብከ) ፡ ለኔ ፡ ለልጅህ ፡ (ወበረከትከ) ፡ ባርኮ ፡ እባርከከ ፡ ወአስተባዝኆ ፡ አስተባዝኀከ ፡ ብለህ ፡ ባርከህ ፡ ለሰጠኸኝ ፡ ለወገኖችህ ፡ ይደረግላቸዋል ፡ ብለህ ፡ ነበር ፡ ቀረን ፡ ይላል ፤ የችኮላ ፡ አነጋገር ፤ ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ አብርሃም ፡ ላምስቱ ፡ ነገሥታት ፡ ሰዶም ፡ ረድቶ ፡ አራቱን ፡ ነገሥት ፡ ከሎዶጎምርን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ ሲመለስ ፡ ደስ ፡ ቢለው ፡ በመዋዕልየኑ ፡ ትፌኑ ፡ ቃለከ ፡ ወሚመ ፡ ታርእየኒሁ ፡ ኪያሃ ፡ ዕለተ ፡ አው ፡ አልቦ ፡ እንዳለ ፤ ዘፍ ፡ ፲፬ ፡ ፲፫ - ፳ ።

## መዝሙር ፡ ፬ ።

፩ ፡ ሶበ ፡ ጸዋዕኩዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰምዓኒ ፡ ጽድቅየ ።

ስለመነናውያን ፡ ተናግሮታል ፤ ከሥሩ ፡ አርእስት ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በማኒ ፡ መነናውያን ፡ ተብለዋል ፡ በሳዶቅ ፡ ሰዱቃውያን ፡ በዔቦር ፡ ዕብራውያን ፡ በፋሬስ ፡ ፈሪሳውያን ፡ በይሁዳ ፡ አይሁድ ፡ እንደተባሉ ። ሳዶቅ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ሰው ፡ ሙቶ ፡ መቃብር ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ ይቀራል ፡ ነፍሱም ፡ እንደጉም ፡ ሽንት ፡ በንና ፡ ትቀራለች ፡ የሚል ፡ ነው ፡ የሱን ፡ ባህል ፡ የያዙ ሁሉ ፡ ሰዱቃውያን ፡ ተብለዋል ፡



ዘሉ ፡ ፳፩ ፡ ፩ ። ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ። ማር ፡ ፲፪ ፡ ፲፱ ። ሉቃ ፡ ፳ ፡ ፳፯ ። ግብ ፡ ፳፫ ፡ ፰ ። ማኒም ፡ ማለት ፡ ዝጉሐዊ ፡ ባሕታዊ ፡ ጸዋሚ ፡ ተሐራሚ ፡ ማለት ፡ ነው ። ገንዘብ ፡ ጠፋበት ፡ ገንዘቡም ፡ አህያ ፡ ነው ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በቀኖና ፡ ስኖር ፡ እንዴት ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡ ይጥፋ ፡ ብሎ ፡ በጸሎቱ ፡ ተመክቶ ፡ የሐሰት ፡ መሥዋዕት ፡ ሠውቶ ፡ ቀኖና ፡ ገባ ፡ ገንዘቤ ፡ (አህያዬ) ፡ ቢገኝ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ አለ ፡ እላለሁ ፡ ባይገኝ ፡ ግን ፡ የለም ፡ እላለሁ ፡ ብሎ ፡ ጌታም ፡ በትህትና ፡ ቢለምኑት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሐሰት ፡ ቢለምኑት ፡ አይሰማምና ፡ ይገኝ ፡ የነበረውን ፡ አጠፋበት ፡ ይቀርብ ፡ የነበረውን ፡ አራቀበት ፤ ዘሌ ፡ ፩ ፡ ፩ ።

ሱባዔው ፡ ሲፈጸም ፡ ወጥቶ ፡ አልባቲ ፡ ሠራዒ ፡ ወመጋቢ ፡ ለዛቲ ፡ ዓለም ፡ ለዚህች ፡ ዓለም ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ የላትም ፤ ብርሃናት ፡ በልማድ ፡ ይመላለሳሉ ፤ አፍላጋት ፡ በልማድ ፡ ይፈሳሉ ፡ ክረምትና ፡ በጋ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ በልማድ ፡ ይፈራረቃሉ ፤ ሰውም ፡ በልማድ ፡ ይወለዳል ፡ በልማድ ፡ ይሞታል ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ፤ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የተነሣ ፡ በማን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ በዳዊት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤ ምነው ፡ ዳዊትን ፡ ያህል ፡ ሰው ፡ በዘመኑ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ መናፍቅ ፡ ሲነሣ ፡ አያጠፋውም ፡ ነበርን ፡ ቢሉ ፤ በሃይማኖታችሁ ፡ሙቱበት ፡ እንጂ ፡ ግደሉበት ፡ አይልምና ፡ እንዲህስ ፡ እንዳንል ፡ መምለኬ ፡ ጣዖት ፡ ነቢየ ፡ ሐሰት ፡ የተነሣ ፡ እንደሆነ ፡ በእሳት ፡ ተቃጥሎ ፡ በድንጋይ ፡ ተወግሮ ፡ ይሙት ፡ ትላለች ፡ ኦሪት ፡ ብሎ ፡ ዘሌ ፡ ፳ ፡ ፩ - ፯ ። በኋላ ፡ ተነሥቷል ፡ ይላሉ ፤ የሕዝቅያስን ፡ የትሩፋንን ፡ የመቃብያንን ፡ አስቀድሞ ፡ እንደተናገረ ፡ አስቀድሞ ፡ ተገልጾለት ፡ ተናግሮታል ። አንተ ፡ ማኒ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ የለም ፡ ብለህ ፤ ብትለምነው ፡ ልመናህን ፡ ሳይሰማህ ፡ ቀረ ፡ እንጂ ፤ እኔስ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ አለ ፡ ብዬ ፡ ብለምነው ፡ የእውነት ፡ ልመናዬን ፡ ሰማኝ ። መዝ ፡ ፻፲፯ ፡ ፭ ።

ወእምንዳቤየ ፡ አርኀብ ፡ ሊተ ።

ከመከራዬ ፡ አውጥቶ ፤ በተድላ ፡ በደስታ ፡ አኖረኝ ፤ አንድም ፡ ከመከራዬ ፡ ይልቅ ፡ ደስታዬን ፡ አበዛልኝ ፤ መጽሐፍ ፡ ለልማዱ ፡ መከራን ፡ በጠባብ ፡ ደስታን ፡ በሰፊ ፡ መስሎ ፡ ይናገራልና ።

ተሠሃለኒ ፡ ወስምዓኒ ፡ ጸሎትየ ።

ይቅር ፡ ብሎ ፡ ልመናዬን ፡ ሰማኝ ፡ አንድም ፡ ልመናዬን ፡ ሰምቶ ፡ ይቅር ፡ አለኝ ።

፪ ፡ ደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ታከብዱ ፡ ልበክሙ ።

የማኒ ፡ ልጆች ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ የለም ፡ በማለት ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ልቦናችሁን ፡ታፀናላችሁ ፤ ወአኒ ፡ አከብድ ፡ ልበ ፡ ለፈርዖን ፡ እንዲል ፤ ዘፀ ፡ ፯ ፡ ፫ ።

2014 04 17

ለምንት ፡ ታሬትሩ ፡ ከንቶ ፡ ወተኃሥ ፡ ሐሰተ ።

ሥራዊ ፡ መጋቢ ፡ የለም ፡ ማለትን ፡ ለ
ምን ፡ ትወዳላችሁ ።

፫፡ አእምሩ ፡ ከመ ፡ ተሰብሐ ፡ እግዚአብሔር ፡
በጻድቁ ።

አዬ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ ኑሮ ፡ በጻድ
ቁ ፡ በኖኅ ፡ በጻድቁ ፡ በሎጥ ፡ እንደ ፡
ተመሰገን ፡ እወቁ ፡ ዘፍ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ ።

እግዚአብሔር ፡ ይሰምዓኒ ፡ ሶበ ፡ ሰራሕኩ ፡ ኀቤሁ ፡
ዮና ፡ ፪ ፡ ፫ ።

እግዚአብሔር ፡ ወደርሱ ፡ መልሺ ፡
የለመንሁትን ፡ ልመናዬን ፡ ይሰማ
ኛል ፤

፬፡ ተምዑ ፡ ወኢተኀብሱ ።

ኢትተምዑ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ አትቆጡ ፡
አንድም ፡ እንዳለ ፡ ይሆናል ፡ (ተምዑ)
ከራቱ ፡ ባሕርያት ፡ የተፈጠረ ፡ ሰው ፡
ቍጣ ፡ ይስማማዋልና ፡ ጊዜ ፡ ቢያጋ
ጥማችሁ ፡ ተቈጡ ፡ (ወኢተዓብሱ) ፡
ሳትታረቁ ፡ ግን ፡ አትደሩ ፡ ወዘእን
በለ ፡ ይዕርብ ፡ ፀሐይ ፡ አቍርሩ ፡ መ
ዓተክሙ ፡ እንዲል ፡ ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፳፮ ።
አንድም ፡ (ተምዑ) ፡ በሚገባ ፡ ተቈ
ጡ ፡ የሚገባ ፡ ቍጣ ፡ አለና ፡ በ ፡ መ
ዓት ፡ ዘበርትዕ ፡ እንዲል ።

ሕፃናት ፡ የተማሩትን ፡ እንዳይገድፉ ፡
ያልተማሩትን ፡ እንዲማሩ ፡ መናፍቃ
ን ፡ ሃይማኖት ፡ እንዳይነቅፉ ፡ (እንዳ
ያጠፉ) ፡ ከህደት ፡ እንዳያሰፉ ፡ ተቆ
ጡ ፡ (ወኢተዓብሱ) ፡ ሕፃናት ፡ ያል
ተማሩትን ፡ ሲማሩ ፡ የተማሩትን ፡
ሳይገድፉ ፡ መናፍቃን ፡ ሃይማኖት ፡
ሳይነቅፉ ፡ ክህደት ፡ ሳያሰፉ ፡ አትቆ
ጡ ፡ አንድም ፡ (ተምዑ) ፡ ሠራዒ ፡
መጋቢ ፡ የለም ፡ የሚለውን ፡ ተቈጡ
(ወኢተዓብሱ) ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ የ
ለም ፡ አትበሉ ፡ ያዕ ፡ ፩ ፡ ፲፱ - ፳ ።

ወዘትሔልዩ ፡ በልብክሙ ፡ ውስተ ፡ ምስካቢክሙ
ይትዓወቅ ።

ይትዓወቀክሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ቀን ፡
ያሰባችሁት ፡ ሌሊት ፡ በመኝታች
ሁ ፡ ይገለጽላችኋል ። የቀን ፡ አእም
ሮ ፡ ዝርው ፡ ነው ፡ ዓይኑ ፡ ሥጋ ፡ ከብ
ርሃን ፡ ፀሐይ ፡ ጋር ፡ ተዋህዶ ፡ ፀሐይ ፡
ከደረሰችበት ፡ ይደርሳል ፡ ሐሳብ ፡
ይበተናል ፡ የሌሊት ፡ አእምሮ ፡ ግን
ክት ፡ ነው ፡ ያን ፡ ብርሃን ፡ ወስዶ ፡
ይህን ፡ ጭለማ ፡ ያመጣ ፡ ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፱ - ፭ ።
ሰብአ ፡ ትካትን ፡ አጥፍቶ ፡ ኖኅን ፡
ዘፍ ፡ ፯ ፡ ፩ - ፳፱ ። ሰብአ ፡ ሰዶም ፡ ሰብአ
ገሞራን ፡ አጥፍቶ ፡ ሎጥን ፡ ዘፍ ፡ ፲፱ ፡
፩ - ፳፱ ። ሰብአ ፡ ግብፅን ፡ አጥፍቶ ፡ እስ
ራኤልን ፡ ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፳፰ - ፳፱ ። ያዳኑ ፡ እሱ
አይደለምን ፡ ብሎ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡
እንዳለ ፡ ለልቡና ፡ ይረዳልና ፡ ሡዑ ፡
ማንሻ ፡ አንድም ፡ (ይትዓወቅሙ) ፡
በመዓልት ፡ ያሰባችሁት ፡ ሌሊት ፡
በመኝታችሁ ፡ ይገለጽላችሁ ፡ ዘንድ

፭፡ ሡዑ ፡ መሥዋዕተ ፡ ጽድቅ ፡ ወተወከሉ ፡ በ
እግዚአብሔር ።

ሡዑ ፡ ከልቹ ፡ ብሎ ፡ መሥዋዕት ፡
አለ ፡ እንጂ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ አለ ፡



ብላችሁ ፡ እውነት ፡ ተናገሩ ፡ በእግ
ዚአብሔርም ፡ እመኑ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
አንድም ፡ ማኒን ፡ የሐሰት ፡ መሥዋ
ዕት ፡ ሠዋ ፡ ብሎት ፡ ነበርና ፡ እውነ
ተኛ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ።

፮፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ይቤሉ ፡ መኑ ፡ ያርእየነ ፡ ሠ
ናይቶ ።

ሀልውናውን ፡ ግን ፡ በነገረን ፡ የሚ
ሉ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፤ ከቀደ
ሙ ፡ ሰዎች ፡ አብርሃም ፡ ከኋላ ፡ ሰዎ
ች ፡ ሙሴ ፡ ጳሊም ።

ተአውቀ ፡ በላዕሌነ ፡ ብርሃነ ፡ ገጽከ ፡ እግዚኦ ።

ለነ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ተነበዩ ፡ ላዕሌኪ ፡
እንዲል ፤ የአካልህ ፡ መኖር ፡ ለኛ ፡
ተገለጸ ፤ አንድም ፡ በዘላዕሌነ ፡ ከኛ ፡
በላይ ፡ ባለ ፡ በፀሐይ ፡ ታወቀ ፡ በከ
በቡ ፡ አብ ፡ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፡ በሙ
ቀቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላልና ።

፯፡ ወወደይከ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ።

ደስታን ፡ በልባችን ፡ ውስጥ ፡ አሳደ
ርከልን ።

እምፍሬ ፡ ሥርናይ ፡ ወወይን ፡ ወቅብዕ ፡ በዝኃ ፡

ከስንዴ ፡ ከወይን ፡ ከዘይት ፡ ይልቅ ፡ ደስ
ታ ፡ በዛልን ፤ አንድም ፡ ስንዴ ፡ በልቶ ፡
ወይን ፡ ጠጥቶ ፡ ዘይት ፡ ተቀብቶ ፡
ደስ ፡ ከሚለው ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ ደ
ስታ ፡ በዛልን ፤ አንድም ፡ (ወወደይ
ከ) ፡ ሃይማኖተ ፡ አሪትን ፡ ሠራህልን ፤
(እምፍሬ ፡ ሥርናይ) ፡ ይኸውም ፡ ሃ
ይማኖት ፡ ከስንዴ ፡ ከወይን ፡ ከዘይ
ት ፡ ፍሬ ፡ ይልቅ ፡ በዛልን ፡ የሃይማኖ
ት ፡ ብዛት ፡ ሌላ ፡ የለውም ፡ አንዱ ፡ ላ
ንዱ ፡ አብነት ፡ ሆኖ ፡ የሚያስረዳ ፡ ስለ
ሆነ ፡ እየቀደም ፡ የሚረዳ ፡ ስለሆነ ፡
የሰሚው ፡ ከርእይ ፡ የሚያደርስ ፡ ስ
ለሆነ ፡ በሃይማኖት ፡ ፀንቶ ፡ የሚሠ
ራ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ አንድም ፡ (ብዙ
ኃን ፡ እለ ፡ ይቤሉ ፡ መኑ ፡ ያርእየ
ነ ፡ ሠናይቶ) ፡ ተሠግዎቶ ፡ ሲል ፡
ነው ፤ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ግን ፡ በነገረ
ን ፡ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፤ ተአው
ቀ ፡ በላዕሌነ ፡ ብርሃነ ፡ ገጽከ ፡ እግዚ
አ) ፡ የአካልህ ፡ መታወቂያ ፡ ወልድ ፡
ለኛ ፡ ተገለፀ ፡ በዘእምኔነ ፡ ይላል ፡
ከእኛ ፡ በነሣው ፡ ሥጋ ፡ ተገለጸ ።
ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፪ ። ዘኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ። (ወወደይከ ፡ ት
ፍሥሕተ ፡ ውስተ ፡ ልብነ) ።

ሃይማኖተ ፡ ወንጌልን ፡ ሠራህልን ።
(እምፍሬ ፡ ሥርናይ ፡ ወወይን ፡ ወቅብ
ዕ ፡ በዝኃ) ፡ ይኸውም ፡ ሃይማኖት ፡ ከ
ስንዴ ፡ ከወይን ፡ ከዘይት ፡ ፍሬ ፡ ይ
ልቅ ፡ በዛልን ። ሐተታ ፡ እንዳለፈው ፡
አንድም ፡ (ወወደ ፡ ትፍ ፡ ውስ ፡ ል ፡
እም ፡ ሥር ፡ ወወ ፡ ወቅ ፡ በዝኃ) ፡
ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ልጅነትን ፡ ከመ
ቀበላችን ፡ የተነሣ ፡ ሃይማኖት ፡ ፀና
ልን ፤ አንድም ፡ (ወወደይከ) ፡ ጸጋ ፡
ክብርን ፡ ሰጠኸን ፤ (እምሥርናይ) ፡
ይኸውም ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ከስንዴ ፡
ከወይን ፡ ከዘይት ፡ ይልቅ ፡ በዛልን
አንድም ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ሃይ
ማኖትን ፡ ከመቀበላችን ፡ የተነሣ ፡

2014 04 17

ጸ.ጋ ፡ ክብር ፡ ፀናልን ፡ ቅዱሳን ፡ እየቀ ደም ፡ እየበቁ ፡ የሚያገኙት ፡ ጸ.ጋ ፡ ክብር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ አይነገርምና ።

፰ ፡ በሰላም ፡ ዐቲ ፡ እሰክብ ፡ ወእነውም ።

ማኒ ፡ አንተ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ የለ ም ፡ በማለትህ ፡ ከፈጣሪህ ፡ ጋራ ፡ ሳ ትስማማ ፡ ሳትታረቅ ፡ ትሞታለህ ፡ ት ቀበራለህ ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ አለ ፡ ብዬ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ ጋራ ፡ ታርቄ ፡ ተስማምቼ ፡ እሞታለሁ ፡ እ ቀበራለሁ ።

እስመ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ በተስፋ ፡ ባሕቲትከ ፡ አኅደርከኒ ።

የብቻህ ፡ በተስፋ ፡ ህልውና ፡ አንድ ም ፡ በሕቲተከ ፡ ብቻህን ፡ በተስፋ ፡ ህልውና ፡ በብቻህ ፡ ተስፋ ፡ ህልው ና ፡ አፅንተኸኛልና ፡ መኑ ፡ አስተዶ ኃረ ፡ ማዕዘኒሃ ፡ ለምድር ፡ እንዲል ። ኢዮ ፡ ፴፰ ፡ ፱-፮ ። እንድም ፡ (በሰላም ፡ ዐቲ ፡ እሰክብ ፡ ወእነውም) ፡ ማኒ ፡ አ ንት ፡ ከሦስቱ ፡ አካል ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ያድነኛል ፡ ሳትል ፡ ትሞታለህ ፡ ትቀበራለህ ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ ከሦስቱ ፡ አካል ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ያድነኛ ል ፡ ብዬ ፡ እሞታለሁ ፡ እቀበራለሁ ፡ (እስመ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ በተስፋ ፡ ባሕቲትከ ፡ አኅደርከኒ) ፡ ብቻህን ፡ በተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ አጽንተኸኛልና ።

## መዝሙር ፡ ፲ ።

፩ ፡ ቃልየ ፡ አጽምዕ ፡ እግዚኦ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ ከአሥ ሩ ፡ አርእስት ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ት ሩፋን ፡ የሚላቸው ፡ አሥሩ ፡ ነገድ ፡ ተማርከው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የቀሩ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ናቸው ። ፪ ሕዐ ፡ ፴፮ ፳- ፳፫ ። እንድም ፡ ሁሉም ፡ ተማርከው ፡ አበው ፡ አልቀው ፡ የቀሩ ፡ ውሉድ ፡ ናቸው ፡ የእምስቱን ፡ ነገሥት ፡ ታሪክ ፡ የሚተርኩ ፡ አሉ ፡ ያስተርካል ፡ እን ደ ፡ ወንጌል ። ማቴ ፡ ፳-፲፭ ። ትሩፍ ፡ ማለት ፡ ፍጹም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ረ ድዕ ፡ ትሩፍ ፡ እንዲል ። ዮሐ ፡ ፩-፩ ። አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወለቡ ፡ ጽራኅየ ።

ልመናዬን ፡ ልብ ፡ አድርገህ ፡ ስማኝ ።

፪ ፡ ወአጽምዓኒ ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ።

ነገረ ፡ ስእለትየ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የልመ ናዬን ፡ ነገር ፡ ስማኝ ፡ የልመና ፡ ስ ልቱ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ መላልሶ ፡ ተና ገረ ።

ንጉሥየ ፡ ወአምላኪየ ።

የባቢሎናውያን ፡ ንጉሣቸው ፡ ብል ጣሶር ፡ አምላካቸው ፡ ቤል ፡ ዳጎን ፡ ነው ፡ የኔ ፡ ንጉሤም ፡ ፈጣሪዬም ፡ አ ንተ ፡ ነህ ፡ እንድም ፡ ንጉሥ ፡ ሠራዊ ቱን ፡ ፈጣሪ ፡ ፍጥረቱን ፡ እንዲረዳ ፡ ፈጥነህ ፡ እርዳኝ ።



እስመ ፡ ኀቤከ ፡ እጼሊ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ እጸልያለ ሁ ፡ እለምናለሁና ።

፫ ፡ በጽባሕ ፡ ስምዓኒ ፡ ቃልየ ።

ዕለት ፡ ዕለት ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ፡ እ ንድም ፡ ፈጥነህ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

በጽባሕ ፡ እቀውም ፡ ቅድሜከ ፡ ወእስተርኢ ፡ ለከ ።

ዕለት ፡ ዕለት ፡ እንድም ፡ ፈጥኜ ፡ በመ ሥዋዕት ፡ በጸሎት ፡ ከቤተ ፡ መቅደ ስ ፡ ገብቼ ፡ እገለጻለሁና ።

፬ ፡ እስመ ፡ ኢኮንከ ፡ አምላከ ፡ ዘአመፃ ፡ ያፈ ቅር ።

(አናበህ) ፡ ዓመፅን ፡ የሚወድ ፡ የባቢ ሎናዊ ፡ እንድም ፡ የብልጣሶር ፡ አም ላክ ፡ አይደለህምና ። እንድም ፡ (እስ መ ፡ ኢኮ ፡ አምላከ ፡ ዘዓመፃ ፡ ታፈቅ ር) ፡ አምላክ ፡ ዓመፅን ፡ የምትወድ ፡ አይደለህምና ።

ወኢየኀድሩ ፡ እኩያን ፡ ምስሌከ ።

እኩያን ፡ ባቢሎናውያን ፡ እንድም ፡ ሲዴቅያስ ፡ ኢኮንያን ፡ ከንተ ፡ ጋራ ፡ አይኖሩም ፡ ማለት ፡ አድረህባቸው ፡ አትኖርምና ፡ ሲል ፡ ነው ።

፭ ፡ ወኢይነብሩ ፡ አማፅያን ፡ ቅድመ ፡ አዕይንቲከ ።

ዓመፀኞች ፡ ባቢሎናውያን ፡ እንድ ም ፡ ሲዴቅያስ ፡ ኢኮንያን ፡ በበለሟል ነትህ ፡ ፀንተው ፡ አይኖሩም ።

ጸላዕከ ፡ እግዚኦ ፡ ኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።

ዓመፅ ፡ የሚሠሩ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ ሁሉ ፡ እንድም ፡ ሲዴቅያስ ፡ ኢኮንያ ንን ፡ ጠላህ ።

፮ ፡ ወትገድፎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነቡ ፡ ሐ ሰተ ።

ከሰብዓ ፡ ዘመን ፡ አትርፈን ፡ እንገዛቸ ዋለን ፡ የሚሉ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ ታ ጠፋቸዋለህ ።

ብእሴ ፡ ደም ፡ ወጕሕላዌ ፡ ያስቈርር ፡ እግዚአብ ሔር ።

ደመ ፡ በግዕን ፡ ለጣዖት ፡ እንድም ፡ የሰው ፡ ደም ፡ የሚያፈስ ፡ ከዳተኛ ፡ የሚሆን ፡ ባቢሎናዊን ፡ እንድም ፡ ብ ልጣሶርን ፡ እንድም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኢ ኮንያንን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፀየፈዋ ል ፡ ማለት ፡ አያድርበትም ፡ እንድም ፡ መፀያየፍ ፡ የጋራ ፡ ነው ፡ ብሶ ፡ እግ ዚአብሔርን ፡ ይጸየፈዋል ፡ ማለት ፡ ያይብኛል ፡ ይሰማብኛል ፡ አይለውም ።

ወአንስ ፡ በብዝኃ ፡ ምሕረትከ ፡ እበውእ ፡ ቤተከ ።

እኔ ፡ ግን ፡ በይቅርታህ ፡ በቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እገባለሁ ።

ወእሰግድ ፡ ውስተ ፡ ጽርሐ ፡ መቅደስከ ፡ በፈሪ ሆትከ ።

አንተን ፡ በመፍራት ፡ አንተን ፡ በማም ለክ ፡ ወሰበ ፡ አኮ ፡ በፍርሃት ፡ ይስሐ ቅ ፡ እምፈነውከኒ ፡ ዕራቅየ ፡ እንዲል ፡ ዘፍ ፡ ፴፩ ፡ ፵፪ ።

መመስገኛህ ፡ የምትሆን ፡ ደብረ ፡ መቅ ደስህ ፡ በተሠራችበት ፡ የአብርሃም ፡ ዕፃ ፡ ክፍል ፡ በምትሆን ፡ በኢየሩሳ ሌም ፡ እሰግዳለሁ ፡ አብርሃምን ፡ መቅ

2014 04 17

ደስ ፡ አለው ፡ ማኅደረ ፡ እግዚአብሔ
ር፡ ነውና፤ ወእስተፍሣሕከ፡ በኃይል
ከ ፡ ተረፈ ፡ መቅደስከ ፡ እንዲል ፡
ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፲፫ ።

፰፤ እግዚኦ ፡ ምርሐኒ ፡ በጽድቅከ ።

አቤቱ ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ኅሊቆ ፡ እት
ቤቀሎ ፡ ለንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ወለዘ
ሉ ፡ ሕዝበ ። ብለህ ፡ በተናገርከው ፡
በጽኑ ፡ ቀጠሮህ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡
መንገድ ፡ መርተህ ፡ አውጣኝ ።

ወበእንተ ፡ ጸላዕትየ ፡ አርትዕ ፡ ፍኖትየ ፡ ቅድሜከ፤

ከሰብአ ፡ ዘመን ፡ አትርፈን ፡ እንገዛቸ
ዋለን፡ የሚሉ፡ ባቢሎናውያንን፡ ደስ
አይበላቸው፡ ብለህ፡ የኢየሩሳሌምን፡
መንገዴን ፡ አቅናልኝ ።

፱፤ እስመ ፡ አልቦ ፡ ጽድቅ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ።

ባንደበታቸው ፡ እውነት ፡ የለምና ፤
ማለት ፡ አይነገርምና ።

ልቦሙኒ ፡ ከንቱ ።

ልበናቸውም ፡ ከንቱ ፡ ነውና ፤ አን
ድም ፡ ይኄሊ ፡ ከንቶ ፡ ይላል ፤ ከንቱ ፡
ነገርን ፡ ያስባልና ።

፲ ፡ መቃብር ፡ ክሡት ፡ ጉራዒቶሙ ።

የተከፈተ ፡ አንደበታቸው ፡ እንደመ
ቃብር ፡ ነው ፤ ሞት ፡ ቢገድል ፡ መቃ
ብር ፡ ቢቀበል ፡ በቃኝ ፡ ጠገብሁ ፡ እን
ዳይል ፤ እነሱም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሲናገሩ ፡
በቃን ፡ ጠገብን ፡ አይሉምና ፤ አንድ
ም ፡ አንደበታቸው ፡ እንደተለሰነ ፡
መቃብር ፡ ነው ፤ ያንን ፡ በላይ ፡ ሉሳን ፡

ወርድ ፡ ይስሉበታል ፤ ሐረግ ፡ ይስቡ
በታል ። አበባ ፡ ያፈነዱበታል ። ከፍ
ተው ፡ ያዩት ፡ እንደሆነ ፡ መግነዙ ፡
ተበጣጥሶ ፤ እገሩ ፡ ፈሶ ፡ ሥጋው ፡ ተል
ከስክሶ ፡ አጥንቱ ፡ ተከስክሶ ፡ ለዓይን ፡
ያስጸይፋል ፤ ላፍንጫ ፡ ይከረፋል ፤ እ
ነሱም ፡ ሰውንም ፡ እግዚአብሔርንም ፡
የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ሲናገሩ ፡ ይኖራ
ሉና ። ኤር ፡ ፭ ፡ ፲፯ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፳፯ - ፳፰ ።
ሮሜ ፡ ፫-፲፫ ።

ወጽልሐዉ ፡ በልሳናቲሆሙ ።

ባንደበታቸው ፡ ከዱ ፤ ለጊዜው ፡ እላ
ንተማ ፡ የዳዊት ፡ የሰሎሞን ፡ ልጆች ፡
አይደላችሁም ፡ ይሏቸዋል ፡ ኋላ ፡
ግን ፡ እኒህ ፡ ባሮች ፡ እውነት ፡ መስ
ሏቸው ፡ አትወጡም ፤ ከሰባ ፡ ዘመን ፡
አትርፈን ፡ እንገዛችኋለን ፡ ይሏቸዋ
ልና ።

፲፩ ኰንኖሙ ፡ እግዚኦ ፡ ወይደቁ ፡ በውዲቶሙ ፡

ነገር ፡ በመሥራታቸው ፤ አንድም ፡
እኔን ፡ ክንተ ፡ በማጣላታቸው ፡ አጥ
ፋቸው ፤ እስመ ፡ አንተ ፡ ትኬንኖ ፡
ለእጉክ ፡ እንዲል ።

ወበከመ ፡ ብዝኀ ፡ ኀብሎሙ ፡ ስድዶሙ ።

ሀሰት ፡ እንደመናገራቸው ፡ መጠን ፡
ከሀገራቸው ፡ ወደሰው ፡ ሀገር ፤ ከሕ
ይወት ፡ ወደሞት ፤ ከተድላ ፡ ወደመ
ከራ ፡ አውጥተህ ፡ ስደዳቸው ።

እስመ ፡ አምረሩከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ አንተን ፡ አሳዝነዋልና ፡ ሰው
ን ፡ መበደል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማሳ



ዘን ፡ ነውና ፤ አንድም ፡ ጣዖት ፡ አም
ልከው ፡ አንተን ፡ አሳዝነዋልና ።

፲፭፤ ወይትፌሥሑ ፡ ብከ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይት
ዌከሉከ ።

አንተን ፡ ያመኑህ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ባንተ ፡
አምነው ፡ በተሠራላቸው ፡ ሥራ ፡
ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ለዓለም ፡ ይትኃሠዩ ፡ ወተኀድር ፡ ላዕሌሆሙ ።

ተኀድር ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ለዓለም ፤ ይት
ኃሠዩ ፡ ለዓለም ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፤ ለዘ
ላለም ፡ አድረኅባቸው ፡ ትኖራለህ ፤
ለዘለዓለም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ይኖ
ራሉ ፤ ራዕ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ።

ወይትሜከሑ ፡ ብከ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ያፈቅሩ ፡
ስመከ ።

ስምህን ፡ የሚወዱ ፡ ሁሉ ፡ ይከብራሉ፤
እምከመ ፡ አድማዕኑ ፡ መንግሥተ ፡
ንትሜከህ ፡ እንዲል ።

፲፪፤ እስመ ፡ አንተ ፡ ትባርኮ ፡ ለጻድቅ ።

ከሰብዓ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ትሩፋን ፡ ታበ
ዛዋለህ ፡ ዘሩባቤልን ፡ በመንግሥት ፡
ታከብረዋለህና ፤

እግዚኦ ፡ ከመ ፡ ወልታ ፡ ሥሙር ፡ ከለልከነ ።

እስከዚያውም ፡ ድረስ ፡ እንዳላባሽ ፡
ጋሻ ፡ ሠወርኸን ፡ ያ ፡ ከተወረወረ ፡
ጦር ፡ ከተጣለ ፡ ጠጠር ፡ እንዲያድን ፤

መዝሙር ፡ ፮ ።

፩፤ እግዚኦ ፡ በመዓትከ ፡ ኢትቅሥፈኒ ።

በአርዮ ፡ ጊዜ ፡ ስለራሱ ፡ ተናግሮታ
ል ፤ ይህስ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤
በ ፡ አመ ፡ ይወጽኡ ፡ ፡ ወበ ፡ አመ ፡
ይበውኡ ፡ ነገሥት ። ነገሥታት ፡ የሚ
ዘምቱበት ፡ የሚመለሱበት ፡ ጊዜ ፡ ደ
ረሰ ። አንድም ፡ ወበጽሐ ፡ መዋዕል ፡
አመ ፡ ይወጽኡ ፡ ወአመ ፡ ይበውዑ ፡
ነገሥት ፡ ይላል ፡ አብነት ። ነገሥታቱ ፡
የሚወጡበት ፡ የሚገቡበት ፡ ጊዜ ፡
ደረሰ ፤ ስለምን ፡ ይወጡ ፡ ነበር ፡ ቢሉ ፤
መንግሥት ፡ ለማዳረስ ፤ የሀገራችን ፡
ነገሥታት ፡ መንግሥት ፡ ለማዳረስ ፡
አክሱም ፡ ይሄዱ ፡ እንደነበረ ፤ ሠራ
ዊት ፡ እንዳይራብ ፡ ደዌ ፡ እንዳይናኝ ፡
ጠላት ፡ እንዳይሠለጥንባቸው ፡ በግን
ቦት ፡ በሰኔ ፡ ዘምተው ፡ በመስከረም ፡
በጥቅምት ፡ ይመለሳሉ ፤ በሀገራችን ፡
ነገሥታቱ ፡ በመስከረም ፡ በጥቅምት ፡
ዘምተው ፡ በግንቦት ፡ በሰኔ ፡ እንዲመ
ለሱ ፤ አራት ፡ ወር ፡ ካንዱ ፡ ከተማ ፡
አራት ፡ ወር ፡ ካንዱ ፡ ከተማ ፡ ይኖ
ራሉ ። ያላመነውን ፡ አሳምነው ፤ ካመ
ነው ፡ ግብር ፡ ተቀብለው ፡ ይመለሳ
ሉ ። ተራ ፡ ጠላት ፡ የተነሣባቸው ፡
እንደሆነ ፡ ጦር ፡ ሰደው ፡ ያስወጉ
ታል ። ኃይለኛ ፡ ጠላት ፡ የተነሣባቸ
ው ፡ እንደሆነ ፡ ክተት ፡ ሠራዊት ፡
ምታ ፡ ነጋሪት ፡ ብለው ፡ ይዘምቱበ
ታል ፤ እነሱስ ፡ ዳዊትንም ፡ ያዘምቱ
ት ፡ ነበር ፡ የቀረበት ፡ ምክንያት ፡ አል

2014 04 17

ታወቀም ፤ እንድም ፡ ታውቋል ፡ ከዕ
ለታት ፡ በንዳቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋር ፡
ገጥሞ ፡ ሲዋጋ ፡ ከራቱ ፡ ረፋይን ፡
አንዱ ፡ የጎልያድን ፡ በቀል ፡ ደገል ፡
እመልሳለሁ ፡ ብሎ ፡ በጭር ፡ ታጥቆ ፡
ዘገር ፡ ነቅንቆ ፡ መጣበት ፡ የአፅላፈ ፡
ሸኤል ፡ ያለህ ፡ ብሎ ፡ ዝልፍልፍ ፡
አለ ፡ ወወውዐ ፡ ሎቱ ፡ አቢሳ ፡ ወል
ደ ፡ ሶርህያ ፡ እኅቱ ፡ አቢሳ ፡ ጋሻ ፡
መክቶ ፡ ዘገሩን ፡ ነጥቆ ፡ አድኖታል ።
ደንግፆ ፡ የማያውቅ ፡ መደንገፁ ፡ ስለ
ምንነው ፡ ቢሉ ፡ ጦር ፡ ሲሠራ ፡ ውሎ ፡
መድኃኒት ፡ ቀምሶ ፡ ከሴት ፡ ደርሶ ፡
ደክሞት ፡ ነበርና ፡ ምሥጢሩ ፡ ግን ፡
ኃይል ፡ የባሕርዩ ፡ ነው ፡ እንዳይል ፡
ነው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኢትጥፋዕ ፡
ማኅቶቶሙ ፡ ለሸኤል ፡ የንጉሥ ፡
ሞት ፡ የፀሐይ ፡ ዕርበት ፡ በሁሉ ፡ ነው ፤
ፀሐይ ፡ ከጠፋ ፡ መተካት ፡ ንጉሥ ፡
ከሞተ ፡ ማስነሣት ፡ ይቻላልን ፡ ከእ
ንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ንጉሥ ፡ ከግንቡ ፡
አይውጣ ፡ ብለው ፡ ሥሬት ፡ ሠርተ
ው ፡ ነበርና ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኢዮአብን ፡ የጦ
ር ፡ አበጋዝ ፡ አድርጎ ፡ አቢሳን ፡ አፅ
ላፊ ፡ እስራኤልን ፡ ከህናቱን ፡ ታቦተ ፡
ጽዮንን ፡ አስይዞ ፡ አራበት ፡ ዘደቂቀ ፡
አሞንን ፡ ወግታችሁ ፡ ኑ ፡ ብሎ ፡ ሰደ
ዷቸው ፡ እሱ ፡ ቀርቷል ፡ በዚያን ፡
ጊዜ ፡ በልቶ ፡ ጠጥቶ ፡ ተኝቶ ፡ ተነ
ሥቶ ፡ በሰገነት ፡ ሲመላለስ ፡ ቤርሳ
ቤህ ፡ ብእሲተ ፡ አርዮ ፡ በተክል ፡
በታ ፡ ገብታ ፡ ስትታጠብ ፡ የገላዋ ፡
ዕርየት ፡ ፀዳለ ፡ ፀሐይ ፡ የብርቱ ፡ የወ
ሀው ፡ ጽርየት ፡ ከሰውነቷ ፡ ተዋሀዶ ፡
እንደፀሐይ ፡ ስትፈልቅ ፡ አይቶ ፡ በሐ
ፀ ፡ ዝሙት ፡ ተነደፈ ፡ ብእሲተ ፡ መኑ ፡
ይእቲ ፡ ዛቲ ፡ ይህቺ ፡ የማን ፡ ሚስት ፡
ናት ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ፡ አከኑ ፡ ቤርሳቤህ ፡
ብእሲተ ፡ አርዮ ፡ ገብርከ ፡ ኬጥያዊ ፡ የ
ባሪያህ ፡ የአርዮ ፡ ሚስት ፡ ቤርሳቤህ ፡
ይሉሃል ፡ እንጂ ፡ ይህች ፡ ናት ፡ አሉት ፡
ከተክል ፡ በታ ፡ ለምን ፡ ገባች ፡ ቢሉ ፡
የተክል ፡ ወሀ ፡ ገላ ፡ ያፀራልና ፤ ከግ
ዳጅዋ ፡ የፀራችበት ፡ ወራት ፡ ነበርና ፡
ብዙ ፡ የምትዘግበው ፡ ሽቱ ፡ ነበራ
ትና ። እሱም ፡ ዝናዋን ፡ ይሰማ ፡ ነበ
ርና ፡ አስጠርቶ ፡ ኢትሑር ፡ ኅበ ፡
ብእሲተ ፡ ብእሲ ፡ ያለውን ፡ አፍርሶ ፡
ዘፀ ፡ ፳-፲፱-፲፯ ። ዘሌ ፡ ፳-፲፰-፳፪ ። ተጫዋ
ውቶ ፡ ሰደዳት ፡ ፀነሰች ፤ ሙሴ ፡ እ
ንድ ፡ ወንድ ፡ ላንድ ፡ ሴት ፡ አንዲት ፡
ሴት ፡ ላንድ ፡ ወንድ ፡ ይሁን ፡ ከዚህ ፡
የወጣ ፡ በድንጋይ ፡ ተወግሮ ፡ በእ
ሳት ፡ ተጠብሶ ፡ ይሙት ፡ ያለውን ፡
ቃል ፡ ታውቃለችና ፤ ዘሌ ፡ ፳-፲ ። እን
ተ ፡ በሠራኸው ፡ እኔ ፡ ልሞት ፡ ነው ፡
ለዚህ ፡ ነገር ፡ ብልሃት ፡ ፈልግለት ፡ ብላ ፡
ትልክበታለች ፡ በምን ፡ አውቃ ፡ ቢሉ ፡
ብልሆች ፡ ሴቶች ፡ ሲፀንሱ ፡ ያውቁ
ታል ፤ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ኩላሊታቸው ፡
ይጮሃል ፤ ጡታቸው ፡ ይጠቁራል ፡
ከንፈራቸው ፡ ያራል ፡ ጺቅ ፡ ጺቅ ፡
ያሰኛቸዋልና ፡ በዚህ ፡ አውቃ ፡ እን



ድም ፡ ዕንስ ፡ አታሳስትም ፡ ነበርና ፡
፪ሳሙ ፡ ፲፩-፩-፳-፩ ።

ዳዊትም ፡ ዖርዮን ፡ የጦር ፡ ወሬ ፡ የም
ጠይቀው ፡ ነኝና ፡ ላክልኝ ፡ ብሎ ፡
ወደ ፡ ኢዮአብ ፡ ይልክበታል ፡ ዕንስ ፡
ያሳስትልኛል ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ለፀብዕ ፡ አይደለም ፡ ሲመጣ ፡ እንደ
ምን ፡ ናችሁ ፡ አለው ። አምላከ ፡ ሸ
ኤል ፡ ፈጣሪህ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡
አንባውን ፡ ከበን ፡ ወህውን ፡ ደፍ
ነን ፡ ደንጊያውን ፡ ኩልኩለን ፡ አስ
ጨንቀን ፡ አስጠብበን ፡ ይዘናቸዋል ፤
ድል ፡ የምንነሣቸው ፡ ይመስለኛል ፡
አለው ፤ አብልቶ ፡ አጠጥቶ ፡ ከቤት
ህ ፡ ግባ ፡ አለው ፤ እንደጃን ፡ ተከል ፡
ድንኳን ፡ አስተክሎ ፡ ድንክ ፡ አልጋ ፡
አስመጥቶ ፡ ከዘበኛው ፡ ጋራ ፡ አደረ ፤
ኢወረደ ፡ ዖርዮ ፡ ከቤቱ ፡ አልገባም ፡
ብለው ፡ ይልኩበታል ፡ እንድም ፡
እሷ ፡ ትልክበታለች ፡ በነጋውም ፡ ከ
ዚያ ፡ አደረ ፤ በሦስተኛው ፡ የሚያ
ስጠግ ፡ ምግብ ፡ መግበ ፡ የሚያሰክር ፡
ጽኑ ፡ መጠጥ ፡ ስጠው ፡ ሲል ፡ አመሸ ፡
ያም ፡ የሚጠጣ ፡ መስሎ ፡ እየተቀ
በለ ፡ ለብላቴኖች ፡ ሲሰጥ ፡ አመሸ ።
ወጽአ ፡ ስኩሮ ፡ የሰከረ ፡ መስሎ ፡ እ
የተንገደገደ ፡ ወጣ ፡ ለዳዊት ፡ ስለመ
ሰለው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከአእምሮው ፡
አልተለየም ፡ ማለት ፡ የሰከረ ፡ ሰው ፡
ስንኳን ፡ ከምትገባው ፡ ከሚስቱ ፡ ከማ
ትገባው ፡ ከሰው ፡ ሚስት ፡ ይሄዳል
ና ፤ አከኑ ፡ እትወትከ ፡ እምሐቅል ፡
የመጣህ ፡ ከዘመቻ ፡ አይደለምን ፡
ከቤትህ ፡ ግባ ፡ የልጅ ፡ ከንፈር ፡ የሴ
ት ፡ ፍቅር ፡ አይናፍቅህምን ፡ በዚያ
ውስ ፡ ላይ ፡ ለሴቶች ፡ ንጽሕና ፡ ይስማ
ማቸዋልን ፡ ይቻላቸዋልን ፡ አለው ፤
ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጌታዬ ፡ ኢ
ዮአብ ፡ ወንድሜ ፡ አቢሳ ፡ አፅላፈ ፡
እስራኤል ፡ የቀን ፡ ሐሩር ፡ የሌሊት ፡
ቍር ፡ እየወረደባቸው ፡ እኔ ፡ ከቤቴ ፡
ተድላ ፡ ደስታ ፡ አደርጋለሁን ፡ አ
ለው ፡ ፪ሳሙ ፡ ፲፩-፮-፲፬ ። ለካ ፡ ይህ ፡
ባርያ ፡ አውቆብኛልሳ ፡ ይከተታት ፡
ብሎኝ ፡ አይደለምን ፡ ብሎ ፡ ጠግረ ፡
ሞቱን ፡ አሲይዞ ፡ ይሰደዋል ፤ ቅድ
መ ፡ አብዕዎ ፡ ለአርዮ ፡ ውስተ ፡ ዓቢ
ይ ፡ ቀትል ፡ ጦባህየ ፡ ይሙት ፡ ብሎ ፡
ምነው ፡ ከመንገድ ፡ አይመለከተው
ም ፡ ነበርን ፡ ቢሉ ፤ መልከዐ ፡ ፊደል ፡
የማያውቅ ፡ ጨዋ ፡ ነበርና ፤ ከሸኤ
ልስ ፡ ለደብዳቤ ፡ ያሀል ፡ ያልተማረ ፡
ጨዋ ፡ የለባቸውም ፡ ብሎ ፡ በፍቅር ፡
ተቀብሎ ፡ በፍቅር ፡ ስለሸኘው ፡ ባይ
ጠራጠር ፤ እንድም ፡ ዳዊትና ፡ ኢዮ
አብ ፡ የሚነጋገሩበት ፡ እንደ ፡ እንቆ
ቅልኽ ፡ ያለ ፡ ነበርና ፡ ቋንቋ ፡ ቢለወጥ
በት ፤ እንድም ፡ ራስ ፡ ራሱን ፡ የሚያ
ይ ፡ ብላቴና ፡ ተከትሎት ፡ ነበርና ፤ እ
ንድም ፡ የንጉሥ ፡ ደብዳቤ ፡ በወርቅ ፡
ቀለም ፡ ተጽፎ ፡ በእንበሳ ፡ ማኅተም ፡
ታትሞ ፡ ከደረሰበት ፡ ተሰብሮ ፡ ይታ
ያል ፡ እንጂ ፡ ከመንገድ ፡ አይታይ
ምና ፤ ወስዶ ፡ ለኢዮአብ ፡ ሰጠው ፡

እሱም ፡ ተመልክቶ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመ
ር ፡ ምነው ፡ ታለቅሳለህ ፡ አለው ፡ ያመ
ጣሃት ፡ ደብዳቤ ፡ አዕንታችሁ ፡ ተዋ
ጉ ፡ ከነዚያ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አይትረፍ
በችሁ ፡ ከናንተ ፡ አንድ ፡ አይሙት
በችሁ ፡ ትላለች ፡ የድል ፡ ነገር ፡ አ
ንድ ፡ ቀን ፡ ላንዱ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡
ላንዱ ፡ ነው ፤ እሕዛብ ፡ ድል ፡ ያደ
ረጉ ፡ እንደሆነ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ይጐዳ
ል ፡ ብዬ ፡ ነዋ ፡ አለው ፤ ጠላት ፡ ሴት ፡
ይመስል ፡ ቢያለቅሱለት ፡ ይመለሳ
ልን ፡ ብጭር ፡ ታጥቆ ፡ ዘገር ፡ ነጥቆ ፡
ቢሄዱበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አሁንም ፡
አንተ ፡ ጌታዬ ፡ ላም ፡ እንዳየ ፡ አን
በሳ ፡ ነህ ፡ ወንድሜ ፡ አቢሳ ፡ ፍየል ፡
እንዳየ ፡ ነብር ፡ ነው ፤ እኔም ፡ እንዳ
ቅሜ ፡ በግ ፡ እንዳየ ፡ ተኩላ ፡ ነኝ ፡
ኃያላኑ ፡ በሉበት ፡ በዕኑ ፡ ስፍራ ፡
አውለኝ ፡ አለው ፤ ይህንንስ ፡ አን
ተም ፡ በትለኝ ፡ ያመጣሃት ፡ ደብዳቤ ፡
ነግራኛለች ፡ አለው ፤ ፪ሳሙ ፡ ፲፩-፲፪-፲፮
በልቦናው ፡ ሠውረህ ፡ አድርግ ፡ ያለ
ውን ፡ ሰላሳ ፡ ስድስት ፡ መማክርት ፡
ነበሩት ፤ ከረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጋራ ፡ የዳዊትን ፡ መንግሥት ፡ ያፀኑ ፡
ናቸው ፡ ከጌታችን ፡ ከዳዊት ፡ አር
ዮን ፡ ግደሉ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ መ
ጥቷልና ፤ የሚድንበትን ፡ ምክንያት ፡
ፈልጉለት ፡ አላቸው ፤ እስመ ፡ ኃያ
ል ፡ ቃለ ፡ ንጉሥ ፡ እንዲል ፡ የንጉሥ ፡
ቃል ፡ አነሰ ፡ ብለው ፡ አይጨምሩ
በት ፤ ረዘመ ፡ ብለው ፡ አያሳጥሩት ፡
የራቀውን ፡ ያቀርባል ፤ የቀረበውን ፡
ይጠቅሳል ፤ በዚያውም ፡ ላይ ፡ ዳዊ
ት ፡ ልበ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ከኛ ፡ ከተ
ለየ ፡ የተገለፀለት ፡ እንዳለ ፡ እናውቃ
ለንን ፡ ይልቅስ ፡ ያዘዘህን ፡ አድርግ ፡
አሉት ፡ ሄደው ፡ ገጠሙ ፡ አርዮም ፡
ጦር ፡ ሲያይ ፡ እንደተጠማ ፡ ዋልያ ፡
ላም ፡ እንዳየ ፡ አንበሳ ፡ ነውና ፤ እየ
ደነፋ ፡ ሄዶ ፡ ገጠመ ፤ ባይን ፡ ጥቅሻ ፡
በከንፈር ፡ ንክሻ ፡ አሉንጋ ፡ አጩኹ
ው ፡ ጥለውት ፡ ሸሹ ፡ ምንተ ፡ ከን
ከሙ ፡ አዕላፈ ፡ ኳኤል ፡ እያለ ፡ ብቻ
ውን ፡ ተደብድቦ ፡ሙቷል ፡ ምንተ ፡
ኮንከሙ ፡ ማለቱ ፡ ስለምን ፡ ነጠ ፡
ቢሉ ፡ ልማድ ፡ ቢለወጥበት ፡ ለልማ
ዱ ፡ ኳኤል ፡ ድልም ፡ ቢሆን ፤ ድልም ፡
ቢያደርጉ ፡ እንደሐማሴን ፡ ሰው ፡
ወደፊት ፡ ጥሰው ፡ ይሄዳሉ ፡ እንጂ ፡
ወደኋላ ፡ አይመለሱም ፡ ነበርና ፡ ይ
ኸውም ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ አርዮ ፡ የጌታ ፡
ጠማሪ ፡ ሞቱን ፡ ይዞ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡
ወደ ፡ አራብት ፡ እንደሄደ ፡ ጌታም ፡
ከሊቶስጥራ ፡ ወደ ፡ ቀራንዮ ፡ መስ
ቀሉን ፡ ተሸከሞ ፡ ሄዷልና ።

ኋላ ፡ ግን ፡ እግበ ፡ መልስ ፡ ብለው ፡
ድል ፡ አድርገዋቸዋል ፤ ኢዮአብም ፡
ወደ ፡ ዳዊት ፡ ከጦር ፡ ያልዋለ ፡ ብላቴ
ና ፡ ይልክል ፡ አሽከሮችህ ፡ እነዕገሌ ፡ እ
ነዕገሌ ፡ አለቁ ፡ ብለህ ፡ ንገረው ፡ ይቈጣ
ል ፡ አርዮ ፡ ባሪያህም ፡ እንጂ ፡ ሞተ ፡
በለው ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ይወሰናል ፡
ብሎ ፡ ሰው ፡ እንደነገሩት ፡ በቅሎ ፡



እንዳሰገሩት ፡ ነውና ፤ ያውም ፡ አፈ
ሌ ፡ ወታደር ፡ ያልነገሩትን ፡ ጨምሮ ፡
መናገር ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፤ ሞዑነ ፡
ወአውጽኡነ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወ
ድኀረ ፡ ተመየጥናሆሙ ፡ ወእግባዕና
ሆሙ ፡ እስከ ፡ ቅዕረ ፡ ሀገር ፡ እስቀ
ድመው ፡ ድል ፡ ነስተው ፡ ወደ ፡ ዱር ፡
አባረሩን ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ እግባ ፡ መል
ስ ፡ ብለን ፡ ድል ፡ አደረግናቸው ፡
ወነደፉነ ፡ ሰብአ ፡ ሐፅ ፡ ወኀልቁ ፡ ደ
ቅከ ፤ በጦር ፡ በጠጠር ፡ ብለው ፡ አ
ሽከሮችህ ፡ አለቁ ፡ አለው ፡ ዳዊትም ፡
ሰምቶ ፡ ዛሬስ ፡ ኢዮአብ ፡ አረጀና ፡
የጦር ፡ መላ ፡ ያጠፋል ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡
ተቈጣ ፡ ለምንት ፡ ቀረብከሙ ፡ ኀበ ፡
ዓረፍት ፡ ኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ ትቈ
ስሉ ፡ ወትመውቱ ፤ መኑ ፡ ቀተሎ ፡
ለአቤሜሌክ ፡ ወልደ ፡ ሮብዓም ፡ አ
ኮኑ ፡ ብእሲት ፡ ወገረት ፡ ላዕሌሁ ፡
ስባረ ፡ ማሕረፅ ፡ ወሞተ ፡ በቴምናስ ፡
ሀገር ፡ መሳ ፡ ፱-፶-፶፫ ። በቅዕር ፡ ተጠግ
ታችሁ ፡ ለምን ፡ ተዋጋችሁ ፡ የሮብዓ
ምን ፡ ልጅ ፡ አቤሜሌክን ፡ ማን ፡ ገደ
ለው ፡ ሴት ፡ የወፍጮ ፡ ስባሪ ፡ በመስ
ኮት ፡ አገልቃ ፡ የገደለችው ፡ አይደ
ለምን ፡ አለው ፡ ኳኤል ፡ ከዚህ ፡ የተነ
ሣ ፡ ቅጽር ፡ ተጠግታችሁ ፡ አትዋጉ ፡
ብለው ፡ ሥርዓት ፡ ሠርተው ፡ ነበርና ፤
ባሪያህ ፡ አርዮም ፡ እንጂ ፡ ሞተ ፡ አለ
ው ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ጠላት ፡ የጠፋል
ኝ ፡ መስሎት ፡ ኢዮአብን ፡ እንዲህ ፡
በለው ፡ በ ፡ እመ ፡ ከመዝ ፡ ወበ ፡ እመ ፡
ከማሁ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
እንደአባቱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ እ
ናቱ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
ደስ ፡ ሲለው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲያዝን ፡
ነው ፤ ድል ፡ አደረግሁ ፡ ብለህ ፡ ደስ ፡
አይበልህ ፤ ሰው ፡ አለቀብኝ ፡ ብለህ ፡
አትዘን ፤ ጦርም ፡ አንሰህ ፡ እንደሆነ ፡
እጨምርልሃለሁ ፡ በለው ፡ ብሎ ፡ ይ
ልከበታል ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፩-፲፮-፭ ።

በዳዊት ፡ ጊዜ ፡ የነበረ ፡ ነቢይ ፡ ናታ
ን ፡ ይባላል ፤ ጌታ ፡ በዳዊት ፡ ናታንን ፡
ያዳኝበታል ፡ የዳዊትን ፡ ነገር ፡ እየ
ሀ ፡ የበጉ ፡ እብነት ፡ ይሆናል ፤ ብዬ ፡
ሳአልን ፡ ገድዬ ፡ በነግሠው ፡ የከፋ ፡
አብነት ፡ ሲሆን ፡ እኔማ ፡ ምን ፡ ዕዳዬ ፡
ለርሱ ፡ ይባሰው ፡ እንጂ ፡ አለው ፡ ቀ
ድሞ ፡ ነቢያት ፡ ዘመን ፡ ሣህል ፡ ወር
ኃ ፡ ሰላም ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ኩፋር ፡ ለብሰ
ው ፡ ኩፋር ፡ ጠምጥመው ፡ በአምባላ
ይ ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጠው ፡ መነሳንስ ፡
ይዘው ፡ ይታያሉ ፤ ዘመን ፡ ፀብዕ ፡ ወ
ርኅ ፡ ኅዘን ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ከል ፡ ለብሰ
ው ፡ ከል ፡ ጠምጥመው ፡ ዘገር ፡ ይዘ
ው ፡ ይታያሉ ፤ በዚህ ፡ ልማድ ፡ እን
ዲህ ፡ ሆኖ ፡ ሄደ ፡ ሰላምኑ ፡ ፡ ምጽአ
ትከ ፡ ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡ እመጣ
ጥህ ፡ ለደህና ፡ ነውን ፡ አለው ፤ ደህና
ስ ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡
እነግርህ ፡ ብዬ ፡ አለው ፡ ንገረኝ ፡ አለ
ው ፡ በዚህ ፡ በከተማህ ፡ ሁለት ፡ ሰዎ
ች ፡ አሉ ፤ አንዱ ፡ ባለፀጋ ፡ አንዱ ፡

2014 04 17

ድኃ ፡ ለባለፀጋው ፡ መቶ ፡ በጐች ፡ አ
ሉት ፡ ለድኃው ፡ አንዲት ፡ በግ ፡ አለ
ችው ፡ እም፲፱በልዐ ፡ ያበልዓ ፡ ወእም
፲፱ሰትየ ፡ ያሰትያ ፡ ከበላው ፡ ያበላታ
ል ፡ ከጠጣው ፡ ያጠጣታል ፡ ከጠገቡ ፡
ያስተኛታል ፤ ወይሬእያ ፡ ከመ ፡ ወለ
ቱ ፡ እንደልጁ ፡ ያያታል ፤ እንዲህ ፡
ሲለው ፡ ያውቅበታል ፤ አንድም ፡ ከ
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተለየበት ፡ ወራት ፡
ነውና ፡ አያውቅበትም ፤ አደራ ፡ እስ
ጠብቆት ፡ ሄዶ ፡ እንግዳ ፡ ቢመጣበ
ት ፡ መቶ ፡ በጎች ፡ እያሉት ፡ ከመንጋ
ው ፡ ያንሱብኛል ፡ ከቊጥር ፡ ይጐሉብ
ኛል ፡ ብሎ ፡ አንዲቱን ፡ የድኃ ፡ በግ ፡
አርዶ ፡ አወራርዶ ፡ እንግዳውን ፡ ሸኘ
ባት ፤ እርሱንም ፡ ለሰው ፡ ይነግርብ
ኛል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያዳኝብኛል ፡
ብሎ ፡ ገደለው ። በዚህ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ አዝኗል ፡ አለው ፤ ዳዊትም ፡
ተቈጣ ፤ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የ
ጦር ፡ ምሳ ፡ እንዳደርገው ፡ ሀየንተ ፡
አሐቲ ፡ በግዕት ፡ ይትፈደይ ፡ ትርብዕ
ተ ፡ ወሀየንተ ፡ አሐቲ ፡ ላሕም ፡ ይትፈ
ደይ ፡ ትሕምስተ ፡ ፲፱ ፡ ፳፱ - ፩ ። በጠፋ
ውም ፡ ገንዘብ ፡ ባንድ ፡ አራት ፡ አምስ
ት ፡ ይከፈላል ፡ አለው ። ፪ ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፩-፯ ።
አንጉሥ ፡ ፈታሕከ ፡ በርእስከ ፡ አኮኑ ፡
አንተ ፡ ገበሬሁ ፡ ለዝ ፡ ኵሉ ፡ ንጉሥ ፡
በራስህ ፡ ፈረድህ ፤ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያ
ደረግህ ፡ አንተ ፡ ነህ ። አንተ ፡ ገበር
ከ ፡ በኀቡዕ ፡ ወአነ ፡ እከሥቶ ፡ በቅ
ድመ ፡ ገጸ ፡ ፀሐይ ፡ አንተ ፡ በስው

ር ፡ ያደረግሁት ፡ ይመስልሃል ፤ እኔ ፡
ግን ፡ በጣይ ፡ በጉባይ ፡ እንዲሉ ፡ በጉ
ባዔ ፡ እገልጽብሃለሁ ፡ ብሏል ፤ ባለ
ፀጋ ፡ የተባልህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ ድኃ ፡
የተባለ ፡ ኦርዮ ፡ ነው ፤ መቶ ፡ በጎች ፡
የተባሉ ፡ አሥሩ ፡ ዕቁባቶችህ ፡ ናቸ
ው ፤ አንዲት ፡ በግ ፡ የተባለች ፡ ቤር
ሳቤህ ፡ ናት ፤ እንግዳ ፡ የተባለ ፡ ፈቃ
ደ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፤ ፈቃደ ፡ ሥጋ ፡ ቢነ
ሣብህ ፡ አሥር ፡ ዕቁባት ፡ እያሉህ ፡
በአንዲት ፡ በኦርዮ ፡ ሚስት ፡ በቤርሳ
ቤህ ፡ ደረስህ ፤ እሱንም ፡ ለሰው ፡ ይ
ነግርብኛል ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ያዳ
ኝብኛል ፡ ብለህ ፡ አስገደልከው ፤ በ
ዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዝኖብሃል ፡
አለው ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፯ - ፲፭ ።

ከእግዚአብሔርማ ፡ ተጣልቼ ፡ የም
ወጣበት ፡ ቀዳዳ ፡ የምሮጥበት ፡ ሜዳ ፡
የምንጠለጠልበት ፡ ቅጠል ፡ የምጠ
ጋበት ፡ ገደል ፡ የምመከተው ፡ ጋሻ ፡
የምሠወርበት ፡ ዋሻ ፡ የለኝ ፤ ምን ፡
ይበጀኛል ፡ እያለ ፡ ከእግሩ ፡ በታ
ች ፡ ይወድቅ ፡ ይነሣ ፡ ጀመረ ፤ መር
ዙንማ ፡ ነግሬ ፡ መድኃኒቱን ፡ ሳል
ነግርህ ፡ እቀራለሁን ፤ ንስሐ ፡ ብትገ
ባ ፡ ይቅር ፡ ይልሃል ፡ አለው ፤ በዚህ ፡
ጊዜ ፡ ጉድጓድ ፡ ምሶ ፡ አመድ ፡ ነስን
ሶ ፡ ማቅ ፡ ምንጣፍ ፡ ለብሶ ፡ ሱባዔ ፡ ገብ
ቶ ፡ ተናግሮታል ። ፪ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፲፪-፲፫ ።
አቤቱ ፡ ሰብአ ፡ ትክትን ፡ በጠፋህበ
ት ፡ መዓትህ ፡ አታጥፋኝ ። ዘፍ ፡ ፮ ፡
፲፯ - ፳፱ ።



ወበመቅሠፍትከ ፡ ኢትገሥፀኒ ።

ሰብአ ፡ ሰዶም ፡ ሰብአ ፡ ገሞራን ፡ በ
ጠፋህበት ፡ መዓትህ ፡ ፡ አታጥፋኝ ።
ዘፍ ፡ ፲፱ - ፳፱ - ፳፭ ።

አንድም ፡ የጉልማሳ ፡ ሚስት ፡ ነሣ ፡ ጉ
ልማሳ ፡ ገደለ ፡ ብለህ ፡ አታጥፋኝ ።
፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፭ - ፱ - ፲፯ ።

አንድም ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ አታጥ
ፋኝ ፡ ለማለት ፡ ደጋገመው ።

፪ ፡ ተሣሃለኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ድውይ ፡ አነ ።

አቤቱ ፡ ድውየ ፡ ኃጢአት ድውየ ፡
ንስሐ ፡ ነኝና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ማረኝ ።

ወፈውሰኒ ፡ እስመ ፡ ተሀውከ ፡ አዕፅምትየ ።

ሥጋዬም ፡ በለመከራ ፡ ሆኗልና ፡ አ
ድነኝ ።

፫ ፡ ነፍስየኒ ፡ ተሀውከት ፡ ፈድፋደ ።

ነፍሴም ፡ ፈጽማ ፡ በለመከራ ፡ ሆናለ
ችና ፤ አንድም ፡ (ወፈውሰኒ ፡ እስመ ፡
ተሀውከ ፡ አዕፅምትየ) ፡ ነፍሴም ፡ ባለ
መከራ ፡ ሆናለችና ፤ አፅም ፡ በሥጋ ፡
ተሠውሮ ፡ ለሥጋ ፡ ኃይል ፡ ፅንዕ ፡ እን
ዲሆን ፡ ነፍስም ፡ በሥጋ ፡ ተሠውራ ፡
ለሥጋ ፡ ኃይል ፡ ፅንዕ ፡ ትሆናለችና ፡
ዓፅም ፡ አሳት ፡ ዓቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ኀሥ
ሥ ፡ ፈውስ ፡ ለሥጋከ ፡ ወሥራየ ፡ ለ
አዕፅምቲከ ፡ እንዲል ። ምሳ ፡ ፫ ፡ ፰ ።
(ነፍስየኒ ፡ ተሀውከት ፡ ፈድፋደ) ፡ ሥ
ጋዬም ፡ በለመከራ ፡ ሆናለች ።

ወአንተኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ።

አንተም ፡ እንደሰው ፡ መች ፡ ይረዳኛ
ል ፡ የሚሉህ ፡ ሆንህን ፡ ሰውን ፡ እር

ዳኝ ፡ ያሉት ፡ እንደሆነ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡
በዚህ ፡ ወር ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ይላል
ና ። አንድም ፡ አንተም ፡ እንደሰው ፡
እንገሮተ ፡ ጽኑ ፡ ሆንህን ። አንድም ፡
ከንቱማ ፡ ጋራ ፡ ተጣልቼ ፡ እስከ ፡ መ
ቼ ፡ ድረስ ፡ ነዋ ፤ ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደ
ሆነ ፡ ሲሞት ፡ ሲሻር ፡ አርፈዋለሁ ፡
ይባላል ፤ ሲሞት ፡ አርፈዋለሁ ፡ እንዳ
ልልህ ፡ በባሕርይህ ፡ ሞት ፡ የለብህ ፡
ሲሻር ፡ አርፈዋለሁ ፡ እንዳልልህ ፡ በ
መንግሥትህ ፡ ኅልፈት ፡ ሽረት ፡ የለ
ብህ ።

፬ ፡ ተመየጥ ፡ እግዚኦ ፡ ወባልሃ ፡ ለነፍስየ ።

እንዲህ ፡ ነውና ፡ አቤቱ ፡ ከመዓት ፡
ወደ ፡ ምሀረት ፡ ከቁጣ ፡ ወደ ፡ ትዕግ
ሥት ፡ ተመልሰህ ፡ ነፍሴን ፡ አድናት ።

ወአድኅነኒ ፡ በእንተ ፡ ምሀረትከ ።

ስምየኒ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ስ
ላልህ ፡ በስምህ ፡ ስለአመንኩ ፡ ስምህ
ን ፡ አማላጅ ፡ ስለአደረግሁ ፡ አድነኝ ።

፭ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ በውስተ ፡ ሞት ፡ ዘይዜክረከ ።

ከሞት ፡ በኋላ ፡ ገነናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡
ለመከር ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ የሚለምን
ህ ፡ የለምና ።

ወበሲኦልኒ ፡ መኑ ፡ የአምነከ ።

በመቃብርም ፡ ልብስ ፡ ጉርስ ፡ ስጠኝ ፡
ብሎ ፡ የሚያመሰግንህ ፡ የለምና ፤ እ
መኖ ፡ ወልድየ ፡ እንዲል ፤ አእኵቶ
ሲል ፡ ነው ፤ አንድም ፡ እልበና ፡ መ
ኑ ፡ ይወራረሳሉ ፤ እስመ ፡ መኑ ፡ ፲፱

ዜነም ፡ መኑ ፡ ዘይክል ፡ ነቢበ ፡ ዕበ
የኪ ፡ እንዲል ፤ (እስመ ፡ አልቦ ፡ በ
ውስተ ፡ ሞት ፡ ዘይዜክረከ ፡ ወበሲ
ኦል ፡ (መኑ) ፡ አልቦ ፡ ዘየአምነከ ፡
ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በመቃብር ፡ ዝናም ፡
ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ ልብስ ፡ ጉ
ርስ ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ የሚያመሰግንህ ፡
የለምና ፡ ኑሬ ፡ አመሰግንህ ፡ ዘንድ ፡
አድነኝ ፡ እንጂ ፥ እኔማ ፡ ከሌለሁ ፡ የ
ሚያመሰግንህ ፡ ማነው ፡ በዚህም ፡ መ
ጻሕፍት ፡ ተባብረውበታል ፤ ሲራክ ፡
መኑ ፡ ዘይሴብሖ ፡ ለልዑል ፡ በውስተ ፡
መቃብር ፡ ብሎ ። ሲራ ፡ ፲፯ ፡ ፳፯ ። ዮ
ሐንስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡
መኑ ፡ ዘይሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
እምዓላውያን ፡ በእንተ ፡ ዓሊዎታ ፡
ለነፍሱ ፡ ብሏል ።

፯ ፡ ወረኀኩ ፡ በምንዳቤየ ።

ወድጄ ፡ በሠራሁት ፡ ሥራ ፡ ጠፋሁ ።

ወእሐፅብ ፡ ኵሎ ፡ ሌሊተ ፡ ዓራትየ ።

በሌሊት ፡ አልጋዬን ፡ አፀብኩ ።

ወበአንብዕየ ፡ አርጥብኩ ፡ ምስካብየ ።

በዕንባዬ ፡ መኝታዬን ፡ አራስኩ ፥ አሁ
ን ፡ ጉድጓድ ፡ ምሶ ፡ አመድ ፡ ነስንሶ ፡
ማቅ ፡ ለብሶ ፡ ንስሓ ፡ ገባ ፡ ብሎ ፡ አል
ነበረምን ፡ ቢሉ ፥ ንጉሥ ፡ የተቀመ
ጠበት ፡ ሁሉ ፡ ዙፋን ፡ ይባላልና ።
እንድም ፡ ሥርዓት ፡ (ዓራተ) ፡ መን
ግሥት ፡ አይጥፋ ፡ ብለው ፡ ድንክ ፡
አልጋ ፡ አስቀምጠውለት ፡ ነበር ፥ ያን ፡
ተጠግቶ ፡ ሲያለቅስ ፡ ዕንባው ፡ እየ
ተፈነጠቀ ፡ ይረጨው ፡ ነበርና ፡ እን
ዲህ ፡ አለ ። የዕንባውንም ፡ መጠን ፡
ከዚህ ፡ ይናገሩታል ፤ ተቀምጦ ፡ ሲያ
ለቅስ ፡ ከንድ ፥ ቆሞ ፡ ሲያለቅስ ፡ ስን
ዝር ፡ ከመሬት ፡ ይገባ ፡ ነበር ፤ ይህ
ም ፡ ሊታወቅ ፡ በእንባው ፡ የበቀለ ፡
ሰርዶ ፡ ሰውነቱን ፡ ተብትቦ ፡ ይዞት ፡
ብላቴኖቹ ፡ በመቀስ ፡ እያረፉ ፡ አው
ጥተውታል ፡ ይላሉ ፤ ይኸውም ፡ በ
ዜና ፡ እስክንድር ፡ ታውቋል ።

፰ ፡ መተሀውከት ፡ እመዓት ፡ ዓይንየ ፤

ሰብእ ፡ ትካትን ፥ ሰብእ ፡ ሰዶም ፥ ሰብአ ፡
ገሞራን ፡ ባጠፋህበት ፡ መዓትህ ፡ ታጠ
ፋኝ ፡ ይሆን ፡ ከማለቴ ፡ የተነሣ ፡ ዓይኔ ፡
ባከነች ፥ እንደ ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡
ጨንገር ፡ ያነሱብቸው ፡ እንደሆነ ፥ ከ
አሁን ፥ አሁን ፡ ጣሉብን ፡ ይሆን ፡
እያሉ ፡ ዓይናቸው ፡ እንዲባክን ፥ እን
ድም ፡ ከመፍረድህ ፡ የተነሣ ፡ ሰው
ነቴ ፡ ባለመከራ ፡ ሆነች ፤ እንድም ፡
(እመዓተ ፡ አንብዕየ ፡ ዐይንየ) ፡ ይላል ፤
ከቊጡ ፥ ዕንባዬ ፡ የተነሣ ፡ ዓይኔ ፡
ሠለተ ፤ ቁጡ ፡ ዕንባ ፡ ፊት ፡ ያንጣ
ጣል ፡ ቅንድብ ፡ ይመልጣልና ፡ እን
ዲህ ፡ አለ ።

ወበለይኩ ፡ በኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ ጸላእትየ ።

በጠላቶቼ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፥ ጠፋሁ ፤
ወበልየ ፡ ነገር ፡ እምእፉክሙ ፡ እን
ዲል ፥ ሳለሁ ፡ እንደሌለሁ ፡ ሳልሞት ፡
እንደሞትኩ ፡ ሆንሁ ።



፱ ፡ ረኀቁ ፡ እምኔየ ፡ ኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ፡
ማቴ ፡ ፯ ፡ ፳፫ ።

ጉልማሳ ፡ ገደለ ፡ የጉልማሳ ፡ ሚስት
ነጣ ፡ እያላችሁ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ ጋራ ፡ የም
ታጣሉኝ ፡ (አጋንንት) ፡ ከኔ ፡ ራቁልኝ ።

እስመ ፡ ሰምዓኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃለ ፡ ብካይየ ።

እግዚአብሔር ፡ አልቅሼ ፡ የለመንሁ
ትን ፥ ልመናዬን ፡ ሰምቶኛልና ።

፲ ፡ መተወከፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስእለትየ ።

እግዚአብሔር ፡ ልመናዬን ፡ ሰምቶ
ኛልና ፥ ናታን ፡ ነቢዩ ፡ መጥቶ ፡ ተዓ
ደዋ ፡ ለኃጢአትከ ፥ በነፍስህ ፡ ይቅር
ብሎሃል ፥ በሥጋህ ፡ ግን ፡ ኃጢአት ፡
ያለፍዳ ፡ አይነፃምና ፥ ከአብራክህ ፡
የተከፈለ ፡ ልጅህ ፡ መንግሥትህን ፡
ይቀማሃል ፡ እዋጋለሁ ፡ አትበል ፡ ብሎ
ታል ፥ ፪ሳሙ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱-፲፰ ። በምንት ፡
አእምር ፡ ከመ ፡ ይከውን ፡ ዝንቱ ፤ ይህ ፡
እንዲደረግ ፡ በምን ፡ አውቃለሁ ፡ አ
ለው ፤ የተፀነሰው ፥ ብላቴና ፡ ይሞ
ታል ፥ ፪ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፲፱ ። እሷን ፡ አግባት ፥
ንጉሥ ፡ የደረሰበትን ፡ አንበሳ ፡ የሰ
በረውን ፡ የሚደፍረው ፡ የለምና ፤
ወንድ ፥ ልጅ ፡ ትወልድልሃለች ፡ ስሙ
ንም ፡ ሰሎሞን ፡ በለው ፤ ሰሎሞንም ፡
ማለት ፡ መስተሳልም ፡ ማለት ፡ ነው ፤
፪ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮-፳፯ ። ያም ፡ ብላቴና ፡
ታመመ ፥ ፪ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭ ። ዳዊትም ፡ እ
ንደገና ፡ ጉድጓድ ፡ ምሶ ፥ አመድ ፡
ነስንሶ ፥ ማቅ ፡ ለብሶ ፡ ሱባዔ ፡ ገባ ፤
ስለምን ፡ ቢሉ ፥ ግደልልኝ ፡ ብሎ ፡
ዳዊትን ፡ ያህል ፡ ሰው ፡ ልጄን ፡ ግደ
ልልኝ ፡ ብሎ ፡ እያመለከትም ፡ ብሎ ፡
እኔን ፡ በነፍሴ ፡ ይቅር ፡ እንዳልከኝ ፡
ብላቴናውንም ፡ በሥጋው ፡ ይቅር ፡ በለ
ው ፡ ብሎ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብላቴና
ው ፡ ሞተ ፤ ታመመ ፡ ብንለው ፡ ሱ
ባዔ ፡ የገባ ፡ ሞተ ፡ ብንለውማ ፡ ዮጊ ፡
ይገብር ፡ እኩየ ፡ ዲበ ፡ ነፍሱ ፡ በገዛ ፡
ጠሩ ፡ ተወግቶ ፡ ይሞት ፡ የለምን ፡ ብለ
ው ፡ ቀስ ፡ ቀስ ፡ እያሉ ፡ ሲጨዋወቱ ፡ ሰም
ቶ ፡ ያ ፡ ብላቴና ፡ ሞተን ፡ አላቸው ፡
አዎን ፡ አሉት ፡ ከሞተማ ፡ ብሎ ፡ በ
ሱባዔ ፡ ጊዜ ፡ የለበሰውን ፡ ጥሎ ፡ ል
ብሰ ፡ መንግሥት ፡ ለብሶ ፡ ከአዳራሹ ፡
ተገኘላቸው ፤ ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሲሆ
ን ፡ መኳንንቱ ፡ ተመራርጠው ፡ ገብ
ተው ፤ ንጉሥ ፡ ፍርድ ፡ ልበስ ፡ ሥ
ርዓት ፡ ተለወጠብን ፡ ጥንቱን ፡ ለል
ማዱ ፡ ሰው ፡ ሲሞት ፡ አጥብቆ ፡ ይታዘ
ንለታል ፡ ይለቀስለታል ፤ አንተ ፡ ግን ፡
ታመመ ፡ ብንልህ ፡ ያን ፡ ያህል ፡ መ
ከራ ፡ ተቀበልከ ፥ ሞተ ፡ ብንልህ ፡ ይ
ህን ፡ ያህል ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አደረ
ግህ ፡ አሉት ፤ ምን ፡ ላድርግ ፡ እኛ ፡
ወደሱ ፡ እንሄዳለን ፡ እንጂ ፡ እሱ ፡ ወ
ደኛ ፥ ይመጣልን ፥ ይገብዕኑ ፡ ማይ ፡
ድኅረ ፡ ተክዕወ ፥ ወሀ ፡ ከፈሰሰ ፡ ይታ
ፈሳልን ፥ ወፍስ ፡ ከበረረ ፡ ይያዛልን ፤
አላቸው ፡ ፪ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፲፮-፳፫ ።

መተወከፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸሎትየ ።

እግዚአብሔር ፡ ልመናዬን ፡ ተቀብሎ
ኛልና ፥ እንድም ፡ (ረኀቁ ፡ እምኔየ ፡

ዞ·ልክሙ ፡ ገበርት ፡ ዓመፃ) ። ዕፀ ፡ በለ
ስን ፡ በላ ፡ እያላችሁ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ ጋራ ፡
የምታጣሉኝ ፡ አጋንንት ፡ ከኔ ፡ ራቁ
ልኝ ፤ (እስመ ፡ ሰምዓኒ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ቃለ ፡ ብካይየ) ፤ እግዚአብሔ
ር ፡ አልቅሼ ፡ የለመንኩትን ፡ ልመና
ዬን ፡ ሰምቶልኛልና ።

፲፡ ለይትኀፈሩ ፡ ወይትኀወኩ ፡ ኵሎሙ ፡ ጸላእትየ ።
ጠላቶቼ ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ።
ለይግብኡ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ ወይትኀፈሩ ፡ ፍጡነ ።
አድጎ ፡ እንስ ፤ አድሮ ፡ እንስ ፡ ይኹኑ ፤
ፈጽመው ፡ ፈጥነው ፡ ይፈሩ ፡ ይዋ
ረዱ ።

## መዝሙር ፡ ፫ ።

፩፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ ብከ ፡ ተወከልኩ ፡ ኢት
ኀድፈኒ ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ፡ ነው ።
በአቤሴሎም ፡ ጊዜ ፡ ስለራሱ ፡ ተናግ
ሮታል ፤ ታሪኩ ፡ እግዚአ ፡ ሚበዝ
ኁ ፡ እለ ፡ ይሣቅዩኒ ፡ ካለው ፡ የተያ
ያዘ ፡ ነው ፤ በአርእስቱ ፡ በእንተ ፡
አኪጦፌል ፡ የሚል ፡ ይገኛል ፤ ይህ
ስ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ ተራ ፡
ሚማ ፡ ተሚምቶ ፡ ነጠላ ፡ ልብስ ፡ ለ
ብሶ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ወጥቶ ፡
ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ሰፈረ ። ስለ
ምን ፡ ቢሉ ፤ ሠራዊት ፡ እስኪከተት
ለት ፡ ድረስ ፤ ፪ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ - ፲፰ ።
ካህናቱ ፡ ሳዶቅ ፡ አብያታር ፡ ታቦተ ፡
ጽዮንን ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ ከፍ ፡
ካለ ፡ ከትይዩ ፡ ቦታ ፤ ሰፈሩ ። ስለም
ን ፡ ቢሉ ፤ ካህናት ፡ ፈሊጥ ፡ አዋቆ
ች ፡ ናቸውና ፡ አይቶ ፡ ተመለሱ ፡ ይ
ለናል ፡ ብለው ፤ እንድም ፡ ስንኳን ፡
ንጉሥና ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ቢሆ
ን ፡ ከቤቱ ፡ ከወጣ ፡ ብዙ ፡ የማይገ
በው ፡ ይከተለዋልና ፡ እንዳይነኩኩ ፤
፪ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፳፬ ። አይቶ ፡ እሊህ ፡ እለማ
ናቸው ፤ እለ ፤ ካህናቱ ፡ ሳዶቅ ፡ አብ
ያታር ፡ ታቦተ ፡ ጽዮንን ፡ ይዘው ፡
መጥተዋል ፡ አሉት ፤ እንደወጣሁስ
ብቀር ፡ የሚነግሠው ፡ ልጄ ፡ አይደ
ለምን ፤ ከቦታዋ ፡ ለምን ፡ አወጣች
ኋት ፤ ይልቅስ ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ የተመ
ከረውን ፡ ላኩብኝ ፤ ፈጣሪዬ ፡ ለመ
መለስ ፡ ቢያበቃኝ ፡ ውለታችሁን ፡
አላጠፋም ፡ እከፍላለሁ ፡ አላቸው ፡
ትላንቱን ፡ ሌት ፡ ጌትያዊ ፡ ስድስት ፡
መቶ ፡ ራሱን ፡ ሆኖ ፡ አድሮለት ፡ ነበ
ረና ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ሲል ፡ አገኘ
ው ፤ አንተሳ ፡ ለምን ፡ መጣህ ፡ በመ
ንግሥት ፡ ሳለሁ ፡ አልተሾምህ ፡ አ
ልተሸለምህ ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ ትከ
ተለኛለህን ፤ ይልቅስ ፡ ሕፃን ፤ ንጉ
ሥ ፡ ነግሦልሃልና ፡ ሂደህ ፡ ተሾም ፡
ተሸለም ፡ አለው ፤ አሕዛብ ፡ በገንዘ
ብ ፡ ምኩሐን ፡ ናቸውና ፡ እኔ ፤ ሹመ
ት ፡ ሽልማት ፡ ሽቼ ፡ መች ፡ መጣሁ ፤



አንተን ፡ ጌታዬን ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እን
ጂ ፡ አለው ፤ ፪ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፳፭ ።
ሁለተኛም ፡ ኩሲ ፡ አረጋዊን ፡ አገ
ኘው ፡ አንተስ ፡ ለምን ፡ መጣህ ፡ አ
ለው ፤ ሞትህን ፡ ሞት ፤ ሕይወትህን ፡
ሕይወት ፡ አድርግ ፡ ብዬ ፡ አለው ፤
አንተሰ ፡ ትከውነኒ ፡ ፆረ ፡ ክቡደ ፤
አንተስ ፡ ዕኑ ፡ ሸክም ፡ ትሆንብኛለ
ህ ፤ ጥዬህ ፡ አልሄድ ፡ አንተን ፡ ሳስ
ዘግም ፡ ከመያዝ ፡ አደርስ ፡ የለምን ፤
ይልቅስ ፡ ሽማግሌ ፡ ከምክር ፡ አይለ
ይምና ፤ የተመከረውን ፡ ለካህናቱ ፡
ንገራቸው ፡ ይልኩብኛል ፡ አለው ።
፪ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፳፪ - ፴፯ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቤሴሎም ፡ ነጋሪቱን ፡
እያስጎሰመ ፡ ከከተማ ፡ ገብቶ ፡ ምክ
ሩ ፡ ምክረ ፡ ዘንገብር ፡ ኢዮአብ ፡ አ
ቢሳን ፡ ዳዊትን ፡ ያህል ፡ ጠላት ፡ ከመ
ንግሥት ፡ አስወጥተን ፡ ሰደን ፡ ገዝም
ትላላችሁን ፤ የምንሠራውን ፡ ምከሩ
አላቸው ፤ አኪጦፌል ፡ አሁን ፡ አባት
ና ፡ ልጅ ፡ ፊት ፡ ተጣቂሩ ፡ ብለን ፡ እ
ንመከራለንን ፤ ዕገሌ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ነበር ፤ እገሌም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነበ
ር ፡ እያላችሁ ፡ ነገራችንን ፡ ፈዝ ፡ ለ
ማድረግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ይልቅስ ፡ ቍ
ርዕ ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ አለው ፡ ከመንግ
ሥት ፡ አስወጥቶ ፡ ከመስደድ ፡ የበለ
ጠ ፡ ፀብ ፡ አለን ፡ አለው ፤ እንኪያስ ፡
ባዕ ፡ ኀበ ፡ ዕቁባቲሁ ፡ ዘኀደጎን ፡
ከመ ፡ ይዕቀባ ፡ ቤቶ ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፭ -
፲፯ ። ዕቁባቱ ፡ ቢከተሉት ፡ እላንተን
ግ ፡ ምን ፡ ያደርጋችኋል ፡ ተመልሳች
ሁ ፡ ከተማውን ፡ ጠብቁ ፡ ብሎ ፡ መል
ሷቸው ፡ ነበርና ፡ ገብተህ ፡ በግብር ፡
እወቃቸው ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሸኤል ፡
በቃላቸው ፡ ከመምከር ፡ በእጃቸው ፡
ከመግደል ፡ አያርፉም ፡ አለው ። ድ
ንኳን ፡ አስተክሎ ፡ በዳራሽ ፡ እያገባ ፡
ተጫዋውቶ ፡ በእልፍኝ ፡ እያስወጣ ፡
ስድዷቸዋል ። ዘሌ ፡ ፳ ፡ ፲፩ ። ነገሩን ፡ እ
ንደተቀበለለት ፡ አይቶ ፡ መቻስ ፡ አን
ተ ፡ የምትሻው ፡ የአባትህን ፡ ቍብቾ
በ ፡ አይደለምን ፡ አለው ፤ እንግዲ
ያ ፡ ምን ፡ እሻለሁ ፡ አለው ፤ ሀበኒ ፡
ዕልፈ ፡ ወኽየ ፡ እምሕዝበ ፡ ሸኤል ፡ ካ
ሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እሥራኤል ፡ ዕል
ፍ ፡ ከኹለት ፡ ሽህ ፡ ጦር ፡ ስጠኝ ፡ የምት
ሻውን ፡ ያባትህን ፡ ቍብቾቤ ፡ ቈርጬ ፡
አመጣልሃለሁ ፡ አለው ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፯ ፡
፳፩ - ፳፪ ። ፲፯ ፡ ፩ - ፱ ። አቤሴሎምም ፡ እ
ስኪ ፡ ባአደባባይ ፡ ሽማግሌ ፡ እንዳ
ለ ፡ እዩ ፡ እለ ፤ ኩሲ ፡ አረጋዊ ፡ አለ ፡
አሉት ፤ አስጠርቶ ፡ አንተ ፡ ዳዊት ፡
ወዳጅህ ፡ አልነበረምን ፡ አለው ፤ እ
ውነት ፡ እንጂ ፡ ወዳጄ ፡ ነው ፡ አለው ፤
እንኪያ ፡ ለምን ፡ ቀረህ ፡ አለው ፤ ማ
ን ፡ ነገሠ ፡ ብዬ ፡ እሄዳለሁ ፤ ጥንቱን
ም ፡ አባት ፡ ሲሞት ፡ ልጅ ፡ ሲተካ ፤
ነው ፤ እሱን ፡ እንዳገለገልሁ ፡ አንተ
ን ፡ አገለግላለሁ ፡ ብዬ ፡ ቀረሁ ፡ አለ
ው ፤ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ - ፲፱ ። እንኪያስ ፡
ምክር ፡ አለው ፡ ቆይታ ፡ ካደረጋች
ሁ ፡ ምክር ፡ ከጀመራችሁ ፡ ብዙ ፡ (አ

ያሴ) ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ነገሩን ፣ አልበላሁ ት ፣ ምን ፣ ብዬ ፣ እመክራለሁ ፣ አለው ፣ ከመ ፣ ከመገ ፣ መከረ ፣ አኪጦፌል ፣ አኪጦፌል ፣ እንዲህ ፣ እንዲህ ፣ ብሎ ፣ መከረ ፣ አለው ፣ ምክርከሙ ፣ አሐ ቲ ፣ ወእኪት ፣ ይእቲ ፣ ምክራችሁ ፣ አ ንዲት ፣ ናት ፣ ያችውም ፣ የፀናች ፣ ና ት ፣ እኪትን ፣ አይሸም ፤ ዳዊት ፣ አባ ትህን ፣ ታውቀዋለህ ፣ የዕልፍ ፣ ጌታ ፣ ነው ፣ የጦር ፣ አበጋዞቹ ፣ ኢዮአብ ፣ ለቢሳን ፣ ታውቃቸዋለህ ፣ የሺህ ፣ የ ሺህ ፣ ጌቶች ፣ ናቸው ፣ አሁን ፣ በዚ ህ ፣ በደም ፣ አፍሳሽ ፣ በሥብ ፣ አጢ ያሽ ፣ ካህን ፣ እጅ ፣ ይያዛል ፣ ብለህ ፣ ነ ውን ፣ እንዲያው ፣ ጦሩን ፣ ቅምት ፣ ይቅር ፣ ብለህ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ እንደኔ ስ ፣ የሆነ ፣ እንደሆነ ፣ ከዳን ፣ እስከ ፣ ቤርሳቤህ ፣ ያሉ ፣ አሥራ ፣ ሁለቱ ፣ ነ ገደ ፣ ሽኤል ፣ እስከ ፣ ፫ ፣ ወር ፣ ይሰብ ሰቡ ፣ እንደ ፣ ሰማይ ፣ ኰከብ ፣ እንደ ፣ ባሕር ፣ አሸዋ ፣ ይብዙ ፤ አንተስ ፣ ቀ ርተህ ፣ ምን ፣ ሥራ ፣ ሲሠራ ፣ ነው ፣ ወላጅቱ ፣ ከቤት ፣ አዋላጅቱ ፣ ከሜዳ ፣ እንዲሉ ፣ አንተ ፣ በፊት ፣ በፊት ፣ እ ኛ ፣ በኋላ ፣ በኋላ ፣ ሁነን ፣ እንገሠግሳ ለን ፣ ከተራራ ፣ ላይ ፣ ያገኘናቸው ፣ እንደሆነ ፣ በኃብል ፣ ስበን ፣ ከሸዋ ፣ እንቀላቅላቸዋለን ፣ ከሜዳ ፣ ላይ ፣ ያ ገኘናቸው ፣ እንደሆነ ፣ እንደ ፣ በረድ ፣ እንዘንምባቸዋለን ፣ አለው ፣ መኳን ንቱ ፣ ፊት ፣ ለፊት ፣ ተያይተዋል ። እ ምክረ ፣ አኪጦፌል ፣ ይኄይስ ፣ ምክ

ረ ፣ ኩሲ ፣ ብለዋል ፣ መሆኑንስ ፣ ለአ ቤሴሎም ፣ የአኪጦፌል ፣ ምክር ፣ ያ ሻለው ፣ ነበረ ።

ነገር ፣ ግን ፣ ዳዊት ፣ አ ፣ እግዚአ ፣ ዕልዋ ፣ ለምክረ ፣ አኪጦፌል ፣ ሚጣ ወልጣ ፣ ሲል ፣ ነው ፣ እያለ ፣ ይጸልይ ፣ ነበርና ፣ የኩሲን ፣ ምክር ፣ እንዲቀበ ልለት ፣ አደረገ ፣ ፪ኛሙ ፣ ፲፮-፴፫ ፣ ፲፯-፲፬ ፣ ኩሲም ፣ ለጊዜው ፣ የኔን ፣ ምክር ፣ ተቀብለውኛል ፣ ከዋለ ፣ ካደረ ፣ ግን ፣ የአኪጦፌል ፣ ምክር ፣ ዕፁ ፣ ነው ፣ እ ሁን ፣ ገብቶ ፣ ያስለውጠዋልና ፣ ኢ ትቢት ፣ ውስተ ፣ አራቦት ፣ አላ ፣ አፍ ጥን ፣ ዓዲወ ፣ ዮርዳኖስ ፣ ከአራቦት ፣ አትዋል ፣ አትደር ፣ ፈጥነህ ፣ ዮርዳ ኖስን ፣ ተሻገር ፣ ብላችሁ ፣ ላኩበት ፣ ብሎ ፣ ለካህናቱ ፣ ይነግራቸዋል ፤ ካ ህናቱም ፣ ጽፈው ፣ ለወህ ፣ ቀጂዎች ፣ ሰጧቸው ። ወህ ፣ ቀጂዎችም ፣ አኪ ማሆስና ፣ ዮናታን ፣ አገር ፣ ለመጐብ ኘት ፣ መጥተው ፣ ነበርና ፣ ሰጧቸው ፣ ተቀብለው ፣ ሲሄዱ ፣ የአቤሴሎም ፣ ወገን ፣ ጠባቂ ፣ አይቶ ፣ ወይ ፣ ከኛ ፣ ወይ ፣ ከነዚያ ፣ አይሆኑ ፣ በመኻል ፣ ለመጐብኘት ፣ ቆመዋል ፣ አለው ፣ ያዟቸው ፣ አያምልጧችሁ ፣ አለ ፣ የ ዳዊት ፣ ወገን ፣ የምትሆን ፣ አንዲት ፣ ሴት ፣ ነበረች ። ሂደው ፣ ሠውሪን ፣ አ ኗት ፣ በክረምት ፣ ወህ ፣ የበላው ፣ ጉ ድጓድ ፣ አለ ፣ ከዚያ ፣ አስተኛታ ፣ ወ ሰጥሀት ፣ በሙ ፣ አረፎተ ፣ ወዓረበ ናተ ፣ ከከም ፣ ፍትግም ፣ ቢሉ ፣ አሰ



ጣችባቸው ፣ ዘዳውያ ፣ ጠቀለለቻቸ ው ፣ ከጋዘና ፣ አገባቻቸው ፣ መጥ ተው ፣ አኪማሆስና ፣ ዮናታን ፣ ከዚ ህ ፣ ገብተዋልን ፣ አሏት ፣ መግባትስ ፣ ገብተው ፣ ነበር ፣ ነገር ፣ ግን ፣ አሁን ፣ ሄዱ ፣ አለቻቸው ፣ መግባታቸውን ፣ ብታምንላቸው ፣ መውጣታቸውን ፣ አምነውላት ፣ ገብተን ፣ እንይ ፣ ሳይሉ ፣ ሂደዋል ፣ አኪማሆስና ፣ ዮናታንም ፣ በኋላ ፣ ወጥተው ፣ ሄደው ፣ ኢትቢት ፣ ውስተ ፣ አራቦት ፣ አላ ፣ አፍጥን ፣ ዐዲወ ፣ ዮርዳኖስ ፣ ብሎሃል ፣ ኩሲ ፣ አሉት ፣ ዮርዳኖስን ፣ ተሻገር ፣ ከ ወይራ ፣ ስር ፣ ሆኖ ፣ ተናግሮታል ፣ ፪ኛሙ ፣ ፲፯-፲፰-፳፪ ።

አቤቱ ፤ ፈጣሪየ ፣ አንተን ፣ አመንኩ ፣ እንዲህም ፤ ከሆነ ፣ በመከራው ፣ አት ጣለኝ ፣ አንድም ፣ በመከራው ፣ እን ዳትጥለኝ ፣ አንተን ፣ አመንሁ ።

ወአድኅንኒ ፣ እምዞሎሙ ፣ እለ ፣ ሮዱኒ ፣ ወባልሐኒ ፣

ከከበቡኝ ፣ ጸላቶቼ ፣ ሁሉ ፣ ፈጽመህ ፣ አድነኝ ፣ አድኅኖ ፤ በመከራው ፣ ሳይ ያዙ ፣ (ባልሐ) ፣ ከተያዙ ፣ በኋላ ፣ ነው ፣ (አድኅነኒ) ፣ ከንጉሡ ፣ (ባልሐኒ) ፣ ከ ሠራዊቱ ፣ ነው ።

፪ ፣ ከመ ፣ ኢይምሥጥዋ ፣ ከመ ፣ አንበሳ ፣ ለነፍ ስየ ፣ እንዘ ፣ አልቦ ፣ ዘያድኅን ፣ ወዘይባልሕ ።

ኀነበ ፣ አልበ ፣ ሲል ፣ ነው ። የሚያድን ፣ ከሌለ ፣ ዘንድ ፣ አንበሳ ፣ ከፀፈቀ ፣ ዱር ፣ ከጉደጉደ ፣ ምድር ፣ ቆይቶ ፣ ላምን ፣ እንዲነጥቅ ፣ የኔንም ፣ ሰውነት ፣ እለ ፣ አቤሴሎም ፣ እንዳይነጥቋት ።

፫ ፣ እግዚኦ ፣ አምላኪየ ፣ እመ ፣ ገበርክዎ ፣ ለዝንቱ ፣

አቤቱ ፣ ፈጣሪየ ፣ እንዲህ ፣ እንደሚ ሉኝ ፣ አድርጌ ፣ እንደሆነ ፣ ምን ፣ አ ደረገ ፣ ብለውታል ፣ ቢሉ ፣ የጕልማሳ ፣ ሚስት ፣ ነጣ ፣ ጕልማሳ ፣ ገደለ ፣ ብለ ውታልና ፣ ፪ኛሙ ፣ ፲፮-፰-፲፮ ። ይህንግ ፣ አድርጎት ፣ የለምን ፣ ቢሉ ፣ በንስሓ ፣ ከታረቅሁ ፣ ብሎ ፣ ዕርቅ ፣ ደም ፣ ያደ ርቅ ፣ እንዲሉ ፣ ፪ኛሙ ፣ ፲፪-፲፫ ። አን ድም ፣ ስንኳን ፣ ንጉሥና ፣ ማናቸው ም ፣ ቢሆን ፣ ሰው ፣ ከቤቱ ፣ ከወጣ ፣ ብዙ ፣ ስም ፣ የሚወጣለት ፣ ስለሆ ፣ ያላደረገውን ፣ ማግለጃ ፣ በላ ፣ ፍርድ ፣ አደላ ፣ ብለውታልና ። ፪ኛሙ ፣ ፲፭-፰-፮ ።

ወእመኒ ፣ ቦ ፣ ዓመፃ ፣ ውስተ ፣ እደውየ ።

በጁ ፣ ነፍስ ፣ መግደል ፣ በቃሌ ፣ መ በደል ፣ በልቡናየ ፣ ቂም ፣ በቀል ፣ ቢኖርብኝ ።

፬ ፣ ወእመኒ ፣ ፈደይክዎሙ ፣ ለእለ ፣ ይፈድዩኒ ፣ እኩየ ።

ክፉ ፣ ላደረጉብኝ ፣ ሰዎች ፣ ክፉ ፣ እን ዳያደርጉብኝ ፣ ክፉ ፣ ላድርግ ፣ ብዬ ፣ እንደሆነ ።

ለያውድቅኒ ፣ ጸላእትየ ፣ ዕራቅየ ።

ጠላቶቼ ፣ ዕራቁቴን ፣ ይጣሉኝ ፣ ማለ ት ፣ ከሠራዊቴ ፣ ይለዩኝ ፣ ምነው ፣ ተለ ይቶ ፣ የለምን ፣ ቢሉ ፣ እንደተለየሁ ፣ ልቅር ፣ ሲል ፣ ነው ፣ አንድም ፣ ከነዚ ሁ ፣ ከጥቂቶቹ ፣ ልለይ ፣ ሲል ፣ ነው ።

፭ ፣ ወይዴግና ፣ ፀሬ ፣ ለነፍስየ ፣ ወይርከባ ።

ፀሬዊ ፣ አቤሴሎም ፣ (አኪጦፌል) ፣

2014 04 17

ነፍሴን ፡ ይከተላት ፡ ተከትሎ ፡ ማጣ
ት ፡ እለና ፡ አይጣት ፡ ያግኛት ።

ወይኪዳ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ለሕይወትየ ።

ሰውነቴን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያዋርዳት ።

ወያኀሥር ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ ለክብርየ ።

ዘውዴን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያዋርደው ።

፯ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ በመዓትከ ።

አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሣ ።

ወተለዓል ፡ መልዕልቶሙ ፡ ለጸላእትየ ።

እኔን ፡ አድነህ ፡ ጠላቶቼን ፡ አጥፍ
ተህ ፡ ልዕልናህን ፡ግለጽ ።

፯ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ በሥርዓት ፡
ዘአዘዝከ ፡ ኢሳ ፡ ፳፰-፳፩ ።

በእንተ ፡ ሥርዓት ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የኔ
ስ ፡ የኔ ፡ ነውና ፡ ያዘዝከው ፡ ሥርዓት ፡
ስለፈረሰ ፡ በሥራ ፡ ለመፍረድ ፡ ተ
ነሣ ፡ አቤሴሎም ፡ ሦስት ፡ ሥርዓት ፡
አፍርሷል ፡ ኢትክሥት ፡ ኀፍረተ ፡
ብእሲተ ፡ አቡከ ፡ ዘሌ ፡ ፲፰-፰ ። ኢት
ዕርግ ፡ ምስካበ ፡ አቡከን ፡ ኢትዘሙ
ን ፡ ዘፀ ፡ ፳-፲፬ ። ኢትዕርግና ፡ ኢትክሥ
ትስ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አክብር ፡
አባከ ፡ ወእመከ ፡ ያለውን ፡ አፍርሷ
ልና ፡ ዘፀ ፡ ፳-፲፪ ። ሦስቱ ፡ ወር ፡ ሲፈ
ጸም ፡ ዳዊት ፡ ጦሩን ፡ በሦስት ፡ ወገ
ን ፡ አድርጎ ፡ ይሰዳል ፡ ኢዮአብን ፡
ባንድ ፡ ወገን ፡ አቢሳን ፡ ባንድ ፡ ወ
ገን ፡ ሴት ፡ ጌትያዊን ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡
አድርጎ ፡ በለቤቱን ፡ አስቀርተውታ
ል ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡ አዕንተው ፡ ይዋ
ጉናል ፡ ብለው ፡ አንድም ፡ ጌታቸው ፡
ሳይኖር ፡ ድል ፡ አደረጉ ፡ ተብሎ ፡
መከበሪያ ፡ ይሆንናል ፡ ብለው ፡ ፪ሳሙ ፡
፲፰-፩-፫ ።

ሲያሠማሩቸው ፡ አቤሴሎምሃ ፡ ወል
ድየ ፡ መሀኩ ፡ ልጄን ፡ አቤሴሎምን ፡
ያገኛችሁት ፡ እንደሆነ ፡ አትግደሉ
ብኝ ፡ በሻሽ ፡ እንቃችሁ ፡ አምጡል
ኝ ፡ አላቸው ፡ ሄደው ፡ ገጠሙ ። እለ ፡
አቤሴሎም ፡ ድል ፡ ሆኑ ፡ ሲሸሽ ፡
የተቀመጠባት ፡ በቅሎ ፡ ይዛው ፡ ወ
ደዱር ፡ ገባች ፡ ወተሰቅለ ፡ ማዕከለ ፡
ሰማይ ፡ ወምድር ፡ ወኀለፈት ፡ በቅ
ል ፡ በታሕቴሁ ፡ ጋንቢሎም ፡ ቢሉ ፡
ቀንጠፋም ፡ ቢሉ ፡ የራስ ፡ ፀጉሩ ፡
ከግንድ ፡ ላይ ፡ የተጠመጠመ ፡ ዘን
ዶ ፡ ይመስል ፡ ነበር ፡ ጠልፎ ፡ አስ
ቀርቶታል ።

ከጦር ፡ ምላሽ ፡ ሲሆን ፡ ኢዮአብ ፡
ከቶ ፡ ዛሬ ፡ አቤሴሎምን ፡ ያየው ፡
የለምን ፡ አለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡
አይቼዋለሁ ፡ አለ ፡ ገድለኸው ፡ ቢ
ሆን ፡ የምትታጠቀው ፡ አፋ ፡ የምት
መክተው ፡ ጋሻ ፡ አሥር ፡ ግርሺ ፡
እሰጥህ ፡ ነበር ፡ ዳሩ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡
ቀረና ፡ አለው ፡ ስንኳን ፡ አሥር ፡
ግርሽ ፡ ሺህ ፡ ግርሽ ፡ ብትሰጠኝ ፡ አ
ልገድለውም ፡ ነበር ፡ በማን ፡ ደም ፡
ማን ፡ ይገባል ፡ ብዮ ፡ ጌታዮ ፡ ዳዊት ፡
አቤሴሎምን ፡ ያገኛችሁት ፡ እንደ
ሆነ ፡ አትግደሉብኝ ፡ በሻሽ ፡ እንቃ
አለው ፡ ያለበትንሳ ፡ ታውቃለህን ፡



ችሁ ፡ አምጡልኝ ፡ ሲል ፡ ሰምቻለሁ ፡
አለው ፡ አዎን ፡ አለው ፡ አድርሰኝ ፡
አለው ፡ ቢደርስ ፡ ደክሞ ፡ ነፍሱ ፡
ከሥጋው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ስትል ፡
አገኘው ፡ በሦስት ፡ ዘገር ፡ መሐል ፡
ልቡን ፡ ወጋው ፡ የተከተሉትም ፡ ብላ
ቴኖች ፡ አሥር ፡ ናቸው ፡ ባሥር ፡
ፍላፃ ፡ ወግተውታል ፡ ሦስቱ ፡ የሦስ
ትነት ፡ አሥሩ ፡ የአሥሩ ፡ ቃላት ፡ ምሳ
ሌ ፡ ቸብቸበውን ፡ ቈርጦ ፡ ግንዱን ፡ አ
ገላብጦ ፡ ጥሎ ፡ ቸብቸበውን ፡ ይዞ ፡
ሄደ ፡ ፪ሳሙ ፡ ፲፰-፱-፲፯ ። አኪማሆ
ስ ፡ አሰናብተኝ ፡ የልጁን ፡ ሞት ፡ ላ
ርዳው ፡ አለው ፡ አይሆንም ፡ የዛ
ሬ ፡ መልእክት ፡ ያንተ ፡ አይደለም ፡
ኩሲ ፡ አረጋዊ ፡ ይንገረው ፡ ብሎታ
ል ፡ ደግሞ ፡ ጥቂት ፡ ቆይቶ ፡ ልሂድ ፡
አለው ፡ ልሂድ ፡ ልሂድ ፡ ትላለህ ፡ ል
ጅህ ፡ ሞተ ፡ ብትለው ፡ አይሾምህ ፡ አይ
ሽልምህ ፡ ሂድ ፡ አለው ፡ ኩሲ ፡ አረጋዊ ፡
ነውና ፡ ዙሮ ፡ ሲሄድ ፡ ወቀደሞ ፡ በፍ
ኖተ ፡ ኬልቃ ፡ ይላል ፡ አኪናሆም ፡
በስርጥ ፡ ጐዳና ፡ አንድም ፡ በዚያው ፡
ጥሶት ፡ ሄደ ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ሁለት ፡ በር ፡ ባላ
ት ፡ ሰገነት ፡ (እልፍኝ) ፡ ተቀምጦ ፡ ነበ
ረ ፡ ሰላዮች ፡ አሉትና ፡ አንድ ፡ ፈጣን ፡
ሰው ፡ እየሮጠ ፡ መጣ ፡ አሉት ፡ አኪ
ማሆስ ፡ ይሆናል ፡ ገባ ፡ በሉት ፡ አለ ፡
ገብቶ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘአግብአ ፡ ፀረከ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡
ጠላቶችህን ፡ በእጅህ ፡ የጣለልህ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ አለ
ው ፡ ልጄ ፡ አቤሴሎምሳ ፡ እንደምን ፡
ሆነ ፡ አለው ፡ የሱ ፡ ነገር ፡ አልተገለጸ
ልኝም ፡ ጦር ፡ ይሂድ ፡ ሲሉ ፡ ነበር ፡
አለው ፡ አሁንም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መጣ ፡
አሉት ፡ ኩሲ ፡ አረጋዊ ፡ ይሆናል ፡
ግባ ፡ በሉት ፡ አለ ፡ አገብቶ ፡ ይትባ
ረከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአግብአ ፡ ፀረ
ከ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ አለው ፡ ልጄ ፡
አቤሴሎምሳ ፡ አለው ፡ ከመ ፡ አቤሴ
ሎምስ ፡ ወልዱ ፡ ለንጉሥ ፡ ይኩኑ ፡
ጸላዕቱ ፡ ለንጉሥ ። ጠላቶችህ ፡ አቤ
ሴሎምን ፡ ይሁኑ ፡ አለው ፡ ቤቱን ፡
ዘግቶ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመረ ፡ ፪ሳሙ ፡ ፲፰ ፡
፲፰-፴፫ ።

ሽኤል ፡ ግዳይ ፡ እንጥላለን ፡ ብለው ፡
ቢሄዱ ፡ ፀር ፡ ተዘግቶባቸው ፡ እያዘኑ
ሲመለሱ ፡ ኢዮአብ ፡ አገኛቸው ፡ ወ
ዴት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ አላቸው ፡ ግዳይ ፡
እንጥላለን ፡ ብለን ፡ ብንሄድ ፡ ዳዊት ፡
ደጁን ፡ ዘግቶ ፡ በልጁ ፡ ሞት ፡ ያለቅ
ሳል ፡ አሉት ፡ አትሂዱ ፡ ከዚህ ፡ ቈዩኝ ፡
ብሎ ፡ ሂዶ ፡ አንተ ፡ ጠላትህን ፡ እንጂ ፡
ወዳጅህን ፡ አያስወድድህም ፡ የዛሬ ፡
ድል ፡ በነአቤሴሎም ፡ እጅ ፡ በሆነ ፡ እን
ዴት ፡ ባደረጉን ፡ ነበር ፡ ይልቁንም ፡
አንተ ፡ እንዴት ፡ በደረጉህ ፡ ነበር ፡
አሁንም ፡ ወጥተህ ፡ ግዳይ ፡ ትቀበል ፡
እንደሆነ ፡ ተቀበል ፡ ያለዚያ ፡ የምት
ወደውን ፡ መንግሥት ፡ በጠላትህ ፡
እጅ ፡ አድርጌ ፡ አሳይሃለሁ ፡ አለው ፡

2014 04 17

እየተንቀጠቀጠ ፡ ወጥቶ ፡ የልጇን ፡
ቍብቍቦ ፡ ግዳይ ፡ ተቀብሏል ፤ ፪ሳሙ ፡
፲፱ ፡ ፩-፰ ።

ወማኅበረ ፡ አሕዛብ ፡ የዓውደከ ።

እንዲህ ፡ የተደረገ ፡ እንደሆነ ፡ ሴት ፡
ጌትያዊ ፡ በምስጋና ፡ ይከብሃል ፤ ማኅ
በር ፡ አለው ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ራሱን ፡
ሆኖ ፡ አድርሰታልና ፤ ፪ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ።

በእንተዝ ፡ ተመየጥ ፡ ውስተ ፡ አርያም ።

ትመሰገን ፡ ዘንድ ፡ ወደ አርያም ፡ ተመ
ለስ ፡ ማለት ፡ ፍረድ ፡ ሲል ፡ ነው ።

፰፡ እግዚአብሔር ፡ ይኴንኖሙ ፡ ለአሕዛብ ።

እኔ ፡ እቸኩላለሁና ፡ እንዲህ ፡ አልሁ ፡
እንጂ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ በአሕዛብ ፡
ይፈርድባቸዋል ፤ የአቤሴሎም ፡ እናቱ ፡
ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ ናትና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ፍታሕ ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ ፡ እምላኪየ ፡ በከመ ፡ ጽድ
ቅየ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እኔ ፡ እውነተኛ ፡
ነኝና ፡ እንደ ፡ እውነተኛነቴ ፡ ፍረድ
ልኝ ፡ አልልም ፡ አንተ ፡ ግን ፡ እውነ
ተኛ ፡ ነህና ፡ እንደእውነተኛነትህ ፡
ፍረድልኝ ፡ እልሃለሁ ፡ እንጂ ።

ወይከውነኒ ፡ በከመ ፡ የዋሃትየ ።

እንደ የዋኽነቴ ፡ እንደ ቅንነቴ ፡ ይደረግ
ልኝ ፡ ማለት ፡ ለመንግሥት ፡ ለደረሰ ፡
ልጅ ፡ ሥርዓተ ፡ መንግሥት ፡ እውጥ
ቶ ፡ ማሳየት ፡ የዋህነት ፡ ነውና ፤ ፩ነገሥ ፡
፲፭ ፡ ፯-፲፫ ። እንድም ፡ ሕግ ፡ እንደመ
ጠበቂ ፡ ይሁንልኝ ፡ የዋህነት ፡ ዋጋ ፡
የሚያሰጥ ፡ ስለሆነ ።

፱፡ የኃልቅ ፡ እከዮሙ ፡ ለኃጥኣን ።

የኃጥኣን ፡ የነአቤሴሎም ፡ ክፉ ፡ ሥራቸ
ው ፡ ያልቅባቸዋል ፤ ዝናም ፡ በላዩ ፡
አለቀ ፡ እንዲሉ ፤ ኃጢአትማ ፡ ቢሠ
ሩት ፡ ቢሠሩት ፡ ይፈጸማልን ፤ ከሞቱ ፡
በኋላ ፡ የማይሠሩት ፡ ስለሆነ ፡ እንድ
ም ፡ በፍዳ ፡ ይፈጸምባቸዋል ፤

ወታረትዖሙ ፡ ለጻድቃን ።

ታሐይዎሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ጻድቃንን ፡
ታድናቸዋለህ ፡ እንድም ፡ ቅንነታቸ
ውን ፡ ትገልጽላቸዋለህ ። ጠዋይኒ ፡
አ.ይከል ፡ ረቲዐ ፡ እንዲል ፤ መክ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ።
እንድም ፡ ቀንተው ፡ እንዲሄዱ ፡ ታደ
ርጋቸዋለህ ፡ ጠላት ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡
አዩኝ ፡ አላዩኝ ፡ እያለ ፡ ተጎንብሶ ፡
ይሄዳልና ።

ይፈትን ፡ ልበ ፡ ወኵልያተ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ልብ ፡ ያሰበውን ፡ ኵ
ላሊት ፡ ያጤሰውን ፡ መርምሮ ፡ ያው
ቃል ፡ እረ ፡ ሳይመረምርም ፡ ያውቃ
ል ፤ ምሳ ፡ ፳-፲፯ ፤ ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፲ ። ሉቃ ፡ ፲፮ ፡
፲፭ ። ግብ ፡ ሐ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ። ራእ ፡ ፪ ፡ ፳፫ ።

፲፡ አማን ፡ ይረድአኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘያድኅ
ኖሙ ፡ ለርቱዓነ ፡ ልብ ።

ቅን ፡ ልቡና ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ የሚ
ያድናቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ በእው
ነት ፡ ይረዳኛል ፤ አማን ፡ ብለህ ፡ ነው ፡
እንድም ፡ እውነተኛ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይረዳኛል ።



ወመላእክቲ ፡ ተጋብኡ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኅቡረ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወላዕለ ፡ መሲሑ ፤
መዝሙር ፡ ፪ ።



እስመ ፡ አንተ ፡ ቀሠፍኮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይፃረሩኒ ፡ በከንቱ ፤ መዝሙር ፡ ፫ ።

፲፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ መኰንን ፡ ጽድቅ ።

እግዚአብሔር ፡ ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡ ኰናኚ ፡ በርትዕ ፡ ነው ።

ኃያል ፡ ወመስተዓግሥ ።

ኃያል ፡ ነው ፡ ታጋሽም ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ኃያል ፡ ቢሆን ፡ ትዕግሥት ፡ አይሰጠውም ፤ ተዓጋሢም ፡ ቢሆን ፡ ኃይል ፡ አይሰጠውም ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘቡ ፡ ነውና ።

ወኢያመጽእ ፡ መንሱተ ፡ ኵሎ ፡ ዓሚረ ።

ትዕግሥቱም ፡ ሊታወቅ ፡ ሰው ፡ በበደለው ፡ ቍጥር ፡ መዓቱን ፡ ላምጣ ፡ አይልም ።

፲፪ ፤ እመሰ ፡ ኢተመየጥክሙ ፡ ሰይፉ ፡ ይመልህ ።

እንዲህም ፡ ማለቱ ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብትመለሱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ካልተመለሳችሁ ፡ ኃይሉን ፡ ሊያስታውቅ ፡ በሰብአ ፡ ትካት ፡ በሰብአ ፡ ሰዶም ፤ በሰብአ ፡ ገሞራ ፡ የመዘዘውን ፡ ሰይፈ ፡ መዓቱን ፡ በእናንተ ፡ ይመዘዋል ፤ ዘፍ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ፡ ፳፱ ። ፲፱ ፡ ፳፬ - ፳፭ ።

አንድም ፡ ወደኔ ፡ የቃጣው ፡ ሰይፈ ፡ መዓቱን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ይመልሰዋል ፤ (ይመልስ) ።

ቀስቶ ፡ ወተረ ፡ ወአስተዳለወ ።

ቀስቱን ፡ ቀፈረ ፡ አዘጋጀ ። ሉቃ ፡ ፲፫ ፡ ፫ ።

፲፫ ፤ ወአስተዳለወ ፤ ቦቱ ፡ ንዋየ ፡ ዘይቀትል ።

ነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ የሚለይበትን ፡ መርገዝ ፡ ቀባው ። ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፳፰ ። የወዲያኛው ፡ ቀስቱን ፡ እያተባ ፡ እያጋለ ፡ መርገዝ ፡ እየቀባ ፡ ይመጣል ፤ ይህን ፡ የወረወው ፡ እንደሆነ ፡ ቀዳማዩን ፡ ከነ ደኃራዩ ፡ ሰውየውንም ፡ ወግቶ ፡ ከመሬት ፡ የሚሰፋ ፡ ነው ፤ የወዲሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥበቡን ፡ ገልጾለት ፤ ጀባውን ፡ ወህ ፡ ነከሮ ፡ ለጋሻው ፡ አልብሶ ፡ ይመጣል ፡ ግለቱን ፡ ወህው ፡ ያቀዘቅዝለታል ፤ መርዙን ፡ ጀባው ፤ ይጠርግለታል ፤ ስለቱን ፡ ጋሻው ፡ ይመልስለታል ።

ወአሕፃሁኒ ፡ እለ ፡ ይነዱ ፡ ገብረ ።

ኢዮአብ ፡ ቀስቱን ፡ የሚናደድ ፡ አደረገ ፤ ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱ ።

፲፬ ፤ ናሁ ፡ ሐመ ፡ ዐመፃ ፡ በዐመፃ ።

አኪጦፌል ፡ አንድም ፡ አቤሴሎም ፡ ዕሮ ፡ ግሮ ፡ በመከረው ፡ ምክር ፡ ጠፋ ።

ፀንሰ ፡ በፃዕር ፡ ወወለደ ፡ ኃጢአተ ።

ፀንሰ ፡ ነቅፀ ፡ ሐልዮን ፡ ወወለደ ፡ ቍርፀ ፡ ሐልዮን ፡ አደረገ ።

፲፭ ፤ ግበ ፡ ከረየ ፡ ወደሐየ ።

ከረየ ፡ ነቢብን ፡ ደሐየ ፡ አፀና ፤ አንድም ፡ (ፀንሰ ፡ በፃዕር) ፡ አኪጦፌል ፡ አቤሴሎምን ፡ ባዕ ፡ ጎበ ፡ ዕቁባቲሁ ፡ ልበለው ፡ ብሎ ፡ አሰበ ፤ (ወወለደ) ፡ ባዕ ፡ ኀበ ፡ ዕቁባቲሁ ፡ አለው ፤ ፪ሳሙ ፡ ፲፮ ፡ ፳፭ ። ግበ ፡ ከረየ ፤ ሽሁ ፡ ጦር ፡ ስጠኝና ፡ ቾብቾበውን ፡ ቂርጬ ፡ ላምጣልህ ፡ አለው ፤ ፪ሳሙ ፡ ፲፯ ፡ ፩ - ፪ ።

ወይወድሶ ፡ ወጸላኢ ፡ ገብረ ፡ ዘገብረ ።

እዉሴሎም ፡ እንድም ፡ አኪጦፌል ፡ በመከረው ፡ ምክር ፡ ጠፋ ።

፲፮ ፡ ወደገባእ ፡ የማው ፡ ሊበ ፡ ርእሶ ።

ፅር ፡ ግር ፡ የመከረው ፡ ምክር ፡ ወደ ራሱ ፡ ይመለሳል ፡ ደንጊያ ፡ ቢያጉኑ ት ፡ ተመልሶ ፡ ከናት ፡ እንዲሉ ።

ወትወርድ ፡ ዓመፃው ፡ ሊበ ፡ ድማኁ ።

ፅር ፡ ግር ፡ የመከረት ፡ ምክር ፡ ወደ ራሱ ፡ ትመለሳለች ። ዘፀ ፡ ፲፰-፲፮ ። አ ኪጦፌል ፡ ምክሩን ፡ እንዳልተቀበለ ለት ፡ አይቶ ፡ እንግዲህማ ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ ታርቀው ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ አፅ ቅ ፡ ዓፅቂን ፡ እየቈረጡ ፡ ሲጫወቱብ ኝ ፡ ሊኖሩ ፡ አይደለምን ፡ አንድ ፡ ቀ ን ፡ እንኳ ፡ አያሳርፉኝ ፡ ብሎ ፡ ወሀበ ን ፡ ዓድጎ ፡ ወሖረ ፡ ውስተ ፡ ሀገሩ ፡ ጉ ናሄም ። ከገሩ ፡ ሄዶ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፡ በዚህ ፡ ዋሉ ፡ በዚህ ፡ እደሩ ፡ ብሎ ፡ ከባዶ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ታንቆ ፡ ሞቷል ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፯ ፡ ፳፫ ።

፲፯ ፡ እገኒ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ ጽድቁ ።

እንደ ፡ እውነተኛነቱ ፡ ለእግዚአብሔ ር ፡ እገዛለሁ ።

ወእዜምር ፡ ለስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ መዝ ፡ ፲፱ ፡ ፯ ።

ልዑል ፡ ለሚሆን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንድም ፡ ልዑል ፡ ለሚሆን ፡ ስሙ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

## መዝሙር ፡ ፱ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚእነ ፡ ጥቀ ፡ ተሰብሐ ፡ ስም ከ ፡ በኵሉ ፡ ምድር ፡ ዮ ፡ ፱ ፡ ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፭ ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ይረቅ ፡ ሐዲስ ፡ ይ ባላል ፡ አዕሩግ ፡ ሕፃናት ፡ በአንድ ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ በዕለተ ፡ ሆሣዕና ፡ ሆ ሣዕና ፡ በአርያም ፡ እያሉ ፡ ሲያመሰግ ኑ ፡ ከጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ እንደደረሰ ፡ ሆኖ ፡ ተገልፆለት ፡ አስቀድሞ ፡ ተና ግሮታል ። አቤቱ ፡ ስምህ ፡ ባራቱ ፡ ማ ዕዘን ፡ ፈጽሞ ፡ ተመሰገነ ። ና ፡ የሚሆን ፡ ጌትነትህ ፡ ተመስግኗ አልና ፡ እንድም ፡ (እግዚእ ፡ እግዚእ ነ) ፡ ስምህ ፡ በደቂቀ ፡ አዳም ፡ ዘንድ ፡ ፈጽሞ ፡ ተመሰገነ ፡ (እስመ ፡ ተለዓ ለ) ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ በመላእክ ት ፡ ዘንድ ፡ ተመስግኗልና ፡ እንድም ፡ (እግዚእ) ፡ በትሑታኑ ፡ ዘንድ ፡ ተመ ሰገነ ፡ (እስመ ፡ ተለዓለ) ፡ ከዚህ ፡ አስ ቀድሞ ፡ በልዑላኑ ፡ ዘንድ ፡ ተመስግ ኗልና ፡ ልዑላን ፡ ትሑታንን ፡ ለመላ እክት ፡ ለደቂቀ ፡ አዳም ፡ ይሰጧል ።

እስመ ፡ ተለዓለ ፡ ዕበየ ፡ ስብሐቲከ ፡ መልዕልተ ፡ ሰማያት ።

ዐቢይ ፡ ስብሐቲከ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ገና

፪ ፡ እምአፈ ፡ ደቂቅ ፡ ወሕፃናት ፡ አስተዳሎከ ፡ ስብሐተ ፡ መዝ ፡ ፳፩ - ፲፮ ።

ነግዕከ ፡ ተወከፍከ ፡ ተመጦከ ፡ ሲል ፡



ነው ፡ ከሕፃናት ፡ እንደበት ፡ ምስጋና ን ፡ ተቀበልህ ፡ ማለት ፡ በኋህ ፡ እንደ በት ፡ ተመሰገንህ ፡ ሕፃናት ፡ የሚላቸ ው ፡ የዓርብ ፡ የሰማንያ ፡ ቀን ፡ ደቂ ቅ ፡ የሚላቸው ፡ ያመት ፡ የሁለት ፡ ዓ መት ፡ ናቸው ፡ ይህስ ፡ አይደለም ፡ ተሐፅነ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ደቂ ቅ ፡ የሚላቸው ፡ የዓርብ ፡ የሰማንያ ፡ ቀን ፡ ሕፃናት ፡ የሚላቸው ፡ ያመት ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ናቸው ፡ ይሏል ፡ እኒህ ፡ በዕለተ ፡ ሆሣዕና ፡ ተገልፆላቸ ው ፡ እንድም ፡ አመስግኑኝ ፡ ብሏቸ ው ፡ ዕጕለ ፡ ርግብ ፡ ዘውገ ፡ ማዕነቅ ፡ ይዘው ፡ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ እያሉ ፡ አመስግነውታል ፡ ጥበብ ፡ ከሠተት ፡ አፈ ፡ ሕፃናት ፡ ወልሳነ ፡ በሐማን ፡ ረ ሰየት ፡ ርቱዐ ፡ ወነበቤ ፡ እንዲል ።

በእንተ ፡ ጸላኢ ።

ዲያብሎስን ፡ ደስ ፡ አይበለው ፡ ብለህ ።

ከመ ፡ ትንሥቶ ፡ ለፀላኢ ፡ ወለገፋዒ ።

ፀላዒ ፡ ገፋዒ ፡ የሚሆን ፡ ዲያብሎ ስን ፡ ትረታው ፡ ትመታው ፡ ዘንድ ፡ አስተዳሎከ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ አምስ ት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ የሰውን ፡ ልቡ ና ፡ እንደ ፡ ዙፋን ፡ ሰውነቱን ፡ እን ደ ፡ ድንኳን ፡ ፍትወታት ፡ እኩያት ፡ ኃጣውእን ፡ እንደ ፡ አጥር ፡ እንደ ፡ ቅ ጥር ፡ አድርጎ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ፡ ጌታ ፡ ሰ ው ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ እየወጣ ፡ ሄ ዷልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እንድም ፡ (በ እንተ ፡ ፀላዒ) ፡ ቢፅ ፡ ሐሳዊን ፡ ደስ ፡ አይበለው ፡ ብለህ ፡ (ከመ ፡ ትንሥቶ ፡ ለጸላዒ ፡ ወለገፋዒ) ፡ ጸላዒ ፡ ገፋዒ ፡ የሚሆን ፡ ቢፅ ፡ ሐሳዊን ፡ ትረታው ፡ ትመታው ፡ ዘንድ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ንሬኢ ፡ ሰማያተ ፡ ግብረ ፡ አፃብዒከ ።

የእጅህ ፡ የቃልህ ፡ ፍጥረት ፡ የሚሆ ኑ ፡ ሰባቱ ፡ ሰማያትን ፡ እናያለንና ።

ወርኅ ፡ ወከዋክብተ ፡ ዘአንተ ፡ ሣረርከ ።

አንተ ፡ የፈጠርካቸው ፡ ፀሐይ ፡ ጨ ረቃ ፡ ከዋክብትን ፡ እናያለንና ፡ ነግዕ ከ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ማንሽ ፡ አንድ ም ፡ የእጅህ ፡ የቃልህ ፡ ፍጥረት ፡ የሚ ሆኑ ፡ ሰባቱ ፡ ሰማያትን ፡ እናያለንና ፡ (ወርኅ ፡ ወከዋክብተ) ፡ ፀሐይ ፡ ጨረ ቃ ፡ ከዋክብትን ፡ አንተ ፡ ፈጠርህ ፡ እ ንላለን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ፈጠረ ፡ እንላ ለንን ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ማንሽ ፡ እን ድም ፡ የእጅህ ፡ የቃልህ ፡ ፍጥረት ፡ የሚሆኑ ፡ ሰባቱ ፡ ሰማያትን ፡ እናያለ ንና ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብትን ፡ አንተ ፡ ፈጥረሃልና ። ኩፋ ፡ ፲ ፡ ፳፩ ።

፬ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ትዝክሮ ።

ሰሚው ፡ ወልድ ፡ ነው ፡ ሰውን ፡ በራ ስህ ፡ ተዋሀዶ ፡ ታስበው ፡ ዘንድ ፡ ም ን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ።

ወምንትኑ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ከመ ፡ ተሐውፆ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፮ ፡ መዝ ፡ ፻፵፫ ፡ ፫ ።

ሰውን ፡ በራስህ ፡ ተዋህዶ ፡ ትጐበኘው ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ መ ሬት ፡ አንተ ፡ ወትገብዕ ፡ ውስተ ፡ መ

ሬት ፡ ተብሎ ፡ የተፈረደበት ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ አይደለምን ። ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ።

፭ ፡ ሕቀ ፡ አንዳእዎ ፡ እመላእክቲከ ።

እንዲህ ፡ ሲል ፡ ያውክል ፤ እንድም ፡ ሰማው ፡ እብ ፡ ነው ፡ (ምንት ፡ ውእቱ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ትዝክሮ) ፡ ሰውን ፡ በልጅህ ፡ ተዋህዶ ፡ ታስበው ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ (ወምንትኑ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ከመ ፡ ተሐውፆ) ፡ በልጅህ ፡ ተዋህዶ ፡ ትጎበኘው ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፤ መሬት ፡ እንተ ፡ ወትገብዕ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ ተብሎ ፡ የተፈረደበት ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ አይደለምን ። ልጅህን ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፤ ከመላእክት ፡ አሳንስከው ፤ መላእክት ፡ ኢሐማምያን ፡ ኢመዋትያን ፡ ናቸው ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ በፈቃዱ ፡ ቢሆን ፡ ታሞ ፡ ሞቶ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ፈጥኖ ፡ ተነሥቷልና ፤ ወአኅፀረ ፡ ዕድሜ ፡ ለርእሱ ፡ እንዲል ።

ክብረ ፡ ወስብሐተ ፡ ከለልኮ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ።

ክብርን ፡ የክብር ፡ ክብርን ፡ ገንዘብ ፡ አደረግሀለት ፤ እንድም ፡ መስቀል ፡ ቀኖትን ፡ ገንዘብ ፡ አደረግሀለት ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘሰምየ ፡ ሕማማተ ፡ ወልዱ ፡ ክብረ ፡ ወስብሐተ ፡ እንዲል ።

፯ ፡ ወሤምኮ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ግብረ ፡ እደዊከ ።

በኻያ ፡ ሁለቱ ፡ ስነ ፡ ፍጥረት ፡ አሰለጠንኸው ።

ወኵሎ ፡ አግረርከ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፯ - ፰ ።

ሁሉን ፡ በእጁ ፡ ጨብጥ ፡ በእግሩ ፡ እርግጥ ፡ አድርገህ ፡ አስገዛህለት ። መዝ ፡ ፻፱-፩ ።

፰ ፡ አባግዓኒ ፡ ወኵሎ ፡ አልሕምተ ።

ላሙን ፡ በጉን ፡ ሁሉ ፡ አስገዛህለት ።

ወዓዲ ፡ እንስሳ ፡ ዘገዳም ።

በበረኃ ፡ ያሉ ፡ ድኩላውን ፡ ብሆሩን ፡ አስገዛህለት ።

፱ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይኒ ፡ ወዓሣተ ፡ ባሕር ።

በሰማይ ፡ የሚበሩ ፡ አዕዋፍን ንስርን ፡ በባሕር ፡ የሚኖሩ ፡ ዓሣ ፡ አንበሬን ፡ አዞ ፡ጉማሬን ፡ አስገዛህለት ።

ወዘኒ ፡ የሐውር ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ባሕር ።

በባሕር ፡ የሚመላለስን ፡ ሁሉ ፡ አስገዛህለት ። እንድም ፡ (ዓባግዓኒ) ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ (ወኵሎ ፡ አልህምት) ፡ ሕዝቡን ፡ (እንስሳ ፡ ገዳም) ፡ አሕዛብን ፡ (አዕዋፈ ፡ ሰማይኒ) ፡ መላእክትን ፡ (ዓሣተ ፡ ባሕር) ፡ በደሴት ፡ የሚኖሩትን ፡ (ዘኒ ፡ የሐውር ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ባሕር) ፡ በባሕር ፡ የሚነግዱ ፡ ነጋድያንን ፡ አስገዛህለት ። እንድም ፡ (ዓባግዓኒ) ፡ ሐዋርያትን ፡ (አልሕምተ) ፡ ሰብአ ፡ አርድእትን ፡ (እንስሳ ፡ ገዳም ፡ ባሕታውያንን ፡ (አዕዋፈ ፡ ሰማይ) ፡ አጋንንትን ፡ (ወዓሣተ ፡ ባሕር) ፡ በመቃብር ፡ ያሉ ፡ ሥጋትን ፤ (ወዘኒ ፡ የሐውር) ፡ በሲኦል ፡ ያሉ ፡ ነፍሳትን ፡ አስገዛኸው ፤ እንድም ፡ (አዕዋፈ ፡ ሰማ



ይኒ) ፡ በአየር ፡ ያሉ ፡ አጋንንትን ፡ ኢትሕሚ ፡ ብዑላነ ፡ ውስተ ፡ ቤትከ ፡ እስመ ፡ ዖፈ ፡ ሰማይ ፡ ያወጽእ ፡ ለነገርከ ፡ እንዲል ።

(ዓሣተ ፡ ባሕር) ፡ በባሕር ፡ በዱር ፡ ያሉ ፡ አጋንንትን ፡ (ወዘኒ ፡ የሐውር) ፡ በውቅያኖስ ፡ ያሉ ፡ አጋንንትን ፡ አስገዛህለት ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፳፯ ። ፲፮ - ፳፯ ። ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፪ - ፱) ።

፲ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚእነ ፡ ጥቀ ፡ ተሰብሐ ፡ ስምከ ፡ በኵሉ ፡ ምድር ፡ ተ ፡ ፩ ።

ቢያምረው ፡ ቢጥመው ፡ ቢርቀው ፡ ደገመው ።

መዝሙር ፡ ፱ ።

፩ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ በኵሉ ፡ ልብየ ።

በእንተ ፡ ርእሱ ፡ ነው ፤ በእንተ ፡ ኀፋዊ ፡ ወተኀፋኢ ፡ ይላል ፤ ኀፋዊ ፡ ዲያብሎስ ፤ ሳኦል ፤ ስናክሬም ፡ ተኀፋዊ ፡ አዳም ፡ ዳዊት ፡ ሕዝቅያስ ። ኀፋዕያን ፡ ወተኀፋዕያን ፡ ይላል ፤ ኀፋዕያን ፡ አሕዛብ ፡ አጋንንት ፡ ተኀፋዕያን ፡ ሽሌል ፡ ምዕመናን ፤ ይህንና ፡ አፈቅረከን ፡ ጠላቶቹ ፡ ተከትተው ፡ ከጠፉለት ፡ መንግሥቱ ፡ ከተደላደለለት ፡ በኋላ ፡ ተናግሮታል ፤ ወዝንቱ ፡ ነገሩ ፡ ለዳዊት ፡ ምዕመን ፡ ሶበ ፡ ገብዑ ፡ ጸላዕቱ ፡ ታህተ ፡ እገሪሁ ፡ እንዲል ። አቤቱ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ አመሰግንሃለሁ ፤ የምስጋና ፡ አገዛዝ ፡ እገዛልሃለሁ ።

ወእነግር ፡ ኵሎ ፡ ስብሐቲከ ።

ጌትነትህ ፡ ቸምራትህን ፡ ሁሉ ፡ እነግራለሁ ፡ አስተምራለሁ ።

፪ ፡ እትፌሣሕ ፡ ወእትኃሠይ ፡ ብከ ።

ባንተ ፤ እምኚ ፤ በተሠራልኝ ፡ ሥራ ፡ እንድም ፤ ባንተ ፤ በማመኔ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

ወእዜምር ፡ ለስምከ ፡ ልዑል ።

ልዑል ፡ የሚሆን ፡ ስምህን ፡ አመሰግናለሁ ፤ ልዑል ፡ ለሚሆን ፡ ስምህ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

፫ ፡ ሶበ ፡ ገብኡ ፡ ጸላእትየ ፡ ድኅሬሆሙ ።

ምን ፡ ጊዜ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ ጠላቶቼ ፡ አድነ ፡ እነስ ፡ አድሮ ፡ እነስ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ይደወዩ ፡ ወይትኀጐሉ ፡ እምቅድመ ፡ ገጽከ ።

የሞት ፡ ደዌ ፡ ይታመሙ ፡ ዘንድ ፡ ከባለሟልነትህ ፡ እንደወጡ ፡ ይቀሩ ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ ይድወዩ ፡ የሞት ፡ ደዌ ፡ ይታመሙ ፤ ወይትኀጐሉ ፡ ከባለሟልነትህ ፡ እንደወጡ ፡ ይቅሩ ፡ ብዬ ።

፬ ፡ እስመ ፡ ገበርከ ፡ ሊተ ፡ ፍትሕየ ፡ ወበቀልየ ።

ፍርዴን ፡ ፍርድ ፡ በቀሌን ፡ በቀል ፡ አድርገሃልና ፡ እንድም ፡ ፈጽመህ ፡ ፈርደህልኛልና ፡ ተበቀል ፡ ሊተ ፡ እምዕድውየ ፡ እንዲል ።

ወነበርከ ፡ ዲበ ፡ መንበርከ ፡ መኰንነ ፡ ጽድቅ ።

ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡ ኰናኒ ፡ በርትዕ ፡ አንተ ፡ በዙፋንህ ፡ ላይ ፡ ተቀመጥህ ፤ ማለት ፡ ፈረድህ ።

፭ ፤ ገሠጽኮሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ወተኀጕሉ ፡ ረሲዓን ።

አሕዛብን ፡ ሠራዊቸው ፡ ቀኖሃቸው ፤ አንተን ፡ የዘነጉ ፡ ሁሉ ፡ ጠፉ ፤ አንድም ፡ (ገሠፅከሙ ፡ ለአሕዛብ) ፡ ረሲዓን ፡ አንተን ፡ የዘነጉ ፡ አሕዛብን ፡ ሠራሃቸው ፡ ቀኖሃቸው ፤ (ወተኀጕሉ) ፡ ጠፉ ።

ወደምሰስከ ፡ ስሞሙ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ስም ፡ አጠራራቸውን ፡ ለዘላለሙ ፡ አጠፋህ ።

፮ ፤ ፀርስ ፡ ተገምሩ ፡ በሾናት ፡ ለዝሉፉ ።

ፀርስ ፡ ስመ ፡ ጭፍራ ፡ ነው ፤ ፀርከ ፡ የሚባሉ ፡ ጠላቶች ፡ ተከትተው ፡ ጠፉ ፤ ወተገምሩ ፡ የዲወ ፡ ዮርዳኖስ ፡ እንዲል ።

አንድም ፡ ጠላቶቹ ፡ እለሳአል ፡ ተከትተው ፡ ጠፉ ።

ወአህጉሪሆሙኒ ፡ ነሠትከ ።

አገራቸውን ፡ ፈታሕ ።

ወትሥዕር ፡ ዝክሮሙ ፡ ኅቡረ ።

ዝክሮሙ ፡ ኅቡረ ፡ ምስለ ፡ ሀገሮሙ ፡ በል ፤ ሀገራቸውን ፡ ከነስማቸው ፡ አጠፋህ ፤ ውሉድ ፡ ወሕንፃ ፡ ሀገር ፡ ያዓብዩ ፡ ስመ ፡ እንዲል ።

ጥንቱን ፡ ለልማዱ ፡ ይህ ፡ የዕገሌ ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ የዕገሌ ፡ ግምብ ፡ ነው ፡ እየተባለ ፡ ስሙን ፡ ሲያስጠራው ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ጠፉ ።

አንድም ፡ (ፀርስ ፡ ተገምሩ ፡ በሾይፍት ፡ ለዝሉፉ) ፡ አጋንንት ፡ በመስቀል ፡ በጥምቀት ፡ ጠፉ ፡ ማለት ፡ ድል ፡ ተነሡ ፤ (ወአህጉሪሆሙኒ ፡ ነሠትከ) ፡ ከማደሪያቸው ፡ ከሰው ፡ ልቡና ፡ አስወጥተህ ፡ ስደድካቸው ፤ (ወትሥዕር ፡ ዝክሮሙ ፡ ኅቡረ) ፡ ከማደሪያቸው ፡ ከሰው ፡ ልቡና ፡ አስወጥተህ ፡ እንደሰደድካቸው ፡ መመለካቸውንም ፡ አጠፋህ ።

፯ ፤ እግዚአብሔርሰ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ።

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፡ ማለት ፡ አጥፊ ፡ ለጥፋት ፡ የሚለው ፡ የለም ፡ ሲፈርድ ፡ ሲያጠፋ ፡ ይኖራል ።

ወአስተዳለወ ፡ መንበሮ ፡ ለኰንኖ ።

ለመፍረድ ፡ ዙፋኑን ፡ አዘጋጀ ፤ በግሥ ፡ ተናገረው ፤ ንጉሥ ፡ ሲፈርድ ፡ ዘውዱን ፡ ደፍቶ ፡ ሕለተ ፡ ወርቁን ፡ ጨብጦ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ እንደ ሆነ ፡ ይፈርዳል ፡ ሲል ፡ ነው ።

፰ ፡ ወውእቱ ፡ ይኴንና ፡ ለዓለም ፡ በጽድቅ ።

በውነቱ ፡ ለዓለም ፡ ይፈርድላታል ፤ በዓለም ፡ ይፈርድባታል ፤ ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተናገረ ፡ ሁለቱንም ፡ ያመጣል ።

ወይኴንኖሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ በርትዕ ።

በአሕዛብ ፡ በውነት ፡ ይፈርድባቸዋል ፤ ይፈርድባታል ፡ ሳለው ።



፱ ፡ ወኮኖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስካዮሙ ፡ ለነዳያን ።

እግዚአብሔር ፡ ለነዳያን ፡ አምባ ፡ መፀጊያ ፡ ይሆናቸዋል ፤ ይፈርድላታል ፡ ሳለው ።

ወረዳኢሆሙ ፡ ውእቱ ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤሆሙ ።

በመከራቸውም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ዋስ ፡ እንደ ፡ ጠበቃ ፡ ሆኖ ፡ ይረዳቸዋል ።

፲ ፤ ወይትዌከሉ ፡ ብከ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ስመከ ፡ መዝ ፡ ፭-፲፭ ።

ስምህን ፡ የሚወዱ ፡ ሁሉ ፡ ባንተ ፡ እምነው ፡ በንተው ፡ ይኖራሉ ።

እስመ ፡ ኢተኀድጎሙ ፡ ለእለ ፡ የኀሥሡከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የሚሹህን ፡ በመከራ ፡ አትጥላቸውምና ።

፲፩ ፤ ዘምሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘየኀድር ፡ ውስተ ፡ ጽዮን ።

በጽዮን ፡ ሰማያዊት ፡ በጽዮን ፡ ምድራዊት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ አድሮ ፡ ለሚኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፤ አንድም ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ከምስት ፡ ቀን ፡ በማኅፀነ ፡ ማርያም ፡ ያደረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ ለሱ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።

ወንግርዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ምግባሮ ።

ሥራውንም ፡ ሁሉ ፡ ለአሕዛብ ፡ ንገሯቸው ፡ አስተምሯቸው ። መዝ ፡ ፶፱ ፡ ፩ ።

፲፪ ፤ እስመ ፡ ተዘከረ ፡ ዘይትኀሠሥ ፡ ደሞሙ ።

እንደፈሰሰ ፡ ይቅር ፡ የማይባል ፡ ደማቸውን ፡ አስቧልና ፡ አስቦ ፡ ጠላታቸውን ፡ አጥፍቷልና ። አንድም ፡ ደማቸውን ፡ የሚመረመር ፡ እግዚአብሔር ፡ አስቧልና ፡ አስቦ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ አጥፍቷልና ፡ አንድም ፡ ደማቸውን ፡ የሚፈላለግ ፡ ጠላታቸውን ፡ አስቦ ፡ አጥፍቷልና ፤ አንድም ፡ ጠላቱን ፡ በፍዳ ፡ የሚመረምር ፡ ደማቸውን ፡ አስቧልና ፡ አስቦ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ አጥፍቷልና ፡ እንደ ፡ ደመ ፡ አቤል ፡ እንደ ፡ ደመ ፡ ዘካርያስ ፡ ደመ ፡ አቤል ፡ መልአኩ ፡ ለጌናከ ፡ መከነ ፡ ኃጥአንን ፡ እያዘረ ፡ ሲያሳየው ፡ ስትከሰስ ፡ ስትንጸረጸር ፡ አየ ፤ ዛመንፈስ ፡ ዘመኑ ፡ አለው ፡ ዘአቤል ፡ ዘቀተሎ ፡ እኁሁ ፡ ትሰኪ ፡ ኪያሁ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይትኀጐሉ ፡ ደቂቁ ፡ እምገጸ ፡ ምድር ፡ በማየ ፡ አይኅ ፤ ወንድሙ ፡ ቃየል ፡ የገደለው ፡ የአቤል ፡ ነፍስ ፡ ልጆቹ ፡ በጥፋት ፡ ወሀ ፡ ከምድር ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ እሱን ፡ ስትከስ ፡ ትኖራለች ፡ አለው ፤ ዘፍ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ -፲፯ ።

ደመ ፡ ዘካርያስም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ና ፡ በዕቃ ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ሰብዓ ፡ ዘመን ፡ ሲፈላ ፡ ኑሯል ፤ ጥጦስ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ሲያፈርስ ፡ ሲፈላ ፡ አይቶ ፡ ይህ ፡ ምንድነው ፡ አለ ፤ የጸገ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ነው ፤ አይሁድ ፡ በግፍ ፡ አስገድለውት ፡ እንዲህ ፡ ሲፈላ ፡ ይኖራል ፡ አሉት ፤ ከገጻዮች ፡ ወገን ፡ ሰባት ፡ ሰዎች ፡ አስመጥቶ ፡ ቢያሳርድ ፡ አርፏል ። ፪ዜሎ ፡ ፳፬ ፡ ፳፪ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፴፭ ።

ወኢረስዓ ፡ አውያቶሙ ፡ ለነዳያን ።

የነዳያንንም ፡ ልመናቸውን ፡ ቸል ፡ አ
ላለምና ።

፲፫ ፡ ተሣሃለኒ ፡ እግዚኦ ፡ ወርኢ ፡ ዘከመ ፡ የሐ
ምሙኒ ፡ ጸላእትየ ።

ጠላቶቼ ፡ መከራ ፡ እንዲያፀኑብኝ ፡ መ
ጠን ፡ እይ ፡ ተመልከት ። እንዲህ ፡ አይ
ተህ ፡ ተመልክተህ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

ዘያሌዕለኒ ፡ እምአናቅጸ ፡ ሞት ።

ሞት ፡ ገድሎ ፡ ከሚጥልበት ፡ ከመቃብ
ር ፡ በላይ ፡ የሚያደርገኝ ፡ እሱ ፡ ነው ፡
አንድም ፡ እንዳልሞት ፡ እንዳልቀበር ፡
የሚያደርገኝ ፡ እሱ ፡ ነው ። አንድም ፡
ምክንያት ፡ ሞት ፡ ከሚሆኑ ፡ ከኃያላኑ ፡
በላይ ፡ የሚያደርገኝ ፡ እሱ ፡ ነው ፡
ማለት ፡ አለዚያን ፡ አጥፍቶ ፡ የሚያ
ድነኝ ፡ እሱ ፡ ነው ።

፲፬ ፡ ከመ ፡ እንግር ፡ ኵሎ ፡ ስብሐቲከ ፡ በአናቅ
ጺሃ ፡ ለወለተ ፡ ጽዮን ። መዝ ፡ ፫፻ ፡ ፳፰ ።

በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ጌትነቱን ፡
ተአምራቱን ፡ እነግር ፡ አስተምር ፡
ዘንድ ፡ ጽዮን ፡ የዳዊት ፡ ከተማ ፡ ወ
ለት ፡ የሰሎሞን ፡ ከተማ ፡ እየቀደም ፡
እየሰፋ ፡ ሐዲስና ፡ አንድም ፡ ጽዮን ፡
የሰሎሞን ፡ ወለት ፡ የዳዊት ፡ ሰሎሞ
ን ፡ ያበቱ ፡ ከተማ ፡ ቢጠብበው ፡ ከ
ውጭ ፡ አስፍቶ ፡ አሠርቷልና ። ፩ነገ
፫ ፡ ፩ ። አንድም ፡ ሕግ ፡ መጠበቅ ፡ በ
ሚገባቸው ፡ በምእመናን ፡ ጉባኤ ፡
እነግር ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
የሚያደርገኝ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወንትፌሣሕ ፡ በአድኅኖትከ ።

በትድግናህ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ ንትፌ
ሣሕ ፡ ደስ ፡ ይበለን ።

፲፭ ፡ ጠግዑ ፡ አሕዛብ ፡ በጌጋዮሙ ፡ ዘገብሩ ።

አሕዛብ ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ ጠፉ ።

ወበዛቲ ፡ መሥገርት ፡ እንተ ፡ ኃብኡ ፡ ተሠ
ግረ ፡ እግሮሙ ።

ሠውረው ፡ በመከሩት ፡ ምክር ፡ በሸ
መቁት ፡ ጦር ፡ ጠፉ ።

፲፮ ፡ ያአምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ገቢረ ፡ ፍትሕ ።

እግዚአብሔር ፡ ፍርድን ፡ መፍረድ ፡
ያውቃል ። አንድም ፡ የፍርድ ፡ ገበሬ ፡
ነው ። አንድም ፡ (ፈሊጠ ፡ ፍትሕ) ፡
ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለይቶ ፡ መፍ
ረድ ፡ ያውቃል ። ሰው ፡ የሆነ ፡ እን
ደሆነ ፡ ከነጋገር ፡ ይፈረዳል ፡ ካያያዝ ፡
ይቀደዳል ፡ እንዲሉ ፡ የቃሉን ፡ ሰም
ቶ ፡ ይፈርዳል ። እሱ ፡ ግን ፡ የሐልዮ
ውን ፡ የነቢቡን ፡ የገቢሩን ፡ መርም
ሮ ፡ አውቆ ፡ ይፈርዳል ። ሮሐ ፡ ፳ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ፡
አንድም ፡ የስዱ ፡ ጳውሎስ ፡ ትርጓሜ ፡
(ይትአመር ፡ እግዚአብሔር ፡ በገቢረ ፡
ፍትሕ) ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ መ
ኖሩ ፡ እውነት ፡ በመፍረዱ ፡ ይታወ
ቃል ። በለጸጋውን ፡ ድኃ ፡ ድኃውን ፡
ባለጸጋ ፡ በለጤናውን ፡ ድዉይ ፡ ድ
ዉዩን ፡ ባለጤና ፡ ኃያሉን ፡ ደካማ ፡
ደካማውን ፡ ኃይለኛ ፡ ባደረገው ፡
ጊዜ ፡ ያ ፡ የተበደለ ፡ ድኃ ፡ ለካ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ አለህን ፡ ይላልና ።



ወበግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ተሠግረ ፡ ኃጥእ ።

ኃጥእ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ በቃሉ ፡
በፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ጠፋ ። አንድም ፡
እሱ ፡ ራሱ ፡ በመከረው ፡ ምክር ፡ ጠፋ ።
በእጁ ፡ የተሠራ ፡ ጣዖቱን ፡ በማም
ለኩ ፡ ጠፋ ። አንድም ፡ ኃጥእ ፡ ሳኦ
ል ፡ በእጁ ፡ በተያዘ ፡ ሰይፍ ፡ ጠፋ ።
ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ሲዋጋ ፡ ውሎ ፡ ወደ
ማታ ፡ አንዱ ፡ መርገዘ ፡ ቀብቶ ፡ በቀ
ስት ፡ ወጋው ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ቢያቃጥ
ለው ፡ ብላቴናውን ፡ ቁም ፡ ላዕሌየ ፡
ወቅትለኒ ፡ በኒህ ፡ በቈላፋን ፡ እጅ ፡
ከሞት ፡ ግደለኝ ፡ አለው ። ቀደህ ፡
ያለበስከኝ ፡ ቈርሰህ ፡ ያጐረስከኝ ፡
ጌታዬን ፡ አብሬህ ፡ እሞትን ፡ እገድ
ልህ ፡ አይሆንም ፡ አለው ። ወመልሐ ፡
ሰይፎ ፡ ወተረግዘ ፡ ለሊሁ ፡ በገዛ ፡
ሰይፉ ፡ ወድዶ ፡ ገብቶበታልና ፡ እን
ዲህ ፡ አለ ፡ ፩ሳሙ ፡ ፴፩ ፡ ፫ ፡ ፱ ።

፲፯ ፡ ይግብኡ ፡ ኃጥአን ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ።

ተማጥኛቸዋለሁ ፡ ኃጥአን ፡ ሙተው ፡
ወደ ፡ መቃብር ፡ ይውረዱ ።

ወኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ ይረስዕዎ ፡ ለእግዚ
አብሔር ።

ማን ፡ ማን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ እገሌ
እገሌ ፡ ምን ፡ አሰኝቶኝ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የሚዘነ
ጉ ፡ ሁሉ ፡ ይውረዱ ፡ እንጂ ።

፲፰ ፡ እስመ ፡ አኮ ፡ ለዝሉፉ ፡ ዘይትረሳዕ ፡ ነዳይ ።

ነዳይ ፡ ዳዊት ፡ አንድም ፡ ማናቸውም ፡
ድኃ ፡ የሚዘነጋ ፡ አይደለምና ፡ ለጊ
ዜውም ፡ ቢዘነጋ ፡ እንደተዘነጋ ፡ አይ
ቀርምና ።

ወኢየኃጕል ፡ ትዕግሥቶሙ ፡ ለነዳያን ፡ ለዓለም ።

ነዳያን ፡ ለዘላለሙ ፡ ዓስበ ፡ ትዕግሥ
ታቸውን ፡ አያጡምና ።

፲፱ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ወኢይጽንዕ ፡ ሰብእ ፡
እምሕያው ።

አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሣ
ሰው ፡ በሰው ፡ አይጽና ።

ወይትኰነኑ ፡ አሕዛብ ፡ በቅድሜከ ።

አሕዛብም ፡ በፊትህ ፡ ይጠፉሉ ፡ ይ
ጥፉ ።

፳ ፡ ሢም ፡ እግዚኦ ፡ መምሕረ ፡ ሕግ ፡ ላዕሌ
ሆሙ ።

አቤቱ ፡ ባዕድ ፡ ንጉሥ ፡ እንግሥባ
ቸው ።

ወያእምሩ ፡ (የአምሩ) ፡ አሕዛብ ፡ በከመ ፡ ሰብእ ፡
እሙንቱ ፡ እሙንቱ ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ተገዥ ፡
እንደሆኑ ፡ ያውቃሉ ፡ ይወቁ ። እን
ድም ፡ (ሢም ፡ እግዚኦ ፡ መምሕረ ፡
ሕግ ፡ ላዕሌሆሙ) ፡ ሞትን ፡ አምጣ
ባቸው ፡ መምር ፡ አለው ፡ መምር ፡
እንዳያደላ ፡ ሞትም ፡ አያደላምና ፡
መምህር ፡ ወመገሥፅ ፡ ዘኢያድሉ ፡
ለገጽ ፡ እንዲል ።
አንድም ፡ ሞት ፡ መምጣቱ ፡ ሕግ ፡
በመፍረሱ ፡ ነውና ፡ ወበትእዛዘ ፡ ሕግ ፡
ተሠርዓ ፡ ሞት ፡ እንዲል ።
አንድም ፡ መምር ፡ መከሮ ፡ አስተም
ሮ ፡ ወደ ገዳም ፡ እንዲወስድ ፡ ሞትም ፡

ከእኃው ፡ አንዱን ፡ ንጽል ፡ አድርጎ ፡ የወሰደው ፡ እንደሆነ ፡ ለዚህ ፡ ፡ ዕድ ሚያችን ፡ እያሉ ፡ ወደገዳም ፡ ይሄዳ ሉና ፤ (ወየአምሩ ፡ ከመ ፡ ዕጓለ ፡ እመ ሕያው ፡ እሙንቱ) ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እደሆነ ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ እንደሆኑ ፡ ያውቃሉ ።

፳፩፤ ለምንት ፡ እግዚኦ ፡ ቆምከ ፡ እምርኁቅ ።

አቤቱ ፡ ለምን ፡ ርቀህ ፡ ቆመሃል ፡ በጊ ታ ፡ መራቅ ፡ መቅረብ ፡ ኑርበት ፡ አይ ደለም ፡ መራዳቱን ፡ መቅረብ ፡ አለ መራዳቱን ፡ መራቅ ፡ ብሎ ፤

ወትትሔወር ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤ ።

በመከራዬክ ፡ ቀን ፡ ለምን ፡ ቸል ፡ ትለኛለህ ።

፳፪፤ በትዕቢቱ ፡ ለኃጥእ ፡ ይውዒ ፡ ነዳይ ።

በባለጸጋ ፡ ኀጢአት ፡ ትዕቢት ፡ ድኃ ው ፡ ከእሳት ፡ እንደገባ ፡ ኸርማት ፡ ያር ራል ፡ ይኰማተራል ። እም ተሀብ ፡ ለኃጥእ ፡ ሀብ ፡ ለጻድቅ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ (ለምንት ፡ እግዚኦ ፡ ቆምከ ፡ እምርኁቅ) ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ አም ስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ምሉ ፡ ለምን ፡ ርቀህ ፡ ቆምህ ፡ (ወትትሔወር ፡ በጊ ዜ ፡ ምንዳቤየ) ፡ በመከራ ፡ ነፍሴ ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ቸል ፡ ትላለህ ፡ ሰው ፡ ሆን ህ ፡ ሥጋ ፡ ለብሰህ ፡ አታድነኝምን ፡ (በ ትዕቢቱ ፡ ለኃጥእ ፡ ይውዒ ፡ ነዳይ) ፡ በዲያብ ሎስ ፡ ክፋት ፡ አዳም ፡ ከእሳት ፡ እን ደ ፡ ገባ ፡ ኸርማት ፡ ይቃጠላል ፤ አሁን ፡ በዲብሎስ ፡ ክፋት ፡ አዳም ፡ የሚጐዳ ፡ ሆና ፡ አይደለም ፡ መስሎ ፡ ቢሠራው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ግብሩ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ የሁሉም ፡ አምላክነቱን ፡ መሻት ፡ ነውና ፡ በትዕቢቱ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ተ ኰነነ ፡ አቡን ፡ አዳም ፡ እንዲል ።

ወይውዒ ፡ በውሂዶሙ ፡ እንተ ፡ ሐለዩ ።

አስበው ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ ጠፉ ፡ ይጥፉ ።

፳፫፤ እስመ ፡ ይትዌደስ ፡ ኃጥእ ፡ በፍትወተ ፡ ነፍሱ ።

ኀጥእ ፡ ሰው ፡ ወድዶ ፡ በሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ይመሰገናል ። ይህ ፡ ሌባ ፡ ነው ። ሲመሽ ፡ ጎመዱን ፡ ነጥቆ ፡ ገመ ዱን ፡ ጠቅልሎ ፡ ይሄዳል ፤ ውሻ ፡ ሳ ይጮኽበት ፡ እጥር ፡ ሳይሰበርበት ፡ ግምቡን ፡ ምሶ ፡ ግድግዳውን ፡ አፍር ሶ ፡ ከልጅነት ፡ እስከ ፡ ዕውቀት ፡ ያጠ ራቀመውን ፡ ገንዘብ ፡ ንቅስ ፡ አድ ርጎ ፡ ይዞበት ፡ ይሄዳል ፤ ወዲያው ፡ ተነሥተው ፡ ባዲስ ፡ ፍለጋ ፡ ተከት ለው ፡ ይሄዳሉ ፡ አጥተው ፡ ይመለሳ ሉ ፤ ከሆነስ ፡ ሆንና ፡ ያን ፡ አጥር ፡ ያን ፡ ቅጥር ፡ ያን ፡ ውሻ ፡ ያን ፡ ጋሻ ፡ ምናበ ፡ ጐልማሳ ፡ እናትህ ፡ ትውለድ ፡ መልሳ ፡ መልሳ ፡ ብለው ፡ ይመርቁ ታል ።

ወዓማፂኒ ፡ ይትባረክ ።

ዓመፀኛም ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ይመ ረቃል ፡ ይህ ፡ ቀማኛ ፡ ነው ፡ ከዐፈቀ ፡ ዱር ፡ ከጐድጓዳ ፡ ምድር ፡ ቆይቶ ፡ ሲቀማ ፡ ይውላል ። ማታ ፡ መሰሎቹ ን ፡ ጠርቶ ፡ የሠባ ፡ እርዶ ፡ የጠራ ፡



አውርዶ ፡ ሲያበላ ፡ ሲያጠጣ ፡ ያመ ሽል ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እየሆኑ ፡ እየ ተነሡ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አብላ ፡ አጠጣ ፡ እንጀራ ፡ ከሌማትህ ፡ ሥጋ ፡ ከገበ ታህ ፡ ጠጅ ፡ ከማቶትህ ፡ አይጥፉ ፡ እያሉ ፡ ሲያመሰግኑት ፡ ያመሽሉና ፡ እንዲህ ፡ እለ ፡ ኢላ ፡ ፩ ፡ ፰ ።

ወሀኮ ፡ ኃጥእ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ እግዚአብ ሔርን ፡ አወከው ፡ እንዳያጠፋው ፡ ያበላል ፡ ያጠጣል ፤ እንዳይምረው ፡ ይሠርቃል ፡ ይቀማል ፡ እንግዲህስ ፡ ብሎ ፡ አይተወውም ፡ ብሎ ፡ በሥ ራው ፡ ሁሉ ፡ አወከው ፡ አንድም ፡ ወሀከ ፤ ቀሰቀሰው ፡ ቅሠፈኝ ፡ ቅሠ ፈኝ ፡ አለው ፤ ኀጢአት ፡ ሠርቶ ፡ ንስሐ ፡ አለመግባት ፡ እግዚአብሔ ርን ፡ ቅሠፈኝ ፡ ማለት ፡ ነውና ።

፳፬፤ ወኢይትኀሠሥ ፡ በከመ ፡ ብዝኃ ፡ መዓቱ ።

ጌታ ፡ እንደመዓቱ ፡ ብዛት ፡ አንድም ፡ እንደ ፡ ሰውየው ፡ ኀጢአት ፡ ብዛት ፡ አይመራመረውም ፡ ምናልባት ፡ ይመ ለስስ ፡ እንደሆን ፡ ብሎ ፡ እንዳይመለ ስስ ፡ ያውቃል ፡ ብሎ ፡ ምክንያት ፡ ለ መንሣት ፡ እገሌ ፡ እንዲህ ፡ እስከሁን ፡ ኑሮ ፡ ቢሆን ፡ ንስሐ ፡ በገባ ፡ ነበር ፡ እንዳይሉ ።

ወአልቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅድሜሁ ።

እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ያይብኛል ፡ ይሰማ ብኛል ፡ አይለውም ።

፳፭፤ ወርኩስ ፡ ፍኖቱ ፡ ፍናዊሁ ።

የዚህ ፡ ሰው ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አይቀበለውም ፡ አን ድም ፡ የኀጢአት ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ የተጠላ ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ።

ወግሙት ፡ ኵነኔከ ፡ በቅድሜሁ ።

አንዱን ፡ ይዞ ፡ ይሄዳል ፡ ሕግህ ፡ በ ዚህ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ የፈረሰ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አይጠብቀውም ።

ወይቀንዮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ጸላእቱ ።

እስከሁን ፡ በሽፍትነት ፡ ያደረገውን ፡ ሲናገር ፡ መጥቶ ፡ ነበር ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ተሾሞ ፡ የሚያደርገውን ፡ ያመ ጣል ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ጠላቶ ቹን ፡ እስዉንቶ ፡ ይገዛቸዋል ፤ ምነው ፡ ተጥዶ ፡ አይፈላ ፡ ተሹሞ ፡ አይበላን ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ በቂም ፡ በበቀል ፡ ይገ ዛቸዋል ፤ ኢትስአል ፡ በጎበ ፡ እግዚ አብሔር ፡ መንግሥተ ፡ ወኢትስአ ል ፡ በጎበ ፡ ንጉሥ ፡ መንበረ ፡ ክብር ፡ ወኢትፍቅድ ፡ ከዊነ ፡ መኰንን ፡ ዮጊ ፡ ኢትክል ፡ ተበቅሎቶ ፡ ለዘአበሰ ፡ እ ንዲል ፤ ሲራ ፡ ፯ ፡ ፬ ፡ ፮ ።

፳፮፤ ወይቤ ፡ በልቡ ፡ ወኢይትሀወክ ፡ ለት ውልደ ፡ ትውልድ ፡ ወኢይረክበኒ ፡ እኩይ ።

አረተው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጠፋሀ ል ፡ ቢሉት ፡ በልቡ ፡ እስበ ፡ በቃሉ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ መከራ ፡ የለብኝም ፡ በልጅ ፡ ልጅ ፡ በልተህ ፡ ጠጥተህ ፡ ና ፡ ብሎኛል ፡ ይላል ።

፳፤ ፡ ምሉእ ፡ አፉሁ ፡ መርገመ ፡ ወጽልሑት ።
እንደበቱ ፡ ክፋት ፡ ሸንገላን ፡ መርገ
ምን ፡ የተመላ ፡ ነው ።

ታሕተ ፡ ልሳኑ ፡ ጻማ ፡ ወሕማም ፡ ርግዒ ፡ ርሁ ።
ታሕተ ፡ መንጸፍ ፡ እንዲል ፡ ባንደበ
ቱ ፡ ሰውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ መር
ገም ፡ አለ ። እንድም ፡ እንደበቱ ፡ ሰ
ውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ መርገምን ፡
የተመላ ፡ ነው ።

፳፰ ፡ ይጸንሕ ፡ ወንደው ፡ ምስለ ፡ ብዑላን ።
እስከሁን ፡ ተሹሞ ፡ የሚያደርገውን ፡
ሲናገር ፡ መጥቶ ፡ ነበር ፡ እንግዲህ ፡
ተሽሮ ፡ የሚያደርገውን ፡ ያመጣል ፡
ይሸምቃል ፡ ከባለጠጎች ፡ ጋራ ፡ ደጅ ፡
ይጠናል ፡ ወደቤቱ ፡ ልሒድ ፡ አይልም ።

ከመ ፡ ይቅትሎ ፡ ለንጹሕ ፡ በጽሚት ።
ድኃውን ፡ ይጉዳው ፡ ዘንድ ፡ ንጹሕ ፡
አለው ፡ ድኃውን ፡ ሳይጣላው ፡ ይጣ
ላዋልና ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከ ፡ ያለ
ውን ፡ ይዞ ፡ ይኖራልና ፡ ገንዘብ ፡ የለ
ውምና ፡ ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።

ወአዕይንቲሁ ፡ ገበ ፡ ነዳይ ፡ ያስተሐይያ ።
ዓይኖቹም ፡ ድኃውን ፡ ይመለከታሉ ፡
እገሌ ፡ መጣ ፡ ምን ፡ ሊናገር ፡ ይሆን ፡
ይላል ።

፳፱ ፡ ይጸንሕ ፡ ወይትኀባእ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡
ውስተ ፡ ግበ ።
አንበሳ ፡ ከጸፈቀ ፡ ዱር ፡ ከጐድጓዳ ፡
ምድር ፡ ቆይቶ ፡ እንዲደፍጥ ፡ እሱ
ም ፡ የባለጸጋውን ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ዱር ፡
አድርጎ ፡ ይደፍጣል ።

ይጸንሕ ፡ ከመ ፡ ይምሥጦ ፡ ለነዳይ ።
ነገር ፡ በመሥራት ፡ ደኻውን ፡ ይጉ
ዳው ፡ ዘንድ ፡ ይደፍጣል ።

ይመስጦ ፡ ለነዳይ ፡ ወይስሐቦ ።
ነገሩን ፡ ይነጥቀዋል ፡ ከነገሩ ፡ ያገባ
ዋል ፡ ማሩን ፡ ሙክቱን ፡ ይዞ ፡ ይመ
ጣል ። ርስቱም ፡ ከዚህ ፡ ግብሬም ፡
ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይሰጣል ። ያ ፡ ሰው ፡
እገሌ ፡ እንዲህ ፡ ትላለህን ፡ ርስትህም ፡
ከዚህ ፡ ከዚህ ፡ ግብርህም ፡ እንዲህ ፡
እንዲህ ፡ ነው ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ እን
ዲህ ፡ ያለ ፡ ውርርድ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ዳኝነት ፡ አለብህ ፡ ብሎ ፡ ለዳኛ ፡ ይ
መራል ።

ወያኀሥሮ ፡ በመሥገርቱ ፡ ዘፀ ፡ ፳፭ ፡ ፲፱ ።
ነገር ፡ በመሥራቱ ፡ ያዋርደዋል ፤ ወ
አውዕአ ፡ ከመ ፡ ያኅሥሮ ፡ በመስገር
ቱ ፡ እንዲል ፤ እንድም ፡ የዓሥሮ ፡
ይላል ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ዳኛው ፡ በሰ
ንሰለቱ ፡ ያሥረዋል ፤ እንድም ፡ ያዓ
ሥሮ ፡ ይላል ፡ አጅሬ ፡ በዚህ ፡ ታሥ
ሮ ፡ ነው ፡ ገንዘብ ፡ የሚወጣው ፡ እረ ፡
የኔ ፡ አንድ ፡ አይፈታሽ ፡ ጅቡ ፡ አለ ፡
ብሎ ፡ ከድጉ ፡ ፈትቶ ፡ ሰጥቶ ፡ ያ
ሳስረዋል ። ኢሳ ፡ ፳፱ ፡ ፳፩ ።

፴ ፡ ይትቀጻዕ ፡ ወይወድቅ ፡ ሶበ ፡ ቀነዮ ፡ ለነዳይ
አሁን ፡ ለ ፡ አይረባም ፡ ቀነዮን ፡ ሲ
ያይ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ እስጨንቆ ፡ እ
ስጠብበ ፡ ባጋዘው ፡ ጊዜ ፡ ድኃው ፡
ይወድቃል ፡ ይነሣል ።



፴፩ ፡ ወይብል ፡ በልቡ ፡ ይረስዓኒ ፡ እግዚአብሔር ።
በልቡ ፡ አስቦ ፡ በቃሉ ፡ ምን ፡ አደር
ጋለሁ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡
ረሥቶኛል ፡ ላውስ ፡ ላጉንብስ ፡ እን
ጂ ፡ ይላል ።

ወሜጠ ፡ ገጾ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይ ፡ ለግሙራ ።
እኔን ፡ እንዳያይ ፡ ገጹ ፡ ምህረቱን ፡
ወደዚያ ፡ መልሶታል ፡ ይላል ። እን
ድም ፡ (ይትቀጻዕ ፡ ወይወድቅ ፡ ሶበ ፡
ቀነዮ ፡ ለነዳይ) ፡ ለ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡
ነው ፤ ባለጸጋው ፡ በድኃው ፡ መከራ ፡
ከአጸናበት ፡ በኋላ ፡ በሱ ፡ መከረ ፡
መጥቶበት ፡ ፈንታውን ፡ ይወድቃ
ል ፡ ይነሣል ፤ (ወይብል ፡ በልቡ ፡ ይረ
ሥዓኒ ፡ እግዚአብሔር) ፡ በልቡ ፡
አስቦ ፡ በቃሉ ፡ ለጊዜው ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ረሥቶኛል ። (ወሜጠ ፡ ገጾ ፡
ከመ ፡ ኢይርአይ ፡ ለግሙራ) ፡ ገጹ ፡
ምሕረት ፡ ገጹ ፡ ረድኤቱን ፡ ከሌላው ፡
ወደኔ ፡ መልሶታል ፡ ይላል ፤ እንድም
ለከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልረሳልኝ ፡
ኑሯል ፡ ገጹ ፡ ምሕረቱንም ፡ ወደዚያ ፡
መልሶታል ፡ ይላል ።

፴፪ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ ወትትለ
ዓል ፡ እዴከ ።
እቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሥ
ተህን ፡ ሥልጣንህን ፡ ግለጸው ።

ወኢትርሥዖሙ ፡ ለነዳያን ።
ነዳያንን ፡ አትዘንጋቸው ፡ ለጊዜውም ፡
ብትዘነጋቸው ፡ እንደዘነጋሃቸው ፡ አ
ይቅሩ ።

፴፫ ፡ በእንተ ፡ ምንት ፡ አምዕዖ ፡ ኃጥእ ፡ ለእግ
ዚአብሔር ።
ኃጥእ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በም
ን ፡ አሳዘነው ፡ ብትል ፡ (ቢሉ) ።

እስመ ፡ ይብል ፡ በልቡ ፡ ኢይትኀሠሠኒ ።
በልቡ ፡ አስቦ ፡ በቃሉ ፡ አይመራም
ረኝም ፡ ስላለ ፡ አይዶለምን ፡ እንድ
ም ፡ ስላለ ፡ ነዋ ።

፴፬ ፡ ትሬኢኑ ፡ ከመ ፡ ለሊከ ፡ ትኔጽር ፡ ጻማ ፡ ወ
ሙስተ ።
ባለጸጋውን ፡ ነው ፡ በድኃው ፡ ጻማ ፡
መዓትህን ፡ እምጥተህበት ፡ ፈንታ
ህን ፡ ጻማ ፡ መዓትህን ፡ እንድታይ ፡ ታ
ያለህን ።

ወከመ ፡ ትግድፍ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ።
በእጅህ ፡ በትረ ፡ መዓትን ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ እንድትሰጠው ፡ ታያለህ
ን ፤ እንደ ፡ ደረቅ ፡ ሴት ፡ ከባሏ ፡ የ
ተጣላች ፡ እንደሆነ ፡ ወንዶ ፡ አታደ
ርገውምን ፡ ግንባሬን ፡ ብላ ፡ ማግለ
ያዋን ፡ ትሰጠዋለችና ።

ላዕሌከ ፡ እንከ ፡ ተገድፈ ፡ ነዳይ ።
ይህ ፡ ድኃ ፡ ባንተ ፡ ፈቃድ ፡ የተፈ
ጠረ ፡ መስሎሃልን ፡ ተገድፈ ፡ ማለ
ት ፡ ሰው ፡ የሚፈጠር ፡ ከባት ፡ ዘር ፡
ከናት ፡ ደም ፡ ተከፍሎ ፡ ነውና ።

ወእንተኑ ፡ ረዳኢሁ ፡ ለእጓለ ፡ ማውታ ።
የድኃውስ ፡ ረዳቱ ፡ አንተ ፡ ነህን ፤ ወ
ተዓቅበ ፡ እምእሳት ፡ ወማይ ፡ እንዲ
ል ፡ የበላችው ፡ እንዳይጫነው ፡ የጠ

ጣችው ፡ እንዳያንዝዘው ፡ የምትጠብቀው ፡ አንተ ፡ ነህን ።

እንድም ፡ (ትሬኢኑ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ይኤድር ፡ ጻማ ፡ ወመዓተ) ፡ ጌታን ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ጌትነትህ ፡ እንደ ፡ ፈታሒነትህ ፡ ድኃውን ፡ ለባለጸጋ ፡ አሳልፈህ ፡ ሰጥተኸው ፡ ጻማ ፡ መዓትን ፡ እንዲያይ ፡ ታያለህን ፡ (ወከመ ፡ ትሚጥዎ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ) ፡ እንደተሸጠ ፡ ባሪያ ፡ ለባለጸጋው ፡ አሳልፈህ ፡ እንደሰጠኸው ፡ ታያለህን ፡ (ላዕሌከኑ ፡ እንከ ፡ ተገድፈ ፡ ነዳይ) ፡ እምኔከኑ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እኔስ ፡ በባለጸጋው ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ፡ ከንተም ፡ ዘንድ ፡ ተለይቷልን ፡ (ወአንተኑ ፡ ረዳኢሁ ፡ ለእጓለ ፡ ማውታ) ፡ የባለ ፡ ጸጋውስ ፡ ረዳት ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ በጥንተ ፡ ግብሩ ፡ ዕጓለ ፡ ማውታ ፡ አለው ፡ ሲወለድ ፡ ያንገት ፡ ፈትል ፡ ድርጎ ፡ እህል ፡ ይዞ ፡ አልተወለደምና ፡ ዕራቅየ ፡ ወፃዕኩ ፡ እምከርሠ ፡ እምየ ፡ ወዕራቅየ ፡ እገብእ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ እንዲል ። ኢዮ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ።

፴፭ ፡ ቀጥቅጥ ፡ መዝራዕቶ ፡ ለኃጥእ ፡ ወለእኩይ ።

እኔስ ፡ የድኃው ፡ ረዳት ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ የባለጸጋውን ፡ ረዳት ፡ አይደለሁም ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ የባለጸጋውን ፡ ሥልጣን ፡ አጥፋ ።

ወትትኃሠሥ ፡ ኃጢአቱ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወኢትትረከብ ።

ድኃውን ፡ ስለበደለ ፡ የባለጸጋው ፡ ኃጢአት ፡ ትመረመራለች ፡ ትትረከብ ፡ በዝታ ፡ ተርፋ ፡ ትገኛለች ፡ (ኢትትረከብ) ከቀጥር ፡ በዝታ ፡ ተርፋ ፡ ልኳ ፡ አይታወቅም ። እንድም ፡ ድኃውን ፡ ስለበደለ ፡ የባለጸጋው ፡ ኀጢአት ፡ ትመረመራለች ፡ ኢትትረከብ ፡ እሱን ፡ ከተፈተለ ፡ ገመድ ፡ ከተተከለ ፡ ግንድ ፡ ከተቈፈረ ፡ ጉድጓድ ፡ አድርሳው ፡ አትገኝም ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ወፎ ፡ ተዋርጄ ፡ እንዲሉ ፡ እንድም ፡ ባለጸጋውን ፡ በደለ ፡ ስለማለት ፡ የድኃው ፡ ኀጢአት ፡ ትመረመራለች ፡ ኢትትረከብ ፡ አትገኝም ፡ ድኅ ፡ ይበደላል ፡ እንጂ ፡ አይበድልምና ፡ ትትረከብ ፡ ጥቂት ፡ ትገኛለች ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ የማይበድል ፡ እንጨት ፡ ሁኖ ፡ የማይጤስ ፡ የለምና ፡ ባይበድልም ፡ እንዲያውስ ፡ አቶ ፡ እገሌን ፡ ከሰው ፡ ፊት ፡ ታቆመውን ፡ አውስ ፡ አጎንብስ ፡ ይሉታልና ፡ እንድም ፡ ወትትኃሠሥ ፡ ኃጢአቶ ፡ ይላል ፡ የባለጸጋውን ፡ ኃጢአት ፡ ትመረምራለህ ፡ ትትረከብ ፡ በምልዓት ፡ ትኖራለህ ፡ ትፈርዳለህ ፡ ኢትትረከብ ፡ በፍዳው ፡ አለፍ ፡ የሚልህ ፡ የለም ።

፴፮ ፡ ይነግሥ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ። ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ።

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ይነግሣል ፡ ማለት ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ይኖራል ።

ወይትሐጐሉ ፡ አሕዛብ ፡ እምድር ።

አሕዛብ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እንድም ፡ ከሰው ፡ ተለይተው ፡ ይጠፋሉ ።



፴፯ ፡ ፍትወቶሙ ፡ ለነዳያን ፡ ሰምዐ ፡ እግዚአብሔር ።

ነዳያን ፡ ወድደው ፡ የለመኑትን ፡ ልመናቸውን ፡ ሰምቷልና ።

መኀሊና ፡ ልበሙኒ ፡ አጽምዐት ፡ እዝኑ ።

አስበው ፡ የለመኑትን ፡ ልመናቸውን ፡ እዝነ ፡ ፈቃዱ ፡ ሰምታለችና ።

፴፰ ፡ ፍትሑ ፡ ለነዳይ ፡ ወለእጓለ ማውታ ።

አባት ፡ እናት ፡ ለሞቱበት ፡ ለድኃ ፡ ፍረዱ ፡ አሁን ፡ አድልታችሁ ፡ ፍረዱ ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ እውነት ፡ ፈረዳችሁ ፡ ቢረታ ፡ ዳኝነት ፡ ቢረታ ፡ ማግለጃ ፡ አትቀበሉ ፡ ሲል ፡ ነው ። እንድም ፡ ድኃ ፡ በደሉን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንገሩ ፡ ፍርዱ ፡ ነው ። ለእግዚአብሔር ፡ ከልነገረ ፡ ለማን ፡ ይንገር ። ዘፀ ፡ ፳፫ ፡ ፮ ፡ ፫ ።

ከመ ፡ ኢይድገሙ ፡ እንከ ፡ ዐቢይ ፡ ኰሥሕያሙ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ በዲበ ፡ ምድር ።

አጥፈን ፡ ዘርግተን ፡ መልሰን ፡ ቀልሰን ፡ እንናገራለን ፡ ማለትን ፡ እንዳይደግሙ ፡ እንድም ፡ አልዕሎ ፡ ቃሎሙ ፡ ገንታ ፡ ብለን ፡ እንናገራለን ፡ ማለትን ፡ እንዳይደግሙ ።

## መዝሙር ፡ ፲፩ ።

፩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተወከልኩ ፡ እፎ ፡ ትብልዋ ፡ ለነፍስየ ።

በሳኦል ፡ ጊዜ ፡ ስለራሱ ፡ ተናግሮታል ። ሲሞን ፡ ኢያሶን ፡ የሚባሉ ፡ መስተዋድያን ፡ ነገር ፡ ነበሩ ፡ ሳኦል ፡ በመንግሥት ፡ ያለ ፡ ነውና ፡ ለጊዜው ፡ ይሾመናል ፡ ይሸልመናል ፡ ብለው ፡ ዳዊት ፡ ከዚህ ፡ ውሏል ፡ ከዚህ ፡ አድሯል ፡ አገኘኸውም ፡ ዛሬ ፡ አጣኸውም ፡ ዛሬ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ይነግሩታል ፡ ዳዊትም ፡ እንደ ፡ ተቀባ ፡ ያውቃሉና ፡ ኋላ ፡ ይሾመናል ፡ ይሸልመናል ፡ ብለው ፡ ዛሬ ፡ ሳኦል ፡ ሊይዝህ ፡ ይመጣል ፡ ከሚሠውርህ ፡ ዱር ፡ ከሚያጠልቅህ ፡ ባሕር ፡ ግባ ፡ ካደርህበት ፡ አትዋል ፡ ከዋልህበት ፡ አትደር ፡ እያሉ ፡ ይነግሩታል ። ፩ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፲፱ ።

ሲሞን ፡ ኢያሶን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምኛለሁ ፡ ሰውነቴን ፡ ምን ፡ በይ ፡ ትኋታላችሁ ።

እንደ ፡ ወፍ ፡ ተጸለሊ ፡ ውስተ ፡ አድባር ።

ወፍ ፡ ከንዱ ፡ ተራራ ፡ ወዳንዱ ፡ ተራራ ፡ እንዲዞር ፡ እኔም ፡ ከሀገሬ ፡ ወጥቼ ፡ ከዘመዴ ፡ ተለይቼ ፡ በረሀ ፡ ለበረሀ ፡ እንከራተታለሁ ፡ ሰውነቴን ፡ ምን ፡ በይ ፡ ትኋታላችሁ ። እንድም ፡ የሲዲ ፡ ጳውሎስ ፡ ትርጓሜ ፡ ብሎ ፡ አኸያዪን ፡ አስራለሁ ፡ አበንም ፡ አምናለሁ ፡ እንዲሉ ። እኔ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምናለሁ ፡ ሰውነቴን ፡ ምን ፡ በይ ፡ ትኋታላችሁ ፡ (ዲሊኑ) ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ ብር ፡ ብለሽ ፡ ጥፊ ፡ ትኋታላችሁን ።

፪ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ኃጥኣን ፡ ወሰቁ ፡ ቀስቶሙ ።

ሲሞን ፡ ኢያሶን ፡ ቀስት ፡ ምክራቸውን ፡ ቀፍረዋልና ።

ወእስተዳለዉ ፡ አሕፃቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ምጕንጳቲሆሙ ። ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ።

በጕራንጕሬ ፡ ልባቸው ፡ ቀስት ፡ ምክ ራቸውን ፡ አዘጋጅተዋልና ።

ከመ ፡ ይንድፍዎሙ ፡ ለርቱዓነ ፡ ልብ ፡ በጽሚት ።

ቅን ፡ ልቡና ፡ ያላቸው ፡ የዳዊትን ፡ ወ ገኖች ፡ በምክራቸው ፡ ይጐዱቸው ፡ ዘንድ ፡ ይንድፍዎ ፡ ይላል ፡ ቅን ፡ ልቡ ና ፡ ያለው ፡ ዳዊትን ፡ ይጐዱት ፡ ዘን ድ ፤ እንድም ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ኃጥአ ን ፡ ወሰቁ ፡ ቀስቶሙ ፡ እለ ፡ ሳኦል ፡ በቁሙ ፡ ቀስታቸውን ፡ ቀፍረዋልና ። (ወእስተዳለው ፡ አሕፃቲሆሙ ፡ ውስ ተ ፡ ምጕንጳቲሆሙ) ፤ ፍላጻቸውንም ፡ በሸፋፍ ፡ ሸፍነዋልና ፤ (ከመ ፡ ይንድ ፍዎሙ ፡ ለርቱዓነ ፡ ልብ ፡ በጽሚት) ፡ የዳዊትን ፡ ወገኖች ፡ ይገድሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ይንድፍዎ ፡ ይላል ፡ ዳዊትን ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ።

፫ ፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ ዘአንተ ፡ ሠራዕከ ፡ እሙንቱ ፡ ነሠቱ ።

ጻድቀ ፡ ኢትቅትል ፡ ያልከውን ፡ አፍ ርሰዋልና ።

ወጻድቅሰ ፡ ምንተ ፡ ገብረ ።

ጻድቅ ፡ ዳዊትማ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ይህስ ፡ አይደለም ፡ አስቀድመው ፡ ያ ልጠበቁትን ፡ በሱ ፡ ጊዜ ፡ ይጠብቁ ታልን ፡ ብሎ ፤ (እስመ ፡ ናሁ ፡ ዘአንተ ፡ ሠራዕከ ፡ እሙንቱ ፡ ነሠቱ) ፡ አፍቅ ሩ ፡ ጸላእተከሙ ፡ ያልከውን ፡ አፍ ርሰዋልና ፤ (ወጻድቅሰ ፡ ምንተ ፡ ገብ ረ) ፡ ጻድቅ ፡ ዳዊትማ ፡ ምን ፡ አደረ ገ ፡ ማለት ፡ ጠላትን ፡ ሊሹት ፡ የተገ ባ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ዳዊትማ ፡ ወዳጆቸው ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ጠላታቸው ፡ ነኝን ፡ እን ድም ፡ (እስመ ፡ ናሁ) ፡ አፍቅር ፡ ቢፀ ከ) ፡ ያለውን ፡ አፍርሰዋልና ፤ ወጻድ ቅስ ፡ እንዳለፈው ።

፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ጽርሐ ፡ መቅደሱ ።

ወሰቁ ፡ እስተዳለዉ ፡ ብለህስ ፡ ነገር ከኝ ፤ ጌታ ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ዝም ፡ አለን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆ ነ ። እግዚአብሔርስ ፡ በሰማያዊት ፡ መቅደሱ ፡ አለ ።

እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ መንበሩ ።

በሰማያዊት ፡ መንበሩ ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ይፈርዳል ፡ ዝም ፡ አይልም ።

ወአዕይንቲሁኒ ፡ ኀበ ፡ ነዳይ ፡ ይኔጽራ ።

ዓይኖቹም ፡ ዳዊትን ፡ እንድም ፡ ማና ቸውንም ፡ ድኃ ፡ ይመለከታሉ ።

ወቀራንብቲሁኒ ፡ የሐቶ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ።

ዓይኖቹም ፡ ሰውን ፡ ይመረምራሉ ። በቀራንብት ፡ መላው ፡ በሕርዩ ፡ ማ ወቁን ፡ መናገር ፡ ነው ። እንድም ፡ (ወቀራንብቲሁኒ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያ ው) ፡ ነው ፡ ሰው ፡ በይን ፡ ጥቅሻ ፡ በከንፈር ፡ ንክሻ ፡ የሚሠራውን ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ያውቃል ።

፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ የሐትቶ ፡ ለጻድቅ ፡ ወለኃጥእ ።

የሐቶም ፡ ይላል ። እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ ዳዊትን ፡ ኀጥእ ፡ ሳኦልን ፡ ይመረምራል ። እንድም ፡ ጻድቁን ፡ ኃጥኡን ፡ ይመረምራል ፤ መርምሮ ፡ ለጻድቁ ፡ ዋጋውን ፡ ይሰጠዋል ፤ በኃ ጥኡ ፡ ፍዳ ፡ ያመጣበታል ።



እምአፈ ፡ ደቂቅ ፡ ወሕፃናት ፡ አስተዳሎከ ፡ ስብሐተ ፤ መዝሙር ፡ ፰ ።



ቀነዊኒ ፡ እደውየ ፡ ወእገርየ ፤ መዝሙር ፡ ፳፩ ።

2014 04 17

ዘሰ ፡ አፍቀራ ፡ ለኃጢአት ፡ ጸልአ ፡ ነፍሶ ። ኢሳ ፩ ፡ ፲፰ ።

ዓመፅን ፡ የወደደ ፡ ሳአል ፡ ሰውነቱ ን ፡ ጠላ ፡ በል ።

፯ ፤ ይዘንም መግገር ፡ ላዕለ ፡ ኃጥኣን ፤ ።

መሣግር ፡ ካለ ፡ ይዘንማ ፡ ይዘንም ፡ ካለ ፡ መሥገርት ፡ ቢል ፡ በቀና ፡ ነበ ር ፡ ልማደ ፡ መጻሕፍት ፡ ነው ፡ መዓ ቱ ፡ በነሳአል ፡ ይዘንምባቸዋል ፡ ምን ው ፡ ምንዳቤያትሰ ፡ ኢከና ፡ ርሑቃ ተ ፡ እምኔኪ ። አላ ፡ ይነቅዓ ፡ እምታ ሕተ ፡ እግርኪ ፡ ይል ፡ የለምን ፤ እ ምሰማይ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ የመዓቱን ፡ ብዛት ፡ መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ ከጌታ ፡ ስለታዘዘ ፤ አንድም ፡ በቁሙ ፡ ከሰማይ ፡ የሚወርድ ፡ መዓት ፡ አለ ና ፡ እንደ ፡ ሰብአ ፡ ትከት ፡ እንደ ፡ ሰብአ ፡ ሰዶም ፡ እንደ ፡ ሰብአ ፡ ገሞራ ፡ አንድም ፡ ለአፍርሆ ፡ ለአደንግፆ ፡ ሰው ፡ ጦር ፡ ተወረወረብህ ፡ መርግ ፡ መጣብህ ፡ ሲሉት ፡ ይፈራልና ፡ እን ደ ፡ ወገርሳም ፡ እንደ ፡ ሰማርድ ፡ መ ሬት ፡ ቆፍረው ፡ ደንጊያውን ፡ ጸፍ ጽፈው ፡ ዕንጨቱን ፡ ረብርበው ፡ ሥ ጋውን ፡ ከውስጥ ፡ አድርገው ፡ ይሔ ዳሉ ፡ አውሬ ፡ ሳብ ፡ ያደረገው ፡ እን ደሆን ፡ በላዩ ፡ ይደፋብታልና ።

እሳት ፡ ወተይ ፡ መንፈስ ፡ ዓውሎ ፡ መክፈልተ ፡ ጽዋዖሙ ።

ገሳት ፡ የሰብአ ፡ ሰዶም ፡ ተይ ፡ ነገው ን ፡ ሊጠፉ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ መላእክት ፡ ድኝ ፡ ሲነሰንሱበት ፡ ታይተዋል ። ዘፍ ፡

፲፱ ፡ ፳፱ ። መንፈስ ፡ ዓውሎ ፡ ጥቅመ ፡ ሰናፆርን ፡ ያጠፋበት ፡ ነው ። ይህን ፡ የ መሰለ ፡ ሁሉ ፡ በነሳአል ፡ ተደርጎባቸ ዋልና ፤ አንድም ፡ እሳት ፡ ቋዱ ፡ ሲቃ ጠል ፡ ተይ ፡ ከደኃራው ፡ ሲገናኝ ፡ መ ንፈስ ፡ ዓውሎ ፡ አካለ ፡ ዓውሎ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ፍጥነቱን ፡ ሲያይ ። አንድም ፡ ነፍስ ፡ አይቶ ፡ ይተነፍሰዋል ፡ መጥቶ ፡ ሲጥል ፡ በጌላቡሄ ፡ የተደረገውን ፡ መናገር ፡ ነው ። ሉቃ ፡ ፴፩ ፡ ፩-፲፫ ።

እስመ ፡ ጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጽድቀ ፡ አፍቀረ ።

እግዚአብሔር ፡ ዕውነትን ፡ ይወድዳ ልና ፡ አንድም ፡ ዕውነትን ፡ የያዘ ፡ ሰ ውን ፡ ይወድዳልና ።

ወርትዐሰ ፡ ትሬእዮ ፡ ገጹ ።

ርትዕ ፡ ዳዊት ፡ ግን ፡ በባለሟልነት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ። አንድም ፡ ወራ ትዓንሰ ፡ ይሬእዩ ፡ ገጾ ። ራትዓን ፡ የዳ ዊት ፡ ባለሟሎች ፡ ግን ፡ በባለሟልነ ት ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉና ። ወአዕይ ንቲሁኒ ፡ ኀበ ፡ ነዳይ ፡ ይኔጽራ ፡ ላለ ው ። አንድም ፡ እስመ ፡ ጻድቅ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ወጽድቀ ፡ አፍቀረ ። እ ግዚአብሔር ፡ ዕውነትን ፡ ይወድዳል ና ፡ አንድም ፡ ዕውነትን ፡ የያዘ ፡ ሰው ን ፡ ይወድዳልና ። ወርትዐሰ ፡ ትሬእ ዮ ፡ ገጾ ። ርትዕ ፡ ዳዊት ፡ በባለሟል ነት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ። አንድም ፡ ወ ራትዓን ፡ ይሬእዩ ፡ ገጾ ። ራትዓን ፡ የ ዳዊት ፡ ወገኖች ፡ በባለሟልነት ፡ ጸን ተው ፡ ይኖራሉ ።

«ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም» ።

አሜን ።

፩ ፡ እድኅንኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ኀልቀ ፡ ኄር ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ፡ ነው ፡ በሳኦል ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግሮታል ፤ ከነሳኦል ፡ ወገን ፡ በጎ ፡ ቸር ፡ ጠፍቷልና ፡ አድነኝ ፡ አቤቱ ፤ ሉቃ ፡ ፲፰ ፡ ፰ ፤

ወውኅደ ፡ ሃይማኖት ፡ እምእጓለ ፡ እመሕያው ።

ከነገደ ፡ ብንያምም ፡ ወገን ፡ መተማመን ፡ ጠፍቷልና ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ አንድነት ፡ ሦስትነት ፡ አይደለም ፡ መተማመን ፡ ሲል ፡ ነው ።

፪ ፡ ከንቶ ፡ ይትናገሩ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ።

ይትናገሩ ፡ ከለ ፡ ፩ዱ ፡ ወካልዑ ፡ ቢል ። ምስለ ፡ ካልኡ ፡ ከለ ፡ ይትናገር ፡ ቢል ፡ ይቀናል ፡ ልማደ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ወኢ ይትገሐሡ ፡ ፩ዱ ፡ ምስለ ፡ ካልዑ ።

ሐናንያ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ተማከረው ፡ ቀሠጡ ፡ መንፈቀ ፡ ሤጡ ፡ ሌሊት ፡ ምስለ ፡ መዓልት ፡ ይትከፈልዎ ፡ ለዘመን ፡ በሰሩይ ፡ እንዲል ፡ እንዱ ፡ ከንዱ ፡ ጋራ ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ይናገራሉ ።

በከናፍረ ፡ ጕሕሉት ፡ ልብ ፡ ወበልብ ፡ ይትናገሩ ።

ያም ፡ የልቡን ፡ በልቡ ፡ አኑሮ ፡ ያም ፡ የልቡን ፡ በልቡ ፡ አኑሮ ፡ በከዳተኛ ፡ አንደበት ፡ ይነጋገራሉ ። እንድም ፡ በአርእስቱ ፡ (በእንተ ፡ ሕፀፀ ፡ ሃይማኖት ፡ በእንተ ፡ ሳምኒት ፡ ዘመን) ፡ ይላል ። (አድኅነኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ኀልቀ ፡ ኄር ፡ ከስምንተኛው ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ በጎ ፡ ቸር ፡ ጠፍቷልና ፡ አድነኝ ። የስምንተኛው ፡ ሺሕ ፡ ነገር ፡ ተገልጾለት ፡ ጸልዮታል ፡ በሚመጣውም ፡ መጸለይ ፡ ልማድ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ ናዖድ ፡ የስምንተኛው ፡ ሺሕ ፡ ነገር ፡ ተገልጾላቸው ፤ ከጊዜው ፡ አታድርሰኝ ፡ ከእሀል ፡ ከወሀው ፡ አታቅምሰኝ ፡ እያሉ ፡ ይጸልዩ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ስምንተኛው ፡ ሺሕ ፡ በመስከረም ፡ ሊገባ ፡ በነሐሴ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ አርፈዋል ። ከንቶ ፡ ይትናገሩ) ፡ እንዳለፈው ። (በከናፍረ ፡ ጕሕሉት ፡ ልብ ፡ ወበልብ ፡ ይትናገሩ) ፡ እየተቋጸሩ ፡ እየተማተሩ ፡ እየተጓመዱ ፡ በከዳተኛ ፡ አንደበት ፡ ይነጋገራሉ ።

፫ ፡ ይሤርዎን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለከናፍረ ፡ ጕሕሉት ።

በከፍናር ፡ መላውን ፡ አካል ፡ መናገር ፡ ነው ። በከዳተኛ ፡ አንደበት ፡ የሚነጋገሩትን ፡ ሰዎች ፡ ያጠፋቸዋል ።

ወለልሳን ፡ እንተ ፡ ተአቢ ፡ ነቢበ ፡ ገላ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ።

መቀባጠር ፡ የምታበዛ ፡ አንደበትንም ፡ ነቃቅሎ ፡ ይጥላታል ። ይሤርዋ ፡ ያለበት ፡ ነው ። ተውህበ ፡ ጳውሎስ ፡ ሙቁሕ ፡ ብሎ ፡ ወካልእኒሁ ፡ ሙቁሐን ፡ ባለጊዜ ፡ ተውህበ ።



ትኤምኃከሙ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብሎ ፡ ወማርቆስ ፡ ወልድየ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ይኤምኃከሙ ፡ እገብዓ ፡ ለኤልዛቤል ፡ ኀበ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ምስካብ ፡ ብሎ ፡ ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ዘመዉ ፡ ምስሌሃ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ እገብዖሙ ፡ እንዲወርድ ።

፬ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ናዓቢ ፡ ልሳናቲነ ።

አጥፊን ፡ ዘርግተን ፡ መልሰን ፡ ቀልሰን ፡ እንናገራለን ፡ የሚሉትንም ፡ ያጠፋቸዋል ። እግዚአብሔር ፡ አንደበት ፡ መስጠቱ ፡ እሱን ፡ ልናመሰግንበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰውን ፡ ልንሰድብበት ፡ አይደለምና ። እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወሀበነ ፡ ልሳነ ፡ አከ ፡ ከመ ፡ ንጽርፍ ፡ ቦቱ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ንሰብሖ ፡ እንዲል ።

ወከናፍሪነኒ ፡ ኀቤነ ፡ እሙንቱ ።

እረ ፡ ተዉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጠፋችኋል ፡ ሲሏቸው ፡ እንዳች ፡ እንደበታችንን ፡ ተውሰነዋል ? ገዝተነዋል ? የሚሉትን ፡ ያጠፋቸዋል ።

፭ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእነ ፡ በእንተ ፡ ሕግሞሙ ፡ ለነዳያን ፡ ወበእንተ ፡ ገዓሮሙ ፡ ለሙቁሓን ።

በድኆች ፡ መከራ ፡ ብናጸናባቸው ፡ የታሠሩትን ፡ እህል ፡ ወሀ ፡ ከልክለን ፡ ፀሐይ ፡ ንሥተን ፡ መከራ ፡ ብናጸናባቸው ፡ ብናስጨንቃቸው ፡ የሚፈርድብን ፡ ጌታ ፡ ማን ፡ ነው ፡ የሚሉትን ፡ ያጠፋቸዋል ። እንድም ፡ (እለ ፡ ይብሉ ፡ ናዓቢ ፡ ልሳናቲነ) ፡ አጥፊን ፡ ዘርግተን ፡ መልሰን ፡ ቀልሰን ፡ እንናገራለን ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ (ወከናፍሪነኒ ፡ ኀቤነ ፡ እሙንቱ) ፡ እረ ፡ ተዉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጠፋችኋል ፡ ሲሏቸው ፡ እንዳች ፡ እንደበታችንን ፡ ተውሰነዋልን ፡ ገዝተነዋል ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ። (መኑ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእነ ፡ በእንተ ፡ ሕግሞሙ ፡ ለነዳያን ፡ ወበእንተ ፡ ገዓሮሙ ፡ ለሙቁሓን) ። በድኆች ፡ መከራ ፡ ብናጸናባቸው ፡ የታሠሩትን ፡ እህል ፡ ወሀ ፡ ነሥተን ፡ ፀሐይ ፡ ከልክለን ፡ ብናስጨንቃቸው ፡ የሚፈርድብን ፡ ጌታችን ፡ ማን ፡ ነው ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ።

ይእዜ ፡ እትነሣእ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ እነሣለሁ ፡ አለ ።

እሬሲ ፡ መድኀኒተ ፡ ወእገሀድ ፡ ቦቱ ።

ድኅነቴን ፡ አደርጋለሁ ። በትድግናዬ ፡ ኃይሌን ፡ እገልጻለሁ ፡ አለ ። እንድም ፡ እግሀድ ፡ ሎቱ ፡ ለድኃው ፡ ድኅነቴን ፡ (ትድግናዬን) ፡ እገልጽለታለሁ ። እግሀድ ፡ ቦቱ ፡ በበለጸጋው ፡ መዓቱን ፡ እገልጽበታለሁ ። እገለጽበታለሁ ። ኢሳ ፡ ፹፪ ፡ ፲ ።

፮ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ንጹሕ ።

እሬሲ ፡ መድኀኒተ ፡ ያለ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሐሰት ፡ ከዝርዉነት ፡ ንጹሕ ፡ ነው ።

2014 04 17

ከመ ፡ ብሩር ፡ ጽሩይ ፡ ንጡፍ ፡ ወፍቱን ፡ እም ድር ፡ ዘአጽረይዎ ፡ ምስብዒተ ።

ከመ ፡ ብሩር ፡ ንጡፍ ፡ እምድር ፡ ጽ ሩይ ፡ ወፍቱን ፡ ዘአጽረይዎ ፡ ምስብ ዒተ ፡ (ሲል ፡ ነው) ፡ ብለህ ፡ አቅና ። ከምድር ፡ ለቅመው ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ መላልሰው ፡ እንዳፀሩት ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ ነው ። ብረቱን ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ከከውር ፡ ወደ ፡ ከውር ፡ ያፀሩት ፡ እንደሆን ፡ ከብር ፡ ማዕርግ ፡ ይደርሳ ል ። ብሩ ፡ ከወርቅ ፡ ወርቁ ፡ ከዕንቍ ፡ ማዕርግ ፡ ይደርሳል ።

እንድም ፡ (መኑ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእነ ፡ በእንተ ፡ ሕማሞሙ ፡ ለነዳያን ፡ ወበ እንተ ፡ ገዓሮሙ ፡ ለሙቁሓን) ። በነ ፍሳት ፡ መከራ ፡ ብናጸናባቸው ፡ ፍዳ ፡ ብናመጣባቸው ፡ የሚያድን ፡ ምን ፡ ጌታ ፡ አላቸው ፡ የሚሉ ፡ አጋንንትን ፡ ያጠፋቸዋል ። እንድም ፡ እንዲህ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ (ይእዜ ፡ እትነሣእ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር) ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ሰው ፡ እሆናለሁ ፡ አለ ። እንድም ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሬ ፡ እነሣለሁ ፡ አለ ። (እሬሲ ፡ መድኀኒ ተ ፡ ወእግህድ ፡ ቦቱ) ፡ ትንሣኤዬን ፡ አደርጋለሁ ፡ ኃይሌን ፡ በትንሣኤየ ፡ እገልጻለሁ ፡ ድኂኖ ፡ አድኅኖሙ ። አከ ፡ ዘድኅነ ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ አድ ኅነ ፡ ከልእነ ፡ ወይመጽእ ፡ ለመድኅ ኒት ፡ ጽንዕ ፡ ወይደመሙ ፡ በእንተ ፡ መንክር ፡ ዳኅናሁ ፡ እንዲል ።

እንድም ፡ አትገሃድ ፡ ሎቱ ፡ ለአዳም ፡ እገለጽለታለሁ ፡ እትገሃድ ፡ ቦቱ ፡ በ ዲያብሎስ ፡ እገለጽበታለሁ ። (ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጹሕ) ፡ እሬሲ ፡ እ ግህድ ፡ ያለ ፡ አክላዊ ፡ ቃል ፡ ከዕሩ ቅ ፡ ብእሲት ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፡ (ከመ ፡ ብሩር ፡ ጽሩይ ፡ ንጡፍ ፡ ወፍቱን ፡ እምድር) ፡ እንዳለፈው ።

፯ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ዐቀብከነ ፡ ወተማኅፀነነ ።

አቤቱ ፡ ጠብቀን ፡ ስትጠብቀንም ፡ ሰማይ ፡ ሩቅ ፡ አደራ ፡ ጥብቅ ፡ እን ዲሉ ፡ አጽንተህ ፡ ጠብቀን ።

እምዛቲ ፡ ትውልድ ፡ ዘለዓለም ።

ዕቀበነ ፡ ዘለዓለም ፡ እምዛቲ ፡ ትው ልድ ፡ ዘለዓለም ፡ ብሎ ፡ ይገጥሟል ። ለዘላለም ፡ ከምትኖር ፡ ከነገደ ፡ ብን ያም ፡ ለዘላለሙ ፡ ጠብቀን ። ዕቀበነ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ እምዛቲ ፡ ትውልድ ፡ ዘለዓለም ፡ ይላል ፡ ትርጓሜው ፡ አ ንድ ፡ ነው ።

፰ ፡ ዓውደ ፡ የሐውሩ ፡ ረሚዓን ።

የሚቀድመው ፡ አለ ።

ወበከመ ፡ ዕበየ ፡ ልዕልናከ ፡ ሠራዕኮሙ ፡ ለደ ቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ።

አንተ ፡ እንደ ፡ ገናንነትህ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ በመልአኩ ፡ ዳኝነት ፡ በኖኅ ፡ ነባሪነት ፡ ግራ ፡ ግራውን ፡ ለካም ፡ ቀኝ ፡ ቀኙን ፡ ለያፌት ፡ መኻል ፡ መ ሀሉን ፡ ለሴም ፡ ይሁን ፡ ብለህ ፡ ሥራ ት ፡ ሠርተህ ፡ ነበር ፡ ይህን ፡ አፍር ሰው ፡ የካም ፡ ልጆች ፡ የሴምን ፡ ዕፃ ፡



ርስት ፡ ለመቀማት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳ ሌም ፡ ይሄዳሉ ።

እንድም ፡ (ወበከመ ፡ ዕበየ ፡ ልዕልና ከ ፡ ሠራዕኮሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው) ፡ ኢይጠፍዕ ፡ ምስፍና ፡ ወምልክና ፡ እምእባሉ ፡ ለይሁዳ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይረክብ ፡ ዘዕኑሕ ፡ ሎቱ ፡ ብለህ ፡ ሥራት ፡ ሠርተህ ፡ ነበር ፡ (ዓ ውደ ፡ የሐውሩ ፡ ረሚዓን) ፡ የብን ያም ፡ ልጆች ፡ ይህን ፡ አፍርሰው ፡ የ ዳዊትን ፡ መንግሥት ፡ እጅ ፡ ለማድ ረግ ፡ ወደ ፡ ዓውደ ፡ መንግሥት ፡ ይ ሄዳሉ ። ፪ኛ ፡ ሳሙ ፡ ፳ ፡ ፲፱ ።

እንድም ፡ (ወበከመ ፡ ዕበየ ፡ ልዕል ናከ) ፡ ኢታምልክ ፡ ባዕደ ፡ አምላከ ፡ ዘእንበሌየ ፡ ብለህ ፡ ሥራት ፡ ሠርተ ህ ፡ ነበር ፡ (ዓውደ ፡ የሐውሩ) ፡ ይህን ፡ አፍርሰው ፡ ወደ ፡ ዓውደ ፡ ጣዖት ፡ ይሄዳሉ ። ዘፀ ፡ ፳ ፡ ፫-፯ ።

እንድም ፡ (ወበከመ ፡ ዕበየ ፡ ልዕል ናከ) ፡ ጸድቀ ፡ ኢትትዐል ፡ ብለህ ፡ ሥራት ፡ ሠርተህ ፡ ነበር ። (ዓውደ ፡ የሐውሩ) ፡ አይሁድ ፡ ይህን ፡ አፍር ሰው ፡ ጌታን ፡ ለመግደል ፡ ወደ ፡ ቀራ ንዮ ፡ ይሄዳሉ ። እንድም ፡ (ወበከመ ፡ ዕበየ ፡ ልዕልናከ) ፡ ንጉሥ ፡ በዘውዱ ፡ ድኃ ፡ ባመዱ ፡ ይኑር ፡ ብለህ ፡ ሥራት ፡ ሠርተህ ፡ ነበር ፡ (ዓውደ ፡ የሐውሩ) ፡ ባለጸጎች ፡ ይህን ፡ አፍርሰው ፡ የድ ኆውን ፡ ርስት ፡ ለመቀማት ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ይሄዳሉ ።

እንድም ፡ ወበከመ ፡ ዕበየ ፡ ልዕል ናከ) ፡ በከብታችሁ ፡ ነግዳችሁ ፡ በሕ ጋችሁ ፡ ጸንታችሁ ፡ ሥጋዬን ፡ ደሜ ን ፡ በሚገባ ፡ ተቀብላችሁ ፡ ጽደቁ ፡ ብለህ ፡ ሥራት ፡ ሠርተህ ፡ ነበር ፡ (ዓውደ ፡ የሐውሩ) ፡ ኃጥአን ፡ ይህን ፡ አፍርሰው ፡ የሐውሩ ፡ እምዓውድ ፡ ዓውደ ፡ ፍትሕ ፡ ወንጌልን ፡ ተረግጠው ፡ ወደ ፡ ዓውደ ፡ ገሃነም ፡ ይሄዳሉ ።

## መዝሙር ፡ ፲ ።

፩ ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ እግዚኦ ፡ ትረስዓኒ ፡ ለ ግሙራ ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ፡ ወትሩፋ ን ፡ ነው ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግሮታል ፡ የትሩፋንም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ ይህን ፡ የተናገረበት ፡ ጊዜ ፡ አልታወቀም ፡ እንድም ፡ ታውቋል ፡ በሳኦል ፡ ጊዜ ፡ ተናግሮታል ፡ አቤቱ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ፈጽመህ ፡ ትዘነጋኛለህ ።

እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ትመይጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔየ ።

ምሕረትህን ፡ ከኔ ፡ ወደዚያ ፡ እንድም ፡ ከዚያ ፡ ወደኔ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ትመልሰዋ ለህ ። እንድም ፡ ገጸ ፡ መዓትህን ፡ ከኔ ፡ ወደዚያ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ትመልሰዋለህ ።

፪ ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ አንበርኩ ፡ ወንጕየ ፡ ውስተ ፡ ነፍስየ ።

እስከ ፡ መቼስ ፡ በሰውነቴ ፡ አሣብ ፡ ተከዤ ፡ እኖራለሁ ።

ወትኄዕረኒ ፡ ልብየ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ።

ልቡናየ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ በመከራ ፡ አን
ድም ፡ ልንገሥ ፡ ልንገሥ ፡ በማለት ፡
ትጨነቅብኛለች ፡ እንድም ፡ ታዜዕር ፡
ብየ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ልቡናዬን ፡ ታስ
ጨንቅብኛለህ ፡ ታስጨንቃታለህ ።
እንድም ፡ ታዜዕረኒ ፡ ልብየ ፡ እስከ ፡
መቼ ፡ ድረስ ፡ ልቡናዬ ፡ ታስጨንቀ
ኛለች ።

እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ይትሌዐሉ ፡ ጸላእትየ ፡ ላዕሌየ ።

ጠላቶቼስ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ይታበዩ
ብኛል ።

፫ ፡ ነጽረኒ ፡ ወስምዐኒ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ልመናዬን ፡ ሰም
ተህ ፡ በዓይነ ፡ ምሕረትህ ፡ እየኝ ፡
ተመልከተኝ ።

አብርሆን ፡ ለአዕይንትየ ፡ ከመ ፡ ኢይኑማ ፡ ለመ
ዊት ።

የሞት ፡ እንቅልፍ ፡ እንዳያንቀላፉ ፡
ዓይኖቼን ፡ አብራቸው ። እንድም ፡
እንዳያንቀላፉ ፡ ዓይኖቼን ፡ አብራቸ
ው ። ለመዊት ፡ ሙቶ ፡ ለመቅረት ።

፬ ፡ ወከመ ፡ ኢይበሉኒ ፡ ጸላእትየ ፡ ሞእናሁ ።

ጠላቶቼም ፡ ተኝቶ ፡ አግኝተነው ፡
ድል ፡ ነሣነው ፡ እንዳይሉ ።

እለሰ ፡ ይሣቅዩኒ ፡ ይትፌሥሑ ፡ ለእመ ፡ ተሀወክ ።

እመ ፡ ተሀውኩሰ ፡ ብዙውስ ፡ ይቅር
ና ፡ ጥቂት ፡ መከራ ፡ አግኝቶኝ ፡ ብ
ታወክ ፡ ሥቃይ ፡ የሚያጸኑብኝ ፡ ጠ
ላቶቼ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፭ ፡ ወአንሰ ፡ በምሕረትከ ፡ ተወከልኩ ።

እኔ ፡ ግን ፡ መታወኩ ፡ እንዳያገኝኝ ፡
በይቅርታህ ፡ በቸርነትህ ፡ አመንሁ ።

ይትፌሥሐኒ ፡ ልብየ ፡ በአድኅኖትከ ።

በትድግናህ ፡ ልቡናዬ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡

፮ ፡ እሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘረድአኒ ።

የረዳኝን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰ
ግነዋለሁ ።

ወእዜምር ፡ ለስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ። መ
ዝ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ።

ልሁል ፡ ለሚሆን ፡ ለእግዚአብሔር ፡
እንድም ፡ ልዑል ፡ ለሚሆን ፡ ስሙ ፡
ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ። እንድም ፡
ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንድም ፡
ልዑል ፡ ስሙን ፡ አመሰግናለሁ ።

## መዝሙር ፡ ፲፫ ።

፩ ፡ ይብል ፡ ዓብድ ፡ በልቡ ፡ አልቦ ፡ እግዚአብ
ሔር ።

ስለሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፤ ከሥሩ ፡
አርእስት ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይህ
ስ ፡ እንደምንድነው ፡ ቢሉ ፤ ወእመ ፡
አሠርቱ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ዓመተ ፡ መን
ግሥቱ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ ፡
ዓርገ ፡ ሰናክሬም ፡ ንጉሠ ፡ ፋርስ ፡
ኀበ ፡ ሕዝቅያስ ። ሕዝቅያስ ፡ በነገ
ሠ ፡ በስምንት ፡ ዓመት ፡ እስራኤል ፡



በተማረኩ ፡ በስድስት ፡ ዓመት ፡ አን
ድም ፡ እስራኤል ፡ በተማረኩ ፡ በስ
ምንት ፡ ዓመት ፡ ሕዝቅያስ ፡ በነገሠ ፡
በስድስት ፡ ዓመት ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡
ሰናክሬም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ዘመ
ተ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ቢሉ ፡ ስል
ምናሶር ፡ ዓሥሩን ፡ ነገድ ፡ ማርኮ ፡
ፋርስ ፡ ባቢሎን ፡ አውርዶ ፡ ሆሴዕ ፡
ወልደ ፡ ዔላን ፡ ባሥሩ ፡ ነገድ ፡ አን
ግሦት ፡ ነበር ፡ ስመ ፡ ትዕይርቱን ፡
ረኣሰቂስ ፡ ብሎታል ፤ ነዊሃ ፡ ቅልጥ
ም ፡ ሊቀ ፡ ቀዳሕያን ፡ ማለት ፡ ነው ፡
፬ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፩ - ፵፰ ። ባለጌ ፡ አያገዝንም ፡
እሱ ፡ ስለገበረ ፡ ባልንጀራው ፡ እንጂ ፡
ስለቀረ ፡ እንዲሉ ፡ አባትህ ፡ እስክንድር ፡
አስሩን ፡ ነገድ ፡ ማርኮ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡
ተባለ ። አንተስ ፡ ያባትህ ፡ ለምን ፡ ይቀ
ርብሃል ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ማርከህ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አትባልምን ፡ ብሎ ፡
ሆሴዕ ፡ ወልደ ፡ ዔላ ፡ ነግሮት ፤ አንድ
ም ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ አስቦ ፡ መጥቷል ፤ አን
ድም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡
ንጉሡ ፡ ሲቀር ፡ ኃጢአት ፡ እየሠሩ ፡
ጣዖት ፡ እያመለኩ ፡ እግዚአብሔር
ን ፡ አሳዝነውት ፡ ነበርና ፡ ታገዘ ፡
ሊያጠፋ ፡ መጥቷል ፡ ይኸውም ፡ ሊ
ታወቅ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ በነጭ ፡
በግ ፡ አምሳል ፡ እየመራ ፡ አምጥቶ
ታል ። ቦኑ ፡ ግልፎ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ እስ
ኪለየው ፡ ድረስ ፤ ወፈነዎሙ ፡ ለተ
ንትን ፡ ወለራፍሰቂስ ፡ ወለራፋስሮስ ፡
ዘምስለ ፡ ብዙኅ ፡ ሠራዊት ፡ ወይቤ ፡
በልዎ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ በመኑ ፡ ተወ
ኪለከ ፡ ዓለውከኒ ፡ በበትረ ፡ ቢሕሩ
ስኑ ፡ ቅጥቁጥ ፡ አንተ ፡ ግብጽ ፡ ወሰ
በ ፡ ተመርጉዘ ፡ ቦቱ ፤ ብእሲ ፡ ይሰ
በር ፡ ወይበውእ ፡ ሥርዋጽ ፡ ውስተ ፡
እዴሁ ፡ ወበህየ ፡ ይቴስል ፡ ወያመ
ውት ፡ ከማሁ ፡ ሰገሎኒ ፡ ንጉሠ ፡ ግ
ብዕ ፡ በከመ ፡ ረሰይከዋ ፡ ለሰማርያ ፡
ከማሁ ፡ እሬስያ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ወለ
ኵሉ ፡ ጣዖታቲሃ ። ቦኑ ፡ ግልፎ ፡ ዘያ
ድኅን ፡ እምእዴየ ፡ በኢየሩሳሌም ፡
በምክርኒ ፡ ወበእንስሐስሑ ፡ ከናፍር ፡
የሸንበቆ ፡ በትር ፡ ቢመረጉዙት ፡ ይሰ
በራል ፡ ስንጣቂው ፡ ከእጅ ፡ ገብቶ ፡
ያቈስላል ፡ ይገድላል ፡ እንደዚህም ፡
ሁሉ ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ሰገሎ ፡ ስን
ኳንስ ፡ ሌላውን ፡ ሊያድን ፡ ራሱን ፡
አያድንም ፡ ኢየሩሳሌምንም ፡ ሰማ
ርያን ፡ እንዳጠፋሁ ፡ አጠፋታለሁ ።
ሰማርያን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ያጠ
ፋት ፡ ቢሉ ፡ ያባቱን ፡ ለሱ ፡ ሰጥቶ ፡
ተናገረ ፤ እንድም ፡ በአቤቶነቱ ፡ ዘ
ምቶ ፡ ነበርና ፡ ጣዖታቱን ፡ ሳይቀር ፡
አጠፋቸዋለሁ ። እንዳች ፡ ያ ፡ ፈጣሪ ፡
አለኝ ፡ የምትለው ፡ ያድነኝ ፡ መስሎ
ሃልን ፡ ጠላትስ ፡ በጭር ፡ ታጥቆ ፡
ዘገር ፡ ነጥቆ ፡ ቢሔዱበት ፡ ነው ፡ እን
ጂ ፡ ሴት ፡ ይመስል ፡ ድንኳን ፡ ቆል
ፎ ፡ እልፍኝ ፡ ዘግቶ ፡ ቢመክሩበት ፡ (ቢ
ያለቅሱለት) ፡ ይመለሳልን ፡ ብላችሁ ፡
ለሕዝቅያስ ፡ ንገሩት ፡ ብሎ ፡ ተንተ

ንን ፡ ራፋስፎስን ፡ ራፍስቂስን ፡ ከብ
ሁ ፡ ሠራዊት ፡ ጋራ ፡ ላከቻው ፡ በዚ
ህ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቅያስን ፡ የነገር ፡ ሰው ፡
እንጂ ፡ የጦር ፡ ሰው ፡ አለማድረጉ ፡
ነው ።

ወቆሙ ፡ ውስተ ፡ ላዕላይ ፡ ገራህተ ፡
መሐፒል ። የሸማ ፡ አጣቢ ፡ ርስት ፡
በምትሆን ፡ ቦታ ፡ የሸማ ፡ አጣቢ ስ ፡
ርስት ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ ሕንድች ፡
በሚያገቡ ፡ በፍታ ፡ በሚያፋጥቁ ፡
ዕፃ ፡ ቁመው ፡ የሕዝቅያስ ፡ ብላቴና ፡
ብለው ፡ ተጣሩ ። ሳምናስን ፡ ዮአስ
ን ፡ ኤልያቄምን ፡ ላከ ፡ እንመልስለ
ታለን ፡ አትበሉ ፡ የሚናገረውን ፡ ሰ
ምታችሁ ፡ ኑ ፡ ብሎ ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡
አናድደው ፡ ንጉሡን ፡ ያመጡብኛ
ል ፡ ብሎ ። እንድም ፡ ፈሪ ፡ በነገሩ ፡
ይታወቃልና ፡ ብሎ ። እንድም ፡ ከአ
ሕዛብ ፡ ጋር ፡ መነጋገር ፡ ፈጣሪን ፡
ማስደብ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አንተማ ፡ ወንድ
ማችን ፡ ሆሴዕ ፡ ወልደ ፡ ኤላ ፡ አይደለህ
ምን ፡ ኢትትናገረነ ፡ ዕብራይስጠ ፡ አላ ፡
ንግረነ ፡ ሱርስተ ፡ ከመ ፡ ኢይደንግፁ ፡
ሕዝብ ፡ ዘንተ ፡ ሰሚያሙ ። ሕዝቡ ፡
ሰምተው ፡ እንዳይሸበሩ ፡ በሱርስት ፡
ቋንቋ ፡ ንገረን ፡ እንጂ ፡ በዕብራይስ
ጥ ፡ አትንገረን ፡ አሉት ። ቦኑ ፡ ፈነ
ወኒ ፡ እግዚእየ ፡ ኀበ ፡ ባሕቲትክሙ ፡
አከኑ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ዓረፍት ፡ ወእ
ለ ፡ ውስተ ፡ ናሕስ ፡ ዘንተ ፡ ሰሚያ
ሙ ፡ ከመ ፡ ይብልዑ ፡ ኵስሐሙ ፡
ወይስተዩ ፡ ስንቶሙ ። እንዳች ፡ ጌታ
ዬ ፡ የላከኝ ፡ ከላንት ፡ ብቻ ፡ ነውን ፡
ባጥር ፡ በቅጥር ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሰም
ተው ፡ መከራ ፡ እንዲቀበሉ ፡ አይደ
ለምን ፡ ብሎ ፡ ርቆ ፡ ነበር ፡ ቢሉ ፡
ቀርቦ ፡ ከሚዳ ፡ ነበር ፡ ቢሉ ፡ ከተራ
ራ ፡ ወጥቶ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ ቢሉ ፡
አሰምቶ ፡ በዚያው ፡ በቋንቋቸው ፡ በዕ
ብራይስጥ ፡ ይህን ፡ ነገራቸው ። ልብ
ሳቸውን ፡ አስልበው ፡ ገብተው ፡ ነገ
ሩት ፡ ፬ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፲፫-፴፯ ። ኢሳ ፡ ፴፮ ፡ ፩-፳፪ ።
ሕዝቅያስም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ እስራ
ኤል ፡ እንዋጋለን ፡ አትበሉ ፡ ይህን ፡
ወንበዴ ፡ በጸሎት ፡ እንጂ ፡ በጦር ፡
የሚመልሰው ፡ የለም ። ያያችሁትን ፡
የሰማችሁትን ፡ ለኢሳይያስ ፡ ንገሩት ፡
ብሎ ፡ ሰደዳቸው ፡ ኢሳይያስም ፡ አይ
ዞህ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የአሕዛብ ፡ አለ
ንጋ ፡ አይጮህባትም ፡ እንግዲ ፡ ፈረ
ስ ፡ አይረግጣትም ፡ አሁን ፡ በመጣ
በት ፡ እግሩ ፡ ተመልሶ ፡ ይሔድልሃ
ል ፡ በሉት ፡ አላቸው ። ሰናክሬምም ፡
መጥቶ ፡ ለኪሶን ፡ ሰፈረ ፡ መልአኩ ፡
ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ጋት ፡ ሙሉ ፡ ሰ
ይፈ ፡ መዓት ፡ መዝዞ ፡ ቢያሳያቸው ፡
መኳንንቱ ፡ ዓሥራ ፡ ስምንት ፡ እልፍ ፡
ካምስት ፡ ሺህ ፡ ነገሥታቱ ፡ ከሱ ፡
ጋራ ፡ ፴፱ ፡ ወአጋረ ፡ ጉልቍስ ፡ ከመ ፡
ኖፃ ፡ ባሕር ። ጋሻ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ የሚ
ያረበርበው ፡ ግን ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡
የለውም ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ የደም ፡ ልጓም ፡
ጉርሶ ፡ አድሯል ፡ እሱ ፡ ወሖረ ፡ መጠነ
ዘይኄልቆ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ የሚቆጥ



ረው ፡ ከሥራ ፡ ሁለት ፡ ከሥራ ፡ ስስ
ት ፡ በላይ ፡ አይቆጥርም ፡ ይህን ፡ ያህ
ል ፡ ሆኖ ፡ ሔዷል ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡
ርኩስ ፡ ደሙ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እን
ዳይፈስ ። እለዚያስ ፡ ርኩሳን ፡ አይ
ደሉምን ፡ ቢሉ ፡ ማን ፡ እንደሱ ።
እንድም ፡ መከራውን ፡ ይቅመሰው ፡
ብሎ ፡ ሲመጣ ፡ በዶጋሬ ፡ በከባቢ ፡
በጅብ ፡ በዘብ ፡ ነበር ፡ ሲሔድ ፡ ግን ፡
መላእክት ፡ የሠረገላ ፡ ድምፅ ፡ የፈ
ረስ ፡ ኮቴ ፡ እያሰሙት ፡ ሕዝቅያስ ፡
መጣብኝ ፡ እያለ ፡ ነውና ። እንድም ፡
ወይከውን ፡ መቃብሪከ ፡ ታሕተ ፡ ሰ
ብኮከ ፡ ያለው ፡ የነቢዩ ፡ ቃል ፡ ይደ
ርስ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ። ካገሩ ፡ ደር
ሶ ፡ ከቤተ ፡ ጣዖቱ ፡ ገብቶ ፡ እጅ ፡
ሲነሣ ፡ አድራማሌክና ፡ ሶርሶር ፡ የሚ
ባሉ ፡ ልጆቹ ፡ ሠራዊቱን ፡ ወዴት ፡
ጥለህ ፡ መጣህ ፡ አሉት ፡ የሕዝቅያ
ስ ፡ አምላክ ፡ ፈረደብኝ ፡ አላቸው ፡
ያን ፡ ያህል ፡ ሰራዊት ፡ አጥፍተህ ፡
ሁለተኛ ፡ በማን ፡ ልትነግሥ ፡ መጣ
ህ ፡ ብለው ፡ በዘነዘና ፡ አናቱን ፡ በጥ
ብጠው ፡ ገድለውታል ፡ ወእንዘ ፡ ይ
ሰግድ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሲድራክ ፡ አ
ምላኩ ፡ ቀተልዎ ፡ አድራሜሌክ ፡ ወ
ሶርሶር ፡ ደቂቁ ፡ እንዲል ፡ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ወሖሩ ፡ ውስተ ፡ አራራት ፡
ሸሽተው ፡ ወደ ፡ አራራት ፡ ሔዱ ፡
ወነግሠ ፡ ህየንቴሁ ፡ አስራዶን ፡ ወል
ዱ ፡ ከነገር ፡ ያልገባ ፡ አስራዶን ፡ የ
ሚባል ፡ ልጁ ፡ ነግሷል ። ፬ ፡ ነገ ፡ ፲፱ ፡
፩ - ፴፯ ። ኢሳ ፡ ፴፯ ፡ ፩ - ፴፰ ።

ሰነፍ ፡ ሰናክሬም ፡ በልቡ ፡ አሰበ ፡ በ
ቃሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ የለም ፡ ይላል ፡
መዝ ፡ ፶፪ ፡ ፩ ።

ኀሥሩ ፡ ወረሰዩ ፡ በምግባሪሆሙ ።

ጎሠራን ፡ ርኩሳን ፡ የሚያሰኛቸው
ን ፡ ሥራ ፡ ሠሩ ። ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፲፯ ። እን
ድም ፡ ጎሥሩ ፡ በነኑ ፡ ወረዙሱ ፡ በ
ለኪሶን ፡ እንድም ፡ ኃሥሩ ፡ በሥጋ ፡
ወረዙሱ ፡ በነፍስ ፡ እንድም ፡ ኃሥሩ ፡
ሬሳ ፡ ሸሽ ፡ ጣሉ ፡ በኀበ ፡ ተራገጸ ፡
ሲግራ ፡ ወበህየ ፡ ኃሥረ ፡ እንዲል ።

ወረዙሱ ፡ ርኩሳን ፡ አብድንት ፡ ተባ
ሉ ፡ በድን ፡ ርኩስ ፡ እንድትል ፡ እሬ
ት ፡ ዛሬ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተለ
የ ፡ ሰውነት ፡ ርኩስ ፡ እንዲባል ፡ የዚ
ያን ፡ ጊዜም ፡ መቃብር ፡ ያፈለሰ ፡
እስከሬን ፡ የዳሰሰ ፡ ርኩስ ፡ እስከ ፡ ሠ
ርክ ፡ ይባል ፡ ነበርና ።

እልፀ ፡ ዘይገብሩ ፡ ለመናይት ፡ እልፀ ፡ ወእኡ
ሑዱ ፡ ጥ ፡ ፫ ።

ከነሰናክሬም ፡ ወገን ፡ ብዙውስ ፡ ይ
ይቅርና ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ በጎ ፡ ነገር
ን ፡ የሚሠራት ፡ ሰው ፡ የለም ።

፪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሐወፀ ፡ እምሰማይ ፡ ላዕለ ፡
ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

እግዚአሔር ፡ በለኪሶን ፡ ወደሰፈሩ ፡
ወደነሰናክሬም ፡ እየ ፡ ተመለከተ ።

ከመ ፡ ይርአይ ፡ እመቦ ፡ ጠቢብ ፡ ዘየሐሥሥ ፡
ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡
የሚሻው ፡ ሰው ፡ እንዳለ ፡ ያይ ፡ ዘንድ ።

፫ ፡ ኵሉ ፡ ኀረየ ፡ ወኀቡረ ፡ አለው ።

እንዲህ ፡ ቢያይ ፡ ቢመለከት ፡ ሁሉ ፡ እንደፈረስ ፡ ገሮ ፡ እንደ ፡ ሰላጢን ፡ ጕረሮ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ በደለ ፡ ወነጀለ ። ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፳፰-፳፱ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፲ ።

አልቦ ፡ ዘይገብራ ፡ ለሠናይት ፡ አልቦ ፡ ወኢአሐዱ ።

ከነሰናከሬም ፡ በጐ ፡ ነገርን ፡ የሚሠራት ፡ ፩ ፡ ሰንኳ ፡ የለም ።

፬ ፡ ከመ ፡ መቃብር ፡ ክሡት ፡ ጕሬዒቶሙ ።

የተከፈተ ፡ እንደበታቸው ፡ እንደ ፡ መቃብር ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ሞት ፡ ቢገድል ፡ መቃብር ፡ ቢቀበል ፡ በቃኝ ፡ ጠገብሁ ፡ እንዳይል ፡ እነሱም ፡ ሰውን ፡ ቢበድሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቢያሳዝኑ ፡ በቃን ፡ ጠገብን ፡ አይሉምና ። ኤር ፡ ፭ ፡ ፲፮ ። አንድም ፡ እንደበታቸው ፡ እንደተከፈተ ፡ መቃብር ፡ ነው ፤ ያ ፡ መግነዙ ፡ ተበጣጥሶ ፡ እገሩ ፡ ፈስሶ ፡ ሥጋው ፡ ተልከስክሶ ፡ እጥንቱ ፡ ተከስክሶ ፡ ላይን ፡ ያስጠይፋል ፡ ላፍንጫ ፡ ይከረፋል ፡ እነሱም ፡ ሰውን ፡ የሚያሳዝን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማያስቀይም ፡ ነገር ፡ ይናገራሉና ።

ወጸልሐዉ ፡ በልሳናቲሆሙ ፡ መዝ ፡ ፭ ።

ባንደበታቸው ፡ ከዱ ፡ ማለት ፡ እሥራኤል ፡ አሁን ፡ ሕዝቅያስ ፡ ያድነናል ፡ ይመስላችኋልን ፡ ይልቅስ ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ ልውሰዳችሁ ፡ ብሔርየኒ ፡ ብሔረ ፡ ሠርናይ ፡ ወወይን ፡ ወቅብዕ ፡ ከመ ፡ ብሔርክሙ ፡ ሀገሬም ፡ እንደ ፡ ሀገራችሁ ፡ የስንዴ ፡ የወይን ፡ የዘይት ፡ ሀገር ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ ስላልኋችሁም ፡ ዛሬ ፡ አይደለም ፡ ተራቅታ ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ወግቼ ፡ ከተመለስሁ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ብዬ፡ቸዋልና ፡ አንድም ፡ በነገራቸው ፡ ከዱ ። ፬ ፡ ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፱-፴፪ ። ኢሳ ፡ ፴፮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ።

፭ ፡ ሕምዘ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ታሕተ ፡ ከናፍሪሆሙ ።

ባንደበታቸው ፡ የእባብ ፡ መርዝ ፡ አለ ፤ ታሕተ ፡ መንጸፍ ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ ታሕተን ፡ ለማውጣት ፡ ከንደበታቸው ፡ በታች ፡ ባለ ፡ በልቡናቸው ፡ የእባብ ፡ መርዝ ፡ አለ ፤ ያ ፡ እንዲገዳ ፡ የሚገዳ ፡ ነገር ፡ አለ ፤ አንድም ፡ ዘምድረ ፡ ለብሰ ፡ እንዲል ፤ አዳምን ፡ ያሳተ ፡ የዲያብሎስ ፡ መርዝ ፡ ከንደበታቸው ፡ በታች ፡ ባለ ፡ በልቡናቸው ፡ አለ ፡ ክህደት ፡ ኑፋቄ ፡ ነው ።

መሪር ፡ አፉሆሙ ፡ ወምሉዕ ፡ መርገመ ።

አንደበታቸው ፡ መሪር ፡ ነው ፡ አንደበታቸውንማ ፡ የቀመሰውን ፡ አለብሎ ፡ ነገራቸው ፡ ጽኑ ፡ ነው ፤ መርገምንም ፡ የተመላ ፡ ነው ፤ አርኅቅ ፡ እምኔከ ፡ አፈ ፡ እኩየ ፡ ወአገንጽሉ ፡ አፉሆሙ ፡ እንዲል ። ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፩-፲፭ ።

፮ ፡ በሊህ ፡ እገሪሆሙ ፡ ለክዒወ ፡ ደም ፡ ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፯ ። ፶፱ ፡ ፯ ፡ ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።

እግራቸው ፡ የሰውን ፡ ደም ፡ ለማፍሰስ ፡ ፈጣን ፡ ነው ፤ ወቀርኑ ፡ ይበልሀ ፡ እንዲል ።



ኀማር ፡ ወቅጥቃጤ ፡ ውስተ ፡ ፍናቶሙ ።

በመንገዳቸው ፡ ላይ ፡ ግንባር ፡ መግመስ ፡ ደም ፡ ማፍሰስ ፡ አባት ፡ ማሳነስ ፡ ጨርቅ ፡ ማልበስ ፡ በሬ ፡ ማረድ ፡ ሞፈር ፡ ቀንበር ፡ መማገድ ፡ አለ ። ዘፍ ፡ ፬ ፡ ፰ ።

፯ ፡ ወኢየአምርዋ ፡ ለፍኖተ ፡ ሰላም ።

ያንድነትን ፡ የፍቅርን ፡ ሥራ ፡ አያውቋትም ።

ወአልቦ ፡ ፍርሀተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅድመ ፡ አዕይንቲሆሙ ። ዘፍ ፡ ፰ ፡ ፲፩ ፡ ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፰ ፡ ፱ ።

በዐይነ ፡ ልቡናቸው ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ የለም ፡ ማለት ፡ በኑ ፡ ግልፎ ፡ ሲሉ ፡ ያይብናል ፡ ይሰማብናል ፡ አይሉም ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።

፰ ፤ ወኢየአምሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ አመፃ ።

ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ እሊህ ፡ በኑ ፡ ግልፎ ፡ ማለት ፡ እንዲገዳ ፡ አያውቁም ።

እለ ፡ ይውሕጥዎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ ከመ ፡ በሊዓ ፡ እክል ።

ወገኖቼ ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ እንደ ፡ ጥሕሎ ፡ ዋጥናቸው ፡ እንደ ፡ እንቀት ፡ ጠጣናቸው ፡ የሚሉ ።

ወለእግዚአብሔርሰ ፡ ኢጸውዕዎ ።

ምነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አለብን ፡ አይሉትምን ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያይብናል ፡ ይሰማብናል ፡ አላሉትም ፡ ጣዖት ፡ አሉት ። አንድም ፤ (በሊህ ፡ እገሪሆሙ ፡ ለክዒወ ፡ ደም) ፤ የአይሁድ ፡ እግራቸው ፡ ደመ ፡ ወልዱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማፍሰስ ፡ ፈጣን ፡ ነው ።

(ኀማር ፡ ወቅጥቃጤ ፡ ውስተ ፡ ፍናቶሙ) ፤ በሕጋቸው ፡ በአሪት ፡ ቅጥቃጤ ፡ ሥጋ ፡ ቅጥቃጤ ፡ ነፍስ ፡ አለ ፤ ቅጥቃጤ ፡ ሥጋ ፡ ፍርዱ ፡ ጽኑ ፡ ነውና ፤ ቅጥቃጤ ፡ ነፍስ ፡ እለፊ ፡ ጥሬ ፡ ካላት ፡ በኋላ ፡ ሲሠሯት ፡ ቢገኙ ፡ ፍዳ ፡ ታመጣለችና ፤ (ወኢየአምርዋ ፡ ለፍኖተ ፡ ሰላም) ፤ ደቂቅየ ፡ ተፋቀሩ ፡ የምትል ፡ ሕገ ፡ ፍቅር ፡ ወንጌልን ፡ አያውቋትም ፤ (ወአልቦ ፡ ፍርሀተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅድመ ፡ አዕይንቲሆሙ) ፤ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ሲሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያይብናል ፡ ይሰማብናል ፡ አይሉትም ፤ (ወኢየአምሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ) ፤ ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ አይሁድ ፡ ዕሩቅ ፡ ብዕሲ ፡ ማለት ፡ እንዲገዳ ፡ አያውቁም ፤ (እለ ፡ ይውሕጥዎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ ከመ ፡ በሊዓ ፡ እክል) ፡ ወገኖቼ ፡ ሐዋርያትን ፡ እንደ ፡ ጥሕሎ ፡ ዋጥናቸው ፡ እንደ ፡ እንቀት ፡ ጠጣናቸው ፡ የሚሉ ፤ (ወለእግዚአብሔርሰ ፡ ኢጸውዕዎ) ፡ ምነው ፡ እግዚአብሔርስ ፡ ወዴት ፡ ሔዶ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ እግዚአብሔርንስ ፡ ሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አሉት ።

፱ ፤ ወበህየ ፡ ፈርሁ ፡ ወገረምሙ ፡ ዘኢኮነ ፡ ግሩመ ።

በነገር ፡ በቦታ ፡ በልቡና ፡ ፈሩ ፡ ግሩም ፡ ሆኖ ፡ የማያውቅ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ግሩም ፡ ሆነባቸው ። ነገሥታቱ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ሠላሳ ፡ አራት ። መኳንንቱ ፡ ዓሥራ ፡ ስምንት ፡ እልፍ ፡

2014 04 17

ከምስት ፡ ሼሕ ፡ ወእጋረ ፡ ጉልቆሰ ፡ ከመ ፡ ኖኅ ፡ ባሕር ፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ የሚያረበርበው ፡ ግን ፡ ስፍር ፡ ቍጥ ር ፡ የለውም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አጥፍ ቷልና ፡ መጽሐፍ ፡ የያዘውን ፡ ማጽ ናት ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ሰብአ ፡ ት ክትን ፡ ሰብአ ፡ ሰዶምን ፡ ሰብአ ፡ ገ ሞራን ፡ ሰብአ ፡ ግብጽን ፡ አጥፍቷ ል ፡ እንድም ፡ ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ በተአምራት ፡ አሳፍሯቸው ፡ አያው ቅምና ፡

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ትውልደ ፡ ጻድቃን ፡

እግዚአብሔር ፡ በአብርሃም ፡ በይስ ሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ በእነ ፡ ሕ ዝቅያስ ፡ በእነ ፡ ኢሳይያስ ፡ በረድኤ ት ፡ አለና ፡ ፈርሁ ፡

፯ ፡ ወአስተኀፈርክሙ ፡ ምክረ ፡ ነዳይ ፡

የነዳይ ፡ የሕዝቅያስን ፡ ምክር ፡ አሳ ፈራችሁ ፡ እንድም ፡ አስተኀፈርክ ሙ ፡ የሕዝቅያስ ፡ ምክር ፡ አሳፈራች ሁ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዕቃቤት ፡ የተገ ኘውን ፡ ወርቁን ፡ ብሩን ፡ ሰብስቦ ፡ ቢያንስበት ፡ ሰሎሞን ፡ ያሰራውን ፡ የቤተ ፡ መቅደሱን ፡ ሣንቃ ፡ ወርቅ ፡ ጨምሮ ፡ እቴዓ ፡ እግዚእየ ፡ ዘአያር ከኒ ፡ እፀውር ፡ ጌታዬ ፡ ወዳገርህ ፡ ተመለስልኝ ፡ የጣልክብኝን ፡ ግብር ፡ እችላለሁ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ፡ ከራት ፡ ቂርስ ፡ ዳረጉት ፡ እንዲሉ ፡ ካንተ ፡ ግዛት ፡ ተከፍሎ ፡ ለኔ ፡ እረ ፡ በውል ፡ ሰልተህ ፡ ገብር ፡ በለው ፡ ብሎ ፡ ተጋ ፍቶ ፡ መጥቷል ፡ ያን ፡ ተቀብሎ ፡ ተ መልሶ ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከ ራ ፡ የለበትም ፡ ነበርና ፡

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተስፋሆሙ ፡ ውእቱ ፡

እግዚአብሔር ፡ የሁለቱ ፡ ነገድ ፡ እ ለኝታቸው ፡ ነውና ፡ ፈርሁ ፡ እንድ ም ፡ የሕዝቅያስ ፡ የኢሳይያስ ፡ አለኝ ታቸው ፡ ነውና ፡ አስተኀፈርክሙ ፡

፲፩ ፡ መኑ ፡ ይሁብ ፡ መድኀኒተ ፡ እምጽዮን ፡ ለእስራኤል ፡ ኢሳ ፡ ፳፯ ፡ ፱ ፡ ፶፱ ፡ ፳ ፡ ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፳፯ ፡

በኢየሩሳሌም ፡ ካሉ ፡ እስራኤል ፡ ለእ ስራኤል ፡ ድኅነቱን ፡ ማን ፡ ይሰጣል ፡ ማለት ፡ ማን ፡ ያድናል ፡ ያለ ፡ ነበር ፡

አመ ፡ ሜጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፄዋ ፡ ሕዝቡ ፡

ፄዋ ፡ ሕዝበ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ የሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ምርኮ ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፡

ይትፌሣሕ ፡ ያዕቆብ ፡ ወይትኃሠይ ፡ እስራኤል ፡

ያዕቆብ ፡ ንጉሡ ፡ እስራኤል ፡ ሰራዊ ቱ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ እንጂ ፡ ያለዚ ያ ፡ ድኅነትን ፡ ለእስራኤል ፡ ማን ፡ ይ ሰጣል ፡ ያለ ፡ ነበር ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተማርከዋልና ፡ ሜጠ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ነሥአን ፡ ወአስተጋብአ ን ፡ በኀሊናሁ ፡ እንዲል ፡ ነገ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ የምገለውን ፡ ገድዬ ፡ የምማር ከውን ፡ ማርኬ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡



አቃጥዬ ፡ አገሬቱን ፡ እጅ ፡ አደርጋ ታለሁ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ እንድም ፡ ዕ ንጨት ፡ ሰብረውን ፡ ወህ ፡ ቀጂውን ፡ እጅ ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፡ እንድም ፡ እን ደ ፡ ቀሀ ፡ እንደ ፡ እንገረብ ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ እጅ ፡ አድርጎ ት ፡ ነበርና ፡ እንድም ፡ (አመ ፡ ሜጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፄዋ ፡ ጽዮን) ፡ ያሥሩ ን ፡ ነገድ ፡ ምርኮ ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፡ (ይትፌሣሕ ፡ ያዕቆብ) ፡ ሁለቱ ፡ ነገ ድ ፡ (ወይትኃሠይ ፡ እስራኤል) ፡ ዓ ሥሩ ፡ ነገድ ፡ ደስ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተመልሰ ዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ተማ ርከው ፡ ወርደው ፡ ቋሚ ፡ ለጓሚ ፡ ገ ረድ ፡ ደንገጡር ፡ ሁነው ፡ ይኖሩ ፡ ነ በር ፡ ሁሉም ፡ በየሥራቸው ፡ መጥ ተዋል ፡ በግብር ፡ የመሰሉ ፡ አብረ ው ፡ አልቀዋል ፡ ያልመሰሉ ፡ እንደ ተራዳ ፡ ምልምላቸውን ፡ አድረው ፡ እልል ፡ እልል ፡ ብለው ፡ አገራቸው ን ፡ ገብተዋልና ፡

## መዝሙር ፡ ፲፬ ፡

፩ ፡ እግዚኦ ፡ መኑ ፡ የኀድር ፡ ውስተ ፡ ጽላሎትከ ፡

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ አቤቱ ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥቶ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገ ብቶ ፡ በጽላሎት ፡ ረድኤትህ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ማነው ፡ ኢሳ ፡ ፴፫ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ፡

ወመኑ ፡ ያጸልል ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ መቅደስከ ፡

ከባቢሎን ፡ ወጥቶ ፡ የአብርሃም ፡ ዕፃ ፡ ክፍል ፡ በምትሆን ፡ መመስገኛህ ፡ በ በተሠራችባት ፡ በኢየሩሳሌምስ ፡ አ ድሮ ፡ የሚኖር ፡ ማነው ፡

፪ ፡ ዘየሐውር ፡ በንጹሕ ፡ ወይገብር ፡ ጽድቀ ፡

በንጹሕ ፡ ግብር ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ዕውነት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራስ ፡ ማነው ፡

ወዘይነብብ ፡ ጽድቀ ፡ በልቡ ፡

በልቡ ፡ አስቦ ፡ በቃሉ ፡ ዕውነት ፡ የ ሚናገር ፡ ማነው ፡ ኢሳ ፡ ፺፯ ፡ ፪ ፡

፫ ፡ ወዘኢጓሕለወ ፡ በልሳኑ ፡

ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፱ ፡ ባንደበቱ ፡ ምሎ ፡ ያል ከዳ ፡ ማን ፡ ነው ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፱ ፡ ፰ ፡

ወዘኢገብረ ፡ እኩየ ፡ ላቢጹ ፡ ቢጹ ፡ ያዕ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ፡

በባልንጀራው ፡ ክፉ ፡ ያላደረገ ፡ ማን ፡ ነው ፡

ወዘኢያጽአለ ፡ አዝማዲሁ ፡ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡

ሰርቶ ፡ ቀምቶ ፡ እናት ፡ አባቱን ፡ ያላ ሰደበ ፡ ማን ፡ ነው ፡ እኩይ ፡ ወልድ ፡ ያጼዕል ፡ አባሁ ፡ ወእሞ ፡ እንዲል ፡

፬ ፡ ወዘምኑን ፡ በቅድሜሁ ፡ እኩይ ፡

እኩይ ፡ ጣዖት ፡ የተናቀለት ፡ ማን ፡ ነው ፡

ዘያከብሮሙ ፡ ለፈራህያን ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልኩ ፡ የ ሚፈሩ ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ ወጥቶ ፡

2014 04 17

ወርዶ ፡ የሚረዳቸው ፡ ማን ፡ ነው ፡፡ አ
ክብር ፡ እባከ ፡ ወእመከ ፡ እንዲል ።

ዘይፈርሆሙ ፡ ለቢጹ ፡ ወኢይሔሱ ።

ለባልንጀራው ፡ ምሎ ፡ ያልከዳ ፡ ማን ፡
ነው ።

፭ ፡ ወዘኢለቅሐ ፡ ወርቆ ፡ በርዴ ፡ ዘ፴ ፡ ፳፪ ፡ ፳፭ ።

ገንዘቡን ፡ በትርፍ ፡ ያላበደረ ፡ ማን ፡
ነው ።

ወዘኢነሥአ ፡ሕልያነ ፡ በዓፀደ ፡ ንጹሐ ።

ከድኃው ፡ መማለጃ ፡ ያልተቀበለ ፡
ማን ፡ ነው ።

ዘይገብር ፡ ከመዝ ፡ ኢይትሀወክ ፡ ለዓለም ።

ይህን ፡ አለማድረጉንም ፡ የሚያደር
ግ ፡ ሰው ፡ መከራ ፡ ሥጋ ፡ መከራ ፡
ነፍስ ፡ መጥቶበት ፡ በመከራው ፡ አይ
ታወክም ። እንድም ፡ (እግዚአ ፡ መኑ ፡
የኃድር ፡ ውስተ ፡ ጽላሎትከ) ፡ ተስአ
ሎ ፡ እምነቢይ ፡ ወተሠጥዎ ፡ እመን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ። ከባቢሎን ፡ ወ
ጥቶ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገብቶ ፡ በጽላሎ
ተ ፡ ረድኤትህ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡
ማን ፡ ነው ። እንድም ፡ በጽላሎተ ፡
ረድኤትህ ፡ ጸንቶ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አ
ርፎ ፡ የሚኖር ፡ ማን ፡ ነው ። (ወመኑ ፡
ያጸልል ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ መቅደ
ስከ) ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥቶ ፡ መመስገ
ኛህ ፡ በምትሆን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አ
ድሮ ፡ የሚኖር ፡ ማን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡
ነቢይ ፡ ይጠይቃል ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡
ተሠጥዎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወይቤ ፡
(፪ ፡ ዘየሐውር ፡ በንጹሕ ፡ ወዘይገብ
ር ፡ጽድቀ) ፡ በንጹሕ ፡ ግብር ፡ ጸንቶ ፡
የሚኖር ፡ (ወዘይነብብ ፡ ጽድቀ ፡ በ
ልቡ) ፡ በልቡ ፡ አስቦ ፡ በቃሉ ፡ እው
ነት ፡ የሚናገር ፡ ያጸልል ፡ የኃድር ፡
ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመልሳል ።
እንድም ፡ (ዘእንበለ ፡ ዘየሐውር ፡ በን
ጹሕ) ። በንጹሕ ፡ ግብር ፡ ጸንቶ ፡ የሚ
ኖር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡ ያ
ለሱ ፡ ከሱ ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ ነው ፡ እን
ድም ፡ በንጹሕ ፡ ግብር ፡ ጸንቶ ፡ የሚ
ኖር ፡ በልቡ ፡ አስቦ ፡ በቃሉ ፡ እው
ነት ፡ የሚናገር ፡ ያጸልል ፡ የኃድር ፡
(፫ ፡ ወዘኢኃሕለወ ፡ በልሳኑ) ፡ ባንደ
በቱ ፡ ምሎ ፡ ያልከዳ ፡ (ወዘኢገብረ ፡
እኩየ ፡ ዲበ ፡ ቢፁ) ፡ በባልንጀራው ፡
ክፉ ፡ ያልሠራ ፡ ያጸልል ፡ የኃድር ።
እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ መ
ከራ ፡ ሥጋ ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ መጥቶ
በት ፡ አይታወክም ። እንድም ፡ ከገን
ዘቡ ፡ በትርፍ ፡ ያላበደረ ፡ ነው ፡ እን
ጂ ፡ ይህን ፡ አለማድረጉንም ፡ የሚ
ያደርግ ፡ ሰው ፡ መከራ ፡ ሥጋ ፡ መከ
ራ ፡ ነፍስ ፡ መጥቶበት ፡ አይታወክም ።
እንድም ፡ (ወዘኢይገብር ፡ ከመዝ ፡
ኢይትሀወክ ፡ ለዓለም) ፡ ይህን ፡ ማ
ድረጉን ፡ የማያደርግ ፡ ሰው ፡ መከራ ፡
ሥጋ ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ መጥቶበት ፡
አይታወክም ። ከዚያ ፡ መኑ ፡ መኑ ፡
ያለውን ፡ ትቶ ፡ ከዚህ ፡ ዘይገብር ፡
ያለውን ፡ ትቶ ፡ ዓሥር ፡ ይሆናል ።
ያሥሩ ፡ ቃላት ፡ ያሥሩ ፡ሕዋሳት ፡



ያሥሩ ፡ አውታረ ፡ በገና ፡ ምሳሌ ።
እድንም ፡ ሁሉም ፡ ዓሥሩ ፡ ሦስት ፡
ይሆናል ፡ ዓሥሩ ፡ አይለወጥም ፡ ሦ
ስቱ ፡ የሦስትነት ፡ ምሳሌ ።

## መዝሙር ፡ ፲፭ ።

፩ ፡ ዕቀበኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ኪያከ ፡ ተወከልኩ ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ፡ ነው ፡ በሳ
አል ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግሮታል ።
አቤቱ ፡ ባንተ ፡ አምኛለሁና ፡ ከመ
ከራ ፡ ሥጋ ፡ ጠብቀኝ ።

፪ ፡ እቤሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እግዚእየ ፡ አንተ ።

ዕብሎ ፡ ዕቀበኒ ፡ እግዚአብሔርን ፡
ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ ጠብቀኝ ፡
እለዋለሁ ።

እስመ ፡ ኢትፈቅዳ ፡ ለሠናይትየ ።

ቢሆንም ፡ የኔን ፡ ተድላ ፡ አትሽምና ፡
ምንም ፡ ባትሻት ።

፫ ፡ ለቅዱሳን ፡ እላ ፡ ውስተ ፡ ምድር ።

ለቅዱሳንስ ፡ በል ፡ በአብርሃም ፡ በይ
ስሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ ግን ።

ተሰብሐ ፡ ኵሉ ፡ ሥምረትከ ፡ በላዕሌሆሙ ።

ፈቃድህ ፡ መከራ ፡ ተመሰገንባቸው ፡
ወደዶ ፡ ስላመጣባቸው ፡ ወድደው ፡
ስለ ፡ ተቀበሉት ።

፬ ፡ በዝኃ ፡ ደዌሆሙ ፡ ወእምዝ ፡ አስተፋጠኑ ።

መከራቸው ፡ በዛ ፡ ከመከራቸው ፡
ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ከካራን ፡ ወደ ፡ ከ
ላውዴዎን ፡ ከከላውዴዎን ፡ ወደ ፡
ካራን ፡ ተመላለሱ ። እንድም ፡ (ዕቀ
በኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ኪያከ ፡ ተወ
ከልኩ) ፡ መከራ ፡ ሥጋውንስ ፡ አይ
ሰቀቀውም ፡ ብሎ ፡ መከራ ፡ ሥጋው
ስ ፡ ይሁንብኝና ፡ ከሞቱ ፡ ጠብቀኝ ፡
እለዋለሁ ። (እስመ ፡ ኢትፈቅዳ ፡ ለ
ሠናትየ) ፡ ቢሆንም ፡ የኔን ፡ መንግ
ሥት ፡ አትሻትምና ። ምንም ፡ ባት
ሻት ፡ ጠብቀኝ ። (ለቅዱሳን ፡ እለ ፡ ው
ስተ ፡ ምድር ፡ ተሰብሐ ፡ ኵሉ ፡ ሥም
ረትከ ፡ በላዕሌሆሙ) ፡ በሙሴ ፡ በአ
ሮን ፡ ግን ፡ ፈቃድህ ፡ መከራ ፡ ተመሰ
ገንባቸው ፡ ወዶ ፡ ስላመጣባቸው ፡ ወ
ድደው ፡ ስለ ፡ ተቀበሉት ። (በዝኃ ፡
ደዌሆሙ) ፡ መከራቸው ፡ በዛ ፡ (ወእ
ምዝ ፡ አስተፋጠኑ) ፡ ከመከራቸው ፡
ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ከግብፅ ፡ ወደ ፡ ም
ድያም ፡ ከምድያም ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡
ተመላለሱ ፡ ዘፀ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ፡ ፬ ፡ ፲፰ ።
እንድም ፡ (ዕቀበኒ ፡ እብሎ) ፡ እሁን
ም ፡ አይቀርለትምና ፡ ሞቱን ፡ አይሰ
ሰቀቀውም ፡ ሞቱስ ፡ ይሁንብኝና ፡ ከ
መከራ ፡ ነፍስ ፡ ጠብቀኝ ፡ እለዋለሁ ።
(እስመ ፡ ኢትፈቅዳ) ፡ ቢሆንም ፡ የ
ኔን ፡ ምግባር ፡ አንተ ፡ ትጠቀምበት ፡
ዘንድ ፡ አትሻትምና ፡ ምንም ፡ ባትሻ
ት ። ለእመ ፡ አንተ ፡ እርታዕከ ፡ ፍና
ዊከ ፡ ምንት ፡ ይረብሖ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ዘእንበለ ፡ ለሰብእ ፡ ዘከማከ ፡

ኅጣኢከ፡ወለዕጓለ፡እመሕያው፡ጽድቅከ፡እንዲል፡ሰው፡በጎ፡ሥራ፡ቢሠራ፡ራሱን፡ይጠቅማል። ክፉ፡ሥራ፡ቢሠራ፡ራሱን፡ይጐዳል፡እንጂ። በጎ፡ሥራ፡ቢሠራ፡እግዚአብሔርን፡የሚጠቅመው። ክፉ፡ሥራ፡ቢሠራ፡እግዚአብሔርን፡የሚጐዳው፡ሆኖ፡አይደለም። ኢዮ፡፴፱፡፫፡፴፭-፯። (ተሰብሐ፡ ኮሉ፡ ሥምረትከ)፡ በእስራኤል፡ ግን፡ ፈቃድህ፡ መከራ፡ ተመሰገንባቸው፡ እሱ፡ ወድዶ፡ ስላመጣባቸው። (በገዦ፡ደዌሆሙ)፡ መከራቸው፡በዛ፡(ወእምዝ፡እስተፋጠኑ)፡ ከመከራቸው፡ብዛት፡የተነሣ፡እውጡን፡ እውጡን፡ እሉ። ዘፀ፡፲፡፴፩፡ (እንድም፡ ለቅዱሳንሰ፡ ተሰብሐ)፡ ፈቃድህ፡ መከራ፡ በግብጻውያን፡ ተመሰገንባቸው። ወርኢኩ፡ረሚዓን፡ ወይወርዱ፡ውስተ፡መቃብር፡ቅዱስ፡እንዲል። (በገዦ)፡ መከራቸው፡ በዛ፡(ወእምዝ)፡ከመከራቸው፡ብዛት፡የተነሣ፡እስራኤልን፡ውጡልን፡ አሏቸው። አጕጕዕዎሙ፡ ግብጻውያውን፡ ለዕብራውያን፡ወአዕሐብዎሙ፡ እንዲል። ዘፀ፡፲፪፡፴፯-፴፫።

ወኢይትጎበር፡ ውስተ፡ ማኅበሮሙ፡ ዘደም።

በገዦ፡ደዌሆሙ፡ ትላለህ፡ እንጂ፡ አንተስ፡ ከነሱ፡ ልዩ፡ነህን፡ትለኝ፡ እንደሆን። ደመ፡ በግዕን፡ ለጣዖት፡ የሰውን፡ ደም፡ ከሚያፈሱ፡ ከኒህ፡ ጋራ፡ አንድነት፡ የለኝም።

ወኢይዜክር፡ አስማቲሆሙ፡ በአፉየ።

ይህ፡ ሁሉ፡ መከራ፡ የመጣብህ፡ እንኪያ፡ በምን፡ ምክንያት፡ ነው፡ ብትለምን፡ ትለኝ፡ እንደሆን፡ ስንኳንስ፡ በድል፡ ጣዖት፡ ብታመልክ፡ እይደ ጣዖት፡ ላመልክ፡ ባንደበቴ፡ ቤል፡ ዳጎን፡ ብዬ፡ ስሙን፡ ጠርቼ፡ አላውቅም።

፭፡ እግዚአብሔር፡ መክፈልተ፡ ርስትየ፡ ወጽዋዕየ።

ደመ፡ በግዕን፡ ለጣዖት፡ የሰውን፡ ደም፡ ከሚያፈስሱ፡ ጋራ፡ አንድነት፡ ስላልኖረኝ። ባንደበቴም፡ ቤል፡ ዳጎን፡ ብዬ፡ የጣዖቱን፡ ስም፡ ስላልጠራሁ፡ የማመልከው፡ እግዚአብሔር፡ ዕድል፡ ተርታዬ፡ ጽዋ፡ ፈንታዬ፡ ሆነልኝ። እንድም፡ ዕድል፡ ተርታዬ፡ ጽዋ፡ ፈንታዬ፡ እግዚአብሔር፡ ነው፡ እንጂ፡ ኢይትኀበር፡ ኢይዜክር።

አንተ፡ ውእቱ፡ ዘታገብዕ፡ ሊተ፡ ርስትየ።

እንዲህ፡ ነውና፡ ርስቴን፡ ቤተ፡ ልሔምን፡ ርስቴን፡ መንግሥትን፡ የምትመልስልኝ፡ አንተ፡ ነህ፡ ታገብዕ፡ ማለት፡ በሳኦል፡ እጅ፡ ተይዞበታልና፡ ቤተ፡ ልሔምንስ፡ ይሁን፡ ርስቴ፡ መንግሥትን፡ ማለቱ፡ ስለ፡ ምን፡ ቢሉ፡ ኢይጠፍዕ፡ ምስፍና፡ ወምልክና፡ እምዓባሉ፡ ለይሁዳ፡ ተብሎ፡ የተነገረ፡ ለሱ፡ ነውና፡ መዝ፡ ፸፱፡ ፲።

፮፡ አኀባለ፡ ወረዉ፡ ሊተ፡ የአኀዝኒ።

እለ፡ ሳኦል፡ ግን፡ ይይዙኝ፡ ዘንድ፡



ጦር፡ ሸመቁብኝ፡ ምክር፡ መከሩብኝ።

ወርስትየሰ፡ እጉኅ፡ ውእቱ፡ ሊተ።

ርስትየኒ፡ እጉኅ፡ ብየ፡ ሲል፡ ነው። ርስቴ፡ መንግሥትም፡ በሳኦል፡ እጅ፡ ተይዞብኛል። እንድም፡ እንዳለ፡ ይሆናል፡ ለነገሩ፡ አልሁ፡ እንጂ፡ ርስቴ፡ መንግሥትስ፡ ባንተ፡ እጅ፡ ተይዞልኛል፡ መቸም፡ መች፡ አላጣውም።

፯፡ እባርኮ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘአለበወኒ።

መዓልተ፡ ያለበት፡ ነው፡ በቀን፡ ጠላቴን፡ ከእጁ፡ ጥሎት፡ ሳለ፡ ሳኦልን፡ ገድዬ፡ እንዳልያዝ፡ ኢትቅትልን፡ ያሳሰበኝ፡ እግዚአብሔርን፡ አመሰግንዋለሁ። ዳዊት፡ ስድስት፡ መቶ፡ ራሱን፡ ሁኖ፡ ሳኦል፡ ሦስት፡ ሺህ፡ ደረቅ፡ ጦር፡ ሁኖ፡ ሐቅለ፡ ዚፋን፡ ዚፋን፡ ከምትባል፡ ዱር፡ ተከታትለው፡ ገቡ፡ ስለምን፡ ቢሉ፡ አንበሳ፡ መደብ፡ ለመመልከት፡ ጠል፡ ለመንሳት፡ ነፋስ፡ ለመለወጥ፡ ከውስጥ፡ ያለ፡ ነው፡ እንጂ፡ ከውጭ፡ ያለ፡ ሲገባ፡ አያይምና፡ ሳኦል፡ አላየውም። አቢሳ፡ ዳዊትን፡ ዮም፡ ዐፀወ፡ እግዚአብሔር፡ ፀረከ፡ ውስተ፡ እዴከ፡ እግዚአብሔር፡ ዛሬ፡ ጠላትህን፡ ጥሎልሃልና፡ አሰናብተኝ፡ ልግደለው፡ አለው። ሚ፡ ላዕሌክሙ፡ አንትሙ፡ ደቂቀ፡ ሱራህያ። እላንት፡ የሱራህያ፡ ልጆች፡ የሰው፡ ግንባር፡ ብትገምሱ፡ (ብትከሰክሱ)፡ ደም፡ ብታፈስሱ፡ ምን፡ ትጠቀማላችሁ። እኔስ፡ ኢታውርድ፡ እዴከ፡ ላዕለ፡ መሲሐ፡ እግዚአብሔር፡ ትላለች፡ እሪት።

ቀብቶ፡ ያነገሠውን፡ ባለቤቱ፡ ይግደለው፡ እንጂ፡ አልገድለውም፡ አለው፡ ብትፈራ፡ እንጂ፡ ነው፡ ብሎታል፡ መፍራቱንስ፡ አሳይሃለሁ፡ ብሎ፡ እፋውን፡ መዝሀ፡ የልብሱን፡ ዘርፍ፡ ቈርጦ፡ አስቀረ፡ ሲወጣ፡ ሳኦል። ዳዊት፡ ቢያገኘኝ፡ አይምረኝም፡ ትላለህ፡ አሉ። እግዚአብሔር፡ እጁ፡ ጥሎህ፡ ነበርና፡ ብገድልህ፡ ይቻለኝ፡ ነበረ፡ ወዲት፡ አለ፡ የገደልሁህ፡ አለው፡ ምን፡ ምልክት፡ አለህ፡ አለው፡ እስኪ፡ ልብስህን፡ ተመልከት፡ አለው። ልብሱን፡ ዙሮ፡ ቢያይ፡ ተቀድዶ፡ አገኘ። ዳዊት፡ ወልድየ፡ ቃልከ፡ ማኅዘኒ። ልጄ፡ ዳዊት፡ አንተና፡ እኔማ፡ ምን፡ ጠብ፡ አለን፡ ሰው፡ ያጣላናል፡ እንጂ፡ እንታረቅ፡ ብሎታልና።

ወካዕበ፡ሌሊተኒ፡ገሠጸኒ፡ኵልያትየ።

መዓልተ፡ መናሩ፡ በዚህ፡ ይታወቃል። ዳግመኛም፡ በሌሊት፡ ጠላቴን፡ ከእጁ፡ ጥሎ፡ እሱን፡ ገድዬ፡ በፍዳው፡ እንዳልያዝ፡ ሕዋሳቴን፡ የገሠፀልኝ፡ ማለት፡ ኢትቅትልን፡ ያላሳሰበኝ፡ እግዚአብሔርን፡ አመሰግነዋለሁ። ዳዊት፡ ስድስት፡ መቶ፡ ራሱን፡ ሁኖ፡ በበረሀ፡ ይኖራል፡ ሐ



2014 04 17

ቅለ ፡ ማእን ፡ ይላታል ። ሳኦል ፡ በመ
ንግሥት ፡ ያለ ፡ ነውና ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡
ደረቅ ፡ ጦር ፡ ሁኖ ፡ ዳዊትን ፡ ለመ
ሻት ፡ ሂዶ ፡ እፋፍ ፡ ላፋፍ ፡ ተሳፈሩ ፤
ላዩ ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ ሲነጋገሩ ፡ በገ
ና ፡ ሲደረድሩ ፡ ይሰማል ። ወማእከ
ሎሙ ፡ ቈላ ፡ ዕሙቅ ፡ ይላ ። ታቹ ፡
ግን ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ የሚያ
ስኬድ ፡ ጕድጓዳ ፡ ነው ። ሲመሽ ፡
ዳዊት ፡ በገና ፡ እየደረደረ ፡ ሙኑ ፡
ሀሎ ፡ ወልደ ፡ ኃይል ። ከሳኦል ፡ ዘን
ድ ፡ የምሔድ ፡ ኃኝና ፡ የሚከተለኝ ፡
ልበ ፡ ሙሉ ፡ አርበኛ ፡ ማን ፡ አለ ፡
አለ ። አቤሜሌክና ፡ አቢሳ ፡ ምነው ፡
እኛ ፡ ወዴት ፡ ሔደን ፡ አሉ ። አቤሜ
ሌክ ፡ እኛ ፡ አለን ፡ ማለቱን ፡ እንጂ ፡
መሔዱን ፡ ያወቀለት ፡ የለም ። ወን
ሕረ ፡ ቤተ ፡ ሳኦል ። ሲገሠግሥ ፡ የዋ
ለን ፡ እንቅልፍ ፡ ይጫነዋልና ፡ ጽኑ ፡
እንቅልፍ ፡ ተጭኗቸው ፡ ተኝተው ፡
ሳለ ፡ ዘበኛውን ፡ እየጠቀጠቀ ፡ ገባ ።
ሳኦልም ፡ ከላይዋ ፡ መላኟን ፡ በተተ
ከለባት ፡ በትርሸማ ፡ ድንኳን ፡ ተኝ
ቶ ፡ ነበረ ፡ አቢሳ ፡ ዮምኒ ፡ ዐበወ ፡
እግዚአብሔር ፡ ፀረከ ፡ ውስተ ፡ እዴ
ከ ፡ ኅድገኒ ፡ እዕምሮ ፡ ውስተ ፡ ምድ
ር ፡ ዘሬም ፡ ጠላትህን ፡ ከእጅህ ፡ ጥ
ሎልሃል ፡ አስናብተኝ ፡ ባንድ ፡ ውጋ ፡
ላስቀረው ፡ ከመሬት ፡ ልሰፋው ፡ አለ
ው ፡ ሚ ፡ ላዕሌክሙ ፡ ብሎ ፡ ገሠፀ
ው ፡ ብትፈራ ፡ አይደለምን ፡ አለው ፡
መፍራቱንስ ፡ አሳይሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ት
ክልት ፡ ውስተ ፡ ትርአሱ ፡ ይላታል ፡
ከራስጌው ፡ የተሰቀለች ፡ ዐፈነ ፡ ማዶን ፡
መከዳውን ፡ አገላብጦ ፡ ንዋ ፡ ያዝ ፡
አለው ። እኔስ ፡ ጓዝም ፡ ልሸከም ፡
አልመጣሁ ፡ አለው ። አንተ ፡ ብት
ተወው ፡ እኔ ፡ መቼ ፡ እተዋለሁ ፡ ብሎ ፡
ራሱ ፡ ተሸክሞ ፡ ሂዶ ፡ ከቦታው ፡
ሲደርስ ፡ የሳኦል ፡ ብላቴና ፡ ብሎ ፡
ጠርቶ ፡ ኵልክሙ ፡ ደቂ ፡ ሞት ፤ ሁላ
ችሁንም ፡ ንጉሥ ፡ ሊሠራችሁ ፡ ሊ
ቀጣችሁ ፡ ይገባዋል ። ይልቁንም ፡
አበኔር ፡ ከልብ ፡ ምዉት ፡ አንተ ፡
የውሻ ፡ ሬሳ ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ (አ
ልቆ) ፡ መሾሙ ፡ ልትጠብቀው ፡ ነበ
ር ፡ መጠበቅህ ፡ ሔት ፡ አለ ። ዛሬ ፡
እግዚአብሔር ፡ ከእጄ ፡ ጥሏችሁ ፡
ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ አሪት ፡ ኢታጠፋ
ርድ ፡ እዴከ ፡ ላዕለ ፡ መሢሐ ፡ እግ
ዚብሔር ፡ ትላለችና ፡ ተውኋችሁ ፡
እንጂ ፡ አለው ።

ምን ፡ ምልክት ፡ አለህ ፡ አሉት ። እ
ስኪ ፡ ገብታችሁ ፡ የቤተ ፡ መንግሥ
ቱን ፡ ዕቃ ፡ እዩ ፡ አላቸው ። ቢገቡ ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ታጣ ፡ ሳኦል ፡ ደነገጠና ፡
እንታረቅ ፡ ልጄን ፡ ሜልኮልን ፡ እሰ
ጥሃለሁ ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ ይልቅ
ስ ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ አልሻምና ፡ ሰው ፡
ልከህ ፡ ገንዘብህን ፡ አስወስድ ፡ ብሎ
ታል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንግዲህ ፡ ወ
ዲህማ ፡ እመሌ ፡ እመሌ ፡ ስል ፡ ከ
መያዝ ፡ አደርስ ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡



ወደ ፡ እንኩስ ፡ ሀገር ፡ ወደ ፡ ጌት ፡
ሔዷል ። ፩ሳሙ ፡ ፳፱ ፡ ፳-፳፫ ። ፳፯ ፡ ፳-፳
፭ ። ፳፯ ፡ ፭ ፡ ፱ ።

፰ ፤ ዘልፈ ፡ እሬእዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅድ
ሜየ ፡ ውእቱ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ መዝ ፡ ፹፰ ፡ ፱ ፡ ፫ ።

እግዚአብሔርን ፡ ሁልጊዜ ፡ አየዋለ
ሁ ፡ በፊቴ ፡ ነው ፡ አለ ። የመብቃት ፤
ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፲፭ ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፪ ፡ ፳፭ ።

እስመ ፡ በየማንየ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ኢይትሀወክ ።
ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ።

ሳኦልን ፡ ገድዬ ፡ በፍዳው ፡ እንዳል
ያዝ ፡ በቀኜ ፡ አለና ፡ ማለት ፡ የእው
ቀት ።

፱ ፤ በእንተዝ ፡ ተፈሥሐ ፡ ልብየ ፡ ወተኀሥየ ፡
ልሳንየ ።

ስለዚህ ፡ ልቡናዬም ፡ እንደበቴም ፡
ደስ ፡ አለው ። የልቡና ፡ ደስታ ፡ ም
ሥጢር ፡ መመርመር ፡ ያንደበት ፡
ደስታ ፡ ምሥጢር ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወዓዲ ፡ በተስፋሁ ፡ ኀደረ ፡ ሥጋየ ።

ዳግመኛም ፡ ሥጋዬ ፡ በተስፋ ፡ መን
ግሥት ፡ ጸና ፤ መኑ ፡ አስተኀደረ ፡ መ
ዓዝኒሃ ፡ ለምድር ፡ እንዲል ።

፲ ፤ እስመ ፡ ኢተኀድጋ ፡ ውስተ ፡ሲኦል ፡ ለነፍ
ስየ ። ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵፬ ።

ሰውነቴን ፡ ሳታነግሥ ፡ ከመቃብር ፡
አትጥላትምና ።

ወኢትሁብ ፡ ለጻድቅከ ፡ ይርአይ ፡ ሙስና ።

ሙስና ፡ መቃብርን ፡ ለዳዊት ፡ ዳዊ
ትን ፡ ለሙስና ፡ መቃብር ፡ አትሰጠ
ውምና ። ይርአይ ፡ ሙስና ፡ መቃብ
ርን ፡ ዳዊት ፡ ያይ ፡ ዘንድ ። አንድም ፡
ሙስና ፡ መቃብር ፡ ዳዊትን ፡ ያይ ፡
ዘንድ ፤ ግር ፡ ፭ ፡ ፳፱ ፡ ፩ ፡ ፯ ።

፲፩ ፤ ወአርአይከኒ ፡ ፍኖተ ፡ ሕይወት ።

አለ ፡ ሳኦል ፡ የሞት ፡ ጕዳና ፡ ቢመ
ሩኝ ፡ አንተ ፡ የሕይወት ፡ ጕዳና ፡ መ
ራኸኝ ።

ወአጽገብከኒ ፡ ሐሤተ ፡ ምስለ ፡ ገጽከ ።

ደስታን ፡ ከባለሟልነት ፡ ጋራ ፡ ሰጥ
ተህ ፡ ደስ ፡ አሰኘኸኝ ። ተሹሞ ፡ ደስ ፡
ሳይለው ። ሳይሾም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡
የሚኖር ፡ አለና ።

ወትፍሥሕት ፡ ውስተ ፡ የማንከ ፡ ለዝሉፉ ።

በኔ ፡ በልጅህ ፡ ደስታ ፡ ጸኖቶ ፡ ይኖ
ራል ። አንድም ፡ (ዘልፈ ፡ እሬእዮ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ቅድሜየ ፡ ውእቱ ፡
በኵሉ ፡ ጊዜ) ፤ ሰሚው ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ወንድ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡
ወልድን ፡ ሁልጊዜ ፡ አየዋለሁ ። በዕ
ሪናዬ ፡ አለ ፡ ይላል ። እግዚአብሔር ፡
አብ ፡ (እስመ ፡ በየማንየ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡
ኢይትሀወክ) ፡ ኢይትፈለጥ ፡ ሲል ፡
ነው ፡ እሱ ፡ ከኔ ፡ እኔ ፡ ከሱ ፡ እንዳንለ
ያይ ፡ በዕሪናዬ ፡ አለ ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፮ ፡ እ
ስመ ፡ ብሂለ ፡ የማን ፡ ይመርሀ ፡ ኅበ ፡
ተዓርዮቶሙ ፡ በክብር ፡ እንዲል ።

(በእንተዝ ፡ ተፈሥሐ ፡ ልብየ ፡ ወተኀ
ሥየ ፡ ልሳንየ) ፡ እኔ ፡ ከሱ ፡ እሱ ፡ ከኔ ፡ የ
ማንለይ ፡ ስለሆነ ፡ ልብነቴ ፡ ለቃሌ ፡ ለ
ወንድ ፡ ደስ ፡ አለው ፤ (እስመ ፡ ኢት

ኀድጋ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ለነፍስየ ፡
እንዲህ ፡ ሲል ፡ ያውከል ። ፩ ፡ ጴጥ ፡
፪ ፡ ፲፭ ። እንድም ፡ (ዘልፈ ፡ እሬእዮ) ፡
ሰሚው ፡ እግዚአብሔር ፡ አብነው ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ አብን ፡ ሁልጊዜ ፡ አየዋ
ለሁ ፡ በዕሪናዬ ፡ እለ ፡ እለ ፡ ወልድ ፡ እ
ስመ ፡ በየማንየ) ፡ እኔ ፡ ከሱ ፡ እሱ ፡ ከኔ ፡
እንዳንለይ ፡ በዕሪናዬ ፡ አለና ፡ (በእን
ተ ፡ ገ) ፡ እኔ ፡ ከሱ ፡ እሱ ፡ ከኔ ፡ የማን
ለይ ፡ ስለሆነ ፡ ቃልነቴ ፡ ልቡናዬ ፡
አብን ፡ ደስ ፡ አለው ፡ (ኢ ፡ ተኀድጋ ፡
ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ለነፍስየ) ፡ ሥጋዬ
ን ፡ ከሙታን ፡ ሳታስነሣ ፡ አትተዋት
ምና ፡ (ወዓዲ ፡ በተስፋሁ ፡ ኀደረ ፡ ሥ
ጋየ ፡ ሥጋየ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት
ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አደረ ፡ እ
ሁን ፡ የተመቸ ፡ (እስመ ፡ ኢ ፡ ተኀድጋ) ፡
ሥጋዬን ፡ ከመቃብር ፡ ሳታስነሣ ፡ እ
ትተዋትምና ፡ (ወኢ ፡ ትሁብ ፡ ለጻድቅ
ከ ፡ ይርአይ ፡ ሙስና) ፡ እኔን ፡ ልጅህ
ን ፡ ለሙስና ፡ መቃብር ፡ አትሰጠኝ
ምና ፡ (እርአይ) ፡ ሙስና ፡ መቃብር
ን ፡ አይ ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ ሙስና ፡
መቃብርን ፡ ለኔ ፡ ለልጅህ ፡ አትሰጠ
ውምና ፡ (ይርአይ) ፡ ሙስና ፡ መቃብ
ር ፡ እኔን ፡ ልጅህን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ (ወ
አርአይከኒ ፡ ፍኖተ ፡ ሕይወት) ፡ እይ
ሁድ ፡ የሞት ፡ ጕዳና ፡ ቢመሩኝ ፡ አን
ተ ፡ የሕይወት ፡ ጕዳና ፡ መራኸኝ ፡
(ወአጽገብከኒ ፡ ሐሤተ ፡ ምስለ ፡ ገጽ
ከ) ፡ ዕርገትን ፡ ከትንሣኤ ፡ ጋራ ፡ ሰጥ
ተህ ፡ ደስ ፡ አሰኘኸኝ ፡ ይህስ ፡ አይደ
ለም ፡ ብሎ ፡ ዕርገትን ፡ ከነቢር ፡ በየ
ማን ፡ ጋራ ፡ ሰጥተህ ፡ ደስ ፡ አሰኘኸ
ኝ ፡ (ወትፍሥሕት ፡ ውስተ ፡ የማንከ ፡
ለዝሉፉ) ፡ ቅብዐ ፡ ትፍሥሕት ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኔ ፡ በልጅህ ፡ ለሌላ ፡
ሲሰጥ ፡ ይኖራል ፡ እንድም ፡ ዕርገት ፡
ከነቢር ፡ በየማን ፡ ጋራ ፡ በኔ ፡ በልጅ
ህ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ ማለት ፡ ተፈል
ጦ ፡ የለባቸውምና ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፳፱ ፡ ፳-
፱ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፱ ።

## መዝሙር ፡ ፲፯ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ ስምዐኒ ፡ ጽድቅየ ።

በሳኦል ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግሮ
ታል ፡ አቤቱ ፡ እውነተኛ ፡ ልመናዬ
ን ፡ ስማኝ ። ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፴ ።

ወአጽምዐኒ ፡ ስእለትየ ።

ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወአጽምዐኒ ፡ ጸሎትየ ፡ ዘኢኮነ ፡ በከናፍረ ፡ ጕ
ሕሉት ፡ መዝ ፡ ጀ፱፱ ፡ ፩ ።

በከዳተኛ ፡ እንደበት ፡ ያይደለ ፡ የእ
ውነት ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ፡ የዳዊት ፡
ልመና ፡ በክት ፡ ልቡና ፡ ነውና ፡ የል
መናም ፡ ስንቱ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ መ
ሳልሶ ፡ ተናገረው ።

፪ ፡ እምቅድመ ፡ ገጽከ ፡ ይወፅእ ፡ ፍትሕየ ።

ከፊትህ ፡ ይፈረድልኛል ። እንድም ፡
ባለሟል ፡ ነኝና ፡ እንደ ፡ ባለሟልነቴ ፡ ከ
ፊትህ ፡ ይፈርድልኛል ። ተራ ፡ ሰው ፡



የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የሕገሴን ፡ ነገር ፡ ባ
ደበባይ ፡ ሰምታችሁ ፡ አምጡልኝ ፡
ይባላል ፡ ባለሟል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡
ግን ፡ ዘውዱን ፡ ደፍቶ ፡ ኀለተ ፡ ወር
ቁን ፡ ጨብጦ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡
ከፊቱ ፡ ይፈርድለታልና ።

አዕይንትየ ፡ ርእያ ፡ ጽድቀከ ።

ዓይኖቼም ፡ ይቅርታህን ፡ ቸርነትህ
ን ፡ አገኙ ፡ አዩ ።

፫ ፡ ሐወጽከኒ ፡ ሌሊተ ፡ ወፈተንከ ፡ ለልብየ ።

በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ጠላቴን ፡
ከእጄ ፡ ጥለህ ፡ ይገድለው ፡ ይሆን ፡
አይገድለው ፡ ይሆን ፡ ብለህ ፡ መረ
መርከኝ ። መዝ ፡ ፻፴፰ ፡ ፩ ።

አመከርከኒ ፡ ወኢተረክበ ፡ በላዕሌየ ፡ ዐመፃ ።

እንዲህ ፡ ብትመረምረኝ ፡ በእጄ ፡ መ
ግደል ፡ በቃሌ ፡ መበደል ፡ በልቡና
ዬ ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ አልተገኘብኝም ።

ከመ ፡ ኢይንብብ ፡ አፉየ ፡ ግብረ ፡ እጓለ ፡ እመ
ሕያው ፡ ኤር ፡ ፲፫ ፡ ፪ ።

ሰው ፡ ሰውኛን ፡ ነገር ፡ እንዳልናገር ፡
እንድም ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ እጓለ ፡ እመ
ሕያው ፡ ይላል ፡ ሰው ፡ በቃሉ ፡ ፈከ
ሮ ፡ ዘምሮ ፡ የሚያደርገውን ፡ ነገር ፡
እንዳላደርግ ፡ እገሌ ፡ ጠላትህን ፡ እ
ንጂ ፡ አግኝቸው ፡ ነበረ ፡ አግኝተኸው ፡
ቢሆን ፡ ምን ፡ ባደረግኸው ፡ ይለዋል ፡
የመቼውን ፡ የዘንጋሁትን ፡ አግኝቼ
ውማ ፡ ቢሆን ፡ አብልቼ ፡ አጠጥቼ ፡
በሰደድኩት ፡ ነበር ፡ ይላል ፡ ቢያገኘ
ው ፡ ሳይተወው ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ከንድ ፡
ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አግኝቶ ፡ ትቶታልና ።
፬ ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ ከናፍሪከ ፡ ኦነ ፡ ዕቀብኩ ፡
ፍኖተ ፡ ዕፁብ ።

እፍቅሩ ፡ ጸላእተክሙ ፡ ስላልህ ፡ ማቴ ፡
፭ ፡ ፵፬ ፡ ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፯ ። ፳፫ ፡ ፴፭ ። ሮሜ ፡ ፲፪ ፡
፲፬ ። ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፳ ። እፍቅሩ ፡ ጸላዕተ
ክሙ ፡ ያልከውን ፡ ጠበቅሁ ፡ ፍናው ፡
ብሉ ፡ ማብዛቴ ፡ ከንድ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡
አግኝቶ ፡ ትቶታልና ፡ ዕፁብ ፡ አለ ፡
ጠላትን ፡ ከፀፈቀ ፡ ዱር ፡ ከጕደጕደ ፡
ምድር ፡ አግኝቶ ፡ መተው ፡ ጭንቅ ፡
ነውና ።

፭ ፡ አጽንዖ ፡ ለመከየድየ ፡ ውስተ ፡ ፍኖትከ ።

ባለፈው ፡ ብትጠብቅ ፡ ለሚመጣው ፡
ሳትበድል ፡ ትቀራለህን ፡ ትለኝ ፡ እን
ደሆነ ፡ ባለፈው ፡ እንደጠበቅኸኝ ፡
ለሚመጣውም ፡ እግሮቼን ፡ በጕዳና
ህ ፡ አጽናቸው ።

ከመ ፡ ኢይድሐፁ ፡ ሰኰናየ ።

ሰኰናየ ፡ እንዳይሰነካከል ። እንድም ፡
እግረ ፡ ልቡናዬን ፡ በአምልኮትህ ፡
አጽናው ፡ ሰኰና ፡ ልቡናዬ ፡ በአምል
ኮተ ፡ ጣዖት ፡ በገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ እ
ንዳይሰነካከል ። መዝ ፡ ፸፪ ፡ ፪ ።

፮ ፡ አንሰ ፡ ጸራሕኩ ፡ እስመ ፡ ሰማዕከኒ ፡ እግዚአብ
ሔር ።

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ልመናዬን ፡ ሰም
ቶኛልና ፡ አሁንም ፡ ወደሱ ፡ መልሼ ፡
ለመንሁ ።

አጽምዕ ፡ እዝነከ ፡ ኀቤየ ፡ ወስምዐኒ ፡ ቃልየ ፡ መ
ዝ ፡ ፳፭ - ፩ ።

ጆሮህን ፡ ወደኔ ፡ መልሰህ ፡ ልመናዬ
ን ፡ ስማኝ ።

፲ ፡ ዕብሎ ፡ ለምሕረትከ ፡ ዘያድኅኖሙ ፡ ለእለ ፡ ይትዌከሉከ ፡ እምእለ ፡ ይትቃወምዋ ፡ ለየማንከ ።

እኔን ፡ ልጅህን ፡ ከሚቃወሙኝ ፡ ከለ ፡ ሳኦል ፡ በንተ ፡ ያመኑ ፡ ወገኖቼን ፡ የሚያድናቸው ፡ ሥልጣንህን ፡ ግለጸው ፡ አንድም ፡ ሥልጣንህን ፡ ከሚቃወሙ ፡ ከአጋንንት ፡ በንተ ፡ ያመኑ ፡ ምእመናንን ፡ የሚያድናቸው ፡ ልጅህን ፡ በሥጋ ፡ ግለጸው ፡ ምሕረት ፡ አለው ፡ በግብሩ ።

፰ ፡ ዕቀበኒ ፡ ከመ ፡ ብንተ ፡ ዓይን ።

ዓይን ፡ ሕዋሳትን ፡ እንድትጠብቅ ፡ እኔንም ፡ ጠብቀኝ ፡ አንድም ፡ እሷ ፡ በሽፋሽፍት ፡ እንድትጠበቅ ፡ ጠብቀኝ ፡ ከመ ፡ ወለተ ፡ ዓይን ፡ ይላል ፡ አንድ ፡ ነው ።

ወበጽላሎተ ፡ ክንፈከ ፡ ክድንኒ ።

በጽላሎተ ፡ ረድኤትህ ፡ ሠውረኝ ።
ሙዝ ፡ ፶፱ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፴፯ - ፴፱ ። ሉቃ ፡ ፲፫ ፡ ፴፬ ።

፱ ፡ እምገጸ ፡ ኃጥኣን ፡ እለ ፡ ያኀሥሩኒ ።

መከራ ፡ ከሚያመጡብኝ ፡ ከነሳኦል ፡ ጠብቀኝ ።

ጸላእትየሰ ፡ አስተሐየዱዋ ፡ ለነፍስየ ።

ጠላቶቼ ፡ እለ ፡ ሳኦልስ ፡ ሰውነቴን ፡ መርዘው ፡ ተከረው ፡ ተመለከቷት ።

፲ ፡ ወቈጸሩ ፡ አማውቆሙ ።

እንጀታቸውን ፡ ቍጥር ፡ አድርገው ፡ መከሩብኝ ፡ አንድም ፡ እንጀተ ፡ ጽኑ ፡ ናቸው ።

ወነበበ ፡ ትዕቢተ ፡ አፉሆሙ ።

እንደበታቸው ፡ ትንቢትን ፡ ይናገራል ። ዳዊት ፡ ያልሁ ፡ እንደሆን ፡ ማክበር ፡ ይሆንብኛል ፡ ብሎ ፡ አይቴ ፡ ሖረ ፡ ዝኩ ፡ ወልደ ፡ ዕሤይ ፡ ብሏልና ። ዝኩ ፡ የጠብ ፡ ንግግር ፡ ነው ።

፲፩ ፡ ሰደዱኒ ፡ ይእዜ ፡ ዐገቱኒ ፡

ፊት ፡ ከሀገር ፡ አስወጥተው ፡ ከዘመድ ፡ ለይተው ፡ ሰደዱኝ ። አሁንም ፡ ከዚህ ፡ ካለሁበት ፡ አላኖር ፡ ብለው ፡ ከበቡኝ ።

ወአትሐቱ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ምድር ።

ደፍጦ ፡ ደፍቶ ፡ መከር ፡ ናቸው ። አንድም ፡ ፍለጋዬን ፡ ለመመልከት ፡ ዓይናቸውን ፡ ወደመሬት ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አደረጉ ።

፲፪ ፡ ወተመጠዉኒ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ ዘጽንሕ ፡ ለመሢጥ ።

አንበሳ ፡ ላምን ፡ ለመንጠቅ ፡ እንዲደፍጥ ።

ወከመ ፡ ዕጓለ ፡ አንበሳ ፡ ዘይነብር ፡ ተኀቢኦ ።

ያንበሳ ፡ ግልገል ፡ ከጨፈቀ ፡ ዱር ፡ ከጐደጐደ ፡ ምድር ፡ ላምን ፡ ለመንጠቅ ፡ እንዲደፍጥ ፡ እጅ ፡ አደረጉኝ ። ተንሥእ ፡ ማንሻ ። አንድም ፡ ያንበሳ ፡ ግልገል ፡ ላምን ፡ ለመንጠቅ ፡ ከፀፈቀ ፡ ዱር ፡ ከጐደጐደ ፡ ምድር ፡ ደፍጦ ፡ ታመልጠኛለች ፡ ሳይል ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲነሣ ።



፲፫ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ብጽሖሙ ፡ ወአዕቅፆሙ ።

አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሣ ። የመከራ ፡ ወሬ ፡ ይዘህ ፡ ደርሰህ ፡ አስነክላቸው ፡ ዳዊት ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ራሱን ፡ ሁኖ ፡ ሲሸሽ ፡ ሳኦል ፡ ሰስት ፡ ሽሕ ፡ ደረቅ ፡ ጦር ፡ ሁኖ ፡ ሲከተል ፡ ከመንታ ፡ መንገድ ፡ ደረሱ ፡ በመካከል ፡ ተራራ ፡ አለ ። ዳዊት ፡ በንዱ ፡ መንገድ ፡ ሒዶ ፡ አልፎ ፡ ይገናኛል ። ሳኦል ፡ ከመንታው ፡ ሲደርስ ፡ ከኋላው ፡ መጥተው ፡ አገርህን ፡ ኢሎፍላውያን ፡ አጠፉልህ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ። አንድ ፡ ብላቴና ፡ ስከታተል ፡ አገሬን ፡ አስጠፋለሁን ፡ ብሎ ፡ ተመልሷል ። አንዱን ፡ መንገድ ፡ ይዞ ፡ ሒዶ ፡ ቢሆን ፡ ከመገናኛው ፡ ይይዘው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ዳዊት ፡ አ ፡ እግዚኦ ፡ ብጽሖሙ ፡ ወአዕቅፆሙ ፡ እያለ ፡ ይጸልይ ፡ ነበርና ፡ እንዲመለስ ፡ አደረገው ፡ ይህችም ፡ ተራራ ፡ ኰኵሐ ፡ መክፈልት ፡ ተብላለች ፡ ዳዊትና ፡ ሳኦል ፡ የተለያዩበት ፡ ማለት ፡ ነው ። ፩ሳሙ ፡ ፳፫ ፡ ፳፮-፳፰ ።

ወበልሓ ፡ እምኵናት ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴንም ፡ ከሳኦል ፡ ጦር ፡ አድናት ፡

፲፬ ፡ ሰይፍከ ፡ ላዕለ ፡ ፀረ ፡ እዴከ ።

ትረድ ፡ ያለበት ፡ ነው ። ሰይፈ ፡ መዓትህ ፡ በኔ ፡ በልጅህ ፡ ጠላት ፡ በሳኦል ፡ ትውረድበት ። አድንም ፡ ሰይፈከ ፡ ምላህ ፡ ይላል ። ሰይፈ ፡ መዓትህን ፡ በኔ ፡ በልጅህ ፡ ጠላት ፡ በሳኦል ፡ ምዘዝበት ። አንድም ፡ ላዕለ ፡ ኰኵሐ ፡ ፀረ ፡ ዳዊት ፡ ወልድከ ፡ ይላል ፡ ሰይፍህ ፡ በኔ ፡ በልጅህ ፡ ጠላት ፡ በሳኦል ፡ እንገት ፡ ትውረድበት ። አንድም ፡ ሰይፍህን ፡ በኔ ፡ በልጅህ ፡ ጠላት ፡ በሳኦል ፡ እንገት ፡ ምዘዝበት ።

እግዚኦ ፡ እምውሑዳን ፡ ምድር ፡ ንፍቆሙ ፡ በሕይወቶሙ ። ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፳፭ ።

አቤቱ ፡ ከሰው ፡ ተለይተው ፡ በዝተው ፡ ከነሡ ፡ ከነገደ ፡ ብንያም ፡ ወገን ፡ የሚሆኑ ፡ እለ ፡ ሳኦልን ፡ እለን ፡ እለን ፡ ሲሉ ፡ እጥፋቸው ። አንድም ፡ ዕድሜያቸውን ፡ በሞት ፡ ከፈልባቸው ። ኃጥእ ፡ ዕድሜውም ፡ እንዲሉ ። አንድም ፡ ከሕይወት ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ከተድላ ፡ ወደ ፡ መከራ ፡ መልሳቸው ፡ ከሀገራቸው ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ሀገር ፡ ስደዳቸው ። አንድም ፡ ነፍሳቸውን ፡ ከሥጋቸው ፡ ለይ ።

ውሑዳን ፡ ምድር ፡ ያሰኘው ፡ እንደ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ካህን ፡ ደብረ ፡ ኤፍሬም ፡ ይለዋል ፡ ሚስቱ ፡ ተጣልታም ፡ ቢሉ ፡ ዘመዶቿን ፡ ልትጠይቅም ፡ ቢሉ ፡ ወደ ፡ ሀገሯ ፡ ሔደች ፡ እሱም ፡ ተከትሎ ፡ ሒዶ ፡ ከደጅ ፡ ተቀመጠ ፡ ወንድሞችን ፡ ከሚስትህም ፡ እንደሆን ፡ እናስታርቅሃለን ፡ ግባ ፡ አሉት ፡ ታርቆ ፡ ገባ ፡ በነጋው ፡ እሔዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ፡ ቈዩ ፡ ምሳችሁን ፡ በልታችሁ ፡ ትሔዳላችሁ ፡ አ

2014 04 17

ኋቸው፡ ረፈደባቸው፡ ዋሉ፡ አደሩ፡
በነጋውም፡ ልሒድ፡ ብሎ፡ ተነሣ፡
ዛሬም፡ ምሳችሁን፡ በልታችሁ፡ ት
ሔዳላችሁ፡ ምሳ፡ ለመንገድ፡ ያግዛ
ልና፡ አሏቸው፡ አይሆንም፡ ከሰው፡
ቤት፡ ከደሩ፡ ከዋሉ፡ መታመም፡
መሞት፡ አለ፡ የሰው፡ ቤት፡ ላይኾነኝ፡
ቤት፡ አድርጌ፡ እኖራለሁን፡ ምሳቸ
ው፡ እስኪሰናዳ፡ ረፈደ፡ ዋሉ፡ አደሩ፡
በሦተኛው፡ ምሳቸውን፡ በልተው፡
ከረፈደ፡ በኋላ፡ ተነሥተው፡ ሔዱ፡
በጢት፡ ቢነሡ፡ ዕለቱን፡ ይገቡ፡ ነበ
ር፡ መሴፋ፡ ሲደርሱ፡ መሸባቸው፡
ብላቴናው፡ ከዚህ፡ እንደር፡ አለው፡
አይሆንም፡ ከዚያ፡ ወንድማችን፡
የሚሆን፡ አለ። እንዋሩ፡ እንደ፡ ሎጥ፡
ሁና፡ ነው። ለኛ፡ ራት፡ ለከብቶቻ
ችን፡ ገፈራ፡ እንልሀም፡ ማደሪያ፡
ስጠን፡ እንለዋለን፡ ብለው፡ ሔዱ።
ወዴት፡ ትሔዳላችሁ፡ የማን፡ ወገን፡
ናችሁ፡ አላቸው። ንሕነ፡ ኃለፍተ፡
ቤተ፡ ልሔም። ወደ፡ ቤተ፡ ልሔም፡
እንሔዳለን፡ ወገናችንም፡ ከነገደ፡
ኤፍሬም፡ ነን፡ አሉት። አላንትማ፡
ወንድሞቻችን፡ አይደላችሁምን፡
ግቡ፡ አላቸው። ራት፡ አግባ፡ ሔዶ፡
ከዕገሌ፡ ቤት፡ እንዲህ፡ ያሉ፡ ሰዎ
ች፡ ገብተዋል፡ ብሎ፡ ለሀገሩ፡ ሰዎ
ች፡ ነገረ፡ እሊህ፡ የገባዎን፡ ሰዎች፡
ግብረ፡ ሰዶም፡ የሚሠሩ፡ ናቸው፤
ዘሌ፡ ፳፡ ፲፫፡ ተሰብስበው፡ ሔደው፡ ስጠ
ን፡ አሉት፡ የእኔን፡ ልጅ፡ ውሰዱ፡
አላቸው፤ ያንተማ፡ ልጅ፡ እኛ፡ እና
ዝዝባታለን፡ እንጂ፡ አንተ፡ ታዝ
ዝባታለህን፡ አሉት። ባይሆንም፡
የሚገባትን፡ ሚስቱን፡ ውሰዱ፡ እን
ጂ፡ እሱን፡ አልሰጣችሁም፡ ብሎ፡
ሚስቱን፡ ሰጣቸው፡ እንደ፡ ጋላ፡
እንደ፡ ሸንቅላ፡ በፈረቃ፡ አደሩባት፡
ዘፍ፡ ፲፱፡ ፩-፲፭። ዘር፡ እስከጌት፡ ሞ
ተች፡ እሱም፡ መቼ፡ ነግቶልኝ፡ አኳ
ኋኗን፡ ጠይቂአት፡ እያለ፡ ሲጨነቅ፡
አደረ፡ ሲነጋ፡ ወስደው፡ ከደጅ፡ አጋ
ድመዋት፡ ሔዱ፡ ያለች፡ መስሎት፡
ተነሺ፡ እንሒድ፡ አላት፡ ዝም፡ አለ
ች፡ ገልጦ፡ ቢያይ፡ ሙታለች፡ ባህ
ያው፡ ጭኖ፡ ወደ፡ ሀገሩ፡ ይዞ፡ ሔዶ፡
ሥጋዋን፡ ከሥራ፡ ሁለት፡ ቦታ፡ ቆር
ጦ፡ ከፍሎ፡ አባቶቻችን፡ ከግብጽ፡
ከወጡ፡ እስካሁን፡ እንዲህ፡ ያለ፡
ግፍዕ፡ ተደርጎ፡ አያውቅም፡ በኔማ፡
አንድ፡ ጊዜ፡ ተደርጎብኝ፡ የለምን፡
የሚያሳዝነኝ፡ የእስራኤል፡ ሥራት፡
መፍረሱ፡ ነው፡ እንጂ፡ ብሎ፡ ላስ
ራሁለቱ፡ ነገደ፡ እስራኤል፡ ይልክ
ላቸዋል፤ ዓሥራሁለተኛውማ፡ ነገ
ደ፡ ብንያም፡ አይደለምን፡ ቢሉ፡
ከዚያው፡ ግብረ፡ አበር፡ ያልሆኑ፡
አሉና። መሳ፡ ፲፱፡ ፩-፴። ፳፡ ፩-፯። ተና
ደው፡ ስንቅ፡ አቅልለው፡ ለሺሁ፡
መቶ፡ ለመቶው፡ ሃምሳ፡ ለሃምሳው፡
ዓሥር፡ ለአሥሩ፡ ሦስት፡ አድርገ
ው፡ ዘወሀበ፡ ወንዶ፡ ወወለቶ፡ ለብ
ንያማዊ፡ ርጉመ፡ ለይኩን፡ ብለው፡



እየረገሙ፡ ተነሥተዋል፡ ኢያውሴ
ዎን፡ ሲደርሱ፡ እረ፡ ከነገር፡ ቀደ
ም፡ ልብ፡ ይነድ፡ ልብ፡ ይበርድ፡
እንዲሉ፡ አድራጊ፡ አውጡ፡ እንበ
ላቸው፡ ብለው፡ ላኩ። አድራጊም፡
የለ፡ ብትመጡም፡ ግድ፡ የለ፡ ብለው፡
መለሱ፡ ሄደው፡ ቢገጥሙ፡ አንዱ፡
ነገድ፡ አሥራ፡ አንዱን፡ ሁለት፡ ጊዜ፡
ድል፡ አደረጋቸው። ነቢያት፡ ካህናት፡
የኒህስ፡ ሥራ፡ ደስ፡ አሰኝቶህ፡ ነውን።
የዚያችስ፡ ሴት፡ ደም፡ እንደፈሰሰ፡
ይቅር፡ ብለህ፡ ነው፡ ብለው፡ መሥ
ዋዕት፡ ሠውተው፡ ወደ፡ እግዚአብ
ሔር፡ ቢያመለክቱ፡ ፈቃዴስ፡ አይ
ደለም። ከናንተም፡ ብዙ፡ ክፉዎች፡
አሉና፡ እነዚያ፡ እስኪያልቁ፡ ድረ
ስ፡ ነው፡ እንጂ፡ አሁንም፡ ድብቅ፡
ጦር፡ አበጅታችሁ፡ ግጠሟቸው፤
ድል፡ ታደርጓቸዋላችሁ፡ አላቸው፤
ድብቅ፡ ጦር፡ አበጅተው፡ በጢስ፡
ሸፍነው፡ ታዩዋቸው፤ ድል፡ የለመ
ደ፡ ልጅ፡ አዋቂ፡ ሴት፡ ወንድ፡ ባ
ልቴት፡ ሽማግሌ፡ አይቀርምና፡ ተሰ
ብስበው፡ ወጡ፡ ያ፡ ድብቅ፡ ጦር፡
ከተማቸውን፡ አቃጠለው። እኒህ፡
በወዲህ፡ እኒያ፡ በወዲያ፡ ሁነው፡
ገጠሟቸው። ድል፡ አደረገው፡ ስድ
ስት፡ መቶ፡ ሰዎች፡ በኩኵሐ፡ አዋ
ሬዎን፡ ሲቀሩ፡ የቀሩትን፡ አጥፍተ
ዋቸዋል። መሳ፡ ፳፡ ፳-፵፰። ለጊዜው፡
ደስ፡ አላቸው። ኋላ፡ ግን፡ እንዴት፡
ዓሥራ፡ ሁለት፡ ነገድ፡ ተብለን፡
ዓሥራ፡ አንድ፡ ነገድ፡ እንባል፡ ብ
ለው፡ አዘኑ። አትታረቋቸውምን፡
አሏቸው። ስንዘምት፡ ዘወሀበ፡ ወለ
ቶ፡ ለብንያማዊ፡ ርጉመ፡ ለይኩን፡
ብለን፡ ረግመን፡ ነበረ። መሐላው፡
እንደምን፡ ይፈርሳል፡ አሉ። ዐምፆ፡
የቀረ፡ ደጃዝማች፡ አለ፡ እሱን፡ ወ
ግታችሁ፡ ከሱ፡ የተገኙትን፡ ደናግ
ል፡ አትሰጧቸውምን፡ አሏቸው። እ
ሱን፡ ወግተው፡ ያልባለቁ፡ ያልባለ
ቁ፡ አራት፡ መቶ፡ ደናግል፡ ተገኙ።
ላራቱ፡ መቶ፡ ሰጧቸው፡ ሁለቱ፡
መቶ፡ እኛሳ፡ እንደምን፡ እንሁን፡
አሏቸው። አበባ፡ አርግፍ፡ የሚባል፡
ዘፈን፡ አላቸው፡ ያን፡ እየዘፈናችሁ፡
ከገበያም፡ ከልቅሶም፡ እየነጠቃችሁ፡
አግቡ፡ ብለው፡ ታርቀዋቸዋል።
መሳ፡ ፳፩፡ ፩-፳፫።

እምነገሥታቲሆሙ፡ አገበት፡ ነፍሶሙ።

ገና፡ እበላ፡ በቀን፡ በዳረጎቱ፡ ከረቂ
ቅ፡ እምባሻ፡ መቅመፍትህ፡ በልተ
ው፡ ጠገቡ። ነፍሰሙ፡ ንጉሣዊ፡ አነ
ጋገር፡ ለከሙ፡ ይብሉከሙ፡ ንጉሥ፡
እንደ፡ ማለት።

ጸገቡ፡ ደቂቆሙ።

ልጆቻቸው፡ ጠገቡ።

ወኀደጉ፡ ትራፋቲሆሙ፡ ለሕፃናቲሆሙ።

ተረፋቸውንም፡ ለልጅ፡ ልጆቻቸው፡
አስቀሩ፡ እስራኤል፡ ከግብጽ፡ ሲወ
ጡ፡ መሐል፡ መሐሉን፡ አጥፉ፡ ዳር፡
ዳሩን፡ አታጥፉ፤ ከመ፡ ኢትኩን፡

ምድር ፡ ፀፀ ፡ ምድር ፡ በዶዋን ፡ እን
ዳትሆን ፡ እየቀደም ፡ እየበዙ ፡ እን
ዲወርዷት ፡ ነው ፡ ሰብአ ፡ ገባዖን ፡
ይህን ፡ ሰምተው ፡ ያለቀ ፡ ልብስ ፡ ለ
ብሰው ፡ ያለቀ ፡ ጫማ ፡ ተጫምተው ፡
ያለቀ ፡ ጥላ ፡ የነቀዘ ፡ በትር ፡ የሻበተ ፡
ዳቦ ፡ ይዘው ፡ መጡ ። ከወዴት ፡ መ
ጣችሁ ፡ አሏቸው ። ከገባዖን ፡ አሉ ፡
ይህች ፡ ገባዖን ፡ የስንት ፡ ቀን ፡ ጉዳ
ና ፡ ናት ፡ አሏቸው ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡
አሏቸው ። እኒህ ፡ ሐሰተኞች ፡ አኗ
ቸው ፡ እሩቅም ፡ ቅርብም ፡ ትሉ ፡
እንደሆነ ፡ ከሀገራችን ፡ ስንወጣ ፡ ል
ብሳችን ፡ ጫማችን ፡ በትራችን ፡ ጥላ
ችን ፡ አዲስ ፡ ነበረ ፡ አለቀ ፡ ዳቦዋ
ችን ፡ ትኩስ ፡ ነበረ ፡ ደረቀ ፡ አሏቸ
ው ። እንዲህ ፡ ያለስ ፡ ከገበያ ፡ ከመ
ንደር ፡ ከከተማ ፡ ብትዋሱ ፡ ይሆናል ፡
ስንቃችሁን ፡ አሳዩን ፡ አሏቸው ፡ አ
ሳዩዋቸው ፡ ወእምኑ ፡ በርእየ ፡ ስን
ቆሙ ፡ ያን ፡ አይተው ፡ አምነዋል ።
ይህንም ፡ አለማወቃቸው ፡ ነው ፡ እ
ንጂ ፡ ያልሆንች ፡ ሴት ፡ የያዘችው ፡
እንደሆነ ፡ ዕለቱን ፡ ተለውጦ ፡ ያድ
ራል ። ለምን ፡ መጣችሁ ፡ አሏቸው ፡
እንዳታጠፉን ፡ ደጅ ፡ እንጠናለን ፡
ብለን ፡ መጣን ፡ አሏቸው ። ፈጣሪያ
ችን ፡ አጥፉ ፡ ያለን ፡ መሐል ፡ መ
ሐሉን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዳር ፡ ዳሩን ፡
መቼ ፡ አጥፉ ፡ አለን ፡ አሏቸው ።
አይሆንም ፡ እስራኤልና ፡ ፀሐይ ፡ የ
ማይደርስበት ፡ የለምና ፡ አገራችንን ፡
እንዳታጠፉብን ፡ ማሉልን ፡ አሏቸ
ው ፡ በውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ጠልፈው ፡
ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስጠርተዋ
ቸው ፡ እነሱ ፡ ዕለቱን ፡ ደርሰዋል ።
እስራኤል ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ጓዝ ፡ ይዘዋ
ልና ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ደርሰው ፡
ይህቺ ፡ አገር ፡ ማን ፡ ትባላለች ፡ አሉ ፡
ገባዖን ፡ ትባላለች ፡ አሏቸው ። እነ
ዚህ ፡ ሐሰተኞች ፡ በሐሰት ፡ አምለ
ውናልሳ ፡ እናጥፋቸው ፡ ብለዋል ፡
እስራኤል ፡ አስቀድሞ ፡ ጠንቅቆ ፡
መማል ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ አሁንማ ፡
መሐላ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደምን ፡
ይፈርሳል ። በይሆንም ፡ ለቤተ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ እንጨት ፡ ለቃሚ ፡ ወሀ ፡
ቀጂ ፡ ፀወርተ ፡ ደብተራ ፡ ይሁኑ ፡
ብሎ ፡ ሠርቷቸዋል ፡ እንደ ፡ ጉንደር ፡
ቅማንት ፡ ላያምንበት ፡ ላይጠመቅምበ
ት ፡ ላይቀበርበት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ሲሠራ ፡ እንዲኖር ። ኢያ ፡ ፱ ፡ ፩-፳፯ ።
ምድረ ፡ ርስትን ፡ ሲከፈሉ ፡ ገባዖን ፡
ለነገደ ፡ ብንያም ፡ ደረሰች ። ኢያ ፡ ፲፰ ፡
፲፩-፳፰ ። ሳኦል ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ እኒህ ፡
በእስራኤል ፡ መከከል ፡ ምን ፡ አገባ
ቸው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ። እኒህማ ፡ አባ
ቶቻችንን ፡ በሐሰት ፡ አምለው ፡ ወር
ሰዋት ፡ የቀሩ ፡ ናቸው ፡ አሉት ። በ
አፍአ ፡ የእስራኤልን ፡ በቀል ፡ ደገ
ል ፡ መለስሁ ፡ ብሎ ፡ በውስጥ ፡ ግን ፡
ርስት ፡ ጠበበኝ ፡ ብሎ ፡ እነሱን ፡ አ
ጥፍቶ ፡ የሱን ፡ ወገን ፡ ሠርቶበታል ፡
ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ በግመል ፡ ወሰብሬ ፡
ሁነው ፡ ሲያመልጡ ።



ሳኦል ፡ ሙቶ ፡ ዳዊት ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡
ወተታሊዎ ፡ ሠለስተ ፡ ዓመተ ፡ ከነ ፡
ረኃብ ። ቀጥሎ ፡ ቀጥሎ ፡ ሦስት ፡
ዓመት ፡ ረኃብ ፡ ሆነ ። በኔ ፡ ኃጢአት ፡
ነውን ፡ ወይስ ፡ በሕዝቡ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር ፡ ቢያመለክት ። በን
ተም ፡ በሕዝቡም ፡ አይደለ ። ነገር ፡
ግን ። በ ፡ ዐመፃ ፡ ላዕለ ፡ ቤተ ፡ ሳኦል ።
በሳኦል ፡ ወገን ፡ ደም ፡ አለና ። ያንን ፡
ተመራምረህ ፡ ካላጠፋህ ፡ ዝናም ፡
ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ አልሰጥህም ፡
አለው ። ነገሩን ፡ ያውቃልና ፡ እኒያ
ን ፡ ሰዎች ፡ አስጠርቶ ፡ ይህ ፡ ረኃብ ፡
የመጣ ፡ በናንተ ፡ ምክንያት ፡ ነውና ፡
ከሳኦል ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ ልስጣችሁን ፡
ወይስ ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ አላቸው ። አ
ሁን ፡ ዳዊት ፡ እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ዘመ
ዶቹን ፡ ሊሰጠን ፡ ነውን ፡ የምንናገ
ረውን ፡ ሰምቶ ፡ እኛንም ፡ ሲርስ ፡ ሊ
ያጠፋን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብለው ። እኛስ ፡
እንሻም ። ደማችን ፡ እንደ ፡ ፈሰሰ ፡
ይቅር ፡ አሉት ። ሕያው ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ ፆሥረዩ ፡ ለነ ፡ ፆሥረዩ ፡ ለነ ፡
ብሎ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠራላ
ቸው ። እውነትህስ ፡ ከሆነ ፡ ዘመነ ፡
ዐፀባ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ኢንፈቅድ ፡ ወ
ርቀ ፡ ወብሩረ ። ወርቅ ፡ ብር ፡ አንሻ
ም ። አላ ፡ ንሥርዎ ፡ በከመ ፡ ሠረወነ ፡
እሱ ፡ ዘራችንን ፡ እንደ ፡ መተረው ፡
እኛም ፡ የሱን ፡ ዘር ፡ እንምተረው ፡
ልጆቹን ፡ ስጠን ፡ አሉት ። ወሀለዉ ፡
፪ ፡ ደቂቃ ፡ ለሩፃፋ ፡ ወሐምስቱ ፡
ውሉዳ ፡ ለሚሮብ ። ከሩፃፋ ፡ የተወ
ለዱ ፡ ሁለቱን ፡ ከሚሮብ ፡ የተወለ
ዱን ፡ አምስቱን ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ሰባ
ቱን ፡ ሰጣቸው ። ወሰደው ፡ ከተራራ ፡
ላይ ፡ ቢያርዷቸው ፡ ደማቸው ፡ ከም
ድር ፡ ጠብ ፡ ሲል ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡
ጠል ፡ ለመከር ፡ ሰጠ ። ወሮጸት ፡ ሩ
ፃፋ ፡ ወረበበት ፡ ሠቀ ፡ ላዕለ ፡ ደቂ
ቃ ። አንበሳ ፡ የሰበረው ፡ ንጉሥ ፡
የገደለው ፡ ይታፈራልና ፡ ለመቅበር ፡
ፈርታ ፡ የማቅ ፡ ድንኳን ፡ አስጥላ ፡
ስታለቅስ ፡ ባለሟሉ ፡ ሄዶ ፡ ነገረላት ።
የሳኦልና ፡ የዮናታን ፡ ዓፅም ፡ ከቤተ ፡
ጣዖት ፡ ይኖር ፡ ነበር ፡ ያን ፡ አስመ
ጥቶ ፡ እነዚህን ፡ አድርጎ ፡ ከባታቸ
ው ፡ ከቂስ ፡ መቃብር ፡ አስቀብሯቸ
ዋል ። ፪ሳሙ ፡ ፳፩ ፡ ፩-፲፱ ። ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፲፮ ።

፲፭ ፡ ወአንሰ ፡ በጽድቅየ ፡ እሬኢ ፡ ገጸከ ።

እኔ ፡ ግን ፡ በይቅርታህ ፡ በቸርነትህ ፡
ገጸ ፡ ረድኤትህን ፡ ገጸ ፡ ምሕረትህ
ን ፡ አገኛለሁ ።

ወእጸግብ ፡ በርእየ ፡ ስብሐቲከ ።

ጌትነትህን ፡ በማየት ፡ አንድም ፡ በረ
ከበ ፡ ተአምራቲከ ፡ ይላል ፡ ተአም
ራትህን ፡ በማግኘት ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

## መዝሙር ፡ ፲፯ ።

፩ ፡ ኢሬቅረከ ፡ እግዚኦ ፡ በኃይልየ ፡ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፳፪ ።

ስለራሱ ፡ ተናገርታል ፤ ይህንንና ፡ እ
ገኒ ፡ ለከን ፡ ጠላቶቹ ፡ ከጠፉለት ፡ መ
ንግሥቱ ፡ ከጸናለት ፡ ከተደላደለለ
ት ፡ በኋላ ፡ ተናገርታል ፤ ወዝንቱ ፡
ነገሩ ፡ ለዳዊት ፡ ምእመን ፡ ሰበ ፡ ገብ
ኡ ፡ ጸላእቱ ፡ ታሕተ ፡ መከየደ ፡ እገ
ሪሁ ፡ እንዲል ። ፪ ሳሙ ፡ ፳፪ ፡ ፩ ። አቤቱ ፡
በደረግሀልኝ ፡ ኃይል ፡ እንድም ፡ ኃ
ይልን ፡ አደረግሀልኝ ፡ ብዬ ፡ እንድ
ም ፡ ታደርግልኛለህ ፡ ብየ ፡ እንድ
ም ፡ እንደ ፡ ችሎቴ ፡ እንደመጠኔ ፡
እወድሃለሁ ፡ አመሰግንሃለሁ ።

፪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይልየ ፡ ወፀወንየ ፡ ወመድ
ኀንየ ።

እግዚአብሔር ፡ ብዋጋ ፡ ኃይሌ ፡ ብ
ሸሽ ፡ እምባ ፡ መጠጊያዬ ፡ ነው ፤ (ወ
መድኀንየ) ፡ አለ ፡ የማያድን ፡ እምባ ፡
አለና ፡ ከዚያ ፡ ሲለይ ፡ የምድንበት ፡
እምባዬ ፡ አለ ።

እምላኪየ ፡ ወረዳእየ ፡ ወእትዌከል ፡ ቦቱ ።

ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረዳቴ ፡ ነ
ው ፤ እንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈ
ጣሪዬ ፡ ነው ፤ ረዳቴም ፡ ነው ፤ እኔም ፡
ይረዳኛል ፡ ብዬ ፡ እምንበታለሁ ።

ምእመንየ ፡ ወቀርነ ፡ ሕይወትየ ፡ ወምስካይየ ።

የታመነ ፡ ወዳጄ ፡ የታመነ ፡ ረዳቴ ፡ ነ
ው ፡ የሰውነቴ ፡ መጠጊያ ፡ ነው ፤ ወ
ሕይወት ፡ ቀርንየ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡
የመንግሥቴ ፡ መጽኛ ፡ ነው ።

፫ ፡ እንተ ፡ ሰበ ፡ ጸዋዕክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እ
ድኅን ፡ እምፀርየ ።

ለ ፡ አይረባም ፡ ጸዋዕክዎን ፡ ሲያይ ፡ የ
መጣ ፡ ነው ፤ በለመንሁት ፡ ጊዜ ፡ ከ
ጠላቶቼ ፡ የምድንበት ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ ነው ።

፬ ፡ አገዘኒ ፡ ፃዕረ ፡ ሞት ።

ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ መከራ ፡ አገኘ
ኝ ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፳፪ ።

ወውኂዝ ፡ ዐመፃ ፡ ሆከኒ ።

የዓመፅ ፡ ፈሳሽ ፡ አወከኝ ።

፭ ፡ አገተኒ ፡ ፃዕረ ፡ ሲኦል ።

ለመቃብር ፡ የሚያበቃ ፡ መከራ ፡ አ
ገኘኝ ።

ወበጽሐኒ ፡ መሣግረ ፡ ሞት ።

ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ መከራ ፡ አገኘ
ኝ ፤ በናቱ ፡ ዕፀቢሁ ፡ ለሞት ፡ ይላል ።
፪ ፡ ሳሙ ፡ ፳፪ ፡ ፮ ። እንድም ፡ አኃዘኒ ፡
ፃዕረ ፡ ሞት ፡ ጎልያድ ፡ (ወውኂዝ ፡
ዐመጻ ፡ ሆከኒ) ፡ ሳኦል ፤ (ዐገተኒ ፡ ፃዕ
ረ ፡ ሲኦል) ፡ አቤሴሎም ፡ (ወበጽሐ
ኒ ፡ መሣግረ ፡ ሞት) ፡ ከራቱ ፡ ረፋይ
ን ፡ እንዱ ። እንድም ፡ አራቱንም ፡
መሥመር ፡ ላራቱ ፡ ረፋይን ፡ ስጥ ፡
እንድም ፡ የዳዊት ፡ ጠላቶች ፡ በየራ
ሳቸው ፡ ዐራት ፡ ሀራት ፡ ወገኖች ፡
ናቸው ፡ ብሎ ፡ እኅዘኒ ፡ በጎልያድ ፡
ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ (ወውኂዝ ፡ ዐመፃ) ፡
መኳንንቱ ፡ (ፃዕረ ፡ ሲኦል) ፡ ኀያላኑ ፡
(መሣግረ ፡ ሞት) ፡ ሠራዊቱ ፡ ፩ ፡ ሳ
ሙ ፡ ፲፯ ፡ ፩ – ፶፰ ። በሳኦል ፡ ጊዜ ፡ (ፃ
ዕረ ፡ ሞት) ፡ ንጉሡ ፡ (ውኂዝ ፡ ዐ
መፃ) ፡ መኳንንቱ ፡ (ፃዕረ ፡ ሲኦል) ፡
ኃያላኑ ፡ (መሣግረ ፡ ሞት) ፡ ሠራዊ
ቱ ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፳ ፡ ፩ – ፵፪ ። ፳፱ ፡ ፩ – ፳፫ ።
፳፮ ፡ ፩ – ፳፭ ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፲፱ ፡ ፱ – ፳ ። በአቤ
ሴሎም ፡ ጊዜ ፡ (ፃዕረ ፡ ሞት) ፡ ንጉ
ሡ ፡ ወውኂዝ ፡ ዐመፃ) ፡ መኳንንቱ ፡
(ፃዕረ ፡ ሲኦል) ፡ ኀያላኑ ፡ (መሣግረ ፡
ሞት) ፡ ሠራዊቱ ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፲፯ ፡ ፩ – ፳
፮ ፡ ፩ – ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፩ – ፴፯ ፡ ፲፯ ፡ ፩ – ፳፫ ።
በራቱ ፡ ረፋይን ፡ ጊዜ ፡ (ፃዕረ ፡ ሞት ፡
ንጉሡ ፡ (ወውኂዝ ፡ ዐመፃ) ፡ መኳን
ንቱ ፡ (ፃዕረ ፡ ሲኦል) ፡ ኀያላኑ ፡ (መሣ
ግረ ፡ ሞት) ፡ ሠራዊቱ ፡ አገኙኝ ።

፮ ፡ ሰበ ፡ ተመንደብኩ ፡ ጸዋዕክዎ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ።

መከራ ፡ ባገኘኝ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ ለመንሁ ።

ወጸራሕኩ ፡ ኀበ ፡ አምላኪየ ፡ ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፵፬ ።

ወደፈጣሪዬም ፡ መልሼ ፡ ለመንሁ ።
ዮሐ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰ ።

ወሰምዐኒ ፡ በጽርሐ ፡ መቅደሱ ፡ ቃልየ ።

ልመናዬን ፡ በሰማያዊት ፡ መቅደሱ ፡
ሁኖ ፡ ሰማኝ ፤ እንድም ፡ በምድራዊ
ት ፡ መቅደሱ ፡ ሁኜ ፡ የለመንሁትን ፡
ልመናዬን ፡ ሰማኝ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፱ – ፲፭ ።

ወጽራሕየኒ ፡ በእ ፡ ቅድሜሁ ፡ ውስተ ፡ እዘኒሁ ።

ልመናዬም ፡ ከፊቱ ፡ ደረሰ ፤ እንድ
ም ፡ ቆመ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወበእ ፡ ውስ
ተ ፡ እዘኒሁ ፡ ልመናዬም ፡ ከፊቱ ፡ ቆ
መ ፡ ከጆሮውም ፡ ገባ ፤ በግሥ ፡ ተና
ገረው ፡ በለሚል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡
ሐዴ ፡ ከፊቱ ፡ ይቆማል ፤ ምን ፡ ሆነ
ሃል ፡ ይለዋል ፤ መልከት ፡ ኑርኝ ፡ ይ
ለዋል ፤ ምነው ፡ ቀርበህ ፡ አትነግረኝ
ምን ፡ ይለዋል ፤ ቀርቦ ፡ ይነግረዋልና ።

፯ ፡ ርእደት ፡ ወአድለቅለቀት ፡ ምድር ፡ መዝ ፡ ፸
፯ ፡ ፲፰ ፡ ፵፯ ፡ ፱ ።

የሰአል ፡ ከተማ ፡ በኢሎፍላውያን ፡
ጦር ፡ የኢሎፍላውያን ፡ ከተማ ፡ በሳ
ኦል ፡ ጦር ፡ ጠፉች ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፲፱ ፡ ፶፯–
፶፰ ። እንድም ፡ የነአቤሴሎም ፡ ከተ
ማ ፡ በዳዊት ፡ ጦር ፡ ጠፉች ። ፪ ፡ ሳሙ ፡
፳ ፡ ፲፰ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ።

ወአንቀልቀሉ ፡ መሠረታተ ፡ አድባር ።

የመኳንንቱ ፡ መሠረት ፡ የሚሆኑ ፡
ነገሥታት ፡ ጠፉ ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፴፩ ፡ ፩–ሳ
ሙ ፡ ፴፩ ፡ ፩ – ፲፫ ።

ተሀውኩ ፡ እስመ ፡ ተምዖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢ
ሳ ፡ ፳፬ ፡ ፲፱ – ፳፩ ።

እግዚአብሔር ፡ ፈርዶባቸዋልና ፡ ጠፉ ፤

፰ ፡ ዐርገ ፡ ጢስ ፡ እመዓቱ ።

ከመዓቱ ፡ መገለጽ ፡ የተነሣ ፡ ጢስ ፡
ወጣ ፤ እለ ፡ ቋዱ ፡ ሲቃጠል ።

ወነደ ፡ እሳት ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ።

ከፊቱ ፡ እሳት ፡ ነደደ ፡ እለ ፤ ከደጎ
ራዩ ፡ ሲገናኝ ።

ሐተወ ፡ አፍሕም ፡ እምኔሁ ።

ፍሕሙ ፡ መረተ ፡ እለ ፡ መትቶ ፡ ሲ
ጥል ፡ በጌላቡሄ ፡ የተደረገውን ፡ መ
ናገር ፡ ነው ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፴፩ ፡ ፰–፲፫ ። እን

ድም ፡ (በርገ) ፡ ነቅዓ ፡ ሐልዮ ፡ (ወነ
ደ) ፡ ነቢብ ፡ (ሐተወ) ፡ ገቢር ።

፱ ፡ አጽንን ፡ ሰማያተ ፡ ወወረደ ።

ኀያላኑን ፡ ይዞ ፡ ረዳኝ ።

ወቆባር ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ።

ተሠውሮ ፡ ረዳኝ ።

፲ ፡ ተጽዕነ ፡ ላዕለ ፡ ኪሩቤል ፡ ወሠረረ ።

አጽንን ፡ ሰማያተ ፡ ያለውን ፡ ደገመ
ው ።

ወሠረረ ፡ በክንፈ ፡ ነፋስ ።

ፈጥኖ ፡ ረዳኝ ።

፲፩ ፡ ወረሰየ ፡ ጽልመተ ፡ ምሥዋሮ ።

ወቆባር ፡ ያለውን ፡ ደገመው ፤ ተሠ
ውሮ ፡ ረዳኝ ።

ወዓውደ ፡ ጽላሎቱ ፡ ኢሳ ፡ ፲፱ ፡ ፱ ፡ ፲፯ ።

ጠላቶቹ ፡ የሚጠፉበት ፡ መቅሠፍት ፡
በባሕርዩ ፡ አለ ፡ እንድም ፡ (አጽንን ፡
ሰማያተ ፡ ወወረደ) ፡ በኀያላኑ ፡ በኪ
ሩብ ፡ መዓቱ ፡ ወረደባቸው ፤ ወቆ
ባር ፡ ተፅዕኖ ፡ ወሠረረ ፡ እንዳለፈው ፡
(ወረሰየ ፡ ጽልመተ ፡ ምሥዋሮ) ፡ ጠ
ላቶቹ ፡ የሚጠፉበትን ፡ መቅሠፍት ፡
አጸና ። (ወዓውዱ ፡ ጽላሎቱ) ፡ በባ
ሕርዩ ፡ ብዙ ፡ የመቅሠፍት ፡ አምሳ
ል ፡ መርገፍ ፡ አለ ፡ ነገሥታቱ ፡ በሚ
ጠፉበት ፡ መኳንንቱ ፡ መኳንንቱ ፡
በሚጠፉበት ፡ ነገሥታቱ ፡ ጠፉ ።

እንድም ፡ (አጽንን) ፡ ልዑል ፡ ባሕ
ርዩን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ሰው ፡
ሆነ ። እንድም ፡ ቅዳሴ ፡ መላእክት ፡
ይበቃኛል ፡ አላለም ፡ የሰውንም ፡ ም
ስጋና ፡ ተቀበለ ። እንድም ፡ የመላእ
ትን ፡ ባሕርይ ፡ ባሕርይ ፡ አላደረገም ፡
እንጂ ። ኢነሥአ ፡ ለዘነሥአ ፡ እመላ
እክት ፡ እንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ እምዘርአ ፡
አብርሃም ፡ እንዲል ፡ ዕብ ፡ ፲፱ ፡ ፲፮ ፡
እንድም ፡ እስከ ፡ ምጽንዓት ፡ ሣልስ ፡
ሚካኤል ፡ ተለውክ ፡ እንዲል ።

እስከ ፡ ሦስተኛው ፡ ሰማይ ፡ ድረስ ፡
ሸኙኝ ፡ በአምሳለ ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡
እገለጽላችኋለሁ ፡ ብሏቸዋልና ፡ (ሊቀ ፡
መላእክት ፡ ሚካኤልን ፡ አስከትሎ ፡
መጣ ፡ (ወቆባር ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ) ፡
በሐዋርያት ፡ በሰብአ ፡ አርድእት ፡
በመስቀል ፡ መርገመ ፡ ሥጋ ፡ መርገመ ፡
ነፍስ ፡ ጠፋ ። (ተጽዕነ ፡ ላዕለ ፡ ኪሩ
ቤል ፡ ወሠረረ) ፡ ንባብ ፡ ሳይሻ ፡ ሥጋ ፡
በተዋህዶ ፡ ዓረገ ። (ወሰረረ ፡ በክንፈ ፡
ነፋስ) ፡ እንድ ፡ ወገን ፡ (ወረሰየ ፡ ጽል
መተ ፡ ምሥዋሮ) ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፡ ባሕ
ርዩን ፡ የማይመረመር ፡ አደረገ ። እ
ንዘ ፡ ሰብእ ፡ መኑ ፡ ይክል ፡ ያእምሮ ፡
እንዲል ። (ወዓውዱ ፡ ጽላሎቱ) ፡
ደኅራዊ ፡ ልደቱን ፡ ለቀዳማዊ ፡ ልደቱ ፡
አምሳል ፡ መርገፍ ፡ አደረገ ። ልደት ፡
ቀዳማዊ ፡ ተዓውቀ ፡ በደኃራዊ ፡ ል
ደት ፡ እንዲል ።

እንድም ፡ (አጽንን) ፡ ከለበት ፡ ዓለም ፡
ወደ ፡ ዓለበት ፡ ዓለም ፡ መጣ ። በግሥ ፡



ተናገረው ። ዛፍ ፡ ነፋስ ፡ በገሠፀው ፡
ጊዜ ፡ ከሥሩ ፡ ሳይነቀል ፡ ጫፉ ፡ ም
ድር ፡ ነክቶ ፡ እንዲነሣ ። ሰውም ፡ ከቆ
መበት ፡ እግሩ ፡ ሳይነቀል ፡ የወደቀ ፡
ዕቃ ፡ ይዞ ፡ እንዲነሣ ፡ እሱም ፡ ከባሕ
ርይ ፡ አባቱ ፡ ከአብ ፡ ከባሕርይ ፡ ሕይ
ወቱ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሳይለይ ፡
ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡
የሰውነት ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ኑሯልና ።
(ወቆባር) ፡ አይለወጥም ፡ (ሠረረ ፡ ወተ
ፅዕነ ፡ ይላል) ፡ ሠረረ ፡ በብርሃን ፡ በሥ
ልጣን ፡ በቅዳሴ ፡ ዓረገ ። (ወተፅዕነ) ፡
በየማነ ፡ አብ ፡ በዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ ተቀ
መጠ ፡ (ወሠረረ ፡ በክንፈ ፡ ነፋስ) ፡
በሐዋርያት ፡ ቃል ፡ ተሰበከ ። ወተለ
ዓለ ፡ በሠረገላተ ፡ መንፈስ ፡ እንዲል ።
(ወረሰየ) ፡ በሰውነቱ ፡ የሠራውን ፡
ሥራ ፡ የማይመረመር ፡ አደረገ ። (ወዓ
ውዱ) ፡ ጌትነቱ ፡ ባሉቱ ፡ ማዕገዝን ፡
ምሉዕ ፡ ነው ። ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሐው
ርተ ፡ መለኮቱ ፡ እንዲል ፡ መዝ ፡ ፻፲፱ ፡ ፶፱ ፡

፲፱ ፡ ጸልሙ ፡ ማያት ፡ በውስተ ፡ ደመናት ።

ውኆች ፡ በደመናት ፡ ጠቆሩ ፡ የወኃ ፡
የደመና ፡ ኅብራቸው ፡ ነጭ ፡ ነው ።
በደመና ፡ አይበት ፡ ተቋጥሮ ፡ በነፋስ ፡
ወደልጋዝ ፡ ተጭኖ ፡ ከውቅያኖስ ፡
ሲመጣ ፡ ጠቍሮ ፡ ይታያልና ። ወእግ
ዚፈ ፡ ደመናት ፡ በራእየ ፡ ነፋሳት ።
እስመ ፡ ነፋስ ፡ ጸሊም ፡ በእርእያሁ ፡
እንዲል ።

ወእምብርሃን ፡ ገጹ ፡ ኃለፉ ፡ ደመናት ።

ብርሃን ፡ ረድኤቱን ፡ ለሰው ፡ ከመስ
ጠቱ ፡ የተነሣ ፡ ደመናት ፡ ዝናም ፡
እያዘነሙ ፡ ሔዱ ።

ቅድሜሁ ፡ በረድ ፡ ወአፍሐመ ፡ እሳት ።

ጽኑ ፡ መቅሠፍት ፡ በባሕርዩ ፡ አለ ።
እንድም ፡ (ጸልሙ ፡ ማያት ፡ በውስተ ፡
ደመናት) ፡ አሕዛብ ፡ በእስራኤል ፡
ጦር ፡ ጠፉ ። (ወእምብርሃን ፡ ገጹ ፡
ኃለፉ ፡ ደመናት) ፡ ብርሃን ፡ ረድኤቱን ፡
ለእስራኤል ፡ ከመስጠቱ ፡ የተነሣ ፡
እስራኤል ፡ አሕዛብን ፡ ድል ፡ አድር
ገው ፡ ሔዱ ። (ቅድሜሁ ፡ በረድ ፡
ወአፍሐመ ፡ እሳት) ፡ እሊህ ፡ የሚጠ
ፉበት ፡ መቅሠፍት ፡ በባሕርዩ ፡ አለ ።
እንድም ፡ (ጸልሙ ፡ ማያት) ፡ እስራ
ኤል ፡ በአሕዛብ ፡ ጦር ፡ ጠፉ ። (ወእ
ምብርሃን ፡ ገጹ) ፡ ብርሃን ፡ ረድኤቱን ፡
ለእስራኤል ፡ ከመንሣቱ ፡ የተነሣ ፡
አሕዛብ ፡ እስራኤልን ፡ ድል ፡ አድር
ገው ፡ ሔዱ ። (ቅድሜሁ ፡ በረድ) ፡
አይለወጥም ።

እንድም ፡ (ጸልሙ ፡ ማያት) ፡ አይ
ሁድ ፡ መናፍቃን ፡ አጋንንት ፡ በሐ
ዋርያት ፡ ጠፉ ። (ወእምብርሃን ፡ ገጹ) ፡
በሐዋርያት ፡ ልጅነትን ፡ ትምርትን ፡
ሥልጣንን ፡ ከማሳደሩ ፡ የተነሣ ፡ ሐ
ዋርያት ፡ እያስተማሩ ፡ ሔዱ ። (ቅድ
ሜሁ ፡ በረድ) ፡ ንዑ ፡ ሑሩ ፡ ብሎ ፡
ይናገራል ።

2014 04 17

፲፫ ፡ አንጐድጐደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰማያት ።

አንጐደጐደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑ
ል ። ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የዳዊት ፡
ጠላቶች ፡ ይጥፉ ፡ ብሎ ፡ በሰማይ ፡
ድምፅ ፡ አሰማ ። ወወሀበ ፡ ቃሎ ።
ረድኤቱንም ፡ ለዳዊት ፡ ሰጠ ። እን
ድም ፡ በቁሙ ፡ (አንጐድጐደ) ፡ ድ
ምፅ ፡ አሰማ ።(ወወሀበ ፡ ቃሎ) ፡ ረድ
ኤቱንም ፡ አደረገ ። በቀላውትምናስ ፡
ድምፅ ፡ አሰማልሃለሁ ። ሒደህ ፡ ግ
ጠማቸው ፡ ድል ፡ ታደርጋቸዋለህ ፡
አለው ፡ ሒዶ ፡ ገጠመ ። የነጐድጓድ ፡
ድምፅ ፡ አሰምቶለት ፡ ድል ፡ አድር
ጓል ።

አንድም ፡ (አንጐድጐደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ልዑል ፡ በሰማያት) ፡ ልዑል ፡
እግዚአብሔር ፡ በነቢያት ፡ አድሮ ፡
ልጄ ፡ ይወርዳል ፡ ይወለዳል ፡ የሚል ፡
ድምፅ ፡ አሰማ ። (ወወሀበ ፡ ቃሎ) ፡
ልጁን ፡ ለኩነተ ፡ ሥጋ ፡ ሰጠ ። እን
ድም ፡ አካላዊ ፡ ቃልም ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡
ወንጌልን ፡ አስተማረ ። (አንድም ፡
አንጐድጐደ) ፡ እግዚአብሔር ፡ ወ
ልድ ፡ በነቢያት ፡ አድሮ ፡ እወርዳ
ለሁ ፡ እወለዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ትንቢት ፡
አናገረ ፡ (ወወሀበ ፡ ቃሎ) ፡ ወልድም ፡
ወንጌልን ፡ አስተማረ ። ቃሎ ፡ ብሎ ፡
ዝርዝሩን ፡ ለወልድ ፡ ሰጠ ። ምንም ፡
የሦስቱ ፡ ሕግ ፡ ብትሆን ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡
የሠራት ፡ መደበኛዋ ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ ወልድ ፡ ነውና ።

፲፬ ፡ ፈነወ ፡ አሕጻሁ ፡ ወዘረዎሙ ።

አሕፃ ፡ መዓቱን ፡ አመጣ ። ዘረዎሙ ፡
አሕፃውን ፡ በተናቸው ፡ ዘረወ ፡ በሙ ፡
በአሕፃ ፡ ሰዎችን ፡ በተነባቸው ፡ አን
ድም ፡ እነኢዮአብን ፡ አስነሣ ፡ ዘረ
ዎሙ ፡ በተናቸው ፡ ዘረወ ፡ በሙ ፡
አሕዛብን ፡ በተነባቸው ።

አብዝኀ ፡ መባርቅቲሁ ፡ ወሆኮሙ ።

መዓቱን ፡ አብዝቶ ፡ አስነሣ ፡ ሆኮ
ሙ ፡ አወከቻቸው ፡ ሆከ ፡ በሙ ፡ አወ
ከባቸው ፡ አብረቀ ፡ መብረቆ ፡ ወአ
ደንገፆሙ ፡ ይላል ፡ አብነት ፡ አንድ
ም ፡ እነኢዮአብን ፡ አብዝቶ ፡ አስነ
ሣቸው ፡ ሆከሙ ፡ አወከቻቸው ፡ ሆከ ፡
በሙ ፡ አወከባቸው ።

አንድም ፡ (ፈነወ ፡ አሕፃሁ) ፡ ሐዋር
ያትን ፡ በመምርነት ፡ ላከ ፡ (ዘረዎሙ)
ፈነዎሙ ፡ በበ፪ ፡ እንዲል ። ሁለት ፡
ሁለት ፡ አድርጎ ፡ ሰደዳቸው ፡ ማር ፡
፮ ፡ ፯ ። ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፩ ። (ዘረወ ፡ በሙ) ፡
አይሁድን ፡ መናፍቃንን ፡ አጋንንት
ን ፡ በተነባቸው ፡ (አብዝኀ ፡ መባር
ቅቲሁ) ፡ ሰብአ ፡ አርድእትን ፡ አብ
ዝቶ ፡ አስነሣቸው ፡ ሆከሙ ፡ አወከ
ቻቸው ፡ ሆከ ፡ በሙ ፡ አይሁድን ፡ መና
ፍቃንን ፡ አጋንንትን ፡ አወከባቸው ።

፲፭ ፡ ወአስተርአዩ ፡ አንቅዕተ ፡ ማያት ።

የውኆች ፡ ምንጮች ፡ በስነ ፡ ፍጥ
ረት ፡ ተገለጹ ።



ወተከሥቱ ፡ መሠረታተ ፡ ዓለም ።

የዓለም ፡ መሠረቶች ፡ የሚሆኑ ፡ ተራ
ራዎች ፡ ኮረብቶች ፡ ተገለጹ ።

እምተግሣፅከ ፡ እግዚኦ ።

ለይትጋባእ ፡ ማይ ፡ ውስተ ፡ ምዕላ
ዲሁ ፡ ብለህ ፡ ከማዘዝህ ፡ የተነሣ ፡
ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፺—፰ ።

ወእምእስትንፋሰ ፡ መንፈሰ ፡ መዓትከ ።

መዓትህን ፡ የምትፈጽምበት ፡ ረቂቅ ፡
ሥልጣንህን ፡ ከመግለጽህ ፡ የተነሣ ።
ከዚህ ፡ እስከ ፡ ብሩህ ፡ ሰማይ ፡ የነበ
ረው ፡ ውሀ ፡ ለይትጋባእ ፡ ማይ ፡ ው
ስተ ፡ ምዕላዲሁ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ከሦስት ፡
ተከፍሏል ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምንጭ ፡
ተራራው ፡ ኮረብታው ፡ ተገልጿልና ።
ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፺—፺።

አንድም ፡ (ወአስተርአዩ ፡ አንቅዕተ ፡
ማያት) ፡ በጦር ፡ ጥላ ፡ ተከበው ፡ ይ
ኖሩ ፡ የነበሩ ፡ መኳንንቱ ። ለምት ፡ ተ
ገለጡ ፡ (ወተከሥቱ ፡ መሠረታተ ፡ ዓ
ለም) ። የመኳንንቱ ፡ የሰራዊቱ ፡ መሠ
ረት ፡ የሚሆኑ ፡ ነገሥታቱ ፡ በጊላቡሄ ፡
ግልድው ፡ ግልድው ፡ ብለው ፡ ታዩ ።
፩ ፡ ሳሙ ፡ ፴፩ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ። (እምተግሣፅከ ፡
እግዚኦ) ፡ ይጥፉ ፡ ብለህ ፡ ከማዘዝህ ፡
የተነሣ ። (ወእምእስትንፋሰ ፡ መንፈሰ ፡
መዓትከ) ፡ መዓትህን ፡ የምትፈጽም
በት ፡ ረቂቅ ፡ ሥልጣንህን ፡ ከመግለ
ጽህ ፡ የተነሣ ።

አንድም ፡ (ወአስተርአዩ) ፡ በጦር ፡ ጥላ ፡
ተከበው ፡ የሚኖሩ ፡ መኳንንቱ ፡ በ
ሞት ፡ ተገለጹ ። (ወተከሥቱ) ፡ የዓለም ፡
መሠረት ፡ የሚሆኑ ፡ ነገሥታቱ ፡ በ
ሞት ፡ ተገለጹ ። (እምተግሣፅከ) ፡ ይ
ጥፉ ፡ ብለህ ፡ ከማዘዝህ ፡ የተነሣ ። (ወ
እምእስትንፋሰ) ፡ እንዳለፈው ።

አንድም ፡ (ወአስተርአዩ) ፡ የልጅነት ፡
የትምህርት ፡ መገኛ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰብአ ፡
አርድእት ፡ ኢጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ በመም
ርነት ፡ ተገለጹ ። (ወተከሥቱ) ፡ የዓ
ለም ፡ መሠረት ፡ የሚሆኑ ፡ ሐዋርያት ፡
አራቱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በመምርነት ፡
ተገለጡ ። (እምተግሣፅከ) ፡ ሑሩ ፡ ወ
መሐሩ ፡ ብለህ ፡ ከማዘዝህ ፡ የተነሣ ፡
(ወእምእስትንፋሰ ፡ መንፈሰ ፡ መዓ
ትከ) ፡ መዓትህን ፡ የምትፈጽምበት ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በሐዋርያት ፡ በሰ
ብአ ፡ አርድእት ፡ በሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡
በኢጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ከማሳደርህ ፡ የተ
ነሣ ።

መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መዓት ፡ አለው ፡
ላመነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ላላመነ ፡ መዓት ፡
ነውና ።

፲፮ ፡ ፈነወ ፡ እምአርያም ፡ ወነሥአኒ ።

እዴሁ ፡ ያለበት ፡ ነው ። ረድኤቱን ፡
አንድም ፡ እጁን ፡ ልኮ ፡ አዳነኝ ።

ወተመጠወኒ ፡ እማይ ፡ ብዙኅ ።

ከወሀው ፡ አወጣኝ ። ውሀ ፡ በበላው ፡
ግሥ ፡ ተናገረው ፡ እንጂ ። ከጦሩ ፡ አዳ
ነኝ ፡ ሲል ፡ ነው ። አንድም ። (ወፈነወ) ፡
ልጁን ፡ ሰዶ ፡ አዳነኝ ። (ወተመጠወኒ) ፡
ከአጋንንት ፡ ከኃጣውእ ፡ ከፍትወታት ፡
እኩያት ፡ አዳነኝ ። መዝ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱ ።

፲፯፡ ወአድኀነኒ፡ እምፀርየ፡ ጽኑዓን ።

ጽኑዓን፡ከሚሆኑ፡ከጠላቶቼ፡አዳነኝ።

ወእምጸላእትየ፡ እለ፡ ይጌይሱኒ ።

(እስፈች)፡ ወደፊት ። ይበረቱብኛ ልና። ጽኑዓን፡ ከሚሆኑ፡ ጠላቶቼ፡ አዳነኝ። እለ፡ ይጌይሱኒ፡ ያለ፡ እን ደሆን፡ ከሚበረቱብኝ፡ ጠላቶቼ፡ አ ዳነኝ።

፲፰፡ ወበጽሑኒ፡ በዕለተ፡ ምንዳቤየ ።

በመከራዬ፡ጊዜ፡ደረሱብኝ።በሳኦል፡ ጊዜ፡ ያሉ፡ እንደሆን፡ ከገሬ፡ ወጥቼ፡ ከዘመዴ፡ ተለይቼ፡ መከራ፡ በምቀበ ልበት፡ ጊዜ። ፩፡ ሳሙ፡ ፳፫፡ ፲፱–፳፮ ። ፳፱-፩-፳፫። በአቤሴሎም፡ ጊዜ፡ ያሉ፡ እንደሆን፡ የጕልማሳ፡ ሚስት፡ነስቼ፡ ጕልማሳ፡ አስገድዬ፡ ፍዳ፡ በምቀበ ልበት፡ ጊዜ። ፪፡ ሳሙ፡ ፲፩፡ ፩-፲፯። ፲፭፡ ፲፫-፲፰። ከራቱ፡ ረፋይን፡ በንዱ፡ ጊዜ፡ ያሉ፡ እንደሆን፡ መድኅኒት፡ ጠጥቼ፡ ጦር፡ ስሠራ፡ ውዬ፡ ደክሞኝ፡ ሳለ። በጕልያድ፡ ጊዜ፡ ያሉ፡ እንደሆን፡ ያልተመቸ፡ አንድም፡ የተመቸ፡ ይ መክቱትን፡ ይወረወሩትን፡ ሳላውቅ፡ ፩፡ ሳሙ፡ ፲፯፡ ፳፯-፶፱። አንድም፡ ምክረ፡ አጋንንትን፡ ሰምቼ፡ ዕፀ፡ በለስን፡ በ ልቼ፡ ከፈጣሪዬ፡ ተጣልቼ፡ ፍዳ፡ በም ቀበልበት፡ ቀን፡ ደረሱብኝ፡ ይላል፡ አዳም። ዘፍ፡ ፪፡ ፲፯-፲፯፡ ፫፡ ፩-፳፱።

ወኮነኒ፡ እግዚአብሔር፡ ምስካይየ ።

እግዚአብሔር፡ ግን፡ አምባ፡ መጠ ጊያ፡ ሆነኝ።

፲፱፡ ወአውፅአኒ፡ ውስተ፡ መርህብ ።

ወደ፡ ወደብ፡አወጣኝ፡ወሀ፡በበላው፡ ግሥ፡ ተናገረው። አንድም፡ ከመከ ራው፡ አውጥቶ፡ በተድላ፡ በደስታ፡ አኖረኝ።

ወአድኀነኒ፡ እስመ፡ ይፈቅደኒ ።

እኔን፡ማዳን፡ፈቃዱ፡ነውና፡አንድም፡ በኔ፡ አድሮ፡ እስራኤልን፡ ማዳን፡ ፈ ቃዱ፡ ነውና፡ አዳነኝ።

፳፡ የዓሥየኒ፡ እግዚአብሔር፡ በከመ፡ ጽድ ቅየ ። ቍ፡ ፳፱ ።

እግዚአብሔር፡እንደ፡እውነተኛነቴ፡ ዋጋዬን፡ ይሰጠኛል።

ወይፈድየኒ፡ በከመ፡ ንጽሐ፡ እደውየ ።

በእጄ፡ መግደል፡ በቃሌ፡ መበደል፡ በልቡናዬ፡ ቂም፡ በቀል፡ እንዳለመ ኖሩ፡ መጠን፡ ዋጋዬን፡ ይሰጠኛል።

፳፩፡ እስመ፡ ዓቀብኩ፡ ፍናዊሁ፡ ለእግዚአብ ሔር ።

እግዚአብሔር፡ የሠራቸውን፡ ዘጠ ኙን፡ ሕገጋት፡ ጠብቄአለሁና።

ወኢአበስኩ፡ ለአምላኪየ ።

ይህ፡ ለ፡ ትግሬ፡ ለ፡ ነው። ኢአበስ ክዎ፡ ሲል፡ ነው፡ ኢታምልክንም፡ ጠብቄአለሁና።

፳፪፡ እስመ፡ ኵሉ፡ ኵነኔሁ፡ ቅድሜየ፡ ውእቱ፡ በኵሉ፡ ጊዜ ።

ወነበበ፡ ወነበበ፡ ያለው፡ ቃሉ፡ ሁሉ፡ ሁል፡ ጊዜ፡ ከፊቴ፡ ነው፡ ማለት፡ እ ጠብቀዋለሁና።



ወጽድቆኒ፡ ኢርሕቀ፡ እምኔየ ።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከኔ፡አልራቀም።

፳፫፡ ወእከውን፡ ንጹሐ፡ ምስሌሁ ።

ከሱ፡ ጋራ፡ ለመኖር፡ እንደሱ፡ ንጹሕ፡ እሆናለሁ። ይህማ፡ እንደምን፡ ይቻ ላል። የሰው፡ ተጠብብቆ፡ ተከላከሎ፡ ነው። የሱማ፡ የባሕርዩ፡ አይደለምን፡ ቢሉ፡ ንጹሐ፡ ባሕርይ፡ እሱ፡ ንጹሕ፡ ቢያደርገኝ፡ ንጹሕ፡ አድርጎ፡ ቢፈጥ ረኝ፡ ሲል፡ ነው።

ወእትዓቀብ፡ እምኀጢአትየ ።

ከኃጢአቴ፡ንጹሕ፡እሆናለሁ፡ማለት፡ ጥቃቅኑን፡ ደጋጉን፡ ኃጢአት፡ ከመ ሥራት፡ እከለከላለሁ። በናቱ፡ ወያቀ ድም፡ ተዓቅቦ፡እምኃጢአቱ፡ይላል። ፪፡ ሳሙ፡ ፳፪፡ ፳፬ ።

፳፬፡ የዐሥየኒ፡እግዚአብሔር፡በከመ፡ጽድቅየ።

ወይፈድየኒ፡ በከመ፡ ንጽሐ፡ እደውየ ።

በቅድመ፡ አዕይንቲሁ ።

እንዳለፈው፡ ነው። በቅድመ፡ አዕይ ንቲሁ፡ ለማለት፡ ደግሞታል፡ በግሥ፡ ተናገረው። ባለሟል፡ የሆነ፡ እንደ ሆነ፡ ከፊቱ፡ አብልቶ፡ አጠጥቶ፡ ወር ቁን፡ በሚዛን፡ እህሉን፡ በላዳን፡ ሰፍሮ፡ ይሰጠዋል። ተራ፡ ሰው፡ የሆነ፡ እንደ ሆነ፡ እንደ፡ ስሜን፡ እንደ፡ በጌም ድር፡ ከለ፡ አገር፡ ሒደህ፡ አምጣ፡ ብሎ፡ ይዳርገዋል። ቢያገኝ፡ ይዞ፡ ይመ ጣል፡ ባያገኝ፡ ደክሞ፡ ይቀራልና፡ (ይመላለሳልና) ። ኢሳ፡ ፶፱፡ ፱-፩ ።

፳፭፡ ምስለ፡ ጻድቅ፡ ትጸድቅ ።

ከጻድቅ፡ ሰው፡ ጋራ፡ ጻድቅ፡ ትሆና ለህ፡ ማለት፡ ዓስበ፡ ጽድቁን፡ ትሰጠ ዋለህ።

ወምስለ፡ ብእሲ፡ ንጹሕ፡ ንጹሐ፡ ትከውን ።

ከንጹሕ፡ ሰው፡ ጋራ፡ ንጹሕ፡ ትሆና ለህ፡ ማለት፡ የንጽሕናውን፡ ዋጋ፡ ዓስበ፡ ንጽሑን፡ ትሰጠዋለህ።

፳፮፡ ወምስለ፡ ኅሩይ፡ ኅሩየ፡ ትከውን ።

ከደግ፡ ሰው፡ ጋራ፡ ደግ፡ ትሆናለህ፡ ማለት፡ የደግነቱን፡ ዋጋ፡ ትሰጠዋ ለህ። አንድም፡ (ምስለ፡ ጻድቅ፡ ትጸ ድቅ)፡ ንጽሐ፡ ሥጋን፡ ከያዘ፡ ሰው፡ ጋራ፡ ንጹሕ፡ ትሆናለህ፡ ማለት፡ የን ጽሐ፡ ሥጋውን፡ ዋጋ፡ ትሰጠዋለህ። (ወምስለ፡ ብእሲ፡ ንጹሕ፡ ንጹሐ፡ ትከውን)፡ ንጽሐ፡ነፍስን፡ ከያዘ፡ ጋራ፡ ንጹሕ፡ ትሆናለህ፡ ማለት፡ የንጽሐ፡ ነፍሱን፡ ዋጋ፡ ትሰጠዋለህ። (ወም ስለ፡ ኅሩይ፡ ኅሩየ፡ ትከውን)፡ ንጽሐ፡ ልቡና፡ ከያዘ፡ ጋራ፡ ንጹሕ፡ ትሆና ለህ፡ ማለት፡ የንጽሐ፡ ልቡናውን፡ ዋጋ፡ ትሰጠዋለህ።

አንድም፡ (ምስለ፡ ጻድቅ)፡ ከወጣኒ፡ ጋራ፡ ወጣኒ፡ ትሆናለህ፡ ማለት፡ የወ ጣኒነቱን፡ ዋጋ፡ ትሰጠዋለህ። (ወም ስለ፡ ብእሲ)፡ ከማእከላዊ፡ ጋራ፡ ማእ ከላዊ፡ ትሆናለህ፡ የማእከላዊነቱን፡ ዋጋ፡ ትሰጠዋለህ። (ወምስለ፡ ኅሩይ)፡ ከፍጹም፡ ጋራ፡ ፍጹም፡ ትሆናለህ፡ ማለት፡ የፍጹምነቱን፡ ዋጋ፡ ትሰጠ

2014 04 17

ዋለሀ። አንድም፡ (ምስለ፡ ጻድቅ)፡
ባለ፡ ሠላሳ። (ምስለ፡ ንጹሕ)፡ ባለ፡
ስድሳ፡ (ምስለ፡ ኅሩይ)፡ ባለ፡ መቶ፡
ነው፡ ከዚህ፡ ይገባል። ሁሉም፡ በግ
ዕዝ፡ ርትዕት፡ አንድ፡ ናቸውና፤ አንድ፡
አርዕስት።

ወምስለ፡ ጠዋይ፡ ትጠዊ።

ከጠማማው፡ ሰው፡ ጋራ፡ ጠማማ፡
ትሆናለህ፡ ማለት፡ የጠማማነቱን፡
ዋጋ፡ ትሰጠዋለህ፡ አንትሙ፡ ተሐ
ውሩ፡ ግድመ፡ ግድመ፡ በኃጢአት፡
ወአነ፡ እሐውር፡ ግድመ፡ ግድመ፡
በመዓት፡ እንዲል። ሁለት፡ አርእስት፤
ለሁለቱም፡ ያመጣል።

፳፯፡ እስመ፡ አንተ፡ እግዚኦ፡ ታድኅን፡ ለሕ
ዝብ፡ ትሑት። ኢሳ፡ ፪፡ ፲፩።

ትሑት፡ ዳዊትን፡ አንድም፡ ማናቸ
ውንም፡ ትሑት፡ ሕዝብ፡ ታድነዋለ
ህና፡ ምስለ፡ ጻድቅ። ምስለ፡ ንጹሕ።
ምስለ፡ ኅሩይ፡ ላለው።

ወታኀሥሮሙ፡ ለአዕይንተ፡ ዕቡያን።

ለዕቡያን፡ አዕይንት፡ ሲል፡ ነው፡ ባይ
ናቸው፡ ብትና፡ ዝቅ፡ አድርገው፡ የሚ
ያዩትን፡ ታዋርዳቸዋለህና። አንድም፡
ትዕቢተኞችን፡ ታዋርዳቸዋለህና፡
ወምስለ፡ ጠዋይ፡ ትጠዊ፡ ላለው፡
ኢሳ፡ ፪፡ ፲፩።

፳፰፡ እስመ፡ አንተ፡ ታበርህ፡ ማኅቶትየ፡ እግዚኦ።

አቤቱ፡ አንተ፡ መንግሥቴን፡ ታበራ
ልኛለህና። አንድም፡ መንግሥቴን፡
አጽንተህ፡ ደስ፡ ታሰኘኛለህና፡ አብ
ርሂ፡ አብርሂ፡ ኢየሩሳሌም፡ እንዲል።
ኢሳ፡ ፷፩።

አምላኪየ፡ ያበርህ፡ ጽልመትየ።

ታርኅቅ፡ ሲል፡ ነው። መከራዬን፡
ታርቅልኛለህ። አንድም፡ መከራዬን፡
አርቀህ፡ ደስ፡ ታሰኘኛለህ። አብርሂ፡
አብርሂ፡ ኢየሩሳሌም፡ እንዲል። ኢሳ፡
፷፡ ፩።

፳፱፡ እስመ፡ ብከ፡ እድኅን፡ እመንሱት።

ባንተ፡ አምኜ፡ ከጥፋት፡ እድናለሁ።

ወበአምላኪየ፡ እትዓደዎ፡ ለዓረፍት።

ባንተ፡ በፈጣሪዬ፡ አምኜ፡ እንደ፡ ግድ
ግዳ፡ የጸና፡ ዓረፍተ፡ እንኩስን፡ መር፡
ብዬ፡ ጥሼው፡ እወጣለሁ። አንድም፡
ጦሩን፡ ጥሼው፡ እወጣለሁ።

ዳዊት፡ ከሳኦል፡ ሸሽቶ፡ ተነሥቶ፡ ወደ፡
እንኩስ፡ ሀገር፡ ሔደ። ያገሩ፡ ሕዝብ።
አሁን፡ ዳዊት፡ ለኛ፡ ሊያግዝ፡ ነው፡
የመጣው፡ የጦሩን፡ ማነስ፡ መብዛ
ቱን፡ የምሽጉን፡ መጽናት፡ አለመጽ
ናቱን፡ ሊሰልል፡ ነው፡ እንጂ፡ እንግ
ደለው፡ ተባብለዋል። ሰናፊሉን፡ ከፍ፡
ከፍ፡ አድርጎ፡ እብድ፡ መስሎ፡ ከበሮ
ውን፡ እየመታ፡ ጦሩን፡ ጥሶት፡ ሔዷ
ልና፤ ፩ሳሙ፡ ፳፩፡ ፲፪-፲፭። አንድም፡
ፈቃደ፡ ሥጋ፡ ብሎ፡ መጽሐፈ፡ መነ
ኮሳት፡ ወስዶታል፡ ብሎ፡ እንዳጥር፡
እንደ፡ ቅጥር፡ የጸና፡ ፈቃደ፡ ሥጋን፡
ጥሼው፡ እሔዳለሁ።



፴፡ አምላኪየሰ፡ ንጹሕ፡ ፍኖቱ።

የፈጣሪዬ፡ መንገዱ፡ ፍጹም፡ ነው፡
የሚሔድበት፡ የለም፡ እንጂ። አን
ድም፡ ሕጉ፡ ንጹሕ፡ ነው፡ የሚሠ
ራው፡ የለም፡ እንጂ።

ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ርሱን።

ትእዛዘ፡ እግዚአብሔር፡ የጋለ፡ ነው፡
የጋለ፡ እንዲያቃጥል። ሕገ፡ እግዚአ
ብሔርም፡ ቢጠብቁት፡ ይጠብቃል፡
ባይጠብቁት፡ ያጠፉልና። አንድም፡
የጋለ፡ የፈላ፡ ነው፡ ያዙኝ፡ ያዙኝ፡
ይላል። ሰማዕታትን፡ አነሣሥቶ፡ ወደ፡
ደም፡ ጻድቃንን፡ አናድዶ፡ ወደ፡
ገዳም፡ ይወስዳል። ምሳ፡ ፳፱፡ ፳፱።

ወምግእመናሙ፡ ውእቱ፡ ለኵሎሙ፡ እለ፡ ይት
ዌከሉ፡ ቦቱ።

ላመኑበት፡ ሁሉ፡ የታመነ፡ ወዳጃ
ቸው፡ የታመነ፡ ረዳታቸው፡ ነው።

፴፩፡ መኑ፡ ውእቱ፡ አምላክ፡ ዘእንበለ፡ እግ
ዚአብሔር።

ከእግዚአብሔር፡ በቀር፡ እግዚአብ
ሔር፡ ነው፡ እንጂ፡ ያለ፡ እግዚአብ
ሔር፡ ሌላ፡ ፈጣሪ፡ ማን፡ ነው።

ወመኑ፡ እግዚአብሔር፡ ዘእንበለ፡ አምላክነ።

ከፈጣሪያችንስ፡ በቀር፡ ፈጣሪያችን፡
ነው፡ እንጂ፡ ከፈጣሪያችን፡ ሌላ፡
እግዚአብሔር፡ ማን፡ ነው።

፴፪፡ እግዚአብሔር፡ ዘያቀንተኒ፡ ኃይለ።

ኃይልን፡ እንደ፡ ዝናር፡ የሚያስታ
ጥቀኝ። እግዚአብሔር። ነው።

ወረሰየ፡ ንጹሐ፡ ፍኖትየ።

ንጽሕተ፡ ሲል፡ ነው። ጕዳናዬን፡
ጠላት፡ የሌለበት፡ የሚያደርጋት፡
እሱ፡ ነው፡ አንድም፡ በንጹሕ፡ ግብር፡
ጸንቼ፡ እንድኖር፡ የሚያደርገኝ፡ እሱ፡
ነው።

፴፫፡ ዘያረትዖን፡ ከመ፡ ኀየል፡ ለእገሪየ፡ ኢሳ፡
፴፭፡ ፮።

እግሮቼን፡ እንደዋልያ፡ የሚያቀና
ቸው፡ እሱ፡ ነው፡ ማለት፡ ቢሮጡ፡
ቢገሠግሡ፡ እንዳይደክሙ፡ የሚያ
ደርጋቸው፡ እሱ፡ ነው። ይህ፡ ዋልያ፡
እግረ፡ ቅን፡ ነው፡ ተራራ፡ አይመል
ሰውም፡ እንደ፡ ሐይቅ፡ እንደ፡ ጣና፡
ካለ፡ ቦታ፡ ወጥቶ፡ ከላይ፡ መርግ፡
ከታች፡ ቀስት፡ እንዳያገኘው፡ ሁኖ፡
ይቀመጣል፡ ባዳኙ፡ ያለምጥበታል፡
ለነፍጥ፡ ለቀስት፡ አይመችም።

ወያቀውመኒ፡ ውስተ፡ መልዕልት።

ጠላቶቼን፡ አጥፍቶ፡ እኔን፡ አድኖ፡
ከሁሉ፡ በላይ፡ የሚያደርገኝ፡ እሱ፡
ነው።

፴፬፡ ዘይሜህሮን፡ ለእደውየ፡ ቀትለ።

ለእጆቼ፡ ሰልፍን፡ አንድም፡ ግራ፡
ቀኝ፡ ማግተብን፡ የሚያስተምራቸው፡
እሱ፡ ነው። መዝ፡ ፻፵፫፡ ፩።

ወረሰየ፡ ቀስተ፡ ብርት፡ ለመዝራዕትየ።

እጆቼን፡ እንደ፡ ብረት፡ ደጋን፡ የሚ
ያደርጋቸው፡ ማለት፡ ቢወጉ፡ ቢመ
ክቱ፡ እንዳይደክሙ፡ የሚያደርጋ
ቸው፡ እሱ፡ ነው።

2014 04 17

፴፭፤ ወወሀብከኒ፡ ምእመነ፡ ለመድኀኒትየ ።

እኔን፡ ማዳን፡ ቢወድ፡ ረድኤቱን፡ አደረገ፡ ማለት፡ እኔን፡ ከንዴት፡ ማዳን፡ ቢወድ፡ ሳሙኤልን ። ከጎልያድ፡ ሊያድነኝ፡ ቢወድ፡ መልአኩን፡ ቅዱስ፡ ሚካኤልን፡ ከራቱ፡ ረፋይን፡ ከንዱ፡ ሊያድነኝ፡ ቢወድ፡ አቢሳን፡ የሰጠኝ፡ እሱ፡ ነው ። ፩ሳሙ፡ ፲፮፡ ፲፩-፲፫ ። ፲፯፡ ፳፮-፶፰ ።

ወየማንከ፡ ተወክፈኒ ።

ሥልጣንህ፡ በረድኤት፡ ተቀበለኝ ።

ወትምህርትከ፡ ዘያጸንዓኒ፡ ለግሙራ ።

ትምህርትህ፡ ኢ.ታምልክ፡ ፈጽሞ፡ የሚያጸናኝ፡ ነው ። እንድም፡ ፈጽሞ፡ የሚያጸናኝ፡ ትምህርትህ፡ ኢ.ታምልክ፡ ነው ።

ወተግሣጽከ፡ ውእቱ፡ ዘይሜህረኒ ።

የሚያስተምረኝ፡ ምክርህ፡ ትምሕርትህ፡ ዘጠኙ፡ ነው ።

፴፮፤ ወአርኀብከ፡ መከየድየ፡ በመትሕቴየ ።

ጫማዬን፡ አሰፋህልኝ ። የጫማ፡ ስፋ.ትስ፡ ያስነቅፋል፡ እንጂ፡ አያስመሰግንም፡ ብሎ፡ ጫማዬን፡ መልቼ፡ እንድሔድ፡ አደረግህልኝ ። ጠላት፡ ያለበት፡ ሰው፡ አዩኝ፡ አላዩኝ፡ ብሎ፡ ይሔዳል፡ እንጂ፡ ጫማውን፡ መልቶ፡ አይረግጥምና ።

ወኢደክመ፡ ሰኰናየ ።

እግሬ፡ ቢሮጥ፡ ቢገሠግሥ፡ አልደከመም ። እንድም፡ ልበናዬ፡ በአምልኮ፡

ጣዖት፡ በገቢረ፡ ኀጢአት፡ አልተሰነከለም ።

፴፯፤ እዴግኖሙ፡ ለፀርየ፡ ወእኀዝሙ ።

ጠላቶቼን፡ እከተላቸዋለሁ ። ተከትሎ፡ ማጣት፡ አለና፡ እይዛቸዋለሁ ።

ወኢይትመየጥ፡ እስከ፡ እጠፍኦሙ ።

ሳላጠፋቸው፡ አልመለስም ።

፴፰፤ እመንድቦሙ፡ ወኢይክሉ፡ ቀዊመ ።

አምሕያመ፡ ሲል፡ ነው ። አሸሽቸዋለሁ ። (ወኢ.ይክሉ)፡ አግባ፡ መልስ፡ ብለው፡ መዋጋት፡ አይቻላቸውም ። እንድም፡ እንዳለ፡ ይሆናል፡ አስጨንቃቸዋለሁ ። (ሐይወ)፡ ይላል፡ በሕይወት፡ ሥጋ፡ መኖር፡ አይቻላቸውም ። (ታሪክ)፡ ሒዶ፡ እንኩስ፡ ንጉሠ፡ ጌትን፡ ሰራዊቱ፡ ብዙ፡ ነውና፡ አቅንቼ፡ የምኖርበት፡ ጠፍ፡ አገር፡ ስጠኝ፡ አለው፡ የንጉ፡ ማረፊያ፡ ትሁንህ፡ ብሎ፡ ሚቂላቅን፡ ሰጠው፡ በዚያ፡ ወራት፡ ንጉሡ፡ ወደ፡ እስራኤል፡ ዘመተ፡ የምውልበትን፡ ንገረኝ፡ ልበለው፡ ብሎ፡ ሒዶ፡ ውሎዬን፡ ንገረኝ፡ አለው፡ እንተስ፡ ትከውነኒ፡ ዓቃቤ፡ ርእስየ ። አንተስ፡ እኔን፡ ትጠብቀኛለህ፡ አለው ። አሕዛብ፡ ዘወር፡ ብለው፡ ቢመለከቱ፡ ዳዊት፡ ፊቱ፡ ደምቆ፡ ጠሩ፡ በዝቶ፡ አዩ ። ንጉሥ፡ አሁን፡ ከኛ፡ ጋራ፡ ዳዊት፡ ዘመዶቹ፡ እስራኤልን፡ ሊወጋ፡ ነውን፡ የኛን፡ ቸብቸበ፡ እየቈረጠ፡ የዘመዶቹ፡ መታረቂያ፡ ሊያደርገን፡ ነው፡ እንጂ፡ ስትመልስ፡ እሱን፡ መልስ፡



አለዚያ፡ ግን፡ እሱን፡ ይዘህ፡ ሒድ፡ እኛ፡ እንመለሳለን፡ አሉት ። አንተ፡ ሰው፡ እኔ፡ አልጠረጠርሁህም፡ ነበር፡ ነገር፡ ግን፡ እሊህ፡ ሰዎች፡ ጠርጥረውሃልና፡ ተመለስ፡ ቀንቶኝ፡ ብመለስ፡ ላገርህ፡ አበቃሃለሁ፡ አለው ። ለጊዜው፡ እንዴት፡ ጦር፡ በተባለበት፡ ወራት፡ ሴት፡ ይመስል፡ ከቤት፡ ልዋል፡ ብሎ፡ አዘነ፡ ውሥጡ፡ ግን፡ ጥበበ፡ እግዚአብሔር፡ ነው ። ምንስ፡ ብጠላቸው፡ ዘመዶቹ፡ እስራኤልን፡ ከአሕዛብ፡ ጋራ፡ ሁኜ፡ ልውጋቸውን፡ እያለ፡ ይጸልይ፡ ነበርና ። ከዚያ፡ ቢመለስ ። ወረከበ፡ በዘአውዓይዋ፡ ለሢቂላቅ ። እንዶራውያን፡ መጥተው፡ አገሪቱን፡ አቃጥለው፡ ሰዉን፡ ማርከው፡ ከብቱን፡ ዘርፈው፡ ሒደው፡ ደረሰ፡ ሠራዊቱ፡ ከዳዊት፡ ጋራ፡ መኖር፡ ሁል፡ ጊዜ፡ መከራ፡ አንድ፡ ቀን፡ ተድላ፡ ደስታ፡ አይገኝበት ። ጥለነው፡ እንሒድ፡ ያሉ፡ አሉ ። እንጣላው፡ ያሉም፡ አሉ፡ መሥዋዕት፡ ሠውቶ፡ እዴግኖሙ፡ ወእኀዝሙ፡ ብሎ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ቢያመለክት፡ ዴግኖሙ፡ ወትእኀዝሙ፡ ብሎታል ። ስድስት፡ መቶ፡ ሰራዊት፡ አስከትሎ፡ ሲገሠግሥ፡ ሁለቱ፡ መቶ፡ ደክመው፡ ቀሩ ። አራቱን፡ መቶ፡ ይዞ፡ ሲገሠግሥ፡ ከነሱ፡ አንዱን፡ ደክሞ፡ ወድቆ፡ አገኘው ። ያን፡ እንሥቶ፡ እህል፡ አብልቶ፡ ወሀ፡ አጠጥቶ ። አደርስባቸዋለሁን፡ ወይስ፡ አልደርስባቸውም፡ ብሎ፡ ጠየቀው፡ አሁን፡ ትደርስባቸዋለህ፡ ከዚህ፡ እልፍ፡ ብሎ፡ ወሀ፡ አለች፡ ከዚያ፡ ታገኛቸዋለህ፡ አለው ። ቢደርስ፡ ሰናፊላቸውን፡ ፈትተው፡ ተዘልለው፡ ግዳይ፡ ሲጥሉ፡ ሲበሉ፡ ሲጠጡ፡ አገኘቶ፡ እርዶ፡ እርዶ፡ ፈጅቷቸዋል ። ጥቂት፡ ሰዎች፡ በግመል፡ ወሳብሬ፡ ሁነው፡ ሲያመልጡ ። ፩ሳሙ፡ ፳፯፡ ፩-፲፪ ። ፳፰፡ ፩-፪ ። ፳፱፡ ፩-፲፩ ። ፴፡ ፩-፲፯ ።

ወይወድቁ፡ ታሕተ፡ እገርየ ።

ከእግሬ፡ በታች፡ ግዳይ፡ ሁነው፡ ይወድቃሉ ።

፴፱፤ ወታቀንተኒ፡ ኀይለ፡ በፀብእ ።

በሰልፍ፡ ጊዜ፡ ኃይልን፡ እንደ፡ ዝናር፡ የምታስታጥቀኝ፡ አንተ፡ ነህ ።

ወአዕቀጽኮሙ፡ ለኵሎሙ፡ እለ፡ ቆሙ፡ ላዕሌየ፡ በመትሕቴየ ። ኢሳ፡ ፵፡ ፴ ።

ከበላዬ፡ የነበሩትን፡ በጠላትነት፡ የተነሡብኝን፡ ሁሉ፡ ከኔ፡ በታች፡ አደረግሃቸው ። እንድም፡ ላዕሌየ፡ ወመትሕቴየ ። በላዩም፡ በታቹም፡ የነበሩትን፡ ጠላቶቼን፡ ሁሉ፡ በሞት፡ አሰነካከልሃቸው ።

፵፤ ወመጠውከኒ፡ ዘባናሙ፡ ለፀርየ ።

ጀርባቸውን፡ መልሰህ፡ እንገታቸውን፡ ቀልሰህ፡ ለውግ፡ አስመችተህ፡ ሰጠኸኝ ። ይሁዳ፡ እዴከ፡ ዲበ፡ ዘባናሙ፡ ለፀርከ፡ ያለው፡ ትንቢት፡ ይደርስ፡ ይፈጸም፡ ዘንድ ። ዘፍ፡ ፵፱፡ ፲ ። ፪ሳሙ፡ ፳፪፡ ፴፰፡ ፴፱ ።

መሥረውቶሙ ፡ ለጸላእትየ ።

ጠላቶችን ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ አጠፋ
ሃቸው ።

፺፩ ። ነሥአ ፡ ወንጥአ ፡ ዘይረድኦሙ ።

ሙ ፡ የሚረዳቸው ፡ አጡ ።

ወገበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢሰምዖሙ ።

እግዚአብሔር፡ከልሰማቸው፡ዘንድ ።
እንድም ፡ (ዓውየዉ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ወኀበ ፡ ሰብእ) ፡ ወደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ መልሰው ፡ ለመኑ ።
(ወኀጥኡ ፡ ዘይረድኦሙ) ፡ የሚሰማቸ
ውም ፡ አጡ ። ታሪክ ፡ ሳኦል ፡
ሠላሳ ፡ ስምንት ፡ ዘመን ፡ እመኒ ፡ በሐ
ላምያን ፡ ወእመኒ ፡ በመንግራን ፡ ወእ
መኒ ፡ በእደ ፡ ነቢይ ፡ ከመልእክም ፡
ቢሉ ፡ ከነቢይ ፡ ቃል ፡ ሳይሰማ ፡ ኑሯል ።
ኢሎፍላውያን ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡ
በት ፡ ወሠዓርን ፡ ለእለ ፡ ያንቅሐ ፡
ምዉተ ፡ በምትሐት ፡ ሙት ፡ የሚያ
ነሡ ፡ እንዶራውያንን ፡ ሁሉ ፡ አጥፍቷ
ቸው ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ ቀርታ ፡
ነበር ። ተራ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ አልባሌ ፡
መስሎ ፡ ሒዶ ፡ ሳሙኤልን ፡ አስነሺ
ልኝ ፡ አላት ። አይሆንም ፡ ሳኦል ፡ ዘመ
ዶቹን ፡ ሁሉ ፡ አጥፍቷቸው ፡ እኔ ፡
ብቻ ፡ ቀርቻለሁ ፡ ታስገድለኛለህ ፡ አለ
ችው ፡ ግድ ፡ የለሽም ፡ አስነሺልኝ ፡
ብቻ ፡ አላት ። አስነሣለሁ ፡ ብላ ፡ ብት
ሔድ ። ሥላሴ ፡ በዚች ፡ በርኩሰት ፡
እጅ ፡ እንዳይነሣ ፡ ብለው ፡ አስነሥ
ተዉት ፡ ብርሃን ፡ ለብሶ ፡ ብርሃን ፡ ተጐ

ናጽፎ ፡ ሲያርግ ፡ አይታ ፡ ሒዳ ፡ ዓረ
ገልህ ፡ ሒደህ ፡ ጠይቀው ፡ አለችው ።
ሒዶ ፡ ቢጠይቀው ፡ ነገ ፡ ልትሞት ፡
ምን ፡ ያደክምሃል ፡ ብሎታል ። ከቤቱ ፡
ንብቶ ፡ እህል ፡ ሳይቀምስ ፡ አድሯል ።
እንድም ፡ ሚስቱ ፡ ጋብዛው ፡ ተመግቦ ፡
አድሯል ፡ በነጋው ፡ ሒዶ ፡ ገጠመ ።
እንዱ ፡ መርገዝ ፡ ቀብቶ ፡ በቀስት ፡
ወጋው ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ቢያቃጥለው ፡
ቁም ፡ ላዕሌየ ፡ ወቅትለኒ ፡ ጋሻ ፡ ዣ
ግሬውን ፡ እሊህ ፡ ቈላፋን ፡ ኪገድ
ሉኝ ፡ አንተ ፡ ግደለኝ ፡ አለው ፡ ቈር
ሰህ ፡ አጕርሰኸኝ ፡ ቀድደኽ ፡ አልብ
ሰኸኝ ፡ አብሬህ ፡ እሞትን ፡ እገድልህ ፡
አይሆንም ፡ አለው ። ወመልሐ ፡ ሰይፎ ፡
ወተረግዘ ፡ ለሊሁ ፡ ይላል ፡ በገዛ ፡ ሰይፉ ፡
ወዶ ፡ ገብቶበታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
፩ሳሙ ፡ ፳፰ ፡ ፯-፳ ። ፴፩ ፡ ፩-፲፫ ። ፪ሳሙ ፡ ፩ ፡ ፱ ።

፺፪ ፡ እሐርዖሙ ፡ ከመ ፡ ጸበለ ፡ ዘቅድመ ፡
ገጸ ፡ ነፋስ ። ኤር ፡ ፲፫ ፡ ፳፬ ።

በነፋስ ፡ ፊት ፡ በነፋስ ፡ አንጻር ፡ እን
ዳለ ፡ ትቢያ ፡ አበናችዋለሁ ። ማለት ፡
አጠፋቸዋለሁ ።

ወእከይዶሙ ፡ ከመ ፡ ጽንጕን ፡ መርኅብ ።

ባደባባይ ፡ እንዳለ ፡ ጭቃ ፡ እጠቀጥቃ
ቸዋለሁ ። ኢሳ ፡ ፲ ፡ ፳፰ ፡ ፲ ፡ ፫ ። ፺፩ ፡ ፲ ።

፺፫ ፡ አድኅነኒ ፡ እምኀበ ፡ እሕዛብ ።

አሕዛብ ፡ በቃላቸው ፡ ፈክረው ፡ ዘም
ረው ፡ ከሚያመጡት ፡ መከራ ፡ አድነ
ኝ ፡ እንድም ፡ (እምባዕስ ፡ አሕዛብ) ፡ አ
ሕዛብ ፡ ከሚያመልኩት ፡ ጣዖት ፡ (አን



ድም ፡ እምስብሐተ ፡ አሕዛብ) ፡ አሕ
ዛብ ፡ ለጣዖት ፡ ከሚያመሰግኑት ፡ ም
ስጋና ፡ አድነኝ ።

ወትሠይመኒ ፡ ውስተ ፡ ርእሰ ፡ ሕዝብ ።

የሕዝቡ ፡ አለቃ ፡ አድርገህ ፡ ትሾመኛ
ለህ ። እንብብ ፡ በውስተ ፡ አሬት ፡ እን
ዲል ።
እንድም ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አ
ድርገህ ፡ ትሾመኛለህ ። እንድም ፡ (ው
ስተ ፡ ርእሰ ፡ ሕዝብ ፡ ርእሰ) ፡ በሕዝቡ ፡
አለቃ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አድርገህ ፡ ትሾ
መኛለህ ፡ ማለት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ታደርገኛለህ ።

ሕዝብ ፡ ዘኢየአምር ፡ ተቀንየ ፡ ሊተ ።

ዘኢየአምር ፡ ተቀንዮ ፡ ተቀንየ ፡ ሊተ ።
መገዛት ፡ የማያውቁ ፡ ታይ ፡ ንጉሠ ፡
ሒማት ። ኪራም ፡ ንጉሠ ፡ ጢሮስ ።
ሴት ፡ ጌትያዊ ፡ ተገዙልኝ ። ፪ሳሙ ፡
፭ ፡ ፲፩ ። ፲፭ ፡ ፲፰-፳፪ ። እንድም ፡ ዘኢየአ
ምሮ ፡ የማላውቀው ፡ ሴት ፡ ጌትያዊ ፡
ተገዛልኝ ። ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፭ ።

፺፬ ውስተ ፡ ምስማዐ ፡ እዝን ፡ ተሠጥዉኒ ።

ላይ ፡ ቤት ፡ ታች ፡ ቤት ፡ እንዲሉ ።
በራስጌ ፡ ቤት ፡ በእግርጌ ፡ ቤት ፡ ያሉ ፡
ሁሉ ፡ ተገዙልኝ ። ብጠራቸው ፡ እ
ቤት ፡ ብልካቸው ፡ ወዴት ፡ አሉኝ ።
እንድም ፡ ገብሩ ፡ ቀቅሉ ፡ ብዬ ፡ እዋጅ ፡
ብነግር ፡ ይበጅ ፡ ያድርግ ፡ አሉ ።

ውሉደ ፡ ነኪር ፡ ሐሰዉኒ ።

እለ ፡ ሳኦል ፡ ግን ፡ አባይ ፡ በል ፡ አሉ ።

፺፭ ፡ ውሉደ ፡ ነኪር ፡ በልዩ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ጠፉ ፡ እንጂ ፡ አልተጠቀ
ሙም ።

ወሐንከሱ ፡ በፍኖቶሙ ። ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፲፭ ።

በጎዳናቸው ፡ ያነክሣ ፡ ሥራ ፡ ሠሩ ።
እንካሣ ፡ ማለት ፡ ተነሥቶ ፡ ሲገሠግሥ ፡
ያረፍዳል ። በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ ይደርስ
በታል ። ወንድሚ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተነ
ሣህ ፡ ይለዋል ፡ እሁን ፡ ከረፈደ ፡ ተነ
ሣሁ ፡ ይለዋል ፡ ለዚህ ፡ አካሔዱ ፡
ብሉ ፡ ምርጕዙን ፡ እምዘግዝጎ ፡ ጥሎ ፡
ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ሒዶ ፡ ይተኛል ። እነ
ሱም ፡ መንግሥቱን ፡ ከሁሉ ፡ አስቀ
ድመው ፡ ገምረው ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡
ጠፍተዋልና ። ፩ሳሙ ፡ ፪ ፡ ፲፬-፳፯ ። ፫ ፡ ፳
፳፯-፵፩ ፡ ፳፲ ።
እንድም ፡ (ውሉደ ፡ ነኪር ፡ ሐሰዉኒ) ፡
እነሳቡሄ ፡ ወልደ ፡ ቢክሪ ፡ አባይ ፡ በል ፡
አሉ ፡ (ውሉደ ፡ ነኪር ፡ በልዩ) ፡ ነገር ፡
ግን ፡ ጠፉ ፡ እንጂ ፡ አልተጠቀሙም ፡
(ወሐንከሱ ፡ በፍኖቶሙ) ፡ በጎዳናቸው ፡
እንካሳ ፡ የሚያሰኛቸውን ፡ ሥራ ፡ ሠሩ ።
አቤሴሎም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ዳዊት ፡
ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ዮርዳኖስን ፡ አሻግሩ
ኝ ፡ አላቸው ፡ ከሥሩ ፡ ነገድ ፡ ቢልኩ
ባቸው ፡ ቀሩ ። እንቃውን ፡ ጀልባውን ፡
ቢድሩን ፡ ድርድሩን ፡ ይዘው ፡ ወርደ
ው ፡ ሲያሻግሩ ፡ ዋሉ ፡ ማታ ፡ ሳቡሄ ፡
ወልደ ፡ ቢክሪ ፡ ያሥሩ ፡ ነገድ ፡ አለቃ ፡
ነውና ፡ ጦር ፡ አስከትቶ ፡ መጣ ። ምነው
ዳዊትን ፡ ስታሻግሩ ፡ ሳትነግሩን ፡ አላ

ቸው ፡ ላከንባችሁ ፡ ብትቀሩ ፡ ምን ፡ እናድርግ ፡ ለኛስ ፡ አሻግረን ፡ ምን ፡ ተደረገልን ፡ እናንተስ ፡ ባታሻግሩ ፡ ምን ፡ ይቀርብችኋል ፡ አሉት ። እስራኤል ፡ ራስህን ፡ ጠብቀው ። እልብነ ፡ ክፍል ፡ ምስለ ፡ ዳዊት ፡ ወኢርስት ፡ ምስለ ፡ ወልደ ፡ እሴይ ፡ እቱ ፡ እስራኤል ፡ አብያቲከ ፡ ብሎ ፡ ጠሩን ፡ አሰልፎ ፡ ሔደ ። ዳዊት ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ኢዮአብን ፡ በሽረት ፡ ዓይን ፡ አይቶት ፡ ነበርና ፡ አሜሳይን ፡ ይህ ፡ ልጅህ ፡ ከእጃችን ፡ ሳይርቅ ፡ ከይሁዳችን ፡ ሳይጠልቅ ፡ ከከተማ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ አስከትተህ ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ላከው ፡ አልከትልህ ፡ ብሎት ፡ ዋለ ፡ አደረ ፡ ምን ፡ አገኘው ፡ ይሆን ፡ ብሎ ፡ አቢሳን ፡ ሒድ ፡ አለው ። ኢዮአብ ፡ ሳይሰናበት ፡ ወንድሙን ፡ ተከትሎ ፡ ሔዶ ፡ አሜሳይ ፡ ጦሩን ፡ አስከትቶ ፡ ሲመጣ ፡ ኢዮአብ ፡ አቢሳ ፡ ከመንገድ ፡ አገኙት ። ኢዮአብ ፡ አሜሳይን ፡ ና ፡ የምጠይቅህ ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ እልፍ ፡ አድርጎ ፡ ጽሕሙን ፡ የሚለቃቅም ፡ መስሎ ፡ ሆዱን ፡ በጩቤ ፡ ቀድዶ ፡ ገድሎታል ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሳቡሄ ፡ ወልደ ፡ ቢክሪ ፡ ደብረ ፡ ምስካይ ፡ ከምትባል ፡ ሀገር ፡ ነበረ ፡ ደብረ ፡ አቤልም ፡ ይላታል ፡ ሔደው ፡ ከበቧት ፡ ባሏ ፡ ሙቶ ፡ በንጽሕና ፡ የምትኖር ፡ አንዲት ፡ ደግ ፡ ሴት ፡ ነበረች ፡ ወጥታ ፡ ይህች ፡ አገር ፡ የሙሴ ፡ የአሮን ፡ ጕልት ፡ ናት ፡ የዳዊት ፡ መንግሥት ፡ የሁሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የላንት ፡ ብቻ ፡ ነውን ። ለምን ፡ ታጠፉታላችሁ ፡ አለቻቸው ። እኛ ፡ የምንፈልገው ፡ ጠላታችንን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አገሪቱማ ፡ ምን ፡ ብላን ፡ አሏት ፡ ወቶ ፡ ናገረቶሙ ፡ በጥበባ ። በቋንቋዋ ፡ አንድም ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡ በቆይታ ፡ ተጨዋውታ ፡ ቸብቸበውን ፡ አስቆርጣ ፡ በዝንግሪር ፡ አውጥታ ፡ ሰጥታቸው ፡ ይዘው ፡ ሔደዋል ። ፪ሳሙ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ ፡ ፳፫ ፡ ፳፪ ።

፵፮ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ወቡሩክ ፡ አምላኪየ ።

እግዚአብሔር ፡ አምላኪየ ፡ ሕያው ፡ ወቡሩክ ፡ ነው ። ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ። ክቡር ፡ ምስጉን ፡ ነው ። አብርሃም ፡ ቡሩኩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአግብዖ ፡ ጸላእተ ፡ ንጉሥ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለንጉሥ ፡ እንዲል ።

ወተለዓለ ፡ አምላከ ፡ መድኀኒትየ ።

ድኅነቴን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ አምላክ ፡ ጠላቴን ፡ አጥፍቶ ፡ እኔን ፡ አድኖ ፡ ልዕልናውን ፡ ገለጸ ። ዮ ፡ ፲፱ ፡ ፳፭ ። ኢሳ ፡ ፵፫ ፡ ፭ ።

፵፯ ፡ አምላኪየ ፡ ያገብዕ ፡ በቀልየ ።

ፈጣሪዬ ፡ በቀሌን ፡ በቀል ፡ ያደርግልኛል ፡ ማለት ፡ ይፈርድልኛል ። ተበቀል ፡ ሊ ፡ እምእድውየ ፡ እንዲል ።

ወአግረረ ፡ ሊተ ፡ አሕዛበ ፡ በመትሕቴየ ።

አሕዛብን ፡ በእግሬ ፡ እርግጥ ፡ በእጄ ፡ ጭብጥ ፡ አድርጎ ፡ አስገዛልኝ ።



፵፰ ፡ ዘይባልሐኒ ፡ እምጸላእትየ ፡ መንበዋን ።

ጥቁዓንም ፡ ይላል ። ጥፋት ፡ ከሚያገኛቸው ፡ ከጠላቶቼ ፡ የሚያድነኝ ፡ እሱ ፡ ነው ። አንድም ፡ ድል ፡ ከተነሡ ። ብልሹ ፡ ከሚሆኑ ፡ ጠላቶቼ ፡ የሚያድነኝ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወዘያሌዕለኒ ፡ እምእለ ፡ ቆሙ ፡ ላዕሌየ ።

በጠላትነት ፡ ከተነሡብኝ ፡ ከጠላቶቼ ፡ በላይ ፡ የሚያደርገኝ ፡ እሱ ፡ ነው ።

እምብእሲ ፡ ገፋዒ ፡ ባልሐኒ ።

ከገፋዒ ፡ ከሳኦል ፡ አድነኝ ።

፵፱ ፡ በእንተዝ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ በውስተ ፡ አሕዛብ ፡ እግዚኦ ። ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፱ ።

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አቤቱ ፡ በሕዝቡ ፡ ጉባዔ ፡ አመሰግንሃለሁ ።

ወእዜምር ፡ ለስምከ ።

ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ። ስምህን ፡ አመሰግናለሁ ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፳፪ ፡ ፶ ።

፶ ፡ ዘያዓብያ ፡ ለመድኀኒተ ፡ ንጉሥ ።

ለንጉሥ ፡ ለዳዊት ፡ ድኅነትን ፡ የሚያደርግ ፡ ስምህን ፡ አመሰግናለሁ ። ለዳዊት ፡ ድኅነትን ፡ ለሚያደርግ ፡ ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

ወይገብር ፡ ምሕረቶ ፡ ለመሲሑ ።

ቀብቶ ፡ ላነገሠው ፡ ለዳዊት ፡ ቸርነትን ፡ የሚያደርግ ፡ ስምህ ፡ ነው ፡ ቸርነትን ፡ የሚያደርግ ፡ ስምህን ፡ አመሰግናለሁ ፡ ቸርነትን ፡ ለሚያደርግ ፡ ስምህ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

ለዳዊት ፡ ወለዘርኡ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

ለመሲሑ ፡ ያለውን ፡ ለዳዊት ፡ ወለዘርኡ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ብሎ ፡ ገለጠው ።

መዝሙር ፡ ፲፱ ።

፩ ፡ ሰማያት ፡ ይነግራ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ።

ስለመነናውያን ፡ ተናግሮታል ። የራሱም ፡ የስነ ፡ ፍጥረትም ፡ ነገር ፡ አለበት ። ማኒ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጌትነቱን ፡ ተአምራቱን ፡ ምስጋናውን ፡ ባትናገር ፡ ላንት ፡ ይበስህ ፡ እንጂ ። የእግዚአብሔርንስ ፡ ጌትነቱን ፡ ተአምራቱን ፡ ምስጋናውን ፡ ሰማያት ፡ ይናገራሉ ፡ ያስተምራሉ ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳ ። ፲፭-፲፯ ።

ወግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ያየድዓ ፡ ሰማያት ።

ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ነው ። የእጁን ፡ የቃሉን ፡ ሥራ ፡ ሰማያት ፡ ይናገራሉ ፡ ያስተምራሉ ። አንድም ፡ ሰማያት ፡ ግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ይነግራ ፡ ወያየድዓ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ የእጁ ፡ የቃሉ ፡ ሥራ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰማያት ፡ ጌትነቱን ፡ ተአምራቱን ፡ ምስጋናውን ፡ ይናገራሉ ፡ ያስተምራሉ ። እሁን ፡ እነሱ ፡ ግእዛን ፡ ኑሯቸው ፡ የሚናገሩ ፡ ሁነው ፡ አይዶለም ፡ ተዘ

ርግተው ፡ በመታየታቸው ፡ ሰው ፡
ጌትነቱን፡ተአምራቱን፡ምስጋናውን፡
የሚናገር፡ስለሆነ፡ሰማይኒ፡ይነግር፡
በአስተርእዮቱ ፡ እንዲል ። እንድም ፡
ሊቃነ፡መላእክት ፡ ጌትነቱን ፡ ተአም
ራቱን፡ምስጋናውን፡ይነግራሉ ፡ ያስ
ተምራሉ ፡ (ወግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ያየ
ድዓ)፡የእጁን፡የቃሉን፡ሥራ፡ሊቃነ፡
መላእክት፡ይነግራሉ፡ያስተምራሉ ።
እንድም ፡ ግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ሊቃነ ፡
መላእክት ፡ ይነግራሉ ። (ወያየድዓ ፡
ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር) ፡ የእጁ ፡
የቃሉ ፡ ፍጥረት ፡ የሚሆኑ ፡ ሊቃነ ፡
መላእክት ፡ ጌትነቱን ፡ ተአምራቱን ፡
ምስጋናውን ፡ ይነግራሉ ፡ ያስተም
ራሉ ፡ የተመቸ ።

፪፡ ዕለት ፡ ለዕለት ፡ ትጐሥዕ ፡ ነቢበ ።

መዓልተ፡እሑድ፡ለመዓልተ፡ሰኑይ፡
ነገሯን፡አውጥታ፡ትነግራለች ። በኔ፡
ይሆን ፡ ያሀል ፡ ፍጥረት ፡ ተፈጠረ ፡
ባንችም ፡ ይህን ፡ ያሀል ፡ ፍጥረት ፡
ይፈጠርባላ ። ወትጐሥዖሙ፡ይእቲ፡
ባሕር ፡ ለነጋድያን ፡ እንዲል ።

ወሌሊት ፡ ለሌሊት ፡ ታየድዕ ፡ ጥበበ ።

ሌሊተ ፡ እሑድም ፡ ለሌሊተ ፡ ሰኑይ ፡
ነገሯን ፡ አውጥታ ፡ ትናገራለች ፡ እን
ዳለፈው ።

፫፡ አልቦ ፡ ነገር ፡ ወአልቦ ፡ ነቢብ ፡ ዘኢተሰምዓ ፡
ቃሎሙ ።

የመዓልተ፡እሑድ፡የመዓልተ፡ሰኑይ፡
የሌሊተ ፡ እሑድ ፡ የሌሊተ ፡ ሰኑይ ፡
ነገራቸው ፡ ያልደረሰበት ፡ ያልተነገ
በት ፡ የለም ፡ ስነ ፡ ፍጥረት ፡ ያልደረ
ሰበት ፡ የለምና ።

፬፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡ ወፅአ ፡ ነገሮሙ ።

ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ተነገረ ፡ እንጂ ።

ወእስከ ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ በጽሐ ፡ ነቢቦሙ ።

ጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ደረሰ ፡ እንጂ ።
አሁን ፡ እነሱ ፡ ግዕዛን ፡ ኑሯቸው ፡
የሚናገሩ ፡ ሁነው ፡ አይደለም ፡ ሰው ፡
በዕለተ ፡ እሑድ ፡ በዕለተ ፡ ሰኑይ ፡
በሌሊተ ፡ እሑድ ፡ በሌሊተ ፡ ሰኑይ ፡
ይህን ፡ ያህል ፡ ፍጥረት ፡ ተፈጠረ ፡
ብሎ ፡ የሚናገር ፡ ስለሆነ ፡ እንዲህ ፡
አለ ፡ እንጂ ። ኢሳ ፡ ፵፱ ፡ ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፲፰ ፡
ቆላ ፡ ፩–፳፫ ።

እንድም ፡ (ዕለት ፡ ለዕለት ፡ ትጐሥዕ ፡
ነቢበ) ። መምሕራን ፡ ሐዲስ ፡ ሐዋር
ያት ፡ ለምእመናን ፡ ሐዲስ ፡ ወረደ ፡ ተወ
ለደ ፡ ብለው ፡ አስተማሩ ፡ (ወሌሊት ፡
ለሌሊት ፡ ታየድዕ ፡ ጥበበ) ፡ ከዚህም ፡
አስቀድሞ ፡ መምሕራን ፡ ብሊት ፡ ነቢ
ያት ፡ ለምእመናን ፡ ብሊት ፡ ይወር
ዳል ፡ ይወለዳል ፡ ብለው ፡ አስተም
ረው ፡ ነበር ፡ (አልቦ ፡ ነገር ፡ ወአልቦ ፡
ነቢብ ፡ ዘኢተሰምዓ ፡ ቃሎሙ) ፡ የሐ
ዋርያት ፡ ስብከታቸው ፡ የነቢያት ፡
ትንቢታቸው ፡ ያልደረሰበት ፡ ያልተ
ነገረበት ፡ የለም ። እንድም ፡ (በቃ
ሎሙ) ፡ ይላል ። ሐዋርያት ፡ በቃላ
ቸው ፡ ያላስተማሩት ፡ ትምርት ፡ ያል
ሰበኩት ፡ ስብከት ፡ ነቢያት ፡ በቃላ



ቸው ፡ ያልተናገሩት ፡ ትንቢት ፡ የለም ።
(ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡ ወፅአ ፡ ነገ
ሮሙ) ፡ የነቢያት ፡ ትንቢታቸው ፡ የሐ
ዋርያት ፡ ስብከታቸው ፡ እንድም ፡ ነቢ
ያት ፡ በቃላቸው ፡ የተናገሩት ፡ ትን
ቢት ፡ ሐዋርያት ፡ በቃላቸው ፡ የሰበ
ኩት ፡ ስብከት ፡ ባራቱ ፡ ማዕዝን ፡
ደረሰ ፡ ተነገረ ፡ እንጂ ። (ወእስከ ፡ አጽ
ናፈ ፡ ዓለም ፡ በጽሐ ፡ ነቢቦሙ) ፡
ጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍም ፡ ደረሰ ፡ እንጂ ።

ወውስተ ፡ ፀሐይ ፡ ሤመ ፡ ጽላሎቶ ።

ጸዳሉን ፡ በከበቡ ፡ አኖረ ። አሁን ፡
ጸዳሉ ፡ በኋላ ፡ ከበቡ ፡ በፊት ፡ የተገኙ ፡
ሁኖ ፡ አይደለም ። ሁሉም ፡ አንድ ፡
ጊዜ ፡ መገኘቱን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፭፡ ውእቱሰ ፡ ከመ ፡ መርዓዊ ፡ ዘይወፅእ ፡
እምጽርሑ ።

ፀሐይ ፡ ከጫጕላው ፡ የወጣ ፡ ሙሽራ ፡
ይመስላል ። ምነው ፡ ሙሽራው ፡ ፀሐይ ፡
ይመስላል ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ፀሐዩ ፡
ሙሽራ ፡ ይመስላል ፡ ይባላልን ፡ ቢሉ ።
መመሳሰል ፡ የጋራ ፡ ከሆነ ፡ ብሎ ።
ምሳሌ ፡ ዘየሐፅፅ ፡ ነው ።

ይትፌሣሕ ፡ ከመ ፡ ይርባሕ ፡ ዘይረውድ ፡ ፍኖቶ ።
ኢሳ ፡ ፷፩–፲ ።

ይረባ ፡ ይጠቀም ፡ ዘንድ ፡ ፀሐይ ፡
በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ጎዳናውን ፡ የሚጠበጥብ ፡
ሰው ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

፮፡ እምአጽናፈ ፡ ሰማይ ፡ መሙጽኡ ።
ወእስከ ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ ምእታዉ ።

ከፀሐይ ፡ መውጫ ፡ እስከ ፡ ፀሐይ ፡
መግቢያ ፡ ጎዳናውን ፡ የሚጠበጥብ ፡
ሰው ። እንድም ፡ ይረባ ፡ ይጠቀም ፡
ዘንድ ፡ ጎዳናውን ፡ የሚጠበጥብ ፡ ከፀ
ሐይ ፡ መውጫ ፡ እስከ ፡ ፀሐይ ፡ መግ
ቢያ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ደስ ፡ ይለዋል ። አልቦ ፡
ዘይትኀባእ ፡ ማንሻ ፡ እንድም ፡ ከፀ
ሐይ ፡ መውጫ ፡ እስከ ፡ ፀሐይ ፡ መግ
ቢያ ፡ ድረስ ።

አልቦ ፡ ዘይትኀባእ ፡ እምላህቡ ።

ከፀሐይ ፡ የሚሠወር ፡ የለም ፡ ፀሐይ ፡
በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ከቆጥ ፡ የተሰቀለው ፡
ከማገር ፡ የተንጠለጠለው ፡ ይገለጻ
ልና ። እንድም ፡ ከፀሐይ ፡ መውጫ ፡
እስከ ፡ ፀሐይ ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ፀሓ
ይን ፡ የማይመኝ ፡ የለም ፡ በዙፋን ፡
ካለ ፡ ንጉሥ ፡ ባደባባይ ፡ እስከ ፡ ወደቀ ፡
ዕንስ ፡ ፀሐይን ፡ የማይመኝ ፡ የለምና ፡
ዓይንም ፡ ጠፈር ፡ ደፈር ፡ ካልከለከላት ፡
ከብርሃን ፡ ፀሐይ ፡ ጋራ ፡ ተዋህዳ ፡ ፀ
ሐይ ፡ ከደረሰችበት ፡ ድረስ ፡ ትደርሳ
ለችና ።

፯፡ ሕጉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ንጹሕ ፡ ወይመይጣ ፡
ለነፍስ ።

ሕጉ ፡ ፀሐይ ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ሰውነ
ትን ፡ ይመልሳል ፡ የበረደው ፡ ሰው ፡
ፀሐይ ፡ ሲሞቀው ፡ እሰይ ፡ ነፍሴ ፡ ገ
ባች ፡ ይላልና ፡ እንድም ፡ ነፍስን ፡
ያራቅቃታል ፡ ከለማወቅ ፡ ወደማወቅ ፡
ይመልሳታል ።

ስምዑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እሙን ፡ ወያጠብብ ፡
ሕፃናተ ።

እምልክቱ ፡ (መመለኪያው) ፡ ፀሐይ ፡
የታመነ ፡ ነው ። ሕፃናት ፡ ሥጋን ፡ ያራ

2014 04 17

ቅቃል ፡ ከባሕር ፡ ጠልቀው ፡ ከገደል ፡ ወድቀው ፡ እንዳያልቁ ፡ አምልኮቱን ፡ እንዲመሰክሩለት ፡ ስለሆነ ፡ ስምዑ ፡ አለው ፡ የተመቸ ። እንድም ፡ ሕፃናት ፡ አእምሮን ፡ ያራቅቃል ፡ በፀሐይ ፡ ተመራምረው ፡ ያመኑ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፡ ከዚያው ፡ ዘንድ ፡ ከቀደሙ ፡ ሰዎች ፡ አብርሃም ፡ ከለዳዊ ፡ ከኋላ ፡ ሰዎች ፡ ሙሴ ፡ ጸሊም ፡ በፀሐይ ፡ በስነ ፡ ፍጥረት ፡ ተመራምረው ፡ አምነዋልና ።

፰ ፡ ኵነኔሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ርቱዕ ፡ ወያስተፌሥሕ ፡ ልበ ።

ፍጥረቱ ፡ ፀሐይ ፡ የቀና ፡ ነው ። ልበ ፡ ሥጋን ፡ ደስ ፡ ያሰኛልና ። ወብሂለ ፡ ትቤ ፡ አመ ፡ ቀዳሚ ፡ ኵነኔከ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ ልቡ ፡ ነፍስን ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።

ትእዛዙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሩህ ፡ ወያበርህ ፡ አዕይንተ ።

ለይኩን ፡ ብሎ ፡ የፈጠረው ፡ ፀሐይ ፡ ብሩህ ፡ ነው ፡ ዓይን ፡ ሥጋን ፡ ብሩህ ፡ ያደርጋል ።

፱ ፡ ፈሪሆ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጹሕ ፡ ወየሐዩ ፡ ለዓለም ።

አምልኮቱ ፡ ፀሐይ ፡ ንጹሕ ፡ (ጽኑዕ) ፡ ነው ፡ እለፍ ፡ እስኪለው ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

ፍትሑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ ወርትዕ ፡ ኅቡረ ።

ፍጥረቶቹ ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ለይኩን ፡ ብሎ ፡ በአንድነት ፡ የፈጠራቸው ፡ ናቸው ።

፲ ፡ ወይትፈተው ፡ እምወርቅ ፡ ወእምዕንቍ ፡ ክቡር ።

ይትፈተውም ፡ ይላል ፡ ከወርቅ ፡ ከዕንቍ ፡ ይልቅ ፡ የተወደደ ፡ ነው ። ለወርቅ ፡ ለዕንቍ ፡ ብሎ ፡ ፈጣሪን ፡ መካድ ፡ አይገባምና ። ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ ለወርቅ ፡ ለዕንቍ ፡ ብለው ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ አይክዱምና ።

ወይጥዕም ፡ እመዓር ፡ ወሦከር ።

ከመዓር ፡ ከሸንኮር ፡ ይመረጣል ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ የታሠረ ፡ ሰው ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ ማር ፡ ሸንኮር ፡ ልስጣችሁ ፡ ፀሐይ ፡ አሙቁኝ ፡ ይላል ። ሕዝ ፡ ፫ ፡ ፫ ። እንድም ፡ (ወውስተ ፡ ፀሐይ ፡ ሤመ ፡ ጽላሎቶ) ፡ ምሳሌውን ፡ በፀሐይ ፡ አኖረ ። በክበቡ ፡ አብ ፡ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፡ በሙቀቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላልና ። ቅዳ ፡ ማርያ ፡ ፳ ፡ ፳፯ ። እንድም ፡ ደሐራዊ ፡ ልደቱን ፡ ለቀዳማዊ ፡ ልደቱ ፡ ምሳሌ ፡ አደረገ ፡ ልደት ፡ ቀዳማዊ ፡ ተአውቀ ፡ በደኃራዊ ፡ እንዲል ። አር ጾም ፡ ፲፪ ፡ ፳፯ ።

እንድም ፡ (ወሤመ ፡ ለፀሐይ ፡ መለክት ፡ ደብተራ ፡ ሥጋት ፡ በሙ) ፡ ይላል ፡ ለፀሐይ ፡ መለኮት ፡ ሥጋትን ፡ ፈጠረለት ፡ ሎሙ ፡ ሊዋሐዳቸው ፡ በሙ ፡ አሴ ፡ ለከሙ ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያን ፡ ብሎ ፡ በጸሐፍት ፡ በፈሪሳውያን ፡ ዘለፋ ፡ ሊሆንባቸው ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፲፫-፴፱ ። ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፶፪ ። (ውእቱሰ ፡ ከመ ፡ መርዓዊ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምጽርሑ) ። ጽርሕ ፡ ንጽሕት ፡ ዘሚልክያስ ፡ ከምትባል ፡ ከመቤታችን ፡ መወለዱ ፡ መርዓዊ ፡ ሰማያዊ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ቅዳ ፡ ማር ፡



፳ ፡ ፳፱ ። (ይትፌሣሕ ፡ ከመ ፡ ይርባሕ ፡ ዘይሜርድ ፡ ፍኖቶ) ፡ ኋላ ፡ ይረባ ፡ ይጠቀም ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ ፍኖተ ፡ ስብከትን ፡ የሚጠበጥብ ፡ ሐዋርያ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ። (እምአጽናፈ ፡ ሰማይ ፡ ሙፃኡ ። ወእስከ ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ ምእታዉ) ፡ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ፍኖተ ፡ ስብከትን ፡ የሚጠበጥብ ። እንድም ፡ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ያለ ፡ ሐዋርያ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ አልበ ፡ ማንሻ ፡ (አልቦ ፡ ዘይትኀባእ ፡ እምላህቡ) ፡ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ከጌታ ፡ ልደት ፡ የሚሠወር ፡ የለም ። እንድም ፡ ከወንጌል ፡ ጉባኤ ፡ የሚሠወር ፡ የለም ፡ ወንጌል ፡ የተሠራ ፡ ጌታ ፡ የተወለደ ፡ ለሁሉ ፡ ነውና ፡ እንድም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከደረበት ፡ ሐዋርያ ፡ የሚሠወር ፡ የለም ። ዘሰበ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኵሎ ፡ ይትኃሠሥ ፡ ወሎቱሰ ፡ አልበ ፡ ዘይትኃሠሦ ፡ እንዲል ፡ ። ፩ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ። (ሕጉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ንጹሕ ፡ ወይመይጣ ፡ ለነፍስ) ፡ ትእዛዙ ፡ ወንጌል ፡ ሕጉ ፡ ኦሪት ፡ ንጹሕ ፡ ነው ። ነፍስን ፡ ወደ ፡ ዕውቀት ፡ ይመልሳል ፡ (ስምዑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እሙን ፡ ወያጠብብ ፡ ሕፃናተ) ፡ አምልኮቱ ፡ ወንጌል ፡ ኦሪት ፡ የታመነ ፡ ነው ። ሕፃናት ፡ አእምሮን ፡ ያራቅቃል ፡ (ኵነኔሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ርቱዕ ፡ ወያስተፌሥሕ ፡ ልበ) ፡ ሕጉ ፡ ወንጌል ፡ ኦሪት ፡ የቀና ፡ ነው ፡ ነፍስን ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። (ትእዛዙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሩህ ፡ ወያበርህ ፡ አዕይንተ) ፡ በቃሉ ፡ ተናገር ፡ የሠራው ፡ ወንጌል ፡ ኦሪት ፡ ብሩህ ፡ ነው ፡ ዓይነ ፡ ልቡናን ፡ ብሩህ ፡ ያደርጋል ። (ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጹሕ ፡ ወየሐዩ ፡ ለዓለም) ፡ አምልኮቱ ፡ ወንጌል ፡ ኦሪት ፡ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ። ሰማይ ፡ ወምድር ፡ የኃልፍ ፡ ወቃልየሰ ፡ ኢየኃልፍ ፡ እንዲል ። ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፴፭ ። (እንድም ፡ ያሐዩ) ፡ ሰውን ፡ ለዘላለሙ ፡ ሕያው ፡ ያደርጋል ። ዘየአምን ፡ በወልድ ፡ ቦሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ እንዲል ። ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፴፮ ። (ፍትሑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ ወርትዕ ፡ ኅቡረ ። ወንጌልና ፡ ኦሪት ፡ በአንድነት ፡ ፈርዶ ፡ የሠራቸው ፡ ሕገጋት ፡ ናቸው ። (ወይትፈተው ፡ እምወርቅ ፡ ወእምዕንቍ ፡ ክቡር) ፡ ከወርቅ ፡ ከእንቍ ፡ ይልቅ ፡ የተወደደ ፡ ነው ፡ ለወርቅ ፡ ለዕንቍ ፡ ብሎ ፡ ሕግ ፡ ማፍረስ ፡ አይገባምና ። ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ ወርቅ ፡ ዕንቍ ፡ እንሰጣችኋለን ፡ ፈጣሪያችሁን ፡ ካዱ ፡ ሕጋችሁን ፡ አፍርሱ ፡ ቢሏቸው ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ አይክዱም ፡ ሕጋቸውን ፡ አያፈርሱምና ። (ወይጥዕም ፡ እመዓር ፡ ወሦከር) ፡ ከማር ፡ ከሸንኮር ፡ ይመረጣል ፡ ሐተታ ፡ እንዳለፈው ። መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፫ ።

እንድም ፡ (ወውስተ ፡ ፀሐይ ፡ ሤመ ፡ ጽላሎቶ) ፡ የሰውን ፡ ምሳሌ ፡ በፀሐይ ፡ አኖረ ፡ በምሥራቅ ፡ መውጣቱ ፡ ሰው ፡ ለመውለዱ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሲመግብ ፡ መኖሩ ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ሕፃናት ፡

ወልዶ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ይዞ ፡ ለመኖ
ሩ ። በምዕራብ ፡ መግባቱ ፡ ለመሞቱ ፡
ተመልሶ ፡ በምሥራቅ ፡ መውጣቱ ፡
በትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ለመነሣቱ ፡ ም
ሳሌ ፡ ነውና ። እንድም ፡ (ወሜመ ፡ ለፀ
ሐይ ፡ ነፍሳት ፡ ደብተራ ፡ ሥጋት ፡
ሎሙ) ፡ ለፀሐይ ፡ ነፍሳት ፡ ሥጋትን ፡
ፈጠረላቸው ፡ ሎሙ ፡ ሊዋሃዷቸው ፡
በሙ ፡ አልቦ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ በ
ሚሉ ፡ በሰዱቃውያን ፡ ዘለፋ ፡ ሊሆ
ኑባቸው ። ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ፡ ፴፫ ። (ውእ
ቱሰ ፡ ከመ ፡ መርዓዊ ፡ ዘይወፅእ ፡ እም
ጽርሑ) ፡ ይኸውም ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጉ
ባኤ ፡ የሚነሣ ፡ ምእመን ፡ ከማጉላው ፡
የወጣ ፡ ሙሽራ ፡ ይመስላል ፡ አምሮ ፡
ለስልሶ ፡ ቀልቶ ፡ እንዲወጣ ፡ በትን
ሣኤ ፡ ዘጉባኤም ፡ የሚነሣ ፡ ምእመን ፡
እንደ ፡ ዘንግ ፡ ተመልምሎ ፡ እንደ ፡ እሸ
ት ፡ ተፈልፍሎ ፡ ብሩህ ፡ መልአክ ፡ መስ
ሎ ፡ ነውና ። አሁን ፡ የተመቸ ። (ይት
ፌሣሕ ፡ ከመ ፡ ይርባሕ ፡ ዘይሚርድ ፡
ፍኖቶ) ፡ ኋላ ፡ ይረባ ፡ ይጠቀም ፡ ዘን
ድ ፡ ዛሬ ፡ ፍኖተ ፡ ትሩፋትን ፡ የሚጠ
በጥብ ፡ ሰው ፡ ደስ ፡ ይለዋል ። (እም
አጽናፈ ፡ ሰማይ ፡ሙፃኡ ፡ ወእስከ ፡
አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ ምእታዊ) ፡ ከምሥ
ራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ዛሬ ፡ ፍኖተ ፡
ትሩፋትን ፡ የሚጠበጥብ ፡ አንድም ፡
ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ያለ ፡
ምእመን ። አልቦ ፡ ማንሻ ። (አልቦ ፡
ዘይትኀባእ ፡ እምላህቡ) ፡ ከምሥራቅ ፡
እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ከትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡
የሚሠወር ፡ የለም ፡ ከአራዊት ፡ ከአ
ንስሳት ፡ በቀር ፡ አሞራ ፡ የበተነው ፡
ጅብ ፡ የጎተተው ፡ ሁሉ ፡ ይነሣልና ፡
እንድም ፡ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕ
ራብ ፡ ከላህበ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚ
ሠወር ፡ የለም ። የሚነሣው ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ሲያድርበት ፡ ነውና ፡ ሰባት ፡
ቀን ፡ እንደ ፡ ከፍያ ፡ ያረበርብበታ
ልና ፡ (ሕጉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡
እንደ ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ አሪት ፡ ብለህ ፡
ጨርስ ።

፲፭ ፡ ወንብርከሰ ፡ የኀቅፀ ።

ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ ኑሮ ፡ የፈጠረው ፡
ፍጥረት ፡ የሠራው ፡ ሥርዓት ፡ እን
ዲህ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነው ። ገብር
ከኒ ፡ እኔ ፡ ባርያህም ፡ እጠብቀዋለሁ ።
እንድም ፡ ይትፌቶ ፡ ይጥዕም ፡ ትላ
ለህ ፡ እንጂ ፡ ሕግ ፡ መጠበቁን ፡ አለ ፡
ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ እነማኒ ፡ አይጠብ
ቁትም ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ባሪያህስ ፡ እጠ
ብቀዋለሁ ።

ወበዓቂቦቱ ፡ ይትዓሠይ ፡ ብዙኃ ።

እትዓሠይ ፡ በመጠበቁም ፡ ብዙ ፡ ዋጋ ፡
አገኛለሁ ። እትኃሠይ ፡ ያለ ፡ እንደ
ሆን ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

፲፪ ፡ ለስሒት ፡ መኑ ፡ ይሌብዋ ።

አንተስ ፡ ሕግ ፡ መጠበቅህ ፡ ሐት ፡
ነዋ ፡ የጉልማሳ ፡ ሚስት ፡ መንሣትህ ፡
ጉልማሳ ፡ ማስገደልህ ፡ ነውን ፡ ትለኝ ፡
እንደሆን ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ ስሕተትንማ ፡
ማን ፡ ልብ ፡ ያደርጋታል ። በንስሐ ፡



ከታረቅኸ ፡ ብሎ ፡ ዕርቅ ፡ ደም ፡ ያደ
ርቅ ፡ እንዲሉ ። እንድም ፡ ኀጢአትን ፡
ከተሠራች ፡ በኋላ ፡ ፍዳ ፡ ስታመጣ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ አስቀድሞ ፡ ሳትሠራ ፡
ማን ፡ ልብ ፡ ያደርጋታል ።

እምኅቡኣትየ ፡ አንጽሐኒ ።

ስለዚህ ፡ እኔ ፡ ከማላውቀው ፡ አንተ ፡
ከምታውቀው ፡ አንድም ፡ እኔና ፡ አን
ተ ፡ ከምናውቀ ፡ ሌላ ፡ ከማያውቀው ፡
ኃጢአቴ ፡ ንጹሕ ፡ አድርገኝ ።

፲፫ ፡ ወእምነኪር ፡ መሐኮ ፡ ለገብርከ ።

ሌላውም ፡ ከሚያውቀው ፡ ኃጢአቴ ፡
አንድም ፡ ከሰይጣን ፡ ከእደ ፡ አረሚ ፡
ጠብቀኝ ፡ አድነኝ ።

እመሰ ፡ ኢቀነዩኒ ፡ ውእተ ፡ ጊዜ ፡ ንጹሐ ፡ እከውን ።

ሰይጣን ፡ እደ ፡ አረሚ ፡ ካልሰለጠኑ
ብኝ ፡ እጅ ፡ ካላደረጉኝ ፡ ከጥቃቅኑ ፡
ኃጢአቴ ፡ ንጹሕ ፡ እሆናለሁ ፡ ተዐቀብ ፡
እምንዑሳት ፡ ከመ ፡ ኢትደቅ ፡ ውስተ ፡
ዓቢያት ፡ እንዲል ።
እንድም ፡ ወእምነኪር ፡ መሐከ ፡ ለገብ
ርከ ። ከጥቃቅኑ ፡ ኃጢአቴ ፡ ጠብቀኝ ፡
አድነኝ ። እመሰ ፡ ኢቀነዩኒ ፡ ጥቃቅኑ ፡
ኀጢአት ፡ ካልሠለጠነብኝ ።

ወእነጽሕ ፡ እምዓቢይ ፡ ኀጢአትየ ።

ንጹሕ ፡ እከውንና ፡ እነጽሕ ፡ አንድ ፡
ወገን ፡ ከዶጋጉ ፡ ኃጢአቴ ፡ ንጹሕ ፡
እሆናለሁ ።

፲፬ ፡ ወይከውን ፡ ሥሙረ ፡ ቃለ ፡ አፉየ ።

በንደበቴ ፡ የለመንሁት ፡ልመና ፡ ያማ
ረ ፡ የተወደደ ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ወድዶ
ይቀበለዋል ።

ወኀሊናሁ ፡ ለልብየኒ ፡ ቅድሜከ ፡ ውእቱ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ መሥራቴ ፡ ይቅ
ርና ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ የሠራሁት ፡
ኀጢአቴም ፡ ሁልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ ነው ፡
አስበዋለሁ ። ይኸውም ፡ ከዶግነት ፡
አያወጣውም ፡ ኀጢአቱን ፡ እሱ ፡ ያስ
በው ፡ እንደሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ አያ
ስብበትምና ። ተዘከር ፡ አንተ ፡ ቅድመ ፡
አበሳከ ፡ ከመ ፡ ኢይዝክር ፡ ብከ ፡ ፈጣ
ሪከ ፡ እንዲል ።

እግዚኦ ፡ ረዳኢየ ፡ ወመድኀንየ ።

ፈጣሪዬ ፡ ረዳቴ ፡ ድኅነቴን ፡ የምታደ
ርግልኝ ፡ አንድም ፡ ድኅነቴን ፡ ረድ
ኤቴን ፡ የምታደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ።

## መዝሙር ፡ ፲፱ ።

፩ ፡ ይስማዕከ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዕለተ ፡ ምን
ዳቤከ ።

ስለሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ። ሕዝቅ
ያስ ፡ በመከራህ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡
ልመናህን ፡ ይስማህ ፡ ይሉታል ፡ ነቢ
ያት ፡ ካህናት ። እንድም ፡ እራሱን ፡ እር
ቆ ፡ ይናገራል ፡ ዳዊት ፡ በመከራህ ፡ ቀን ፡
እግዚአብሔር ፡ ልመናህን ፡ ይስማህ ።

ወይቁምከ ፡ ስሙ ፡ ለአምላከ ፡ ያዕቆብ ።

የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ስሙ ፡ እንደ ፡ ዋስ ፡ እንደ ፡ ጠበቃ ፡ ሁኖ ፡ ይቁምልህ ።

፪ ፤ ወይፈኑ ፡ ለከ ፡ ረድኤተ ፡ እመቅደሱ ።

ከሰማያዊት ፡ መቅደሱ ፡ ከምድራዊት ፡ መቅደሱ ፡ ያለ ፡ ረድኤቱን ፡ ይላክልህ ። እንድም ፡ በሰማያዊት ፡ መቅደሱ ፡ በምድራዊት ፡ መቅደሱ ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረድኤቱን ፡ ይላክልህ ።

ወእምጽዮን ፡ ይትወከፍከ ።

ከሰማያዊት ፡ መቅደሱ ፡ ከምድራዊት ፡ መቅደሱ ፡ በሚገኝ ። አድሮ ፡ በሚኖር ፡ ረድኤቱ ፡ ይቀበልህ ። እንድም ፡ በሰማያዊት ፡ መቅደሱ ፡ በምድራዊት ፡ መቅደሱ ፡ አድሮ ፡ የሚኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቀበልህ ።

፫ ፤ ወይዘከር ፡ ለከ ፡ ኵሎ ፡ መሥዋዕተከ ።

መሥዋዕትህን ፡ ሁሉ ፡ ይቀበልልህ ።

ወያጥልል ፡ ለከ ፡ ቍርባነከ ።

መሥዋዕትህን ፡ ወድዶ ፡ ይቀበልልህ ። ወርቅ ፡ ብር ፡ ከሰጠ ፡ እሸት ፡ ሥጋ ፡ የሰጠ ፡ ይወደዳልና ። ጸሎቱ ፡ ለጻድቅ ፡ ያጠልሉ ፡ ለምሥዋዕ ፡ እንዲል ።

፬ ፤ የሀብከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘከመ ፡ ልብከ ።

እግዚአብሔር ፡ የልቡናህን ፡ ይስጥህ ። ምነው ፡ ልብማ ፡ ክፋውንስ ፡ በጎውን ፡ ያስብ ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ ክፋውን ፡ ትቶ ፡ በጎውን ፡ ይስጥህ ። እንድም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ያለ ፡ በደዌ ፡ ነውና ፡ ክፋትን ፡ ያስብናል ።

ወይፈጽም ፡ ኵሎ ፡ ምክረከ ።

ወድደህ ፡ የለመንኸውን ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽምልህ ።

፭ ፤ ወንትፈሣሕ ፡ በአድኅኖትከ ።

ይህ ፡ ተደርጎልህ ፡ እኛንም ፡ ደስ ፡ ይበለን ። እንድም ፡ ይህ ፡ የተደረገልህ ፡ እንደሆነ ፡ ንትፈሣሕ ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

ወንዓቢ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

በፈጣሪያችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ አምነን ፡ ከብረን ፡ገንነን ፡ እንኖራለን ፡ ይላሉ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ።

ወይፈጽም ፡ ለከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኵሎ ፡ ስእለተከ ።

እግዚአብሔር ፡ ልመናህን ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽምልህ ።

፮ ፤ ይእዜ ፡ አእመርኩ ፡ ከመ ፡ አድኃኖ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመሲሑ ።

ከነቢያት ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ እያንዳንዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀብቶ ፡ ያነገሠው ፡ ሕዝቅያስን ፡ እንደ ፡ አዳነው ፡ ዛሬ ፡ አወቅሁ ፡ ይላል ።

ወይሰጠዎ ፡ እምሰማዩ ፡ መቅደሱ ።

ከሰማያዊት ፡ መቅደሱ ፡ በተገኘ ፡ ረድኤቱ ፡ እንዲያድነው ፡ አወቅሁ ።

በኃይለ ፡ አድኅኖተ ፡ የማኑ ።

ወዳጆቹ ፡ አብርሃም ፡ ይሥሐቅ ፡ ያዕቆብን ፡ በሚታደግበት ፡ በትድግናው ፡ ሥልጣን ፡ ኃይል ። እንድም ፡ በየማኑ ፡ ኃይለ ፡ አድኅኖቱ ። ትድግናውን ፡ በሚገልጽበት ፡ ሥልጣኑ ፡ ኃይል ።



፳ ፤ እሙንቱሰ ፡ በአፈራስ ፡ ወበሠረገላት ።

ሰ ፡ ሥራ ፡ አልያዘም ፡ የኋላውን ፡ ሲያይ ፡ የገባ ፡ ነው ። እነ ፡ ሰናክሬም ፡ በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡ መጥተው ፡ ነበረ ።

ወንሕነሰ ፡ ንዓቢ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

እኛ ፡ ግን ፡ በፈጣሪያችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ አምነን ፡ ከብረን ፡ ገንነን ፡ እንኖራለን ።

፳፩ ፤ እሙንቱሰ ፡ ተዓቅፁ ፡ ወወድቁ ።

እነሱ ፡ ግን ፡ ፈጽመው ፡ ጠፉ ። ተዓቅፁ ፡ በለኪሶን ፡ ወወድቁ ፡ በነነዌ ። እንድም ፡ ተዓቅፁ ፡ በሥጋ ፡ ወወድቁ ፡ በነፍስ ፡ ጠፉ ። ኢሳ ፡ ፴፫ ፡ ፲፯ ።

ወንሕነሰ ፡ ተንሣእነ ፡ ወረታዕነ ።

እኛ ፡ ግን ፡ ፈጽመን ፡ ጸናን ። ተዓቅፁ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ተንሣእነ ፡ ወድቁ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ረታዕነ ፡ አለ ። ጠዋይኒ ፡ ኢይክል ፡ ረቲዓ ፡ እንዲል ። መክ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ።

፳፪ ፤ እግዚኦ ፡ አድኅኖ ፡ ለንጉሥ ።

አቤቱ ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስን ፡ አድነው ። የትንቢት ፡ ነገር ፡ ከዚያ ፡ አዳነው ፡ ከዚህ ፡ አድነው ፡ አለ ። እንድም ፡ ከዚያ ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ ሁኖ ፡ ይታየዋልና ፡ አድኅኖ ፡ አለ ። ጊዜው ፡ ገና ፡ ነውና ፡ ከዚህ ፡ አድኅኖ ፡ አለ ።

ወስምዓነ ፡ በዕለተ ፡ ንጼውዓከ ።

እኛም ፡ እንዲህ ፡ ብለን ፡ በለመንህ ፡ ጊዜ ፡ ልመናችንን ፡ ስማን ፡ ይላሉ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ።

## መዝሙር ፳ ።

፩ ፤ እግዚኦ ፡ በኃይልከ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ንጉሥ ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ። አቤቱ ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ባደረግህለት ፡ ኃይል ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

ወብዙኃ ፡ ይትሐሠይ ፡ በአድኅኖትከ ።

በትድግናህም ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ። ይትዓሠይ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ብዙ ፡ ዋጋ ፡ ያገኝበታል ።

፪ ፤ ፍትወተ ፡ ነፍሱ ፡ ወሀብኮ ።

ሰውነቱ ፡ ወድዶ ፡ የለመነውን ፡ ሰጠኸው ።

ወስእለተ ፡ ከናፍሪሁ ፡ ኢከላእኮ ።

ባንደበቱ ፡ የለመነውን ፡ ልመና ፡ አላስቀረህበትም ።

፫ ፤ እስመ ፡ በጻሕኮ ፡ በበረከት ፡ ሠናይ ።

ከበጎ ፡ ወሮታ ፡ በበጎ ፡ ረድኤት ፡ ደርሰህለታልና ። ሰናክሬም ፡ ዓመተ ፡ ኅድገትን ፡ ዓይቶ ፡ ቢመጣ ፡ ጥቂቱን ፡ አበርክቶለታልና ። ብላዕ ፡ ዘንተ ፡ ዓመተ ፡ ዘዘራዕከ ፡ ወበካልእ ፡ ዓመት ፡ ዘአትረፍከ ፡ ወበሣልስ ፡ ዓመት ፡ ትዘርዕ ፡ ወተዓርር ፡ እንዲል ። ኖኅ ፡ ልጆቹን ፡ ይዞ ፡ ከመርከብ ፡ ቢገባ ፡ ሎጥም ፡ ልጆቹን ፡ ይዞ ፡ ከዋሻ ፡ ቢገባ ፡ ጥቂቱን ፡ አበርክቶ ፡ እንደመገባቸው ። ዘፍ ፡ ፯ ፡ ፩-፳፬ ። ፰ ፡ ፩ ፡ ፳፪ ። ፱ ፡ ፩ ፳፱ ። ፲፱ ፡ ፩-፴፰ ።

ወአንበርከ ፡ አክሊለ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ ዘእምዕንቍ ፡ ክቡር ።

ከከበረ ፡ ዕንቍ ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ አክ

ሊልን ፡ ማለት ፡ የዕንቍ ፡ ፈርጥ ፡ ያለ
በት ፡ ዘውድን ፡ ደፋህለት ። ሰናክሬም ፡
ጌታ ፡ የመብረቅ ፡ የነጐድጓድ ፡ ድምፅ ፡
እያሰማው ፡ ሕዝቅያስ ፡ መጣብኝ ፡ እ
ያለ ፡ ሲሸሽ ፡ ዘውዱ ፡ ወልቆ ፡ ወድቆ ፡
ነቢያት ፡ ካህናት ፡ አግኝተው ፡ ይህላን
ተ ፡ ይገባል ፡ ብለው ፡ ሰጥተውታልና ።

፬ ፡ ሐይወ ፡ ሰአለከ ፡ ወወሀብኮ ፡ ፪ ፡ ነገ ፡ ፰ ፡ ፯ ።

ዕድሜ ፡ ለመነህ ፡ ሰጠኸው ። እንድም ፡
ለጌታ ፡ ነው ፡ የባሕርይ ፡ አምላክነትን ፡
ለመነህ ፡ ሰጠኸው ።

ለንዋኅ ፡ መዋዕል ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ነዋኅ ፡ መዋዕለ ፡ ሲል ፡ ነው ። ረጅም ፡
ወራትን ፡ ሰፊ ፡ ዘመናትን ፡ ሰጠኸው ፡
ምነው ፡ ወናሁ ፡ ወሰኩከ ፡ ዲበ ፡ ክራ
ማቲከ ፡ ፲ ፡ ወ፭ ፡ ዓመተ ፡ እንዲል ።
የሰጠውማ ፡ ዓሥራ ፡ አምስት ፡ አይ
ደለምን ፡ ቢሉ ፡ ያው ፡ ሲመላለስ ፡ ይኖ
ራልና ። እንድም ፡ የሕዝቅያስ ፡ ዘመኑ ፡
በደዌ ፡ ተከፍሎበታል ፡ ያሉ ፡ እንደ
ሆነ ፡ የተመቸ ፡ መለሰለት ፡ ሲል ፡ ነው ።
አልተከፈለበትም ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡
የሰናክሬምን ፡ ጨመረለት ፡ ማለት ፡
ነው ። ኢሳ ፡ ፴፰ ፡ ፭ ።

፭ ፡ ዐቢይ ፡ ክብሩ ፡ በአድኅኖትከ ።

በትድግናህ ፡ ያገኘው ፡ የሕዝቅያስ ፡
ክብሩ ፡ ፍጹም ፡ ነው ።

ክብረ ፡ ወስብሐተ ፡ ወሰኮ ።

ክብረ ፡ የሰናክሬምን ፡ ወስብሐተ ፡ የ
መሮዳህን ፡ ጨመርህለት ።

፮ ፡ እስመ ፡ ወሀብኮ ፡ በረከተ ፡ ዘለዓለመ ፡ ዓለም ።

ያያቶቹ ፡ ያባቶቹን ፡ የነዳዊት ፡ የነሰሎሞ
ንን ፡ ሰጥተኸው ፡ ነበርና ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡
የሰናክሬምን ፡ የመሮዳህን ፡ ጨመርህ
ለት ። ታሪክ ፡ ሰሎሞን ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡
ሲገባ ፡ እስከትሎት ፡ የሚገባ ፡ ሦስት ፡
መቶ ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡
እፋ ፡ ነበረው ። ፈርዖን ፡ ኒካዑ ፡ ለሮ
ብዓም ፡ ረድቶ ፡ ኢዮርብዓምን ፡ ወግቶ ፡
ሲሔድ ፡ ግብዕ ፡ ይዞት ፡ ሔዷል ፡ ናቡ
ከደነጾር ፡ ፈርዖንን ፡ ወግቶ ፡ ባቢሎን ፡
ዘግብዕ ፡ አሰኝቶ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከም
ስት ፡ ወር ፡ ኑሮ ፡ ሲሔድ ፡ ፋርስ ፡ ባቢሎን ፡
አውርዶታል ፡ ሕዝቅያስ ፡ ከደዌው ፡
በተፈወሰበት ፡ ቀን ፡ ፀሐይ ፡ ግብሯን ፡
ለውጣለች ፡ መሮዳህ ፡ ዛሬ ፡ ፀሐይ ፡
ግብሯን ፡ የለወጠችበት ፡ ምንድነው ፡
አለ ። የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስ ፡
ከደዌው ፡ የተፈወሰበት ፡ ቀን ፡ ነው ፡
አሉት ። ለዚህስ ፡ ሊገብሩለት ፡ ይገ
ባል ፡ ብሎ ፡ ይህ ፡ ያባቶችህ ፡ የዳዊት ፡
የሰሎሞን ፡ ገንዘብ ፡ ይህ ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡
ነው ፡ ብሎ ፡ ልኮለታል ፡ ወፈነወ ፡ መሮ
ዳህ ፡ ወልደ ፡ በልዳን ፡ መጻሕፍተ ፡ ወ
መሐና ፡ ዘምስለ ፡ ብዙኅ ፡ እምኃ ፡ ኀበ ፡
ሕዝቅያስ ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ ፡ እንዲል ።

ወታስተፌሥሖ ፡ በሐሤት ፡ ገጽከ ።

ያንተ ፡ በለሟል ፡ በማድረግ ፡ ደስ ፡
ታሰኘዋለህና ።

፯ ፡ እስመ ፡ ተወከለ ፡ ንጉሥ ፡ በእግዚአብሔር ።

ሕዝቅያስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምኗ
ልና ።



ወኢይትሀወክ ፡ በምሕረቱ ፡ ለልዑል ።

ቸርነቱን ፡ አግኝቶ ፡ በማግኘት ። እን
ድም ፡ ቸርነቱን ፡ አጥቶ ፡ በማጣት ፡
አይታወክምና ።

፰ ፡ ትርከበሙ ፡ እዴከ ፡ ለኵሎሙ ፡ ፀርከ ።

ሥልጣንህ ፡ ጠላቶችህን ፡ ሁሉ ፡ ታግ
ኛቸው ።

ወትትረከበሙ ፡ እዴከ ፡ ለኵሎሙ ፡ ጸላእትከ ።

እንዲያው ፡ በዶዋን ፡ ትለኝ ፡ እደሆን ፡
መቅሠፍትን ፡ ይዞ ፡ ታገኛቸው ፡ እንጂ ፡
በዶዋንማ ፡ ለምና ።

፱ ፡ ወትረስዮሙ ፡ ከመ ፡ እቶነ ፡ እሳት ፡ ለጊዜ ፡
ገጽከ ።

መዓትህን ፡ የምትፈጽምበት ፡ ፊት
ህን ፡ በምትገልጽበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡
እሳት ፡ ምድጃ ፡ ታድርጋቸው ። እን
ድም ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ እቶን ፡ ይላል ፡
እሳት ፡ ምድጃን ፡ እንዲያቃጥል ፡ ታጥ
ፋቸው ።

እግዚእ ፡ በመዓትከ ፡ ሁኮሙ ፡ ወትብልዖሙ ፡
እሳት ።

አቤቱ ፡ በመዓትህ ፡ አውካቸው ፡ ጦር
ህም ፡ ታጥፋቸው ።

፲ ፡ ወፍሬሆሙኒ ፡ ሠዓር ፡ እምድር ።

ልጆቻቸውን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አጥፋ
ቸው ።

ወዘርዖሙኒ ፡ እምእጓለ ፡ እመሕያው ።

የልጅ ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ከሰው ፡ ለይ
ተህ ፡ እንድም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አጥፋ
ቸው ። እንድም ፡ (ወፍሬሆሙኒ ፡ ሠ
ዓር ፡ እምድር) ። ልጆቻቸውን ፡ የል
ጅ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አ
ጥፋ ፡ (ወዘርዖሙኒ ፡ እምእጓለ ፡ እመ
ሕያው) ፡ ወገኖቻቸውን ፡ ከሰው ፡ ለይት
ህ ፡ አጥፋባቸው ።

፲፩ ፡ እስመ ፡ ሜጠጡ ፡ እኩየ ፡ ላዕሌከ ።

የነሱን ፡ በደል ፡ ወደኔ ፡ መልሰዋታል
ና ። በኑ ፡ ግልፎ ፡ ዘያድኅን ፡ እምእዴየ ፡
በኢየሩሳሌም ፡ ማለት ፡ ጥንቱን ፡ እነ ፡
ሕዝቅያስ ፡ ጣዖት ፡ ያመልኩሉ ፡ ማለ
ት ፡ ነውና ። መዝ ፡ ፲፲ ፡ ፭ ። ፺፱ ፡ ፭ ።

ወሐለዩ ፡ ምክረ ፡ እንተ ፡ ኢይክሉ ፡ ገቢሮ ።

መፈጸም ፡ መወሰን ፡ የማይቻላቸውን ፡
አሰቡ ፡ አስበውን ፡ ቀሩ ። በኑ ፡ ግልፎ ፡
ዘያድኅን ፡ እምእዴየ ፡ በኢየሩሳሌም ፡
አሉ ፡ እንጂ ። እግዚአብሔርን ፡ ጣዖት ፡
ማለት ፡ የማይፈጸም ፡ ሐሳብ ፡ ነውና ።

፲፪ ፡ ወታገብኦሙ ፡ ድኅሬሆሙ ።

እኔ ፡ ብቸኩል ፡ እንዲህ ፡ አላለሁ ፡ እ
ንጂ ፡ አንተስ ፡ እንዲህ ፡ እንደተቀማ
ጠሉ ፡ አትተዋቸውም ፡ አድን ፡ እነስ ፡
አድር ፡ እነስ ፡ ታደርጋቸዋለህ ። ድል ፡
ተነሥተው ፡ እኔን ፡ ከመከተል ፡ ወደ ፡
ኋላ ፡ እንዲቀሩ ፡ ታደርጋቸዋለህ ።

ወታስተደሉ ፡ ገጸሙ ፡ ለጊዜ ፡ መዓትከ ።

መዓትህን ፡ በምትፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡
ሰውነታቸውን ፡ ለመዓትህ ፡ ጥርጊያ ፡
ታደርጋለህ ። ጽሕርት ፡ ትኩል ፡ ማእከ
ለ ፡ እሳት ፡ ወገጹ ፡ ትኩል ፡ ማእከለ ፡ ፀ
ሜን ፡ እንዲል ።

2014 04 17

፳፫ ተለዓልኬ ፡ እግዚኦ ፡ በኃይልከ ።

አቤቱ ፡ እኔን ፡ አድነህ ፡ ለናከሬምን ፡ አጥፍተህ ፡ ልዕልናህን ፡ ገለጽህ ።

ንሴብሕ ፡ ወንዜምር ፡ ለጽንዕከ ።

ለከሃሊነትህ ፡ ምስጋና ፡ እናቀርባለን ። (በጽንዕከ) ፡ በከሃሊነትህ ፡ አንተን ፡ እናመሰግናለን ። (ጽንዓከ) ፡ ከሃሊነትህን ፡ እናመሰግናለን ፡ ንሴብሕ ፡ በቃል ። ንዜምር ፡ በልቡና ። አንድም ፡ (ንሴብሕ) ፡ በንባብ ፡ (ንዜምር) ፡ በዜማ ። አንድም ፡ (ንሴብሕ) ፡ በዜማ ፡ (ንዜምር) ፡ በበገና ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዘላለሙ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ።

አሜን ።

መዝሙር ፡ ፳፩ ።

፩ አምላኪየ ፡ አምላኪየ ፡ ነጽረኒ ፡ ወለምንት ፡ ኀደጉከኒ ። ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፵፮ ። ማር ፡ ፲፭ ፡ ፴፬ ።

በአቤሴሎም ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግሮታል ። የጌታም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ የአርሞንኤም ፡ ራሱ ፡ ራእስ ፡ እንዲባል ። የደብረ ፡ ዘይትም ፡ ራሱ ፡ አርዴስ ፡ ይባላል ። በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ሲወጣ ፡ እየወደቀ ፡ እየተነሣ ፡ እየሰገደ ፡ እየማለደ ፡ ተናግሮታል ። ፈጣሪዬ ፡ ፈጣሪዬ ፡ በዓይነ ፡ ምሕረትህ ፡ እዩኝ ፡ ተመልከተኝ ። በመከራውም ፡ አትጣለኝ ። አንድም ፡ እዩኝ ፡ ተመልከተኝ ፡ እንጂ ፡ በመከራው ፡ ለምን ፡ ትጥለኛለህ ። ለዕብራውያን ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ ልማዳቸው ፡ ነው ። አብርሃም ፡ አብርሃም ፡ አልዓዛር ፡ አልዓዛር ፡ ማርታ ፡ ማርታ ፡ እንዲል ። ዘፍ ፡ ፳፪ ፡ ፩ ። ዮሐ ፡ ፲፩ ፡ ፵፫ ። ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፵፩ ። አንድም ፡ የነፍሴ ፡ የሥጋዬ ፡ ፈጣሪ ፡ ነህ ፡ ሲል ፡ አንድም ፡ ለጊዜው ፡ ለዘላለሙ ፡ ሲል ፡ ነው ።

አንድም ፡ ጌታ ፡ በጎዱ ፡ ጋኑ ፡ ተገብቶ ፡ ተናግሮታል ። የበደለ ፡ ይክስ ፡ የቀማ ፡ ይመልስ ፡ እንዲሉ ። አዳም ፡ በበደለ ፡ እኔ ፡ ከካስሁ ፡ በኋላ ፡ ምእመናንን ፡ በመከራው ፡ ለምን ፡ ትጥልብኛለህ ። አምላኪየ ፡ ማለቱ ፡ ለነፍስ ፡ ለሥጋ ፡ ለጻድቃን ፡ ለኃጥአን ፡ ለሕዝብ ፡ ለአሕዛብ ፡ እንደ ፡ ካሠ ፡ ለማጠየቅ ፡ ነው ።

ርሑቅ ፡ እምአድኅኖትየ ፡ ቃለ ፡ ኃጢአትየ ።

ብሉዩን ፡ ይዞ ፡ ይሔዳል ፡ በኃጢአት ፡ ሳለሁ ፡ የለመንሁት ፡ ልመናዬ ፡ እኔን ፡ ከማዳን ፡ የራቀ ፡ ነው ፡ ማለተ ፡ አያድነኝም ።



፪ አምላኪየ ፡ እጸርሕ ፡ ኀቤከ ፡ ዕለትየ ፡ ወኢ ፡ ተሰጠኒ ።

ፈጣሪዬ ፡ ለኔ ፡ ብለህ ፡ በፈጠርህልኝ ፡ ቀን ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ብለምን ፡ ልመናዬን ፡ አልሰማኸኝም ።

ወሌሊትየኒ ፡ ቅድሜከ ፡ ወኢሐሰይከኒ ።

ለኔ ፡ ብለህ ፡ በፈጠርህልኝም ፡ ሌሊት ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለመንሁ ። በቸርነትህ ፡ አላሰብኸኝም ። ዕለትየ ፡ ሌሊትየ ፡ ማለቱ ፡ መዓልትንና ፡ ሌሊትን ፡ መፍጠሩ ፡ ለሰው ፡ ብሎ ፡ ነውና ፤ ወበእንቲአከሙ ፡ ፈጠርክዋ ፡ ለዓለም ፡ እንዲል ።

፫ ወአንተሰ ፡ ውስተ ፡ ቅዱሳኒከ ፡ ተኀድር ፡ ስቡሐ ፡ እስራኤል ።

ውስተ ፡ ቅዱሳኒከሰ ፡ ተኀድር ፡ አንተ ፡ ስቡሐ ፡ እስራኤል ፡ ብለህ ፡ አቅና ። በወዳጆችህ ፡ በአብርሃም ፡ በይስሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ ግን ፡ ጽኑዓ ፡ እስራኤል ፡ ክቡረ ፡ እስራኤል ፡ የምትሆን ፡ አንተ ፡ አድረህባቸው ፡ ትኖር ፡ ነበር ።

፬ ኪያከ ፡ ተወከሉ ፡ አበዊነ ።

አባቶቻችን ፡ ባንተ ፡ አምነው ፡ ነበር ፡

ተወከሉከኒ ፡ ወአድኀንኮሙ ።

ባንተ ፡ አምነው ፡ ነበር ። አንተም ፡ ከመከራ ፡ ሥጋ ፡ ከመከራ ፡ ነፍስ ፡ አድነሃቸው ፡ ነበር ።

፭ ኀቤከ ፡ ጸርሑ ፡ ወድኅኑ ።

ወዳንተ ፡ መልሰው ፡ ለመኑ ፡ ከመከራውም ፡ ዳኑ ።

ኪያከ ፡ ተወከሉ ፡ ወኢተኀፍሩ ።

ባንተ ፡ አመኑ ፡ መከራ ፡ አግኝቷቸው ፡ በመከራው ፡ አላፈሩም ።

፮ አንሰ ፡ ዕፄ ፡ ወኢኮ ፡ ሰብእ ።

አንተስ ፡ ብታምንብኝ ፡ እንደለዚያ ፡ አድንህ ፡ አልነበረምን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ እኔስ ፡ እንስሳ ፡ ነኝ ። ባለ ፡ አእምሮ ፡ ሰው ፡ አይደለሁም ። አእምሮ ፡ ቢኖረኝ ፡ የጉልማሳ ፡ ሚስት ፡ በነጣሁ ፡ ጉልማሳ ፡ ባስገደልሁ ፡ ነበርን ።

ምኑን ፡ በኀበ ፡ ሰብእ ፡ ወትሑት ፡ በውስተ ፡ሕዝብ ።

በነ ፡ አቤሴሎም ፡ ዘንድ ፡ የተናቅሁ ፡ በሰራዊቱም ፡ ዘንድ ፡ የተዋረድሁ ፡ ነኝ ።

፯ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይሬእዩኒ ፡ ይትቃጸቡኒ ።

የሚያዩኝ ፡ ሁሉ ፡ የጉልማሳ ፡ ሚስት ፡ የነሣ ፡ ጉልማሳ ፡ ያስገደለ ፡ ይህ ፡ አንጂ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ይጠቃቀሱብኛል ።

ይብሉ ፡ በከናፍሪሆሙ ፡ ወየሐውሱ ፡ ርእሶሙ ። ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፯ ። ኤር ፡ ፶፰ ፡ ፳፮ ።

እንዘ ፡ ይሔውሱ ። ራሳቸውን ፡ እየነቀነቁ ፡ ባንደበታቸው ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ። ሉቃ ፡ ፲፰ ፡ ፴፯ ።

፰ ተወከለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ለያድኅኖ ። ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፵፫ ። ሉቃ ፡ ፳፱ ፡ ፴፮ ።

በእግዚአብሔር ፡ አመነሁ ፡ ይላል ፡ እስኪ ፡ ያድነው ።

ወያድኅኖ ፡ እመ ፡ ይፈቅዶ ።

ይወድደው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስኪ ፡ ያድነው ፡ እያሉ ፡ ይጠቃቀሱብኛል ።

እንድም፡(እንስ፡ዕፂ፡ወእኮ፡ሰብእ)፡
ንህብ፡ነኝ፡በዘርእ፡ብእሲ፡የተጸነ
ስሁ፡አይደለሁም ። ንህብ፡የሚወ
ለድ ። ወተእነዝር፡እግዝእቶን፡ለእ
ንህብት፡እንዲል ። የንብ፡እውራ፡ሲ
ሞኝ፡በድምፅ፡ነው፡የጌታም፡ጽንስ፡
በድምፅ፡ገብርኤል፡ነውና ።ከመ፡ንህ
ብ፡ዘእምቃል፡ንባብ፡እንዲል ። ቅዳ፡ማር፡
፯ ፡ ፱ ። እንድም፡(እንስ፡ዕፂ)፡ወላፍ፡
ትል፡ነኝ፡(ወእኮ፡ሰብእ)፡ዕሩቅ፡
ብእሲ፡አይደለሁም ። ይህን፡ወላፍ፡
ትል፡ዓሣ፡ይወድደዋል ።ነጋድያን፡
አምጥተው፡በመቃጥን፡አድርገው፡
ከባሕር፡ይጥሉታል ። ያንን፡ሊመ
ገብ፡ሲመጣ፡በመቃጥን፡እየጠለፉ፡
ከወደብ፡ይጥሉታል ። ጌታም፡በዕ
ለተ፡ዓርብ፡ተሰቅሎ ። አምላኪየ፡
አምላኪየ፡ሲል፡ዲያብሎስ፡ሰምቶ ።
እኔ፡የባሕርይ፡አምላክ፡መስሎኝ ።
ለካ፡ዕሩቅ፡ብእሲ፡ኑሯል ። ይህማ፡
የላሜ፡ልጅ፡ያውራዬ፡ውላጅ፡አይ
ደለምን፡የዕሩቅ፡ብእሲ፡ነፍስ፡ያለኔ፡
ሥልጣን፡ትለያለችን፡ብሎ፡ደፋር፡
ነውና፡የጌታን፡ነፍስ፡ከሥጋው፡
ለመለየት፡እስበ፡ቀረበ፡በነፋስ፡እው
ታር፡ወጥሮ፡በእሳት፡ዛንጅር፡ዓሥሮ
መኑ፡መኑ፡እያሰኘ፡አስቀባጥሮታል ።
ወላፍ፡ትል፡የትስብእት፡መቃጥን፡
የመለኮት ። (ምኑን፡በኀበ፡ሰብእ)፡
በሐና፡በቀያፋ፡ዘንድ፡የተናቅሁ፡
ነኝ፡(ወትሑት፡በውስተ፡ሕዝብ)፡
በሕዝቡም፡ዘንድ፡የተዋረድሁ፡ነኝ ።

(ዘሎሙ፡እለ፡ይሬእዩኒ፡ይትቃፀ
ቡኒ)፡የሚያዩኝ፡ሁሉ፡አ፡ዘይነሥቶ፡
ለቤተ፡መቅደስ፡ወያነሥእ፡በሠሉ
ስ፡ዕለት፡እያሉ፡ይጠቃቀሱብኛል ።
(ይብሉ፡በከናፍሪሆሙ፡ወየሐውሱ፡
ርእሶሙ)፡ራሳቸውን፡እየነቀነቁ፡ባን
ደበታቸው፡እንዲህ፡ይላሉ ። ወእለ፡
የኃልፉ፡ፍኖተ፡ይጸርፉ፡ላዕሌሁ፡
እንዘ፡የሐውሱ፡ርእሶሙ፡እንዲል ።
ማቴ፡፳፯፡፴፱ ። (ተወከለ፡በእግዚአብ
ሔር፡ለያድኅኖ)፡የእግዚአብሔር፡
የባሕርይ፡ልጅ፡ነኝ፡ይላል፡እስኪ
ያድነው ።(ወያድኅኖ፡እመ፡ይፈቅዶ)፡
ስንኳን፡ይወልደው፡ይወድደው፡
እንደሆነ፡እያሉ፡ይጠቃቀሱብኛል ።

፱ ፡ እስመ፡አንተ፡አውጻእከኒ፡እምከርሥ ።
ከናቴ፡ማሕፀን፡አንተ፡አወጣኸኝ ።

ወተወከልኩ፡እንዘ፡ሀሎኩ፡ውስተ፡እጥባተ፡
እምየ ።

በናቴ፡ማሕፀን፡ሳለሁ፡ባንተ፡አመ
ንሁ ። እትብቱን፡እየጠባ፡ያድጋልና፡
እጥባት፡አለው ።

፲ ፡ ላዕሌከ፡ተገደፍኩ፡እማሕፀን ።
በናቴ፡ማሕፀን፡ሳለሁ፡ዠምሮ፡
ባንተ፡ፈቃድ፡ሰው፡ሆንሁ ። ተገደ
ፍኩ፡ማለቴ፡ከባት፡ዘር፡ከናት፡
ደም፡ተከፍሎ፡ይፈጠራልና ። ኢሳ፡
፵፮፡፫ ።

እምከርሠ፡እምየ፡አንተ፡አምላኪየ ።
ከናቴ፡ማሕፀን፡ዠምሮ፡ፈጣሪዬ፡
አንተ፡ነህ ።



፲፩ ፡ ኢትርኃቅ፡እምኔየ፡እስመ፡ትእጽፍ፡
እትመነደብ ።

እንዲህም፡ከሆነ፡በመከራው፡ልያዝ፡
ቀርቤአለሁና፡ከኔ፡አትራቅ ። እን
ድም፡ከናቴ፡ማሕፀን፡ዠምሮ፡ፈጣ
ሪዬ፡አንተ፡ነህና፡በረድኤት፡ከኔ፡
አትራቅ፡በመከራው፡ልያዝ፡ቀር
ቤአለሁና፡ስለቀረብሁ ።

እስመ፡አልቦ፡ዘይረድእኒ ።

የሚረዳኝ፡የለምና፡ስላልኖረ ።

፲፪ ፡ ዓገቱኒ፡አልሕምት፡ብዙኃን ።

እነ፡አቤሴሎም፡ከበቡኝ፡ግብረ፡
እንስሳ፡ይሠራሉና፡በግብራቸው፡
አልሕምት፡አላቸው ።

ወእጎዙኒ፡አሥዋር፡ሥቡሐን ።

ያልታሹ፡ገቾች፡ያዙኝ ። ያልታሸ፡
ገች፡ሞፈር፡ቀንበር፡ሠብሮ፡እንዲ
ሔድ፡እለ፡አቤሴሎምም፡ሦስቱን፡
ሕገጋት፡አፍርሰዋልና ። ምን፡ጊዜ፡
ይዘውታልና፡አኀዙኒ፡አለ፡ቢሉ፡
አግኝተነው፡ይዘነው፡ስላሉ ።

፲፫ ፡ ወአብቀዉ፡አፉሆሙ፡ላዕሌየ ።
ከመ፡አንበሳ፡ዘይትኀሣእ፡ለመሢጥ ።

ትእምርተ፡ፀብእ፡ነው ። አንበሳ፡
ከጸፈቀ፡ዱር፡ከጉደጉደ፡ምድር፡
ሁኖ፡ላምን፡ለመንጠቅ፡እንዲያፋ
ሽግ፡ነገራቸውን፡አበዙብኝ ። ኢዮ፡
፲፮፡፲ ። ፫፡፵፯ ።

፲፬ ፡ ተክዕውኩ፡ከመ፡ማይ፡ወተዘርወ፡
ኵሉ፡አዕጽምትየ ።

ተከዕውኩ፡ሲል፡ነው ። እስመ፡ተዘ

ኃሬ፡አዋልደ፡ጽዮን፡እንዲል፡ተዝ
ኀሬ፡ሲል ። ኢሳ፡፫፡፲፮ ። እንደ፡ወሀ፡
ፈሰስሁ ። ሰውነቴ፡በመከራው፡አለይ፡
አለይ፡አለ፡ማለት፡የድንጋጤ፡እን
ድም፡ከሰራዊቴ፡ለዩኝ ።

ወኮነ፡ልብየ፡ከመ፡ሰምዕ፡ዘይትመሰው፡
በማእከለ፡ከርሥየ ።

ልብየ፡በማእከለ፡ከርሥየ፡ነው ።
በሰውነቴ፡ያለ፡ልቡናዬ፡እንደ፡ሰም፡
ቀለጠ፡የድንጋጤ፡ነው ።

፲፭ ፡ ወየብሰ፡ከመ፡ገልዕ፡ኃይልየ ።

ኃይሌ፡ልምላሜ፡እንደሌለው፡እን
ደገል፡ደረቀ ።

ወጠግዐ፡ልሳንየ፡በጕርዔየ ።

እንደበቴ፡በጽምዕ፡ተያዘ ። እንድም፡
እንደበቴ፡ከጕሮሮዬ፡ጋራ፡ተጣጋ ።
ሕዝ፡፫፡፳፮ ።

ወአውረድከኒ፡ውስተ፡መሬተ፡ሞት ።

ሞት፡ገድሎ፡ወደሚጥልበት፡ወደ፡
መቃብር፡አወረድኸኝ፡ብዬ፡ነበረ ።
እንድም፡(ዓገቱኒ፡አልሕምት፡ብዙ
ኃን)፡አይሁድ፡ከበቡኝ፡አልሕምት፡
አላቸው ። ላም፡ሳሩን፡እሚዶ፡ወሀ
ውን፡ገድቦ፡የሚመግበውን፡ጌታ
ውን፡ወግቶ፡እንዲገድለው ። አይ
ሁድም፡ኅብስት፡አበርክቶ፡የሚመ
ግባቸው፡ድውይ፡የሚፈውስላቸው፡
ሙት፡የሚያነሣላቸው፡ፈጣሪያቸ
ውን፡ጠልተው፡ተመቅኝተው፡ሰቅ
ለው፡ገድለውታልና ።(ወእኃዙኒ፡አሥ
ዋር፡ሥቡሐን)፡ደናቍርት፡የሚ

ሆኑ ፡ አይሁድ ፡ ያዙኝ ። ዓገቱኒ ፡ አኃ
ዙኒ ፡ አሁን ፡ የተመቸ ፡ ከብበው ፡ ይዘ
ውታልና ። ሰው ፡ የሚደነቍር ፡ ልቡ ፡
ሲሰባ ፡ ነውና ፡ ስብሀን ፡ ለድንቍርና ፡
ምልክት ፡ አደረገው ። ወአስባሕክሙ ፡
ልበክሙ ፡ ከመ ፡ ዘያሰብሀ ፡ ላህመ ፡
ለዕለተ ፡ ጥብሕ ፡ እንዲል ። ያዕ ፡ ፭ ፡ ፭ ።
(ወአብቀዉ ፡ አፉሆሙ ፡ ላዕሌየ ፡ ከመ ፡
አንበሳ ፡ ዘጽኑሕ ፡ ለመሢጥ/ ፡ ትእም
ርተ ፡ ፀብዕ ፡ ነው ። አንበሳ ፡ ከፀፌቀ ፡
ዱር ፡ ከጕደጕደ ፡ ምድር ፡ ሆኖ ፡
ላምን ፡ ለመንጠቅ ፡ እንዲያፋሽግ ፡
ነገራቸውን ፡ አበዙብኝ ፡ /ተከዓውኩ ፡
ከመ ፡ ማይ ፡ ወተዘርወ ፡ ኵሉ ፡ አዕፅ
ምትየ/ ፡ እንደ ፡ ወሀ ፡ ፈሰስሁ ። ሰው
ነቴ ፡ በመከራው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ አለች ፡
አለ ፡ የድካም ። (ወኮነ ፡ ልብየ ፡ ከመ ፡
ሰምዕ ፡ ዘይትመሰው ፡ በማዕከለ ፡ ከር
ሥየ) ፡ በሰውነቴ ፡ ያለ ፡ ልቡናዬ ፡ እንደ ፡
ሰም ፡ ቀለጠ ። የድካም ፡ (ወየብሰ ፡
ከመ ፡ ገልዕ ፡ ኃይልየ) ፡ ኃይሌ ፡ ልም
ላሜ ፡ እንደሌለው ፡ እንደ ፡ ገል ፡
ደረቀ ፡ የድካም ፡ (ወጠግዓ ፡ ልሳንየ ፡
በጕርዔየ) ፡ አንደበቴ ፡ በዕምዕ ፡ ተያዘ ፡
ጸማዕኩ ፡ ብኋልና ። ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፳፰ ።
(ወአውረድከኒ ፡ ውስተ ፡ መሬተ ፡ ሞት) ፡
ሞት ፡ ገድሎ ፡ ወደሚጥልበት ፡ ወደ ፡
መቃብር ፡ አወረድኸኝ ፡ ሦስት ፡ መዓ
ልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃ
ብር ፡ አድሯልና ።

፲፯ ፡ ዓገቱኒ ፡ ከለባት ፡ ብዙኃን ።

እንአቤሴሎም ፡ ከበቡኝ ፡ ውሻ ፡ ከዚ
ያም ፡ ከዚያም ፡ እንዲደርስ ፡ እነሱም ፡
ከባታቸው ፡ ዕቁባት ፡ ደርሰዋልና ።

ወአኃዙኒ ፡ ማኅበርሙ ፡ ለእኩያን ።

እንአቤሴሎም ፡ በንድነት ፡ ያዙኝ ።
አግኝተነው ፡ ይዘነው ፡ ስላሉ ።

ቀነዉኒ ፡ እደውየ ፡ ወእገርየ ።

እጆን ፡ እግሬን ፡ ቸነከሩን ፡ አግኝተ
ነው ፡ እጁን ፡ እግሩን ፡ ቸንክረነው ።
ስላሉ ፡ አንድም ፡ እግሬ ፡ ከእርካብ ፡
እጄ ፡ ከዛብ ፡ እንዲለይ ፡ አደረጉኝ ።
አንድም ፡ ከሰራዊቴ ፡ ለዩኝ ፡ በእግር ፡
እንዲሔዱበት ፡ በእጅ ፡ እንዲሠፉ
በት ፡ እነሱም ፡ ግዳጁን ፡ ይፈጽሙለ
ታልና ። ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵ ፡ ፵፱ ።

፲፰ ፡ ወኈለቁ ፡ ኵሎ ፡ አዕጽምትየ ።

አጥንቴን ፡ ቈጠሩ ፡ አግኝተነው ፡
አጥንቱ ፡ እስኪታይ ፡ ገርፈነው ፡ ስላሉ ።
አንድም ፡ ለቍጥር ፡ አበቁኝ ፡ ኢዮ
አብ ፡ አቢሳ ፡ ሴት ፡ ጌትያዊ ፡ አይደ
ሉምን ፡ ምን ፡ ሰው ፡ አለው ፡ እያሉ ።

እሙንቱሰ ፡ ጠይቆሙ ፡ ወተዓወሩኒ ።

ምነው ፡ አክብር ፡ አባክ ፡ ወእመክ ፡
ያለውን ፡ አያውቁምን ፡ ትለኝ ፡ እን
ደሆን ። ዘፀ ፡ ፳ ፡ ፲፪ ። እለዚህስ ፡ አው
ቀው ፡ ቸል ፡ አሉኝ ። ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፲፪ ።

፲፱ ፡ ወተካፈሉ ፡ አልባስየ ፡ ለርእሶሙ ።

ልብሴን ፡ ለራሳቸው ፡ ተካፈሉ ።

ወተዓፀዉ ፡ ዲበ ፡ አራዝየ ።

በመጕናጸፍያየም ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ ።
ሕዝቡ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዕቃ



ቤት ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ዘርፈው ፡ አም
ጥተው ፡ ለአቤሴሎም ፡ ግዳይ ፡ ጣሉ
ለት ፡ መርቄላችኋለሁ ፡ በዕፃ ፡ እየተ
ከፈላችሁ ፡ ውሰዱት ፡ ብሏቸው ፡ ተካ
ፍለው ፡ ወስደውታልና ።

አንድም ፡ (ዓገቱኒ ፡ ከለባት ፡ ብዙኃን) ፡
አይሁድ ፡ ከበቡኝ ። ውሻ ፡ ከፋ ፡ ያወ
ጣውን ፡ መልሶ ፡ ስምግብነት ፡ ይፈል
ገዋል ፡ እነሱም ፡ አሪትን ፡ እለፈ ፡ ጥፈ ፡
ካላት ፡ በኋላ ፡ ሊሠርዋት ፡ ተገኝተዋ
ልና ፡ (ወአኃዙኒ ፡ ማኅበሮሙ ፡ ለእኩ
ያን) ፡ አይሁድ ፡ በአንድነት ፡ ያዙኝ ፡
አለ ፡ የተመቸ ፡ ከብበው ፡ ይዘዉታ
ልና ፡ (ቀነዉኒ ፡ እደውየ ፡ ወእገርየ) ፡
እጄን ፡ እግሬን ፡ ቸነከሩኝ ፡ የተመቸ ።
(ወኈለቁ ፡ ኵሎ ፡ አዕፅምትየ) ፡ አጥ
ንቴ ፡ እስኪታይ ፡ ገረፉኝ ፡ ስድስት ፡
ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ፷ስድስት ፡
ገርፈው ፡ እንደ ፡ ብራና ፡ በወዲያና ፡
በወዲህ ፡ ወጥረው ፡ ሲሰቅሉት ፡ አጥ
ንቱ ፡ ታይቶ ፡ የሚቆጠር ፡ ሁኗልና ።
አንድም ፡ በፍና ፡ ተሣልቆ ፡ አንድ ፡
ሁለት ፡ እያሉ ፡ ቈጥረውታልና ። አን
ድም ፡ ለቍጥር ፡ አበቁኝ ። ምን ፡ ሰው ፡
አለው ፡ ሐዋርያት ፡ ሰብአ ፡ አርድእት ፡
አይደሉምን ፡ እያሉ ፡ (እሙንቱሰ ፡ ጠ
ይቆሙ ፡ ወተዓወሩኒ) ፡ ምነው ፡ ኢት
ቅትል ፡ ጻድቀ ፡ ወኢታሕዩ ፡ ኃጥአ ፡
ያለውን ፡ አያውቁምን ፡ ትለኝ ፡ እን
ደሆን ፡ እነሱስ ፡ አውቀው ፡ ቸል ፡
አሉኝ ።

(ወተካፈሉ ፡ አልባስየ ፡ ለርእሰሙ) ፡
ልብሴን ፡ ለራሳቸው ፡ ተካፈሉ ። (ወ
ተዓፀዉ ፡ ዲበ ፡ አራዝየ) ፡ በመጕና
ጸፊያዬም ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ ። ዘፍየ
ቱን ፡ መጠምጠምያውን ፡ አንድ ፡ ወ
ገን ፡ መጕናጠፊያውን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡
ማማውን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ልባልባ
ውን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ አድርገው ፡ በ
ራቱ ፡ ሁሉ ፡ ዕፃ ፡ ተጣጥለው ፡ ተከፋ
ፍለውታል ፡ ቀሚሱን ፡ ግን ፡ ምንንት ፡
ልብሰ ፡ ባሕታዊ ፡ ብለው ፡ ትተዋታ
ል ። ምን ፡ ምንንት ፡ ናታ ፡ በተሐ ፡
ወርቅ ፡ ሥረ ፡ ወጥ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፡
የገበሩለት ፡ ሲያድግ ፡ የምታድግ ፡
እለ ፡ እንተ ፡ ደም ፡ ይውኅዝ ፡ የተፈወ
ሰችባት ፡ ክብርት ፡ ናት ፡ እንጂ ። ወዲ
ያውም ፡ ኢንሥጥጥ ፡ ወኢንገምድ ፡
ያለው ፡ ይፈርሳል ፡ ብሎ ፡ ዘፍየት ፡
መጠምጠምያ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ልባ
ልባ ፡ ማማ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ መጕናጸ
ፊያ ፡ አንድ ፡ ወገን ። በዚህ ፡ በሦስቱ ፡
አራት ፡ ዕፃ ፡ ተጣጣሉበት ። አንዱ ፡
ከመሬት ፡ ይወድቃል ፡ በንዱ ፡ አራቱ ፡
ሁሉ ፡ ይጣጣላሉ ፡ ሳልደረሰው ፡ የደ
ረሰ ፡ እንደሆን ፡ የተመቸ ፡ ለደረሰው ፡
የደረሰ ፡ እንደሆን ፡ ፈት ፡ የደረሰውን ፡
ትቶ ፡ ያን ፡ ይዞ ፡ ይሔዳል ። ይህን ፡
ማድረጋቸው ፡ ለጊዜው ፡ ዘበ ፡ ክልኤ ፡
ከዳናት ፡ የሀብ ፡ ፩ደ ፡ ለዘአልቦቱ ፡
ብሎ ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ። የሚያስተምር ፡
ያንድ ፡ ባሕታዊ ፡ ልብስ ፡ ላራት ፡ ቤት ፡
ጭፍራ ፡ ሮማውያን ፡ በቃ ፡ ለማለት ፡

2014 04 17

ምሥጢሩ ፡ ግን ፡ ወንጌል ፡ አራት ፡ ክፍል ፡ ሁና ፡ የመጻፉ ፡ ምሳሌ ፡ አን ድም ፡ አራቱ ፡ ሁሉ ፡ ባንዲቱ ፡ ዕፃ ፡ መጣጣላቸው ፡ ወንጌል ፡ አራት ፡ ክ ፍል ፡ ስትሆን ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ለመሆ ኗ ፡ ምሳሌ ። ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፴፭ ። ማር ፡ ፲፭ ፡ ፳፬ ። ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴፬ ። ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፳፫ ።

፲፱ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ኢትርኀቅ ፡ እምኔየ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ከኔ ፡ በረድኤት ፡ አ ትራቅ ።

ወነጽር ፡ ውስተ ፡ ረዲኤትየ ።

እኔን ፡ ወደ ፡ መርዳት ፡ እይ ፡ ተመልከት ።

፳ ፡ አድኅና ፡ እምሀናት ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ ከአቤሴሎም ፡ ጦር ፡ አድ ናት ።

ወእምእደ ፡ ከለባት ፡ ለብሕቱትየ ።

ብቸኝነቴን ፡ አይተህ ፡ አንድም ፡ ብቸ ኝነቴን ፡ ከነአቤሴሎም ፡ አድናት ። ከለባት ፡ እንዳለፈው ።

፳፩ ፡ አድኅነኒ ፡ እምአፈ ፡ አንበሳ ።

ከአቤሴሎም ፡ እጅ ፡ አድነኝ ።

ወምእቅርንት ፡ ዘ፩ ፡ ቀርኑ ፡ ለብሕቱትየ ።

ብዙ ፡ ሥልጣን ፡ ካላቸው ፡ ከነገሥ ታት ፡ ተለይቶ ፡ ባንድ ፡ ሥልጣኑ ፡ ከሚመካ ፡ ከአቤሴሎም ፡ አንድም ፡ ብዙ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ካላቸው ፡ ከፀ ሐይ ፡ ከጨረቃ ፡ ከከዋክብት ፡ ተለይ ቶ ፡ ባንድ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃኑ ፡ ከሚመካ ፡ ከፀሐይ ፡ አቤሴሎም ፡ አንድም ፡ ብዙ ፡ ቀንድ ፡ ካላቸው ፡ ከአራዊት ፡ ተለይቶ ፡ ባንዱ ፡ ቀንዱ ፡ ከሚመካ ፡ ከርኤም ፡ አቤሴሎም ፡ አድነኝ ፡ ርኤም ፡ ዕዒም ፡ ከረከንድ ፡ ይለዋል ፡ አካሉ ፡ ቲንሽ ፡ ነው ፡ ቀንዱ ፡ ሰብአ ፡ ሰማንያ ፡ ክንድ ፡ ይሆናል ፡ ነፍጥ ፡ አይመታውም ፡ ቀ ስት ፡ አይወጋውም ፡ ላዳኞች ፡ አይመ ችም ፡ ሲመጡበት ፡ ክትት ፡ ብሎ ፡ ከቀንዱ ፡ ይገባል ። አንድም ፡ በቀንዱ ፡ ተተክሎ ፡ ይቆማል ። እንደምን ፡ አድ ርገው ፡ ይገድሉታል ፡ ቢሉ ፡ ገዘሙት ፡ ይጸናበታል ፡ ሴት ፡ አስጊጠው ፡ ኰ ለው ፡ ቀብተው ፡ አርቀው ፡ ያቆማሉ ፡ ሴቲቱን ፡ ሲመለከት ፡ በነፍጥ ፡ በቀ ስት ፡ መትተው ፡ ይገድሉታል ። ሽታ ው ፡ ነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ የሚለይ ፡ ነው ። ዕለቱን ፡ አይቀርቡትም ። ብዙ ፡ ፀሐይ ፡ ብዙ ፡ ክረምት ፡ ካለፈበት ፡ በኋላ ፡ ቀ ርበው ፡ እያጣፈጡ ፡ ይወስዱታል ፡ ወዴት ፡ ይገኛል ፡ ቢሉ ። ዛሬ ፡ እንጂ ፡ ነጋድያን ፡ ቂርበት ፡ ከሪም ፡ እያሉ ፡ የሚያመጡት ፡ እሱ ፡ ነው ። ይኸው ም ፡ ለገዘከረ ፡ ነገር ፡ በዳርዮስ ፡ አደባ ባይ ፡ ነገ ፡ ፳ ፡ ክንድ ፡ ወድቆ ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

፳፪ ፡ እነግሮሙ ፡ ስመከ ፡ ለአኃውየ ።

ያምላክነትህን ፡ ስም ፡ አንድም ፡ ያን ድነትህን ፡ የሦስትነትህን ፡ ስም ፡ ለሁ ለቱ ፡ ነገድ ፡ እነግራቸዋለሁ ።

ወበማእከለ ፡ ማኅበር ፡ እሴብሐከ ።

ባሥሩ ፡ ነገድ ፡ መሐልም ፡ አመሰግ ንሃለሁ ። አንድም ፡ (እነግሮሙ ፡ ስመ ከ ፡ ለአኃውየ) ፡ ስመ ፡ ወላዲነትህን ፡ ለሐዋርያት ፡ እነግራቸዋለሁ ። (ወበ ማእከለ ፡ ማኅበር ፡ እሴብሐከ) ፡ በሰ ብአ ፡ አርድእትም ፡ መሐከል ፡ አመ ሰግንሃለሁ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።

፳፫ ፡ እለ ፡ ትፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰብሕዎ ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የምትፈሩትን ፡ አንድም ፡ የምታመ ልኩት ፡ አመስግኑት ።

ሎሉ ፡ ዘርአ ፡ ያዕቆብ ፡ አክብርዎ ።

ማን ፡ ማን ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ ዕገሌ ፡ ዕገሌ ፡ ምን ፡ አሰኝቶኝ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ መላችሁ ።

ወፍርህዎ ፡ ኵልክሙ ፡ ዘርአ ፡ እስራኤል ።

የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ።

፳፬ ፡ እስመ ፡ ኢመነነ ፡ ወኢተቈጥዓ ፡ ስእለተ ፡ ነዳይ ።

አክብርዎ ፡ ፍርህዎ ፡ ትላለህ ፡ ምን ፡ አድርጐልሃል ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ የድኃውን ፡ ልመና ፡ ቸል ፡ አላለም ፡ አላነጠበምና ።

ወኢሜጠ ፡ ገጾ ፡ እምኔየ ።

ሶበ ፡ ጸራኅኩ ፡ ኀቤሁ ፡ ይሰምዓኒ ።

የድኃን ፡ ልመና ፡ ቸል ፡ ባይል ፡ ባያ ነጥብ ፡ ላንተ ፡ ምን ፡ ይጠቅምሃል ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ እኔም ፡ ይልቁን ፡ ወደሱ ፡ መልሼ ፡ በለመንሁ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኖ ፡ ፈጥኖ ፡ ይሰማኛል ፡ እንጂ ፡ ገጸ ፡ ረድኤት ፡ ገጸ ፡ ምሕረቱን ፡ ከኔ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አልመለሰውም ፡ አንድም ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ከኔ ፡ ወደሌላ ፡ መ ልሶት ፡ አያውቅም ፡ እንግዲህ ፡ ወዲ ህም ፡ ወደሱ ፡ መልሼ ፡ በለመንሁ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኖ ፡ ይሰማኛልና ፡ አክብ ርዎ ፡ ፍርህዎ ።

፳፭ ፡ እምኀቤከ ፡ ክብርየ ፡ በማኅበር ፡ ዓቢይ ።

ይህም ፡ ሊታወቅ ፡ በማኅበር ፡ የምክ ብረው ፡ ፍጹም ፡ ክብሬ ፡ ካንተ ፡ (ከሱ) ፡ ዘንድ ፡ የተገኘ ፡ ነው ። አንድም ፡ ካንተ ፡ ዘንድ ፡ የተገኘ ፡ ክብሬ ፡ በማኅበረ ፡ እስራኤል ፡ ፍጹም ፡ ነው ።

ወእዕሥብ ፡ ብፅዓትየ ፡ በቅድመ ፡ እለ ፡ ይፈርህዎ ።

ይህን ፡ ብታደርግልኝ ፡ ይህን ፡ እሰጣ ለሁ ፡ ብዬ ፡ የተሳልሁትን ፡ (ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን) ፡ ስለቴን ፡ በሚፈሩት ፡ በሚ ያመልኩት ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ፊት ፡ እሰጣለሁ ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ የተ ሳሉትን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ለብቻ ፡ የተሳ ሉትን ፡ ለብቻ ፡ መስጠት ፡ ይገባልና ።

፳፮ ፡ ይብልዑ ፡ ነዳያን ፡ ወይጸግቡ ።

ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ዓሥራቱን ፡ በኵራ ቱን ፡ መባውን ፡ በልተው ፡ ደስ ፡ ይላ ቸው ፡ ዘንድ ፡ ወለሥዩማን ፡ ቤተ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ መባዓ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ምርከበሙ ፡ እንዲል ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲፫ ። ዘኍ ፡ ፲፰ ፡ ፰-፲፩ ። ዘዳ ፡ ፲፰ ፡ ፩-፫ ።

ወይሴብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘ ሎሙ ፡ እለ ፡ የኃሥሥዎ ።

በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚሹት ፡ ሁሉ ፡ ለነቢያት ፡ ለካህናት ፡



2014 04 17

ዓሥራቱን ፡ መባውን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ ያሰኛቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ ፡ እሁብ ።

ወየሐፀ ፡ ልበሙ ፡ ለጎለሙ ፡ ጎለም ።

ይሕየው ፡ ሲል ፡ ነው ። ልቡናቸውን ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይለው ፡ ዘንድ ። ወሐ ይወ ፡ ልቡ ፡ ለያዕቆብ ፡ እንዲል ፡ ዘፍ ፡ ፵፭ ፡ ፳፯-፳፰ ። እንድም ፡ ይህን ፡ ብታደርግልኝ ፡ ይህን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብዬ ፡ የተሳልሁትን ፡ ስለቱን ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ፊት ፡ እሰጣለሁ ፡ (ይበልዑ ፡ ወይፀግቡ) ፡ ነቢያት ፡ ካህናትም ፡ መባውን ፡ በልተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። (ወይሴብሕዎ) ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የሚሹት ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ። (ወየሐዩ) ፡ ልቡናቸውንም ፡ ደስ ፡ ይለዋል ። እንድም ፡ ይህን ፡ ብታደርግልኝ ፡ ይህን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብዬ ፡ የተሳልሁትን ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ፊት ፡ እሰጣለሁ ፡ (ወይብልዑ ፡ ወይጽግቡ) ፡ ነቢያት ፡ ካህናትም ፡ መባውን ፡ በልተው ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፡ (ወይሰብሕዎ) ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የሚሹት ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግኑት ፡ (ወይሕየው) ፡ ልቡናቸውንም ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይበለው ።

፳፯ ፡ ይዜከሩ ፡ ወይትመየጡ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኵሎሙ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ባራቱ ፡ ማዕዝን ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ይመለሳሉ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ በምስጋና ፡ ይጠራሉ ። እንድም ፡ ይህ ፡ ተደርጎ ፡ በአራቱ ፡ ማዕዝን ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ይመለሱ ። የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ በምስጋና ፡ ይጥሩ ።

ወይስግዱ ፡ ቅድሜሁ ፡ ኵሎሙ ፡ በሐውርተ ፡ አሕዛብ ።

እንጋደ ፡ አሕዛብ ፡ ሲል ፡ ነው ። የአሕዛብ ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ከፊቱ ፡ ይስገዱ ፡ ይሰግዳሉ ።

፳፰ ፡ እስመ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ አብ ፡ ፩-፳፩ ።

የባሕርይ ፡ መንግሥት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ ናትና ። እንድም ፡ የጸጋ ፡ መንግሥት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ ናትና ። አእምሮ ፡ ከመ ፡ ልዑል ፡ ይኴንን ፡ መንግሥተ ፡ ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመ ሕያው ፡ እንዲል ።

ወውእቱ ፡ ይኴንኖሙ ፡ ለአሕዛብ ።

እሱም ፡ አሕዛብን ፡ ይገዛቸዋልና ፡ ሆሴ ፡ ፪ ፡ ፳ ።

፳፱ ፡ ብልዑ ፡ ወሰገዱ ፡ ኵልክሙ ፡ ጥሉላነ ፡ ምድር ። ኢሳ ፡ ፷፩ ፡ ፩ ።

ቅቡዓን ፡ ምድር ፡ ሲል ፡ ነው ። ደቂቀ ፡ ጠላት ፡ እንዲል ። ደቂቀ ፡ ቅብዓት ፡ ሲል ። ለክህነት ፡ ለመንግሥት ፡ የተ



መረጣችሁ ፡ በልጅነት ፡ የሉመለማ ችሁ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ዓሥራቱን ፡ በኵራቱን ፡ እየበላችሁ ፡ ጸልዩ ፡ ስገዱ ። እንድም ፡ እንጉዓ ፡ ለምድር ፡ ይላል ። ከምድር ፡ የተገኘውን ፡ እየበላችሁ ፡ በ እንተ ፡ ፍሬ ፡ ምድርን ፡ ጸልዩ ። የሰው ፡ በልቶ ፡ አያድሩም ፡ ተኝቶ ፡ እንዲሉ ።

ቅድሜሁ ፡ ይወድቁ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይወርዱ ፡ ውስተ ፡ ምድር ።

ይኸውም ፡ እላንት ፡ ብቻ ፡ አይደላች ሁም ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ከፊቱ ፡ ይሰግዳሉ ። እንድም ፡ ሙተው ፡ ወደመቃብር ፡ የሚወርዱ ፡ ሁሉ ፡ ከፊቱ ፡ ይሰግዳሉ ፡ የጻድቅም ፡ የኃጥእም ፡ ነፍስ ፡ ብትሆን ፡ ከፊቱ ፡ ሳትደ ርስ ፡ አትሔድምና ። ወትገብእ ፡ ነፍስ ፡ ኀበ ፡ ዘወሀባ ፡ ቀዲሙ ፡ ወታቀድም ፡ ሰጊደ ፡ ለስብሐተ ፡ ልዑል ፡ እንዲል ።

፴ ፡ ነፍስየኒ ፡ ሎቱ ፡ ተሐዩ ።

የኔም ፡ ሰውነቴ ፡ ለሱ ፡ ስትገዛ ፡ ትኖራ ለች ። ወሐይወ ፡ አዳም ፡ ሰብአተ ፡ ዓመተ ፡ በገነት ፡ እንዲል ።

ወዘርእየኒ ፡ ሎቱ ፡ ይትቀነይ ።

ልጁ ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ ሁሉ ፡ ለሱ ፡ ይገ ዛል ። እንድም ፡ ወዘርእየኒ ፡ ብእሲ ፡ እንቀጽ ፡ አድርገህ ፡ እኔ ፡ ለሱ ፡ ስገዛ ፡ ያየኝ ፡ ሁሉ ፡ ለሱ ፡ ይገዛል ።

፴፩ ፡ ትዜንዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትውልድ ፡ እንተ ፡ ትመጽእ ።

እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የምትነሣ ፡ ትውልድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተግባር ፡ አድ ርጋ ፡ ትጨዋወታለች ።

ወይዜንዉ ፡ ጽድቀ ፡ ዚአሁ ።

ሕዝብ ፡ ዘይትወለድ ፡ ዘገብረ ፡ እግዚአብሔር ።

ትዜንዎና ፡ ይዜንዉ ፡ አንድ ፡ ወገን ። ትውልድ ፡ እንተ ፡ ትመጽእና ፡ ሕዝብ ፡ ዘይትወለድ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ የሚነሡ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠራቸው ፡ ሕዝብ ፡ ይቅርታውን ፡ ቸርነቱን ፡ ይነግራሉ ፡ ያስተምራሉ ። እንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረገውን ፡ ይቅርታውን ፡ ቸርነቱን ፡ ይነግራሉ ፡ ያስተምራሉ ። ኢሳ ፡ ፵፫ ፡ ፳፩ ።

## መዝሙር ፡ ፹፰ ።

፩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፌእየኒ ፡ ወአልቦ ፡ ዘየኀጥአኒ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ። የምዕ መናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ።

ስልምናሶር ፡ ዓሥሩን ፡ ነገድ ፡ ማርኮ ፡ ባቢሎን ፡ አውርዷቸው ፡ ከዚያ ፡ ሚ ስት ፡ አግብተው ፡ ሕፃናት ፡ ወልደው ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ይዘው ፡ ዘር ፡ ዘርተው ፡ ተክል ፡ ተክለው ፡ የሚኖሩ ፡ ሁነዋል ። ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ በተማረኩበት ፡ ዘመን ፡ ናቡከደነፆር ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ማርኮ ፡ አውርዷቸዋል ። ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ መ ውጫ ፡ መግቢያውን ፡ ያውቁታል ፡ ስ ንቅ ፡ ሰጥተው ፡ ጎዳና ፡ አሳይተው ፡

2014 04 17

ሽኝተው፡ያስኰበልሉብኛል፡ብሎ፡ ዓሥሩን፡ ነገድ፡ ቁላተ፡ ኀዘር፡ ወደ ሚባል፡ ዘር፡ ተክል፡ ወደሌለበት፡ ወደጽኑ፡ በረሀ፡ አውርደ፟ቸዋል ፤ በ ሥሩ፡ ነገድ፡ በታ፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ አኑሯቸዋል፤ቃሉ፡ያሥሩ፡ነገድ፡ነው። አላንት፡ባቢሎናውያን፡ቁላተ፡ኀዘር፡ ብታወርዱኝ፡ እግዚአብሔር፡ ከሰ ብዓ፡ዘመን፡ በኋላ፡ ወደ፡ ኢየሩሳ ሌም፡ውጣ፡በማለት፡ያየኛል።እኔን፡ የሚያጣበት፡የለም፡ቁላተ፡ኀዘርም፡ ቢሆን፡ የሱ፡ ግንዘቡ፡ ነውና፡ ይርዕ የኒ፡ ልብስ፡ ምግብ፡ ብትነሡኝ፡እግ ዚአብሔር፡ ይጠብቀኛል።(ዘያኀጥ እኒ)፡ከልብስ፡ከምግብ፡ወገን፡እኔን፡ የሚያሳጣበት፡ የለውም።

፬፡ ውስተ፡ ብሔር፡ ሥዑር፡ ሀየ፡ ያኀድረኒ።

ሰብዓ፡ዘመን፡በተፈታች፡ በኢየሩሳ ሌም፡ ያኖረኛል።እንድም፡ ከሰብአ፡ ዘመን፡ በኋላ፡ በዘር፡ በተክል፡ በለ መለመች፡በኢየሩሳሌም፡ያኖረኛል። ወእምዝናም፡ይሥዕር፡ሐመልማል፡ እንዲል።

ወኀበ፡ ማየ፡ ዕረፍት፡ ሐፀነኒ።

ያሳደገኝ፡ማየ፡ዕረፍት፡ባለበት፡በኢ የሩሳሌም፡ ያኖረኛል። የሀገራቸው፡ ወሀ፡ የኮሬ፡ ወሀ፡ነው፡ እንደ፡ ሀገ ራችን፡ ወሀ፡ ድካም፡ የለበትምና፡ ማየ፡ ዕረፍት፡ አለው።ምነው፡ ሐፀ ነኒ፡ አለ። ትሩፍ፡ የተወለደ፡ ከባቢ ሎን፡ያደገስ፡ከባቢሎን፡አይደለምን፡ ቢሉ፡ ያባቶቹን፡ ለሱ፡ ሰጥቶ፡ ተና ገረ፡ እንድም፡ እንደነ፡ ኤርምያስ፡ ተወልደው፡ተማርከው፡ፋርስ፡ባቢ ሎን፡ ወርደው፡ ተመልሰው፡ ኢየሩ ሳሌም፡ የወጡ፡ አሉና፡ ኢሳ፡፷፭፡፰። ፶፰፡ ፲፩። ኤር፡ ፴፭፡ ፱። ሶፎ፡ ፯፡ ፲፯።

፫፡ ሚጣ፡ለነፍስየ፡ወመርሐኒ፡ፍኖተ፡ጽድቅ።

ሰውነቴን፡ ከፋርስ፡ ከባቢሎን፡ መ ልሶ፡እውነተኛውን፡የኢየሩሳሌምን፡ ጐዳና፡ መርቶ፡ አወጣኝ።

በእንተ፡ ስመ፡ ዚአሁ።

በስሙ፡ ስላመንሁ። ስሙን፡ አማ ላጅ፡ ስላደረግሁ። ስምየኒ፡ መሐሪ፡ ወመስተሣህል፡ ስላለ።

፬፡ እመኒ፡ ሖርኩ፡ ማእከለ፡ ጽላሎተ፡ሞት።

ለሞት፡ የሚያበቃ፡ ጽኑ፡ መከራ፡ ወዳለበት፡ ወደ፡ ባቢሎን፡ ምንም፡ ብወርድ።

ኢይፈርሆ፡ ለእኩይ፡ እስመ፡ አንተ፡ ምስሌየ። መዝ፡ ፻፲፯፡ ፯። ዘኍ፡ ፲፬፡ ፱። ሮሜ፡ ፰፡ ፴፭።

አንተ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ በረድኤት፡ አለ ህና፡ መከራ፡ ሥጋውን፡ አልፈራ ውም። እንድም፡ ምክንያተ፡ ሞት፡ የሚሆን፡ ብልጣሶር፡ ወዳለበት፡ ወደ ባቢሎን፡ ምንም፡ ብወርድ። አንተ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ በረድኤት፡ አለህና፡ ብል ጣሶርን፡ አልፈራውም።

እንድም፡(እግዚአብሔር፡ይሬእየኒ)፡ አጋንንት፡ገሃነም፡ብታወርዱኝ፡ከም ስት፡ ሺሕ፡ አምስት፡ መቶ፡ ዘመን፡ በኋላ፡ ወደ፡ገነት፡ወደ፡መንግሥተ፡ ሰማያት፡ ላውጣህ፡ በማለት፡ እግዚ አብሔር፡ ያየኛል።(ወአልበ፡ ዘየኀ ጥእኒ)፡ እኔን፡ የሚያጣበት፡ በታ፡ የለም።(እንድም፡ ይርእየኒ)፡ምግበ፡ ነፍስ፡ ልብሰ፡ ነፍስ፡ ልስጥህ፡ በማ ለት፡ ይጠብቀኛል። (ዘያኀጥእኒ)፡ ከምግበ፡ነፍስ፡ከልብሰ፡ነፍስ፡ወገን፡ እኔን፡ የሚያሳጣበት፡ የለውም፡ በነ ፍስ፡መመገብ፡ኑሮ፡አይደለም፡ ክብ ሩን፡ መናገር፡ነው፡እንጂ፡(ውስተ፡ ብሔር፡ ሥዑር፡ ሀየ፡ ያኀድረኒ)፡ አምስት፡ሺሕ፡አምስት፡መቶ፡ዘመን፡ ሙሉ፡ ልጅነት፡ በታጣበት፡ በገነት፡ ያኖረኛል።እንድም፡ከምስት፡ሺሕ፡ አምስት፡ መቶ፡ ዘመን፡ በኋላ፡ በል ጅነት፡ በለመለመች፡ በገነት፡ ያኖረ ኛል።(ወኀበ፡ ማየ፡ ዕረፍት፡ ሐፀ ነኒ)፡ ያሳደገኝ፡ ልጅነት፡ ባለበት፡ በገነት፡ ያኖረኛል፡ ማየ፡ ዕረፍት፡ አለው፡ ልጅነትን፡ የሚሰጥ፡ በጥም ቀት፡ምክንያት፡ነውና።ሐፀነኒ፡አለ። ያባቶቹን፡ ለሱ፡ ሰጥቶ፡ እንድም፡ እንዲህ፡ የሚሉ፡ አዳምና፡ ሔዋን፡ ናቸው፡(ሚጣ፡ለነፍስየ፡ወመርሐኒ፡ ፍኖተ፡ጽድቅ)፡ነፍሴን፡ከሲኦል፡ከገ ሃነም፡ መልሶ፡ እውነተኛውን፡ የገ ነት፡ የመንግሥተ፡ ሰማያትን፡ መን ገድ፡ መርቶ፡ አወጣኝ።(በእንተ፡ ስመ፡ ዚአሁ)፡ በክርስቶስ፡ ክርስቲ ያን፡በወልድ፡ውሉድ፡ስለተባልሁ። (እመኒ፡ ሖርኩ፡ ማእከለ፡ ጽላሎተ፡ ሞት)፡ለሞተ፡ነፍስ፡የሚያበቃ፡መከ ራ፡ነፍስ፡ወዳለበት፡ወደ፡ሲኦል፡ብወ ርድ፡(ኢይፈርሆ፡ለእኩይ፡እስመ፡ አንተ፡ምስሌየ)፡አንተ፡ከኔ፡ጋራ፡አለ ህና፡ መከራ፡ ነፍሴን፡ አልፈራም። እንድም፡ምክንያተ፡ሞት፡የሚሆን፡ ዲያብሎስ፡ ወዳለበት፡ ወደ፡ ሲኦል፡ ምንም፡ ብወርድ፡ አንተ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ አለህና፡ ዲያብሎስን፡ አልፈራውም፡ ነፍሰሙሰ፡ ለጻድቃን፡ ውስተ፡ እደ፡ እግዚአብሔር፡ ወኢለከፎሙ፡ ሥ ቃይ፡ እንዲል። ጥበ፡ ፫፡ ፩። ምንም፡ ገሃነም፡ ቢወርዱ፡ እደ፡ እግዚአብ ሔር፡ እንደ፡ አጥር፡ እንደ፡ ቅጥር፡ ሆኖላቸው፡ መከራ፡ ነፍስ፡ ያላገኛ ቸው፡ አሉና። ኢሳ፡ ፵፫፡ ፲፭። ሮሐ፡ ፲፡ ፲።

በትርከ፡ ወቀስታምከ፡ እማንቱ፡ ገሠጻኒ።

ጠርሙዝ፡በሉታሕ፡ሠሩኝ፡ቀጡኝ፡ በግሥ፡ ተናግሮታል፡ ይኸውም፡ ከቤተ፡መንግሥት፡ይገኛል።በዚያ፡ ወዳጆቻቸውን፡ ይጠብቁበታል፡ ጠላ ታቸውን፡ ይበቀሉበታልና። ስልም ናሶር፡ ናቡከደነፆር። ዮልማሮዲቅ፡ ብልጣሶር፡ ሠሩኝ፡ ቀጡኝ፡ ሲል፡ ነው።

፭፡ ወሠራዕከ፡ ማዕደ፡ በቅድሜየ።

ማዕድ፡ ገንዘቤን፡ ለእሕዛብ፡ አሳል ፈህ፡ ሰጠህብኝ።

በአንጻረሆሙ፡ ለእለ፡ ይሣቅዩኒ።

ይንደደው፡ ይቍጨው፡ ብለህ፡ ሥ ቃይ፡በሚያጸኑብኝ፡በእሕዛብ፡ፊት።





2014 04 17

ወአዕረፍከ ፡ በቅብዕ ፡ ርእስየ ።

ርእሰ ፡ ልቡናዬን ፡ ግን ፡ በተሰፋው ፡ ደስ ፡ አሰኘኸው ፡ ሚጠቱን ፡ ሰምተው ፡ የወረዱ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ። ወዘይበ ገዙ ፡ ሕዝበ ፡ አውረድከ ፡ በተስፋ ፡ እንዲል ። ኤር ፡ ፴፮ ፡ ፲፱ ።

ጽዋዕከኒ ፡ ጽኑዕ ፡ ወያረዊ ።

ጼዋዌህ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ አያዳግምም ፡ አንዱ ፡ በቃኝ ፡ ነው ።

፮፤ ምሕረትከ ፡ ይትልወኒ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወትየ ።

ባለዘመኔ ፡ ሁሉ ፡ ይቅርታህ ፡ ቸርነ ትህ ፡ ይከተለኝ ፡ አይለየኝ ።

ከመ ፡ ታንብረኒ ፡ ቤቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለነዋህ ፡ መዋዕል ።

ነዋኅ ፡ መዋዕለ ፡ ሲል ፡ ነው ። ሰፊ ፡ ዘመናት ፡ ረጅም ፡ ወራት ፡ እግዚአብ ሔር ፡ በረድኤት ፡ አድሮበት ፡ በሚ ኖር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ታኖረኝ ፡ ዘንድ ፤ አንድም ፡ በወጣሁበት ፡ በወረድሁ በት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ታኖረኝ ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ (በትርከ ፡ ወቀስታምከ ፡ እማ ንቱ) ፡ ዮሴዕ ፡ ዘሩባቤል ። አንድም ፡ ቂሮስ ፡ ዳርዮስ ፡ አሕዛብን ፡ ሠሩልኝ ፡ ቀጡልኝ ፡ (ወሠራዕከ ፡ ማዕደ ፡ በቅድ ሜየ) ፡ አሕዛብን ፡ ሠርተህ ፡ ቀጥተህ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ሰጠኸኝ ። (በአንፃረ ሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይሣቅዩኒ) ፡ ይንደዳ ቸው ፡ ይቍጣቸው ፡ ብለህ ፡ በአሕ ዛብ ፡ ፊት ። (ወአዕሐድከ ፡ በቅብዕ ፡ ርእስየ) ፡ ርእሰ ፡ ልቡናዬንም ፡ በሚ ጠት ፡ ደስ ፡ አሰኘኸው ። (ጽዋዕከኒ ፡ ጽኑዕ) ፡ ሚጠትህ ፡ ጽኑ ፡ ነው ። (ወያ ረዊ) ፡ አንዱ ፡ በቃኝ ፡ ነው ፡ አያዳግ ምም ።

አንድም ፡ (በትርከ ፡ ወቀስታምከ) ፡ አጋንንት ፡ ሠሩኝ ፡ ቀጡኝ ፡ (ወሠራ ዕከ ፡) ፡ ጼዋዌ ፡ ነፍስን ፡ ሠራህብኝ ፡ (በአንፃረሆሙ) ፡ ይንደደው ፡ ይቍጠ ው ፡ ብለህ ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ በሚያ ጸኑብኝ ፡ በአጋንንት ፡ ፊት ፡ (ወአዕሐ ድከ) ፡ ርእሰ ፡ ልቡናዬን ፡ ግን ፡ በሐ ሙስ ፡ ዕለት ፡ ባልከው ፡ ተስፋ ፡ ደስ ፡ አሰኘኸው ፡ (ጽዋዕከኒ) ፡ ጼዋዌ ፡ ነፍ ስህ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ (ወያረዊ) ፡ አያዳግ ምም ፡ አንዱ ፡ በቃኝ ፡ ነው ። አንድም ፡ (በትርከ) ፡ ሐዋርያት ፡ ሰብአ ፡ አርድ እት ፡ መስቀል ፡ ቀኖት ፤ አይሁድ ፡ መና ፍቃን ፡ አጋንንትን ፡ ሠሩልኝ ፡ ቀጹ ልኝ ፡ (ወሠራዕከ) ፡ ሥጋህን ፡ ሰጠኸኝ ፡ (በአንጻረሆሙ) ፡ ይንደዳቸው ፡ ይቍ ጣቸው ፡ ብለህ ፡ በአጋንንት ፡ ፊት ፡ (ወአዕሐድከ) ፡ ርእሰ ፡ ልቡናዬንም ፡ በልጅነት ፡ ደስ ፡ አሰኘኸው ፡ (ጽዋዕ ከኒ) ፡ ሥጋህ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ (ወያረዊ) ፡ አያዳግምም ፡ አንዱ ፡ በቃኝ ፡ ነው ፡ ምዕረ ፡ ሦዐ ፡ ርእሶ ፡ እንዲል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ የተሰጠው ፡ ሥጋው ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ቢ ሰጥ ፡ ቢሰጥ ፡ አይፈጸምምና ።

አንድም ፡ (በትርከ) ፡ ሥጋህ ፡ ደምህ ፡ አጋንንትን ፡ ሠሩልኝ ፡ ቀጡልኝ ፡ (ወ ሠራዕከ) ፡ መስቀልን ፡ ተሸክምህልኝ ፡



…ንደዳቸው ፡ ይቍ … አይሁድ ፡ በአጋን … ሐድከ) ፡ ርእሰ ፡ … ንት ፡ ደስ ፡ አሰኘ … ደምህ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ (ወያረዊ) ፡ አያዳግምም ፡ አንዱ ፡ በቃኝ ፡ ነው ። በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ የፈሰሰው ፡ ደሙ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ቢቀዱ ፡ ቢቀዱ ፡ አይፈጸምምና ። አንድም ፡ ሕማሙን ፡ ሞቱን ፡ ለማዘከር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በሚገባ ፡ ከተቀ በሉት ፡ በኋላ ፡ ኃጢአት ፡ ካላሳደፉት ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ አያሻምና ። (ምሕረትከ ፡ ይትል ወኒ) ፡ ባለ ፡ ዘመኔ ፡ ሁሉ ፡ ታምራት ፡ ይደረግልኝ ። ወዘተ ፡ ተአምር ፡ ትተ ልዎሙ ። ለእለ ፡ አምኑ ፡ በስምየ ፡ እን ዲል ። ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ። ከመ ፡ ታንብረኒ ፡ ቤቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለነዋህ ፡ መዋ ዕል ። ነዋኅ ፡ መዋዕለ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ሰፊ ፡ ዘመናት ፡ ረጅም ፡ ወራት ፡ በመ ንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ታኖረኝ ፡ ዘንድ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከገቡ ፡ መው ጣት ፡ ካገኙ ፡ ማጣት ፡ የለምና ። መዝ ፡ ፳፯ ፡ ፬ ።

## መዝሙር ፡ ፹፰ ።

፩፤ ለእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ በምልኣ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ። ታሪኩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሬእየኒ ፡ ካለው ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። እስራኤል ፡ በኢየ ሩሳሌም ፡ ሳሉ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ከቤ ታችሁ ፡ ጸሎት ፡ አትጸልዩ ፡ መሥዋ ዕት ፡ አትሠዉ ፡ ብለዋቸዋል ። ስለ ፡ ምን ፡ ቢሉ ፡ ጣዖት ፡ ያመልካሉ ፡ ፈጣ ሪያቸውን ፡ ይክዳሉ ፡ ብለው ፡ ተማ ርከው ፡ ፋርስ ፡ ባቢሎን ፡ በወረዱ ፡ ጊዜ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዳንጸልይ ፡ በፋ ርስ ፡ በባቢሎን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የለ ፡ ከቤታችን ፡ እንዳንጸልይ ፡ አትጸልዩ ፡ አሉን ፡ ብለው ፡ ጸሎት ፡ ትተዋል ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ይህን ፡ ሰምተው ፡ እኛ ፡ አትጸልዩ ፡ ያልነው ፡ እንደ ፡ ቅዳሴ ፡ እንደ ፡ ኪዳን ፡ እንደ ፡ ወንጌል ፡ ያለውን ፡ ደጋጉን ፡ ጸሎት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሊጦን ፡ እንደ ፡ መስተብቍዕ ፡ ያለውን ፡ መቸ ፡ አትጸልዩ ፡ አልን ፡ ዓለም ፡ በሙሉ ፡ በጥቅሉ ፡ የእግዚ አብሔር ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ። ለከ ፡ ይደሉ ፡ እግዚኦ ፡ ስብሐት ፡ በጽዮን ። መዝ ፡ ፷፬ ፡ ፩ ። እግዚአብሔር ፡ ይሬእየኒ ፡ ብትል ፡ አንድ ፡ ነው ። መዝ ፡ ፳፪ ፡ ፩ ። አንድም ፡ ዓለም ፡ በምሉ ፡ በጥቅሉ ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ፡ ጸልዩ ። ዘዳ ፡ ፲፱ ፡ ፭ ።

ዓለምኒ ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ።

ሸ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፳፮ ። ዓለም ፡ በቁሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ በዚች ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ። አንድም ፡ ዓለም ፡ ባቢሎን ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡ በባቢሎን ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የሱ ፡ ገንዘብ ፡ ናቸውና ።

፪፤ ወውእቱ ፡ በባሕር ፡ ሣረራ ።

እሱ ፡ ይህቺን ፡ ዓለም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡

2014 04 17

ወእጽሐድከ ፡ በቅብዕ ፡ ርእስየ ።

ርእሰ ፡ ልቡናዬን ፡ ግን ፡ በተስፋው ፡ ደስ ፡ አሰኘኸው ፡ ሚጠቱን ፡ ሰምተው ፡ የወረዱ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ። ወዘይበዝኁ ፡ ሕዝበ ፡ አውረድከ ፡ በተስፋ ፡ እንዲል ። ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፲፬ ።

ጽዋዕከኒ ፡ ጽኑዕ ፡ ወያረዊ ።

ጺዋዊህ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ አያዳግምም ፡ አንዱ ፡ በቃኝ ፡ ነው ።

፮፡ ምሕረትከ ፡ ይትልወኒ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወትየ ።

ባለዘመኔ ፡ ሁሉ ፡ ይቅርታህ ፡ ቸርነትህ ፡ ይከተለኝ ፡ አይለየኝ ።

ከመ ፡ ታንብረኒ ፡ ቤቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለነዋኅ ፡ መዋዕል ።

ነዋኅ ፡ መዋዕለ ፡ ሲል ፡ ነው ። ሰፊ ፡ ዘመናት ፡ ረጅም ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ አድሮበት ፡ በሚኖር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ታኖረኝ ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ በወጣሁበት ፡ በወረድሁበት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ታኖረኝ ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ (በትርከ ፡ ወቀስታምከ ፡ እማንቱ) ፡ ዮሴፍ ፡ ዘሩባቤል ። እንድም ፡ ቂሮስ ፡ ዳርዮስ ፡ እሕዛብን ፡ ሠሩልኝ ፡ ቀጡልኝ ፡ (ወሠራዕከ ፡ ማዕደ ፡ በቅድሜየ) ፡ እሕዛብን ፡ ሠርተህ ፡ ቀጥተህ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ሰጠኸኝ ። (በአንፃረሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይሣቅዩኒ) ፡ ይንደዳቸው ፡ ይቍጣቸው ፡ ብለህ ፡ በእሕዛብ ፡ ፊት ። (ወእፅሐድከ ፡ በቅብዕ ፡ ርእስየ) ፡ ርእሰ ፡ ልቡናዬንም ፡ በሚጠት ፡ ደስ ፡ አሰኘኸው ። (ጽዋዕከኒ ፡ ጽኑዕ) ፡ ሚጠትህ ፡ ጽኑ ፡ ነው ። (ወያረዊ) ፡ አንዱ ፡ በቃኝ ፡ ነው ፡ አያዳግምም ።

እንድም ፡ (በትርከ ፡ ወቀስታምከ) ፡ አጋንንት ፡ ሠሩኝ ፡ ቀጡኝ ፡ (ወሠራዕከ ፡ ) ፡ ጺዋዊ ፡ ነፍስን ፡ ሠራህብኝ ፡ (በአንፃረሆሙ) ፡ ይንደደው ፡ ይቍጨው ፡ ብለህ ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ በሚያጸኑብኝ ፡ በአጋንንት ፡ ፊት ፡ (ወእፅሐድከ) ፡ ርእሰ ፡ ልቡናዬን ፡ ግን ፡ በሐሙስ ፡ ዕለት ፡ ባልከው ፡ ተስፋ ፡ ደስ ፡ አሰኘኸው ፡ (ጽዋዕከኒ) ፡ ጺዋዊ ፡ ነፍስህ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ (ወያረዊ) ፡ አያዳግምም ፡ አንዱ ፡ በቃኝ ፡ ነው ። እንድም ፡ (በትርከ) ፡ ሐዋርያት ፡ ሰብአ ፡ አርድእት ፡ መስቀል ፡ ቀኖት ፡ አይሁድ ፡ መናፍቃን ፡ አጋንንትን ፡ ሠሩልኝ ፡ ቀጹልኝ ፡ (ወሠራዕከ) ፡ ሥጋህን ፡ ሰጠኸኝ ፡ (በአንጻረሆሙ) ፡ ይንደዳቸው ፡ ይቍጣቸው ፡ ብለህ ፡ በአጋንንት ፡ ፊት ፡ (ወእፅሐድከ) ፡ ርእሰ ፡ ልቡናዬንም ፡ በልጅነት ፡ ደስ ፡ አሰኘኸው ፡ (ጽዋዕከኒ) ፡ ሥጋህ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ (ወያረዊ) ፡ አያዳግምም ፡ አንዱ ፡ በቃኝ ፡ ነው ፡ ምዕረ ፡ ሦዐ ፡ ርእሶ ፡ እንዲል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ የተሰጠው ፡ ሥጋው ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ቢሰጥ ፡ ቢሰጥ ፡ አይፈጸምምና ።

እንድም ፡ (በትርከ) ፡ ሥጋህ ፡ ደምህ ፡ አጋንንትን ፡ ሠሩልኝ ፡ ቀጡልኝ ፡ (ወሠራዕከ) ፡ መስቀልን ፡ ተሸከምህልኝ ፡



(በእንጻረሆሙ) ፡ ይንደዳቸው ፡ ይቍጣቸው ፡ ብለህ ፡ በአይሁድ ፡ በአጋንንት ፡ ፊት ፡ (ወእጽሐድከ) ፡ ርእሰ ፡ ልቡናዬን ፡ በልጅነት ፡ ደስ ፡ አሰኘኸው ፡ (ጽዋዕከኒ) ፡ ደምህ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ (ወያረዊ) ፡ አያዳግምም ፡ አንዱ ፡ በቃኝ ፡ ነው ። በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ የፈሰሰው ፡ ደሙ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ቢቀዳ ፡ ቢቀዳ ፡ አይፈጸምምና ። እንድም ፡ ሕማሙን ፡ ሞቱን ፡ ለማዘከር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በሚገባ ፡ ከተቀበሉት ፡ በኀጢአት ፡ ካላሳደፉት ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ አያሻምና ። (ምሕረትከ ፡ ይትልወኒ) ፡ ባለ ፡ ዘመኔ ፡ ሁሉ ፡ ታምራት ፡ ይደረግልኝ ። ወዘቲ ፡ ተአምር ፡ ትተልዎሙ ። ለእለ ፡ እምኑ ፡ በስምየ ፡ እንዲል ። ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ። ከመ ፡ ታንብረኒ ፡ ቤቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለነዋህ ፡ መዋዕል ። ነዋኅ ፡ መዋዕለ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ሰፊ ፡ ዘመናት ፡ ረጅም ፡ ወራት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ታኖረኝ ፡ ዘንድ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከገቡ ፡ መውጣት ፡ ከገኙ ፡ ማጣት ፡ የለምና ። መዝ ፡ ፳፮ ፡ ፬ ።

## መዝሙር ፡ ፹፱ ።

፩፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ በምልኣ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ። ታሪኩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሬእየኒ ፡ ካለው ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። እስራኤል ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሳሉ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ከቤታችሁ ፡ ጸሎት ፡ አትጸልዩ ፡ መሥዋዕት ፡ አትሠዉ ፡ ብለዋቸዋል ። ስለ ፡ ምን ፡ ቢሉ ፡ ጣዖት ፡ ያመልኩሉ ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ ይክዱሉ ፡ ብለው ፡ ተማርከው ፡ ፋርስ ፡ ባቢሎን ፡ በወረዱ ፡ ጊዜ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዳንጸልይ ፡ በፋርስ ፡ በባቢሎን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የለ ፡ ከቤታችን ፡ እንዳንጸልይ ፡ አትጸልዩ ፡ አሉን ፡ ብለው ፡ ጸሎት ፡ ተተዋል ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ይህን ፡ ሰምተው ፡ እኛ ፡ አትጸልዩ ፡ ያልነው ፡ እንደ ፡ ቅዳሴ ፡ እንደ ፡ ኪዳን ፡ እንደ ፡ ወንጌል ፡ ያለውን ፡ ድጋጉን ፡ ጸሎት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሊጦን ፡ እንደ ፡ መስተብቍዕ ፡ ያለውን ፡ መቼ ፡ አትጸልዩ ፡ አልን ፡ ዓለም ፡ በሙሉ ፡ በጥቅሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ። ለከ ፡ ይደሉ ፡ እግዚኦ ፡ ስብሐት ፡ በጽዮን ። መዝ ፡ ፷፬ ፡ ፩ ። እግዚአብሔር ፡ ይሬእየኒ ፡ ብትል ፡ አንድ ፡ ነው ። መዝ ፡ ፳፪ ፡ ፩ ። እንድም ፡ ዓለም ፡ በምሉ ፡ በጥቅሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ፡ ጸልዩ ። ዘዳ ፡ ፲፬ ፡ ፩ ።

ዓለምኒ ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ።

፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፳፮ ። ዓለም ፡ በቁሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ በዚች ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ። እንድም ፡ ዓለም ፡ ባቢሎን ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡ በባቢሎን ፡ ያሉ ፡ እሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የሱ ፡ ገንዘብ ፡ ናቸውና ።

፪፡ ወውእቱ ፡ በባሕር ፡ ሣረራ ።

እሱ ፡ ይህቺን ፡ ዓለም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡

ፈጥሯታልና ፡ መርከብ ፡ በወሀ ፡ ላይ ፡ እንዲሔድ ፡ ዘእጽንዓ ፡ ለምድር ፡ ዲበ ፡ ማይ ፡ እንዲል ። መዝ ፡ ፻፴፭ ፡ ፮ ። እንድም ፡ ከወሀ ፡ ጋራ ፡ አቀላቅሎ ፡ ፈጥሯታልና ።

ወበአፍላጊሁ ፡ ውእቱ ፡ አጽንዓ ፡ ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፱-፲ ።

በእራቱ ፡ አፍላጋት ፡ አጽንቷታልና ። ዘይወቅዮሙ ፡ ለአድባር ፡ እምውሣጥ ያቲሆሙ ፡ እንዲል ። መዝ ፡ ፻፫ ፡ ፲፫ ። ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ ባያጠጣት ፡ እንደ ፡ ሬቅ ፡ እንደ ፡ ጎታ ፡ እንደ ፡ ጎተራ ፡ ሁና ፡ በፈረሰች ፡ ነበርና ። ምድር ፡ ምን ፡ ትመስላለች ፡ ቢሉ ፡ ሰውን ፡ ትመስላለች ፡ እንደ ፡ ደሙ ፡ በወሀ ፡ እንደ ፡ አጥንቱ ፡ በደንጊያ ፡ እንደ ፡ ሥሩ ፡ በእንጨት ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ፡ እንደ ፡ ሥጋው ፡ መሬትነቷ ፡ እንደ ፡ ፀጕሩ ፡ ሣሩ ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ፵፪ ፡ ፭ ። ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፴፭ ። ዘሌዋ ፡ ፫ ፡ ፭ ።

፫፡ መኑ ፡ የዓርግ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ እግዚአብሔር ።

እንዲህ ፡ ነውና ፡ ከየቤታችሁ ፡ ሁናችሁ ፡ በተዓቅቦ ፡ ጸልዩ ፡ እንጂ ፡ እለ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አንጸልይም ፡ ብላችሁ ፡ ጸሎት ፡ ትተውማ ፡ ዘንድ ፡ ሰብዓው ፡ ዘመን ፡ ሳይፈጸም ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመግባት ፡ የሚችል ፡ ማነው ፡ ጊዜውስ ፡ ቢደርስ ፡ የሚገቡ ፡ በልክ ፡ አይደሉምን ።

ወመኑ ፡ ይቀውም ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ መቅደሱ ።

ባምስቱ ፡ በስድስቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ ቱሞ ፡ የሚጸልይ ፡ ማን ፡ ነው ።

፬፡ ዘንጹሕ ፡ ልቡ ፡ ወንጹሕ ፡ እደዊሁ ።

ከዚያው ፡ ቅሉ ፡ ልቡ ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ቃሉ ፡ ከመበደል ፡ እጁ ፡ ከመግደል ፡ ንጹሕ ፡ የሆነለት ፡ አይደለምን ።

ወዘኢነሥአ ፡ ከንቶ ፡ በላዕለ ፡ ነፍሱ ።

በሰውነቱ ፡ ከንቱ ፡ ጣዖትን ፡ ያላመለከ ፡ አይደለምን ። ማቴ ፡ ፭ ፡ ፰ ።

ወዘኢመሐለ ፡ በጕሕሉት ፡ ለቢጹ ።

ለባልንጀራው ፡ ምሎ ፡ ያልካዳ ፡ አይደለምን ።

እንድም ፡ ተስእሎ ፡ እምነቢይ ፡ ወተ ፡ ሰጥዎ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ። (መኑ ፡ የዓርግ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ እግዚአብሔር) ፡ ሰብዓ ፡ ዘመን ፡ ተፈጽሞ ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የሚገባ ፡ ማን ፡ ነው ። እንድም ፡ አምስት ፡ ሽህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ተፈጽሞ ፡ ከሲኦል ፡ ወጥቶ ፡ ገነት ፡ የሚገባ ፡ ማን ፡ ነው ። (ወመኑ ፡ ይቀውም ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ መቅደሱ) ፡ ባምስቱ ፡ በስድስቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ ቱሞ ፡ የሚጸልይ ፡ ማን ፡ ነው ። እንድም ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡ በሚመሰገንበት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚኖር ፡ ማነው ፡ ብሎ ፡ ነቢዩ ፡ ይጠይቃል ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ተሠጥወ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ወይቤ ፡ (ዘንጹ ፡ ልቡ ፡ ወንጹሕ ፡ እደዊሁ) ፡ ልቡ ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ቃሉ ፡ ከመበደል ፡ እጁ ፡ ከመግደል ፡ ንጹሕ ፡ የሆነለት ፡ (ወዘኢነሥአ ፡ ከንቶ ፡ በላዕለ ፡ ነፍሱ) ፡ በሰውነቱ ፡ ከንቱ ፡ ጣዖ



ትን ፡ ያላመለከ ፡ (ወዘኢመሐለ ፡ በጕሕሉት ፡ ለቢፁ) ፡ ለባልንጀራው ፡ ምሎ ፡ ያልካዳ ፡ የዓርግ ፡ ይቀውም ፡ ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመልሳል ።

እንድም ፡ (መኑ ፡ የዓርግ) ፡ ሰብዓ ፡ ዘመን ፡ ተፈጽሞ ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥቶ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የሚገባ ፡ ማነው ። እንድም ፡ አምስት ፡ ሽሕ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ተፈጽሞ ፡ ከሲኦል ፡ ከገሃነም ፡ ወጥቶ ፡ ገነት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገባ ፡ ማን ፡ ነው ። (ውመኑ ፡ ይቀውም) ፡ በአምስቱ ፡ በስድስቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ ቱሞ ፡ የሚጸልይ ፡ ማን ፡ ነው ። እንድም ፡ መመስገኛው ፡ በምትሆን ፡ በገነት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚኖር ፡ ማን ፡ ነው ። (ዘንጹሕ ፡ ልቡ) ፡ ልቡ ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ቃሉ ፡ ከመበደል ፡ እጁ ፡ ከመግደል ፡ ንጹሕ ፡ የሆነለት ፡ ማን ፡ ነው ። (ወዘኢነሥአ) ፡ በሰውነቱ ፡ ከንቱ ፡ ጣዖትን ፡ ያላመለከ ፡ ማን ፡ ነው ። (ወዘኢመሐለ) ፡ ለባልንጀራው ፡ ምሎ ፡ ያልካዳ ፡ ማን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነቢይ ፡ ይጠይቃል ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ።

፭፡ ውእቱ ፡ ይነሥእ ፡ በረከተ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በረከተ ፡ ሥጋ ፡ በረከተ ፡ ነፍስን ፡ ያገኛል ።

ወሣህሉኒ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ።

ይቅርታውም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይደረግለታል ፡ ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመልሳል ። እንድም ፡ ያገኛል ፡ ይደረግለታል ፡ ብሎ ፡ ለነቢይ ፡ ይሰጧል ።

፮፡ ዛቲ ፡ ትውልድ ፡ ተኀሥሦ ፡ ሎቱ ።

ስለዚህ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ረድኤተ ፡ ሥጋን ፡ ትሻለች ።

ወተኀሥሥ ፡ ገጸ ፡ አምላከ ፡ ያዕቆብ ።

የያዕቆብን ፡ ፈጣሪ ፡ ገጸ ፡ ረድኤት ፡ ገጸ ፡ ምሕረቱን ፡ ትሻለች ።

፯፡ አርኅዉ ፡ ኖኃተ ፡ መኳንንት ። ቍ ፡ ፱ ።

መኳንንት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኖኃተ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ (የኢየሩሳሌምን ፡ በሮች) ፡ ክፈቱ ።

ወይትረኀዋ ፡ ኖኃት ፡ እለ ፡ እምፍጥረት ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ተከፍተው ፡ የማያውቁ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ በሮች ፡ ይከፈቱ ።

ወይባእ ፡ ንጉሠ ፡ ስብሐት ። ኢሳ ፡ ፳፮ ፡ ፪ ።

የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታ ፡ እስራኤልን ፡ ለማስማረክ ፡ ከዚያ ፡ ይግባ ። የትንቢት ፡ ነገር ፡ የሚጠትን ፡ ሲናገር ፡ መጥቶ ፡ የዉዋዉን ፡ አመጣ ፡ ያልተያያዘ ፡ ነው ። ነቢይ ፡ የሚጠትን ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ መጥቶ ፡ የዉዋዉን ፡ ይእተ ፡ አሚረ ፡ እንዳለ ።

እንድም ፡ (ዛቲ ፡ ትውልድ ፡ ተኀሥሦ ፡ ሎቱ) ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ ትሻዋለችና ፡ (ወተኀሥሥ) ፡ ገጸ ፡ ምሕረት ፡ ገጸ ፡ ረድኤቱን ፡ ትሻለችና ፡ (ወአርኅዉ ፡ ኖኃት) ፡ መኳንንት ፡ ባቢ

2014 04 17

ሎን ፣ የባቢሎንን ፣ በሮች ፣ ክፈቱ ። (ወይትረኃዋ ፣ ኆኃት) ፣ ከጥንት ፣ ጀምሮ ፣ ተከፍተው ፣ የማያውቁ ፣ የባቢሎን ፣ በሮች ፣ ይከፈቱ ። (ወይባእ ፣ ንጉሠ ፣ ስብሐት) ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ጌታ ፣ ትሩፋንን ፣ ለማውጣት ፣ ከዚያ ፣ ይግባ ፣ አሁን ፣ የተመቸ ።

አንድም ፣ (አርኅዉ) ፣ መኳንንተ ፣ ባቢሎን ፣ ቂሮስ ፣ ዳርዮስ ፣ ኆኃተ ፣ ባቢሎንን ፣ ክፈቱ ። (ወይትረኃዋ) ፣ ከጥንት ፣ ጀምሮ ፣ ተወግተው ፣ የማያውቁ ፣ መኳንንተ ፣ ባቢሎን ፣ ይወጉ ። (ወይባእ) ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ጌታ ፣ በቂሮስ ፣ በዳርዮስ ፣ አድሮ ፣ እለዚያን ፣ ለመውጋት ፣ ከዚያ ፣ ይግባ ።

አንድም ፣ (አርኅዉ) ፣ መኳንንተ ፣ ይሁዳ ፣ መኳንንተ ፣ ሰማርያ ፣ እለ ፣ አጀምክንታ ። የይሁዳን ፣ የሰማርያን ፣ በሮች ፣ ክፈቱ ። (ወይትረኃዋ) ፣ ከጥንት ፣ ጀምሮ ፣ ተከፍተው ፣ የማያውቁ ፣ የይሁዳ ፣ የሰማርያ ፣ ደጆች ፣ ይከፈቱ ። (ወይባእ) ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ጌታ ፣ ትሩፋንን ፣ ይዞ ፣ ከዚያ ፣ ይግባ ።

አንድም ፣ (አርኅዉ) ፣ መኳንንተ ፣ ትንቢት ፣ ነቢያት ፣ መኳንንተ ፣ ትምህርት ፣ ክህናት ፣ ኆኃተ ፣ ትንቢት ፣ ኆኃተ ፣ ትምህርትን ፣ ክፈቱ ። (ወይትረኃዋ) ፣ ከጥንት ፣ ጀምሮ ፣ ተከፍተው ፣ የማያውቁ ፣ ኆኃተ ፣ ትንቢት ፣ ኆኃተ ፣ ትምህርት ፣ ይከፈቱ ። (ወይባእ) ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ጌታ ፣ በልበ ፣ ሰማዕያን ፣ በዕዝነ ፣ ሰማዕያን ፣ ይደር ።

አንድም ፣ (አርኅዉ) ፣ መኳንንተ ፣ ትንቢት ፣ ነቢያት ፣ መኳንንተ ፣ ትምህርት ፣ ክህናት ፣ ኆኃተ ፣ ትንቢት ፣ ኆኃተ ፣ ትምህርትን ፣ ክፈቱ ። (ወይትረኃዋ) ፣ ከጥንት ፣ ጀምሮ ፣ ተከፍተው ፣ የማያውቁ ፣ አልባበ ፣ ሰማዕያን ፣ አዕዛነ ፣ ሰማዕያን ፣ ይከፈቱ ። (ወይባእ) ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ጌታ ፣ በእዝነ ፣ ሰማዕያን ፣ በልበ ፣ ሰማዕያን ፣ ይደር ።

አንድም ፣ (አርኅዉ) ፣ መኳንንተ ፣ ትንቢት ፣ መኳንንተ ፣ ትምህርት ፣ ነቢያት ፣ ክህናት ፣ ይወርዳል ፣ ይወለዳል ፣ ብላችሁ ፣ ደገኛውን ፣ ትንቢት ፣ ተናገሩ ። (ወይትረኃዋ) ፣ ከጥንት ፣ ጀምሮ ፣ ተነግሮ ፣ የማያውቅ ፣ ትንቢት ፣ ይነገር ። (ይወባእ) ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ጌታ ፣ ሰው ፣ ይሁን ፣ ሥጋ ፣ ይልበስ ።

አንድም ፣ (አርኅዉ) ፣ መኳንንተ ፣ ሲኦል ፣ አጋንንት ፣ ኆኃተ ፣ ሲኦልን ፣ ክፈቱ ። (ወይትረኃዋ) ፣ ከጥንት ፣ ጀምሮ ፣ ተከፍተው ፣ የማያውቁ ፣ ኆኃተ ፣ ሲኦል ፣ ይከፈቱ ። (ወይባእ) ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ጌታ ፣ ነፍሳትን ፣ ይዞ ፣ ለመውጣት ፣ ከዚያ ፣ ይግባ ።

አንድም ፣ (አርኅዉ) መኳንንተ ፣ ገነት ፣ ኪሩቤል ፣ ሱራፌል ፣ ኆኃተ ፣ ገነትን ፣ ክፈቱ ። (ወይትረኃዋ) ፣ ከጥንት ፣ ጀምረው ፣ ተከፍተው ፣ የማያውቁ ፣ ኆኃተ ፣ ገነት ፣ ይከፈቱ ። ወአግሐሦ ፣ ለሱራፌ ፣ ዘውስተ ፣ እዴሁ ፣ ኵናተ ፣ እሳት ፣ እንዲል ።



(ወይባእ) ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ጌታ ፣ ነፍሳትን ፣ ይዞ ፣ ከዚያ ፣ ይግባ ።

አንድም ፣ (አርኅዉ) ፣ መኳንንተ ፣ ቅዳሴ ፣ መላእክት ፣ ኆኃተ ፣ ቅዳሴን ፣ ክፈቱ ። (ወይትረኃዋ) ፣ ከጥንት ፣ ጀምሮ ፣ ተከፍተው ፣ የማያውቁ ፣ ኆኃተ ፣ ቅዳሴ ፣ ይከፈቱ ። (ወይባእ) ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ጌታ ፣ በየማነ ፣ አብ ፣ በዘባነ ፣ ኪሩብ ፣ ይቀመጥ ።

አንድም ፣ (አርኅወ ፣ ኆኃተ ፣ መኳንንት) ፣ መኳንንተ ፣ ሰማይ ፣ ሚካኤል ፣ ገብርኤል ፣ ሩፋኤል ፣ ኆኃተ ፣ ሰማይን ፣ ክፈቱ ። (ወይትረኃዋ ፣ ኆኃት ፣ እለ ፣ እምፍጥረት) ፣ ከጥንት ፣ ጀምሮ ፣ ተከፍተው ፣ የማያውቁ ፣ ኆኃተ ፣ ሰማይ ፣ ይከፈቱ ። አሁን ፣ በሰማይ ፣ መከፈት ፣ መዘጋት ፣ ኑሮበት ፣ አይደለም ፣ የተዘጋ ፣ ቤት ፣ በተከፈተ ፣ ጊዜ ፣ ከውስጡ ፣ ያለው ፣ ዕቃ ፣ እንዲታይ ፣ ያልተገለጠ ፣ ምሥጢር ፣ ይገለጽ ፣ ሲል ፣ ነው ፣ (ወይባእ ፣ ንጉሠ ፣ ስብሐት) ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ጌታ ፣ በብርሃን ፣ በሥልጣን ፣ በቅዳሴ ፣ ይኑር ።

፰ ፣ መኑ ፣ ውእቱ ፣ ዝንቱ ፣ ንጉሠ ፣ ስብሐት ።

ንጉሠ ፣ ስብሐት ፣ ቢለው ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ማን ፣ ነው ፣ ባለው ፣ ጊዜ ።

እግዚአብሔር ፣ ኃያል ፣ ወጽኑዕ ።

የባሕርይ ፣ ኃያል ፣ ጽኑዕ ፣ የሚሆን ፣ እግዚአብሔር ፣ ነዋ ፣ ይላል ፣ የተየካሽ ፣ መላሽ ።

እግዚአብሔር ፣ ኃያል ፣ በውስተ ፣ ቀትል ።

በሰልፍ ፣ ጊዜ ፣ ኃያል ፣ ጽኑዕ ፣ የሚሆን ፣ እግዚአብሔር ፣ ነው ። ጽቀር ፣ ፩-፯ ።

፱ ፣ አርኅዉ ፣ ኆኃተ ፣ መኳንንት ።

መኳንንተ ፣ ሰማይ ፣ ሚካኤል ፣ ገብርኤል ፣ ሩፋኤል ፣ ኆኃተ ፣ ሰማይን ፣ ክፈቱ ። እንዳለፈው ።

ወይትረኃዋ ፣ ኆኃት ፣ እለ ፣ እምፍጥረት ።

ከጥንት ፣ ጀምሮ ፣ ተከፍተው ፣ የማያውቁ ፣ ኆኃተ ፣ ሰማይ ፣ ይከፈቱ ፣ እንዳለፈው ።

ወይባእ ፣ ንጉሠ ፣ ስብሐት ።

የክብር ፣ ባለቤት ፣ ጌታ ፣ በብርሃን ፣ በሥልጣን ፣ በቅዳሴ ፣ ይኑር ። ቍ ፣ ፮ ።

፲ ፣ መኑ ፣ ውእቱ ፣ ዝንቱ ፣ ንጉሠ ፣ ስብሐት ።

ንጉሠ ፣ ስብሐት ፣ ቢለው ፣ የክብር ፣ ባለቤት ፣ ማን ፣ ነው ፣ ሲለው ።

እግዚአብሔር ፣ አምላከ ፣ ኃያላን ፣ ውእቱ ፣ ዝንቱ ፣ ንጉሠ ፣ ስብሐት ።

አምላከ ፣ ኃያላን ፣ ለማለት ፣ ደገመው ፣ አንድም ፣ ቢርቀው ፣ ቢያምረው ። አንድም ፣ ስለሁለቱ ፣ ነገድ ፣ ስለ፱ ፣ ሥሩ ፣ ነገድ ። አንድም ፣ ግዕመ ፣ ዝማሬ ፣ ነው ፣ የክብር ፣ ባለቤትማ ፣ የኃያላኑ ፣ ፈጣሪ ፣ እግዚአብሔር ፣ ነዋ ። ኃይል ፣ ሥጋዊ ፣ ኃይል ፣ መንፈሳዊ ፣ ኃይል ፣ መልአካዊ ፣ አለ ። ኃይል ፣ ሥጋዊ ፣ እንደ ፣ ጌዴዎን ፣ እንደ ፣ ዮፍታሔ ፣ እንደ ፣ ሶምሶን ፣ እንደ ፣ ዳዊት ፣ ጠላትን ፣ ድል ፣ መንሣት ፣ ነው ። ኃይል ፣ መንፈሳዊ ፣ ኀጢአትን ፣ አጋንንትን ፣

ድል ፡ መንግሥት ፡ ነው ፡፡ ወይቤ ፡ ዝኩ ፡ አብርሃም ፡ ኢሞጻኒ ፡ ሰይፈ ፡ ጸላኢ ፡ እንዲል ፡፡

ኃይል ፡ መልአከዊ ፡ ወነሥአ ፡ ፩ ፡ መልአክ ፡ ኀያል ፡ ወጽኑዕ ፡ ዕብነ ፡ ዐቢየ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ማኅረፅ ፡ እንዲል ፡፡ ራእ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ፡፡ መላእክት ፡ ጥንቱን ፡ በተፈጥሮ ፡ ኀያላን ፡ ናቸው ፡ ኋላም ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ እያገለገሉ ፡ ኃይል ፡ ሲጨመርላቸው ፡ ይኖራሉና ፡፡

## መዝሙር ፡ ፳፭ ፡፡

፩ ፡ ኀቤከ ፡ እግዚኦ ፡ አንቃዕደኩ ፡ ነፍስየ ፡ አምላኪየ ፡፡

ስለ ፡ ትሩፋት ፡ ተናግሮታል ፡፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ ኀቤከ ፡ አንቃዕዶኩ ፡ ነፍስየ ፡ ሲል ፡ ነው ፡፡ አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ በተዘክሮ ፡ ልቡና ፡ በአንቃዕድዎ ፡ ኅሊና ፡ በሠፊሐ ፡ እእዳው ፡ በጸልዮ ፡ ጸሎት ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለመንሁ ፡፡

፪ ፡ ወኪያከ ፡ ተወከልኩ ፡ ወኢይትኃፈር ፡ ለዓለም ፡፡ ኢሳ ፡ ፰ ፡ ፲፰ ፡፡ ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ፡፡

ባንተ ፡ አመንሁ ፡ እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ በመከራው ፡ አላፍርም ፡ አልፈር ፡፡ እንድም ፡ በመከራው ፡ እንዳላፍር ፡ ባንተ ፡ አመንሁ ፡፡

ወኢይሥሐቁ ፡ ጸላዕትየ ፡፡

ጠላቶቼም ፡ አይዘብቱብኝም ፡ አይዘብቱብኝ ፡፡ እንድም ፡ እንዳይዘብቱብኝ ፡ ባንተ ፡ አመንሁ ፡፡ መዘበትማ ፡ ዘብተውበት ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ እንደ ዘበቱብኝ ፡ አይቅሩ ፡ ሲል ፡ ነው ፡፡

፫ ፡ እስመ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይሴፈዉከ ፡ ኢይትኀፈሩ ፡፡ ኢሳ ፡ ፳፰ ፡ ፲፮ ፡፡ ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ፡፡

አንተን ፡ አለኝታ ፡ ያደረጉ ፡ ሁሉ ፡ አያፍሩምና ፡፡ ኢይትኃፈር ፡ ላለው ፡፡ ለይትኃፈሩ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይኤብሱ ፡ ዘልፈ ፡፡

እነ ፡ ማን ፡ ይፈሩ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ፡፡ ሐፋርሰ ፡ ማፈርስ ፡ አንተን ፡ የሚበድሉ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ፡፡

፬ ፡ ፍናዊከ ፡ እግዚኦ ፡ አምርኒ ፡፡

አቤቱ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ጐዳና ፡ መርተህ ፡ አውጣኝ ፡፡ እንድም ፡ ዘጠኙን ፡ ሕገጋት ፡ ግለጽልኝ ፡፡

ወአሠሪ ፡ ሊኦከ ፡ ምሀረኒ ፡፡

ፍለጋህንም ፡ አመልክተኝ ፡፡ እንድም ፡ ኢታምልክን ፡ ግለጽልኝ ፡፡ ፍለጋ ፡ ከዋና ፡ ጎዳና ፡ ከመንደር ፡ እንዲያደርስ ፡፡ ኢታምልክም ፡ ከዘጠኙ ፡ ታደርሳለችና ፡ አሥር ፡ አላት ፡፡

፭ ፡ ወምርሐኒ ፡ በጽድቅከ ፡፡

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ሐሊቆ ፡ ባልኸው ፡ በጽኑ ፡ ቀጠሮህ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ጎዳና ፡ መርተህ ፡ አውጣኝ ፡፡ እንድም ፡ ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፡ አስተምረኝ ፡፡

ወምሕረኒ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ አምላኪየ ፡ ወመድኃኒየ ፡፡

ድኅነቴን ፡ የምታደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ እዘንልኝ ፡ ራራልኝ ፡፡

ወኪያከ ፡ እሴፎ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡፡

ዘወትርም ፡ አንተን ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁና ፡፡



፮ ፡ ተዘከር ፡ ግሀለከ ፡ እግዚኦ ፡፡

አቤቱ ፡ ይቅርታህን ፡ አስብ ፡፡

ወምሕረትከኒ ፡ እስመ ፡ ለዓለም ፡ ውእቱ ፡፡

ምሕረተከኒ ፡ ብለህ ፡ ቸርነትህንም ፡ አስብ ፡፡ ለዘላለም ፡ ነውና ፡፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንድም ፡ ለሰው ፡ ነውና ፡ ለሰው ፡ ስለ ሆነ ፡፡ እንድም ፡ ይቅርታህን ፡ አስብ ፡ ዋዌውን ፡ ትተህ ፡ ቸርነትህ ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ፡ ስለሆነ ፡፡ እንድም ፡ ቸርነትህም ፡ ለዘላለም ፡ ለሰው ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራል ፡፡

፯ ፡ ኃጢአትየ ፡ ዘበንእስየ ፡ ወእበድየ ፡ ኢትዝከር ፡ ሊተ ፡፡

በሕፃንነቴ ፡ በስንፍናዬ ፡ የሠራሁትን ፡ ኃጢአቴን ፡ ዕዳ ፡ አታድርግብኝ ፡ እንድም ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሮ ፡ የሠራሁትን ፡ ኀጢአቴን ፡ ዕዳ ፡ አትበልብኝ ፡ ይህንንም ፡ መጸለይ ፡ የሚገባ ፡ ከሚመጣው ፡ ኃጢአት ፡ ተጠብቆ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሚመጣው ፡ ሳይከለከሉ ፡ መጸለይ ፡ ባለፈው ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ በሚመጣው ፡ ቅሠፈኝ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ወስዶታል ፡፡

ወበከመ ፡ ግሀልከ ፡ ተዘከረኒ ፡፡

እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ እንደ ፡ ይቅርታህ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ አስበኝ ፡፡

በእንተ ፡ ምሕረትከ ፡ እግዚኦ ፡፡

አቤቱ ፡ ቸርነትህን ፡ አማላጅ ፡ ስላደረግሁ ፡ በቸርነትህ ፡ ስላመንሁ ፡፡

፰ ፡ ኄር ፡ ወጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡፡

እግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ቸር ፡ የባሕርይ ፡ ጻድቅ ፡ ነው ፡፡ ሰው ፡ ቸር ፡ ቢሆን ፡ እውነተኛ ፡ አይሆንም ፡ እውነተኛ ፡ ቢሆን ፡ ቸር ፡ አይሆንም ፡፡ እሱ ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ የባሕርዩ ፡ ነውና ፡፡ እንድም ፡ ኄርኒ ፡ እንደወታደር ፡ ጻድቅኒ ፡ እንደ ፡ መኰንን ፡፡ ወታደር ፡ ቸር ፡ ነው ፡ ገንዘቡን ፡ ይሰጣል ፡ እውነት ፡ ግን ፡ የለውም ፡ መኰንንም ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፡ ገንዘቡን ፡ ግን ፡ አይሰጥም ፡፡ እንድም ፡ ፈጽሞ ፡ ቸር ፡ ነው ፡፡

በእንተዝ ፡ ይመርሖሙ ፡ ፍኖተ ፡ ለእለ ፡ ይስሕቱ ፡፡

የኢየሩሳሌም ፡ መንገድ ፡ ለጠፋቸው ፡ ለትሩፋን ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ መንገድ ፡ ይመራቸዋል ፡፡

፱ ፡ ወይሜህሮሙ ፡ ፍትሐ ፡ ለየዋሃን ፡፡

ለቅኖችም ፡ ፍርድን ፡ ይገልጽላቸዋል ፡፡ ኢሳ ፡ ፵፰ ፡ ፲፯ ፡፡

ወይኤምሮሙ ፡ ፍኖቶ ፡ ለልቡባን ፡፡

ጭምት ፡ ገራም ፡ ለሚሆኑ ፡ ጎዳና ፡ ያሳያቸዋል ፡፡ ከመ ፡ ኖኅ ፡ ልቡብ ፡ በየውሀቱ ፡ እንዲል ፡፡

እንድም ፡ የጠበቀ ፡ እንደሆን ፡ ብልህ ፡ አዋቂ ፡ ለሚሆኑ ፡ በል ፡፡ እንድም ፡ (በእንተዝ ፡ ይመርሖሙ ፡ ፍኖተ ፡ ለእለ ፡ ይስሕቱ) ፡ የከተማው ፡ ጎዳና ፡ ለጠፋቸው ፡ ለሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ አንትሙ ፡ ሲድራቅ ፡ ወሚሳቅ ፡ ወአብደናጎ ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንዑ ፡ ፃኡ ፡ ዝየ ፡ ብሎ ፡ የከተማውን ፡ መን

ገድ ፡ መርቶ ፡ ያወጣቸዋል ። ፍኀ ፡ ፫ ፡ ፳፯ ፡ ወይሚሕሮሙ ፡ ፍትሐ ፡ ለየዋሃን ፡ ብልሀ ፡ አዋቂ ፡ ለሚሆኑ ፡ ለነዳንኤል ፡ ፍርድን ፡ ይገልጽላቸዋል ፡ ሶስና ፡ የምትባል ፡ ደግ ፡ ሴት ፡ ነበረች ። ረበናት ፡ ሔደው ፡ በጂ ፡ በይን ፡ አሏት ፡ አይሆንም ፡ አለቻቸው ። ከእለታት ፡ ባንዳቸው ፡ ከትክልት ፡ ቦታ ፡ ገብታ ፡ ስትታጠብ ፡ ደርሰው ፡ በጂ ፡ በይን ፡ ያለዚያ ፡ ከወንድ ፡ አገኘናት ፡ ብለን ፡ እንሥሃለን ፡ አሏት ። አድርጌው ፡ ፈጣሪየ ፡ ኪፈርድብኝ ፡ ሳላደርገው ፡ ሞት ፡ ቢፈረድብኝ ፡ ይሻለኛል ፡ አለቻቸው ። ከወንድ ፡ አገኘናት ፡ ብለው ፡ ነገር ፡ ሠሩባት ፡ አእሩግ ፡ እስራኤል ፡ ተሰብስበው ፡ በደንጊያ ፡ ተወግራ ፡ ትሙት ፡ ብለው ፡ ፈረዱባት ። ዳንኤል ፡ እንደ ፡ ሕፃናት ፡ ከታች ፡ ተቀምጦ ፡ ነበርና ፡ አብዳንኑ ፡ አንትሙ ፡ አዕሩግ ፡ እስራኤል ፡ ዘእንበለ ፡ ታእምሩ ። ወትጠይቁ ፡ ዘገብረት ፡ ትኴንኑ ፡ ወለተ ፡ እስራኤል ፡ መርምራችሁ ፡ ማድረግ ፡ አለማድረጓን ፡ ሳታውቁ ፡ በደንጊያ ፡ ትወገር ፡ ብላችሁ ፡ ትፈርዳላችሁን ፡ አላቸው ፡ ምን ፡ እናድርግ ፡ አሉት ። እየብቻ ፡ አድርጋችሁ ፡ መርምሯቸው ፡ አላቸው ። ቢመረምሯቸው ፡ አንዱ ፡ ከዕፀ ፡ ሰኪኖን ፡ ሥር ፡ አንዱ ፡ ከዕፀ ፡ ጵልንትዩ ፡ እግር ፡ አየናት ፡ አሉ ፡ ከመገኑ ፡ ከነ ፡ ነገርከሙ ፡ ገዘርወ ፡ ወገዘርዞረ ፡ ነገራችሁ ፡ እንደዚህን ፡ ብላሽ ፡ ሆነ ። ወናሁ ፡ ተአዘዘ ፡ መልአክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሥጥቅሙ ፡ ከመ ፡ እርጋሄ ። እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ እንዳክርማ ፡ ሊሰነጥቃችሁ ፡ ታዟል ፡ አላቸው ። ወዲያው ፡ ከሁለት ፡ ከሁለት ፡ ተሰንጥቀዋል ። እሱንም ፡ ነዓ ፡ ንበር ፡ ማእከሌነ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልሐቀ ፡ ኪያከ ፡ ብለውታል ።

ወይኤምሮሙ ፡ ፍኖቶ ፡ ለልቡባን ። ፍኀ ፡ ፱ ፡ ፳፮ ። ለትሩፋን ፡ ፍኖተ ፡ አበውን ፡ ይመራቸዋል ፡ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ ከዘጠኙ ፡ ነገድ ፡ ከመንፈቅ ፡ ተወፃዕተው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የዘሩባትን ፡ ታበቅላለች ፡ የተከሉባትን ፡ ታጸድቃለች ፡ በልተን ፡ ጠጥተን ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በድለን ፡ ሁለተኛ ፡ ይህ ፡ ጺዋዌ ፡ ሊያገኘን ፡ አይደለምን ፡ ብለው ፡ ዕዝራን ፡ አለቃ ፡ አድርገው ፡ እግራቸው ፡ እንዳደረሳቸው ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሔደዋል ፡ ከምዉት ፡ ባሕር ፡ ደረሱ ፡ ይኸውም ፡ የዶሮ ፡ ላባ ፡ ዳመጠ ፡ ጥጥ ፡ የሚያሰጥም ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ፍንጃል ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ጸንቶላቸው ፡ ተሻግረው ፡ ብሔረ ፡ ዓዚፍ ፡ ደረሱ ፡ መካነ ፡ ዕረፍት ፡ ማለት ፡ ነው ። በሦስት ፡ ሩካቤ ፡ ሦስት ፡ ልጅ ፡ ይወልዳሉ ፡ ሁለቱ ፡ ወንዶች ፡ አንዲቱ ፡ ሴት ፡ አንዱ ፡ አባቱን ፡ አንዱ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግላል ። ሴቲቱ ፡ እናቷን ፡ ታገለግላለች ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ኑረው ፡ ይሞታሉ ። በሐማዊ ፡ መሲሕ ፡ ጊዜ ፡ በሕ

ሩ ፡ ተከፍሎላቸው ፡ ተሻግረው ፡ በሰማዕትነት ፡ ይሞታሉ ። ዘሲማስ ፡ የሚባል ፡ ባሕታዊ ፡ ከወዲያና ፡ ከወዲህ ፡ የበቀለ ፡ ዛፍ ፡ ተገናኝቶለት ፡ ተሻግሮ ፡ ገብቷል ። የሚላኩት ፡ ብላቴኖች ፡ ሰጡት ፡ ሥራ ፡ ያስፈቱኛል ፡ ብሎ ፡ አባቶቻችሁ ፡ የመጡ ፡ እንደሆነ ፡ የለም ፡ በኋቸው ፡ አላቸው ። መጥተው ፡ ንገሩልን ፡ አሏቸው ፡ በሀገራቸው ፡ እውነት ፡ እንጂ ፡ ሐሰት ፡ የለምና ፡ የለም ፡ በኋቸው ፡ ብሎናል ፡ አሏቸው ፡ በሀገራችን ፡ የጠላነውን ፡ ሐሰት ፡ ተከትሎ ፡ መጥቶ ፡ ሊያስተምርብን ፡ ነውን ፡ ብለው ፡ ውጣልን ፡ አሉት ። ቢሔድ ፡ ዛፉ ፡ ተለያይቶ ፡ አገኘው ፡ ተመልሰ ፡ ማሩኝ ፡ አላበጀሁም ፡ አላቸው ፡ ይቅር ፡ ብለዉት ፡ ቢሔድ ፡ ተገናኝቶለት ፡ ተሻግሮ ፡ ወጥቷል ።

፲ ፡ ኵሉ ፡ ፍኖቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ግሀል ፡ ወጽድቅ ።

የሚሔድበት ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ የሚሔድበት ፡ ቢኖር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጎዳናው ፡ ሁሉ ። እንድም ፡ የሚሠራው ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ የሚሠራው ፡ ቢኖር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ይቅርታ ፡ ቸርነት ፡ ነው ።

ለእለ ፡ የኀሥሡ ፡ ሕጎ ፡ ወስምዖ ።

ያው ፡ ግን ፡ ለሁሉ ፡ አይደለም ፡ ሕጎ ፡ ዘጠኙን ፡ ወስምዖ ፡ ኢታምልክን ፡ ለሚጠብቁ ፡ ነው ።

፲፩ ፡ በእንተ ፡ ስምከ ፡ እግዚእ ።

እቤቱ ፡ በስምህ ፡ ስላመንሁ ፡ ስምህን ፡ እግላጅ ፡ ስላደረግሁ ። ስምየኒ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ስላልሀ ።

ወሥረይ ፡ ሊተ ፡ ኵሉ ፡ ኃጢአትየ ፡ እስመ ፡ ብዙኅ ፡ ውእቱ ።

ብዙ ፡ ነውና ፡ ኃጢአቴን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ። ይህስ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ምንም ፡ ብዙ ፡ ቢሆን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ይኋል ።

፲፪ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘይፈርሆ ፡ ለእግዚአብሔር ። ኢሳ ፡ ፶ ፡ ፲ ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የሚፈራው ፡ የሚያመልከው ፡ ማን ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ያነቃቃል ።

ወይመርሆ ፡ ፍኖተ ፡ እንተ ፡ ኃረየ ።

እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ሥራ ፡ የሚገልጽለት ፡ ማነው ። እንድም ፡ ራሱ ፡ ሊሠራው ፡ የሚወደውን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚፈጽምለት ፡ ማነው ።

፲፫ ። ወነፍሱሂ ፡ ውስተ ፡ ሠናይ ፡ ተኃድር ።

አይገኝም ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሰውነቱ ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ነፍሱ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ትኖራለች ።

ወዘርዑሂ ፡ ይወርስዋ ፡ ለምድር ።

ልጆቹ ፡ የልጅ ፡ ልጆቹ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ የወዲያኛውንም ፡ ዓለም ፡ ይወርሳሉ ።

፲፬ ፡ ኀይሎሙ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእለ ፡ ይፈርህዎ ።

እግዚአብሔር ፡ ለሚፈሩት ፡ ለሚያመልኩት ፡ ኃይላቸው ፡ ነው ።

ወዕፀዊ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለእለ ፡ ይፈርህዎ ።

እግዚአብሔር ፡ ስሙን ፡ ለሚጠሩት ፡ ለሚያመሰግኑትም ፡ ኃይላቸው ፡ ነው ።

ወሕጎ ፡ ይሜህሮሙ ።

ሕጉንም ፡ ይገልጽላቸዋል ፡ ያስተምራቸዋል ።

፲፭ ፡ አዕይንትየሰ ፡ ዘልፈ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

የኔም ፡ ዓይኖቼ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመለከታሉ ። እንደ ፡ በለቀጠሮ ፡ ከሁን ፡ አሁን ፡ ይመጣል ፡ እያለ ፡ መንገዱን ፡ እንዲመለከት ፡ እኔ ስም ፡ ከዘንድሮ ፡ ከርሞ ፡ ያወጣን ፡ ይሆንን ፡ በማለት ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይባልሆን ፡ እመሥገርት ፡ ለእገርየ ።

እሱ ፡ ወገናቼን ፡ እንድም ፡ ሕዋሳቶቼን ፡ ከመከራ ፡ ያድናቸዋልና ።

፲፮ ፡ ነጽር ፡ ላዕሌየ ፡ ወተሣሃለኒ ።

እኔን ፡ በዓይነ ፡ ምሕረትህ ፡ እዩኝ ፡ ተመልከተኝ ፡ እንዲህ ፡ አይተህ ፡ ተመልከተህ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

እስመ ፡ ባሕታዊ ፡ ወነዳይ ፡ አነ ።

ብቸኛ ፡ (ባሕታዊ) ፡ ነኝና ፡ ነዳይም ፡ ነኝና ፡ ባሕታዊ ፡ የሚባል ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ንቆ ፡ አጥቅቶ ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ኑሮን ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ በበረሀ ፡ ያደረገ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ አባት ፡ እናቱ ፡ ነገዱ ፡ ወገኑ ፡ የሞተበት ፡ የተጠቃ ፡ የሚበላውን ፡ የሚጠጣውን ፡ የሚለብሰውን ፡ ያጣ ፡ ሁሉ ፡ ባሕታዊ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በትሩፋን ፡ ተደርጎበቸዋል ።

፲፯ ፡ መብዙኀ ፡ ሐዘኑ ፡ ለልብየ ።

የልቡናዬ ፡ ሐዘኑ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ብዙ ፡ ነውና ።

አድኅነኒ ፡ እምንዳቤየ ።

ከገኘኝ ፡ መከራ ፡ አድነኝ ።

፲፰ ፡ ርኢ ፡ ሕማምየ ፡ ወሥራኅየ ። ስቆ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

መከራዬንም ፡ እይ ፡ ተመልከት ፡ ተቀርዶዬንም ፡ እይ ፡ ተመልከት ። እንድም ፡ አይተህ ፡ ተመልከተህ ።

ወኅድግ ፡ ሊተ ፡ ኵሎ ፡ ኃጢአትየ ።

ኀጢአቴን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ተውልኝ ።

፲፱ ፡ ወርኢ ፡ ከመ ፡ በዝኁ ፡ ጸላእትየ ።

ጠላቶቼ ፡ እንደበዙ ፡ መጠን ፡ እይ ፡ ተመልከት ።

ጽልአ ፡ በዓመፃ ፡ ይጸልኡኒ ።

ትሩፍ ፡ ቢጠሉት ፡ አይጠላ ፡ ቢያሙት ፡ አያማን ፡ አለ ፡ ብትጠላቸው ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ ሳልጠላቸው ፡ በግፍ ፡ ጠሉኝ ።

፳ ፡ ዕቀብ ፡ ለነፍስየ ፡ ወአድኅና ።

እንዲህ ፡ ነውና ፡ ነፍሴን ፡ (ሰውነቴን) ፡ ከመከራው ፡ ጠብቀህ ፡ አድናት ።

ወኢይትኃፈር ፡ እስመ ፡ ኪያከ ፡ ተወከልኩ ።

ባንተ ፡ እምኖለሁና ፡ በመከራው ፡ አልፈር ፡ አላፍርም ።



፳፩ ፡ የዋሃን ፡ ወራትዓን ፡ ተለወኒ ።

ትሩፍ ፡ ቢጨንቅህ ፡ ብትያዝ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ እንደ ፡ ወትሮ ፡ አይምሰልህ ። ቅኖች ፡ መምህራን ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ተከትለውኛል ፡ እኒያ ፡ ያስተምሩኛል ። እምኖት ፡ ጸልኡ ፡ ዘይጌሥፆሙ ፡ እንዲል ። ቀድሞ ፡ ሊያስተምሯቸው ፡ ሲሔዱ ። ይህ ፡ ለካፋ ፡ የመጣበትን ፡ ቀላውጠ ፡ መሔድ ፡ ይመስል ፡ ማን ፡ አስተምረኝ ፡ ብሎታል ፡ ይሏቸው ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ግን ፡ እየሔዱ ፡ አስተምሩን ፡ የሚሏቸው ፡ ሁነዋልና ።

እስመ ፡ ተሰፈውኩከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ አንተን ፡ አለኝታ ፡ አድርጌሃለሁና ።

፳፪ ፡ ያድኅኖ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ እምኵሉ ፡ ምንዳቤሁ ።

እኔ ፡ እቸኩላለሁ ፡ እንጂ ፡ እስከዚያውም ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ከገኘው ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ ያድነዋል ። ኢሳ ፡ ፳፭ ፡ ፱ ።

## መዝሙር ፡ ፳፭ ።

፩ ፡ ፍታሕ ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ አንሰ ፡ በየውሐትየ ፡ አሐውር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ። አቤቱ ፡ በቅንነቴ ፡ እንድም ፡ በሕግ ፡ ጸንቼ ፡ እኖራለሁና ፡ ፍረድልኝ ።

ወተወከልኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኢይድክም ።

በእምልኩተ ፡ ጣዖት ፡ እንዳልደክም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመንሁ ። እምልኩተ ፡ ጣዖትን ፡ ድካም ፡ አለው ። ከዱር ፡ ገብቶ ፡ የጠመመውን ፡ ትቶ ፡ የቀናውን ፡ ቆርጦ ፡ ንድፉን ፡ ቅቡን ፡ ሲያከናውኑ ፡ ብዙ ፡ ድካም ፡ አለበትና ። እንድም ፡ በኃጢአት ፡ እንዳልደክም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመንሁ ። ድካም ፡ ዘይቤ ፡ ኃጢአት ፡ ውእቱ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ (ከመ ፡ ኢይድግም) ፡ ይላል ። እግዚአብሔርን ፡ መበደልን ፡ እንዳልደግም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመንሁ ።

፪ ፡ ፍትንኒ ፡ እግዚኦ ፡ ወአመክረኒ ።

ብትያዝ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ። አቤቱ ፡ እውነቴም ፡ ሐሰቴም ፡ እንደሆነ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አውጥተህ ፡ መርምረህ ፡ ፍተነኝ ።

ፍትን ፡ ልብየ ፡ ወኵልያትየ ።

ኵላሊቴ ፡ ያጤሰውን ፡ ልቡናዬ ፡ ያሰበውን ፡ መርምረህ ፡ እወቅ ። መዝ ፡ ፲፱ ፡ ፳፫ ፡ ፳፪ ።

፫ ፡ ከመ ፡ ምሕረትከ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንትየ ፡ ወእቱ ።

ቸርነትህ ፡ በፊቴ ፡ እንዳለ ፡ ሕግህን ፡ እንድጠብቅ ።

ወተፈሣሕኩ ፡ በአድኅኖትከ ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፪ ፡ ፩ ።

በትድግናህ ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

፬ ፡ ወኢነበርኩ ፡ ውስተ ፡ ዓውደ ፡ ከንቱ ።

ከዚህ ፡ ቀድም ፡ ጣዖት ፡ ለማምለክ ፡ በጣ

ዖት ፡ አደባባይ ፡ አልተቀመጥሁም ።

ወኢቦእኩ ፡ ምስለ ፡ ዓማፅያን ።

ከባቢሎናውያን ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ አልገባሁም ።

፭፡ ጸላእኩ ፡ ማኅበረ ፡ እኩያን ።

የባቢሎናውያንን ፡ አንድነት ፡ ጠላሁ ፡ ጠላሁ ፡ እንጂ ።

ወኢይነብር ፡ ምስለ ፡ ረሲዓን ።

ከዳተኞች ፡ ከሚሆኑ ፡ ከባቢሎናውያን ፡ ጋራ ፡ አልኖርም ። ኤር ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ።

፮፡ ወእሐፅብ ፡ በንጹሕ ፡ እደውየ ።

አንዳችም ፡ የምግባር ፡ ሕፀፅ ፡ ቢኖር ብኝ ፡ እጄ ፡ ልቡናዬን ፡ በማየ ፡ ንስሐ ፡ እጥባለሁ ።

ወእዑውድ ፡ ምሥዋዒከ ፡ እግዚኦ ።

እንዳስቆራቢ ፡ ምሥዋዓ ፡ ብርቱን ፡ ከብቤ ፡ እቆማለሁ ።

፯፡ ከመ ፡ እስማዕ ፡ ቃለ ፡ ስብሐቲከ ።

ያልተማርሁትን ፡ እማር ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ እንግር ፡ ኵሎ ፡ መንክረከ ።

የተማርሁትንም ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ።

፰፡ እግዚኦ ፡ አፍቀርኩ ፡ ስነ ፡ ቤትከ ።

አቤቱ ፡ የቤተ ፡ መቅደስን ፡ ጌጥ ፡ ወደ ድሁ ፡ ሱሳን ፡ ወርድ ፡ ይስቡበታል ፡ አበበ ፡ ያፈነዱበታል ፡ ዛፍ ፡ ይቀርጹ በታልና ።

ወመካነ ፡ ማኅደረ ፡ ስብሐቲከ ።

መላውን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወደድሁ ።

አንድም ፡ (እግዚኦ ፡ አፍቀርኩ) ፡ ነቢ ያት ፡ ከህናትን ፡ ወደድሁ ። ወንሣእኩ ፡ ዪተ ፡ አብትረ ፡ ለእሐቲ ፡ ሰመይክዋ ፡ ስነ ፡ ወለካልእታ ፡ ሐብለ ፡ እንዲል ። (ወመካነ) ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ወደድሁ ። አንድም ፡ (ስነ ፡ ቤትከ) ፡ መላውን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ (ወመካነ) ፡ ማደሪያህ ፡ የሚሆን ፡ መቅደሱን ፡ ብቻ ፡ አንድም ፡ (ስነ ፡ ቤትከ) ፡ (ማኅደረ ፡ ስብሐቲከ) ፡ የምስጋናህ ፡ ማደሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ የከ ህናቱን ፡ ቤት ፡ ወደድሁ ። ቤትከ ፡ ስብ ሐቲከ ፡ ብሎ ፡ ዘረዘረላቸው ፡ ገባዒ ፡ ይነገርበታል ፡ ይመሰገንበታልና ።

፱፡ ኢትግድፋ ፡ ምስለ ፡ ኃጥአን ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ ከባቢሎናውያን ፡ ጋራ ፡ አታጥፋት ።

ወኢምስለ ፡ እድወ ፡ ደም ፡ ለሕይወትየ ።

የሰው ፡ ግንባር ፡ ከሚከሰክሱ ፡ ደመ ፡ በግዕን ፡ ለጣዖት ፡ ከሚያፈሱ ፡ ከባቢ ሎናውያን ፡ ጋራ ፡ ሰውነቴን ፡ በመከ ራው ፡ አትጣላት ።

፲፡ እለ ፡ ዓመፃ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ።

እጃቸው ፡ ነፍስ ፡ መግደልን ፡ የተመላ ፡

ወምልእት ፡ ህልያን ፡ የማናሙ ።

ቀኝ ፡ እጃቸውም ፡ ማማለጃን ፡ የተ መላ ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ።

፲፩፡ አንሰ ፡ በየውሀትየ ፡ አሐውር ።

እኔ ፡ ግን ፡ በቅንነቴ ፡ ጸንቼ ፡ እኖራለሁ ።

አድኅንኒ ፡ እግዚኦ ፡ ወተሣሃለኒ ።

አቤቱ ፡ አንተም ፡ ይቅር ፡ ብለህ ፡ አድነኝ ።



፲፪፡ እስመ ፡ በርቱዕ ፡ ቆመ ፡ እገርየ ።

ወገኖቼ ፡ አንድም ፡ እግሮቼ ፡ በተስ ፋው ፡ በመርህበ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቆመ ዋልና ፡ አንድም ፡ በሕግ ፡ ጸንተዋልና ።

በማኅበር ፡ እባርከከ ፡ እግዚኦ ። መዝ ፡ ፳፩ ፡ ፪ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ማለት ፡ ይቅር ፡ ብት ለኝ ፡ ብታድነኝ ፡ አቤቱ ፡ በጉባዔ ፡ አመ ሰግንሃለሁ ።

## መዝሙር ፡ ፳፮ ።

፩፡ እግዚአብሔር ፡ ያበርሀ ፡ ሊተ ፡ ያድኅነኒ ፡ ምንትኑ ፡ ያፈርሃኒ ።

ስለሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ። ከመከ ራዬ ፡ ያድነኝ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡ ረድኤቱን ፡ ያበራልኛል ፡ የባ ለዚያ ፡ ጌታ ፡ ምን ፡ ያስፈራኛል ። አን ድም ፡ ከመከራዬ ፡ አድኖ ፡ በተድላ ፡ በድስታ ፡ ያኖረኛል ፡ የባለዚያ ፡ ጌታ ፡ ምን ፡ ያስፈራኛል ፡ አብርሂ ፡ አብርሂ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዲል ። ኢሳ ፡ ፷ ፡ ፩ ።

እግዚአብሔር ፡ ምዕመና ፡ ለሕይወትየ ፡ ምንትኑ ፡ ያደነግጸኒ ።

እግዚአብሔር ፡ ለሰውነቴ ፡ ወዳጅዋ ፡ ድኅነቷን ፡ የሚያደርግላት ፡ ነው ፡ የባ ለዚያ ፡ ጌታ ፡ ምን ፡ ያስፈራኛል ።

፪፡ ሶበ ፡ ይቀርቡኒ ፡ እኩያን ፡ ይብልዑኒ ፡ ሥጋየ ።

እለ ፡ ሰናክሬም ፡ ሥጋዬን ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ሰውማ ፡ ሰውን ፡ ይበላዋልን ፡ ብሎ ፡ ገንዘቤን ፡ ሊዘርፉ ፡ እኔን ፡ ሊያጠፉ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ኤፍ ሬም ፡ ይበልዖ ፡ ለምናሴ ፡ ወምናሴ ፡ ይበልዖ ፡ ለኤፍሬም ፡ እንዲል ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፳፩ ።

ጸላእትየሰ ፡ እለ ፡ ይሣቅዩኒ ፡ እሙንቱ ፡ ደከሙ ፡ ወወድቁ ።

ጠላቶቼ ፡ ከጠፉ ፡ በኋላ ፡ ተናግሮታል ፡ ብሎ ፡ መከራ ፡ የሚያመጡብኝ ፡ ጠላ ቶቼ ፡ እለ ፡ ሰናክሬም ፡ ደከሙ ፡ በለኪ ሶን ፡ (ወወድቁ) ፡ በነነዌ ። አንድም ፡ በነ ፍስ ፡ በሥጋ ፡ ጠፉ ።

፫፡ እመኒ ፡ ጸብእኒ ፡ ተዓይኒ ፡ ኢይፈርሃኒ ፡ ልብየ ።

ሰናክሬም ፡ ቢጣላኝ ፡ ልቡናዬ ፡ አይሸበ ርብኝም ።

ወእመኒ ፡ ሮዱኒ ፡ ፀዓዲት ፡ አንስ ፡ በቱ ፡ ተወከልኩ ።

ሰራዊቱም ፡ ቢከቡኝ ፡ በሱ ፡ እምኖለ ሁና ፡ አልፈራም ፡ አንድም ፡ ጠላቶቼ ፡ ሳይጠፉ ፡ አስቀድሞ ፡ ተናግሮታል ፡ ብሎ ፡ (ጸላእትየሰ ፡ እለ ፡ ይሣቅዩኒ) ፡ መከራ ፡ የሚያመጡብኝ ፡ ጠላቶቼ ፡ እነ ፡ ሰናክሬም ፡ (ይደክሙ ፡ ወይወ ድቁ) ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ይጠፋሉ ። (እመኒ ፡ ፀብዓኒ) ፡ የነሰናክሬምስ ፡ ይቅ ርና ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በጠላትነት ፡ የሚነሳብኝ ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ ቢጣላኝ ፡ ልቡናዬ ፡ አይሸበርብኝም ፡ (ወእመኒ ፡ ሮዱኒ) ፡ ሠራዊቱም ፡ ቢከቡኝ ፡ ባንተ ፡

2014 04 17

እምኛለሁና ፡ እልፈራም ። ኢሳ ፡ ፶ ፡ ፯ ።

፬ ፡ አሐተ ፡ ሰአልክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወኪያሃ ፡ እኀሥሥ ።

እግዚአብሔርን ፡ አንዲት ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ለመንሁት ፡ እሷኑ ፡ እሻለሁ ። እንድም ፡ እሷን ፡ ብቻ ፡ የምፈልገውን ፡ አንዲት ፡ ነገር ፡ ለመንሁት ።

ከመ ፡ እንድር ፡ ቤቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወትየ ።

እሷውም ፡ በለ ፡ ዘመኔ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ አድሮበት ፡ በሚኖር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያኖረኝ ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንድኖር ፡ ያደርገኝ ፡ ዘንድ ፡ ናት ።

ወእርአይ ፡ ሥርጉተ ፡ ዘያሠምር ፡ ለእግዚአብሔር ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ነገር ፡ ይገልጽልኝ ፡ ዘንድ ፡ እንዲያደርገኝ ፡ መሆን ፡ ናት ። እንድም ፡ ዘእሠምር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የማሰኝበትን ፡ ነገር ፡ ይገልጽልኝ ፡ ዘንድ ፡ እንዲያደርገኝ ፡ መሆን ፡ ናት ።

ወእሑር ፡ እስመ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደሱ ።

ቤተ ፡ መቅደሱንም ፡ ጽሙድ ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ ቅኑት ፡ እንደ ፡ ገበሬ ፡ ሁኜ ፡ እገለግል ፡ ዘንድ ፡ እንዲያደርገኝ ፡ መሆን ፡ ናት ።

፭ ፡ እስመ ፡ ኀብአኒ ፡ ውስተ ፡ ጽላሎቱ ፡ በዕለተ ፡ መንሱትየ ።

በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ በጽላሎተ ፡ ረድኤቱ ፡ ሠውሮኛልና ።

ወሠወረኒ ፡ በምኅባአ ፡ ጽላሎቱ ።

በምኅባእ ፡ ጽላሎቱ ፡ በጽላሎተ ፡ ረድኤቱ ፡ ሠዋሪነት ፡ ሠውሮኛልና ። እንድም ፡ (በምኅባእ ፡ ጽላሎቱ) ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብን ፡ በሚሠውርበት ፡ በጽላሎተ ፡ ረድኤቱ ፡ ሠውሮኛልና ። መዝ ፡ ፴ ፡ ፳ ።

ወዲበ ፡ ኰኵሕ ፡ አልዓለኒ ።

ከመከራው ፡ አውጥቶ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ አኖረኝ ። እንድም ፡ ከአሕዛብ ፡ በላይ ፡ አደረገኝ ፡ ኰኵሕ ፡ አላቸው ፡ እንጨት ፡ ጠርበው ፡ ደንጊያ ፡ አለዝበው ፡ ጣዖት ፡ ያመልካሉና ። እንድም ፡ ልቡናቸው ፡ በአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ እንደ ፡ ደንጊያ ፡ የጸና ፡ ነውና ፡ እንድም ፡ ብዑለ ፡ አሕዛብን ፡ ሰጥቶ ፡ አከበረኝ ፡ እንድም ፡ ባምስቱ ፡ በስድስቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ እንድሔድ ፡ አደረገኝ ፡ እንድም ፡ በሁለቱ ፡ ጽላት ፡ በተጻፉ ፡ በዓሠርቱ ፡ ቃላት ፡ አጸናኝ ።

፮ ፡ ናሁ ፡ ይእዜ ፡ አልዓለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርእስየ ፡ ዲበ ፡ ጸላእትየ ።

እነሆ ፡ ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠላቶቼን ፡ አጥፍቶ ፡ እኔን ፡ አድኖ ፡ ከጠላቶቼ ፡ በላይ ፡ አደረገኝ ።

ዖድኩ ፡ ወሦዕኩ ፡ ውስተ ፡ ደብተራሁ ፡ መሥዋዕተ ፡ ወየበብኩ ፡ሎቱ ፡

ዖድኩ ፡ ውስተ ፡ ደብተራሁ ፡ ወሦዕኩ ፡ መሥዋዕተ ፡ ወየበብኩ ፡ ሎቱ ፡ ብለህ ፡ አቅና ፡ ደብተራ ፡ ኦሪትን ፡ ከብቤ ፡ ቆምሁ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠውቼ ፡ እሱን ፡



አመሰገንሁ ። ምነው ፡ በሕዝቅያስ ፡ ጊዜማ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ተሠርታ ፡ የለምን ። ደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ወዷት ፡ አለች ፡ ቢሉ ፡ በደብተራ ፡ ኦሪት ፡ እግር ፡ ስለ ፡ ገባች ። እንድም ፡ የሙሴ ፡ ሥርዓት ፡ አይፍረስ ፡ ብለው ፡ መቃረቢያ ፡ አድርገዋት ፡ ነበርና ፡ ዛሬ ፡ የጥምቀት ፡ መቃረቢያ ፡ እንዷለ ።

እሴብሕ ፡ ወእዜምር ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ አመሰግናለሁ ። ወእዜምር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ። መዝ ፡ ፺ ፡ ፲፯ ። ፲፱ ፡ ፺ ።

፯ ፡ ስምዐኒ ፡ እግዚኦ ፡ ቃልየ ፡ ዘሰዓልኩ ፡ ገቢረ ።

አቤቱ ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ የለመንሁትን ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ። መዝ ፡ ፳፫ ፡ ፩ ።

ተሣሀለኒ ፡ ወስምዐኒ ፡ ለከ ፡ ይብለከ ፡ ልብየ ።

ልቡናዬ ፡ ይቅር ፡ ብለህ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ፡ ይልሃል ፡ ልቡ ፡ ልዩ ፡ እሱ ፡ ልዩ ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ሲል ፡ ደገመው ።

፰ ፡ ወኀሠሥኩ ፡ ገጸከ ።

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ገጸ ፡ ረድኤትህን ፡ ገጸ ፡ ምሕረትህን ፡ ሻሁ ።

ገጸ ፡ ዚአከ ፡ እኀሥሥ ፡ እግዚኦ ።

እንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ገጸ ፡ ረድኤትህን ፡ እሻለሁ ።

ወኢትሚጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔየ ።

ገጸ ፡ ምሕረትህን ፡ ገጸ ፡ ረድኤትህን ፡ ከኔ ፡ አታርቀው ። ለአጠይቆ ፡ ሠለስቱ ፡ እካላት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ ተናገረው ።

፱ ፡ ወኢትትገሐሥ ፡ እምገብርከ ፡ተምዒዓከ ።

ተቀርበህ ፡ ከኔ ፡ ከባሪያህ ፡ በረድኤት ፡ አትራቅ ።

ረዳኢ ፡ ኩነኒ ፡ ወኢትግድፈኒ ።

ረዳት ፡ ሁነኝ ፡ እንጂ ፡ በመከራው ፡ አትጣለው ። እንድም ፡ ረዳት ፡ ሁነኝ ፡ በመከራውም ፡ አትጣለኝ ።

ወኢትትሀየየኒ ፡ አምላኪየ ፡ ወመድኀኒየ ።

ድኅነቴን ፡ የምታደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ቸል ፡ አትበለኝ ።

፲ ፡ እስመ ፡ አቡየ ፡ ወእምየ ፡ ገደፉኒ ።

አባት ፡ እናቴ ፡ የጥጋባቸውን ፡ ያህል ፡ ተገናኝተው ፡ በማኅፀን ፡ ጥለውኛልና ።

ወእግዚአብሔር ፡ ተወከፈኒ ።

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ ተቀበለኝ ። እንድም ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ የረሀባቸውን ፡ ያህል ፡ ለገንዘብ ፡ ብለው ፡ ለሞት ፡ አሳልፈው ፡ ሰጡኝ ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ ተቀበለኝ ። ሕግመ ፡ ኵብሽ ፡ የሚባል ፡ ደዌ ፡ የታመመ ፡ እንድ ፡ ነበረ ። ከበላው ፡ አብልቶ ፡ ከጠጣው ፡ አጠጥቶ ፡ የሚያኖሩቸው ፡ ዓቀብተ ፡ ሥራይ ፡ ነበሩትና ፡ ማዳን ፡ ባይሆንላቸው ፡ መቼም ፡ አይገኝ ፡ ብለው ፡ ለናት ፡ ላባቱ ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ልጅ ፡ አስፈልገህ ፡ እናቱ ፡ ይዛ ፡ አባቱ ፡ አርዶ ፡ በደሙ ፡ የታጠብህ ፡ እንደሆነ ፡ ትድናለህ ፡ አሉት ። ንጉሥ ፡

ላስፈልግ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የሚቸግረው ፡ የለምና ፡ አስፈልጎ ፡ አገኘ ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ ብዙ ፡ ዕንቍ ፡ ሰጥቶ ፡ አስመ ጥቶ ፡ እናቱ ፡ ይዛ ፡ አባቱ ፡ ሊያርደው ፡ ቀረበ ፡ ወደሰማይ ፡ አየ ፡ ምነው ፡ አንተ ፡ ወደሰማይ ፡ ታያለህ ፡ አለው ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ ጥንቱን ፡ ለልማዱ ፡ ለልጅ ፡ የሚያዝኑ ፡ የሚራሩ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ ነበሩ ፡ ወክነው ፡ ሊያርዱኝ ፡ ሊቀርቡ ፡ ጊዜ ፡ በዚያውም ፡ ላይ ፡ መኾውለት ፡ የሚያድን ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። ግደሉ ፡ ሲል ፡ ጊዜ ፡ ለማን ፡ ልንገር ፡ ለማ ያደላው ፡ ለሰማያዊው ፡ ንጉሥ ፡ እን ግራለሁ ፡ እንጂ ፡ አለው ፡ ተዉት ፡ አለ ። እሱንም ፡ ወዲያው ፡ መልአኩ ፡ ከእ ግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ ፡ ፈውሶ ታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

፲፩ ፡ ምርሐኒ ፡ እግዚኦ ፡ ፍኖተከ ፡ መዝ ፡ ፹፭ ። ፲፩ ።

አቤቱ ፡ ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፡ አስተም ረኝ ።

ወምርሐኒ ፡ ፍኖተ ፡ ርትዕከ ፡ በእንተ ፡ ጸላእትየ ።

ጠላቶቼን ፡ ደስ ፡ አይበላቸው ፡ ብለህ ፡ የቀናውን ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ጐዳና ፡ መርተህ ፡ አውጣኝ ።

፲፪ ፡ ኢትመጥወኒ ፡ ለነፍስ ፡ እለ ፡ ይሣቅዩኒ ።

መከራ ፡ ለሚያጸኑብኝ ፡ ለነሰናክሬም ፡ ሰውነቴን ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጠኝ ። እን ድም ፡ (ኢትመጥዋ ፡ ለነፍስየ ፡ ለእለ ፡ ይሣቅዩኒ) ። መከራ ፡ ለሚያጸኑብኝ ፡ ለነሰናክሬም ፡ ሰውነቴን ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጣት ። እንድም ፡ ኢትመጡ ፡ ብየ ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጥብኝ ።

እስመ ፡ ቆሙ ፡ ላዕሌየ ፡ ሰማዕተ ፡ ዓመፃ ።

የሐሰት ፡ ምስክሮች ፡ በጠላትነት ፡ ተነ ሥተውብኛልና ። እኩ ፡ ሰበረ ፡ መ ባዓ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለው ።

ወሐሰት ፡ ርእሰ ፡ ዓመፃ ።

ሐሰትም ፡ የዓመፃ ፡ አበጋዝ ፡ ናት ።

፲፫ ፡ እትአመን ፡ ከመ ፡ እርእይ ፡ ሠናይቶ ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ በብሔረ ፡ ሕያዋን ።

ሕያዋን ፡ የሚሆኑ ፡ የአብርሃም ፡ የይ ስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ አገር ፡ በምትሆን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ተ ድላ ፡ ደስታውን ፡ (አይ ፡ ዘንድ) ። እን ዳይ ፡ አምናለሁና ።

አንድም ፡ (እስመ ፡ ቆሙ ፡ ላዕሌየ ፡ ሰማ ዕተ ፡ ዓመፃ) ፡ እስመ ፡ ታግሠህ ፡ የሐ ሰት ፡ ምሽክሮች ፡ አይሁድ ፡ በጠላት ነት ፡ ተነሡብኝ ፡ (ወሐሰት ፡ ርእሰ ፡ ዓመፃ) ፡ እኔን ፡ እሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ማለት ፡ ዓመፃ ፡ ነውና ፡ ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፲፪ ። ማር ፡ ፲፭ ፡ ፬-፭ ። ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፩-፳፫ ። ዮሐ ፡ ፲፰ ፡ ፲፫ ። (እትአመን ፡ ከመ ፡ እርእይ ፡ ሠናይቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በብሔረ ፡ ሕያዋን) ፡ በመላእክት ፡ በጻድቃን ፡ አገር ፡ በመ ንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ልጅነትን ፡ ተድላ ፡ ነፍስን ፡ እንዳይ ፡ አምናለሁ ። ተወከለ ፡ ተሰፈወ ፡ ተአመነ ፡ በከልአይ ፡ እንጂ ፡ በሣልሳይ ፡ አይወድቅም ።

፲፬ ፡ ወተሰፈዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ አልህ ፡ አበጀህ ፡ እመንበት ።



ተዓገሥ ፡ ወእጽንዕ ፡ ልበከ ፡ መዝ ፡ ፴ ፡ ፳ ፡ ፲፩ ።

መከራውን ፡ ታግሠህ ፡ ተቀበል ። ልቡ ናህንም ፡ በትዕግሥት ፡ አጽናው ።

ወተሰፈዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ ተስፋ ፡ አድርገው ። ሰቆ ፡ ፫ ፡ ፳፮ ።

## መዝሙር ፡ ፳፯ ።

፩ ፡ ኀቤከ ፡ እግዚኦ ፡ ጸራሕኩ ፡ አምላኪየ ፡ ኢት ጸመመኒ ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ እግ ዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ ኀቤከ ፡ ጸራሕኩ ፡ ብለህ ፡ አቅና ። አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ወዳ ንተ ፡ መልሼ ፡ ለመንሁ ፡ እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ቸል ፡ አትበለኝ ። አንድም ፡ ለምኘለሁና ፡ ልመናዬን ፡ ቸል ፡ አት በልብኝ ።

እመሰ ፡ ተጸመምከኒ ፡ እከውን ፡ ከመ ፡ እለ ፡ ይወ ርዱ ፡ ውስተ ፡ ዓዘቅት ።

እመ ፡ ተጸመምከኒሰ ፡ ቸል ፡ ብትለኝ ፡ ግን ፡ ተማርከው ፡ ፋርስ ፡ ባቢሎን ፡ እንደ ፡ ወረዱት ፡ እሆናለሁ ። አንድም ፡ ሙተው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ እንደወረ ዱት ፡ እሆናለሁ ።

፪ ፡ ስምዓኒ ፡ እግዚኦ ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ፡ ዘአ ራሕኩ ፡ ኀቤከ ።

አቤቱ ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ የለመንሁ ትን ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ ስማኝ ። መዝ ፡ ፳፯ ፡ ፯ ።

ሶበ ፡ አንሥእ ፡ እደውየ ፡ በጽርሐ ፡ መቅደስከ ።

ከቤተ ፡ መቅደስህ ፡ እደ ፡ ልቡናዬን ፡ ለአንክሮ ፡ ለተዘክሮ ፡ እደ ፡ ቃሌን ፡ ለጸሎት ፡ እደ ፡ ሥጋዬን ፡ ለመሥዋ ዕት ፡ ባቀረብሁ ፡ ጊዜ ። ሀሎት ፡ እደ ፡ ለኢዮአብ ፡ እንዲል ፡ ፪ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፲፱ ።

፫ ፡ ኢትስሐባ ፡ ምስለ ፡ ኃጥኣን ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ ከነሰናክሬም ፡ ጋራ ፡ አታ ጥፋት ። አንድም ፡ እንዳታጠፋት ፡ ወዳ ንተ ፡ መልሼ ፡ ለመንሁ ።

ወኢትገድፈኒ ፡ ምስለ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።

ዓመፅን ፡ ከሚሠሩ ፡ ከነሰናክሬም ፡ ጋራ ። አንድም ፡ እንደነ ፡ ሰናክሬም ፡ አትጣለኝ ። አንድም ፡ እንዳታጠፋኝ ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለመንሁ ። መዝ ፡ ፳፭ ፡ ፱ ።

እለ ፡ ይትናገሩ ፡ ሰላመ ፡ ምስለ ፡ ቢጾሙ ።

ከወንድሞቻቸው ፡ ጋራ ፡ አንድነትን ፡ ፍቅርን ፡ ከሚናገሩ ፡ ከነዚህ ፡ ጋራ ፡ ይህንስ ፡ አይጠላባቸውም ፡ ብሎ ፡ ያምጣው ።

ወእኩይ ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ። መዝ ፡ ፲፩ ፡ ፪ ።

እንዘ ፡ እኩይ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በልቡና ቸው ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ይዘው ፡ ሳለ ።

፬ ፡ ሀቦሙ ፡ በከመ ፡ ምግባሮሙ ። ኤር ፡ ፶፱ ፡ ፲፱ ።

እንደ ፡ ሥራቸው ፡ ስጣቸው ። ፪ጢሞ ፡ ፫-፲፱ ።

ወበከመ ፡ ዕከየ ፡ ሐሊናሆሙ ።

እስበው፡እንደሚሠሩት፡እንደ፡ክፉ፡ ሥራቸው ።

ፍድዮሙ ፡ በከመ ፡ ግብረ ፡ እደዊሆሙ ።

በቃላቸው፡ፈከረው፡ዘምረው፡እን ደሚሠሩት ፡ ፍዳቸውን ፡ አምጣባ ቸው ። ዘቀ ፡ ፫ ፡ ፳፱ ።

ፍድዮሙ ፡ ፍዳሆሙ ፡ ዓስበ ፡ ርእዮሙ ።

በልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ያይደለ ፡ በራሳ ቸው ፡ ፍዳቸውን ፡ አምጣባቸው ። ዘጸአ ፡ ፱ ፡ ፲፱ ።

፭ ፡ እስመ ፡ ኢሐለዩ ፡ ውስተ ፡ ግብረ ፡ እግዚ አብሔር ።

የእግዚአብሔርን ፡ ሥራውን ፡ አላወ ቁምና ፡ ማለት ፡ በመዓልት ፡ ሳንጸም ፡ መሸብን ፡ በሌሊት ፡ ሳንጸልይ ፡ ነጋ ብን ፡ አላሉምና ።

ወኢውስተ ፡ ግብረ ፡ እደዊሁ ።

ግብረ፡እደዊሁ፡ለማለት፡ደገመው ። እንድም፡(አስመ፡ኢሐለዩ)፡ፀሐይ፡ ጨረቃ፡ ከዋክብትን፡ አላወቁምና፡ ማለት፡እሱ፡ፈጣሪ፡እነሱ፡ፍጡራን፡ መሆናቸውን ። እንድም፡(ግብረ፡እግ ዚአብሔር)፡ ኢታምልክን፡ (ግብረ፡ እደዊሁ)፡ዘጠኙን ። እንድም፡(ግብረ፡ እግዚአብሔር)፡፲፡ቃላትን፡(ግብረ፡ እደዊሁ)፡ ወነበበ፡ ወነበበ፡ ያለውን፡ አላወቁምና ።

ንሥቶሙ ፡ ወኢትሕንጾሙ ።

በሕንፃ ፡ መስሎ ፡ ይናገራል ። በሞት ፡ አፍርሳቸው፡በሕይወት፡አትነጻቸው ።

፮ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ሰም ዓኒ ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ።

ንሥቶሙ ፡ ወኢትሕንጾሙ ፡ ብዬ ፡ የለመንሁትን ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ ሰምቶኛልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክ በር ፡ ይመስገን ። መዝ ፡ ፳፩ ፡ ፳ ።

እግዚአብሔር ፡ ረዳእየ ፡ ወመድኃኒየ ።

እግዚአብሔር፡የታመነ፡ረዳቴ፡ነው ።

፯ ፡ ወቦቱ ፡ ተወከለ ፡ ልብየ ፡ ወይረድአኒ ።

ልቡናዬ ፡ በሱ ፡ አምኗልና ፡ በመከ ራዬ ፡ ጊዜ ፡ ይረዳኛል ። ኢሳ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱ ።

ወሠረፀ ፡ ሥጋየ ።

በደዌ ፡ ደርቆ ፡ የነበረ ፡ ሥጋየ ፡ በጥ ዒና ፡ ለመለመ ፡ የደዌና ፡ የሕይወት ፡ መልክ ፡ ልዩ ፡ ነውና ።

ዘእምፈቃድየ ፡ እገኒ ።

ካሥር ፡ አንድ ፡ ሰጥቼ ፡ አመሰግነዋ ለሁ ። እመኖ ፡ ወልድየ ፡ እንዲል ። ይህስ ፡ የግድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከዘጠኙ ፡ አንድ ፡ ሰጥቼ ።

፰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይሎሙ ፡ ውእቱ ፡ ለሕ ዝቡ ።

እግዚአብሔር፡ለሕዝቡ፡ኃይላቸው፡ ረዳታቸው ፡ ነው ።

ወምዕመነ ፡ መድኃኒተ ፡ መሲሑ ፡ ውእቱ ።

ይልቁንም ፡ ቀብቶ ፡ ላነገሠው ፡ ለሕ ዝቅያስ ፡ የታመነ ፡ ድኅነቱን ፡ የሚያ ደርግለት ፡ ነው ።

፱ ፡ አድኅን ፡ ሕዝበከ ፡ ወባርክ ፡ ርስተከ ።

ሕዝበከ ፡ ዓሥሩን ፡ ነገድ ። ርስተከ ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ። እንድም ፡ ሕዝበከ ፡ ሰራዊቱን ፡ ርስተከ ፡ ንጉሡን ፡ አድ ነህ ፡ አክብር ፡ አብዛ ።

ሬዕዮሙ ፡ ወአልዕሎሙ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ጠብቃቸው ።



## መዝሙር ፡ ፳፰ ።

፩ ፡ አምጽኡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውሉደ ፡ እግ ዚአብሔር ።

ስለሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ። የካህ ናት ፡ ልጆች ፡ ካህናት ። እንድም ፡ የሥላሴ፡ልጆች፡የምትሆኑ፡ካህናት፡ ለእግዚአብሔር፡አምጡ ። አምጽኡ፡ ያለውን ፡ ያምጣው ።

አምጽኡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዕጐለ ፡ ሐራጊት ።

ለመሥዋዕት፡የሚገባውን፡ጊደሩን፡ ወረሞውን ፡ አምጡ ።

አምጽኡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብረ ፡ ወስብሐተ ።

ክብር ፡ ስብሐትን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ። አሁን ፡ ክብር ፡ ስብሐት ፡ እንደ ፡ ላም ፡ ተነድቶ ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ተጎትቶ ፡ የሚመጣ ፡ ሁኖ ፡ አይደ ለም ። ክቡር ፡ ስቡሕ ፡ እያላችሁ ፡ አመስግኑት ፡ ሲል ፡ ነው ።

አምጽኡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስብሐተ ፡ ለስሙ ።

ለስሙ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ ስሙን ፡ አመስግኑት፡እሱ፡ልዩ፡ስሙ፡ልዩ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ። ስሙን ፡ እየጠራ ችሁ ፡ አመስግኑት ፡ ሲል ፡ ነው ።

ስግዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በዓጸደ ፡ መቅደሱ ።

ለእግዚአብሔር፡ባምስቱ፡በስድስቱ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ እጅ ፡ ንሡ ። መዝ ፡ ፺፭ ፡ ፯—፰ ።

፫ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዲበ ፡ ማያት ።

ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነ ፡ ሰናክ ሬም ። ላይ ፡ ነው ፡ ማያት ፡ አላቸው ፡ ለማጥፋት ፡ መጥተዋልና ።

አምላከ ፡ ስብሐት ፡ አንጐድጐደ ።

ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ስብ ሐት ፡ አንጐድጐደ ፡ ላዕለ ፡ ማያት ፡ ብለህ ፡ ግጠም ። የክብር ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ በውኆች ፡ ላይ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ ፡ ማለት ፡ እነ ፡ ሕዝቅ ያስ ፡ ይዳኑ ፡ እነ ፡ ሰናክሬም ፡ ይጥፉ ፡ አለ ።

እግዚአብሔር ፡ ዲበ ፡ ማያት ፡ ብዙኅ ።

ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነ ፡ ሰናክ ሬም ፡ ላይ ፡ ነው ።

፬ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኀይል ።

ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይልን ፡ ከማድረግም ፡ ጋራ ፡ ነው ። ተቀፀደ ፡ ቃል ፡ በሥጋ ፡ ወተወግዐ ፡ በእሳት ፡ እንዲል ።

ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዓቢይ ፡ ስብሐት ።

ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብዙ ፡ ተአ ምራትን ፡ ከማድረግ ፡ ጋራ ፡ ነው ። እምከመ ፡ ተአመንኪ ፡ ትሬእዪ ፡ ስብ

ሖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ። ዮሐ ፡ ፲፩ ፡ ፵ ።

፭ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቀጠቅጥ ፡ ኣርዘ ።

ትእዛዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቄላውን ፡ ዛፍ ፡ ይጨፈጭፈዋል ፡ ማለት ፡ ሠራዊቱን ፡ ያጠፋል ።

ወይቀጠቅጦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኣርዘ ፡ ሊባኖስ ።

የደጋውንም ፡ ዛፍ ፡ ይጨፈጭፈዋል ፡ ማለት ፡ ንጉሡን ፡ ያጠፋል ፡ ከቄላ ፡ ዛፍ ፡ የደጋ ፡ ዛፍ ፡ በቁመትም ፡ በወርድም ፡ እንዲበልጥ ፡ ከሰራዊቱም ፡ ንጉሡ ፡ ይበልጣልና ፡ ሰራዊቱን ፡ በቄላ ፡ ዛፍ ፡ ንጉሡን ፡ በደጋ ፡ ዛፍ ፡ መስሎ ፡ ተናገረ ።

፮ ፡ ወያደቅቆ ፡ ከመ ፡ ላሕመ ፡ ሊባኖስ ።

እንደ ፡ ደጋ ፡ ላም ፡ ያከሳዋል ። ድርቅ ፡ በሆነ ፡ ዘመን ፡ ሥጋው ፡ አልቆ ፡ በጥንቱ ፡ ይቆማልና ። እንድም ፡ የደጋ ፡ ላም ፡ የሚበላው ፡ ቅጠል ፡ የሚጠጋበት ፡ ዋሻ ፡ አያገኝም ። የቄላ ፡ ላም ፡ ግን ፡ የሚበላው ፡ ቅጠል ፡ የሚጠጋበት ፡ ዋሻ ፡ አያጣም ። ለእመ ፡ ርእየ ክሙ ፡ ንጉሥ ፡ ድግዱጋኒክሙ ፡ ይኬንኒ ፡ ርእሰየ ፡ እንዲል ፡ ዳን ፡ ፩ ፡ ፲ ። እንድም ፡ ላህበ ፡ ሊባኖስ ፡ ይላል ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ እንዳለ ፡ ተክል ፡ የሚያደርገው ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ያለ ፡ ተክል ፡ በበጋ ፡ ፀሐይ ፡ አያገኝም ፡ በክረምት ፡ ወሀ ፡ ሲንጠፈጠፍበት ፡ ይከርማል ፡ አያፈራም ፡ ደርቆ ፡ ይቀራልና ።

ወፍቁርሰ ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ ዘአሐዱ ፡ ቀርኑ ።

ሕዝቅያስ ፡ ግን ፡ ቀንዱ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደርዌም ፡ ፍጥረት ፡ ነው ። አሪት ፡ ዘልደት ፡ እንዲል ። እንድም ፡ ወልድ ፡ ግን ፡ ከባሕርይ ፡ አባቱ ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ በሥራ ፡ በሥልጣን ፡ አንድ ፡ መሆኑ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

፯ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመትር ፡ ነደ ፡ እሳት ።

ያልተመለሰ ፡ ንባብ ፡ ነው ። ትእዛዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰናክሬምን ፡ ያጠፋል ።

፰ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያድለቀልቆ ፡ ለገዳም ።

ትእዛዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረሀውን ፡ ያናውጸዋል ። ሰራዊቱን ፡ ያጠፋል ።

ወያድለቀልቆ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሐቅለ ፡ ቃዴስ ። ኢሳ ፡ ፴፯ ፡ ፯ ።

ጽኑውንም ፡ በረሀ ፡ ያናውጠዋል ፡ ማለት ፡ ንጉሡን ፡ ያጠፋዋል ፡ በበረሀ ፡ እህል ፡ ተክል ፡ እንዳይገኝ ፡ በነ ሰናክሬምም ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡ አይገኝምና ፡ እንድም ፡ ሐቅለ ፡ ቁድስ ፡ ይላል ። የቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዕፃ ፡ ክፍል ፡ በምትሆን ፡ በለኪሶን ፡ የሰፈረ ፡ ሰናክሬምን ፡ ያጠፋዋል ።

፱ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጸንዖሙ ፡ ለኀየላት ።

ትእዛዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ በረድኤት ፡ ያጸናቸዋል ።

ወይከሥት ፡ አዕዋመ ።

ዛፉን ፡ ይገልጸዋል ። ቅጠሉን ፡ ሲጨፈጭፉት ፡ ግንዱ ፡ ብቻ ፡ እንዲቀር ።



ንጉሡም ፡ ሰራዊቱ ፡ አልቀው ፡ ብቻውን ፡ ቀርቷልና ።

ወበጽርሑ ፡ ኵሉ ፡ ይብል ፡ ስብሐት ።

በቤተ ፡ መቅደስ ። እንድም ፡ በበጽርሑ ፡ ይላል ፡ በየቤቱ ፡ ሁኖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ፡ እያለ ፡ ያመሰግናል ።

፲ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስተጋብኦ ፡ ለማየ ፡ አይኅ ።

እግዚአብሔር ፡ ሰናክሬምን ፡ ለጥፋት ፡ በለኪሶን ፡ ይሰበስበዋል ።

ይነብር ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይነግሥ ፡ ለዓለም ።

እግዚአብሔር ፡ ለዘላለም ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ይኖራል ፡ አጥፊ ፡ ለጥፋት ፡ የሚለው ፡ የለም ።

፲፩ ፡ ወይሁበሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይለ ፡ ለሕዝቡ ።

እግዚአብሔር ፡ ለሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ኃይልን ፡ ይሰጣቸዋል ።

እግዚአብሔር ፡ ይባርኮሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ በሰላም ።

እግዚአብሔር ፡ ወገኖቹን ፡ ባንድነት ፡ በፍቅር ፡ ያከብራቸዋል ፡ ያበዛቸዋል ። ኢሳ ፡ ፴፱ ፡ ፲፫ ።

እንድም ፡ (እግዚአብሔር ፡ ያጸንዖሙ ፡ ለኀየላት) ፡ ሁለቱን ፡ መቶ ፡ ኤጺስ ፡ ቆጵሳት ፡ ያጸናቸዋል ። ዳዊት ፡ ያጸንዖሙ ፡ ለኀየላት ፡ ያለውን ፡ ኢሳይያስ ፡ በኀበ ፡ ተጋብአ ፡ ኀየላት ፡ ያለውን ።

ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ኤጺስ ፡ ቆጵሳት ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ። ይህ ፡ የበረሀ ፡ ፍየል ፡ እባቡን ፡ ሰንጥቆ ፡ ከስከሶ ፡ እንዲበላው ፡ እነሱም ፡ ሐዲስ ፡ ከይሲ ፡ ንስጥሮስን ፡ አውግዘው ፡ ለይተዋል ። (ወይከሥት ፡ አዕዋመ) ፡ የንስጥሮስን ፡ ባሕሉን ፡ ይገልጽበታል ፡ (ወበጽርሑ ፡ ኵሉ ፡ ይብል ፡ ስብሐት) ፡ እንዳለፈው ፡ (እግዚአብሔር ፡ ያስተጋብኦ ፡ ለማየ ፡ አይኅ) ፡ ንስጥሮስን ፡ ለማጥፋት ፡ በኤፌሶን ፡ ይሰበስበዋል ፡ (ይነብር ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይነግሥ ፡ ለዓለም) ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ አጥፊ ፡ ለጥፋት ፡ የሚለው ፡ የለም ፡ ነግሦ ፡ ይኖራል ፡ (ወይሁበሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይለ ፡ ለሕዝቡ) ፡ ለሁለቱ ፡ መቶ ፡ ኤጺስ ፡ ቆጵሳት ፡ ኃይለ ፡ ቃልን ፡ ይገልጽላቸዋል ። (እግዚአብሔር ፡ ይባርኮሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ በሰላም) ፡ ያከብራቸዋል ፡ ያበዛቸዋል ።

## መዝሙር ፡ ፳፱ ።

፩ ፡ እእኵተከ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ተወከፍከኒ ።

ስለሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ። አቤቱ ፡ በረድኤት ፡ ተቀበለኸኛልና ፡ አመሰግንሃለሁ ።

ወስላተ ፡ ጸላኢ ፡ ኢረሰይከኒ ።

ያልተመለሰ ፡ ንባብ ፡ ነው ፡ ስላተ ፡ ጸላእየ ፡ ሲል ፡ ነው ። የጠላቶቼም ፡ መዘበቻ ፡ አላደረግኸኝምና ።

፪ እግዚኦ፡ አምላኪየ፡ ጸራኅኩ፡ ኀቤከ፡ ወተ ፈወስኩ።

አቤቱ፡ ፈጣሪዬ፡ ወዳንተ፡ መልሼ፡ ለመንሁ። አንተም፡ ይቅር፡ አልኸኝ።

፫ እግዚኦ፡ አውፃእካ፡ እምሲኦል፡ ለነፍስየ።

አቤቱ፡ ሰውነቴን፡ ሙቶ፡ ወደ፡ መቃብር፡ ከመውረድ፡ ነፍሴን፡ ወደ፡ ሲኦል፡ ከመውረድ፡ አዳንሃት።

ወአድኀንከኒ፡ እምእለ፡ ይወርዱ፡ ውስተ፡ ግብ። ኢሳ፡ ፴፰፡ ፲፯።

ተማርከው፡ ፋርስ፡ ባቢሎን፡ ከወረዱ፡ ከሥሩ፡ ነገድ፡ ለይተህ፡ እንድም፡ ሙተው፡ ወደ፡ መቃብር፡ ከወረዱ፡ ከነሰናክሬም፡ ለይተህ፡ አዳንኸኝ። ኢዮ፡ ፴፫፡ ፳፰። ኢሳ፡ ፲፡ ፱። ኢሳ፡ ፴፰፡ ፲-፰። ዮና፡ ፩፡ ፲፭።

፬ ዘምሩ፡ ለእግዚአብሔር፡ ጻድቃኑ።

ሁለቱ፡ ነገድ፡ እንድም፡ ነቢያት፡ ካህናት፡ ለእግዚአብሔር፡ ምስጋና፡ አቅርቡ፡ እሱን፡ አመስግኑ።

ወግነዩ፡ ለዝክረ፡ ቅድሳቱ።

ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ተብሎ፡ ለሚመሰገን፡ ለስሙ፡ መታሰቢያ፡ ተገዙ።

፭ እስመ፡ መቅሠፍት፡ እመንቱ፡ ወሕይወት፡ እምፈቃዱ።

ከመዓቱ፡ የተነሣ፡ መቅሠፍት፡ ከፈቃዱ፡ የተነሣ፡ ምሕረት፡ ይታዘዛልና።

በምሴት፡ ይደምፅ፡ ብካይ፡ ወበጽባሕ፡ ፍሥሐ።

እንድም፡ ሠረገ፡ ከመዓት፡ የተነሣ፡ መቅሠፍት፡ ይታዘዛልና፡ በምሴት፡ ይደምፅ፡ ብካይ፡ ልቅሶ፡ ይደረጋል፡ ከፈቃዱም፡ የተነሣ፡ ምሕረት፡ ይደረጋልና። በጽባሕ፡ ፍሥሐ። ተድላ፡ ደስታ፡ ይደረጋል። እንድም፡ በምሴት፡ ይደምፅ፡ ብካይ፡ ሰናክሬም፡ መጣ፡ መጣ፡ በተባለ፡ ጊዜ፡ ልቅሶ፡ ይደረጋል። ምሽት፡ እንዲከብድ፡ የሰናክሬምም፡ አመጣጥ፡ ይከብዳልና። (ወበጽባሕ፡ ፍሥሐ)፡ በሞተ፡ ጊዜ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ይደረጋል። ንጋት፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ የሰናክሬምም፡ ሞት፡ ደስ፡ ያሰኛልና። እንድም፡ (በምሴት)፡ ማታ፡ በለኪሶን፡ ሰፍሮ፡ ባዩት፡ ጊዜ። (ወበጽባሕ)፡ ጧት፡ ሙቶ፡ ባዩት፡ ጊዜ። እንድም፡ በምሴት፡ ሕዝቅያስ፡ በታመመ፡ ጊዜ፡ ምሽት፡ እንዲከብድ፡ የሕዝቅያስም፡ ደዌ፡ ከቡድ፡ ነውና። (ወበጽባሕ)፡ ድኖ፡ ባዩት፡ ጊዜ፡ ንጋት፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ የሕዝቅያስም፡ ሕይወት፡ ደስ፡ ያሰኛልና። እንድም፡ በምሴት፡ ማታ፡ ደዌ፡ ጸንቶበት፡ አይተውት፡ ዛሬስ፡ አይድንም፡ ይሞታል፡ ብለው፡ እያለቀሱ፡ ሂደዋል። ወበጽባሕ፡ በነጋው፡ ቢመለሱ፡ ድኖ፡ አግኝተውት፡ ደስ፡ ብሏቸዋልና። እንድም፡ (በምሴት)፡ በኦሪት፡ ልቅሶ፡ ይደረጋል፡ ማለት፡ ልጅነት፡ አልተገኘባትም፡ ሀብት፡ ሥርየት፡ አልተወበትምና። (ወበጽባሕ፡ ፍሥሐ)፡ በወንጌል፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ይደረጋል፡ ማለት፡ ልጅነት፡ ተገኝቶባታል፡ ሀብት፡ ሥርየት፡ ተሰጥቶባታልና። እንድም፡ በምሴት፡ በምሴተ፡ ሐሙስ፡ በሐዋርያት፡ ዘንድ፡ ልቅሶ፡ ይደረጋል። (ወበጽባሕ፡ ፍሥሐ)፡ በጽባሐ፡ እሑድ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ይደረጋል።



፮ አንሰ፡ እቤ፡ በተድላየ፡ ኢይትሀወክ፡ ለዓለም።

እኔስ፡ ባለ፡ ዘመኔ፡ ሁሉ፡ መከራ፡ አግኝቶኝ፡ በመከራው፡ አልታወክም፡ በዚህም፡ ሐዊ፡ ነቅፎታል፡ እንዴት፡ ሰው፡ ሆኖ፡ ባለዘመኑ፡ ብዙውስ፡ ይቅርና፡ አንድ፡ ቀን፡ ስንኳ፡ መከራ፡ የማያገኘው፡ አለ፡ ብሎ። እንሰ፡ እቤ፡ እምግዕዝየ፡ ኵሉ፡ ሰብእ፡ ሐሳዊ፡ ውእቱ፡ ባለው፡ ግን፡ አመስግኖታል። እንድም፡ እኔስ፡ ባለዘመኔ፡ ሁሉ፡ መከራ፡ አግኝቶኝ፡ በመከራ፡ አልታወክም፡ ብዬ፡ ነገር፡ አለ፡ የተመቸ።

፯ እግዚኦ፡ በሥምረትከ፡ ሀብ፡ ኀይለ፡ ለሕይወትየ።

አቤቱ፡ ወድደህ፡ ለሰውነቴ፡ ኀይልን፡ ሕይወትን፡ ስጣት።

ሜጥከ፡ ገጸከ፡ ወኮንኩ፡ ድንጉፀ።

እመ፡ ሚጥከሰ፡ ኮንኩ፡ ድንጉፀ። ገጽ፡ መዓትህን፡ ብትመልስብኝ፡ ግን፡ የደንገፅሁ፡ ሆንሁ።

፰ ኀቤከ፡ እግዚኦ፡ ጸራኅኩ፡ ወኀበ፡ አምላኪየ፡ እስእል።

እንዘ፡ እስእል፡ አቤቱ፡ ፈጣሪዬ፡ ስለምን፡ ወዳንተ፡ መልሼ፡ እለምናለሁ።

፱ ምንተ፡ ይበቍዕ፡ ደምየ፡ ለእመ፡ ወረድኩ፡ ውስተ፡ ሙስና።

ሙቼ፡ ወደ፡ መቃብር፡ ብወርድ፡ የኔ፡ ደም፡ ምን፡ ግዳጅ፡ ይፈጽምልሃል፡ እያልሁ።

መሬትኑ፡ የአምነከ፡ ወይነግር፡ ጽድቀከ።

መቃብር፡ የሕዝቅያስን፡ ሥጋውን፡ አበላኝ፡ ደሙን፡ አጠጣኝ፡ ብሎ፡ ያመሰግንሃልን። እመኖ፡ ወልድየ፡ እንዲል። እንድም፡ መሬትየኑ፡ ይላል፡ መሬትነቴ፡ ያመሰግንሃልን። እንድም፡ (ምንት፡ ያሠልጥ)፡ ተማርኬ፡ ፋርስ፡ ባቢሎን፡ ብወርድ፡ የኔ፡ መማረክ፡ ምን፡ ግዳጅ፡ ይፈጽምልሃል። (መሬትኑ)፡ ሰናክሬም፡ ሕዝቅያስን፡ በእጄ፡ ጣለልኝ፡ ብሎ፡ ያመሰግንሃልን። መዝ፡ ፮፡ ፭። ኢሳ፡ ፴፰፡ ፲፰።

፲ ሰምዐ፡ እግዚአብሔር፡ ወተሣሃለኒ።

እግዚአብሔር፡ ልመናዬን፡ ሰምቶ፡ ይቅር፡ አለኝ።

ወኮነኒ፡ እግዚአብሔር፡ ረዳእየ።

እግዚአብሔር፡ ረዳት፡ ሆነኝ።

፲፩ ሜጥከ፡ ላሕየ፡ ወአስተፍሥሐከኒ።

ልቅሶዬን፡ አርቀህ፡ ደስ፡ አሰኘኸኝ። እንድም፡ ላህይየ፡ ይላል፡ መልኬን፡ ለውጠህ፡ ደስ፡ ያሰኘኸኝ፡ የሕይወት፡ መልክና፡ የደዌ፡ መልክ፡ ልዩ፡ ነውና።

ሠጠጥከ፡ ሠቅየ፡ ወሐገተ፡ አቅናትከኒ።

ሠቅ፡ መከራዬን፡ አርቀህ፡ ተድላ፡ ደስታን፡ እንደ፡ ዝናር፡ አስታጠቅኸኝ። እንድም፡ ደዌዬን፡ አርቀህ፡ በተድላ፡ በደስታ፡ አኖርኸኝ፡ ወትፍሥሕተ፡ ልብ፡ ያነጡሁ፡ መዋዕለ፡ እንዲል። ኢር፡ ፴፩፡ ፲፫። ሮሜ፡ ፲፭፡ ፰።

፺፫



፲፪ ፡ ከመ ፡ እዘምር ፡ ለከ ፡ ክብርየ ፡ ወኢይደን ግፅ ።

ክብሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ አመሰግንህ ፡ ዘንድ ፡ እንዳልደነግጥ ፡ ሠጠኸኝ ፡ እ ግዚእ ፡ አምላኪዬ ፡ ማንኛ ፡ እንድም ፡ አመሰግንህ ፡ ዘንድ ፡ በመከራ ፡ እንዳ ልያዝ ።

እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ ለዓለም ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ለዘላለሙ ፡ እገዛል ሃለሁ ።

## መዝሙር ፡ ፴ ።

፩ ፡ ኪያከ ፡ ተወከልኩ ፡ እግዚኦ ፡ ወኢይትኀፈር ፡ ለዓለም ። መዝ ፡ ፳፬ ፡ ፪ ። ፳ ፡ ፩ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ። አቤቱ ፡ በንተ ፡ አመንሁ ። እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ በመከራው ፡ አላፍርም ፡ አልፈር ፡ እ ንድም ፡ በመከራው ፡ እንዳላፍር ፡ በ ንተ ፡ አመንሁ ። እንድም ፡ በንተ ፡ እም ኛለሁና ፡ በመከራው ፡ አላፍርም ።

ወበጽድቅከ ፡ አንግፈኒ ፡ ወባልሐኒ ።

በይቅርታህ ፡ በቸርነትህ ፡ ፈጽመህ ፡ አድነኝ ።

፪ ፡ አጽምዕ ፡ እዝነከ ፡ ኀቤየ ፡ ወፍጡነ ፡ አድኅነኒ ።

እዝን ፡ ምሕረትህን ፡ እዝን ፡ ፈቃድ ህን ፡ ወደኔ ፡ መልሰህ ፡ ፈጥነህ ፡ አድ ነኝ ።

ኩነኒ ፡ አምላኪየ ፡ ወመድኃኒየ ።

ወቤተ ፡ ፀወንየ ፡ ከመ ፡ ታድኅነኒ ።

ኩነኒ ፡ ቤተ ፡ ፀወንየ ፡ አምላኪየ ፡ ወ መድኀንየ ፡ ከመ ፡ ታድኅነኒ ፡ ብለህ ፡ አቅና ፡ ድኅነቴን ፡ የምታደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ከመከራው ፡ ታድነኝ ፡ ዘን ንድ ፡ ያምባ ፡ የመጠጊያ ፡ ቤት ፡ ሁነኝ ፡ አንድም ፡ ወፀወን ፡ ቤትየ ፡ ይላል ፡ የአ ብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ አምባ ፡ መጠጊያ ፡ የምትሆን ፡ አቤቱ ፡ ኩነኒ ፡ ዘታድኅነኒ ፡ የምታድነኝ ፡ ሁን ።

፫ ፡ እስመ ፡ ኃይልየ ፡ ወፀወንየ ፡ አንተ ።

አንተ ፡ ብዋጋ ፡ ኀይሌ ፡ ብሸሽ ፡ አምባ ፡ መጠጊያዬ ፡ ነህና ።

ወበእንተ ፡ ስምከ ፡ ምርሐኒ ፡ ወሴሰየኒ ።

በስምህ ፡ ስላመንሁ ፡ ስምህን ፡ አማ ላጅ ፡ ስላደረግሁ ። ስምየኒ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ስላልህ ፡ የኢየሩሳ ሌምን ፡ መንገድ ፡ መርተህ ፡ አውጣኝ ። ከዚያም ፡ አግብተህ ፡ መናውን ፡ መግ በኝ ፡ አንድም ፡ እንደአባቶቼ ፡ ምር ሃኒ ፡ ፍና ፡ ወሴሰየኒ ፡ መና ።

፬ ፡ ወአውፅአኒ ፡ እምዛቲ ፡ መሥገርት ፡ እንተ ፡ ኀብኡ ፡ ሊተ ።

ሠውረው ፡ ከመከሩብኝ ፡ ከዚች ፡ ም ክር ፡ ከሸመቁብኝ ፡ ጦር ፡ አድነኝ ።

እስመ ፡ አንተ ፡ ረዳእየ ፡ እግዚኦ ። ኢሳ ፡ ፳፭ ፡ ፱ ።

አቤቱ ፡ ረዳቴ ፡ አንተ ፡ ነህና ።

ውስተ ፡ እደዊከ ፡ አመሐፅን ፡ ነፍስየ ።

ሰማይ ፡ ሩቅ ፡ አደራ ፡ ጥብቅ ፡ እንዲሉ ፡ ሰውነቴን ፡ ባንተ ፡ አስጠብቃለሁ ።

ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፵፮ ። ግብ ፡ ፯ ፡ ፶፱ ። ፩ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፲፱ ።



ቤዝወኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ጽድቅ ።

የክብር ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ አድ ነኝ ። አንድም ፡ ቤዘወኒ ፡ አዳነኝ ።

፮ ፡ ጸላእከ ፡ እግዚኦ ፡ ኵሎ ፡ ዘየዓቅብ ፡ ከንቶ ፡ ለዝሉፉ ።

ጸላእከ ፡ ለዝሉፉ ፡ ዘየዓቅብ ፡ ከንቶ ፡ ለዝሉፉ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ አቤቱ ፡ ከን ቱ ፡ ጣዖትን ፡ የሚያመልከውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመህ ፡ ጠላህ ።

ወአንሰ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተወከልኩ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መጠላቱ ፡ እንዳያገ ኝኝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመንሁ ።

፯ ፡ እትፌሣሕ ፡ ወእትኃሠይ ፡ በአድኅኖትከ ።

በትድግናህ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

መዝ ፡ ፱ ። ኢሳ ፡ ፷፩ ፡ ፲ ።

እስመ ፡ ርኢከኒ ፡ በሕማምየ ።

በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ በዓይነ ፡ ምሕረት ፡ አይተኸኛልና ።

ወአድኃንከ ፡ እምንዳቤሃ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴንም ፡ ካገኛት ፡ መከራ ፡ አድን ሃታልና ።

፰ ፡ ወኢዘጋሕከኒ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ፀርየ ።

በጠላቶቼ ፡ እጅ ፡ ተይገር ፡ እንድቀር ፡ አላደረግኸኝምና ። ኢዮ ፡ ፲፮ ፡ ፲፩ ።

ወአቀምኮን ፡ ውስተ ፡ መርሀብ ፡ ለእገርየ ።

ወገኖቼን ፡ እንድም ፡ ሕዋሳቴን ፡ ከመ ከራው ፡ አውጥተህ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ አኖርሃቸው ።

፱ ፡ ተሣሀለኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ሐመምኩ ።



አቤቱ ፡ በለመከራ ፡ ሁኛለሁና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

ወተሐውከት ፡ እመዓት ፡ ዓይንየ ።

ሰብእ ፡ ትካት ፡ ሰብአ ፡ ሰዶም ፡ ሰብአ ፡ ገሞራን ፡ በጠፋበት ፡ መዓቱ ፡ ያጠፋ ኝን ፡ ይሆን ፡ በማለት ፡ ዓይኔ ፡ ባከነች ፡ እንደ ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ሊመቷ ቸው ፡ ጨንገር ፡ ባነሡባቸው ፡ ጊዜ ፡ ከሁን ፡ አሁን ፡ አሳረፉብን ፡ እያሉ ፡ ዓይናቸው ፡ እንዲባክን ። መዝ ፡ ፮ ፡ ፯ ። አንድም ፡ ጣዖት ፡ ከማምለኬ ፡ የተነሣ ፡ ሰውነቴ ፡ በለመከራ ፡ ሆነች ፡ መዓተ ፡ አረሚ ፡ እንዲል ።

ነፍስየኒ ፡ ወከርሥየኒ ።

ነፍሴም ፡ ሥጋዬም ፡ ባለመከራ ፡ ሆኑ ።

፲ ፡ እስመ ፡ ሐልቀ ፡ በሕማም ፡ ሕይወትየ ።

ሰውነቴ ፡ በመከራው ፡ ተፈጸሟልና ።

ወዓመትየኒ ፡ በገዓር ።

ዘመኔም ፡ በመከራው ፡ ተፈጽሟልና ።

ወደከመ ፡ በተፅናስ ፡ ኃይልየ ።

ኃይሌ ፡ በቀጠና ፡ ደከመ ። ወገኔ ፡ ሰው ነቴ ፡ በመከራው ፡ ተፈጸመ ።

ወአንቀልቀለ ፡ ኵሉ ፡ አዕፅምትየ ።

ሰውነቴ ፡ እንድም ፡ ወገኔ ፡ በመከራው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ብሏልና ። ኢዮ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ።

፲፩ ፡ ወተፅዕልኩ ፡ በኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ ጸላእትየ ።

በጠላቶቼ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ገብሮ ፡ ገዶ ፡ ዓመፆ ፡ ወለቶ ፡ ተብዬ ፡ ተሰደብሁ ።

ወረፈ፡ረደ፡ ወነበ፡ ነርየ ።

ይልቁንም ፡ በእምነና ፡ በምንብ ፡ በጎ ረቤቶቼ ፡ ዘንድ ፡ ከላወቀ ፡ ያወቀ ፡ ሲሰ ድብ ፡ ይቆጣልና ።

ግሩመ ፡ ኮንኩ ፡ ለአዝማድየ ።

ለዘመዶቼ ፡ ላሥሩ ፡ ነገድ ፡ ግሩም ፡ ሆንሁባቸው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ኃይል ፡ አግኝተው ፡ ተ ዋግተው ፡ ያወጡናል ፡ እያሉ ፡ ተስፋ ፡ አድርገው ፡ ነበር ። ተማርከው ፡ በወ ረዱ ፡ ጊዜ ፡ በባቢሎን ፡ ያሉ ፡ ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ ኃይል ፡ አግኝታችሁ ፡ ተዋግ ታችሁ ፡ ታወጡናላችሁ ፡ ስንል ፡ እና ንተም ፡ ተማርካችሁ ፡ መጣችሁን ፡ ግሩም ፡ ብለዋልና ። ኢሳ ፡ ፳፮ ፡ ፭ ።

ወእለ ፡ ይሬእዩኒ ፡ አፍኣ ፡ ይጕዩ ፡ እምኔየ ።

እለ ፡ ይሬእዩኒ ፡ አፍኣ ፡ ነው ። በውጭ ፡ የሚያዩኝ ፡ ሁሉ ፡ ከኔ ፡ ይሸሻሉ ። ከደ ባባይ ፡ ከልቅሶ ፡ የተያዩ ፡ እንደሆን ፡ እገሌ ፡ ወንድሜ ፡ ከዚያ ፡ እለ ፡ ተገና ኝቼ ፡ ልምጣ ፡ ብሎ ፡ ይሔዳል ። አት ምጣብኝ ፡ ከእገሌ ፡ ጋራ ፡ ውሎ ፡ ነበር ፡ ሊያስኝኝ ፡ እያለ ፡ ይሸሸዋልና ። እን ድም ፡ ይጐዩ ፡ አፍኣ ፡ ነው ። የሚያ ዩኝ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይሸሻሉ ፡ ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ገዝተ ው ፡ ይኖራሉ ። እስኪ ፡ ከእገሌ ፡ ዘንድ ሒጄ ፡ ተጨዋውቼ ፡ ወሬት ፡ አሳልፌ ፡ ልምጣ ፡ ብሎ ፡ የሔደ ፡ እንደሆነ ፡ ገና ፡ ሲመጣ ፡ እይቶ ፡ ይሀ ፡ ለክፉ ፡ መጣ ፡

ቤቱን ፡ ጥዬለት ፡ ልሒድ ፡ ብሎ ፡ በሥ ርቆሽ ፡ በር ፡ ወጥቶ ፡ ይሔዳልና ። ኢሮ ፡ ፲፱ ፡ ፲፰-፲፱ ።

፲፱ ፡ ተረሳዕኩ ፡ እምልብ ፡ ከመ ፡ ዘሞተ ።

ትሩፍ ፡ ምነው ፡ እንዲህ ፡ የሚሉህ ፡ ዘመዶችህ ፡ አይደሉምን ፡ ትለኝ ፡ እን ደሆን ፡ ዘመዶቼስ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ሰው ፡ ተስፋ ፡ ቈረጡብኝ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ይ መጣል ፡ እንዳይባል ።

ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ ንዋይ ፡ ዘተኀጕለ ።

እንደ ፡ ጠፋ ፡ በግ ፡ ሆንኩ ። በግ ፡ ከበ ረረ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከተመረረ ፡ አይመ ለስም ፡ እንዲሉ ። ተመልሶ ፡ አይመጣ ም ፡ የሚሉኝ ፡ ሆንሁ ። አንድም ፡ እን ደ ፡ ተሰበረ ፡ ብርሌ ፡ ሆንኩ ። ያን ፡ እን ደገና ፡ ሰፍተን ፡ ጠግነን ፡ ሥራ ፡ እንሠራ በታለን ፡ አይሉም ፡ የሰው ፡ እግር ፡ እንዳ ይወጋ ፡ ከውጭ ፡ አውጥታችሁ ፡ ወዲያ ፡ ጣሉት ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ። አንድም ፡ ያስቆብ ፡ ሰኪኖን ፡ በሚባል ፡ እንጨት ፡ ስር ፡ ቀብሮት ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ወርቅ ፡ ሆንሁ ። ወእኅጕሎ ፡ እስከ ፡ ዮም ፡ እን ዲል ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተገኘ ፡ አልተባለ ምና ።

፲፫ ፡ እስመ ፡ ሰማዕኩ ፡ ድምፀ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ዐገቱኒ ፡ ዓውድየ ።

በዙርያዬ ፡ የከበቡኝን ፡ ብዙ ፡ የሚ ሆኑ ፡ የባቢሎናውያንን ፡ ድምፅ ፡ ሰም ቻለሁና ።

ሶበ ፡ ተጋብኡ ፡ ኅቡረ ፡ ላዕሌየ ።

በኔ ፡ አንድነት ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ።



ወተማከሩ ፡ ይምሥጥዋ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ በሞት ፡ ሊነጥቋት ፡ በመ ከሩ ፡ ጊዜ ።

፲፬ ፡ ወአንሰ ፡ ብከ ፡ ተወከልኩከ ፡ እግዚኦ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ተሰብስቦ ፡ ቢመክር ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ባንተ ፡ አመንሁ ።

ወእቤለከ ፡ አምላኪየ ፡ አንተ ።

ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ብዬ ፡ አንድም ፡ ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እልሃለሁ ።

፲፭ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ ርስትየ ።

ርስቴ ፡ ይሁዳ ፡ ሰማርያ ፡ መንግሥቴ ፡ በጅህ ፡ ተይዞልኛልና ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ትሰጠኛለህ ።

አድኅነኒ ፡ እምእደ ፡ ፀርየ ።

ከንጉሡ ፡ እጅ ፡ አድነኝ ።

ወእምእለ ፡ ሮዱኒ ።

ከከበቡኝ ፡ ሰራዊቱም ፡ አድነኝ ።

፲፮ ፡ አብርህ ፡ ገጸከ ፡ ላዕለ ፡ ገብርከ ።

ብርሃን ፡ ረድኤትህን ፡ አብራልኝ ። መዝ ፡ ፳፲፰ ፡ ፳፱፭ ። አንድም ፡ ከመከራዬ ፡ አድነህ ፡ ደስ ፡ አሰኘኝ ። አብርሂ ፡ አብ ርሂ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዲል ። ኢሳ ፡

ወአድኅነኒ ፡ በእንተ ፡ ምሕረትከ ።

ስለቸርነትህም ፡ አድነኝ ።

፲፯ ፡ ወኢይትኀፈር ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ጸዋዕኩከ ።

እምኟሃለሁና ፡ በመከራው ፡ አላፍር ም ፡ አልፈር ።

ለይትኀፈሩ ፡ ኃጥኣን ፡ ወይረዱ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ።

እኔ ፡ ግን ፡ ይፈሩ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ ከዳተኞች ፡ ባቢሎናውያን ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ፡ ሙተው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ አንድም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ይውረዱ ።

፲፰ ፡ አፈ ፡ ሐሰት ፡ ለከናፍረ ፡ ጕሕሉት ። እለ ፡ ይነባ ፡ ኃመፀ ፡ ላዕለ ፡ ጻድቅ ። በትዕቢት ፡ ወበመንኖ ፡ ኢሳ ፡ ፱-፲፯ ።

በመናቅ ፡ በማቃለል ፡ ከሰብአ ፡ ዘመን ፡ አትርፈን ፡ እንዝዋለን ፡ አይወጣም ፡ እያሉ ፡ በትሩፍ ፡ ላይ ፡ ዓመፅን ፡ ለሚ ናገሩ ፡ ለከዳተኞች ፡ ለባቢሎናውያን ፡ እንደበቶች ፡ ወዮላቸው ፡ ወዮታ ፡ አለ ባቸው ፡ ወዮ ፡ ሊሉላቸው ፡ ይገባል ። አንድም ፡ በመናቅ ፡ በማቃለል ፡ እሩቅ ፡ ብእሲ ፡ እያሉ ፡ በባሕርይ ፡ አምላክ ፡ በክርስቶስ ፡ ላይ ፡ ዓመፅን ፡ ለሚናገሩ ፡ ለከዳተኞች ፡ ለአይሁድ ፡ እንደበቶች ፡ ወዮላቸው ፡ ወዮታ ፡ አለባቸው ፡ ወዮ ፡ ሊሉላቸው ፡ ይገባል ፤ በከናፍር ፡ ሰም ቼን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፲፱ ፡ ወበዙኅ ፡ ብዝኃ ፡ ምሕረትከ ፡ እግዚኦ ። ዘዐቀብኮሙ ፡ ለእለ ፡ ይፈርሁከ ።

እቤቱ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ መ ጠን ፡ የሚፈሩህ ፡ የሚያመልኩህ ፡ ባሮክ ፡ አቤሜሌክን ፡ ከመከራው ፡ ሠወርሃቸው ።

ወአድኅንኮሙ ፡ ለእለ ፡ ይትዌከሉ ፡ ብከ ።

ባንተ ፡ ያመኑ ፡ እነ ፡ ዕንባቆምንም ፡ ከመከራው ፡ አዳንሃቸው ።

ወቅድመ፡ ደቂቀ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ፱፡ ወትገብሮሙ፡ በጽላሎትከ፡ እምሐዘን፡ ዕዝራ፡ ኢሳ፡ ፵፱፡ ፪።

(ወበቅድመ፡ ደቂቀ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ተኃብሮሙ)፡ ይንደዳቸው፡ ይቀጣቸው፡ ብለህ፡በባቢሎናውያን፡ፊት፡ እነ፡ ዳንኤልን፡ ከሰው፡ ፀብ፡ ክርክር፡በጽላሎት፡ረድኤትህ፡ትሠውራቸዋለህ፡ንጉሡ፡ዳርዮስ፡ነው። ዳንኤልን፡ምነው፡ አንተ፡ለኔ፡ አምላክ፡ ያለመስገድህ፡ አለው፡ እኔስ፡ ለማይበላ፡ለማይጠጣ፡ለማያይ፡ለማይሰማ፡ እጅ፡ እግር፡ ለሌለው፡ አልሰግድም፡ አለው። ምነው፡ እየበላ፡ እየጠጣ፡ አለው። ካህናቱ፡ ጣዖቱ፡ ይበላል፡ ይጠጣል፡ እያሉ፡ ነጩ፡ ዝግኑ፡ ጠጁ፡ ሲሔድላቸው፡ ሚስቶቻቸውን፡ ልጆቻቸውን፡ እየያዙ፡ ይመገቡታል። አለመብላቱንስ፡ ና፡ አሳይሃለሁ፡ ብሎ፡ ነጩን፡ ዝግኑን፡ ጠጁን፡ ወስደው፡ በንጉሡ፡ መቈለፊያ፡ ቈልፈው፡ ሔዱ። ዳንኤል፡ እንደሚያስረግጥ፡ ደብተራ፡ የኋሊት፡ አመድ፡እየነሰነሰ፡ወጥቷል፡ቢመጡ፡ ተዘግቶ፡ አገኙት፡ በሥርቆሽ፡ በር፡ ገብተው፡ በልተው፡ ጠጥተው፡ ሔደዋል። ሲነጋ፡ ቢሔዱ፡ ይህ፡ ሁሉ፡ የለም፡ ንጉሡ፡ አስተኃፈርከኝ፡ ለዳንኤል፡ ቤል፡ ዐቢይ፡ አምላክ። ገናናው፡ አምላክ፡ ቤል፡ ሆይ፡ ዳንኤልን፡ አሳፈርከውን፡ አለ። ዳንኤልም፡ ዝ፡ዓሠር፡ዘመኑ፡ዝ፡ዓሠር፡ዘመኑ፡ ይህ፡ይህ፡ፍለጋ፡የማን፡ነው፡እያለ፡ በዝንግ፡ አሳይቶታል፡ የሴቶች፡ ቈልመም፡ ቈልመም፡ ብሎ፡ የወንዶቹ፡ ቀንቶ፡ የሕፃናቱ፡ እንደመጠናቸው፡ ሁኖ፡ ተገኝቷል። ለክ፡ እንዚህ፡ ቀጣፊዎች፡ በሐሰት፡ ይበላል፡ ይጠጣል፡ እያሉ፡ሲያታልሉኝ፡ኑረዋልን፡ብሎ፡ በሰይፍ፡ አስፈጅቷቸዋል።

እኒህ፡ ባቢሎናውያን፡ ጣዖት፡ የሚያመልኩ፡ ደንጊያ፡ አለገዘበው፡ እንጨት፡ ጠርበው፡ ብቻ፡ አይዶለም፡ ባንድ፡ ወገን፡ ዘንዶ፡ ያመልኩ፡ ነበርና፡ ያስ፡ አይበላም፡ አይጠጣም፡ አልህ፡ ለዚህ፡ ለሚበላው፡ ለሚጠጣው፡ አትሰግድምን፡ አለው። ይህንም፡ አሰናብተኝ፡ ጋሻ፡ ጦር፡ ሳልይዝ፡ በዶ፡ እጄን፡ ሔጄ፡ ልግደለው፡ አለው። ከተቻለህ፡ ግደለው፡ አለው፡ ከዚያ፡አስቀድሞ፡ላም፡ሠውተው፡ ደሙን፡ በብርት፡ ተቀብለው፡ ስብ፡ሲያጠሉለት፡እያስከከ፡መጥቶ፡ ስቡን፡ በልቶ፡ ደሙን፡ ጠጥቶ፡ ይሔዳል። በዚያ፡ ልማድ፡ ስቡን፡ ጠጉሩን፡ጨርቁን፡ገሉን፡ባንድነት፡ቀጥቅጦ፡ አለሎውን፡ አግሎ፡ ስቡን፡ አጤሰለት። እያስከከ፡ መጥቶ፡ አፉን፡ ሲከፍት፡ በዚያ፡ ጠቅሎ፡ ከፉ፡ ላይ፡ ጣለለት። ልቡን፡ሠንጥቆ፡ገድሎታል። ባቢሎናውያንም፡ እንዲህ፡ የሚያደርገን፡ዳንኤል፡ አይደለምን፡ ብለው፡ እስከ፡ ሦስት፡ ቀን፡ ድረስ፡ ስምዓኒ፡ ዳርዮስ፡ እያላችሁ፡ ጻልዩ፡ ብለህ፡



አዋጅ፡ነግረህ፡ወዳጅህንና፡ጠላትህን፡ ዕወቀው፡እንበለው፡ብለው፡ሒደው፡ ነገሩት፡ አዋጅ፡ ነገረላቸው፡ በዳንኤል፡ሰላይ፡አስቀምጠውበታል። በ፫ኛው፡ ቀን፡ ወጸለየ፡ ዳንኤል፡ ኀበ፡ አምላኩ፡ ጊዜ፡ ፫፡ ሰዓት፡ ወአርኅወ፡ መሳክወ፡ቤቱ፡ይላል። በኢየሩሳሌም፡ አንፃር፡ ያለውን፡ መስኮት፡ ከፍቶ፡ ወደፈጣሪው፡ ሲጸልይ፡ አዋጅ፡ አፍርሶ፡ ወደፈጣሪው፡ ሲጸልይ፡ አገኘነው፡ ብለው፡ ለንጉሡ፡ ነገሩት፡ የተፈረደበትን፡ ሰው፡ የሚመገቡ፡ አናብስት፡ አሉ፡ ወስደው፡ ጣሉት። በነጋው፡ቢሔዱ፡ሳይበሉት፡አግኝተውታል። በይርባቸው፡ እንጂ፡ ነው፡ ብለው፡ምግባቸውን፡ነስተዋቸዋል፡ ንጉሡ፡ ዳንኤልን፡ ይወደው፡ ነበርና፡ዳንኤልን፡ፈጣሪው፡ አድኖት፡ ይሆን፡ ወይስ፡ በልተውት፡ ይሆን፡ ብሎ፡ በሦስተኛው፡ ቀን፡ ቢሔድ፡ እሱ፡ ከመካከላቸው፡ ቁሞ፡ ብሩህ፡ መልአክ፡ መስሎ፡ ሲጸልይ፡ አናብስቱ፡ ወኮኑ፡ ከመ፡ ድመታት፡ ይላቸዋል። እንደ፡ ውሻ፡ እንደ፡ ድመት፡ ከእግሩ፡ በታች፡ ቆልመም፡ ቆልመም፡ ብለው፡ ተኝተው፡ አገኛቸው። ዐቢይ፡ አምላኩ፡ ለዳንኤል፡ የዳንኤል፡ አምላክ፡ታላቅ፡ነው፡ና፡ ውጣ፡ ብሎታል። ንጉሥ፡ በሥራዩ፡ እንጂ፡ነው፡ብለውታል። በሥራይማ፡ ከሆነ፡ከላንት፡ የበለጠን፡አለ። እስኪ፡ በሥራያችሁ፡ዳኑ፡ብሎ፡ቢጥላቸው፡ ተርበዋልና፡ ከጐዳና፡ እየተቀበሉ፡ ሰብረው፡ሰብረው፡ፈጅተዋቸዋልና፡ እንዲህ፡ አለ። ዳን፡ ፮፡ ፳፡ ፳፪።

ወትከድኖሙ፡ በመንጦላዕትከ፡ እምጓሕሉ፡ ልሳን።

ወበቅድመ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ትከድኖሙ፡ ነው፡ ይንደዳቸው፡ ይቀጣቸው፡ ብለህ፡ በባቢሎናውያን፡ ፊት፡ ሠለስቱ፡ደቂቅን፡ ከሰው፡ነገር፡ሥራ፡ በመንጦላዕተ፡ ረድኤትህ፡ ትሠውራቸዋለህ፡ንጉሡ፡ናቡከደነፆር፡ነው። ዳንኤል፡ ርእሱ፡ ዘወርቅን፡ ከተረጐመ፡በኋላ፡ቀኛዝማች፡ግራዝማች፡ እያለ፡ ሹሟቸዋል። ዳንኤል፡ ርእሱ፡ ዘወርቅን፡የተረጐመላቸው፡ባቢሎናውያን፡ ናቡከደነፆርን፡ በሕልምህ፡ እንዳየኸው፡ ቁመቱ፡ ስድሳ፡ክንድ፡ ደረቱ፡ ስድስት፡ ክንድ፡ ጣዖት፡ በአዱራን፡ሜዳ፡ አቁመህ፡ ወዳጅህንና፡ ጠላትህን፡ አትለየውምን፡ አሉት፡ ያን፡ አቁሞ፡ ዘኢሰገደ፡ ለምስል፡ ዘወርቅ፡ ዘገበርኩ፡ በእዴየ፡ ይትበርበር፡ ቤቱ፡ ወይትሐየድ፡ ንዋዩ፡ ወይትኰነን፡ ነፍሱ። በእጄ፡ ሠርቼ፡ በቃሌ፡ አገዝገር፡ ላቆምሁት፡ የወርቅ፡ ምስል፡ ያልሰገደ፡ ከብቱ፡ ለማዕድ፡ ቤት፡ እጁ፡ ለሰንሰለት፡ አንገቱ፡ ለስለት፡ ይሁን፡ ብሎ፡ አዋጅ፡ ነገረ፡ የወንድ፡ መኰንን፡ የሴት፡ ወይዘሮ፡ ይሰግድ፡ ይረበረብ፡ ጀመረ። ሠለስቱ፡ ደቂቅም፡ አንሰግድም፡ አሉ፡ ሂደው፡ አሉ፡ እደው፡ ዘሤምከሙ፡ ለግብረ፡ በሐው

2014 04 17

ርተ ፡ ባቢሎን ፡ እበየ ፡ ሰጊደ ፡ ለም
ስል ፡ ዘወርቅ ፡ ዘገበርከ ፡ ቀኖዝማች ፡
ግራዝማች ፡ አድርገህ ፡ የሾምሃቸው ፡
ሰዎች ፡ አምነው ፡ እንደማሳመን ፡ ሰ
ግደው ፡ እንደማሰገድ ፡ እናምንም ፡
አንሰግድም ፡ አሉ ፡ አሉት ፡ ወአዘዘ ፡
ያምጽእዎሙ ፡ ዕደው ፡ ኃያላን ፡ ያመ
ጢቸው ፡ ዘንድ ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ አ
ዘዘ ፡ አመጢቸው ፡ አማንኑ ፡ አንትሙ ፡
ሲድራቅ ፡ ወሚሳቅ ፡ ወአብደናጎ ፡ ዓበ
ይክሙ ፡ ሰጊደ ፡ ለምስል ፡ ዘወርቅ ፡
ዘገበርኩ ፡ በእዴየ ፡ ሲድራቅ ፡ ሚ
ሳቅ ፡ አብደናጎ ፡ በውኑ ፡ በእጄ ፡ ሠ
ርቼ ፡ በቃሌ ፡ አዝዤ ፡ ላቆምሁት ፡
ጣዖት ፡ መስገድን ፡ እይሆንም ፡ አላ
ችሁ ፡ መኑ ፡ ያድኅነክሙ ፡ እምእዴየ ፡
ወእምዕቶኑ ፡ እሳት ፡ ከነደደ ፡ እሳት ፡ ባገ
ባችሁ ፡ ከእጄ ፡ የሚያድናችሁ ፡ ማን ፡
ነው ፡ አላቸው ፡ እወ ፡ አ ፡ ንጉሥ ፡ ኢን
ከል ፡ ንሥጠውከ ፡ በዝንቱ ፡ ግብር ፡ ወኢ
ንሰግድ ፡ ለምስል ፡ ዘወርቅ ፡ ዘገበርከ ፡
በእዴከ ፡ ሀሉ ፡ አምላክነ ፡ ዘፈጠረ ፡
ኪያከ ፡ ወኪያነ ፡ ውእቱ ፡ ያድኅነነ ፡
እምእዴከ ፡ ወእምዕቶነ ፡ እሳት ፡ ን
ጉሥ ፡ ሆይ ፡ አዎን ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡
ልንታዘዝልህ ፡ አንችልም ፡ በእጅህ ፡
ሠርተህ ፡ በቃልህ ፡ አገዘህ ፡ ላቆምከ
ው ፡ ጣዖት ፡ አንሰግድም ፡ ከነደደ ፡
እሳትም ፡ ብታገባን ፡ የሚያድነን ፡ አን
ተንም ፡ እኛንም ፡ የፈጠረ ፡ የምናመ
ልከው ፡ አምላክ ፡ አለ ፡ አሉት ፡ እሳት ፡
አስነድዶ ፡ ጣላቸው ፡ ወተለዓለ ፡ ነበ

ልባለ ፡ እሳት ፡ መጠነ ፡ ፵ ፡ ወ፱ ፡ በእ
መት ፡ እሳቱ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አርባ ፡ ዘጠኝ ፡
ክንድ ፡ ተመዝዞ ፡ ወጥቷል ፡ በምን ፡
ይታወቃል ፡ ቢሉ ፡ ባጠገቡ ፡ አርባ ፡
ዘጠኝ ፡ ክንድ ፡ ጥድ ፡ ነበር ፡ ያን ፡ ጫ
ፉን ፡ በልቶታል ፡ እንድም ፡ ዳንኤል ፡
በእመት ፡ ጸጋ ፡ ሰፍሮታል ፡ ወወረደ ፡
መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዘበጦ ፡
ለነበልባለ ፡ እሳት ፡ ወረሰዮ ፡ ከመ ፡
ነፋስ ፡ ቈሪር ፡ ዘጊዜ ፡ ጽባሕ ፡ መል
አኩ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ወርዶ ፡ በበ
ትረ ፡ ብርሃን ፡ ቢመታው ፡ እንዳረረ ፡
ውርጭ ፡ ሆኗል ፡ ወውስተ ፡ እሳቱሰ ፡
ይወድዩ ፡ ፒሳ ፡ ወቀለምጢዳ ፡ ወሰጠ
ጽዮን ፡ የቀደመው ፡ ቢጠፋባቸው ፡ እን
ደገና ፡ እንዲያጸናው ፡ የሰባውን ፡ ደም ፡
ያለበትን ፡ እንጨት ፡ ቅንጭቡን ፡ ወር
ካውን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስበው ፡ አግብተው
በታል ፡ በነጋው ፡ ናቡከደነፆር ፡ ፫ቱ ፡
ደቂቅን ፡ ፈጣሪያቸው ፡ አድኗቸው ፡
ይሆን ፡ ወይስ ፡ አቃጥሏቸው ፡ ይሆን ፡
ብሎ ፡ ከሰገነት ፡ ሆኖ ፡ ሲመለከት ፡
አራት ፡ ሁነው ፡ በእሳቱ ፡ መካከል ፡
ሲመላለሱ ፡ አይቶ ፡ ወናሁ ፡ ትግልም ፡
ዓሚረነ ፡ ፫ ፡ ዕደወ ፡ ወደይነ ፡ ውስተ ፡
ዕቶነ ፡ እሳት ፡ ወዮምሰ ፡ እሬኢ ፡ ፬ ፡
ዕደወ ፡ እንዘ ፡ ያንሶስዉ ፡ ማዕከለ ፡
እሳት ፡ ፍቱሐኒሆሙ ፡ ወራብዖሙሰ ፡
ይመስል ፡ ከመ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ እነሆ ፡ ትላንት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡
አስረን ፡ ከእሳት ፡ ጨምረን ፡ ነበረ ፡
ዛሬ ፡ ግን ፡ አራት ፡ ሰዎች ፡ ተፈትተው ፡



በእሳቱ ፡ መካከል ፡ ይመላለሳሉ ፡ አራ
ተኛውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡
ይመስላል ፡ ብሎ ፡ አንትሙ ፡ ሲድራቅ ፡
ወሚሳቅ ፡ ወአብደናጎ ፡ አግብርተ ፡
እግዚአብሔር ፡ ንዑ ፡ ጻእ ፡ ዝየ ፡ እላ
ንት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባለሟሎች ፡
ሲድራቅ ፡ ሚሳቅ ፡ አብደናጎ ፡ ኑ ፡ ወ
ዲህ ፡ ውጡ ፡ አላቸው ፡ መልሕቅ ፡
ጣሉልን ፡ አላግ ፡ ትከሉልን ፡ ሳይሉ ፡
እንደ ፡ ሳቢሳ ፡ ብር ፡ ብር ፡ እያሉ ፡ ወጥ
ተዋል ፡ ወኢለከፎሙ ፡ ጼና ፡ ዘእሳት ፡
ጠለሸት ፡ እንኳ ፡ አላሳረፈባቸውም ፡
በምትሐታቸው ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ አሉት ፡
በምትሐትማ ፡ ከሆነ ፡ እላንት ፡ ትበ
ልጡ ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ ከእሳት ፡ ጨመ
ራቸው ፡ ከሰል ፡ አድርጓቸዋል ፡ ዳን ፡
፫ ፡ ፳፲ ።

[illegible]

በብዙ ፡ መከራዬ ፡ ጊዜ ፡ ለኔ ፡ ቸርነ
ቱን ፡ የገለጠልኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይከ
በር ፡ ይመስገን ።

[illegible]

እኔስ ፡ ከባለሟልነትህ ፡ እንደወጣሁ ፡
ቀረሁ ፡ ብዬ ፡ ነበር ።

[illegible]

ከባለሟልነቱ ፡ ስላልወጣሁ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ወደሱ ፡ መልሺ ፡ የለመንሁ
ትን ፡ የልመናዬን ፡ ነገር ፡ ሰማኝ ።

[illegible]

ትሩፋኑ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እውነት ፡
ይሻችሁ ፡ እንድም ፡ ትሕትና ፡ ይሻችሁ ፡
ውደዱት ።

[illegible]

እግዚአብሔር ፡ እውነትን ፡ ትሕትናን ፡
ይወዳልና ፡ እንድም ፡ ትሕትና ፡ የያዘ ፡
ሰውን ፡ ይወዳልና ።

[illegible]

ሐሰተኞችን ፡ ትዕቢተኞችን ፡ ተበ
ቅሎ ፡ ያጠፋቸዋል ።

[illegible]

መከራችሁን ፡ ታግሣችሁ ፡ ተቀበሉ ፡
ግቡናችሁንም ፡ በትዕግሥት ፡ አጽ
ኑት ።

[illegible]

ማን ፡ ማን ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆን ፡ ዕገሌ ፡
ዕገሌ ፡ ምን ፡ አሰኝቶኝ ፡ በእግዚብሔር ፡
ያመናችሁ ፡ መላችሁ ።

[illegible]

ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዘ
ላለሙ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ።

አሜን ።



2014 04 17

፩ ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ተኀድገ ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ የምእመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ። ኃጢአታቸው ፡ በንስሐ ፡ የተሠረየላቸው ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

ወእለ ፡ ኢተሐሰበ ፡ ሎሙ ፡ ዘሎሙ ፡ ጌጋዮሙ ።

በደላቸውም ፡ ኵሉ ፡ በንስሐ ፡ ያልተቈጠረባቸው ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ። እንድም ፡ (ብፁዓን ፡ ለእለ ፡ ተኀድገ ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ) ፡ ኃጢአታቸው ፡ በንስሐ ፡ ለተሠረየላቸው ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ መባል ፡ ይገባቸዋል ። (ወለእለ) ፡ ኃጢአታቸውም ፡ ሁሉ ፡ በንስሐ ፡ ላልተቈጠረባቸው ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ መባል ፡ ይገባቸዋል ።

ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢኈለቈ ፡ ሎቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃጢአቶ ።

ይልቁንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃጢአቱን ፡ ያልቈጠረበት ፡ ሕዝቅያስ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። እንድም ፡ (ለዘኢኈለቈ ፡ ሎቱ) ፡ ኃጢአቱን ፡ ላልቈጠረበት ፡ ለሕዝቅያስ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ መባል ፡ ይገባዋል ።

ወዘአልቦ ፡ ጽልሑት ፡ ውስተ ፡ ልቡ ።

በልቡናው ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ክዳት ፡ ሽንገላ ፡ የሌለበት ፡ ሕዝቅያስ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። እንድም ፡ (ወለዘአልቦ) ። በልቡናው ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ክዳት ፡ ሽንገላ ፡ ለሌለበት ፡ ለሕዝቅያስ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ መባል ፡ ይገባዋል ። እንድም ፡ (ብፁዓን) ፡ ኃጢአታቸው ፡ በጥምቀት ፡ የተሠረየላቸው ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ። (ለእለ) ፡ ለተሠረየላቸው ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ መባል ፡ ይገባቸዋል ። (ወእለ ፡ ኢሐሰበ) ፡ በደላቸውም ፡ ሁሉ ፡ በጥምቀት ፡ ያልተቈጠረባቸው ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ። (ወለዘኢሐሰበ) ፡ በደላቸው ፡ በጥምቀት ፡ ላልተቈጠረባቸው ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ መባል ፡ ይገባቸዋል ። ብፁዕ ፡ (ብእሲ ፡ ዘኢኈለቈ ፡ ሎቱ) ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃጢአቱን ፡ በጥምቀት ፡ ያልቈጠረበት ፡ ምእመን ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። (ለዘኢኈለቈ) ፡ ኃጢአቱን ፡ በጥምቀት ፡ ላልቈጠረበት ፡ ምእመን ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ መባል ፡ ይገባዋል ። (ወዘአልቦ) ፡ በልቡናው ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ክዳት ፡ ሽንገላ ፡ የሌለበት ፡ ምእመን ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። (ወለዘአልቦ) ፡ በልቡናው ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ክዳት ፡ ሽንገላ ፡ የሌለበት ፡ ምእመን ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ መባል ፡ ይገባዋል ። ሮሜ ፡ ፬ ፡ ፯-፰ ። ፰ ፡ ፩ ።

፫ ፡ እስመ ፡ አርመምኩ ፡ በልየ ፡ አዕፅምትየ ፡ እም ገበ ፡ እጸርሕ ፡ ኵሉ ፡ አሚረ ።

ዕለት ፡ ዕለት ፡ ከምለምነው ፡ ልመና ፡ ተከልክያለሁና ፡ ሰውነቶቼ ፡ ባለመከራ ፡ ሆኑ ።

፬ ፡ እስመ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ክብደት ፡ እዴከ ፡ ላዕሌየ ። ፀቀ ፡ ፫ ፡ ፫ ።

በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ እጁ ፡ መዓትህ ፡ ስለፀናችብኝ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ከምጸልየው ፡ ጸሎት ፡ ተከልክያለሁና ፡ ሰውነቴ ፡ ባለመከራ ፡ ሆነ ።

ወተመየጥኩ ፡ ለኀርትምና ፡ ሶበ ፡ ወግዓኒ ፡ ሦክ ።

መከራ ፡ ባገኘኝ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ተመለስኁ ። እንድም ፡ ኃጢአት ፡ በሠራኁ ፡ ጊዜ ፡ ለጥፋት ፡ ሆንኁ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ተመለስኁ ። ፀናሕከዎ ፡ ለወይንየ ፡ ይፍረይ ፡ አስካለ ። ወፈረየ ፡ ሦክ ። ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፪-፬ ። ጠበቆ ፡ ሦክ ፡ ወሐነቆ ። ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፯ ። ወእመሰ ፡ አውዕአት ፡ ሦክ ፡ ወአሜከላ ፡ ቅሩብ ፡ ለመርገም ፡ እንዲል ። ዕብ ፡ ፮ ፡ ፰ ።

፭ ፡ ኃጢአትየ ፡ ነገርኩ ፡ ወአበሳየ ፡ ኢኀባዕኩ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ያገኘህ ፡ ኃጢአት ፡ ብትሠራ ፡ አይደለምን ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አዎን ፡ ጥቃቅኑን ፡ ኃጢአቴን ፡ ነገርኁ ፡ ታላላቁን ፡ ኃጢአቴንም ፡ አልሠወርሁም ፡ ነገርሁ ፡ እንጂ ።

ወእቤ ፡ እስተዋዲ ፡ ርእስየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ኃጢአትየ ። ሸቀር ፡ ፲፩-፴፩ ።

ስለ ፡ ኃጢአቴም ፡ ሰውነቴን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አጻናለኁ ፡ አዋቅሳለኁ ፡ አካስሳለኁ ፡ አልኁ ።

ወአንተ ፡ ኀደግ ፡ ጽልሑተ ፡ ልብየ ።

አንተም ፡ የልቡናዬን ፡ ክዳት ፡ ሽንገላውን ፡ ተው ፡ አልኁ ። እንድም ፡ እንዘ ፡ አስተዋዲ ። ራሴን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ሳጣላ ፡ ሳዋቅስ ፡ ሳካስስ ፡ የልቡናዬን ፡ ክዳት ፡ ሽንገላውን ፡ ተው ፡ አልኁ ። እንድም ፡ ከመ ፡ አስተዋዲ ። ራሴን ፡ አጣላ ፡ አዋቅስ ፡ አካስስ ፡ ዘንድ ፡ የልቡናዬን ፡ ክዳት ፡ ሽንገላውን ፡ ተው ፡ አልኁ ።

፮ ፡ በእንተዝ ፡ ይጼሊ ፡ ኀቤከ ፡ ኵሉ ፡ ጻድቅ ፡ በ ጊዜ ፡ ርቱዕ ።

ንባብ ፡ ቢጣላ ፡ በምስጢር ፡ ማስታረቅ ፡ ነው ። በድሎ ፡ ንስሓ ፡ መግባት ፡ የሚገባ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ፍጹም ፡ ጻድቅ ፡ ሕዝቅያስ ፡ በሰባቱ ፡ ባሥራ ፡ ሁለቱ ፡ በሸያ ፡ አራቱ ፡ ጊዜያት ፡ ወዳንተ ፡ መልሶ ፡ ይለምናል ። ዘላዕሌሁ ፡ ኃደረ ፡ ኵሉ ፡ መለኮቱ ፡ በሥጋ ፡ እንዲል ። ቈላ ፡ ፪ ፡ ፱ ። እንድም ፡ ማናቸውም ፡ ጻድቅ ፡ ሁሉ ፡ ወዳንተ ፡ መልሶ ፡ ይለምናል ።

ወባሕቱ ፡ ማየ ፡ አይኅ ፡ ብዙኅ ፡ ኢይቀርብ ፡ ኀቤሁ ።

ባሕቱ ፡ ዋዌ ፡ ነው ። ማየ ፡ አይኅ ፡ ሰናክሬም ፡ ወዳንተ ፡ አይቀርብም ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ።

፯ ፡ አንተ ፡ ምስካይየ ፡ እምዛቲ ፡ ምንዳቤየ ፡ እንተ ፡ ረከበተኒ ።

አዎን ፡ ከዚች ፡ ካገኘችኝ ፡ መከራ ፡ ታድነኝ ፡ ዘንድ ፡ አምባ ፡ መጸጊያዬ ፡ ነህ ።

ወትፍሥሕትየ ፡ ከመ ፡ ታድኅነኒ ፡ እም ፡ እለ ፡ ርደኒ ። ዘዳ ፡ ፴፩ ፡ ፲፯ ። ኢሳ ፡ ፴፩ ፡ ፩ ።

ከከበቡኝም ፡ ጠላቶቼ ፡ ታድነኝ ፡ ዘንድ ፡ ተድላ ፡ ደስታዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ። ዕብ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ።



2014 04 17

፯ ፡ ወሌብወከ ፡ ወእሜህረከ ፡ በዛቲ ፡ ፍኖት ፡ እንተ ፡ ሖርከ ፡

ወትፍምሕትየኒ ፡ እለሀ ፡ ሕዝቅያስ፡ አበድሀ፡በሐድሀበት፡ፍኖት፡ንሴሐ፡ እፀናለኍ፡እንድም ፡ ዛተ ፡ ፍኖተ ፡ ይላል ፡ ንሴሐን ፡ ልብ ፡ አስደርግሃ ለኍ፡እፀንዓከ ፡ ብለህ ፡ አጥብቀህ ፡ ነው፡እንድም ፡ በሕግ ፡ እፀናሃለሁ ፡

ወዐመገ ፡ እለፎንተየ ፡ ላዕሌከ ፡

ዓይኑም ሕረቴም፡ወዳንተ፡እፀናለኍ ፡

፰ ፡ ኢትኩኑ ፡ ከመ ፡ ፈረስ ፡ ወበቅል ፡ እለ ፡ አል ቦሙ ፡ ልብ ፡

ምንም፡ባይሰሙት፡እለ፡ሰናከሬምን፡ ይመክሩቸዋል ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ ሌላ ቸው ፡ እንደ ፡ ፈረስ ፡ እንደ ፡ በቅሉ፡ አትሁኑ ፡ ልብማ ፡ መከዳ ፡ መከዳ ፡ ያ ሀል ፡ ብሎ ፡ እእምሮ ፡ ለብዎ ፡ እንደ ፡ ሌላቸው ፡ እንደ ፡ እንስሳት ፡ አትሁኑ ፡

እለ ፡ በልጓም ፡ ወበልጓም ፡ ይመይጥዎሙ ፡ መላትሒሆሙ ፡

በሽብ ፡ በልባብ ፡ በልጓም ፡ ገጭተው ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ እንደሚመልሷቸው ፡

እንድም ፡ (ኢትኩኑ) ፡ ወገኖቹን ፡ ይመ ክሩቸዋል ፡ እእምሮ ፡ እንደሌላቸው ፡ እንደነሰናከሬም ፡ አትሁኑ ፡ (እለ ፡ በ ሐላል) ፡ ፍትሑ ፡ ርቱዑ ፡ ሥላሴ ፡ በ ሽብ ፡ መዓት ፡ በልጓመ ፡ መዓት ፡ ከለ ኪሶን ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ከሕይወት ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ከተድላ ፡ ወደ መከራ ፡ እንደሚ መልሷቸው ፡ እወዲ ፡ ልጓመ ፡ ውስተ ፡ አፉከ ፡ መዝማማተ ፡ ውስተ ፡ ከናፍ ሪከ ፡ ወእመይጠከ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ መጻእከ ፡ እንዲል ፡

ከመ ፡ ኢይቅረቡ ፡ ኀቤከ ፡

ኢይቅረቡ፡ለላይኛው፡ለነሰናከሬም፡ ነው ፡ ወዳንተ ፡ እንዳይቀርቡ ፡ ያስቡ ፡

፱ ፡ ብዙኅ ፡ መቅሠፍቶሙ ፡ ለኃጥኣን ፡

የነሰናከሬም፡መቅሠፍታቸው፡ብዙ፡ ነው ፡ መቅሠፍቱስ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሰውን ፡ ብዛት ፡ መናገር ፡ ነው ፡

እለሰ ፡ ይትዌከሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሣህል ፡ ይዕ ገቶሙ ፡

ለ· የቀረው ፡ ነው ፡ ለእለሰ ፡ ሊል ፡ ነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያመኑትን ፡ ግን ፡ ይቅርታ ፡ እንደ ፡ እሬቅ ፡ ግመ ሬ ፡ ሁና ፡ ይጠብቃቸዋል ፡ እንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ በይቅርታው ፡ ይጠ ብቃቸዋል ፡ እንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅርታውን ፡ ይመግባቸዋል ፡

፲ ፡ ተፈሥሑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወተሐሠዩ ፡ ጻድ ቃን ፡ መዝ ፡ ፹፪ ፡ ፩ ፡

ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እም ናችኍ ፡ በተደረገላችኍ ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ይበላችኍ ፡

ወተመክሑ ፡ ኵልክሙ ፡ ርቱዓነ ፡ ልብ ፡

ቅን ፡ ልቡና ፡ ትሑት ፡ ሰብእና ፡ ያላ ችሁ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ መላችኍ ፡ ደስ ፡ ይበላችኍ ፡ እምከመ ፡ አድማዕነ ፡ መንግሥት ፡ ንትሜከሕ ፡ እንዲል ፡



መዝሙር ፡ ፴፪ ፡

ተፈሥሑ ፡ ጻድቃን ፡ በእግዚአብሔር ፡

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ ጻድ ቃን ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ እንድም ፡ ነቢ ያት ፡ ካህናት ፡ በእግዚአብሔር ፡ እም ናችኍ ፡ በተሠራላችኍ ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ይበላችኍ ፡ ወለራትዓን ፡ ይደልዎሙ ፡ ክብር ፡

ለኢሳይያስ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ ክብር ፡ ይ ገባቸዋል ፡ ማለት ፡ እላንተ ፡ ልታከብ ሯቸው ፡ ይገባል ፡

፪ ፡ ግነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመሰንቆ ፡

መሰንቆ ፡ እየመታችኍ ፡ ለእግዚአብ ሔር ፡ ተገዙ ፡

ወበመዝሙር ፡ ዘ፲ቱ ፡ አውታሪሁ ፡ ዘምሩ ፡ሎቱ ፡ ሉቃ ፡ ፴፱ ፡ ፲፭ ፡

ዓሥር ፡ አውታር ፡ ያለው ፡ በገና ፡ እየ ደረደራችኍ ፡ ተገዙ ፡ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ፡ ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ፡

፫ ፡ ወሰብሕዎ ፡ ስብሐተ ፡ ሐዲሰ ፡ መዝ ፡ ፺፭ ፡ ፩ ፡ ፺፯ ፡ ፩ ፡ ፻፵፱ ፡ ፩ ፡ ኢሳ ፡ ፵፪ ፡ ፲ ፡

እንግዳ ፡ ምስጋና ፡ እያመሰገናችኍ ፡ ምስጋናውስ ፡ ጥንተ ፡ ምስጋናው ፡ ነው ፡ ግብሩ ፡ ሐዲስ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስብሐቲሁ ፡ እምኅቤሁ ፡ ወው ዳሴሁ ፡ እምዚአሁ ፡ እንዲል ፡ ቅዳ ፡ ዮሐ ፡ እንድም ፡ (ግነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመሰንቆ) ፡ በሃይማኖት ፡ ፀንታችኍ ፡ ተገዙ ፡ መሰንቆ ፡ ዘይቤ ፡ ይእቲ ፡ ሃይ ማኖት ፡ እንተ ፡ ለብስዋ ፡ ሰማዕት ፡ እ ንዲል ፡ (ወበመዝሙር ፡ ዘ፲ቱ ፡ አው ታሪሁ ፡ ዘምሩ ፡ ሎቱ) ፡ ዓሥር ፡ ሕዋ ሳት ፡ ባለው ፡ ሰውነት ፡ ምግባር ፡ ይዛ ችኍ ፡ ተገዙ ፡ እንድም ፡ (በመሰንቆ) ፡ በወንጌል ፡ ፀንታችኍ ፡ (ወበመዝሙ ር) ፡ ሕግጋቱ ፡ ዓሥር ፡ በሚሆኑ ፡ በኦ ሪት ፡ ፀንታችኍ ፡ በመዓልትም ፡ በሌ ሊትም ፡ ተገዙ ፡ (ወሰብሕዎ ፡ ስብሐተ ፡ ሐዲሰ) ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ እያላችኍ ፡ አመስግኑት ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ፡

መናየ ፡ ዘምሩ ፡ ወየብቡ ፡ ሎቱ ፡

በጎ ፡ ምስጋና ፡ አመስግኑ ፡ ለእሱ ፡ ምስ ጋና ፡ አቅርቡ ፡ ኤፌ ፡ ፭፲፱ ፡

፬ ፡ እስመ ፡ ጽድቅ ፡ ቃሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔር ፡ ቃሉ ፡ እውነት ፡ ነ ውና ፡ እንድም ፡ እከላዊ ፡ ነውና ፡

ወኵሉ ፡ ግብሩ ፡ በሃይማኖት ፡

ሥራውም ፡ ኊሉ ፡ በአምንታ ፡ ይፈጸ ማልና ፡ እንድም ፡ (ወኵሉ ፡ ግብሩ ፡ ሃይማኖት) ፡ ሥራው ፡ ኊሉ ፡ ሃይማ ኖት ፡ ነውና ፡

፭ ፡ ያፈቅር ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽድቀ ፡ ወምጽ ዋተ ፡

ጽድቀ ፡ እውነትን ፡ ወምጽዋተ ፡ ምጽ ዋትን ፡ እንድም ፡ ጽድቀ ፡ ሃይማኖ ትን ፡ ምጽዋተ ፡ ምግባርን ፡ ይወድዳ ልና ፡ እንድም ፡ እውነትን ፡ ምጽዋ ዋትን ፡ ሃይማኖትን ፡ ምግባርን ፡ የያዘ ፡ ሰውን ፡ ይወድዳልና ፡ እንድም ፡ ይወ ድዳል ፡

2014 04 17

ግሀት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መልዓ ፡ ምድር ።

የእግዚአብሔር ፡ ይቅርታው ፡ ምድ ርን ፡ መላ ፡ ማለት ፡ ምድርን ፡ ፈጠረ ፡ ኢሣ ፡ ፶፫ ።

፮ ፡ ወበቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀንዓ ፡ ሰማያት ።

ለይኩን ፡ ባለው ፡ ቃሉም ፡ ሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ ተፈጠሩ ። እንድም ፡ ፀንተ ው ፡ ይኖራሉ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፫ ። ቆላ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ። ዕብ ፩ ፡ ፪ ። ፲፩ ፡ ፫ ።

ወእምእስትንፋሰ ፡ አፉሁ ፡ ኵሉ ፡ ኃይሎሙ ።

ከረቂቅ ፡ ሥልጣኑም ፡ የተነሣ ፡ ሰማይ ፡ ከነግሡ ፡ ምድር ፡ ከነ ፡ ልብሱ ፡ ተፈ ጠሩ ። እንድም ፡ ፀንተው ፡ ይኖራሉ ። እንድም ፡ (ሣህሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መልዓ ፡ ምድረ) ፡ ደቂቀ ፡ አዳምን ። (ወበቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀንዓ ፡ ሰ ማያት) ፡ መላእክትን ፡ ፈጠረ ፡ (ወእ ምእስትንፋሰ ፡ አፉሁ ፡ ኵሉ ፡ ኃይሎ ሙ) ፡ ከረቂቅ ፡ ሥልጣኑ ፡ የተነሣ ፡ መላእክት ፡ ደቂቀ ፡ አዳም ፡ ፀንተው ፡ ይኖራሉ ። እንድም ፡ (ሣህሉ ፡ ለእግ ዚአብሔር) ፡ ትሑታኑን ፡ (ወበቃለ ፡ እግዚአብሔር) ፡ ልዑላኑን ፡ ፈጠረ ። (ወእምእስትንፋሰ ፡ አፉሁ ፡ ከረቂቅ ፡ ሥልጣኑ ፡ የተነሣ ፡ የትሑታን ፡ የል ዑላን ፡ ወገኖች ፡ ፀንተው ፡ ይኖራሉ ። ልዑላን ፡ ትሑታንን ፡ ለመላእክት ፡ ለደቂቀ ፡ አዳም ፡ ስጥ ፡ እንድም ፡ (ሣ ሀሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መልዓ ፡ ም ድረ) ፡ ይቅርታው ፡ ምድርን ፡ መላ ፡ ማለት ፡ ባሬቱ ፡ መዓዘን ፡ ደረሰ ። እን

ድም ፡ ለኔ ፡ ያደረገውን ፡ ይቅርታ ፡ ለሌላውም ፡ አደረገው ። እንድም ፡ ለኔ ፡ ያደረገውን ፡ ይቅርታ ፡ (ለሌላ ውም ፡ አደረገው) ፡ ሁሉ ፡ ሰማው ፡ ለአጠይቆተ ፡ ፫ቱ ፡ አካላት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ ተናገረው ። ሣህሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ወልድን ። ወእምእስትንፋሰ ፡ አፉሁ ፡ ኵሉ ፡ ኃይሎሙ ፡ ብሎ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሲ.ቲ ፡ ግን ፡ ወበቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባለው ፡ አብቅቷል ።

፯ ፡ ዘያስተጋብዖ ፡ ከመ ፡ ዝቅ ፡ ለማየ ፡ ባሕር ።

ዘእስተጋብዖ ፡ ሲል ፡ ነው ። ወሀውን ፡ እንደ ፡ ራዋት ፡ ወሀ ፡ የወሰነው ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወይሠይሞ ፡ ውስተ ፡ መዛግብተ ፡ ቀላያት ።

(ወዘሤሞ) ፡ በውቅያኖስ ፡ ሣጥንነት ፡ የወሰነው ፡ እሱ ፡ ነው ። እንድም ፡ (ዘያ ስተጋብዖ ፡ ከመ ፡ ዝቅ ፡ ለማየ ፡ ባሕር) ፡ ሰናክሬምን ፡ ለጥፋት ፡ በለኪሶን ፡ የሚ ሰበስበው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወይሠይሞ ፡ ውስተ ፡ መዛግብተ ፡ ቀላያት) ። ባያ ቶቹ ፡ በለናምሩድ ፡ መቃብር ፡ እንዲ ቀበር ፡ የሚያደርገው ፡ እሱ ፡ ነው ።

፰ ፡ ትፈርሆ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵላ ፡ ምድር ።

ምድር ፡ በመላዋ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትፈራዋለች ፡ ማለት ፡ ታመልከዋለች ፡ በምድር ፡ ሰዎችን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወእምኔሁ ፡ ይደነግጹ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ።

ከስነ ፡ ፍጥረቱም ፡ የተነሣ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ይደነግጻሉ ። የምያስደነግጽ ፡ ስነ ፡ ፍጥረት ፡ አለና ፡ እንድም ፡ እለ ፡ ሰናክሬምን ፡ አጥፍቶ ፡ እስራኤልን ፡ ታድጎ ፡ ከደረገው ፡ ተአ ምራት ፡ የተነሣ ፡ ይደነግጣሉ ።



፱ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ወኮኑ ።

አፍገዘዛታል ፡ ይገለጠው ።

ወውእቱ ፡ አዘዘ ፡ ወተፈጥሩ ።

ይቤ ፡ ያለውን ፡ አዘዘ ፡ ኮኑ ፡ ያለውን ፡ ተፈጥሩ ፡ ብሎ ፡ ገለጸው ። እሱ ፡ ይፈ ጠሩ ፡ ብሎ ፡ አገዘዚልና ፡ እነሱም ፡ ተፈ ጥረዋልና ። እንድም ፡ እለ ፡ ሰናክሬም ፡ ይጥፉ ፡ ብሎ ፡ አገዘዚልና ፡ እነሱም ፡ ጠፍተዋልና ፡ መዝ ፡ ፻፵፰ ፡ ፭ ።

፲ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመይጥ ፡ ምክሮሙ ፡ ለአ ሕዛብ ።

እግዚአብሔር ፡ የአሕዛብን ፡ ምክራ ቸውን ፡ ይለውጣል ፡ ነገ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡን ፡ ገድለን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ አፍርሰን ፡ የምንገድለውን ፡ ገድለን ፡ የምንማርከውን ፡ ማርከን ፡ እንሔዳ ለን ፡ ብለው ፡ መጥተው ፡ ነበር ፡ ይህን ፡ አስቀርቶባቸዋልና ። ኢሳ ፡ ፰ ፡ ፰ ።

ወይመይጥ ፡ ሕሊናሆሙ ፡ ለሕዝብ ።

ወይዌልጥ ፡ ይላል ፡ የሕዝቡን ፡ አሳ ባቸውን ፡ ይለውጣል ፡ ማለት ። ነገ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ትፈር ሳለች ፡ እኛም ፡ የምንሞተው ፡ እንሞ ታለን ፡ የምንማረከው ፡ እንማረካለን ፡ ንጉሡም ፡ ይያዛል ፡ ብለው ፡ ነበረ ፡ ይህ ፡ ቀርቶላቸዋልና ።

ወያረስዮሙ ፡ ምክሮሙ ፡ ለመላእክት ።

ያለቆቹን ፡ ምክራቸውን ፡ ያዘጋጃ ዋል ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ከቤተ ፡ ክህነት ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ የተገኘውን ፡ ወርቅ ፡ ሰብ ስቦ ፡ እቱእ ፡ እግዚእየ ፡ ዘአፆርከኒ ፡ እፀውር ፡ ብሎ ፡ ቢልክለት ፡ ከሬት ፡ ቈርሶ ፡ ለዳረጎት ፡ እንዲሉ ። እረ ፡ በውል ፡ ሰልተህ ፡ ገብር ፡ በለው ፡ ብሎ ፡ ተጋፍቶ ፡ መጥቷል ። ያን ፡ ተቀብሎ ፡ ሔዶ ፡ ቢሆን ፡ አገር ፡ ጤና ፡ ነበርና ። ፬ነ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ።

፲፩ ፡ ወምክሩሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሄሉ ፡ ለዓ ለም ። ምሳ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ።

የለዚያን ፡ ይለውጣል ፡ ብሎ ፡ ነበርና ። የእግዚአብሔር ፡ ምክር ፡ ግን ፡ ለዘላ ለም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

ወሕሊና ፡ ልቡኒ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ።

የልቡናውም ፡ አሳብ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ። እንድም ፡ (ወምክ ሩሰ) ፡ በነቢብ ፡ የፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ። (ወሕ ሊና ፡ ልቡኒ) ፡ በሐልዮ ፡ የፈጠረውም ፡ ፍጥረት ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖ ራል ።

፲፪ ፡ ብፁዕ ፡ ሕዝብ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ አምላኩ ።

ፈጣሪው ፡ እግዚአብሔር ፡ የሆነለት ፡ ሕዝቅያስ ። እንድም ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። እግዚአ ብሔርማ ፡ ያልፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ አለን ፡ ብሎ ፡ የፈጠረውን ፡ እግዚአ ብሔር ፡ የሚያመሰግን ። መዝ ፡ ፻፵፫ ።

ሕዝብ ፡ ዘኀረየ ፡ ሎቱ ፡ ለርስቱ ።

ለርስቱ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ የመረጠው ፡ ሕዝቅያስ ። አንድም ፡ ለመንግሥት ፡ ለማያት ፡ የመረጠው ፡ ምዕመን ።

፲፫ ፡ እምሰማይ ፡ ሐወጸ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ በልዕልና ፡ ሁኖ ፡ ጎበኘ ።

ወርእየ ፡ ኵሎ ፡ ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

እለ ፡ ሕዝቅያስን ፡ በምሕረት ፡ እለ ፡ ሰናክሬምን ፡ በመዓት ፡ አየ ፡ ተመለከተ ።

፲፬ ፡ ወእምድልው ፡ ጽርሐ ፡ መቅደሱ ።

እምሰማይና ፡ እምድልው ፡ ጽርሐ ፡ መቅደሱ ፡ አንድ ፡ ወገን ። ዝግጅ ፡ በምትሆን ፡ በሰማያዊት ፡ መቅደሱ ፡ ሁኖ ፡ ጎበኘ ።

ወርእየ ፡ ኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ኀዱሩን ፡ ዲበ ፡ ምድር ። ኢሳ ፡ ፹፫ ፡ ፲፭ ።

ርእየና ፡ ርዕየ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኵሉ ፡ ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያውና ፡ እለ ፡ ኅዱሩን ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ አንድ ፡ ወገን ። በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ እለ ፡ ሕዝቅያስን ፡ በምሕረት ። በለኪሶን ፡ የሰፈሩ ፡ እለ ፡ ሰናክሬምን ፡ በመዓት ፡ አየ ፡ ተመለከተ ።

፲፭ ፡ ዘውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ፈጠረ ፡ልቦሙ ።

ሐወጸ ፡ ርእየ ፡ ብሎ ፡ ብናገርም ፡ ያየ ፡ የተመለከተ ፡ እንዲያውቅ ፡ ማወቁን ፡ ስናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ። እንደ ፡ ገናስ ፡ ርእየ ፡ እንዳልለው ፡ ልቡናቸውን ፡ የፈጠረ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ማለት ። በሐልዮ ፡

የሥራትን ፡ አውቆ ፡ የሚፈርድባቸው ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወዘየሐምር ፡ ኵሎ ፡ ምግባሮሙ ።

ሥራቸውንም ፡ ሁሉ ፡ መርምሮ ፡ የሚያውቅ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ማለት ። በነቢብ ፡ በገቢር ፡ በተሠራው ፡ ኃጢአት ፡ መርምሮ ፡ አውቆ ፡ የሚፈርድ ፡ እሱ ፡ ነው ።

፲፮ ፡ ኢይድኅን ፡ ንጉሥ ፡ በብዝኃ ፡ ሠራዊቱ ።

በሐልዮ ፡ በነቢብ ፡ በገቢር ፡ በተሠራው ፡ ኃጢአት ፡ መርምሮ ፡ አውቆ ፡ የሚፈርድ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰናክሬም ፡ በሠራዊቱ ፡ ብዛት ፡ አይድንም ።

ወያርብሀኒ ፡ ኢይድኅን ፡ በብዝኃ ፡ ኀይሉ ።

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ያርብኃዊ ፡ ፈርዖን ፡ ስንኳን ፡ በሠራዊቱ ፡ ብዛት ፡ አልዳነም ። ሚሬ ፡ ፲፬ ፡ ፯ ።

፲፯ ፡ ወፈረስኒ ፡ ሐሰት ፡ ኢያድኅን ፡ ኢያ፵፪ ፡ ፲፯ ።

ፈረስኒ ፡ ሐሰት ፡ ፈረስ ፡ ሐሰት ፡ ነው ። ወኢያድኅን ፡ አያድንም ፡ አንድም ፡ ሐሰት ፡ በሐሰት ፡ ሳሉ ፡ አያድንም ፡ እስራኤል ፡ ኤርትራን ፡ ከተሻገሩ ፡ በኋላ ፡ ግብፃውያን ፡ እንሻገራለን ፡ ብለው ፡ ቢገቡ ፡ ጌታ ፡ ሙሴን ፡ ዝብጣ ፡ ለባሕር ፡ አለው ፡ በትሩን ፡ እንደ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ አድርጎ ፡ አመሳቅሎ ፡ ቢመታት ፡ ፈረሶች ። የፈርዖን ፡ ፈረስ ፡ ወደላይ ፡ ዘለለ ። መልአኩ ፡ ቢመታው ፡ ተመልሷል ። ኢሳ ፡ ፴፭ ፡ ፲፫ ።



ወኢያመሥጦ ፡ በብዝኃ ፡ ጽንዑ ።

በኃይሉም ፡ ጽናት ፡ አያመልጠውም ። አሞ ፡ ፪ ፡ ፲፬–፲ ።

፲፰ ፡ ናሁ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ እለ ፡ ይፈርህዎ ። ሚሬ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ ።

እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አዕይንተ ፡ ምሕረቱ ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ ወደሚፈሩት ፡ ሰዎች ፡ ነው ።

እለሰ ፡ ይትዌከሉ ፡ በምሕረቱ ።

በቸርነቱ ፡ ለሚያምኑ ፡ ሰዎች ።

፲፱ ፡ ያድኅና ፡ እሞት ፡ ለነፍሶሙ ።

ሰውነታቸውን ፡ ከጦር ፡ ያድናታል ።

ወይሴስዮሙ ፡ እመ ፡ ረኃብ ።

ከጦር ፡ ቢድኑ ፡ በረኀብ ፡ ይሞቱ ፡ የለምን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ። በረኀብ ፡ ጊዜ ፡ ጥቂቱን ፡ አበርክቶ ፡ ይመግባቸዋል ። ናኅን ፡ ሎጥን ፡ እንደመገበ ፡ ብላዕ ፡ ዘንተ ፡ ዓመተ ፡ ዘዘራዕከ ፡ ወበካልዕ ፡ ዓመት ፡ ዘአትረፍከ ፡ ወበሣልስ ፡ ዓ

መት ፡ ትዘርዕ ፡ ወተዓርር ፡ እንዲል ። ፬ነገ ፡ ፲፱–፳፱ ።

፳ ፡ ነፍስነ ፡ ትሴፈዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ስለዚህ ፡ ልቡናችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተስፋ ፡ ታደርገዋለች ።

እስመ ፡ ረዳኢነ ፡ ወምስካይነ ፡ ውእቱ ።

ብንዋጋ ፡ ኃይላችን ፡ ብንሸሽ ፡ አምባ ፡ መፀግያችን ፡ ነውና ።

፳፩ ፡ እስመ ፡ ቦቱ ፡ ይትፌሣሕ ፡ልብነ ። ዘካ ፡ ፲፯ ።

ልቡናችንም ፡ በሱ ፡ አምኖ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

ወተወከልነ ፡ በስሙ ፡ ቅዱስ ።

ዕኑ ፡ በሚሆን ፡ ስሙ ፡ (ስምህ) ፡ አምነናልና ።

ለትኩን ፡ እግዚኦ ፡ ምሕረትከ ፡ ላዕሌነ ።

አቤቱ ፡ ለኛ ፡ ይቅርታህ ፡ ቸርነትህ ፡ ትደረግልን ።

ወበከመ ፡ ላዕሌከ ፡ ተወከልነ ።

ባንተ ፡ እንዳመንን ፡ መጠን ።

## መዝሙር ፡ ፺ ።

፩ ፡ እባርኮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ። እግዚአብሔርን ፡ በሰባቱ ፡ በሥራ ፡ ሁለቱ ፡ በህያ ፡ አራቱ ፡ ጊዜያት ፡ አመሰግነዋለሁ ።

ወዘልፈ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ውስተ ፡ አፉየ ።

ይትነገር ፡ ያለበት ፡ ነው ። ጌትነቱ ፡ ክብሩ ፡ ተአምራቱ ፡ ዘወትር ፡ ባንደ

በቴ ፡ ሲነገር ፡ ይኖራል ። ከፋፍ ፡ ላይ ፡ ነፋስ ፡ ከፍ ፡ ላይ ፡ እስትንፋስ ፡ እንዳ ይጠፋ ፡ ከቅዱሳንም ፡ እንደበት ፡ ምስጋና ፡ አያቋርጥምና ።

፪ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትከብር ፡ ነፍስየ ።

ሰውነቴ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምና ፡ ክብራ ፡ ገንና ፡ ትኖራለች ።

2014 04 17

ይሰምዑ ፡ የዋሃን ፡ ወይትፌሥሑ ።

ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ይህን ፡ ሰምተው ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ። እንድም ፡ ደስ ፡ ይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ይስሙ ።

፫ ፡ አዕብዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስሌየ ።

እግዚአብሔርን ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ እንደኔ ፡ አመስግኑት ፡ አክብሩት ።

ወናልዕል ፡ ስሞ ፡ ኅቡረ ።

እኔም ፡ እናንተም ፡ አንድ ፡ ሁነን ። አንዳንድ ፡ ልብ ፡ መክሪ ፡ አንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ሁነን ፡ ስሙን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እናድርግ ፡ አሁን ፡ ፍጡር ፡ ፈጣሪውን ፡ የምያከብረው ፡ የምያገንነው ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ። ክቡር ፡ ልዑል ፡ እያልን ፡ እናመስግነው ፡ ሲል ፡ ነው ።
ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፵፮ ።

፬ ፡ ኃሠሥክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወተሰጥወኒ ።

ሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ የምትል ፡ ምን ፡ አድርጎልሃል ፡ ትሉኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እኔ ፡ በሕግ ፡ በአምልክ ፡ ሻሁት ። እሱም ፡ ልመናዬን ፡ ሰማኝ ።

ወእምኵሉ ፡ ምንዳቤየ ፡ አድኃነኒ ።

ከመከራዬ ፡ ሁሉ ፡ አዳነኝ ። ኢሳ ፡ ፴፰ ፡ ፳፪ ።

፭ ፡ ቅረቡ ፡ ኀቤሁ ፡ ወያበርህ ፡ ለክሙ ።

ላንተ ፡ ቢደረግልህ ፡ ለኛም ፡ ይደረግልናልን ፡ ትሉኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እዎን ፡ በሕግ ፡ በአምልክ ፡ ወደሱ ፡ ቅረቡ ፡ ብርሃን ፡ ረድኤቱን ፡ ያበራላችኋል ። እንድም ፡ ከመከራው ፡ አድኖ ፡ ደስ ፡ ያሰኛችኋል ።

ወኢይትኃፈር ፡ ገጽክሙ ።

ፊታችሁ ፡ አያፍርም ፡ ማፈር ፡ በፊት ፡ ነውና ። እንድም ፡ ፊታውራሪያችሁ ፡ ድል ፡ አይነሳም ።

፮ ፡ ዝንቱ ፡ ነዳይ ፡ ዐርአ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ሰምዖ ።

ሕዝቅያስ ። እንድም ፡ ማናቸውም ፡ ድኃ ፡ እንድም ፡ አዳም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በለመነ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልመናውን ፡ ሰማው ።

ወእምኵሉ ፡ ምንዳቤሁ ፡ አድኃኖ ።

ከመከራው ፡ ሁሉ ፡ አዳነው ።

፯ ፡ ይትዓየን ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓውዶሙ ።
ለእለ ፡ ይፈርህዎ ፡ ወያድኅኖሙ ። ዘፍ ፡ ፴፪ ፡ ፩ ።

ይኸውም ፡ ዛሬ ፡ መጀመሩ ፡ አይደለም ። ጥንትም ፡ ለሚፈሩት ፡ ለሚያመልኩት ፡ ሰዎች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ በዙሪያቸው ፡ ይከትማል ። (ወያድኅኖሙ) ፡ ያድናቸዋል ። (ይትዓየን ፡ መልአክ) ፡ እንደምን ፡ ይመቻል ፡ ቢሉ ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ መልአክ ፡ አለ ። አለቃው ፡ ከለበት ፡ ጭፍራው ፡ አይለይምና ፡ ይትዓየን ፡ አለ ። መገ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ። ኢሳ ፡ ፴፫ ፡ ፳ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ። በያዕቆብ ፡ በኤልሳዕ ፡ እንደከተመ ፡ ያዕቆብ ፡ ከወንድሙ ፡ ተጣልቶ ፡ ወደ ፡ አጎቱ ፡ ወደ ፡ ላባ ፡ ሶርያ ፡ ሒዶ ፡ ሁለቱን ፡ ልጆቹን ፡ ድሮለት ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ አበጅቶ ፡ ሲኖር ፡ ከዕለታት ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ አባቴ ፡ አገሬን ፡ ልሒድ ፡ አሰናብተኝ ፡ አለው ። ጉልበቱ ፡ ጣፍ



ጦት ፡ አላሰናብትህም ፡ አለው ፡ ከቤቱ ፡ ገብቶ ፡ ሚስቶቼን ፡ እኔ ፡ አገሬን ፡ ልሒድ ፡ ነው ። እላንተ ፡ እንደምን ፡ ትሆኑ ፡ ትሒዱን ፡ ወይስ ፡ ትቀሩ ፡ አላቸው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ላንተ ፡ ተገዢ ፡ አድርጎ ፡ ሰጥቶን ፡ የለምን ፡ አብረንህ ፡ እንሒዳለን ፡ እንጂ ፡ ወዴት ፡ እንቀራለን ፡ አሉት ። ሚስቶቹን ፡ ልጆቹን ፡ ገንዘቡን ፡ ይዞ ፡ ሒዱ ፡ ያዕቆብ ፡ እንጂ ፡ ኮበለለ ፡ አሉት ፡ ያዕቆብ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ የተጓዘውን ፡ ላባ ፡ በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡ ሁኖ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ደረሰበት ። መልአኩ ፡ ሰይፉን ፡ መዝዞ ፡ ኢታውርድ ፡ እዴከ ፡ ላዕለ ፡ ቍልዔየ ፡ ያዕቆብ ፡ እያለ ፡ ዛፉን ፡ ቅጠሉሉን ፡ ሲያረግፈው ፡ አድሯል ። ብትመጣ ፡ እንዲህ ፡ አደርግሃለሁ ፡ ሲል ፡ በነጋው ፡ እኔ ፡ ልጣላህ ፡ መጥቼ ፡ ነበረ ፡ ያባትህ ፡ ፈጣሪ ፡ እንዲህ ፡ ሲለኝ ፡ አደረ ። ለምንት ፡ ትሠርቀኒ ፡ ደቂቅየ ፡ ወአዋልድየ ፡ ከመ ፡ ዘበኵናት ፡ ፄወወ ። ወሚመ ፡ ኢይደልወኒ ፡ እስዓም ፡ ደቂቅየ ፡ ወአዋልድየ ። ልጆቼን ፡ በጦር ፡ እንደበት ፡ በፈረስ ፡ እንገት ፡ እንደማረከ ፡ ሰው ፡ ለምን ፡ ሠውረህ ፡ ትወስድብኛለህ ፡ ወይስ ፡ ልጆቼን ፡ መሳም ፡ አይገባኝምን ፡ አሁንም ፡ ልጆቼን ፡ አትበድልብኝ ፡ ብሎ ፡ ጠቦት ፡ አርደው ፡ ተራርቀው ፡ ተማምለው ፡ ተለያይተዋል ። ዕርቅ ፡ ደም ፡ ያደርቅ ፡ እንዲሉ ። ዘፍ ፡ ፴፩ ፡ ፳–፶፭ ። ኤልሳዕም ፡ በሰማርያና ፡ በሶርያ ፡ መካከል ፡ ሬማት ፡ የምትባል ፡ አገር ፡ አለች ። የሰማርያው ፡ ሲበረታ ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ የሶርያው ፡ ሲበረታ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ የምትገዛ ፡ ባገራችን ፡ ዋግ ፡ እንዳለች ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ጨምሮ ፡ ሊቀጥራት ፡ መከረ ፡ ኤልሳዕ ፡ ይህን ፡ አውቆ ፡ ኢዮራምን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መክሮብሃልና ፡ አንተ ፡ አስቀድመህ ፡ ቅጠርበት ፡ አለው ፡ ቀጠራት ። ለወልደ ፡ አዴር ፡ ሔደው ፡ ነገሩት ፡ ይህን ፡ ብዬ ፡ ድንኳን ፡ ቂልፌ ፡ ሰው ፡ መርጬ ፡ በቂይታ ፡ መከርኍ ፡ ነገሬን ፡ እያወጣ ፡ የሚነግርብኝ ፡ ማን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተበሳጨ ። ወርኃዐት ፡ ነፍሱ ፡ ለወልደ ፡ አዴር ፡ እንዲል ። ንጉሥ ፡ በእንጀራው ፡ የሚገባ ፡ የለም ። ስንኳንስ ፡ የተናገርከውን ፡ ያሰብከውን ፡ መርምሮ ፡ የሚያውቅ ፡ ነቢይ ፡ አለው ፡ ያ ፡ ነግሮት ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ አሉት ። ወዴት ፡ አለ ፡ አላቸው ። ዶታይን ፡ አሉት ፡ ሄዳችሁ ፡ አምጡ ፡ አላቸው ፡ ነቢዩም ፡ እንዲመጡበት ፡ አውቆ ፡ በገዛያች ፡ ሌሊት ፡ ተግቶ ፡ ሲጸልይ ፡ አድሯል ። ብላቴናው ፡ ልብም ፡ ለማፍሰስ ፡ ወጥቶ ፡ ሳለ ፡ አይቶ ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ከብበውናል ፡ አለው ። ክሥት ፡ ልበ ፡ ለገዛ ፡ ሕፃን ፡ ብሎ ፡ ጸለየ ። እስኪ ፡ ወጥተህ ፡ እያቸው ፡ አለው ። ወጥቶ ፡ ቢያይ ፡ መላእክት ፡ በእፍራስ ፡ እሳት ፡ በሠረገላ ፡ እሳት ፡ ሁነው ፡ ከዚያ ፡ ወደዚያ ፡ እርቀዋቸዋል ። ፊታቸውን ፡ ወደዚያ ፡ ጀርባቸውን ፡ ወደዚህ ፡ አድ

2014 04 17

ርገው ፡ ቁመው ፡ አያቸው ። አሁንስ ፡ ሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ እነዚያን ፡ አርቀው ፡ ፊታቸውን ፡ ወደነዚያ ፡ መልሰው ፡ ጆርባቸውን ፡ ወደዚሁ ፡ አድርገው ፡ ቁመዋል ፡ አለው ። እነዚያ ፡ ምንም ፡ ባይኀዱን ፡ ጠላቶቻችን ፡ ናቸው ። እኒህ ፡ ጠባቆቻችን ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ሲነጋ ፡ አውርሞ ፡ ብሎ ፡ ጸለየባቸው ። ዓይን ፡ ሥጋቸውን ፡ ሠወራቸው ። እንድም ፡ ዓይነ ፡ ሕሊናቸውን ፡ ሠወራቸው ። ወጥቶ ፡ ማንን ፡ ትሻላችኍ ፡ አላቸው ። ኤልሳዕን ፡ አሉት ። እከ ፡ ገዢ ፡ ማኀደሩ ። በታው ፡ ከዚሁ ፡ አይደለም ፡ ኑ ፡ ካለበት ፡ ልውሰዳችኍ ፡ ብሎ ፡ እየመራ ፡ ይዟቸው ፡ ሔዶ ፡ ከከተማው ፡ ሲደርሱ ፡ ከሥት ፡ ሎሙ ፡ ብሎ ፡ ጸለየባቸው ። ዓይነ ፡ ሥጋቸውን ፡ ግለጽላቸው ፡ አለ ። ከተማውን ፡ ዓይተው ፡ ደነገጡ ። አይዟችሁ ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፡ ለኢዮራም ፡ የወልደ ፡ አዴር ፡ መላእክተኞች ፡ ሊይዙኝ ፡ መጥተው ፡ ነበረ ። ይገርቸው ፡ መጥቻለኍ ፡ አለው ። ስጠኝ ፡ ልግደላቸው ፡ አለው ፡ አይሆንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምርኮኞች ፡ ናቸው ፡ በጦርህ ፡ እንደበት ፡ በፈረስህ ፡ አንገት ፡ ማርከህ ፡ ግደል ፡ ለነዚህስ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ አብልቶ ፡ አጠጥቶ ፡ ሰደቻቸዋል ። ፬ነገ ፡ ፮ ፡ ፰-፳፫ ።

፳ ፡ ጠዓሙ ፡ ወታእምሩ ፡ ከመ ፡ ኄር ፡ እግዚአብሔር ።

ላንተ ፡ ቢደረግልህ ፡ ለኛም ፡ ይደረግ ልናልን ፡ ትሉኛ ፡ እንደሆን ፡ አዎን ፡ ይደረግላችኋልና ፡ በልመና ፡ ቅመሱት ። የባሕርይ ፡ ቸር ፡ እንደሆነ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ (ጠዓሙ) ፡ በልመና ፡ ቅመሱት ። (ወተእምሩ) ፡ እንዲህም ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የባሕርይ ፡ ቸር ፡ እንደሆነ ፡ ታውቃላችኍ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፫ ።

ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘተወከለ ፡ ቦቱ ።

በሱ ፡ ያመነ ፡ ሕዝቅያስ ፡ እንድም ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

፱ ፡ ፍርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵልክሙ ፡ ቅዱሳን ።

ነቢያት ፡ ካህናት ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ ፍሩት ፡ አክብሩት ።

እስመ ፡ አልቦሙ ፡ ተፅናስ ፡ ለእለ ፡ ይፈርህዎ ።

በሚፈሩት ፡ በሚያመልኩት ፡ በነሕዝቅያስ ፡ ረኀበ ፡ ሥጋ ፡ ረኀበ ፡ ነፍስ ፡ የለባቸውምና ።

፲ ፡ ብዑላን ፡ ነድዩ ፡ ወርኀቡ ።

እነሰናክሬም ፡ ግን ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ጠፉ ። እንድም ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ገንዘባቸውን ፡ በንዲት ፡ ሰዓት ፡ አጥተው ፡ ተቸገሩ ፡ ተራቡ ።

ወእለሰ ፡ የኀሥሥዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኢተፀነሱ ፡ እምኵሉ ፡ ሠናያት ።

በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ የሚሹት ፡ እለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ግን ፡ ከበጎ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አጥተው ፡ አልተቸገሩም ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፶፫ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩-፯ ።



፲፩ ፡ ንዑ ፡ ደቂቅየ ፡ ወስምዑኒ ።

ነቢይ ፡ ነውና ፡ ሁሉን ፡ ልጆቼ ፡ ይላል ። ልጆቼ ፡ ኑ ፡ ምክሬን ፡ ትምርቴን ፡ ስሙኝ ።

ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምህረክሙ ።

አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስተምራችኍ ፡ ዘንድ ።

፲፪ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ሐይወ ።

በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ፀንቶ ፡ መኖርን ፡ የሚወድ ፡ ማነው ።

ወያፈቅር ፡ ይርአይ ፡ መዋዕለ ፡ ሠናያተ ።

በጎ ፡ በጎ ፡ ዘመናትን ። እንድም ፡ መዋዕለ ፡ ሠናያት ፡ ብለህ ፡ አናብበህ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸው ፡ ዘመናትን ፡ እንድም ፡ (መዋዕለ ፡ ሠናያን) ፡ በጎ ፡ በጎ ፡ ነገሥታት ፡ የነገሡባቸው ፡ ዘመናትን ፡ ሊያይ ፡ የሚወድ ፡ ማን ፡ ነው ። ፩ጥ ፡ ፱ ፡ ፳፮ ።

፲፫ ፡ ክላዕ ፡ ልሳነከ ፡ እምዕኩይ ።

እኔ ፡ አለኍ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ እንደ በትህን ፡ ንጉሥን ፡ ንግሥትን ፡ ጳጳሳትን ፡ ከማማት ፡ ከልክል ።

ወከናፍሪከኒ ፡ ከመ ፡ ኢይንብባ ፡ ጕህሉተ ።

እንደበቶችህ ፡ ከዳትን ፡ ሽንገላን ፡ እንዳይናገሩ ። ያዕ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ። ኢጥ ፡ ፫ ፡ ፲ ።

፲፬ ፡ ተገሐሥ ፡ እምዕኩይ ፡ ወግበር ፡ ሠናየ ።

ንጉሥን ፡ ንግሥትን ፡ ጳጳሳትን ፡ ከማማት ፡ ተከልከል ። (ግበር) ። ገብር ። ቀቅል ። ሲራ ፡ ፯ ፡ ፬ ።

እንድም ፡ (መኑ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ሐይወ) ፡ ሐያው ፡ ከመ ፡ መላእክትን ፡ የሚወድ ፡ ማን ፡ ነው ፡ (ወያፈቅር ፡ ይርአይ ፡ መዋዕለ ፡ ሠናያት) ፡ ክብር ፡ ሊያገኝ ፡ የሚወድድ ፡ ማን ፡ ነው ። ዘንተ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ሕይወት ፡ እንተ ፡ ሀየ ፡ ወይመጽእ ፡ ለከ ፡ መዋዕለ ፡ ማህል ፡ እንዲል ።

(ክላዕ ፡ ልሳነከ ፡ እምዕኩይ) ፡ እኔ ፡ አለኍ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ። ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አትበል ፡ (ወከናፍሪከኒ ፡ ከመ ፡ ኢይንብባ ፡ ጕሕሉተ) ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ ከማለት ፡ እንደበትህን ፡ ከልክል ። (ተገሐሥ ፡ እምዕኩይ) ፡ ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ አትበል ። (ወግበር ፡ ሠናየ) ፡ ክርስቶስን ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ። ወንጌልን ፡ ፍጽምት ፡ ሕግ ፡ በል ።

ኅሥሥ ፡ ሰላመ ፡ ወዴግኖ ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ።

ፍቅርን ፡ ሻት ፡ ተከተላት ። ኃጢአ ፡ ተሊው ፡ እንደምንድን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ኃጢአ ፡ መታረቅ ፡ ተሊው ፡ በዕርቁ ፡ መዕናት ። እንድም ፡ ኃጢአ ። እንተም ፡ ተው ፡ እንተም ፡ ተው ፡ ብሎ ፡ ማስታረቅ ። ተሊው ፡ አይሆንም ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ከነዳና ፡ እንዳይጣሉ ፡ መሸኘት ። እንድም ፡ ኀጢአ ፡ አስታርቁኝ ፡ ብሎ ፡ መታረቅ ። ተሊው ፡ የሚያስታርቅም ፡ ቢታጣ ፡ ያባት ፡ የናት ፡ ደመኛም ፡ ቢሆን ፡ ወንድ

2014 04 17

ሚን ፡ ብበድለው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ማ ረኝ ፡ ብሎ ፡ ከእግሩ ፡ ወድቆ ፡ መታ ረቅ ፡ ነው ። ሮሜ ፡ ፲፱ ፡ ፲፰ ። ፪ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፳፰ ። ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፲፱ ። ፩ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።

፲፭ ፡ እስመ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ጻድቃን ።

የእግዚአብሔር ፡ አዕይንት ፡ ምሕረቱ ፡ ወደ ፡ ወዳጆቹ ፡ ናቸውና ።

ወዕዝኒሁ ፡ ኀበ ፡ ስእለቶሙ ።

ዕዝኑ ፡ ፈቃዱ ፡ ዕዝኑ ፡ ምህረቱም ፡ ወደ ፡ ልመናቸው ፡ ነውና ፡ ኀሥሣ ፡ ለሰላም ፡ ሳለው ።

፲፯ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ እኩየ ።

ገጹስ ፡ ይላል ፡ ገጸ ፡ መዓቱ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ወደሚያደርጉ ፡ ነውና ፡ ተገሐሥ ፡ እምዕኩይ ፡ ላለው ። እንድም ፡ ክፉ ፡ ወደሚሠሩ ፡ ነው ። ምነው ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ ገጸ ፡ ምሕረት ፡ እንጂ ፡ ገጸ ፡ መዓት ፡ አለውን ፡ ቢሉ ፡ አዎን ፡ አ ለው ። ወበእንተ ፡ መዓቶሙ ፡ ተሰ ምዑ ፡ ሴጊዎን ፡ እንዲል ። ለመዓት ፡ እ ንጂ ፡ ለምሕረት ፡ የማይታዘዙ ፡ ቀጣ ዓን ፡ ይላቸዋል ፡ ከነገደ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካ ኤል ፡ ፲፪ ፡ ነገድ ፡ ናቸው ። በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ቤተ ፡ አንሳ ፡ ሰቃይ ፡ ቤተ ፡ አይጥ ፡ ቀራጭ ፡ እንዳሉ ፡ አን ድም ፡ አንዱ ፡ መልአክ ፡ ቅሉ ፡ መል አክ ፡ ምሕረት ፡ መልአክ ፡ መዓት ፡ ይሆናል ። ለሰብአ ፡ ትካት ፡ መልአከ ፡ መዓት ፡ ለኖኅ ፡ መልአከ ፡ ምሕረት ፡ ለሰብአ ፡ ሰዶም ፡ መልአከ ፡ መዓት ፡

ለሎጥ ፡ መልአከ ፡ ምሕረት ፡ ለሰናከ ሬም ፡ መልአከ ፡ መዓት ፡ ለሕዝቅያስ ፡ መልአከ ፡ ምሕረት ፡ እንደሆነ ። ዘፍ ፡ ፯ ፡ ፩–፳፬ ። ፲፱ ፡ ፩–፳፱ ። ፪ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፲፫–፴፯ ። ፲፱ ፡ ፩–፴፯ ፡ ኢሳ ፡ ፴፯ ፡ ፩–፳፱ ፡ ፴፯ ፡ ፩–፴፯ ።

ከመ ፡ ይሥሩ ፡ እምድር ፡ ዝክሮሙ ።

ስም ፡ አጠራራቸውን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እንድም ፡ ከሰው ፡ ለይቶ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ።

፲፯ ፡ ጸርሁ ፡ ጻድቃን ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ሰም ዖሙ ።

ኢሳይያስ ፡ ሕዝቅያስ ። እንድም ፡ ጻድ ቃን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መል ሰው ፡ ለመኑ ፡ እሱም ፡ ልመናቸውን ፡ ሰማቸው ።

ወእምኵሉ ፡ ምንዳቤሆሙ ፡ አድኃኖሙ ።

ምንዳቤሆሙ ፡ ከገኛቸው ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ ምንዳቤሁ ፡ እሱ ፡ ከመጣበ ቸው ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ አዳናቸው ። ያድኅኖሙ ፡ ያድናቸዋል ።

፲፰ ፡ ቅሩብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለየዋሃነ ፡ ልብ ።

እግዚአብሔር ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ላላ ቸው ፡ ሰዎች ፡ ቅርብ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ልመናቸውን ፡ ፈጥኖ ፡ ይሰማቸዋል ።

ወያድኅኖሙ ፡ ለትሑታን ፡ መንፈስ ።

ትሑት ፡ ሰብእና ፡ ያላቸውንም ፡ ማ ለት ፡ ሰውነታቸውንም ፡ እንደ ፡ ኢም ንት ፡ የሚያደርጉን ፡ ያድናቸዋል ። ወይሬእዩ ፡ ርእሶሙ ፡ ከመ ፡ መንፈስ ፡ እንተ ፡ ኃለፈት ፡ እንዲል ። ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ። ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፯ ።



፲፱ ፡ ብዙኅ ፡ ሕማሞሙ ፡ ለጻድቃን ።

ለጊዜው ፡ እከን ፡ የጻድቃን ፡ መከራ ቸው ፡ ብዙ ፡ ነው ። ግብ ፡ ፲፫ ፡ ፶ ።

ወእምኵሉ ፡ ያድኅኖሙ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከገኛቸው ፡ መ ከራ ፡ ሁሉ ፡ ያድናቸዋል ። ፪ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ፪ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

፳ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዓቅብ ፡ ኵሎ ፡ አዕፅምቲ ሆሙ ። ኤር ፡ ፳፫ ፡ ፱ ።

እግዚአብሔር ፡ ወገናቸውን ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቃል ።

ወኢይትቀጠቀጥ ፡ ፩ ፡ እምውስቴቶሙ ።

ከወገናቸው ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ አይጎ ዳም ፡ (አንድም) ፡ እግዚአብሔር ፡ የዓ ቅብ ፡ ኵሎ ፡ አዕፅምቲሆሙ ፡ አፅማ ቸውን ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቃል ። ወኢይ ትቀጠቀጥ ፡ ፩ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ከአ ፅማቸው ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ አይጠፋም ። አፅመ ፡ ኤልሳዕን ፡ እንደጠበቀ ፡ የሶ ርያና ፡ የሰማርያ ፡ ሰዎች ፡ ሲዋጉ ፡ ከእስራኤል ፡ አንዱ ፡ ተወግቶ ፡ ከኤ ልሳዕ ፡ መቃብር ፡ ወደቀ ። ዐፅሙ ፡ ቢነካው ፡ ተነሥቷል ። እንድም ፡ የሶ ርያ ፡ ሰዎች ፡ በእስራኤል ፡ በጠላት ነት ፡ ተነሱባቸው ። ለመዋጋት ፡ ሲ ሔዱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሞተባቸው ። ለመቅበር ፡ የማያደርሷቸው ፡ ቢሆን ፡ እንዳይገራቸው ፡ ከኤልሳዕ ፡ መቃብር ፡ ጭረው ፡ ቢቀብሩት ፡ አፈፍ ፡ ብሎ ፡ ተነሥቶ ፡ መግነዙን ፡ አጠርቅሞ ፡ በሰ ይፍ ፡ ሲገርፍ ፡ ውሏል ። ፪ነገ ፡ ፲፫ ። ፳ ፡ ፳፩ ።

፳፩ ፡ ሞቱ ፡ ለኃጥእ ፡ እኩይ ።

የኃጥእ ፡ ሰው ፡ ሞቱ ፡ ልዩ ፡ ነው ። ተፈልጠውማ ፡ አንድ ፡ አይደሉምን ፡ ቢሉ ፡ ተፈልጠውስ ፡ አንድ ፡ ነው ። ግብሩን ፡ ሲያይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኃጥእ ፡ ሰው ፡ ከዛሬ ፡ ነገ ። ከዘንድሮ ፡ ከርሞ ። ኃጢአቱን ፡ ለመምሕረ ፡ ንስሐዬ ፡ ነ ግሬ ፡ የወድያ ፡ ዓለም ፡ ቤቴን ፡ ሠርቼ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ ጋራ ፡ ታርቄ ፡ እሞታለሁ ፡ ሲል ። ንስሐ ፡ ሳይገባ ፡ ከፈጣሪው ፡ ሳይታረቅ ፡ ንግድም ፡ ቢሉ ፡ ዘመቻም ፡ ቢሉ ፡ በሔደበት ፡ ግልድው ፡ ብሎ ፡ ይቀራል ። ጻድቅ ፡ ግን ፡ ኃጢአቱን ፡ ለመምሕረ ፡ ንስሐው ፡ ነግሮ ፡ ከፈጣ ሪው ፡ ጋራ ፡ ታርቆ ፡ የወድያ ፡ ዓለም ፡ ቤቱን ፡ ሠርቶ ፡ ይሞታል ። እንድም ፡ ተፈልጠው ፡ ቅሉ ፡ ልዩ ፡ ነው ። የጻ ድቅ ፡ ነፍስ ፡ በመዓዛ ፡ ገነት ፡ በመዝ ሙረ ፡ ዳዊት ፡ በይባቤ ፡ መላእክት ፡ ትለያለች ። የኃጥእ ፡ ነፍስ ፡ ግን ፡ ዲያ ብሎስ ፡ ጽሉም ፡ ገጹን ፡ ሕሡም ፡ ራእዩን ፡ ይለውጥባታል ፡ ትደነግጣ ለች ። ደም ፡ ይደርቃል ፡ ነፍስ ፡ ትለ ያለችና ። እስመ ፡ ነፍስ ፡ ተኃድር ፡ በደም ፡ እንዲል ።

እለሰ ፡ ይጸልእዎ ፡ ለጻድቅ ፡ ይኔስሑ ።

ጻድቅን ፡ የሚጠሉ ፡ ሰዎች ፡ ኍሉ ፡ ይጸጸታሉ ።

፳፪ ፡ ይቤዙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነፍሶሙ ፡ ለአግብርቲሁ ።

እመ ፡ ያለበት ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ የወዳጆቹን ፡ ነፍስ ፡ በዳነ ፡ ጊዜ ፡ አ

2014 04 17

ንድም፡የጠላቶቼን፡ሰውነት፡ለወዳጆቼ፡ለውጥ፡አድርጎ፡የወዳጆቼን፡ሰውነት፡ባዳን፡ጊዜ። ወረሰይኩ፡ለከ፡ተውላጠከ፡ግብፀ፡ወሲዎንሃ፡ቤዛከ፡እንዲል።

ወኢይኀሥሡ፡ኵሎሙ፡እለ፡ይትዌከሉ፡ቦቱ።

በሱ፡ያመኑ፡ጉሉ፡ግን፡መከራ፡መጥቶባቸው፡በመከራው፡አያፍሩም። እንደ፡ገበሬ፡ሲጥር፡ሲግር፡ከርሞ፡በኅዳር፡በታኅሣሥ፡አዝመራውን፡ዙር፡እያየ፡ይህን፡ይህን፡ጨምረበት፡ቢሆን፡እንዲህ፡እንዲህ፡በሆን፡ነበር፡እያለ፡በቀረው፡ይጸጸታል፡እንጂ፡በደከመበት፡እንዳይጸጸት፡ጻድቃንም፡ብዙ፡መከራ፡ተቀብለው፡ጥቂት፡ክብር፡ያገኙ፡እንደሆን፡ከመከራው፡በጨመርንበት፡ብዙ፡ክብር፡ባገኘን፡ነበር፡ብለው፡ይጸጸታሉ፡እንጂ፡ባለፈው፡መከራ፡አይጸጸቱምና።

## መዝሙር፡፴፬።

፩፤ ፍትሖሙ፡እግዚኦ፡ለእለ፡ይገፍዑኒ።

ስለኤርምያስ፡ተናገርታል፡የጌታም፡ነገር፡አለበት። ከሥሩም፡አርእስት፡አንዱ፡ይህ፡ነው። ኤርምያስ፡ባምስቱ፡ነገሥታት፡የነበረ፡ነው፡እስራኤልን፡ቢመከራቸው፡ቢያስተምራቸው፡ምክሩን፡ትምርቱን፡የማይቀበሉት፡ሆን። የብረት፡ጥሩር፡ቀንበር፡አበጅቶ፡ወይፋፍን፡አስመጥቶ፡ጠምዶ፡ሒዱ፡ይላቸዋል፡ይጨነቃሉ፡ይጠበባሉ። እንዲህ፡አስጨንቆ፡አስጠብቦ፡የሚገዛ፡ንጉሥ፡ይመጣባችኋል። ይህን፡ሰብሮ፡መሔድ፡ይሆንላችኋልን፡ብሏቸዋል። ጳስኮር፡ሐናንያ፡የሚባሉ፡ከሀናት፡ሐሰት፡አሉ። ቅንባብላ፡የሚባል፡እንጨት፡አለ፡ያን፡አምጥተው፡ጥሩር፡ቀንበር፡አብጅተው፡ወይፋፍን፡ጠምደው፡ሒዱ፡ይሏችዋል። ሰብረውት፡ይሔዳሉ። እንዲህ፡እናጠፋዋለን፡ሲሉ፡ነው። ታሪኩን፡በውስጡ፡ይጨርሳል። ፲፱፡፲፱። ፰፡፮። ፳፯፡፩–፳፱። ፳፰፡፩–፲፯።

አቤቱ፡ሳልበድላቸው፡የሚበድሉኝ፡እስራኤልን፡አጥፋቸው።

ፅባዖሙ፡እግዚኦ፡ለእለ፡ይፀብኡኒ።

ሳልጣላቸው፡የሚጣሉኝ፡እስራኤልን፡አጥፋቸው። አንድም፡ግፍዖሙ፡ሳልበድላቸው፡የሚበድሉኝ፡አይሁድን፡አጥፋቸው። ፅብዖሙ፡ሳልጣላቸው፡የሚጣሉኝ፡አይሁድን፡አጥፋቸው። ከዚህ፡ግፍዖሙ፡ፅብዖሙ፡አለ። ከዚያ፡አባ፡ሥረይ፡ሎሙ፡አለ። ሉቃ፡፳፫፡፴፬። እንደምንድን፡ነው፡አይለያዩምን፡ቢሉ። አይለያዩም። ከዚህ፡የማይመለሱ፡



ወተካፈሉ፡አልባስየ፡ለርእሶሙ፤መዝሙር፡፳፩።



ወሠራዕከ፡ማእደ፡በቅድሜየ፤ ጽዋዕከኒ፡ጽኑዕ፡ወያረዊ፤ መዝሙር፡፳፪።

አሉና ፡ ግፍያሙ ፡ ዕብያሙ ፡ አለ ፡ ከዚያ ፡ የሚመለሱ ፡ አሉና ፡ አባ ፡ ሥረይ ፡ ሎሙ ፡ አለ ፡ እንድም ፡ አው ቀው ፡ የሐዱ ፡ አሉና ፡ ከዚህ ፡ ግፍ ያሙ ፡ አለ ፡ ሳያውቁ ፡ የሐዱ ፡ አሉ ና ፡ ከዚያ ፡ በዘኢየአምሩ ፡ አለ ፡ ከ ዚያ ፡ በዘኢየአምሩ ፡ ይገብሩ ፡ አለ ፡ እንድም ፡ በኢተነሳሒ ፡ ኃጥእ ፡ ሊጸ ልዩበት ፡ ይገባልና ፡ ከዚህ ፡ ግፍያሙ ፡ አለ ፡ ለተነሳሒ ፡ ኃጥእ ፡ ሊጸልዩለት ፡ ይገባልና ፡ ከዚያ ፡ አባ ፡ ሥረይ ፡ ሎሙ ፡ አለ ።

፳፪ ንግሕ ፡ ወልታ ፡ ወኲናተ ፡ ወተንሥኢ ፡ ውበተ ፡ ረዲኦትየ ።

ጋሻ ፡ ጦርህን ፡ ይዘህ ፡ እኔን ፡ ወደመ ርዳት ፡ ተነሣ ፡ ማለት ፡ የባሕርይ ፡ ሥልጣንህን ፡ ገልፀህ ፡ እርዳኝ ።

፫ ምላህ ፡ ስይፈከ ፡ ወዕግቶሙ ፡ ለእለ ፡ ሮዱኒ ።

ሰይፍህን ፡ መዝዘህ ፡ የከበቡኝን ፡ ከበ ባቸው ፡ ማለት ፡ የባሕርይ ፡ ሥልጣ ንህን ፡ ገልፀህ ፡ የከበቡኝን ፡ አጥፋ ቸው ።

በላ ፡ ለነፍስየ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ረዳኢኪ ።

ሰውነቴን ፡ ረዳትሽ ፡ እኔ ፡ ነኝና ፡ አይ ዞሽ ፡ በላት ።

፬ ለይትኃፈሩ ፡ ወይኅሥሩ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ የኃሥሥዋ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ ለማጥፋት ፡ የሚሿት ፡ ሁሉ ፡ ይፍሩ ፡ ይዋረዱ ።

ለይግብኡ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ ወይትኃፈሩ ፡ እለ ፡ መከሩ ፡ ዕኩየ ፡ ላዕሌየ ። ኢሳ ፡ ፵፩ ፡ ፲፩ ።

በኔ ፡ ክፉ ፡ ሊያመጡብኝ ፡ የመከሩ ብኝ ፡ ሁሉ ፡ እድጎ ፡ እነስ ፡ እድር ፡ እነስ ፡ ይሁኑ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ።

፭ ለይኩኑ ፡ ከመ ፡ ጸበል ፡ ዘቅድመ ፡ ገጸ ፡ ነፋስ ።

በነፋስ ፡ ፊት ፡ በነፋስ ፡ እንፃር ፡ እን ዳለ ፡ ትቢያ ፡ ይሁኑ ።

ወመልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለይሣቅዮሙ ።

የእግዚአብሔር ፡ መላክተኛ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ መከራ ፡ ያጽናባቸው ። እን ድም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መላክተኛ ፡ ናቡከደነፆር ፡ አገዛዙን ፡ ያፅናባቸው ። ምንም ፡ ባያመልከው ፡ እጥፋ ፡ ያለ ውን ፡ ያጠፋልና ፡ ኢዮብ ፡ ገብርየ ፡ ዳዊት ፡ ገብርየ ፡ እልእከ ፡ ኅበ ፡ ናቡ ከደነፆር ፡ ገብርየ ፡ እንዲል ።

፮ ለትኩን ፡ ፍኖቶሙ ፡ ጻሕፀ ፡ ወጽልመተ ።

ጎዳናቸው ፡ ዳሕፅ ፡ ጨለማ ፡ ትሑን ባቸው ፡ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ በሐ ምሌ ፡ ባሥራ ፡ እራት ፡ ተማርከው ፡ በነሐሴ ፡ በዘጠኝ ፡ ወርደዋል ፡ ይህስ ፡ አይደለም ፡ በሀገራቸው ፡ ነሐሴ ፡ በጋ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በጥር ፡ በአሥራ ፡ አራት ፡ ተማርከው ፡ በየካቲት ፡ ወርደዋልና ፡ የተከበቡበትን ፡ ሲያይ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እንድም ፡ በዳጥ ፡ በጨለማ ፡ ትሁን ፡ ማለት ፡ በጨለማ ፡ ላይ ፡ የዛፍ ፡ የገ ደል ፡ ጥላ ፡ ሲጨመር ፡ ጨለማው ፡ እንዲፀና ፡ በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ ይፅናባቸው ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ኤር ፡ ፳፫ ፡ ፲፪ ።

ወመልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለይስድዶሙ ።

የእግዚአብሔር ፡ መላክተኛ ፡ ናቡከ

ደነፃር ፡ ከገሬቸው ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ሀገር ፡ ከሕይወት ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ከተድላ ፡ ወደ ፡ መከራ ፡ አስወጥቶ ፡ ይሰደዳ ቸው ። እንድም ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ይሰደዳቸው ። መላእክት ፡ ቲያቲያቸ ውን ፡ አብርተው ፡ በር ፡ ከፍተው ፡ ባሉ ፡ ከለዳውያን ፡ ወሚውውዖሙ ፡ ለዕብራውያን ፡ ብለው ፡ አስግርከዋ ቸዋልና ።

ጀ ፡ እስመ ፡ በከንቱ ፡ ኅብኡ ፡ ሊተ ፡ መስገርተ ፡ ሞተሞሙ ፡ ኤር ፡ ፲፰ ፡ ፳፪ ።

ሳልበድላቸው ፡ በግፍ ፡ ያጠፉኝ ፡ ዘን ድ ፡ ምክር ፡ መከረውብኛል ፡ ጦር ፡ ሸምቀውብኛልና ።

ወበከንቱ ፡ አመንዘዙዋ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ በግፍዕ ፡ አዕንተው ፡ ተጣ ዓት ፡ እንድም ፡ መርዘው ፡ ተከረው ፡ ተመለከቷት ።

፰ ፡ ለትምጽኦሙ ፡ መሥገርት ፡ እንተ ፡ ኢያአ ሙሩ ።

አሁን ፡ እኔ ፡ ምን ፡ አላለኹ ፡ ያላወ ቁት ፡ ፄዋዌ ፡ እንድም ፡ ያላወቁት ፡ መከራ ፡ ትምጣባቸው ።

መሥገርት ፡ እንተ ፡ ኃብኡ ።

ሠውረው ፡ የመከሯት ፡ ምክር ፡ ታጥ ፉቸው ።

ወይደቁ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ መሥገርት ።

በዚች ፡ በመከሯት ፡ ምክር ፡ ይጥፉ ።

፱ ፡ ነፍስየሰ ፡ ትትፌሣሕ ፡ በእግዚአብሔር ።

የኛ ፡ ሰውነት ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምና ፡ ደስ ፡ ይላታል ።

ወትትሌሣይ ፡ በአድኅኖቱ ፡ ኢላዩ ።

ነፍስነሰ ፡ ትትፌሣሕ ፡ ወትትሐሠይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወበአድኅኖቱ ፡ ብ ለሀ ፡ እቅና ፡ በትድግናው ፡ ደስ ፡ ይ ላታል ።

፲ ፡ ኵሉ ፡ አዕፅምትየ ፡ ይብሉከ ። እግዚኦ ፡ መኑ ፡ ከማከ ።

አቤቱ ፡ ወገኖቼ ፡ እንድም ፡ ሕዋሳቴ ፡ ሁሉ ፡ ጠላቶቼን ፡ የሚጎዳ ፡ ወዳጆቼን ፡ የሚ ጠቅም ። እድንኝ ፡ እርዳኝ ፡ ብሉት ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኖ ፡ የሚያድን ፡ የሚረዳ ፡ ማን ፡ ነው ፡ ይሉሃል ።

ታድኅኖ ፡ ለነዳይ ፡ እምእደ ፡ ዘይትኄየሎ ።

ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ኤርም ያስን ፡ ከኤልያቄም ፡ እጅ ፡ እንድም ፡ ግናቸውንም ፡ ድኃ ፡ ከጠላት ፡ እጅ ፡ ታድነዋለሀ ።

ለነዳይ ፡ ወለምስኪን ፡ እምእደ ፡ ዘይመሥጦ ።

ወለምስኪን ፡ ለማለት ፡ ደግሞታል ። ችግረኛ ፡ ጦም ፡ አዳረውንም ፡ ከሚ ቀማው ፡ እጅ ።

ተንሥኡ ፡ ላዕሌየ ፡ ሰማዕተ ፡ ዓመፃ ።

የሐሰት ፡ ምስክሮች ፡ በጠላትነት ፡ ተነ ሱብኝ ።

ወዘኢየአምር ፡ ነበቡ ፡ ላዕሌየ ።

በኔ ፡ ላይም ፡ የማላውቀውን ፡ ነገር ፡ ተናገሩብኝ ። እስራኤል ፡ ቢመከራ ቸው ፡ ቢያስተምራቸው ፡ ምክሩን ፡ ትምርቱን ፡ እንቀበልም ፡ ብለዋል ። ምክሬን ፡ ትምርቴን ፡ ተቀብለውኝ ፡



ቢሆን ፡ የመጣውንም ፡ መከራ ፡ አብሬ ፡ በተቀበልኊ ፡ ነበር ፡ ምክሬን ፡ ትም ርቴን ፡ ካልተቀበሉኝማ ፡ ከመከራ ቸው ፡ ምን ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ አገር ፡ ሲሔድ ፡ በርኛው ፡ ሰርዋስ ፡ ይለዋል ። ወደ ፡ ት ፡ ትሔዳለህ ፡ አለው ። ወደእናቴ ፡ አገር ፡ አለው ። አትሔ ድም ፡ ሐሰተኛ ፡ ነቢይ ። የተናገር ኸው ፡ ቢቀርብህ ፡ ባቢሎን ፡ ወርደህ ፡ ወበት ፡ ገብተህ ፡ ናቡከደነፆርን ፡ ልታ መጣ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ገርፎ ፡ አሳልፎ ፡ ናታን ፡ ከሚባል ፡ ጸሐፊ ፡ ቤት ፡ አሥ ሮታል ። ወተዓሥረ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ናታን ፡ ጸሐፊ ፡ እንዲል ። ኤር ፡ ፳ ፡ ፩ ። ፴፪ ፡ ፪ ። ፴፯ ፡ ፲፫—፲፭ ።

፲፪ ፡ ፈደዩኒ ፡ እኪተ ፡ ህየንተ ፡ ሠናይት ። ሲራ ፡ ፲፪ ፡ ፩ ።

በጎ ፡ ስላደረግኊላቸው ፡ ፈንታ ፡ የክፉ ፡ ብድራት ፡ መለሱልኝ ። መዝ ፡ ፴፯ ፡ ፳ ። ፻፰ ፡ ፭ ። ኤር ፡ ፲፰ ፡ ፳ ።

ወኀጕለ ፡ ውሉደ ፡ ለነፍስየ ።

ለሰውነቴ ፡ ባሮክ ፡ አቤሜሌክን ፡ አሳ ጧት ። እንድም ፡ መጻሕፍትን ፡ አሳ ጧት ፡ ልጅ ፡ ከባቴ ፡ ባሕርይ ፡ እንዲገኝ ፡ ምስጢርም ፡ ከባሕርያቸው ፡ ይነቃልና ፡ ኤርምያስ ፡ ከእሥር ፡ ቤት ፡ ሳለ ፡ ባ ሮክ ፡ ሊጠይቀው ፡ መጣ ። ምስጢር ፡ ተገልጾልኛልና ፡ ቀለም ፡ በጥብጠህ ፡ ብራና ፡ ዳምጠህ ፡ ብርዕ ፡ ቀርፀህ ፡ አ ምጣልኝ ፡ አለው ። አምጥቶ ፡ ሰጠው ፡ ጽፎ ፡ ወስደህ ፡ ለካህናቱ ፡ ለሕዝቡ ፡ ስጣቸው ፡ አለው ። ፍኖተ ፡ ንግርዶ ፡ ይለዋል ። ከሀናቱ ፡ ሕዝቡ ፡ የሚገኙ በት ፡ ቦታ ፡ አለ ። ከዚያ ፡ ወስዶ ፡ ሰጥ ቷቸዋል ፡ አንተ ፡ ተመለስ ፡ ለንጉሡ ፡ እኛ ፡ እንሰጥልሃለን ፡ አንተ ፡ የሰጠ ኸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያጣላናል ። መም ርሀንም ፡ መከራ ፡ ያጸናበታል ፡ ብለው ፡ ሰደዱት ። ፀአተ ፡ ከረምት ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እሳት ፡ ሲሞቅ ፡ ቢጋ ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እሳት ፡ ያመልክ ፡ ነበርና ፡ ሳያሻርት ፡ ከኤርምያስ ፡ የ መጣ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሰጡት ። ወእን በበ ፡ ይሁዲ ፡ ፩ደ ፡ ገጸ ፡ እው ፡ ፪ተ ። እው ፡ ፫ተ ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ ሁለት ፡ ገጽ ፡ ሦስት ፡ ገጽ ፡ አንድ ፡ ቅጠል ፡ ሁለት ፡ ቅጠል ፡ ሦስት ፡ ቅጠል ፡ ተመልከቶ ፡ ኤርምያስ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚናገረው ፡ መከራችንን ፡ ነው ፡ እንጂ ። እንድ ፡ ቀን ፡ ስንኳ ፡ ተድላችንን ፡ ተናግሮ ፡ አያ ውቅም ፡ ብሎ ፡ በመቀስ ፡ እያረፍሀ ፡ እያረፍሀ ፡ ከእሳት ፡ አግባው ፡ (ጣለው) ፡ አለው ። እያረረ ፡ ከእሳት ፡ አግብቶ ታል ። ወመተርዋ ፡ በመጥባሕተ ፡ ጸ ሐፊ ፡ ወሐልቀት ፡ በምንዳድ ፡ እን ዲል ። ይኸውም ፡ አልቀረ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተገልጦለት ፡ ጽፎታል ። እንድም ፡ (ወኀጕለ ፡ ውሉደ ፡ ለነፍስየ) ፡ ባሮክ ፡ አቤሜሌክ ፡ ሰውነቴን ፡ አጧት ። ኤር ፡ ፴፮ ፡ ፩-፴፪ ።

፲፫ ፡ ወአንሰ ፡ ሶበ ፡ አሥርሐኒ ፡ ለበስኩ ፡ ሠቀ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ኤርምያስ ፡ ይህ ፡ የምትና ገረው ፡ ነገር ፡ እንዳያገኘን ፡ እዘንልን ፡ ጸልይልን ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ማቅ ፡ ምን

2014 04 17

ጣፍ ፡ ለብሼ ፡ እዘንጉላቸው ፡ ጸለይ ጉላቸው ።

ወአሕመምክዋ ፡ በጾም ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ በቀጠና ፡ በስልት ፡ አደከ ምኋት ።

ወረሰይክዎ ፡ ሠቅ ፡ ለልብስየ ።

ልመናዩም ፡ እኔን ፡ ወደ ፡ መጥቀም ፡ ተመለሰልኝ ፡ ጸሎት ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ አ ይቀርምና ።

ናቡከ ፡ ደነፆር ፡ ታሥሮ ፡ አገኘው ። ምን ፡ ሁኖ ፡ ነው ፡ የታሠረ ፡ አላቸው ፡ ያንተን ፡ ተስፋ ፡ ቢናገር ፡ አሥረውት ፡ ይኖራል ፡ አሉት ። ይህስ ፡ ለኔ ፡ ይሆ ናል ፡ ብሎ ፡ እከብር ፡ አኑሮታል ። እን ድም ፡ እኔን ፡ ወደ ፡ መጉዳት ፡ ተመ ለሰ ፡ ነፍጥ ፡ ቢያጓር ፡ የጌታውን ፡ ጐ ድን ፡ ይሰብር ፡ እንዲሉ ።

ከመ ፡ ዘለእጋውየ ፡ ወለቢፅየ ፡ ከማሁ ፡ እድሎኩ ።

ለወንድሞቼ ፡ ለባልንጀሮቼ ፡ እንዳ ዝን ፡ እንድቆረቆር ፡ እዘንሁላቸው ፡ ጸለይሁላቸው ። እንድም ፡ ወንድሞቼ ፡ ባልንጀሮቼ ፡ እንደ ፡ መሆናቸው ፡ ለሁ ለቱ ፡ ነገድ ፡ ላሥሩ ፡ ነገድ ፡ ጸለይሁላ ቸው ። እንድም ፡ ለሁለቱ ፡ ነገድ ፡ እን ዳዝን ፡ ላሥሩ ፡ ነገድ ፡ እዘንሁላቸው ።

ከመ ፡ ዘይላሁ ፡ ወይቴክዝ ፡ ከማሁ ፡ አትሐትኩ ፡ ርእስየ ። ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፴፮ ። ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭ ።

ገንዘቡ ፡ ጠፍቶበት ፡ ወገኑ ፡ ሞቶበት ፡ እንደሚያዝን ፡ ራሴን ፡ ዘለፍ ፡ አድርጌ ፡ እዘንጉላቸው ።

፲፭ ፡ ተጋብኡ ፡ ላዕሌየ ፡ ወተፈሥሑ ።

ባቢሎናውያን ፡ በኔ ፡ ተሰበሰቡ ። በመ ሰብሰባቸውም ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ኢሮ ፡ ፲፮ ፡ ፲ ።

ተግህሩ ፡ ይቅሥፉኒ ፡ ወኢያእመርኩ ።

ይገርፉኝ ፡ ዘንድ ፡ መከሩብኝ ። የምግ ረፍበትን ፡ ዕዳዬን ፡ አላወቅጉትም ። ኤር ፡ ፲፰ ፡ ፳፫ ። እንድም ፡ ግርፋቱን ፡ አላ ወቅሁትም ። ከሚጠት ፡ በኋላ ፡ ደን ጊያ ፡ ተለውጣ ፡ ተገርፋለታለችና ።

ተሰብሩ ፡ ወኢደንገጹ ።

ድል ፡ ተነሡ ። ንስሐ ፡ አልገቡም ። (ወ ተሰብሩ) ፡ ነገሥት ፡ ሰዶም ፡ ወገሞራ ፡ በቃለ ፡ ብእሲት ፡ ስብርት ፡ እንዲል ።

፲፮ ፡ ፈተኑኒ ፡ ወተሣለቁ ፡ ላዕሌየ ፡ ወሰሐቁኒ ።

ኤርምያስ ፡ የምትናገረው ፡ ነገር ፡ እን ዳያገኝን ፡ እዘንልን ፡ ብለው ፡ ፈተኑኝ ። ፈተኑኝና ፡ ይህ ፡ ሞኝ ፡ ተላላ ፡ አሁን ፡ እስራኤል ፡ ከክፋት ፡ ወደ ፡ በጐነት ፡ ይመለሳሉ ፡ ብሎ ፡ ነውን ፡ ብለው ፡ ፈ ጽመው ፡ ዘበቱብኝ ። ኤር ፡ ፳ ፡ ፯ ።

እንድም ፡ (ተንሥኡ ፡ ላዕሌየ ፡ ሰማ ዕተ ፡ ዓመፃ) ፡ የሐሰት ፡ ምስክሮች ፡ አይሁድ ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡብኝ ። (ወዘኢ.የአምር) ፡ የሌለብኝን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አሉኝ ። (ፈደዩኒ) ፡ ኀብስት ፡ አበርክቼ ፡ ስለ ፡ መግብኋቸው ፡ ድውይ ፡ ስለ ፡ ፈወስጉላቸው ፡ ሙት ፡ ስላነሣ ጉላቸው ፡ ፈንታ ፡ የክፉ ፡ ብድራት ፡ መለሱብኝ ። (ወአኅጥእዋ) ፡ ለሰው ነቴ ፡ ሐዋርያትን ፡ አሳጡት ። እንድም ፡ (ወኃጥእዋ) ፡ ሰውነቴን ፡ ሐዋርያት ፡ አጡት ። (ወአንሰ) ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አን ሥእ ፡ ኃይለከ ፡ ፈኑ ፡ እዴከ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ሆንጉላቸው ፡ ሥጋ ፡ ለ ብስጉላቸው ። በለበሰው ፡ ሥጋ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ተቀብኋልና ፡ ሠቅ ፡ አለው ፡ (ወአሕመምክዋ) ፡ ወጸመ ፡ ፵ ፡ መዓ ልተ ፡ ወ፵ ፡ ሌሊተ ፡ ይለዋልና ። (ወጸ ሎትየኒ) ፡ ልመናዩም ፡ ምዕመናንን ፡ ወደ ፡ መጥቀም ፡ ተመለሰልኝ ። (ከመ ፡ ዘለእኃውየ) ፡ ለሐዋርያት ፡ ለሰብአ ፡ አርድእት ፡ እንዳዝን ፡ እዘንጉላቸው ። (ከመ ፡ ዘይላሁ) ፡ ሰቢረ ፡ ከሳድን ፡ አድ ርጌ ፡ እዘንጉላቸው ፡ (ተጋብኡ) ፡ አይ ሁድ ፡ ግን ፡ በኔ ፡ ተሰበሰቡ ፡ በመሰብሰ ባቸውም ፡ ደስ ፡ አላቸው ። (ተማከሩ) ፡ ይገርፉኝ ፡ ዘንድ ፡ መከሩብኝ ፡ የምግ ረፍበትን ፡ ሥራ ፡ አልሠራሁም ። (ተሰ ብሩኒ) ፡ በፈለገ ፡ እርገ ፡ መነሃ ፡ ተኃ ሥሡ ፡ ቢላቸው ፡ ኢየሱስሃ ፡ ናዝራዊ ፡ ነኃሥሥ ፡ አሉት ። እነ ፡ ውእቱ ፡ ቢላ ቸው ፡ የንግልሊት ፡ ወድቀዋል ። ወ ሶበ ፡ ይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ እነ ፡ ውእቱ ፡ ገብኡ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ ወ ወድቁ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ እንዲል ፡ ዮሐ ፡ ፲፰ ፡ ፬ ፡ -፰ ። (ወኢ.ደንገጹ.) ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ቢሆን ፡ አይደለምን ፡ ብለው ፡ ንስሐ ፡ አልገቡም ፡ (ፈተኑኒ) ፡ ፊቴን ፡ በሻሽ ፡ ሸፍነው ፡ ተነበይ ፡ ለነ ፡ ክርስ ቶስ ፡ መኑ ፡ ጸፍአከ ፡ እያሉ ፡ ፈተኑኝ ፡ ፈተኑኝና ፡ ፈጽመው ፡ ዘበቱብኝ ።





ወሐቀዩ ፡ ስነኒሆሙ ፡ ላዕሌየ ።

ጥርሳቸውን ፡ አፋጩብኝ ። ማለት ፡ አፅንተው ፡ ተጣሉኝ ። እንድም ፡ የባ ዕድ ፡ ሥራ ፡ ሠሩብኝ ። ኢዮ ፡ ፲፯ ፡ ፱ ።

፲፯ ፡ እግዚኦ ፡ ማዕዜኑ ፡ ትሬእይ ፡ ሊተ ።

ብሉዩን ፡ ይዞ ፡ ይሐዳል ፡ አቤቱ ፡ የም ትፈርድልኝ ፡ መቼ ፡ ነው ። መቼ ፡ ትፈ ርድልኛለህ ።

አድኅና ፡ ለነፍስየ ፡ እምእከየ ፡ ምግባሮሙ ።

እምዕኩይ ፡ ምግባሮሙ ፡ ይላል ፡ ሰው ነቴን ፡ ከክፉ ፡ ሥራቸው ፡ አድናት ።

ወእምአናብስት ፡ ለብሕቴትየ ።

ብቸኝነቴን ፡ አይተህ ። እንድም ፡ ብቸ ኝነቴን ፡ ከኤልያቄም ፡ ከኢኮንያን ፡ እጅ ፡ አድናት ።

፲፰ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ በውስተ ፡ ማኅበር ፡ ዐቢይ ።

አቤቱ ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ እገ ዛልሃለሁ ። ወእሴብሐከ ፡ በውስተ ፡ ሕዝብ ፡ ክቡድ ። በብዙ ፡ ጉባኤ ፡ አመ ሰግንሃለሁ ፡ ወመጽአ ፡ ክቡድ ፡ እን በጣ ፡ እንዲል ።

፲፱ ፡ ወኢይትፈሥሑ ፡ ላዕሌየ ፡ እለ ፡ ይጻልዑኒ ፡ በዓመፃ ።

ሳልጸላቸው ፡ በግፍ ፡ የሚጸሉኝ ፡ ደስ ፡ አይበላቸው ።

እለ ፡ ይፃረሩኒ ፡ በከንቱ ፡ ወይትቃፀቡኒ ፡ በአዕይንቲሆሙ ።

ሳልጸላቸው ፡ የሚጸሉኝ ፡ ባይናቸው ፡ የሚጠቃቀሱብኝ ፡ ሰዎች ፡ ደስ ፡ አይበ

ላቸው ፡ እንደም ፡ ጥቂውን ፡ ምግም ፡
ሳልጸላቸው ፡ የሚጠሉኝ ፡ ሰዎች ፡ ባ
ይናቸው ፡ ይጠቃቀሱብኛል ።
፳ ፡ እስመ ፡ ሊተሰ ፡ ሰላመ ፡ ይትናገሩኒ ።
ለኔማ ፡ እኮን ፡ ለጊዜው ፡ እንደነትን ፡
ፍቅርን ፡ ያነጋግሩኛል ።
ወያመክሩ ፡ በቍጥር ፡ ያመንስዉኒ ።
ኋላ ፡ ግን ፡ በጠጢ ፡ በሳንባ ፡ ጠለፍ ፡
በቴጠርጣሬ ፡ ጠፍር ፡ ሊገርፉኝ ፡ ይ
መክሩብኛል ። እንድም ፡ እንጀተ ፡
ፅኑ ፡ ናቸው ።
፳፩ ፡ ወአብቀወ ፡ አፉሆሙ ፡ ላዕሌየ ፡ መዝ ፡ ፳፩ ፡ ፲፫ ።
ነገራቸውን ፡ አበዙብኝ ።
ወይቤሉ ፡ እንቋዕ ፡ እንቋዕ ፡ ርእየት ፡ አዕይንቲነ ።
እሰይ ፡ እሰይ ፡ እሰ ፡ እሰ ፡ ኢርምያስን ፡
አይመስሉ ፡ መስሉ ፡ አይሆኑ ፡ ሁኖ ፡
ባይናችን ፡ ዓየነው ፡ ይላሉ ።
፳፪ ፡ ርኢ ፡ እግዚኦ ፡ ወኢትርምም ። ዕን ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።
አቤቱ ፡ ሥራቸውን ፡ አይ ፡ ተመል
ከት ። ዝም ፡ አትበል ፡ አይ ፡ ተመል
ከት ፡ እንጂ ፡ ዝም ፡ አትበል ።
እግዚኦ ፡ ኢትርሐቅ ፡ እምኔየ ።
አቤቱ ፡ ከኔ ፡ በረድኤት ፡ አትራቅ ።
፳፫ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ወአፅምዕ ፡ ፍትሕየ ።
አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተንሥ
ተህ ፡ ፍረድብኝ ፡ ንጉሥ ፡ ቢገሥም ፡
ቢያስከስም ፡ ነገሩን ፡ ሰምቶ ፡ ነውና ፡
እንድም ፡ ልመናዬን ፡ ፍረድልኝ ፡
እስ ። የሚያስፈርድ ፡ ስለሆነ ፡ በነገረ ፡
ግበበት ።
አምላኪየ ፡ ወእግዚእየ ፡ ውስተ ፡ ቅስትየ ።
እግዚአ ፡ አምላኪየ ፡ ወእግዚእየ ፡ ብ
ለህ ፡ ግጠም ፡ አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ጌታ
ዬ ፡ በፀቤ ፡ በክርክሬ ፡ ጊዜ ፡ በሥራ ፡
በመፍረድ ፡ ተንሥተህ ፡ ፍረድልኝ ።
፳፬ ፡ ፍታሕ ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ በከመ ፡ ጽድቅከ ። መዝ ፡ ፯ ፡ ፰ ።
አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እኔ ፡ እውነተኛ ፡
ነኝና ፡ እንደ ፡ እውነተኛነቴ ፡ ፍረድ
ልኝ ፡ አለልህም ። አንተ ፡ እውነተኛ ፡
ነህና ፡ እንደ ፡ ውነተኛነትህ ፡ ፍረድ
ልኝ ፡ እንጂ ።
ወኢይትፈሥሑ ፡ ላዕሌየ ።
በኔ ፡ መከራ ፡ ደስ ፡ አይበላቸው ።
፳፭ ፡ ወኢይበሉ ፡ በልቦሙ ፡ ሰናይ ፡ ሰናይ ፡ ለነፍስነ ።
በልባቸው ፡ አስበው ፡ በቃላቸው ፡
ኢርምያስን ፡ አይመስሉ ፡ መስሉ ፡
አይሆኑ ፡ ሁኖ ፡ አየነው ፡ አይበሉ ፡
እንዳሉ ፡ አይቅሩ ።
ወኢይበሉ ፡ ውኅጥናሁ ።
እንደዋጥሁት ፡ ዋጥነው ፡ እንደ ፡ እን
ቀት ፡ ጠግነው ፡ አይበሉ ፡ እንዳሉ ፡
አይቅሩ ።
፳፮ ፡ ለይትኃፈሩ ፡ ወይትኀፈሩ ፡ እለ ፡ ይትፈሥሑ ፡ በሕማምየ ።
በኔ ፡ መከራ ፡ ደስ ፡ የሚላቸው ፡ ይፈ
ሩ ፡ ይዋረዱ ።



ወይልበሱ ፡ ኃፍረተ ፡ ወኃሣረ ፡ እለ ፡ ያዐብዩ ፡ አፉሆሙ ፡ ላዕሌየ ። ኢዮ ፡ ፰ ፡ ፳፪ ።
ነገራቸውን ፡ የሚያበዙብኝ ፡ ሁሉ ፡
ሐፍረትን ፡ ተዋርዶን ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡
ይጐናጸፉ ።
፳፯ ፡ ለይትፈሥሑ ፡ ወይትሐሠዩ ፡ እለ ፡ ይፈቅ
ዱ ፡ ለጽድቅየ ።
የኔን ፡ ድኅነት ፡ እንድም ፡ የኔን ፡ ትም
ርት ፡ ምክር ፡ የሚወዱ ፡ የሚሰሙ ፡
ግን ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ።
ወይበሉ ፡ በዘኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ።
በሰባቱ ፡ ባሥራ ፡ ሁለቱ ፡ በሐያ ፡ አ
ራቱ ፡ ጊዜያት ፡ እግዚአብሔር ፡ ገናና ፡
አምላክ ፡ ነው ፡ ይበሉ ።
እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ሰላመ ፡ ገብርከ ።
የኔን ፡ የባሪህን ፡ ድኅነት ፡ የሚወድ
ዱ ፡ ጉሉ ።
፳፰ ። ልሳንየ ፡ ያነብብ ፡ ጽድቀከ ። ወኵሎ ፡ አ
ሚረ ፡ ስብሐቲከ ።
ልሳንየ ፡ ያነብብ ፡ ጽድቀከ ፡ ወስብሐ
ቲከ ፡ ሁሉ ፡ አሚረ ፡ ብለህ ፡ አቅና ፡
አንደበቴ ፡ ይቅርታህን ፡ ቸርነትህን ፡
ጌትነትህን ፡ ተአምራትህን ፡ ዘወትር ፡
ይናገራል ።

## መዝሙር ፡ ፴፭ ።

፩ ፡ ይነብብ ፡ ኃጥእ ፡ በዘያስሕት ፡ ርእሶ ።
በሳኦል ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግር
ታል ። ሳኦል ፡ እኔን ፡ ገድሎ ፡ ራሱን ፡
ሲሉት ፡ በሚያሰኝ ፡ ገንዘብ ፡ ያሰኝ ፡ ዘ
ንድ ፡ የሚያሰኝበትን ፡ ነገር ፡ ይናገራ
ል ። እንድም ፡ በዘያስሕት ፡ ይላል ።
እኔን ፡ ገድሎ ፡ ራሱን ፡ ከሥጋት ፡ ያ
ሳርፍ ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ በመንግሥ
ት ፡ ያሳርፍ ፡ ዘንድ ፡ በሚያሳርፍ ፡ ገን
ዘብ ፡ የሚያሳርፍበትን ፡ ነገር ፡ ይናገ
ራል ።
ወአልቦ ፡ ፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅድመ ፡ አዕይ
ንቲሁ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።
ባይናቹ ፡ ፊት ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡
የለም ፡ ማለት ፡ ያይብኛል ፡ ይሰማብ
ኛል ፡ አይለውም ። ዘሁ ፡ ፰ ፡ ፲፭ ።
፪ ፡ እስመ ፡ ጸለሐዎ ፡ በልሳኑ ።
ባንደበቱ ፡ ከዳ ። ዶይቅ ፡ ወልድየ ፡ ቃ
ልከ ፡ ማኅዘኒ ፡ ልጄ ፡ ዳዊት ፡ እኔና ፡
አንተማ ፡ ምን ፡ ፀብ ፡ አለን ። ሰው ፡
ያጣላናል ፡ እንጂ ፡ ይለዋል ፡ ቢያገኘ
ው ፡ ላይተው ። ፩ሳሙ ፡ ፳፪ ፡ ፲፮ ።
የበ ፡ ትርጓሜ ፡ ኃጢአቱ ፡ ይጸልእ ።
ኃጢአቱ ፡ መቅሠፍት ፡ ይዞ ፡ በተገና
ኙቸው ፡ ጊዜ ፡ ይጸላታል ።
፫ ፡ ቃለ ፡ አፉሁ ፡ ዓመፃ ፡ ወጕሕሉት ።
ባንደበቱ ፡ የሚናገረው ፡ ነገር ፡ ጉሉ ፡
ዓመፃ ፡ ክዳት ፡ ሸንገላ ፡ ነው ። ዶይቅ ፡
ወልድየ ፡ ቃልከ ፡ ማኅዘኒ ፡ ማለቱን ፡
መናገር ፡ ነው ። ፩ሳሙ ፡ ፳፪ ፡ ፲፭ ።
ወኢፈቀደ ፡ ይለቡ ፡ ከመ ፡ ያሠኒ ።
በጎ ፡ ሥራ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ልቢ ፡ ሊ

ያደርግ ፡ አልወደደም ። እንድም ፡ ልቡ ፡ እንድም ፡ በልቡ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ልብ ፡ ሊያደርግ ፡ አ ልወደደም ። ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፫ ።

፱ ፡ ወሐለየ ፡ ዓመፃ ፡ በውስተ ፡ ምስካቡ ።

በመኝታው ፡ ዓመፅ ፡ የሚሆን ፡ ነገርን ፡ አሰበ ።

ወቆመ ፡ በፍኖት ፡ እንተ ፡ በዘ ፡ ኢኮነት ፡ ሠናይተ ።

በጎ ፡ ባይደለች ፡ ግብር ፡ ሁሉ ፡ ፀና ፡ ማለት ፡ በሰውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በጎ ፡ ባይደለ ፡ ሥራ ፡ ፀና ፡ ጎ ድን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወሐንቆ ፡ መ ንፈስ ፡ ርኩስ ፡ ይላል ። ዳዊት ፡ በተቀ ባ ፡ ጊዜ ፡ ሳኦልን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተለይቶት ፡ እንደ ፡ ወሎ ፡ ቃልቻ ፡ ዘ ፈን ፡ ጭዋታ ፡ የሚያስወድድ ፡ ጋኔን ፡ አደረበት ። ዳዊት ፡ በገና ፡ ሲደረድር ለት ፡ ይድን ፡ ነበረ ፡ ከዕለታት ፡ ባንዳ ቸው ፡ ጣለው ። ለዳዊት ፡ ነገሩት ፡ መ ጥቶ ፡ በገና ፡ ሲደረድር ፡ መጣሉን ፡ ተወው ። መንፈሰ ፡ ቅንዓት ፡ አደረ በት ። ከራስጌው ፡ የተሰቀለ ፡ ዘገር ፡ ነበር ፡ ያን ፡ አንሥቶ ፡ ሊወጋው ፡ ሲሰ ብቅ ፡ አይቶ ፡ አድኅነኒ ፡ እግዚእ ፡ እም ብእሲ ፡ እኩይ ፡ ብሎ ፡ መዝ ፡ ፻፴፱ ፡ ፩ ። ወለም ፡ ብሎ ፡ ወጥቶ ፡ ሔዷል ። ቢወ ረውረው ፡ ዳዊት ፡ ቁሞበት ፡ የነበረ ውን ፡ ግድግዳ ፡ ወጋው ፡ ወደርበያ ፡ ለኩናት ፡ መንገለ ፡ ዐረፍት ፡ እንዲል ። ዳዊት ፡ ከቤቱ ፡ ሔዶ ፡ ሜልኮልን ፡ ዛሬ ፡ አባትሽ ፡ ሊወጋኝ ፡ ኑሮ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ አወጣኝ ፡ አላት ። ምን ፡ እግዚ አብሔር ፡ አወጣኝ ፡ ትላለህ ፡ የኔ ፡ አ ባት ፡ ተኳር ፡ ነው ፡ የገመረውን ፡ ሳይ ጨርስ ፡ አይቀርም ፡ ሒድ ፡ ብላ ፡ በዝ ንግሬር ፡ አውጥታ ፡ ሰደዳ ፡ ጠበት ፡ አርዳ ፡ ደሙን ፡ በኩስኩስት ፡ ተቀብላ ፡ ከራስጌው ፡ አድርጋ ፡ ከብሸሸቱ ፡ አሥ ራ ፡ ቀምቀሞ ፡ ራስ ፡ አስመስላ ፡ አጎና ጽፋ ፡ አስተኝታ ፡ ተቀመጠች ፡ ሳኦል ፡ ዛሬ ፡ ዳዊትን ፡ ወግቼዋለሁ ፡ እጄን ፡ ሙ ቆኛል ፡ ሔዳችሁ ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ፡ ሔደው ፡ ዳዊት ፡ ወዴት ፡ ሔደ ፡ አለ ፡ አሏት ፡ ዛሬ ፡ ዳዊትን ፡ ያገኘውን ፡ አላ ውቅም ፡ ለጠላታችን ፡ አይስጠው ፡ አለቻቸው ፡ ምን ፡ ሆን ፡ አሏት ፡ ከና ንት ፡ ከተለየ ፡ ደም ፡ እየፋ ፡ ሊሞት ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ደሙን ፡ አስየቻቸው ፡ ሔ ደው ፡ እሱስ ፡ ደም ፡ ተፍቶ ፡ ሊሞት ፡ ነው ፡ አሉት ፡ እኔማ ፡ አልነገርኋች ሁምን ፡ የበላን ፡ ሆድ ፡ የወጋን ፡ ክንድ ፡ ያውቃል ፡ እንዲሉ ፡ እጄን ፡ ሙቆኛል ፡ ሔዳችሁ ፡ አምጡልኝ ፡ ከፊቴ ፡ ልጨ ርሰው ፡ አላቸው ። ቢሔዱ ፡ ምስል ፡ ሁኖ ፡ ተገኘ ፡ እሷን ፡ አስጠርቶ ፡ ለም ንት ፡ ከመገ ፡ አእቀዕከኒ ፡ ወለትየ ፡ ልጄ ፡ ምነው ፡ እንዲህ ፡ አደረግሽን ፡ አላት ፡ የዳዊትን ፡ ነገር ፡ ታውቃለህ ፡ ስንኳንስ ፡ ለኔ ፡ ለሴቲቱ ፡ ላንተ ፡ አይ ደፈር ፡ ስታደርጊ ፡ ይህን ፡ አድርጊ ፡ ያለዚያ ፡ ግን ፡ እጣላሻለሁ ፡ አለኝ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ ብላዋለች ፡ ፩ሳሙ ፡ ፲፯ ፡ ፲፫-፳፫ ። ፲፱ ፡ ፱-፲፯ ።



መኢይትሐከያ ፡ ለእኪት ።

ኃጢአትን ፡ ቢሠራት ፡ ቢሠራት ፡ አይ ሰለቻትም ፡ ይህች ፡ ቀረች ፡ እያለ ፡ ንቅስ ፡ እያደረገ ፡ ይሠራታል ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ በሰማይ ፡ ማህልከ ።

አቤቱ ፡ ይቅርታህ ፡ ሰማይን ፡ በመፍ ጠር ፡ ታወቀ ።

ወጽድቅከኒ ፡ እስከ ፡ ደመናት ።

ቸርነትህም ፡ ደመናትን ፡ በመፍጠር ፡ ታወቀ ። እንድም ፡ (እግዚኦ ፡ በሰማይ) ፡ መላእክትን ፡ (ወጽድቅከኒ) ፡ ደቂቀ ፡ አዳምን ፡ እንድም ፡ (እግዚኦ) ፡ ልዑ ላኑን ፡ (ወጽድቅከኒ) ፡ ትሑታኑን ፡ በመፍጠር ፡ ታወቀ ። እንድም ፡ ከሰ ማይ ፡ ከደመና ፡ የደረሰ ፡ እንጂ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ብዛቱን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፯ ፡ ወርትዕከኒ ፡ ከመ ፡ አድባረ ፡ እግዚአብሔር ።

ርትዓ ፡ አምላክነትህ ፡ ቅንነትህ ፡ ለሰ ው ፡ የምታደርገው ፡ ቸርነትህ ፡ ቀርዱ ፡ አራራት ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ ለዘ ላለሙ ፡ ለሰው ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራል ። ዘፍ ፡ ፰ ፡ ፬

ኰነኔከ ፡ ዕሙቅ ፡ ጥቅ ።

ፍርድህ ፡ እጅግ ፡ ጥልቅ ፡ ነው ። የሚ ያውቀው ፡ የለም ።

ሰብእ ፡ ወእንስሳ ፡ ታድኅን ፡ እግዚኦ ።

አድኃንከ ፡ ሲልነው ። ይኸውም ፡ ሊታ ወቅ ፡ ሰውን ፡ ከእንስሳ ፡ ለይተህ ፡ አዳ ንህ ፡ በኖኅ ፡ በሎጥ ፡ ጊዜ ፡ የተደረ ገውን ፡ መናገር ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ፯ ፡ ፩ ፡ ፳፱ ።

፲፱ ፡ ፩-፴፱ ። እንድም ፡ ታድኅን ። እን ግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ታድናለህ ።

፯ ፡ ወበከመ ፡ አብዛኅከ ፡ ምሕረተከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ቸርነትህን ፡ እንዳበዛህ ፡ መ ጠን ፡ ታድኅን ፡ እንድም ፡ እንደ ፡ ቸር ነትህ ፡ ብዛት ፡ መጠን ።

ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይትዌከሉ ፡ በታሕተ ፡ ክንፈከ ።

የአዳም ፡ ልጆች ፡ በክንፈ ፡ረድኤትህ ፡ አምነው ፡ ተጠብቀው ፡ ይኖራሉ ።

፰ ፡ ወይረውዩ ፡ እምጠለ ፡ ቤትከ ።

ጠለ ፡ እምቤትከ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ የተ ገኘውን ፡ ዐሥራት ፡ በኵራት ፡ ቀዳም ያቱን ፡ አግኝተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። እንድም ፡ ጠለ ፡ ረድኤትህን ፡ አግኝ ተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወትሰቅዮሙ ፡ እምፈለገ ፡ ትፍሥሕትከ ።

ከደስታህ ፡ ወንዝ ፡ ታጠጣቸዋለህ ፡ ማለት ፡ ደስ ፡ ታሰኛቸዋለህ ። ሐጌ ፡ ፩ ፡ ፮ ። ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲ ።

፱ ፡ እስመ ፡ እምኀቤከ ፡ ነቅዐ ፡ ሕይወት ።

ነቅዐ ፡ ብለህ ፡ አንቀጽ ፡ አድርገህ ፡ ሕይ ወት ፡ ካንተ ፡ ዘንድ ፡ ተገኝቷልና ። እ ንድም ፡ (አናብበህ) ፡ የሕይወት ፡ ምን ጭ ፡ ካንተ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ። እንድም ፡ (ሰሚ ፡ አድርገህ) ፡ ነቅዓ ፡ ሕይወት ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ሕይወት ፡ ካንተ ፡ ዘንድ ፡ ተገኝቷልና ፡ ጠለ ፡ ረድኤት ፡ ፈለገ ፡ ትፍሥሕትን ፡ ታጠጣቸዋለህ ። ሉቃ ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ ።

ወብርሃኑ ፡ ንጉሥ ፡ ብርሃን ፡ ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭ ።

በሰጠኸን ፡ ባይናችን ፡ ብርሃን ፡ ብር
ሃን ፡ ፀሐይን ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ ጸጎክን ፡
ብርሃን ፡ ፀሐይን ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ ጸጎ
ክን ፡ ብርሃን ፡ ያይናችንን ፡ ብርሃን ፡ ሰ
ጠኸን ፡ ስፋህ ፡ ማንሻ ፡ ፩ ፡ ፭ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ፡
፯ ፡ ፴፰ ።

፯ ፡ ልፋህ ፡ ልፋህ ፡ ምሕረትክ ፡ እግዚአ ፡ ላዕለ ፡
እለ ፡ የአምሩከ ።

በሰጠኸን ፡ ባይናችን ፡ ብርሃን ፡ ብር
ሃን ፡ ፀሐይን ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ ቅን ፡
ልቡና ፡ ላለን ፡ ለምናውቅህ ፡ ለኛ ፡ ይቅ
ርታህን ፡ ቸርነትህን ፡ ስጠን ።

ወጽድቀከኒ ፡ ለርቱዓነ ፡ ልብ ።

ቸርነትህንም ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ላለን
ለኛ ፡ አድርግልን ፡ እንድም ፡ (ደቂቀ
ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይትቄከሉ) ፡ ምዕ
መናን ፡ በመስቀል ፡ በስብከተ ፡ (ወን
ጌል ፡ ሐዋርያት ፡ አምነው ፡ ተጠብ
ቀው ፡ ይኖራሉ ። (ወይረውዩ) ፡ ከቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ የተገኘውን ፡ ሥጋህን ፡
ደምህን ፡ ተቀብለው ፡ ደስ ፡ ይላቸ
ዋል ። (ወትሠቅዮሙ) ፡ ልጅነትን ፡
ተሰጣቸዋለህ ፡ (እስመ ፡ እምኀቤከ) ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ካንተ ፡ ተገኝቷልና ።
እንድም ፡ የሕይወት ፡ መገኛ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ካንተ ፡ ተገኝቷልና ።
እንድም ፡ ሰሚ ፡ አድርገህ ፡ ነቅዓ ፡ ሕይ
ወት ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱ
ስ ፡ ካንተ ፡ ተገኝቷልና ። (በብርሃንከ) ፡
በልጅህ ፡ ልጅነትን ፡ እናገኝ ፡ ዘንድ ፡
ጸጎክን ፡ ልጅነትን ፡ ሰጠኸን ፡ ስፋህ ፡ ማ
ንሻ ፡ እንድም ፡ በልጅህ ፡ ልጅነትን ፡
እናገኝ ፡ ዘንድ ፡ (ስፋህ) ፡ ለምናውቅህ ፡
ለኛ ፡ ልጅህን ፡ በሥጋ ፡ ስጠን ፡ በጎ
ብሩ ፡ ምሕረት ፡ አለው ፡ (ጽድቀከ) ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ላለ
ን ፡ ለኛ ፡ ስጠን ።

፲፩ ፡ ኢይምጽአኒ ፡ እግረ ፡ ትዕቢት ።

ሳኦል ፡ አይምጣብኝ ።

ወእደ ፡ ኃጥእ ፡ ኢይሁክኒ

ሳኦል ፡ አያውከኝ ፡ እግር ፡ እጅ ፡ አለው ፡
በእግሩ ፡ ሒዶ ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ነውና ፡
የምያጠፋ ፡ ሀየ ፡ ይወድቁ ፡ ማንሻ ፡
እንድም ፡ እግረ ፡ ትዕቢት ፡ እደ ፡ ኃጥእ ፡
ሳኦል ፡ እንዳይመጣብኝ ፡ እንዳያው
ከኝ ።

፲፪ ፡ ህየ ፡ ይወድቁ ፡ ኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።

በጊልቦዔ ፡ ግልድው ፡ ግልድው ፡ ብ
ለው ፡ ይቀራሉ ።

ይሰደዱ ፡ ወኢይክሉ ፡ ቀዊመ ።

ድል ፡ ይነሳሉ ፡ እግባ ፡ መልስ ፡ ብሎ ፡
መዋጋት ፡ አይቻላቸውም ። እንድም ፡
ይጠፋሉ ፡ በሕይወት ፡ ሥጋ ፡ መኖር ፡
አይቻላቸውም ።

## መዝሙር ፡ ፴፮ ።

፩ ፡ ኢትቅናእ ፡ ላዕለ ፡ እኩያን ። ዘዳ ፡ ፳፫ ፡ ፩-፫ ።

እንዲህ ፡ ያለው ፡ ምዕዳን ፡ ይባላል ።
ከክፉ ፡ ሰዎች ፡ ሰብእ ፡ ትካት ፡ ሰብእ ፡
ሰዶም ፡ ሰብእ ፡ ገሞራ ፡ ሰብእ ፡ ግብፅ ፡



ሰብእ ፡ ፋርስ ፡ ሰብእ ፡ ባቢሎንን ፡ ስና
ክሬምን ። ከበጎዎች ፡ ናጎን ፡ ሉጥን ፡
ዳዊትን ፡ ሕዝቅያስን ፡ አብነት ፡ እያደ
ረገ ፡ ያመጣል ። ሠርቀው ፡ ቀምተው ፡
ዓምረው ፡ ፈትተው ፡ በሚኖሩ ፡ ሰ
ዎች ፡ አትቅና ። በነዚህ ፡ መቅናት ፡
እኔም ፡ የነሱን ፡ ሥራ ፡ ልሥራ ፡ ማ
ለት ፡ ነውና ። ምሳ ፡ ፳፫ ፡ ፲፯ ።

ወኢትቅናእ ፡ ላዕለ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።

ደንጊያ ፡ አለዝበው ፡ እንጨት ፡ ጠር
በው ፡ ጣዖት ፡ በሚያመልኩ ፡ ሰዎች ፡
አትቅና ። ምሳ ፡ ፳፬ ፡ ፲፱ ።

፪ ፡ እስመ ፡ ከመ ፡ ሣዕር ፡ ፍጡነ ፡ ይየብሱ ።

እንደ ፡ ሣር ፡ ፈጥነው ፡ ከብዕላቸው ፡
ይለያሉና ፡ የእካላቸውን ፡ ኋላ ፡ ያመ
ጣዋል ።

ወከመ ፡ ሐመልማለ ፡ ሐምል ፡ ፍጡነ ፡ ይወድቁ ።

እንደ ፡ ጉመን ፡ ቅጠል ፡ ፈጥነው ፡ ይወ
ድቃሉ ፡ ማለት ፡ ከብዕላቸው ፡ ይለያ
ሉና ።

፫ ፡ ተወከል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወግበር ፡ ሠናየ ።

አንተስ ፡ ይህን ፡ ጉሉ ፡ ትተህ ፡ ይህ ፡
ጉሉ ፡ እንዳይደርስብህ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ እመን ። በጎ ፡ በጎውን ፡ ሥራ ፡
ሥራ ። የጉሉንም ፡ ግበር ፡ በማለት ፡
ተናገረው ።

ወያንድርከ ፡ ዲበ ፡ ምድር ።

ይህን ፡ ያደረግህ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ በዚህ ፡
ዓለም ። እንድም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማ
ያት ፡ አጽንቶ ፡ ያኖርሃል ።

ወይሬዕየከ ፡ ዲበ ፡ ብዕላ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ በወድያኛው ፡ ዓለም ፡
ብዕል ፡ ያከብርሃል ።

፬ ፡ ተፈገዕ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወይሁበከ ፡ ስእ
ለተ ፡ ልብከ ። ኢሳ ፡ ፶፰ ፡ ፲፬ ።

በእግዚአብሔር ፡ እምነህ ፡ በተሠራ
ልህ ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ይበልህ ። በልቡ
ናህ ፡ አስበህ ፡ የለመንከውን ፡ ያደር
ግልሃል ። ማቴ ፡ ፯-፰ ።

፭ ፡ ክሥት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፍኖተከ ።

ስትለምነውም ፡ ይህን ፡ አድርግልኝ ፡
ብለህ ፡ ለይተህ ፡ ለምነው ። ጌታ ፡ ወዘ
እንበለ ፡ ንስእሎ ፡ ይሁብ ፡ ፍትወተነ ፡
አለ ። ኪሩ ፡ ፪ ፡ ፭ ። ቅ ፡ ጳውሎስ ፡ ወእ
ንዘ ፡ ተአዘዙ ፡ ከሥቱ ፡ ስእለተክሙ ፡
አለ ። ከዚህ ፡ ዳዊት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡
አይለያይምን ፡ ቢሉ ፡ አይለያይም ፡
ጌታ ፡ ወዘእንበለ ፡ ንስእሎ ፡ ማለቱ ፡
እንድያሻን ፡ አውቆ ፡ አካል ፡ ዘየአከ
ልን ፡ ሰጥቶናልና ። እለዚያም ፡ ከሥቱ ፡
ማለታቸው ፡ ለምነው ፡ ብዙ ፡ ያደር
ግልናልና ።

እንድም ፡ ለወጣንያን ፡ ለምነው ፡
ያደርግላቸዋልና ፡ እነዚያ ፡ የወማን
ያንን ፡ ለፍጹማን ፡ ሳይለምኑት ፡ ያደ
ርግላቸዋልና ፡ ጌታ ፡ የፍጹማኑን ፡ ተ
ናገረ ። እንድም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለምን
ው ፡ ያ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የ
ሰው ፡ ሃይማኖቱ ፡ እየፀና ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ እየበዛ ፡ ይሔዳልና ።

ተወከል ፡ ቦቱ ፡ ወውእቱ ፡ ይገብር ፡ ለከ ።

በሱ ፡ እመን ፡ እሱም ፡ የለመንከውን ፡ ያደርግልሃል ።

፮ ፡ ወያመጽእ ፡ ከመ ፡ ብርሃን ፡ ለጽድቅከ ።

የዓረቦኑን ፡ ማለት ፡ የሥጋውን ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ ጎህ ፡ ብርሃን ፡ አድርጎ ፡ በመጠን ፡ ይሰጥሃል ።

ወፍትሕከኒ ፡ ከመ ፡ መዓልት ።

የወዲያኛውን ፡ ማለት ፡ የነፍሱን ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ አድርጎ ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ አብዝቶ ፡ ይሰጥሃል ። የሥጋውን ፡ ክብር ፡ በጎሕ ፡ የነፍሱን ፡ ክብር ፡ በፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ መስሎ ፡ ተናገረ ። ከጎሑ ፡ ብርሃን ፡ የፀሐዩ ፡ ብርሃን ፡ እንዲበልጥ ፡ ከሥጋውም ፡ ክብር ፡ የነፍሱ ፡ ክብር ፡ ይበልጣልና ። ኢዮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፯ ። ኢሳ ፡ ፶፰ ፡ ፰-፲ ። ሆሴ ፡ ፮ ፡ ፭ ።

፯ ፡ ገነይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወተፀመድ ።

ለእግዚአብሔር ፡ ስትገዛ ፡ ቅኑት ፡ እንደ ፡ ገበሬ ፡ ዕሙድ ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ ጕነህ ፡ ተገዛ ።

ወኢትቅናዕ ፡ ላዕለ ፡ ዘይደሉ ፡ በሕይወቱ ።

ሠርቶ ፡ ቀምቶ ፡ ሸፍጦ ፡ ተሟግቶ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ በሚያደርግ ፡ ሰው ፡ አትቅና ። በሱ ፡ መቅናት ፡ እኔም ፡ እንደሱ ፡ ልሁን ፡ ማለት ፡ ነውና ።

ወላዕለ ፡ ሰብእ ፡ ዘይገብር ፡ ዓመፃ ።

በሰው ፡ ላይ ፡ ዓመፅን ፡ በሚሠራ ፡ ሰው ፡ አትቅና ። እንድም ፡ ዓመፅን ፡ በሚሠራ ፡ ሰው ፡ አትቅና ። ዘፀ ፡ ፳፫ ፡ ፳፫ ።

፰ ፡ ኅድጋ ፡ ለመዓት ፡ ወግድፋ ፡ ለቍጥዓ ።

እፍእዊት ፡ ውሳጣዊት ፡ ቍጣን ፡ ተዋት ።

ወኢትቅናዕ ፡ ከመ ፡ ታእኪ ።

ለበጎ ፡ መቅናት ፡ አለና ፡ ክፉ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ አትቅና ።

፱ ፡ እስመ ፡ እለ ፡ የአምሙ ፡ ይሤረዉ ።

ክፉ ፡ የሚያደርጉ ፡ ተነቃቅለው ፡ ይጠፋሉና ።

እለሰ ፡ ይትዔገሥዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እሙንቱ ፡ ይወርስዋ ፡ ለምድር ።

በሃይማኖት ፡ ለፈተና ፡ መከራ ፡ በመጣባቸው ፡ ጊዜ ፡ መከራ ፡ እንጂ ፡ ለወዳጆቹ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መከራውን ፡ ታግሠው ፡ የተቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይወርሷታልና ። መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ምድር ፡ አላት ። ምድር ፡ አልፋ ፡ የምትተካ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ምድራውያን ፡ ጻድቃን ፡ በምድር ፡ ስለ ፡ ሠሩት ፡ ሥራ ፡ የሚወርሷት ፡ ስለ ፡ ሆነ ። በምድር ፡ ተድላ ፡ ሥጋ ፡ እንዲፈጸምበት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ተድላ ፡ ነፍስ ፡ ይፈጸምባታልና ።

፲ ፡ ወዓዲ ፡ ሕዳጠ ፡ ኢይሄሉ ፡ እንከ ፡ ኃጥእ ።

ኃጥእ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ የኖረውን ፡ ያህል ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይኖርም ።



ተኀሥሥ ፡ ወኢትረክብ ፡ መካኖ ።

ትሻዋለህ ፡ ስንኳን ፡ ሰውነቱን ፡ ቦታውን ፡ አታገኘውም ። ቦታውማ ፡ ዓለም ፡ ሳያልፍ ፡ ወዴት ፡ ይሔዳል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ተልበ ፡ ተከበ ፡ ባጥር ፡ በቅጥር ፡ በውሻ ፡ በጋሻ ፡ አታገኘውም ። የብዕላቸውን ፡ ጩርሶ ፡ የሰውነታቸውን ፡ አመጣ ።

፲፩ ፡ ወየዋሃንሰ ፡ ይወርስዋ ፡ ለምድር ።

ቅኖች ፡ ኃዳግያን ፡ በቀል ፡ ግን ፡ ይህችን ፡ ዓለም ፡ አንድም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ወርሰዋት ፡ ይኖራሉ ።

ወይትፌሥሑ ፡ በብዙኅ ፡ ሰላም ። ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፲፫ ።

በፍጹም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። ማቴ ፡ ፭ ፡ ፭ ።

፲፪ ፡ ያስተሐይዮ ፡ ኃጥእ ፡ ለጻድቅ ። ቍ ፡ ፴፪ ።

ኃጥእ ፡ ሰው ፡ ጻድቁን ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ ሰባ ፡ ረባ ፡ እያለ ፡ መርዞ ፡ ተኩሮ ፡ ይመለከተዋል ። ሳኦል ፡ ዳዊትን ፡ ሰናክሬም ፡ ሕዝቅያስን ፡ መርዞ ፡ ተኩሮ ፡ ይመለከተው ፡ እንደ ፡ ነበረ ።

ወየሐቂ ፡ ስነኒሁ ፡ ላዕሌሁ ።

ጥርሱን ፡ ያፋጭበታል ፡ ማለት ፡ ትእምርተ ፡ ፀብዕ ፡ ነው ። አጽንቶ ፡ ይጣላዋል ፡ ሲል ፡ ነው ።

፲፫ ፡ ወእግዚአብሔርሰ ፡ ይስሕቆ ።

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡ እንደ ፡ ዋዛ ፡ ያይበታል ። ትስሕቅ ፡ ሰገኖ ፡ ላዕለ ፡ ፈረስ ፡ ወላዕለ ፡ ዘይጼዕኖ ፡ እንዲል ።

እስመ ፡ ያቀድም ፡ አእምሮ ፡ ከመ ፡ በጽሐ ፡ ዕለቱ ።

ይህ ፡ ሰው ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ ሳይደርስ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃልና ።

፲፬ ፡ ሰይፈሙ ፡ መልሑ ፡ ኃጥኣን ።

እለ ፡ ሳኦል ፡ እለ ፡ ሰናክሬም ፡ ምክራቸውን ፡ አፀኑ ፡ አንድም ፡ ሰይፋቸውን ፡ መዘዙ ።

ወወሰቁ ፡ ቀስቶሙ ።

ምክራቸውን ፡ አፀኑ ፡ አንድም ፡ ቀስታቸውን ፡ ቀፈፉ ።

ከመ ፡ ይቅትልዎ ፡ ለነዳይ ፡ ወለምስኪን ።

ዳዊትን ፡ አንድም ፡ ሕዝቅያስን ፡ በምክራቸው ፡ ይጎዱት ፡ በቀስታቸው ፡ ይወጉት ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ይርግዝዎሙ ፡ ለርቱዓነ ፡ ልብ ።

ቅን ፡ ልቡና ፡ ትሑት ፡ ሰብእና ፡ ያላቸው ፡ የዳዊት ፡ አንድም ፡ የሕዝቅያስን ፡ ወገኖችም ፡ በምክራቸው ፡ ይጎዱቸው ። አንድም ፡ በቀስታቸው ፡ ይወጓቸው ፡ ዘንድ ።

፲፭ ፡ ሰይፎሙ ፡ ይባእ ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ።

ቦእ ፡ ሲል ፡ ነው ። ምክራቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ወደመጉዳት ፡ ተመለሰ ፡ ማለት ፡ በምክራቸው ፡ እነሱ ፡ ተጎዱበት ፡ በሰይፋቸው ፡ እነሱ ፡ ተመቱበት ፡ እንጂ ። በምክራቸው ፡ አልጎዱበትም ፡ በሰይፋቸው ፡ አልመቱበትምና ። እንድም ፡ ቃለ ፡ መርገም ፡ ይባዕ ፡ ይመለስ ።

2014 04 17

ሰኔ፡ይበደራል፡ከፈለኝ፡ያሉት፡አ
ገደሀን፡መቼ፡ሰጠኸኝ፡እጂን፡አግ
ሬን፡አንባር፡ጎይኔን፡ግንባር፡ያይ
ርገው፡ብሎ፡ዘንጉን፡ይመዝባል።

ጻድቅ፡ሰው፡ግን፡ዘር፡ከዋር፡ብሎ፡
ይበደራል። ይሁብ፡ይቀድማል። ያን
ኑ፡የተበደረውን፡ይከፍላል። ወይም
ህር፡አትርፎ፡ይመጸውታል። እን
ድም፡(ይትሌቃሕ፡ኃጥእ)፡ኃጥእ፡
ሰው፡ከእግዚአብሔር፡ዝናም፡ለዘር፡
ጠል፡ለመከር፡ይበደራል። አሁን፡
እሱ፡የሚበደር፡እግዚአብሔር፡የ
ሚያበድር፡ሁና፡አይደለም። እንድ
ያሻው፡አውቆ፡መስጠቱን፡መናገር፡
ነው፡እንድም፡ዝናም፡ለዘር፡ጠል፡
ለመከር፡መስጠቱ፡እኩል፡ያለው፡
ሠርቶ፡ድውዩን፡ሊረዳበት፡ነውና፡
(ወይፈዲ)፡ዝናም፡ለዘር፡ጠል፡ለ
መከር፡ለሠጠው፡ለእግዚአብሔር፡
ዓሥራቱን፡በኩራቱን፡ልስጥ፡አይ
ይልም። (ወጻድቅሰ)፡ጻድቅ፡ሰው፡
ግን፡ከእግዚአብሔር፡ዝናም፡ለዘር፡
ጠል፡ለመከር፡ይበደራል፡(ይሁብ)፡
ዓሥራቱን፡በኩራቱን፡ይሰጣል።
(ወይምሕር)፡ከዚያው፡አትርፎ፡ይ
መጸውታል፡እንድም፡(ይትሌቃሕ)፡
ኃጥእ፡መምር፡ከእግዚአብሔር፡ት
ምህርትን፡ይበደራል፡እንድያሻው፡
አውቆ፡ምስጢር፡መግለጹን፡መና
ገር፡ነው። (ወኢይፈዲ)፡ልብሱን፡

እንደ፡ሰፋሉን፡አንሰርቶ፡ መጎሳ
ሱን፡ይዞ፡አምጥ፡ጠምጥም፡መን
ደር፡ለመንደር፡ከተማ፡ለከተማ፡
ሲዞር፡ይውላል። (ወጻድቅሰ)፡ጻድቅ፡
መምህር፡ግን፡ከእግዚአብሔር፡ት
ምርትን፡ይበደራል፡(ይምሕር፡ወ
ይሁብ)፡ሐዲስ፡የተማረ፡እንደሆነ፡
ሐዲሱን፡እያስተማረ፡ብሉዩን፡ይ
ማራል። ብሉይ፡የተማረ፡እንደሆነ፡
ብሉዩን፡እያስተማረ፡ሐዲሱን፡ይ
ማራል፡እንድም፡እንዘ፡ይሁብ፡ይ
ምሕር፡እያበላ፡እያጠጣ፡ያስተም
ራል። ይህንም፡ያደረጉ፡ብዙ፡ናቸ
ው። እንድም፡(ይትሌቃህ)፡ኃጥእ፡
ሰው፡ሕዋሳትን፡ከእግዚአብሔር፡
ይበደራል፡እንድያሻው፡አውቆ፡አ
ካል፡ዘየንካልን፡መስጠቱን፡መና
ገር፡ነው። ወኢይፈዲ፡ባይኑ፡ምስ
ጢር፡ሊመለከትበት፡በጆሮዩ፡ስብ
ሐተ፡እግዚአብሔር፡ሊሰማበት፡በ
እጁ፡ሊመጽውትበት፡በእግሬ፡ወደ፡
ቤተ፡እግዚአብሔር፡ሊሔድበት፡
በልቡናዩ፡በጎ፡ሊስብበት፡በንደበቴ፡
በጎ፡ሊናገርበት፡አይልም፡(ወጻድ
ቅሰ)፡ጻድቅ፡ግን፡ከእግዚአብሔር፡
ሕዋሳትን፡(አካላትን)፡ይበደራል።
(ይምሕር)፡በዚ፡ይመጸውትበታል።
በእግሩ፡ወደቤተ፡እግዚአብሔር፡
ይሄድበታል። በጆሮው፡ስብሐተ፡እ
ግዚአብሔር፡ይሰማበታል፡ባይኑ፡
ምስጢር፡ይመለከትበታል፡በልቡ፡
ናው፡ያስብበታል፡በንደበቱ፡በጎ፡

ወይትቀጥቀጥ፡ እቅሰስቲሆሙ ።

መጽሐፍ፡ ምስጢር ፡ እንጂ ፡ ዘይቤ ፡ አይጠነቀቅምና ፡ ይትቀጥቀጥ ፡ ብሎ ፡ እቅሰስቲሆሙ ፡ አለ ፡ ይትቀጥቀጥ ፡ ከለ ፡ ቀስቶሙ ፡ እቅሰስቲሆሙ ፡ ከለ ፡ ይትቀጥቀጣ ፡ ቢል ፡ ይቀናል ፡ ተቀጥቀጠ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ምክራቸው ፡ ጠፋ ፡ ቀስታቸው ፡ ተሰበረ ፡ እንድም ፡ ይትቀጥቀጥ ፡ ምክራቸው ፡ ይጥፋ ፡ ቀስታቸው ፡ ይሰበር ።

፳፮፡ [illegible] ፳፰ ፡ ፳፮-፳፱ ።

እምብዙኅ ፡ ብዕለ ፡ ኃጥኣን ።

ሥርቀው ፡ ቀምተው ፡ ሽፍጠው ፡ ተሟግተው ፡ ከሰበሰቡት ፡ ከባለጸጎች ፡ ብዙ ፡ ብዕል ፡ ይልቅ ፡ ወጥቶ ወርዶ ፡ ነዶ ፡ በርዶ ፡ በውነት ፡ የተገኘ ፡ ጥቂት ፡ የድኃ ፡ ገንዘብ ፡ ይበልጣል ፡ ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፳፮ ፡ ጢሞ ፡ ፯ ፡ ፳፬ ።

፳፯፡ እስመ ፡ ይትቀጥቀጥ ፡ ኃይሎሙ ፡ ለኃጥኣን ።

የባለጸጎች ፡ ገንዘብ ፡ ፈጥኖ ፡ ይጠፋልና ፡ እምብዙኅ ፡ ብዕለ ፡ ኃጥኣን ፡ ላለው ፡ ኃይለ ፡ ደግስቶ ፡ እንዲል ።

ያጸንዖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጻድቃን ።

እግዚአብሔር ፡ ድኆችን ፡ በጥቂት ፡ ገንዘብ ፡ ያጸናቸዋል ፡ ማለት ፡ ጥቂቱን ፡ አበርክቶ ፡ ይመግባቸዋልና ፡ ይኽ ይስ ፡ ጎዳጥ ፡ ላለው ።

፳፰፡ ያአምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍኖተ ፡ ንጹሓን ።

እግዚአብሔር ፡ የንጹሐንን ፡ ግብር ፡ ይወድዳልና ።

ወይከውን ፡ ርስቶሙ ፡ [illegible] ።

የዘለዓለም ፡ ርስታቸው ፡ እሱ ፡ ነውና ።

፳፱፡ ወኢይትኀፈሩ ፡ በመዋዕለ ፡ እኩያት ።

መቅሠፍታት ፡ በታዘዙባቸው ፡ ወራት ፡ አያፍሩም ፡ በመዋዕለ ፡ እኩያን ፡ እንደሆነ ፡ ዓላውያን ፡ ነገሥታት ፡ በሚነሡበት ፡ ወራት ፡ አያፍሩም ።

ወይጸግቡ ፡ በመዋዕለ ፡ ረኃብ ።

ረኃብ ፡ በታዘዘበት ፡ ወራትም ፡ ጥቂቱን ፡ አበርክቶ ፡ ይመግባቸዋል ፡ ኖኅን ፡ ሎጥን ፡ እንደ ፡ መገበ ።

፴፡ ወኃጥኣንሰ ፡ ይትኀጐሉ ።

ኃጥኣንን ፡ ግን ፡ የበሉት ፡ ቁርጠት ፡ ሆኖ ፡ ያጠፋቸዋል ።

ጸላእቱሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ [illegible] ።

የእግዚአብሔር ፡ ጸላቶቹ ፡ በክበሩ ፡ በገነኑ ፡ ጊዜ ።

የኃልቁ ፡ ወይጠፍኡ ፡ [illegible] ፡ ፳፮ ፡ ፳፱ ።

እንደ ፡ ጢስ ፡ ተንነው ፡ እንደ ፡ ትቢያ ፡ በንነው ፡ ይጠፋሉ ፡ እንድም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጠላቶቹ ፡ የሚጠፉት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ በክበሩ ፡ በገነኑ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እንድም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጠላቶቹ ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ተደላደሉ ፡ እንደተቀማጡ ፡ እንደከበሩ ፡ እንደገነኑ ፡ አይቀሩም ፡ እንደ ፡ ትብያ ፡ በንነው ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ ተንነው ፡ ይጠፋሉ ፡ እንጂ ።

፴፩፡ ይትሌቃሕ ፡ ኃጥእ ፡ ወኢይፈዲ ።

ኃጥእ ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ ከቸር ፡ ብሎ ፡ በሰኔ ፡ ይበደራል ፡ ከፈለኝ ፡ ያሉት ፡ እንደሆነ ፡ መቼ ፡ ሰጠኸኝ ፡ እጄን ፡ እግሬን ፡ አንባር ፡ ዓይኔን ፡ ግንባር ፡ ያድርገው ፡ ብሎ ፡ ዘንጉን ፡ ይመገዛል ።

ወጻድቅሰ ፡ ይምሕር ፡ ወይሁብ ፡ ምሳ ፡ ፳፪ ፡ ፲፡፲፮ ።

ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ዘር ፡ ከቸር ፡ ብሎ ፡ ይበደራል ፡ ይሁብ ፡ ይቀድማል ፡ ያንኑ ፡ የተበደረውን ፡ ይከፍላል ፡ ወይምህር ፡ አትርፎ ፡ ይመጸውታል ፡ እንድም ፡ (ይትሌቃሕ ፡ ኃጥእ) ፡ ኃጥእ ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ገንዘም ፡ ለዘርጠል ፡ ለመከር ፡ ይበደራል ፡ አሁን ፡ እሱ ፡ የሚበደር ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያበድር ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ፡ እንድ ያሻው ፡ አውቆ ፡ መስጠቱን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እንድም ፡ ገንዘም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ መስጠቱ ፡ አካል ፡ ያለው ፡ ሥርቶ ፡ ድውዩን ፡ ሊረዳበት ፡ ነውና ፡ (ወይፈዲ) ፡ ገንዘም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ ለሠጠው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዓሥራቱን ፡ በኵራቱን ፡ ልስጥ ፡ አይ ይልም ፡ (ወጻድቅሰ) ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ገንዘም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ ይበደራል ፡ (ይሁብ) ፡ ዓሥራቱን ፡ በኵራቱን ፡ ይሰጣል ፡ (ወይምሕር) ፡ ከዚያው ፡ አትርፎ ፡ ይመጸውታል ፡ እንድም ፡ (ይትሌቃሕ) ፡ ኃጥእ ፡ መምር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ትምህርትን ፡ ይበደራል ፡ እንድያሻው ፡ አውቆ ፡ ምስጢር ፡ መግለጹን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወኢይፈዲ) ፡ ልብሱን ፡ እንጽቶ ፡ ሰናፊሉን ፡ አንሰርቶ ፡ መነሳሱን ፡ ይዞ ፡ እምጥ ፡ ጠምጥጥ ፡ መንደር ፡ ለመንደር ፡ ከተማ ፡ ለከተማ ፡ ሲዞር ፡ ይውላል ፡ (ወጻድቅሰ) ፡ ጻድቅ ፡ መምህር ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ትምርትን ፡ ይበደራል ፡ (ይምሕር ፡ ወይሁብ) ፡ ሐዲስ ፡ የተማረ ፡ እንደሆነ ፡ ሐዲሱን ፡ እያስተማረ ፡ ብሉዩን ፡ ይማራል ፡ ብሉይ ፡ የተማረ ፡ እንደሆነ ፡ ብሉዩን ፡ እያስተማረ ፡ ሐዲሱን ፡ ይማራል ፡ እንድም ፡ እንዘ ፡ ይሁብ ፡ ይምሕር ፡ እያበላ ፡ እያጠጣ ፡ ያስተምራል ፡ ይህንም ፡ ያደረጉ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፡ እንድም ፡ (ይትሌቃህ) ፡ ኃጥእ ፡ ሰው ፡ ሕዋሳትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይበደራል ፡ እንድያሻው ፡ አውቆ ፡ አካል ፡ ዘየዓከልን ፡ መስጠቱን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ወኢይፈዲ ፡ ባይኔ ፡ ምስጢር ፡ ልመልከትበት ፡ በጆሮዬ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልስማበት ፡ በእጄ ፡ ልመጽውትበት ፡ በእግሬ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልሔድበት ፡ በልቡናዬ ፡ በጎ ፡ ላስብበት ፡ ባንደበቴ ፡ በጎ ፡ ልናገርበት ፡ አይልም ፡ (ወጻድቅሰ) ፡ ጻድቅ ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሕዋሳትን ፡ (አካላትን) ፡ ይበደራል ፡ (ይምሕር) ፡ በጁ ፡ ይመጸውትበታል ፡ በእግሩ ፡ ወደቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሄድበታል ፡ በጆሮው ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰማበታል ፡ ባይኑ ፡ ምስጢር ፡ ይመለከትበታል ፡ በልቡ ፡ በጎ ፡ ያስብበታል ፡ ባንደበቱ ፡ በጎ ፡



2014 04 17

ይናገርበታል ፡ (ወይሁብ)፡ በፍጻሜ ፡
ዘመኑ ፡ በሰማዕትነት ፡ ይሞታል ።

፳፪ ፡ እስመ ፡ እስ ፡ ይባርክዎ ፡ ይወርስዋ ፡ ለምድር ።

በሃይማኖት ፡ ለፈተና ፡ መከራ ፡ ቢያ
መጣባቸው ፡ መከራ ፡ እንጂ ፡ ለወዳ
ጆቹ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መከራውን ፡ በ
እኩቴት ፡ የሚቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ መን
ግሥት ፡ ሰማያትን ፡ ይወርሷታልና ፡
ጻድቅስ ፡ ላለው ።

እለሰ ፡ ይረግሞ ፡ ይሤረው ።

በሃይማኖት ፡ ለፈተና ፡ መከራ ፡ ቢያ
መጣባቸው ፡ ዓሥራት ፡ በኵራት ፡ አ
ውጥተን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ ፀንተን ፡
ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ተቀብለን ፡ በገን
ዘባችን ፡ ወጥተን ፡ ወርደን ፡ በኖርን ፡
መከራ ፡ ያመጣብኛል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
እግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ የሚያማርሩ ፡
ሰዎች ፡ ተነቃቅለው ፡ ይወድቃሉና ፡
ይትሌቃሕ ፡ ኃጥእ ፡ ላለው ።

፳፫ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፀንዕ ፡ ሑረቱ ፡
ለሰብእ ።

ይፀንሕ ፡ ሲል ፡ ነው ። የሰው ፡ ሥራው ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዋጋውን ፡
ተቀብሎ ፡ ይጠብቀዋል ። ምሳ ፡ ፳ ፡ ፲፰ ።

ለዘይፈቅድ ፡ ፍኖቶ ፡ ፈድፋደ ። ዘቆሮ ፡ ፫ ፡ ፱ ።

ያው ፡ ግን ፡ ሕጉን ፡ ለሚጠብቅ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ ለሁሉ ፡ አይደለም ።

፳፬ ፡ እመኒ ፡ ወድቀ ፡ ኢይደነግፅ ።

በመከራ ፡ ቢሰነከከል ፡ አይደነግፅም ።

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሠውቆ ፡ እዴሁ ።

እግዚአብሔር ፡ እጁን ፡ ይደግፈዋ
ልና ፡ ማለት ፡ ይረዳዋልና ፡ አንድም ፡
(እመኒ ፡ ወድቀ) ፡ በኃጢአት ፡ ቢሰነ
ከከል ፡ አይፈራም ። (እስመ ፡ እግዚ
አብሔር) ፡ እግዚአብሔር ፡ በንስሐ ፡
ይመልሰዋልና ። ኢሳ ፡ ፳፯ ፡ ፯ ። ዘቆሮ ፡ ፱ ፡ ፱ ።

፳፭ ፡ ወርዘውኩ ፡ ወረሣዕኩ ።

ከልጅነት ፡ እስከ ፡ እውቀት ፡ ከኮተት ፡
እስከ ፡ ሽበት ፡ ደረስኩ ።

ወጻድቅሰ ፡ ዘይትገደፍ ፡ ኢርኢኩ ።

የሚጎዳ ፡ ጻድቅን ፡ አላየሁም ፡ አን
ድም ፡ ጻድቅሰ ፡ እንዘ ፡ ይትገደፍ ፡
ይላል ። ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ሲጎዳ ፡ አላየ
ሁም ።

ወዘርዑሂ ፡ ኢይጼነስ ፡ እክለ ። ኢዮ ፡ ፭ ፡ ፭ ።
ዘቆሮ ፡ ፱ ፡ ፱ ።

ብዕለም ፡ ይላል ። ልጁ ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡
እክለ ፡ ጸጋ ፡ ብዕለ ፡ ጸጋ ፡ ብዕለ ፡ ሥጋ ፡
ብዕለ ፡ ነፍስ ፡ አጥቶ ፡ አይቸገርም ።

፳፮ ፡ ወኵሎ ፡ አሚረ ፡ ይምሕር ፡ ወይሌቅህ ።

ስንኳን ፡ ለራሱ ፡ ሊያጣ ፡ ተርፎት ፡
ዘወትር ፡ ልቃሕ ፡ መንፈሳዊ ፡ ያበድ
ራል ፡ ሲያበድር ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡
ምጽዋቱን ፡ ብድር ፡ አለው ፡ ሰው ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ መስጠቱ ፡ መመጽ
ወቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋጋዬን ፡ ይከ
ፍለኛል ፡ ብሎ ፡ ነውና ። ናብልዮሙ ፡
ለነዳያን ፡ ከመ ፡ ናብልዮ ፡ ለክርስቶስ ።
ዘለቅሐ ፡ ለነዳይ ፡ ለቅሐ ፡ ለእግዚአብ



ማህሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መልአ ፡ ምድረ ፤ ወበቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸንዓ ፡ ሰማያት ፤ ወእም
እስትንፋሰ ፡ አፉሁ ፡ ኵሉ ፡ ኀይሎሙ ፤ መዝሙር ፡ ፴፪ ።



ዐርገ ፡ እግዚአብሔር ፡ በይባቤ ፤ ወእግዚእነ ፡ በቃለ ፡ ቀርን ፤ መዝሙር ፡ ፵፮ ።





ሔር ፣ እንዲል ። እንድም ፣ ነፍስ ፣ በነ ፈሰበት ፣ ዘመን ፣ አበድሮት ፣ ቀን ፣ ሲወጣ ፣ ትርፍ ፣ ሳይል ፣ ገንዘቡን ፣ ቢቀበል፣ከምጽዋት፣ይቈጠርለታል።

ወዘርዑኒ ፣ ውስተ ፣ በረከት ፣ ይሄሉ ።

እንዲህ፣ያለው፣ሰው ፣ ልጁ ፣ የልጅ፣ ልጁ ፣ በበረከት ፣ ሥጋ ፣ በበረከት ፣ ነፍስ ፣ ፀንቶ ፣ ይኖራል ።

፳፯ ፣ ተገሐሥ፣እምዕኩይ፣ወግበር፣ሠናየ።

ከክፉ ፣ ሥራ፣ተለይ፣በጎውን፣ሥራ፣ ሥራ ። መዝ ፣ ፴፫ ፣ ፲፬ ።

ወትነብር ፣ ለዓለመ ፣ ዓለም ። ሚል ፣ ፯ ፣ ፩-፪ ።

እንዲህ ፣ ያደረግህ ፣ እንደሆነ ፣ ለዘላ ለሙ፣ፀንተህ፣ትኖራለህ ። እሞ ፣ ፩ ፣ ፲፱ ።

፳፰ ፣ እስመ፣ጽድቀ፣ያፈቅር፣እግዚአብሔር ።

መዝ ፣ ፴ ፣ ፳፫ ። እግዚአብሔር ፣ እውነ ትን ፣ እንድም ፣ እውነትን ፣ የያዘ ፣ ሰ ውን ፣ ይወድዳልና ።

ወኢይገድፎሙ ፣ ለጻድቃን ።

ጻድቃንን፣በመከራው፣አይጥላቸው ምና፣ለጊዜውም፣ቢጥላቸው፣እንደ ጣላቸው ፣ አይቀርምና ።

ወለዓለም ፣ የዓቅቦሙ ።

ለዘላለሙ፣እንድም፣በነፍስ፣በሥጋ፣ ይጠብቃቸዋል ።

ወይትቤቀል፣ሎሙ፣ለንጹሐን ። ሚል ፣ ፴፪ ፣ ፳፪ ።

ለንጹሐን ፣ ይፈርድላቸዋል ። ተበቀ ል ፣ ሊተ ፣ እምዕደውየ ፣ እንዲል ። እንድም፣ይትቤቀል፣ሎሙ ፣ ይላል ፣ ተበቅሎ ፣ ጠላታቸውን ፣ ያጠፋላቸ ዋል ።

ወይማስን ፣ ዘርዖሙ ፣ ለኃጥኣን ።

የኃጥአን ፣ ልጃቸውን ፣ የልጅ ፣ ልጃ ቸውን ፣ ነቃቅሎ ፣ ያጠፋቸዋል ።

፳፱ ፣ ወጻድቃንሰ ፣ ይወርስዋ ፣ ለምድር ።

ጻድቃን ፣ ግን ፣ ይህቺን ፣ ዓለም ፣ እን ድም ፣ መንግሥተ ፣ ሰማያትን ፣ ይወ ርሳሉ ።

ወይነብሩ ፣ ውስቴታ ፣ ለዓለመ ፣ ዓለም ።

በውሥጢ ፣ ለዘላለም ፣ ይኖራሉ ።

፴ ፣ አፉሁ ፣ ለጻድቅ ፣ ይትሜሀር ፣ ጥበበ ።

የጻድቅ ፣ ሰው ፣ አንደበቱ ፣ ጥበብን ፣ እንድም ፣ ሕግን ፣ ይማራል ።

ወልሳኑ ፣ ይነብብ ፣ ጽድቀ ።

አንደበቱም ፣ ጽድቅን ፣ እንድም ፣ ሕ ግን ፣ ይማራል ።

፴፩ ፣ ወሕገ ፣ አምላኩ ፣ ውስተ ፣ ልቡ ።

ጽሑፍ ፣ ውስተ ፣ ልቡ ፣ ሲል ፣ ነው ፣ የፈጣሪው፣ሕግ፣በልቡናው፣ተጽፎ፣ ይኖራል ፣ የተጻፈ፣እንዳይጠፋ፣አይ ጠፋም ።

ወኢይድሕፅ ፣ ሰኰናሁ ።

ሰኰና ፣ ሥጋው ፣ በመከራ ። ሰኰና ፣ ነፍሱ ፣ በኃጢአት ፣ አይሰነካከልም ።

፴፪ ፣ ያስተሐይጽ ፣ ኃጥእ ፣ ለጻድቅ ። ኍ ፣ ፲፪ ።

ኃጥእ፣ሰው፣ጻድቁን፣መርዞ፣ተሠር፣ ይመለከተዋል ።

ወይፈትድ፡ ይትትሎ።

ቢያገኘው፡ ሊገድለው፡ ይወድዳል።

፴፫፡ ወኢየሐድጎ፡ እግዚአብሔር፡ ውስተ፡ እደዊሁ።

ነገር፡ ግን፡ እግዚአብሔር፡ በእጁ፡ አይጥለውም። እንድም፡ አይጥለውም፡ እንጂ።

ወኢይመውዖ፡ ሶበ፡ ይትዋቀሶ።

በተጻላውም፡ ጊዜ፡ አይረታውም። እንድም፡ ኢያመውዖ፡ እግዚአብሔር፡ ድል፡ አያስነሳውም። ፪ቆሮ፡ ፬፡ ፱።

፴፬፡ ተኀገሥ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወዕቀብ፡ ፍናቶ።

በሃይማኖት፡ ለፈተና፡ መከራ፡ ቢያመጣብህ፡ መከራውን፡ ታግሠህ፡ ተቀበል፡ ሕጉን፡ ጠብቅ።

ወያነብርከ፡ ከመ፡ ትረሳ፡ ለምድር።

እንዲህም፡ ያደረግህ፡ እንደሆን፡ ይህችን፡ ዓለም። እንድም፡ መንግሥተ፡ ሰማያትን፡ ወርሰሃት፡ ትኖር፡ ዘንድ፡ በነፍስ፡ በሥጋ፡ ያከብርሃል።

ወትሬኢ፡ ከመ፡ ይሜረው፡ ኃጥአን።

እንዘ፡ ይሜረው፡ ሲል፡ ነው፡ ኃጥአን፡ ሲጠፉ፡ ታያለህ።

፴፭፡ ርኢክዎ፡ ለኃጥእ፡ ዐብየ፡ ወተለዓለ፡ ከመ፡ ዓርዘ፡ ሊባኖስ። ኢዮ፳፡ ፱-፲።

እንደ፡ ደጋ፡ ዛፍ፡ እኔም፡ እንዳቅሚ፡ ሳአልን፡ ከብሮ፡ ገንኖ፡ ዓየሁት።

፴፮፡ ወሶበ፡ እንግብዕ፡ ኃጣእክዎ።

ጥቂት፡ ቀን፡ ሲቈላግ፡ ኑሬ፡ ብመለስ፡ በተመለስኩ፡ ጊዜ፡ አጣሁት።

ኃሠሥኩ፡ ወኢረከብኩ፡ መካኖ። ኢሳ፡ ፲፡ ፴፫-፴፬።

ሻሁት፡ ስንኳን፡ ሰውነቱን፡ በታውን፡ አላገኘሁትም።

፴፯፡ ዕቀብ፡ የውሃት፡ ወትሬኢ፡ ጽድቀ።

እኔ፡ ይህን፡ ያየሁትን፡ ቅንነትን፡ እንድም፡ ሕጉን፡ ጠብቁ፡ ነውና፡ እንተም፡ ቅንነትን፡ እንድም፡ ሕጉን፡ ጠብቅ፡ እንዲህ፡ የሆነ፡ እንደሆነ፡ እውነት፡ ይደረግልሃል። እውነት፡ ነገር፡ ሲደረግልህ፡ ታያለህ።

እስመ፡ በቱ፡ ተረፈ፡ ብእሲ፡ ሰላም።

ተረፈ፡ ብእሴ፡ ሰላም፡ ሲል፡ ነው። የብእሴ፡ ሰላም፡ የኖኅ፡ ልጅ፡ ሜም፡ ድኗልና። ተረፎሙ፡ ለአሕዛብ፡ እንዲል፡ እንድም፡ ተረፈ፡ ብእሴ፡ ሰላም፡ ኖኅ፡ ድኗልና።

፴፰፡ ወአማፅያንሰ፡ ይሜረው፡ ምሳ፡ ፫፡ ፴፫።

ዓመፀኞች፡ ግን፡ በነፍስ፡ በሥጋ፡ ተነቃቅለው፡ ይጠፋሉ።

ወይሜረው፡ ትራፋቲሆሙ፡ ለኃጥአን።

የኃጥአን፡ ልጆቻቸው፡ የልጅ፡ ልጆቻቸው፡ ተነቃቅለው፡ ይጠፋሉ።

፴፱፡ መድኃኒቶሙ፡ ለጻድቃን፡ እምኀበ፡ እግዚአብሔር።

የጻድቃን፡ ግን፡ ድኅነታቸው፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ይታዘዝላቸዋል። ይደረግላቸዋል።

ወቀዋሚሆሙ፡ ውእቱ፡ በጊዜ፡ ምንዳቤሆሙ።

እሱ፡ በመከራቸው፡ ጊዜ፡ (መከራ፡ በሚቀበሉበት፡ ጊዜ)፡ ዋስ፡ ጠበቃ፡ ሁኖ፡ ይጠብቃቸዋል።

፵፡ ይረድኦሙ፡ እግዚአብሔር፡ ወያድኅኖሙ።

እግዚአብሔር፡ ረድቶ፡ ያድናቸዋል።

ወያገግሮሙ፡ እምእደ፡ ኃጥአን።

ከባለጸጎች፡ እጅ፡ ያስለቅቃቸዋል።

ወያድኅኖሙ፡ እስመ፡ ተወከሉ፡ በቱ።

እምነውበታልና፡ ያድናቸዋል።

## መዝሙር፡ ፴፯።

፩፡ እግዚኦ፡ በመዓትከ፡ ኢትቅሥፈኒ።

በአቤሴሎም፡ ጊዜ፡ ስለራሱ፡ ተናግሮታል። አቤቱ፡ ሰብእ፡ ትካትን፡ ባጠፋህበት፡ መዓትህ፡ አታጥፋኝ።

ወበመቅሠፍትከ፡ ኢትገሥጸኒ።

ሰብአ፡ ሰዶም፡ ሰብአ፡ ገሞራን፡ ባጠፋህበት፡ መቅሠፍትህ፡ አታጥፋኝ። እንድም፡ በነፍስ፡ በሥጋ፡ አታጥፋኝ።

፪፡ እስመ፡ አሕፃከ፡ ደገጸኒ።

አሕፃ፡ መዓትህ፡ ጐንጸውኛል፡ እንድም፡ እውከውኛልና።

ወአፅናዕከ፡ እዴከ፡ ላዕሌየ።

እደ፡ መዓትህ፡ ስለፀናብኝ።

፫፡ ወአልቦ፡ ፈውስ፡ ለሥጋየ፡ እምገጸ፡ መዓትከ።

ገጸ፡ መዓትህ፡ ከመገለጹ፡ የተነሣ። እንድም፡ ከገጸ፡ መዓትህ፡ ብዛት፡ የተነሣ። ለሰውነቴ፡ ድኅነት፡ የላትም።

ወአልቦ፡ ሰላም፡ ለአዕፅምትየ፡ እምገጸ፡ ኃጢአትየ።

ኃጢአቴ፡ ከመገለጽ። ከኃጢአቴ፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ እንድ፡ ኃጢአቴን፡ ከመመልከትህ፡ የተነሣ፡ ለወገናቼ፡ እንድም፡ ለሰውነቴ፡ ድኅነትን፡ አላገኘሁም። ኢሮ፡ ፯፡ ፮-፰።

፬፡ እስመ፡ ኀጣውእየ፡ እምዐእርተ፡ ርእስየ፡ ኀለፋ።

በዝኃ፡ ሲል፡ ነው። ወያነውኖ፡ ለተረፈ፡ እስራኤል፡ እንዲል። ኃጢአቴ፡ በደሌ፡ ከራስ፡ ጸጕሬ፡ በዝቷልና።

ከመ፡ ፆር፡ ክቡድ፡ ከብደ፡ ላዕሌየ።

እንደ፡ ጨው፡ እንደ፡ እርሳስ። በርብ፡ እንዲል፡ ፈተና፡ ደንግያ፡ በኔ፡ ጸና። ኢሳ፡ ፴፡ ፳፯።

፭፡ ወበኑበኑ፡ ወአዕፅምትየ፡ እምገጸ፡ እበድየ።

በስንፍናዬ። እንድም፡ ሰንፌ፡ የሠራሁት፡ ኃጢአቴ፡ ከመገለጹ፡ የተነሣ፡ ሰውነቴ፡ ወዛ፡ ወገዝ፡ ለወጠ። ዓቀበ፡ ብርሀምን፡ ሲወጣ፡ ወዛ፡ ከወዛ፡ ዘንድ፡ ወገዝ፡ ይለወጣልና። ከመ፡ ብኅበኄ፡ እንበሳ፡ እንዲል። ምሳ፡ ፲፪፡ ፴፱። ዮሐ፡ ፭፡ ፲፱።

፮፡ ሐርተምኩ፡ ወተቀጻዕኩ፡ ለዝሉፉ።

ፈጽሜ፡ ለዘለዓለም፡ በለመከራ፡ ሆንሁ።

2014 04 17

ወዘሎ ፡ እግረ ፡ ትኩዝየ ፡ አንሶሱ ።

ዕለት ፡ ዕለት ፡ ያዘንጉ ፡ የተከዝጉ ፡ ሁኜ ፡ እኖራለሁ ።

፮ ፡ እስመ ፡ ዐገበት ፡ ዕእለተ ፡ ነፍስየ ።

ሰው ፡ ቴ ፡ ስድቡን ፡ ሰልችታዋለችና ። ኤር ፡ ፱፭ ፡ ፲፱ ።

ወኃጣእኩ ፡ ፈውስ ፡ ለሥጋየ ።

ለሰውነቴ ፡ ድኅነትን ፡ አጣሁላት ።

፯ ፡ ደወይኩ ፡ ወሐመምኩ ፡ ፈድፋደ ።

ፈጽሜ ፡ ባለመከራ ፡ ሆንሁ ።

ወእትኀሥዕ ፡ እምኃዘነ ፡ ልብየ ።

ከልቡናዬ ፡ ኃዘን ፡ የተነሣ ፡ እኽ ፡ እኽ ፡ እልእለሁ ። አንድም ፡ ወእጉሥዕ ፡ ኀዘነ ፡ እምልብየ ። ከልቡናዬ ፡ ኃዘኔን ፡ አውጥቼ ፡ እናገራለሁ ፡ ወትጉሥዖሙ ፡ ባሕር ፡ ለነጋድያን ፡ እንዲል ።

፱ ፡ ወትድኅኒከ ፡ ኵሉ ፡ ፍትወትየ ።

ወድጄ ፡ የሠራሁት ፡ ኃጢአት ፡ አንድም ፡ የምወድደው ፡ መንግሥቴ ፡ ከፊትህ ፡ ነው ፡ ታውቀዋለህ ፤

ወገዓርየኒ ፡ ኢይትኃባእ ፡ እምኔከ ።

መከራዬም ፡ ከንተ ፡ አይሠወርም ፡ ታውቀዋለህ ።

፲ ፡ ልብየኒ ፡ ደንገጸኒ ፡ ወኃይልየኒ ፡ ኃደገኒ ።

ልቡናዬ ፡ ተሸበረብኝ ። እውቀትም ፡ ተለየኝ ።

ወብርሃነ ፡ አዕይንትየኒ ፡ ለከወኒ ።

ዓይኖቼ ፡ ብርሃንን ፡ አጡብኝ ። አንድም ፡ ወብርሃነ ፡ አዕይንትየኒ ፡ ለከ ወኒ ፡ ብለህ ፡ አናብበህ ። ያይኖቼ ፡ ብርሃን ፡ ፈዘዙብኝ ።

፲፩ ፡ እዕርክትየኒ ፡ ወቢጽየኒ ፡ ዕድወ ፡ ኮኑኒ ፡ ወደበዩኒ ።

ባልንጀሮቼ ፡ ወዳጆቼ ፡ ባላጋራ ፡ ሆኑኝ ፡ ከበቡኝ ፡ ደበደቡኝ ፡ ውደቅ ፡ አሉኝ ፡ ዘረፉኝ ፡ ውደቅ ፡ ወደበዩ ፡ ቤተ ፡ ኢያሱን ፡ እንዲል ።

ወእዝማድየኒ ፡ ተባዕኒ ፡ ወተናከሩኒ ።

ዘመዶቼ ፡ ተስፋ ፡ ቈረጡኝ ። ባዕድ ፡ ሆኑኝ ፡ ተለዩኝ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እሱ ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ ሊመላ ፡ ብለው ። ሰቆ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

፲፪ ፡ ወተኃየሉኒ ፡ እለ ፡ የኃሥሥዋ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ ለሞት ፡ ለጥፋት ፡ የሚ ሿት ፡ ሁሉ ፡ በረቱብኝ ።

ወእለሂ ፡ ይፈቅዱ ፡ ሕማምየ ፡ ነበቡ ፡ ከንቶ ።

መከራዬን ፡ የሚወድዱ ፡ ሰዎች ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ተናገሩ ።

ወዘሎ ፡ እግረ ፡ ይመክሩ ፡ በቀሥር ፡ ያመንክ ዉኒ ።

በቈጠርጣራ ፡ ጠፍር ፡ በጢጢ ፡ በሳ ንባ ፡ ጠለፍ ፡ ይገርፉኝ ፡ ዘንድ ፡ ዘወ ትር ፡ ይመክሩብኛል ።

፲፫ ፡ ወእንስ ፡ ከመ ፡ ፅሙም ፡ ዘኢይሰምዕ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ቢመክር ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ደን ቆሮ ፡ ሆንሁ ።

ወከመ ፡ በሐም ፡ ዘኢይከሥት ፡ አፉሁ ።

እንደበቱን ፡ እንዳልፈታ ፡ እንደ ፡ ድዳ ፡ ሆንሁ ።



፲፬ ፡ ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢይሰምዕ ።

በጆሮው ፡ እንደማይሰማ ፡ ሰው ፡ ሆንሁ ።

ወከመ ፡ ዘኢይክል ፡ ተናግሮ ፡ በአፉሁ ።

በንደበቱ ፡ መናገር ፡ እንደማይችል ፡ ሆንሁ ፡ በናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ድዳ ፡ ደን ቆሮ ፡ ሆኖ ፡ የሚወለድ ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ በደዌ ፡ ምክንያት ፡ ድዳ ፡ ደን ቆሮ ፡ የሚሆን ፡ አለና ፡ መላልሶ ፡ ተና ገረው ።

፲፭ ፡ እስመ ፡ ኪያከ ፡ ተወከልኩ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ባንተ ፡ አምኜለሁና ።

አንተ ፡ ስምዓኒ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ።

ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

፲፮ ፡ እስመ ፡ እቤ ፡ ኢትረስየኒ ፡ ስላተ ፡ ጸላእየ ።

ስላቀ ፡ ጸላእትየ ፡ ሲል ፡ ነው ። የጸላ ቶቼ ፡ መዘበቻ ፡ አታድርገኝ ፡ ብዬ ፡ አምኜለሁና ።

ወእመኒ ፡ ድኅፀ ፡ ስጉናየ ፡ ያዐብዩ ፡ አፉሆሙ ፡ ላዕሌየ ።

ብዙውስ ፡ ይቅርና ፡ ጥቂት ፡ ሰውነቴ ፡ በኃጢአት ፡ አንድም ፡ በመከራ ፡ ቢሰ ነካከል ፡ ነገራቸውን ፡ ያበዙብኛል ።

፲፯ ፡ እስመ ፡ ሊተስ ፡ እዕንሑኒ ፡ ይቅሥፉኒ ።

ለኔማ ፡ እኮን ፡ ይገርፉኝ ፡ ዘንድ ፡ የግ ርፋት ፡ መጥን ፡ አቂዩኝ ። ጥንቱን ፡ ለልማዱ ፡ የንጉሥ ፡ መጥን ፡ ፍሪዳ ፡ ማር ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ ነበር ። ኤር ፡ ፯—፯ ።

ወተቀበልየኒ ፡ ቅድሜየ ፡ ውእቱ ፡ በዠሉ ፡ ጊዜ ።

መከራዬ ፡ ጉል ፡ ጊዜ ፡ በፊቴ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ እስበዋለሁ ።

፲፰ ፡ ወእነግር ፡ ጌጋይየ ።

በደሌን ፡ እናገራለሁ ።

ወእቴክዝ ፡ በእንተ ፡ ኃጢአትየ ።

ኃጢአት ፡ ስለ ፡ ሠራሁም ፡ አዝናለ ሁ ። አንድም ፡ እነግር ፡ መበደሌን ፡ እናገራለሁ ። (ወእቴክዝ ፡ በእንተ ፡ ኃጢአትየ ፡ ረዳት ፡ ማጣቴን ፡ አይቼ ፡ አዝናለሁ ፡ ሳሚ ፡ ወልደ ፡ ጌራ ፡ በዮ ርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ሁኖ ፡ አፈር ፡ እየበ ተነ ፡ ጠጠር ፡ እየጣለ ፡ ገዥ ፡ ፃዕፃዕ ፡ ብእሴ ፡ ደም ፡ ፈደየከ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ በቀለ ፡ ደሙ ፡ ለሳኦል ፡ ጭን ጋፍ ፡ ያራት ፡ ወር ፡ ብላቴና ፡ እግዚ አብሔር ፡ እንደ ፡ ወጣህ ፡ ያስቀርህ ፡ እያለ ፡ ሰድቦታል ፡ ረግሞታል ። አቢ ሳ ። ከልብ ፡ ምውት ፡ ለምንት ፡ ይጸ ርፎ ፡ ለእግዚእየ ፡ እሑር ፡ ወእዕዱ ፡ ወእምትር ፡ ርእሰ ፡ በሰይፍ ፡ ይህ ፡ የውሻ ፡ ሬሳ ፡ ጌታዬን ፡ ለምን ፡ ይሰ ድበዋል ፡ ሒጄ ፡ ተሻግሬ ፡ ቸብቸበ ውን ፡ ቈርጬ ፡ ላምጣው ፡ አሰናብ ተኝ ፡ አለው ። ኅድግ ፡ ይርግሞ ፡ ለዳ ዊት ። እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘዘ ፡ ይርግሞ ፡ ለዳዊት ፡ ተወው ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ይስደበው ፡ ቢል ፡ ተወው ፡ ይስደበኝ ፡ ብሎታል ፡ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፮ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ።

፲፱ ፡ ጸላእትየሰ ፡ ሕያዋን ፡ ወይኄይሉኒ ፡ ኢዮ ፡ ፴፰ ፡ ፲ ።

ጠላቶቼ ፡ ሞት ፡ አይነካሽ ፡ ናቸው ። ይበረቱብኛል ። አንድም ፡ የሚበረቱብኝ ፡ ጠላቶቼ ፡ ሞት ፡ አይነካሽ ፡ ናቸው ። አንድም ፡ አለን ፡ አለን ፡ ባዮች ፡ ናቸው ።

ወበዝኁ ፡ እለ ፡ በዓመፃ ፡ ይጸልዑኒ ።

ሳልጠላቸው ፡ በግፍዕ ፡ የሚጠሉኝ ፡ ጠላቶቼ ፡ እለ ፡ አቤሴሎም ፡ በዙ ።

፳ ፡ እለ ፡ ይፈድዩኒ ፡ እኪተ ፡ ህየንተ ፡ ሠናይት ።

በጎ ፡ ስላደረግሁላቸው ፡ የክፉ ፡ ብድራት ፡ የሚመልሱልኝ ፡ በፍና ፡ ተሣልቆ ፡ ጠላቶቼ ፡ ከኔ ፡ ከኃጢአት ፡ ንጹሐን ፡ ናቸው ።

ወያስተዋድዩኒ ፡ በተሊወ ፡ ጽድቅ ።

እውነት ፡ የያዝነ ፡ መስሎአቸው ። አንድም ፡ በኢተሊወ ፡ ጽድቅ ፡ ይላል ፡ እውነት ፡ ባለመያዛቸው ፡ ማለት ፡ አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ፡ ያለውን ፡ ባለመያዛቸው ።

ወገደፉኒ ፡ አኀዊሆሙ ፡ ከመ ፡ በድን ፡ ርኩስ ።

እኔን ፡ ወንድማቸውን ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ሬሳ ፡ አሽግረው ፡ ጣሉኝ ። ውሻ ፡ በከተማ ፡ መኻል ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሠራዊቱ ፡ ደዌ ፡ እንዳይናኝ ፡ ወድያ ፡ አውጥታችኍ ፡ ጣሉት ፡ ይባላልና ። አንድም ፡ (ጸላእትየሰ ፡ ሕያዋን) ፡ ጠላቶቼ ፡ አይሁድ ፡ አለን ፡ አለን ፡ ባዮች ፡ ናቸው ። (ወበዝኁ) ፡ ሳልጸላቸው ፡ በግፍዕ ፡ የሚጸሉኝ ፡ አይሁድ ፡ በዙ ፡ እለ ፡ ይፈድዩኒ ፡ ዕኪተ ፡ ህየንተ ፡ ሠናይት ፡ በጎ ፡ ስላደረግሁላቸው ፡ ፈንታ ፡ የክፉ ፡ ብድራት ፡ የሚመልሱልኝ ፡ ማለት ፡ ኅብስት ፡ አበርክቼ ፡ ስለመገብኋቸው ፡ ድውይ ፡ ስለ ፡ ፈወስሁላቸው ፡ ሙት ፡ ስላስነሣሁላቸው ፡ ፈንታ ፡ የሚሰቅሉኝ ፡ የሚገድሉኝ ፡ (ወያስተዋድዩኒ ፡ በተሊወ ፡ ጽድቅ ፡) ጻድቁ ፡ ኢ.ትቅትል ፡ ያለውን ፡ ባለማወቃቸው ። (ወገደፉ) ፡ እንደ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አደረጉኝ ። ወእሙንቱ ፡ አኃዊሁ ፡ እመንገለ ፡ ሥጋሁ ፡ ድኩም ፡ እንዲል ።

፳፩ ፡ ኢትኅድገኒ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ ወኢትርኃቅ ፡ እምኔየ ።

አንተ ፡ እግዚአ ፡ አምላኪየ ፡ ኢትግድፈኒ ። ወኢ.ትርኃቅ ፡ እምኔየ ፡ ብለህ ፡ አቅና ። አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ በመከራው ፡ አትጣለኝ ፡ በረድኤትም ፡ አትለየኝ ።

ወነጽር ፡ ውስተ ፡ ረዲኦትየ ፡ እግዚኦ ፡ አምላከ ፡ መድኃኒትየ ።

ድኅነትን ፡ የምታደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እኔን ፡ ወደ ፡ መርዳት ፡ እይ ፡ ተመልከት ።

## መዝሙር ፡ ፴፰ ።

፩ ፡ እቤ ፡ አዐቅብ ፡ ፍኖትየ ፡ ከመ ፡ ኢይስሐት ፡ በልሳንየ ።

በሳኦል ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግሮታል ። ታሪኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተወከልኩ ፡ ካለው ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። ሲሞን ፡ ኢያሶን ፡ ሳኦል ፡ ሊገድልህ ፡ መጣ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ምነው ፡ እኔስ ፡ እንዳልል ፡ እንደቤቴን ፡ እጠብቃለኍ ፡ እልሁ ፡ ኢዮ ፡ ፲፮ ፡ ፭ ። ምሳ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ። ሲራ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ። ማቴ ፡ ፲፪ ።

፪ ፡ ወአንበርኩ ፡ ዐቃቤ ፡ ለአፉየ ።
ሶበ ፡ ይትቃወሙኒ ፡ ኃጥአን ፡ ቅድሜየ ።

ሲሞን ፡ ኢያሶን ፡ ሳኦል ፡ ሊገድልህ ፡ መጣ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ላንደበቴ ፡ አርምሞን ፡ ትእግሥትን ፡ ገንዘብ ፡ አደረግሁ ።

፫ ፡ ተፀመምኩ ፡ ወአትሐትኩ ፡ ርእስየ ።

ሳኦል ፡ ሊገድልህ ፡ መጣ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ እልሁ ፡ ራሴን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አደረግሁ ፡ ማለት ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ፡ እልሁ ።

ወአርመምኩ ፡ ለሠናይ ።

ለክፉ ፡ ነገር ፡ ዝምታ ፡ አለና ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ ዝም ፡ እልሁ ።

ወተሐደሰኒ ፡ ቍስልየ ።

መከራዬ ፡ ፀናብኝ ። ኢዮ ፡ ፲፮-፲፱ ።

፬ ፡ ወሞቀኒ ፡ ልብየ ፡ በውስጥየ ።

በሰውነቴ ፡ ያለ ፡ ልቡናዬ ፡ ጋል ፡ ጋል ፡ አለብኝ ። ተናደደብኝ ፡ ተናገር ፡ ተናገር ፡ አለብኝ ።

ወነደ ፡ እሳት ፡ እምአንብቦትየ ።

ከመናገሬ ፡ የተነሣ ፡ እሳት ፡ ነደደ ፡ ማለት ፡ ተናድጄ ፡ የማይገባ ፡ ነገር ፡ ተናገርሁ ።

፭ ፡ ወእቤ ፡ በልሳንየ ፡ ንግረኒ ፡ እግዚኦ ፡ ፍጻሜየ ።

በልቡናዬ ፡ አስቤ ፡ በቃሌ ፡ የዘመኔን ፡ ፍጻሜ ፡ ንገረኝ ፡ አልሁ ።

ምንት ፡ እማንቱ ፡ ኍልቆን ፡ ለመዋዕልየ ።

የዘመኔ ፡ ልክ ፡ ቍጥር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ።

ወከመ ፡ ኣእምር ፡ ለምንት ፡ እጸንሕ ፡ አነ ።

ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እላለኍ ፡ ማለት ፡ አነግሥህ ፡ የለምን ፡ ቢለው ፡ ከመንግሥት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ለምን ፡ እላለሁ ። ኢዮ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ።

፮ ፡ ናሁ ፡ ብሉያተ ፡ ረሰይኮን ፡ ለመዋዕልየ ።

እንሆ ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ መልቶኛል ፡ ከመንግሥት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ለምን ፡ እላለሁ ፡ አታነግሠኝና ፡ አላርፍምን ።

ወእካልየኒ ፡ ወኢከመ ፡ ምንት ፡ በቅድሜከ ።

ስንኳን ፡ መንግሥቴ ፡ ሰውነቴ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ኢምንት ፡ ነው ። አንድም ፡ (ወእቤ ፡ በልሳንየ) ፡ የዘመኔን ፡ ፍጻሜ ፡ ንገረኝ ፡ (ምንት ፡ እማንቱ) ፡ የዘመኔ ፡ ልክ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ። ሰብዓ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ የለምን ፡ ቢለው ፡ (ከመ ፡ አእምር) ፡ እንከያ ፡ ከሞት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ለምን ፡ እላለኍ ፡ የማይገባ ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ነው ። (ናሁ ፡ ብሉያተ) ፡ እነሆ ፡ ዘመኔን ፡ በመከራ ፡ ፈጸምኸው ። (ወእካልየኒ) ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ኢምንት ፡ ሰውነቴ ፡ ለመንግሥት ፡ በቅቷል ።



2014 04 17

ወባሕቱ ፡ ከንቱ ፡ ኵሉ ፡ ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕ
ያው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ኢምንት ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ አይ
ደለሁም ። ሰው ፡ ኁሉ ፡ ኢምንት ፡
ነው ። ኢሳ ፡ ፵፲፯ ።

፯፣ ወከመ ፡ ጽላሎት ፡ ያንሶሱ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ይመላለ
ሳል ። ጥላ ፡ ጢት ፡ ሰባ ፡ ሰማኒያ ፡
ክንድ ፡ ይሆናል ። በቀትር ፡ ጊዜ ፡
ከዚህ ፡ ደረሰ ፡ አይባልም ፡ ሰውም ፡
ታይቶ ፡ ይጠፋልና ።

ወባሕቱ ፡ ከንቶ ፡ ይትሀወኩ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ መሆን ፡ ሳለ ፡
እናኑር ፡ እንክበር ፡ በማለት ፡ ይታ
ወከሉ ።

ይዘግቡ ፡ ወኢየአምሩ ፡ ለዘያስተጋብኡ ።

በሪቅ ፡ በጎታ ፡ በጎተራ ፡ ይሰበስባሉ ።
(ወኢየአምሩ ፡ ዘያስተጋብኡ) ፡ የሚ
ሰበስቡትን ፡ የገንዘባቸውን ፡ ልክ ፡
አያውቁትም ። አንድም ፡ ለዘያስተጋ
ብኡ) ፡ በዪውን ፡ አያውቁትም ፡ አን
በጣ ፡ ይበላው ፡ በረዱም ፡ ይመታው ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ይበሉትም ፡ አይበሉ
ትም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አያውቁም ። መክ ፡
፱ ፡ ፳፰ ። ሲራ ፡ ፲፱ ፡ ፱-፲፩ ። ኢዮ ፡ ፲፭ ፡ ፯ ።
ኤር ፡ ፲፯-፲፩ ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፲፰ ።

፯፣ ወይእዜኒ ፡ መኑ ፡ ተስፋየ ፡ አኮኑ ፡ እግዚአ
ብሔር ።

አሁንስ ፡ አለኝታዬ ፡ ማን ፡ ነው ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ አይደለምን ።

ወትእግሥትየኒ ፡ እምኀቤከ ፡ ውእቱ ፡ ኢዮ ፡ ፲፯ ።

፲፩ ፡ ትእግሥቴም ፡ ከንተ ፡ ዘንድ ፡ ይ
ደረግልኛል ፡ ይታዘዝልኛል ።

፰፣ ወእምኵሉ ፡ ኃጢአትየ ፡ አድኅንከኒ ።

ኃጢአት ፡ ሠርቼ ፡ ከገኘኝ ፡ መከራ ፡
ሁሉ ፡ አዳንኸኝ ።

ወረሰይከኒ ፡ ፅዕለተ ፡ ለአብዳን ።

እስከዚያውም ፡ ድረስ ፡ የነሳአል ፡ መ
ዘበቻ ፡ አደረግኸኝ ።

፱፣ ተፀመምኩ ፡ ወኢከሠትኩ ፡ አፉየ ።

ሲሞን ፡ ኢያሶን ፡ ሊገድልህ ፡ መጣ ፡
ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ምነው ፡ እኔ ፡ እንዳልል ፡
ዝም ፡ አልጉ ።

እስመ ፡ አንተ ፡ ፈጠርከኒ ።

አንተ ፡ ዕጉሥ ፡ ባሕርይ ፡ አድርገኸ ፡
ፈጥረኸኛልና ፤ አንድም ፡ ዕጉሥ ፡ ባሕ
ርይ ፡ አንተ ፡ ፈጥረኸኛልና ፡ የጌታ
ውን ፡ አመክከት ፡ ሎሌው ፡ ይመለከ
ት ፡ እንዲል ።

፲፣ አርሕቅ ፡ እምኔየ ፡ መቅሠፍተከ ።

መዓትህን ፡ ኁሉ ፡ ከኔ ፡ አርቅልኝ ።

እስመ ፡ እምዕንዐ ፡ እዴከ ፡ ኀለቁ ፡ አነ ።

ከፅደ ፡ መዓትህ ፡ ፅናት ፡ የተነሣ ፡ በመ
ከራው ፡ ተፈጽሜአለኁና ።

፲፩፣ በተግሣፅከ ፡ በአንተ ፡ ኃጢአቱ ፡ ተዘለፍኮ ፡
ለሰብእ ።

ፈርደህ ፡ ዳዊትን ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡
ዘለፍኸው ።

ወመሰውከ ፡ ከመ ፡ ሣሬት ፡ ለነፍሱ ።

ሰውነቱን ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ አቀለጥ
ሃት ፡ ሸረሪት ፡ አጥንት ፡ ጉልጥምት ፡
የላትም ፡ ከእሳት ፡ የገባች ፡ እንደሆን ፡
ቀልጣ ፡ ታልቃለች ፤ እሱም ፡ ባለ ፡ መ
ከራ ፡ ኁኗልና ፤ አንድም ፡ ወመሰከ ፡
ከመ ፡ ፈትለ ፡ ሣሬት ፡ ለነፍሱ ፡ ይላል ፡
ሰውነቱን ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ድር ፡ አ
ቀጠንሃት ፤ አንድም ፡ ሰሐብከ ፡ አቅረ
ብከ ፡ ሲል ፡ ነው ። መሰኩከ ፡ ይሁዳ ፡
መንገሴየ ፡ እንዲል ፡ ሰሐብኩከ ፡ አቅ
ረብኩከ ፡ ሲል ።

ወባሕቱ ፡ ከንቶ ፡ ይትሀወኩ ፡ ኵሉ ፡ ሰብዕ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ድር ፡ መ
ሆን ፡ ሳለ ፡ ሰው ፡ ኁሉ ፡ እናኑር ፡ እና
ኑር ፡ እናብዛ ፡ በማለት ፡ በከንቱ ፡ ይ
ታወከሉ ።

፲፪፣ ስምዓኒ ፡ እግዚኦ ፡ ጸሎትየ ፡ ወስዕለትየ ።

አቤቱ ፡ ፍጹም ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወአጽምአኒ ፡ አንብዕየ ፡ ወኢትጸመመኒ ።

አልቅሼ ፡ የለመንኩህንም ፡ ልመና
ዬን ፡ ስማኝ ፤ አንድም ፡ ዕንቤን ፡ አፀ
ማኝ ፡ ማለት ፡ እንዳላለቅስ ፡ አድርገኝ ።

እስመ ፡ ፈላሲ ፡ አነ ፡ ውስተ ፡ ምድር ።

እኔ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስደተኛ ፡ መጻ
ተኛ ፡ ነኝና ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፲፫ ።

ወነግድ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ አበውየ ፡ ዘፍ ፡ ፳፫ ፡ ፬ ፡ ግፃ ።

እንዳባቶቼ ፡ እንደ ፡ አብርሃም ፡ እን
ደ ፡ ይስሐቅ ፡ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ ስደ
ተኛ ፡ መፃተኛ ፡ ነኝና ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

፲፫፣ ስሕተኒ ፡ ከመ ፡ አዕርፍ ።

ከመከራ ፡ ሥጋ ፡ አርፍ ፡ ዘንድ ፡ በመ
ንግሥት ፡ አሳርፈኝ ።

ዘእንበለ ፡ እሑር ፡ ኀበ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ኢዮ ፡ ፯ ፡ ፱-፲ ።

ከሔድኁ ፡ ወደማልመለስበት ፡ ወደ ፡
ሞት ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ሳልሔድ ፡ አ
ንድም ፡ (እስመ ፡ ፈላሲ) ፡ እኔ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ ስደተኛ ፡ ነኝና ፡ (ወንግድ) ፡
አዳዊት ፡ ለምንት ፡ ትከውን ፡ ፈላሲ ፡
ብትለው ፡ የኔማ ፡ ፍልስት ፡ እንዳባ
ቶቼ ፡ የግብር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የእግር ፡
ነውን ፡ ብሎ ፡ ይመልስልሃል ፡ ብሎ ፡
ወስዶታል ፤ (ስሕተኒ) ፡ ከኃጢአት ፡
አርፍ ፡ ዘንድ ፡ በንስሐ ፡ አሳርፈኝ ፡
አንድም ፡ ከመከራ ፡ ነፍስ ፡ ዐርፍ ፡ ዘ
ንድ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አሳርፈ
ኝ ፡ (ዘእንበለ ፡ እሑር) ፡ ወደማልመ
ለስበት ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡
ሳልወርድ ፡ ጽ-ጽ፩ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲ ።

## መዝሙር ፡ ፴፱ ።

፩፣ ፀኒሖ ፡ ፀናሕክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ስለትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ የምዕመ
ናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ በጸሎት ፡ በቅኖና ፡
ደጅ ፡ ጸናኁ ።

ሰምዓኒ ፡ ወተመይጠኒ ።

ከቁጥዓ ፡ ወደ ፡ ትዕግሥት ፡ ከመዓት ፡

ወደምሕረት ፡ ተመልሶ ፡ ልመናዬን ፡ ሰማኝ ፡ እንድም ፡ ልመናዬን ፡ ሰምቶ ፡ ከቁጥዓ ፡ ወደ ፡ ትዕግሥት ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ተመለሰልኝ ።

፱ ፡ ወአውፅኣኒ ፡ እምኅዘቅተ ፡ ኀርትምና ።

ጥፋት ፡ ካለበት ፡ ዓዘቅት ፡ ማለት ፡ ከባቢሎን ፡ እንድም ፡ በባቢሎን ፡ ካገኘኝ ፡ መከራ ፡ አወጣኝ ፡ እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ናቸው ።

ወእምፅቡር ፡ እምዓም ።

ከረግረጉ ፡ ጭቃ ፡ አውጣኝ ፡ ይህ ፡ ረግረግ ፡ ወገብ ፡ ይዞ ፡ እንዲያስቀር ፡ ከፅኑ ፡ መከራ ፡ አዳነኝ ፡ እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ ናቸው ። በቦታ ፡ አርቀዋቸዋል ፡ መከራ ፡ አፅንተውባቸዋል ፡ ዘመን ፡ አብዝተውባቸዋልና ።

ወአቀሞን ፡ ውስተ ፡ ኰኵሕ ፡ ለእግርየ ።

ሕዋሳቱን ፡ እንድም ፡ ወገኖቹን ፡ ከመከራ ፡ አውጥቶ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ አኖራቸው ። እንድም ፡ እግሮቹን ፡ በምስቱ ፡ በስድስቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ እንዲሔዱ ፡ አደረጋቸው ። እንድም ፡ ብዕለ ፡ አሕዛብን ፡ ሰጥቶ ፡ አከበረኝ ። እንድም ፡ በሁለቱ ፡ ጽላት ፡ ዕብን ፡ በተጻፉት ፡ ሕግጋት ፡ አፀናኝ ።

ወዐፅንዖን ፡ ለመከየድየ ።

መከየደ ፡ ልቡናዬን ፡ በሕጉ ፡ አፀናቸው ።

፫ ፡ ወወደየ ፡ ውስተ ፡ አፉየ ፡ ስብሐተ ፡ ሐዲስ ፡ ኢሳ ፡ ፵፩ ፡ ፲፪ ።

ባንደበቴ ፡ እንግዳ ፡ ምስጋና ፡ እንዳመሰግነው ፡ አደረገኝ ። ግብሩ ፡ አዲስ ፡ ስለሆነ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ምስጋናውስ ፡ ጥንተ ፡ ምስጋናው ፡ ነው ።

ስብሐቲሁ ፡ ዘእምኀቤሁ ፡ ወውዳሴሁ ፡ እምዚአሁ ፡ እንዲል ።

ስብሐቲሁ ፡ ለአምላክነ ።

ስብሐት ፡ ሐዲስም ፡ ያልሁት ፡ የፈጣሪያችን ፡ ምስጋና ።

እንድም ፡ (ጸኒሐ ፡ ጸናሕክዎ ፡ ለእግዚአብሔር) ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ከምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በጸሎት ፡ በቀኖና ፡ ደጅ ፡ ጠናሁት ፡ (ሰምዓኒ) ፡ ከቁጣ ፡ ወደ ፡ ትዕግሥት ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ተመልሶ ፡ ልመናዬን ፡ ሰማኝ ። (ወሰምዓኒ) ፡ የልመናዬን ፡ ነገር ፡ ሰማኝ ፡ (ወአውፅዓኒ) ፡ ፅኑ ፡ ፍዳ ፡ ካለበት ፡ ከሲኦል ፡ አወጣኝ ። እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ በሐልዮ ፡ ፍዳ ፡ የተያዙ ፡ ናቸው ። (ወእምፅቡር) ፡ ከገሐነም ፡ አወጣኝ ። እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ በነቢብ ፡ በገቢር ፡ ፍዳ ፡ የተያዙ ፡ ናቸው ፡ (ወአቀሞን) ፡ አፅጋረ ፡ ልቡናዬን ፡ በሕግ ፡ አፀናቸው ፡ (ወአፅንዖን) ፡ መከየደ ፡ ነፍሴን ፡ በተድላ ፡ ነፍስ ፡ አፀናቸው ፡ (ወወደየ) ፡ ቃለ ፡ ሥጋ ፡ ከነ ፡ ብዬ ፡ አንደበቴን ፡ መልቼ ፡ እንዳመሰግነው ፡ አደረገኝ ። (ስብሐቲሁ) ፡ አዲስም ፡ ያልሁት ፡ ፈጣሪያችን ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ከነ ፡ ተብሎ ፡ የሚመሰገነው ፡ ምስጋና ፡ ነው ።



ይርአዩ ፡ ብዙኃን ፡ ወይፍርሁ ።

ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ይህን ፡ አይተው ፡ ይፍሩ ። እንድም ፡ አይተው ፡ ይፈሩ ፡ ዘንድ ፡ አፅንአን ።

ወይትወከሉ ፡ በእግዚአብሔር ።

በእግዚአብሔር ፡ ይመኑ ።

፱ ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትውክልቱ ።

እምነቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የሆነለት ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፯ ።

ወዘኢነጸረ ፡ ውስተ ፡ ከንቱ ፡ ወውስተ ፡ መዓት ፡ ወሐሰት ።

አንድ ፡ ወገን ፡ ወደ ፡ ከንቱ ፡ ጣዖት ፡ ያልተመለከተ ፡ ማለት ፡ ጣዖት ፡ ያላመለከ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። ከንቱ ፡ አለው ፡ በከንቱ ፡ ያመልኩታልና ። መዓት ፡ አለው ፡ መዓት ፡ የሚያመጣ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መዓተ ፡ አርዮስ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ ጣዖት ፡ ብታመልክ ፡ አምልክ ፡ ያለዝያ ፡ ግን ፡ እንጣልሃለን ፡ (ወእምሐሰት) ፡ ጣዖት ፡ ብታመልክ ፡ እንሾምሃለን ፡ እንሸልምሃለን ፡ ከማለታቸው ፡ የተነሣ ፡ ጣዖቱን ፡ ያላመለከ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

፭ ፡ ብዙኀ ፡ ገበርከ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ መንክረከ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ተአምራትህን ፡ አብዝተህን ፡ አብዝተህ ፡ ሠራህ ።

ወአልቦ ፡ ዘይመስሎ ፡ ለሕሊናከ ።

ፍርድህንም ፡ የሚመስለው ፡ የለም ።

አይደለዉ ፡ ወነገርኩ ፡ ወበዝኁ ፡ እምኍልቆ ።

ተአምራትን ፡ ፈጽሚ ፡ ነገርኹ ፡ ከቁጥር ፡ በዛ ።

፮ ፡ መሥዋዕተ ፡ ወቍርባነ ፡ ኢፈቀድከ ።

በኃጢአት ፡ ሳሉ ፡ ኃጢአት ፡ ስለ ፡ ማስተሥረይ ፡ የሚሠዉትን ። እንድም ፡ ከኃጢአት ፡ ቅሉ ፡ ነጽተው ፡ ኃጢአት ፡ ስለ ፡ ማስተሥረይ ፡ የሚሠዉትን ፡ መሥዋዕት ፡ አሪቱን ፡ ቍርባኑ ፡ አሪቱን ፡ አልወደድሁም ። ኢፈቀድከ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ አልወደድህም ፡ አልኀ ። ኤር ፡ ፯ ፡ ፳፪ ።

ሥጋከ ፡ አንጽሕ ፡ ሊተ ።

አላ ፡ ያለበት ፡ ነው ። ንጹሕ ፡ ሁን ፡ አልኸኝ ፡ እንጂ ።

መሥዋዕተ ፡ ዘበእንተ ፡ ኃጢአት ፡ ኢሠመርከ ።

በኃጢአት ፡ ሳሉ ፡ ኃጢአት ፡ ስለ ፡ ማስተሥረይ ፡ የሚሠዉትን ፡ መሥዋዕት ፡ አልወደድኍም ። ኢሠመርከ ፡ አልወደድህም ፡ አልኀ ።

፯ ፡ ውእተ ፡ ጊዜ ፡ እቤ ፡ ነየ ፡ መጻእኩ ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ እሽ ፡ በጀ ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ ንጽሕና ፡ ተመለስኍ ።

ውስተ ፡ ርእሰ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽሕፈ ፡ በእንቲአየ ።

የኔ ፡ ነገር ፡ ሥጋከ ፡ አንጽሕ ፡ ሊተ ፡ ተብሎ ፡ ከሁለቱ ፡ መሥመር ፡ በላይ ፡ ተጽፏል ።

እንድም ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ርእስ ፡ ይላል ። የነገሥታት ፡ አለቃ ፡ በሚሆን ፡

2014 04 17

በዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ሥጋከ ፡ እንጽሕ ፡ ሊተ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ።

እንድም ፡ ውስተ ፡ ርእሰ ፡ መጽሐፍ ። የመጻሕፍት ፡ አበጋዝ ፡ በምትሆን ፡ በ ኦሪት ። እንድም ፡ መጽሐፈ ፡ ርእስ ፡ የመሰፍንት ፡ አለቃ ፡ በሚሆን ፡ በሙ ሴ ፡ መጽሐፍ ፡ ንጹሐን ፡ ሁናችኊ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ። ሚክ ፡ ፮ ፡ ፮ ። ዕብ ፡ ፲ ፡ ፱—፱ ።

፰ ፡ ከመ ፡ እንግር ፡ ፈቃደከ ፡ መከርኩ ፡ እም ኀቤየ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ወድደህ ፡ የሠራሃ ትን ፡ ሕግ ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ድኊ ። ዮሐ ፡ ፱ ፡ ፴፱ ። ፮ ፡ ፴፰-፵ ።

እንድም ፡ (መሥዋዕት ፡ ወቍርባነ ፡ ኢ ፈቀድኩ) ፡ በኀጢአት ፡ ሳሉ ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ማስተሥረይ ፡ የሚሠዉትን ፡ መ ሥዋዕት ፡ ኦሪትን ፡ አልወደድሁም ፡ (ሥጋከ ፡ እንጽሕ ፡ ሊተ) ፡ አላ ፡ አልበ ስከኒ ፡ ሥጋ ፡ ብሎ ፡ ሊቁ ፡ ወስዶታል ። ሰው ፡ ሁን ፡ ሥጋ ፡ ልበስ ፡ አልከኝ ፡ እ ንጂ ። (መሥዋዕት) ፡ በኀጢአት ፡ ሳሉ ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ማስተሥረይ ፡ የሚሠዉትን ፡ መሥዋዕት ፡ አልወደ ድሁም ። (ውእተ ፡ ጊዜ) ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እሽ ፡ በጀ ፡ ብዬ ፡ ሰው ፡ ሆንሁ ፡ ሥጋ ፡ ለበስሁ ፡ (ውስተ ፡ ርእሰ ፡ መጽሐፍ) ፡ የኔ ፡ ነገር ፡ አላ ፡ አልበስከኒ ፡ ሥጋ ፡ ተብሎ ፡ ከሁለቱ ፡ መስመር ፡ በላይ ፡ ተጽፏል ። እንድም ፡ የመጻሕፍት ፡ አበጋዝ ፡ በምትሆን ፡ በኦሪት ፡ ስቅ ልተ ፡ ትሬእያ ፡ ለሕይወትከ ፡ እስራኤ ል ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ። እንድም ፡ መ ጽሐፈ ፡ ርእስ ፡ የነገሥታት ፡ አለቃ ፡ በሚሆን ፡ በዳዊት ፡ መዝሙር ፡ አላ ፡ አልበስከኒ ፡ ሥጋ ፡ ተብሎ ፡ የመሳፍ ንት ፡ አለቃ ፡ በሚሆን ፡ በሙሴ ፡ መ ጽሐፍ ፡ በኦሪት ፡ ስቅልተ ፡ ትሬእያ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ። ዘኍ ፡ ፳፩ ፡ ፰-፱ ። (ከመ ፡ እንግር) ፡ ዳዊት ፡ እንግር ፡ ያ ለውን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እግበር ፡ ብሎታል ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እግበር ፡ ያለውን ፡ ሊቁ ፡ እመጡ ፡ ብሎታል ። መጥዎተ ፡ ርእስን ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ ወደድኊ ። ዕብ ፡ ፲ ፡ ፱ ። ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፵፪ ።

፱ ፡ ወሕግከኒ ፡ በማዕከለ ፡ ከርሥየ ።

ጽሑፍ ፡ ያለበት ፡ ነው ፤ ሕግህ ፡ በል ቡናዬ ፡ ተጽፎ ፡ ይኖራል ፡ ማለት ፡ አ ስበዋለኊ ።

፲ ፡ ዜኖኩ ፡ ጽድቀከ ፡ ለማኅበር ፡ ዐቢይ ።

ዜነውኩም ፡ ይላል ፡ ቸርነትህን ፡ ለ ብዙ ፡ ጉባዔ ፤ እንድም ፡ በማኅበር ፡ ይ ላል ፡ በብዙ ፡ ጉባዔ ፡ ነገርኊ ።

ወናሁ ፡ ኢከላዕኩ ፡ ከናፍርየ ።

እንደበቴን ፡ ቸርነትህን ፡ ከመንገር ፡ አልከለከልኩም ።

እግዚኦ ፡ ለሊከ ፡ ተአምር ፡ ጽድቅየ ።

አቤቱ ፡ እውነተኛነቴን ፡ አንተ ፡ ታ ውቀዋለህ ።

፲፩ ፡ ወኢኀባእኩ ፡ ውስተ ፡ ልብየ ፡ ርትዓከ ።

ርትዓ ፡ እምላክነትህን ፡ ሕግህን ፡ በል ቡናዬ ፡ አልሠወርኹም ።

ወነገርኩ ፡ አድኅኖተከ ።

ትድግናህን ፡ ነገርኊ ፡ አስተማርኊ ።

ወኢሠወርኩ ፡ ግህለከ ፡ ወምሕረተከ ፡ እማኅበር ፡ ዐቢይ ።

ይቅርታህን ፡ ቸርነትህን ፡ ከብዙ ፡ ጉ ባዔ ፡ አልሠወርሁም ።

፲፪ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ኢታርሕቅ ፡ ግህለከ ፡ እም ኔየ ።

አቤቱ ፡ አንተም ፡ ቸርነትህን ፡ ከኔ ፡ አ ታርቅ ።

ምሕረትከ ፡ ወጽድቅከ ፡ ዘልፈ ፡ ይርከባኒ ።

ይቅርታህ ፡ ቸርነትህ ፡ ኊል ፡ ጊዜ ፡ ያ ግኙኝ ፡ መገናኘት ፡ የጋራ ፡ ከሆነ ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ላግኛቸ ው ፡ ሲል ፡ ነው ። ገንት ፡ ይረክቦ ፡ ለ ብእሲ ፡ እንዲል ።

፲፫ ፡ እስመ ፡ ረከበተኒ ፡ ዕኪት ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡ ኊልቈ ።

ሥፍር ፡ ቊጥር ፡ የሌላት ፡ መከራ ፡ አ ግኝታኛለችና ።

ወተረከባኒ ፡ ኀጣውእየ ፡ ወስዕንኩ ፡ ነጽሮ ።

በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ የሠራኊ ቸው ፡ ኀጣውእ ፡ በፍዳ ፡ ተገናኙኝ ። ኀልቆቶ ፡ መቍጠሩ ፡ ተሳነኝ ፤ ተወ ከሮቶ ፡ ፍዳ ፡ መቀበሉ ፡ ተሳነኝ ።

ወበዝኁ ፡ እምስእርተ ፡ ርእስየ ።

ከራስ ፡ ጸጉሬ ፡ በዛ ።



ልብየኒ ፡ ኀደገኒ ።

አእምሮዬም ፡ ተለየኝ ።

፲፬ ፡ ሥምር ፡ እግዚኦ ፡ ከመ ፡ ታድኅነኒ ።

አቤቱ ፡ ታድነኝ ፡ ዘንድ ፡ ፈቃድህ ፡ ይሁን ።

እግዚኦ ፡ ነጽር ፡ ውስተ ፡ ረዲኦትየ ። መዝ ፡ ፸፱ ፡ ፩ ።

አቤቱ ፡ እኔን ፡ ወደ ፡ መርዳት ፡ እይ ፡ ተመልከት ።

፲፭ ፡ ይትኀፈሩ ፡ ወይኅሠሩ ፡ ኅቡረ ፡ እለ ፡ ይፈ ቅዱ ፡ ያዕትትዋ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ በሞት ፡ ሊያርቋት ፡ የሚ ወድዱ ፡ ሁሉ ፡ ባንድነት ፡ ፈጽመው ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ።

ለይግብኡ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ ወይትኀፈሩ ፡ እለ ፡ ይ ፈቅዱ ፡ ሊተ ፡ እኩየ ።

በኔ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሊያመጡብኝ ፡ የሚ ወድዱ ፡ ሁሉ ፡ አድኅ ፡ እነስ ፡ አድር ፡ እነስ ፡ ይሁኑ ፡ ድል ፡ ተነስተው ፡ እኔ ፡ ከመከተል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ይቅሩ ።

፲፮ ፡ ወይትፈደዩ ፡ በጊዜ ፡ ኀፍረቶሙ ፡ እለ ፡ ይብሉኒ ፡ እንቋዕ ፡ እንቋዕ ። ኢሳ ፡ ፶፰-፲፫ ።

ትሩፍን ፡ አይመስሉ ፡ መስሎ ፡ አይ ሆኑ ፡ ሆኖ ፡ አየነው ፡ የሚሉ ፡ ሁሉ ፡ እንድም ፡ እሰይ ፡ እሰይ ፡ በሚሉበት ፡ ጊዜ ፡ ፍዳቸውን ፡ ይቀበሉ ።

፲፯ ፡ ለይትፌሥሑ ፡ ወይትሐሠዩ ፡ ብከ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ የኃሥሥዎ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ አንተን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የሚሹህ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ባንተ ፡ አምነው ፡ ፀንተው ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ።

2014 04 17

ወይበሉ ፡ ዘልፈ ፡ ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ዘወትር ፡ ገናና ፡ አም ላክ ፡ ነው ፡ ይበሉ ።

እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ አድኅኖተከ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ትድግናህን ፡ ጉል ፡ ጊዜ ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ ጉሉ ፡ ጉል ፡ ጊዜ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ገናና ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ይበሉ ።

፲፯ ፡ አንሰ ፡ ነዳይ ፡ ወምስኪን ፡ አነ ።

ትሩፍ ፡ ጉል ፡ ጊዜ ፡ ማርዳት ፡ ተቀ ግተህ ፡ አትወጣምን ፡ ትለኝ ፡ እንደ ሆን ፡ እኔስ ፡ ተቀግቼ ፡ መውጣት ፡ አይ

ቻለኝም ፡ ድኃ ፡ ችጋረኛ ፡ ነኝ ።

ወእግዚአብሔር ፡ ይሄሊ ፡ ሊተ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቅል ኛል ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያውቅል ል ፡ ያውቅልኛል ፡ እንጂ ፡ አንሰ ፡ ነዳይ ።

ረዳእየ ፡ ወመድኃንየ ፡ አንተ ፡ አምላኪየ ፡ ወኢ ትጐንዲ ።

ረዳቴ ፡ ድኅነቴንም ፡ የምታደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ቢሆንም ፡ አት ዘግይ ፡ ቶል ፡ አትበል ። አትዘግይ ፡ ቶል ፡ አትበል ፡ እንጂ ፡ ረዳቴ ፡ አንተ ፡ ነህ ። መዝ ፡ ፴፱ ፡ ፩—፭ ።

## መዝሙር ፡ ፵ ።

፩ ፡ ብፁዕ ፡ ዘይሌቡ ፡ ላዕለ ፡ ነዳይ ፡ ወምስኪን ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ። ለነዳ ይ ፡ ወለምስኪን ፡ የሚያስብ ፡ ሕዝቅ ያስ ፡ እንድም ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ነው ። እንድም ፡ ዘላዕለ ፡ ነዳ ይ ፡ ወምስኪን ፡ ይላል ። በነዳይ ፡ በም ስኪን ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መከራ ፡ አስበ ፡ ምግቡን ፡ በከርሠ ፡ ርኅብን ፡ መጠ ጡን ፡ በጕርዔ ፡ ዕሙዓን ፡ ልብሱን ፡ በዘባነ ፡ ዕሩቃን ፡ የሚያኖር ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

እምዕለት ፡ ዕኪት ፡ ያድኅኖ ፡ እግዚአብሔር ። ምሳ ፡ ፲፱ ፡ ፳፯ ።

እንዲህ ፡ ያለዉን ፡ ሰው ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ከዕለተ ፡ ሞት ፡ ከዕለተ ፡ ምጽ አት ፡ ያድነዋል ። ገላ ፡ ፱—፲፯ ።

፪ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዓቅቦ ፡ ወያሐይዎ ፡ ወያበ ጽዖ ፡ ዲበ ፡ ምድር ።

እግዚአብሔር ፡ ከመከራው ፡ ጠብቆ ፡ ያድነዋል ፡ ዕፀ-ብ ፡ ዕፀ-ብ ፡ እንዲባል ፡ ያደርገዋል ። ሦስት ፡ አርእስት ፡ ተና ገረ ፡ ለሦስቱም ፡ ያመጣል ።

ወኢያገብዖ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ጸላኢሁ ።

በጠላቱ ፡ እጅ ፡ አያስይዘውምና ፡ የዓ ቅበ ፡ ላለው ።

፫ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረድኦ ፡ ውስተ ፡ አራተ ፡ ሕማሙ ።

ታሞ ፡ ሳለ ፡ በመኝታው ፡ ይረዳዋልና ። ያሐይዎ ፡ ላለው ።

ወይመይጥ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎ ፡ ምስካቢሁ ፡ እምደዌሁ ።

ከደዌው ፡ አድኖ ፡ ምስካበ ፡ ጥኢና ውን ፡ ይመልስለታል ። እንድም ፡ ከ



ደዌው ፡ የተነሣ ፡ የተኛበትን ፡ ምንጣ ፉን ፡ ይለውጥለታል ። ለወዘት ፡ ይመ ቻው ፡ ብለው ፡ አልጋውን ፡ ገልብጠ ው ፡ ያስተኙታልና ፡ ያበዕዖ ፡ ላለው ።

፬ ፡ አንሰ ፡ እቤ ፡ እግዚኦ ፡ ተሣሀለኒ ።

አቤቱ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ የሚያበቃ ፡ ሥራ ፡ የለኝምና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ አ ልጉ ።

ወሥረይ ፡ ላቲ ፡ ለነፍስየ ፡ እስመ ፡ አበስኩ ፡ ለከ ።

አንተን ፡ በድያለሁና ፡ ሰውነቴን ፡ ይ ቅር ፡ በላት ።

፭ ፡ ጸላእትየሰ ፡ ዕኩየ ፡ ይቤሉ ፡ ላዕሌየ ። ማዕዜ ፡ ይመውት ፡ ወይሠዓር ፡ ስሙ ።

ጠላቶቼ ፡ ግን ፡ መቼ ፡ ይሞታል ፡ ስ ሙስ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ። እንድም ፡ ከሰ ው ፡ ተለይቶ ፡ መቼ ፡ ይጠፋል ፡ እያ ሉ ፡ በኔ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይናገራሉ ።

፮ ፡ ይባእ ፡ ወይርአይ ፡ ዘከንቶ ፡ ይነብብ ።

የእኅቴ ፡ ልጅ ፡ ጠሉሽ ፡ የኔን ፡ መፈ ወስ ፡ ገብቶ ፡ ይይ ፡ ደስ ፡ አይበለው ።

ልቡ ፡ አስተጋብአ ፡ ኃጢአተ ፡ ላዕሌሁ ።

ልቡናው ፡ ዕዳ ፡ የሚሆንበትን ፡ ነገር ፡ ሰበሰበ ።

ይወፅእ ፡ አፍኣ ፡ ወይትናገር ፡ ወየኀብር ፡ ላዕሌየ ።

ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወጣል ። የኔን ፡ ነገር ፡ ይናገራል ። ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ ይተባበ ርብኛል ። እንድም ፡ ያኅብር ፡ ይላል ። አሁን ፡ የሚድን ፡ ይመስላችኋልን ። የሞት ፡ ቍል ፡ ተኵሏል ፡ ይልቅስ ፡

የሚሆናችሁን ፡ እንግሙ ፡ እያለ ፡ ሕ ዝቡን ፡ ያሳብርብኛል ። ዮሐ ፡ ፪—፯ ።

ወይትቃጸቡኒ ፡ ኵሎሙ ፡ ጸላእትየ ።

ጠላቶቼ ፡ ሁሉ ፡ እውነቱ ፡ ነው ፡ የሞ ት ፡ ኵል ፡ ተኵሏል ፡ እይድንም ፡ እ ያሉ ፡ ይጠቃቀሱብኛል ።

ወይመክሩ ፡ ዕኩየ ፡ ላዕሌየ ። ሉቃ ፡ ፲፩—፶፫ ።

ሌላ ፡ እናንግሥ ፡ እያሉ ፡ ክፉ ፡ ክፉ ፡ ይመክሩብኛል ።

፯ ፡ ነገረ ፡ ጌጋይ ፡ አውፅኡ ፡ ላዕሌየ ።

በኔ ፡ ዕዳ ፡ የሚሆንብኝን ፡ ነገር ። እን ድም ፡ ዕዳ ፡ የሚሆንባቸውን ፡ ነገር ፡ በኔ ፡ ይናገራሉ ።

ዘኖመሰ ፡ ኢይትቀሐው ፡ እንከ ።

እኒህ ፡ ሞኞች ፡ ተላሎች ፡ የተኛ ፡ ሰ ው ፡ አይነሳምን ፡ እንደዚሁስ ፡ ሁሉ ፡ የታመመ ፡ ሕዝቅያስ ፡ አይድንምን ፡ እንደታመመ ፡ ይቀራልን ።

፰ ፡ ብእሲ ፡ ሰላምየ ፡ ዘቦቱ ፡ እትአመን ። ኢ ዮ ፡ ፴-፲፱ ።

እነሳቸውስ ፡ እነሳቸው ፡ ናቸው ፡ ፍቅሬ ፡ ወዳጄ ፡ የእኅቴ ፡ ልጅ ፡ ጠሉሽ ። አብ ፡ ፩-፯ ።

ዘይሴሰይ ፡ እክልየ ፡ አንሥአ ፡ ሰኰናሁ ፡ ላዕሌየ ።

ግብረ ፡ በላዬ ፡ ጠሉሽ ፡ ሰኰናውን ፡ አነሣብኝ ። ወጥቶ ፡ ሲሔድ ፡ ረግጦት ፡ ሔዷልና ። እንድም ፡ ሰኰና ፡ ምክሩ ን ፡ አነሣብኝ ። ዳን ፡ ፲፩ ፡ ፴፯ ።

አንድም ፡ (ይባእ ፡ ወይርአይ ፡ ዘከንቶ ፡ ይ ነብብ) ። ከንቱ ፡ ነገርን ፡ የሚናገር ፡ ይሁዳ

የኔን፡ትንግኤ፡አይቶ፡ደስ፡አይበለው፡ (ልቡ ፡ እስተጋብአ) ፡ ልቡናው ፡ በኔ ፡ ዕዳ ፡ የሚሆንበት ፡ ነገር ፡ ሰበሰበ ። (ይ ወፅእ ፡ አፍአ) ፡ ዕኑ ፡ ጠላት ፡ እንደመ ሆኑ ፡ በሴሊት ፡ ወጥቶ ፡ የኔን ፡ ነገር ፡ ይናገራል ፡ ወፅአ ፡ በሴሊት ፡ እንዲለ ው ። ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፴ ። የጎብር ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ይተባበርብኛል ፡ ያጎብር ፡ ሕዝ ቡን ፡ ያሳብርብኛል ። (ወይትቃጸቡኒ)፡ አይሁድ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ አፍርሼ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ እሠራዋለሁ ፡ እያለ ፡ የሚዋሽ ፡ ይህ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ይጠቃቀሱብኛል ። ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፵ ። ማር ፡ ፲፭ ፡ ፳፱ ። ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴፭ ። ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፱-፳፩ ። (ወይመክሩ) ፡ እንግደለው ፡ እያሉ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይመክሩብኛል ። (ነገረ ፡ ጌጋይ) ፡ በኔ ፡ ዕዳ ፡ የሚሆንብኝን ፡ ነ ገር ፡ ይናገራሉ ። እንድም ፡ ዕዳ ፡ የሚ ሆንባቸውን ፡ ነገር ፡ በኔ ፡ ይናገራሉ ። (ዘኖመሰ) ፡ እኒህ ፡ ሞኞች ፡ ተላሎች ፡ የታመመ ፡ ሰው ፡ አይድንምን ፡ እን ደዚህስ ፡ ጉሉ ፡ የሞተ ፡ ክርስቶስ ፡ አይነሣምን ፡ እንድያው ፡ እንደ ፡ ሞ ተ ፡ ይቀራልን ፡ (ብእሴ ፡ ሰላምየ) ፡ እን ሳቸውስ ፡ እነሳቸው ፡ ናቸው ። ፍቅሬ ፡ ወዳጄ ፡ የማምነው ፡ ግብረ ፡ በላዬ ፡ ማለት ፡ እህል ፡ ትምርቴን ፡ የሚመ ገብ ፡ ይሁዳ ፡ ሲሳሳ ፡ ዓይቶት ፡ በጅሮ ንድነትን ፡ ፎሞት ፡ ከሥር ፡ እንድ ፡ ይወስድ ፡ ነበርና ፡ እየሠረቀም ፡ ያነ ሣሳ ፡ ነበርና ፡ እኮ ፡ ዘያዕሕቆ ፡ ምሒ ረ ፡ ነዳያን ፡ አላ ፡ እስመ ፡ ሠራቂ ፡

ውእቱ ፡ እንዲል ። ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፮ ። ሰኰና ፡ ምክሩን ፡ አነሳብኝ ። እንድም ፡ በቁሙ ፡ ሰኰናውን ፡ አነሣብኝ ። እንድም ፡ በ ቁሙ ፡ ሰኰናውን ፡ አነሳብኝ ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ከአይሁድ ፡ ጋራ ፡ ለመም ከር ፡ ሔደልና ። ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፳፩ ። ፲፱ ፡ ፲፰ ። ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፴፰ ፡ ፲፫-፲፯ ።

፲ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ተሣሀለኒ ፡ ወአንሥአኒ ፡ እፍ ድዮሙ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ይቅር ፡ ብለህ ፡ አድነ ኝ ፡ የበጎ ፡ ብድራት ፡ ልከፈላቸው ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ሰይፍ ፡ ገዥ ሬው ፡ ነበር ፡ አልሻረውም ።

በእንተዝ ፡ አእመርኩ ፡ ከመ ፡ ሠመርከኒ ።

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ማለት ፡ አንሥእኒ ፡ እ ፍድዮሙ ፡ ያልሁትን ፡ ስለ ፡ ተቀበል ህ ፡ ልመናዬን ፡ እንደ ፡ ተቀበልህ ፡ አ ወቅሁ ።

ወኢተፈሥሑ ፡ ጸላእትየ ፡ ላዕሌየ ።

ጠላቶቼ ፡ በኔ ፡ ደስ ፡ አላላቸውም ።

፲፪ ፡ ሊተሰ ፡ በእንተ ፡ የዋሃትየ ፡ ተወከፍከኒ ።

እኔን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ቅንነቴ ፡ በረድ ኤት ፡ ተቀበልኸኝ ።

ወአፅናዕከኒ ፡ ቅድሜከ ፡ ለዓለም ።

ለዘላለሙ ፡ በለሞዋል ፡ በመሆን ። እ ንድም ፡ በባለሟልነት ፡ አፀናኸኝ ።

፲፫ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ እስራ ኤል ።

የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ። ኢሳ ፡ ፵፫ ፡ ፩ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፷፰ ። ፯-፲፯ ።



እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን ።

ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ይኸ ውም ፡ ይሁን ፡ ይሁን ፡ ይደረግ ፡ ይደ ረግ ። እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ በአንድ ፡ ለይ ኩን ፡ ከፍሎ ፡ ተናግሮታል ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወ ለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምፅአት ፡ ከፅ ለቱ ፡ ምጽአት ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ።

አሜን ፡ በውነት ።

## መዝሙር ፡ ፵፮ ።

፩ ፡ ከመ ፡ ያፈቅር ፡ ኃየል ፡ ገበ ፡ አንቅዕተ ፡ ማያት ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ። ዋልያ ፡ የወሃ ፡ ምንጮችን ፡ እንዲወድ ፡ ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፳፭ ።

ከማሁ ፡ ታፈቅር ፡ ነፍስየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ የኔም ፡ ሰውነት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ናፈቀች ፡ ወደደች ።

፪ ፡ ፀምዓት ፡ ነፍስየ ፡ ኀበ ፡ አምላኪየ ፡ ሕያው ።

ሰውነቴ ፡ ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ ፈጣሪዬን ፡ ናፈቀች ፡ ወደደች ። እንድም ፡ ጎበን ፡ ለማውጣት ። (ከመ ፡ ያፈቅር ፡ ሃየል ፡ ኀበ ፡ አቅዕተ ፡ ማያት) ፡ ዋልያ ፡ የው ሀ ፡ ምንጮት ፡ ባሉበት ፡ መኖርን ፡ እ ንዲወደድ ። (ከማሁ) ፡ እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ የኔ ፡ ሰውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ አድሮባት ፡ በሚኖሩ ፡ በ ኢየሩሳሌም ፡ መኖርን ፡ ወደደች ፡ ና ፈቀች ። (ፀምዓት) ፡ ሰውነቴ ፡ ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ ፈጣሪዬ ፡ አድሮባት ፡ በሚ

ኖር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ መኖርን ፡ ወ ደደችና ፡ ፈቀደች ። ይህ ፡ ዋልያ ፡ እ ንደ ፡ በረኃ ፡ ፍየል ፡ እባቡን ፡ ሰንጥ ቆ ፡ ከስከሶ ፡ ይበለዋል ። ወዛ ፡ እንዳ ይጠማው ፡ ዓለት ፡ ላለት ፡ ጓሳ ፡ ለጓሳ ፡ ይሔዳል ። ወዛ ፡ የጠማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፀሐይ ፡ ሲነካው ፡ መርዙ ፡ ከአካሉ ፡ ተሰራጭቶ ፡ የሚገድለው ፡ ነውና ፡ እን ዳይሞት ፡ ነው ።

ማዕዜ ፡ እበጽሕ ፡ ወእሬኢ ፡ ገጸ ፡ ለአምላኪየ ።

ከባቢሎን ፡ ወጥቼ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መቼ ፡ እገባለሁ ። ከዚያስ ፡ ገብቼ ፡ የፈጣሪ ዬን ፡ ገጸ ፡ ምሕረቱን ፡ ገጸ ፡ ረድኤቱ ን ፡ መቼ ፡ እያለሁ ፡ እያለች ። እንድም ፡ መቼ ፡ አየዋለሁ ።

፫ ፡ ሲሳየ ፡ ኮነኒ ፡ አንብዕየ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ።

በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ዕንባዬ ፡ ም ግብ ፡ ሆነኝ ። ምግብን ፡ በጧት ፡ በማ ታ ፡ እንዲመገቡት ፡ በጧት ፡ በማታ ፡

ያለቅሳሉና ። እንድም ፡ ምግባቸውን ፡ ሲሰጧቸው ፡ እየሰደቡ ፡ እየመቱ ፡ ይሰጧቸዋል ፡ ሆድ ፡ ብሷቸው ፡ ያለቅሳሉ ፡ ከሚመገቡት ፡ ጠብ ፡ ጠብ ፡ ይልበታል ፡ አብረው ፡ ይመገቡታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

እስመ ፡ ይብሉኒ ፡ ዦሎ ፡ አግረ ፡ እይቴ ፡ ውእቱ ፡ እምኣክክ ።

ትሩፍ ፡ ፈጣሪ ፡ አለኝ ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ ፈጣሪማ ፡ ከለህ ፡ ለመቼ ፡ ይሆንሃል ፡ አያድንህምን ፡ ብለውኛልና ፡ ሲሳየ ፡ ከነኒ ። እንድም ፡ እንዲህ ፡ ብለውኛልና ።

፬ ፡ ዘንተ ፡ ተዘኪርየ ፡ ተዘዕወት ፡ ነፍስየ ፡ በላዕሌየ ።

ይህን ፡ አስቤ ፡ በኔ ፡ ያለች ፡ ሰውነቴ ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ ፈሰሰችብኝ ፡ ማለት ፡ ታወከችብኝ ፡ ኢዮ ፡ ፴ ፡ ፲፭ ።

እስመ ፡ እበውእ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ግኁደረ ፡ ስብሐት ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ።

ግዱን ፡ ከሰብዓ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ አድሮበት ፡ ወደሚኖር ፡ መመስገኛው ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እገባለሁ ። ግዱን ፡ አለ ፡ ወሰብዓ ፡ ዓሞ ፡ ሐሊቆ ፡ እትቤቀሎ ፡ ለንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ወለኵሉ ፡ ሕዝባ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ አይቀርምና ።

በቃለ ፡ አሚን ፡ ወበትፍሥሕት ፡ ደምፁ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ በዓለ ።

ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥተው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገብተው ፡ በሃይማኖት ፡ በደስታ ፡ ቃል ፡ በዓል ፡ አድርገው ፡ ሲያመሰግኑ ፡ ተሰሙ ። እንድም ፡ በቃለ ፡ ፈቃድከ ፡ በቃለ ፡ እኰቴትከ ፡ ይላል ። አንተን ፡ በማመስገን ፡ በንተ ፡ ፈቃድ ። ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ሁኖ ፡ እየታየው ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እንድም ፡ በዓል ፡ የሚያደርጉ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትወጣላችሁ ፡ ሲሉ ፡ ተሰሙ ።

፭ ፡ ለምንት ፡ ትቴክዚ ፡ ነፍስየ ፡ ወለምንት ፡ ተዘውከኒ ።

የባለዝያ ፡ ጌታ ፡ ልቡናዬ ፡ ለምን ፡ አዝነሽ ፡ ተክዘሽ ፡ ትኖሪያለሽ ። ጊዜውስ ፡ ሳይደርስ ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ልውጣ ፡ ልውጣ ፡ በማለት ፡ ለምን ፡ ታውኪኛለሽ ።

እመኒ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ እገኒ ፡ ሎቱ ።

ይህንስ ፡ ትተሽ ፡ ለሱ ፡ እንድገዛ ፡ አውቀሽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እመኚ ። እመኝ ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ ታውኪኛለሽ ።

መድኃኒ ፡ ገጽየ ፡ እምላኪየ ።

ፈጣሪዬ ፡ ፊት ፡ መከታዬ ፡ ፊት ፡ መከታዬ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነውና ።

፮ ፡ ተሐውከት ፡ ነፍስየ ፡ በላዕሌየ ።

ሰውነቴ ፡ ታወከችብኝ ፡ የቀቢፀ ፡ ተስፋ ፡ ነው ።

በእንተዝ ፡ እዜከረከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አስብሐለሁ ።

በምድረ ፡ ዮርዳኖስ ፡ በአርሞንኤም ፡ በደብር ፡ ንዑስ ።

ዮርዳኖስ ፡ አርሞንዔም ፡ ደብር ፡ ንዑስ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ቀድሞ ፡ ለአበው ፡



ያደረግኸውን ፡ ቸርነትህን ፡ ለኔም ፡ ታደርግልኛለህ ፡ ብዬ ፡ ኤግሎም ፡ ዓሥራ ፡ ስምንት ፡ ኵሳርስዓም ፡ ዓሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ዘመን ፡ ገገዙ ፡ ተዋቾቸው ፡ አልፎላቸው ፡ ደስ ፡ ብሏቸዋል ። እኔም ፡ ታሰልፍልኛለህ ፡ ብዬ ፡ አስብሀለሁ ። ትኵሱ ፡ ሬሳ ፡ ደረቁን ፡ እስኪሣ ፡ እንዲሉ ።

፯ ፡ ቀላይ ፡ ለቀላይ ፡ ትጼውዕ ፡ በቃለ ፡ አስሬቢክ ።

ተጸውዓ ፡ ባለ ፡ ይቀና ፡ ነበር ። ቀላየ ፡ ኤርትራና ፡ ቀላየ ፡ ዮርዳኖሽ ፡ በሻሻቱ ፡ ቃል ፡ ሲጣሩ ፡ ተሰሙ ። እኔ ፡ ለአበው ፡ ከሁለት ፡ ከሦስት ፡ ተከፈልጉላቸው ። አንቺም ፡ ለሙሴድ ፡ ከሁለት ፡ ከሦስት ፡ ተከፈይላቸው ፡ ብላ ፡ አሁን ፡ እነሱ ፡ ግዕዛን ፡ ኑሯቸው ፡ የሚናገሩ ፡ ሁነው ፡ አይደለም ። ሰው ፡ ኤርትራ ፡ ለአበው ፡ ከሁለት ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለችላቸው ፡ ዮርዳኖስም ፡ ለውሉድ ፡ ከሁለት ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለችላቸው ፡ ብሎ ፡ የሚናገር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ኵሉ ፡ ማዕበልከ ፡ ወሞገድከ ፡ እንተ ፡ ላዕሌየ ፡ ኃለፈ ።

ማዕበሉ ፡ ሞገዱ ፡ ሁሉ ፡ በላዬ ፡ ተመላለሰ ። ወይደኝን ፡ እንተ ፡ ተድባብ ፡ እንዲል ። መኃ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ከላይ ፡ እንደ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ከታች ፡ እንደ ፡ ተራዳ ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡ እንደ ፡ ግድግዳ ፡ ሁኖላቸው ፡ ተሻግረዋልና ። እንድም ፡ ትብትብ ፡ ምንጣፍ ፡ አሸከሙኝ ። ዮና ፡ ፪ ፡ ፬ ።

እንድም ፡ (ተሐውከት ፡ ነፍስየ ፡ በላዕሌየ) ፡ በኔ ፡ ያለች ፡ ሰውነቴ ፡ ታወከችብኝ ፡ ማለት ፡ በተስፋው ፡ (በእንተዝ) ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አቤቱ ፡ አስብሃለሁ ። (በምድረ ፡ ዮርዳኖስ) ፡ ለአበው ፡ ኤርትራት ፡ ከሁለት ፡ ከሦስት ፡ ከፍለህ ፡ ኃይል ፡ እንዳደረግህ ፡ (በአርሞንዔም) ፡ ለባራቅ ፡ ኃይል ፡ እንዳደረግህ ። የተደረገለትማ ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ አባራው ፡ እስከ ፡ አርሞንዔም ፡ ደርሶ ፡ ነበርና ፡ (በደብር ፡ ንዑስ) ፡ ለዳዊት ፡ በቀላውትሞኖስ ፡ ኃይል ፡ እንዳደረግህ ፡ ለኔም ፡ ታደርግልኛለህ ፡ ብዬ ፡ አስብሃለሁ ። ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፳፩-፳፪ ። ኢያ ፡ ፫ ፡ ፲፫-፲፯ ። መሳ ፡ ፬ ፡ ፮-፳፫ ።

(ቀላይ ፡ ለቀላይ) ፡ ስልምናሶር ፡ ናቡከደነጾር ፡ ባንተ ፡ ትእዛዝ ፡ ባንተ ፡ ፈቃድ ፡ ተጣሩልኝ ። አሁን ፡ እነሱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነግሠው ፡ አይደለም ፡ ስልምናሶር ፡ ዓሥሩን ፡ ነገድ ። ናቡከደነጾር ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ማርከው ፡ አወረዷቸው ፡ ብሎ ፡ ሰው ፡ የሚናገር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ (ኵሉ ፡ ማዕበልከ) ፡ ሰብዓ ፡ ዘመን ፡ ማዕበለ ፡ መከራው ፡ ሞገደ ፡ መከራው ፡ በላዬ ፡ ተመላለሰብኝ ። እንድም ፡ (ቀላይ ፡ ለቀላይ) ፡ ቂሮስ ፡ ዳርዮስ ፡ ዮሴዕ ፡ ዘሩባቤል ፡ እኛን ፡ ከባቢሎን ፡ ለማውጣት ፡ ባንተ ፡ ፈቃድ ፡ ባንተ ፡ ትዛዝ ፡ ተጣሩልኝ ። (ኵሉ ፡ ማዕበልከ) ፡ ሰብዓ ፡ ዘመን ፡ በላዬ ፡ የነበረ ፡ መከራ ፡ ሥጋ ፡

2014 04 17

አለፈልኝ ። እንድም ፡ (ተሐውከት) ፡ ነፍሲ ፡ ታወከችብኝ ፡ ማለት ፡ የተሰፋ ፡ ነው ፡ (በእንተዝ) ፡ አቤቱ ፡ ስለዚህ ፡ አስብሃለሁ ፡ (በምድረ ፡ ዮርዳኖስ) ፡ በአርሞንኤም ፡ ብርሃን ፡ መለኮትህን ፡ ገልፀህ ። ምነው ፡ ይህማ ፡ የተደረገ ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ ብርሃኑ ፡ እስከ ፡ አርሞንኤም ፡ ደርሷልና ፡ (በደብር ፡ ንዑስ) ፡ በቀራንዮ ፡ ተሰቅለህ ፡ ታድነኛለህ ፡ ብዬ ፡ አስብሃለሁ ፡ (ቀላይ ፡ ለቀላይ) ፡ ነቢያት ፡ ይወርዳል ፡ ይወለዳል ፡ ብለው ፡ የተናገሩት ፡ ሐዋርያት ፡ ወረደ ፡ ተወለደ ፡ ብለው ፡ ያስተማሩት ፡ አንድ ፡ ሆነ ፡ የሐብር ፡ ቀስም ፡ ምስለ ፡ ማዕረር ፡ ወሠርፅ ፡ ምስለ ፡ ዘርዕ ፡ እንዲል ፡ (ኵሉ ፡ ማዕበልከ) ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ከምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ በላዬ ፡ ተመላለሰብኝ ።

እንድም ፡ (ተሐውከት) ፡ በኔ ፡ ያለች ፡ ሰውነቴ ፡ ታወከችብኝ ። ምንም ፡ መከራውን ፡ ባይሰቀቁት ፡ ይሰማቸዋልና ፡ የመሰማት ፡ ነው ፡ (በእንተዝ) ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አስብሃለሁ ፡ (በምድረ ፡ ዮርዳኖስ) ፡ መከራ ፡ በሚቀበል ፡ ሰውነት ፡ ሁኜ ፡ ጥምቀት ፡ እንዳያነጻ ፡ መከራም ፡ ያነጻልና ፡ መከራውን ፡ ጥምቀት ፡ አለው ፡ (በአርሞንኤም) ፡ በልዑል ፡ ተስፋ ፡ (በደብር ፡ ንዑስ) ፡ በትሑት ፡ ሰብእና ፡ ሁኜ ፡ (ቀላይ ፡ ለቀላይ) ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ መክስምያኖስ ፡ ተጣሩብኝ ። አሁን ፡ የተመቸ ፡ አንድነት ፡ ተነስተዋልና ፡ (ኵሉ ፡ ማዕበልከ) ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ መከራ ፡ ሥጋ ፡ በላዬ ፡ ላይ ፡ ተመላለሰብኝ ። እንድም ፡ (ቀላይ ፡ ለቀላይ) ፡ ዘይኑን ፡ አርቃዲዎስ ፡ ቴስጠንጢኖስ ፡ ባንተ ፡ ፈቃድ ፡ ባንተ ፡ ትእዛዝ ፡ ተጣሩልኝ ፡ (ኵሉ ፡ ማዕበልከ) ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ የነበረ ፡ መከራ ፡ ሥጋ ፡ አለፈልኝ ።

፰፡ መዓልተ ፡ ይኤዝዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሣህሎ ፡ ወሌሊተ ፡ ይነግር ።

እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ መዓልት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሚጠትን ። እንደ ፡ ሌሊት ፡ የሚከብድ ፡ ጻዋዌን ፡ ይናገራል ። እንድም ፡ ሌሊተ ፡ ይኤዝዝ ፡ ወመዓልተ ፡ ይነግር ፡ ይላል ። ሌሊት ፡ ለነቢዩ ፡ ሲነግረው ፡ ያድራል ። ቀን ፡ በነቢይ ፡ አድሮ ፡ አንተ ፡ በዚህ ፡ ውረድ ፡ አንተ ፡ በዚህ ፡ ውጣ ፡ እያለ ፡ ያገዛል ።

እምኀቤየ ፡ ብፅዓት ፡ ሕይወትየ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እሁብ ፡ ያለበት ፡ ነው ። ይህን ፡ ብታደርግልኝ ፡ ይህን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብዬ ፡ የተሳልሁትን ። ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ስዕለቴን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እሰጣለሁ ።

፱፡ እብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምሳኪየ ፡ አንተ ፡ ለምንት ፡ ትረሥዐኒ ።

እግዚአብሔርን ፡ ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እንዲህስ ፡ ከሆነ ፡ በመከራው ፡ ለምን ፡ ትዘነጋኛለህ ፡ እለዋለሁ ። እንድም ፡ አንተ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ለምን ፡ በመከራው ፡ ትዘነጋኛለህ ፡ እለዋለሁ ።



ለምንት ፡ ተኀድገኒ ፡ ወለምንት ፡ ትክዝየ ፡ አንሶሱ ።

ለምን ፡ በመከራው ፡ ትጥለኛለህ ። ለምንስ ፡ ያዘንሁ ፡ የተከዝሁ ፡ ሁኜ ፡ እኖራለሁ ። መዝ ፡ ፵፪ ፡ ፪ ።

፲፡ ሶበ ፡ ያመንድቡኒ ፡ ፀርየ ።

ጠላቶቼ ፡ ሲያስጨንቁኝ ፡ ሲያስጠብቡኝ ።

ወያጸንዕዎሙ ፡ አዕፅምትየ ።

ሰውነቴን ፡ ሲጠመዝቡኝ ፡ ሲቆለምሙኝ ።

ወይቤልዎኒ ፡ ኵሎሙ ፡ ጸላእትየ ።

ገብሮ ፡ ገዶ ፡ እያሉ ፡ ሲሰድቡኝ ።

አይቴ ፡ ሀሎ ፡ አምላክከ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ አይቴ ፡ ውእቱ ፡ አምላክከ ። መዝ ፡ ፵፪ ፡ ፪ ። ፸፰ ፡ ፲ ። ፻፲፫ ፡ ፲ ።

ትሩፍ ፡ ፈጣሪ ፡ አለኝ ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ ፈጣሪህ ፡ ወዴት ፡ አለ ። ፈጣሪማ ፡ ከለህ ፡ ለመቼ ፡ ይሆንሃል ፡ እያድንህ ፡ ምን ፡ እያሉ ።

፲፩፡ ለምንት ፡ ትቴክዚ ፡ ነፍስየ ፡ ወለምንት ፡ ተሀውክኒ ።

የበለዚያ ፡ ጊታ ፡ ልቡናዬ ፡ ለምን ፡ አዝነሽ ፡ ተከዘሽ ፡ ትኖሪያለሽ ። ጊዜውስ ፡ ሳይደርስ ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ልውጣ ፡ በማለት ፡ ለምን ፡ ታውኪኛለሽ ። ቍ ፡ ፩ ።

እመኒ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ እገኒ ፡ ሎቱ ።

ይህንስ ፡ ትተሽ ፡ ለሱ ፡ እንድገዛ ፡ አውቀሽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እመኚ ። እንጂ ፡ ለምን ፡ ታውኪኛለሽ ።

መድኃኒ ፡ ገጽየ ፡ አምላኪየ ።

ፈጣሪዬ ፡ ፊት ፡ መከታዬ ፡ ነው ። ፊት ፡ መከታዬ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነውና ።

## መዝሙር ፡ ፵፪ ።

፩፡ ፍታሕ ፡ሊተ ፡ እግዚኦ ፡ ወተበቀል ፡ በቀልየ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ። አቤቱ ፡ ፍርዴን ፡ ፍርድ ፡ በቀሌን ፡ በቀል ፡ አድርግልኝ ። እንድም ፡ ፈጽመህ ፡ ፍረድልኝ ። ተበቀል ፡ ሊተ ፡ እምዕደውየ ፡ እንዲል ። ኢሳ ፡ ፳፱ ፡ ፳ ።

እምሕዝብ ፡ ውፁዓን ፡ እምጽድቅ ። ኢሳ ፡ ፵፱ ፡ ፲፱ ።

ከጽድቅ ፡ ከወጡ ፡ ከሠራዊቱ ፡ አድነኝ ። ገብተው ፡ ወጡ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ጥንቱን ፡ ያልገቡ ፡ ማለት ፡ ነው ። እንድም ፡ ኢኃደጋ ፡ ለምድር ፡ እንበለ ፡ ካህናት ፡ ወነቢያት ፡ እንዲል ። ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ሲያስተምሩ ፡ ይሰማሉ ። መስማታቸውን ፡ ከመግባት ፡ ቈጥሮ ። እንድም ፡ እንደ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ገብተው ፡ የወጡ ፡ አሉና ።

እምብእሲ ፡ ዓማፂ ፡ ወጽልሀው ፡ ባልሐኒ ።

ዓመፀኛ ፡ ከዳተኛ ፡ ከሚሆን ፡ ከብልጣሶር ፡ አድነኝ ።

፪፡ እስመ ፡ አንተ ፡ አምላኪየ ፡ ወኃይልየ ።

አንተ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ብዋጋ ፡ ኃይሌ ፡ ነህና ።

2014 04 17

ለምንት ፡ ተኀደገኒ ፡ ወለምንት ፡ ትትኤዘዞ ፡ እን ዕሉ ።

በመከራው ፡ ለምን ፡ ትጥለኛለህ ፡ ለም ንስ ፡ አገዤ ፡ እኖራለኁ ።

ሶበ ፡ ያመንድቡኒ ፡ ፀርየ ።

ጠላቶቼ ፡ ሲያስጨንቁኝ ፡ ሲያስጠብ ቡኝ ፡ በመከራው ፡ ለምን ፡ ትጥለኛ ለህ ፡ መዝ ፡ ፵፩ ፡ ፱-፲ ።

፫ ፡ ፈኑ ፡ ብርሃነከ ፡ ወጽድቀከ ።

ፈኑ ፡ ማንሻ ። እንድም ፡ ጠላቶቼ ፡ በስ ጨንቁኝ ፡ በስጠበቡኝ ፡ ጊዜ ፡ ብርሃን ፡ ረድኤትህን ፡ ላክልኝ ። ቸርነትህ ፡ አ ድርግልኝ ። እንድም ፡ ዮሴፅ ፡ ዘሩባ ቤልን ፡ ቂሮስ ፡ ዳርዮስን ፡ ላክልኝ ።

እማንቱ ፡ ይምርሃኒ ፡ ወይሰዳኒ ፡ ደብረ ፡ መቅደስከ ።

እነሱ ፡ መርተው ፡ መመስገኛህ ፡ ወደ ምትሆን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይወ ስዱኝ ፡ ዘንድ ።

ወውስተ ፡ አብያቲከ ፡ እግዚኦ ።

በረድኤት ፡ አድረህበት ፡ ወደምትኖ ር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ።

፬ ፡ እበውእ ፡ ኀበ ፡ ምሥዋዒሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ከሰብዓ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ግዱን ፡ ምሥ ዋዓ ፡ ብርት ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ኢየሩ ሳሌም ፡ እገባለሁና ፡ ግዱን ፡ አለ ፡ ወ ኀሊቆ ፡ ሰብዓ ፡ ዓም ፡ ያለው ፡ አይቀ ርምና ።

ወኀበ ፡ እምላኪየ ፡ ዘአስተፍሥሖ ፡ ለውርዙትየ ።

ጐልማስነቴን ፡ እንድም ፡ መንግሥ ቴን ፡ ያደሳት ፡ ፈጣሪዬ ፡ ወዳለባት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቀድሞ ፡ ዳዊት ፡ ሰሎሞን ፡ ዓርባ ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ ነግ ሠው ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ መንግሥት ፡ ጠ ፍቶባቸው ፡ ባቢሎን ፡ ወርርደው ፡ ፸ ፡ ዘመን ፡ ተገዝተዋል ፡ ኋላ ፡ መንግሥ ት ፡ ተመልሶላቸዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፳፱ ።

እንድም ፡ (ፈኑ ፡ ብርሃነከ) ፡ ወልድን ፡ (ወጽድቀከ) ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ እ ንድም ፡ (ብርሃነከ) ፡ ሐዋርያትን ፡ (ወ ጽድቀከ) ፡ ሰብአ ፡ አርድዕትን ፡ እን ድም ፡ (ብርሃነከ) ፡ መስቀልን ፡ (ወጽ ድቀከ) ፡ ቀኖትን ፡ እንድም ፡ (ብርሃነ ከ) ፡ ሥጋውን ፡ (ወጽድቀከ) ፡ ደሙን ፡ ላክልኝ ፡ (እማንቱ) ፡ እሊህ ፡ መርተው ፡ ወደገነት ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያ ት ፡ ያገቡኝ ፡ ዘንድ ፡ (ወውስተ) ፡ አብ ያቲከ) ፡ አብያት ፡ ብሎ ፡ አበዛት ፡ መ ንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ የምትወረስ ፡ ስለሆነ ። እንድም ፡ ስለ ማዕርጓ ፡ ብዛት ። እስመ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አቡየ ፡ ብዙኅ ፡ ማኅደር ፡ ወምዕራፍ ፡ ቦቱ ፡ እንዲል ። (እበውእ) ፡ ግዱን ፡ ከምስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመ ን ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምሥዋ ዓ ፡ ቅዳሴ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ወደ ፡ መንግስተ ፡ ሰማያት ፡ እገባለ ሁና ፡ ግዱን ፡ አለ ፡ በሐሙስ ፡ ዕለት ፡ ያለው ፡ አይቀርምና ፡ (ወኀበ ፡ እምላ ኪየ) ፡ ልጅነቴን ፡ የመለሳት ፡ ፈጣሪ ዬ ፡ ወዳለባት ፡ (እገኒ ፡ ለከ ፡ እምላኪየ ፡ በመሰንቆ) ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፲፮ ። ፲፫ ፡ ፳፫ ።



ፈጣሪዬ ፡ መሰንቆ ፡ እየመታሁ ፡ እገ ዛልሃለሁ ፡ እንድም ፡ በሃይማኖት ፡ (በ ምግባር) ፡ ዐንቼ ፡ እገዛልሃለሁ ፡ መሰ ንቆ ፡ ይዕቲ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲል ።

፭ ፡ ለምንት ፡ ትቴከዚ ፡ ነፍስየ ፡ ወለምንት ፡ ተ ሀውክኒ ።

እመኒ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ እገኒ ፡ ሎቱ ።

መድኀኒ ፡ ገጽየ ፡ እምላኪየ ። መዝ ፡ ፵፩ ፡ ፭-፲፩ ።

እንዳለፈው ፡ ሦስቱን ፡ መስመር ፡ ሦ ስት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ ተናገረው ፡ እስ ራኤል ፡ የወጡ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፡ ይኸውም ፡ በካልዕ ፡ ዕዝራ ፡ በኤር ምያስ ፡ በዘሩባቤል ፡ ነው ።

## መዝሙር ፡ ፵፫ ።

፩ ። እግዚኦ ፡ ሰማዕነ ፡ በዕዘኒነ ። ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፳፩ ።

ስለመቃብያን ፡ ተናግሮታል ። ካሥሩ ም ፡ አርእስት ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በባ ታቸው ፡ በመቃቢስ ፡ መቃብያን ፡ ተ ብለዋል ፤ በባትም ፡ ስም ፡ መጠራት ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ በኤቦር ፡ ዕብራውያን ፡ በፋሬስ ፡ ፈሪሳውያን ፡ በይሁዳ ፡ አይ ሁድ ፡ እንደተባሉ ፡ መቃብያንም ፡ ማ ለት ፡ ዕጉሣን ፡ በስደት ፡ ፅኑዓን ፡ በም ግባር ፡ ወበሃይማኖት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እስራኤል ፡ ከሚጠት ፡ ሀኋላ ፡ እያንሱ ፡ ሔደዋል ። ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ አልዓዛር ፡ ይባላል ፡ ክህነት ፡ ከመንግሥት ፡ አን ድ ፡ አድርጎ ፡ የሚገዛቸው ፡ ሁኗል ። ሕዝቡን ፡ መክሮ ፡ አስተምሮ ፡ በሥ ራት ፡ ያኖራቸዋል ፤ እሱም ፡ በሥርዓ ት ፡ ይኖራል ። ስምዖን ፡ አልፍሞስ ፡ መበልስ ፡ የሚባሉ ፡ ንዑሳን ፡ ካህናት ፡ ነበሩ ። ሔደው ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱን ፡ ሹመት ፡ በተርታ ፡ ሥጋ ፡ በገበታ ፡ እንዲሉ ፡ ፋንታችንን ፡ እንሾም ፡ ስ ጠን ፡ አሉት ፡ ከሕዝቡ ፡ አስፈቅዳ ችሁ ፡ ተሾሙ ፡ አላቸው ። ሔደው ፡ ሕዝቡን ፡ ፋንታችንን ፡ እንሾም ፡ ስ ጡን ፡ አሏቸው ። እሱ ፡ ከእግዚአብ ሔር ፡ አግኝቶ ፡ ተሹሞታል ፡ እናንተ ም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አግኝታችሁ ፡ ተሾሙ ፡ አሏቸው ። ይህማ ፡ የማድ ላት ፡ አማርኛ ፡ አይደለምን ። ዛሬስ ፡ በገዛ ፡ ሹመታችን ፡ ሱባኤ ፡ ግቡበት ፡ ይሉናል ፡ ሆን ፡ ብለው ፡ ከዕርዕ ፡ ንጉ ሥ ፡ ከአንጥያኮስ ፡ ዘንድ ፡ ወርደው ፡ የዳዊት ፡ የሰሎሞን ፡ መንግሥት ፡ የ ሚጸናት ፡ አጥታ ፡ በካህን ፡ እጅ ፡ ት ንከራተትልሃለች ። ሔደህ ፡ እጅ ፡ አ ታደርጋትምን ፡ በኔ ፡ ተጀመረ ፡ እን ዳትል ። አባታህ ፡ እስከድርም ፡ ይገዛ ቸው ፡ ነበር ፡ አሉት ፡ አሁን ፡ የተናገ ራችሁን ፡ ነገር ፡ ሳላስበው ፡ ውዬ ፡ አ ድሬ ፡ አላውቅም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እስራ ኤል ፡ ሰዎቹ ፡ ፅኑዓን ፡ ናቸው ። እም ባቸውም ፡ ፅኑ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ እሰማለ ሁ ፡ ፈጣሪያቸውም ፡ ይረዳቸዋልና ፡ መቅረቴ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አላ

ቸው ። ይህስ ፡ ነገር ፡ ላምዊው ፡ ይግ ደደው ፡ ነው ። እኛ ፡ ባወቅን ፡ እናስገ ብሃለን ፡ አንተም ፡ አመንሁ ፡ ብለህ ፡ አዋጅ ፡ ነግረህ ፡ መሥዋዕት ፡ እረያ ውን ፡ በኋላ ፡ በኋላ ፡ እያስጐተትህ ፡ ላሙን ፡ በጉን ፡ በፊት ፡ በፊት ፡ እያስ ነዳህ ፡ ና ፡ ብለው ፡ መከረውት ፡ ሒደ ው ፡ ከፈቱልን ፡ አሏቸው ። እስከሁን ፡ ወደት ፡ ሒዳችኍ ፡ ኑሯል ፡ አሏቸው ። አላንት ፡ ከሁለት ፡ ሹመት ፡ አንዱን ፡ ብትነሱን ፡ እኛ ፡ በደለኛ ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ ይከስ ፡ ብለን ፡ ዕርዕ ፡ ወርደ ን ፡ አንጥያኮስን ፡ ያህል ፡ ንጉሥ ፡ በ ሃይማኖት ፡ ወልደን ፡ በምግባር ፡ አሳ ድገን ፡ መጣን ፡ አሏቸው ። አመሰ ፡ አ ማን ፡ ጽድቀ ፡ ትነቡ ፡ ብለዋቸዋል ። መዝ ፡ ፺፯ ፡ ፩ ። አንጥያኮስም ፡ ኃይለኛ ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ። በያደረበት ፡ ሁሉ ፡ አዋጅ ፡ እያስነገረ ፡ መጥቶ ፡ በኢየሩ ሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ሰፍሮ ፡ ከፈቱልኝ ፡ መሥዋዕታችሁን ፡ መሥዋዕት ፡ በዓ ላችሁን ፡ በዓል ፡ አደርጋለሁ ፡ ለሥዕ ለ ፡ ኪሩብ ፡ እሰግዳለሁ ፡ ለቤተ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እነጽፋለሁ ፡ እጋርድአለሁ ፡ አ ላቸው ። እነሱም ፡ ኢ.ይበእ ፡ ሞአባዊ ፡ ወአሞናዊ ፡ ያለውን ፡ ያውቃሉና ፡ አይሆንም ፡ አሉት ፡ እኔ ፡ ለሥዕለ ፡ ኪሩብ ፡ እሰግዳለሁ ፡ መሥዋዕት ፡ በ ግዕ ፡ እሠዋለሁ ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ እነጽፋለሁ ፡ እጋርዳለሁ ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ አይሆንም ፡ ካላችሁማ ፡ ምን ፡ ዕዳዬ ፡ ብሎ ፡ ለማስወደድ ፡ ፈ ቱን ፡ መለሰ ። ምስቱም ፡ ከሀናት ፡ እያ ችሁን ፡ ገና ፡ ርስት ፡ ይጠብናል ፡ ብለ ው ፡ በእግዚአብሔር ፡ አማኒ ፡ ሲከለ ከሉበት ፡ እያሉ ፡ እየዘሩ ፡ ይለፍፉ ፡ ገርመረ ። ሥጋ ፡ ጠጅ ፡ የለመደ ፡ እን ድያ ፡ ነውና ። አይግባ ፡ ካሉ ፡ ይግባ ፡ ያሉ ፡ በዘ ፡ ጥቂት ፡ ራስህን ፡ ሁነህ ፡ ሰው ተህ ፡ ሒድ ፡ አሉት ፡ ንጉሥ ፡ ከገባ ፡ እን ድያ ፡ ነውና ፡ ይህ ፡ ፈታውራሪዬ ፡ ይህ ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ደጃዝማች ፡ ቀኛዝማች ፡ ግራዝማች ፡ ቋሚ ፡ ለን ሚ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሠራዊቱን ፡ ሁሉ ፡ ይዞ ፡ ገባ ። መቃብያን ፡ ቁጥራቸው ፡ ታውቋል ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ዓሥሬ ፡ ሁለቱ ፡ እልፍ ፡ ናቸው ። እሱ ፡ ሐያ ፡ አራት ፡ እልፍ ፡ ሁኗል ፡ አልታወቀም ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ አጽፈዋቸዋል ፡ መቃ ብያን ፡ እንዳነሱ ፡ የሱ ፡ ሠራዊት ፡ እ ንደበዙ ፡ አይቶ ፡ አልዓዛርን ፡ አስጠ ርቶ ፡ አንተ ፡ ጽዩፍ ፡ ነህ ፡ ሲሉ ፡ እሰማ ለሁና ፡ ለኔና ፡ ላንተ ፡ መሥዋዕት ፡ በ ግዕ ፡ ትሠዋለህ ። መሥዋዕት ፡ እሪያ ፡ ሠውተህ ፡ በቀኝ ፡ እጅህ ፡ ፀላዋ ፡ በ ግራ ፡ እጅህ ፡ ሥጋ ፡ ይዘህ ፡ የበላህ ፡ መስለህ ፡ ሕዝቡን ፡ አሳምንልኝ ፡ አ ለው ። ፈጣሪዬ ፡ የሃይማኖት ፡ አብነት ፡ ቢያደርገኝ ፡ የክህደት ፡ የጥብዓት ፡ አ ብነት ፡ ቢያደርገኝ ፡ የፍርሃት ፡ የበጎ ፡ አብነት ፡ ቢያደርገኝ ፡ የከፋት ፡ አብነ ት ፡ እሆናለሁን ፡ አይሆንም ፡ አለው ። ይመለስ ፡ እንደሆነ ፡ ብሎ ፡ ለክህነት ፡ የደረሱ ፡ ሰባት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፡ ከ

ፊቱ ፡ በሰይፍ ፡ አስመትቷቸዋል ፡ የማ ይመለስ ፡ ሆነ ። ሚስቱ ፡ መክብዩ ፡ (መብ ክዩ) ፡ ይላታል ፡ በጡትና ፡ በጡቷ ፡ መሐ ል ፡ በኩላብ ፡ አሰቅሏታል ፡ በሰይፍ ፡ አስ መትቷታል ። የማይመለስ ፡ ቢሆን ፡ በ ቍመቱ ፡ ልክ ፡ ሻሽ ፡ ጠምጥሞ ፡ በሰ ም ፡ ጠምቆ ፡ ብረት ፡ ምጣድ ፡ አግሎ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ደፋበት ። ተንጠቅጥቆ ፡ ሙቷል ። አራቱ ፡ እልፍ ፡ አብረው ፡ አልቀዋል ። አራቱ ፡ እልፍ ፡ ተማርከ ዋል ። አራቱን ፡ እልፍ ፡ ይሁዳ ፡ መቅ ብዩ ፡ አጥር ፡ ጥሶ ፡ እየተዋጋ ፡ ይዟቸ ው ፡ ወጥቷል ፡ የተማረኩትና ፡ የተሰ ደዱት ፡ በታ ፡ ሳያገናኛቸው ፡ አንዳንድ ፡ ልብ ፡ መከሬ ፡ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተና ጋሬ ፡ ሁነው ፡ ተናግረውታል ።

እግዚኦ ፡ ሰማዕነ ፡ በእዘኒነ ።

የሚቀድመው ፡ አለ ።

ወአበዊነ ፡ ዜነዉነ ።

አባቶቻችን ፡ ነግረዉን ፡ ነበረ ፡ እኛም ፡ በገሯችን ፡ ሰምተን ፡ ነበር ፡

ግብረ ፡ ዘገበርከ ፡ በመዋዕሊሆሙ ፡ በመዋዕለ ፡ ትካት ።

በመዋዕሊሆሙና ፡ በመዋዕለ ፡ ትክት ፡ እንድ ፡ ወገን ፡ በሄኖን ፡ በቅሩብ ፡ ሳሌም ፡ እንዲል ፡ ባባቶቻችን ፡ ዘመን ፡ ያደረ ግኸውን ።

፪ ፡ እዴከ ፡ ሠረወቶሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ወተከልኮሙ ፡ ሊ ያሆሙ ።

ሥልጣንህ ፡ ኃያ ፡ ዘጠኙ ፡ ነገሥተ ፡ ከነዓንን ፡ አጠፋቻቸው ። አባቶቻችን ንም ፡ በደረሰ ፡ መከራቸው ፡ በታነፀ ፡ ግምባቸው ፡ ሠራሃቸው ፡ ሲሉ ፡ ሰማ ተን ፡ ነበር ።

ግቀድኮሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ወሰደድኮሙ ።

አሕዛብን ፡ ሥቃይ ፡ አጽንተህ ፡ ከሀገ ራቸው ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ አገር ፡ ከሕይወት ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ከተድላ ፡ ወደ ፡ መከራ ፡ አስወጥተህ ፡ ሰደድሃቸው ፡ ሲሉ ፡ ሰ ምተን ፡ ነበር ።

፫ ፡ ዘእኮ ፡ በኲናቶሙ ፡ ወረሱ ፡ ለምድር ።

አባቶቻችን ፡ ከነዓንን ፡ የወረሷት ፡ በ ጦራቸው ፡ እንደበት ፡ በፈረሳቸው ፡ አንገት ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ ነግረው ን ፡ ነበር ።

ወመዝራዕቶሙኒ ፡ ኢያድኃኖሙ ።

ኃይላቸው ፡ አላዳናቸውም ፡ ብለው ፡ ነግረውን ፡ ነበር ።

ዘእንበለ ፡ የማንከ ፡ ወመዝራዕትከ ፡ ወብርሃነ ፡ ገጽከ ።

ያዳናቸው ፡ ሥልጣንህ ፡ ኃይልህ ፡ ረ ድኤትህ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

እስመ ፡ ተሠሃልኮሙ ።

ይቅር ፡ ብለሃቸዋልና ።

፬ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ንጉሥየ ፡ ወአምላኪየ ።

የዕርዓውያን ፡ ፈጣሪያቸው ፡ ሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ ንጉሣቸው ፡ አንጥያኮስ ፡ ነው ፡ የኔ ፡ ግን ፡ ፈጣሪዬም ፡ ንጉሤም ፡ አንተ ፡ ነህ ።

[illegible]

ለያዕቆብ ፡ ከላባ ፡ ከኤሳው ፡ ድኅነቱን ፡

ያዘገሀለት ፡ ያደረግሀለት ፡ አንተ ፡ ነህ ። አንድም ፡ በያዕቆብ ፡ ሁሉን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፭ ፡ ብከ ፡ ንወግዖሙ ፡ ለፀርነ ፡ ወበ...ሙ ፡ ዐርነ ።

እኛም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ባንተ ፡ እም ነን ፡ ጠላቶቻችንን ፡ ድል ፡ እንነሳ ፡ ነ በር ። እንስሳት ፡ በቀንዳቸው ፡ አራዊ ትን ፡ ድል ፡ እንዲነሱ ።

ወበስምከ ፡ ናኅሥሮሙ ፡ ለዐለ ፡ ቆሙ ፡ ላዕሌነ ።

በጠላትነት ፡ የተነሡብንን ፡ ጠላቶቻ ችንንም ፡ በስምህ ፡ አምነን ፡ ድል ፡ እን ነሳቸው ፡ ነበር ።

፮ ፡ ዘአኮ ፡ በቀሥትየ ፡ እትአመን ።

ዘአኮ ፡ በኲናቶሙ ፡ ወረስዋ ፡ ለም ድር ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ አባቶቻችን ፡ በሥ ልጣንህ ፡ በኃይልህ ፡ በረድኤትህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በጦራቸው ፡ አንደበት ፡ በፈረሳቸው ፡ አንገት ፡ ከነዓንን ፡ እን ዳልወረሷት ፡ አውቄ ፡ እኔም ፡ በሥ ልጣንህ ፡ በኃይልህ ፡ በረድኤትህ ፡ ነው ፡ እንጂ ። በጦሬ ፡ አንደበት ፡ በፈ ረሴ ፡ አንገት ፡ የምታመን ፡ አይደለ ሁም ።

ወኲናትየኒ ፡ ኢያድኅነኒ ።

ወመገረ ዐቶሙኒ ፡ ኢያድኅኖሙ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ኃይላቸው ፡ እንዳላዳ ናቸው ፡ አውቄ ፡ በኃይልህ ፡ ነው ፡ እ ንጂ ፡ በፈረሴ ፡ አንገት ፡ በጦሬ ፡ አንደ በት ፡ የምታመን ፡ አይደለሁም ፡ እሱ ም ፡ አላዳነኝም ፡ ኢያድኅነኒ ፡ አያ ድነኝም ።

፯ ፡ ወአድኀንከነ ፡ እምእለ ፡ ሮዱነ ።

ስለዚህ ፡ ከከበቡን ፡ ጠላቶቻችን ፡ አድ ነኸን ፡ ነበር ።

ወአስተኃፈርኮሙ ፡ ለእለ ፡ ጸላዕትነ ።

ጠላቶቻችንን ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ እንዲነሱ ፡ አድርገሃቸው ፡ ነበር ።

፰ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ንከብር ፡ ኵሎ ፡ እሚረ ።

በእግዚአብሔር ፡ አምነን ፡ ዕለት ፡ ዕ ለት ፡ ከብረን ፡ገንነን ፡ እንኖር ፡ ነበር ።

ወለስምከ ፡ ንገኒ ፡ ለዓለም ።

ለስምህም ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ተገዝተን ፡ እንኖር ፡ ነበር ።

፱ ፡ ይእዜሰ ፡ ገደፍከነ ፡ ወአስተኃፈርከነ ።

ዛሬ ፡ ግን ፡ በጠላቶቻችን ፡ እጅ ፡ ጣ ልኸን ፡ ድል ፡ እናደርግ ፡ የነበርን ፡ ድል ፡ እንድንሆን ፡ አደረግኸን ። አን ድም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዲህ ፡ እን ዲህ ፡ ታደርግልን ፡ ነበር ፡ አልከኝ ፡ ዛሬሳ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ ዛሬስ ፡ ድል ፡ እንነሳ ፡ የነበረ ፡ ድል ፡ እንድንሆን ፡ አደረግኸን ።

ወኢትወፅእ ፡ እምላዕለ ፡ ምስለ ፡ ኃይልነ ።

ቀድሞ ፡ ከኃይላችን ፡ ከሠራዊታችን ፡ የማትለይ ፡ ነበር ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ከኃይላ ችን ፡ ከሠራዊታችን ፡ የማትወጣ ፡ ዘ መቻ ፡ ፈሪ ፡ ሆንህ ። መዝ ፡ ፶፱ ፡ ፲ ።

፲ ፡ ወአግባዕከነ ፡ ድኅሬነ ፡ ኀበ ፡ ፀርነ ።

የጠላቶቻችን ፡ ድኅር ፡ አደረግኸን ፡ ድል ፡ እንነሳ ፡ የነበር ፡ ድል ፡ እንድን ነሳ ፡ አደረግኸን ፡ ጠላቶቻችን ፡ ጀርባ ፡ ጀርባችንን ፡ እንዲሉን ፡ አደረግኸን ፡ አንድም ፡ የጠላቶቻችንን ፡ ድኅር ፡ እ ንድንከተል ፡ አደረግኸን ፡ ማ...፡ የ በረታ ፡ ተማራኪ ፡ ያልበረታ ፡ እንደ ሆነ ፡ ጓዝ ፡ አሸክሞ ፡ አንተ ፡ በሪያ ፡ ተ ከተለኝ ፡ እሞራ ፡ ይበላኻል ፡ እያለ ፡ በፊት ፡ በፊት ፡ ይሔዳል ። ተማራኪ ፡ የበረታ ፡ ማራኪ ፡ ያልበረታ ፡ እንደ ሆነ ፡ መሣሪያውን ፡ ተቀብሎ ፡ በፊት ፡ በፊት ፡ አድርጎ ፡ እያዳፋ ፡ እየገፋ ፡ ይ ዞት ፡ ይሔዳልና ።

ወተማሠጡነ ፡ ጸላእትነ ።

ጠላቶቻችን ፡ ተሻሙን ።

፲፩ ፡ ወወሀብከነ ፡ ይብልዑነ ፡ ከመ ፡ አባግዐ ።

እንደበግ ፡ ይበሉን ፡ ዘንድ ፡ ለጠላቶ ቻችን ፡ ሰጠኸን ፡ ሰውማ ፡ ሰውን ፡ እ ንደምን ፡ ይበላዋል ፡ ብሎ ፡ ገንዘባች ንን ፡ ይዘርፉን ፡ ሰውነታችንን ፡ ይገድ ሉን ፡ ዘንድ ፡ ማለት ፡ ነው ። ኤፍሬም ፡ ይ በልዖ ፡ ለምናሴ ፡ ወምናሴ ፡ ይበልዖ ፡ ለኤ ፍሬም ፡ እንዲል ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፳፩ ። አንድም ፡ እ ንደ ፡ ባለጌ ፡ የልደት ፡ የጥምቀት ፡ ሙክ ቱን ፡ ስቦ ፡ ለጌታው ፡ እንዲሰጥ ።

ወዘረውከነ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ። ኤር ፡ ፲፰ ፡ ፳፰ ።

ዘረውከነም ፡ ይላል ፡ በዐራቱ ፡ መዓ ዝን ፡ በተንኸን ፡ ፋርስ ፡ ባቢሎን ፡ ዕር ዕ ፡ ሚዶን ፡ ኤር ፡ ፳፱ ፡ ፲፰ ።

፲፪ ፡ ወመጦከ ፡ ሕዝበከ ፡ ዘእንበለ ፡ ሤጥ ።

መጠውከም ፡ ይላል ፡ እኛን ፡ ወገኖ ችህን ፡ ሤጠ ፡ ሃይማኖት ፡ ሤጠ ፡ ምግ ባር ፡ ለሌላቸው ፡ ለአሕዛብ ፡ አንድም ፡ ለድመት ፡ ለውሻ ፡ ስንኳ ፡ ዋጋ ፡ አላቸ ው ፡ እኛን ፡ ወገኖችህን ፡ ግን ፡ ያለዋጋ ፡ አሳልፈህ ፡ ሰጠኸን ።

ወአልበ ፡ ብዙኀ ፡ ለሥያጤነ ። ኢሳ ፡ ፶፪ ፡ ፫ ።

ለምስጋናችን ፡ ብዛት ፡ የለውም ። እ ሁን ፡ በገጸር ፡ ዓሥር ፡ ሰሞነኛ ፡ ቢያ ም ፡ አራቱ ፡ እሩፍ ፡ አልቀዋል ፡ እ ራቱ ፡ እልፍ ፡ ተማርከዋል ፡ አራቱን ፡ እልፍ ፡ ይሁዳ ፡ መቅብዩ ፡ እየተዋጋ ፡ አጥር ፡ ጥሶ ፡ ይዟቸው ፡ ሔዷልና ።

፲፫ ፡ ወረሰይከነ ፡ ፅዕለተ ፡ ለጎርነ ።

ለጎረቤቶቻችን ፡ መዘበቻ ፡ አደረግ ኸን ።

ሠሐቀ ፡ ወሥላቀ ፡ ለእድያሚነ ። መዝ ፡ ፸፰ ፡ ፬ ።

ይልቁንም ፡ ለጎረቤቶቻችን ፡ ለሞዓ ብና ፡ ለአሞን ፡ ፌጽመህ ፡ መዘበቻ ፡ አደረግኸን ። ኤር ፡ ፲፪ ፡ ፲፬ ።

፲፬ ፡ ወረሰይከነ ፡ አምሳለ ፡ ለአሕዛብ ። ሕቶ ፡ ፲፩ ፡ ፲፮ ።

ለአሕዛብ ፡ ተረት ፡ አደረግኸን ። የከነ ፡ ጉልማሳ ፡ ያዩ ፡ እንደሆን ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ማነን ፡ ይመስላል ፡ መቃቢስን ። የከ ሰች ፡ ሴት ፡ ያዩ ፡ እንደሆን ፡ ይህቺ ፡ ሴት ፡ የማን ፡ ትመስላለች ፡ የመቃቢ ስን ፡ የተፈታች ፡ አገር ፡ ያዩ ፡ እንደ ሆን ፡ ይህች ፡ አገር ፡ የማን ፡ ትመስላ ለች ፡ የመቃቢስን ፡ እያሉ ፡ ይተርቱ ባቸዋል ።

ወሖለቅ ፡ ርእሶ ፡ ለሕዝብ ። ኢዮ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ። ሕዝ ፡ ፳ ፡ ፲፮ ።

የምስቱ ፡ ክህናት ፡ ራስ ፡ መነቅነቅያ ፡ አደረግኸን ፡ ከሁለት ፡ ሹመት ፡ አን ዱን ፡ ነስተኸን ፡ እያሉ ፡ እንድም ፡ የዕርዓውያን ፡ ራስ ፡ መነቅነቅያ ፡ አደ ረግኸን ። ቆይ ፡ ዕርዕ ፡ አውርደን ፡ ለሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ ሳናሰግዳችሁ ፡ መሥ ዋዕተ ፡ እሪያ ፡ ሳናበላችሁ ፡ እያሉ ።

፲፮ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ትድሙኒየ ፡ ውእቱ ፡ ሐፍረትየ ።

ለሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ ስገድ ፡ መሥዋዕተ ፡ እሪያ ፡ ብላ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ያፈርሁት ፡ ሐፍረት ፡ በፊቴ ፡ ነው ። ዕለት ፡ ዕለት ፡ እስበዋለሁ ።

ወከደነኒ ፡ ኃፍረተ ፡ ገጽየ ። ኤር ፡ ፫ ፡ ፳፭ ።

ይኸውም ፡ ኃፍረት ፡ ፊቴን ፡ እንደ ፡ ሻሽ ፡ ሸፈነኝ ።

፲፯ ፡ እምቃለ ፡ ከይዕዕል ፡ ወይዘረኪ ።

ከሚሳደብ ፡ ከሚላገድ ፡ ከንጥያኮስ ፡ የተነሣ ። እንድም ፡ (እምቃለ ፡ ዘይዕ ዕል) ፡ ከሚሳደብ ፡ ከሚላገድ ፡ እንጥ ያኮስ ፡ አነጋገር ፡ የተነሣ ።

እምገጸ ፡ ፀሬዊ ፡ ዘይረውድ ።

ከሚከብ ፡ ከንጥያኮስ ፡ ፊት ፡ መገለጽ ፡ ዕርዓዊ ፡ ይላል ። ከሚያስፈራ ፡ ከንጥ ኮስ ፡ ፊት ፡ መገለጽ ፡ የተነሣ ።

፲፰ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ በጽሐ ፡ ላዕሌነ ፡ ወኢረሳዕናከ ።

ይህ ፡ ኵሉ ፡ መከራ ፡ መጣብን ፡ እልዘነ ጋንህም ። እንድም ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ መከ ራ ፡ የመጣብን ፡ ዘንግተንህ ፡ አይደለም ።

ወኢዐመፅነ ፡ ኪዳነከ ።

ይህ ፡ ኹሉ ፡ መከራ ፡ ቢመጣብን ፡ ሕ ግህን ፡ አላፈረስንም ። እንድም ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ መከራ ፡ የመጣብን ፡ ሕግህን ፡ አፍርሰን ፡ አይደለም ።

፲፱ ፡ ወኢገብኣ ፡ ድኅሬሁ ፡ ልብነ ።

ልቡናችን ፡ ከአምልኮትህ ፡ ወደ ፡ አ ምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ሒዶ ፡ አይደለም ። እንድም ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ መከራ ፡ ቢመ ጣብን ፡ ልቡናችን ፡ ከአምልኮትህ ፡ ወደ ፡ አምልኮ ፡ ጣዖት ፡ አልሔደም ።

ወኢተገኀሠ ፡ ፀሠርነ ፡ እምፍኖትከ ።

ዓሠረ ፡ ልቡናችን ፡ ከሕግሕ ፡ አልወ ጣም ። እንድም ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ መከራ ፡ የመጣብን ፡ ፀሠረ ፡ ልቡናችን ፡ ከሕ ግሕ ፡ ወጥቶ ፡ አይደለም ። መቃብያን ፡ እንደ ፡ ትሩፋን ፡ የታወቀ ፡ ኃጢአት ፡ የላቸውም ፡ ይኸውም ፡ ኢዓመፅነ ፡ ኪዳነከ ፡ ኢገብአ ፡ ድኅሬሁ ፡ ልብነ ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ።

፳ ፡ እስመ ፡ አሕመምከነ ፡ በብሔር ፡ ዕኩይ ።

በአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ በፀና ፡ በአንጥ ያኮስ ፡ አገር ፡ በዕርዕ ፡ በብሔረ ፡ እ ኩይ ፡ ብለህ ፡ ነው ። እንድም ፡ ክፉ ፡ በሚሆን ፡ በዕርዕ ፡ መከራ ፡ አምጥተ ህብናልና ።

ወደፈነነ ፡ ጽላሎተ ፡ ሞት ።

ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ መከ[…]

ኝን ፡ ውጠ ፡ እስቀረን[…]



፳ ፡ ዕበዉ ፡ ረሳዕነ ፡ ስሞ ፡ ለአምላክነ ።

የፈጣሪያችንን ፡ ስም ፡ ዘንግተን ፡ ቢሆን ።

ወሰፈሕነ ፡ እንግዕነ ፡ ኀበ ፡ አምላክ ፡ ነኪር ።

እደ ፡ ልቡናችንን ፡ ለተዘክሮ ፡ እደ ፡ ቃላችንን ፡ ለጸሎት ፡ እደ ፡ ሥጋችን ን ፡ ለመሥዋዕት ፡ ወደ ፡ ጣዖት ፡ እን ሥተንም ፡ ቢሆን ።

፳፩ ፡ አኮኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምተኃሥሦ ፡ ለ ዝንቱ ።

አዋቂ ፡ ነውና ፡ ባወቀው ፡ ነበር ፡ ማ ለት ፡ አውቆ ፡ መከራ ፡ አመጣብን ፡ ባልን ፡ ነበ[…]

እስመ ፡ […] ኅቡኣት ፡ ልብነ ።

[…]ል ። ገለጠው ። ል

[…] ፡ መርምሮ ፡ ያው

[…] ፡ ይቀትሉነ ፡ ኵሎ ፡ አ

[…]ን ፡ በሱ ፡ ስም ፡

[…]ሱ ፡ ስም ፡ ስለተ

[…]ራ ፡ ያመጡብ

[…]ል ፡ ብዙኃ ፡

[…]ላኩ ፡ እንዲል ።

[…]

[…] መከራ ፡ ስላመ

[…]ጥምቀት ፡ ለፋ

[…] ፡ በጎች ፡ ሆን ፡

[…] ፡ ይላል ።

[…] ፡ እንደ

ሚያርዷቸው ፡ በጎች ፡ ሆንን ። ያመት ፡ በዓልን ፡ በግ ፡ ከሳና ፡ ይወፍር ፡ እነ ሰና ፡ ይደግ ፡ የሚለው ፡ የለም ፡ ሁሉ ፡ ደሙ ፡ ይፍሰስ ፡ ይለዋል ። እነሱንም ፡ ያገኟቸው ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ያፀናባቸ ዋልና ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴፮ ። ፪ቆሮ ፡ ፬ ― ፲፩ ።

፳፪ ፡ ንቃሕ ፡ እግዚኦ ፡ ለምንት ፡ ትነውም ።

አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሣ ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ ትተኛለህ ። አሁን ፡ በ ጌታ ፡ መተኛት ፡ መነሣት ፡ ኑሮበት ፡ አይደለም ፡ አለመራዳቱን ፡ በመተኛት ፡ መራዳቱን ፡ በመነሣት ፡ መስሎ ፡ ተና ገረ ፡ እንጂ ።

ተንሥእ ፡ ወኢትግድፈን ፡ ለዝሉፉ ።

በሥራ ፡ ተነሣ ። ፈጽመህ ፡ በመከራ ፡ አትጣለን ።

፳፫ ፡ ወለምንት ፡ ትመይጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔነ ።

ለምንት ፡ ትነውም ፡ ወለምንት ፡ ትመ ይጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔነ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ። ገጸ ፡ ረድኤትህን ፡ ገጸ ፡ ምሕረትህንስ ፡ ከኛ ፡ ወደዚያ ፡ ለምን ፡ ትመልሰዋለህ ፡ ለጊዜውስ ፡ ብትመልሰው ፡ ለምን ፡ እንደመለስኸው ፡ ትቀራለህ ።

ወትረስዖ ፡ ሕማምነ ፡ ወተጽናስነ ።

በፋርስ ፡ በባቢሎን ፡ የተቀበልነው ፡ መከራ ፡ ተዘነጋን ፡ ትኩሱ ፡ ሬሳ ፡ ደረ ቱን ፡ ያስነሣ ፡ እንዲሉ ፡ ሁሉ ፡ በፋ ርስ ፡ በባቢሎን ፡ ከተቀበሉት ፡ መከ ራ ፡ በዕርዕ ፡ የተቀበሉት ፡ መከራ ፡ ይበ ልጣልና ። እንድም ፡ (ለምንት ፡ ትረ

ወሖለቶ ፡ ርእሰ ፡ ለሕዝብ ። ኢዮ ፡ ፲፰ ፡ ፯ ። ሕዝ ፡ ፳ ፡ ፲፰ ።

የምስቱ ፡ ከሀናት ፡ ራስ ፡ መንቅንቅያ ፡ አደረግኸን ፡ ከሁለት ፡ ሹመት ፡ አን ዱን ፡ ነስተኸን ፡ እያሉ ፡ አንድም ፡ የዕርዓውያን ፡ ራስ ፡ መንቅንቅያ ፡ አደ ረግኸን ። ቆይ ፡ ዕርዕ ፡ አውርደን ፡ ለሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ ሳናሰግዳችሁ ፡ መሥ ዋዕተ ፡ እሪያ ፡ ሳናበላችሁ ፡ እያሉ ።

፲፭ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ትድኅኒየ ፡ ውእቱ ፡ ሐፍረትየ ።

ለሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ ስገድ ፡ መሥዋዕተ ፡ እሪያ ፡ ብላ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ያፈርሁት ፡ ሐፍረት ፡ በፊቴ ፡ ነው ። ዕለት ፡ ዕለት ፡ እስበዋለሁ ።

ወከደነኒ ፡ ኃፍረት ፡ ገጽየ ። ኤር ፡ ይ ፡ ጽ፭ ።

ይኸውም ፡ ኃፍረት ፡ ፊቴን ፡ እንደ ፡ ሻሽ ፡ ሸፈነኝ ።

፲፮ ፡ እምቃለ ፡ ዘይፀዕል ፡ ወይዘረኪ ።

ከሚሳደብ ፡ ከሚላገድ ፡ ከንጥያኮስ ፡ የተነሣ ። አንድም ፡ (እምቃለ ፡ ዘይፅ ዕል) ፡ ከሚሳደብ ፡ ከሚላገድ ፡ አንጥ ያኮስ ፡ አነጋገር ፡ የተነሣ ።

እምገጸ ፡ ፀሬዊ ፡ ዘይረውድ ።

ከሚከብ ፡ ከንጥያኮስ ፡ ፊት ፡ መገለጽ ፡ ዕርዓዊ ፡ ይላል ። ከሚያስፈራ ፡ ከንጥ ኮስ ፡ ፊት ፡ መገለጽ ፡ የተነሣ ።

፲፯ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ በጽሐ ፡ ላዕሌነ ፡ ወኢረሳዕናከ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ መጣብን ፡ አልዘነ ጋነህም ። አንድም ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ መከ ራ ፡ የመጣብን ፡ ዘንግተንህ ፡ አይደለም ።

ወኢዐመፅነ ፡ ኪዳነከ ።

ይህ ፡ ኹሉ ፡ መከራ ፡ ቢመጣብን ፡ ሕ ግህን ፡ አላፈረስንም ። አንድም ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ መከራ ፡ የመጣብን ፡ ሕግህን ፡ አፍርሰን ፡ አይደለም ።

፲፰ ፡ ወኢገብአ ፡ ድኅሬሁ ፡ ልብነ ።

ልቡናችን ፡ ከአምልኮትህ ፡ ወደ ፡ አ ምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ሒዶ ፡ አይደለም ። አንድም ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ መከራ ፡ ቢመ ጣብን ፡ ልቡናችን ፡ ከአምልኮትህ ፡ ወደ ፡ አምልኮ ፡ ጣዖት ፡ አልሔደም ።

ወኢተገኀሠ ፡ ፀሠርነ ፡ እምፍኖትከ ።

ዓሠረ ፡ ልቡናችን ፡ ከሕግሕ ፡ አልወ ጣም ። አንድም ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ መከራ ፡ የመጣብን ፡ ፀሠረ ፡ ልቡናችን ፡ ከሕ ግሕ ፡ ወጥቶ ፡ አይደለም ። መቃብያን ፡ እንደ ፡ ትሩፋን ፡ የታወቀ ፡ ኃጢአት ፡ የላቸውም ፡ ይኸውም ፡ ኢዓመፅነ ፡ ኪዳነከ ፡ ኢገብአ ፡ ድኅሬሁ ፡ ልብነ ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ።

፲፱ ፡ እስመ ፡ አሕመምከነ ፡ በብሔር ፡ ዕኩይ ።

በአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ በፀና ፡ በአንጥ ያኮስ ፡ አገር ፡ በዕርዕ ፡ በብሔረ ፡ እ ኩይ ፡ ብለሀ ፡ ነው ። አንድም ፡ ክፉ ፡ በሚሆን ፡ በዕርዕ ፡ መከራ ፡ አምጥተ ህብናልና ።

ወደፈነነ ፡ ጽላሎተ ፡ ሞት ።

ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ መከራም ፡ አገ ኘን ፡ ውጦ ፡ አስቀረን ።



፳ ፡ ዕበሁ ፡ ረሳዕነ ፡ ስሞ ፡ ለአምላክነ ።

የፈጣሪያችንን ፡ ስም ፡ ዘንግተን ፡ ቢሆን ።

ወዕበሁ ፡ አንሣዕነ ፡ እደዊነ ፡ ኀበ ፡ አምላክ ፡ ነኪር ።

እደ ፡ ልቡናችንን ፡ ለተዘከሮ ፡ እደ ፡ ቃላችንን ፡ ለጸሎት ፡ እደ ፡ ሥጋችን ን ፡ ለመሥዋዕት ፡ ወደ ፡ ጣዖት ፡ አን ሥተንም ፡ ቢሆን ።

፳፩ ፡ አኮኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምተኃሠሥ ፡ ለ ዝንቱ ።

አዋቂ ፡ ነውና ፡ ባወቀው ፡ ነበር ፡ ማ ለት ፡ አውቆ ፡ መከራ ፡ አመጣብን ፡ ባልን ፡ ነበር ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ የአምር ፡ ኅቡዓተ ፡ ልብነ ።

ኅቡዓተ ፡ ልብ ፡ ይላል ። ገለጠው ። ል ቡናችን ፡ ያሰበውን ፡ መርምሮ ፡ ያው ቃልና ። ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ።

፳፪ ፡ እስመ ፡ በእንቲአሁ ፡ ይቀትሉነ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ።

በሱ ፡ ስም ፡ ስላመንን ፡ በሱ ፡ ስም ፡ ስለ ፡ አስተማርን ፡ በሱ ፡ ስም ፡ ስለተ ጠራን ፡ ዘወትር ፡ መከራ ፡ ያመጡብ ናልና ። ወሞተ ፡ ዳንኤል ፡ ብዙኃ ፡ ጌዜያተ ፡ በእንተ ፡ አምላኩ ፡ እንዲል ።

ወኮነ ፡ ከመ ፡ አባግዕ ፡ ዘይጠብሑ ።

ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ መከራ ፡ ስላመ ጡብን ። ለልደት ፡ ለጥምቀት ፡ ለፋ ሲካ ፡ እንደሚታረዱ ፡ በጎች ፡ ሆን ፡ አንድም ፡ ዘይጠብሕዎሙ ፡ ይላል ። ለልደት ፡ ለጥምቀት ፡ ለፋሲካ ፡ እንደ ሚያርዷቸው ፡ በጎች ፡ ሆንን ። ያመት ፡ በዓልን ፡ በግ ፡ ከሳና ፡ ይወፍር ፡ እን ሰና ፡ ይደግ ፡ የሚለው ፡ የለም ፡ ሁሉ ፡ ደሙ ፡ ይፍሰስ ፡ ይለዋል ። እነሱንም ፡ ያገኛቸው ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ያፀናባቸ ዋልና ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴፯ ። ፪ቆሮ ፡ ፬ — ፲፩ ።

፳፫ ፡ ንቃሕ ፡ እግዚኦ ፡ ለምንት ፡ ትነውም ።

አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሣ ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ ትተኛለሀ ። እሁን ፡ በ ጌታ ፡ መተኛት ፡ መነሣት ፡ ኑሮበት ፡ አይደለም ፡ አለመረዳቱን ፡ በመተኛት ፡ መረዳቱን ፡ በመነሣት ፡ መስሎ ፡ ተና ገረ ፡ እንጂ ።

ተንሥእ ፡ ወኢትግድፈነ ፡ ለዝሉፉ ።

በሥራ ፡ ተነሣ ። ፈጽመሀ ፡ በመከራ ፡ አትጣለን ።

፳፬ ፡ ወለምንት ፡ ትመይጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔነ ።

ለምንት ፡ ትነውም ፡ ወለምንት ፡ ትመ ይጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔነ ፡ ብለሀ ፡ ግጠም ። ገጽ ፡ ረድኤትህን ፡ ገጽ ፡ ምሕረትህንስ ፡ ከኛ ፡ ወደዚያ ፡ ለምን ፡ ትመልሰዋለሀ ፡ ለጊዜውስ ፡ ብትመልሰው ፡ ለምን ፡ እንደመለስኸው ፡ ትቀራለሀ ።

ወትረስዕ ፡ ሕማምነ ፡ ወተፅናስነ ።

በፋርስ ፡ በባቢሎን ፡ የተቀበልነው ፡ መከራ ፡ ተዘነጋን ፡ ትኩሱ ፡ ፈሳ ፡ ደረ ቁን ፡ ያስነሣ ፡ እንዲሉ ፡ ሁሉ ፡ በፋ ርስ ፡ በባቢሎን ፡ ከተቀበሉት ፡ መከ ራ ፡ በዕርዕ ፡ የተቀበሉት ፡ መከራ ፡ ይበ ልጣልና ። አንድም ፡ (ለምንት ፡ ትረ

ሥዓን ፡ በሕማምን) ፡ ይላል ፡ በመከራ ፡ ሳለን ፡ ለምን ፡ ትዘነጋናለህ ። እንዘ ፡ በሕማም ፡ በመከራ ፡ እየኖርን ። እንድም ፡ (ሶበ ፡ በሕማምን) ፡ በመከ ራችን ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ትዘነጋናለህ ። እንድም ፡ (ለምንት ፡ ትረሥዕ ፡ ብነ ፡ ሕማመነ) ፡ ይላል ፡ መከራችንን ፡ ለ ምን ፡ ትዘነጋብናለህ ።

፳፭ ፡ እስመ ፡ ኃሥረት ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ነፍስነ ።

ሰውነታችን ፡ በዕርዕ ፡ ጐስቍላለችና ።

ወጠግዓት ፡ በምድር ፡ ከርሥነ ።

ሰውነታችን ፡ ከመከራ ፡ ጋራ ፡ ተጣግ ታለችና ። ቀጠና ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ ፀ ሐይን ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ እይሆን ለትምና ። እንድም ፡ ድንኒ ፡ ወንትዓዶ ፡ ብከ ፡ እያሉ ፡ ፈረፈር ፡ ይሸገሩባቹ ዋል ፡ ከር ፡ ይወጡባቹዋል ። የመሸ ታ ፡ ጠላ ፡ ይቀዱባቹዋልና ።

፳፮ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ርድኦነ ።

አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሥ ተህ ፡ እርዳን ።

ወአድኅነነ ፡ በእንተ ፡ ስምከ ።

በስምህ ፡ ስላመንን ፡ በስምህ ፡ ስለተ ጠራን ፡ ስምየኒ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተ ሣህል ፡ ስላልህ ፡ አድነን ።

መገሙር ፡ ፃ፬ ።

፩ ፡ ጐሥዐ ፡ ልብየ ፡ ቃለ ፡ ሠናየ ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ደረቅ ፡ ሐዲስ ፡ ይባ ላል ። ልቡናዬ ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ አውጥ ቶ ፡ ይናገራል ። ወትጐሥዖሙ ፡ ባሕር ፡ ለነጋድያን ፡ እንዲል ።

ወአነ ፡ እየድዕ ፡ ግብርየ ፡ ለንጉሥ ።

እኔን ፡ አይሸም ፡ ጐሥዓ ፡ ልብየ ፡ ያለ ፡ እሱ ፡ ነውና ፡ ወእየድዕ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ግብሬንም ፡ ለንጉሠ ፡ ሰማይ ፡ ወምድ ር ፡ ለክርስቶስ ፡ አቀርባለሁ ። የነቢይ ፡ ግብሩ ፡ ትንቢት ። የካህን ፡ ግብሩ ፡ መ ሥዋዕት ፡ እንዲሉ ።

እንድም ፡ (ጐሥዓ ፡ ልብየ ፡ ቃለ ፡ ሠ ናየ) ፡ ልብነቴ ፡ አካላዊ ፡ ቃልን ፡ አስ ገኘ ። ወአነ ፡ እየድዕ ፡ ግብርየ ፡ ለንጉ ሥ ። አሁንም ፡ እኔን ፡ እያሸም ። ግብሬ ንም ፡ ገዘንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ብዬ ፡ ለንጉሠ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ ለክርስ ቶስ ፡ አቀርባለሁ ።

እንድም ፡ (ጐሥዓ ፡ ልብየ) ፡ ልቡናዬ ፡ አብ ፡ እኔን ፡ አካላዊ ፡ ቃልን ፡ አስገኘ ። (ወአነ ፡ እየድዕ) ፡ እነ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እኔም ፡ አቡየ ፡ ፈነወኒ ፡ ወእነ ፡ ተፈነውኩ ፡ ብዬ ፡ ግብሬን ፡ ለንጉሠ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ አቀርባለሁ ።

ከመ ፡ ቀለመ ፡ ጸሐፊ ፡ ዘጠበጠበ ፡ ይጽሕፍ ፡ ልሳንየ ።

ከመ ፡ ቀለመ ፡ ጸሐፊ ፡ ዘሠናየ ፡ ሲል ፡ ነው ። ወርእየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኵሎ ፡ ዘፈጠረ ፡ ከመ ፡ ጡብ ፡ እንዲል ፡ እን ዳማረ ፡ እንደ ፡ ተወደደ ፡ ብርዐ ፡ ጸሐ





ፊ ፡ እንደበቴ ፡ ይናገራል ፡ እጇ ፡ ይ ጽፋል ። ጽሑፍ ፡ ኃጢአታ ፡ ለይሁዳ ፡ በቀለመ ፡ ሐፂን ፡ ወበብርዐ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እንዲል ፡ (እንድም) ፡ ከመ ፡ ቀለመ ፡ ዘጠበጠበ ፡ ይጽሕፍ ፡ ጸሐፊ ፡ ይላል ። ጸሐፊ ፡ ጠብ ፡ ጠብ ፡ እያደረ ገ ፡ እንዲጽፍ ። እንደበቴ ፡ ይናገራል ፡ እጇ ፡ ይጽፋል ። እንደ ፡ ጸሐፊ ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ። እንደ ፡ ብርዑ ፡ እንደ በቱ ። እንደ ፡ ሰሌዳው ፡ ልቡናው ። እ ንደ ፡ ቀለሙ ፡ ምሥጢሩ ፡ ነው ።

፪ ፡ ይሤኒ ፡ ላህዩ ፡ እምውሉደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

መልኩ ፡ ከሰው ፡ ልጅ ፡ መልክ ፡ ይበ ልጣል ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ከም ስቱ ፡ ገባያ ፡ ሰው ፡ እንዱ ፡ ገባያ ፡ የ ሚከተለው ፡ መልኩን ፡ ለማየት ፡ ነ ውና ።

እንድም ፡ (ይሤኒ) ፡ ላህዩ ፡ ተአምራ ቱ ፡ ከነቢያት ፡ ከሐዋርያት ፡ ይበልጣ ል ። ነቢያት ፡ ቢያስተምሩ ፡ ከመገ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እያሉ ፡ ነው ። እሱ ፡ ግን ፡ እንሰ ፡ እብለከሙ ፡ እያለ ፡ ነውና ። ሐዋርያት ፡ ተአምራት ፡ ቢያ ያደርጉ ፡ ፃእ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ፡ በስ ሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተንሥእ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እያሉ ፡ ነው ፤ እሱ ፡ ግን ፡ እኤገዝዘከ ፡ ከመ ፡ ት ፃዕ ፡ እምኔሁ ፡ ፈቀድኩ ፡ ንጻሕ ፡ እ ያለ ፡ ነውና ።

ተከዕወ ፡ ሞገስ ፡ እምከናፍሪከ ።

ካንደበትህ ፡ ባለሟልነት ፡ መልቶ ፡ ፈሰሰ ፡ መፍሰስ ፡ እንጂ ፡ ሲመላ ፡ ነው ፡ በገዘቶ ፡ ተነገረ ። እንድም ፡ ገቢረ ፡ ተአ ምራት ፡ ወመንክራት ፡ ሥርየተ ፡ ኃ ጢአት ፡ በገዘቶ ፡ በአንደበትህ ፡ ተነ ገረ ፡ ተደረገ ።

በእንተዝ ፡ ባረከከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለም ።

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔርነትህ ፡ ለዘላለሙ ፡ በተዋህዶ ፡ አከበረህ ፡ ኢሳ ፡ ፶፱ ። ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፳፪ ።

፫ ፡ ቅንት ፡ ሰይፈከ ፡ ኃያል ፡ ውስተ ፡ ሐቌከ ።

ኃያል ፡ ሰይፍህን ፡ በወገብህ ፡ ታጠቅ ።

በሥንከ ፡ ወበላህይከ ።

በደም ፡ ግባትህ ፡ በመልክ ፡ ቅንነትህ ፡ ላይ ፡ በተ ፡ መልከም ፡ ቀይ ፡ ጉል ማሳ ፡ አፋውን ፡ ታጥቆ ፡ ባደባባይ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሲል ፡ ደስ ፡ እንዲ ያሰኝ ።

እንድም ፡ (ቅንት ፡ ሰይፈከ) ፡ ኃያል ፡ ወልድ ፡ በባህርይህ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ህን ፡ ግለፅ ፡ (በሥንከ) ፡ በላህየ ፡ ተአ ምራትህ ፤ በላህየ ፡ ትምርትህ ፡ ላይ ፤ እንድም ፡ በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ በምታ ደርገው ፡ ተአምራት ፡ ላይ ።

፬ ፡ አርትዕ ፡ ተሠራህ ፡ ወንግሥ ።

ተሠራኅ ፡ ይቀድማል ፡ ተከናወን ፡ ማለት ፡ ሎሌ ፡ ገረድህን ፡ አልብስ ፡ ፈረስ ፡ በቅሎህን ፡ አጠጥር ፡ (አርትዕ) ፡ ጉዞህን ፡ ወደ ፡ መናገሻህ ፡ አቅና ፤ (ወን ግሥ) ፡ ከዚያ ፡ ሄደህ ፡ ንገሥ ፤ እን ድም ፡ (ተሠራህ) ፡ ሕገ ፡ ተሰብአን ፡

2014 04 17

ፈጽም ፡ (አርትዕ) ፡ ጉዞህን ፡ ወደ ፡
ቀራንዮ ፡ አቅና ፡ (ወንግሥ) ፡ ከዚያ ፡
ሂደህ ፡ ተሰቀል ፡ የመንግሥት ፡ ምል
ክት ፡ የሚሆኑ ፡ ሰባቱ ፡ ተአምራት ፡
ተደርገው ፡ በታልና ፡ መስቀሉን ፡ መን
ግሥት ፡ አለው ።

በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ ወርትዕ ፡ ወየውሃት ።

ስለ ፡ እውነት ፡ ስለ ፡ ቅንነት ፡ ማለት ፡
ጌታ ፡ ለሎሌው ፡ ነጋዴ ፡ ላሞሌው ፡
ተላልፎ ፡ መሞት ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡
ስለ ፡ የዋህነት ፡ ማለት ፡ ተበድሎ ፡
መካስ ፡ የዋህነት ፡ ነውና ። አንድም ፡
አንድ ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ አዳም ፡ ንስሐ ፡
አንድም ፡ (በእንተ ፡ ጽድቅ) ፡ ስለ ፡
ትንቢተ ፡ ነቢያት ፡ (ወርትዕ) ፡ ስለ ፡
ኦሪት ፡ (ወየውሃት) ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡
አንድም ፡ (ወርትዕ) ፡ አይለወጥም ፡
ስለ ፡ ኦሪት ፡ (ወየውሃት) ፡ ስለ ፡ ወን
ጌል ፡ ወንጌልን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ተናገ
ራት ፡ በመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ጊዜ ፡ ታይታ ፡
ጠፍታለችና ፡ (ተሠውራለች) ።

ወይመርሐከ ፡ ስብሐተ ፡ የማንከ ።

ስቡሕ ፡ የማንክ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ክቡር ፡
ሥልጣንህ ፡ አንድም ፡ ስብሐተ ፡ የማ
ንክ ፡ ብሎ ፡ የባህርይ ፡ አባትህ ፡ የአ
ብ ፡ የባህርይ ፡ ሕይወትህ ፡ የመንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ፈቃድ ፡ መርቶ ፡ ወደ ፡ መስ
ቀል ፡ ወደ ፡ ቀኖት ፡ ያደርስሃል ፥ በፈ
ቃድ ፡ አንድ ፡ ናቸውና ።

፭ ፡ አሕፃኪ ፡ ስሑል ፡ ኃያል ።

አሕፃክ ፡ ካለ ፡ ሥሑላን ፡ ሥሑልም ፡
ካለ ፡ ሐፅከ ፡ ቢል ፡ ይቀና ፡ ነበር ፡ ል
ማደ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፡ ፍላጻችህ ፡
የተቡ ፡ የጋሉ ፡ ናቸው ።

አሕዛብ ፡ ይወድቁ ፡ ታሕቴከ ።

አሕዛብ ፡ ከእግርህ ፡ በታች ፡ ይወድ
ቃሉ ፡ ማለት ፡ ይገብራሉ ፡ ይቀቅላሉ ።

ውስተ ፡ ልበሙ ፡ ለጸላዕተ ፡ ንጉሥ ።

ለአሕዛብ ፡ ጸላዕተ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡
ያንት ፡ የንጉሥ ፡ ጠላት ፡ የሚሆኑ ፡
አሕዛብ ፡ ይገብራሉ ፡ ይቀቅላሉ ። (ው
ስተ ፡ ልበሙ) ፡ ብላቴኖችህ ፡ በፍላፃ ፡
ልብ ፡ ልባቸውን ፡ ብለዋቸው ፡ አን
ድም ፡ (አሕፃክ) ፡ ሐዋርያት ፡ በመን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የጋሉ ፡ የትቡ ፡ የተና
ደዱ ፡ ናቸው ፡ (አሕዛብ) ፡ ያንተ ፡ የን
ጉሥ ፡ ጠላት ፡ የሚሆኑ ፡ አሕዛብ ፡
ባንተ ፡ ያምናሉ ፡ (ውስተ ፡ ልበሙ) ፡
ሐዋርያት ፡ በተአምራት ፡ ልብ ፡ ልባ
ቸውን ፡ ብለዋቸው ፡ አንድም ፡ ይወ
ድቁ ፡ ታህቴከ ፡ አሕዛብ ፡ ዘውስተ ፡
ልበሙ ፡ ጸላዕተ ፡ ንጉሥ ፥ ያንት ፡ የን
ጉሥ ፡ ጠላት ፡ የሚሆኑ ፡ አጋንንት ፡
አድረውባቸው ፡ የነበሩ ፡ አሕዛብ ፡
ባንተ ፡ ያምናሉ ፡ (እምውስተ ፡ ልበ
ሙ ፡ ለጸላዕተ ፡ ንጉሥ) ፡ ያንተ ፡ የን
ጉሥ ፡ ጠላት ፡ የሚሆኑ ፡ አጋንንትን ፡
ሐዋርያት ፡ ከልበናቸው ፡ አስወጥተ
ውአቸዋል ።

፮ ፡ መንበርከ ፡ እግዚኦ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ኢሳ ፡
፱ ፡ ፯ ፡ ፱ ። ጌትነትህ ፡ ቀዳማዊ ፡ ነው ፡
ዕብ ፡ ፩ ፡ ፰ ።



በትረ ፡ ጽድቅ ፡ ወበትረ ፡ መንግሥትከ ።

ወበትረ ፡ መንግሥትከ ፡ በትረ ፡ ጽድ
ቅ ፡ ይላል ፤ የጌትነትህ ፡ ሥልጣንም ፡
ባህርያዊ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ (መንበ
ርከ ፡ በትረ ፡ ጽድቅ ፡ ወበትረ ፡ መን
ግሥትከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም) ፡ ብለህ ፡
ጌትነትህ ፡ በሕርያዊ ፡ ነው ፤ የጌትነ
ትህም ፡ ሥልጣን ፡ ቀዳማዊ ፡ ነው ፤
አንድም ፡ ባህርያዊ ፡ የሚሆን ፡ ጌትነ
ትህ ፤ የጌትነትህ ፡ ሥልጣንም ፤ ቀዳ
ማውያን ፡ ናቸው ፤ ዳዊት ፡ ለዓለመ ፡
ዓለም ፡ ያለውን ፤ ሠለስቱ ፡ ምዕት ፡
ቀዳማዊ ፡ ዘእምቀዳማዊ ፡ ብለውታል ፤
ሠለስቱ ፡ ምዕት ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘእምቀዳ
ማዊ ፡ ያሉትን ፡ ሊቁ ፡ ቴዎፍሎስ ፡
ዓለም ፡ ዘለዓለም ፡ ብሎታል ፤ ቶማስ ፡
እግዚእየ ፡ ወአምላኪየ ፡ ያለውን ፡ አን
ተ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ወአንተ ፡ ዘይእዜ ፡ እን
ዳለው ።

፯ ፡ አፍቀርከ ፡ ጽድቀ ፡ ወዐመፃ ፡ ጸላዕከ ።

እውነትን ፡ ወደድህ ፡ ሐሰትን ፡ ጠላህ ፡
ማለት ፤ ትንቢተ ፡ ነቢያትን ፡ መፈጸ
ምን ፡ ወደድህ ፤ አለመፈጸምን ፡ ጸላህ ፤
አንድም ፡ ሰው ፡ መሆንን ፡ ወደድህ ፡
አለመሆንን ፡ ጠላህ ፤ ሰው ፡ እሆናለሁ ፡
ብሎ ፡ በነቢያት ፡ አናግሮ ፡ መቅረት ፡
መጽላት ፤ የነቢያትን ፡ ነገር ፡ ሐሰት ፡
ማድረግ ፡ ነውና ፤ አንድም ፡ ቀጠሮ ፡
መፈጸምን ፡ ወደድህ ፡ አለመፈጸምን ፡
ጠላህ ። አንድም ፡ (ጻድቀ) ፡ አምላክ ፡
ወልደ ፡ አምላክ ፡ የሚልህን ፡ ወደ
ድህ ፤ (ወአማፂ) ፡ ሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወልደ ፡
ዮሴፍ ፡ የሚልህን ፡ ጸላህ ።

በእንተዝ ፡ ቀብዐከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ።

ሰው ፡ መሆንን ፡ ስለ ፡ ወደድህ ፤ አለ
መሆንን ፡ ስለ ፡ ጠላህ ፡ ፈጣሪህ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ አዋሃደህ ።

ቅብዐ ፡ ትፍሥሕት ፡ እምእለ ፡ ከማከ ፡ ኢሳ ፡
፷፩ ፡ ፩ ።

እንዳንት ፡ ያሉ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡
ከተቀቡት ፡ ልዩ ፡ የሚሆን ፡ ቅብዓ ፡
ትፍሥሕትን ፡ ማለት ፡ ልዩ ፡ ተዋሕ
ዶን ፡ አዋሐደህ ፡ ግብ ፡ ፲ ፡ ፴፰ ። ቅዱስ ፡
ጳውሎስ ፡ ዘይኄይስ ፡ ያለውን ፡ ዮሐ
ንስ ፡ አፈወርቅ ፡ በዘይተ ፡ ፍሥሐ ፡
ብሎ ፡ ወስዶታል ፥ ዘይኄይስ ፡ ማለቱ ፤
የሱ ፡ የማይነሣ ፡ ሕፀፅ ፡ የሌለበት ፡
የባህርይ ፤ የነሱ ፡ የሚነሣ ፡ ሕፀፅ ፡ ያለ
በት ፡ የጸጋ ፤ የሱ ፡ ከራሱ ፡ የነሱ ፡
ግን ፡ ከርሱ ፡ ነውና ።

፰ ፡ ከርቤ ፡ ወቀንዓት ፡ ወሰሊሆት ፡ እምነ ፡ አል
ባሲከ ።

ከርቤ ፡ ቀናንሞ ፡ አበሞ ፡ ከልብሶችህ ፡
ይገኛሉ ፤ ይህስ ፡ ከማናቸውም ፡ ነጋ
ዴ ፡ ይገኛል ፡ ብሎ ፡ አስማተ ፡ ሥላሴ ፡
ከሐዋርያት ፡ ይገኛሉ ፤ አልባሲሁስ ፡
ለክርስቶስ ፡ እሙንቱ ፡ መሃይምናን ፡
እንዲል ፤ አንድም ፡ በሐዋርያት ፡
ቃል ፡ ይነገራል ።

እምህብዓን ፡ አቅርንት ፡ ዘእምኔሆሙ ፡ አስተፈ
ሥሑከ ።

ብዙ ፡ ሥልጣን ፡ ካላቸው ፡ ሥልጣና

ቸው ፡ ከጻና ፡ ከነቢያት ፡ ከነገሥታት ፡ ይልቅ ፡ ደስ ፡ ያሰኙሁህ ፡ ወልድ ፡ እንድም ፡ እስተፌሥሐከ ፡ ጐሥዓ ፡ ልብየ ፡ ቃለ ፡ ሠናየ ፡ ወእነ ፡ እየድዕ ፡ ግብርየ ፡ ለንጉሥ ፡ ብዬ ፡ ደስ ፡ እሰኝ ሃለሁ ፡ እንድም ፡ ዘአስተፍሥሐከ ፡ አብ ፡ ደስ ፡ ያሰኘህ ፡ ወልድ ፡ እስማተ ፡ ሥላሴ ፡ በሐዋርያት ፡ ቃል ፡ ይነገራሉ ።

፱፣ አዋልደ ፡ ንገሥት ፡ ለክብርከ ።

የእቴጌ ፡ ልጆች ፡ ለጌትነትህ ፡ ናቸው ።

ወትቀውም ፡ ንግሥት ፡ በየማንከ ።

እቴጌ ፡ በቀኝህ ፡ ትቀመጣለች ። ኢሳ ፡ ፷፩ ። ራዕ ፡ ፲፱ ፡ ፰ ።

ባልባሰ ፡ ወርቅ ፡ ዑፅፍት ፡ ወኁብርት ።

ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ ደርበ ፡ ደራርበ ፡ ለብሳ ፡ ተጐናፅፋ ።

፲፣ ስምዒ ፡ ወለትየ ፡ ወርእዪ ፡ ወአፅምዒ ፡ ዕዝነኪ ።

ልጂ ፡ ምክሬንና ፡ ትምህርቴን ፡ ፀጥ ፡ ብለሽ ፡ ስሚ ፤ ነቢይ ፡ ነውና ፡ ሁሉን ፡ ልጂ ፡ ይላል ።

ርስዒ ፡ ሕዝበኪ ፡ ወቤተ ፡ አቡኪ ።

የዚያ ፡ የባሌጌ ፡ ያባትሽን ፡ ወገን ፡ እርሺ ፡ ማለት ፡ ተዪ ።

፲፩፣ እስመ ፡ ፈተወ ፡ ንጉሥ ፡ ስነኪ ።

ንጉሥ ፡ የመልክሽን ፡ ደም ፡ ግባት ፡ ወዷልና ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእኪ ።

ጌታሽ ፡ ስለሆነ ፡ ለሚስትነት ፡ መምረጡ ፡ ጌታዋ ፡ ቢሆን ፡ ነውና ፤ እንድም ፡ (አዋልደ ፡ ንግሥት ፡ ለክብርከ) ፡ የምዕመን ፡ ልጆች ፡ ለጌትነትህ ፡ ይገዛሉ ፤ (ወትቀውም) ፡ ምእመንም ፡ በሰጠሃት ፡ ክብር ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ፡ (በአልባሰ ፡ ወርቅ) ፡ ምግባርን ፡ ሃይማኖትን ፡ ይዛ ፡ (ስምዒ) ፡ ልጂ ፡ ምክሬን ፡ ትምህርቴን ፡ ስሚኝ ፤ ወልድየ ፡ እድንን ፡ ለርእየ ፡ ሕልመ ፡ እስከ ፡ ወርእዮ ፡ ሕልመ ፡ አቡሁ ፡ ገብዓ ፤ እንዲል ፡ (ርስዒ) ፡ ያባቶችሽ ፡ የሰናክርን ፡ ግብር ፡ ማለት ፡ ጣዖት ፡ አመልክለሁ ፡ ማለትን ፡ ተዪ ፤ እከ ፡ ረሲዓ ፡ ሕዝበ ፡ አላ ፡ እከያቲሃ ፡ እንዲል ፤ (እስመ ፡ ፈተወ) ፡ ንጉሥ ፡ ክርስቶስ ፡ ምግባርሽን ፡ ሃይማኖትሽን ፡ ወዷልና ፤ (እስመ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእኪ) ፡ ፈጣሪሽ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መምረጡ ፡ ፈጣሪዋ ፡ ቢሆን ፡ ነውና ፡ እንድም ፡ (አዋልደ ፡ ንግሥት) ፡ የመቤታችን ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ልጆች ፡ ለጌትነትህ ፡ ይገዛሉ ፡ (ወትቀውም) ፡ እመቤታችን ፡ በሰጠሃት ፡ ክብር ፡ ፀንታ ፡ ትኖራለች ። እንድም ፡ በቀኝህ ፡ ትቀመጣለች ። ወነበረት ፡ ድንግል ፡ በየማነ ፡ ወልዳ ፡ ወአምላካ ፡ እንዲል ፡ (በአልባሰ ፡ ወርቅ) ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ ንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ ንጽሐ ፡ ልቡና ፡ አንድ ፡ አድርጋ ፡ ይዛ ፡ (ስምዒ ፡ ወለትየ) ፡ ልጂ ፡ ምክሬን ፡ ትምህርቴን ፡ ስሚኝ ፡ ወለትየ ፡ የተመቸ ፡ (ርስዒ ፡ ሕዝበኪ) ፡ በዘር ፡ በሩካቤ ፡ እወልዳለሁ ፡ ማለትን ፡ ተዪ ፤ አሁን ፡ እሱ ፡ መክሮ ፡ አስተምሮ ፡ የሚያስተዋት ፡ ሆኖ ፡



አይደለም ፤ በቅታ ፡ መገኘቷን ፡ መናገር ፡ ነው ፤ (እስመ ፡ ፈተወ) ፡ ሥጋሽን ፡ ለመዋሃድ ፡ መርጧልና ፡ (ወዷልና) ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፤ ፈጣሪሽ ፡ ስለሆነ ፤ ለናትነት ፡ መምረጡ ፡ ፈጣሪዋ ፡ ቢሆን ፡ ነውና ፡ ፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፪ ። ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፯ ።

፲፪፣ ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ አዋልደ ፡ ጢሮስ ፡ በአምኃ ።

የጢሮስ ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ይዘው ፡ ይሰግዱለታል ።

ወለገጽኪ ፡ ይትመሐለሉ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ብዑላነ ፡ ምድር ።

ያንችንም ፡ ፊት ፡ ለማየት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የከበሩ ፡ የገነኑ ፡ አሕዛብ ፡ ይለምናሉ ፤ በአዳራሽ ፡ ገብታ ፡ እልፍኝ ፡ ተከታ ፡ ነውና ፡ የምትኖር ፡ መልኳን ፡ ለማየት ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ እየያዙ ፡ ይመጣሉና ፡ ኢሳ ፡ ፵፱ ፡ ፳፫ ።

፲፫፣ ኵሉ ፡ ክብራ ፡ ለወለተ ፡ ንጉሥ ፡ ሐሴቦን ።

ለሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ለእቴጌ ፡ ሁሉ ፡ ክብሯ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ብስጡ ፡ ብስያጡ ፡ ምንጣፉ ፡ ወርቁ ፡ ብሩ ፡ መርገፉ ።

በዘአገዘፈ ፡ ወርቅ ፡ ዑፁፍት ፡ ወኁብርት ፡ ራዕ ፡ ፲፱ ፡ ፰ ።

ወርቀዘቦ ፡ ግምጃ ፡ ደርበ ፡ ደራርበ ፡ ለለበሰች ፡ ለእቴጌ ።

፲፬፣ ወይወስድዋ ፡ ለንጉሥ ፡ ደናግለ ፡ ድኅሬሃ ።

ለንጉሡ ፡ ከሷ ፡ በኋላ ፡ እንደሷ ፡ ያሉ ፡ ደናግልን ፡ ይወስዱለታል ።

ወቢጻኒሃ ፡ ይወስዱ ፡ ለከ ። ኢሳ ፡ ፷፩ ፡ ፲ ።

የምታውቃቸውን ፡ ባልንጀሮቿን ፡ መሰሎቿን ፡ ይወስዱለታል ።

፲፭፣ ወይወስድዎን ፡ በትፍሥሕት ፡ ወበሐሤት ።

ሲወስዷቸውም ፡ ደስ ፡ እያሰኙ ፡ ይወስዷቸዋል ፡ ማለት ፡ እይዟችሁ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ገብታችሁ ፡ ትዛመዳላችሁ ፡ እያሉ ።

ወያበውዕዎን ፡ ውስተ ፡ ጽርሐ ፡ ንጉሥ ።

ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትም ፡ ያገቧቸዋል ።

፲፮፣ ህየንተ ፡ አበዊኪ ፡ ተወልዱ ፡ ለኪ ፡ ደቂቅ ።

ርስዒ ፡ ሕዝበኪ ፡ ወቤተ ፡ አቡኪ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ስለ ፡ አባቶችሽ ፡ ልጆች ፡ ተተኩልሽ ።

ወትሠይሚዮሙ ፡ መላእክተ ፡ ለኵሉ ፡ ምድር ።

በራቱ ፡ ማዕዘን ፡ አለቆች ፡ አድርገሽ ፡ ትሾሚያቸዋለሽ ፤ ምነው ፡ የሚሾምማ ፡ ንጉሡ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ እገሌ ፡ ይሾምልኝ ፡ እያለች ፡ እያማለደች ፡ የምታሾም ፡ ስለሆነ ፤ እንድም ፡ እሷም ፡ በበኵኋ ፡ ግራዝማች ፡ ቀኛዝማች ፡ ፊታውራሪ ፡ ደጃዝማች ፡ እያለች ፡ ትሾማለችና ።

፲፯፣ ወይዜከሩ ፡ ስመኪ ፡ በኵሉ ፡ ትውልደ ፡ ትውልድ ።

የሰብለ ፡ ወንጌል ፡ የሮማነ ፡ ወርቅ ፡ ልጆች ፡ ነን ፡ እያሉ ፡ ስምሽን ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ይጠራሉ ።

እንድም ፡ ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ ምእመ

2014 04 17

ናን ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡ ይዘው ፡ ይሰግዱለታል ፡ (ወለገጽከ ፡) ፡ ምእመ ናን ፡ አሕዛብም ፡ ፊትሽን ፡ ለማየት ፡ ይመኛሉ ፤ ቆርኔሌዎስ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥ ሮስ ፡ ጢባርዮስ ፡ ዮሐንስን ፡ ለማ የት ፡ ይመኙ ፡ እንደነበረ ፡ (ኵሉ ፡ ክ ብራ) ፡ ለባለ ፡ አእምሮ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ልጅ ፡ ለምእመን ፡ እሳቱ ፡ ስ ለቱ ፡ ሁሉ ፡ ክብሯ ፡ ነው ፡ (በዘአገዘ ፋረ ፡ ወርቅ) ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡ ለያዙቹ ፡ ለምእመን ፡ (ወይወስዱ) ፡ ም እመናን ፡ አሕዛብንም ፡ እያሳመኑ ፡ ይወስዱለታል ፡ (ወቢጻሂ) ፡ መሰሎ ቿን ፡ እለ ፡ ማቴዎስ ፡ መጸብሐዊን ፡ እለ ፡ ዘኬዎስን ፡ (ወይወስድዎን) ፡ ሲ ወስዷቸውም ፡ ደስ ፡ እያሰኙ ፡ ይወስ ዷቸዋል ፡ ማለት ፡ መከራ ፡ ብትቀበ ሉ ፡ ገነት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ትገባ ላችሁ ፡ እያሉ ፡ (ወያበውእዎን) ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፤ ወደ ፡ ወንጌል ፤ ወደ ፡ ጥምቀት ፤ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያ ት ፡ ያገቧቸዋል ፤ አብአኒ ፡ ንጉሥ ፡ ውስተ ፡ ጽርሑ ፡ እንዲል ፡ መሐ ፡ ፩ ፡ ፬ ። እንድም ፡ ወደ ፡ መስቀል ፡ ያገቧ ቸዋል ፡ ወልድዮ ፡ በአ ፡ ውስተ ፡ ጽ ርሑ ፤ ወበህየ ፡ ወድቀ ፡ ወሞተ ፡ እን ዲል ። (ህየንተ ፡ አበውኪ) ።

ስለ ፡ ዐበይተ ፡ ነቢያት ፡ ፈንታ ፡ ሐዋ ርያት ፡ ስለ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ ፈንታ ፡ ሰብዓ ፡ አርድእት ። እንድም ፡ ስለ ፡ ዐ በይተ ፡ ነቢያት ፡ ፈንታ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢ ያት ፡ ስለ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ ፈንታ ፡ ሐዋርያት ፡ ስለ ፡ ሐዋርያት ፡ ፈንታ ፡ ሰብዓ ፡ አርድእት ፡ ስለ ፡ ሰብዓ ፡ አር ድእት ፡ ፈንታ ፡ ሊቃውንት ፡ ተተኩ ልሽ ፡ (ወትሠይሚዮሙ) ፡ ባሬቱ ፡ መ ዓዝን ፡ አለቆች ፡ አድርገሽ ፡ ትሾሚ ያቸዋለሽ ፡ ማኅበሩ ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ የሚሾሙ ፡ ስለሆነ ፡ እንድም ፡ ትሰም ዪዮሙ ፡ ይላል ፡ ሐዋርያት ፡ ሰብአ ፡ አርድእት ፡ እያልሽ ፡ ስም ፡ ታወጪላ ቸዋለሽ ፡ (ወይዘከሩ) ፡ ተዘከሬ ፡ ለአ ሐቲ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ እምጽንፍ ፡ እስከ ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ እያሉ ፡ ስምሽን ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ይጠራሉ ።

እንድም ፡ (ወይሰግዱ ፡ ሎቱ) ፡ እንዳለ ፈው ፡ ወለገጽኪ ፡ ገጸ ፡ ምሕረትሽን ፡ ገጸ ፡ ረድኤትሽን ፡ ለማግኘት ፡ እንድ ም ፡ በቁሙ ፡ ፊትሽን ፡ ለማየት ፡ ይለም ናሉ ፡ እንደ ፡ አባ ፡ ይስሐቅ ፡ አርእየኒ ፡ እመከ ፡ እያለ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ሲጸ ልይ ፡ ኑሯል ፡ ከሰባት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ እመቤታችን ፡ ተገልጻ ፡ ዕረፍትህ ፡ ደርሷል ፡ ክፍልህ ፡ ከኔ ፡ ነው ፡ ብላው ፡ ዓርጋለችና ፡ ተአምረ ፡ ማርያም ፡ (ኵሉ ፡ ክብራ) ፡ ለንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ለመቤታች ን ፡ ክብሯ ፡ ሐሴበን ፡ ዘእምሐሴቦን ፡ ይላል ፡ አፍአዊ ፡ ምድራዊ ፡ ሥጋዊ ፡ ያይደለ ፡ ውሣጣዊ ፡ ሰማያዊ ፡ መንፈ ሳዊ ፡ ነው ፡ (በዘአገዘፋረ ፡ ወርቅ) ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ ንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ ንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ለያዙቹ ፡ ለእመቤታችን ፡ (ወይወስዱ) ፡ ከመቤታን ፡ በኋላ ፡



ሠላሳ ፡ ስድስቱ ፡ ቅዱሳት ፡ አንስትን ፡ ለንጉሥ ፡ ክርስቶስ ፡ ይወስዱለታል ። (ወቢጻሂ) ፡ መሰሎቿንም ፡ ማለት ፡ በ ስም ፡ ደናግል ፡ መበል ፡ (ወትሠይሚ ዮሙ) ፡ ባሬቱ ፡ መዓዝን ፡ አለቆች ፡ አድርገሽ ፡ ትሾሚያቸዋለሽ ፡ የሿሚ ፡ የክርስቶስ ፡ እናት ፡ ስለ ፡ ሆነች ። እን ድም ፡ ሹመት ፡ ከዚህን ፡ ይበልጣል ። ለዶቅስዮስ ፡ ወንበር ፡ ለኒቆላዎስ ፡ ዐ ፅፍ ፡ ሰጥታቸዋለች ። (ወይዘከሩ ፡ ስ

መኪ ፡ በኵሉ ፡ ትውልደ ፡ ትውልድ) ፡ ስምሽን ፡ ባሬቱ ፡ ማዕዘን ፡ ይጠራሉ ። ሰአሊ ፡ ለነ ፡ ቅድስት ፡ ሳይላት ፡ የሚ ውል ፡ የለምና ።

በእንተዝ ፡ ይገንዩ ፡ ለከ ፡ አሕዛብ ፡ እገዚኡ ።

አቤቱ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አሕዛብ ፡ ይገ ዙልሃል ።

ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለሙ ።

መዝሙር ፡ ፵፭ ።

፩ ፤ እምላክነሰ ፡ ኃይልነ ፡ ወፀወንነ ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ። መጽ ሐፍ ፡ በሰ ፡ በወ ፡ መጀመር ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ በሰ ፡ ሲጀምር ፡ ዳዊትሰ ፡ ልሕ ቀ ፡ ወረሥዓ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ይላል ። ፩ ፡ ነገ ፡ ፩ ፡ ፩ ። በወ ፡ ሲጀምር ፡ ወሀሎ ፡ ፩ ፡ ብእሲ ፡ በሀገረ ፡ አውሲጢድ ፡ ፈ ራሄ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘስሙ ፡ ኢዮብ ። ኢዮ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ወሀሎ ፡ ፩ ፡ ብእሲ ፡ በሀገረ ፡ ባቢሎን ፡ ዘስሙ ፡ ኤልያቄም ፡ ይላል ። ፈጣሪያችን ፡ ብንዋጋ ፡ ኃይላችን ፡ ብ ንሸሽ ፡ አምባ ፡ መጠጊያችን ፡ ነው ። የነሰናክሬም ፡ ፈጣሪያቸው ፡ አያድና ቸውም ፡ እንጂ ፡ የኛስ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ብንዋጋ ፡ ኃይላችን ፡ ብንሸሽ ፡ አምባ ፡ መጠጊያችን ፡ ነው ።

ወረዳኢነ ፡ ውእቱ ፡ ለምንዳቤነ ፡ ዘረከበነ ፡ ፈድፋደ ።

ረዳኢነ ፡ ፈድፋደ ፡ ለምንዳቤነ ፡ ፈድ ፋደ ፡ ዘረከበነ ፡ ፈድፋደ ። ፈጽሞ ፡ ላ ገኘን ፡ ጽኑ ፡ መከራ ። እንድም ፡ ጽኑ ፡ መከራ ፡ ፈጽሞ ፡ ባገኘን ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ረዳታችን ፡ ነው ።

፪ ፤ በእንተዝ ፡ ኢንፈርህ ፡ ለእመ ፡ አድለቅለቀት ፡ ምድር ።

ምድር ፡ ብትናወጥ ፡ ማለት ፡ ሠራዊቱ ፡ ቢመጡ ፡ አንፈራም ።

ወለእመኒ ፡ ፈለሱ ፡ አድባር ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ባሕር ።

ነገሥታቱም ፡ ከባቢሎን ፡ ፈልሰው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ተሠራች ፡ ከተ ማ ፡ ቢመጡ ፡ አንፈራም ።

፫ ፤ ደምፁ ፡ ወተሐምጉ ፡ ማያቲሆሙ ።

መጡ ፡ መጡ ፡ ሲባሉ ፡ ተሰሙ ። ወተ ሐምጉ ፡ ጦርነታቸው ፡ ግን ፡ ጠፋ ።

ወአድለቅለቁ ፡ አድባር ፡ እምኃይሉ ።

የእግዚአብሔር ፡ ኃይሉ ፡ ከመገለጹ ፡ የተነሣ ፡ ነገሥታቱ ፡ ጠፉ ። ኢሳ ፡ ፴፯ ፡ ፴፮ ፡ ፴፯ ፡ ፴፰ ። ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፳፭ ።

፱፡ ፈለግ፡ ዘይውኅዝ፡ ያስተፌሥሖ፡ ሀገረ፡ እግዚአብሔር።

በእግዚአብሔር፡ ታዝዞ፡ የመጣ፡ ገዛ
ናም፡ ኢየሩሳሌምን፡ ደስ፡ ያሰኛታ
ል፡ ማለት፡ የዘሩባትን፡ እንድታበቅ
ል፡ የተከሉባትን፡ እንድታጸድቅ፡
ያደርጋታል። አንድም፡ ከሰማይ፡ የ
ወረደ፡ ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ ሀገረ፡ እግ
ዚአብሔር፡ ኢየሩሳሌምን፡ ጠላቷ፡
ሰናክሬምን፡ አጥፍቶ፡ ደስ፡ ያሰኛታ
ል። አንድም፡ ከፋርስ፡ የመጣ፡ ሰና
ክሬም፡ ገንዘቡን፡ ሁሉ፡ ትቶላት፡
ሔዶ፡ ሀገረ፡ እግዚአብሔር፡ ኢየሩ
ሳሌምን፡ ደስ፡ ያሰኛታል።
አንድም፡ (እምላክነሰ)፡ በአርእስቱ፡
በእንተ፡ አካዝ፡ ይላል። ይኸውም፡
ከልጁ፡ ከሕዝቅያስ፡ ገብቶ፡ ይቆጠ
ራል፡ እንጂ፡ አሥራ፡ አንደኛ፡ አር
እስት፡ ተብሎ፡ አይቆጠርም። ይህስ፡
እንደምንድን፡ነው፡ ቢሉ፡ አካዝ፡ በ
ኢየሩሳሌም፡ በሁለቱ፡ነገድ፡ ፋቁሄ፡
ወልደ፡ ሮሜልዩ፡ በሰማርያ፡ በሥሩ፡
ነገድ፡ ረዓሶን፡ በሶርያ፡ ቴልጌልቴል
ፌልሶር፡ በፋርስ፡ በባቢሎን፡ ነግሠ
ዋል። በሰማርያና፡ በሶርያ፡ መኻከል፡
ሬማት፡ ዘገለዓድ፡ የምትባል፡ አገር፡
አለች። የሰማርያው፡ ሲበረታ፡ ለሰ
ማርያው፡ የሶርያው፡ ሲበረታ፡ ለሶ
ርያው፡ የምትገዛ፤ በሀገራችን፡ እን
ዳለች፡ እንደ፡ ዋግ፡ የትግሬው፡ ሲ
በረታ፡ ለትግሬው፡ የበጌምድሩ፡ ሲ
በረታ፡ ለበጌምድሩ፡ ትገዛ፡ እንደ፡ነ
በረ። አሁን፡ በፋቁሄ፡ እጅ፡ ናት። ረ
ዓሶንን፡ ላባቶቼ፡ ላያቶቼ፡ ሲገዙ፡ የነ
አንተ፡ እነሱን፡ አስገዛኝ፡ እኔ፡ ሬማ
ት፡ ዘገለዓድን፡ አስገዛሃለሁ፡ ብሎት፡
ተማምለው፡ ሲሔዱ፡ አካዝ፡ ሰምቶ፡
ደነገጠ። ወሰበ፡ ሰምዐ፡ ዘንተ፡ ዳዊ
ት፡ ደንገፀት፡ ነፍሱ፡ ወነፍሰ፡ ኵሉ፡
ሕዝቡ፡ እንዲል። ወደ፡ ቴልጌልቴል
ፌልሶር፡ ይልክበታል። ገብርከኒ፡ ወ
ወልድከኒ፡ ነዓ፡ ርድዓኒ፡ እምዕቱ፡
ነገሥት፡ እለ፡ ተንሥኡ፡ በላዕሌየ፡
የግድ፡ ባሪያህ፡ የውድ፡ ልጅህ፡ ነኝ
እርዳኝ፡ ብሎ፡ እጥንት፡ ጅማት፡ ጨ
ምሮ፡ ይልክለታል። የሥጋህ፡ ቍራ
ጭ፡ ያጥንትህ፡ ፍላጭ፡ ነኝ፡ ሲል፡
ነው። እሱም፡ ገናና፡ ንጉሥ፡ ነውና፡
ልዋል፡ ልደር፡ ሳይል። ወመጽአ፡ እ
ንዘ፡ ያድለቀልቃ፡ ለምድር። ምድር
ን፡ እያነዋወጣት፡ መጥቶ፡ ደማስቆ፡
አጠገብ፡ ሠፈረ፡ ይህች፡ ሀገር፡ የማ
ን፡ ናት፡ ብሎ፡ ጠየቀ። የወዳጅህ፡ የ
ጠላቱ፡ አገር፡ ናት፡ አሉት። አንድ
ም፡ አጠማጥመው፡ ይነግሩታል። የ
ወዳጅህ፡ የአካዝ፡ ጠላት፡ የፋቁሔ፡
ወዳጅ፡ የረአሶን፡ አገር፡ ናት፡ አሉት።
እሱ፡ ወዴት፡ ሔዷል፡ አለ። ኢየሩ
ሳሌም፡ አሉት፡ ምን፡ ሊያደርግ፡ አለ፡
አካዝን፡ ሊወጋ፡ አሉት። የአካዝን፡
ብላቴና፡ ጥሩ፡ ብሎ፡ አስጠርቶ፡ ጌ
ታህ፡ እርዳኝ፡ ብሎ፡ የላከብኝ፡ ወዴ
ት፡ ድረስ፡ ነው፡ አለው፡ ኢየሩሳሌ
ም፡ ድረስ፡ አለው። ልጅ፡ ቢሆን፡ የ
ጦር፡ መላ፡ ባያውቅ፡ ነው። ጠላትን፡
እንጂ፡ ሲጉዱ፡ ከቤት፡ ጀምሮ፡ነው፡
ውጋ፡ ተኵስ፡ አለ። ብላቴናው፡ ሒዶ፡
የቆጡን፡ አወርድ፡ ብላ፡ የብብቷ፡
አመለጣት፡ እንዲሉ፡ የሰው፡ አገር፡
እናጠፋለን፡ ብላችሁ፡ አገራችሁን፡
አጠፋላችሁ፡ ብሎ፡ ነገራቸው። አን
ድም፡ እነሱ፡ አይተው፡ ተመልሰው፡
ገጠሙ። ፋቁሔ፡ ከዚያው፡ ተወግቶ፡
ሙቷል፡ ረአሶንን። ወአምሠጠ፡ በረ
ዋጺ፡ ፈረስ፡ ይላል፡ ተወግቶ፡ ከገሩ፡
ሒዶ፡ ሙቷል። ፬፡ ነገ፡ ፲፯፡ ፳፱። የነፋ
ቁሔ፡ ወልደ፡ ሮሜልዩ፡ የነረአሶን፡
ፈጣሪያቸው፡ አያድናቸውም፡ እንጂ፡
የኛስ፡ ፈጣሪያችን፡ ብንዋጋ፡ ኃይላ
ችን፡ ብንሸሽ፡ አምባ፡ መጠጊያችን፡
ነው። (ወረዳኢነ)፡ ፈጽሞ፡ ላገኘን፡
ጽኑ፡ መከራም፡ ፈጽሞ፡ ረዳታችን፡
ነው። (በእንተዝ)፡ ረዳታችን፡ ስለ፡
ሆነ፡ ሰራዊቱ፡ ቢመጡ፡ አንፈራም።
(ወለእመኒ)፡ ነገሥታቱም፡ ፈልሰው፡
ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ቢመጡ። (ደምፁ)፡
መጡ፡ መጡ፡ ሲባል፡ ተሰሙ። (ወተ
ሐምጉ)፡ ጦርነታቸው፡ ግን፡ ጠፋ።
(ወአድለቅለቀ)፡ የእግዚአብሔር፡ ኃ
ይሉ፡ ከመገለጽ፡ የተነሣ፡ ነገሥታቱ፡
ጠፉ። (ፈለግ)፡ ከፋርስ፡ የመጣ፡ ቴል
ጌልቴልፌልሶር፡ እነፋቁሔ፡ ወልደ፡
ሮሜልዩን፡ እነረዓሶንን፡ አጥፍቶ፡ ኢ
የሩሳሌምን፡ ደስ፡ ያሰኛታል።



ቀደሰ፡ ማኅደሮ፡ ልዑል።

ልዑል፡ እግዚአብሔር፡ ማደሪያው፡
ኢየሩሴምን፡ በረድኤት፡ አፀናት።

፭፡ እግዚአብሔር፡ ውስተ፡ ማእከላ፡ ኢትትሀወክ።

ሀገሪቱ፡ እንዳትፈታ፡ እግዚአብሔር፡
ከሷ፡ ጋራ፡ በረድኤት፡ አለ።

ወይረድኣ፡ እግዚአብሔር፡ ፍጽመ።

እግዚአብሔር፡ ፊታውራሪ፡ ሁኖ፡
ይረዳታል።

፮፡ ደንገፁ፡ አሕዛብ፡ ወተመይጡ፡ ነገሥት።

ሰራዊቱ፡ የሞት፡ ድንጋፄ፡ደነገጡ፡
እነሰናክሬምም፡ የሰራዊቱን፡ ሞት፡
አይተው፡ ወደ፡ ሀገራቸው፡ ተመለሱ።
አንድም፡ ደንገፁ፡ አሕዛብ፡ ነገሥት፡
ወተመይጡ፡ አሕዛብ፡ የሚሆኑ፡ ፋ
ቁሔ፡ ወልደ፡ ሮሜልዩ፡ ረዓሶን፡ ን
ጉሠ፡ ሶርያ፡ የሀገራቸውን፡ ጥፋት፡
አይተው፡ ደንግጠው፡ ወደ፡ ሀገራ
ቸው፡ ተመለሱ።

ወወሀበ፡ ቃሎ፡ ልዑል፡ ወአድለቅለቀት፡ ምድር።

ልዑል፡ እግዚአብሔር፡ እለ፡ ሰናከ
ሬም። አንድም፡ እነ፡ ፋቁሔ፡ ወልደ፡
ሮሜልዩ፡ እለ፡ ረዓሶን፡ ንጉሠ፡ ሶርያ፡
ይጥፉ፡ እለ፡ ሕዝቅያስ፡ እለ፡ አካዝ፡
ይዳኑ፡ የሚል፡ ቃሉን፡ አሰማ፡ ማ
ለት፡ ረድኤቱን፡ ለሕዝቅያስ፡ ለአ
ካዝ፡ ሰጠ። ለኪሶን። አንድም፡ ሰማ
ርያ፡ ሶርያ፡ ጠፉች።

፯፡ እግዚአ፡ ኃያላን፡ ምስሌነ።
ወምስካይነ፡ አምላኩ፡ ለያዕቆብ።

እግዚአ፡ ኃያላን፡ እምላኩ፡ ለያዕቆብ፡

2014 04 17

ምስሌነ ፡ ወምስካይነ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ አምባ ፡ መጠጊያችን ፡ የሚሆን ፡ የያ ዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ የኀያላኑ ፡ ባለቤት ፡ በረድኤት ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አለ ።
አንድም ፡ (ፈለግ ፡ ዘይውኅዝ ፡ ያስተ ፌሥሕ ፡ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር) ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ሀገረ ፡ እ ግዚአብሔር ፡ እመቤታችንን ፡ ትፀ ንሰ ፡ ወትወልዲ ፡ ወልደ ፡ ብሎ ፡ ደስ ፡ ያሰኛታል ። ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላት ፡ ንጉሥ ፡ በከተማው ፡ እንዲ ኖር ፡ ማኅፀንዋን ፡ ዓለም ፡ አድርጎ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ከምስት ፡ ቀን ፡ ሲመሰ ገንባት ፡ ኑሯልና ፡ ነኪር ፡ ነገሩ ፡ በእ ንተ ፡ እኪ ፡ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ እንዲያመጣው ። መዝ ፡ ፹፯ ። (ቀደሰ) ፡ እግዚአብሔር ፡ ማደሪያው ፡ እመቤ ታችንን ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ አጸናት ። ሦስቱ ፡ አካላት ፡ ስለ ፡ አምስት ፡ ነገር ፡ አድረውባታል ። አብ ፡ ለአጽንዖ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለአን ጽሖ ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ ለመ ወለድ ፡ ለመከፈል ፡ ለመዋሐድ ፡ (እግ ዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ማእከላ) ፡ በዘ መዶቿ ፡ ፍዳ ፡ እንዳትያዝ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ በማኅፀኗ ፡ አደረ ። (ወይረ ድአ) ፡ በዝር ፡ ሆኖ ፡ ይረዳታል ። (ደ ንገፁ) ፡ አሕዛብ ፡ ሠራዊት ፡ አጋንንት ፡ ነገሥት ፡ ሊቃነ ፡ አጋንንት ፡ ድል ፡ ተነሥተው ፡ ከሰው ፡ ልቡና ፡ ወጥ ተው ፡ ወጥተው ፡ ሔዱ ። ሰብእ ፡ አ ላቸው ፡ ይገዟቸዋል ፡ ያድሩባቸዋ ልና ፡ (ወወሀበ ፡ ቃሎ) ፡ ልዑል ፡ እግ ዚአብሔር ፡ አብ ፡ በነቢያት ፡ አድሮ ፡ ልጄ ፡ ይወርዳል ፡ ይወለዳል ፡ ብሎ ፡ ትንቢት ፡ አናገረ ። አንድም ፡ አካላዊ ፡ ቃሉን ፡ ለኩነተ ፡ ሥጋ ፡ ሰጠ ። (ወአ ድለቅለቀት) ፡ ትስብእት ፡ ከመቤታ ችን ፡ ተከፈለ ። (እግዚአ ፡ ኃያላን ፡ ወምስካይነ) ፡ የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ የኀያ ላኑ ፡ ባለቤት ፡ ከሥጋችን ፡ ሥጋን ፡ ከ ነፍሳችን ፡ ነፍስን ፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ ሆነ ።
፳ ፡ ንዑ ፡ ትርአዩ ፡ ግብሮ ፡ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ታዩ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ። አንድም ፡ ኑ ፡ እዩ ።
ዘገብረ ፡ መንክረ ፡ በዲበ ፡ ምድር ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያደረገውን ፡ ድንቅ ፡ ሥራውን ።
፱ ፡ ይሥዕር ፡ ጸብአ ፡ እምአጽናፈ ፡ ምድር ። ሆሴ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ።
ከለኪሶን ፡ እንድም ፡ ከሰማርያ ፡ ከሰ ርያ ፡ ፀብን ፡ አጠፋ ። እንድም ፡ ፀባዔ ፡ ይላል ፡ ፀበኛ ፡ ሰናክሬምን ፡ አንድም ፡ ፀበኛ ፡ ፋቂሔን ፡ ረዓሶንን ፡ አጠፋ ፡ ፀበኛ ፡ ከሌለ ፡ ፀብ ፡ የለምና ።
ይሰብር ፡ ቀስተ ፡ ወይቀጠቅጥ ፡ ወልታ ።
ቀስቱን ፡ ይሰብራል ፡ ጋሻውን ፡ ይቆ ጠቅጣል ። አሁን ፡ ጌታ ፡ የሚሰብር ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ። ግብሩን ፡ አጠፋ ፡ በጦሩ ፡ እንዳይወጉበት ፡ በጋሻው ፡ እ ንዳይመክቱበት ፡ አደረገ ፡ ሲል ፡ ነው ።
ወያውዒ ፡ በእሳት ፡ ንዋየ ፡ ሐቅል ።
የሚዳ ፡ ፀብቱን ፡ በእሳት ፡ አቃጠለ ።



አሁን ፡ የሚያቃጥል ፡ ሁኖ ፡ አይደ ለም ፡ ግብሩን ፡ አጠፋ ፡ ሲል ፡ ነው ። አንድም ፡ የሰናክሬም ፡ ሠራዊት ፡ ይ ዘው ፡ የመጡትን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እስራኤል ፡ የቀና ፡ የቀናውን ፡ ይዘው ፡ ጠማማ ፡ ጠማማውን ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ማግደውታልና ። አንድም ፡ ሠራዊት ፡ አጋንንትን ፡ ሊቃነ ፡ አጋንንትን ፡ አ ጠፋ ።
፲ ፡ አስተርክቡ ፡ ወአእምሩ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ።
ተለዐልኩ ፡ እምአሕዛብ ፡ ወተለዐልኩ ፡ እምድር ።
አስተርኪ ፡ በከሙ ፡ አእምሩ ፡ በሰብእ ፡ ትከት ፡ በሰብእ ፡ ሰዶም ፡ በሰብእ ፡ ገ ሞራ ፡ በሰብእ ፡ ግብፅ ፡ የተደረገውን ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አድርጋችሁ ፡ ከሸኤል ፡ ልዑላኑን ፡ ትሑታኑን ፡ ታ ድጌ ፡ ከአሕዛብ ፡ ልዑላኑን ፡ ትሑታ ኑን ፡ አጥፍቼ ፡ ልዕልናዬን ፡ የገለጽሁ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ እወቁ ።
እግዚአ ፡ ኃያላን ፡ ምስሌነ ።
ወምስካይነ ፡ አምላኩ ፡ ለያዕቆብ ።
አምባ ፡ መጠጊያችን ፡ የሚሆ ፡ የያዕ ቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ የኀያላኑ ፡ ባለቤት ፡ በረ ድኤት ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አለ ።

## መዝሙር ፡ ፵፯ ።

፩ ፡ ኵሉክሙ ፡ አሕዛብ ፡ ጥፍሑ ፡ እደዊክሙ ።
ስለትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ የምእመ ናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ አመ ስግኑ ፡ አሕዛብ ፡ አላቸው ፡ ግብረ ፡ አ ሕዛብ ፡ ይሠራሉና ፡ እንድም ፡ ብዛታ ቸውን ፡ ሲያይ ፡ በጸያፍ ፡ የገባ ፡ አን ድም ፡ ምእመናን ፡ ሸኤል ፡ ምእመናን ፡ አሕዛብ ፡ ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ አመስግኑ ። ይህንንም ፡ ሊቁ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ በሥርዓተ ፡ ቅዳሴ ፡ ወርቅ ፡ አድርጎ ፡ ወስዶታል ።
ወየብቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በቃለ ፡ ትፍሥሕት ።
ለእግዚአብሔር ፡ በደስታ ፡ ቃል ፡ ም ስጋናን ፡ አቅርቡ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ።
፪ ፡ እስመ ፡ ልዑል ፡ መፈርህ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ግሩም ፡ ነውና ።
ወንጉሥ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ።
ባራቱ ፡ ማዕዝን ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ።
፫ ፡ አግረረ ፡ ለነ ፡ አሕዛበ ፡ ወሕዝበ ፡ ታሕተ ፡ እገሪነ ።
ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ዓሥሩን ፡ ነገድ ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ በእጃችን ፡ ጭብጥ ፡ በእግራችን ፡ እርግጥ ፡ አድርጎ ፡ አስ ገዛልን ፡ ይላሉ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ አ ንድም ፡ ምእመናን ፡ ሸኤልን ፡ ምእመ ናን ፡ አሕዛብን ፡ በእጃችን ፡ ጭብጥ ፡ በእግራችን ፡ እርግጥ ፡ አድርጎ ፡ አስ ገዛልን ፡ ይላሉ ፡ ሐዋርያት ፡ አርድእት ።
ወኀረየነ ፡ ሎቱ ፡ ርስቶ ።
ርስት ፡ ልንሆነው ፡ ርስት ፡ ሊሆነን ፡ ርስ

ቱ፡ኢየሩሳሌምን፡እንድም፡መንግሥ
ተ፡ሰማያትን፡ለመውረስ፡መረጠን፡
፬፡ ሥና፡ለያዕቆብ፡ዘአፍቀረ፡ኢሳ፡፲፱፡፩—፬፡
የያዕቆብን ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡ የ
ወደደ ፡ እሱ ፡ ነው ። እንድም ፡ የወ
ደደ ፡ እሱ ፡ ጎረየን ፡ መረጠን ። እን
ድም፡የያዕቆብን፡ሥጋ፡ለመዋሐድ፡
የወደደ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ የወደደ ፡ እሱ፡
መረጠን፡ወሥኑሰ፡ለያዕቆብ፡ዘይቤ፡
ይእቲ ፡ ሥጋ ፡ እንተ ፡ ነሥአ ፡ መድ
ኅን ፡ እማርያም ፡ እንዲል ።

፭፡ ዐርገ ፡ እግዚአብሔር ፡ በይባቤ ።
ወእግዚእን ፡ በቃለ ፡ ቀርን ።

ዐርገ ፡ እግዚአብሔር ፡ እግዚእነ ፡ በ
ይባቤ ፡ ወበቃለ ፡ ቀርን ፡ ብለህ ፡ ግ
ጠም፡ጌታችን፡እግዚአብሔር፡ከሰ
ብዓ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በዘሩባቤል ፡ አ
ድሮ ፡ ትሩፋንን ፡ ይዞ ፡ ነጋሪቱን ፡ እያ
ስመታ ፡ ሳንቲ ፡ ዘጉፍ ፡ መለከት ፡ እ
ያስነፋ ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳ
ሌም፡ወጣ፡የዘሩባቤል፡መንግሥት፡
የጌታ፡ፈቃድ፡ስለሆነ፡የዘሩባቤልን፡
ለጌታ፡ሰጥቶ፡ዐርገ፡አለ፡እንድም፡
በይባቤ ፡ መላእክት ፡ በቅዳሴ ፡ በብር
ሃን ፡ በሥልጣን ፡ ዓረገ ።

፮፡ ዘምሩ ፡ ለአምላክነ ፡ ዘምሩ ።

ለፈጣሪያችን ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።
እንድም ፡ ፈጣሪያችንን፡ፈጽማችሁ፡
አመስግኑ ።

ዘምሩ ፡ ለንጉሥነ ፡ ዘምሩ ።

ለንጉሣችን ፡ ለክርስቶስ ፡ ምስጋና ፡
አመስግኑ ።

፯፡ እስመ ፡ ንጉሥ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኵሉ ፡
ምድር ።

እግዚአብሔር ፡ ላራቱ ፡ ማዕዝን ፡ እ
ንድም፡ለሰው፡ሁሉ፡ንጉሥ፡ነውና።
ቀ ፡ ፬ ።

፰፡ ዘምሩ ፡ ልብወ ፡ ነግሠ ፡ እግዚአብሔር ፡
ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አሕዛብ ።

እግዚአብሔር ፡ በአራቱ ፡ ማዕዝን ፡
ሁሉ ፡ አስታውቆ ፡ ነግሧልና ። አን
ድም ፡ ልብዋን ፡ እንደነገሠ ፡ አውቃ
ችሁ ፡ አመስግኑ ።

እግዚአብሔርሰ ፡ ይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ፡ ቅዱስ ።

ዐርገ ፡ ብዮም ፡ ብናገር ፡ ግብሩ ፡ ሐ
ዲስ፡ስለሆነ፡ነው፡እንጂ፡እንደገናስ፡
ወጣ ፡ ወረደ ፡ አይበልም ። እንዳይበ
ልስ ፡ ጽኑዕ ፡ ክቡር ፡ በሚሆን ፡ በሰ
ማያዊ ፡ መንበሩ ፡ አለ ። እንድም ፡ ዐ
ርገ ፡ ብዮ ፡ ብናገርም ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ እ
ንግድነት ፡ ነው ፡ እንጂ ። እንደገናስ፡
ወጣ ፡ ወረደ ፡ እንዳይበል ፡ በሰማያ
ዊት ፡ መቅደሱ ፡ አለ ። ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፩ ። ሕዝ፡
፩ ፡ ፳፯ ።

፱፡ መላእክተ ፡ አሕዛብ ፡ ተጋብኡ ፡ ምስለ ፡ አም
ላከ ፡ አብርሃም ።

የአሕዛብ ፡ አለቆች ፡ ቂሮስ ፡ ዳርዮስ፡
ከአብርሃም ፡ ከይስሐቅ ፡ ከያዕቆብ ፡
ፈጣሪ ፡ ጋራ ፡ በፈቃድ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ።

እስመ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጽኑዓን ፡ ምድር ፡ ፈድ
ፋደ ፡ ተለዐሉ ።

ጽኑዓን ፡ ምድር ፡ ክቡራን ፡ ምድር ፡ የ
ሚሆኑ ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብ፡



በፈቃድ ፡ አንድ ፡ ቢሆኑ ፡ ከብረዋል፡
እነዚያም ፡ እንከብራለን ፡ ብለው ፡ ይ
ከብሩ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ። እንድም፡
መላእክተ ፡ አሕዛብ ፡ ጽኑዓን ፡ ምድር፡
ጽኑዓን ፡ ክቡራን ፡ የሚሆኑ ፡ የአሕ
ዛብ ፡ አለቆች ፡ ቂሮስ ፡ ዳርዮስ ፡ ከአብ
ርሃም ፡ ከይስሐቅ ፡ ከያዕቆብ ፡ ፈጣሪ፡
ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ። አብርሃም ፡ ይስ
ሐቅ ፡ ያዕቆብ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቢ
ገዙ ፡ ከብረዋል ፡ ገነዋልና ። እነዚያም፡
እንከብራለን ፡ ብለው ፡ ይከብሩ ፡ ዘን
ድ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ። እንድም ፡ ሰሚ ፡ አ
ንቀጽ ፡ አድርገህ ፡ የአሕዛብ ፡ አለቆች፡
ቂሮስ ፡ ዳርዮስ ፡ ከአብርሃም ፡ ከይስ
ሐቅ ፡ ከያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ጋራ ፡ በፈ
ቃድ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ። እነዚያም ፡ አንድ፡
ቢሆኑ ፡ ከብረዋልና ። እላንተም ፡ ትከ
ብሩ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ሁኑ ። እንድም፡
የአሕዛብ ፡ አለቆች ፡ ዘኬዎስ ፡ ማቴ
ዎስ ፡ ከሐዋርያት ፡ ፈጣሪ ፡ ጋራ ፡ በሃ
ይማኖት ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ሁኑ ። ሐ
ዋርያት ፡ አንድ ፡ ቢሆኑ ፡ ከብረዋልና ።
እነዚያም ፡ እንከብራለን ፡ ብለው ፡ ይ
ከብሩ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ።

## መዝሙር ፡ ፺፰ ።

፩፡ ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወብዙኅ ፡ አኰቴቱ ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ገናና ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ም
ስጋናውም ፡ ፍጹም ፡ ነው ።

በሀገረ ፡ አምላክነ ፡ በደብረ ፡ መቅደሱ ።

በሀገርና ፡ በደብር ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ በ
ሄኖን ፡ በቅሩብ ፡ ሳሌም ፡ እንዲል ። ደ
ብረ ፡ መቅደሱ ፡ በተሠራችበት ፡ የፈ
ጣሪያችን ፡ አገር ፡ በምትሆን ፡ በኢየ
ሩሳሌም ፡ ዘፀ ፡ ፳፭ ፡ ፰ ፡ ፱ ።

፪፡ ዘይኤገዝዝ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ለኵሉ ፡ ምድር ።

ዘያሠርቅ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ለሰው ፡ ሁሉ፡
ዐሐይን ፡ የሚያወጣ ፡ ትፍሥሕት ፡ አ
ለው ፡ በግብሩ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ስለ፡
ሆነ ።
እንድም ፡ ዘይሁብ ፡ ተድላ ፡ ደስታን፡
የሚሰጥ ።
እንድም ፡ ልጅነትን ፡ የሚሰጥ ። እዘ
ዙኒ ፡ አበው ፡ በእንተ ፡ ግብረ ፡ እደ
ውየ ፡ ወይትኤዘዝ ፡ ቃል ፡ በሥጋ ፡
እንዲል ።

አድባረ ፡ ጽዮን ፡ በገቦ ፡ መስዕ ።

በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት፡
በጌታ ፡ ረድኤት ፡ ተጠብቀው ፡ ይኖ
ራሉ ። ወያፈቅሩ ፡ ምንዳቤ ፡ በገበ ፡
ትሩፋት ፡ እንዲል ። እንድም ፡ በኢየ
ሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ መላው ፡ እስራኤል ፡
ከመ ፡ ዘበገቦ ፡ መስዕ ፡ ይላል ፡ ገቦ ፡ ገቦ፡
እንዲል ፡ ትግሬ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል፡
ሲል ፡ እንደ ፡ ቀርዱ ፡ እንደ ፡ አራራት፡
ናቸው ። እነዚያ ፡ ብርሃን ፡ እንዳይለ
ያቸው ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ እነዚ
ህም ፡ በረድኤት ፡ ተጠብቀው ፡ ጸን
ተው ፡ ይኖራሉና ።

2014 04 17

ሞገሪ፡ ለንጉሥ፡ ዐቢይ።

የደብረ፡ ጽዮን፡ ቅጽል፡ የዐቢይ፡ ንጉሥ፡ የክርስቶስ፡ ማደሪያ፡ የምት ሆን። ማቴ፡ ፭፡ ፴፭።

፫፡ እግዚአብሔር፡ የአምር፡ ክበዲሃ፡ ሶበ፡ ተመጠውዋ።

እለ፡ ሰናክሬም፡ ብዙ፡ ግንዘቧን፡ እጅ፡ አደረግነው፡ ፡ ባሉ፡ ጊዜ፡ እጅ፡ እን ዳላደረጉ፡ እግዚአብሔር፡ ያውቃል።

፬፡ እስመ፡ ናሁ፡ ነገሥተ፡ ምድር፡ ተጋብኡ፡ ወመጽኡ፡ ኅቡረ።

እነሆ፡ የዚህ፡ ዓለም፡ ነገሥት፡ የሚ ሆኑ፡ እለ፡ ሰናክሬም፡ ተሰብስበው፡ መጥተዋልና፡ እንዲህ፡ ቢመጡ።

፭፡ እሙንቱ፡ ዘንተ፡ ርእዮሙ፡ አንከሩ።

እነ፡ ሕዝቅያስ፡ የሰናክሬምን፡ ብዛት፡ እንድም፡ ሞት፡ አይተው፡ አደነቁ። አንድም፡ እነ፡ ሰናክሬም፡ የሠራዊ ታቸውን፡ ጥፋት፡ አይተው፡ አደነቁ።

ደንገፁ፡ ወፈርሁ፡ ወአንዘዞሙ፡ ረዓድ።

የሞት፡ ድንጋጼ፡ ደነገጡ፡ ፈሩ፡ ማ ለት፡ ፍርሃት፡ ረዓድ፡ አደረባቸው። ድንጋጼ፡ የናላ፡ ፍርሃት፡ የልቡና፡ ረ ዓድ፡ የጉልበት፡ ነው።

፮፡ ወሐሙ፡ በህየ፡ ከመ፡ እንተ፡ ትወልድ።

በህየ፡ በልቡና፡ በነገር፡ በለኪሶን፡ ምጥ፡ እንደ፡ ተያዘች፡ ሴት፡ ሆኑ። ኢሳ፡ ፲፫፡ ፰። ፳፩፡ ፲፯። ኤር፡ ፬፡ ፴፩፡ ፯፡ ፳፬።

፯፡ በነፋስ፡ ኃያል፡ ትቀጠቅጦን፡ ለአሕማረ፡ ተርሴስ።

የብሱን፡ በእግር፡ ባሕሩን፡ በመርከ ብ፡ ተዋግነው፡ የመጡ፡ እነ፡ ሰናክ ሬምን፡ በቅዱስ፡ ሚካኤል፡ በረቂቅ፡ ሥልጣንህ፡ ታጠፋቸዋለህ። እሌ ሎን፡ ለአሕማር፡ እለ፡ በን፡ ከንፍ፡ እ ንዲል።

፰፡ በከመ፡ ሰማዕነ፡ ከማሁ፡ ርኢነ።

እለ፡ ሰናክሬም፡ መጡ፡ ሲባል፡ እንደ፡ ሰማን፡ መጥተው፡ በለኪሶን፡ ሰፍረው፡ አየን። አንድም፡ መሞታቸውን፡ ከነ ቢያት፡ ቃል፡ እንደ፡ ሰማን፡ ሙተው፡ አንድም፡ ሞታቸውን፡ ከኢሳይያስ፡ ቃል፡ እንደ፡ ሰማን፡ ሲሞቱ፡ አየን። አንድም፡ በከመ፡ ርኢነ፡ ከማሁ፡ ሰ ማዕነ፡ ይላል። የሠራዊቱን፡ ሞት፡ እንዳየን፡ የንጉሡን፡ ሞት፡ ሰማን። ይህስ፡ እንደ፡ ምንድን፡ ነው፡ ቢሉ፡ ለ ኪሶን፡ ሲደርስ፡ ቦኑ፡ ግልፎ፡ ዘያድ ኅነኒ፡ እምእዴየ፡ በኢየሩሳሌም፡ አለ። ሙሉ፡ መገዘዘ፡ ቢያሳየው፡ ከሱ፡ ... ሠላሳ፡ ዐራት፡ ነገሥታት፡ ዐሥራ፡ ስምንት፡ እልፍ፡ ከራት፡ ሺሕ፡ መኳ ንንት፡ ወአጋረ፡ ኍልቍሰ፡ ከመ፡ ኆፃ፡ ባሕር፡ ይላል። ጋሻ፡ ጦር፡ ይዞ፡ የማያረበርበው፡ ስፍር፡ ቍጥር፡ የ ሌለው፡ ይህ፡ ሁሉ፡ የደም፡ ልጓም፡ ጕርሶ፡ አደረ። እሱ፡ ወሖረ፡ መጠነ፡ ዘይኋልቆ፡ ሕፃን፡ ይላል፡ ዓሥራ፡ ሁለት፡ ዓሥራ፡ ሦስት፡ ሆኖ፡ ጌታ፡ የመብረቅ፡ የነጐድጓድ፡ ድምጽ፡ እ ያሰማው፡ ሕዝቅያስ፡ መጣብኝ፡ እያለ፡ እየወደቀ፡ እየተነሣ፡ ፋርስ፡ ባቢሎን፡



ሔዶ፡ ሙቷል። ምነው፡ በኢየሩሳ ሌም፡ እንዲሞት፡ ያላደረገው፡ ቢሉ፡ ሐተታ፡ እንዳሰፈው፡ መዝ፡ ፲፫፡ እይ።

በወገሪ፡ እግዚኡ፡ ኃያላን፡ በወገሪ፡ አምላክነ።

አንድ፡ ወገን፡ በሄኖን፡ በትሩብ፡ ሞ ሌም፡ እንዲል። በኢየሩሳሌም፡ አንድም፡ (በከመ፡ ሰማዕነ)፡ ነቢያት፡ ይወርዳል፡ ይወለዳል፡ ሲሉ፡ እንደ፡ ሰማን፡ (ከማሁ፡ ርኢነ)፡ ከመቤታ ችን፡ ተወልዶ፡ አየነው። አንድም፡ ናሁ፡ ነዐርግ፡ ኢየሩሳሌም፡ ወይእኅ ዝዎ፡ ለወልደ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ወይሰቅልዎ፡ ሲል፡ እንደ፡ ሰማነው፡ ተሰቅሎ፡ አየነው። አንድም፡ ናሁ፡ ነዐርግ፡ ኢየሩሳሌም፡ ወይእኅዝዎ፡ ለወልደ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ወይሰ ቅልዎ፡ ወይቀትልዎ፡ ወይትነሣእ፡ በሣልስት፡ ዕለት፡ ሲል፡ እንደ፡ ሰማ ነው፡ ሙቶ፡ ተነሥቶ፡ አየነው። (በ ሀገረ፡ እግዚእ፡ ኃያላን)፡ የኃያላኑ፡ ባለቤት፡ የኃያላኑ፡ ፈጣሪ፡ ማደሪያ፡ በምትሆን፡ በኢየሩሳሌም።

እግዚአብሔር፡ ሣረራ፡ ለዓለም።

እግዚአብሔር፡ ኢየሩሳሌምን፡ በረ ድኤት፡ አጸናት፡ ማለት፡ አገሪቱ፡ እ ንዳትፈታ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ እንዳት ፈርስ፡ አደረጋት።

፱፡ ተወከፍነ፡ እግዚኦ፡ ሣህለከ፡ በማእከለ፡ ሕዝብከ።

አቤቱ፡ በነቢያት፡ በካህናት፡ ጸሎት፡ ይቅርታህን፡ ቸርነትህን፡ አገኘን፡ ይ ላሉ፡ ሕዝቡ።

፲፡ ወበከመ፡ ስምከ፡ ከማሁ፡ ስብሐቲከ፡ ዲበ፡ አጽናፈ፡ ምድር።

ስምህ፡ ባሩክ፡ ማዕገን፡ ምሉዕ፡ እ ንደሆነ፡ ጌትነትህም፡ ባሩክ፡ ማዕገን፡ ምሉ፡ ነው።

ጽድቅ፡ ምሉእ፡ የማንከ።

ሥልጣንህ፡ ቸርነትን፡ የተመላ፡ ነው። አንድም፡ ጽድቅ፡ ምሉዕ፡ የማንከ፡ ቸርነት፡ በሥልጣንህ፡ ምሉ፡ ነው።

፲፩፡ ይትፌሣሕ፡ ደብረ፡ ጽዮን።

የጽዮን፡ ተራራዎች፡ ደስ፡ ይላቸዋ ል፡ ልዑላኑ፡ ደስ፡ ይላቸዋል።

ወይትሐሠያ፡ አዋልደ፡ ይሁዳ።

ትሐሥያኒሃ፡ ለይሁዳ፡ ሲል፡ ነው። ከቤተ፡ ይሁዳ፡ የተወለዱ፡ የሴቶች፡ ትሐሥታኑ፡ ደስ፡ ይላቸዋል። አዋል ዲሃ፡ ለይሁዳ፡ እንዲል።

በእንተ፡ ፍትሕከ፡ እግዚኦ።

አቤቱ፡ ፈርደህ፡ እሕዛብን፡ ስለጠ ፋህ፡ እነሱን፡ ስላዳንሃቸው።

፲፪፡ ዑደዋ፡ ለጽዮን፡ ወሕቀፍዋ።

ሰናክሬም፡ ነው። ኢየሩሳሌምን፡ ፈጽ ማችሁ፡ ከበቧት፡ ይላል።

ወተናገሩ፡ በውስተ፡ ማኅፈዲሃ።

ከበቧት፡ ብሎ፡ ነበርና፡ ባምስቱ፡ በስ ድስቱ፡ በ፯ቱ፡ ቆመ፡ ብእሲ፡ ሆና ችሁ፡ አውኩባት፡ አግርሩባት፡ ደን ፋብት።

፲፫፡ ልብየሙ፡ ውስተ፡ ኃይላ።

ልቡናችሁን፡ ወደ፡ ብዕል፡ ጣሉ፡

ማለት ፡ ገንዘቧን ፡ እንዘርፈዋለን ፡ ብላችሁ ፡ ታመኑ ።

ወትትከፈልዎ ፡ ለክበዲሃ ።

እመኑብት ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብዙ ፡ ገንዘቧን ፡ ትዘርፉላችሁ ።

ከመ ፡ ትንግሩ ፡ ለካልእ ፡ ትውልድ ።

ሁለተኛ ፡ ለሚነሣ ፡ ትውልድ ፡ ማለት ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ትነግሩ ፡ ታስተምሩ ፡ ዘንድ ።

፲፫ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ አምላክነ ። ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ፈጣሪያችን ፡ ለዘላለሙ ፡ ተራዳኢ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ።

ወውእቱ ፡ ይርእየነ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

ለዘላለሙ ፡ የሚጠብቀን ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ያውካል ፡ እንድም ፡ ያኑ ፡ ጣዖቱን ፡ አምላክ ፡ ይሉታልና ።

አንድም ፡ (ዕግትዋ ፡ ለጽዮን) ፡ ሕዝ ቅያስ ፡ ነው ፡ ፈጽማችሁ ፡ በምስጋና ፡ ከበቧት ፡ ይላል ፡ (ወተናገሩ) ፡ ከበ ቧት ፡ ብሎ ፡ ነበርና ። በምስቱ ፡ በስ ድስቱ ፡ በሰባቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ ሁና ችሁ ፡ ጸልዩበት ፡ (ደዩ) ፡ ታድነናለች ፡ ብላችሁ ፡ እመኑባት ፡ (ወትትከፈል ዎ) ፡ እመኑባት ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ እን ዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሰናከሬ ምን ፡ ገንዘቡን ፡ ትዘርፉታላችሁ ። አንድም ፡ ገንዘባችሁን ፡ የሚዘርፉ ችሁ ፡ የለም ። ብላዕ ፡ ዘንተ ፡ ዓመተ ፡ ዘዘራዕከ ፡ ወበካልዕ ፡ ዓመት ፡ ዘአት ረፍከ ፡ ወበሣልስ ፡ ዓመት ፡ ትዘርእ ፡ ወተዓርር ፡ እንዲል ። ፬ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፳፱ ። ከበዲሃ ፡ ብሎ ፡ ዝርዝሩን ፡ ለጽዮን ፡ መስጠቱ ፡ ገንዘቡ ፡ የመጣ ፡ በሷ ፡ ኃይል ፡ ነውና ፡ (ከመ ፡ ትንግሩ) ፡ ሁለ ተኛ ፡ ለሚነሣ ፡ ትውልድ ፡ ትነግሩ ፡ ታስተምሩ ፡ ዘንድ ። (ከመ ፡ ዝንቱ) ፡ ፈጣሪያችን ፡ ለዘላለሙ ፡ ተራዳኢ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ። (ወው እቱ) ፡ ለዘላለሙም ፡ የሚጠብቀን ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ። አሁን ፡ የተመቸ ። አንድም ፡ ለዘላ ለሙ ፡ ይጠብቀናል ፡ ብለህ ፡ እሥር ።

## መዝሙር ፡ ፵፰ ።

፩ ፡ ስምዑ ፡ ዘንተ ፡ ኵልክሙ ፡ አሕዛብ ፡ ኢሳ ፡ ፵፰ ፡ ፩ ።

ተግሣፀ ፡ ነዳያን ፡ ተግሣፀ ፡ ብዑላን ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ምዕዳን ፡ ይበ ላል ። አሕዛብ ፡ መላችሁ ፡ ይህን ፡ ተግ ሣፅ ፡ ስሙ ፡ ዘንተ ፡ ያለውን ፡ ያም ጣው ፡ ያመጣዋል ። ኢሳ ፡ ፵፰ ፡ ፲፱ ።

ወአጽምዑ ፡ ኵልክሙ ፡ እለ ፡ ትነብሩ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ የምትኖሩ ፡ መላችሁ ፡



ልብ ፡ አድርጋችሁ ፡ አድምጡ ።

፬ ፡ በበበሐውርቲክሙ ፡ ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመ ሕያው ።

በየሀገራችሁ ። በበአንጋዲክሙ ፡ በየ ነገዳችሁ ፡ ሁናችሁ ፡ የአዳም ፡ ልጆች ፡ ስሙ ።

አብዕልትኒ ፡ ወነዳይኒ ።

ባለጸጎችም ፡ ድኆችም ፡ አብዕልትኒ ፡ ብሎ ፡ ነዳይኒ ፡ ባይል ፡ ነዳያን ፡ ተግ ሣፀ ፡ ብዑላን ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ተግሣፀ ፡ ነዳያን ፡ አለን ፡ ይህ ፡ ለኛ ፡ ምናችን ፡ ነው ፡ ባሉ ፡ ነበርና ። አብዕልትኒ ፡ ወነ ዳይኒ ፡ አለ ።

፫ ፡ አፉየ ፡ ይነግር ፡ ጥበበ ።

አንደበቴ ፡ ጥበብን ። አንድም ፡ ሕግን ። አንድም ፡ አንድነት ፡ ሦስትነትን ፡ ይና ገራልና ።

ወሕሊና ፡ ልብየ ፡ ምክረ ። ኢዮ ፡ ፴፫ ፡ ፩—፫ ።

ወምክረ ፡ ሕሊና ፡ ልብየ ፡ ይላል ። የልቡናዬ ፡ አሳብ ፡ የሚሆን ፡ ምክር ንም ፡ ይናገራል ። አንድም ፡ ልቡናዬ ፡ ምክርን ፡ ያስባል ።

፬ ፡ አፀምእ ፡ ምሳሌ ፡ በዕዝንየ ።

ስናገርም ፡ አንደበቴ ፡ ሰላ ፡ ልቤ ፡ በላ ፡ ብዬ ፡ አልናገርም ፡ ከወግ ፡ ከታሪክ ፡ ያገኘሁትን ፡ እናገራለሁ ፡ እንጂ ።

ወእከሥት ፡ በመዝሙር ፡ ነገርየ ፡ ሲራ ፡ ፲፰ ፡ ፳፱ ።

ነገሬን ፡ በበገና ። አንድም ፡ በስምዑ ፡ ዘንተ ፡ አንቀጽ ፡ እገልጻለሁ ።

፲፭ ፡ ለምንት ፡ እፈርህ ፡ እምዕለት ፡ እኪት ።

ከዕለተ ፡ ሞት ፡ ከዕለተ ፡ ምጽአት ፡ የተነሣ ፡ ለምን ፡ እፈራለሁ ።

ኃጢአት ፡ ሰኰናየ ፡ ትገትኒ ።

ሰውነቴን ፡ ኃጢአት ፡ ከበኛል ፡ (ትች ፡ አድርገህ) ፡ በንስሐ ፡ አላርቀው ፡ ይመ ስል ፡ ምን ፡ ያስፈራኛል ። በዚያን ፡ ቀን ፡ በተነሣሕያን ፡ ፍርሃት ፡ እንደሌ ለባቸው ፡ ያጠይቃል ። አንድም ፡ (ለ ምንት ፡ እፈርህ) ፡ ከዕለተ ፡ ሞት ፡ ከዕ ለተ ፡ ምጽአት ፡ የተነሣ ፡ ለምን ፡ እፈ ራለሁ ፡ (ኃጢአት ፡ ሰኰናዬ) ፡ እን ዳች ፡ ሰውነቴን ፡ ኃጢአት ፡ ከብበኛ ልን ፡ በዚያን ፡ ቀን ፡ በፍጹማን ፡ ፍር ሃት ፡ እንደሌለባቸው ፡ ያጠይቃል ።

፯ ፡ እለ ፡ ይትአመኑ ፡ በኃይሎሙ ።

መፍራትስ ፡ ብንወረውር ፡ እናርቃ ለን ፡ ብናስር ፡ እናጠብቃለን ፡ ብን መታ ፡ እናደቃለን ፡ ብለው ፡ በኃይላ ቸው ፡ የሚታመኑ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ።

ወይዜኃሩ ፡ በብዝኀ ፡ ብዕሎሙ ።

ወርቁ ፡ ለገዝና ፡ ልብሱ ፡ ለርግና ፡ እህ ሉ ፡ ለቀጠና ፡ ብለው ፡ በገንዘባቸው ፡ ብዛት ፡ የሚመኩ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ።

፰ ፡ እኁኒ ፡ ኢያድኅን ፡ እጓለ ፡ ወኢያድኅን ፡ ሰብእ ።

ስለምን ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ። ስንኳን ፡ ባዕዱን ፡ ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ እን ኳን ፡ አያድንምና ።

፱ ፡ ወኢይሁብ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤዛሁ ።

ገንዘቡን ፡ ለራሱ ፡ ቤዛ ፡ አድርጎ ፡ ኦይ

ሰጥምና፡ ማለት፡ ገንዘቤን፡ ውሰድ፡ እኔን፡ ተወኝ፡ ይቅር፡ በለኝ፡ አይል ምና ።

ወኢተወከፈ፡ ጌጋ፡ ነፍሶ ።

ራሱን፡ ለወንድሙ፡ ለውጥ፡ አድ ርጎ፡ አይሰጥምና ። እኔን፡ ውሰድ፡ ወንድሜን፡ ተወው፡ ብሎ ። አንድም፡ ወንድሜን፡ ውሰድ፡ እኔን፡ ተወኝ፡ ብሎ፡ ወንድሙን፡ ለራሱ፡ ለውጥ፡ አድርጎ፡ አይሰጥምና ።

፱፡ ዘየሐዩ፡ በኀለፍ፡ የሐዩ፡ ለዝሉፉ ።

እንኪያ፡ የሚያድን፡ ማን፡ ነው፡ ትለኝ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ያንጊዜስ፡ ፈጽሞ፡ የሚድን፡ በገድል፡ በትሩፋት፡ የደ ከመ፡ ነው ፤ አንድም፡ ዘየመወስ ። በገ ድል፡ በትሩፋት፡ የደከመ፡ ግን፡ ፈጽሞ፡ ይድናል፡ አንድም፡ በገድል፡ በትሩፋት፡ የደከመ፡ ይድናል፡ እንጂ ። ኢይሁብ ።

እስመ፡ ኢይሬኢ፡ ሙስና ።

ጥፋትን፡ አያይምና ።

፲፡ ሶበ፡ ትሬእዮሙ፡ ለጠቢባን፡ ይመውቱ ።

ጻድቃንን፡ በሥጋ፡ ሲሞቱ፡ ባየህ፡ ጊዜ፡ በነሱም፡ ሞት፡ አለባቸውን፡ ብለህ፡ አታድንቅ፡ ለበጎ፡ ነገር፡ ይራ ቀቃሉና፡ ጠቢባን፡ አላቸው ።

ወኅቡረ፡ ይትኀጐሉ፡ አብዳን፡ እለ፡ አልቦሙ፡ ልብ ።

ጻድቃን፡ በሥጋ፡ ሲሞቱ፡ እንዳየህ፡ አእምሮ፡ ለብዎ፡ የሌላቸው፡ ኃጥአን፡ በነፍስ፡ ሲሞቱ፡ ታያለህና፡ ይህን፡ አድንቅ፡ እንጂ፡ አብዳን፡ አላቸው ። ለበጎ፡ ነገር፡ ሰነፎች፡ ናቸውና ። አን ድም ። (ሶበ፡ ትሬእዮሙ) ፡ ኀጥአን፡ በሥጋ፡ ሲሞቱ፡ ባየህ፡ ጊዜ፡ አታድ ንቅ፡ ይህን፡ የሥጋውን፡ ሞት፡ ጻድቃ ንም፡ ይሞታሉና ። ጠቢባን፡ አላቸው፡ ለክፉ፡ ነገር፡ ይራቀቃሉና፡ ለአከይ ሰ ። ጠቢባን፡ እሙንቱ፡ እንዲል ፡ (ወከማሁ) ፡ አእምሮ፡ ለብዎ፡ የሌላ ቸው፡ ኃጥአን፡ በሥጋ፡ ሲሞቱ፡ እንዳየሃቸው፡ በነፍስም፡ ፍዳ፡ ሲቀ በሉ፡ ታያለህና፡ ይህን፡ አድንቅ፡ እ ንጂ ።

ወየኀድጉ፡ ለባዕድ፡ ብዕሎሙ ።

ገንዘባቸውን፡ ለባዕድ፡ ይሰጣሉ ። እ ሁን፡ ከሞተ፡ በኋላ፡ መብት፡ ኑሮት፡ ለሌላ፡ የሚሰጥ፡ ሁኖ፡ አይደለም፡ እግዚአብሔር፡ ለወደደው፡ የሚሰ ጠው፡ ስለሆነ፡ እንዲህ፡ አለ፡ እንጂ፡ ለሚስቶቻቸው፡ ለልጆቻቸው፡ ይሰ ጣሉ ። ባዕድ፡ አላቸው፡ ከሞተ፡ በኋ ላ፡ ቀብረው፡ ተመልሰው፡ ይህ፡ የጓ ሌ፡ ገንዘብ፡ ይህ፡ የአባቴ፡ ገንዘብ፡ እያሉ፡ ሲጣሉ፡ ይኖራሉና ።

፲፩፡ መቃብሪሆሙ፡ አብያቲሆሙ፡ ለዓለም ።

የዘላለም፡ ቤታቸው፡ መቃብራቸው፡ ነው፡ መቃብራቸው፡ የዘላለም፡ ቤ ታቸው፡ ነው ።

መኃደሪሆሙኒ፡ ለትውልደ፡ ትውልድ ።

ለልጅ፡ ልጅ፡ ማደሪያቸው፡ መቃብ ራቸው፡ ነው ።



ወይሰምዩ፡ አስማቲሆሙ፡ በበበሐውርቲሆሙ ።

ስማቸው፡ በየሀገራቸው፡ ይጠራል ። ውሉድ፡ ወሕንፃ፡ ሀገር፡ ያፀብዩ፡ ስመ፡ እንዲል ። ሲራ፡ ፵፡ ፲፱ ። ልጅ፡ የ ወለደ፡ ሕንፃ፡ የሠራ፡ እንደሆነ፡ ይህ፡ የእገሌ፡ ልጅ፡ ይህ፡ የእገሌ፡ ሕንፃ፡ ነው፡ ተብሎ፡ ስሙን፡ ሲያስጠራ፡ ይኖራልና ። ዘፍ፡ ፫፡ ፲፱ ። ሉቃ፡ ፲፪፡ ፳ ። ሶብ፡ ፱፡ ፳፮ ።

፲፪፡ ወሰብእ፡ እንዘ፡ ክቡር፡ ውእቱ፡ ኢያእመረ ።

ሰው፡ አዋቂ፡ ሲሆን፡ እንደ፡ አላዋቂ፡ ሆነ ። ኢዮ፡ ፲፱፡ ፳፭፡ ፳፱ ።

ወኮነ፡ ከመ፡ እንስሳ፡ ዘአልቦ፡ ልብ፡ ወተመሰሎሙ ።

ኮነ፡ መሰለ፡ አንድ፡ ጊዜ፡ አይፈታ ም፡ አዕምሮ፡ እንደሌላቸው፡ እንደ፡ እንስሳት፡ ሆነ ። አንድም፡ እየራሱ፡ ለማውጣት፡ እንደ፡ እንስሳት፡ አዕ ምሮ፡ የሌለው፡ ኸነ፡ እንስሳትንም፡ መሰለ ። ከዚህ፡ ዳዊት፡ አከብሮ፡ አን ድዮ፡ ተናገረ ፤ ዕገሪ፡ ግን፡ እንስሳት፡ ይኄይሱን፡ ብሎታል ። ላም፡ ከፋፍ፡ ላይ፡ ሁና፡ ሲመገብ፡ ከገደል፡ ሥር፡ ለምለም፡ ሣር፡ ጥሩ፡ ወሀ፡ ያዬ፡ እንደሆነ፡ የረገጠው፡ መሬት፡ ካልከ ዳው፡ በቀር፡ ወርጄ፡ ልመገበው፡ አ ይልም ፤ ሰው፡ ግን፡ ጽድቅ፡ እንዲጠ ቅም፡ ኀጢአት፡ እንዲጎዳ፡ ሲያውቅ፡ ጨለማ፡ ለብሶ፡ ሊሠርቅ፡ ሊቀማ፡ የጉልማሳ፡ ሚስት፡ ሊነሣ፡ ይሔዳ ልና ። ዘፍ፡ ፩፡ ፳፮-፳፱፡ ሉቃ፡ ፲፮፡ ፳፭ ።

፲፫፡ ወዛቲ፡ ፍኖቶሙ፡ ዕቅፍቶሙ ።

ሕጋቸው፡ መሰናከላቸው፡ መሰናከ ላቸው፡ ሕጋቸው፡ ናት ።

እንዘ፡ ይሠምሩ፡ በአፉሆሙ ።

ከዘንድሮ፡ ከርሞ፡ ወጥተን፡ ወርደን፡ ነግደን፡ አርሰን፡ ቆፍረን፡ ጽፈን፡ ደ ጉሰን፡ እንከብራለን፡ ሲሉ ።

፲፬፡ ከመ፡ አባግዕ፡ ሞት፡ ይርዕዮሙ፡ በሲኦል ።

ሞት፡ በመቃብር፡ እንደ፡ በጎች፡ እጅ፡ አድርጎ፡ ይጠብቃቸዋል ።

ወይቀንዮሙ፡ ራትዓን፡ በጽባሕ ።

እስከዚያውም፡ ድረስ፡ የእግዚአብ ሔር፡ ቅን፡ ጭፍሮች፡ ፍልጠት፡ ቁ ርጠት፡ ውጋት፡ ምታት፡ ዕለት፡ ዕለት፡ ይጣቀይጥቸዋል ። ራትዓን፡ አላቸው፡ አታውሉ፡ ያላቸውን፡ አያውሉምና፡ አታሳድሩ፡ ያላቸውን፡ አያሳድሩምና ። አንድም፡ (እንዘ፡ ይሠምሩ)፡ ከነግ፡ ከማልስት፡ ሰጥተን፡ መጽውተን፡ ጹ መን፡ ጸልየን ፤ ቆመን፡ ሰግደን፡ ንስ ሐ፡ ገብተን፡ ከፈጣሪያችን፡ ታርቀን፡ እያሉ፡ በፋቸው፡ ሲያወሩ፡ (ከመ፡ አባግዕ) ፡ ዲያብሎስ፡ በሲኦል፡ እጅ፡ አድርጎ፡ ይጠብቃቸዋል፡ ሞት፡ አለ ው ፤ በግብሩ ፤ (ወይቀንዮሙ) ፡ እስ ከዚያውም፡ ድረስ፡ አጋንንት፡ ዕለት፡ ዕለት፡ ይገዟቸዋል፡ ማለት፡ ኀጢአ ት፡ ሲያሠሯቸው፡ ባዖት፡ ሲያስመ ልኳቸው፡ ይኖራሉ ።

ወትበሊ፡ ረድኤቶሙ፡ በሲኦል፡ እምክብሮሙ ።

ከክብረ፡ ሥጋቸው፡ ተለይተው፡ ወደመቃብር፡ በወረዱ፡ ጊዜ፡ ረድኤት፡ ሚስታቸው፡ ለሌላ፡ ትሔዳለች። ንግበር፡ ሎቱ፡ ቢፀ፡ ዘትረድኦ፡ እንዲል ። ዘፍ፡ ፪፡ ፲፰ ። እንድም፡ ከክብረ፡ ነፍሳቸው፡ ተለይተው፡ ወደ፡ ሲኦል፡ በወረዱ፡ ጊዜ፡ ነፍሳቸው፡ በሲኦል፡ መከራ፡ ትቀበላለች ። እንድም፡ ከክብራቸው፡ ተለይተው፡ ወደ፡ መቃብር፡ በወረዱ፡ ጊዜ፡ ከብዕለ፡ ሥጋቸው፡ የተነሣ፡ ይገዙላቸው፡ የነበሩ፡ ሎሌ፡ ገረድ፡ ይትወሀቡ፡ ለካልእን፡ ለሌላ፡ ይሆናሉ ።

ወባሕቱ፡ እግዚአብሔር፡ ያድኅና፡ ለነፍስየ ። እምእደ፡ ሲኦል፡ ሶበ፡ ይነሥኡኒ ። ሉቃ፡ ፲፭፡ ፳፯ ።

ነገር፡ ግን፡ ሕማማተ፡ ሥጋዬን፡ በመቃብር፡ እጅ፡ አደረግናት፡ ባሉ፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ሥጋዬን፡ ወደ፡ መቃር፡ ከመውረድ፡ ያድናታል ። እንድም፡ አጋንንት፡ ነፍሴን፡ በሲኦል፡ እጅ፡ አደረግናት፡ ባሉ፡ ጊዜ፡ ነፍሴን፡ ሲኦል፡ ከመውረድ፡ ያድናታል ።

፲፮፤ ኢትፍርሆ፡ ለሰብእ፡ ሶበ፡ ይብዕል ።

ሰውን፡ በክበረ፡ በገነነ፡ ጊዜ ።

ወሶበ፡ ይበዝኅ፡ ክብረ፡ ቤቱ ።

ወርቁ፡ ዕንቁ፡ ብስጡ፡ ብስያጡ፡ ፈረስ፡ በቅሎው፡ ላም፡ በሬው፡ ገረድ፡ ሎሌውም፡ በበዛለት፡ ጊዜ፡ አትፍራው፡ ማለት፡ ስደበው፡ አዋርደው፡ ማለት፡ አይደለም፡ ይህን፡ ሁሉ፡ ብትሰበስበው፡ ምን፡ ይሆንሃል፡ ስጥ፡

መጽውት፡ እያልህ፡ ምከረው፡ ማለት፡ ነው፡ እንጂ ።

፲፯፤ እስመ፡ ኢይነሥእ፡ ምስሌሁ፡ ኵሎ፡ አመ፡ ይመውት ።

ሰው፡ ሁሉ፡ በሞተ፡ ጊዜ፡ ገንዘቡን፡ እንድም፡ ኵሎ፡ ይላል ። ሰው፡ በሞተ፡ ጊዜ፡ ገንዘቡን፡ ሁሉ፡ ይዞ፡ አይሔድምና፡ ሰስት፡ ክንድ፡ ከስንዝር፡ ከፈንን፡ ሲያይ፡ ኵሎ፡ በማለት፡ ተናገረው፡ ያንም፡ ቢሆን፡ ቀባሪዎቹ፡ አከበርን፡ በማለት፡ ያደርጉለታል፡ እንጂ፡ እሱ፡ አድርጉልኝ፡ አይላቸውምና ።

ወኢይወርድ፡ ምስሌሁ፡ ኵሉ፡ ክብረ፡ ቤቱ ። ኢዮ፡ ፳፯፡ ፲፱ ።

ቤቱ፡ ንብረቱ፡ ገንዘቡም፡ ሁሉ፡ ከሱ፡ ጋራ፡ ወደ፡ መቃብር፡ አይወርድምና።

፲፰፤ እስመ፡ ፈግዓት፡ ነፍሱ፡ በሕይወቱ ።

በሕይወቱ፡ ሳለ፡ ሰውነቱ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ስላደረገች ። ተዘከር፡ ወልድየ፡ ዘከመ፡ ፈጋዕከ፡ በሕይወትከ፡ እንዲል ። ሉቃ፡ ፲፮፡ ፳፭ ።

የአምነከ፡ ሰብእ፡ ሶበ፡ ታሤኒ፡ ሎቱ ።

እንዲህ፡ ያደረግህለት፡ እንደሆነ፡ ሰው፡ ያመሰግንሃል፤ እመኖ፡ ወልድየ፡ እንዲል ። በለጸጋ፡ ገምግሞ፡ ሸልጎ፡ አይናገርም፡ አፉ፡ እንዳመጣ፡ ይናገራል ። ድኀ፡ ይሰቀቃል ። ባጠገቡ፡ ያለጨዋ፡ አንተ፡ ጌታ፡ እንጂ፡ እንዲህ፡ ማለታቸው፡ ነው፡ ላንተ፡ ሲሉ፡ ነው፡ ይለዋል፡ ዓይናማ፡ ጨዋ፡ የልቤን፡ በምን፡ አወቀው፡ ይለዋልና።



፲፱፤ ወይወርድ፡ ውስተ፡ ኅለመ፡ አበዊሁ ።

አይሆንም፡ ቢል፡ ግን፡ ወዳባቶቹ፡ ዓለም፡ ወደ፡ መቃብር፡ ይወርዳል።

ወኢይሬኢ፡ እንከ፡ ብርሃነ፡ እስከ፡ ለዓለም ።

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ እስከ፡ ዘላለሙ፤ ብርሃን፡ ፀሐይን፤ እንድም፡ ተድላ፡ ደስታን፡ አያይም ። እንድም፡ አብራ፡ ቅዱ፡ ስጥ፡ ለእንግዲ፡ ማለትን፡ አያገኝም ። ኢዮ፡ ፳፩፡ ፳፫-፴፬ ። ሉቃ፡ ፲፪፡ ፲፯-፳፩ ።

፳፤ ሰብእ፡ እንዘ፡ ክቡር፡ ውእቱ፡ ኢያእመረ ።

ሰው፡ አዋቂ፡ ሲሆን፡ አላዋቂ፡ ሆነ ።

ወኮነ፡ ከመ፡ እንስሳ፡ ዘአልቦ፡ ልብ፡ ወተመሰሎሙ ። ተረ፡ ፲፱ ።

አዕምሮ፡ እንደ፡ ሌላቸው፡ እንደ፡ እንስሳት፡ ሆነ ። እንስሳትን፡ መሰለ።

## መዝሙር፡ ፵፱ ።

፩፤ አምላከ፡ አማልክት፡ እግዚአብሔር፡ ነበበ፡ ወጸውዓ፡ ለምድር ።

ዘለፋ፡ ከህናት፡ ነው፤ የምእመናንም፡ ነገር፡ አለበት፤ ከሥሩ፡ አርእስት፡ አንዱ፡ ይህ፡ ነው ። ከህናትን፡ የፈጠረ፡ ጣዖታትን፡ ቀጥቅጦ፡ የሚያጠፋ፡ እግዚአብሔር፡ ተናገረ፤ ምድርንም፡ ጠራት፡ ማለት፡ ከህናት፡ በድለዋልና ። የዘሩባትን፡ እንዳታበቅል፡ የተከሉባትን፡ እንዳታጸድቅ፡ አደረገ ። እንድም፡ በበጎዎች፡ ከህናት፡ አድሮ፡ ከፉዎች፡ ከህናትን፡ ለዘለፋ፡ ጠራ ።

እምሥራቀ፡ ፀሐይ፡ እስከ፡ ዓረብ ።

ከፀሐይ፡ መውጫ፡ እስከ፡ ፀሐይ፡ መግቢያ፡ ድረስ፡ በምልዓት፡ ያለ፡ እግዚአብሔር፤ እንድም፡ ከፀሐይ፡ መውጫ፡ እስከ፡ ፀሐይ፡ መግቢያ፡ ያሉ፡ ከፎች፡ ከህናትን፡ ጠራ ።

፪፤ ወእምጽዮን፡ ሥነ፡ ስብሐቲሁ ።

የምሥጋናው፡ ጌጽ፡ በምትሆን፡ በኢየሩሳሌም፡ አድሮ፡ ያለ፡ እግዚአብሔር። እንድም፡ የጌትነቱ፡ ጌጥ፡ በሚሆኑ፡ በበጎዎች፡ ከህናት፡ አድሮ፡ ያለ፡ እግዚአብሔር፡ ወነሣእኩ፡ ፪ተ፡ አብትረ፡ ለአሐቲ፡ ሰመይክዋ፡ ሥነ፡ ወለካልእታ፡ ሀብለ፡ እንዲል ።

፫፤ እግዚአብሔርሰ፡ ገሃደ፡ ይመጽእ ። ወአምላክነኒ፡ ኢያረምም ።

እግዚአሔር፡ አምላክነ፡ ገሃደ፡ ይመጽእ፡ ወኢያረምም፡ ብለህ፡ ግጠም ። ፈጣሪያችን፡ እግዚአብሔር፡ ተገልጦ፡ ይመጣል፡ መጥቶም፡ ዝም፡ አይልም፡ በበጎዎች፡ ከህናት፡ አድሮ፡ ከፎች፡ ከህናትን፡ ይዘልፋል ።

እሳት፡ ይነድድ፡ ቅድሜሁ ።

ከፊቱ፡ እሳት፡ ይነዳል ።

ዓውደ፡ ዓውዱ፡ ብዙኅ ።

በዙሪያውም፡ ጥቅል፡ ነፋስ፡ አለ፡ ማለት፡ እኒህ፡ የሚጠፉበት፡ መቅሠፍት፡ በባሕርዩ፡ አለ ። ዳን፡ ፯፡፲ ።

፬ ፡ ይጼውዖን ፡ ለሰማይ ፡ በላዕሉ ።

ላዕሉ ፡ ለምድር ፡ ነው ፡ ከምድር ፡ በ
ላይ ፡ ያለች ፡ ሰማይን ፡ ይጠራታል ፡
ማለት ፡ ካህናት ፡ በድለዋልና ፡ ሰማ
ይ ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ እ
ንዳይሰጥ ፡ ማድረጉን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወለምድርኒ ፡ ከመ ፡ ይኰንን ፡ ሕዝቦ ።

በሕዝቡ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ምድርን
ም ፡ ይጠራል ፡ ማለት ፡ ምድር ፡ የዘሩ
ባትን ፡ እንዳታበቅል ፡ የተከሉባትን ፡
እንዳታጸድቅ ፡ ማድረጉን ፡ መናገር ፡
ነው ።

አንድም ፡ (እግዚአብሔርስ) ፡ በሥጋ ፡
ማርያም ፡ ይመጣል ፡ (ወእምላከነሂ) ፡
መጥቶ ፡ ዝም ፡ አይልም ፡ እሴ ፡ ለክ
ጸሐፍት ፡ ወፈሪሳውያን ፡ እያለ ፡ ይዘ
ልፋል ፡ (እሳት) ፡ ከፊቱ ፡ እሳት ፡ ይነ
ዳል ፡ (ዓውዶሂ) ፡ በዙሪያው ፡ ጥቅል ፡
ነፋስ ፡ አለ ፡ ማለት ፡ እኒህ ፡ የሚጠፉ
በት ፡ መቅሠፍት ፡ በባሕርዩ ፡ አለ ፡
(ይጼውዓ) ፡ ልዑላኑን ፡ ካህናቱን ፡ ለ
ዘለፋ ፡ ይጠራል ፡ (ወለምድርኒ) ፡ በ
ሕዝቡ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ትሑታኑን ፡
ካህናት ፡ ለዘለፋ ፡ ይጠራል ።

አንድም ፡ (እግዚአብሔርስ) ፡ በክበበ ፡
ትስብእት ፡ ይመጣል ፡ (ወእምላከነሂ) ፡
መጥቶም ፡ ዝም ፡ አይልም ፡ ጻድቃን
ን ፡ ንዑ ፡ ኅቤየ ፡ ብሎ ፡ ይጠራል ፡ ኃጥ
አንን ፡ ሑሩ ፡ እምኔየ ፡ ብሎ ፡ ያሰናብታ
ል ፡ (እሳት) ፡ ከፊቱ ፡ እሳት ፡ ይነዳል ።
(ዓውዶሂ) ፡ በዙሪያውም ፡ ጥቅል ፡ ነ
ፋስ ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ጻድቃን ፡ የሚድ
ኑበት ፡ ሕይወት ፡ ኃጥአን ፡ የሚጠፉ
በት ፡ መቅሠፍት ፡ በባሕርዩ ፡ አለ ፡ (ይ
ጼውዓ) ፡ መላእክት ፡ እንዳያማልዱ ፡
ይከለክላል ፡ (ወለምድርኒ) ፡ ጻድቃን ፡
እንዳያማልዱ ፡ ይከለክላል ፡ (አንድ
ም ፡ ይጼውዓ ፡ ለሰማይ ፡ ወለምድርኒ) ፡
በሕዝቡ ፡ ይፈርድበት ፡ ዘንድ ፡ ሰማ
ይን ፡ ምድርን ፡ ያሳልፋል ፡ ዘዳ ፡ ፴፪ ፡
፴፩ ፡ ፴፯ ። ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፴፭ ። ማር ፡ ፲፫ ፡ ፴፩ ።
ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፴፫ ። ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፮ ። ዕብ ፲ ፡ ፴፩ ።

፭ ፡ አስተጋብኡ ፡ ሎቱ ፡ ጻድቃኒሁ ።

ጻድቃኑ ፡ ሰሚ ፡ ናቸው ። በጎዎች ፡ ካህ
ናት ፡ ክፉዎች ፡ ካህናትን ፡ ሰበሰቡለት ።

እለ ፡ ይገብሩ ፡ መሥዋዕተ ፡ በሕጉ ።

እንደ ፡ ወጉ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ መሥዋዕት ፡
የሚሠዉ ፡ ክፎች ፡ ካህናትን ፡ ሰበሰ
ቡለት ። ምንም ፡ ቢሆን ፡ ለመሥዋዕት ፡
ጊዜ ፡ ይጠብቁለታልና ፡ በነግህ ፡ በሠለ
ስት ፡ በሰዓት ፡ አንድም ፡ እለ ፡ ትገብ
ሩ ፡ መሥዋዕተ ፡ ዘበሕጉ ። እንደ ፡ ወጉ ፡
እንደ ፡ ሕጉ ፡ መሥዋዕት ፡ የምትሠዉ ፡
በጎዎች ፡ ካህናት ፡ ክፎች ፡ ካህናት ፡ ሰ
በሰቡለት ።

፮ ፡ ይነግሩ ፡ ሰማያት ፡ ጽድቆ ፡ ዚአሁ ። መዝ ፡ ፺፰ ፡ ፮ ።

ለሳቸው ፡ ይባሳቸው ፡ እንጂ ፡ የእግዚ
አብሔርንስ ፡ ቸርነቱን ፡ ሰማያት ፡ ይ
ነግራሉ ፡ ያስተምራሉ ። ተዘርግተው ፡
እየታዩ ፡ የሚያመሰግኑት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡
ሰማይኒ ፡ ይነግር ፡ በእስተርእዮቱ ፡ እ
ንዲል ። መዝ ፡ ፲፰ ፡ ፩ ።



እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኰንን ፡ ውእቱ ። መዝ ፡
፸፬ ፡ ፯

እግዚአብሔር ፡ ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡
ኰናኒ ፡ በርትዕ ፡ ነውና ።

፯ ፡ ስምዓኒ ፡ ሕዝብየ ፡ ወእነግርከ ።
እስራኤል ፡ አሰምዕ ፡ ለከ ።

ስምዓኒ ፡ ሕዝብየ ፡ እስራኤል ፡ እንግ
ርከ ፡ ወእሰምዕ ፡ ለከ ፡ ብለህ ፡ አቅና ።
ወገኔ ፡ እስራኤል ፡ ምክሬን ፡ ትምርቴ
ን ፡ አሰምቼ ፡ እነግርሃለሁና ፡ ስማኝ ።
አንድም ፡ ወገኔ ፡ እስራኤል ፡ ምክሬ
ን ፡ ትምርቴን ፡ አሰምቼ ፡ እነግረህ ፡ ዘ
ንድ ፡ ስማኝ ፡ (አንድም ፡ ስምዓኒ ፡ ሕ
ዝብየ ፡ እስራኤል ፡ እንግርከ) ፡ ወገኔ ፡
እስራኤል ፡ ምክሬን ፡ ትምርቴን ፡ ስ
ማኝ ፡ (ወእሰምዕ ፡ ብከ) ፡ አልሰማም ፡
ብትል ፡ ግን ፡ እዳኝብሃለሁ ፡ የተበደ
ለ ፡ ሰው ፡ የእገሌን ፡ ነገር ፡ ታያላችሁ
ን ፡ ብሎ ፡ ባደባባይ ፡ እንዲያረዳ ።

እምላክከሰ ፡ አምላክ ፡ አነ ፡ ውእቱ ።

እንደዚህ ፡ የምትለኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ አይ
ደለህም ፡ ብዬሃለሁን ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ፈጣሪህስ ፡ የግድ ፡ ፈጣሪህ ፡ ነኝ ።
ግን ፡ ፈጠረኝ ፡ ልትል ፡ ኑሯል ።

፰ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ መሥዋዕቲከ ፡ ዘእዛልፈከ ።

መሥዋዕት ፡ ወቍርባን ፡ ኢፈቀድኩ ፡
ብሎ ፡ ነበርና ። እንግዲያ ፡ መሥዋዕት ፡
ካልሠዋልኝ ፡ ብለህ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እ
ንደ ፡ ሆነ ፡ የምዘልፍህ ፡ መሥዋዕት ፡
ካልሠዋህልኝ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ።

መቍርባኒከኒ ፡ ቅድሜየ ፡ ውእቱ ፡ ዘልፈ ፡ ጊዜ ።

አልቀበለውም ፡ እንጂ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡
የምትሠዋው ፡ መሥዋዕት ፡ የምታቀ
ርበው ፡ ቍርባን ፡ በፊቴ ፡ ነው ። ቍር
ባን ፡ የሚለው ፡ የስንዴ ፡ የወይን ፡ ወ
ገን ፤ መሥዋዕት ፡ የሚለው ፡ የላም ፡
የበግ ፡ ወገን ፡ ነው ። አንድም ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ያልተሠዋው ፡ ቍርባን ፡ የተ
ሠዋው ፡ ነው ። ገላ ፡ ፲፯ ፡ ፳፩ ።

፱ ፡ ኢይነሥእ ፡ እምቤትከ ፡ እጕልተ ።

እንግዲያ ፡ ላሙን ፡ ከቤትህ ፡ እምቦ
ተህ ፡ አልሠዋህልኝ ፡ ብለህ ፡ ነዋ ፡ ት
ለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከቤትህ ፡ እምቦተ
ህ ፡ የምትሠዋውን ፡ ላሙን ፡ አልቀ
በለውም ።

ወእምአብሬትከ ፡ አጣሌ ። ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፳፫ ።
ዕብ ፡ ፲ ፡ ፬ ።

እንግዲያ ፡ ጊደሩን ፡ ወረዋውን ፡ ካ
ልሠዋህልኝ ፡ ብለህ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እ
ንደ ፡ ሆነ ። ከመንጋህ ፡ እምቦተህ ፡ የ
ምትሠዋውን ፡ አልቀበለውም ፤ ለመ
ሥዋዕት ፡ የሚወደደው ፡ ይህ ፡ ነውና ።

፲ ፡ እስመ ፡ ዚአየ ፡ ውእቱ ፡ ኵሉ ፡ አራዊተ ፡ ገዳም ።

እንግዲያ ፡ ዘኖኑን ፡ ጉሹን ፡ አጋዘኑ
ን ፡ ካልሠዋልኝ ፡ ብለህ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ የምዘልፍህ ፡ ይሆን ፡ ሁሉ ፡
ካልሠዋህልኝ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ። በ
በረሀ ፡ የሚኖሩ ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ የኔ ፡
ገንዘቦች ፡ ናቸውና ።

አንስሳ ፡ ገዳምኒ ፡ ወአልህምት ።

እንግዲያ ፡ ብሑሩን ፡ ድኩላውን ፡ ካል

ሠዋልኝ ፡ ብለህ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ፤ አልቀበለውም ።

፲፩ ፡ ወአእምር ፡ ኵሎ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ።

እንግዲያ ፡ ቆቁን ፡ ዥግራውን ፡ ከል ሠዋልኝ ፡ ብለህ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ አንተስ ፡ የምታውቀው ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፡ ነው ። እኔ ፡ ግን ፡ ከፆፌ ፡ ንስር ፡ ገርምር ፡ እስከ ፡ ፆፈ ፡ ድንቢጥ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ አውቀዋለሁና ፡ አልቀበለውም ።

ወሥነ ፡ ገዳምኒ ፡ ኀቤየ ፡ ሀሎ ።

ይህን ፡ ሁሉ ፡ ብሠዋልህ ። (ብትሠዋልኝ) ፡ አልቀበለውም ፡ ማለትህ ። በጎውን ፡ መዓዛ ፡ ሎሚውን ፡ ትርንጐውን ፡ ከልሠዋልኝ ፡ ብለህ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ። አንተስ ፡ የምታውቀው ፡ ሎሚውን ፡ ትርንጐውን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ለኔስ ፡ ባራቱ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ባሥራ ፡ ሁለቱ ፡ አውራኅ ፡ ከልምላሜ ፡ ከጽጌ ፡ ከፍሬ ፡ የማይለዩ ፡ አትክልት ፡ በገነት ፡ አሉኝ ፡ እንዲህ ፡ የሚላቸው ፡ ጻድቃንን ፡ ነው ።

፲፪ ፡ እመኒ ፡ ርኅብኩ ፡ ኢይበለከ ።

አልራብም ፡ እንጂ ፡ ብራብ ፡ ቅሉ ፡ ካንተ ፡ ብሺ ፡ አብላኝ ፡ አጠጣኝ ፡ ብዬ ፡ አልለምንህም ።

እስመ ፡ ዚአየ ፡ ውእቱ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ በምልዑ ።

ዓለም ፡ በምሉ ፡ በጥቅሉ ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ።

፲፫ ፡ ኢይበልዕ ፡ ሥጋ ፡ ላህም ፡ ወኢይሰቲ ፡ ደመ ፡ ጠሊ ።

የላም ፡ ሥጋ ፡ አልበላም ፡ የፍየል ፡ ደም ፡ አልጠጣም ። እግዚአብሔርማ ፡ የፍየል ፡ ደም ፡ የሚጠጣ ፡ ጋላን ፡ ነው ፡ ሻንቅላ ፡ ብሎ ፡ የላሙን ፡ የፍየሉን ፡ የበጉን ፡ መሥዋዕት ፡ አልቀበልም ፡ ሲል ፡ ነው ። ዘሌ ፡ ፯ ፡ ፳፮—፳፯ ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፩-፲፫ ።

፲፬ ፡ ሡዕ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕተ ፡ ስብሐት ።

ቸገረኝሳ ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ብሠዋልህ ፡ አልቀበለውም ፡ ማለትህ ፡ ምን ፡ ያድርግልኝ ፡ ብለህ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደ ሆን ፡ ይቀበልልኝ ፡ ካልህ ። ሡዕ ፡ ካልሁ ፡ ብሎ ፡ መሥዋዕት ፡ ብሏል ፡ እንጂ ፡ የምሥጋና ፡ ጸሎት ፡ ጸልይ ፡ እልሀለሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አድርግልኝ ፡ አላልሁህ ።

ወሀብ ፡ ለልዑል ፡ ጸሎተከ ።

ስትጸልይም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አበርክት ፡ ማለት ። እንድቀበልልህ ፡ አድርገህ ፡ በንጹሕ ፡ ልቡና ፡ ጸልይ ፡ በቂም ፡ በበቀል ፡ ቢጸልዩ ፡ አይቀበልምና ።

፲፭ ፡ ትጼውዓኒ ፡ በዕለተ ፡ ምንዳቤከ ፡ እድኅነከ ፡ ወተአኵተኒ ።

እንዲህ ፡ የሆን ፡ እንደሆን ፡ በመከራህ ፡ ቀን ፡ ትለምነኛለህ ፡ እኔም ፡ ልመናህን ፡ ሰምቼ ፡ ከመከራህ ፡ አድንሃለሁ ። አንተም ፡ ከመከራዬ ፡ ያዳነኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ ብለህ ፡ ታመሰግነኛለህ ። ኢዮ ፡ ፩ ፡ ፳፩—፳፪ ። ዮሐ ፡ ፱ ፡ ፳፱ ፡ ፪ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ። ያዕ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ።



፲፮ ፡ ወለኃጥእሰ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ።

ኃጥእን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለው ። ምነው ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ሲናገረው ፡ የመጣው ፡ ኃጥእ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ እስካሁን ፡ ሲናገረው ፡ የመጣ ፡ ተነሣሂ ፡ ኃጥእ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሚያመጣው ፡ ግን ፡ ኢተነሣሂ ፡ ኃጥእ ፡ ነውና ።

ለምንት ፡ ለከ ፡ ትነግር ፡ ሕግየ ።

ሕጌን ፡ ለምን ፡ ታስተምራለህ ።

ወትነሥእ ፡ በአፉከ ፡ ሥርዓትየ ።

መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፡ እያልህ ፡ በንደበትህ ፡ እየጠቃቀስኸ ፡ ሕጌን ፡ ለምን ፡ ትናገራለህ ።

፲፯ ፡ ወአንተሰ ፡ ጸላእከ ፡ ተግሣፅየ ።

እንዲህ ፡ የምትለኝ ፡ ምክርህን ፡ ትምሕርትህን ፡ አልተቀበልሁምና ፡ ነውን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ። ስንኳን ፡ ልትቀበለው ፡ ለመስማት ፡ ጠላኸው ።

ወአግባዕከ ፡ ድኅሬከ ፡ ቃልየ ።

ሕግህንስ ፡ አልጠበቅሁምና ፡ ነውን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ ስንኳን ፡ ልትጠብቀው ፡ ወደ ፡ ኋላህ ፡ ጣልኸው ። ወደ ፡ ኋላ ፡ የጣሉት ፡ እንዲረሳ ፡ ረሣኸው ። ጌታ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ሙሴ ፡ ነበሩ ፡ ለከሙ ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያን ፡ ኵሎ ፡ ዘይቤሉክሙ ፡ ግበሩ ፡ አለ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፪—፫ ። ከዚህ ፡ ነቢይ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ አይጣላምን ፡ ቢሉ ። አይጣላም ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ነቢዩ ፡ ነው ። ሃይማኖትም ፡ ምግባርም ፡ ካለው ፡ መማር ፡ ይገባል ። ባይሆንም ፡ እንደ ፡ ጌታ ፡ ሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ካለው ፡ መማር ፡ ይገባል ።

፲፰ ፡ እመኒ ፡ ርኢከ ፡ ሰራቄ ፡ ትረውጽ ፡ ምስሌሁ ።

እንዲህ ፡ የምትለኝ ፡ ምን ፡ አድርጌአለሁ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ አንተ ፡ የማታደርገው ፡ ምን ፡ አለ ። ሌባ ፡ ሊሠርቅ ፡ ሲሔድ ፡ ያየህ ፡ እንደሆን ። ገመድህን ፡ ጠቅልለህ ፡ ጎመድህን ፡ ነጥቀህ ፡ ቈዩኝ ፡ አብረን ፡ እንሒድ ፡ ትላለህ ።

ወረሰይከ ፡ መክፈልተከ ፡ ምስለ ፡ ዘማውያን ።

በዚህም ፡ ላይ ፡ ዕድል ፡ ተርታህን ፡ ጽዋ ፡ ፈንታህን ፡ ከዘማውያን ፡ ጋራ ፡ አደረግህ ፡ ማለት ። ሥራህን ፡ ሁሉ ፡ ዝሙት ፡ አደረግህ ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፬ ። ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፳፩ ።

፲፱ ፡ አፉከ ፡ አብዝኃ ፡ ለእኪት ።

ይህም ፡ አልበቃ ፡ ብሎህ ። እንደበትህ ፡ ኃጢአትን ፡ አብዝቶ ፡ ሠራት ፡ ያመጣዋል ።

ወልሳንከ ፡ ጸፈረ ፡ ስሕተተ ።

የተፈተለ ፡ ክፅት ፡ የተታታ ፡ ከሦስት ፡ እንዲሉ ። ከተፈተለ ፡ የተታታ ፡ እንዲጸና ፡ እንደበትህ ፡ ከዳትን ፡ ተንኰልን ፡ አብዝቶ ፡ ሠራት ። ኢዮ ፡ ፲፭ ፡ ፭ ።

፳ ፡ ትነብር ፡ ወትሐምዮ ፡ ለእኁከ ።

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ። ወንድምህን ፡ በደባባይ ፡ ተቀምጠህ ፡ ታማዋለህ ።

2014 04 17

ወእንበርከ ፡ ዕቅፍተ ፡ ለወልደ ፡ እምከ ።

ለናትህ ፡ ለሔዋን ፡ ልጅ ። እንድም ፡ ለሕግ ፡ ለወንጌል ፡ ልጅ ፡ ለምእመን ፡ ዕቅፍተ ፡ ነፍስ ፡ እናርህበት ፡ ማለት ፡ እምተህ ፡ ላሚታ ፡ ንቅፈህ ፡ ለንቃሬ ፡ ሰጠኸው ።

፳፩ ፡ ዘንተ ፡ ገበርከ ፡ አርመምኩ ፡ ለከ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ፅጉሠ ፡ ባሕርይ ፡ ነኝና ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስታደርግ ፡ እያየኹ ፡ ዝም ፡ አልኩህ ፡ ታገሥሁኽ ፡ ፍርድህ ፡ ነው ፡ ይገባሃል ፡ ይኸውም ፡ ሲያንስህ ፡ ነው ።

አድመተከኑ ፡ ኀጢአት ፡ ገዘብከኑ ፡ እኩየ ፡ ከማከ ።

ኀጢአት ፡ አማረችህ ፡ ደስ ፡ ደስ ፡ አሰኘችህ ፡ ጣፈጠችህ ፡ ጨው ፡ ጨው ፡ አለችህ ። ቢሆንስ ፡ እኔ ፡ እንዳንተ ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፡ ትጠረጥረኛለህን ። ኀጢአት ፡ መሥራት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አላዋቂ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። ንስሐም ፡ አለመግባት ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍቀሬ ፡ ኀጢአት ፡ ማድረግ ፡ ነውና ።

እዛለፍከኑ ፡ ወእቀውም ፡ ቅድመ ፡ ገጽከ ።

ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የቀረህ ። ከፊትህ ፡ ቆሜ ፡ ልዘልፍህ ፡ ትችላለህ ።

፳፪ ፡ ለብዉ ፡ ዘንተ ፡ ኵልክሙ ፡ እለ ፡ ትረሥዕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የምትዘነጉት ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ ተግሣፅ ፡ ስሙ ፡ እወቁ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።

ወኢመ ፡ ኢይመሥጥ ፡ ወአልቦ ፡ ዘያድኅን ።

ያለዚያ ፡ ግን ፡ በሞት ፡ እየነጠቀ ፡ ይወስዳችኋል ፡ የሚያድናችሁ ፡ የለም ፡ የምሢጢ ፡ ንዳ ፡ አያስጥል ፡ የረዳ ፡ እንዲሉ ።

፳፫ ፡ መሥዋዕት ፡ ክብርት ፡ ትሴብሐኒ ።

ለሳቸው ፡ ይበሳቸው ፡ እንጂ ፡ ለኔስ ፡ የበጎ ፡ የበጎ ፡ ሰዎች ፡ መሥዋዕት ፡ ክብሬን ፡ ትገልጽልኛለች ። ይህን ፡ መናገሬ ፡ ችግር ፡ ኑሮብኝ ፡ አይደለም ።

ህየ ፡ ፍኖት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ አርእዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ አድኅኖቶ ።

ይህችውም ፡ ጌታ ፡ ትድግናውን ፡ የገለጸባት ፡ ናት ፡ ማለት ፡ እሳቸውም ፡ በፍጹም ፡ ልቡና ፡ እንደሠዉለት ፡ ጌታም ፡ ትድግናውን ፡ እንዳደረገላቸው ፡ የምታስረዳ ፡ ናት ።

አንድም ፡ (መሥዋዕት ፡ ክብርት) ፡ መሥዋዕተ ፡ ኖኅ ፡ ክብሬን ፡ ትገልጽልኛለች ፡ (ህየ ፡ ፍኖት) ፡ ይህችውም ፡ ጌታ ፡ በመርከብ ፡ ትድግናውን ፡ የገለጸባት ፡ ናት ።

አንድም ፡ (መሥዋዕት) ፡ መሥዋዕተ ፡ ሙሴ ፡ ክብሬን ፡ ትገልጽልኛለች ፡ (ህየ ፡ ፍኖት) ፡ ይህችውም ፡ ጌታ ፡ በግብፅ ፡ ትድግናውን ፡ የገለጸባት ፡ ናት ። አንድም ፡ (መሥዋዕት ፡ ክብርት) ፡ መሥዋዕተ ፡ አርጋ ፡ ክብሬን ፡ ትገልጽልኛለች ፡ (ህየ ፡ ፍኖት) ፡ ይህችውም ፡ ጌታ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ትድግናውን ፡ የገለጸባት ፡ ናት ። እርጋ ፡ ኢየሩሳሌም ፡



ሙቼ ፡ ገበና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ልጆቹ ፡ በሱ ፡ ሕግ ፡ ጸንተው ፡ ስለኖሩ ። አንድም ፡ (መሥዋዕት ፡ ክብርት) ፡ መሥዋዕተ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ክብሬን ፡ ትገልጽልኛለች ፡ (ህየ ፡ ፍኖት) ፡ ይህችውም ፡ ጌታ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ትድግናውን ፡ የገለጸባት ፡ ናት ። አንድም ፡ መሥዋዕት ፡ ክብርት) ፡ መሥዋዕተ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክብሬን ፡ ትገልጽልኛለች ፡ (ህየ ፡ ፍኖት) ፡ ይህችውም ፡ ጌታ ፡ በቀራንዮ ፡ ትድግናውን ፡ የገለጸባት ፡ ናት ።

## መዝሙር ፡ ፶ ።

፩ ፡ ተሣሃለኒ ፡ እግዚኦ ፡ በከመ ፡ ዐበየ ፡ ምሕረትከ ።

ስለራሱ ፡ ተናገርታል ፡ የትሩፋንም ፡ የምእመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ አቤቱ ፡ እንደ ፡ ይቅርታህ ፡ ብዛት ፡ ገናንነት ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

ወበከመ ፡ ብዝኀ ፡ ምሕረትከ ፡ ደምስስ ፡ ኃጢአትየ ።

እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ብዛትም ፡ መጠን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

፪ ፡ ሕፅበኒ ፡ ወእንጽሐኒ ፡ እምኀጢአትየ ። ኢሳ ፡ ፩-፲፮ ፲፰ ።

ከኃጢአቴ ፡ ፈጽመህ ፡ ንጹሕ ፡ አድርገኝ ።

ወእምዐበሳየኒ ፡ አንጽሐኒ ።

ኀጢአት ፡ ታናሽ ፡ አበሳ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ ታላቅ ፡ ታናሽ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርቼ ፡ ከመጣብኝ ፡ ፍዳ ፡ አድነኝ ፡ ያዕ ፡ ፬-፰ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ለልየ ፡ አአምር ፡ ጌጋይየ ። ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፲፪ ።

እኔ ፡ ባለቤቱ ፡ በደሌን ፡ በሰውነቴ ፡ አውቄዋለሁና ።

ወኃጢአትየኒ ፡ ቅድሜየ ፡ ወእቱ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ኀጢአቴም ፡ ሁልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ ነው ፡ አስበዋለሁ ፡ ይኸውም ፡ ከደግነት ፡ አያወጣውም ። ኃጢአትን ፡ ሠርቶ ፡ ማሰብ ፡ ከደግነት ፡ አያወጣምና ። ተዘክር ፡ አንተ ፡ ቅድመ ፡ ዐበሳከ ፡ ከመ ፡ ኢይዝክር ፡ ብከ ፡ ፈጣሪከ ፡ እንዲል ።

፬ ፡ ለከ ፡ ለባሕቲትከ ፡ ዐበስኩ ፡ ወእኩየ ፡ በቅድሜከ ፡ ገበርኩ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ያገኘህ ፡ እየበደልህ ፡ አይደለምን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ ብበድልስ ፡ አንተን ፡ መሐሪውን ፡ አይደለምን ፡ (ወእኩየኒ) ፡ በፊትህ ፡ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ እየሠራሁ ።

ከመ ፡ ትጽድቅ ፡ በነቢብከ ፡ ወትማዕ ፡ በፍትሕከ ።

ዙሉ ፡ አበ[illegible] ፡ በቅድሜየ ፡ ሰማይኒ ፡ ኢኮነ ፡ ንጹሐ ፡ ሙኑ ፡ ዘይነጽሕ ፡ እምኀጢአት ፡ ብለህ ፡ በተናገርከው ፡ እዋቂ ፡ ትባል ፡ ዘንድ ፡ (ወትማዕ) ፡ እንዲሁ ፡ ብለህ ፡ በፈረድኸው ፡ ፍርድ ፡ ትረታ ፡ ትመታ ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ሰማይኒ ፡ ኢኮነ ፡ ንጹሐ ፡ በቅድሜየ ፡

2014 04 17

ብለህ ፡ በተናገርከው ፡ አዋቂ ፡ እንድ
ትባል ፡ እንድትረታ ፡ እንድትመታ ፡
እያወቅሁ ። ኢሳ ፡ ፵፫ ፡ ፳፯ ። ሉቃ ፡ ፲፰ ፡
፲፫ ። ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፬ ። ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

፭ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ በኀጢአት ፡ ተፀነስኩ ።

እነሆ ፡ በኀጢአት ፡ ተፀንሻለሁና ።

ወበኀጣውእ ፡ ወለደተኒ ፡ እምየ ።

እናቴም ፡ በዓመፃ ፡ ወልዳኛለችና ፡
የዳዊት ፡ እናቱ ፡ ሁብሊ ፡ አባቱ ፡ ዕሴ
ይ ፡ ይባላሉ ። አንድ ፡ ጕልማሳ ፡ ጕረ
ቤት ፡ አላቸው ፡ ዓይኑ ፡ ሲፈቅዳት ፡
አይቶ ፡ መንገድ ፡ እሔዳለሁና ፡ ስን
ቄን ፡ አሰናጅልኝ ፡ አላት ፡ አሰናድታ ፡
ሰጥታው ፡ ይዞ ፡ ሔዶ ። ሌሊት ፡ ተመ
ልሶ ፡ መጥቶ ፡ ጕረቤቱን ፡ መስሎ ፡
ሳይታወቅ ፡ ተገናኝቷት ፡ ሒዷልና ፡
እንዲህ ፡ አለ ።

አንድም ፡ ኃጢአት ፡ በሠለጠነበት ፡
ወራት ፡ ተወልጃለሁና ፡ ይላል ፤ ትሩ
ፍ ፤ አንድም ፡ እናቴ ፡ ሔዋን ፡ ኀጢ
አትን ፡ በኋላዮ ፡ ፀንሳ ፡ በነቢብ ፡ ወ
ልዳ ፡ በገቢር ፡ በምታሳድግበት ፡ ወራ
ት ፡ ተወልጃለሁና ። ኢሳ ፡ ፵፯ ፡ ፰ ፡ ኤር ፡
፫ ፡ ፲፱ ። ሉቃ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ።

፮ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ጽድቀ ፡ አፍቀርከ ።

እነሆ ፡ እውነትን ፡ ወደሃልና ።

ዘኢይትነበብ ፡ ኅቡዐ ፡ ጥበበከ ፡ አይዳዕከኒ ።

ዋጋው ፡ ይህ ፡ ተብሎ ፡ የማይነገር ፡
ሕግህን ፡ ሠራህልኝ ።

፯ ፡ ትነዝኀኒ ፡ ወእነጽሕ ፡ ወእነጽሕ ።

በማየ ፡ ንስሐ ፡ ታጽበኛለህ ፡ እኔም ፡
ንጹሕ ፡ እሆናለሁ ።

ተሐፅበኒ ፡ ወእምበረድ ፡ እፀዐዱ ።

በማየ ፡ ንስሐ ፡ ታዕበኛለህ ፡ እኔም ፡ ከበ
ረድ ፡ ይልቅ ፡ ንጹሕ ፡ እሆናለሁ ። እዳ
ዘፍ ፡ ፱ ፡ ፯ ። ኢዮ ፡ ፱ ፡ ፴ ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ። ሮሜ ፡
፮ ፡ ፳፫ ።

፰ ፡ ታሰምዐኒ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ወሐሤተ ።

ተዓደዋ ፡ ለኃጢአትከ ፡ ብለህ ፡ ፈጽሞ ፡
ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ቃል ፡ ታሰማኛለህ ።

ወይትፌሥሑ ፡ አዕፅምተ ፡ ጻድቃን ።

የጻድቃን ፡ ወገኖች ። አንድም ፡ ሕዋ
ሳት ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

አንድም ፡ (እስመ ፡ ናሁ ፡ ጽድቀ ፡ አፍ
ቀርከ) ፡ እነሆ ፡ እውነትን ፡ ወደሃልና ፡
(ዘኢይትነበብ) ፡ ዋጋው ፡ ይህ ፡ ተብ
ሎ ፡ የማይነገር ፡ ሕግህን ፡ ከአሕዛብ ፡
ሠውረህ ፡ ሠራህልኝ ። (ትነዝኀኒ) ፡
በማየ ፡ ምንዛሕ ፡ ታጽበኛለህ ፡ እኔም ፡
ንጹሕ ፡ እሆናለሁ ። (ተሐፅበኒ) ፡ በማ
የ ፡ ምንዛሕ ፡ ታጽበኛለህ ፡ እኔም ፡ ከበ
ረድ ፡ ይልቅ ፡ ንጹሕ ፡ እሆናለሁ ፡ (ታሰ
ምዓኒ) ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ሐሲቆ ፡ ብ
ለህ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ቃል ፡ ታሰማ
ኛለህ ። (ወይትፌሥሑ) ፡ ትሩፋን ፡
ደስ ፡ ይላቸዋል ።

አንድም ፡ (እስመ ፡ ናሁ) ፡ እነሆ ፡ ሰው ፡
መሆንን ፡ ወደሃልና ፡ (ዘኢይትነበብ ፡





ዋጋው ፡ ይህ ፡ ተብሎ ፡ የማይነገር ፡
ሥጋዌህን ፡ ከአይሁድ ፡ ከመናፍቃን ፡
ከአጋንንት ፡ ሠውረህ ፡ ገለጽህልኝ ።
አጋንንት ፡ የጌታን ፡ ጽንስ ፡ አውቀ
ው ፡ ቢሆን ፡ ብዙ ፡ ዕንስ ፡ ባበላሹ ፡
ነበርና ፡ (ትነዝኀኒ) ፡ በማየ ፡ ገቦ ፡ በ
ደመ ፡ ገቦ ፡ ታዕበኛለህ ፡ እኔም ፡ ንጹ
ሕ ፡ እሆናለሁ ። አንድም ፡ የአሪቱ ፡
ሳይቀር ፡ ዛቲ ፡ ቃል ፡ ተሜረየት ፡ በ
ደም ፡ ህየንተ ፡ ቄዕለ ፡ ሐሰጼ ፡ እን
ዲል ፡ ቀድሞ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ጊ
ደር ፡ አምጥተው ፡ አባላ ፡ መትተው ፡
ደሟን ፡ በብርት ፡ ተቀብለው ፡ ውትት ፡
ጨምረው ፡ አመድ ፡ ነስንሰው ፡ አዋ
ህደው ፡ እንዶድ ፡ ስምዕዛ ፡ ቅጠል ፡
በሐር ፡ ጕንጕነው ፡ ሕዝቡን ፡ ይረጯ
ቸዋል ፡ በዚህ ፡ ከጥቃቅኑ ፡ ኃጢአት ፡
ይነጹበታልና ። (ተሐጽበኒ) ፡ በማየ ፡
ገቦ ፡ በደመ ፡ ገቦ ፡ ታዕበኛለህ ፡ እኔም ፡
ከበረድ ፡ ይልቅ ፡ ንጹሕ ፡ እሆናለሁ ፡
(ታሰምዓኒ) ፡ በሐሙስ ፡ ዕለት ፡ ብለ
ህ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ቃል ፡
ታሰማኛለህ ፡ (ወይትፌሥሑ) ፡ ምእ
መናን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፱ ፡ ሚጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኃጢአትየ ።

ከኃጢአቴ ፡ መገለጽ ። አንድም ፡ ከኃ
ጢአቴ ፡ ብዛት ፤ አንድም ፡ ኃጢአ
ቴን ፡ ከመመልከትህ ፡ የተነሣ ፡ ከኔ ፡
ወደዚያ ፡ የመለስኸውን ፡ ገጽ ፡ ምሕ
ረትህን ፡ ከዚያ ፡ ወደኔ ፡ መልሰው ።
አንድም ፡ ከዚያ ፡ ወደኔ ፡ የመለስከ
ውን ፡ ገጹ ፡ መዓትህን ፡ ከኔ ፡ ወደዚያ ፡
መልሰው ።

ወደምስሳ ፡ ሊተ ፡ ኵሉ ፡ አበሳየ ።

ኀጢአቴንም ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።
፵፫ ፡ ፳፭ ።

፲ ፡ ልበ ፡ ንጹሐ ፡ ፍጥር ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ንጹሕ ፡ ልቡና ፡ ፍጠርልኝ ፡
እንደ ፡ ገናማ ፡ ሲፈጥር ፡ ይኖራልን ፡
ብሎ ፡ ይገለጸው ።

መንፈስ ፡ ርቱዐ ፡ ሐድስ ፡ ውስተ ፡ ከርሥየ ።

ልበ ፡ ያለውን ፡ መንፈስ ። ንጹሕ ፡
ያለውን ፡ ርቱዐ ፤ ፍጥር ፡ ያለውን ፡
ሐድስ ፡ ብሎ ፡ ገለጸው ። ልቡናዬን ፡
በእውቀት ፡ አድስልኝ ። ፩ ፡ ፮ ።

፲፩ ፡ ኢትግድፈኒ ፡ እምቅድመ ፡ ገጽከ ።

ከባለሟልነትህ ፡ እንዳወጣኸኝ ፡ አት
ቅር ።

ወመንፈስከ ፡ ቅዱስ ፡ ኢታውፅእ ፡ እምላዕሌየ ።

ዳዊት ፡ ትሩፍ ፡ መንፈስ ፡ ረድኤት
ህን ፤ ምእመን ፡ ልጅነትህን ፡ ከኔ ፡ አት
ለየው ፡ እንደ ፡ ለየኸው ፡ አትቅር ።

፲፪ ፡ ዕሥየኒ ፡ ፍሥሐ ፡ በአድኅኖትከ ።

በትድግናህ ፡ ደስ ፡ አሰኘኝ ፤ አንድም ፡
(ዕሥየኒ ፡ ፍሥሐ) ፡ ተድላ ፡ ደስታን ፡
(ወአድኅኖተከ) ፡ ትድግናህንም ፡ ስ
ጠኝ ። አንድም ፡ በትድግናህ ፡ ልጅ
ነትን ፡ ስጠኝ ።

ወበመንፈስ ፡ እዚዝ ፡ አጽንዐኒ ።

ዳዊት ፡ ትሩፍ ፡ በመንፈስ ፡ ረድኤት ፡
ምእመን ፡ በልጅነት ፡ አጽናኝ ።

፲፫፡ ከመ፡ እምሀሮሙ፡ ለኃጥኣን፡ ፍናዊከ። ወረሲዓን፡ ይትመየጡ፡ ኀቤከ።

ከመ፡ እምሀርሙ፡ ለኃጥአን፡ ረሲ
ዓን፡ ፍናትከ፡ ወይትመየጡ፡ ኀቤከ፡
ብለህ፡ ግጠም፡ ሕግህን፡ ለዘንጉ፡ ኃጥ
እን፡ ሕግሕን፡ አስተምራቸው፡ ዘን
ድ፡ ወዳንተም፡ ይመለሱ፡ ዘንድ፡
አጽንዓኒ።

፲፬፡ አድኅነኒ፡ እምደም፡ እግዚአብሔር፡ አምላኪየ፡ መድኃኒትየ።

ዳዊት፡ ድኅነቴን፡ የምታደርገኝ፡
እግዚአብሔር፡ ደመ፡ ኦርዮን፡ አፍ
ስሼ፡ ከመጣብኝ፡ ፍዳ፡ አድነኝ፡ ይ
ላል። ትሩፍ፡ ደመ፡ በግዕን፡ ለማ
ምት፡ ከማፍሰሴ፡ የተነሣ፡ ምእመን፡
ደመ፡ በለስን፡ ከማፍሰሴ፡ የተነሣ፡
ከመጣብኝ፡ ፍዳ፡ አድነኝ፡ ተነሣሀ
ያን፡ አይሁድም፡ ደመ፡ ወልደ፡ እግ
ዚአብሔርን፡ ከማፍሰሳችን፡ የተነሣ፡
ከመጣብን፡ ፍዳ፡ አድነን፡ ይላሉ።

ይትፌሣሕ፡ ልሳንየ፡ በጽድቅ፡ ዚአከ፡ እግዚኦ።

አቤቱ፡ አንደበቴ፡ ቸርነትህን፡ በመ
ናገር፡ ደስ፡ ይለዋል።

፲፭፡ ትከሥት፡ ከናፍርየ፡ ወአፉየ፡ ያየድዕ፡ ስብሐቲከ።

አንደበቶቸን፡ በውቀት፡ ትገልጻለህ፡
እነሱም፡ ጌትነትህን፡ ተአምራትህን፡
ይናገራሉ፡ (አንድም፡ ከሥት፡ ከና
ፍርየ፡ ወአፉየ፡ ያይድዓ)፡ አንደበቴ
ን፡ መልቼ፡ አመሰግንህ፡ ዘንድ፡ ም
ሥጢር፡ ግለጽልኝ። ትሖ፡ ፳፪፡ ፴፱።
ሮሜ፡ ፲፩፡ ፱፡ ፲፪፡ ፲፩።

፲፮፡ ሶበሰ፡ ፈቀድከ፡ መሥዋዕተ፡ እምወሀብኩ።

መሥዋዕት፡ ወቍርባን፡ ኢፈቀድኩ፡
ትላለህ፡ እንጂ፡ መሥዋዕት፡ የምትወደ
ድ፡ ቢሆንስ፡ መሥዋዕቱን፡ በውዋ
ሁልህ፡ ነበር።

ወጽንሐሐ፡ ኢትሠምር።

ወምን፡ ገዳምን፡ ኀቤየ፡ ሀሉ፡ ትላለህ፡
እንጂ፡ መሥ፡ ዓ፡ የምትወድስ፡ ቢ
ሆን፡ ዕጣኑንም፡ ባቀረብሁልህ፡ ነበር።

፲፯፡ መሥዋዕቱሰ፡ ለእግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ የዋህ።

መሥዋዕቱስ፡ የእግዚአብሔር፡ መ
ሥዋዕቱ፡ የዋህ፡ ልቡና። አንድም፡
የየዋህ፡ ሰው፡ ልቡና፡ ነው።

ልበ፡ ትሑተ፡ ወየዋሀ፡ ኢይሜንን፡ እግዚአብሔር።

እግዚአብሔር፡ ትሑት፡ የዋህ፡ ልቡ
ናን፡ አይንቅም፡ አያቃልልም። አን
ድም፡ ልበ፡ ትሑት፡ ይላል፡ የትሑ
ት፡ የየዋህ፡ ልቡናን፡ አይንቅም፡ አ
ያቃልልም።

፲፰፡ አሠንይ፡ እግዚኦ፡ በሥምረትከ፡ ለጽዮን።

የዳዊትን፡ ሰውነት፡ በፈቃድህ፡ አከ
ናውናት።

ወይትሐነጽ፡ አረፋቲሃ፡ ለኢየሩሳሌም።

ሕዋሳቴም፡ በመንግሥት፡ ይከናወኑ።
አንድም፡ (አሠንያ)፡ ትሩፍን፡ በሚ
ጠት፡ ሥጋ፡ አከናውናት፡ (ወይትሐ
ነፅ)፡ ሕዋሳቷ፡ በሚጠት፡ ይከናወኑ።
አንድም፡ አሠንያ፡ ኢየሩሳሌምን፡
በሚጠት፡ አከናውናት፡ (ወይትሐ
ነፅ)፡ አገሪቱ፡ እንድትቀና፡ ቤተ፡



መቅደስ፡ እንድትሠራ፡ ግምቧ፡ ቅጽ
ሯ፡ እንዲታደስ፡ አድርግ።
አንድም፡ (አሠንያ)፡ ምእመናን፡ በ
በሚጠተ፡ ነፍስ፡ አከናውናት። (ወይ
ትሐነፅ)፡ ሕዋሳቷ፡ በሚጠተ፡ ነፍስ፡
በልጅነት፡ ይከናወኑ።
አንድም፡ (አሠንያ)፡ ልጅነትን፡ አከ
ናወናት፡ ማለት፡ እንድትሰጥ፡ አድ
ርጋት። (ወይትሐነፅ)፡ ትሩፋቶቿ፡
ይታደሱ።

፲፱፡ ከመ፡ ትሠምር፡ መሥዋዕተ፡ ጽድቅ።

እውነተኛውን፡ መሥዋዕት፡ በወደ
ድህ፡ ጊዜ።

መባኒ፡ ወቍርባኒ።

የበጎ፡ የበጎ፡ ሰዎች፡ መሥዋዕት፡
ቍርባናቸውን፡ መባቸውን፡ አንድ
ም፡ የወልደ፡ እግዚአብሔር፡ መሥ
ዋዕት፡ ቍርባንነቱን፡ መባዕነቱን፡
በወደድህ፡ ጊዜ።

አሜሃ፡ ያዓርጉ፡ ውስተ፡ ምሥዋዒከ፡ አልሕምተ።

ያዓርጉ፡ ስለ፡ አልሕምተ፡ ነቢያት፡
ካህናት፡ እልሀምትን፡ ይሠዉልሃል፡
አንድም፡ ዓላውያን፡ ሐዋርያትን፡ ይ
ይሠዉልሃል። አንድም፡ ሐዋርያት፡
እንደ፡ ላም፡ ይሠዉልሃል።

ስብሐት፡ ለአብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ለዓለም፡ ወለዓለመ፡ ዓለም።

ለአብ፡ ለወልድ፡ ለመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ለዘ
ላለሙ፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይገባቸዋል፤

አሜን።

## መዝሙር፡ ፶፩።

፩፡ ለምንት፡ እዜኀር፡ ኃያል፡ በእከይ።

ስለሕዝቅያስ፡ ተናግሮታል። ሰናክ
ሬም፡ በክፋቱ፡ ለምን፡ ይመካል።
በጎ፡ ነገር፡ ያስመካል፡ እንጂ፡ ክፋት፡
ያስመካልን።

ወይኤምዕ፡ ኵሎ፡ አሚረ።

ወለምንት፡ ይዔምዕ፡ ዘወትርስ፡ ለ
ምን፡ ይበድላል፡ ሰው፡ አንድ፡ ቀን፡
ሁለት፡ ቀን፡ እንጂ፡ ዕለት፡ ዕለት፡
ይበድላልን። አንድም፡ ዕለት፡ ዕለት፡
ይበድላል፡ ብለህ፡ ከዚሁ፡ እሠር።

፪፡ ኀጢአተ፡ ገብረ፡ ልሳኑ።

ሰናክሬም፡ ልቡናህ፡ ክዳትን፡ ተን
ኰልን፡ አሰበ።

ከመ፡ መላጼ፡ በሊኅ፡ ገበርከ፡ ጕሕሉተ።

ክዳትን፡ ተንኰልን፡ እንደተሳለ፡ ም
ንጭ፡ አድርገህ። የተሣለ፡ ምላጭ፡
ጠጕር፡ ቈረጥ፡ ቢሉት፡ አልፎ፡ ቈ

ርበት ፡ ይቀዳል ። እሱም ፡ እስራኤል
ን ፡ አጥፉ ፡ ቢሉት ፡ እስራኤልን ፡ አ
ጠፋለሁ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ጣዖት ፡
እላለሁ ፡ ብኋልና ።
አንድም ፡ ከመ ፡ በዓለ ፡ መላጺ ፡ ይላ
ል ። ኀጢአትን ፡ እንደበለ ፡ ምላጭ ፡
አደረግህ ፡ በሀገራቸው ፡ ራስ ፡ የሚላ
ጭ ፡ በለወግ ፡ አለ ፡ እገሌን ፡ ጠላቴን ፡
መርገዝ ፡ ቀብተህ ፡ ግደልልኝ ፡ ብዙ ፡
ገንዘብ ፡ እሰጥሀለሁ ፡ ይለዋል ። መ
ርገዝ ፡ ቀብቶ ፡ ገድሎ ፡ ከዚያም ፡ ከዚ
ህም ፡ ዋጋውን ፡ ይቀበላል ። እሱም ፡
እስራኤልን ፡ አጠፋለሁ ፡ እግዚአብ
ሔርንም ፡ ጣዖት ፡ እላለሁ ፡ ብኋልና ።
፫ ፡ አብደርከ ፡ እኪተ ፡ እምሠናይት ።
በጎ ፡ ሥራ ፡ ከምትሠራ ፡ ይልቅ ፡ ክ
ፋትን ፡ ወደድህ ።
ወትኒምዕ ፡ እምትንብብ ፡ ጽድቀ ።
እውቀትን ፡ ከትናገር ፡ ይልቅ ፡ ትበ
ድላለህ ፡ ማለት ፡ ሐሰትን ፡ ትወዳለህ ፡
ወደድህ ።
፬ ፡ አፍቀርከ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ ልሳን ፡ መሥጥመ ።
ለነገር ፡ ቢቀጽሉ ፡ መሥጥመ ። ለልሳ
ን ፡ ቢቀጽሉ ፡ መሥጥም ፡ ይኋል ። ሥ
ጥም ፡ አድርጎ ፡ ውጦ ፡ የሚያስቀርህ
ን ፡ ያንደበት ፡ ነገር ። አንድም ፡ የሚ
ጎዳ ፡ ነገርን ፡ ወደድህ ።
፭ ፡ በእንተዝ ፡ ይነሥተከ ፡ እግዚአብሔር ፡ለግሉፋ ።
በሕንፃ ፡ መስሎ ፡ ይናገራል ። ስለዚህ ፡
ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘላለሙ ፡ ያፈ
ርስሃል ። ማለት ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋሃል ።

ይመልሐከ ፡ ወያፈልስከ ፡ እምቤትከ ።
በተክል ፡ መስሎ ፡ ይናገራል ። ከነነዌ ፡
ያስነሣሃል ፡ በለኪሶን ፡ ያጠፋሃል ። እ
ልስሃል ። ወያፈልስከ ፡ ባገርህ ፡ በነነዌ ፡
ያጠፋሃል ።
ወሥርወከኒ ፡ እምድረ ፡ ሕያዋን ።
ሥረወ ፡ ትውልድህን ፡ ሥረወ ፡ መ
ንግሥትህንም ፡ ከአብርሃም ፡ ከይስ
ሐቅ ፡ ከያዕቆብ ፡ አገር ፡ ከኢየሩሳሌ
ም ፡ ያጠፋል ። ምን ፡ ሥረወ ፡ ትው
ልድ ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ አለውና ፡
እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ እስራኤልን ፡ አጥ
ፍቼ ፡ የኔን ፡ ወገኖች ፡ ሠርቼ ፡ መንግ
ሥትን ፡ እጅ ፡ አድርጌ ፡ እኖራለሁ ፡
ብሎ ፡ ስለመጣ ። ኢሳ ፡ ፳፭ ፡ ፲፭ ።
፮ ፡ ይርአዩ ፡ ጻድቃን ፡ ወይፍርሁ ።
ነቢያት ፡ ካህናት ። አንድም ፡ ሁለቱ ፡
ነገድ ፡ የሰናክሬምን ፡ ጥፋት ፡ አይተ
ው ፡ ይፍሩ ። ይፈሩ ፡ ዘንድ ፡ ይዩ ። የ
አንክሮ ፡ ነው ።
ይስሐቁ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወይበሉ ።
እንዲህ ፡ እያሉ ፡ ይዘብቱበት ።
፯ ፡ ነዋ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢረሰዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ረዳኢሁ ።
እግዚአብሔርን ፡ ረዳቱ ፡ ያላደረገ ፡
ሰናክሬም ፡ እነሆ ፡ ጠፋ ፡ እያሉ ።
ወተአመነ ፡ በብዝኃ ፡ ብዕሉ ።
በገንዘቡ ፡ ብዛት ፡ የታመነ ።
ወተኀየለ ፡ በከንቱ ።
በጣዖቱ ፡ አንድም ፡ በጕልበቱ ፡ የታ



መነ ፡ ሰናክሬም ፡ እነሆ ፡ ጠፋ ፡ እያ
ሉ ። የዘበቱበት ፡ ረፋስቂስ ፡ አምጽ
ኦ ፡ ብእሴ ፡ ዘይክል ፡ ተፅዒኖቶሙ ፡
ለአፍራሲነ ፡ ይላቸዋል ፡ ዘመዶቹንስ ፡
እንዲህ ፡ አይላቸውም ፡ እንዲያውቁ ፡
ያውቃል ፡ ብሎ ፡ እስኪ ፡ ከጌታዬ ፡
አንድ ፡ ደጃዝማች ፡ ሰደንላችሁ ፡ እና
ንተ ፡ አንድ ፡ ሁናችሁ ፡ መመለስ ፡
ይቻላችሁ ፡ እንደሆነ ፡ እያለ ፡ ሲመካ
በቸው ፡ ፈጥኖ ፡ ጠፍቷልና ።
፪ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፫-፳፱ ።
፰ ፡ አንሰ ፡ ከመ ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡ ሥሙር ፡ ው
ስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ።
ዕፀ ፡ ዘይት ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡
ያማረ ፡ የተወደደ ፡ እንደሆነ ፡ እኔም ፡
ያማርሁ ፡ የተደድሁ ፡ ነኝ ። አንድም ፡
አንሰ ፡ ከመ ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡ ዘውስተ ፡
ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቤተ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እንዳለ ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡ ያማ
ርሁ ፡ የተወደድሁ ፡ ነኝ ። ያ ፡ ብዙ ፡
ፍሬ ፡ እንዲያፈራ ፡ ብዙ ፡ ጸጋ ፡ ከብ
ር ፡ አገኛለሁ ። አንድም ፡ ቀን ፡ ከአፅ
ዋፍ ፡ ሌሊት ፡ ከአራዊት ፡ ባጥር ፡ በ
ቅጥር ፡ ተጠብቆ ፡ እንዲኖር ፡ እኔም ፡
በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠብቄ ፡
እኖራለሁ ።
ወተወከልኩ ፡ በምሕረቱ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ይደረግልኛል ፡ ብዬ ፡ በእግዚአብሔ
ር ፡ ቸርነት ፡ አመንሁ ።
ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።
ለዘላለሙ ።
፱ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ ለዓለም ፡ እስመ ፡ ገበርከ ፡ ሊተ ።
ሥራ ፡ ሠርተህልኛልና ፡ ለዘላለሙ ፡
እገዛልሃለሁ ።
እሴፎ ፡ ለምሕረትከ ፡ እስመ ፡ ሠናይቲከ ፡ ኀበ ፡
ጻድቃኒከ ።
ይቅርታህ ፡ ቸርነትህ ፡ ለወዳጆችህ ፡
ይደረግላቸዋልና ፡ ለኔም ፡ ይደረግል
ኛል ፡ ብዬ ፡ ይቅርታህን ፡ ተስፋ ፡ አደ
ርጋለሁ ።

## መዝሙር ፡ ፶፪ ።

፩ ፡ ይብል ፡ ዓብድ ፡ በልቡ ፡ አልቦ ፡ እግዚአብ
ሔር ። መዝ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ።
ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ ምነው ፡
ይህንማ ፡ ተናግሮት ፡ አልነበረምን ፡
ቢሉ ፡ በውስጡ ፡ የሚለውጠው ፡ ዘር ፡
አለና ። አንድም ፡ ፊት ፡ በቃል ፡ የላ
ከበትን ፡ በኋላ ፡ ጽፎ ፡ ሰዶለታል ። ከ
ወደ ፡ ኋላው ፡ ተራቅታ ፡ ንጉሡ ፡ ኢት
ዮጵያን ፡ አስነሥተውበታል ። ሲሔድ ፡
እስራኤልን ፡ ኢያስሕትከሙ ፡ ሕዝቅ
ያስ ፡ እስራኤል ፡ ሕዝቅያስ ፡ የሚያጸ
ናችሁ ፡ አይምሰላችሁ ። እኔ ፡ ወደ ፡
ሀገሬ ፡ ልውሰዳችሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡
አይደለም ፡ ተራቅታ ፡ ንጉሡ ፡ ኢት
ዮጵያን ፡ ድል ፡ አድርጌ ፡ ስመለስ ፡ ነው ፡
ብሎ ፡ ሰነፍ ፡ ዕርቅ ፡ ታርቆ ፡ ሔዷል ።

2014 04 17

ሬፍስቴስ ፡ እታይ ፡ እታይ ፡ ሲል ፡ ከ
ዚያው ፡ ወድቆ ፡ ቀርቷል ። ሰናክሬም ፡
ተራቅታን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ሲመለስ ፡
ዳግመኛ ፡ ይህን ፡ ጽር ፡ ሰዶለታል ።
ወተመጠዋ ፡ እምእደ ፡ ሐዋርያት ፡ በ
ውስተ ፡ ዓረፍት ፡ በመስኮት ፡ ከመሳ
ከተኛቹ ፡ እጅ ፡ ተቀብሎ ፡ ዛሬ ፡ ቂስ ፡
ወንጌል ፡ ብሎ ፡ ሲወጣ ፡ ገበታውን ፡
ወደሱ ፡ ቀለሙን ፡ ወደ ፡ ታቦቱ ፡ አድ
ርጎ ፡ እንዲወጣ ፡ ቀለሙን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡
ወረቀቱን ፡ ወደሱ ፡ አድርጎ ፡ ርኢ ፡
እግዚአ ፡ ትዕይርቶ ፡ ለሰናክሬም ፡ ብሎ ፡
ቢጸልይ ፡ ተፍቆለታል ። ዘነ ፡ ፲፰ ፡ ፲፫ ፡
፴፮ ። ፲፱ ፡ ፩—፴፯ ። ኢሳ ፡ ፴፮ ፡ ፩-፴፰ ። ፴፯ ፡
፩—፴፰ ። ሰንፍ ፡ ሰናክሬም ፡ በልቡ ፡ አ
ስቦ ፡ በቃሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ የለም ፡
ይላል ።

ጎምሩ ፡ ወረኵሱ ፡ በጌጋዮሙ ።

ጎሙራን ፡ ወርኩሳን ፡ የሚያሰኛቸው
ን ፡ ሥራ ፡ ሠሩ ።

አልቦ ፡ ዘይገብር ፡ ሠናይተ ።

ከነሰናክሬም ፡ ወገን ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ የ
ሚሠራት ፡ የለም ።

፪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሐወጸ ፡ እምሰማይ ፡ ላዕለ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ።

እግዚአብሔር ፡ በልዕልና ፡ ሁኖ ፡ ወደ ፡
ሰናክሬም ፡ ሰፈር ፡ አየ ፡ ተመለከተ ።

ከመ ፡ ይርአይ ፡ እመቦ ፡ ጠቢብ ፡ ዘየኃሥሥ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ምናልባት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚ
ሻው ፡ አዋቂ ፡ እንዳለ ፡ ያይ ፡ ዘንድ ።

፫ ፡ ኵሉ ፡ ዐርየ ፡ ወተዐረ ፡ ዐበሰ ።

እንዲህ ፡ ቢያይ ፡ ቢመለከት ፡ ሁሉ ፡
እንደ ፡ ፈረስ ፡ ጆሮ ፡ እንደ ፡ ሰላጢን ፡
ጉረሮ ፡ አንድ ፡ ሁኖ ፡ በደለ ፡ ወነጀለ ።

አልቦ ፡ ዘይገብር ፡ ሠናይተ ፡ አልቦ ፡ ወኢ፩ ።

ከነሰናክሬም ፡ ወገን ፡ ብዙዉስ ፡ ይቅ
ርና ፡ አንድስንኳ ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ የሚ
ሠራት ፡ የለም ።

ወኢየአምሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።

እኒህ ፡ ዐመፀኞች ፡ በኑ ፡ ግልጥ ፡ ግለ
ትእንዲጎዱ ፡ አያውቁም ። ፲፰ ፡ ፳፫ ፡ ፳፪ ።

፬ ፡ እለ ፡ ይውሕጥዎ ፡ ለሕዝብየ ፡ ከመ ፡ ብልዐተ ፡ እክል ።

ሁሉቱን ፡ ነገድ ፡ እንደ ፡ ጥሁሉ ፡ ጥጥ
ናቸው ፡ እንደ ፡ ዕንቅት ፡ ጠማናቸው ፡
የሚሉ ።

ወለእግዚአብሔርሰ ፡ ኢጸውዕዎ ።

ምነው ፡ እግዚአብሔር ፡ አለብን ፡ አ
ይሉምን ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እግዚ
አብሔርንስ ፡ አያይብንም ፡ አይሰማብ
ንም ፡ አሉት ።

፭ ፡ ወበህየ ፡ ፈርሁ ፡ ወገረሞሙ ፡ ዘኢኮነ ፡ ግሩመ ።

በነገር ፡ በቦታ ፡ በልቡና ፡ ፈሩ ። ግሩ
ም ፡ ሆኖ ፡ የማያውቅ ፡ እግዚአብሔር ፡
ግሩም ፡ ሆነባቸው ።

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘረወ ፡ አዕፅምቲሆሙ ፡ ለመደልዋን ።

እግዚአብሔር ፡ የግብዞች ፡ የነሰናክ
ሬምን ፡ ወገኖች ፡ አጥፍቷልና ። እን



ድም ፡ በቁሙ ፡ ዐፅማቸውን ፡ በትኗ
ልና ፡ ዕለቱን ፡ የሰብዓ ፡ የሰማንያ ፡ ዘ
መን ፡ ዐፅም ፡ አድርጎ ፡ ጠፍቶስ ፡ በት
ኗቸው ፡ ገንዘባቸውን ፡ ዘርፈውታ
ልና ።

ወተኀፍሩ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አኅሰሮሙ ።

እግዚአብሔር ፡ ይጥፉ ፡ ብሏቸዋልና ፡
ጠፉ ።

፮ ፡ መኑ ፡ ይሁብ ፡ መድኃኒተ ፡ እምጽዮን ፡ ለእስራኤል ።

በኢየሩሳሌም ፡ ካሉ ፡ እስራኤል ፡ ለእ
ስራኤል ፡ ድኅነትን ፡ ማን ፡ ይሰጣል ።

አመ ፡ ሚጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፄዋ ፡ ሕዝቡ ።

እግዚአብሔር ፡ የሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ም
ርኮ ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ግን ።

ይትፌሣሕ ፡ ያዕቆብ ፡ ወይትሐሠይ ፡ እስራኤል ።

ንጉሡ ፡ ሰራዊቱ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይለ
ዋል ። መዝ ፡ ፲፫ ፡ ፲፮ ።

## መዝሙር ፡ ፶፫ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ በስምከ ፡ አድኅነኒ ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ። የዳ
ዊት ፡ የትሩፋን ፡ የመቃብያን ፡ የምዕ
መናንም ፡ አለበት ፡ አቤቱ ፡ በስምህ ፡
በማመኔ ፡ አድነኝ ።

ወበኀይልከ ፡ ፍታሕ ፡ ሊተ ።

በኀይልህም ፡ ፍረድልኝ ። ኀይለኛ ፡
የፈረደው ፡ ፍርድ ፡ አይገሠሥምና ።
አንድም ፡ በዕውነተኛነትህ ፡ ፍረድ
ልኝ ።

፪ ፡ እግዚኦ ፡ ስምዐኒ ፡ ጸሎትየ ።

አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወአፅምዕ ፡ ቃለ ፡ አፉየ ።

የልመናዬን ፡ ነገር ፡ ስማኝ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ነኪራን ፡ ቆሙ ፡ ላዕሌየ ።

እነ ፡ ሰናክሬም ። አንድም ፡ እነ ፡ ሳአ
ል ። አንድም ፡ ባቢሎናውያን ። አን
ድም ፡ ጽርዓውያን ። አንድም ፡ አጋን
ንት ፡ በጠላትነት ፡ ተነሥተውብኛልና ፡

ወኃያላን ፡ ገሠሥዋ ፡ ለነፍስየ ።

ኃያላን ፡ የሚሆኑ ፡ እኒህ ፡ ሰውነቴን ፡
ለጥፋት ፡ ሽተዋታልና ።

ወኢረሰይዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅድሜሆሙ ።

ምነው ፡ እግዚአብሔርሳ ፡ ወዴት ፡
ሔዶ ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብ
ሔርንስ ፡ ከፊታቸው ፡ አላደረጉትም ፡
ማለት ፡ ያይብናል ፡ ይሰማብናል ፡ ይ
ፈርድብናል ፡ አላሉትም ።

፬ ፡ ናሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረድአኒ ።
ወእግዚእየ ፡ ያድኅና ፡ ለነፍስየ ።

ናሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ እግዚእየ ፡ ይ
ረድእኒ ፡ ወያድኅና ፡ ለነፍስየ ፡ ብለህ ፡
ግጠም ። እነሆ ፡ ጌታዬ ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ ሰውነቴን ፡ ረድቶ ፡ ያድናታልና ።

፭ ፡ ወይመይጦ ፡ ለዕኪት ፡ ላዕለ ፡ ጸላእትየ ።

መከራን ፡ ወደ ፡ ጠላቶቼ ፡ ይመልሳ



2014 04 17

ታል ፡ ሑር ፡ ዲቤሆሙ ፡ ለመንዚሬን ፡ እንዲል ።

ወበጽድቅከ ፡ ሠርዎሙ ።

በቸርነትህ ፡ አጥፋቸው ፡ በጽድቅከ ፡ አለ ፡ የለዚያ ፡ ጥፋት ፡ ለነዚህ ፡ ድኅነት ፡ ሁኗልና ።

፲ ፡ ዘእምፈቀድኩ ፡ እሡውዕ ፡ ለከ ።

የምወደውን ፡ ከሥር ፡ አንድ ፡ ሰጥቼ ፡ ደስ ፡ እሰኝዋለሁ ። ይህስ ፡ የግድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከዘጠኝ ፡ አንድ ፡ ሰጥቼ ፡ ደስ ፡ እሰኝሃለሁ ።

እገኒ ፡ ለስምከ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ሠናይ ።

አቤቱ ፡ ለስምህ ፡ እገዛለሁ ። ስምህን ፡ አመሰግናለሁ ፡ ለስምህ ፡ መገዛት ፡ ስምህን ፡ ማመስገን ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነውና ።

እስመ ፡ እምኵሉ ፡ ምንዳቤየ ፡ አድኀንከኒ ።

ከመከራዬ ፡ ሁሉ ፡ አድነኸኛልና ።

ወርእየት ፡ ዓይንየ ፡ በጸላእትየ ። መዝ ፡ ፶፩ ፡ ፲፩ ።

ዓይኔ ፡ ጠላቶቼ ፡ ጠፍተው ፡ አየች ። አንድም ፡ ዘከነ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በጠላቶቼ ፡ የተደረገውን ፡ አየች ።

## መዝሙር ፡ ፶፬ ።

፩ ፡ አፅምዓኒ ፡ እግዚኦ ፡ ጸሎትየ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ፡ የራሱም ፡ የሕዝቅያስም ፡ ነገር ፡ አለበት ። አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወኢትትሐየየኒ ፡ ስእለትየ ።

ልመናዬን ፡ ቸል ፡ አትበል ፡ አንድም ፡ ቸል ፡ አትበልብኝ ።

፪ ፡ ነጽረኒ ፡ ወስምዓኒ ።

በዓይነ ፡ ምሕረትህ ፡ ዓይተህ ፡ ተመልከተህ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ተከዝኩ ፡ ደንገጽኩ ፡ ወተዛዋዕኩ ።

እንጥያኮስ ፡ መጣ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ አዘንሁ ። ለስእለ ፡ ፀሐይ ፡ ስገድ ፡ መሥዋዕተ ፡ እሪያ ፡ ብላ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ደነገጥሁ ። መከራው ፡ ከለፈልኝ ፡ በኋላ ፡ ተጫወትሁት ።

እምቃለ ፡ ጸላኢ ፡ ወእምሥቃየ ፡ ኃጥእ ።

ከንጥያኮስ ፡ እነጋገር ። ለስእለ ፡ ፀሐይ ፡ ስገድ ፡ መሥዋዕተ ፡ እሪያ ፡ ብላ ፡ ብሎ ፡ ከሚያመጣብኝም ፡ መከራ ፡ የተነሣ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ሚጥዋ ፡ ለዓመፃ ፡ ላዕሌየ ። መዝ ፡ ፰ ፡ ፲፩ ።

የሳቸውን ፡ ዓመፅ ፡ ወደኔ ፡ መልሰዋታልና ፡ ለስእለ ፡ ፀሐይ ፡ ስገዱ ፡ መሥዋዕተ ፡ እሪያ ፡ ብሉ ፡ ማለት ፡ ጥንቱን ፡ መቃብያን ፡ ጣዖት ፡ ያመልኩ ፡ መሥዋዕተ ፡ እሪያ ፡ ይበላሉ ፡ ማለት ፡ ነውና ።

አንድም ፡ (ተከዝኩ) ፡ ሳአል ፡ መጣ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ አዘንሁ ፡ (ደንገፅኩ) ፡ ሐቅለ ፡ መዓን ፡ ሰፍሮ ፡ ባየሁት ፡ ጊዜ ፡ ደነገፅሁ ፡ (ወተዛዋዕኩ) ፡ መከራው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ተጫወትሁት ፡ (እምቃለ ፡ ጸላኢ) ፡ ከሳኦል ፡ እነጋገር ፡ (ወእምሥቃየ ፡ ኃጥእ) ፡ አይቴ ፡ ሖረ ፡ ገዝኩ ፡ ወልደ ፡ እሴይ ፡ ብሎ ፡ ከሚያመጣብኝ ፡ መከራ ፡ የተነሣ ። (እስመ ፡ ሚጥዋ) ፡ የሳቸውን ፡ ዐመፅ ፡ ወደኔ ፡ መልሰዋታልና ። ዳዊት ፡ ቢያገኘኝ ፡ አይተወኝም ፡ ነበር ፡ ይገድለኝ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ጥንቱን ፡ እነዳዊት ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዮች ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነውና ።

አንድም ፡ (ተከዝኩ) ፡ ሰናክሬም ፡ መጣ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ አዘንሁ ። (ደንገፅኩ) ፡ ለኪሶን ፡ ሰፍሮ ፡ ባየሁት ፡ ጊዜ ፡ ደነገጥሁ ። (ወተዛዋዕኩ) ፡ መከራው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ተጫወትሁት ፡ (እምቃለ ፡ ጸላኢ) ፡ ከሰናክሬም ፡ እነጋገር ። (ወእምሥቃየ ፡ ኃጥእ) ፡ በመኑ ፡ ተወኪለከ ፡ ዓለውከኒ ፡ ብሎ ፡ ከሚያመጣብኝ ፡ መከራ ፡ የተነሣ ። (እስመ ፡ ሚጥዋ) ፡ የሳቸውን ፡ ዓመፅ ፡ ወደኔ ፡ መልሰዋታልና ፡ በኑ ፡ ግልፎ ፡ ዘያድኅን ፡ ማለት ፡ ጥንቱን ፡ እነ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ጣዖት ፡ ያመልካሉ ፡ ማለት ፡ ነውና ።

ወቀሠፉ ፡ ላዕሌየ ፡ ያመንስዉኒ ።

ያጠፉኝ ፡ ዘንድ ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡብኝ ።

፬ ፡ ወደንገፀኒ ፡ ልብየ ፡ በላዕሌየ ።

በኔ ፡ ያለ ፡ ልቡናዬ ፡ ደነገጠብኝ ፡ ተሸበረብኝ ።

ወመጽአኒ ፡ ድንጋጼ ፡ ሞት ።

የሞት ፡ ድንጋጼ ፡ መጣብኝ ፡ ማለት ፡ ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ መከራ ፡ አገኘኝ ።

፭ ፡ ፍርሃት ፡ ወረዓድ ፡ አኃዘኒ ፡ ወደፈነኒ ፡ ጽልመት ። ኢዮ ፡ ፫ ፡ ፳፭ ።

ፍርሃት ፡ ረዓድ ፡ አደረብኝ ። ፍርሃት ፡ የልቡና ፡ ረዓድ ፡ የጕልበት ፡ ድንጋፄ ፡ የናላ ፡ ነው ። ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ መከራም ፡ አገኘኝ ።

፯ ፡ ወእቤ ፡ መኑ ፡ ይሁበኒ ፡ ክንፈ ፡ ከመ ፡ ርግብ ።

እንደ ፡ ርግብ ፡ ክንፍን ፡ ማን ፡ በሰጠኝ ፡ አልሁ ።

እስርር ፡ ወእዕርፍ ።

ብር ፡ ብዬ ፡ ከመከራው ፡ አርፍ ፡ ዘንድ ፡ አንድም ፡ እስርር ፡ ከመ ፡ ርግብ ፡ ክንፈ ፡ ከመ ፡ ርግብ ፡ ብለህ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ብር ፡ ብዬ ፡ ከመከራው ፡ አርፍ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ክንፍን ፡ ማን ፡ በሰጠኝ ፡ አልሁ ።

፰ ፡ ናሁ ፡ አርኀቁ ፡ ተኀጥእ ፡ ወቤትኩ ፡ ውስተ ፡ በድው ።

እነሆ ፡ መታጣትን ፡ አራቅሁ ። በበረሀም ፡ አደርሁ ፡ ማለት ፡ ከዘመድ ፡ ተለይቼ ፡ ከሀገር ፡ ወጥቼ ፡ በረሀ ፡ ለበረሀ ፡ እንከራተታለሁ ። ከዚህ ፡ ካለሁበት ፡ እየወጡ ፡ አላኖር ፡ ካሉኝ ፡ ብር ፡ ብዬ ፡ ከመከራው ፡ አርፍ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ክንፍ ፡ ማን ፡ በሰጠኝ ፡ አልሁ ። መዝ ፡ ፻፵፰ ፡ ፱ ።

፱ ፡ እሴፈዎ ፡ ለዘያድኅነኒ ።
እምዕንባዜ ፡ ነፍስየ ፡ ከመ ፡ ዓውሎ ።

ለዘያድኅነኒ ፡ ከመ ፡ ዓውሎ ፡ እምዕንባዜ ፡ ነፍስየ ፡ ከመ ፡ ዓውሎ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ሰውነቴን ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡

ከሚቅበዘበዝ ፡ መከራ ፡ ፈጥኖ ፡ የሚ
ያድናት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተስፋ ፡
አደርገዋለኍ ። ኢሮ ፡ ፩፡፳፰ ።

፱ ፡ እሥጥሞሙ ፡ እግዚኦ ፡ ወምትር ፡ ልሳና
ቲሆሙ ።

እሥ ጥሞሙ ፡ ከመ ፡ ዓውሎ ፡ እንደ ፡
አዝዋሪ ፡ ባሕር ፡ አሥጥማቸው ፡ ነገ
ራቸውን ፡ አንድም ፡ ሰውነታቸውን ፡
አጥፋ ።

እስመ ፡ ርኢኩ ፡ ዓመፃ ፡ ወቅስተ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ።

በነአንጥያኮስ ፡ በነሰናክሬም ፡ በሀገራ
ቸው ፡ በነሳኦል ፡ በልቡናቸው ፡ ፀብ ፡
ክርክር ፡ ዓመፅን ፡ አንድም ፡ ክህደት ፡
ኑፋቄን ፡ አይቻለሁና ።

፲ ፡ እስመ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ዕጉት ፡ ውስተ ፡
አረፋቲሃ ።

በለአንጥያኮስ ፡ በለሰናክሬም ፡ በግን
ባቸው ፡ በቅጽራቸው ፡ በለ ፡ ሳኦል ፡
በሰውነታቸው ፡ በመዓልትም ፡ በሌ
ሊትም ፡ ክዳት ፡ ተንኰል ፡ ተመል
ቷልና ።

፲፩ ፡ ዓመፃ ፡ ወሥራኅ ፡ ወኃጢአት ፡ ማዕከላ ።

ዓመፃ ፡ እንሠረው ፡ ሥራኅ ፡ እንግደ
ለው ፡ ማለት ፡ ኃጢአት ፡ በቈሙ ፡
በነአንጥያኮስ ፡ በነሰናክሬም ፡ በደባ
ባያቸው ፡ በነሳኦል ፡ በልቡናቸው ፡
አለና ፡፡ አንድም ፡ ዓመፃ ፡ እንሰረው ፡
እንግደለው ፡ ማለት ፡ ሥራህ ፡ ጣዖት ፡
ማምለክ ፡ ብዙ ፡ ድካም ፡ ያለበት ፡
ነውና ፡ ኃጢአት ፡ በቈሙ ፡ በነአንጥ
ያኮስ ፡ በነሰናክሬም ፡ በልቡናቸው ፡
አለና ። ኤር ፡ ፮ ፡ ፯-፯ ። ናሆ ፡ ፫ ፡ ፩ ።

ወኢየርኅቅ ፡ እምርኅባ ፡ ጉሕሉት ።

ከነአንጥያኮስ ፡ ከነሰናክሬም ፡ ከደባ
ባያቸው ፡ ከነሳኦል ፡ ከልቡናቸው ፡
ክዳት ፡ ሽንገላ ፡ አይርቅም ፡ ኢሳ ፡ ፶፱ ።
፶፱ ፡ ፸፱ ፡ ፱ ።

፲፪ ፡ ሶበሰ ፡ ጸላዒ ፡ ፀዓለኒ ፡ እምተፀገሥኩ ።

ሌላስ ፡ ጠላት ፡ ሰድቦኝ ፡ ቢሆን ፡ በታ
ገሥሁት ፡ ነበር ።

ወሶበኒ ፡ ጸላዒ ፡ እዐበየ ፡ አፉሁ ፡ ላዕሌየ ፡ እም
ተኀባዕክዎ ።

ሌላም ፡ ጠላት ፡ ነገር ፡ አብዝቶብኝ ፡
ቢሆን ፡ ተሰውሬ ፡ ባሳለፍሁት ።

፲፫ ፡ ወአንተሰ ፡ ብእሲ ፡ ዘከመ ፡ ነፍስየ ።

አንተማ ፡ እንደ ፡ ሰውነቴ ፡ የምወድ
ድህ ፡ ሰው ፡ አይደለህምን ።

ማእምርየ ፡ ወአውትየ ።

ጸላህምን ፡ አያት ፡ ቅድምአያቴን ፡
የምታውቅ ፡ ወዳጄ ፡ እጥላቶቼ ፡ እጅ ።

፲፬ ፡ ዘኀቡረ ፡ አስተተጣዓምከ ፡ ሲተ ፡ መባልዕተ ።

አስተጥዓምከነ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ሦስቱ ፡
ክህናት ፡ ተረፈ ፡ መሥዋዕቱን ፡ ባን
ድነት ፡ እንመገብ ፡ የነበረ ። ሳኦል ፡
እስመ ፡ ሣልሳይ ፡ ብእሲሁ ፡ ይለዋል ፡
በቀኝ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ከላይ ፡ ሳኦል ፡
ቀጥሎ ፡ ዮናታን ፡ ቀጥሎ ፡ ዳዊት ፡
በግራ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ከላይ ፡ ሳኦል ፡
ቀጥሎ ፡ አበኔር ፡ ቀጥሎ ፡ ዳዊት ፡ ተቀ
ምጠው ፡ ይመገቡ ፡ ነበርና ፡ ረፋስ
ቂስ ፡ ርስቱን ፡ ጉልቱን ፡ ያጠረውን ፡
በድግር ፡ የረዘመውን ፡ በጠፍር ፡ የም
ንከፈል ፡ አልነበረንምን ።



ወንሐውር ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በ፩ ፡ ልብ ።

እንደ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ መከሬ ፡ እንደ ፡
አንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ሁነን ፡ ወደ ፡
ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንሔድ ፡ የነ
በርነ ፡ አይደለምን ።

፲፭ ፡ ይምጽኦሙ ፡ ሞት ፡ ወይረዱ ፡ ውስተ ፡
ሲኦል ፡ ሕያዋኒሆሙ ።

አሁን ፡ እኔ ፡ ምን ፡ እላለኍ ፡ ሞት ፡
ይምጣባቸው ፡ ገድሎ ፡ ገድሎ ፡ ወደ
ሚጥልበት ፡ ወደመቃብር ፡ አለን ፡
አለን ፡ ሲሉ ፡ ይውረዱ ፡ አንድም ፡
እንደ ፡ ዳታንና ፡ እንደ ፡ አቤሮን ፡ ነፍ
ሳቸው ፡ ከሥጋቸው ፡ ሳትለይ ፡ ወደ
መቃብር ፡ ይውረዱ ። ዘኍ ፡ ፲፮ ፡ ፴-፴፱ ።

እስመ ፡ ዕኩይ ፡ ማዕከሎሙ ፡ ውስተ ፡ አብያቲ
ሆሙ ።

በለአንጥያኮስ ፡ በለሰናክሬም ፡ በደባ
ብያቸው ፡ በለሳኦል ፡ በልቡናቸው ፡
አንድም ፡ በቈሙ ፡ በቤታቸው ፡ ክፉ ፡
ነገር ፡ አለና ።

፲፮ ፡ አንሰ ፡ ጸራኅኩ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እም
ላኪየ ፡ ወሰምዓኒ ።

እኔስ ፡ ወደ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ወደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ መልሼ ፡ ለመንኍ ፡ እሱም ፡
ልመናዬን ፡ ሰማኝ ። ዮና ፡ ፪ ፡ ፪ ።

፲፯ ፡ ሠርከ ፡ ወነግሀ ፡ ወመዓልተ ፡ እነግር ።

በጧት ፡ በማታ ፡ በቀትር ፡ በመዓልት ፡
በሌሊት ፡ እነግራለሁ ፡ አስተምራ
ለሁ ።

እየድዕ ፡ ወኢሰምዑኒ ፡ ቃልየ ።

ብመከራችሁ ፡ ምክሬን ፡ ትምርቴን ፡
አልሰሙኝም ።

፲፰ ፡ አድኅና ፡ በሰላም ፡ ለነፍስየ ፡ እምእለ ፡
ይትቃረቡኒ ።

አድኅና ፡ በሰላም ፡ እምእለ ፡ ይትቃ
ረቡኒ ፡ በሰላም ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ እም
እለ ፡ ይትቃረቡኒ ፡ በሰላም ፡ ማለት ፡
ወዳጅ ፡ መስለው ፡ ከሚቀርቡኝ ፡ ከጠ
ላቶቼ ፡ ሰውነቴን ፡ አድናት ፡ አንድም ፡
በሰላም ፡ ለያት ፡ አንጥያኮስ ፡ ለቤተ ፡
መቅደስ ፡ እነጽፋለኍ ፡ እጋርዳለሁ ፡
ማለቱን ፡ ሳኦል ፡ ሊገድለው ፡ ሲሻው ፡
ዳዊት ፡ ወልድየ ፡ ቃልከ ፡ ማኅዘኒ ፡
ማለቱን ። ሰናክሬም ፡ እወስደክሙ ፡
ውስተ ፡ ሀገርየ ፡ ብሔርየኒ ፡ ብሔረ ፡
ሥርናይ ፡ ወወይንን ፡ ከመ ፡ ብሔር
ክሙ ፡ ማለቱን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ አን
ድም ፡ እምእለ ፡ ይትቃረኑኒ ፡ ይላል ፡
ከሚጠሉኝ ፡ አድናት ።

እስመ ፡ ይበዝኍ ፡ እምእለ ፡ ምስሌየ ።

ከኔ ፡ ጋራ ፡ ካሉ ፡ ከወገኖቼ ፡ ይልቅ ፡
እነሱ ፡ ይበዛሉና ፡ መቃብያን ፡ ቍጥ
ራቸው ፡ ታውቋል ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡
ዓሥራ ፡ ሁለት ፡ እልፍ ፡ ዕርዓውያን ፡
ሐያ ፡ አራት ፡ እልፍ ፡ ናቸው ፡ አልታ
ወቀም ፡ ቢሉ ፡ አጽፈዋቸዋልና ፡ ዳ
ዊት ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ራሱን ፡ ሁኖ ፡
ሲሸሽ ፡ ሳኦል ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ደረቅ ፡
ጦር ፡ ሆኖ ፡ ተከትሎታልና ። ሰናክ
ሬም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ሠላሳ ፡ አራት ፡ ነገ
ሥታት ፡ ካሥራ ፡ ስምንት ፡ እልፍ ፡
ካራት ፡ ሺሕ ፡ መኳንንት ፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡
ይዞ ፡ የምያረበርበው ፡ ግን ፡ ሥፍር ፡
ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ሁኖ ፡ መጥቷልና ።

2014 04 17

፲፱ ፡ ይሰማዕ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወያኅሥርሙ ። ዘሀሎ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ።

እግዚአብሔር ፡ ዘሀሎ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ፡ ይሰማዕ ፡ ወያኅሥርሙ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ዓለም ፡ ሳይ ፈጠር ፡ የነበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እን ዲህ ፡ ማለታቸውን ፡ ሰምቶ ፡ ያጥፋ ቸው ።

እስመ ፡ አልቦሙ ፡ ቤዛ ።

ቤዛ ፡ የሚሆናቸው ፡ የላቸውምና ። እንድም ፡ ዘጠኙን ፡ ሕገጋት ፡ አልጠ በቁምና ።

ወኢፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርንም ፡ አልፈሩትም ፡ አላመለኩትምና ።

፳ ፡ ወሰፍሐ ፡ እዴሁ ፡ ለፈዲይ ።

እሱም ፡ እንክያስ ፡ ብሎ ፡ እደ ፡ መዓ ቱን ፡ ዘረጋባቸው ።

ወአርኩሱ ፡ ሥርዓቶ ።

ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ሕጉን ፡ አፈረሱ ። ከህ ናት ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ መቅደስ ፡ ያረዙ ስዋ ፡ ለሰንበት ፡ እንዲል ።

ወተናፈቁ ፡ እመዓተ ፡ ገጹ ።

ከመአቱ ፡ መገለጽ ፡ የተነሣ ፡ በሞት ፡ ተለያዩ ።

ወቀርበ ፡ ልቡ ።

ልቡ ፡ ቅርብ ፡ ቅርብ ፡ አለ ። ለሥዕለ ፡ ኪሩብ ፡ እሰግዳለሁ ፡ መሥዋዕት ፡ በ ግእ ፡ እበላለሁ ፡ ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ አ ነጽፋለሁ ፡ እጋርዳለሁ ፡ ባንተም ፡ ተ ጀመረ ፡ እንዳትሉ ፡ አባቴ ፡ እስክንድ ርም ፡ ለሥዕለ ፡ ኪሩብ ፡ ይሰግድ ፡ መ ሥዋዕተ ፡ በግዕ ፡ ይበላ ፡ ለቤተ ፡ መ ቅደስ ፡ ያነጽፍ ፡ ይጋርድ ፡ ነበር ፡ እያለ ።

፳፩ ፡ ወዕሕደ ፡ እምቅብዕ ፡ ነገሩ ።

ነገሩ ፡ ከቅቤ ፡ የለዘበ ፡ ሆነ ። እንድም ፡ (ወቀርበ ፡ ልቡ) ፡ የሳኦል ፡ ልብ ፡ ቅርብ ፡ ቅርብ ፡ አለ ፡ (ወዕሕደ) ፡ ነገሩ ፡ ከቅቤ ፡ ለዘበ ፡ ዳዊት ፡ ወልደየ ፡ ቃልከ ፡ ማኅዘኒ ፡ ልጄ ፡ ዳዊት ፡ እኔና ፡ አንተማ ፡ ምን ፡ ፀብ ፡ አለን ፡ ሰው ፡ ያጣላናል ፡ እንጂ ፡ እያለ ። እንድም ፡ (ወቀርበ) ፡ የሰናክሬም ፡ ልቡ ፡ ቅርብ ፡ ቅርብ ፡ አለ ። (ወጽሕደ) ፡ ነገሩ ፡ ከቅቤ ፡ ለዘበ ፡ ብሔርየኒ ፡ ብ ሔረ ፡ ሥርናይ ፡ ወወይን ፡ ከመ ፡ ብ ሔርክሙ ፡ ይገርችሁስ ፡ ብሔድ ፡ ምን ፡ ትሆናላችሁ ፡ የኔም ፡ ሀገር ፡ እ ንደናተ ፡ ሀገር ፡ የሥንዴ ፡ የወይን ፡ የዘይት ፡ ሀገር ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ነው ።

እሙንቱሰ ፡ ማዕበል ፡ ያስጥሙ ።

ነገሮቹ ፡ ማዕበል ፡ ናቸው ፡ ወያሠጥ ሙ ፡ ያሰጥማሉ ፡ እንድም ፡ ማዕበል ፡ የሚሆኑ ፡ እኒህ ፡ ያሰጥማሉ ፡ የምያ ሠጥሙ ፡ እኒህ ፡ ማዕበል ፡ ናቸው ፡ ያጠፋሉ ።

፳፪ ፡ ገድፍ ፡ ላእለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕሊናከ ፡ ወ ውእቱ ፡ ይሴሰየከ ። ማቴ ፡ ፮ ፡ ፳፭ ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፳፪ ። ፊል ፡ ፬ ፡ ፮ ። ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፯ ። ፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

አንተ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ትተህ ፡ አ ሳብህን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሸክመው



ምን ፡ እበላለሁ ፡ ምን ፡ እጠጣለሁ ፡ ብለህ ፡ አታስብ ፡ እሱ ፡ ይመግብሃል ።

ወኢይሁብ ፡ ውከተ ፡ ለጻድቅ ፡ ለዓለም ።

በመቃቢስ ፡ በሕዝቅያስ ፡ በዳዊት ፡ ፈጽሞ ፡ መከራ ፡ አይመጣበትም ፡ ለ ጊዜውም ፡ ቢያመጣበት ፡ እንዳመጣ በት ፡ አይቀርም ።

፳፫ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ አጽድፎሙ ፡ ውስተ ፡ አዘቅ ተ ፡ ሞት ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ሞት ፡ ገድሎ ፡ ገድ ሎ ፡ ወደሚያወርድበት ፡ ወደመቃ ብር ፡ አውርዳቸው ፡ እንድም ፡ እያፋ ጠንህ ፡ ወደሲኦል ፡ አውርዳቸው ።

ዕደወ ፡ ደም ፡ ወጽልሕዋን ፡ ኢይናፍቁ ፡ በመዋዕ ሊሆሙ ።

የሰውን ፡ ደም ፡ የምያፈስሱ ፡ ደመ ፡ በግዕን ፡ ለጣዖት ፡ የምያፈስሱ ፡ ከዳ ተኞች ፡ የሚሆኑ ፡ እኒህ ፡ ዘመናቸው ን ፡ አይጠራጠሩም ፡ ማለት ፡ ያጠፋ ናል ፡ አይሉም ፡ እንድም ፡ ይናፍቁ ፡ ይጠራጠራሉ ፡ ያጠፉን ፡ ይሆን ፡ ያጠ ፋን ፡ ይሆን ፡ ብለው ፡ እንድም ፡ ይነ ፍቁ ፡ መዋዕሊሆሙ ፡ ዘመናቸውን ፡ ይከፍላሉ ። ኃጥእ ፡ ሰው ፡ ዕድሜው ን ፡ አይፈጽምምና ። እንድም ፡ ኢይ ናፍቁ ፡ በዘመናቸው ፡ ኃጥዕ ፡ ጻድቅ ፡ አማኒ ፡ መናፍቅ ፡ አይለዩም ።

ወአንሰ ፡ ብከ ፡ ተወከልኩ ፡ እግዚኦ ።

እኔ ፡ ግን ፡ አቤቱ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እንዳ ይደርስብኝ ፡ በአንተ ፡ አመንሁ ። ተወከልኩከ ፡ ተወከልኩ ፡ ይላል ።

## መዝሙር ፡ ፶፮ ።

፩ ፡ ተሣሃለኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ኬደኒ ፡ ሰብእ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ። አቤ ቱ ፡ ዕርኄዊ ፡ እጅ ፡ አድርጉኛል ፡ አ ጥቅቶኛልና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

ወኵሎ ፡ አሚረ ፡ አሥርሐኒ ፡ ቀቲል ።

መከራውም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ አማት ቶኛልና ።

፪ ፡ ወኬዱኒ ፡ ፀርየ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ በኑኃ ፡ ዕለት ።

ሰርዓውያን ፡ ዘወትር ፡ ቀን ፡ ቀጥረው ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ ቀን ፡ ቀጥረው ፡ እጅ ፡ አድርገውኛል ።

እስመ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ፀብዑኒ ፡ ወፈራህኩ ።

የተጣሉኝ ፡ ጠላቶቼ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፡ እኔም ፡ ፈርቻለሁና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ እንድም ፡ የተጣሉኝ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ና ፡ ራራኊ ።

፫ ፡ ወአንሰ ፡ ኪያከ ፡ ተወከልኩ ፡ እግዚኦ ። መዝ ፡ ፶፱ ፡ ፳፫ ።

አቤቱ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አንተን ፡ አመንሁ ።

፬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እሴብሖ ፡ ቃልየ ። ቁ ፡ ፲ ።

ልመናዬን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አከብራለሁ ፡ እገልጻለሁ ።

ወበእግዚአብሔር ፡ ተወከልኩ ፡ ኢይፈርህ ፡ ምንተ ፡ ይሬስየኒ ፡ ዘሥጋ ። መዝ ፡ ፻፲፯ ፡ ፮ ። ኢሳ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ። ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፮ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴፩ ።

በእግዚአብሔር ፡ አምኛለሁና ፡ አል

ፈራም ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ። እንድም ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፡ ብዬ ፡ አልፈራም ።

፭ ፡ ወኵሎ ፡ አሚረ ፡ ያስቆርሩኒ ፡ ዘነበብኩ ።

ዘወትር ፡ የምናገረውን ፡ ሁሉ ፡ ይጸየፉኛል ።

ወላዕሌየ ፡ ይመክሩ ፡ ኵሎ ፡ ዕኩየ ።

በኔ ፡ ክፋውን ፡ ሁሉ ፡ ይመክሩብኛል ።

፮ ፡ ይጸንሑኒ ፡ ወይትኀብዑኒ ።

ተሠውረው ፡ ይሸምቁብኛል ፡ ይደፍጡብኛል ።

እሙንቱሰ ፡ ሰኰናየ ፡ ያስተሐይፁኒ ።

እኔህስ ፡ እግሬን ፡ ይመለከቱኛል ፡ የታሠረውን ፡ አላልቶ ፡ እንደሆነ ። ያልታሠረውን ፡ ወጣ ፡ ወረደ ፡ መጣ ፡ ሔደ ፡ እያሉ ፡ ይሸምቁብኛል ።

ወዘልፈ ፡ ይጸንሕዋ ፡ ለነፍስየ ።

ዘወትር ፡ ሰውነቴን ፡ ለሞት ፡ ለጥፋት ፡ ይሿታል ።

፯ ፡ ወኢታድኅኖሙ ፡ ወኢበምንትኒ ።

በማናቸውም ፡ ኃጢአቸው ። እንድም ፡ በማናቸውም ፡ መቅሠፍትህ ፡ አታድናቸውም ፡ ለሕይወት ፡ ካላለው ፡ የበሉት ፡ እንቆ ፡ የጠጡት ፡ እንገዘ ፡ ይሁኛልና ።

ወታጸድፎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ በመንትክ ። ኢላ ፡ ፷፫ ፡ ፮ ።

አሕዛብን ፡ በመቅሠፍትህ ፡ ታጠፋቸዋለህ ፡ ዕን ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።

፰ ፡ እምላኪየ ፡ እነግረከ ፡ ሕይወትየ ።

ፈጣሪዬ ፡ በመከራ ፡ መኖሬን ፡ እነግርሃለሁ ።

ወአንበርኩ ፡ አንብዕየ ፡ ቅድሜከ ፡ በከመ ፡ አዘዝከ ።

እንዳዘዝህ ፡ ዕንባዬን ፡ በፊትህ ፡ አኖራለሁ ፡ ማለት ፡ አልቅሱ ፡ ብለህ ፡ እንዳዘዝህ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ አለቀስን ። ምታብያን ፡ እንደ ፡ ትሩፋን ፡ የታወቀ ፡ ኃጢአት ፡ የላቸውም ፡ በዕሚት ፡ ላይ ፡ ዕሚት ፡ በክብር ፡ ላይ ፡ ክብር ፡ ለመጨመር ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፱ ፡ ለይግብኡ ፡ ፀርየ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ እመ ፡ ዕለተ ፡ ዕጸውዐከ ።

በለመንኩህ ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቼ ፡ አድጎ ፡ እንስ ፡ አድሮ ፡ እንስ ፡ ይሁኑ ።

ናሁ ፡ አእመርኩ ፡ ከመ ፡ አምላኪየ ፡ አንተ ።

ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ እንደሆንህ ፡ አውቅለሁና ። እንድም ፡ በለመንኩህ ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቼ ፡ አድጎ ፡ እንስ ፡ አድሮ ፡ እንስ ፡ ሁነዋልና ፡ ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ እንደሆንህ ፡ አወቅሁ ።

፲ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እሴብሕ ፡ ቃልየ ።

ስለዚህ ፡ ነገሬን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አከብራለሁ ።

በእግዚአብሔር ፡ ይከብር ፡ ዘነበብኩ ።

ያስቈርሩኒ ፡ ዘነበብኩ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ የተናገርሁት ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ይሆናል ።

፲፩ ፡ ወበእግዚአብሔር ፡ ተወከልኩ ፡ ኢይፈርህ ፡ ምንተ ፡ ይሬስየኒ ፡ ሰብእ ።

በእግዚአብሔር ፡ አምኛለሁና ፡ አልፈራም ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ።

፲፪ ፡ እምኀቤየ ፡ እሁብ ፡ ብፅዓትየ ፡ ለስብሐቲከ ።

ይህን ፡ ብታደርግልኝ ፡ ይህን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብዬ ፡ የተሳልሁትን ፡ ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ስእለቴን ፡ ለጌትነትህ ፡ እሰጣለሁ ።

፲፫ ፡ እስመ ፡ አድኀንካ ፡ ለነፍስየ ፡ እሞት ።

ሰውነቴን ፡ ከሞተ ፡ ሥጋ ፡ ነፍሴን ፡ ከሞተ ፡ ነፍስ ፡ አድነሃታልና ።

ወለአዕይንትየኒ ፡ እምአንብዕ ።

ዓይኔ ፡ ሥጋዬን ፡ ከዓንብዓ ፡ ሥጋ ። ዓይኔ ፡ ነፍሴን ፡ ከዓንብዓ ፡ ነፍስ ፡ አድነሃታልና ። በነፍስስ ፡ ልቅሶ ፡ የለምና ፡ የክብሩን ፡ መቅረት ፡ መናገር ፡ ነው ።



ወለእገርየ ፡ እምዳኅፅ ።

እግሬ ፡ ሥጋዬን ፡ ከዳሕፀ ፡ ሥጋ ፡ እግሬ ፡ ነፍሴን ፡ ከዳሕፀ ፡ ነፍስ ፡ አዳንሃት ።

ከመ ፡ አሥምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በቅድሜሁ ፡ እንተ ፡ ...

በአብርሃም ፡ በይሥሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ አገር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በመላእክት ፡ በጻድቃን ፡ በሰማዕታት ፡ አገር ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገለግለው ፡ ደስ ፡ አሰኘው ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ አመሰግነው ፡ ዘንድ ።

መዝሙር ፡ ፶፮ ።

፩ ፡ ተሣሃለኒ ፡ እግዚኦ ፡ ተሣሃለኒ ። መዝ ፡ ፻፳፫ ፡ ፫ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ። አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

እስመ ፡ ኪያከ ፡ ተወከለት ፡ ነፍስየ ።

ሰውነቴ ፡ (ልቡናዬ) ፡ ባንተ ፡ አምናለችና ።

ወተወከልኩ ፡ በጽላሎተ ፡ ክንፊከ ።

በክንፈ ፡ረድኤትህ ፡ በጽላሎተ ፡ ረድኤትህ ፡ አምኛለሁና ።

እስከ ፡ ተኃልፍ ፡ ኃጢአት ።

መከራይቱ ፡ እስክታልፍ ፡ ድረስ ። መዋውን ፡ በምዋው ፡ ኃጢአት ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ።

፪ ፡ እጸርሕ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ። ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘረድአኒ ።

እጸርሕ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ዘረድእኒ ፡ ብለህ ፡ አቅና ። ልዑል ፡ ወደ ሚሆን ፡ ወደረዳኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሼ ፡ እለምናለሁ ።

፫ ፡ ፈነወ ፡ እምሰማይ ፡ ወአድኀነኒ ።

ረድኤቱን ፡ ከሰማይ ፡ ልኮ ፡ እንድም ፡ ልጁን ፡ በሥጋ ፡ ልኮ ፡ አዳነኝ ።

ወወሀቦሙ ፡ ኃሳረ ፡ ለእለ ፡ ኬዱኒ ።

ባጠቁኝ ፡ እጅ ፡ ባደረጉኝ ፡ በዕርዓውያን ፡ ተዋርዶን ። በአጋንንት ፡ ድል ፡ መነሣትን ፡ አምጣባቸው ።

ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሣህሎ ፡ ወጽድቆ ።

ይቅርታውን ፡ ቸርነቱን ፡ አደረገልኝ ። እንድም ፡ ልጁን ፡ የባሕርይ ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ልኮ ፡ አዳነኝ ።

፬ ፡ ወአድኀና ፡ ለነፍስየ ፡ እምማእከለ ፡ እጓለ ፡ አናብስት ።

ሰውነቴን ፡ ከዕርዓውያን ፡ እጅ ፡ ነፍሴን ፡ ከአጋንንት ፡ እጅ ፡ አዳናት ፡ ስለ ፡ ኃያልነታቸው ፡ አናብስት ፡ አላቸው ።

መዮምሮ ፡ ድንጋፅየ ።

ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በመከራ ፡ ሥጋ ። አምስት ፡ ሺህ ፡ ከምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በመከራ ፡ ነፍስ ፡ የደነገጸ ፡ ሁኚ ፡ ኖርጉ ።

ዶቀቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ በንኒሆሙ ፡ ሐፅ ፡ መኰናት ።

ለ ፡ የቀረው ፡ ነው ። የዕርዓውያን ፡ አንደበታቸው ፡ ፍላጻ ፡ ጦር ፡ ነው ።

ወልሳኖሙኒ ፡ በሊህ ፡ መጥባሕት ። ኤር ፡ ፱-፱ ።

ያንደበታቸ ፡ ላንቃም ፡ የተሣለ ፡ ሰይፍ ፡ ነው ። ያ ፡ እንዲጎዳ ፡ የሚጎዳ ፡ ነገር ፡ ይናገራሉ ።

፲፩ ፡ ተለዓለ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልዕልተ ፡ ሰማያት ።

ሰማያትን ፡ በመፍጠር ።

ወበኵሉ ፡ ምድር ፡ ስብሐቲሁ ። ቀኍ ፡ ፲፩ ።

ምድርን ፡ በመፍጠር ፡ ልዕልናውን ፡ ገለጠ ።

እንድም ፡ (ተለዓለ) ፡ ከእስራኤል ፡ ልዑላኑን ፡ በመታደግ ፡ ከአሕዛብ ፡ ልዑላኑን ፡ በማጥፋት ። (ወበኵሉ) ፡ ከእስራኤል ፡ ትሑታኑን ፡ በመታደግ ፡ ከአሕዛብ ፡ ትሑታኑን ፡ በማጥፋት ፡ ልዕልናውን ፡ ገለጸ ።

፮ ፡ መሥገርተ ፡ አስተዳለዉ ፡ ለእገርየ ።

በሕዋሳቱ ፡ በወገኖቼ ፡ ምክር ፡ መከሩ ፡ ጦር ፡ ሸመቁ ።

ወቀጸፅዋ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ አስጎበጧት ።

ከረዩ ፡ ግበ ፡ ቅድሜየ ፡ ወወድቁ ፡ ውስቴቱ ። ዘዳ ፡ ፳፰ ፡ ፴፬-፴፭ ።

ጉድጓድ ፡ ቈፈሩ ፡ በቈፈሩት ፡ ጉድጓድ ፡ ወደቁ ፡ ማለት ። ምክር ፡ መከሩ ፡ ጦር ፡ ሸመቁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልተጠቀሙም ፡ በመከሩት ፡ ምክር ፡ ጠፉ ። ኤር ፡ ፲፰ ፡ ፳፱ ። ዕርዓውያን ፡ መቃብያንን ፡ ማርከው ፡ ካወረዱ ፡ በኋላ ፡ ሦስቱን ፡ ካህናት ፡ እነዚህ ፡ ለዘመዶቻቸው ፡ ያልሆኑ ፡ ለኔ ፡ ምን ፡ ይሆኑኛል ፡ ብሎ ፡ ንጉሡ ፡ አንዱን ፡ በሰይፍ ፡ አስመትቶታል ፡ አንዱን ፡ በርጥብ ፡ ቆርበት ፡ አስጠቅልሎ ፡ ገደል ፡ አስጥሎታል ። አንዱ ፡ ከዚህ ፡ ደረሰ ፡ አልተባለም ።

፰ ፡ ጥቡዕ ፡ ልብየ ፡ እግዚኦ ፡ ጥቡዕ ፡ ልብየ ። መዝ ፡ ፻፯ ፡ ፩-፭ ።

አቤቱ ፡ የኔ ፡ ግን ፡ ልቡናዬ ፡ ትጉሕ ፡ ነው ።

ጥቡዕ ፡ ልብየ ፡ እሴብሕ ፡ ወእዜምር ።

ልቡናዬ ፡ ትጉሕ ፡ ነው ። ትጉሕ ፡ መሆኑም ፡ ለሃይማኖት ፡ እንጂ ፡ ለክህደት ። ለምስጋና ፡ እንጂ ፡ ለዕርዓት ፡ አይዶለምና ። ተግቼ ፡ (እሴብሕ) ፡ አመሰግናለሁ ። እዜምር ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

፱ ፡ ወይትነሣእ ፡ ክብርየ ።

ስለዚህ ፡ ክብሬ ፡ ይመለስልኝ ፡ ይመለስልኛል ።

ወይትነሣእ ፡ በመዝሙር ፡ ወበመሰንቆ ።

ሲመለስልኝም ፡ ከበገናዬ ፡ ከመሰንቆዬ ፡ ጋራ ፡ ይመለስልኝ ።



ወእትነሣእ ፡ በጽባሕ ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ። በገናዬን ፡ መሰንቆዬን ፡ ይገር ፡ ለምስጋና ፡ ፈጥኜ ። እንድም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እነሣለሁ ። ፈጣሪን ፡ ማመስገን ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ነውና ።

፱ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ በውስተ ፡ አሕዛብ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ በአሕዛብ ፡ ጉባዔ ፡ እገዛልሃለሁ ።

ወእዜምር ፡ ለከ ፡ በውስተ ፡ ሕዝብ ።

በሕዝቡም ፡ ጉባዔ ፡ ምስጋና ፡ አቀርብልሃለሁ ።

፲ ፡ እስመ ፡ ዐብየት ፡ እስከ ፡ ሰማያት ፡ ምሕረትከ ።

ቸርነትህ ፡ ሰማያትን ፡ እስከ ፡ መፍጠር ፡ ደርሷ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብላለችና ።

ወእስከ ፡ ደመናት ፡ ጽድቅከ ።

ደመናትንም ፡ እስከ ፡ መፍጠር ፡ ደርሳ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብላለችና ።

፲፩ ፡ ተለዐለ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልዕልተ ፡ ሰማያት ።

እግዚአብሔር ፡ ሰማያትን ፡ በመፍጠር ፡ ልዕልናውን ፡ ገለጸ ።

ወበኵሉ ፡ ምድር ፡ ስብሐቲሁ ። ቀኍ ፡ ፩ ።

ጌትነቱም ፡ ባሬቱ ፡ መግዛቱ ፡ ምሉዕ ፡ ነው ። መዝ ፡ ፻፲ ፡ ፩-፩ ።

## መዝሙር ፡ ፶፯ ።

፩ ፡ እመሰ ፡ አማን ፡ ጽድቀ ፡ ትነቡ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ። ሦስቱ ፡ ካህናት ፡ ከዕርዕ ፡ ወጥተው ፡ ከፈቱልን ፡ አሉ ። እስካሁን ፡ ወዴት ፡ ሔዳችሁ ፡ ኑራችኋል ፡ አኋቸው ፡ እላት ፡ ሥጋዊ ፡ ሹመትን ፡ ብትከለክሉን ፡ እኛ ፡ በደለኛ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይከስ ፡ ብለን ፡ ዕርዕ ፡ ወርድን ፡ እንጥያከስን ፡ ያሀል ፡ ንጉሥ ፡ በሃይማኖት ፡ ወልደን ፡ በምግባር ፡ አሳድገን ፡ መጣን ፡ አኋቸው ። ነገራችኍ ፡ ዕውነት ፡ አይሆንም ፡ (አይመስልም) ፡ እንጂ ፡ ዕውነትስ ፡ ተናግራችኍ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ እንዲህስ ፡ አድርጋችኍ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

ወርትዕ ፡ ትኴንኑ ፡ ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

የሰው ፡ ልጆች ፡ በውነት ፡ በሚገባ ፡ ትገዛላችሁ ። ለእግዚአብሔር ፡ መገዛት ፡ አይቀርባችሁም ። እንድም ፡ ርትዓ ፡ ትትኴንኑ ፡ እናንተ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (በቅን) ፡ በውነት ፡ ትገዛላችሁ ። ትኴንኑ ፡ እኛንም ፡ መግዛት ፡ አይቀርባችሁም ።

፪ ፡ እስመ ፡ በልብክሙ ፡ ኀጢአተ ፡ ትገብሩ ፡ በ ፡ ዲበ ፡ ምድር ።

ነገር ፡ ግን ፡ በልባችሁ ፡ አስባችሁ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ዕዳ ፡ የሚሆንባችሁን ፡ ሥራ ፡ ትሠራላችሁና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ይቀርባችኋል ፡ እንጂ ።

ወጽአሉተ ፡ ደጸኤፈ ፡ እደዊከሙ ።

የተፈተለ ፡ ከሁለት ፡ የተታታ ፡ ከሦ ስት ፡ እንዲሉ ። ከተፈለ ፡ የተታታ ፡ እንዲ ፡ ፀና ፡ እደ ፡ ልቡናችሁ ፡ ከዳት ን ፡ ተንኰልን ፡ አጽንቷልና ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ይቀርብችኋል ፡ እንጂ ። እ ንዲህስ ፡ ከደረጋችሁ ፡ የሰውን ፡ ልጆ ች ፡ በውነት ፡ በሚገባ ፡ ትገዛላችሁ ። የሰው ፡ ልጆች ፡ እናንተም ፡ በውነት ፡ በሚገባ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትገዛላ ችሁ ።

፫፤ ተነከሩ ፡ ኃጥአን ፡ እማኅፀን ።

ምስቱ ፡ ከሀናት ፡ ከሕግ ፡ ወጡ ።

እምከርሥ ፡ ዕሕቱ ፡ ወነበቡ ፡ ሐሰተ ። ኢ.ሳ ፡ ፵፰ ፡ ፰ ።

ማኅፀንና ፡ ከርሥ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ከ ሕግ ፡ ወጡ ።

በልሳኑ ፡ ሥጋ ፡ ሐሰት ፡ ተናገሩ ። ማ ኅፀን ፡ ሕግ ፡ እላት ፡ ልሕቀት ፡ መን ፈሳዊ ፡ ያድጉበታልና ። እምነቱ ፡ ማይናር ፡ ዕርዕ ፡ ወርደን ፡ እንጥያከ ስን ፡ ያሀል ፡ ንጉሥ ፡ በሃይማኖት ፡ ወ ልደን ፡ በምግባር ፡ አሳድገን ፡ መጣን ፡ ግለታቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ። እን ድም ፡ ከመቅደስ ፡ ወጡ ። ማኅፀን ፡ መ ዋኛ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ መገናኛ ፡ እን ዲሉ ። ተረፈ ፡ መሥዋዕቱን ፡ እየበሉ ፡ ያድጉበታልና ። አንድም ፡ ለሁሉ ፡ እ ድርጎ ፡ ተናግሮታል ፡ ብሎ ፡ (ተነከሩ) ፡ ኃጥአን ፡ ከናታቸው ፡ ማኅፀን ፡ ጀም ረው ፡ በናታቸው ፡ ማኅፀን ፡ ሳሉ ፡ በ ደሉ ፡ (እምከርሥ) ፡ በልሳኑ ፡ ነፍስ ፡ ሐሰትን ፡ ተናገሩ ፡ አሁን ፡ ሕፃናት ፡ በማኅፀን ፡ ሳሉ ፡ የሚበድሉ ፡ ሐሰት ፡ የሚናገሩ ፡ ሁነው ፡ አይደለም ፡ ነቢይ ፡ ኋላ ፡ የሚሠሩትን ፡ ያውቃልና ፡ እን ዲህ ፡ አለ ፡ እንጂ ።

፬፤ መመንሱመሰ ፡ ከመ ፡ ሕምዘ ፡ አርዌ ፡ ምድር ።

በሰው ፡ የሚያመጡት ፡ መከራ ፡ እን ደ ፡ እባብ ፡ መርዝ ፡ ነው ። እባብ ፡ ስት ነድፍም ፡ ስትገድልም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እነሱም ፡ ሲመክሩም ፡ ሲያመ ጡም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። አንድም ፡ የስዲ ፡ ጳውሎስ ፡ ትርጓሜ ፡ ብሎ ፡ በራሳቸው ፡ የሚያመጡት ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ መርዝ ፡ ነው ። እባብ ፡ ስትነድፍም ፡ ስትገድልም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እነሱም ፡ ሲበድሉም ፡ ሲ ጠፉም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ና ።

ወከመ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ፅምምት ፡ ዕዘኒሃ ።

በጆሮዋ ፡ እንደማትሰማ ፡ እባብ ፡ ነው ።

፭፤ እንተ ፡ ኢትሰምዕ ፡ ቃለ ፡ ዘይረቅዩ ፡ ኢር ፡ ፰ ፡ ፲፯ ።

እየደገመ ፡ ሲረግት ፡ እንደማትሰማ ።

ወእንዘ ፡ ይሜርይ ፡ መሠርይ ፡ ጠቢብ ።

ብልሀ ፡ ደጋሚ ፡ እየደገመ ፡ ሲረግት ፡ እንደማትሰማ ፡ እባብ ፡ ነው ። እባብ ፡ ዓይን ፡ እንጂ ፡ ጆሮ ፡ የላትም ፡ አካል ፡ ዘየአከልሱአል ተከፈለባትም ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስላልሰማ ችበት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ከነደፈች ፡ በኋላ ፡ እንዱን ፡ ጆሮዋን ፡ ከምድር ፡ ትቀብረዋለች ፡ በንዱ ፡ ጆ ሮዋ ፡ አክኗን ፡ ትቀልልበታለች ፡ ስብ ሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አትሰማም ፡ የ ነደፈችው ፡ ሰው ፡ ይሞታልና ። እን ድም ፡ በራሳቸው ፡ የሚያመጡትን ፡ መከራ ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ ነድፋ ፡ መጥታ ፡ አንዱን ፡ ጆሮዋ ፡ ከምድር ፡ ትቀብረ ዋለች ። አንዱን ፡ ጆሮዋን ፡ በጅራቷ ፡ ትጎስጉሰዋለች ፡ መርዟ ፡ ያለ ፡ ከጅ ራቷ ፡ ነው ። ፀሐይ ፡ ሲነካው ፡ ቀልጦ ፡ ከአካሏ ፡ ተሠራጭቶ ፡ ይገድላታልና ። ከመ ፡ ኢትስማዕ ፡ ቃለ ፡ እንዚራ ፡ ወ መሰንቆ ፡ ትወዲ ፡ ዘነባ ፡ ውስተ ፡ ዕገዝና ፡ ወትመውት ፡ በሕምዛ ፡ እንዲል ። እ ነሱም ፡ በመከሩት ፡ ምክር ፡ ጠፍተዋ ልና ።

፮፤ እግዚአብሔር ፡ ይሰብር ፡ ስነኒሆሙ ፡ በው ስተ ፡ አፉሆሙ ።

እግዚአብሔር ፡ አፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ የፊት ፡ ጥርሳቸውን ፡ ይሰብረዋል ፡ ማለት ። በባሕርያቸው ፡ ያለ ፡ የሠራ ዊቱን ፡ ሥልጣን ፡ ያጠፋል ።

ወይሰብር ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥረሲሆሙ ፡ ለአና ብስት ።

የአናብስት ፡ የኋላ ፡ ጥርሳቸውን ፡ ይ ሰብራል ፡ ማለት ፡ የንጉሥታቱን ፡ ሥ ልጣን ፡ ያጠፋል ። ከፊት ፡ ጥርስ ፡ የ ኋላ ፡ ጥርስ ፡ እንዲፀና ። ከሠራዊቱም ፡ ሥልጣን ፡ የንጉሥታቱ ፡ ሥልጣን ፡ ይ ፀናል ። ፪ ፡ ፲ ።

፯፤ መየኀሥሩ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ዘይትከዐው ።

ታጥበው ፡ እንደሚያፈስሱት ፡ ውሀ ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ተዋርዶ ፡ ቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወይሬስዮ ፡ ቀስቶ ፡ እስከ ፡ ያደክምሙ ።

ይሁዳ ፡ መቅብዩ ፡ ቀስቱን ። አንድም ፡ ጌታ ፡ ቀስተ ፡ መዓቱን ፡ እስኪያጠፋ ቸው ፡ ይስባል ።

፰፤ ወየሐልቁ ፡ ከመ ፡ ስምዕ ፡ ዘይትመሰው ።

የደረ ፡ ማር ፡ ሰም ፡ ቀልጦ ፡ እንዲጠ ፋ ፡ ይጠፋሉ ።

ወድቀት ፡ እሳት ፡ ወኢርኢክዋ ፡ ለፀሐይ ።

ቀጠና ፡ መጣች ፡ ፀሐይን ፡ ቀና ፡ ብዬ ፡ አላየሁም ፡ ቀጠና ፡ ስልት ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ ፀሐይን ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ አይሆንለትምና ። አንድም ፡ (ወድቀ ት) ፡ መከራ ፡ መጣች ፡ (ወኢርኢክዋ) ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አላየሁም ። አንድም ፡ (ወድቀት ፡ እሳት) ፡ ጻሕሉ ፡ ብርት ፡ መ ጣች ፡ (ወኢርኢክዋ ፡ ለፀሐይ) ፡ ለሥ ዕለ ፡ ፀሐይ ፡ አልሰገድሁም ፡ መሥዋ ዕት ፡ እሪያ ፡ አልበላሁም ።

፱፤ ዘእንበለ ፡ ይትኃወቅ ፡ ሦግኩሙ ፡ ህልተ ፡ ኮን ።

ይህ ፡ ቍጥቋጦ ፡ ምክራችሁ ፡ ሳይታ ወቅ ፡ ቀርከሃ ፡ ቀርከሃ ፡ ያህል ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። እንዲጎዳ ፡ ቢያውቅ ፡ ስንኳን ፡ ከሁለት ፡ እንዱን ፡ ይነግቸው ፡ ሁሉ ንስ ፡ ባልተወላቸውም ፡ ነበርን ።

ከመ ፡ ሕያዋን ፡ በመዓቱ ፡ ይውኅጦሙ ።

እንዘ ፡ ሕያዋን ፡ ሲል ፡ ነው ። እሳን ፡



2014 04 17

አለን ፡ ስትሉ ፡ በመዓቱ ፡ ያጠፋች ኋል ። እንድም ፡ እንዳለ ፡ ይሆናል ። እንደ ፡ ዳታንና ፡ እንደ ፡ አቤሮን ፡ ነፍ ሳችኍ ፡ ከሥጋችኍ ፡ ሳትለይ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ያወርዷችኋል ።

፲፤ ይትፌሣሕ ፡ ጻድቅ ፡ ሶበ ፡ ይሬኢ ፡ በቀለ ።

ይሁዳ ፡ መቅብዩ ፡ በቀሉን ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

ወይትሐፀብ ፡ እደዊሁ ፡ በደመ ፡ ኃጥእ ።

እጁንም ፡ በኃጥእ ፡ ደም ፡ ይታጠባል ። የገዳይ ፡ ምልክቱ ፡ ደም ፡ በጣቱ ፡ እን ዲሉ ። ድል ፡ ማድረጉን ፡ መናገር ፡ ነው ። እንድም ፡ በዕርዓዊ ፡ ደም ፡ ይ ታጠባል ። ይሁዳ ፡ መቅብዩ ፡ እየተ ዋጋ ፡ አጥር ፡ ጥሶ ፡ ይዟቸው ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ እሱ ፡ ወደቀ ፡ እጁ ፡ በደሙ ፡ ከውላጋው ፡ ተጣብቆ ፡ የማይላቀቅ ፡ ሆነ ። ከሉበት ፡ በታ ፡ ወሀ ፡ አልነበ ረምና ፡ አንድ ፡ ዕርዓዊ ፡ አርደው ፡ በ ዚያ ፡ ደም ፡ አስለቅቀውታል ። እነሱ ንም ፡ ወንድሙ ፡ ሕልቃሉስ ፡ ይዟ ቸው ፡ሔዷልና ።

፲፩፤ ወይብል ፡ ሰብእ ፡ ቦኑ ፡ እንጋ ፡ ፍሬ ፡ ለጻድቅ ።

በውኑ ፡ እንዳች ፡ ለመቃቢስ ፡ ደም ፡ የሚመልስ ፡ የበቃ ፡ የነቃ ፡ ልጅ ፡ ኑ ሮታልን ፡ (አለውን) ፡ ይላል ።

ወቦኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈትሕ ፡ሎሙ ፡ በዲበ ፡ ምድር ።

ለመቃብያንም ፡ በወድያ ፡ ዓለም ፡ ብቻ ፡ መስሎን ፡ በወዲህም ፡ ዓለም ፡ ይፈር ድላቸዋልን ፡ ይላል ።

እንድም ፡ (ይትፌሣሕ) ፡ አዳም ፡ በቀ ሉን ፡ ጌታ ፡ ሲመልስለት ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ (ወይትሐፀብ) ፡ አይሁ ድ ፡ ኃጥእ ፡ በሚሉት ፡ በጌታ ፡ ደም ፡ እጁን ፡ ይታጠባል ፡ (ወይብል) ፡ በውኑ ፡ እንዳች ፡ ለአዳም ፡ በቀሉን ፡ የሚመ ልስ ፡ ልጅ ፡ ኑሮታልን ፡ ይላል ፡ ሰው ። ወቦኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈትሕ ፡ ሎሙ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ ለምእመናን ፡ በወድያው ፡ ዓለም ፡ ብቻ ፡ መስሎን ፡ ነበር ፡ ለካ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይፈርድላቸዋልን ፡ ይላል ።

## መዝሙር ፡ ፶፱ ።

፩፤ አድኅነኒ ፡ እግዚኦ ፡ እምፀርየ ። መዝ ፡ ፶፱ ፡ ፱ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ። አ ቤቱ ፡ ከጠላቴ ፡ ከንጉሡ ፡ አድነኝ ።

ወእንግፈኒ ፡ እምእለ ፡ ቆሙ ፡ ላዕሌየ ።

በጸላትነት ፡ ከተነሡብኝ ፡ ከመኳንን ቱም ፡ አድነኝ ።

፪፤ ወባልሐኒ ፡ እምገበርተ ፡ ዓመፃ ።

ዓመፅንም ፡ ከሚሠሩ ፡ ከሠራዊቱ ፡ አድነኝ ።

ወአድኅነኒ ፡ እምዕድወ ፡ ደም ።

የሰውን ፡ ደም ፡ ከሚያፈሱ ፡ ከኃያላኑ ፡ አድነኝ ።



፫፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ ነዐውዋ ፡ ለነፍስየ ።

እነሆ ፡ ሰውነቴን ፡ ለሞት ፡ ለጥፋት ፡ ሸተዋታልና ።

ወቆሙ ፡ ላዕሌየ ፡ ኃያላን ።

ኃያላኑም ፡ በጸላትነት ፡ ተነሥተውብ ኛልና ።

አኮ ፡ በአበሳየ ፡ ወአኮ ፡ በኃጢአትየ ፡ እግዚኦ ።

ይኸውም ፡ በጥቃቅኑ ፡ በታላላቁ ፡ ኃጢአቱ ፡ አይደለም ፡ ከዚያ ፡ እስከ ፡ ተኃልፍ ፡ ኃጢአት ፡ አለ ፡ ከዚህ ፡ አኮ ፡ በአበሳየ ፡ አለ ፡ እንደ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ አይጣላምን ፡ ቢሉ ፡ አይጣላም ፡ የመ ቃብያን ፡ ምርኮ ፡ በክብር ፡ ላይ ፡ ክ ብር ፡ በዕሤት ፡ ላይ ፡ ዕሤት ፡ ለመጨ መር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ትሩፋን ፡ የታወቀ ፡ ኃጢአት ፡ የለባቸውምና ፡ ከዚህ ፡ አኮ ፡ በአበሳየ ፡ አለ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ የማይበድል ፡ እንጨት ፡ ሁኖ ፡ የማይጤስ ፡ የለምና ፡ ከዚያ ፡ እስከ ፡ ተኃልፍ ፡ ኃጢአት ፡ አለ ። መዝ ፡ ፶፮ ፡ ፭ ። እንድም ፡ እሳቸውን ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ በድያቸው ፡ አይደለም ።

፬፤ ዘእንበለ ፡ ዓመፃ ፡ ሮፅኩ ፡ ወአርታዕኩ ።

ኃጢአት ፡ ሳልሠራ ፡ ጣዖት ፡ ሳላመ ልክ ፡ ተማረኩኍ ፡ ዕርዕ ፡ ወረድኍ ። እንድም ፡ ለስዕለ ፡ ፀሐይ ፡ ሳልሰግድ ፡ መሥዋዕተ ፡ እሪያ ፡ ሳልበላ ፡ ከዕርዕ ፡ ወጣሁ ።

ተንሥእ ፡ ተቀበለኒ ፡ ወርኢ ።

በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሥተህ ፡ መ ከራዬን ፡ ዓይተህ ፡ በረድኤት ፡ ተቀ በለኝ ።

፭፤ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ አምላከ ፡ ኃያላን ፡ ንጉሠ ፡ እስራኤል ።

የኃያላኑ ፡ ፈጣሪ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ አቤቱ ፡ ተነሣ ። እንድም ፡ የኃያላኑ ፡ ፈጣሪ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ አቤቱ ።

ሐውጾሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ወተማሃሎሙ ።

ከእስራኤል ፡ በጎዎቹን ፡ በረድኤት ፡ ጎብኝተህ ፡ ይቅር ፡ በላቸው ።

ወኢትማሃሎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።

ክፎችን ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ አትበላቸው ። እንድም ፡ (ሐውፆሙ) ፡ ከአሕዛብ ፡ በላዎቹን ፡ በረድኤት ፡ ጎብኝተህ ፡ ይ ቅር ፡ በላቸው ፡ (ወኢትማሃሎሙ) ፡ ክፎችን ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ አትበላቸው ፡ እንድም ፡ (ሐውፆሙ) ፡ እስራኤልን ፡ ይቅር ፡ በላቸው ፡ አሕዛብ ፡ አላቸው ፡ ስለብዛታቸው ፡ በጸያፍ ፡ የገባ ፡ (ወኢ ትማሃሎሙ) ፡ አሕዛብን ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ አትበላቸው ።

፮፤ ይትመየጡ ፡ ሠርከ ፡ ወይርኅቡ ፡ ከመ ፡ ከል ብ ፡ ወይዑዱ ፡ ሀገረ ።

ይርኀቡ ፡ ከመ ፡ ከልብ ፡ ወይዑዱ ፡ ሀገረ ፡ ወይትመየጡ ፡ ሠርከ ፡ ብለህ ፡ አቅና ። እንደ ፡ ውሻ ፡ ተርበው ፡ አፍ ሙሉ ፡ ቍራሽ ፡ ለመቀላወጥ ፡ አገር ፡ ላገር ፡ ይዙሩ ። የሚያቀላውጣቸው ፡ አጥተው ፡ በሠርክ ፡ ይመለሱ ። እን ድም ፡ በሠርክ ፡ ዕድሚያቸው ፡ ተር በው ፡ ተላውጠው ፡ ለመብላት ፡ እ

ንደ ፡ ውሻ ፡ አገር ፡ ላገር ፡ ዙረው ፡ ይመለሱ ፡ እንድም ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመናቸው ፡ ተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ ይጡ ። ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ ።

፯ ፤ [illegible] ።

እንሆ ፡ ባንደበቻቸው ፡ የማይገባ ፡ ነገር ፡ ይናገራሉ ።

[illegible] ።

ባንደበታቸውም ፡ ሰይፍ ፡ አለ ፡ ማለት ፡ የሚጎዳ ፡ ነገር ፡ ይናገራሉ ።

፰ ፤ [illegible] ።

ነገራቸውን ፡ የምትሰማ ፡ አንተም ፡ አቤቱ ፡ እንደ ፡ ዋዛ ፡ እንደ ፡ ፌዛዛ ፡ ነገራቸውን ፡ ታይብቸዋለህ ።

[illegible] ።

አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ ናቅሃቸው ፡ አቃለልሃቸው ፡ ብቅና ፡ ዝቅ ፡ አድርገህ ፡ አየሃቸው ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ አጠፋሃቸው ፡ ሲል ፡ ነው ።

፱ ፤ [illegible] ።

አደራ ፡ ጥብቅ ፡ ሰማይ ፡ ሩቅ ፡ እንዲሉ ፡ ወገኖቼን ፡ ሕዋሳቴን ፡ ባንተ ፡ አስጠብቃለሁ ።

[illegible] ።

አምባ ፡ መፀጊያዬ ፡ አንተ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነህና ፡ አንተ ፡ ፈጣሪዬ ፡ አምባ ፡ መፀጊያዬ ፡ ነሕና ።

፲ ፤ [illegible] ።

የፈጣሪዬ ፡ ይቅርታው ፡ ይደረግልኛል ፡ ይደረግልኛል ።

[illegible] ።

ፈጣሪዬ ፡ ጠላቶቼን ፡ አጥፍቶ ፡ ያሳየኛል ። እንድም ፡ ዘከነ ፡ ያለበት ፡ ነው ። በጠላቶቼ ፡ የተደረገውን ፡ ያሳየኛል ፡ አሳየኝ ።

፲፩ ፤ [illegible] ።

ሕግህን ፡ እንዳያፈርሱ ፡ አሕዛብን ፡ አታጥፋቸው ፡ አሕዛብኒ ፡ እለ ፡ አልበሙ ፡ ሕግ ፡ የሐግጉ ፡ ሕገ ፡ ዘከመ ፡ ሕጎሙ ፡ እንዲል ። ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ። ነፍሰ ፡ የገደለ ፡ መቶ ፡ ጊደር ፡ ቋንጃ ፡ የቈረጠ ፡ ቤት ፡ ያቃጠለ ፡ ሃምሳ ፡ ጉማ ፡ ወሰከምት ፡ የሰበረ ፡ ዓሥር ፡ ጊደር ፡ ይክፈል ፡ እያሉ ፡ ይወስናሉና ፡ ይህንስ ፡ ሕግ ፡ አይልላቸውም ፡ ብሉ ፡ ምናልባት ፡ ቢመለሱ ።

[illegible] ።

ባይመለሱ ፡ ግን ፡ አጥፋቸው ። እንድም ፡ (ኢትቅትሎሙ) ፡ እስራኤል ፡ ሕግህን ፡ እንዳያፈርሱ ፡ አሕዛብን ፡ አታጥፋቸው ፡ ሰው ፡ ጠላት ፡ የጠፋለት ፡ እንደሆነ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አያስብምና ፡ (ዝርዎሙ) ፡ እስራኤል ፡ ሕግህን ፡ ሳያፈርሱ ፡ አሕዛብ ፡ በጠላትነት ፡ ቢነሡባቸው ፡ ግን ፡ የጊዜው ፡ ጊዜ ፡ አጥፋቸው ። እንድም ፡ (ኢትቅትሎሙ) ፡ እስራኤልን ፡ በዕ



ርዕ ፡ ሳሉ ፡ አታጥፋቸው ፡ ከዚያ ፡ ሳሉ ፡ ያጠፋቸው ፡ እንደሆነ ፡ እንድናለን ፡ መስዓቸው ፡ ሕጉን ፡ አፍርሰው ፡ የጥፋት ፡ ጥፋት ፡ ያጠፋሉና ። (ዝርዎሙ) ፡ ብታጠፋቸውም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አግብተህ ፡ አጥፋቸው ፡ በሥጋቸው ፡ ቢጠፉ ፡ በነፍሳቸው ፡ ይድናሉና ።

[illegible] ።

ረዳቴ ፡ የምትሆን ፡ ፈጣሪዬ ፡ አሕዛብንስ ፡ ፈጥነህ ፡ አጥፋቸው ።

፲፪ ፤ [illegible] ።

በፍጹም ፡ አንደበታቸው ፡ ተናግረው ፡ የሚሠሩትን ፡ ኃጢአት ፡ ዓይተህ ።

[illegible] ።

በመታበያቸው ፡ ይጠፋሉ ፡ ይጥፉ ።

[illegible] ።

ሰውን ፡ በመርገማቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማማዘናቸው ፡ ሐሰት ፡ በመናገራቸው ፡ ፍጻሜ ፡ ጥፋታቸው ፡ ይታወቃል ፡ ይታወቅ ።

፲፫ ፤ [illegible] ።

በኋላው ፡ መቅሠፍት ፡ ይጠፋሉ ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ሰብአ ፡ ትካት ፡ ሰብአ ፡ ሰዶም ፡ ሰብአ ፡ ግብፅ ፡ ሰብአ ፡ ፋርስ ፡ ከጠፉ ፡ በኋላ ፡ ጠፍተዋል ። እንድም ፡ በታናሽ ፡ መቅሠፍት ፡ በታናሽ ፡ ጥፋት ፡ ይጠፋሉ ። ገመስ ፡ ደኃሪት ፡ እንዲል ።



ቡኒ ፡ ወለተ ፡ ዱሬ ፡ ይላታል ። እንጥያከስ ። መጥቶ ፡ ላገባሽ ፡ አላት ። ላገባሽ ፡ አልከኝ ፡ አለችው ፡ አዎን ፡ አሁነህ ፡ ውሰደኝ ፡ ብላ ፡ ጥቂት ፡ ራቅሃን ፡ ሰደደችው ፡ በሚመጣበት ፡ ቀን ፡ ቀጥሬ ፡ ባሪያ ፡ እንደምን ፡ ደፈረኝ ፡ ብላ ፡ ድብቅ ፡ ጦር ፡ አበጅታ ፡ ስቡር ፡ ጉንድ ፡ ሥውር ፡ ጉድብ ፡ ይላል ፡ ጉድጓድ ፡ ስታስቆፍር ፡ ሰነበተች ፡ ሲመጣ ፡ ከወደ ፡ ኋላ ፡ ጦር ፡ አስነግችበት ። ወሰይጣን ፡ ጺቅ ፡ ብሉበት ፡ ጠምጺ ፡ ብሉ ፡ ተንጣምዶ ፡ ሙቷል ።

[illegible] ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ እንዲገዛ ፡ የአምሩ ፡ ያውቃሉ ። እንድም ፡ ይህ ፡ ተደርጎባቸው ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ የሐልቁ ።

፲፬ ፤ [illegible] ።

እንደ ፡ ውሻ ፡ ተርበው ፡ ለቅልውጥ ፡ አገር ፡ ላገር ፡ ይዞሩ ፡ ማታ ፡ እፍሙሉ ፡ ቁራሽ ፡ አጥተው ፡ ይመለሱ ።

፲፭ ፤ [illegible] ።

የሚቀድመው ፡ አለ ።

[illegible] ።

በልተው ፡ ጠግበው ፡ ጥጋብስ ፡ አልቻላቸው ፡ ካሉ ፡ ለቅልውጥ ፡ ይበተኑ ።

2014 04 17

እንድም ፡ ገንዘባቸውን ፡ በልተው ፡ የእስራኤል ፡ ገንዘብ ፡ ቀረብን ፡ ብለው ፡ ከዙኑስ ። ገንዘባቸውን ፡ ዘረፈ ፡ ገፋፈ ፡ ወስዶባቸው ፡ ለቅልውጥ ፡ ይበተኑ ።

፲፮ ፡ ወአንበ ፡ እሌብሕ ፡ በኃይልከ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ከሃሊነትህን ፡ አመሰግና ለኍ ። እንድም ፡ በከሃሊነትህ ፡ አን ተን ፡ አመሰግናለኍ ፡ ላንተም ፡ ምስ ጋና ፡ አቀርባለኍ ።

ወእትፌሣሕ ፡ በጽባሕ ፡ ምሕረትከ ።

እንደ ፡ ንጋት ፡ ደስ ፡ የምያሰኝ ፡ ምሕ ረትህን ፡ አግኝቼ ። እንድም ፡ ፈጥኖ ፡ የሚደረግ ፡ ቸርነትህን ፡ አግኝቼ ። እ ንድም ፡ በጽባሕ ፡ (በምሕረትከ) ፡ በቸ ርነትህ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

እስመ ፡ ኮንከኒ ፡ ምስካይየ ።

አምባ ፡ መፀግያ ፡ ሁነኸኛልና ።

ወፀወንየ ፡ በዕለተ ፡ ምንዳቤየ ።

በመከራዬ ፡ ቀን ፡ መፀግያ ፡ ሁነኸኛ ልና ። ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፲፪ ።

፲፯ ፡ ረዳእየ ፡ አንተ ፡ ወለከ ፡ እዜምር ፡ አ ምላኪየ ።

አንተ ፡ ረዳቴ ፡ ነህ ፡ እኔም ፡ ላንተ ፡ ለ ፈጣሪዬ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

እስመ ፡ አምላኪየ ፡ ወምስካይየ ፡ አንተ ።

አንተ ፡ ፈጣሪዬ ፡ መፀግያዬ ፡ ነህና ።

አምላኪየ ፡ ውእቱ ፡ ግህልየ ።

ይቅርታዬን ፡ የምያደርግልኝ ፡ ፈጣ ሪዬ ፡ ነው ። እንድም ፡ ፈጣሪዬ ፡ ይቅ ርታዬን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ ነው ።

## መዝሙር ፡ ፹፱ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ ገጸፍከነ ፡ ወነሠትከነ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ፡ ያባቶ ቻቸውን ፡ የትሩፋትንም ፡ ያዘክራሉ ። አቤቱ ፡ ሰብዓ ፡ ዘመን ፡ በመከራ ፡ ጣ ልኸን ፡ በሞት ፡ አፈረስከን ።

ቀሠፍከነኒ ፡ ወተሣሃልከነ ።

ሰብዓ ፡ ዘመን ፡ በሠውጠ ፡ መከራ ፡ ገረፍኸን ፡ ከሰብዓ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ይ ቅር ፡ አልከን ። ሆሴ ፡ ፮ ፡ ፩ ።

፪ ፡ አድለቅለቃ ፡ ለምድር ፡ ወሆካ ።

ኢየሩሳሌምን ፡ በዊዋዌ ፡ ጊዜ ፡ በመ ከራ ፡ አናወጥኻት ፡ አወከኻት ።

ወፈወስካ ፡ ቍስላ ፡ እስመ ፡ አንቀልቀለት ።

ሰብዓ ፡ ዘመን ፡ በመከራ ፡ ሥጋ ፡ እጠ ፋ ፡ እጠፋ ፡ ብላ ፡ ነበርና ፡ በሚጠተ ፡ ሥጋ ፡ መከራ ፡ ሥጋዋን ፡ አራቅህ ላት ፡ ፀጥ ፡ አደረግላት ።

፫ ፡ አርኢይኮሙ ፡ ዕፁባተ ፡ ለሕዝብከ ።

በወገኖችህ ፡ በትሩፋን ፡ ጭንቅ ፡ ጭ ንቅ ፡ የሚሆን ፡ ጊዋዌ ፡ ሥጋን ፡ አመ ጣህባቸው ።

ወአስተይከነ ፡ ወይነ ፡ መደንግፅ ።

ወይነ ፡ መደንግፅም ፡ ይላል ፡ አስተይ ከነ ፡ ካልሁ ፡ ብሎ ፡ ወይነ ፡ ብሏል ፡





እንጂ ፡ መከራን ፡ አመጣህብን ። አን ድም ፡ ወይን ፡ መከራን ፡ አጠጣኸን ። እንድም ፡ የሚያስደነግጥ ፡ ወይንን ፡ አጠጣኸን ፡ ወይን ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ ሲጠጡት ፡ ይመራልና ። ሚሴ ፡ ኮነ ፡ መሪረ ፡ ለእለ ፡ ይሰትይዎ ፡ እንዲል ።

፬ ፡ ወወሀብኮሙ ፡ ትእምርተ ፡ ለእለ ፡ ይፈር ሁከ ።

ለሚፈሩህ ፡ ለሚያመልኩህ ፡ ለትሩ ፋን ፡ ለሚጠተ ፡ ሥጋ ፡ ምልክት ፡ የሚሆን ፡ ሞተ ፡ ብልጣሶርን ፡ ሰጠሃ ቸው ።

ከመ ፡ ያምስጡ ፡ እምገጸ ፡ ቀስት ።

እምገጸ ፡ ቅስት ፡ ሲል ፡ ነው ። ከመ ከራ ፡ ሥጋ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ።

፭ ፡ ወይድኃኑ ፡ ፍቁራኒከ ።

እለ ፡ ይፈርሁከ ፡ ፍቁራኒከ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ። የሚያመልኩህ ፡ የሚወ ዱህ ፡ ትሩፋን ፡ ከመከመራ ፡ ሥጋ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ (ወወሀብ ኮሙ) ፡ ለሚያመልኩህ ፡ ለሚፈሩህ ፡ ለሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ ለድኅነተ ፡ ነፍስ ፡ ምልክት ፡ የሚሆን ፡ ተአምራትን ፡ ሰጠኻቸው ። (ከመ ፡ ያምስጡ ፡ ወይ ድኀኑ) ፡ የሚወድዱህ ፡ የሚያመል ኩህ ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ ከመከራ ፡ ሥጋ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡ ቀስት ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ጦር ፡ ወርውረውብቸዋል ፡ ሰይፍ ፡ መዘውብቸዋልና ፡ እንድም ፡ (እግዚኦ ፡ ገጸፍከነ) ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ከምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በመከራ ፡ ነፍስ ፡ ጣልከኝ ፡ በሞተ ፡ ነፍስ ፡ አፈረ ስኸን ፡ (ቀሠፍከነኒ) ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ከምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በሠውጠ ፡ መከራ ፡ ገረፍኸን ። ከምስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ይቅር ፡ አልኸን ፡ (አድለቅለቃ ፡ ለምድር) ፡ ምእመንን ፡ በዊዋዌ ፡ ነፍስ ፡ ጊዜ ፡ በመከራ ፡ አናወጥሃት ፡ አወከኻት ፡ (ወፈወስካ) ፡ አምስት ፡ ሽህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በመከራ ፡ ነፍስ ፡ እጠፋ ፡ እጠፋ ፡ ብላ ፡ ነበርና ፡ በሚጠተ ፡ ነፍስ ፡ መከራ ፡ ነፍሷን ፡ አራቅህላት ፡ ፀጥ ፡ አደረግህላት ፡ (አርዓይከሙ) ፡ በወገ ኖችህ ፡ በምእመናን ፡ ጭንቅ ፡ ጭንቅ ፡ የሚሆን ፡ ጊዋዌ ፡ ነፍስን ፡ አመጣህበ ቸው ፡ (ወአስተይከነ) ፡ የሚያስደነግ ጥ ፡ መከራን ፡ አመጣህብን ፡ (ወወሀ ብኮሙ) ፡ ለሚፈሩህ ፡ ለሚያመልኩህ ፡ ለምእመናን ፡ ለሚጠተ ፡ ነፍስ ፡ ምል ክት ፡ የሚሆን ፡ የዲያብሎስን ፡ ድል ፡ መነሣት ፡ ሰጠኻቸው ፡ (ከመ ፡ ያም ስጡ ፡ ወይድኃኑ) ፡ የሚወድዱህ ፡ ምእመናን ፡ ከመከራ ፡ ነፍስ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ (ወወሀብከሙ) ፡ ለሚፈሩህ ፡ ለሚያመልኩህ ፡ ለበሕታ ውያን ፡ የተመውዖ ፡ አጋንንት ፡ ምል ክት ፡ የሚሆን ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ማመተ ብን ፡ ስመ ፡ ሥላሴን ፡ መጥራትን ፡ ሰጠኻቸው ፡ ከመ ፡ ያምሥጡ ፡ ወይ ድኃኑ ፡ ከፀብዓ ፡ አጋንንት ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ።

አድኅን ፡ በየማንከ ፡ ወስምዓኒ ፡

ልመናዬን ፡ ሰምተህ ፡ በሥልጣንህ ፡ አድነኝ ፡

፰፡ እግዚአብሔር ፡ ነበበ ፡ በመቅደሱ ፡

እንደ ፡ ዛሬ ፡ ሳይሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሁኖ ፡ እንድም ፡ በነ ቢይ ፡ አድሮ ፡ ለእመ ፡ ዓቀብከ ፡ እሬ ተከ ፡ ትበልዕ ፡ ከራሚ ፡ ከራሚከ ፡ ወይሰፍፍ ፡ ማኅበብተ ፡ ወይንከ ፡ ወት ሬኢ ፡ ውሉደ ፡ ውሉድከ ፡ እስከ ፡ ማልስ ፡ ወራብዕ ፡ ትውልድ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ ነበር ፡

እትረግሕ ፡ ወእትካፈል ፡ ምህርካ ፡

እኔም ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ምርኮውን ፡ እካ ፈል ፡ ነበር ፡

ወእማሬር ፡ አዕጻዳተ ፡ ቈላት ፡ መዝ ፡ ፶፱ ፡ ፮ ፡ ፯ ፡

የእሕዛብንም ፡ ቦታ ፡ ያጠረውን ፡ በድ ግር ፡ የረዘመውን ፡ በጠፍር ፡ እካፈል ፡ ነበር ፡ እንድም ፡ እንተ ፡ በዚህ ፡ ውጣ ፡ አንተ ፡ በዚህ ፡ ውረድ ፡ እያልኍ ፡ ጠ ፉን ፡ እየከፈልኍ ፡ እሰድደው ፡ ነበር ፡

፱፡ ዚአየ ፡ ውእቱ ፡ ገለዓድ ፡ ወዚአየ ፡ ምናሴ ፡

ነገደ ፡ ገለዓድ ፡ ነገደ ፡ ምናሴ ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡ ነበር ፡ እንድም ፡ ከነገደ ፡ ገለ ዓድ ፡ የተወለደ ፡ ዮፍታሔ ፡ ከነገደ ፡ ምናሴ ፡ የተወለደ ፡ ጌዴዎን ፡ የኔ ፡ ነበረ ፡ ዮፍታሔን ፡ ባባቱ ፡ ጌዴዎንን ፡ በእናቱ ፡ ተናገረ ፡

ወኤፍሬም ፡ ምስማከ ፡ ርእስየ ፡

ነገደ ፡ ኤፍሬም ፡ የራሴ ፡ መፀግያ ፡ ነበር ፡ እንድም ፡ ከነገደ ፡ ኤፍሬም ፡ የተወለደ ፡ ኢያሱ ፡ የራሴ ፡ መጠጊያ ፡ ነበር ፡

ወይሁዳ ፡ ንጉሥየ ፡

ነገደ ፡ ይሁዳ ፡ የኔ ፡ ወገን ፡ ነበር ፡ እን ድም ፡ ከነገደ ፡ ይሁዳ ፡ የተወለደ ፡ ጎቶንኤል ፡ የኔ ፡ ወገን ፡ ነበረ ፡

፲፡ ወሞዓብ ፡ ከህን ፡ ተስፋየ ፡

ልዑክየ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ካህን ፡ ሞዓ ብም ፡ አገልጋዬ ፡ ነበር ፡ እንድም ፡ ወካህን ፡ ሞዓብ ፡ ይነግር ፡ ተስፋየ ፡ ካህን ፡ ሞዓብ ፡ በልዓምም ፡ ኮከብ ፡ ይሠርቅ ፡ እምያዕቆብ ፡ ብሎ ፡ የኔን ፡ ተስፋ ፡ ይናገር ፡ ነበር ፡

ዲበ ፡ ኤዶምያስ ፡ እሰፍሕ ፡ መከየድየ ፡ ሕዝ ፡ ፳፭ ፡ ፲፫ ፡

በኤዶምያስ ፡ እግሬን ፡ እዘረጋ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ለኤዶምያስ ፡ ጦር ፡ እልሰለ ችም ፡ ስወጣ ፡ ስገባ ፡ የእግር ፡ ትቢያ ፡ ማራገፊያዬ ፡ የድካም ፡ ማረፊያዬ ፡ ነበረች ፡ ዳዊት ፡ እልፍ ፡ ከሁለት ፡ ሺህ ፡ ጦር ፡ ሠርቆበት ፡ ነበርና ፡

ሊተ ፡ ይገንዩ ፡ ኢሎፍሊ ፡

ኢሎፍላውያን ፡ ለኔ ፡ ይገዙ ፡ ነበር ፡ ሲቲ ፡ ጌታያዊ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ራሱን ፡ አድሮለት ፡ ነበርና ፡

፲፩ መኑ ፡ ይወስደኒ ፡ ሀገር ፡ ጥቅም ፡

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዲህ ፡ ነበር ፡ አሁ ን ፡ ግን ፡ ቅጥር ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ኢያሪኮ ፡ ማን ፡ በወሰደኝ ፡ ሀገረ ፡ ጥ ቅም ፡ ከልሁ ፡ ብሎ ፡ ኢያሪኮ ፡ ብኋል ፡ እንጂ ፡ ያምጣው ፡

መኑ ፡ ይመርሐኒ ፡ እስከ ፡ ኤዶምያስ ፡

አመጣው ፡ ወደ ፡ ኤዶምያስ ፡ ማን ፡ መርቶ ፡ በደረሰኝ ፡

፲፪ አኮኑ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ዘገደፍከነ ፡

በመከራው ፡ የጣልኸኝ ፡ አንተ ፡ አይ ደለህምን ፡ እንድም ፡ ቀድሞ ፡ እን ዲህ ፡ እንዲህ ፡ ታደርግ ፡ ነበር ፡ አል ኾ ፡ ዛሬሳ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ ዛሬስ ፡ በመከራው ፡ ጣልኸኝ ፡

ወኢትወፅእ ፡ እምላክነ ፡ ምስለ ፡ ኃይልነ ፡

ፈጣሪያችን ፡ ቀድሞ ፡ ከኃይላችን ፡ ከሠራዊታችን ፡ የማትለይ ፡ ነበር ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ከኃይላችን ፡ ከሠራዊታ ችን ፡ የማትወጣ ፡ ዘመቻ ፡ ፈሪ ፡ ሆንህ ፡ መዝ ፡ ፵፫ ፡ ፱ ፡

፲፭ ሀበነ ፡ ረድኤተ ፡ ለምንዳቤነ ፡

አሁንም ፡ በመከራችን ፡ ጊዜ ፡ መከራ ችንን ፡ ለማራቅ ፡ ረድኤትህን ፡ ስጠን ፡ ማለት ፡ እርዳን ፡

ወከንቱ ፡ ተአምኖ ፡ በሰብእ ፡

እኛም ፡ በሰጎል ፡ ንጉሥ ፡ ግብፅ ፡ መታ መን ፡ ከንቱ ፡ መሆኑን ፡ አውቀናል ፡ እርዱን ፡ እያሉ ፡ ያልኩ ፡ ነበርና ፡ እንድም ፡ በይሁዳ ፡ መቅብዩ ፡ መታ መን ፡ ከንቱ ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ፡ ይሂቸው ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ እሱ ፡ ወድ ቋልና ፡

፲፬፡ በእግዚአብሔር ፡ ንገብር ፡ ኃይለ ፡

በሰው ፡ መታመን ፡ ከንቱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምነን ፡ ኃይልን ፡ እናደርጋለን ፡ እንጂ ፡

ወውእቱ ፡ ያኀሥርሙ ፡ ለእለ ፡ ይገፉዑነ ፡

እሱም ፡ መከራ ፡ የሚያመጡብን ፡ አሕዛብን ፡ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ተደላ ደሉ ፡ እንደ ፡ ተቀማጠሉ ፡ አያስቀራ ቸውም ፡ ያጠፋቸዋል ፡

እንድም ፡ በዘርዓ ፡ ዳዊት ፡ ሥጋ ፡ ብቻ ፡ መታመን ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ (በእግዚአብ ሔር) ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ በተዋሐደው ፡ በሥጋው ፡ ቃል ፡ አምነን ፡ ኃይልን ፡ እናደርጋለን ፡ እንጂ ፡ (ውእቱ) ፡ እሱ ም ፡ ሥቃይ ፡ የሚያፀኑብን ፡ አጋንን ትን ፡ ያጠፋቸዋል ፡

## መዝሙር ፡ ፸፰ ፡

፩፡ ስምዓኒ ፡ እምላኪየ ፡ ስእለትየ ፡

ስለራሱ ፡ ተናግሮታል ፡ የተሩፋንም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ ፈጣሪዬ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ፡

ወአፅምዓኒ ፡ ጸሎትየ ፡

ልመናዬን ፡ ስማኝ ፡

፪፡ እምእፍናፈ ፡ ምድር ፡ ጸራሕኩ ፡ ኀቤከ ፡ ሶበ ፡ ተከበደኒ ፡ ልብየ ፡

ልመናዬ ፡ ተስፋ ፡ በቈረጠብኝ ፡ ጊዜ ፡

በጥልቅ ፡ ልቡናዬ ፡ እንድም ፡ የም
ድር ፡ ዳርቻ ፡ በምትሆን ፡ በባቢሎን፡
ሆኜ ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለመንኹ ።

ወእምዕብን ፡ አልዐልከኒ ።

ከአሕዛብ ፡ በላይ ፡ አደረግኸኝ ፡ አን
ድም ፡ ብዕለ ፡ አሕዛብን ፡ ሰጥተህ ፡ አ
ከበርከኝ ። እንድም ፡ በምስቱ ፡ በስድ
ስቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ እንዲሔድ ፡ አደ
ረግኸኝ ። እንድም ፡ በሁለቱ ፡ ጽላት ፡
ዕብን ፡ በተጻፉ ፡ ሕግጋት ፡ አፀናኸኝ ።

፫ ፡ ወመራህከኒ ፡ እስመ ፡ ተስፋየ ፡ ኮንከኒ ።

አለኝታዬ ፡ ሁነኸኛልና ፡ ከባቤሎን ፡
አውጥተህ ፡ እየመራህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፡ አገባኸኝ ።

ማኅፈድ ፡ ጽኑዕ ፡ ቅድመ ፡ ገጸ ፡ ፀላኢ ።

በጠላት ፡ ፊት ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ዕኑዕ ፡
ግምብ ፡ ነህ ፡ ያ ፡ ከቀን ፡ ወራሪ ፡ ከሌ
ሊት ፡ ሰባሪ ፡ ከተጣለ ፡ ጠጠር ፡ ከተ
ወረወረ ፡ ጦር ፡ እንድያድን ፡ ከመከ
ራ ፡ የምታድነኝ ።

፬ ፡ እንብር ፡ ቤተከ ፡ ለዓለም ።

በኢየሩሳሌም ፡ በቤትህ ፡ ለዘላለሙ ፡
ፀንቼ ፡ እኖራለሁ ።

ወእትከደን ፡ በጽላሎተ ፡ ክንፊከ ።

በክንፈ ፡ ረድኤትህም ፡ ተጠብቄ ፡ እ
ኖራለሁ ።

፭ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ አምላኪየ ፡ ሰማዕከኒ ፡ ጸሎትየ ።

አንተ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነህና ፡ ልመናዬን ፡
ሰማኸኝ ። እንድም ፡ አንተ ፡ ነህና ፡
(ወሰማዕከኒ) ፡ ልመናዬንም ፡ ሰምተ
ኸኛልና ፡ እነብር ፡ ቤተከ ።

ወወሀብኮሙ ፡ ርስተ ፡ ለእለ ፡ ይፈርሁከ ።

ለሚፈሩህ ፡ ለሚያመልኩህ ፡ ለትሩ
ፋን ፡ ርስታቸው ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ሰ
ጠኻቸው ።

፮ ፡ እምዕለት ፡ ዕለተ ፡ ይዌስክ ፡ ንጉሥ ፡ ዓመተ።

ዘሩባቤል ፡ ከቀን ፡ በቀን ፡ እውነት ፡
እየፈረደ ፡ እውነት ፡ እየተቸ ፡ ዘመ
ኑን ፡ ያበዛል ።

ወእስከ ፡ መዋዕለ ፡ ትውልደ ፡ ትውልድ ።

የልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ እስከ ፡ ማየት ፡
ደረሰ ፡ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ የዘሩባ
ቤል ፡ ዘመን ፡ ፵ዘጠኝ ፡ ነው ፡ የልጅ ፡
ልጅ ፡ ዓይቶ ፡ ሙቷል ።

፯ ፡ ወይነብር ፡ ለዓለም ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሐር ፡ ባለሟል ፡ በመሆን ።
እንድም ፡ በባለሟልነት ፡ ዘላለም ፡
ፀንቶ ፡ ይኖራል ።

መኑ ፡ የኀሥሥ ፡ ሣህሎ ፡ ወጽድቆ ።

የእግዚአብሐር ፡ ይቅርታው ፡ ቸርነ
ቱን ፡ የሚሻ ፡ ማነው ፡ እያለ ፡ የሰውን ፡
ልቡና ፡ ያነቃቃል ። እንድም ፡ እንደ ፡
ዘሩባቤል ፡ እውነት ፡ ፈርዶ ፡ እውነት ፡
ተችቶ ፡ ከቀን ፡ በቀን ፡ ዘመኑን ፡ አብ
ዝቶ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ዓይቶ ፡ የሚሞ
ት ፡ ማን ፡ ነው ።

፰ ፡ ከመዝ ፡ እዜምር ፡ ለስምከ ፡ ለዓለም ።

መኑ ፡ የኀሥሥ ፡ ሣህሎ ፡ ወጽድቆ ፡
እያልሁ ። እንድም ፡ እውነት ፡ ለሚ
ፈርድ ፡ ሰው ፡ ይቅርታ ፡ ቸርነት ፡ ማ
ድረግህና ፡ ለዘላለሙ ፡ በባለሟልነት ፡
ፀንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ማድረግህን ፡ እያ



ሰብኩ ፡ ለዘላለሙ ፡ ለስምህ ፡ ምስጋና ፡
አቀርብለታ ።

ከመ ፡ ተሀበኒ ፡ ተምኔትየ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ።

ተሀበኒ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ተምኔትየ ፡
ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ዘወትር ፡ የለመንኩ
ህን ፡ ዘወትር ፡ ታደርግልኝ ፡ ዘንድ ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ።

## መዝሙር ፡ ፺፩ ።

፩ ፡ እኮኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትገኒ ፡ ነፍስየ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ። ዕር
ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ። ዕር
ዓውያን ፡ ለሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ ሰገድ ፡
መሥዋዕት ፡ እሪያ ፡ ብላ ፡ ትሉኝማ ፡
ዘንድ ፡ ሰውነቴ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ትገዛ ፡ የለምን ፤ ትገዛለችና ።

እስመ ፡ ኀቤሁ ፡ መድኀኒትየ ።

ድኅነቴ ፡ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ የሚደረግልኝ ፡
የሚታዘዝልኝ ፡ ስለሆነ ።

፪ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ አምላኪየ ፡ ወመድኀኒየ ።

እሱ ፡ ድኅነቴን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ ፈ
ጣሪዬ ፡ ነውና ።

ወውእቱ ፡ ረዳእየ ፡ ወኢይትሐወክ ፡ ለዝሉፉ ።

ረዳቴ ፡ እሱ ፡ ስለሆነ ፡ እኔም ፡ ፈጽሜ ፡
በመከራው ፡ የማልታወክ ፡ ስለሆነ ፡
(እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ማንኛ) ፡ እንድም ፡
(አኮኑ) ፡ ሰውነቴ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
የምትገዛ ፡ ስለሆነ ፡ (እስመ) ፡ ድኅነቴ ፡
ከሱ ፡ ዘንድ ፡ ይታዘዝልኛልና ፡ (እስ
መ ፡ ውእቱ) ፡ ድኅነቴን ፡ የሚያደር
ግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነውና ፡ (ወውእቱ) ፡
እሱ ፡ ረዳቴ ፡ ነውና ፡ (ወይትሐወክ) ፡
እኔም ፡ በመከራው ፡ ፈጽሜ ፡ አልታ
ወክምና ።

፫ ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ትቀውሙ ፡ ላዕለ ፡ ብእሲ ።

ራሱን ፡ አርቆ ፡ ይናገራል ፡ ዕርዓውያ
ን ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ በመቃብያን ፡
በጸላትነት ፡ ትነሡባቸዋላችኁ ፡ መ
ቃብያንን ፡ ብእሲ ፡ አላቸው ፡ ካንድ ፡
ከመቃቢስ ፡ ስለተገኙ ።

ወትቀትልዎ ፡ ኵልክሙ ።

መላችሁ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ በሞት ፡ ታ
ፈርሷቸዋላችኁ ።

ከመ ፡ ዓረፍት ፡ ጽኑንት ፡ ወከመ ፡ ጥቅም ፡ ንዑል።

እንዳዘነበለ ፡ ግድግዳ ፡ (ዕንዕት) ፡ ይ
ላል ፡ አስቀድሚ ፡ ፀንታ ፡ ኋላ ፡ እንደ ፡
ፈረሰች ፡ ግድግዳ ፡ እንድም ፡ (ዕንጽ
ንት) ፡ ይላል ፡ እንደ ፡ ነቀዘ ፡ ግድግዳ ፡
እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ታፈርሷቸዋላ
ችሁ ፡ ቀተለና ፡ ነሠተ ፡ ይዋረሟሉ ፡
ነሠተ ፡ ብሎ ፡ ቀተለ ፡ ሲሆን ፡ ንሥት
ዎ ፡ ለገዘንቱ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወበው
ሉስ ፡ ዕለት ፡ አነሥእ ፡ ይላል ፡ ዮሐ፪፡፲፱።
ቀተለ ፡ ብሎ ፡ ነሠተ ፡ ሲሆን ፡ ቅትል
ዎ ፡ ለቤተ ፡ ምዐጋይ ፡ ወለቤተ ፡ ምክ
ራም ፡ ይላል ።

፱ ፡ ወባሕቱ ፡ መዝሩ ፡ ይደምሩ ፡ ከዐርየ ።

ባሕቱ ፡ ዋዌ ፡ ነው ፡ ከሃይማኖቴም ፡ ሊለዩኝ ፡ መከሩብኝ ፡ እንድም ፡ ከሃይማኖቴ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ነፍሴን ፡ ከሥጋዬ ፡ ሊለዩም ፡ መከሩ ፡ እንጂ ።

ወሮፅኩ ፡ በዕምዕየ ።

ኃጢአት ፡ ሳልሠራ ፡ ዕርዕ ፡ ወረድሁ ፡ እንድም ፡ ለሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ ሣልሠግድ ፡ መሥዋዕት ፡ እሪያ ፡ ሳልበላ ፡ ከዕርዕ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጣሁ ።

በአፉሆሙ ፡ ይድኅሩ ፡ ወበልቦሙ ፡ ይረግሙ ።

ሦስቱ ፡ ካህናት ፡ በፉቻቸው ፡ ይመርቃሉ ፡ ማለት ፡ እናንተ ፡ ከሁለት ፡ ሹመት ፡ አንዱን ፡ ብትነሡን ፡ እኛ ፡ በደለኛ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይክስ ፡ ብለን ፡ ዕርዕ ፡ እንጣያኮስን ፡ ያህል ፡ ንጉሥ ፡ በሃይማኖት ፡ ወልደን ፡ በምግባር ፡ አሳድገን ፡ መጣን ፡ ይላሉ ። (ወበልበሙ ፡ ይረግሙ) ፡ በልባቸው ፡ ግን ፡ ይረግሙ ፡ ማለት ፡ ቆይ ፡ እውነት ፡ መስሎህ ፡ የያዝንልህን ፡ ምን ፡ እውቀህ ፡ ይኸውም ፡ ሲያንስህ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። እንድም ፡ ዕርዓውያን ፡ በፉቻቸው ፡ ይመርቃሉ ፡ ማለት ፡ ለሥዕለ ፡ ኪሩብ ፡ እንሰግዳለን ፤ መሥዋዕት ፡ በግዕ ፡ እንሠዋለን ፡ እቤተ ፡ መቅደስ ፡ እናነጽፋለን ፡ እንጋርዳለን ፡ ይላሉ ። በልባቸው ፡ ግን ፡ ይረግማሉ ፡ ማለት ፡ ቆይ ፡ ለሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ ሳላሰግድህ ፡ መሥዋዕት ፡ እሪያ ፡ ሳላበላህ ፡ የቀረሁ ፡ እንደሆነ ፡ ሁን ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ፡ ይላሉ ።

ምላ ፡ ጽጹ፡ጽ፱ ። ኢሳ ፡ ፱፡፲፫ ። ኤር ፡ ፱ ፡ ፰ ።

፲ ፡ ወባሕቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትገኒ ፡ ነፍስየ ።

እንዲህማ ፡ ትጓት ፡ ዘንድ ፡ ነፍሴ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትገዛ ፡ የለምን ። እንድም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እንዳያገኛት ፡ ነፍሴ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትገዛለች ።

እስመ ፡ ኀቤሁ ፡ ተስፋየ ።

አለኝታዬ ፡ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ ይታዘዝልኛልና ።

፲፩ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ አምላኪየ ፡ ወመድኃኒየ ።

እሱ ፡ ድኅነትን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነውና ።

ወረዳእየ ፡ ውእቱ ፡ ወኢይትሐወስ ።

ረዳቴ ፡ እሱ ፡ ነውና ፡ እኔም ፡ በመከራው ፡ አልታወከምና ።

፲፪ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መድኃኒትየ ።

ድኅነቴ ፡ በሚሆን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምናለሁ ። እንድም ፡ ድኅነቴ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምኜ ፡ ይደረግልኛል ።

ወበእግዚአብሔር ፡ ክብርየ ።

ክብሬ ፡ በሚሆን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምናለሁ ። እንድም ፡ ክብሬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምኜ ፡ ይደረግልኛል ። እንድም ፡ አለኝታዬን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ረድኤትን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነው ።

አምላክየ ፡ ረድኤትየ ፡ ወተስፋየ ፡ እግዚአብሔር ።

ይኸውም ፡ ረድኤትን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ አለኝታዬን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

፲፫ ፡ ተመከሉ ፡ በቱ ፡ ኵልክሙ ፡ ማኅበረ ፡ አሕዛብ ።

እንጋዶ ፡ አሕዛብ ፡ ሲል ፡ ነው ። የአሕዛብ ፡ ወገኖች ፡ መላችሁ ፡ በሱ ፡ እምኑ ፡ ወንታችሁ ፡ ኑሩ ።

ወከዕዉ ፡ ልበክሙ ፡ ቅድሜሁ ።

ልመናችሁንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አቅርቡ ፡ እከዕዋ ፡ ለነፍስየ ፡ እንዲል ፡ እንድፋ ፡ አቀርባ ፡ ሲል ፡ ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ።

ወእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ረዳኢነ ።

ረዳታችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ።

ኢሳ ፡ ጽ፮ ፡ ፱ ።

፲፬ ፡ ወባሕቱ ፡ ከንቱ ፡ ኵሉ ፡ ደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ።

ነገር ፡ ግን ፡ የዕርዓውያን ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ናቸው ።

ሐሳውያን ፡ ደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይኄምዑ ፡ መዳልወ ።

ሐሰተኞች ፡ ናቸው ። (ወይዔምፁ) ፡ በሚዛንም ፡ ያብላሉ ። እንድም ፡ ሚዛንን ፡ የሚያሳብሉ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ። እንድም ፡ ሐሰተኞች ፡ የሚሆኑ ፡ እኒህ ፡ ሚዛንን ፡ የሚያሳብሉ ፡ በሚዛን ፡ የሚያብሉ ፡ እኒህ ፡ ሐሰተኞች ፡ ናቸው ። በታናሽ ፡ ሚዛን ፡ ሰጥተው ፡ በታላቅ ፡ ሚዛን ፡ ይቀበላሉና ። እንድም ፡ በታላቅ ፡ ተቀብለው ፡ በታናሽ ፡ ይሰጣሉና ። እንድም ፡ ሦስቱ ፡ ካህናት ፡ ሐሰተኞች ፡ ናቸው ። (ወይዔምፁ) ፡ ሕግ ፡ ያሳብላሉ ። በሕግ ፡ ያብላሉ ፡ ሕግን ፡ የሚያሳብሉ ፡ በሕግ ፡ የሚያብሉ ፡ ሦስቱ ፡ ካህናት ፡ ሐሰተኞች ፡ ናቸው ። ሚዛን ፡ ግራ ፡ ቀኙን ፡ እንዲያስተካክል ፡ አንድ ፡ እንዲያደርግ ፡ ሕግም ፡ ሕዝብና ፡ አሕዛብን ፡ ታስተካክላለች ፤ አንድ ፡ ታደርጋለችና ።

እመንቱሰ ፡ እምከንቱ ፡ ውስተ ፡ ከንቱ ፡ ኅቡረ ።

ዕርዓውያን ፡ ከከንቱ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ ከንቱ ፡ ጣዖት ፡ ይሔዳሉ ፡ ማለት ፡ ከንዱ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ጣዖት ፡ ይሔዳሉ ። ዛሬ ፡ በሀገራችን ፡ አላዋቂ ፡ ሰው ፡ ከዕገሌ ፡ ታቦት ፡ የዕገሌ ፡ ታቦት ፡ ከብት ፡ ያበዛል ፡ ልጅ ፡ ይሰጣል ፡ እያለ ፡ ከንዱ ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ታቦት ፡ እንዲሔድ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳ ።

፲፭ ፡ ኢትትአመኑ ፡ በዐመፃ ።

ጥበብን ፡ ተስፋ ፡ እንድታደርጓት ፡ ጥበብ ፡ ከበዛ ፡ ዘንድ ፡ ዓመፃ ፡ ያሠራልና ።

ወኢትትአመንዎ ፡ ለሐይድ ። ኤር ፡ ፳፩ ። ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፪ ።

ኃይልን ፡ እንዳትታመኑት ፡ ብንሮጥ ፡ እንቀድማለን ፡ ብንይዝ ፡ እናጠብቃለን ፡ ብንመታ ፡ እናደቃለን ፡ ብላችሁ ፡ በኃይላችሁ ፡ አትመኩ ። ኃይልን ፡ ቅምያ ፡ አለው ፡ ከመቀማት ፡ የሚደርስ ፡ ኃይል ፡ ከተሰማው ፡ ዘንድ ፡ ነውና ።

ብዕል ፡ ለእመ ፡ በዝኃ ፡ ኢታትልዉ ፡ ልበክሙ ።

ብዕል ፡ ሥጋ ፡ ከበዛልን ፡ ብላችሁ ፡ ልባችሁን ፡ እንዳታስታብዩ ። ማቴ ፡ ፮ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱ ፡ ፳፪ ። ማር ፡ ፲ ፡ ፳፱ ። ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፳ ። ፪ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፯ ።



2014 04 17

ምዕረ ፡ ነበበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዘንተ ፡ ዘመ ፡ ሰማዕኩ ።

እግዚአብሔር ፡ በሐና ፡ እመ ፡ ሳሙኤል ፡ አድሮ ፡ ኢይትመከህ ፡ ጠቢብ ፡ በጥበቡ ፡ ኢይትመከህ ፡ ኃያል ፡ በኃይሉ ፡ ኢይትመከህ ፡ ባዕል ፡ በብዕሉ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተናገረ ፡ እኔም ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡ ሰማሁ ።

እስመ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ግህል ።

ጥበብ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ፡ ኢትሰፈውዋ ፡ ለዓመፃ ፡ ላለው ።

፲፪ ፡ ወዚአከ ፡ እግዚኦ ፡ ኃይል ።

ወዚአሁ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ኃይልም ፡ የሱ ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ፡ ኢትትአመንዎ ፡ ለኃይድ ፡ ላለው ።

እስመ ፡ አንተ ፡ ትፈድዮ ፡ ለኵሉ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይፈድዮ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ለሁሉ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ይከፍለዋልና ፡ በሐና ፡ እመ ፡ ሳሙኤል ፡ አድሮ ፡ ኢይትመከሕ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተናገረ ። ብዕል ፡ ለእመ ፡ በዝኃ ፡ ላለው ። አንድም ፡ አቅርበህ ፡ አቤቱ ፡ ኃይል ፡ ያንተ ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ፡ አንተ ፡ ለሁሉ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ትከፍለዋለህ ፡ ሚሬ ፡ ፴፪ ፡ ፳፱ ። ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፩ ። ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፲ ። ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፳፯ ። ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፳፱ ። ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፮ ። ፩ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲ ። ራእ ፡ ፳፪ ፡ ፲፪ ። ዳን ፡ ፲፪ ፡ ፪ ።

# መዝሙር ፡ ፷፪ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ አምላኪየ ፡ እገይስ ፡ ኀቤከ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ። የምእመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ፤ ፈጣሪዬ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ሰበ ፡ ዘመን ፡ በጸሎት ፡ በቀኖና ፡ ወዳንተ ፡ እማልዳለሁ ፡ (እገሰግሣለሁ) ።

ጸምአት ፡ ነፍስየ ፡ ለከ ።

ሰውነቴ ፡ አንተን ፡ ናፍቃለችና ። ኢሳ ፡ ፳፮ ፡ ፱ ።

እፎ ፡ እስፋሕ ፡ ለከ ፡ ሥጋየ ።

አምላኪዬ ፡ አምላኪዬ ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ መሥዋዕት ፡ መሠዋዕትን ፡ አለ ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ እንደምን ፡ መሥዋዕቱን ፡ ልሠዋልህ ፡ የበሉት ፡ የጠጡት ፡ ከሥጋ ፡ ይዋሀዳል ፡ መሥዋዕቱን ፡ ሥጋየ ፡ አለው ።

በምድረ ፡ በድው ፡ ኀበ ፡ አልቦ ፡ ዕፅ ፡ ወማይ ።

ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሌለበት ፡ በባቢሎን ፡ ዕፅ ፡ አውባን ፡ ቅጠል ፡ ወማይ ፡ ማየ ፡ ምንዛህ ፡ በሌለበት ። አንውም ፡ ዕፅ ፡ ኢታምልክ ፡ ወማይ ፡ ዘጠኙ ፡ ሕገጋት ። እንድም ፡ ዕፅ ፡ ዓሠርቱ ፡ ቃላት ፡ ወማይ ፡ ወንበቦ ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ በሌለበት ፡ በባቢሎን ፡ እንደምን ፡ ልሠዋልህ ።

፪ ፡ ከመዝ ፡ በመቅደስከ ፡ አስተርአይኩከ ።

እንዲህስ ፡ ጊዜው ፡ ደርሶ ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥቼ ፡ ቢሆን ፡ በቤተ ፡ መቅደስህ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠውቼ ፡ በተገለጽኹልህ ። አንድም ፡ ከመ ፡ ዘበመቅደስከ ፡ ይላል ፡ ቀድሞ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሳለሁ ፡ ዕሠዋልህ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ዛሬም ፡ መሥዋዕት ፡ ሠውቼ ፡ በተገለጽኹልህ ፡ ነበር ።

ወከመ ፡ አእምር ፡ ኀይለከ ፡ ወስብሐቲከ ።

ከሃሊነትህን ፡ ጌትነትህን ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡ እንገይስ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ይኄይስ ፡ እምሕይው ፡ ሣህልከ ። ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፫ ፡ ፰ ።

በባቢሎን ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከመኖር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገብቶ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አድሮ ፡ መሞት ፡ ይሻላልና ።

አንድም ፡ (አምላኪየ ፡ አምላኪየ) ፡ ፈጣሪዬ ፡ ፈጣሪዬ ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በጸሎት ፡ በቀኖና ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ እማልዳለሁ ፡ (እገሰግሣለሁ) ፡ (ፀምዐት) ፡ ነፍሴ ፡ አንተን ፡ ናፍቃለችና ። (እፎ) ፡ አምላኪየ ፡ አምላኪየ ፡ የምትል ፡ ተሰቀል ፡ ልኝ ፡ ማለትህ ፡ አይደለምን ፤ ይህንማ ፡ ትለኝ ፡ ዘንድ ፡ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ እንደምን ፡ ልሰቀልልህ ፡ እስፋህ ፡ አለ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ነውና ፡ የሚሰቀል ። (በምድረ ፡ በድው) ፡ ልጅነት ፡ በሌለበት ፡ ዘመን ፡ መስቀል ፡ የሚተከልበት ፡ ማየ ፡ ገቦ ፡ የሚፈስስበት ፡ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ (ከመዝ) ፡ እንዲህስ ፡ ጊዜው ፡ ደርሶ ፡ ቢሆን ፡ በተሰቀልኩልህ ፡ ነበር ፡ (ከመ ፡ ዘበመቅደስከ) ፡ ቀድሞ ፡ ለኤርምያስ ፡ ተሰቅዬ ፡ እንደ ፡ ተገለጽኹለት ፡ በተገለጽኹለህ ፡ ነበር ። ኤርምያስ ፡ የቤተ ፡ መቅደስን ፡ መፍረስ ፡ እያየ ፡ ሲያለቅስ ፡ ዓይኑ ፡ ጠፍቷል ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ተደጥ ፡ መጥቶበታል ፡ ወሮድዎ ፡ እርዳኢሁ ፡ ከመ ፡ ይቅብርዎ ፡ ይላል ፡ የሞተ ፡ መስሏቸው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሊቀብሩት ፡ ቀረቡ ፡ መልአኩ ፡ መጥቶ ፡ ዑቁ ፡ ኢትቅብርዎ ፡ ለኤርምያስ ፡ ሀለወት ፡ ነፍሱ ፡ በላዕሌሁ ፡ አላቸው ፡ ተነሥቶ ፡ የሥጋዌ ፡ ነገር ፡ ተገልጾለት ፡ ለሊሁ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ አምላክ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ይመጽእ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወየኀሪ ፡ ዓሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ሐዋርያተ ፡ ወይከይድ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ዘአነ ፡ ርኢኩ ፡ ሥግወ ፡ ብሏል ። (ወከመ ፡ አእምር ፡ ኀይለከ) ፡ ከሃሊነትህን ፡ ጌትነትህን ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡ (እስመ ፡ ይኄይስ) ፡ ከሕይወትህ ፡ ሞትህ ፡ ይሻለኛልና ፤ ወይጠይቁ ፡ ጠቢባን ፡ ሣህሎ ፡ እምዘ ፡ ወሀብከዎሙ ፡ አነ ፡ እንዲል ።

ከናፍርየ ፡ ይሴብሓከ ።

አንደበቶቼ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ያመሰግኑሃል ።

፬ ፡ ከመዝ ፡ እባርከከ ፡ በሕይወትየ ።

ባለ ፡ ዘመኔ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ አመሰግንሃለሁ ።

ወበስመ ፡ ዚአከ ፡ እነሥእ ፡ እደውየ ።

በስምህ ፡ አምኜ ፡ እደ ፡ ቃሌን ፡ ለጸሎት ፡ እደ ፡ ሥጋዬን ፡ ለመሥዋዕት ፡ ለምጽዋት ፡ እደ ፡ ልቡናዬን ፡ ለአንክሮ ፡ ለተዘክሮ ፡ አነሣለሁ ።

፩ ፡ ከመ ፡ ዘእምሥቡሕ ፡ ወእምሥንንቱ ፡ ጽገብት ፡ ነፍስየ ።

ስቡን ፡ በልቶ ፡ ቅልጥሙን ፡ ጠጥቶ ፡ ደስ ፡ ከሚለው ፡ ሰው ፡ ይልቅ ። አንድም ፡ ያፈራውን ፡ የተፈተገውን ፡ ስንዴ ፡ አንድም ፡ አንጉዳ ፡ ለምድር ፡ ይላል ፡ ከምድር ፡ የተገኘውን ፡ በልቶ ፡ ደስ ፡ ከሚለው ፡ ሰው ፡ ይልቅ ።

ከናፍርየ ፡ ፍሡሓት ፡ ይሴብሓ ፡ ለስምከ ።

ደስ ፡ ያላቸው ፡ አንደበቶቼ ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ ያቀርባሉ ፡ ስምህን ፡ ያመሰግናሉ ።

፯ ፡ ወበምስካብየኒ ፡ እዜከረከ ።

ሌሊት ፡ በመኝታዬ ፡ አመሰግንሃለሁ ።

ወበጽባሕ ፡ አነብብ ፡ ለከ ፡ እስመ ፡ ኮንከኒ ፡ ረዳእየ ።

ረዳት ፡ ሁነኸኛልና ፡ በቀን ፡ አመሰግንሃለሁ ። አንድም ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ አመሰግንሃለኊ ፡ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ አመሰግንሃለኊ ።

፯ ፡ ወእትዌከል ፡ በጽላሎተ ፡ ክነፊከ ።

በክንፈ ፡ ረድኤትህም ፡ አምናለሁ ፡ እጠጋለሁ ።

፰ ፡ ተለወት ፡ ነፍስየ ፡ ድኅሬከ ።

ኪያከ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ሰውነቴ ፡ አንተን ፡ ናፈቀች ።

ሊተሰ ፡ ተወክፈተኒ ፡ የማንከ ።

የሚቀድመው ፡ አለ ።

፱ ፡ እሙንቱሰ ፡ ለከንቱ ፡ ኀሠሥዋ ፡ ለነፍስየ ።

ባቢሎናውያን ፡ ሰውነቴን ፡ ለሞት ፡ ለጥፋት ፡ ሺቶት ፡ ነበር ፡ ሥልጣንህ ፡ ግን ፡ በረድኤት ፡ ተቀበለችኝ ።

ለይባኡ ፡ ውስተ ፡ መዓምቅቲሃ ፡ ለምድር ።

አሁን ፡ እኔ ፡ ምን ፡ እላለሁ ፡ ሞት ፡ ገድሎ ፡ ገድሎ ፡ ወደሚያወርድበት ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ይውረዱ ።

፲ ፡ ወይትገብኡ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ሰይፍ ።

ውስተ ፡ ሰይፈ ፡ እድ ፡ ሲል ፡ ነው ። በሰው ፡ እጅ ፡ በተያዘ ፡ ሰይፍ ፡ ይሙቱ ።

ክፍለ ፡ ቈናጽል ፡ ለይኩኑ ።

የሚቀብራቸው ፡ አጥተው ፡ የአራዊት ፡ ምግብ ፡ ይሁኑ ። አንድም ፡ በሰይፍ ፡ እንደበት ፡ ይሙቱ ።

፲፩ ፡ ንጉሥሰ ፡ ይትፌሣሕ ፡ በእግዚአብሔር ።

ዘሩባቤል ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምኖ ፡ በተሠራለት ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

ወይከብር ፡ ኵሉ ፡ ዘይምሕል ፡ ቦቱ ።

በረከተ ፡ ዘሩባቤልን ፡ የሚል ፡ ሁሉ ፡ ክብር ፡ ገንኖ ፡ ይኖራል ። በረከተ ፡ ፋሲልን ፡ በረከተ ፡ ኢያሱን ፡ እንዲል ።

እስመ ፡ ይትፈጸም ፡ አፉ ፡ ዘይነብብ ፡ ዓመፃ ።

ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ትፋታን ፡ እንገዛቸዋለን ፡ የሚል ፡ የባቢሎናውያን ፡ አንደበት ፡ ምላሽ ፡ ያጣልና ። ሕዝ ፡ ፲፪ ፡ ፳፫ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ። ገላ ፡ ፫ ፡ ፳፪ ።



## መዝሙር ፡ ፷፫ ።



፩ ፡ ስምዐኒ ፡ እግዚኦ ፡ ጸሎትየ ፡ ዘበእለክኩ ፡ ኀቤከ ።

በሰአል ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግሮታል ። አቤቱ ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ የለመንሁትን ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

እምግርማሁ ፡ ለጸላኢ ፡ አድኅና ፡ ለነፍስየ ።

ከሳኦልም ፡ መጠራጠር ፡ መተሳሰብ ፡ ሰውነቴን ፡ አድናት ፡ ሳኦል ፡ አገኘው ፡ ይሆን ፡ አጣው ፡ እያለ ፡ ይጠራጠራል ፡ ያስበልና ፡ ዳዊት ፡ ያገኘኝ ፡ ይሆን ፡ አምልጠው ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ ይጠራጠራል ፡ ያስባልና ።

፪ ፡ ወሠውረኒ ፡ እምዐሊቶሙ ፡ ለእኩያን ።

ከሳኦል ፡ ከክፉ ፡ ሥራቸው ፡ አድነኝ ።

ወእምብዝኆሙ ፡ ለገበርተ ፡ ዓመፃ ።

ወእምብዙኃን ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ብዙ ፡ ከሚሆኑ ፡ ዓመፅን ፡ ከሚሠሩ ፡ ከነሳኦል ፡ አድነኝ ።

፫ ፡ እለ ፡ አብልሑ ፡ ልሳናቲሆሙ ፡ ከመ ፡ አርዌ ፡ ምድር ።

አንደበታቸውን ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ መርዝ ፡ ከሚያፋጥኑ ፡ ያ ፡ መርዝ ፡ ሲቀባም ፡ ሲገድልም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እነሱም ፡ ሲመክሩም ፡ ሲገድሉም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነውና ።

ወወሰቁ ፡ ቀስቶሙ ፡ ለገቢረ ፡ መሪር ።

ክፉ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ቀስታቸውን ፡ ቀፈፉ ፡ ማለት ፡ ምክራቸውን ፡ መከሩ ፡

፬ ፡ ከመ ፡ ይትኳሐዎ ፡ በኅቡእ ፡ ለንጹሕ ።

ዳዊትን ፡ ተሠውረው ፡ ያጠፉት ፡ ዘንድ ።

ግብተ ፡ ይንድፍዎ ፡ ወኢይፈርሁ ።

ፍትሐ ፡ ርትዕ ፡ ሥላሴ ፡ ድንገት ፡ መከራ ፡ ያመጡባቸዋል ፡ ይህ ፡ ሊደረግ ፡ ባቸው ፡ አልፈሩም ፡ ግብተ ፡ በነሳኦል ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሥላሴስ ፡ አውቀው ፡ ነው ፡ መከራ ፡ የሚያመጡባቸው ። አንድም ፡ እለ ፡ ዳዊት ፡ ድንገት ፡ አደጋ ፡ ይጥሉባቸዋል ። ይህ ፡ ሊደረግባቸው ፡ አልፈሩም ፡ አሁን ፡ የተመቸ ፡ ይንድፍዎሙ ፡ አለ ፡ ንጉሥ ፡ ዊ ፡ አነጋገር ።

፭ ፡ ወአጽንዑ ፡ ሎሙ ፡ ነገረ ፡ እኩየ ።

የሚረቡቸው ፡ የሚጠቅማቸው ፡ መስሏቸው ፡ የማይረባቸው ፡ የማይጠቅማቸውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አፀኑባቸው ።

ወተማከሩ ፡ ይሕባኡ ፡ ሎሙ ፡ መሥገርተ ።

ጦር ፡ ይሸምቁባቸው ፡ ዘንድ ፡ መከሩባቸው ።

ወይቤሉ ፡ አልቦ ፡ ዘይሬእየነ ።

እረ ፡ ተዉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያይባችኋል ፡ ይሰማባችኋል ፡ ቢሏቸው ፡ የሚያይብን ፡ የሚሰማብን ፡ የለም ፡ አሉ ።

፮ ፡ ወኀሠሡ ፡ ለዓመፃ ።

ዓመፅን ፡ ይህቺ ፡ ቀረች ፡ እያሉ ፡ ንቅስ ፡ እያደረጉ ፡ ሠሯት ።

ወሐለቁ ፡ እንዘ ፡ ይፈትኑ ፡ ወይፄሩ ።

ሲያንፁ ፡ ሲያፈርሱ ፡ ሲጥሉ ፡ ሲያነሱ ፡ አለቁ ።

፮ ፡ ወይበውዕ ፡ ሰብእ ፡ በልብ ፡ ዕሙቅ ።

አጅሬ ፡ ሳኦል ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ ገብቶ ፡ አውቃለሁ ፡ ይላል ፡ ዳዊት ፡ እንጂ ፡ ቢያገኘኝ ፡ ይገድለኝ ፡ ነበር ፡ አይተወኝም ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ ገብቶ ፡ አውቃለሁ ፡ ማለት ፡ ነውና ።

ወይትሌዓል ፡ እግዚአብሔር ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ የሚሉትን ፡ አውቆ ፡ ልዕልናውን ፡ በመግለጽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይበልጣል ፡ አንድም ፡ (ወይበውዕ ፡ ሰብእ) ፡ ሰው ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ ገብቶ ፡ ያውቃል ፡ ዳዊት ፡ በኢዮአብ ፡ ኢዮአብ ፡ በዳዊት ፡ ሳኦል ፡ በአበኔር ፡ አበኔር ፡ በሳኦል ፡ ልቡና ፡ ያለውን ፡ እንዳወቀ ፡ ዳዊት ፡ በኢዮአብ ፡ ልቡና ፡ ያለውን ፡ አውቆ ፡ ሀሎኑ ፡ እዴሁ ፡ ለኢዮአብ ፡ በገዝ ፡ ነገርኪ ፡ እንዳለ ፡ ኢዮአብ ፡ በዳዊት ፡ ልቡና ፡ ያለውን ፡ አውቆ ፡ ሔደሀ ፡ አሽከሮችሀ ፡ አለቁ ፡ በለው ፡ ይቆጣል ፡ እርዮ ፡ ባሪያህም ፡ እንጂ ፡ ሞተ ፡ በለው ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ እንዳለ ፡ አበኔር ፡ በሳኦል ፡ ልቡና ፡ ያለውን ፡ አውቆ ፡ ዳዊትን ፡ ዝኩ ፡ ወልደ ፡ መኑ ፡ ቢለው ፡ እንደ ፡ ተጣላው ፡ አውቆ ፡ እንሰ ፡ ኢየአምሮ ፡ እግዚእየ ፡ እንዳለው ፡ (ወይትሌዓል) ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ በእውቀት ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጣል ።

፯ ፡ ከመ ፡ ሐንፃ ፡ ደቂቅ ፡ ኮነ ፡ መቅሠፍቶሙ ።

በሰው ፡ የሚያመጡት ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ ሕፃናት ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ሕፃናት ፡ ቤት ፡ ሲሠሩ ፡ ውለው ፡ ማታ ፡ አፍርሰውት ፡ ይሔዳሉ ፡ እነሱም ፡ በምክራቸው ፡ ሰውን ፡ አልጐዱበትምና ፡ አንድም ፡ በራሳቸው ፡ የሚያመጡት ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ ሕፃናት ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ሕፃናት ፡ ቤት ፡ ሠርተው ፡ ይገቡበታል ፡ በላያቸው ፡ ይወድቃል ፡ ይፈርሳል ፡ እነሱም ፡ በመከሩት ፡ ምክር ፡ ጠፍተዋልና ፡ አንድም ፡ ከመ ፡ ሐፀ ፡ ደቂቅ ፡ ይላል ፡ ሕፃናት ፡ እንቧጮውን ፡ ቈርጠው ፡ ልጡን ፡ ልጠው ፡ ወትሮ ፡ እንጨቱን ፡ ደጋን ፡ አድርገው ፡ የዶሮ ፡ ላባ ፡ ይሰዱበታል ፡ ግንባር ፡ አይበጣም ፡ ደም ፡ አያወጣም ፡ እነሱም ፡ በሰው ፡ የሚያመጡት ፡ መከራ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ በራሳቸው ፡ የሚያመጡት ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ አርበኛ ፡ ቀስት ፡ ነው ፡ ለይትነሥኡ ፡ ደቅነ ፡ ወይትዋነዩ ፡ በቅድሜነ ፡ እንዲል ፡ ያ ፡ አላዋቂ ፡ የሰደደው ፡ እንደሆነ ፡ ተመልሶ ፡ ይገድለዋል ፡ እነሱም ፡ በመከሩት ፡ ምክር ፡ ጠፍተዋልና ፡ አንድም ፡ ከመ ፡ ወግረ ፡ ደቂቅ ፡ ይላል ፡ እንደ ፡ ጥቅመ ፡ ሰናዖር ፡ እንደ ፡ ሐራ ፡ ጸራግሞን ፡ ነው ፡ አንድም ፡ የለንስጥሮስ ፡ በሕላቸው ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ ሥራ ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ፶፮ ፡ ፩ ።



፰ ፡ ወደከመ ፡ ልሳኖሙ ፡ በላዕሌሆሙ ።

በሰውነታቸው ፡ ያለ ፡ ሥልጣናቸው ፡ እንደበታቸው ፡ ደከመ ፡ አንድም ፡ የለንስጥሮስ ፡ ባህላቸው ፡ ጠፋባቸው ፡ አንድም ፡ እንደበታቸው ፡ ሥልጣናቸው ፡ ጠፋ ፡ ማለት ፡ ምክር ፡ ተሣናቸው ፡ ንስጥሮስ ፡ ተረትቶ ፡ ተወግዞ ፡ ተሰድዶ ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ሳለ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ተከትሎ ፡ ሔደ ፡ እመቤታችንንም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ በላት ፡ እሱንም ፡ አምላክ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ብለህ ፡ እመንበት ፡ እኔ ፡ የጎዳሁህ ፡ ልሁን ፡ አለው ፡ እኔስ ፡ ባህሌ ፡ ተስማምቶኛል ፡ አይሆንም ፡ አለው ፡ ለኔ ፡ እንዳልታዘዝህ ፡ ላንተም ፡ አንደበትህ ፡ አይታዘዝልህ ፡ ብሎ ፡ ረገመው ፡ መላሱ ፡ ተጐልጕሎ ፡ ወጥቶ ፡ እንደ ፡ ሴት ፡ ጡት ፡ ከደረቱ ፡ ወድቆ ፡ እእምሮውን ፡ አጥቶ ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ሐገዝ ፡ ሐገዝ ፡ እያለ ፡ ሞቷል ፡ ወሞተ ፡ እንዘ ፡ ይነብሕ ፡ ከመ ፡ ከልብ ፡ እንዲል ።

ወደንገጹ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ርእዮሙ ።

እለ ፡ ሳኦልን ፡ አንድም ፡ እለ ፡ ንስጥሮስን ፡ ያዩ ፡ ሁሉ ፡ የአንክሮ ፡ ድንጋጤ ፡ ደነገፁ ።

፱ ፡ ወፈርሀ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ ፈራ ።

ወነገሩ ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ነገሩ ፡ አስተማሩ ።

ወአእመሩ ፡ ምግባሮ ።

ሥራውን ፡ አወቁ ።

፲ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ጻድቅ ፡ በእግዚአብሔር ።

ዳዊት ፡ አንድም ፡ ቄርሎስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምኖ ፡ በተሠራለት ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

ወይትዌከሉ ፡ በቱ ።

በሱም ፡ ያምናሉ ።

ወይከብሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ርቱዓነ ፡ ልብ ።

ወይከብሩ ፡ ርቱዓነ ፡ ልብ ፡ እለ ፡ ይትዌከሉ ፡ በቱ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ትሑት ፡ ሰብእና ፡ ያላቸው ፡ በሱ ፡ ያመኑ ፡ የዳዊት ፡ ወገኖች ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሠራዊት ፡ አንድም ፡ የቄርሎስ ፡ ወገኖች ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ከብረው ፡ ገንነው ፡ ይኖራሉ ።

## መዝሙር ፡ ፷፬ ።

፩ ፡ ለከ ፡ ይደሉ ፡ እግዚኦ ፡ ስብሐት ፡ በጽዮን ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ የምእመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ ታሪኩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ በምልዓ ፡ ካለው ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። አቤቱ ፡ ቀድሞ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በከተማው ፡ ላንት ፡ ምስጋና ፡ ይገባ ፡ ነበር ።

ወበኢየሩሳሌም፡ይትፌኖ፡ጸሎት፡በኢየሩሳሌም።

በኢየሩሳሌምም፡በመላዋ፡ጸሎት፡ላንተ፡ይቀርብ፡ነበር።

፪፤ ስማዕ፡ጸሎትየ፡ዘትሰምዕ፡ዘሥጋ፡ዘመጽአ፡ኀቤከ።

ዛሬም፡ወዳንተ፡የቀረበ፡በአንተ፡ያመነ፡የትሩፍን፡ጸሎት፡ስማ፤አንድም፡ሥጋዊ፡ደማዊ፡ትሩፍ፡ወዳንተ፡ያቀረበውን፡ጸሎት፡ስማ።

፫፤ ነገረ፡ኃጥኣን፡ኃየለነ።

የባቢሎናውያን፡ነገር፡በረታብን።

ወኃጢአተነሰ፡አንተ፡ትሠሪ፡ለነ።

ጥቃቅኑን፡ኃጢአታችንን፡በጥቃቅኑ፡ጸሎታችን፡ይቅር፡ብለኸን፡ነበር፤ታላላቁን፡ኃጢአታችን፡በታላላቁ፡ጸሎታችን፡ይቅር፡እንድትለን፡የባቢሎናውያን፡ነገር፡በረታብን፡አንሰድም፡አሉ፡በሰባ፡ዘመን፡አትወጡም፡ከሰባ፡ዘመን፡አትርፈን፡እንገዛችኋለን፡እያሉ፡ነው።

፬። ብፁዕ፡ዘኃረይኮ፡ወዘተወከፍኮ።

በሃይማኖት፡የመረጥኸው፡በረድኤት፡የተቀበልከው፡ትሩፍ፡ንፁድ፡ክቡር፡ነው፡አንድም፡በሃይማኖት፡የመረጥኸው፡በልጅነት፡የተቀበልከው፡ምእመን፡ንፁድ፡ክቡር፡ነው።

ወዘአኅደርኮ፡ውስተ፡አዕፃዲከ።

በኢየሩሳሌም፡በቤተ፡መቅደስ፡ያኖርኸው፡ትሩፍ፤አንድም፡በገነት፡በመንግሥት፡ለማያት፡ያኖርኸው፡ምእመን፡ንፁድ፡ክቡር፡ነው።

ጸገብነ፡እግዚኦ፡እምበረከተ፡ቤትከ።

በረከተ፡እምቤትከ፡ሲል፡ነው፡አቤቱ፡ከቤተ፡መቅደስ፡የተገኘውን፡ተረፈ፡መሥዋዕቱን፡በሎቱን፡በኩራቱን፡ቀዳምያቱን፡አገኘተን፡ደስ፡አለን፤አንድም፡ከቤተ፡ክርስቲያን፡የተገኘውን፡ሥጋውን፡ደሙን፡ተቀብለን፡ልጅነትን፡አግኝተን፡ደስ፡አለን።

፭፤ ቅዱስ፡ጽርሕከ፡ወመንክር፡በጽድቅ።

ቤተ፡መቅደስ፡ድንቅ፡ነው፡ወመንክር፡በጽድቅ፡የሐሰት፡ድንቅ፡አለና፡ከዚያ፡ሲለይ፡በውነት፡ድንቅ፡ነው፡አለ፤ሱሳን፡ወርድ፡ይስሉበታል፡ሐረግ፡ይስቡበታል፡ዛፍ፡ይቀርፁበታልና፤አንድም፡ወመንክር፡ይትገበር፡ውስቴቱ፡ይላል፡በውስጡ፡ድንቅ፡ተአምራት፡ይደረግበታል፡ከምስአል፡ከአዕናቍ፡ድምፅ፡ሰምተው፡ይወጣሉና፤አንድም፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ክቡር፡ነው፡ወመንክር፡በውነት፡ድንቅ፡ነው፤አንድም፡ወመንክር፡ይትገበር፡በውስጡ፡ድንቅ፡ተአምራት፡ይደረግበታል፡ኅብስቱ፡ተለውጦ፡ሥጋ፡መለኮት፡ወይኑ፡ተለውጦ፡ደመ፡መለኮት፡ይሆንበታልና።

ስምዐነ፡አምላክነ፡ወመድኃኒነ።

ድኅነታችን፡የምታደርግልን፡ፈጣሪያችን፡ልመናችንን፡ስማን።





ተስፋሆሙ፡ለኵሎሙ፡አጽናፈ፡ምድር።

ጽንፈ፡ምድር፡በምትሆን፡በባቢሎን፡ላሉ፡ለሁለቱ፡ነገድ፡አለኝታቸው፡ተስፋቸው፡የምትሆን።

ወለእለሂ፡ውስተ፡ባሕር፡ርኁቅ።

ይልቁንም፡በቄላት፡ጎዘር፡ላሉ፡ለአሥሩ፡ነገድ፡አለኝታቸው፡የምትሆን፡አንድም፡ተስፋሆሙ፡በሐልዮ፡ፍዳ፡ለተያዙት፡አለኝታቸው፡የምትሆን፡(ወለእለሂ)፡ይልቁንም፡በነቢብ፡በገቢር፡ፍዳ፡ለተያዙት፡አለኝታቸው፡የምትሆን፡አቤቱ፡ልመናችንን፡ስማን።

፮፤ አጽናዕኮሙ፡ለአድባር፡በኃይልከ።

ፈርዖንን፡እንዲሰጥም፡ያደረግኸው፡አቤቱ፡ቀርዱን፡አራራትን፡በከሃሊነትህ፡አጸናኻቸው።

ወቅኑታን፡እሙንቱ፡በኃይል።

ቀርዱ፡አራራትም፡ኀይልን፡እንደ፡ዝናር፡የታጠቁ፡ናቸው፡ፀንተው፡መኖራቸውን፡መናገር፡ነው።

፯፤ ዘየሐውኮ፡ለእንበሬ፡ባሕር፡ኢላ፡ጽጽ፡ጸ፩።

ብሔሞትን፡በውቅያኖስ፡የወሰንክ፡አንተ፡ነህ፡ብሔሞትማ፡የሚኖረው፡በየብስ፡አይደለምን፡ቢሉ፡ሌዋታንን፡ሲያይ።

ወመኑ፡ይትቃወሞ፡ለድምፀ፡ማዕበሉ።

አንተ፡እስከ፡ዝየ፡ብጽሒ፡ወኢትትዓደዊ፡እምወሰንኪ፡አላ፡ይትከወሥ፡ማዕበልኪ፡በውስቴትኪ፡ብለህ፡ባትወስነው፡የውቅያኖስን፡ማዕበል፡ሞገድ፡ማን፡በተቃወመው፡ነበር፡ማቴ፡፰፡፳፯።

፰፤ ይደነግጹ፡አሕዛብ፡ወይፈርሁ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡አጽናፍ፡እምተአምራቲከ።

አሕዛብ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡አጽናፍ፡ይደነግጹ፡ወይፈርሁ፡እምተአምሪከ፡ብለህ፡ግጠም።በጽንፈ፡ምድር፡የሚኖሩ፡አሕዛብ፡ከሥነ፡ፍጥረትህ፡የተነሣ፡የሞት፡ድንጋጤ፡ይደነግጣሉ፡ይፈራሉ፡የሚያስደነግጥ፡ሥነ፡ፍጥረት፡አለና፤አንድም፡ከረምትና፡በጋ፡ሌሊትና፡መዓልት፡ከመፈራረቁ፡የተነሣ፡ብርሃናትን፡ማመላለሱን፡ነፋሳትን፡ማንፈሱን፡ሲያይ፡እንዲህ፡አለ፤አንድም፡(አጽናእከሙ)፡ሙሴ፡አሮንን፡በከሃሊነትህ፡አጸናኻቸው፡(ወቅኑታን)፡ሙሴ፡አሮን፡ኃይልን፡እንደ፡ዝናር፡የታጠቁ፡ናቸው፡(ዘየሀውኮ)፡ፈርዖንን፡በኤርትራ፡ሰጥሞ፡እንዲቀር፡ያደረግህ፡አንተ፡ነህ፡(ወመኑ)፡አንተ፡ከሁለት፡ከሦስት፡ከፍለህ፡ፀጥ፡ባታደርገው፡የኤርትራን፡ማዕበል፡ሞገዷን፡ማን፡በተቃወመው፡ነበር፡(ይደነግጹ፡እለ፡ይነብሩ)፡በጽንፈ፡ኤርትራ፡የሚኖሩ፡አሕዛብ፡ፈርዖንን፡አስጥመህ፡እስራኤልን፡አድነኸ፡ካደረግኸው፡ተአምራት፡የተነሣ፡ይደነግጻሉ፡ይፈራሉ።

እንድም ፡ አዕናእከሙ ፡ ዮሴዕ ፡ ዘሩ
ባቤልን ፡ በከሃሊነትህ ፡ አዳናኻቸው ፡
(ወቅኑታን) ፡ ዮሴዕ ፡ ዘሩባቤል ፡ ኀይ
ልን ፡ እንደ ፡ ዝናር ፡ የታጠቁ ፡ ናቾ
ው ፡ (ዘየሀውክ) ፡ ብልጣሶርን ፡ በከተ
ማው ፡ ቸብቸበው ፡ ተቈርጦ ፡ እንዲቀ
ር ፡ ያደረግህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ (ወመኑ) ፡
አንተ ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ሀሊቆ ፡ እትቤ
ቀሉ ፡ ለንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ወለዙሉ ፡
ሕዝባ ፡ ብለህ ፡ ባትወስነው ፡ የባቢሎ
ንን ፡ የመከራዋን ፡ ዕናት ፡ ማን ፡ በተ
ቀዋወመው ፡ ነበር ፡ (ይደንግጹ ፡ እለ ፡
ይነብሩ) ፡ ባቢሎናውያንን ፡ አጥፍተ
ህ ፡ ትሩፋንን ፡ ታድገህ ፡ ካደረግኸው ፡
ተአምራት ፡ የተነሣ ፡ በጽንፈ ፡ ምድ
ር ፡ የሚኖር ፡ አሕዛብ ፡ ይደነግጣሉ ።
(እንድም ፡ አዕናዕከሙ) ፡ ሐዋርያትን ፡
ሰብዓ ፡ አርድዕትን ፡ በተአምራት ፡ አ
ፀናኻቸው ፡ (ወቅኑታን) ፡ ሐዋርያት ፡
ሰብዓ ፡ አርድእትም ፡ ገቢረ ፡ ተአም
ራት ፡ ወመንክራትን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱ
ስን ፡ ልጅነትን ፡ የተመሉ ፡ ናቸው ፡
አንትሙሰ ፡ ንበሩ ፡ ሀገረ ፡ ኢየሩሳሌ
ም ፡ እስከ ፡ ትለብሱ ፡ ኀይለ ፡ እምአ
ርያም ፡ እንዲል ፡ (ዘየሀውክ) ። ዲያብ
ሎስን ፡ በጥምቀት ፡ በመስቀል ፡ ድል ፡
የነሣኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ (ወመኑ) ፡ አ
ንተ ፡ በሐሙስ ፡ ዕለት ፡ ወበመንፈቃ ፡
ለዕለት ፡ እትወለድ ፡ እምወለትከ ፡ ብ
ለህ ፡ ባትወስነው ፡ የሲኦልን ፡ የመከ
ራ ፡ ነፍስን ፡ ዕናት ፡ ማን ፡ በተቀዋ
ወመው ፡ ነበር ፡ (ይደነግጹ ፡ እለ ፡ ይ

ነብሩ) ፡ አጋንንትን ፡ ድል ፡ ነሥተህ ፡
ነፍሳትን ፡ አድነህ ፡ ካደረግኸው ፡ ተ
አምራት ፡ የተነሣ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡
ይደነግጣሉ ፡ ይፈራሉ ።

ይወጽኡ ፡ በጽባሕ ፡ ወሠርክ ፡ ይትፌሥሑ ።

ጧት ፡ ሲወጡ ፡ እያዘኑ ፡ ይወጣሉ ፡
ላዩ ፡ ውሀ ፡ ታቹ ፡ ውሀ ፡ ሁኖባቸው ፡
ሲሔዱ ፡ ማታ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋ
ል ፡ ትልሙ ፡ ተከናውኖላቸው ፡ ዘሩ ፡
በቅቷቸው ፡ ሲመለሱ ፡ እንድም ፡ (በ
ጽባሕ) ፡ በሐምሌ ፡ በነሐሴ ፡ እያዘኑ ፡
ይወጣሉ ፡ ሞፈር ፡ ቀንበር ፡ ተሸክመ
ው ፡ ላም ፡ በሬ ፡ ነድተው ፡ ጭቃ ፡ እ
ስከ ፡ ጉልበታቸው ፡ እየዋጣቸው ፡
ሲሔዱ ፡ (ወሠርክ) ፡ በኅዳር ፡ በታኅ
ሣስ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ እሸቱን ፡
አንኩተው ፡ በልተው ፡ ምርቱን ፡ አም
ርተው ፡ በሪቅ ፡ በጎተራ ፡ መልተው ።
እንድም ፡ (በጽባሕ) ፡ በዔዋዊ ፡ ጊዜ ፡
ተማርከው ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ሲወርዱ ፡
እያለቀሱ ፡ ይሔዳሉ ፡ ወሠርክ ፡ (በሚ
ጠት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡
እንድም ፡ በጽባሕ) ፡ በጧት ፡ ከባቢ
ሎን ፡ ሲወጡ ፡ እያዘኑ ፡ ይወጣሉ ፡
እገሌ ፡ ወጥቶ ፡ ይሆንን ፡ ወይስ ፡ ቀር
ቶ ፡ ይሆንን ፡ እያሉ ፡ ወሠርክ ፡ ማታ ፡
ከሰፈር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከትቶላቸው ፡
ተገናኝተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ (እን
ድም) ፡ በጽባሕ ፡ ነፍሳት ፡ አምስት ፡
ሺህ ፡ ከምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ሐዋር
ያት ፡ በምሴተ ፡ ሐሙስ ፡ ያዝናሉ ፡





ወሠርክ ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ በትንሣኤ ፡
ግን ፡ ልጅነት ፡ ተመልሶላቸው ፡ ጌታ ፡
ተነሥቶላቸው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፱ ፡ ሐወጽከ ፡ ለምድር ፡ ወአርወይካ ።

ይህችን ፡ ዓለም ፡ በረድኤት ፡ ጎበኘ
ሃት ፡ እንድም ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከሰ
ብዓ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በረድኤት ፡ ጎበ
ኘሃት ፡ ማለት ፡ የዘሩባቤልን ፡ እንድታበ
ቅል ፡ የተከሉባትን ፡ እንድታጸድቅ ፡
አደረግሃት ።

ወአብዛህኮ ፡ ለብዕላ ።

የዚህችን ፡ ዓለም ፡ እንድም ፡ የኢየ
ሩሳሌምን ፡ ብዕል ፡ ሥጋዋን ፡ አበዛ
ኸው ።

ፈለገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሉዕ ፡ ማያተ ።

እግዚአብሔር ፡ የፈጠራቸው ፡ አራ
ቱ ፡ አፍላግ ፡ እንድም ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በረድኤት ፡ ያደረባት ፡ የኢየ
ሩሳሌም ፡ ወንዝ ፡ ወሀን ፡ የተመላ ፡
ነው ፡ ወእሦጡ ፡ ቀሳውስቲሆሙ ፡ ዕራ
ቃቲሆን ፡ እንዲል ። ተማርከው ፡ ባቢ
ሎን ፡ ሲወርዱ ፡ ወንዙ ፡ ሁሉ ፡ ደርቆ
ባቸው ፡ የሚጠጡት ፡ አጥተው ፡ ባዶ ፡
ዕቃቸውን ፡ ይዘው ፡ እያለቀሱ ፡ ወርደ
ዋል ፡ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ዝናም ፡
ዘንሞላቸው ፡ ወንዙ ፡ ሁሉ ፡ ወሀ ፡
መልቶላቸው ፡ እነሱ ፡ እየጠጡ ፡ ወገ
ኖቻቸውንም ፡ እያጠጡ ፡ ደስ ፡ ብሏ
ቸው ፡ ወጥተዋልና ።

አስተዳሉከ ፡ሲሳዮሙ ፡ እስመ ፡ ከማሁ ፡ ታስተ
ደሉ ።

ምግባቸውን ፡ አዘጋጀህላቸው ፡ አስ
ተዳሉከ ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ተናገርሁ ፡
ታዘጋጅላቸዋለህና ፤ እንድም ፡ ምግ
ባቸውን ፡ አዘጋጀህላቸው ፡ እንዲህ ፡
በስነ ፡ ፍጥረት ፡ ለአዳም ፡ ማዘጋጀት ፡
ልማድህ ፡ ነውና ።

፲ ፡ አርውዮ ፡ ለትለሚሃ ።

የዚህችን ፡ ዓለም ፤ እንድም ፡ የኢየ
ሩሳሌምን ፡ ትልሟን ፡ አርካው ።

ወአብዝኆ ፡ ለማዕረራ ።

መከሯን ፡ አብጀው ።

ወበነጠብጣብከ ፡ ትበቍል ፡ ተፈሢሓ ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ጠብ ፡
ጠብ ፡ ብሎ ፡ በሚዘንመው ፡ ዝናም ፡
ደስ ፡ ብሏት ፡ ተካክላ ፡ ትበቅላለች ።
ብርቱ ፡ ዝናም ፡ የዘነመ ፡ እንደሆነ ፡
ከነመሬቱ ፡ ድሶት ፡ ይሔዳል ፡ ለሰስ ፡
ብሎ ፡ ዝናም ፡ እንደ ፡ ቢዘን ፡ የወ
ረደ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ብሏት ፡
ተካክላ ፡ ትበቅላለችና ።

፲፩ ፡ ወትባርክ ፡ አክሊለ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረትከ ።

በቸርነትህ ፡ ዘመን ፡ የተገኘውን ፡ እህ
ሉን ፡ ታበዛዋለህ ፡ ገበሬው ፡ እንደ ፡
ዘውድ ፡ አድርጎ ፡ ያመርተዋልና ፡ አክ
ሊል ፡ አለው ። እንድም ፡ በርእሰ ፡
ዕፅ ፡ ይገኛልና ፡ እንድም ፡ የስንዴ ፡
የገብስ ፡ ትቱ ፡ እንደ ፡ ዘውድ ፡ ነውና ።

2014 04 17

ወይፀግቡ ፡ ጠላተ ፡ ገጻም ።

ገዳማት ፡ ልምላሜውን ፡ አግኝተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፲፱ ፡ ወይረውዩ ፡ አድባረ ፡ በድው ።

በበረሃ ፡ ያሉ ፡ ተራራዎች ፡ ዝናሙን ፡ ይረካሉ ።

ይትሐሰዩ ፡ አውግር ፡ ወይትቀነቱ ።

ኮረብታዎችም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ልምላሜውን ፡ እንደ ፡ ዝናር ፡ ይታጠቃሉ ።

፳ ፡ ወይለብሱ ፡ ስብሐ ፡ አባሕኩ ፡ አባግዕ ።

አባግዕ ፡ አባሕኩ ፡ በል ፡ አውራዎች ፡ አባግዕን ፡ ይንጠላጠሏቸዋል ፡ ይትላፀቃ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ስብሐ ፡ ያለ ፡ እንደ ሆን ፡ የአባግዕ ፡ አውራዎች ፡ ስብን ፡ ይለብሳሉ ።

ወቆላትኒ ፡ ይመልኡ ፡ ሥርናየ ።

ቆላትም ፡ ስንዴውን ፡ ያገኛሉ ፡ ብላጊ ፡ ዘመን ፡ ሲሆን ፡ ቆላ ፡ ደጋ ፡ አይልምና ፡ እንድም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ አይለወጥም ።

እንድም ፡ ሐወፅከ ፡ ትሩፍን ፡ ከሰብዓ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በረድኤት ፡ ጐበኘኸት ፡ ግበዕ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ እስመ ፡ ምድር ፡ አንተ ፡ ዘምድረ ፡ ለብሰ ፡ እን ዲል ፡ (ወአብዛህኮ) ፡ ብዕለ ፡ ሥጋዌን ፡ አበዛኸው ፡ (ፈለገ ፡ እግዚአብሔር) ፡ ነቢያት ፡ ትንቢትን ፡ ካህንት ፡ ትምህርትን ፡ የተመሉ ፡ ናቸው ። (አስተዳሎከ) ፡ ገቢረ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ አዘጋጀህላቸው ፡ (እስመ ፡ ከማሁ ፡ እንዲህ ፡ ለሙሴ ፡ ለአሮን ፡ ማዘጋጀት ፡ ልማድህ ፡ ነውና ፡ (እርውዮ) ፡ ልቡናዋን ፡ ደስ ፡ አሰኛት ፡ (ወአሥምሮ) ፡ ሚጠተ ፡ ሥጋዋን ፡ አብጀው ፡ (ወበነጠብጣብከ) ፡ በነጠብጣብ ፡ ምሕረትህ ፡ ደስ ፡ ብሏት ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትወጣለች ፡ (ወትበርከ) ፡ የዘሩባቤልን ፡ ዘውድ ፡ ታከብረዋለህ ፡ (ወይፀግቡ) ፡ አሕዛብ ፡ አሪትን ፡ ይቀበላሉ ፡ (ወይረውዩ) ፡ ነገሥት ፡ አሕዛብም ፡ አሪትን ፡ ይቀበላሉ ፡ (ይትሐሠዩ) ፡ መኳንንት ፡ አሕዛብም ፡ አሪትን ፡ ይቀበላሉ ፡ (ወይለብሱ) ፡ እስራኤልም ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ አብነት ፡ ያደርጋሉ ፡ ስብሐ) ፡ ያለ ፡ እንደ ሆን ፡ የነቢያት ፡ የካህናትን ፡ ትምርት ፡ ይቀበላሉ ፡ (ወቆላትኒ) ፡ አሕዛብም ፡ አሪትን ፡ ይቀበላሉ ።

እንድም ፡ ሐወፅከ ፡ ምእመንን ፡ ከምስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በልጅነት ፡ ጐበኘሃት ፡ (ወአብዛህኮ) ፡ ብዕለ ፡ ነፍሷን ፡ አበዛኸው ፡ (ፈለገ ፡ እግዚአብሔር) ፡ ሐዋርያት ፡ ሰብዓ ፡ አርድዕት ፡ ትምርትን ፡ ገቢረ ፡ ተአምራትን ፡ ልጅነትን ፡ የተመሉ ፡ ናቸው ፡ (አስተዳሎከ) ፡ ሥጋህን ፡ ደምህን ፡ አዘጋጀህላቸው ፡ (እስመ ፡ ከማሁ) ፡ እንዲህ ፡ በመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ማዘጋጀት ፡ ልማድህ ፡ ነውና ።

እንድም ፡ (አስተዳሎከ) ፡ ልጅነትን ፡ ትምርትን ፡ አዘጋጀህላቸው ፡ (እስመ ፡ ከማሁ) ፡ እንዲህ ፡ በአዳም ፡ ማዘጋጀት ፡ ልማድህ ፡ ነውና ፡ (እርውዮ) ፡ (ወ ልቡና ፡ ነፍሷን ፡ ደስ ፡ አሰኘው ፡ (ወ አሥምሮ) ፡ ሚጠተ ፡ ነፍሷንም ፡ አብ ጀው ፡ (ወበነጠብጣብከ) ፡ ጠብ ፡ ጠብ ፡ ብሎ ፡ በፈሰሰ ፡ ማየ ፡ ገቦህ ፡ ተጠምቃ ፡ ደስ ፡ ብሏት ፡ ከሲኦል ፡ ከገሃነም ፡ ወ ደገነት ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ትወጣለች ፡ (ወትበርከ) ፡ በቸርነትህ ፡ ወንጌላዊውን ፡ ታከብረዋለህ ፡ እን ድም ፡ ልጅነትን ፡ ታከብረዋለህ ፡ ማ ለት ፡ እንዲሰጥ ፡ ታደርገዋለህ ፡ (ወይ ፀግቡ) ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ወንጌል ን ፡ ይቀበላሉ ፡ (ወይረውዩ) ፡ ነገሥት ፡ እስራኤልም ፡ ወንጌልን ፡ ይቀበላሉ ፡ (ይትሐሠዩ) ፡ መኳንንተ ፡ እስራኤ ልም ፡ ወንጌልን ፡ ይቀበላሉ ፡ (ወይለ ብሱ ፡ ስብሐ) ፡ ምእመናን ፡ የሐዋር ያትን ፡ የሰብዓ ፡ አርድእትን ፡ ትም ርት ፡ ይቀበላሉ ፡ እንድም ፡ ሐዋር ያት ፡ ሰብዓ ፡ አርድዕት ፡ ልጅነትን ፡ የተመሉ ፡ ናቸው ፡ (ወቆላትኒ) ፡ ምእ መናን ፡ አሕዛብ ፡ በወንጌል ፡ ያም ናሉ ። እንድም ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ይቀበላሉ ፡ ወእንዘ ፡ ዝሩት ፡ ይእቲ ፡ ማዕከለ ፡ አድባር ፡ ወአውግር ፡ ወቈላተ ፡ ገዳም ፡ ወተጋቢአ ፡ ትከውን ፡ አሐተ ፡ ጽርስፎራ ፡ እንዲል ።

ይፀርሑ ፡ እንዘ ፡ ይሴብሑ ።

እንዘ ፡ ይፀርሑ ፡ ይሴብሑ ፡ ነው ፡ እ ንዲህ ፡ እያሉ ፡ ያመሰግናሉ ።



## መዝሙር ፡ ፹፱ ።

፩ ፡ የብቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በነኮሉ ፡ ምድር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ በአርእ ስቱ ፡ በእንተ ፡ አስቴር ፡ ወመርዶክዮ ስ ፡ የሚል ፡ አብነት ፡ ይገኛል ። ይህስ ፡ እንደምንድን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ትሩፋን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አልወጡም ፡ የወጡት ፡ ወጥተው ፡ ያልወጡት ፡ በባቢሎን ፡ ሳሉ ፡ አርጤክስስ ፡ የሚባል ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። ከገናንነቱም ፡ የተነሣ ፡ መቶ ፡ ሐያ ፡ ሰባት ፡ አህጉር ፡ ይገዛ ፡ ነ በር ። ለመቶ ፡ ሐያ ፡ ሰባት ፡ አህጉር ፡ ሰማንያ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ አዳራሽ ፡ ተ ገኝቶላቸዋል ። ሰማንያውን ፡ ቀን ፡ ከ ዳር ፡ ከድንበር ፡ ለመጡ ፡ ስድስቱን ፡ ቀን ፡ በከተማ ፡ ላሉ ፡ ሁለቱን ፡ ቀን ፡ ለቋሚ ፡ ላሳላፊ ፡ ከዚህ ፡ ማኀል ፡ ሚ ስቱ ፡ አስጢን ፡ ትባላች ፡ እግረ ፡ ወ ርኅ ፡ ማለት ፡ ነው ። ነይ ፡ ብሎ ፡ ይል ክባታል ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡ ፈቃድ ፡ ቢ ነሣበት ፡ ለዚህስ ፡ ጊዜውም ፡ አይደ ል ፡ ብሎ ፡ አሕዛብ ፡ ምኩሐን ፡ ናቸው ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ናትና ፡ ሚስቴን ፡ ይዩልኝ ፡ ብሎ ። እንድም ፡ እቴጌነት ፡ አልደረበላትም ፡ ነበርና ፡ ለመደረብ ፡ እሷም ፡ አልመጣም ፡ ብላ ፡ ትልከበ ታለች ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡

ዓይን፡ሊያስወጋኝ፡ሊያስገመግመኝ፡
ብላ ። አንድም ፡ እሷም ፡ በበኩሷ ፡ አ
ርዳ ፡ ጠጅታ ፡ አዳራሽ ፡ ተገኝታ ፡ ነበ
ርና ፡ ግብር ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ለመ
ኳንንቱ ፡ ሚስቱን ፡ ነይ ፡ ብዬ ፡ ብል
ከባት ፡ አልመጣም ፡ አለችኝ፡ፍረዱ
ኝ፡አላቸው ። ንጉሥ ፡ ፍርድ ፡ ልበስ፡
ያንተ ፡ ሚስት ፡ ካልታዘዘችልህማ ፡
የኛ ፡ ሚስቶች ፡ ጣቢታ ፡ አፍስሰው ፡
ወጥ ፡ ጠብሰው ፡ ይሰጡናልን ፡ በዶ ፡
እጇዋን ፡ ወጥታ ፡ ስትሔድ ፡ ይታየ
ናል፡አሉት ። አስወጥቶ፡ሰድዷታል ።
አንድ ፡ ዓመት ፡ ሚስት ፡ ሳያገባ ፡ ተቀ
መጠ ። አስቴ ፡ ፩ ፡ ፩-፳፪ ። ከንድ፡ዓመት፡
በኋላ ፡ መኳንንቱ ፡ ንጉሡን ፡ ሚስ
ትህን ፡ ፍታ ፡ ብለን ፡ አስፈትተን ፡
እኛ ፡ ከሚስቶቻችን ፡ ጋራ ፡ ብንኖር ፡
ደግ ፡ ነውን ፡ ብለው ፡ ተመራርጠው ፡
ገብተው ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ለንጉሥ ፡ እን
ጅ ፡ ግልሙትና ፡ አይስማማውም ፡ ሚ
ስት ፡ አግባ ፡ አሉት ። የቀድሞ ፡ ሚስ
ቱን ፡ ይወድዳት ፡ ነበርና ፡ እሷን ፡ የ
መሰለ ፡ አታገኙልኝማ ፡ አላቸው ። ከ
እስራኤልም ፡ ከአሕዛብ ፡ ብለን ፡ እና
ጣም ፡ አሉት ። እንግዲያማ ፡ ፈልጉ
ልኝ ፡ አላቸው ። ከእስራኤልም ፡ ከአ
ሕዛብም ፡ ብለው ፡ ሺህ ፡ ሴት ፡ መለ
መሉ ። ከሺሁ ፡ መቶ ፡ ከመቶው ፡ ዓ
ሥር ፡ ከሥሩ ፡ ሦስት ፡ መርጠዋል ።
ሦስተኛዪቱም ፡ አስቴር ፡ ትባላለች ።
አስቴርም ፡ ማለት ፡ ሠረገላ ፡ ፀሐይ ፡
ማለት ፡ ነው ። የመርዶክዮስ ፡ የወን

ድሙ ፡ ልጅ ፡ ናት ። የወንድም ፡ ልጅ ፡
ባይወልዱትም ፡ ልጅ ፡ እንዲሉ ፡ ተ
ከባክቦ ፡ አሳድጓታል ። አንድም ፡ ከአ
ሕዛብ ፡ እጠባበቃታለሁ ፡ ብሎ ፡ አሳ
ድጓታል ። ለሁቱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡
አዳራሽ ፡ እየተገኙ ፡ ልብሰ ፡ ቀለም ፡
ርስት ፡ ጕልት ፡ እየሰጠ ፡ አኑሯቸዋል ።
ለአስቴር ፡ ግን ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ አዳራሽ ፡
ተገኝቶላታል ። ወአዕበያ ፡ ለመርዓ ፡
አስቴር ፡ እንዲል ፡ ጋዶ ፡ የሚባል ፡
ጃንደረባ ፡ ነበረው ፡ ለርሱ ፡ ስጢት ፡
መንፈቅ ፡ የውስጥ ፡ ሰውነቷን ፡ የሚ
ያጠራ ፡ ይመግባታል ፡ መንፈቅ ፡ የአ
ፍአ ፡ ሰውነቷን ፡ የሚያጠራ ፡ ሽቱ ፡
ይቀባታል ። የአሕዛብ ፡ ነገሥታት ፡ በ
ዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሽቱ ፡ ሊዘግቡላቸው ፡ ይ
ወድዳሉ ፡ እያለ ፡ ነገሥታቱ ፡ የሚወ
ድዱትን ፡ ሁሉ ፡ ይመክራታል ። ቢት
ወደዱ ፡ ሐማ ፡ ይባላል ። ዘኢሰገደ ፡
ለሐማ ፡ ይትበርበር ፡ ቤቱ ፡ ወይትሐ
የድ ፡ ንዋዩ ፡ ወይትኰነን ፡ ነፍሱ ፡ ብሎ ፡
አዋጅ ፡ ነግሮለት ፡ ሁሉ ፡ ይሰግድለት ፡
ይታጠቅለት ፡ ነበር ። መርዶክዮስ ፡ ግን ፡
ይህ ፡ መምለኪ ፡ ጣዖት ፡ እያለ ፡ እያ
ከብረውም ፡ አይሰግድለትም ። አሁን ፡
እንደኔ ፡ ያለ ፡ ባለሟል ፡ ማን ፡ አለ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ በመርዶክዮስ ፡ አ
ይሁዳዊ ፡ ዘንድ ፡ ኢምንት ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡
ሔዶ ፡ ንጉሥ ፡ ጠላትህን ፡ ላጥፋልህ ፡
በማጥንህ ፡ ዕልፍ ፡ ወርቅ ፡ ልምላልህ ፡
አለው ። በማጥኔ ፡ ወርቅ ፡ ልትመላል
ኝ ፡ ጠላቴንም ፡ ልታጠፋልኝን ፡ አለ



ው ። እዎን ፡ አለው ፡ ወርቁ ፡ ይቅርብ
ኝ ፡ ጠላቴን ፡ አጥፋልኝ ፡ አለው ። ከ
ዚህ ፡ በኋላ ፡ ፈላስፋ ፡ ነውና ፡ እስራ
ኤል ፡ የሚጠፉበትን ፡ ቀን ፡ ቴጠሮ ፡
አዳር ፡ በገባ ፡ መጋቢት ፡ ማለት ፡ ነው ።
በዓሥራ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ እስራእልን ፡
ፍጁ ፡ የሚል ፡ ጽፎ ፡ላከ ። አስቴር ፡ ፫ ፡ ፩-፲፪ ።
መርዶክዮስም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ተራ ፡
ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ሔዶ ፡ ንገሩልኝ ፡ አለ ፤
ዛሬና ፡ ነገ ፡ ምን ፡ ከልካይ ፡ አለብህ ፡
አትገባምን ፡ ብላ ፡ ትልክበታለች ፡ እ
ኔስ ፡ የኃዘን ፡ ልብስ ፡ ለብሼ ፡ ከቤተ ፡
መንግሥት ፡ አልገባም ። ሲሆን ፡ አን
ቺ ፡ ዘልቀሽ ፡ እነጋግሪኝ ፡ ባይሆንም ፡
የምታምኚውን ፡ አሽከር ፡ ላኪቢኝ ፡
ብሎ ፡ ላከባት ። አክራታዎስ ፡ የሚባ
ል ፡ ያሳደገችው ፡ አሽከር ፡ ነበር ፡ ላከ
ችለት ፡ ጥንቱን ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡
መጋባት ፡ ያጣ ፡ ሊያገኝ ፡ የከፋው ፡
ደስ ፡ ሊለው ፡ ነበር ፤ በዕልፍ ፡ ወቄት ፡
ወርቅ ፡ ተሸጠን ፡ ማለቃችን ፡ በምን ፡
ምክንያት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይልክባታል ።
ሻጩስ ፡ ማን ፡ ነው ፡ ገዥውስ ፡ ማን ፡
ነው ፡ ብላ ፡ ትልክበታለች ፡ ሻጭው ፡
ንጉሡ ፡ ገዥው ፡ ሐማ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡
ይልክባታል ፡ አልሰማሁም ፡ እንጂ ፡
ብሰማስ ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ ፡ በዚያም ፡
ላይ ፡ ከንጉሡ ፡ ከተገናኘሁ ፡ ሦስት ፡
ቀን ፡ ሆኖኛል ፡ የአሕዛብ ፡ ነገሥታት ፡
ሚስቶች ፡ ሳይጠሯቸው ፡ አይሔዱ ፡
ምን ፡ አደርጋለሁ ፡ ብላ ፡ ትልክበታ
ለች ። እስራኤልንማ ፡ እግዚአብሔር ፡

በማናቸውም ፡ ቸርነቱ ፡ ያድናቸዋል ።
ነገር ፡ ግን ፡ አንች ፡ ከእስራኤል ፡ ተለ
ፋ ፡ እንደወጣሽ ፡ እወቂው ፡ ብሎ ፡ ይ
ልክባታል ። በአጥር ፡ ዘልቃ ፡ ቸል ፡ ያ
ለች ፡ መስሎህ ፡ ነውን ፡ እናንተም ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አመልክቱ ፡ እ
ኔም ፡ አመለክታለሁ ፡ አለችው ። የኃ
ዘን ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ ብታገዘን ፡ በሦስ
ተኛው ፡ ቀን ፡ የምታጠፋበትን ፡ ምክ
ንያት ፡ አገኘታለች ። አስቴ ፡ ፬ ፡ ፩-፲፯ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የምትጠላት ፡ ገረዷ
ን ፡ በፊት ፡ የምትወድዳት ፡ ገረዷን ፡
በኋላ ፡ አድርጋ ፡ ሒዳለች ። ስለምን ፡
ቢሉ ፡ ነገሥት ፡ አሕዛብ ፡ ሳይጠሩት ፡
የሔደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ዓይነ ፡
ወርቅ ፡ ያለ ፡ አለባቸው ፡ ገዘልፍል
ፍ ፡ ብሎ ፡ ይወድቃል ። ተራ ፡ ሰው ፡
የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡ ይ
ቀራል ፡ የታወቀ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ሀለተ ፡ ወርቅ ፡ ያስነኩታል ፡ ይነሣል
ና ፡ ብትጠላት ፡ ትሙትልኝ ፡ ብላ ፡ እ
ንዲህስ ፡ አታደርግም ፡ ብሎ ፡ የምት
ወድዳትን ፡ በፊት ፡ የምትጠላትን ፡ በ
ኋላ ፡ አድርጋ ፡ ሒዳለች ። ስለምን ፡
ቢሉ ፡ ሕለተ ፡ ወርቁ ፡ ይትረፋት ፡ (ይ
ድረሳት) ፡ ብላ ፡ ከፊቱ ፡ ሲደርሱ ፡ ገ
ልፍልፍ ፡ ብለው ፡ ወደቁ ። በሕለተ ፡
ወርቅ ፡ አስነሥቷቸዋል ። ምነው ፡ ምን ፡
ሆንሽ ፡ ቀድሞ ፡ የምታውቂኝ ፡ አይ
ደለሁምን ፡ አላት ። አንተ ፡ ጌታዬ ፡ ግ
ሩም ፡ መልአክ ፡ መስለህ ፡ ብትታየ
ኝ ፡ ነዋ ፡ አለችው ። ለምን ፡ መጣሽ ፡

አላት፡ ግብር፡ አድርገህ፡ አዳራሽ፡
ትገኝልኝ፡ ብዬ፡ ነው፡ ወዲያውም፡
የምነግርህ፡ አለኝ፡ ሐማም፡ እንዳይ
ቀርብኝ፡ አለችው፡ ሔዶ፡ አዳራሽ፡
ተገኝቶ፡ ከመኳንንቱ፡ ፊት፡ ሲያመ
ሰግናት፡ ዋለ፡ እያችሁን፡ የቀድሞ
ይቱ፡ ሚስቱ፡ ነይ፡ ብዬ፡ ብልክባት፡
አልመጣም፡ አለችኝ፡ ይህች፡ ግን፡
መጥታ፡ መራችኝ፡ እያለ፡ ከዚህ፡ በ
ኋላ፡ ጉዳይሽን፡ ንገሪኝ፡ አላት፡ ነገ፡
እነግርሃለሁ፡ አለችው፡ ሐማም፡ ከ
ቤቱ፡ ሔዶ፡ አሁን፡ እንደ፡ እኔ፡ ያለ፡
በለጸጋል፡ ምን፡ አለ፡ ይህች፡ እንኳ፡
እንግዳዪቱ፡ ንግሥት፡ እንደ፡ ንጉሡ፡
አድርጋ፡ ታከብረኛለች፡ ነገር፡ ግን፡
በመርዶክዮስ፡ ዘንድ፡ ኢምንት፡ ነኝ፡
ብሎ፡ ግብር፡ አላገባም፡ አለ፡ ቢትወ
ደድ፡ የወደደውን፡ ያደርግ፡ እንዲ
ሉ፡ እስራኤልን፡ በመላ፡ አጥፋ፡ ብ
ሎሃል፡ እንድ፡ ሰው፡ ብታሰቅል፡ ምን፡
ያደርግሃል፡ አሉት፡ ቸኩሎ፡ ገመድ፡
አስፈተለ፡ ግንድ፡ አስተከለ፡ ኋላ፡
ግን፡ እንዲያውም፡ ንጉሡ፡ ያውቀ
ዋል፡ ከንጉሡ፡ አስፈቅጄ፡ ነገ፡ እሰ
ቅለዋለሁ፡ ብሎ፡ አሳደረው። አስቴ፡
፭፡ ፩-፲፭ ።

በዚያ፡ ሌሊት፡ ነፍፀ፡ ንዋም፡ እምአ
ዕይንተ፡ ንጉሥ፡ ይላል፡ ንጉሡ፡ እ
ንቅልፍ፡ አጥቶ፡ አድሯል። የቀድሞ፡
ነገሥታት፡ እንቅልፍ፡ ያጡ፡ እንደ፡
ሆነ፡ ወግ፡ ታሪክ፡ ሲመለከቱ፡ ያድሩ፡
ነበረ፡ ታሪክ፡ ነገሥት፡ ሲመለከት፡
ወረከበ፡ አኰቴቶ፡ ለመርዶክዮስ፡ ይ
ላል፡ ወረታውን፡ አገኘለት፡ እንደ፡

ምን፡ ነው፡ ቢሉ፡ የቀድሞ፡ ሚስቱ፡
ዘመዶች፡ ግብራቸው፡ ጣማ፡ ነበር፡
ከሞተ፡ አቴቴ፡ ምን፡ አለኝ፡ ከሐማ
ቴ፡ እንዲሉ፡ እኅታችንን፡ ከፊት፡ እ
ንግዲህ፡ ወዲህ፡ ምን፡ ዘመዳችን፡
ነው፡ ብለው፡ ጣማውን፡ መርዝ፡ ቀ
ብተ፡ አምጥተውለታል፡ ወመርዶክ
ዮስ፡ ይፌውስ፡ ዓፀደ፡ ንጉሥ፡ ይላ
ል፡ በምክሩ፡ ሰውን፡ ይጠቅም፡ ነበ
ርና፡ ንጉሥ፡ ይህን፡ ጣማ፡ ሳታስፈ
ትሽ፡ ከእግርህ፡ አታግባ፡ አለው፡ ይ
ዞት፡ የመጣውን፡ ቢያስፈትነው፡ ጠ
ምቧ፡ ብሎ፡ ሙቷል፡ ይህ፡ ተጽፎ
ለታል፡ በቤተ፡ መንግሥት፡ አስታ
ዋሽ፡ ከሌለው፡ መጠቀም፡ የለምና፡
ልብስ፡ ቀለብ፡ እየተቀበለ፡ ይኖር፡ ነ
በር፡ ይህን፡ ላደረገ፡ ለመርዶክዮስ፡
ምን፡ አድርገንለታል፡ ብሎ፡ ጠየቀ፡
ከሰው፡ የበለጠማ፡ ምን፡ ተደርጎለ
ታል፡ ልብስ፡ ቀለብ፡ እየተቀበለ፡ ይ
ኖሃል፡ አሉት፡ ሐማ፡ ሲመጣ፡ እን
ድትነግረኝ፡ አለ፡ ሐማ፡ ነግቶልኝ፡ ከ
ንጉሡ፡ አስፈቅጄ፡ መርዶክዮስን፡
አሰቅየው፡ ሲል፡ ንጉሡም፡ ነግቶል
ኝ፡ የመርዶክዮስን፡ ወሮታ፡ ከፍየው፡
ሲል፡ አድረዋል፡ ሲነጋ፡ ሐማ፡ ሠራ
ዊቱን፡ አስከትሎ፡ ግር፡ ግር፡ እያለ፡
መጣ፡ ሐማ፡ ንጉሡን፡ ከሞት፡ ላዳ
ነ፡ የንጉሡን፡ ጠላት፡ ላጠፋ፡ ምን፡
ሊያደርጉለት፡ ይገባል፡ አለው፡ የን
ጉሡን፡ ጠላት፡ ላጥፋ፡ ያልሁ፡ እኔ፡
ነኝ፡ ብሎ፡ እንዲህማ፡ ላደረገ፡ ንጉ



ሡ፡ በሚቀመጥበት፡ በመደቡ፡ አስ
ቀምጦ፡ ራስ፡ ወርቅ፡ አስሮ፡ ከተማ
ውን፡ ሦስት፡ ጊዜ፡ አዙሮ፡ ንጉሥ፡
የወደደው፡ እንዲህ፡ ይሆናል፡ ብሎ፡
አዋጅ፡ ሊነግሩለት፡ ይገባል፡ አለው፡
ከመ፡ ከመ፡ ገብር፡ ለመርዶክዮስ፡ አ
ይሁዳዊ፡ ወኢታትርፍ፡ ምንተኒ፡ እ
ምዘነበብከ፡ አሁን፡ ከተናገርከው፡
ለመርዶክዮስ፡ ምንም፡ አታስቀርበ
ት፡ ሁሉንም፡ አድርግለት፡ አለው፡
ወጸልመ፡ ገጹ፡ ለሐማ፡ ይላል፡ ፊቱ፡
ከቁራ፡ ሰባት፡ እጅ፡ ጠቆረ፡ የንጉሥ፡
ቃል፡ ረዘመ፡ ብለው፡ አያሳጥሩት፡
አጠረ፡ ብለው፡ አያስረዝሙትምና፡
ንጉሥ፡ ያዘዘውን፡ አድርጎ፡ አዋጅ፡
አስነገረለት። አስቴ፡ ፮፡ ፩-፲፬ ። ከዚህ፡
በኋላ፡ በሐማ፡ መቀመጫ፡ መርዶክዮስ፡
በመርዶክዮስ፡ መቀመጫ፡ ሐማ፡ ተቀ
ምጠው፡ ሳለ፡ ንገሪኝ፡ አላት፡ ጥንቱ
ን፡ ከቤተ፡ መንግሥት፡ መጋባት፡
ያጣ፡ ሊያገኝ፡ የከፋው፡ ደስ፡ ሊለ
ው፡ ነበር፡ እኔስ፡ ዘመዶቼ፡ እስራኤ
ልስ፡ በዕልፍ፡ ወቄት፡ ወርቅ፡ መሸ
ጣችን፡ ለምንድን፡ ነው፡ አለችው፡
ገዥውስ፡ ማን፡ ነው፡ ሻጭውስ፡ ማን፡
ነው፡ አላት፡ ገዢው፡ ፀላዒን፡ ሐማ፡
ብላ፡ በእጅዋ፡ ጠቅሳ፡ አሳየችው፡ የ
ሱንስ፡ ነገር፡ ቆይ፡ አሳይሻለሁ፡ ብሎ፡
ተቈጥቶ፡ በስርቆሽ፡ በር፡ ወጥቶ፡
ሔደ፡ ስለ፡ ምን፡ ቢሉ፡ እንበሳ፡ መ
ደብ፡ ለመቀመጥ፡ ለመናፈስ። አን
ድም፡ የአሕዛብ፡ ነገሥታት፡ የሰከሩ፡

እንደ፡ ሆነ፡ የሰከሩበትን፡ ይሰፍሩ፡
ነበርና፡ ለመሥፈር፡ ሐማም፡ ለካ፡
ከሹመቴ፡ ያሻረችኝ፡ ከመዓርጌ፡ ያዋ
ረደችኝ፡ እሷ፡ ናትና፡ ብሎ፡ ንግሥ
ት፡ ሆይ፡ የሰቀልሽውን፡ አውርጅው፡
ያነደድሽውን፡ አብርጅው፡ እያለ፡ ከ
እግሯ፡ በታች፡ ሲንከባለል፡ አገኘው፡
ሐማ፡ ትትዒገለኒኑ፡ ብእሲትየ፡ በቤ
ትየ፡ ብሎ፡ ተቈጥቶ፡ ቡኩቴር፡ የሚ
ባል፡ ሰይፈ፡ ገርግሬው፡ ነበረ፡ ንጣ፡
በሰይፍ፡ በለው፡ አለው፡ ንጉሥ፡ ለ
ምን፡ ትቆጣለህ፡ የንጉሥ፡ ቁጡ፡ እ
ለውን፡ አለው፡ ምን፡ ላድርግ፡ ሚስ
ቴን፡ በቤቴ፡ ስትቀማኝ፡ አለው፡ እ
ንዲህ፡ የማያስመልስ፡ ከሆነማ፡ ትላ
ትና፡ መርዶክዮስን፡ ለማሰቀል፡ ያስ
ፈተለው፡ ገመድ፡ ያስተከለው፡ ግን
ድ፡ አለ፡ በዚያ፡ አትሰቅለውምን፡ አ
ሉት፡ በዚያ፡ አሰቅሎ፡ አስገድሎታል።
አስቴ፡ ፯፡ ፩-፲ ።

ከዚህ፡ በኋላ፡ አሁን፡ እንዳች፡ አድ
ርጌ፡ የምወድደው፡ ምን፡ አለኝ፡ ይኸ
ውም፡ ሊታወቅ፡ ያሳደግሁትን፡ አሽ
ከሬን፡ ላንቺ፡ ብዬ፡ አሰቀልሁት፡ እ
ላት፡ ያንድ፡ የሐማ፡ ሞት፡ ለእአላፈ፡
እስራኤል፡ ቤዛ፡ ይሆናልን፡ እስራኤ
ልን፡ በያሉበት፡ አጥፋ፡ ብሎ፡ ጽፎ፡
ሰድዶ፡ የለምን፡ አለቺው፡ ይህስ፡ እ
ንዳይሆን፡ አንቺና፡ ወንድምሽ፡ እስ
ራኤል፡ ጠላታቸውን፡ ያጥፉ፡ እንጂ፡
እነሱን፡ የሚነካቸው፡ አይኑር፡ እያ
ላችሁ፡ ጽፋችሁ፡ ስደዱ፡ አላት። የ
ሐማ፡ በአሥራ፡ አራት፡ ቀን፡ ገብቷ

ል ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእስራኤል ፡
አሥራ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ይገባል ፡ በአሥ
ራ ፡ አራት ፡ በዓል ፡ ያደርጋሉ ። የሐ
ማ ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ገብቷ
ል ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእስራኤል ፡ በ
አሥራ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ገብቷል ፡ በአ
ሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ግንገ ፡ ጥጥ ፡
አሥረው ፡ በግ ፡ ሠውተው ፡ በዓል ፡
አድርገው ፡ ተናግረውታል ።
ባሬቱ ፡ መዓዝን ፡ መልቶ ፡ ያለ ፡ እግ
ዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ። እንድም ፡
ባሬቱ ፡ መዓዝን ፡ ያላችሁ ፡ እስራኤል ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።
መዝ ፡ ፳፱ ፡ ፱ ።

፬ ፡ ወዘምሩ ፡ ለስሙ ።

ለስሙም ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ ስሙ
ን ፡ አመስግኑ ።

፭ ፡ በልዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ግሩም ፡ ግብርከ ።

እግዚአብሔርን ፡ ሥራህ ፡ ግሩም ፡
ነው ፡ በሉት ፡ እሞታለሁ ፡ ያለውን ፡
ማዳን ፡ እገድላለሁ ፡ ያለውን ፡ መግደል ።

እንዘ ፡ ብዙኀ ፡ ኀይልከ ፡ ሐሰዉከ ፡ ጸላእትከ ።

ከሃሊነትህ ፡ ብዙ ፡ ሲሆን ፡ ጠላቶች
ህ ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፡ አሉህ ፡ ማለት ፡
ማዳን ፡ መታደግ ፡ ሲቻልህ ፡ አያድን
ም ፡ አይታደግም ፡ አሉህ ።

፬ ፡ ኵላ ፡ ምድር ፡ ትሰግድ ፡ ወትገኒ ፡ ለከ ።

ለሳቸው ፡ ይበሳቸው ፡ እንጂ ፡ ላንተ
ስ ፡ ምድር ፡ በመላዋ ፡ ትሰግድልሃለ
ች ፡ ትገዛልሃለች ።

ወትዜምር ፡ ለስምከ ።

ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ ታቀርባለች ፡ ስም
ህን ፡ ታመሰግናለች ።

፭ ፡ ንዑ ፡ ትርአዩ ፡ ግብረ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
መዝ ፡ ፵፭ ፡ ፰ ።

የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ታዩ ፡ ዘን
ድ ፡ ኑ ፡ እንድም ፡ ኑ ፡ እዩ ።

ግሩም ፡ ምክሩ ፡ እምዕጓለ ፡ እመሕያው ።

ፍሉጥ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡
ምክሩ ፡ ከሰው ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ ሰው ፡
የሆን ፡ እንደሆን ፡ ቢቆይድ ፡ የወደደ
ውን ፡ ያደርግ ፡ ነው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡
ብትገድል ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ያደርግ
ሃል ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡
እሞታለሁ ፡ ያለ ፡ መርዶክዮስን ፡ ማ
ዳን ፡ እገድላለሁ ፡ ያለ ፡ ሐማን ፡ መግ
ደል ፡ ነው ።

፮ ፡ ዘይሬስያ ፡ ለባሕር ፡ የብሰ ።

ዘረስያ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ጥንትም ፡ ይህ
ችን ፡ ዓለም ፡ የብስ ፡ ያደረጋት ፡ እሱ ፡
ነው ፡ በዕለተ ፡ ፍጥረት ፡ ከዚህ ፡ እስ
ከ ፡ ብሩህ ፡ ሰማይ ፡ ወሀ ፡ መልቶ ፡
ነበረ ፡ ለይትጋባዕ ፡ ማይ ፡ ውስተ ፡ ምዕ
ላዲሁ ፡ ብሎ ፡ ከሦስት ፡ ከፍሎታል ።

ወበተከዚ ፡ የሐልፉ ፡ በእግር ።

ወበተከዚ ፡ ይላል ፡ ፈሳሹንም ፡ ወሀ ፡
በእግር ፡ እንዲሻገሩ ፡ የሚያደርግ ፡
እሱ ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፲ ።
እንድም ፡ (ዘይሬስያ) ፡ ግብፅን ፡ እስ



ራኤልን ፡ አውጥቶ ፡ በዮዋን ፡ የሚ
ያደርጋት ፡ እሱ ፡ ነው ፡ (ወበተከዚ) ፡
ኤርትራንም ፡ በእግር ፡ እንዲሻገሩ ፡
የሚያደርግ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ከሁለት ፡
ከሦስት ፡ ከፍሎ ፡ አንድም ፡ (ዘይሬ
ስያ) ፡ በቢሎንን ፡ ትሩፋንን ፡ አወ
ጥቶ ፡ በዮዋን ፡ የሚያደርጋት ፡ እሱ ፡
ነው ፡ (ወበተከዚ) ፡ ፈሳሹንም ፡ ወሀ ፡
በእግር ፡ እንዲሻገሩ ፡ የሚያደርግ ፡
እሱ ፡ ነው ፡ ወይቀስፍ ፡ ሰብዓተ ፡
አፍላግ ፡ እንዲል ፡ ሰባት ፡ ወንዝ ፡
ተከፍሎላቸው ፡ ወጥተው ፡ ሰባት ፡
አህጉር ፡ አጥፍተው ፡ ወጥተዋልና ፡
አንድም ፡ (ዘይሬስያ) ፡ ነፍሳትን ፡ አወ
ጥቶ ፡ ገሃነምን ፡ በዮዋን ፡ ያስቀራት ፡
እሱ ፡ ነው ፡ (ወበተከዚ) ፡ በመስቀሉ ፡
ትርክዛ ፡ እየቀዘፈ ፡ ባሕረ ፡ ገሃነምን ፡
እንዲሻገሩ ፡ ያደረገ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወበህየ ፡ ንትፌሣህ ፡ ኅቡረ ።

በህየ ፡ ማለት ፡ በነገር ፡ በልቡና ፡ በቦ
ታ ፡ ነው ፡ አንድነት ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡
ደስ ፡ ይበለን ።

፯ ፡ ዘይኴንን ፡ በኃይሉ ፡ ዘለዓለም ።

ዘይኴንን ፡ ዘለዓለም ። በኃይሉ ፡ ዘለ
ዓለም ፡ በኃይሉ ፡ ፈጥኖ ፡ ዘለዓለም ፡
የሚገዛ ፡ ዘለዓለም ፡ በኃይሉ ፡ የሚ
ገዛ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወአዕይንቲሁ ፡ ኀበ ፡ ንዳይ ፡ ይኔጽራ ።

አዕይንቱ ፡ መዓቱ ፡ ኢሕዛብን ፡ ይመ
ለከታሉ ።

እለ ፡ ተኀምሩ ፡ ኢትትዐበዩ ፡ ርእሰክሙ ።

ድዱቅ ፡ እንዲጠቅም ፡ ኃጢአት ፡ እን
ዲጎዳ ፡ የምታውቁ ፡ ሰዎች ፡ ርእሰ ፡
ልቡናችሁን ፡ አታስታብዩ ።

፰ ፡ ባርኩዎ ፡ አሕዛብ ፡ ለአምላክነ ። ኤር ፡
፲፱-፲፭ ፡ ፲፯ ።

አሕዛብ ፡ ፈጣሪችንን ፡ አመስግኑት ፡
ማለት ፡ የተማራችሁትን ፡ አስተምሩ ።

ወአጽምዑ ፡ ቃለ ፡ ስብሐቲሁ ።

የጌትነቱንም ፡ ቃል ፡ አድምጡ ፡ ማለ
ት ፡ ያልተማራችሁትን ፡ ተማሩ ።

፱ ፡ ዘአንበራ ፡ ለነፍስየ ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ።

ሰውነቴን ፡ በሕይወት ፡ የሚያኖራት ፡
እሱ ፡ ነው ።

ወኢይሁቦን ፡ ሁከተ ፡ ለእገርየ ። መዝ ፡ ፻፳ ፡ ፫ ።

በወገኖቼ ፡ አንድም ፡ በሕዋሳቴ ፡ መ
ከራን ፡ አያመጣባቸውም ፡ ቢያመጣ
ባቸውም ፡ እንዳመጣባቸው ፡ አይቀ
ርም ።

፲ ፡ እስመ ፡ አመከርከነ ፡ እግዚኦ ።

አስፈትነው ፡ ወደፊት ፡ ነው ፡ ሁለት ፡
መቶ ፡ ዓሥራ ፡ አምስት ፡ ዘመን ፡
በግብፅ ፡ ፈትነኸናልና ።

ወፈተንከነ ፡ ከመ ፡ ይፈትንዎ ፡ ለብሩር ።

ወርቅ ፡ ብርን ፡ በእሳት ፡ እንዲፈት
ኑት ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዓሥራ ፡ አም
ስት ፡ ዓመት ፡ በመከራ ፡ ፈትነኸና
ልና ። ኢሳ ፡ ፵፰ ፡ ፲ ።

፲፩ ፡ ወአባዕከነ ፡ ውስተ ፡ መሥገርት ።

ዕኑ ፡ መከራ ፡ ወዳለበት ፡ ወደግብፅ ፡ አግብተኸናልና ።

ወአምጻእከ ፡ ሕማመ ፡ ድኅሬነ ፡

በፊታችን ፡ መከራ ፡ አምጥተኸብናልና ።

፲፪ ፡ ወአዕረግከ ፡ ሰብአ ፡ ዲበ ፡ አርእስቲነ ።

ጠላቶቻችን ፡ ግብፃውያን ፡ አሰልጥነኸብናልና ።

አኅለፍከነ ፡ ማዕከለ ፡ እሳት ፡ ወማይ ።

እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ስለተቀበልን ፡ ፈንታ ፡ በወሀና ፡ በእሳት ፡ መኻከል ፡ አሳለፍኸን ፡ መንገድ ፡ ፀራጊ ፡ ደመና ፡ አለ ፡ ሌሊት ፡ በደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሲያበራላቸው ፡ ያድራል ፡ ቀን ፡ ኀዳና ፡ ሲጠርግላቸው ፡ ይውላል ፡ ከወደ ፡ ኋላ ፡ ጠላት ፡ የተነሳባቸው ፡ እንደሆነ ፡ ረግረግ ፡ ሁኖ ፡ ያሠጥምላቸዋልና ።

ወአውፃእከነ ፡ ውስተ ፡ ዕረፍት ።

ወደ ፡ ዕረፍት ፡ ፍልስጥም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አወጣኸን ።

፲፫ ፡ እበውእ ፡ ቤተከ ፡ ምስለ ፡ መባዕየ ።

ግዱን ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ ዓሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ መባዬን ፡ ይዤ ፡ ማደሪያህ ፡ ወደምትሆን ፡ ወደቤተ ፡ መቅደስ ፡ እገባለሁ ።

እንድም ፡ (እስመ ፡ አመከርከነ) ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ በባቢሎን ፡ መከራ ፡ ፈትነኸናልና ፡ (ወፈተንከነ) ፡ ወርቅ ፡ ብርን ፡ በእሳት ፡ እንዲፈትኑት ፡ በመከራ ፡ ሥጋ ፡ ፈትነኸናልና ፡ (ወአባዕከነ) ፡ ዕኑ ፡ መከራ ፡ ወዳለበት ፡ ወደባቢሎን ፡ አግብተኸናልና ፡ (ወአምጻእከ) ፡ መከራ ፡ አምጽተኸብናልና ፡ (ወአዕዓንከ) ፡ ባቢሎናውያንን ፡ አሰልጥነህብናልና ፡ (አኅለፍከነ) ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ስለተቀበልን ፡ ፈንታ ፡ እሳትና ፡ ማይ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ከጠፉ ፡ መኻከል ፡ አወጣኸን ፡ እመኒ ፡ ዓዶከ ፡ ባሕረ ፡ አፍላጋትኒ ፡ ኢያሠጥሙከ ፡ ወእመኒ ፡ አዶከ ፡ እሳተ ፡ ነበልባልኒ ፡ ኢያውዕየከ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ አምላክከ ፡ ሀሎኩ ፡ ምስሌከ ፡ እንዲል ።

(ወአውፃዕከነ) ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አወጣኸን ፡ እበውእ ፡ ግዱን ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡ እገባለሁና ።

እንድም ፡ (እስመ ፡ አመከርከነ) ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ በባቢሎን ፡ ፈትነኸናልና ፡ (ወፈተንከነ) ፡ ወርቅ ፡ ብርን ፡ በእሳት ፡ እንዲፈትኑት ፡ ፈትነኸናልና ፡ (ወአባዕከነ) ፡ ዕኑ ፡ መከራ ፡ ወዳለበት ፡ ወደዕቶን ፡ እሳት ፡ አግብተኸናልና ፡ (ወአምጻዕከ) ፡ መከራ ፡ አምጥተህብናልና ፡ (ወአዕዓንከ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ አሠልጥነኸብናልና ፡ (አኅለፍከነ) ፡ እንዲህ እንዲህ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ስለተቀበልን ፡ ፈንታ ፡ በወሀና ፡ በእሳት ፡ መኻከል ፡ አሳለፍከን ፡ እሳት ፡ አለው ፡ በቀደመ ፡ ግብሩ ፡ ወሀ ፡ አለው ፡ በኋላ ፡ ግብሩ ፡ ወተለዓለ ፡ ነበልባል ፡ መጠነ ፡ አርብዓ ፡ በእመት ፡ ይላል ፡ እሳቱ ፡ ዓርባ ፡ ክንድ ፡ ወደላይ ፡ ተመገዘ ፡ ወዋዕአ ፡ ወወረደ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘስሙ ፡ ገብርኤል ፡ ይላል ፡ በበትረ ፡ ብርሃን ፡ ቢመታው ፡ እንዳደረ ፡ ውርጭ ፡ ሁኗል ፡ እንደገና ፡ ወውስተ ፡ እሳቱስ ፡ ይወድዩ ፡ ፒሳ ፡ ወቀለምጢ ፡ ወሰጠቀ ፡ ይላል ፡ የሰባውን ፡ እንጨት ፡ ወርካውን ፡ ቀልቋሉን ፡ ቅንጭቡን ፡ ጨምረውበታል ፡ (ወአውፃዕከነ) ፡ ወደከተማ ፡ አወጣኸን ። (እበውእ) ፡ ግዱን ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ እገባለሁና ። እንድም ፡ (እስመ ፡ አመከርከነ) ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በገሃነም ፡ ፈትነኸናልና ፡ (ወፈተንከነ) ፡ ወርቅ ፡ ብርን ፡ በእሳት ፡ እንዲፈትኑት ፡ በእሳተ ፡ ገሃነም ፡ ፈትነኸናል ፡ (ወአባዕከነ) ፡ ዕኑ ፡ መከራ ፡ ወዳለበት ፡ ወደገሃነም ፡ አግብተኸናል ፡ (ወአምጻእከ) ፡ በፊታችን ፡ ዕኑ ፡ መከራ ፡ አምጥተህብናልና ፡ (ወአዕዓንከ) ፡ አጋንንትን ፡ በጸላትነት ፡ አስነሥተህብናልና ፡ ሰብአ ፡ አላቸው ፡ በማደሯቸው ። እንድም ፡ ሰው ፡ በባሕርዩ ፡ እንዲራባ ፡ እነሱም ፡ በግብር ፡ ይራባሉና ፡ ይገዟቸዋልና ፡ (አኅለፍከነ) ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ስለተቀበልን ፡ ፈንታ ፡ ጥምቀትን ፡ ልጅነትን ፡ ሰጠኸን ፡ እንድም ፡ ባሕረ ፡ ገሃነምን ፡ አሻገርከን ፡ (ወአውፃእከነ) ፡ ወደገነት ፡ ወደመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አወጣኸን ፡ (እበውዕ) ፡ ግዱን ፡ ከአምስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ እገባለሁና ።



ወእሁብ ፡ ብፅዓትየ ፡ ዘነበብኩ ፡ በከናፍርየ ።

መከራ ፡ ባገኘኝ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ብታደርግልኝ ፡ ይህን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብዬ ፡ በአንደበቴ ፡ የተማልሁትን ፡ ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ስለቴን ፡ እሰጣለሁ ።

፲፬ ፡ ዘእቤ ፡ በከናፍርየ ፡ አመ ፡ ምንዳቤየ ።

በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ ባንደበቴ ፡ ይህን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብዬ ፡ የተማልሁትን ፡ እሰጣለሁ ።

መሥዋዕተ ፡ ንጹሐ ፡ ዘአልቦ ፡ ነውር ።

ያልተቀማ ፡ ያልተሠረቀውን ፡ ቀንዱ ፡ ያልተከረከረውን ፡ ጥፍሩ ፡ ያልዘረዘረውን ፡ ጠጉሩ ፡ ያላረረውን ፡ ነውር ፡ ነቀፋ ፡ የሌለበትን ፡ መሥዋዕት ፡ እሠዋለሁ ፡ እንድም ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ መብራት ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ዕጣን ፡ አቀርባለሁ ።

፲፭ ፡ አበውዕ ፡ ለከ ፡ ዕጣነ ፡ ምስለ ፡ ሐራጊት ።

ዕጣኑን ፡ ጊደሩን ፡ አቀርብልሃለሁ ፡ እንድም ፡ ዕጣን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብዬ ፡ ተስዬ ፡ እንደሆነ ፡ ጊደር ፡ እሰጣለሁ ። እንድም ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ዕጣን ፡ በግ

ሬ ፡ እጇ ፡ መብረት ፡ አቀርበለት ።

እሠውዕ ፡ ለከ ፡ አልሕምተ ፡ ወአጣሌ ።

ፍየልና ፡ በሬ ፡ እሠዋልሃለሁ ። እን ድም ፡ በግ ፡ እሠዋለሁ ፡ ብዬ ፡ ተስ ዬ ፡ እደሆን ፡ ፍየል ፡ በሬ ፡ ጨመሬ ፡ እሠዋለሁ ። እንድም ፡ በቀኝ ፡ እጇ ፡ መብረት ፡ በግሬ ፡ ዕጣን ፡ አቀርበ ለት ። ዘዐ ፡ ፹፩ ፡ ፩—፫ ። ዘሌ ፡ ፩ ፡ ፩—፲፯ ።

፲፯ ፡ ንዑ ፡ ስምዑኒ ፡ ወእነግርክሙ ።

እነግራችሁ ፡ አስተምራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፡ ምክሬን ፡ ትምርቴን ፡ ስሙ ፡

ኵልክሙ ፡ እለ ፡ ትፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ማን ፡ ማን ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ ዕገሌ ፡ ዕገሌ ፡ ምን ፡ አሰኝቶኝ ፡ እግዚአብሔ ርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የምትፈ ሩት ፡ መላችሁ ።

መጠነ ፡ ገብረ ፡ ላቲ ፡ ለነፍስየ ።

ዘገብረ ፡ ላቲ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ለሰውነቴ ፡ ያደረገላትን ፡ ያሀል ፡ እንዳደረገላት ።

፲፰ ፡ ዘጸራህክዎ ፡ ገቢሁ ፡ በአፉየ ።

ወደሱ ፡ መልሼ ፡ በንደበቴ ፡ የለመን ሁትን ፤

ወከላህክዎ ፡ በልሳንየ ።

በንደበቴ ፡ የለመንሁትን ፡ እንዳደረ ልኝ ፡ መጠን ፤

፲፱ ፡ እመሰ ፡ ነጸርኩ ፡ ዐመፃ ፡ ውስተ ፡ ልብየ ።

በልቡናዬ ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ በቃሌ ፡ መበደል ፡ በእጇ ፡ መግደል ፡ ቢኖር ብኝ ፤

ኢይሰምዓኒ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ልመናዬን ፡ ባልሰማ ኝም ፡ ነበር ።

፳ ፡ በእንተዝ ፡ ሰምዓኒ ፡ እግዚአብሔር ።

በልቡናዬ ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ በቃሌ ፡ መበደል ፡ በእጇ ፡ ሰው ፡ መግደል ፡ ባይኖርብኝ ። እግዚአብሔር ፡ ልመና ዬን ፡ ሰማኝ ፡ እንጂ ፡ እንዲህስ ፡ ቢኖ ርብኝ ፡ ባልሰማኝም ፡ ነበር ።

ወአጽምዓኒ ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ።

የልመናዬን ፡ ነገር ፡ ሰማኝ ።

፳፩ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኢከልዐኒ ፡ ጸሎትየ ።

ልመናዬን ፡ ቸል ፡ ያላለ ፡ ያላነጠበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

ወኢያርኃቀ ፡ ሣህሎ ፡ እምኔየ ።

ይቅርታውን ፡ ከኔ ፡ ኣላራቀምና ፡ እን ድም ፡ ይቅርታውን ፡ ከኔ ፡ ያላራቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።



## መዝሙር ፡ ፺፮ ።

፩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባርከነ ፡ ወይሣህለነ ።

ስለትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ እሥራ ኤል ፡ ከግብፅ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ሙሴና ፡ አሮንን ፤ እንትሙ ፡ ሙሴ ፡ ወአሮን ፡ ትባርክዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወ እነ ፡ አምላክሙ ፡ ዘእባርከሙ ፡ ይላ ል ፤ እላት ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ ትዳርጋላ ችሁ ፡ እኔ ፡ ፈጣሪቸው ፡ እነብራቸ ዋለሁ ፤ ብሏቸዋል ፡ እንደ ፡ ሞጅና ፡ እንደ ፡ አብረንታንት ፡ እንደ ፡ ዋል ድብ ፡ ከለ ፡ ገዳም ፡ በሕታውያን ፡ ለመ ፍትደ ፡ ደብር ፡ ወደዓለም ፡ ሲመጡ ፡ በዕድሜ ፡ በመዓርግ ፡ የሚበልጡ ፡ ሰይጣን ፡ ያደረበት ፡ ሰው ፡ አይግጠ መን ፡ ወደበዓታችን ፡ በደኅና ፡ ይመ ልሰን ፡ ይላሉ ፡ በዕድሜ ፡ በመዓርግ ፡ የሚያንሱ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ፤ ነጋድ ያን ፡ ከሀገራቸው ፡ ሲወጡ ፡ በሀብት ፡ በዕድሜ ፡ የሚበልጡ ፡ እኛን ፡ ገንዘ ባችንን ፡ መርከብ ፡ ተሠብሮ ፡ ከመ ሥጠም ፡ ከዳንደ ፤ ከወንበዴ ፡ ያድ ነን ፡ ይላሉ ፤ በሀብት ፡ በዕድሜ ፡ የሚ ያንሱት ፡ አሜን ፡ ይላሉ ፡ እንደዚህ ም ፡ ሁሉ ፡ ሌዋውያን ፡ እግዚአብሔ ር ፡ ተዋርደናልና ፡ ያክብረን ፡ አንስ ናልና ፡ ያብዛን ፡ ይላሉ ፡ አሜን ፡ ያለ በት ፡ ነው ፡ ሕዝቡ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ፡ እንድም ፡ (እግዚአብሔር ፡ ባርከነ ፡ ወተሣሃለነ) ፡ ተዋርደናልና ፡ አክብ ረን ፡ አንሰናልና ፡ አብዛን ፡ ይላሉ ፡ ሌዋውያኑ ፡ ሕዝቡ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ፡ ዘሌ ፡ ፱ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ። ዘኍ ፡ ፮ ፡ ፳፪—፳፯ ። ኤር ፡ ፵ ፡ ፲፱ ።

ወያርኢ ፡ ገጾ ፡ ላዕሌነ ፡ ወይሣሃለነ ።

ወንሕዮም ፡ ይላል ፤ ገጹ ፡ ምሕረት ፡ ገጹ ፡ ረድኤቱን ፡ ይገልጽልን ፡ ዘንድ ፡ እኛም ፡ ከመከራው ፡ እንድ ነ ፡ ዘንድ ፡ ይላሉ ፡ ሌዋውያኑ ፡ ሕዝቡም ፡ አሜ ን ፡ ይላሉ ።

፪ ፡ ከመ ፡ ናእምር ፡ በምድር ፡ ፍኖቶ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሥራህን ፡ እንድም ፡ ሕግህን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ወበኵሉ ፡ አሕዛብ ፡ አድኅኖቶ ።

በአሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ትድግናህን ፡ እና ውቅ ፡ ዘንድ ።

፫ ፡ ይገንዩ ፡ ለከ ፡ አሕዛብ ፡ እግዚኦ ። ሞ ፡ ፩ ።

አቤቱ ፡ እንዲህ ፡ ያደረግህ ፡ እንደ ሆነ ፡ በኛ ፡ ምክንያት ፡ አሕዛብ ፡ ይገ ዙልሃል ።

ይገንዩ ፡ ለከ ፡ አሕዛብ ፡ ኵሎሙ ።

ኹሉሙ ፡ ለማለት ፡ ደግሞታል ።

፬ ፡ ይትፌሥሑ ፡ ወይትሐሠዩ ፡ አሕዛብ ።

እስራኤል ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤

እስመ ፡ ትኴንኖሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ በርትዕ ።

አሕዛብን ፡ በውነት ፡ ትፈርድባቸዋ ለህና ።

መተርጕሙ ፡ ለሕዝብ ፡ በምድር ።

እስራኤልን ፡ ከፋርስ ፡ ከባቢሎን ፡ እ ውጥተህ ፡ መርተህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳ ሌም ፡ ታገባቸዋለህና ።

፳፡ ይትገነይ ፡ ለከ ፡ አሕዛብ ፡ እግዚኦ ። ይትገነዩ ፡ ለከ ፡ አሕዛብ ፡ ኵሎሙ ።

አቤቱ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ይገዙልሃል ፡ ቍ ፡ ፫ ።

፳፩ ምድርኒ ፡ ወሀበት ፡ ፍሬሃ ።

ኢየሩሳሌም ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ የዘሩባትን ፡ ታበቅላለች ፡ የተከሉባ ትን ፡ ታጸድቃለች ፡ እንድም ፡ ይህች ፡ ዓለም ፡ በሥን ፡ ፍጥረት ፡ ፍሬዋን ፡ አቀረበች ፡ እንድም ፡ ትሩፍ ፡ ሕግን ፡ እምልከን ፡ አቀረበች ፡ እንድም ፡ እ

መቤታችን ፡ ነፍሷን ፡ ሥጋዋን ፡ ለተ ዋህዶ ፡ አበቃች ፡ ይህስ ፡ መንገዱም ፡ (መንደሩም) ፡ እይደል ፡ ያልተያያዘ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ምእመን ፡ ሃይማኖት ፡ ም ግባርን ፡ ይዞ ፡ ተገኝች ።

ወይባርከነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያከብረ ናል ፡ ይበዛናል ፡ እንድም ፡ ያከብረን ፡ ያብዛን ።

፳፪ ወይባርከነ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ያከብረን ፡ ያብዛን ።

ወይፈርህዎ ፡ ኵሎሙ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ።

ይፈርሁዎሙ ፡ ይላል ፡ በረቱ ፡ መን ግን ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ ያፍሩታል ፡ ይፈሩት ።

መዝሙር ፡ ፷፯ ።

፩፡ ይትንሣእ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይዘረዉ ፡ ፀሩ ።

ስለትሩፋን ፡ ተናገሮታል ፡ የምእመ ናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ እሥራኤል ፡ ከግብፅ ፡ ሲወጡ ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ ጠቢት ፡ ከሚነሱበት ፡ ተንሥእ ፡ እግ ዚእ ፡ ወይዘረው ፡ ፀርከ ፡ ወይጉየዩ ፡ ኵሎሙ ፡ እምቅድመ ፡ ገጽከ ፡ ይላ ሉ ፡ ማታ ፡ ከሚሰፍሩበት ፡ ተመየጥ ፡ እግዚእ ፡ ላዕለ ፡ እሥራኤል ፡ ሕዝብ ከ ፡ በእልፍ ፡ ወበአዕላፍ ፡ እያሉ ፡ ይ ጸልዩ ፡ ነበረ ፡ በየጊዜው ፡ ሥርዓት ፡ መለዋወጥ ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ ዳዊት

ም ፡ ከቤተ ፡ አቤዳራ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮ ንን ፡ ይዞ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ተናግ ሮታል ፡ ትንቢት ፡ አድርገህ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በ ሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ይነሣል ፡ አሕዛ ብም ፡ ይጠፋሉ ፡ ትእዛዝ ፡ አድርገህ ፡ ይነሣ ፡ አሕዛብም ፡ ይጥፉ ፡ ቍ ፡ ፶፱ ፡ ፵፱ ።

ወይጕየዩ ፡ ጸላእቱ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ።

ይጕይዩም ፡ ይላል ፡ ከመዓቱ ፡ መገ ለጽ ፡ የተነሣ ፡ አሕዛብ ፡ ይጠፋሉ ፡ ይጕየዩ ፡ ይጥፉ ።



ዐረገ ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡ ፄዊወከ ፡ ፄዋ ፡ ወወሀብከ ፡ ጸጋከ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ መዝሙር ፡ ፷፯ ።



ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ መዝሙር ፡ ፷፯ ።

፰፤ ከመ ፡ የሐልቅ ፡ ጢስ ፡ ከማሁ ፡ የሐልቁ ።

ጢስ ፡ ወጥቶ ፡ ወጥቶ ፡ እንዲጠፋ ፡ ከዚህ ፡ ደረሰ ፡ እንዳይባል ።

ወከመ ፡ ይትመሰው ፡ ሰምዕ ፡ እምቅድመ ፡ ገጸ ፡ እሳት ።

በእሳት ፡ ፊት ፡ በእሳት ፡ አንጻር ፡ ያለ ፡ ሰም ፡ የዶሮ ፡ ማር ፡ ቀልጦ ፡ እንዲ ጠፋ ።

ከማሁ ፡ ይትሐጐሉ ፡ ኃጥአን ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የኀልቁና ፡ ይትሐጐሉ ፡ አንድ ፡ ወገ ን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገጸ ፡ መዓቱ ፡ ከመገለጹ ፡ የተነሣ ፡ አሕዛብ ፡ ይጠ ፋሉ ፡ ይኀልቁ ፡ ይትሐጐሉ ፡ ይጥፉ ፡ ኢሳ ፡ ፳፱ ፡ ፱ ።

፱፤ ወጻድቃንሰ ፡ ልትፈሥሑ ።

ትሩፋን ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወይትሐሠዩ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ በወቀወ ፡ ነገር ፡ የእ ግዚአብር ፡ ባለሟል ፡ በመሆን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወይትፌሥሑ ፡ በሐሤት ።

በፍጹም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ ይላ ቸዋል ።

፲፤ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወዘምሩ ፡ ለ ስሙ ።

እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ ስሙ ንም ፡ አመግስኑ ፡ ለስሙ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።

ፍኖተ ፡ ገበሩ ፡ ለዘዓርገ ፡ እንተ ፡ ዓረብ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ስሙ ።

ስሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚባል ፡ ከ ዓረብ ፡ ፋርስ ፡ ትሩፋንን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለወጣ ፡ ለእግዚአብሔ ር ፡ ምሥጋና ፡ አቅርቡ ፡ አንድም ፡ ፍኖተ ፡ ልቡናችሁን ፡ ጽረጉ ፡ አንድ ም ፡ ፍኖቶ ፡ ግበሩ ፡ ይላል ፡ ሕጉን ፡ ጠብቁ ፤

አንድም ፡ ይትነሣእ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ይነሣ ል ፡ ይነሣ ፡ ጠላቶቹ ፡ አጋንንት ፡ አይ ሁድ ፡ መናፍቃን ፡ ይጠፋሉ ፡ ይጥፉ ፡ (ወይጉዩ) ፡ ገጸ ፡ መዓቱ ፡ ከመገለጹ ፡ የተነሣ ፡ ይጠፋሉ ፡ ይጥፉ ፡ (ከመ ፡ የሐልቅ ፡ ጢስ) ፡ ወጥቶ ፡ ወጥቶ ፡ እንዲጠፋ ፡ ከዚህ ፡ ደረሰ ፡ እንዳይባ ል ፡ (ወከመ ፡ ይትመሰው) ፡ በእሳት ፡ አንጻር ፡ ያለ ፡ ሰም ፡ የዶሮ ፡ ማር ፡ ቀልጦ ፡ እንዲጠፋ ፡ (ከማሁ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሰ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ከመነሣቱ ፡ የተ ነሣ ፡ አጋንንት ፡ አይሁድ ፡ መናፍቃ ን ፡ ይጠፋሉ ፡ ይጥፉ ፡ (ጻድቃንሰ) ፡ ጻድቃን ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ (ወ ይትሐሠዩ) ፡ እግዚአብሔር ፡ ባወቀ ው ፡ ነገር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባለሟ

ል ፡ በመሆን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ (ወ
ይትፌሥሑ) ፡ በፍጹም ፡ ተድላ ፡ ደ
ስታ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ (ሰብሕዎ) ፡
እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ፡ ለስ
ሙም ፡ ምሥጋና ፡ አቅርቡ ፡ (ፍኖተ ፡
ግበሩ) ፡ ስሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚ
ባል ፡ ከአረብ ፡ ሲኦል ፡ ነፍሳትን ፡
ይዞ ፡ ለወጣ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሥ
ጋና ፡ አቅርቡ ።

ወተፈሥሑ ፡ በቅድሜሁ ፡

እግዚአብሔር ፡ በወቀው ፡ ነገር ፡ የእ
ግዚአብሔር ፡ ባለሟል ፡ በመሆን ፡
ደስ ፡ ይበላችሁ ።

ወይደንግጹ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ።

ይትነሣእ ፡ ወይደንግጹ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡
ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በሥራ ፡ በመ
ፍረድ ፡ ይነሳል ፡ አሕዛብ ፡ ይጠፋሉ ፡
አንድም ፡ ይነሣ ፡ ይጥፉ ፡ አንድም ፡ አ
ምስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡
ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡
ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡
አድሮ ፡ ይነሣል ፡ ይነሣ ፡ አጋንንት ፡
አይሁድ ፡ መናፍቃን ፡ ይጠፉሉ ፡ ይ
ጥፉ ፡ ኢሳ ፡ ፳፱ ፡ ፪ ።

፭፡ አብ ፡ ለዕጓለ ፡ ማውታ ፡ ወመኰንኖን ፡ ለዕ
ቤራት ።

እናት ፡ አባቱ ፡ ለሞቱበት ፡ ለድኻው ፡
አባት ፡ ለባልቴቶቹ ፡ የሚፈርድላ
ቸው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ፈርዶ ፡ ልብስ ፡
ምግብ ፡ ይሰጣቸዋል ።

እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደሱ ።

እግዚአብሔር ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡
ከፋርስ ፡ ከባቢሎን ፡ ትሩፋንን ፡ ይዞ ፡
ጉዞው ፡ ወደ ኢየሩሳሌም ፡ ነው ፡ እን
ድም ፡ ከአምስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡
መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ከገሃነም ፡ ነፍ
ሳትን ፡ ይዞ ፡ ጉዞው ፡ ወደ ፡ መንግ
ሥተ ፡ ሰማያት ፡ ነው ።

፮፡ እግዚአብሔር ፡ ያኃድሮሙ ፡ ለባሕታው
ን ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ።

እግዚአብሔር ፡ ትሩፋንን ፡ በኢየሩ
ሳሌም ፡ ምእመናንን ፡ በገነት ፡ በመ
ንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ያኖራቸዋል ።

ወያወፅኦሙ ፡ ለሙቁሓን ፡ በኃይሉ ።

ታስረው ፡ በመከራ ፡ የተያዙትን ፡ ሁ
ለቱን ፡ ነገድ ፡ በከሃሊነቱ ፡ ከባቢሎን ፡
ያወጣቸዋል ።

ከማሁ ፡ ለምሩራን ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ መቃ
ብር ።

ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ከባቢሎን ፡ እንዳወ
ጣቸው ፡ በቈላተ ፡ ገዘር ፡ ያሉትን ፡
እሥሩን ፡ ነገድም ፡ ከቈላተ ፡ ገዘር ፡
ያወጣቸዋል ፡ ዘመን ፡ በገዛቶባቸዋል ፡
መከራ ፡ አፅንተው ባቸዋል ፡ በቦታ ፡
አርቀዋቸዋልና ፡ ምሩራን ፡ አላቸው ፡
አንድም ፡ (ወያወጽኦሙ) ፡ በሐልዮ ፡
ፍዳ ፡ የተያዙትን ፡ ከገሃነም ፡ ያወጣ
ቸዋል ፡ (ከማሁ) ፡ በሐልዮ ፡ ፍዳ ፡ የተ
ያዙትን ፡ እንዳወጣቸው ፡ በነቢብ ፡ በ
ገቢር ፡ የተያዙትንም ፡ ያወጣቸዋል ፡



በሐልዮ ፡ ከሚቀበሉት ፡ ፍዳ ፡ በነቢ
ብ ፡ በገቢር ፡ የሚቀበሉት ፡ ፍዳ ፡ ይፀ
ናልና ።

፯፡ እግዚኦ ፡ አመ ፡ ወፃእከ ፡ ቅድመ ፡ ሕዝ
ብከ ።

አቤቱ ፡ የሕዝቡ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሁነህ ፡
በወጣህበት ፡ ወራት ።

ወአመ ፡ እንተ ፡ ገዳም ፡ ገለፍከ ።

ወይገዳመ ፡ ግብፅ ፡ በወጣህበት ፡ ወ
ራት ።

፰፡ ምድርኒ ፡ አድለቅለቀት ፡ ወሰማይኒ ፡ አን
ጠብጠበ ።

ግብፅ ፡ ተናወጠች ፡ ማለት ፡ ተሳቦ ፡
ቀንዳማ ፡ ትል ፡ ጓጉንቸር ፡ ዝጉል ፡
ልብሱ ፡ አወጣች ፡ ዘፀ ፡ ፰ ፡ ፫ ። ሰማይም ፡
እሳት ፡ በረድ ፡ አዘነመ ፡ ዘፀ ፡ ፱ ፡ ፳፫ ።
አንድም ፡ (ምድርኒ) ፡ የግብፃውያን ፡
ትሑታኑ ፡ (ሰማይኒ) ፡ ልዑላኑ ፡ ጠፉ ፡
አንድም ፡ (እግዚእ) ፡ አቤቱ ፡ የሕዝ
ቡ ፡ ሁሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሁነህ በወ
ጣህበት ፡ ወራት ፡ (ወአመኒ) ፡ ወይገ
ዳመ ፡ ኤርትራ ፡ በወጣህበት ፡ ወራት ፡
(ምድርኒ) ፡ ኤርትራ ፡ እንደ ፡ የብስ ፡
ሆነች ፡ ማለት ፡ ከሁለት ፡ ከሦስት ፡
ተከፈለች ፡ ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፳፪ ። (ወሰማይኒ) ፡
ወይደንን ፡ እንተ ፡ ተድባብ ፡ እንዲ
ል ። ከላይ ፡ እንደ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡
ከታች ፡ እንደ ፡ ተራዳ ፡ በቀኝ ፡ በግ
ራ ፡ እንደ ፡ ግድግዳ ፡ ሆኖላቸው ፡ ተ
ሻግረዋልና ። አንድም ፡ ለእስራኤል ፡
እንደ ፡ ግድግዳ ፡ ፀንታ ፡ የነበረች ፡
ኤርትራ ፡ በግብፃውያን ፡ ፈረሰች ፡
ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፳፯ - ፳፰ ።

አንድም ፡ (እግዚእ) ፡ የሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡
ፊታውራሪ ፡ ሁነህ ፡ በወጣህበት ፡ ወ
ራት ፡ ወአመኒ ፡ ወይገዳመ ፡ ኢሉን ፡
በወጣህበት ፡ ወራት ፡ (ምድርኒ) ፡ ወፀ ፡
ከጭንጫ ፡ ፈለቀላቸው ፡ ዘፀ ፡ ፲፯ ፡ ፲፫ ፡ ፲፩ ፡
(ወሰማይኒ) ፡ መና ፡ ከደመና ፡ ወረደ
ላቸው ። ዘፀ ፡ ፲፮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ።

አንድም ፡ (እግዚእ) ፡ የሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡
ፊታውራሪ ፡ ሁነህ ፡ በወጣህበት ፡ ወ
ራት ፡ (ወአመኒ) ፡ ወይገዳመ ፡ ሲና ፡
በወጣህበት ፡ ወራት ፡ (ምድርኒ) ፡ ደ
ብረ ፡ ሲና ፡ ተናወፀች ፡ (ወሰማይኒ) ፡
ሰማያዊ ፡ ሕግ ፡ ተወረ ፡ ዘፀ ፡ ፲፱ ፡ ፲፰ ።

እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለአምላኩ ፡ ሲና ።

የሲና ፡ ፈጣሪ ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ገጽ ፡ ከመገለጹ ፡ የተነሣ ።
አንድም ፡ (እግዚእ) ፡ የሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡
በዙር ፡ ሁነህ ፡ በወጣህ ፡ ጊዜ ፡ (ወአ
መኒ) ፡ ወይገዳመ ፡ ቀራንዮ ፡ በወጣህ ፡
ጊዜ ፡ (ወምድርኒ) ፡ በምድር ፡ አራት ፡
(ወሰማይኒ) ፡ በሰማይ ፡ ሦስት ፡ ተአ
ምራት ፡ ተደረገ ። ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፵፭-፶፫ ።
አንድም ፡ (እግዚእ) ፡ የሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡
በዙር ፡ ሁነህ ፡ በወጣህ ፡ ጊዜ ፡ (ወአ
መኒ) ወይመስቀልም ፡ በወጣህ ፡ ጊዜ ፡
(ምድር ፡ ወሰማይ ፡ አድለቅለት) ፡ ት
ስብዕት ፡ ከመለኮት ፡ ጋራ ፡ ተወጋ ፡
(ሰማይ ፡ ወምድር ፡ አንጠብጠበ) ፡

መለከት ፡ ከትስብዕት ፡ ጋሬ ፡ ጥሩ ፡
ወሀ ፡ ትኩስ ፡ ደም ፡ አፈሰሰ ፡ ጉቱ ፡
፹፯ ፡ ፶ ። ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፴፬ ።
(ወእምቅድመ ፡ ገጹ) ፡ በአጋንንት ፡
በአይሁድ ፡ በመናፍቃን ፡ ገጹ ፡ መዓ
ቱ ፡ በምእመናን ፡ ገጹ ፡ ምሕረቱ ፡ ከመ
ገለጹ ፡ የተነሣ ፡ ዘር ፡ ነው ፡ (እምቅድ
መ ፡ ገጹ ፡ ለእምላከ ፡ እስራኤል) ።
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ ገጹ ፡ ምሕረቱ ፡
ከመገለጹ ፡ የተነሣ ፡ ኢሳ ፡ ፷፱ ፡ ፲፰ ።

፲፣ ዝናመ ፡ ዘእምፈቃዱ ፡ ዘፈለጠ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ለርስትከ ።

ዝናም ፡ ዘፈለጥከ ፡ በፈቃድከ ፡ ሲል ፡
ነው ፡ ከደመና ፡ ለየኸው ፡ ዝናም ፡ ለ
ፍጥረትህ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

እመኒ ፡ ደከመ ፡ አንተ ፡ ታፀንዖ ።

ቢደክምም ፡ አንተ ፡ ታፀናዋለህ ፡ በዝ
ናም ፡ ድካም ፡ ኑሮበት ፡ አይደለም ፡
አንድ ፡ ቀን ፡ ዘንሞ ፡ ይቅር ፡ አትል
ም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እንዲዘንም ፡ ታደ
ርገዋለህ ፡ አንድም ፡ ባንድ ፡ ሀገር ፡
ዘንሞ ፡ እንዲቀር ፡ አታደርገውም ፡
ባሬቱ ፡ መዓዘን ፡ እንዲዘንም ፡ ታደ
ርገዋለህ ፡ እንጂ ፡ አንድም ፡ በደጋ ፡
ብቻ ፡ ዘንሞ ፡ እንዲቀር ፡ አታደርገ
ውም ፡ በቈላም ፡ እንዲዘንም ፡ ታደር
ገዋለህ ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ደመና ፡ እንደ ፡
ወንፈት ፡ እንደ ፡ ወንጠፍት ፡ ያለ ፡
ነው ፡ እንዲህ ፡ ከሆንሁ ፡ ብሎ ፡ ከማ
ናቸውም ፡ በታ ፡ አያዘንብምም ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ከዘዘበት ፡ አገር ፡ ይዘን

ማል ፡ እንጂ ፡ ወኢይሠጠጥ ፡ ደመ
ናሁ ፡ እንዲል ።

፲፩ ፡ እንስሳከ ፡ የኀድሩ ፡ ውስቴቱ ።

ፍጥረትህ ፡ ሁሉ ፡ በዝናም ፡ ፀንተው ፡
ይኖራሉ ።

አስተዳሎከ ፡ ለነዳያን ፡ በኂሩትከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ በይቅርታህ ፡ በቸርነትህ ፡ ዝ
ናሙን ፡ ለነዳያን ፡ አዘጋጀህላቸው ።
አንድም ፡ ዝናም ፡ ከብዕብዕነቱ ፡ የለ
የኸው ፡ መና ፡ ለእስራኤል ፡ ነው ፡
(እመኒ) ፡ ቢደክም ፡ አንተ ፡ ታፀናዋ
ለህ ፡ በመናው ፡ ድካም ፡ ኑሮበት ፡
አይደለም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ዘንሞ ፡
ይቅር ፡ አትልም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እን
ዲዘንም ፡ ታደርገዋለህ ፡ እንጂ ፡ ሲል ፡
ነው ፡ ይህ ፡ መና ፡ በእሳት ፡ ቢቆሉ
ትም ፡ ቢቀቅሉትም ፡ ቢጋግሩትም ፡
አይቀልጥም ፡ ፀሐይ ፡ የነካው ፡ እን
ደሆነ ፡ግን ፡ ይቀልጣል ፡ (ወእምከመ ፡
ሠረቀ ፡ ፀሐይ ፡ ይመሐው ፡ መና ፡ በን
ስቲት ፡ ላህበ ፡ ፀሐይ ፡ ተመዊቆ ፡
ከመ ፡ ይትአመር ፡ እስመ ፡ ዘኢያማ
ስኖ ፡ እሳት) ፡ እንዲል ።
(እንስሳከ) ፡ እስራኤል ፡ በመናው ፡ ፀን
ተው ፡ ይኖራሉ ፡ (አስተዳሎከ) ፡ በቸ
ርነትህ ፡ መናውን ፡ ለእስራኤል ፡ አዘ
ጋጀህላቸው ፡ አንድም ፡ (ዝናም) ፡
በቸርነትህ ፡ ከሕገ ፡ አሪት ፡ የለየኸው ፡
አሪት ፡ ወንጌል ፡ ለእስራኤል ፡ ለም
እመናን ፡ ነው ፡ (እመኒ) ፡ ቢደክምም ፡



አንተ ፡ ታፀናዋለህ ፡ በሕግ ፡ ድካም ፡
ኑሮበት ፡ አይደለም ፡ ከሬቱ ፡ ባሕር
ያት ፡ የተፈጠረ ፡ ሰው ፡ ደካማ ፡ ነው
ና ፡ እንዲፀና ፡ ታደርገዋለህ ፡ ሲል ፡
ነው ፡ (እንስሳከ) ፡ ምእመናን ፡ በሕግ ፡
ፀንተው ፡ ይኖራሉ ፡ (አስተዳሎከ) ፡
በቸርነትህ ፡ ለምእመናን ፡ ሕግን ፡ አዘ
ጋጀህላቸው ።

፲፪፣ እግዚአብሔር ፡ ይሁቦሙ ፡ ቃለ ፡ ለእለ ፡
ይዜንዉ ፡ ኃይለ ፡ ብዙኀ ። ኢሳ ፡ ፶ ፡ ፱ ።

እግዚአብሔር ፡ ይሁቦሙ ፡ ኃይለ ፡
ብዙኅ ፡ ለእለ ፡ ይዜንዉ ፡ ቃለ ፡ ብለ
ህ ፡ ግጠም ፡ እግዚአብሔር ፡ አሪትን ፡
ለሚያስተምሩ ፡ ለነቢያት ፡ ለካህናት ፡
ተአምራትን ፡ ወንጌልን ፡ ለሚያስተ
ምሩ ፡ ለሐዋርያት ፡ ለሰብዓ ፡ አርድ
ዕት ፡ ኃይለ ፡ ቃልን ፡ ይሰጣቸዋል ።

፲፫፣ ንጉሠ ፡ ኃያላን ፡ ለፍቁሩ ።

እንደ ፡ ዛሬ ፡ ሳይሆን ፡ የኃያላኑ ፡ ን
ጉሥ ፡ ለወዳጁ ፡ ድሩግ ፡ ነበር ።

ለፍቁሩ ፡ ወለሥን ፡ ቤትከ ፡ ተካፈልን ፡ ምህርከ ።

ለፍቁርከ ፡ ወለሥን ፡ ቤትከ ፡ ሲል ፡
ነው ፡ ለፍቁርከ ፡ ለንጉሡ ፡ ወለሥን ፡
ቤትከ ፡ ለሌቀ ፡ ካህናቱ ፡ የሚገባውን ፡
ሰጥተን ፡ ምርኮውን ፡ ተካፍለን ፡ እን
ኖር ፡ ነበር ፡ ንጉሡ ፡ ከስድስት ፡ አን
ድ ፡ ይወስድ ፡ ነበር ፡ ከጦር ፡ ከጓዝ ፡
የዋሉ ፡ እኩል ፡ ይከፈላሉ ፡ ሌዋው
ያን ፡ ካህናት ፡ ከጓዝ ፡ ከዋሉ ፡ ከሃ
ምሳ ፡ አንድ ፡ ይወስዱ ፡ ነበር ፡ ሌቀ ፡
ካህናቱ ፡ ከጦር ፡ ከዋሉ ፡ ከምስት ፡
መቶ ፡ አንድ ፡ ይወስድ ፡ ነበር ።

፲፬፣ እመኒ ፡ ቤትክሙ ፡ ማእከለ ፡ መዋርስት ።

ሰብአ ፡ ገባዖን ፡ ወደ ፡ ወረዒት ፡ ወደ
ሚም ፡ ዕፃ ፡ ብትደርሱ ።

ክንፈ ፡ ርግብ ፡ ዘብሩር ፡ ዘግቡር ።

በወርቅ ፡ በብር ፡ የተሠራች ፡ ጣዖት
ን ፡ ታገኛላችሁ ።

ወገበዋቲሃኒ ፡ በሐመልሚለ ፡ ወርቅ ።

ጐንና ፡ ጐኗ ፡ በወርቅ ፡ መሸቢያ ፡ የተ
ያዘ ።

፲፭፣ እመ ፡ አዘዘ ፡ ሰማያዊ ፡ ንጉሥ ፡ ላዕሌሃ ።

ኪያሃ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እሷን ፡ አጥፋ ፡
ብለህ ፡ ባዘዝኸን ፡ ጊዜ ፡ አጥፍተን ፡
ነበር ፡ የቀድሞ ፡ ፈጻምያንነታችንን ፡
እይ ፡ ተመልከት ፡ እንዲህ ፡ አይተህ ፡
ተመልክተህ ፡ አውጣን ፡ አንድም ፡
አውጣን ፡ እንጂ ፡ የዛሬውን ፡ ለምን ፡
ታየዋለህ ።

አንድም ፡ (እመኒ ፡ ቤትክሙ) ፡ ሰብ
አ ፡ ከነዓን ፡ ወደ ፡ ወረዒት ፡ ወደ ፡
ሴም ፡ ዕፃ ፡ ብትደርሱ ፡ (ክንፈ ፡ ርግ
ብ) ፡ ጽሪት ፡ ሕግ ፡ ታገኛላችሁ ፡ (ወገ
በዋቲሃኒ) ፡ ሕገጋቷ ፡ በኢታምልክ ፡
የፀኑ ፡ (እመ ፡ አዘዘ) ፡ ኪያሃ ፡ ሲል ፡
ነው ፡ እሷን ፡ ጠብቁ ፡ ብለህ ፡ ባዘዝ
ኸን ፡ ጊዜ ፡ ጠብቀን ፡ ነበር ፡ የቀድ
ሞውን ፡ ሕግ ፡ መጠበቃችንን ፡ እይ ፡
ተመልከት ፡ እንዲህ ፡ አይተህ ፡ ተመ

ልክተህ ፡ አውጣን ፡ እንጂ ፡ የዛረው
ን ፡ ለምን ፡ ታየዋለህ ።

አንድም ፡ (እመኒ) ፡ ሰብአ ፡ ከነዓን ፡
ወደወረዷት ፡ ወደሴም ፡ ዕፃ ፡ ብትደ
ርሱ ፡ (ከነፈ ፡ ርግብ) ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋ ፡
ንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ ንጽሐ ፡ ልቡና ፡ የያዘ
ች ፡ ድንግል ፡ ታገኛላችሁ ፡ (ወገበ
ዋቲሃኒ) ፡ ልቡናዋ ፡ በይኩነኒ ፡ የፀና ፡
(እመ ፡ አሀዘ) ፡ በሷ ፡ ሥጋ ፡ የነገሥ
ሀ ፡ ንጉሥ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሷ ፡ ተወ
ልጄ ፡ አድናችኋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ፡
ቀረን ፡ ብለን ፡ ይላል ፡ የችኩላ ፡ እነ
ጋገር ።

በረድ ፡ ይዘንም ፡ ላዕለ ፡ ሰልሞን ።

ፀሰልሞን ፡ በረድ ፡ ይዘንማል ፡ ሰል
ሞን ፡ ምጽራየ ፡ በረድ ፡ ነው ፡ መላእ
ክት ፡ ጥሩ ፡ ጥሩውን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
አዝንመው ፡ በረድ ፡ በረዱን ፡ ከዚያ ፡
ያዘንሙታል ፡ አንድም ፡ በረዱን ፡
አስቀድመው ፡ ከዚያ ፡ አዝንመው ፡
ጥሩውን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያዘንሙታል ፡
አንድም ፡ በረድ ፡ ጦራችን ፡ በአሕ
ዛብ ፡ ይዘንብባቸዋል ፡ አንድም ፡ ዘን
መኑ ፡ ከድንኳናችን ፡ ብዛት ፡ ከልብ
ሶችን ፡ ጽርየት ፡ የተነሣ ፡ በእሥራ
ኤል ፡ ከተማ ፡ በረድ ፡ ዘንሟልን ፡
ይባል ፡ ነበር ፡ አንድም ፡ በረድ ፡ ትምር
ታችን ፡ በአሕዛብ ፡ ይዘንምባቸዋል ፡
ይላሉ ፡ ሐዋርያት ።

፲፭ ፡ ደብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ደብር ፡ ጥሉል ።

የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ የሚሆን ፡
ትሩፋ ፡ በረድኤት ፡ የለመለመ ፡ ነው ።
አንድም ፡ ምእመን ፡ በልጅነት ፡ የለ
መለመ ፡ ነው ።

ደብር ፡ ርጉዕ ፡ ወደብር ፡ ጥሉል ።

ርጉዕ ፡ ትሩፋ ፡ በሃይማኖት ፡ የፀና ፡
ጥሉል ፡ በረድኤት ፡ የለመለመ ፡ ነው ።
አንድም ፡ ርጉዕ ፡ ምእመን ፡ በሃይማ
ኖት ፡ የፀና ፡ ጥሉል ፡ በልጅነት ፡ የለ
መለመ ፡ ነው ።

፲፯ ፡ ለምንት ፡ ይትነሥኡ ፡ አድባር ፡ ርጉዓን ።

በኢየሩሳሌም ፡ ፀንተው ፡ ይኖሩ ፡ የነ
በረ ፡ ሰብአ ፡ ከነዓን ፡ ከሀገራቸው ፡
ወጥተው ፡ ለምን ፡ ይሔዳሉ ፡ ቢሉ ፡
(ብትል) ።

ደብር ፡ ዘሰምር ፡ እግዚአብሔር ፡ የኀድር ፡ ውስ
ቴቱ ።

እግዚአብሔር ፡ የወደደው ፡ ትሩፋ ፡
ወርሷት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ (እል
ሃለሁ) ፡ ብዬ ፡ እመልስልሃለሁ ።

እስመ ፡ የኀድሮን ፡ እግዚአብሔር ፡ እስከ ፡ ለዝሉፉ ።

እግዚአብሔር ፡ ለዘላለሙ ፡ አድሮብ
ቸው ፡ ይኖራልና ።

አንድም ፡ (ለምንት ፡ ይትነሥኡ) ፡
በኢየሩሳሌም ፡ ፀንተው ፡ የሚኖሩ ፡
እሥራኤል ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወጥተ
ው ፡ ለምን ፡ ይሔዳሉ ፡ ቢሉ ፡ (ደብር ፡
ዘሠምሮ) ፡ ቢበድሉ ፡ አይደለም ፡ ቢ
መለሱ ፡ ወርሰዋት ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡
ነው ።



አንድም ፡ (ለምንት) ፡ በይሁዳ ፡ በሰ
ማርያ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ እነ ፡ አጀም ፡
ክንታ ፡ ከይሁዳ ፡ ከሰማርያ ፡ ለምን ፡
ወጥተው ፡ ይሔዳሉ ፡ ቢሉ ፡ (ደብር) ፡
እግዚአብሔር ፡ የወደደው ፡ ትሩፋ ፡
ወርሷት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።
አንድም ፡ ለምንት ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡
ፀንተው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ አጋንንት ፡
ከሰው ፡ ልቡና ፡ ወጥተው ፡ ለምን ፡
ይሔዳሉ ፡ ቢሉ ፡ (ውስቴቱ ፡ ለደብር ፡
ዘሠምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይኀድር) ፡
ብለህ ፡ አቅና ፡ ማደሪያው ፡ በሚሆን ፡
በምእመን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያድር
በት ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ (እስመ ፡ የ
ኀድሮን) ፡ አድሮባቸው ፡ ይኖራልና ።

፲፯ ፡ ሠረገላቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምእል
ፊተ ፡ አዕላፍ ፡ ፍሡሓን ፡ ኤር ፡ ፪ ፡ ፲፫ ።

የብዙ ፡ ብዙ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደ
ሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ እስራኤል ፡ ከንዷት ፡
ቀን ፡ በቀር ፡ ኃዘን ፡ አላገኛቸውም ፡
ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ይኖራሉ ፡ እንጂ ፡
እስራኤል ፡ ከግብፅ ፡ ወጥተው ፡ ዮር
ዳኖስን ፡ ከተሻገሩ ፡ በኋላ ፡ ኢያሱ ፡
ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ እስከሁን ፡
ያገኘነውን ፡ ገንዘብ ፡ ለየመፍቅዳችን ፡
ስናደርገው ፡ መጣን ፡ እንግዲህ ፡ ወ
ዲህ ፡ ያገኛችሁትን ፡ ገንዘብ ፡ ለቤተ ፡
እግዚአብሔር ፡ ይሁን ፡ አታጥፉ ፡
ምንም ፡ ቢሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገ
ንዘብ ፡ ነውና ፡ ብሎ ፡ አዋጅ ፡ ነገረ ፡
አካን ፡ ወልደ ፡ ከርሚ ፡ ይለዋል ፡ አ
ሦር ፡ ምዝምዝ ፡ ወርቅ ፡ ዓሬት ፡
ኅብር ፡ አምስተኛ ፡ በወርቅ ፡ የተሠ
ራች ፡ መዳ ፡ ግምጃ ፡ አግኝቶ ፡ እፍ
ቀርኩ ፡ ተውላጠኪ ፡ ለዚችስ ፡ ለው
ጥ ፡ እሰጣለሁ ፡ እንጂ ፡ እሷን ፡ አልሰ
ጥም ፡ ብሎ ፡ ከተራዳ ፡ ሥር ፡ ሠውሮ ፡
አኖረ ፡ ከኢያሪኮ ፡ አጠገብ ፡ ጋይ ፡
የምትባል ፡ አገር ፡ አለች ፡ አጥፍታ
ችኍ ፡ ኑ ፡ ብሎ ፡ ሰደዳቸው ፡ ወዲ
ያው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ረድኤተ ፡
እግዚአብሔር ፡ ተለያቸውና ፡ አሕ
ዛብ ፡ አግባ ፡ መልስ ፡ ብለው ፡ ፈጅተ
ዋቸዋል ፡ ሠላሳ ፡ ያህል ፡ ኃያላን ፡ አ
ለቁባቸው ፡ ኢያሱ ፡ ከደብተራ ፡ እ
ሪት ፡ ገብቶ ፡ ለምንት ፡ አዕድዎ ፡ አዕ
ደዎሙ ፡ ገብርከ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ሚጠ ፡
ዘበና ፡ እሥራኤል ፡ ዲበ ፡ ፀሩ ፡ ይ
ላል ፡ ምድረ ፡ ርስትን ፡ ላታወርሳቸው ፡
ዮርዳኖስን ፡ አሻግረህ ፡ ለምን ፡ አመጣ
ኻቸው ፡ እንግዲህማ ፡ ወዲህ ፡ እስ
ራኤል ፡ ፊቱን ፡ መለሰ ፡ አንገቱን ፡
ቀለሰ ፡ የአሕዛብ ፡ መዘበቻ ፡ ሊሆን ፡
አይደለምን ፡ እያለ ፡ ይፀድቅ ፡ ይነግ ፡
ጀመረ ።

አንተ ፡ ከተናገርከው ፡ ያስቀረ ፡ አለና ፡
ያን ፡ ተመራምረህ ፡ ካላጠፋህ ፡ በረ
ድኤት ፡ አላድርብህ ፡ አለው ፡ ሌዋ
ውያኑን ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ አልብሶ ፡
ከፀባብ ፡ ሥፍራ ፡ ሁኖ ፡ በየነገዳችሁ ፡
እለፉ ፡ አላቸው ፡ ከነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ሲ
ደርስ ፡ ጠቆረ ፡ ከአካን ፡ ወልደ ፡ ከር

ሚን ፡ ሲደርስ ፡ ተነፋ ፡ እቀደድ ፡ እቀ
ደድ ፡ አለ ፡ ወዲያው ፡ እንተነህ ፡ ያ
ዘው ፡ ያዘው ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ ፡
ተራምዶ ፡ ይዘ ፡ እመኖ ፡ ወልድየ ፡
እመኖ ፡ ልጄ ፡ ምን ፡ አድርገሃል ፡ ን
ገረኝ ፡ አለው ፡ አሥር ፡ ምዝምዝ ፡
ወርቅ ፡ ዓሬት ፡ ጎብር ፡ አምስተኛ ፡
በወርቅ ፡ የተሠራ ፡ መጎ ፡ ግምጃ ፡
አግኝቼ ፡ ግምጋሜውን ፡ እሰጣለሁ ፡
ብዬ ፡ አትሬአለሁ ፡ አለው ፡ ለግምጃ
ውስ ፡ ግምጋሚ ፡ እሰጣለሁ ፡ አልህ ፡
ለወርቁ ፡ ምን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብለህ ፡
አስቀረኸው ፡ አለው ፡ ምላሽ ፡ አጣ ፡
ቂላቱ ፡ ኢሚቃኮር ፡ ከሚባል ፡ በረት ፡
ወስዶ ፡ ጉድጓድ ፡ አስቆፍሮ ፡ ከነወ
ገኑ ፡ ከነገንዘቡ ፡ እሳት ፡ አስነድዶ ፡
አስጨምሮታል ። ኢያ ፡ ፯ ፡ ፩-፳፮ ።

እግዚአብሔር ፡ ውስቴቶን ፡ በሲና ፡ መቅደሱ ።

በሲና ፡ በተሠራች ፡ መቅደሱ ፡ አድሮ ፡
የሚኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ አድሮባ
ቸው ፡ ይኖራል ።

፲፰ ፡ ዓረገ ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡ ፄዊወከ ፡ ፄዋ ።

እስራኤልን ፡ ይዘህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳ
ሌም ፡ ወጣህ ።

ወወሀብከ ፡ ፀጋከ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ።

ለእስራኤልም ፡ ሚጠትን ፡ ሰጠሃቸው ።

እስመ ፡ ይክህዱ ፡ ከመ ፡ ይሕድሩ ።

ሚጠትን ፡ በትሰጣቸው ፡ ይክዱ ፡ ነበ
ርና ፡ እንዳይክዱ ፡ በሃይማኖት ፡ ፀን
ተው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ሚጠትን ፡ ሰ
ጠሃቸው ፡ እንድም ፡ (ዓረገ) ፡ እስራ
ኤልን ፡ ከግብፅ ፡ የፍትር ፡ ምርኮ ፡ ማ
ርከህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጣህ ፡
(ወወሀብከ) ፡ ለሰብአ ፡ ገባዖን ፡ ድኅ
ነትን ፡ ሰጠሃቸው ፡ ታሪክ ፡ እንዳለፈ
ው ፡ መዝ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ፡ ኢያ ፡ ፱ ፡ ፩-፳፯ ። ፲፮-፲፰ ፡
፳፯ ። (እስመ ፡ ይክህዱ) ፡ በሀገራቸው ፡
መኖርን ፡ ወደደው ፡ አገራቸውን ፡
መክዳ ፡ ይወድዳሉና ፡ እንድም ፡ አገ
ራቸውን ፡ እስከ ፡ መክድ ፡ ደርሰው ፡
በገራቸው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አገራቸ
ውን ፡ ሰጠኻቸው ፡ እንድም ፡ ለጎዲ
ር ፡ ለከሐድያን ፡ ይላል ፡ በሀገራቸው ፡
መኖርን ፡ ለሚወዱ ፡ አገራቸውን ፡
ለሚከዱ ፡ ለሰብአ ፡ ገባዖን ፡ አገራቸ
ውን ፡ ሰጠኻቸው ።

እንድም ፡ (ዓረገ) ፡ ነፍሳትን ፡ ይዘህ ፡
ከሲኦል ፡ ወደገነት ፡ ወጣህ ፡ (ወወ
ሀብከ) ፡ ለምእመናን ፡ ልጅነትን ፡ ሰጠ
ኻቸው ፡ (እስመ ፡ ይክህዱ) ፡ ልጅነ
ትን ፡ ባትሰጣቸው ፡ ይክዱ ፡ ነበርና ፡
እንዳይክዱ ፡ በሃይማኖት ፡ ፀንተው ፡
ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ልጅነትን ፡ ሰጠኻቸ
ው ። መሳ ፡ ፭ ፡ ፲፪ ። ዳን ፡ ፯ ፡ ፱ ። ሉቃ ፡
፳፬ ፡ ፵፱ ፡ ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፰ ፡ ቆላ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ። ዕብ ፡
፪ ፡ ፳፬ ። ራእ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ፡ ፲-፲፭ ።

፲፱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ቡሩክ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ክቡር ፡
ምስጉን ፡ ነው ፡ እንድም ፡ ይክበር ፡ ይ
መስገን ፡ አብራም ፡ ቡሩኩ ፡ ለእግዚ



አብሔር ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘእግብዓ ፡ ጸላእት ፡ ንጉሥ ፡ ውስተ ፡
እዴሁ ፡ እንዲል ።

ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ መዋዕል ።

እግዚአብሐር ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡
ለዘላለሙ ፡ ይመስገን ።

፳ ፡ ይረድአነ ፡ አምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ።

ድኅነታችንን ፡ የሚያደርግልን ፡ ፈጣ
ሪያችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይረ
ዳናል ።

አምላክነሰ ፡ አምላክ ፡ አድኅኖ ።

የኛስ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ድኅነታችንን ፡
የሚያደርግልን ፡ ነው ፡ ድኅነታችን
ን ፡ የሚያደርግልን ፡ ፈጣሪያችን ፡
ነው ።

ወፍናዊሁኒ ፡ ለሞት ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ።

የሞት ፡ ጎዳና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጎዳ
ና ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጎዳና ፡
የሞት ፡ ጎዳና ፡ ነው ። ኢዮ ፡ ፭ ፡ ፲፫-፳፪ ።

፳፩ ፡ ወባሕቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰብር ፡ አር
እስተ ፡ ጸላእቱ ።

ባሕቱ ፡ ዋዌ ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡
በሞት ፡ የጠላቶቹን ፡ ቸብቸቦ ፡ ያጠ
ፋበታል ። እንድም ፡ (ወፍናዊሁኒ ፡
ለሞት ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ) ፡
[illegible] ፡ አምላክ ፡ አድኅኖ ፡ ብዬ
[illegible] ነገር ፡ ሞትንም ፡ የሚያስተብ
[illegible] ው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ግደል ፡
አትግደል ፡ ብሎ ፡ (ወባሕቱ) ፡ ነገር ፡
ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሞት ፡ የጠላ
ቶቹን ፡ ቸብቸቦ ፡ ያጠፋበታል ።

ወበዘተግ ፡ በእርቶሙ ፡ የሐውር ፡ ጌጋዮሙ ።

ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ይ
ሄዳል ። መከራ ፡ የሚመጣው ፡ በኃጢ
አታቸው ፡ ነውና ፡ ጌጋይ ፡ አለው ። እን
ድም ፡ ጣዖታቸው ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡
ይሔዳል ፡ በሀገራችን ፡ ሠናያን ፡ ነገ
ሥታት ፡ ሲዘምቱ ፡ ታቦት ፡ አሲዘው ፡
እንዲዘምቱ ፡ እነሱም ፡ ጣዖት ፡ አሲ
ዘው ፡ ይዘምታሉና ፡ እንድም ፡ ኃጢ
አታቸው ፡ ከራስ ፡ ፀጉራቸው ፡ ይበ
ዛል ፡ እንድም ፡ የምእመናን ፡ ኃጢ
አታቸው ፡ በበኩራቸው ፡ በክርስቶ
ስ ፡ ያሰረያል ፡ ንሕነ ፡ አባል ፡ ወው
እቱ ፡ ርእስ ፡ እንዲል ።

፳፪ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢይእቲ ፡ እንግብእ ።

እስራኤልን ፡ ይገፎ ፡ ከግብፅ ፡ ከወ
ጣሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ እመለሳ
ለኁ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ።

ወእትመየጥ ፡ እንተ ፡ ቀላየ ፡ ባሕር ።

እገብእ ፡ ወእትመየጥ ፡ ብለህ ፡ ግጠ
ም ፡ እስራኤልን ፡ ይዘህ ፡ ከግብፅ ፡
ከወጣህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ትመ
ለስ ፡ ዘንድ ፡ ምናለህ ።

፳፫ ፡ ከመ ፡ ይሲረያ ፡ እገሪከ ፡ በደም ።

ፈርዖንን ፡ እነሳስተህ ፡ እጅህ ፡ እግ
ርህ ፡ በደም ፡ ይታለል ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡

እንድም ፡ (ይቤ ፡ እግዚአብሔር) ፡ እስራኤልን ፡ ይገር ፡ ከኤርትራ ፡ ከወጣሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኤርትራ ፡ ከወሰሰሁ ፡ (ወእትመየጥ) ፡ እመን ፡ ይዘህ ፡ ከኤርትራ ፡ እስራኤል ላማ ፡ ወደ ፡ ኤርትራ ፡ ከወጣህ ፡ በኋድ ፡ በኤርትራ ፡ ትመለስ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ አለህ ፡ (ከመ ፡ ይሴረያ) ፡ ከፈርዖን ፡ ጋራ ፡ ተጣልተህ ፡ ፈርዖንን ፡ አስጥመህ ፡ እጅህ ፡ እግርህ ፡ በደም ፡ ይታለል ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንድም ፡ (ይቤ ፡ እግዚአብሔር) ፡ ከሲኦል ፡ ነፍሳትን ፡ ይገር ፡ ከወጣሁ ፡ በኋላ ወደሲኦል ፡ እመለሳለሁ ፡ (ወእትመየጥ) ፡ ነፍሳትን ፡ ይዘህ ፡ ከሲኦል ፡ ከወጣህ ፡ በኋላማ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ትመለስ ፡ ዘንድ ፡ በሲኦል ፡ ምን ፡ አለህ ፡ (ከመ ፡ ይሴረያ) ፡ ዲያብሎስን ፡ ድል ፡ ነስተህ ፡ እጅህ ፡ እግርህ ፡ በደም ፡ ይታለል ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ድል ፡ ማድረጉን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ የገዳይ ፡ ምልክቱ ፡ ደም ፡ በጣቱ ፡ እንዲሉ ፡ ቀጥቀጥክምሙ ፡ ለፀርየ ፡ ወተነዝኃ ፡ ደሞሙ ፡ ዲበ ፡ አልባስየ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ (ይቤ) ፡ ከመቃብር ፡ ከተነሣሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ እመለሳለሁ ፡ (ወእትመየጥ) ፡ ከመቃብር ፡ ከተነሣህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ትመለስ ፡ ዘንድ ፡ በመቃብር ፡ ምን ፡ አለህ ፡ (ከመ ፡ ይሴረያ) ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ አጥፍተህ ፡ እጅህ ፡ እግርህ ፡ በደም ፡ ይታለል ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

እንድም ፡ (ይቤ) ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ከረግኍ ፡ በኋላ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ እመለሳለኍ ፡ (ወእትመየጥ) ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ከረግህ ፡ በኋላ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ትመለስ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምን ፡ አለህ ፡ (ከመ ፡ ይሴረያ) ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ አሳልፈህ ፡ እጅህ ፡ እግርህ ፡ በደም ፡ ይታለል ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በደም ፡ አለ ፡ ዓሠረ ፡ ቅንዋቱን ፡ ዓሠረ ፡ ርግዘቱን ፡ እትራቱን ፡ ሳያጠፋ ፡ ይመጣልና ፡ ኢይደምሰስ ፡ ልዑል ፡ ዓሠረ ፡ ርግዘት ፡ ዘገበሁ ፡ ወአሠረ ፡ ቅንዋት ፡ ዘእደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ እንዲል ። ለአባ ፡ ጳኵሚስ ፡ እንደ ፡ ታያቸው ፡ በጸሎታቸው ፡ ይመኩ ፡ ነበር ፡ ጌታ ፡ መጥቶ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መከራ ፡ መቀበልህ ፡ ለማን ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ አላቸው ፡ ላንተ ፡ ብዬ ፡ ነዋ ፡ አሉት ፡ በነጋው ፡ ጌታ ፡ መስቀል ፡ ተሸክሞ ፡ ታያቸው ፡ ሁለተኛ ፡ መስቀልህ ፡ ለማን ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ አሉት ፡ ላንተ ፡ ብዬ ፡ ነዋ ፡ አላቸው ፡ እንዲህ ፡ ማድረጉ ፡ ትላንት ፡ በተናገርሁት ፡ አይደለምን ፡ አላበጀሁም ፡ ብለው ፡ ተመልሰዋል ፡ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ መምጣቱ ፡ ለአዘክሮ ፡ በቀል ፡ በኃጥአን ፡ ለአዘክሮ ፡ እሤት ፡ ለጻድቃን ፡ ነው ።

ልሳን ፡ ከለባቲክ ፡ ላዕለ ፡ ጸላዕቱ ።

የሙሴ ፡ የአሮን ፡ እንደበት ፡ በረድ ፡ ይገዝንም ፡ እሳት ፡ ይወረድ ፡ ብሎ ፡ መጸለዩ ፡ በግብፃውያን ፡ ላይ ፡ ነው ።



እንድም ፡ የሙሴ ፡ የአሮን ፡ የእስራኤል ፡ እንደበት ፡ በግብፃውያን ፡ ሥጥመት ፡ የበበ ፡ ዘመረ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ንሴብሖ ፡ ብሎ ፡ አመሰገነ ፡ እንድም ፡ የምእመናን ፡ እንደበት ፡ በአጋንንት ፡ በአይሁድ ፡ በመናፍቃን ፡ ድል ፡ መነሣት ፡ የበበ ፡ ዘመረ ፡ ውሻ ፡ ለጌታው ፡ እንዲገዛ ፡ እነሱም ፡ ሕጉን ፡ ይጠብቃሉና ፡ ከለበት ፡ አላቸው ።

፳፱ ፡ አበተርአየ ፡ ፍናዊከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ጐዳናህ ፡ በኤርትራ ፡ ተገለጸ ፡ እንድም ፡ ሕግህ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተገለጸ ።

ፍናዊሁ ፡ ለአምላክነ ፡ ለንጉሥ ፡ ዘውስተ ፡ መቅደስ ።

ፍናም ፡ ሕግም ፡ ያልሁት ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሚመሰገን ፡ የፈጣሪያችን ፡ የንጉሣችን ፡ መንገድ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

፳፮ ፡ በጽሑ ፡ መላእክት ፡ ወበሙ ፡ መዘምራን ።

ሙሴ ፡ አሮን ፡ ለምስጋና ፡ ደረሱ ፡ ሰብዓ ፡ ሊቃናትም ፡ አሏቸው ።

ማዕከለ ፡ ደናግል ፡ ዘባጥያተ ፡ ከበሮ ።

ከበሮውን ፡ እያስማሙ ፡ ከሚመቱ ፡ ከነማርያም ፡ እኅተ ፡ ሙሴ ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ከተሻገሩ ፡ በኋላ ፡ ግብፃውያን ፡ ቢደርሱ ፡ ወህው ፡ ሳይገጥም ፡ ገመገም ፡ መስሎ ፡ አገኙት ፡ እስራኤልን ፡ ያሻገረ ፡ የሀገራችን ፡ ወህ ፡ እኛን ፡ አያሻግረንምን ፡ ብለው ፡ ለከ ፡ ለለከ ፡ ተያይዘው ፡ ገቡ ፡ እስራኤል ፡ ይህን ፡ አይተው ፡ እንግዲህማ ፡ በገባንበት ፡ ገብተው ፡ በወጣንበት ፡ ወጥተው ፡ ሊያጠፉን ፡ አይደለምን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ሸሽተዋል ፡ የኋላው ፡ ጭራው ፡ ሲቀር ፡ የፊተኛው ፡ ገሮሮው ፡ ሲዘልቅ ፡ ጌታ ፡ ሙሴን ፡ ዝብጣ ፡ ለባሕር ፡ በበትርከ ፡ አለው ፡ ቢመታት ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡ እንደ ፡ ግድግዳ ፡ የነበረው ፡ ባሕር ፡ ገጥሞ ፡ ሰጥመዋል ፡ ጠላቶቻችን ፡ ግብፃውያን ፡ ሰጠሙ ፡ ብለው ፡ ፈረሰኛ ፡ ሰድደው ፡ የፊተኞችን ፡ መልሰዋቸዋል ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ የወንድ ፡ ማርያም ፡ እኅተ ፡ ሙሴ ፡ የሴት ፡ ቀንቃኝ ፡ ሁነው ፡ ንሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስቡሐ ፡ ዘተሰብሐ ፡ ብለው ፡ አመስግነዋል ። ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ። እንድም ፡ (በጽሑ) ፡ ሐዋርያት ፡ ለምስጋና ፡ ደረሱ ፡ (ወበሙ) ፡ ሰብዓ ፡ አርድእት ፡ አሏቸው ፡ (ማዕከለ ፡ ደናግል) ፡ ሰባ ፡ ሕያት ፡ ሰባሒ ፡ ይላል ፡ ሥጋ ፡ ከነ ፡ እያሉ ፡ ከሚያመሰግኑ ፡ ከሠላሳ ፡ ስድስቱ ፡ ቅዱሳት ፡ አንስት ፡ ጋራ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፴ ።

፳፯ ፡ በማኅበር ፡ ባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ። ወለአምላክነ ፡ በአንቅዕተ ፡ እስራኤል ።

በማኅበር ፡ እንቅዕተ ፡ እስራኤል ፡ ባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ የእስራኤል ፡ አለቆች ፡ መሰብሰቢያ ፡ በሚሆን ፡ በጉባዔ ፡ አንድነት ፡ ሁናችሁ ፡ ፈጣሪያችን ፡

2014 04 17

እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑት ፡ አን ድም ፡ ወሀው ፡ ለእስራኤል ፡ በመ ከፈሉ ፡ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔ ርን ፡ በጉባዔ ፡ አመስግኑት ።

፳፯ ፡ ሀየ ፡ ብንያም ፡ ወሬዛ ፡ በኃይሉ ።

ወሀው ፡ ለእስራኤል ፡ በተከፈለ ፡ ጊዜ ፡ ብንያማዊ ፡ ኤሎ ፡ ከዝያ ፡ ነበረ ፡ እስራኤል ፡ የሚጓዙ ፡ በየነገዳቸው ፡ እንደ ፡ ትውልዳቸው ፡ ነው ፡ የነገደ ፡ ብንያም ፡ የቤት ፡ አለቃ ፡ ዔሎ ፡ ይባ ላል ፡ መንገድ ፡ ፀራጊ ፡ ደጀን ፡ ሆኖ ፡ ውሎ ፡ ነበረ ፡ ዓሥራ ፡ አንዱ ፡ ነገድ ፡ በፊት ፡ ደረሱ ፡ ወሀው ፡ ተከፍሎ ፡ ገመገም ፡ መስሎ ፡ አገኙት ፡ ተንዶ ፡ ያሰጥመናል ፡ ብለው ፡ ፈርተው ፡ ተቀ ምጠው ፡ ሳሉ ፡ ኋላ ፡ ነገደ ፡ ብንያም ፡ ደርሶ ፡ ምን ፡ ሁናችሁ ፡ ተቀምጣች ኋል ፡ አላቸው ፡ እንደምታየው ፡ ወ ሀው ፡ ተከፍሎ ፡ ፈርተን ፡ የሚሻገር ፡ ጠፍቶ ፡ አሉት ፡ ወሀ ፡ ከጭንጫ ፡ አፍልቆ ፡ መና ፡ ከደመና ፡ አውርዶ ፡ የመገበኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ባሕር ፡ ከፍሎ ፡ ተሻገር ፡ ቢለኝ ፡ አይሆንም ፡ አላልኁ ን ፡ ብሎ ፡ ልብሱን ፡ ከሥራ ፡ ሁለት ፡ ቀድዶ ፡ ላሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እስ ራኤል ፡ ሰጥቶ ፡ እሱ ፡ ቀድሞ ፡ ገብቶ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ተሻግሯል ፡ የቀሩት ፡ እሱን ፡ አብነት ፡ አድርገው ፡ ተሻግ ረዋልና ፡ ወሀው ፡ ከሦስት ፡ ተከፍ ሏል ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ አራት ፡ አራ ቱ ፡ ነገድ ፡ ከራት ፡ ተከፍሏል ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ሦስት ፡ ሦስቱ ፡ ነገድ ፡ ተሻ ግረዋል ፡ አንድም ፡ ዓሥራ ፡ አንዱን ፡ ነገድ ፡ ብንያም ፡ ድል ፡ አድርጓቸዋ ልና ፡ ይህስ ፡ አይደለም ፡ የመቅሠፍ ት ፡ ነው ፡ አልተጠቀሙበትም ፡ በኋ ላ ፡ ጠፍተውበታል ፡ ብሎ ፡ ሺዊትን ፡ በወጋ ፡ ጊዜ ፡ ብንያማዊ ፡ አይሎ ፡ ውሎ ፡ ነበርና ፡ አንድም ፡ ከነገደ ፡ ብንያም ፡ የተወለደ ፡ ሳኦል ፡ ከዚያ ፡ ነበር ፡ በጎበ ፡ ሐረ ፡ ይበውዕ ፡ እን ዲል ፡ በሔደበት ፡ ድል ፡ ሳያደርግ ፡ አይመለስም ፡ ነበርና ። አንድም ፡ ከነ ገደ ፡ ብንያም ፡ የተወለደ ፡ ጳውሎስ ፡ ከዚያ ፡ ነበር ፡ ወይመጡዎሙ ፡ ለአይ ሁድ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ደማስቆ ፡ ይላል ፡ በደማስቆ ፡ የነበሩ ፡ አይሁን ፡ ተከራ ክሮ ፡ ምላሽ ፡ ያሳጣቸው ፡ ነበርና ።

መላእክተ ፡ ይሁዳ ፡ መላፍንቲሆሙ ።

አለቆቻቸው ፡ ከነገደ ፡ ይሁዳ ፡ የተወ ለዱ ፡ ናቸው ፡ ከነገደ ፡ ይሁዳ ፡ የተ ወለዱ ፡ አለቆቻቸው ፡ ናቸው ፡ አን ድም ፡ መምሮቻቸው ፡ ከነገደ ፡ ይሁ ዳ ፡ የተወለዱ ፡ ሐዋርያት ፡ ናቸው ፡ ከነገደ ፡ ይሁዳ ፡ የተወለዱ ፡ ሐዋር ያት ፡ መምሮቻቸው ፡ ናቸው ።

መላእክተ ፡ ዛብሎን ፡ ወመላእክተ ፡ ንፍታሌም ።

ከነገደ ፡ ዛብሎን ፡ ከነገደ ፡ ንፍታሌም ፡ የተወለዱ ፡ አለቆቻቸው ፡ ናቸው ፡ አለቆቻቸው ፡ ከነገደ ፡ ዛብሎን ፡ ከነ ገደ ፡ ንፍታሌም ፡ የተወለዱ ፡ ናቸው ፡



አንድም ፡ ከነገደ ፡ ዛብሎና ፡ ከነገደ ፡ ንፍታሌም ፡ የተወለዱ ፡ ሐዋርያት ፡ መምሮቻቸው ፡ ናቸው ፡ መምሮቻ ቸው ፡ ከነገደ ፡ ዛብሎን ፡ ከነገደ ፡ ንፍታሌም ፡ የተወለዱ ፡ ሐዋርያት ፡ ናቸው ።

፳፰ ፡ አዝዝ ፡ እግዚኦ ፡ በኃይልከ ።

አቤቱ ፡ ሚጠቱን ፡ በከሃሊነትህ ፡ እ ዘዝ ።

ወአጽንዖ ፡ እግዚኦ ፡ ለዝንቱ ፡ ዘሠራዕከ ፡ ለነ ።

አቤቱ ፡ ይህንም ፡ ያደረግኸውን ፡ ሚ ጠቱን ፡ አፅናው ።

፳፱ ፡ ውስተ ፡ ጽርሕከ ፡ ዘኢየሩሳሌም ።
ለከ ፡ ያመጽኡ ፡ ነገሥት ፡ አምኃ ፡ ኢሳ ፡ ፲፰ ፡ ፯ ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በኢየሩ ሳሌም ፡ ወደ ፡ ተሠራች ፡ ወደቤተ ፡ መቅደስህ ፡ ነገሥታቱ ፡ እጅ ፡ መን ሻውን ፡ ይዘው ፡ ይቀርባሉ ።

፴ ፡ ገሥፆሙ ፡ ለአራዊተ ፡ ሀለት ።

የቀርከሃ ፡ እባቦች ፡ ባቢሎናውያን ፡ አጥፋቸው ፡ የቀርከሃ ፡ እባብ ፡ ቅጠ ል ፡ እየበላ ፡ መልኩ ፡ ቅጠል ፡ ይመ ስላል ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ሲያደርስ ፡ ኃይሉን ፡ ለመፈተን ፡ ሁለቱን ፡ ሦስ ቱን ፡ ቀርከሃ ፡ በመኻል ፡ ሠንጥቆት ፡ ይሔዳል ፡ ከቀርከሃውም ፡ ውስጥ ፡ የሚቀር ፡ አለ ፡ ባቢሎናውያንም ፡ ኃይለኞች ፡ ናቸውና ።

ማኅበረ ፡ አልህምት ፡ ውስተ ፡ እጐላተ ፡ሕዝብ ።

የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ትሩፋን ፡ በባቢሎናውያን ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተያዙ ፡ እንዳይቀሩ ።

ከመ ፡ ኢይትዓፀዉ ፡ እለ ፡ ፍቱናን ፡ ከመ ፡ ብሩር ።

ማኅበረ ፡ አልኅምት ፡ እለ ፡ ፍቱናን ፡ ከመ ፡ ብሩር ፡ ከመ ፡ ኢይትዓፀው ፡ ውስተ ፡ እጓላተ ፡ ሕዝብ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ወርቅ ፡ ብርን ፡ በእሳት ፡ እን ዲፈትኑት ፡ በእሳተ ፡ መከራ ፡ የተፈ ተኑ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያ ዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ትሩፋን ፡ በመከራ ፡ ተይዘው ፡ (እንደ ፡ ተያዙ) ፡ እንዳይ ቀሩ ፡ ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፲፱ ።

ዝርዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ቀትለ ።

እምባ ፡ ጓሮ ፡ ወዳጆች ፡ ባቢሎናው ያንን ፡ አጥፋቸው ።

፴፩ ፡ ይምጽኡ ፡ ተናብልት ፡ እምግብጽ ።

አማላጆች ፡ አጓደጆች ፡ እንገብራለን ፡ እንቀቅላለን ፡ የሚሉ ፡ ይምጡ ።

ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የምድያ ም ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ይዘው ፡ ይቀርባሉ ፡ ከኛ ፡ ወዲያ ፡ ያሉ ፡ ግብፃ ውያን ፡ ሲገብሩ ፡ ከዚህ ፡ እኛ ፡ አንገ ብርም ፡ እንላለንን ፡ ብለው ።

፴፪ ፡ ነገሥተ ፡ምድር ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገሥታት ፡ እግዚአ ብሔርን ፡ አመሰገኑት ።

መዘምሩ ፡ ለአምላክነ ።

ለፈጣሪያችን ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።

፴፫ ፡ ዘምሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘዓርገ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ።

እስራኤልን ፡ ይዞ ፡ ከግብፅ ፡ ወደ ኢየሩሳሌም ፡ ለወጣ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ።

ሰማይ ፡ ዘመንገለ ፡ ጽባሕ ።

ይህችውም ፡ ግብፅ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ምዕራብ ፡ ናት ፤ አንድም ፡ (ዘምሩ) ፡ ትሩፋንን ፡ ይዞ ፡ ከፋርስ ፡ ወደ ኢየሩሳሌም ፡ ለወጣ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፤ እሱን ፡ አመስግኑ ፤ (ሰማይ) ፡ ይችውም ፡ ፋርስ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ምዕራብ ፡ ናት ፤ ምነው ፡ ፋርስ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ምሥራቅ ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ምዕራብ ፡ ናትና ፡ እንዲህን ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ አንዱ ፡ ላዱ ፡ ምዕራብ ፡ ነውና ፤ አንድም ፡ (ዘምሩ) ፡ ነፍሳትን ፡ ይዞ ፡ ከሲኦል ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ለወጣ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፤ እሱን ፡ አመስግኑ ፤ (ሰማይ) ፡ ይህችውም ፡ ሲኦል ፡ ለገነት ፡ ምዕራብ ፡ ናት ።

አንድም ፡ (ዘምሩ) ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ በኩል ፡ ላረገ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ እሱን ፡ አመስግኑ ፤ (ሰማይ) ፡ ይህችውም ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ምሥራቅ ፡ ናት ፡ ጽባሒ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ይላታልና ።

ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵፱ ።

ናሁ ፡ ይሁብ ፡ ቃሎ ፡ ቃለ ፡ ኃይል ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ አሕዛብ ፡ ይጥፉ ፡ እሥራኤል ፡ ይዳኑ ፡ ብሎ ፡ ቃሉን ፡ ያሰማል ፤ አንድም ፡ ኃያል ፡ አብ ፡ አካላዊ ፡ ቃሉን ፡ በሥጋ ፡ ይወጣል ፤ አንድ ፡ ወልድ ፡ ተወልዶ ፡ ወንጌልን ፡ ያስተምራል ፤ ሕጊቱ ፡ ምንም ፡ የሦስቱ ፡ ብትሆን ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ የወራት ፡ መደበኛዋ ፡ ወልድ ፡ ነውና ፤ ቃሎ ፡ ብሎ ፡ ገርገሩን ፡ ለሱ ፡ ብቻ ፡ ሰጥቶ ፡ ተናገረ ፤ አንድም ፡ በምጽአት ፡ ንዑ ፡ ሑሩ ፡ ብሎ ፡ ቃሉን ፡ ያሰማል ።

፴፬ ፡ ሀቡ ፡ አኰቴተ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ።

ላዕለ ፡ እስራኤል ፡ ዐቢይ ፡ ስብሐቲሁ ።

በእስራኤል ፡ ጉባኤ ፡ የሚመሰገነው ፡ ምስጋና ፡ ፍጹም ፡ ነውና ።

ወኃይሉኒ ፡ እስከ ፡ ደመናት ።

ከሃሊነቱም ፡ ደመናትን ፡ እስከ ፡ መፍጠር ፡ ደርሶ ፡ ታወቀ ፤ አንድም ፡ ልዑላኑን ፡ በመፍጠር ፡ ታወቀ ። አንድም ፡ ብዛቱን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፴፭ ፡ መንክር ፡ እግዚአብሔር ፡ በላዕለ ፡ ቅዱሳኒሁ ።

እግዚአብሔር ፡ በወዳጆቹ ፡ አድሮ ፡ የሚመሰገነው ፡ አንድም ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ድንቅ ፡ ነው ።

አምላኩ ፡ እስራኤል ፡ ውእቱ ፡ ይሁብ ፡ ኃይለ ፡ ወጽንዐ ፡ ለሕዝቡ ።

የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እሱ ፡ ለወገኖቹ ፡ ኃይልን ፡ ፅንዕን ፡ ይሰጣቸዋል ።

ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ።

ይህን ፡ ያደረገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፳፱ ።



መዝሙር ፡ ፷፰ ።

፩ ፡ አድኅነኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ በጽሑኒ ፡ ማያት ፡ እስከ ፡ ነፍስየ ።

ስለመቃብያን ፡ ተናገሮታል ፤ የጌታም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ አቤቱ ፡ ማዕበሉ ፡ በሞገዱ ፡ ሰውነቴን ፤ አንድም ፡ (እስከ ፡ ርእስየ) ፡ ይላል ፡ ራሴን ፡ እስከ ፡ ማስጠም ፡ ደርሷልና ፤ ከሥጥመት ፡ አድነኝ ፤ አንድም ፡ ጦሩ ፡ ሰውነቴን ፡ እስከ ፡ ማጥፋት ፡ ደርሷልና ፡ ከመከራው ፡ ከጦሩ ፡ አድነኝ ፤ ዮና ፡ ፪ ፡ ፮ ።

፪ ፡ ጠጋዕኩ ፡ ውስተ ፡ ዕሙቅ ፡ ቀላይ ፡ ወኃይል ፡ አልቦቱ ። ሰቆ ፡ ፫ ፡ ፶፬ ።

ከጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ዘገጥሁ ፡ ዋኘቼ ፡ የምወጣበት ፡ ኃይል ፡ የለኝም ፤ አንድም ፡ ተማርኬ ፡ ወደ ዕርዕ ፡ ወረደሁ ፡ ተዋግቼ ፡ የምመጣበት ፡ ኃይል ፡ የለኝምና ፡ አድነኝ ።

በጽሑኒ ፡ ውስተ ፡ ማዕምቀ ፡ ባሕር ፡ ወአውሎ ፡ አሥጠመኒ ።

ከባሕር ፡ አሂሬ ፡ ደረስሁ ፤ አሂሬ ፡ ባሕር ፡ ቀብሮ ፡ አስቀረኝ ፤ አንድም ፡ ተማርኬ ፡ ከከተማው ፡ ደረስሁ ፡ አንጥያኮስ ፡ ውጦ ፡ አስቀረኝ ።

፫ ፡ ወሳሕኩ ፡ በከልሖ ፡ ወሰሐከኒ ፡ ጉርዔየ ።

ብጮህ ፡ ብጮህ ፡ ጉሮሮዬ ፡ ደከመ ፤ አንድም ፡ ሰለለ ፡ ሻከረ ።

ደከማ ፡ አዕይንትየ ፡ እንዘ ፡ እሴፎ ፡ ለአምላኪየ ፤

ፈጣሪዬን ፡ ተስፋ ፡ ሳደርገው ፡ ዓይኖቼ ፡ ደከሙ ፡ ፈዘዙ ፤ እንደ ፡ በለቀጠር ፡ አሁን ፡ አሁን ፡ ይመጣል ፡ እያለ ፡ እንዲመለከት ፡ እነሱም ፡ ከዛሬ ፡ ነገ ፡ ከነገ ፡ ከርሞ ፡ ያወጣን ፡ ይሆንን ፡ በማለት ።

፬ ፡ በዝኁ ፡ እምዕእርተ ፡ ርእስየ ፡ እለ ፡ ይጸልዑኒ ፡ በከንቱ ።

ሳልጸላቸው ፡ በግፍዕ ፡ የሚጸሉኝ ፡ ጠላቶቼ ፡ ከራስ ፡ ፀጉሬ ፡ በዙ ።

ጸንዑ ፡ ጸርየ ፡ እለ ፡ ይረውዱኒ ፡ በዓመፃ ።

በዓመፅ ፡ የሚከቡኝ ፡ ጠላቶቼ ፡ በከፋት ፡ ፀኑ ።

ወዘኢነሣእኩ ፡ ይትፈደዩኒ ።

ወዘኢሰቃሕክዎሙ ፡ ይፈድዩኒ ፡ ሲል ነው ፤ ያላበደርኋቸውን ፡ ይከፍሉኛል ፡ ማለት ፡ ሳልጣላቸው ፡ ይጣሉኛል ፤

2014 04 17

ሳልበድላቸው ፡ ይበድሉኛል ፡ አን
ድም ፡ ያልተበደርሁትን ፡ ይከፈሉ
ኛል ፡ ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፳፭ ።

፭፡ ለሊከ ፡ እግዚኦ ፡ ተአምር ፡ እበድየ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ድጋጉን ፡ ኃጢአቴን ፡
ታውቃለህ ።

ወኢይትኀባእ ፡ እምኔከ ፡ ኃጢአትየ ።

ታናናሹ ፡ ኃጢአቴም ፡ ከንተ ፡ አይ
ሠወርም ፡ ታውቀዋለህ ፡ አንድም ፡
(ለሊከ) ፡ መቃቢስ ፡ ዘወትር ፡ ማር
ዳት ፡ ተዋግተህ ፡ አትወጣምን ፡ ትለ
ኝ ፡ እንደሆነ ፡ አቤቱ ፡ ስንፍናዬን ፡
አንተ ፡ ታውቀዋለህ ፡ (ወኢይትኀባ
ዕ ፡ እምኔከ ፡ ኃጢአትየ) ፡ ረዳት ፡ ማ
ጣቴም ፡ ከንተ ፡ አይሠወርም ፡ ታው
ቀዋለህ ፡ ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ።

፮፡ ወኢይትኀፈሩ ፡ ብየ ፡ እለ ፡ የኀሡከ ፡ እግ
ዚኦ ፡ እግዚአ ፡ ኀያላን ።

አቤቱ ፡ የኀያላኑ ፡ ባለቤት ፡ ሆይ ፡
የኔስ ፡ እኔ ፡ ነውና ፡ የኃጥኡ ፡ ዳፋ ፡
ጻድቁን ፡ ይዳፋ ፡ እንዲሉ ፡ አንተን ፡
በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የሚሹህ ፡ ነቢያት ፡
ካህናት ፡ የኔ ፡ ፍዳ ፡ ደርሶባቸው ፡ አይ
ፈሩብኝ ።

ወኢይኀሠሩ ፡ ብየ ፡ እለ ፡ ይሴፈዉከ ፡ አምላከ ፡
እስራኤል ።

የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ አንተን ፡ ተስፋ ፡
የሚያደርጉህ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ አይ
ዋረዱብኝ ።

፯፡ እስመ ፡ በእንቲአከ ፡ ተዐገሥኩ ፡ ጽዕለተ ።

ባንተ ፡ ስላመንሁ ፡ ስድቡን ፡ ታግሼ ፡
ተቀብያለሁና ፡ ኤር ፡ ፲፭ ፡ ፲፭ ።

ወከደነኒ ፡ ኀፍረት ፡ ገጽየ ።

ለሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ ስገድ ፡ መሥዕት ፡
እራ ፡ ብላ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ያፈርሁት ፡
ዕፍረት ፡ ፊቴን ፡ እንደ ፡ ሻሽ ፡ ሸፈ
ነኝ ።

፰፡ ከመ ፡ ነኪር ፡ ኮንክዎሙ ፡ ለአኀውየ ።

ለወንድሞቼ ፡ ለሦስቱ ፡ ካህናት ፡ እ
ንደ ፡ ባዕድ ፡ ሆንኩባቸው ፡ አንድም ፡
ለአይሁድ ፡ እንደ ፡ ባዕድ ፡ ሆንኩባ
ቸው ፡ ማለት ፡ ዕሩቅ ፡ ባእሲ ፡ አሉኝ ።

ወነግድ ፡ ለደቂቀ ፡ እሙየ ፡ ወእምየ ።

ለናት ፡ ላባቴ ፡ ወገኖች ፡ እንግዳ ፡ ሆ
ንሁባቸው ፡ አንድም ፡ ለናቴ ፡ ላባት ፡
ለናቷ ፡ ዘመዶች ፡ ለአይሁድ ፡ እን
ግዳ ፡ ሆንሁባቸው ፡ ማለት ፡ እሩቅ ፡
ብእሲ ፡ አሉኝ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፯ ፡ ፩ ።

፱፡ እስመ ፡ ቅንዓተ ፡ ቤትከ ፡ በልዓኒ ፡ ዮሐ ፡
፪ ፡ ፲፯ ።

በቤት ፡ መቅደስህ ፡ ሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡
አቁመውበት ፡ መሥዋዕት ፡ እሪያ ፡
ሠውተውበት ፡ ዓይቼ ፡ የቀናሁት ፡
ቅናት ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ አቃጥሎኛ
ልና ።

ትዕይርቶሙ ፡ ለእለ ፡ ይትዔየሩከ ፡ ወድቀ ፡ ላዕ
ሌየ ።

አንተን ፡ የተገዳደሩህ ፡ ተግዳሮት ፡



ወአስተዩኒ ፡ ብሒአ ፡ ለጽምእየ ፤ መዝሙር ፡ ፷፰ ።



ነገሥተ ፡ ሳባ ፡ ወዐረብ ፡ ጋዳ ፡ ያመጽኡ ፤ መዝሙር ፡ ፸፩ ።

በኔ ፡ ደረሰ ፡ ማለት ፡ ሥዕለ ፡ ዐሐይ ፡ አቁመው ፡ መሥዋዕት ፡ እሪያ ፡ ሠውተው ፡ እንዴ ፡ ተገዳደሩህ ፡ እኔንም ፡ ለሥዕለ ፡ ዐሐይ ፡ ስገድ ፡ መሥዋዕት ፡ እሪያ ፡ ብላ ፡ ብለው ፡ ተገዳደሩኝ ። ሮሜ ፡ [illegible] ።

አንድም ፡ (እስመ ፡ ቅንዓት) ፡ በቤተ ፡ መቅደስህን ፡ ገበያ ፡ አቁመውበት ፡ ዓይቼ ፡ የቀናሁት ፡ ቅናት ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ አቃጥሎኛልና ፤ (ትዕይርቶሙ) ፡ አንተን ፡ በቤተ ፡ መቅደስህ ፡ ገባያ ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ተገዳደሩህ ፡ እኔንም ፡ ገበያውን ፡ ብፈታባቸው ፡ መኑ ፡ አብሐከ ፡ ትግበር ፡ ዘንተ ፡ አሉኝ ፡ ዮሐ ፡ [illegible] ።

አንድም ፡ (ትዕይርቶሙ) ፡ አንተን ፡ በደብተራ ፡ አሪት ፡ ሁለት ፡ እንሳት ፡ ሳህም ፡ አቁመው ፡ እንደ ፡ ተገዳደሩህ ፡ እኔም ፡ አበው ፡ ፈነወኒ ፡ ወእነ ፡ ተፈኖኩ ፡ ብላቸው ፡ በእሮ ፡ ይብለነ ፡ እምሰማይ ፡ ወረድኩ ፡ እንዘ ፡ ለሊነ ፡ ነአምር ፡ አባሁ ፡ ወእሞ ፡ ብለው ፡ ተገዳደሩኝ ። ዮሐ ፡ [illegible] ።

አንድም ፡ (ትዕይርቶሙ) ፡ አንተን ፡ መና ፡ ከደመና ፡ አውርደህ ፡ ብትመግባቸው ፡ ምንት ፡ ጣዕሙ ፡ ለዝ ፡ መና ፡ ብለው ፡ እንደተፈታተኑህ ፡ እኔንም ፡ እመ ፡ ኢበላእክሙ ፡ ሥጋሁ ፡ ለወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወኢሰተይክሙ ፡ ደሞ ፡ አልብክሙ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም ፡ ብላቸው ፡ በ

እሮ ፡ ይክል ፡ ዝንቱ ፡ የሀበነ ፡ ሥጋሁ ፡ ንብላዕ ፡ ብለው ፡ ተገዳደሩኝ ። [illegible] ።

[illegible] ወቀጻዕክዋ ፡ በጾም ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ በቀጠና ፡ በስልት ፡ አደከምኋት ፡ ይላል ፡ መቃቢስ ፡ አንድም ፡ ጌታ ፡ ሰውነቴን ፡ በስልት ፡ ይላል ፡ ጌታ ፡ ወጸመ ፡ አርብዓ ፡ መዓልተ ፡ ወአርብዓ ፡ ሌሊተ ፡ እንዲል ። [illegible] ።

ወኮነኒ ፡ ዕዕለተ ።

ይኸውም ፡ ተረት ፡ ሆኑብኝ ፡ አንድም ፡ ጌታ ፡ በሰውነቱ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ስድብ ፡ ሁኖበታልና ።

[illegible] ለበስኩ ፡ ሠቀ ፡ ወኮንክዎሙ ፡ ነገረ ፡ [illegible] ።

ማቅ ፡ ምንጣፍ ፡ ለብሼ ፡ አዘንሁላቸው ፤ ስለዚህም ፡ መተረቻ ፡ ሆንሁላቸው ፤ አሁን ፡ መቃቢስ ፡ የሚጸልየው ፡ ከኛ ፡ ሊያመልጥ ፡ ነውን ፡ ብለውታልና ፡ አንድም ፡ የከሳች ፡ ሴት ፡ ያዩ ፡ እንደሆነ ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ የማን ፡ ሚስት ፡ ትመስላለች ፡ የመቃቢስን ፡ የከሳ ፡ ወንድ ፡ ያዩ ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ማንን ፡ ይመስላል ፡ መቃቢስን ፡ እያሉ ፡ ይተርቱበታልና ።

አንድም ፡ (ለበስኩ) ፡ ሥጋ ፡ ለበስኩ ፡ ላቸው ፡ በሰውነቱ ፡ መከራ ፡ ተቀብሎበታልና ፡ ሠቅ ፡ አለው ፡ (ወኮንክዎሙ) ፡ ተረት ፡ ትውኔት ፡ ሆንኋቸው ። [illegible] ።

፲፪፡ ነበሩ፡ ላዕሌየ፡ ይዛውዑ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ውስተ፡ አናቅጽ።

በደባባይ፡ የተቀመጡ፡ ሰዎች፡ በኔ፡ ይጫወታሉ፡ እየው፡ መቃቢስን፡ ገልበ፡ ሲሸሺ፡ እያሉ፡ አንድም፡ በደባባይ፡ የተቀመጡ፡ አይሁድ፡ ተነበይ፡ ለነ፡ ክርስቶስ፡ መኑ፡ ጸፍዓከ፡ እያሉ፡ የኔን፡ነገር፡ ያነሣሉ፡ ይጥላሉ፡ ማቴ፡ ፳፯፡ ፳፰።

ወኪያየ፡ የኀልዩ፡ እለ፡ ይሰትዩ፡ ወይነ።

በቤተ፡ ንጉሥ፡ ጋሬዳ፡ የሚጠጡ፡ ሰዎች፡ ሲባባ፡ ገደል፡ ገባ፡ እያሉ፡ በኔ፡ ይዘፍናሉ፡ አንድም፡ በዓል፡ አድርገው፡ ጸጅ፡ የሚጠጡ፡ ሰዎች፡ አዘይኑሥቶ፡ ለቤተ፡ መቅደስ፡ ወያነሥአ፡ በሠሉስ፡ ዕለት፡ እያሉ፡ የኔን፡ ነገር፡ ያነሣሉ፡ ይጥላሉ፡ ማቴ፡ ፳፯፡ ፳፮፡ ዮሐ፡ ፪፡ ፲፱።

፲፫፡ ወአንሰ፡ በጸሎትየ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር።

እኔ፡ ግን፡ በምጸልየው፡ ጸሎት፡ ወደ፡እግዚአብሔር፡እመለከታለሁ። ሊቀ፡ካህናት፡ነውና፡ አንድም፡ እኔ፡ ግን፡ አባ፡ ሥረይ፡ሎሙ፡ ብዬ፡ እጸልይላቸዋለሁ። ሉቃ፡ ፳፫፡ ፴፬።

ሣህሉ፡ ለእግዚአብሔር፡ በጊዜሁ።

የእግዚአብሔር፡ ይቅርታው፡ በጊዜው፡ ጊዜ፡ ይደረጋል፡ በነግህ፡ የሚያደርገውን፡ በቀትር፡ በቀትር፡ የሚያደርገውን፡ በሠርክ፡ አያደርገውምና። መዝ፡ ፻፲፰፡ ፻፳፮።

እንዘ፡ ብዙኅ፡ ሣህልከ።

ሣህሉ፡ ሲል፡ ነው፡ ይቅርታው፡ ብዙ፡ ሲሆን።

ስምዓኒ፡ ዘበአማን፡ መድኃኒትየ።

ስምዓኒ፡ ዘበአማን፡ መድኃኒትየ፡ ዘበ አማን፡ እውነተኛው፡ መድኃኒቴ፡ እግዚአብሔር፡ እውነተኛ፡ ልመናዬን፡ ስማኝ።

፲፬፡ ወአድኅነኒ፡ እምዓምዓም፡ ከመ፡ ኢይኅጠኒ።

ረግረግ፡ውጦ፡እንዳያስቀረኝ፡አድነኝ፡ አንድም፡ ከረግረጉ፡ አድነኝ፡ አንድም፡ ከጠፉ፡ አድነኝ፡ ጠፉ፡ እንዳያጠፉኝ፡ አድነኝ።

ወአንግፈኒ፡ እምጸላእትየ።

ከጠላቶቼ፡ አድነኝ።

ወእምቀላየ፡ ማይ።

ከውሀ፡ ጥልቅ፡ አድነኝ፡ አንድም፡ ከኃይለኛ፡ ጦር፡ አድነኝ።

፲፭፡ ወኢያሥጥመኒ፡ ዓውሎ፡ ማይ።

አዚሬ፡ ባሕር፡ ውጦ፡ እንዳያስቀረኝ፡ አንድም፡ እንጥያከስ፡ እንዳያጠፉኝ፡ አድነኝ።

ወኢየኅጠኒ፡ ቀላይ።

ባሕሩ፡ እዳያሰጥመኝ፡ አንድም፡ በከተማ፡ ያለ፡ ጦር፡ እንዳያጠፉኝ፡ አድነኝ።



ወኢያብቍዑ፡ አፉሆሙ፡ ዓዘቃት፡ ላዕሌየ።

ረግረጎች፡ውጠው፡እንዳያስቀሩኝ። አንድም፡በዳር፡በዳር፡ያሉ፡ሰዎች፡ ነገራቸውን፡ እንዳያበዙብኝ፡ አድ አድነኝ።

፲፮፡ ስምዓኒ፡ እግዚኦ፡ እስመ፡ ሠናይ፡ ምሕረትከ።

አቤቱ፡ቸርነትህ፡ያማረ፡የተወደደ፡ ነውና፡ ልመናዬን፡ ስማኝ።

ወበከመ፡ ብዝኀ፡ ምሕረትከ፡ ነጽር፡ ላዕሌየ።

ኪያየ፡ሲል፡ነው፡ እንደ፡ቸርነትህ፡ ብዛት፡ መጠን፡ እኔን፡ በዓይነ፡ ምሕረትህ፡ እየኝ፡ ተመልከተኝ።

፲፯፡ ወኢትሚጥ፡ ገጸከ፡ እምኔየ፡ መዝ፡ ፳፮፡ ፱፡ ፻፵፪፡ ፯።

ከኔ፡ ከባርያህ፡ ገጸ፡ ረድኤት፡ ገጸ፡ ምህረትህን፡ አታርቅ።

እስመ፡ ተመንደብኩ፡ ፍጡነ፡ ስምዓኒ።

ባለመከራ፡ ሁኛለሁና፡ ፈጥነህ፡ ልመናዬን፡ ስማኝ።

፲፰፡ ነጽራ፡ ለነፍስየ፡ ወአድኅና።

ሰውነቴን፡ በዓይነ፡ ምሕረት፡ አይተህ፡ ተመልከተህ፡ አጽናት።

ወአድኅነኒ፡ በእንተ፡ ጸላእትየ።

ጠላቶቼን፡ ደስ፡ አይበላቸው፡ ብለህ፡ አድነኝ።

፲፱፡ ለሊከ፡ እግዚኦ፡ ተአምር፡ ዕበለትየ።

አቤቱ፡ አንተ፡ ስድቤን፡ ታውቀዋለህ።

ኃፍረትየ፡ ወኀሣርየ።

ስምዕለ፡ ፀሐይ፡ ስገድ፡ መምዋዕተ፡ እሪያ፡ ብላ፡ ባሉኝ፡ ጊዜ፡ ያፈርሁትን፡ ዕፍረቴን፡ ተዋርዶዬን፡ አንተ፡ ታውቀዋለህ።

በቅድሜ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ይሣቅዩኒ።

ሥቃይ፡ በሚያፀኑብኝ፡ ሁሉ፡ ፊት።

፳፡ ተዐገሠት፡ ነፍስየ፡ ፅዕለተ፡ ወኅሣረ።

ሰውነቴ፡ ስድቡን፡ ተዋርዶውን፡ ታግሣ፡ ተቀበለች።

ነበርኩ፡ ትኩዝየ፡ ወገሠሥኩ፡ ዘይናዝዘኒ።

ሦስት፡ ዓመት፡ ከሦስት፡ ወር፡ አዝኜ፡ ተከዝኜ፡ኖርሁ፡ አይዞህ፡ መከራ፡ እንጂ፡ ያልፋል፡ ብሎ፡ የሚያጽናናኝ፡ አጣሁ፡ አንድም፡ ተዋግቼ፡ አወጣሃለሁ፡ ብሎ፡ የሚያጽናናኝ፡ አጣሁ።

፳፩፡ ወወደዩ፡ ሐሞተ፡ ውስተ፡ መብልዕየ።

በምግቤ፡ ሐሞትን፡ ጨመሩበት፡ ለባሪያ፡ ጥሩ፡ ምግብ፡ ምን፡ ያደርግለታል፡ እያሉ፡ ሐሞት፡ የሚሆነውን፡ነገር፡ ብጣሪውን፡ እሻሮውን፡ ዕሴቱን፡ ዘንጋዳውን፡ ይሰጡኝቸዋልና።

ወአስተዩኒ፡ ብሒአ፡ ለጽምዕየ።

ዕሜንም፡ ለማራቅ፡ እንቡላውን፡ አተላውን፡ አጠጡኝ፡ ለባሪያ፡ ጥሩ፡ መጠጥ፡ ምን፡ ነው፡ እያሉ። ማቴ፡ ፳፯፡ ፴፬-፵፰፡ ማር፡ ፲፭፡ ፳፫፡ ሉቃ፡ ፳፫፡ ፴፮፡ ዮሐ፡ ፲፱፡ ፳፱።

፳፪፡ ለትኩኖሙ፡ ማዕደሙ፡ መሥገርተ፡ ወቅድሜሆሙ።

አሁን፡ እኔ፡ ምን፡ እላለሁ፡ ማዕድ፡ ምክራቸው፡ ወጥመድ፡ ትሁንባቸው፡ ለማዕድ፡ ሰው፡ እንዲጠብቁለት፡ ለምክርም፡ ሰው፡ ይጠብቁለታልና። እንድም፡ ለማዕድ፡ ሰው፡ እንዲመርጡለት፡ ለምክርም፡ ሰው፡ ይመርጡለታልና፡ እንድም፡ ለማዕድ፡ ሰው፡ እንዲሰበሰቡለት፡ ለምክርም፡ ሰው፡ ይሰበስቡለታልና፡ ወማዕገተ፡ ዕቅፍት፡ ለፍዳሆሙ። ሮሜ፡ ፲፩፡ ፱። ፍዳቸውንም፡ ለመቀበል፡ ከባቢ፡ ወጥመድ፡ ትሁንባቸው።

፳፫፡ ወይጽለማ፡ አዕይንቲሆሙ፡ ወኢይርአዩ።

ዓይኖቻቸው፡ በስልት፡ በቀጠና፡ ይጥፉ፡ (ኢይርዓያ)፡ ዓይኖቻቸው፡ አያዩ፡ (ኢይርዓዩ)፡ ሰዎቹ፡ አይዩ፡

ወይትቀጻዕ፡ ዘባናቲሆሙ፡ በኵሉ፡ ጊዜ።

ጀርባቸው፡ በረኀብ፡ ይበጥ፡ ይጉበጥ፡ እንድም፡ በይሁዳ፡ መቅበዩ፡ መንዶ፡ መንደርቶ፡ ይበጥ፡ ይጉበጥ፡ እንድም፡ ትብትብ፡ በመሸከም፡ ይበጥ፡ ይጉበጥ፡ ይላጥ፡ ይመለጥ። እንድም፡ (ወወደዩ)፡ ሐሞተ፡ ውስተ፡ መብልዕየ፡ በምግቤ፡ በክርስቶስ፡ ሐሞትን፡ ጨመሩበት፡ ይላል፡ ነቢይ፡ እንድም፡ (ምብላዕየ)፡ በምበላበት፡ በፈ፡ ሐሞት፡ ጨመሩበት፡ ይላል፡ ጌታ፡ (ወአስተዩኒ)፡ ፅሜንም፡ ለማራቅ፡ ማፃፃ፡ አጠጡኝ፡ በሀገራቸው፡ አምስት፡ ነገር፡ ያመጽኣሉ፡ የበለስ፡ የስንዴ፡ ቅጥሬን፡ እዝ፡ ከል፡ ዝፍት፡ ወይን፡ በናግሬ፡ ለጊዜው፡ ግባቸው፡ ቂጣ፡ ነውና፡ እንዲያጠፋላቸው፡ ነው፡ ፍጻሜው፡ ግን፡ ይህ፡ የተነገረ፡ ለጌታ፡ ነውና፡ ትንቢቱ፡ እንደ፡ ደረሰ፡ እንደ፡ ተፈጸመ፡ ለማጠየቅ፡ ሐሞቱን፡ ግን፡ እነሱ፡ አው ቀው፡ አልጨመሩበትም፡ በሀገራቸው፡ ከገባያ፡ የማይውል፡ የለም፡ ሁሉ፡ ይሸጣል፡ ከገባያ፡ ይዞት፡ ተቀምጦ፡ ሳለ፡ በጋጣቹ፡ ንዋየ፡ ውስጥ፡ ለማራገፍ፡ አልፎ፡ ሲሔድ፡ ወተወጢጦ፡ በእ፡ ውስተ፡ ዝኩ፡ ፃሕብ፡ ይላል፤ ተቀድዶ፡ ገብቶ፡ በል፡ የሚገዛው፡ አጥቶ፡ ወፈቀደ፡ ይግድፎ፡ ይላል፡ ሊጥለው፡ ወድዶ፡ ሳለ፡ አይሁድ፡ መጥተው፡ ሸጥልን፡ አሉት፡ ተቀድዶ፡ ሐሞትን፡ ገብቶ በታል፡ አላቸው፡ (ሎቱ፡ ስብሐት)፡ ለዝያ፡ ለጊጉይ፡ ይሆናል፡ መቼስ፡ ያዝለዋል፡ እንጂ፡ ምን፡ ይለዋል፡ ብለው፡ ወስደው፡ አጠጥተውታልና፡ (ለትኩኖሙ)፡ ሕጋቸው፡ በፊታቸው፡ ያለች፡ ወጥመድ፡ ትሁንባቸው፡ እሰፊ፡ ጥፊ፡ ከላት፡ በኋላ፡ ሲሠሯት፡ ቢገኙ፡ ፍዳ፡ የምታመጣ፡ ስለሆነ፡ ማዕድ፡ አላት፡ ከብበው፡ ይማሯታልና፡ (ወማዕገተ፡ ዕቅፍት)፡ ሕጋቸው፡ ከባቢ፡ ወዕመድ፡ ትሁንባቸው፡ (ወይፅለማ)፡ ዓይን፡ ልቦናቸው፡ ይጥፋ፡ ምሥጢር፡ አይዩ፡ (ወይትቀጻዕ)፡ ዘባን፡ ልቡናቸው፡ ይጉበጥ፡ ምሥጢር፡ አይመርምሩ፡ እንድም፡ በጥጦስ፡ መንዶ፡ መንደልቶ፡ ይበጥ፡ ይጉበጥ፡ ይላጥ፡ ይመለጥ፡ እንድም፡ ትብትብ፡ በመሸከም፡ ይጉበጥ፡ እንድም፡ ተስፋ፡ ትንሣኤ፡ ይጡ፤ እንድም፡ (ወይጽለማ)፡ ዓይኖቻቸው፡ ይጥፉ፡ ዕርቃን፡ ወልደ፡ እግዚአብሔርን፡ አይዩ፡ (ወይትቀጻዕ)፡ ጀርባቸው፡ ይጉበጥ፡ ይኸውም፡ ሊታወቅ፡ ቀኖት፡ ለማስማማት፡ እንደ፡ ተጉነበሱ፡ ቀርተዋል።

፳፬፡ ከዐው፡ መንተከ፡ ላዕሌሆሙ።

መዓትህን፡ አብዝተህ፡ አምጣባቸው።

ወይርከቦሙ፡ መቅሠፍተ፡ መዓትከ።

ፍጹም፡ መዓትህ፡ እንድም፡ ፈርደህ፡ የምታመጣው፡ መዓትህ፡ ያግኛቸው፡ ኢዮ፡ ፵፡ ፲፩።

፳፭፡ ለትኩን፡ ሀገሮሙ፡ በድወ።

በዕርዓውያን፡ ሀገራቸው፡ ዕርዕ፡ ምድረ፡ በዳ፡ ትሁን፤ እንድም፡ የአይሁድ፡ ሀገራቸው፡ ኢየሩሳሌም፡ ከሳቸው፡ ምድረ፡ በዳ፡ ትሁን፤ እንድም፡ ሀገራቸው፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ ከሳቸው፡ ምድረ፡ በዳ፡ ትሁን፤ እንድም፡ የይሁዳ፡ ሀገሩ፡ ኢየሩሳሌም። እንድም፡ ሀገረ፡ ስብከቱ፡ እንድም፡ ሀገሩ፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ እሱን፡ አጥታ፡ ምድረ፡ በዳ፡ ትሁን፡ ግብ፡ ፩-፳።



ወአልቦ፡ ዘይነብር፡ ውስተ፡ አብያቲሆሙ።

በቤታቸው፡ የሚኖር፡ አይኑር፡ ኢሳ፡ ፩፡ ፱፡ ፳፬፡ ፲፡ ኤርም፡ ፮-፳፯።

፳፮፡ እስመ፡ ዘአንተ፡ ቀሠፍከ፡ እሙንቱ፡ ተለዉ።

አንተ፡ በፈቃድህ፡ ያስማረከኸኝን፡ እነሱ፡ መከራ፡ አፅንተውብኛልና፡ የመቃብያን፡ መማረክ፡ የጌታ፡ ፈቃድ፡ ነው፡ በዕሜት፡ ላይ፡ ዕሜት፡ በክብር፡ ላይ፡ ክብር፡ ለመጨመር፡ ነው፡ ከገዛያ፡ በኋላ፡ ያለውን፡ እነሱ፡ አድርገውታልና፡ ለእመ፡ አንተ፡ ተማዕከኒ፡ ሕዳጠ፡ እሙንቱ፡ ወሰኩኒ፡ ዕኪተ፡ በዲበ፡ ዕኪት፡ እንዲል። እንድም፡ አንተ፡ ሰው፡ ሁን፡ ያልኸኝን፡ እነሱ፡ መከራ፡ አፅንተውብኛልና፡ የጌታ፡ ሰው፡ መሆን፡ የሥስቱ፡ ፈቃድ፡ ነው፡ ሞቱን፡ ግን፡ በምቀኝነት፡ አድርገውታልና።

ወሰኩኒ፡ ዲበ፡ ሕማምየ፡ ቍስለ።

በመከራዬ፡ ላይ፡ መከራ፡ አፀኑብኝ፡ ማለት፡ በፍልጥ፡ መትተው፡ በጥጠ፡ በሳንባ፡ ጠለም፡ ይገርፉቸዋልና። እንድም፡ በተኰርፆተ፡ ርእስ፡ ላይ፡ አክሊለ፡ ሦከን፡ በተጸፍዖ፡ መልታሕት፡ ላይ፡ ወሪቀ፡ ምራቅን፡ በተአሥሮ፡ ድኅሪት፡ ላይ፡ ተቀሥፎ፡ ዘበንን፡ ጨመሩብኝ፡ ማለት፡ በዕለተ፡ ዓርብ፡ የተደረገውን፡ ዓሥ

2014 04 17

ራ ፡ ሦስቱን ፡ ሕማማት ፡ መስቀል ፡ መናገር ፡ ነው ።

፳፮ ፡ ወለኮሙ ፡ ጌጋየ ፡ በዲበ ፡ ጌጋዮሙ ።

በፍዳ ፡ ላይ ፡ ፍዳ ፡ አምጣባቸው ።

ወኢይባኡ ፡ በጽድቅከ ።

በቸርነትህ ፡ ውለው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ አይግቡ ፡ አንድም ፡ ወደ ፡ መንግሥ ተ ፡ ሰማያት ፡ አይግቡ ።

፳፯ ፡ ወይደምሰሱ ፡ እመጽሐፈ ፡ሕያዋን ።

ከአብርሃም ፡ ከይስሐቅ ፡ ከያዕቆብ ፡ መጽሐፍ ፡ ይፋቁ ፡ አንድም ፡ ከልበ ፡ ሥላሴ ፡ ይጥፉ ።

ወኢይጸሐፉ ፡ ምስለ ፡ ጻድቃን ።

ከጻድቃን ፡ ጋራ ፡ አይቈጠሩ ፡ ዘዐ፡፴፪.፴፫ ።

፳፱ ፡ ነዳይ ፡ ወቍሱል ፡ አነ ።

መቃቢስ ፡ ዘወትር ፡ ማርዳት ፡ ተቀ ግተህ ፡ አትወጣምን ፡ ትለኛ ፡ እንደ ሆነ ፡ እኔስ ፡ ተዋግቶ ፡ ለመውጣት ፡ አልችልም ፡ ድኃ ፡ ነኝ ፡ በለመከራ ፡ ነኝ ።

መድኀኒ ፡ ገጽየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተወከፈኒ ።

ስለዚህ ፡ ፊት ፡ መከታዬ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ በረድኤት ፡ ተቀበለኝ ።

፴ ፡ እሴብሖ ፡ ለስመ ፡ አምላኪየ ፡ በማኅሌት ።

እኔም ፡ ይህ ፡ ስለተደረገልኝ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ፈጣሪዬን ፡ አመሰግናለሁ ፡ ለስሙ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ፡ አን ድም ፡ ለፈጣሪዬ ፡ ስም ፡ ፍጹም ፡ ም ስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

ወእዕብዮ ፡ በስብሐት ፡ ዳን ፡ ፱ ፡ ፴፯ ፡

በጥንተ ፡ ምሥጋናው ፡ አመሰግነዋ ለሁ ።

፴፩ ፡ ወአሠምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምላ ህም ፡ ጣዕዋ ።

ላህም ፡ ጣዕዋን ፡ ሠውቼ ፡ ደስ ፡ እሰ ኝዋለሁ ፡ የሚሠዋውን ፡ እያልቡበ ትም ፡ ስድ ፡ ያድጋል ፡ ፈጥኖ ፡ ያድ ጋልና ፡ ላህም ፡ አለው ፡ ዕድሜው ፡ ጥቂት ፡ ነውና ፡ ጣዕዋ ፡ አለው ፡ አን ድም ፡ ከላህም ፡ የተገኘ ፡ ጣዕዋን ፡ ሠውቼ ፡ ደስ ፡ አሰኝዋለሁ ።

ዘኢያብቈለ ፡ ቀርነ ፡ ወጽፍረ ።

ጥፍሩ ፡ ያልዘረዘረ ፡ ቀንዱ ፡ ያልከረ ከረ ፡ ጠጉሩ ፡ ያላረረውን ፤ አንድም ፡ ቀንድ ፡ ጥፍር ፡ ያላወጣውን ፡ በኋላ ፡ የሚወጣ ፡ ቀንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጥፍ ርማ ፡ አብሮት ፡ አይደለም ፡ የሚወ ለድን ፡ ቢሉ ፡ ያልፀና ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ወከፈ ፡ ይላል ፡ በአሪት ።

አንድም ፡ (ወአሠምሮ) ፡ ከመቤታ ችን ፡ የተገኘ ፡ ጌታን ፡ (እምጣዕዋ ፡ ላህም) ፡ ከጣዕዋ ፡ እመቤታችን ፡ የተ ገኘ ፡ ላህም ፡ ጌታን ፡ ሠውቼ ፡ ደስ ፡ አሰኝዋለሁ ፤ ሐዳስዩ ፡ ጣዕዋ ፡ እን ዲላት ፡ ጌታን ፡ ወአምጽኡ ፡ ላህመ ፡ መግዝዓ ፡ እንዲለው ።



(ዘኢያብቈለ) ፡ መርገመ ፡ ሥጋ ፡ መ ርገመ ፡ ነፍስ ፡ ያላነቃ ፡ ዘሌ ፡ ፩ ፡ ፪-፱ ።

፴፪ ፡ ይርአዩ ፡ ነዳያን ፡ ወይትፈሥሑ ።

መቃብያን ፡ አንድም ፡ በቁሙ ፡ ነዳ ያን ፡ ይህን ፡ አይተው ፡ ደስ ፡ ይበላ ቸው ፡ አንድም ፡ ደስ ፡ ይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ይዩ ፡ ኢዮ ፡ ፳፪ ፡ ፲፱ ።

ኅሥሥዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወተሐዩ ፡ ነፍስክሙ ።

ማየታችሁም ፡ ለዚህ ፡ ነው ፡ እግዚ አብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ ሹት ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ሰውነታ ችኑ ፡ ትድናለች ፡ አንድም ፡ (ታሐ ይዉ ፡ ነፍሰክሙ) ፡ ይላል ፡ ሰውነታ ችኁን ፡ ታድናላችሁ ፡ አሞ ፡ ፭ ፡ ፬-፯ ።

፴፫ ፡ እስመ ፡ ሰምዖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለነ ዳያን ።

እግዚአብሔር ፡ የመቃብያንን ፡ ልመ ና ፡ ሰምቷልና ።

ወኢመነኖሙ ፡ ለሙቁሓን ።

ችግረኞች ፡ መቃብያንንም ፡ ቸል ፡ አላላቸውምና ።

፴፬ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ።

ስለዚህ ፡ ሰማይ ፡ ምድር ፡ አንድም ፡ መላእክት ፡ ደቂቀ ፡ አዳም ፡ አንድም ፡ ልዑላን ፡ ትሑታን ፡ ያመሰግኑታል ፡

ወባሕርኒ ፡ ወኵሉ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ውስቴታ ።

ባሕር ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ የሚመላለ ስ ፡ ዓሣ ፡ አንበሪ ፡ አዞ ፡ ጉማሬ ፡ ሁሉ ፡ ያመሰግኑታል ፡ አንድም ፡ (ሰማያት) ፡ ከተማው ፡ ምድር ፡ በከተማው ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ (ባሕር) ፡ ገጠር ፡ (ዘይት ሐወስ) ፡ በገጠር ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ያመሰግኑታል ።

፴፭ ፡ እስመ ፡ አድኀና ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጽዮን ።

እግዚአብሔር ፡ ጽዮንን ፡ አድኗታ ልና ፡ በሀገሪቱ ፡ ሰዎቹን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወይትሐነፃ ፡ አህጉረ ፡ ይሁዳ ።

የይሁዳ ፡ አውራጃች ፡ ይሰራሉ ፡ ሀገ ሪቱ ፡ እንድትቀና ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንድትሰራ ፡ ማድረጉን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፴፮ ፡ ይነብሩ ፡ ህየ ፡ ወይወርስዋ ።

ወርሰዋት ፡ ይኖራሉ ።

ወዘርዐ ፡ አግብርቲከ ፡ ይነብርዋ ።

የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ መቃብያን ፡ ይኖሩባታል ።

ወእለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ስሙ ፡ የኀድሩ ፡ ውስቴታ ።

ስምህን ፡ መጽራት ፡ የሚወዱ ፡ ሁሉ ፡ በውስጧ ፡ ይኖራሉ ፡ ይኸውም ፡ ሊ ታወቅ ፡ ከሚጠት ፡ በኋላ ፡ ደቂቀ ፡ ከስሙናይን ፡ ወርሰዋት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ፡ ፶፱ ፡ ፫ ።

## መዝሙር ፡ ፷፱ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ ነፅር ፡ ውስተ ፡ ረድኤትየ ፡ መዝ ፡ ፴፱ ፡ ፲፫-፲፯ ።

በአቤሴሎም ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግሮታል ፡ አቤቱ ፡ እኔን ፡ ወደ ፡ መርዳት ፡ እይ ፡ ተመልከት ፡ ይህንም ፡ በቀትር ፡ ዮርዳኖስን ፡ ሲሻገር ፡ ከረሞጪው ፡ ላይ ፡ በልቡ ፡ ወድቆ ፡ ተናግሮታል ፡ ምነው ፡ ወዓደወ ፡ ባሕረ ፡ እንዘ ፡ ይገውሕ ፡ ይል ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ ዮርዳኖስ ፡ እንደ ፡ ተከዜ ፡ ተመላላሽ ፡ ወሀ ፡ ነው ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ እስከ ፡ ቀትር ፡ የሚያስኬድ ፡ ነው ፡ በቀትር ፡ ተሻግሮ ፡ ከረሞጪው ፡ በልቡ ፡ ወድቆ ፡ ተናግሮታል ፡ አንድም ፡ የሌላ ፡ ቤት ፡ አብነት ፡ ብሎ ፡ ጧት ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ከሚቆረጥም ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ከሚያቃጥል ፡ በታ ፡ ወድቆ ፡ ተናግሮታል ።

እግዚኦ ፡ አፍጥን ፡ ረዲኦትየ ።

አቤቱ ፡ ፈጥነህ ፡ እርዳኝ ።

፪ ፡ ይትኀፈሩ ፡ ወይኅሠሩ ፡ እለ ፡ የኃሥሥዋ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ ለሞት ፡ ለጥፋት ፡ የሚሿት ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ።

ለይግብኡ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ ወይትኀፈሩ ፡ እለ ፡ መከሩ ፡ እኩየ ፡ ላዕሌየ ።

በኔ ፡ ክፉ ፡ የመከሩብኝ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ፡ አድጎ ፡ እነስ ፡ አድሮ ፡ እነስ ፡ ይሁኑ ።

፫ ፡ ለይግብኡ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ በጊዜሃ ፡ ተኃፊሮሙ ፡ እለ ፡ ይብሉኒ ፡ እንቋዕ ፡ እንቋዕ ።

ዳዊትን ፡ አይመስሉ ፡ መስሎ ፡ እይ ፡ ሆኑ ፡ ሆኖ ፡ ዓየነው ፡ እሰይ ፡ እሰይ ፡ ዕሰ ፡ ዕሰ ፡ የሚሉኝ ፡ ሰዎች ፡ ፈጥነው ፡ አንድም ፡ እሰይ ፡ እሰይ ፡ በሚሉበት ፡ ጊዜ ፡ አድጎ ፡ እነስ ፡ አድሮ ፡ እነስ ፡ ይሁኑ ፡ ድል ፡ ነስተው ፡ እኔን ፡ ከመከተል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ይቅሩ ።

፬ ፡ ለይትፌሥሑ ፡ ወይትኃሠዩ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ የኃሥሡከ ።

አንተን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የሚሹ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ባንተ ፡ አምነው ፡ በንተው ፡ ፈጽመው ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ።

ወይበሉ ፡ ዘልፈ ፡ ዓቢይ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ገናና ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ይበሉ ።

እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ አድኅኖተከ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ አድኅኖትከ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ትድግናህን ፡ የሚሹ ፡ ሁሉ ።

፭ ፡ አንሰ ፡ ነዳይ ፡ ወምስኪን ፡ አነ ።

ዳዊት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ማርዳት ፡ አትዋጋምን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ እኔስ ፡ ነዳይ ፡ ምስኪን ፡ ነኝ ።





ወእግዚአብሔር ፡ ይረድአኒ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛል ፡ አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛል ፡ እንጂ ፡ እንሰ ፡ ነዳይ ።

ረዳእየ ፡ ወምስካይየ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ እምላኪየ ፡ ወኢትጐንዲ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ረዳቴ ፡ እምባ ፡ መጸግያዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ቸል ፡ አትበል ፡ አትዘግይ ፡ አንድም ፡ ቢሆንም ፡ አትዘግይ ፡ አትዘግይ ፡ እንጂ ፡ ረዳቴ ፡ እምባ ፡ መፀግያዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ።

## መዝሙር ፡ ፸ ።

፩ ፡ ኪያከ ፡ ተወከልኩ ፡ እግዚኦ ፡ ወኢይትኃፈር ፡ ለዓለም ።

ስለትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ አቤቱ ፡ ባንተ ፡ አመንኁ ፡ እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ለዘለዓለም ፡ በመከራው ፡ አላፍርም ። አንድም ፡ በመከራው ፡ እንዳላፍር ፡ ባንተ ፡ አመንኁ ፡ መዝ ፡ ፴ ፡ ፩ ።

፪ ፡ ወበጽድቅከ ፡ አንግፈኒ ፡ ወባልሐኒ ።

በቸርነትህ ፡ በይቅርታህ ፡ ፈጽመህ ፡ አድነኝ ። አንድም ፡ (አንግፈኒ) ፡ ከንጉሡ ፡ (ባልሀኒ) ፡ ከሠራዊቱ ፡ አድነኝ ።

አፅምእ ፡ እገዘነከ ፡ ኀቤየ ፡ ወፍጡነ ፡ አድኅነኒ ።

ዕዝነ ፡ ፈቃድህን ፡ ወደኔ ፡ መልሰህ ፡ ፈጥነህ ፡ አድነኝ ።

፫ ፡ ኩነኒ ፡ አምላኪየ ፡ ወመድኃንየ ።

ድህነቴን ፡ የምታደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እንዲህ ፡ ሁነኝ ።

ውስተ ፡ ብሔር ፡ ፅኑዕ ፡ ከመ ፡ ታድኅነኒ ።

ዘታድኅነኒ ፡ ይላል ፡ ፅኑዕ ፡ በሚሆን ፡ በባቢሎን ፡ ሀገር ፡ የምታድነኝ ፡ ሁነኝ ፡ አንድም ፡ ከመ ፡ ታድኅነኒ ፡ ከባቢሎናውያን ፡ ታድነኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቀኝ ።

እስመ ፡ ኃይልየ ፡ ወጸወንየ ፡ አንተ ።

አንተ ፡ ብዋጋ ፡ ኃይሌ ፡ ብሸሽ ፡ እምባ ፡ መፀግያዬ ፡ ነህና ።

፬ ፡ አምላኪየ ፡ አድኅነኒ ፡ እምዕደ ፡ ኃጥእን ።

ፈጣሪዬ ፡ ከኃጥአን ፡ ከሠራዊቱ ፡ እጅ ፡ አድነኝ ።

ወእምዕደ ፡ ዓማፂ ፡ ወገፋዒ ።

አማፂ ፡ ገፋዒ ፡ ከሚሆን ፡ ከንጉሡ ፡ ከብልጣሰር ፡ እጅ ፡ አድነኝ ።

፭ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ተስፋየ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ አለኝታዬ ፡ ነህና ።

እግዚእየ ፡ ተስፈውኩከ ፡ እምንእስየ ።

አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሮ ፡ አንድም ፡ ከግብፅ ፡ ከወጣሁ ፡ ጀምሮ ፡ አንድም ፡ እምንዑስየ ፡ ይላል ፡ ከቀ

ቂትንቴ ፡ ከአብርሃም ፡ ከይስሐቅ ፡ ከ
ያዕቆብ ፡ ጀምሮ ፡ ተስፋ ፡ አድርጌሃ
ለኹና ።

፮ ወብከ ፡ ጸናዕኩ ፡ እምከርሠ ፡ እምየ ።

በናቴ ፡ ማኅፀን ፡ ሳለሁም ፡ ባንተ ፡
ሥልጣን ፡ ፀናኹ ። መዝ ፡ ፳፩ ፡ ፱ ።

ወእምከርሠ ፡ ማህፀን ፡ አንተ ፡ ከደንከኒ ።

በናቴ ፡ ማኅፀን ፡ ሳለኹ ፡ የበላችው ፡
ተጭኖ ፡ የጠጣችው ፡ አንገዝዞ ፡ እን
ዳይገለኝ ፡ የምትሰውረኝ ፡ አንተ ፡
ነህ ፡ ኢሳ ፡ ፵፮ ፡ ፫ ።

ወአንተ ፡ ዝክርየ ፡ በዅሉ ፡ ጊዜ ።

ሁልጊዜም ፡ ስም ፡ አጸራሬ ፡ አንተ ፡
ነህ ።

፯ ከመ ፡ ጊጉየ ፡ ኮንክዎሙ ፡ ለብዙኃን ።

ለባቢሎናውያን ፡ እንደ ፡ ጥንግ ፡ ሆ
ንኋቸው ፡ ጥንግን ፡ ያገኛት ፡ ሁሉ ፡
ያበርራታል ፡ ያላጋታል ፡ እነሱንም ፡
ያገኛቸው ፡ ሁሉ ፡ ይማርካቸዋልና ፡
እንድም ፡ እንደ ፡ አላማ ፡ ሆንኋቸው ፡
አላማን ፡ ሁሉ ፡ ይመለከተዋል ፡ እነ
ሱንም ፡ ሁሉ ፡ ለመማረክ ፡ ይመለከታ
ቸዋልና ። እንድም ፡ እንደ ፡ ጊጤ ፡ ሆን
ኋቸው ፡ ጊጤን ፡ ሁሉ ፡ ይወጋዋል ፡
እነሱንም ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ያፀናባቸ
ዋልና ፡ እንድም ፡ ባደባባይ ፡ እንደ ፡
ወደቀ ፡ ግንድ ፡ ሆንኋቸው ፡ ያን ፡
ሁሉ ፡ ስለቱን ፡ ይፈትንበታል ፡ በነ
ሱም ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ያፀናባቸዋልና ፡
እንድም ፡ ባደባባይ ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡
ጭቃ ፡ ሆንኋቸው ፡ ያን ፡ ሁሉ ፡ ይጠ
ቀጥቀዋል ፡ በነሱም ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡
ያፀናባቸዋልና ፡ አንድም ፡ እንደ ፡
ግትቻ ፡ ሆንኋቸው ፡ ያ ፡ የቀን ፡ ሐ
ሩር ፡ የሌሊት ፡ ቍር ፡ ሲቀበል ፡ ይኖ
ራል ፡ እነሱም ፡ መከራ ፡ ሲቀበሉ ፡
ኑረዋልና ።

አንተ ፡ ረዳእየ ፡ ወኃይልየ ።

አንተ ፡ ግን ፡ ብዋጋ ፡ ረዳቴ ፡ ኃይሌ ፡
ነህ ።

፰ ምላዕ ፡ አፉየ ፡ ስብሐቲከ ።

ምሥጢር ፡ ግለጽልኝ ።

ከመ ፡ እሰብሕ ፡ አኰቴተከ ።

አመሰግንህ ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ ስብ
ሐቲከ ፡ ወአኰቴተከ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡
አፌን ፡ መልቼ ፡ አመሰግንህ ፡ ዘንድ ።

ወዅሎ ፡ አሚረ ፡ ዕበየ ፡ ስብሐቲከ ።

የጌትነትህንም ፡ ገናንነት ፡ ዘወትር ፡
አመሰግን ፡ ዘንድ ።

፱ ኢትግድፈኒ ፡ በመዋዕለ ፡ ርስእየ ።

በዕርግናዬ ፡ በመከራው ፡ አትጣለኝ ፡
ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ ጣለኝ ፡ ማለት ፡
አይደለም ፡ በፀናው ፡ ተናገረ ።

ወአመ ፡ ኀልቀ ፡ ኃይልየ ፡ ኢትግድፈኒ ፡ እምላ
ኪየ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ኃይሌ ፡ በደከመ ፡
ጊዜ ፡ አንድም ፡ ወገኔ ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡
በመከራ ፡ አትጣለኝ ።





፲ እስመ ፡ ነበቡ ፡ ጸላዕትየ ፡ ላዕሌየ ።

ጸላቶቼ ፡ በኔ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተና
ግረውብኛልና ።

ወእለሂ ፡ የዐቅምዋ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴንም ፡ ለሞት ፡ ለጥፋት ፡ የሚ
ሿት ፡ ሁሉ ።

ተማከሩ ፡ ኅቡረ ፡ ወይቤሉ ።

አንድ ፡ ሁነው ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡
ተማከሩ ።

፲፩ ገደፎ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ ተለይቶ
ታልና ።

ዴግንዎ ፡ ወትእኀዝዎ ።

ተከተሉት ፡ ትይዙታችኍ ፡ አሉ ።

እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘያድኅኖ ።

የሚያድነው ፡ የለምና ፡ ስላልኖረ ፡
በምን ፡ አውቆ ፡ ቢሉ ፡ አክዮር ፡ አ
ሞናዊ ፡ ባወቀ ፡ አውቆ ፡ ንጉሡ ፡ ፍ
ሕሥዮስ ፡ ቄሳር ፡ ምሕስዮስ ፡ ቄሣር ፡
ይባላል ፡ ስመ ፡ ትዕይርቱን ፡ ናቡከደ
ነፆር ፡ በሉኝ ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ ባጥና ፡
የምትባል ፡ ሀገር ፡ አለች ፡ ገዥዋ ፡
አርፋስክድ ፡ ይባላል ፡ ገብር ፡ ብሎ ፡
ላከበት ፡ አይሆንም ፡ ብሎ ፡ አምባ ፡
ገባ ፡ ሔዶ ፡ ከበበው ፡ ኃይል ፡ ቢሰ
ማው ፡ ወጥቶ ፡ ገጠመው ፡ ድል ፡ አ
ድርጎ ፡ አሥሮ ፡ ሲሔድ ፡ ሆሎፎርኒ
ስን ፡ የጦር ፡ አበጋዝ ፡ ሹም ፡ ጠላት ፡
አጥፋ ፡ ድንበር ፡ አስፋ ፡ ካመነው ፡
እጅ ፡ መንሻ ፡ እየተቀበልህ ፡ ያላመነ
ውን ፡ እያሳመንህ ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ሰደ
ደው ።

ካመነው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ እየተቀበለ ፡
ያላመነውን ፡ እያሳመነ ፡ ሲሔድ ፡ አ
ሞን ፡ ደረሰ ፡ አክዮር ፡ አሞናዊ ፡ መ
ጥቶ ፡ ወበት ፡ ገባላት ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡
ይሆናል ፡ ብሎ ፡ አከብሮ ፡ አኑሮታል ፡
እስራኤል ፡ ከፋርስ ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥ
ተው ፡ ደብረ ፡ ቢጥልዋ ፡ ከምትባል ፡
ቦታ ፡ ዳስ ፡ ጥለው ፡ ጎጆ ፡ ሠርተው ፡
እንስንስ ፡ ብለው ፡ ተቀምጠው ፡ አይ
ቶ ፡ እነዚያ ፡ ምን ፡ ባዮች ፡ ናቸው ፡
እንችላለን ፡ ብለው ፡ አይዋጉ ፡ ወይ
ም ፡ አይገብሩ ፡ ይምጡብን ፡ ባዮች ፡
እንጂ ፡ ይሆናሉ ፡ አለ ። አክዮር ፡ አሞ
ናዊ ፡ የነሱስ ፡ ነገር ፡ ግሩም ፡ ነው ።
ስማኝ ፡ ልንገርህ ፡ አለው ፡ ምንድር ፡
ነው ፡ ብሎታል ፡ ባገራቸው ፡ በኢየ
ሩሳሌም ፡ ሳሉ ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠሩ ፡
ጣዖት ፡ ቢያመልኩ ፡ እስግርከ ፡ ፋ
ርስ ፡ ባቢሎን ፡ አውርዷቸው ፡ ሰባ ፡
ዘመን ፡ ኑረው ፡ ከዝያ ፡ ንስሓ ፡ ቢገቡ ፡
ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽ
ድቅ ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አም
ልኮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢመለሱ ፡ ተአ
ምራት ፡ አድርጎላቸው ፡ አሕዛብን ፡
አጥፍተው ፡ ሰበት ፡ አህጉር ፡ ወግተው ፡
ሰባት ፡ አፍላግ ፡ ተከፍሎላቸው ፡ ተሻ
ግረው ፡ መጥተዋል ፡ ገና ፡ ፍቅሩን ፡ አ
ልፈጸመላቸውም ፡ እሺ ፡ ቅብ ፡ እሺ ፡

ቅብ ፡ ይላቸዋል ፤ የተጣላቸው ፡ እን
ደሆን ፡ አንድ ፡ አሽከር ፡ ብትሰድድ ፡
ማርከ ፡ ያመጣልሃል ፡ ያልተጣላቸው
እንደሆን ፡ ግን ፡ ስንኳን ፡ አንተ ፡ ንጉ
ሡም ፡ ቢመጣ ፡ አይችላቸውም ፡ አ
ርፈህ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ፤ አንተኑ ፡
ገባዒሁ ፡ ለኤፍሬም ፡ የኤፍሬም ፡ ወ
ድዶ ፡ ገቡ ፡ ጠንቋዩ ፡ አንተ ፡ ነህን ፡
እነሱን ፡ ማላጠፉ ፡ አንተን ፡ አላጠፉ
ህም ፤ እነሱን ፡ በምቀጣበት ፡ እቀጣሃ
ለሁ ፡ ብሎ ፡ አሥሮ ፡ ከነሱ ፡ በታች ፡
አስጥሎታል ። ወአመርግሑ ፡ መር
ግሐ ፡ ይላል ፡ እስራኤልም ፡ ጦር ፡
መጣብን ፡ ብለው ፡ ደንግፆ ፡ ይኰለ
ችሁ ፡ አክዮር ፡ አሞናዊ ፡ ነኝ ፡ አላ
ቸው ፤ ምን ፡ ሆነኻል ፡ አሉት ፡ የላ
ንተን ፡ ተስፋ ፡ ብናገር ፡ አሥሮ ፡ ከዚ
ህ ፡ አስጥሎኛል ፡ አላቸው ፤ ወርደው ፡
ፈትተው ፡ አውጥተው ፡ እንደ ፡ ምን
ድን ፡ ነው ፡ ብንገጥመው ፡ እንችለዋ
ለንን ፡ ወይስ ፡ አንችለውም ፡ አሉት ፡
እግዚአብሔር ፡ ቢረዳን ፡ ድል ፡ እን
ነሣለን ፡ ባይረዳንስ ፡ ወዴት ፡ እንሔ
ዳለን ፡ አላቸው ፡ እነሱም ፡ ብንችል ፡
እንዋጋለን ፡ ባንችል ፡ እንገብራለን ፡
አሉ ። ዮዲት ፡ የምትባል ፡ ደግ ፡ ሴት ፡
ነበረች ፡ ባሏ ፡ ሞቶ ፡ በጾም ፡ በቀኖና ፡
በትኅርምት ፡ በኀዘን ፡ በጸሎት ፡ ትኖ
ራለች ፤ እንዲህን ፡ ያላችሁ ፡ ናችሁ ፡
ፈጣሪችሁን ፡ ለምን ፡ ትፈታተኑታ
ላችኁ ፡ ያድነናል ፡ አትሉትምን ፡ ብላ ፡

ግብር ፡ በገባች ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡
የምታጠፋበትን ፡ ግብር ፡ አገኘች ፡
ወዴት ፡ ትሔጃለሽ ፡ አትበሉኝ ፡ እም
ላከ ፡ እስራኤል ፡ ይከተልሽ ፡ በሉኝ ፡
ብላ ፡ ባሏ ፡ ሳለ ፡ የምትለብሰውን ፡ የ
ክት ፡ ልብሷን ፡ ለብሳ ፡ አጊጣ ፤ ወወ
ሰከ ፡ ላቲ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልክዐ ፡
በዲበ ፡ መልክዐ ፡ ይላል ፤ በመልክ ፡
ላይ ፡ መልክ ፡ ጨምሮላት ፡ ስንቋን ፡
አሲዛ ፡ ብላቴናዋን ፡ አስከትላ ፡ ሔዳ
ለች ፡ ሽማ ፡ አጣቢዎች ፡ አገኟት ፡
ዛሬስ ፡ እስራኤል ፡ መዋጋት ፡ ቢሳና
ቸው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እያሉ ፡ ወባት ፡
ሊገቡ ፡ መጡን ፡ ብለው ፡ ለኔ ፡ ትገባ
ለች ፡ ለኔ ፡ ትገባለች ፡ እያሉ ፡ ተሻ
ሟት ፡ ጋይ ፡ የሚባል ፡ የንጉሡ ፡ ጃን
ደረባ ፡ አለ ፡ ይህችስ ፡ ለእናንተ ፡ አት
ገባችሁም ፡ ለጌታዬ ፡ ትገባለች ፡ ብሎ ፡
ወስዶ ፡ ሰጣት ። የጠመኛ ፡ ምቀኛ ፡
እንዳሉ ፤ ለምን ፡ መጣሽ ፡ አላት ።
እስራኤል ፡ ሊገቡ ፡ ጥቂት ፡ ቀርቷቸ
ዋል ፤ ርስት ፡ ሔደብኝ ፡ እንድትመ
ልስልኝ ፡ አስቀድሜ ፡ ደጅ ፡ እጠና
ለሁ ፡ ብዬ ፡ መጣሁ ፡ አለችው ። አት
ከልክሏት ፡ ትውጣ ፡ ትግባ ፡ ትቀመ
ጥ ፡ ብሎ ፡ አክብሮ ፡ አስቀምጧታል ።
እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ በእጅ
ህ ፡ የሚጥልበትን ፡ ምክንያት ፡ እንዳ
መለክትህ ፡ ምግባል ፡ ቦታ ፡ ስጠኝ ፤
አለችው ፡ ሰጣት ፤ ብላቴናዋን ፡ ከእን
ዲህ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ቆዩኝ ፡ ብላ ፡ አስ
ቀድማ ፡ ትሰዳታለች ፡ አሕዛብ ፡ የተ



ወለዱበትን ፡ ቀን ፡ ያከብራሉ ፡ በዚ
ህ ፡ ቀን ፡ ተወልደን ፡ ከዚህ ፡ ማዕ
ርግ ፡ ደርሰን ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብር
ሃን ፡ ከጠባብ ፡ ወደ ፡ ሰፊ ፡ የወጣን
በት ፡ ሲሉ ፡ በዓል ፡ አድርጎ ፡ ሲያ
በላ ፡ ሲያጠጣ ፡ ያችን ፡ ዕብራዊት ፡
ጥሩ ፡ ብሎ ፡ አስጠርቶ ፡ ከፊቱ ፡ አኑ
ሮ ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ሲበላ ፡ ሲጠጣ ፡
ውሏል ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ በዓይኑ ፡ ዝሙ
ት ፡ ሲመለከታት ፡ ብላቴናው ፡ አይቶ ፡
ድንኳኑን ፡ የኋሊት ፡ ቆልፎባቸው ፡ ሔ
ዷል ። ሰክሯልና ፡ ያኰርፍ ፡ ዠመረ ፤
እሷም ፡ ተነስታ ፡ ትጸልያለች ፤ በኃያ
ላኑ ፡ አድረህ ፡ ሥራ ፡ ብትሠራ ፡ አት
መሰገንም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በኔ ፡ በደካ
ማዪቱ ፡ አድረህ ፡ ሥራ ፡ ብትሠራ ፡
ትመሰገናለህ ፡ ብላ ፡ ከራስጌው ፡ መ
ከድ ፡ ሰይፍ ፡ ነበር ፡ ያን ፡ አንሥታ ፡
ቸብቸበውን ፡ ቆርጣ ፡ ወአዕረፈት ፡
በበንስቲት ፡ ይላል ፤ ሴት ፡ ደካማ ፡
ናትና ፡ እያረፈች ፡ ቆርጣ ፡ በአቁማዳ ፡
ቋጥራ ፡ ግንዱን ፡ በታች ፡ ገልብጣ ፡
ዘሩፉኑ ፡ በላይ ፡ አድርጋ ፡ ወጥታ ፡ ሔ
ዳለች ፤ ከፊቱልኝ ፡ ሥራ ፡ ሠርቼ ፡
መጥቻለኁ ፡ አለቻቸው ፡ ከፊቱላት ፡
ግዳይ ፡ ጣለችላቸው ፤ ይህች ፡ የጠገ
በች ፡ ጋለሞታ ፡ ያንዱን ፡ ወታደር ፡
ራስ ፡ ቆርጠሺ ፡ መጥተሻል ፡ እንጂ ፡
ከሱ ፡ ማን ፡ አድርሶሽ ፡ አሏት ፡ አከ
ዮር ፡ አሞናዊ ፡ ያውቀዋል ፡ ጥሩት ፡
ብለው ፡ አስመጡት ። አይቶ ፡ በእ
ማን ፡ ሆሎፎርኒስ ፡ በውነት ፡ ያለ ፡

ሐሰት ፡ እሱ ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ብሏ
ቸዋል ። እስራኤል ፡ ልበ ፡ ቀላል ፡
ናቸውና ፡ ሔዶን ፡ እንግጠም ፡ ብለ
ው ፡ ተነሥተዋል ፤ አይሆንም ፡ ንጉ
ሣቸው ፡ መሞቱን ፡ አላወቁም ፡ ያለ ፡
መስሏቸው ፡ አዕንተው ፡ ይዋጓችኋ
ል ፡ አትችሏቸውም ። ሲነጋ ፡ ቸብቸ
በውን ፡ በተራዳው ፡ ሰቅላችኁ ፡ የጠ
ር ፡ አበጋዝ ፡ ሹማችኁ ፡ ገጠሙ ፤
አውራ ፡ የሌለው ፡ ንብ ፤ እለቃ ፡ የሌ
ለው ፡ ሕዝብ ፤ መቆም ፡ አይሆንለት
ምና ፡ ድል ፡ ታደርጓቸዋላችኁ ፡ አለ
ቻቸው ። ሲነጋ ፡ ቸብቸበውን ፡ በተ
ራዳ ፡ ሰቅለው ፡ ሔደው ፡ ገጠሙ ፤
ወተታብዑ ፡ ብነ ፡ እሉ ፡ ዕደው ፡ እረ ፡
ዛሬስ ፡ እስራኤል ፡ ወንዳወንድ ፡ ሆኑ
ብን ፤ ሑር ፡ አንቅሆ ፡ ለእግዚእነ ፡
ሆሎፎርኒስ ፡ ይህች ፡ ዕብራዊት ፡ የ
ሌሊቱ ፡ አልበቃ ፡ ብሏት ፡ ቀኑንም ፡
ልትደግመው ፡ ነውን ፡ ሒደህ ፡ ንጉ
ሣችንን ፡ አሥነሣው ፡ ብለው ፡ ብላ
ቴና ፡ ላኩ ። ቢሔድ ፡ ግንዱ ፡ በታች ፡
ዘሩፉኑ ፡ በላይ ፡ ሁኖ ፡ አገኘው ፡ ዛቲ ፡
ዕብራዊት ፡ ኃሠረ ፡ ገብረት ፡ ላዕለ ፡
ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ይህች ፡ ዕብራዊ
ት ፡ እንዴት ፡ ተጫወተችብን ፡ ብ
ለው ፡ ሸሽተዋል ፡ እግር ፡ በራስ ፡
እየሆኑ ፡ አልቀዋል ፡ እስከ ፡ ዮርዳ
ኖስ ፡ እየተከተሉ ፡ አጥፍተዋቸዋል ፡
ከዚያ ፡ ሲመለሱ ፡ ዘንባባ ፡ ይዘው ፡
አመስግነዋታል ፡ ኀያሊት ፡ ነሽ ፡ መ
ዋዒት ፡ ነሽ ፡ ሊሉ ።

፲፪ ፡ እምላኪየ ፡ ኢትርኀቅ ፡ እምኔየ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ በረድኤት ፡ ከኔ ፡ አትራቅ ፡ ለጊዜውም ፡ ብትርቅ ፡ እንደ ፡ ራቅህ ፡ አትቅር ።

እምላኪየ ፡ ነጽር ፡ ውስተ ፡ ረዲኦትየ ።

ፈጣሪዬ ፡ እኔን ፡ ወደ ፡ መርዳት ፡ እይ ፡ ተመልከት ፡ እንድም ፡ እስተውለህ ፡ እርዳኝ ።

፲፫ ፡ ይትኀፈሩ ፡ ወይኅሥሩ ፡ እለ ፡ ያስተዋድዱ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ የሚያጣሏት ፡ የምያሳጧት ፡ ባቢሎናውያን ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ።

ወይልበሱ ፡ ሐፍረተ ፡ ወኀሣረ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ሊተ ፡ ሕማመ ።

የኔን ፡ መከራ ፡ የሚወዱ ፡ ባቢሎናውያን ፡ ኃፍረትን ፡ ተዋርዶን ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ ይጐናፀፉ ።

፲፬ ፡ ወአንሰ ፡ ዘልፈ ፡ እሴፈወከ ፡ እግዚኦ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ አንተን ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

ወእዌስከ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ስብሐቲከ ።

በምስጋናህ ፡ ላይ ፡ ምስጋና ፡ እጨምራለሁ ።

፲፭ ፡ አፉየ ፡ ይነግር ፡ ጽድቀከ ፡ ወኵሎ ፡ አሚረ ፡ አድኅኖተከ ።

አፉዬ ፡ ይነግር ፡ ጽድቀከ ፡ ወአድኅኖተከ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ብለህ ፡ አቅና ፡ እንደበቴም ፡ ትድግናህን ፡ ቸርነትህን ፡ ዘወትር ፡ ይናገራል ።

እስመ ፡ ኢየአምር ፡ ተግባረ ፡ ኢላጸጽ ፡ ፲፮ ።

ትሩፋ ፡ ሁልጊዜ ፡ ማርዳት ፡ ተቀግተህ ፡ አትወጣምን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ በቀኝ ፡ እጄ ፡ መወርወር ፡ በግራ ፡ እጄ ፡ መመከት ፡ አላውቅምና ፡ ዕበውዕ ፡ እንድም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ የመጣብህ ፡ ጣዖት ፡ ብታመልክ ፡ አይደለምን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ ሰው ፡ ሠራሺ ፡ ጣዖት ፡ አላመለከሁምና ፡ አፉዬ ፡ ይነግር ፡ ላለው ።

፲፯ ፡ እበውእ ፡ በኀይለ ፡ እግዚአብሔር ።

በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ድል ፡ ነሥቼ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እገባለሁ ።

እግዚኦ ፡ እዜክር ፡ ጽድቀከ ፡ ባሕቲቶ ።

አቤቱ ፡ ቸርነትህን ፡ ብቻ ፡ እናገራለሁ ።

፲፰ ፡ ወምሀርከኒ ፡ እምላኪየ ፡ እምንዕስየ ።

ፈጣሪዬ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሮ ፡ ይቅር ፡ አልከኝ ፡ አዘንከልኝ ።

እስከ ፡ ይዕዜ ፡ እነግር ፡ ስብሐቲከ ።

እነግር ፡ እምንዕስየ ፡ እስከ ፡ ይዕዜ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ጌትነትህን ፡ እነግራለሁ ፡ አስተምራለሁ ።

፲፱ ፡ እስከ ፡ እልሕቅ ፡ ወእረሥእ ፡ ኢትኅድገኒ ፡ እምላኪየ ።

ፈጣሪዬ ፡ ፈጽሜ ፡ እስከረጅ ፡ ድረስ ፡ በመከራው ፡ አትጣለኝ ።



እስከ ፡ እነግር ፡ መዝራዕተከ ፡ ለትውልድ ፡ ዘይመጽእ ።

እምንዕስየ ፡ እስከ ፡ ይዕዜ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ሥልጣንህን ፡ ሁለተኛ ፡ ለሚነሣ ፡ ትውልድ ፡ እነግራለሁ ፡ አስተምራለሁ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጣለኝ ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ ፍጻሜው ፡ የሌለው ፡ እስከ ፡ ነው ፡ ኢተመይጠ ፡ ቋዕ ፡ እስከ ፡ እመ ፡ ነትገ ፡ ማየ ፡ አይኅ ፡ ኢወለደት ፡ ሜልክል ፡ እስከ ፡ ሞተት ፡ እንዲል ።

ኀይለከኒ ፡ ወጽድቀከኒ ፡ ኢላ ፡ ፀ፳ ፡ ፱ ።

ከሃሊነትህን ፡ ቸርነትህን ፡ እስከነግር ፡ ድረስ ።

፳፱ ፡ እግዚኦ ፡ እስከ ፡ አርያም ፡ ገበርከ ፡ ዓቢያተ ።

አቤቱ ፡ ሰማያትን ፡ እስከ ፡ መፍጠር ፡ ድረስ ፡ እንድም ፡ ከአርያም ፡ የደረሰ ፡ እንጂ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ተአምራትን ፡ አብዝተህ ፡ ሠራህ ፡ እንድም ፡ ከእስራኤል ፡ ልዑላኑን ፡ ታደግህ ፡ ከአሕዛብ ፡ ልዑላኑን ፡ አጥፍተህ ፡ ኃይልህን ፡ ገለጽህ ።

እግዚኦ ፡ መኑ ፡ ከማከ ፡ መዝ፹፱ ፡ ፳፱ ፡ ፰ ።

አቤቱ ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ አለ ፡ ጠላቱን ፡ የሚያጠፋ ፡ ወዳጁን ፡ የሚጠቅም ።

፳ ፡ እስመ ፡ አርአይከኒ ፡ ሕማመ ፡ ወምንዳቤ ፡ ብዙኀ ።

ድኅረ ፡ አርአይከኒ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ፀዋትወ ፡ መከራ ፡ ከመጣብኝ ፡ በኋላ ።

ተመየጥከኒ ፡ ወአሕየውከኒ ።

ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ከቍጣ ፡ ወደ ፡ ትዕግሥት ፡ ተመልሰህ ፡ አድነኸኛልና ።

እግዚኦ ፡ መኑ ፡ ከማከ ።

እንድም ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ፀዋትወ ፡ መከራ ፡ አምጥተህብኝ ፡ ነበረና ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ከቍጣ ፡ ወደ ፡ ትዕግሥት ፡ ተመልሰህ ፡ ከመከራው ፡ አዳንከኝ ።

ወእምቀላየ ፡ ምድር ፡ አውፃእከኒ ።

ከግብፅ ፡ አወጣኸኝ ፡ ከዕበ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ከመከራው ፡ እንዳወጣኸኝ ፡ ከሀገሩም ፡ አወጣኸኝ ።

፳፩ ፡ ወአብዛኅከ ፡ ለጽድቅከ ።

ቸርነትህን ፡ አብዝተህ ፡ ሠራህልኝ ፡ ወገባዕከ ፡ ታሥተፍሥሐኒ ፡ ደስ ፡ ታሰኘኝ ፡ ዘንድ ፡ ደስ ፡ ወደ ፡ ማሰኘቱ ፡ ተመለስህልኝ ።

ወእምቀላየ ፡ ምድር ፡ ካዕበ ፡ አውፃእከኒ ።

ከግብፅ ፡ እንዳወጣኸኝ ፡ ከባቢሎን ፡ አወጣኸኝ ፡ እንድም ፡ ከግብፅ ፡ መከራ ፡ እንዳወጣኸኝ ፡ ከባቢሎን ፡ መከራ ፡ አወጣኸኝ ።

፳፪ ፡ ወአንሂ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ በንዋየ ፡ መዝሙር ፡ ለጽድቅከ ።

እኔም ፡ በበገና ፡ ዕቃ ፡ ለቸርነትህ ፡ እገዛለሁ ።

ወእዜምር ፡ ለከ ፡ አምላኪየ ፡ በመሰንቆ ፡ ቅዱስ ፡ እስራኤል ።

አምላኪየ ፡ ቅዱስ ፡ እስራኤል ፡ እዜም ር ፡ ለከ ፡ በመሰንቆ ፡ ብለህ ፡ እቅና ፡ ዕኑ ሪዮ ፡ መሰንቆውን ፡ እየመታሁ ፡ ላ ንተ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ፤ ዘሌ ፡ ፲፩ -፵፱ ፡ ፩ኢት ፡ ፩-፲፯ ።

፳፫ ፤ ይትፈሥሓኒ ፡ ከናፍርየ ፡ ሶበ ፡ እዜምር ፡ ለከ ።

ላንተ ፡ ምስጋና ፡ ባቀረብኩ ፡ ጊዜ ፡ አንደበቶቼ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወለነፍስየኒ ፡ እንተ ፡ አድኃንካ ።

ሰውነቴንም ፡ አንተ ፡ አዳንካት ።

፳፬ ፤ ወልሳንየ ፡ ያነብብ ፡ ጽድቀከ ፡ ኵሎ ፡ እሚረ ።

ዳግመኛ ፡ አንደበቴ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ቸርነትህን ፡ ይናገራል ፡ ያስተምራል ።

ሶበ ፡ ተኃፍሩ ፡ ወኃሥሩ ፡ እለ ፡ የኃሡ ፡ ሊተ ፡ እኩየ ።

ምን ፡ ጊዜ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ በኔ ፡ ክፉ ፡ ሊያመጡብኝ ፡ የሚወዱ ፡ ጉሉ ፡ ባፈሩ ፡ በተዋረዱ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዘላለሙ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይገባ ቸዋል ።

አሜን ።

## መዝሙር ፡ ፸፩ ።

፩ ፤ እግዚኦ ፡ ኵነኔከ ፡ ሀብ ፡ ለንጉሥ ።

ስለ ፡ ልጁ ፡ ስለ ፡ ሰሎሞን ፡ ተናግሮ ታል ፡ ከሥሩም ፡ አርዕስት ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የጌታም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ ዳዊትስ ፡ ልሕቀ ፡ ወረስዓ ፡ በመዋዕ ሊሁ ፡ ይላል ፡ ፈጥኖ ፡ አረጀ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ቢሉ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ዘ ጠኝ ፡ መቶ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ይኖሩ ፡ ነበረ ፡ ከኖህ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ ዘመን ፡ እየተከፈለ ፡ ሔዷል ፡ እም ስት ፡ መቶ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ፪ ፡ መቶ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሁኗል ፡ ወይከውን ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ፡ ምዕተ ፡ ወእሥራ ፡ እን ዲል ። በመቃብያንም ፡ ወገብዑ ፡ ሺ ኤል ፡ ኀበ ፡ ምዕት ፡ ወእሥራ ፡ ብሎ ፡ ያቀናዋል ።

እሱ ፡ ባለቤቱ ፡ ዳዊትም ፡ ወመዋዕለ ፡ ዓመቲነኒ ፡ ሰብዓ ፡ ክራማት ፡ ወእመሰ ፡ ብዝኃ ፡ ሰማንያ ፡ ዓም ፡ ወፈድፋዶ



ንሰ ፡ እምእላ ፡ ፃማ ፡ ወሕማም ፡ ብሎ ፡ በተናገረው ፡ መዝ ፡ ፹፱ ፡ ፲ ። አንድም ፡ መልአክ ፡ መደምሰስ ፡ በዓውደ ፡ አ ርና ፡ ሲቀሥፍ ፡ ታይቶት ፡ ደንግጦ ፡ ነበርና ፡ አንድም ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጦር ፡ ሲወራ ፡ ውሎ ፡ መድኃ ኒትም ፡ ጠጥቶ ፡ ቢሉ ፡ ደከሞት ፡ ሳለ ፡ ከራቱ ፡ ሬፋይን ፡ አንዱ ፡ የጎል ያድን ፡ በቀል ፡ ደገል ፡ እመልሳለሁ ፡ ብሎ ፡ ዘገር ፡ ነቅንቆ ፡ መጣበት ፡ ወ የው ፡ የእእላፈ ፡ እስራኤል ፡ ያለህ ፡ አለ ፡ ወወውዐ ፡ ሎቱ ፡ አቢሳ ፡ ወ ልደ ፡ ሶርህያ ፡ እኅቱ ፡ ይላል ፡ አድ ኖታል ።

አንድም ፡ የሌሊት ፡ ግሥገሣ ፡ የቀን ፡ ዘለሳ ፡ ያማታው ፡ ነበርና ፡ አንድም ፡ እግሩ ፡ ከእርከብ ፡ እጁ ፡ ከዛብ ፡ አይ ለይም ፡ ነበርና ፡ በዚያም ፡ በዚያም ፡ ብሎ ፡ ፈጥኖ ፡ አረጀ ፡ አዶንያስ ፡ ወ ልደ ፡ አጊት ፡ አቤሴሎም ፡ ሞተ ፡ አባቴ ፡ ዳዊትም ፡ አረጀ ፡ ወንድሜ ፡ ሰሎሞንም ፡ እንዳይነግሥ ፡ ሕፃን ፡ ኾነ ፡ የአባቴ ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሲኼድ ፡ ዝም ፡ እላለሁን ፡ ብሎ ፡ የወ ንድሜ ፡ የአቤሴሎም ፡ ምክሩ ፡ የአ ልጸናለት ፡ ከኢዮአብ ፡ ጋራ ፡ ባይመ ከር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወከነ ፡ ምክሩ ፡ ም ስለ ፡ ኢዮዓብ ፡ ይላል ፡ ምክሩን ፡ ከ ኢዮአብ ፡ ጋራ ፡ አድርጓል ፡ መብቱ ፡ ለአንተ ፡ ስሙ ፡ ለእኔ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ መከሮ ፡ የሚቀባውን ፡ አብያታርን ፡ ይዞ ፡ ሔዶ ፡ የሰባ ፡ የፀራ ፡ አውርዶ ፡ በኪሊቲ ፡ ዘዘኤልቲ ፡ ነግሦ ፡ አለ ፡ ወከ ፡ እሰን ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ሔዶ ፡ ቤርሳቤህን ፡ ኢሰማ ዕኪኑ ፡ ከመ ፡ ነግሠ ፡ አዶንያስ ፡ ወ ልደ ፡ አጊት ፡ አላት ፡ ምነው ፡ ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ወሬ ፡ ቢሉ ፡ ከዝከር ፡ ያልጠሩት ፡ ደብተራ ፡ ው ቅር ፡ ይወሬ ፡ እንዲሉ ፡ ካልተማከ ሩኝ ፡ ብሎ ፤ አንድም ፡ ተዘምዶተ ፡ ሥጋ ፡ ኑሮት ፡ አድልቶ ፤ አንድም ፡ የአዶንያስ ፡ መንግሥት ፡ እንዳይፀና ፡ የሰሎሞን ፡ እንዲፀና ፡ ያውቃልና ፡ እሷም ፡ አልሰማሁም ፡ እንጂ ፡ ብሰ ማስ ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ ፡ ሴት ፡ አይ ደለሁምን ፡ አለችው ፡ ሒደሽ ፡ ተሐ ሰወኑ ፡ ቃልከ ፡ እግዚእየ ፡ ከመ ፡ ሰ ሎሞን ፡ ወልድየ ፡ ይነግሥ ፡ እምድ ድኅሬየ ፡ ጌታዬ ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፡ ልጄ ፡ ሰሎሞን ፡ ይነግሣል ፡ ብለህ ፡ አልነበ ረምን ፡ ቃልህ ፡ ይታበላልን ፡ በዪው ፡ እኔ ፡ ኋላ ፡ መጥቼ ፡ ነገርሽን ፡ እቃና ልሻለሁ ፡ አላት ፡ ሒዳ ፡ ንገሩልኝ ፡ አለቻቸው ፡ ምነው ፡ ንግሥት ፡ አይ ደለችምን ፡ እንዲህ ፡ ማለቷ ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡ አቤሴሎም ፡ ከሚስቶቹ ፡ ከተ ገናኘ ፡ በኋላ ፡ አልተገናኛቸውም ፡ ነበርና ፡ ግቢ ፡ በኋት ፡ አለ ፡ ገብታ ፡ ስትነጋገር ፡ ሳይመልስላት ፡ ናታን ፡ መጥቷል ፡ አሉት ፡ ግባ ፡ በሉት ፡ አላቸው ፡ ገብቶ ፡ ከዚህ ፡ አስቀድ ሞ ፡ ለኔ ፡ ሳታማክር ፡ የምትወራው ፡ ሥራ ፡ አልነበረም ፡ ቤተ ፡ መቅደ



2014 04 17

ስን ፡ ስንኳ ፡ በሠራህ ፡ ጊዜ ፡ እማክ
ረኸኝ ፡ ነበረ ፡ ምነው ፡ ደገኛውን ፡
ልጅህን ፡ አዶንያስን ፡ ስታነግሥ ፡ ሳ
ንድ ፡ እንደሆነ ፡ አውቆ ፡ ጸውዕዋ ፡
ለቤርሳቤህ ፡ አለ ፡ ምነው ፡ ከዚያው ፡
ቁማለች ፡ አላልንም ፡ ቢሉ ፡ ነገሥት ፡
ሸኤል ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ እንደ ፡ አ
ባት ፡ ያከብሯቸው ፡ እንደ ፡ መምር ፡
ይፈሯቸው ፡ ነበር ፡ ከሴት ፡ ጋራ ፡ ተቀ
ምጠው ፡ አይቈይዋቸውምና ፡ ወደ ፡
እልፍኝ ፡ አልፋ ፡ ነበር ፡ ሕያው ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ዘቤዘዋ ፡ ለነፍስየ ፡ እም
ኵሉ ፡ ምንዳቤየ ፡ ከመ ፡ ሰሎሞን ፡
ወልድየ ፡ ይነግሥ ፡ እምድኅሬየ ፡ አ
ላቸው ፤ ወድያው ፡ የዋለ ፡ ያደረ ፡
እንደሆነ ፡ ጠላት ፡ ይበዛበታል ፡ ነ
ገር ፡ ይበረታበታል ፡ ብሎ ፡ ጸውዑ ፡
ናታንሃ ፡ ነቢየ ፡ ወሳዶቅሃ ፡ ካህነ ፡
ወብንያስሃ ፡ ወልደ ፡ ዮዳሔ ፡ ፌል
ቲ ፡ ኬልቲ ፡ ስመ ፡ ጭፍራ ፡ ነው ፡
ጥሩ ፡ አላቸው ፤ ወአዕዕንዎ ፡ ለሰሎ
ሞን ፡ ወልድየ ፡ ዲበ ፡ በቅልየ ፡ ወአ
ውረድዎ ፡ ውስተ ፡ ግዮን ፡ ወበህየ ፡
ቅብዕዎ ፡ ወአንግሥዎ ፡ ወበልዎ ፡ ሕ
ያው ፡ አበ ፡ ነጋሢ ፡ ልጁን ፡ ሰሎሞ
ንን ፡ እኔ ፡ በምቀመጥበት ፡ መደቡት ፡
በምትባል ፡ በቅሎ ፡ አስቀምጣችኍ ፡
ግዮን ፡ ወደሚባል ፡ መናገሻ ፡ አው
ርዳችኍ ፡ ቀብታችኍ ፡ አንግሡት ፡
አላቸው ፤ ወስደው ፡ ቀብተው ፡ አነገ
ሡት ፡ ሸኤልም ፡ ሕያው ፡ አበ ፡ ነጋሢ ፡

ብለውታል ፤ ሕያው ፡ አበ ፡ ነጋሢ ፡
ማለትም ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ያንግሥሕ ፡
ማለት ፡ ነው ፡ እንድም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡
ወልደህ ፡ ለበርናስ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡
ወልደህ ፡ ለፈረስ ፡ አድርስ ፡ ሲሉት ፡
ነው ፡ ምድርም ፡ እልል ፡ ብላ ፡ ተቀ
ብላዋለች ። ፩ ፡ ነገ ፡ ፩-፶፫ ።

ወእምድኅረ ፡ አኅለቁ ፡ መሢሐ ፡ አለ ፡
ናታን ፡ ሰሎሞንን ፡ ቀብተው ፡ ካነ
ገሡ ፡ በኋላ ፡ ምሳሐ ፡ አለ ፡ አዶንያስ ፡
በልተው ፡ ከጠገቡ ፡ በኋላ ፡ የአብያ
ታር ፡ ልጅ ፡ አኪማሆስ ፡ ሐጀ ፡ አበ
ቱን ፡ ከነገር ፡ ላድን ፡ ብሎ ፡ ሒዶ ፡
ሲያደባ ፡ አዶንያስ ፡ ድንኳን ፡ ገልጠ ፡
ሲመለከት ፡ ሲያደባ ፡ አይቶ ፡ ባእ ፡
እስመ ፡ ብእሴ ፡ ሰላም ፡ አንተ ፡ ወሠ
ናየ ፡ ዜና ፡ ትዜኑ ፡ አለው ፡ አባቱን ፡
ዳዊትን ፤ ኢትብኢት ፡ ውስተ ፡ አራ
ቦት ፡ አላ ፡ አፍጥን ፡ ዓዲወ ፡ ዮርዳ
ኖስ ፡ ሲል ፡ ሰምቶ ፡ ነበርና ፡ በጎ ፡
ወሬ ፡ ይነግረኛል ፡ ብሎ ፡ እስኪ ፡
ወሬ ፡ ንገረኝ ፡ ይህ ፡ የምሰማው ፡ እ
ልልታ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ አለው ፡
ምን ፡ ልንገርህ ፡ እናንተ ፡ ከዚህ ፡ እ
ግር ፡ ዝርጊት ፡ ሁናችሁ ፡ ተቀምጣች
ኋል ፡ አባትህ ፡ ዳዊት ፡ ግን ፡ ልጁን ፡
ሰሎሞንን ፡ አነገሠው ፡ ምድርም ፡ እ
ልል ፡ ብላ ፡ ተቀበለችው ፡ አላቸው ፡
ወአኃዞ ፡ ይሠረቁ ፡ ጽውዓኒሁ ፡ ለአ
ዶንያስ ፡ ወሖረ ፡ ብእሲ ፡ ብእሲ ፡
ፍኖቶ ፡ ይላል ፤ አንዱም ፡ አንዱ ፡
እያንዳንዱ ፡ እየከዳ ፡ ከሰሎሞን ፡ ገባ ፡



ብሎ ፡ ቤቱ ፡ አዶንያስ ፡ ኢዮአብ ፡ አ
ብያታርም ፡ ከአቅርንተ ፡ ምሥዋዕ ፡
ሒደው ፡ ተማፀኑ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ተ
በቅሎ ፡ እንዲያጠፋቸው ፡ ያውቃልና ፡
ለጊዜው ፡ አልፈለጋቸውም ፡ ከዚያ ፡
ሲመለስ ፡ ዳዊት ፡ ዝቅ ፡ ካለ ፡ ዙፋን ፡
ሁኖ ፡ ሰሎሞንን ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ዙፋን ፡
አስቀምጠ ፡ ይህን ፡ ተናግሮለታል ፤
ስለምን ፡ ቢሉ ፡ እኔ ፡ ወደመሬትነቴ ፡
እሔዳለሁ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ መንግሥ
ትህ ፡ እየፀናች ፡ ሀብትህ ፡ እየበዛች ፡
ትሔዳለህ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አንድም ፡
ዳዊት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዙፋን ፡ ሰሎሞን ፡
ዝቅ ፡ ዙፋን ፡ ሳለ ፡ ተናግሮታል ፡ በ
አንብሮተ ፡ እድ ፡ ለመባረክ ፡ ይመ
ቻኛል ፡ ብሎ ፡ እግዚእ ፡ ኰነኔከ ፡
ሀበ ፡ ለንጉሥ ፡ ብሎ ፡ ለሱ ፡ ይጸልይ
ለታል ። ኰንን ፡ በጽድቅ ፡ ብሎ ፡ እ
ሱን ፡ ለሕዝቡ ፡ ይመክርላቸዋል ።
ወአኅስሮ ፡ ለዕቡይ ፡ ብሎ ፡ ሥራት ፡
ያስተምርላቸዋል ። ወይወርድ ፡ ከመ ፡
ጠል ፡ ውስተ ፡ ፀምር ፡ ብሎ ፡ ሕዝ
ቡን ፡ ይመክርለታል ፤ ያሥራ ፡ ሁለ
ት ፡ ዓመት ፡ ሕፃን ፡ አነገሠብን ፡ ብላ
ችኍ ፡ ልባችኍ ፡ አይዘን ፡ ጠል ፡ ከሰ
ማይ ፡ ወርዶ ፡ ከምድር ፡ እንዲሰማማ ፡
የሰሎሞንም ፡ ነገሩ ፡ ከሰው ፡ ልቡና ፡
ይሰማማል ፡ ይስማማ ።

አቤቱ ፡ የባሕርይህን ፡ መንግሥት ፡
ለሰሎሞን ፡ በጸጋ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ ስ
ጠው ።

ጽድቀከኒ ፡ ለወልደ ፡ ንጉሥ ።

እውነተኛውን ፡ ፍርድህንም ፡ በፀጋ ፡
ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ለኔ ፡ ለንጉሡ ፡ ልጅ ፡
ለሰሎሞን ፡ ግለጽለት ፤ አንድም ፡ (እ
ግዚእ) ፡ አቤቱ ፡ የባሕርይህን ፡ ግዛት ፡
ለክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡
ስጠው ። (ጽድቀከኒ) ፡ የባሕርይህን
ም ፡ ፍርድ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ ይፈር
ደው ፡ ዘንድ ፡ ላንተ ፡ ለንጉሡ ፡ ልጅ ፡
ለክርስቶስ ፡ ገንዘብ ፡ አድርግለት ፡
ማለት ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ እንግድነት ፤ አን
ድም ፡ ለኔ ፡ ለንጉሡ ፡ ለዳዊት ፡ ልጅ ፡
ለክርስቶስ ፡ ገንዘብ ፡ አድርግለት ፡
ወልደ ፡ ዳዊት ፡ ይለዋልና ፤ ዕውሩን ፡
በሆሣዕና ፡ ተማሃለነ ፡ ወልደ ፡ ዳዊት ፡
እንዳሉ ።

አሁን ፡ ዳዊት ፡ ለምኖ ፡ እግልዶ ፡
የሚያሰጠው ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ፡ የ
ሥጋ ፡ እምላክነት ፡ ተገልጾለት ፡ ትን
ቢት ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ።

፪ ፡ ከመ ፡ ይኰንኖሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ በጽድቅ ።

ወገኖችህ ፡ ጭዎችን ፡ በውነት ፡ ይገ
ዛቸው ፡ ዘንድ ፡ (ሀበ) ።

ወለነዳያኒከ ፡ በፍትሕ ።

ከህናቱንም ፡ እውነት ፡ ፈርዶ ፡ ይገዛ
ቸው ፡ ዘንድ ፤ አንድም ፡ (ለሕዝብከ) ፡
ባለጸጎቹን ፡ (ለነዳያኒከ) ፡ ድኆችን ፡
በውነት ፡ ፈርዶ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ (ሀበ) ።

2014 04 17

፫፡ ይትወከፉ፡ አድባር፡ ወአውግር፡ ሰላመ፡ ሕዝብከ።

ነገሥታቱ፡ መኳንንቱ፡ የሕዝቡን፡ አንድነት፡ ፍቅር፡ ይቀበሉ፡ ዘንድ፡ ማለት፡ ገገር፡ ከተገገር፡ አንድ፡ ሁነ ው፡ ባንድነት፡ ይኖሩ፡ ዘንድ፡ አን ድም፡ ምእመናን፡ ሽኤል፡ ምእመናን፡ አሕዛብ፡ የሐዋርያትን፡ የሰብዓ፡ አር ድእትን፡ ትምርት፡ ደስ፡ ብሏቸው፡ ይቀበሉ፡ ዘንድ።

፬፡ ኰንን፡ በጽድቅ፡ ነዳያነ፡ ሕዝብከ።

አንድም፡ አንተም፡ ልጁ፡ ሰሎሞን፡ ወገኖችህን፡ ነዳያን፡ በውነት፡ ፈር ደህ፡ ግዛ። አንድም፡ አንተም፡ ልጁ፡ ክርስቶስ፡ በውነት፡ ፈርደህ፡ ግዛ።

ወአድኅኖሙ፡ ለደቂቀ፡ ምስኪናንከ።

የድኆችን፡ አንድም፡ የአዳም፡ የሔ ዋንን፡ ልጆች፡ አድናቸው።

፭፡ ወአኅሥር፡ ለዐቡይ።

ሌባ፡ ቀማኛውን፡ ግን፡ አዋርደው፡ አንድም፡ ያረጀ፡ የኢዮአብን፡ ሰው ነት፡ በደም፡ አልለህ፡ ወደ፡ መቃ ብር፡ እንድታወርደው፡ እወቅ፡ አእ ምር፡ ከመ፡ ታወርድ፡ ሲበቲሁ፡ በ ደም፡ እንዲል፡ ፩፡ ነገ፡ ፪፡ ፯፡ አንድም፡ ዲያብሎስን፡ በጥምቀት፡ በመስቀል፡ ድል፡ ነስተህ፡ አዋርደው።

ወይጸንዕ፡ ምስለ፡ ፀሐይ።

የሰሎሞን፡ መንግሥት፡ ከፀሐይ፡ ጋራ፡ ይኑር፡ ማለት፡ ፀሐይ፡ ሳያልፍ፡ አይለፍ።

ወእምቅድመ፡ ወርኅ፡ ለትውልደ፡ ትውልድ።

ኢይልፍ፡ ያለበት፡ ነው፡ ከጨረቃ ም፡ አስቀድሞ፡ ለልጅ፡ ልጅ፡ አይ ለፍ፡ አንድም፡ ይጸንዕ፡ ምስለ፡ ፀ ሐይ፡ ዘእምቅድመ፡ ወርኅ፡ ይላል፡ ከጨረቃ፡ አስቀድሞ፡ የተፈጠረ፡ ፀሐይ፡ ሳያልፍ፡ አይለፍ፡ ይህስ፡ ፀሐይን፡ የማክሰኞ፡ ጨረቃን፡ የረ ቡዕ፡ ፍጥረት፡ ማድረግ፡ ነው፡ ብሎ፡ ፀሐይ፡ ዘበእንጻረ፡ ወርኅ፡ ይላል፡ በጨረቃ፡ አንጻር፡ የተፈጠረ፡ ፀሐ ይ፡ ሳያልፍ፡ አይለፍ፡ ፀሐይ፡ በም ዕራብ፡ ባራተኛው፡ መስኮት፡ ተፈ ጥሮ፡ ሲገባ፡ ጨረቃም፡ በምሥራቅ፡ ሲፈጠር፡ ብርሃን፡ ለብርሃን፡ ተያይ ተዋል። ይህም፡ ወይትናጸሩ፡ በገ ሃሁ፡ ያለው፡ ይፈርሳል፡ ብሎ፡ ፀሐ ይ፡ በምዕራብ፡ ተፈጥሮ፡ በአድማ ስና፡ በናጌብ፡ መኻል፡ ሲያበራ፡ አ ድሮ፡ በምሥራቅ፡ ሲወጣ፡ ጨረቃ ም፡ በምሥራቅ፡ ተፈጥሮ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ያሥራ፡ አምስት፡ ሙሉ፡ ብር ሃን፡ ሁና፡ ስታበራ፡ አድራ፡ በምዕ ራብ፡ ስትገባ፡ ተያይተዋል።

፮ ወይወርድ፡ ከመ፡ ጠል፡ ውስተ፡ ፀምር።

ጠል፡ ከሰማይ፡ ወርዶ፡ ከፀምር፡ እን ዲስማማ፡ የሰሎሞንም፡ ነገሩ፡ ከሰ ው፡ ልቡና፡ ይሰማማል፡ ይስማማ፤ አንድም፡ ጠል፡ ከሰማይ፡ ወርዶ፡ ከፀምር፡ እንዲስማማ፡ ጌታም፡ በማኅፀነ፡ ማርያም፡ ያድራል፡ ይደር፤ አን ድም፡ ጠል፡ ምሳሌው፡ እንደመሆኑ፡ ፀምር፡ ምሳሌዋ፡ በሚሆን፡ በእመ ቤታችን፡ ማኅፀን፡ ያድራል፡ ይደር፤ ፀምር፡ ዘጌዴዎን፡ እንዲላት።

ወከመ፡ ነጠብጣብ፡ ዘያንጠበጥብ፡ ዲበ፡ ምድ ር፡ ሆሴዕ፡ ፮፡ ፪።

ለስ፡ ያለ፡ ዝንም፡ ከሰማይ፡ ወርዶ፡ ከምድር፡ እንዲስማማ፡ የሰሎሞንም፡ ነገሩ፡ ከሰው፡ ልቡና፡ ይሰማማል፡ ይ ስማማ። አንድም፡ ለስ፡ ያለ፡ ዝናም፡ ከሰማይ፡ ወርዶ፡ ከምድር፡ እንዲስ ማማ፡ ጌታም፡ በማኅፀነ፡ ማርያም፡ ያድራል፡ ይደር፤ አንድም፡ እንተ፡ በአማን፡ ንጹሕ፡ ዝናም፤ የሚባል፡ ጌታ፡ ምድር፡ ዕምዕት፡ ዘኢሳይያስ፡ በምትባል፡ በመቤታችን፡ ማኅፀን፡ ያድራል፡ ይደር።

፯፡ ወይሠርፅ፡ ጽድቅ፡ በመዋዕሊሁ።

በሰሎሞን፡ ዘመን፡ እውነት፡ ይፈረ ዳል፤ አንድም፡ በጌታ፡ ዘመን፡ ወን ጌል፡ ትነገራለች።

ወብዙኅ፡ ሰላም፡ እስከ፡ የኃልፍ፡ ወርኅ።

ዓርብ፡ ዘመን፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ፡ ብዙ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ይደረጋል። ወይበልፀ፡ ታሕተ፡ በለሰሙ፡ ወወ ይኖሙ፡ ተአሚኖሙ፡ ይላል፤ ዓርብ፡ ዘመን፡ ሙሉ፡ ሥጋዊ፡ ጠላት፡ ጠፍ ላቸው፡ በወይናቸው፡ በበለሳቸው፡ ጥላ፡ አርፈው፡ ይኖሩ፡ ነበረና፡ አን ድም፡ ሠላሳ፡ ሦስት፡ ዓመት፡ ከሦ ስት፡ ወር፡ ብዙ፡ ታምራት፡ ይደረ ጋል፤ ስንኳን፡ ሥጋዊ፡ መንፈሳዊ፡ ጠላት፡ ጠፍቶላቸው፡ በዕረፍት፡ ይ ኖሩ፡ ነበረና፤ አጠፍዕ፡ ሠረገላ፡ እም ኤፍሬም፡ ወአፍራሰ፡ እምይሁዳ፡ እን ዲል፤ ኢሳ፡ ፱፡ ፮-፯። ዘካ፡ ፩-፱፡ ፯፡ ፱

፰፡ ወይኬንን፡ እምባሕር፡ እስከ፡ ባሕር።

ሰሎሞን፡ ከጢግሮስ፡ እስከ፡ ኤፍራ ጥስ፡ ይገዛል፤ አንድም፡ ጌታ፡ ከው ቅያኖስ፡ እስከ፡ ውቅያኖስ፡ ይገዛል።

ወእምአፍላግ፡ እስከ፡ አጽናፈ፡ ዓለም።

ሰሎሞን፡ ከዳን፡ እስከ፡ ቤርሳቤህ፡ ድረስ፤ አንድም፡ ጌታ፡ ከአድማስ፡ እስከ፡ አድማስ፡ ይገዛል። ኢሳ፡ ፳፡ ፲፩ ዘካ፡ ፱፡ ፲።

፱፡ ይገንዩ፡ ቅድሜሁ፡ ኢትዮጵያ።

የኢትዮጵያ፡ ሰዎች፡ ይገዙለታል፤ ማከዳ፡ ይላታል፤ የኢትዮጵያ፡ ንግ ሥት፡ መቶ፡ ኻያ፡ መክሊተ፡ ወር ቅ፡ ዝባድ፡ ሉል፡ ተንከራ፡ ዘኢት ዮጵያ፡ ይለዋል፡ ገብራለታለችና። አንድም፡ ለጌታ፡ ፍጥረት፡ ሁሉ፡ ይገዙለታል።

ጸላእቱሂ፡ ሐመደ፡ ይቀምሑ።

የሰሎሞን፡ ጠላቶቹ፡ አመድ፡ ይመ ገባሉ፡ ማለት፡ ተዋርዷቸውን፡ መና ገር፡ ነው፤ አንድም፡ ግዳይ፡ ብለው፡



2014 04 17

ሲጥሏቸው ፡ በግንባራቸው ፡ በከንፈ
ራቸው ፡ ይዘውት ፡ ይነሣሉና ፤ አሠ
ሩን ፡ ብጣሪውን ፡ አሸር ፡ ባሸሩን ፤
ባቊላውን ፤ ዘንጋዳውን ፡ ይመግቧቸ
ዋልና ፤ አንድም ፡ አጋንንት ፡ እንደ ፡
ትብያ ፡ በንነው ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ ተን
ነው ፡ ይጠፋሉ ። ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፵፪ ።

፲ ፤ ነገሥተ ፡ ተርሴስ ፡ ወደሰያት ፡ አምኃ ፡
ያበውኡ ።

የተርሴስ ፡ የደሰያት ፡ ነገሥታት ፡ እጅ ፡
መንሻ ፡ ግብር ፡ ያቀርቡለታል ፡ ማለ
ት ፡ የፋስ ፡ ቆሎ ፡ ንጉሥ ፡ ገብሮለ
ታልና ፤ አንድም ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፡
ለጌታ ፡ ሦስቱን ፡ ንዋያት ፡ ይገብሩ
ለታል ።

ነገሥተ ፡ ሳባ ፡ ወዓረብ ፡ ጋዳ ፡ ያመጽኡ ።

የሳባ ፡ የዓረብ ፡ ነገሥታት ፡ እጅ ፡
መንሻ ፡ ያመጡለታል ፤ አንድም ፡ ለጌ
ታ ፡ ባዜን ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይገ
ብርለታል ፡ ወአመ ፲ወ፫ ፡ ዓመት ፡
መንግሥቱ ፡ ለባዜን ፡ ንጉሠ ፡ ኢት
ዮጵያ ፡ ተወልደ ፡ እግዚእነ ፡ እንዲል ፡
በዘመኑ ፡ ስለ ፡ ተወለደ ፡ እንዲህ ፡
አለ ፡ ኢሳ፲፰ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ፯ ፡ ማቴ፪ ፡ ፲፩ ።

፲፩ ፤ ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡ ነገሥተ ፡
ምድር ።

ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ያሉ ፡ ነገሥት ፡
ሁሉ ፡ እየመጡ ፡ ይሰግዱለታል ።

ወይትቀነዩ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ።

አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ይገዙለታል ።

፲፪ ፤ እስመ ፡ አድኃኖ ፡ ለነዳይ ፡ እምእደ ፡
ዘይትዔገሎ ።

ድኃውን ፡ ከሚቀማው ፡ ከዳንደ ፡ ከወ
ንበዴ ፡ እጅ ፡ አድኖታልና ፤ አንድ
ም ፡ ጌታ ፡ አዳምን ፡ ልጅነቱን ፡ ከሚ
ያስወስድበት ፡ ከዲያብሎስ ፡ እጅ ፡
አድኖታልና ።

ለምስኪን ፡ ዘአልቦ ፡ ረዳኢ ፡ ኢሳ፶፭ ፡ ፩ ።

ዘአልቦ ፡ ረዳኢ ፡ ለማለት ፡ ደገመው ፡
ረዳት ፡ የሌለውንም ፡ ድኃ ፡ አድኖ
ታልና ።

፲፫ ፤ ወይምህክ ፡ ነዳየ ፡ ወምስኪነ ።

ለነዳይ ፡ ለምስኪን ፡ ያዝናል ፡ ይራ
ራል ፤ አንድም ፡ ለአዳምና ፡ ለሔዋን ፡
ያዝናል ፡ ይራራል ።

ወያድኅን ፡ ነፍሰ ፡ ነዳያን ፡ ኤር፰ ፡ ፲፫ ።

የድኆችን ፡ ሰውነት ፤ አንድም ፡ የአ
ዳምና ፡ የሔዋንን ፡ ነፍስ ፡ ያድናል ።

፲፬ ፤ እምርደ ፡ ወእምትዕግልት ፡ ያድኅና ፡
ለነፍሶሙ ።

ከራጣ ፡ ከሚቀማ ፡ ሰውነታቸውን ፡
ያድናታል ፡ በሰሎሞን ፡ ጊዜ ፡ የምያ
በድር ፡ የሚበደር ፡ የሚቀማ ፡ የሚ
ቀማ ፡ የለም ፡ ነበር ፡ ቢያበድር ፡ ቅሉ ፡
አራጣ ፡ ትርፍ ፡ የሚቀበል ፡ አልነበ
ረምና ፡ አንድም ፡ በሐልዮ ፡ በነቢ
ብ ፡ በገቢር ፡ ከሚመጣው ፡ ፍዳ ፡ ነፍ
ሳቸውን ፡ ያድናታል ።



ወክቡር ፡ ስሙ ፡ በቅድሜሆሙ ።

ስሙ ፡ በሳቸው ፡ ዘንድ ፡ የከበረ ፡ የገ
ነነ ፡ ነው ።

፲፭ ፤ የሐዩ ፡ ወይሁብዎ ፡ እምወርቀ ፡ ዓረብ ።

እንዘ ፡ ይሁብዎ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ከም
ዕራብ ፡ ጽሩይ ፡ ወርቅ ፡ ሲገብሩለት ፡
ይኖራል ፡ አንድም ፡ ጽሩይ ፡ ምግባር ፡
ሃይማኖት ፡ ሲያቀርቡለት ፡ ይኖራል ።

ወዘልፈ ፡ ይጼልዩ ፡ በእንቲአሁ ።

ስለሱ ፡ ዘወትር ፡ ይጸልያሉ ፡ ጸልዩ ፡
በእንተ ፡ ንጉሥን ፡ ናቡከደነፆር ፡ ወብ
ልጣሶር ፡ ወልዱ ፡ እንዲል ፡ ስንኳን ፡
ለምእመናን ፡ ንጉሥ ፡ ለአሕዛብም ፡
ንጉሥ ፡ ሊጸልዩለት ፡ ይገባልና ፤ አን
ድም ፡ በቅንነው ፡ ወልድከ ፡ በስቁል ፡
ወልድከ ፡ እያሉ ፡ በሱ ፡ ለራሳቸው ፡
ስለምያገኙት ፡ ድኅነት ፡ ይጸልያሉ ።

ወኵሎ ፡ እሚረ ፡ ይድኅርዎ ።

ዕለት ፡ ዕለት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ያንግ
ሥህ ፡ እያሉ ፡ ይመርቁታል ፤ አንድ
ም ፡ ጌታን ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ያመሰግ
ኑታል ።

፲፮ ፤ ወይከውን ፡ ምስማከ ፡ ለኵሉ ፡ ምድር ።

ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ሁሉ ፡ አምባ ፡ መ
ፀግያ ፡ ይሆናል ።

ውስተ ፡ አርእስተ ፡ አድባር ።

ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሁኖ ፤ አንድም ፡ በኵ
ረ ፡ ነቢያት ፡ በኵረ ፡ ሐዋርያት ፡ ሁኖ ።

ወይነውኅ ፡ እምሊባኖስ ፡ ፍሬሁ ።

ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ከዛፍ ፡ ፍሬ ፡ ይበዛል ፡
ኢሳ፵፱ ፡ ፬ ፡ ፶፫ ፡ ፬ ።

ወይበቍል ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ከመ ፡ ሣዕረ ፡ ምድር ፡
ኢዮ፭ ፡ ፳፭ ።

ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ እንደበቀለ ፡ ሣር ፡
ይሆናል ፡ ወነበበ ፡ ሰሎሞን ፡ ፴፻፭ ፡
ምሳሌ ፡ ፲ወ፭፻ ፡ መኃልየ ፡ እንዲል ፡
አንድም ፡ እንዲህ ፡ ባለው ፡ አፀፋ ፡
ወነበበ ፡ ሰሎሞን ፡ ፫፻አምሳለ ፡ ወ፭፻ ፡
መኃልየ ፡ ይላል ።

አንድም ፡ የጌታ ፡ ነገሩ ፡ ባራቱ ፡ መዓ
ዝ ፡ እንደበቀለ ፡ ሣር ፡ ይሆናል ፡
ወሰበ ፡ ተጽሕፈ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩፩ ፡ እም
ኢያግመሮ ፡ ዓለም ፡ ጥቀ ፡ መጻሕፍ
ቲሁ ፡ እንዲል ፡ ዮሐ፳፩ ።

፲፯ ፤ ወይከውን ፡ ቡሩክ ፡ ስሙ ፡ ለዓለም ።

ስሙ ፡ ለዘላለም ፡ የከበረ ፡ የገነነ ፡ ይሆ
ናል ፡ (ይከበር ፡ ይመስገን) ።

እምቅድመ ፡ ፀሐይ ፡ ፀሎ ፡ ስሙ ።

ስሙ ፡ ከፀሐይ ፡ አስቀድሞ ፡ ነበረ ፡
ሰሎሞን ፡ ማለት ፡ መስተሳልም ፡ መ
ስተፋቅር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የጌታ ፡ ስም ፡
ነውና ፤ አንድም ፡ ተወልዶ ፡ ፀሐይ ፡
ሳያየው ፤ አንድም ፡ ከፀሐይ ፡ ልደቱ ፡
አስቀድሞ ፡ ነበረ ፤ ናታን ፡ ዳዊትን ፡
ቤርሳቤህ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወልድ
ሃለች ፡ ስሙን ፡ ሰሎሞን ፡ በለው ፡
ብሎታልና ፡ ለጌታ ፡ የተመቸ ።

ወይትባረኩ ፡ ቦቱ ፡ ኵሉ ፡ አሕዛብ ፡ ምድር ።

ባሬቱ ፡ መዓዝን ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ በሱ ፡ ከብረው ፡ ገንነው ፡ ይኖራ ሉ ፡ ማለት ፡ ሰሎሞንን ፡ ያከበረ ፡ (ው) ፡ አምላክ ፡ ያከብርህ ፡ እየተባባሉ ።

ወያስተበፅዕዎ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ።

ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ዕፁብ ፡ ዕፁብ ፡ እያሉ ፡ ያደንቁታል ፡ አንድም ፡ ጌታን ፡ ያመ ሰግኑታል ፡ ኤር፱ ፡ ፪ ።

፲፰ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ እስራ ኤል ፡ ዘገብረ ፡ ...

እስራኤልን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔ ር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

ዘገብረ ፡ ንቢሮ ፡ ወመንክረ ፡ ባሕቲቱ ።

ብቻውን ፡ ታላቅ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራ ት ፡ ያደረገ ፡ ማለት ፡ ዓይኔን ፡ ባይኔ ፡ እስከዚህ ፡ በሁለት ፡ ለይኩን ፡ ከፍሎ ፡ ተናግሮታል ።

ያሳየኝ ፡ አንድም ፡ ሥጋን ፡ የባሕር ይ ፡ አምላክ ፡ ያደረገ ፡ ኢሳ ፡ ፶፪ ፡ ፩ ።

፲፱ ፡ ወይትባረክ ፡ ስሙ ፡ ስብሐቲሁ ።

የጌትነቱም ፡ ስም ፡ ይክበር ፡ ይመስ ገን ፡ ቅዱስ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያባ ጊዮርጊስ ፡ ቃል ፡ ነው ።

ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለሙ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡

ወይምላእ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ኵሉ ፡ ምድረ ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን ።

ጌትነቱም ፡ ባሬቱ ፡ መዓዝን ፡ ምሉዕ ፡ ይሁን ፡ ይኸውም ፡ ይደረግ ፡ ይደረግ ፡

መዝሙር ፡ ፸፪ ።

፩ ፡ ጥቀ ፡ ኄር ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ለርቱዓነ ፡ ልብ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታልና ፡ ለ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዘ ረድእን ፡ ለጋይዮስ ፡ ለእጉን ፡ ለብእ ሲት ፡ ለመርዓት ፡ በግዑ ፡ ለካህናት ፡ ለደቂቀ ፡ አሮን ፡ እንዲል ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ላላቸው ፡ ለእ ስራኤል ፡ እጅግ ፡ ቸር ፡ ነው ።

አንድም ፡ (ኄር ፡ እግዚአብሔር) ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ቸር ፡ ነው ፤ (ለርቱዓን ፡ ልብ ፡ ጥቀ) ፡ ይልቁንም ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ትሑት ፡ ሰብእና ፡ ላላ ቸው ፤ አንድም ፡ ለመላው ፡ እስራ ኤል ፡ ቸር ፡ ነው ፤ ይልቁንም ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ትሑት ፡ ሰብእና ፡ ላላቸው ፡ ለነቢያት ፡ ለካህናት ፡ ቸር ፡ ነው ።

፪ ፡ ሊተሰ ፡ ሕቀ ፡ ከመ ፡ ዘእምተንተና ፡ እገርየ ፡

ሊ.ተኒ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እግረ ፡ ልቡናዬ ፡ በአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ እንዲሰነካከል ፡ ያላደረገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኔም ፡ እጅግ ፡ ቸር ፡ ነው ።



ወሕቀ ፡ ከመ ፡ ዘእምድሕፀ ፡ ሰኰናየ ።

ሰኰና ፡ ልቡናዬ ፡ በገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ እንዲሰነካከል ፡ ያላደረገ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ለኔም ፡ እጅግ ፡ ቸር ፡ ነው ፡

፫ ፡ እስመ ፡ ቀናዕኩ ፡ ላዕለ ፡ ኃጥኣን ።

በባቢሎናውያን ፡ ላይ ፡ ቀንቻለሁና ፡

ሰላሞሙ ፡ ርእይየ ፡ ለኃጥዓን ፡ ሚል ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።

የዓማፅያን ፡ ባቢሎናውያንን ፡ ተድላ ፡ ደስታቸውን ፡ ዓይቼ ።

፬ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ግሕት ፡ ለሞቶሙ ።

ለአሙቶቶሙ ፡ ለሞትናሆሙ ፡ ይላ ል ፡ ሞት ፡ ለመሆናቸው ፤ አንድም ፡ (ለቀቲሎቶሙ) ፡ ሰውን ፡ ለመግደላ ቸው ፡ ዕረፍት ፡ የለውምና ።

ወኢኃይል ፡ ለመቅሠፍቶሙ ።

በእስራኤል ፡ ለሚያመጡትም ፡ መከ ራ ፡ ኃይል ፡ የለውምና ፤ መላእክት ፡ ብር ፡ ከፍተው ፡ ቲሃቲሃቸውን ፡ አብ ርተው ፡ ነጋሪት ፡ መትተው ፡ አስማ ርከዋቸዋል ፡ እንጂ ፡ በነሱ ፡ ኃይል ፡ አይደለምና ፤ ዘኍ ፡ ፲፯ ፡ ፳፪ ፡ ፳፯ ።

፭ ፡ ወበፃማሂ ፡ ኢኮኑ ፡ ዕድወ ።

እስራኤል ፡ ጽረው ፡ ግረው ፡ ባላጋ ራን ፡ አልሆኗቸውምና ።

ወኢተቀሥፉ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ።

ከሰው ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ አልጠፉ ምና ፡ ማለት ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጅተ ው ፡ እነሱ ፡ በኋላ ፡ ቀርተዋልና ።

፮ ፡ ወበእንተዝ ፡ አኃዞሙ ፡ ትዕቢት ።

ይህ ፡ ስለተደረገባቸው ፡ ትዕቢት ፡ ያዛ ቸው ፤ (ትች) ፡ እኔ ፡ በአምልኮተ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ በገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ እየና ርጉ ፡ በመከራ ፡ መኖሬን ፡ እነሱ ፡ በእ ምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ በገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ እየኖሩ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ መኖራ ቸውን ፡ ዓይቼ ፡ እንዲህ ፡ መሆኑ ፡ እንዳች ፡ የኔን ፡ ጠልቶ ፡ የነሱን ፡ ወድዶት ፡ ነውን ፡ ብዬ ፡ እግረ ፡ ሕሊ ናዬ ፡ ሰኰና ፡ ልቡናዬ ፡ በአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ በገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ሊሰነካ ከል ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ቀርቶት ፡ (ትች) ፡ ነበር ፤ እግረ ፡ ሕሊናዬ ፡ ሰኰና ፡ ልቡ ናዬ ፡ በአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ በገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ እንዲሰነካከል ፡ ያላደረገ ፡ እግዚአዚአብሔር ፡ ለኔም ፡ እጅግ ፡ ቸር ፡ ነው ።

፬ ፤ አንድም ፡ (እስመ ፡ አልቦ) ፡ ለሞ ተ ፡ ሥጋቸው ፡ ዕረፍት ፡ የለውምና ፤ ማለት ፡ ግብር ፡ ገብተን ፡ ቀኖና ፡ ይዘ ን ፡ እናርቀው ፡ አይሉምና ፡ (ወኢኃ ይል) ፡ ለመቅሠፍተ ፡ ሥጋቸውም ፡ ኃይል ፡ የለውምና ፤ ማለት ፡ መላእ ክት ፡ ባእ ፡ ከላዳውያን ፡ ወጊዉው ዎሙ ፡ ለኃብራውያን ፡ ብለው ፡ አስ ማርከዋቸዋል ፡ እንጂ ፡ በነሱ ፡ ኃይል ፡ አልማረኳቸውምና ፡ (ወበፃማሂ) ፡ እስ ራኤልን ፡ ጽረው ፡ ግረው ፡ ባላጋራን ፡ አልኾኗቸውምና ፡ (ወኢተቀሥፉ) ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ አልጠፉ

ምና ፣ ማለት ፣ ሌላው ፣ የሆነ ፣ እንደ ሙቶ ፣ አባት ፣ ሙቶ ፣ ልጅ ፣ ልጅ ፣ ሙቶ ፣ አባት ፣ ይቀራል ፣ እነሱ ፣ ግን ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ጠፍተዋልና ፣ (ወበእ ተገዝ) ፣ ይህ ፣ ሊደረግባቸው ፣ ትዕቢ ት ፣ ያዛቸው ፣ (ትች) ፣ እንዲህ ፣ ዛሬ ፣ በኔ ፣ መከራ ፣ ቢያፀኑብኝ ፣ እሳቸውስ ፣ ኋላ ፣ ፈንታቸውን ፣ መከራ ፣ ይቀበሉ ፣ የለምን ፣ ብዬ ፣ ልቡናዬን ፣ በትዕግ ሥት ፣ ፀፀናሁት ፣ እንጂ ፣ እንዲህስ ፣ በላፀናው ፣ እኔ ፣ በአምልኮተ ፣ እግዚ አብሔር ፣ በገቢረ ፣ ጽድቅ ፣ እየኖ ርኩ ፣ በመከራ ፣ መኖሬን ፣ እነሱ ፣ በአ ምልኮተ ፣ ጣዖት ፣ በገቢረ ፣ ኃጢአት ፣ የኖሩ ፣ በተድላ ፣ በደስታ ፣ መኖራቸ ውን ፣ ዓይቼ ፣ መሆኑን ፣ የኔን ፣ ጠል ቶት ፣ የሳቸውን ፣ ወድዶት ፣ ነውን ፣ ብዬ ፣ እግረ ፣ ሕሊናዬ ፣ ሰኰና ፣ ልቡ ናዬ ፣ በአምልኮተ ፣ ጣዖት ፣ በገቢረ ፣ ኃጢአት ፣ ሊሰነካከል ፣ ጥቂት ፣ ብቻ ፣ ቀርቶት ፣ (ትች) ፣ ነበር ፣ እግረ ፣ ሕሊ ናዬ ፣ ሰኰና ፣ ልቡናዬ ፣ በአምልኮተ ፣ ጣዖት ፣ በገቢረ ፣ ኃጢአት ፣ እንዲሰ ነካከል ፣ ያላደረገ ፣ እግዚአብሔር ፣ ለኔም ፣ እጅግ ፣ ቸር ፣ ነው ።

እንድም ፣ (እስመ ፣ አልበ) ፣ ለሞት ፣ ነፍሳቸው ፣ ዕረፍት ፣ የለውምና ፣ ዕፄ ሁ ፣ ዘኢይነውም ፣ ወእሳቱ ፣ ዘኢይ ጠፍእ ፣ እንዲል ።

(ወኢኃይል) ፣ ለመቅሠፍተ ፣ ነፍሳቸ ውም ፣ ኃይል ፣ የለውምና ፣ (ወበፃ ማሂ) ፣ ለመቅሠፍተ ፣ ነፍሳቸውም ፣ ዕረው ፣ ግረው ፣ ባላጋራን ፣ አልሆኑ ትምና ፣ ማለት ፣ ገሃነም ፣ ከወረዱ ፣ በኋ ላ ፣ ሃይማኖት ፣ ይዞ ፣ ምግባር ፣ ሠርቶ ፣ ንስሐ ፣ ገብቶ ፣ መዳን ፣ አይቻልምና ፣ አልበቱ ፣ ለሰብእ ፣ ንስሓ ፣ እምድኅረ ፣ ሞት ፣ እንዲል ።

(ወኢተቀሥፉ) ፣ ከሰው ፣ ጋራ ፣ እንደ ሰው ፣ አልጠፉምና ፣ ሰው ፣ በሥጋ ፣ ቢጎዳ ፣ በነፍስ ፣ ይጠቀማል ፣ እሳቸው ፣ ግን ፣ በሥጋ ፣ በነፍስ ፣ ጠፍተዋልና ፣ (ወበእንተዝ) ፣ ይህ ፣ ሊደረግባቸው ፣ ትዕቢት ፣ ያዛቸው ፣ (ትች) ፣ እንዲ ህ ፣ ዛሬ ፣ በኔ ፣ መከራ ፣ ሥጋ ፣ ቢያ ፀኑብኝ ፣ እሳቸውስ ፣ በነፍስ ፣ ፍዳቸ ውን ፣ ይቀበሉ ፣ የለምን ፣ ብዬ ፣ ልቡ ናዬን ፣ በትዕግሥት ፣ አፀናሁት ፣ እን ጂ ፣ እንዲህስ ፣ ባላፀናው ፣ እኔ ፣ በአ ምልኮተ ፣ እግዚአብሔር ፣ በገቢረ ፣ ጽድቅ ፣ እየኖርሁ ፣ በመከራ ፣ መኖ ሬን ፣ እሳቸው ፣ በአምልኮተ ፣ ጣዖት ፣ በገቢረ ፣ ኃጢአት ፣ እየኖሩ ፣ በተድላ ፣ በደስታ ፣ መኖራቸውን ፣ ዓይቼ ፣ መሆ ኑን ፣ እንዳች ፣ የኔን ፣ ጠልቶት ፣ የሳ ቸውን ፣ ወድዶት ፣ ይሆንን ፣ ብዬ ፣ እግረ ፣ ሕሊናዬ ፣ ሰኰና ፣ ልቡናዬ ፣ በአምልኮተ ፣ ጣዖት ፣ በገቢረ ፣ ኃጢ አት ፣ ሊሰነካከል ፣ ጥቂት ፣ ብቻ ፣ ቀር ቶት ፣ (ትች) ፣ ነበር ፣ እግረ ፣ ሕሊናዬ ፣ ሰኰና ፣ ልቡናዬ ፣ በአምልኮተ ፣ ጣ ዖት ፣ በገቢረ ፣ ኃጢአት ፣ እንዲሰነካ



ከል ፣ ያላደረገ ፣ እግዚአብሔር ፣ ለኔ ም ፣ እጅግ ፣ ቸር ፣ ነው ።

ወተፀፅፍዋ ፣ ለኃጢአቶሙ ፣ ወለኀመፃሆሙ ።

ዓመፃቸውን ፣ ኃጢአታቸውን ፣ አብ ዝተው ፣ ሠሯት ፣ አንድም ፣ በሕይ ወት ፣ ሥጋ ፣ ሳሉ ፣ የሠሯት ፣ ዓመፃ ቸው ፣ ኃጢአታቸው ፣ በፍዳ ፣ ተገና ኘቻቸው ።

፯፣ ወይወፅእ ፣ ከመ ፣ ዘእምአንጉዕ ፣ ኃጢአ ቶሙ ።

ቅልጥም ፣ ከጉልበት ፣ እንዲነቃ ፣ ኃ ጢአታቸውም ፣ ከባሕርያቸው ፣ ይነ ቃል ።

ወኀለፈ ፣ እምትዕቢት ፣ ልበሙ ።

ልቡናቸው ፣ ከትዕቢት ፣ ወደ ፣ ትዕ ቢት ፣ ይሔዳል ፣ ናቡከደነፆር ፣ የሠ ራዊቱን ፣ ብዛት ፣ ዓይቶ ፣ እነ ፣ እሠ ርቅ ፣ ፀሐየ ፣ ብሏልና ።

፰፣ ሐለዩ ፣ ወነበቡ ፣ ከንቶ ።

በልቡናቸው ፣ አሰበው ፣ በቃላቸው ፣ ከንቱ ፣ ነገርን ፣ ተናገሩ ።

ወነበቡ ፣ ዓመፃ ፣ ውስተ ፣ አርያም ።

በአርያም ፣ ዓመፅን ፣ ተናገሩ ፣ ማለት ፣ በአርያም ፣ አምላክ ፣ የለም ፣ አሉ ።

ዘፍ ፣ ፲፩ ፣ ፬-፱ ።

፱፣ ወአንበሩ ፣ ውስተ ፣ ሰማይ ፣ አፉሆሙ ።

እንደበታቸውን ፣ በሰማይ ፣ አኖሩ ፣ ማለት ፣ በሰማይ ፣ አምላክ ፣ የለም ፣ አሉ ፤ ኢሳ ፣ ፫ ፣ ፰ ።

ወአንሶሰወ ፣ ውስተ ፣ ምድር ፣ ልሳኖሙ ።

እንደበታቸው ፣ በምድር ፣ ተመላለሰ ፣ ማለት ፣ በምድርም ፣ አምላክ ፣ የለም ፣ አሉ ፣ ፲፫፣፪።

፲፣ በእንተዝ ፣ ይትመየጡ ፣ሕዝብየ ፣ እምዝየ ።

ስለዚህ ፣ ወገኖቼ ፣ እስራኤል ፣ ከባቢ ሎን ፣ ወደ ፣ ኢየሩሳሌም ፣ ይመለሳሉ ፣ ኤር ፣ ፳፱ ፣ ፲-፲፭ ።

ወይትረከብ ፣ ፍጹም ፣ መዋዕል ፣ በላዕሌሆሙ ።

እሳቸው ፣ ፍጹም ፣ ተድላ ፣ ደስታ ፣ ይደረግላቸዋል ።

እንድም ፣ (ወአንበሩ) ፣ በሰማይ ፣ ፀሐይ ፣ ጨረቃ ፣ ከዋክብትን ፣ አመለኩ ፣ (ወ አንሶሰወ) ፣ በምድርም ፣ ዕፀው ፣ አዕ ባን ፣ እንስሳት ፣ አራዊትን ፣ አመለኩ ፣ (ወይትረከብ) ፣ በዘመናቸው ፣ ፍጹም ፣ ተድላ ፣ ደስታ ፣ ይደረግላቸዋል ።

አንድም ፣ (ወአንበሩ) ፣ ቃልን ፣ ከ ሥጋ ፣ ለይተው ፣ አምላክ ፣ አሉ ፣ (ወአንሶሰወ) ፣ በምድርም ፣ ዘርዐ ፣ ዳዊት ፣ ሥጋን ፣ ከቃል ፣ ለይተው ፣ ሰው ፣ አሉ ፣ አሕዛብም ፣ ከጣዖት ፣ ወደ ፣ ጣዖት ፣ ይሔዳሉ ፣ (ወይትረ ከብ ፣ ለጊዜው ፣ ተድላ ፣ ደስታ ፣ ይደ ረግላቸዋል ።

እንድም ፣ (ወአንበሩ) ፣ ሥግው ፣ ቃልን ፣ በኅድረት ፣ አምላክ ፣ አሉ ፣ (ወአንሶ ሰወ) ፣ ይህን ፣ የተናገሩበት ፣ እንደበ ታቸው ፣ በፍዳ ፣ ተመላለሰባቸው ፤ መምሩ ፣ ቅዱስ ፣ ቄርሎስ ፣ ነው ፣ ንስ

2014 04 17

ጥርስ፡ተሰድዶ፡ላዕላ፡ግብዕ፡ሐዶ፡
ተከትሎ፡ሒዶ፡ልጁ፡እኔ፡የጎዳ
ሁህ፡ልሁን፡እሷንም፡ወላዲተ፡
አምላክ፡በላት፡እሱንም፡የባሕርይ፡
አምላክ፡በለው፡አለው፡አይሆንም፡
ለኔስ፡ባህሌ፡ተስማምቶኛል፡አለው፡
ለኔ፡እንዳልታዘዝህልኝ፡ምላስህ፡
አይታዘዝልህ፡አለው፡ምላሱ፡ተ
ጎልጕሎ፡እንደ፡ሴት፡ጡት፡ከደ
ረቱ፡ወድቆ፡ወሞተ፡እንዘ፡ይነብህ፡
ከመ፡ከልብ፡ይላል፡እንደ፡ውሻ፡
ሐገ፡ሐገ፡እያለ፡ሙቷልና፡(ወበ
አንተገ፡ወይትረከብ)፡ለአሕዛብ፡
ተድላ፡ደስታ፡ሲደረግላቸው፡አይ
ተው፡ወገኖቼ፡እስራኤል፡ከሃይማ
ኖት፡ወደ፡ጣዖት፡ይሔዳሉ፡ለአ
ሕዛብ፡እንደተደረገላቸው፡ለኛም፡
ይደረግልናል፡መስሏቸው።

፲፩ ወይቤሉ፡እፎ፡የአምር፡እግዚአብሔር።

እግዚአብሔር፡ያውቃል፡አያው
ቅም፡አሉ።

ወቦኑ፡ዘየአምር፡በአርያም።

አረ፡ተጠ፡እግዚአብሔር፡ያውቅ
ባችኋል፡ቢሏቸው፡በአርያም፡ያለ፡
እግዚአብሔር፡ያውቃልን፡አያው
ቅም፡አሉ።

፲፪ ናሁ፡እሉ፡ኃጥአን፡ይትረገዑ።

እንሆ፡እሊህ፡ባቢሎናውያን፡እን
ዲህ፡እያሉ፡በተድላ፡በደስታ፡ይ
ኖራሉ፡ተዘከር፡ወልድየ፡ዘከመ፡
ፈጋዕከ፡በሕይወትከ፡እንዲል።

ወለዓለም፡ያፀንዕዎ፡ለብዕሎሙ።

ኀላፊ፡ብላቸውን፡ለዘለዓለም፡የማ
ታልፍ፡አስመሰለው፡ይይዟታል።

፲፫ ወእቤ፡ከንቶ፡እንጋ፡አጽደቅዋ፡ለል
ብየ።

እንዳች፡በሐሰት፡እንግዲህ፡ወዲህ፡
ጻድቅ፡ነኝ፡አልሁን።

ወሐፀብኩ፡በንጹሕ፡እደውየ።

እጄን፡በንጽሕና፡ወህ፡አፀብኍ፡
ማለት፡ንጹሕ፡ነኝ፡አልኍ፡ኢሳ፡
፵፱፡፱።

፲፬ ወኮንኩ፡ቅሡፈ፡ኵሎ፡አሚረ።

እንዲህ፡እያልኍ፡ሰባ፡ዘመን፡ዕ
ለት፡ዕለት፡በሠውጠ፡መከራ፡የተ
ገረፍኍ፡ሆንኍ።

ወዘለፋየኒ፡በጽባሕ።

ራሴን፡የምዘልፍም፡ዕለት፡ዕለት፡
ነው።

፲፭ ሶበ፡እቤሁ፡ነበብኩ፡ከመዝ።

ሶበና፡ከመገ፡አንድ፡ወገን፡እን
ዲህ፡ብዬ፡ነገር፡በጀመርኍ፡ጊዜ።

ናሁ፡ሠራዕኩ፡ለትውልደ፡ደቂቅከ።

እነሆ፡ሚጠትን፡ለልጅ፡ልጅ፡ሠራ
ሁልህ፡አልከኝ፡ዕብ፡፲፱፡፰።

፲፮ ወተወከፍኩ፡ከመ፡አእምር።

ከመ፡አእምርን፡አቂየው፡(አስጠ
ብቅ)፡እስከዚያም፡ድረስ፡በረድ
ኤት፡ተቀበልከኝ።

ዝንቱሰ፡ፃማ፡ውእቱ፡በቅድሜየ።

ናሁ፡ሠራዕኩ፡ለትውልደ፡ደቂቅከ፡
ብሎ፡ነበርና፡በባቢሎን፡የምኖረው፡
ዘመን፡ምን፡ያህል፡ነው፡ብሎ
ታል፡ሰባ፡ዘመን፡ብዬህ፡የለምን፡
ቢለው፡ይህ፡ሰባ፡ዘመን፡በኔ፡ዘ
ንድ፡ፃር፡ጋር፡ነው፡ይላል።

፲፯ እስከ፡እበውእ፡ውስተ፡መቅደሱ፡ለእ
ግዚአብሔር።

የእግዚአብሔር፡ማደሪያ፡ወደምት
ሆን፡ወደኢየሩሳሌም፡እስከገባ፡
ድረስ።

ከመ፡አእምር፡ደኀሪቶሙ።

ፍጻሜ፡ጥፋታቸውን፡እስካውቅ፡
ድረስ።

፲፰ ወባሕቱ፡በእንተ፡ጽልሑቶሙ፡አቅናሕ
ኮሙ።

ነገር፡ግን፡አሕዛብን፡ኃጢአት፡
ስለ፡ሠሩ፡ሰባ፡ዘበን፡እስኪፈጸም፡
አቆየሃቸው፡እፀንሐ፡ለአሞሬዎን፡
እስከ፡ይትፌጸም፡ኃጢአቱ፡እን
ዲል።

ወነፃሕኮሙ፡በተንሥኦቶሙ።

በፍላ፡መንግሥታቸው፡አንድም፡
በእሥራኤል፡በጠላትነት፡በተነሡ
በቸው፡ጊዜ፡ጣልሃቸው፡አንድም፡
(ወባሕቱ)፡እስራኤል፡ኃጢአት፡ስ
ለሠሩ፡ሰባ፡ዘበን፡በባቢሎን፡አቆ
የኃቸው፡(ወነፃሕኮሙ)፡እንሥተህ፡
ጣልካቸው፡እንሥተው፡የጣሉት፡
እንዲጎዳ፡አከብረህ፡አዋረድኃቸው፡
ንጉሥ፡ነገሥት፡አድርገህ፡ቋሚ፡
ለጓሚ፡አደረግኻቸው።

፲፱ እፎ፡ኮኑ፡ለሙስና።

እንዴት፡ለጥፋት፡ኾኑ፡እንዴት፡
ለጥፋት፡ኾኑ።

ግብተ፡ኀልቁ፡ወተኀጕሉ፡በእንተ፡ኀጢአቶሙ።

ኃጢአት፡ስለሠሩ፡ድንገት፡በመ
ከራው፡ተፈጸሙ፡አለቁ፡ግብት፡
በሳቸው፡ነው፡እንጂ፡ሥላሴስ፡አው
ቀው፡ነው፡የምያጠፋቸው።

፳ ከመ፡ዘንቃሕ፡እምንዋም።

የተኛ፡ሰው፡ፈጥኖ፡እንዲነሣ፡ፈ
ጥነው፡ጠፉ።

እግዚኦ፡በሀገርከ፡አኅሥሮሙ፡ወረኀዮሙ።

አቤቱ፡በሀገርህ፡በኢየሩሳሌም፡
ከእስራኤል፡ከፎችን፡አጥፋቸው፡
በጎችን፡ግን፡ጠብቃቸው፡አንድም፡
ከአሕዛብ፡ከፎችን፡በሀገርህ፡በባ
ቢሎን፡አጥፋቸው፡በተፈጥሮ፡እ
ገሩ፡ናትና፡በጎችን፡ግን፡ጠብቃ
ቸው፡አንድም፡አሕዛብን፡አጥፋ
ቸው፡እስራኤልን፡ግን፡ጠብቃቸው።

፳፩ እስመ፡ውዕየ፡ልብየ፡ወተመሰወ፡ኵል
ያትየ።

ልቡናዬ፡በመከራው፡እንደ፡እሳት፡

ተቃጥኋል ፣ ሰውነቴም ፣ እንደ ፣ ሰም ፣ ቀልጧልና ፣ ኢሳ ፣ ፲፯ ፣ ፲፭ ።

፳፪ ፣ ወእንስ ፣ ምንትን ፣ ኢያእመርኩ ፣ ኤር ፣ ፬ ፣ ፲፱ ።

ትሩፍ ፣ ጉል ፣ ጊዜ ፣ ማርዳት ፣ ተቀጣ ተህ ፣ አትወጣምን ፣ ትለኝ ፣ እንደሆነ ፣ እኔስ ፣ ተቀጣቼ ፣ የምወጣበት ፣ ኀይል ፣ የለኝም ፣ ተራ ፣ ነኝ ፣ መዋጋትም ፣ አላውቅ ።

ወኮንኩ ፣ ከመ ፣ እንስሳ ፣ በኀቤከ ።

ባንተ ፣ ዘንድ ፣ እንደ ፣ እንስሳ ፣ ነኝ ፣ ማለት ፣ ደካማ ፣ ነኝ ፣ እንድም ፣ ትሩፍ ፣ ይህ ፣ ኹሉ ፣ መከራ ፣ የመጣብህ ፣ ጣዖት ፣ ብታመልክ ፣ አይደለምን ፣ ትለኛ ፣ እንደሆነ ፣ (ምኑን) ፣ እኔስ ፣ ሰው ፣ ሠራሽ ፣ ጣዖትን ፣ አላመለክሁም ፣ (ወከንኩ) ፣ እንስሳ ፣ ለጌታው ፣ እንዲገዛ ፣ ያንተ ፣ ተገዥ ፣ ነኝ ፣ እንጂ ።

፳፫ ፣ ወእንስ ፣ ዘልፈ ፣ ምስሌከ ።

እኔስ ፣ ዘወትር ፣ በባቢሎን ፣ በተስፋው ፣ በኢየሩሳሌም ፣ በረድኤት ፣ ካንተ ፣ ጋራ ፣ እኖራለሁ ።

አንገዝከኒ ፣ እዴየ ፣ ዘየማን ።

ቀኝ ፣ እጄን ፣ ይዘህ ፣ ከባቢሎን ፣ ወደ ፣ ኢየሩሳሌም ፣ አወጣኸኝ ።

፳፬ ፣ በምክረ ፣ ዚአከ ፣ መራህከኒ ።

ወሰብዓ ፣ ዓም ፣ ብለህ ፣ በተናገርከው ፣ ቃል ፣ የኢየሩሳሌምን ፣ መንገድ ፣ መርተህ ፣ አወጣኸኝ ።

ወምስለ ፣ ስብሐት ፣ ተወከፍከኒ ፣ ኢሳ ፣ ፵፩ ፣ ፩ ።

ከአሕዛብ ፣ ገንዘብ ፣ ጋራ ፣ በረድኤት ፣ ተቀበልከኝ ።

፳፭ ፣ ምንት ፣ ብከ ፣ ቦሀሉ ፣ ውስተ ፣ ሰማይ ፣ ሮሐ ፣ ፲፱ ፣ ፫ ።

ትሩፍ ፣ ጌታን ፣ ይወቅሣል ፣ በሰማይ ፣ ትኖር ፣ ዘንድ ፣ ምን ፣ አለህ ፣ በመላእክት ፣ የቀን ፣ ወራሪ ፣ የሌሊት ፣ ሠባሪ ፣ አለባቸውና ፣ መላእክትን ፣ ትጠብቃለህን ።

ወምንተ ፣ እፈቅድ ፣ ኀቤከ ፣ ውስተ ፣ ምድር ።

እንበሌየ ፣ ሲል ፣ ነው ፣ በምድርስ ፣ ያለኔ ፣ ምን ፣ አለህ ፣ አሕዛብ ፣ ያመልኩሃልና ፣ እነዚያን ፣ ትጠብቃለህን ፣ እንድም ፣ (ምንት) ፣ ጌታ ፣ ትሩፍን ፣ ይወቅሳል ፣ በሰማይ ፣ እኖር ፣ ዘንድ ፣ ምን ፣ አለኝ ፣ በመላእክት ፣ የቀን ፣ ወራሪ ፣ የሌሊት ፣ ሠባሪ ፣ አለባቸውና ፣ መላእክትን ፣ እጠብቃለሁን ፣ የምጠብቀው ፣ አንተን ፣ አይደለምን ፣ (ወምንተ) ፣ በምድርስ ፣ ያላንተ ፣ ማን ፣ አሻለሁ ፣ አሕዛብ ፣ ያመልኩኛልና ፣ እነዚያን ፣ እሻለሁን ፣ የምሻ ፣ አንተን ፣ አይደለምን ፣ እንድም ፣ (ምንት) ፣ ጌታ ፣ ትሩፍን ፣ ይወቅሣል ፣ በሰማይ ፣ ትኖር ፣ ዘንድ ፣ ምን ፣ አለህ ፣ ፀሐይ ፣ ጨረቃ ፣ ከዋክብት ፣ ፈጥረውኻልና ፣ እነዚያን ፣ ታመልካለህን ፣ እኔን ፣ አታመልከኝምን ፣ (ወምንተ) ፣ በምድርስ ፣ ማንን ፣ ትሻለህ ፣ ዕፀው ፣ አዕ



ባን ፣ እንስሳት ፣ አራዊት ፣ ፈጥረውኻልና ፣ እነዚያን ፣ ታመልካለህን ፣ እኔን ፣ አታመልከኝምን ፣ እንድም ፣ (ምንት) ፣ ትሩፍ ፣ ለጌታ ፣ ይመልሳል ፣ እውነትህ ፣ እንጂ ፣ ነው ፣ በሰማይ ፣ እኖር ፣ ዘንድ ፣ ምን ፣ አለኝ ፣ ፀሐይ ፣ ጨረቃ ፣ ከዋክብት ፣ ፈጥረውኛልና ፣ እነዚያን ፣ አመልካለሁን ፣ የማመልከው ፣ አንተን ፣ አይደለምን ፣ (ወምንተ) ፣ ጌታ ፣ ለትሩፍ ፣ ይመልሳል ፣ እኔስ ፣ እምኀቤከ ፣ ካንተ ፣ ዘንድ ፣ ምን ፣ እሻለሁ ፣ አምልከኝ ፣ እልኻለሁ ፣ እንጂ ፣ አብላኝ ፣ አጠጣኝ ፣ አልኻለሁን ፣ ሮሐ ፣ ፲፱ ፣ ፳፮ ።

፳፮ ፣ ኀልቀ ፣ ልብየ ፣ ወሥጋየ ፣ በአምላኩ ፣ መድኀኒትየ ።

ድኅነቴን ፣ በምያደርግልኝ ፣ ፈጣሪዬ ፣ አምኜ ፣ ነፍሴም ፣ ሥጋዬም ፣ ተፈጸመ ፣ እንድም ፣ በክብር ፣ ተፈጸመ ፣ ማለት ፣ በዛለት ፣ ወኀልቀ ፣ ክብሩ ፣ ለያዕቆብ ፣ እንዲል ።

እግዚአብሔር ፣ መክፈልትየ ፣ ለዓለም ።

ለዘላለሙ ፣ ዕድል ፣ ፈንታዬ ፣ ጽዋ ፣ ተርታዬ ፣ እግዚአብሔር ፣ ነው ።

፳፯ ፣ እስመ ፣ ናሁ ፣ እለ ፣ ይርኅቁ ፣ እምኔከ ፣ ይትኀጐሉ ።

ብአምልኮ ፣ ካንተ ፣ የሚርቁ ፣ እነሆ ፣ ይጠፋሉና ፣ እግዚአብሔር ፣ መክፈልትየ ፣ ላለው ፣ እንድም ፣ እንዲህ ፣ ነውና ።

ወሠረውኮሙ ፣ ለዘሖሩ ፣ እለ ፣ ይዜምዉ ፣ እምኔከ ።

አንተን ፣ ከማምለክ ፣ ወጥተው ፣ በአምልኮ ፣ ጣዖት ፣ የፀኑትን ፣ ኹሉ ፣ አጠፋኻቸው ፣ ሴሰኝነት ፣ የሴትና ፣ የወንድ ፣ ብቻ ፣ አይደለም ፣ ጣዖት ፣ ማምለክ ፣ ሴሰኝነት ፣ ነውና ፣ ኤር ፣ ፲፯ ፣ ፲፫ ።

፳፰ ፣ ሊተሰ ፣ ተሊወ ፣ እግዚአብሔር ፣ ይኄይሰኒ ።

ለኔ ፣ ግን ፣ ይህ ፣ ሁሉ ፣ መከራ ፣ እንዳያገኘኝ ፣ በእግዚአብሔር ፣ ማመን ፣ ይሻለኛል ፣ ይበልጠኛል ።

ወትውክልትየ ፣ ላዕለ ፣ እግዚአብሔር ።

እምነቴንም ፣ በእግዚአብሔር ፣ ባደርግ ፣ ይሻለኛል ፣ ማለት ፣ በእግዚአብሔር ፣ አምኜ ፣ እኖራለሁ ።

ከመ ፣ እንግር ፣ ኵሎ ፣ ስብሐቲከ ።

ጌትነቱን ፣ እነግር ፣ አስተምር ፣ ዘንድ ።

በአናቅጺሃ ፣ ለወለተ ፣ ጽዮን ።

በኢየሩሳሌም ፣ አደባባይ ።

## መዝሙር ፣ ፻፷፫ ።

፩ ፣ ለምንት ፣ ገደፍከነ ፣ እግዚኦ ፣ ለዝሉፉ ፣ ኤር ፣ ፲፱ ፣ ፲፱ ።

ስለ ፣ መቃብያን ፣ ተናግሮታል ፣ አ ቤቱ ፣ ፈጽመህ ፣ በመከራው ፣ ስምን ፣ ጣልኸን ፣ አንድ ፣ ጊዜስ ፣ ብትጥለን ፣ ለምን ፣ እንደጣልኸን ፣ ቀረህ ።

ወተዘከረ ፡ መንፈቅ ፡ ዘአልአበ ፡ አብገበ ፡ መርኒትከ ።

መርዒት ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብ ፡ አባግዕ ፡ መቃብያን ፡ ናቸው ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ በሚሆኑ ፡ በመቃብያን ፡ ለምን ፡ ፈረድህባቸው ፡ ሰፋ ፡ ፩ ፡ ፳፪ ።

፪ ፡ ተዘከር ፡ ማኅበረከ ፡ ዘአቅደምከ ፡ ፈጢረ ።

አክቢረ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ስምዕ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘፈጠሮሙ ፡ ለሙሴ ፡ ወለአሮን ፡ እንዲል ፡ አስቀድመህ ፡ ያከበርሃቸው ፡ የሙሴ ፡ የአሮን ፡ ወገኖች ፡ የሚሆኑ ፡ መቃብያንን ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣቸው ።

ወአድኃንከ ፡ በትረ ፡ ርስትከ ።

ርስትህ ፡ ጉልትህ ፡ የሚሆኑ ፡ ትሩፋንን ፡ ያዳንህላቸው ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብን ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ።

ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ዘኀደርከ ፡ ውስቴታ ።

አድረህባት ፡ የምትኖር ፡ ደብረ ፡ ጽዮንንም ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ።

፫ ፡ አንሥእ ፡ እዴከ ፡ ዲበ ፡ ትዕቢቶሙ ፡ ለዝሉፉ ፡ ሚልኽ ፡ ፪ ።

ፈጽመው ፡ መታበያቸውን ፡ ዓይተህ ፡ እደ ፡ መዓትህን ፡ አንሣባቸው ፡ ሲራፀፎ ፡ ፫ ፡ ሕዝጼ ፡ ፲፩ ።

መጠነ ፡ አኅሰመ ፡ ፀራዊ ፡ ዲበ ፡ ቅዱሳኒከ ።

አንጥያኮስ ፡ ስንኳ ፡ በወገኖችህ ፡ በመቃብያን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳመጣባቸው ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ፤

እንድም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መከራ ፡ አመጣባቸው ።

፬ ፡ ወተዘኀሩ ፡ ጸላእትከ ፡ በማዕከለ ፡ በዓልከ ።

በዓልህን ፡ በምያከብሩ ፡ በመቃብያን ፡ ላይ ፡ ጠላቶችህ ፡ ዕርዓውያን ፡ ታበዩ ።

ወረሰዩ ፡ ትእምርቶሙ ፡ ትእምርተ ፡ ዘኢያእመሩ ።

ሦስቱ ፡ ካህናት ፡ ለድኅነት ፡ ነፍስ ፡ ምልክት ፡ የሚሆን ፡ ድኅነት ፡ ሥጋ ፡ የሚገኝበት ፡ ሕግ ፡ አሪትን ፡ ምንም ፡ እግኝተውበት ፡ እንደማያውቁ ፡ አደረጉ ።

፭ ፡ ከመ ፡ ዘውስተ ፡ ላዕላይ ፡ ፍኖት ።

ለድኅነተ ፡ ነፍስ ፡ ምልክት ፡ የሚሆን ፡ ድኅነተ ፡ ሥጋ ፡ ማስጠቷም ፡ ሰማያዊት ፡ ሕግ ፡ እንደመኾኗ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ (ወረሰዩ) ፡ ምንም ፡ አግኝተውበት ፡ የማያውቋ ፡ ጣዖቱን ፡ ትእምርት ፡ በላዖር ፡ እንዲል ፡ (ከመ ፡ ዘውስተ ፡ ላዕላይ) ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ እንደ ፡ ተሠራው ፡ ሕግ ፡ አደረጉ ።

ወከመ ፡ ዕፀወ ፡ ገዳም ፡ በጕድብ ፡ ወበሩ ፡ ኆኅቲሃ ።

እንደ ፡ በረኃም ፡ እንጨት ፡ ደጃፎቿን ፡ በገጀሞ ፡ ሰበሩ ።

፮ ፡ ከማሁ ፡ በማሕጼ ፡ ወበመፍጽሕ ፡ ሰበርዋ ።

ደጃፎቿን ፡ በገጀሞ ፡ እንደሰበሩ ፡ እሷንም ፡ በመጥረቢያ ፡ በድጅኖ ፡ አፈረሷት ።



፯ ፡ ወአውዐዩ ፡ በእሳት ፡ መቅደሰከ ፡ ኢሳ ፷፬ ፡ ፲፩ ።

መመስገኛህ ፡ ማደሪያህ ፡ የምትኾን ፡ መቅደስንም ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ ፡ እነሱስ ፡ አላቃጠሉም ፡ መቃብያን ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ዕርዕ ፡ ኑረው ፡ ቢመለሱ ፡ የምሥራቁን ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ የምዕራቡን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ አዙረውት ፡ አገኙ ፡ ሕልዳና ፡ የምትባል ፡ ደግ ፡ ሴት ፡ ነበረች ፡ ባሏ ፡ ሙቶ ፡ በንጽሕና ፡ የምትኖር ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እናድርግ ፡ አሏት ፡ የምዕራቡን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ የምሥራቁን ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ አዙሩት ፡ ምሥዋዕት ፡ ጣዖት ፡ በተሠዋበት ፡ መሥዋዕት ፡ በግዕ ፡ ሠውበት ፡ አለቻቸው ፡ ሲያዞሩ ፡ የረዘመውን ፡ ቈርጠው ፡ የወፈረውን ፡ ጠርበው ፡ በእሳት ፡ አቃጥለውታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ አንድም ፡ ማደሪያህ ፡ የሚሆን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አልዓዛርን ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ ።

ወአርኰሱ ፡ ማኅደረ ፡ ስምከ ፡ ውስተ ፡ ምድር ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ የስምህ ፡ መጸሪያ ፡ መመስገኛ ፡ የሚሆን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ አሳደፉ ፡ ካህናት ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ያረኵስዋ ፡ ለሰንበት ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ የስምህ ፡ መጸሪያ ፡ የሚሆን ፡ አልዓዛርን ፡ ሠዓሩ ፡ በሞት ፡ ገደሉ ።

፰ ፡ ወይቤሉ ፡ በልቦሙ ፡ ኅቢሮሙ ፡ ለበሐኒሆሙ ።

በልባቸው ፡ አስበው ፡ በቃላቸው ፡ በየወገናቸው ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ባንድነት ፡ እንዲህ ፡ ብለዋልና ።

ንዑ ፡ ንሥዓር ፡ በዓላቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምድር ።

የእግዚአብሔር ፡ በዓሉን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አንድም ፡ በዓሉን ፡ የምያከብሩ ፡ መቃብያንን ፡ ከሰው ፡ ለይተን ፡ እናጥፋ ፡ አሉ ፤ በዓል ፡ የምያከብር ፡ ሰው ፡ ከሌለ ፡ በዓል ፡ የለምና ።

፱ ፡ ወትእምርቶሂ ፡ ኢነአምር ።

ምነው ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ የተደረገባት ፡ ሕግ ፡ አይደለችምን ፡ ቢሏቸው ፡ ብዙ ፡ ተአምራትም ፡ መደረጉን ፡ አናውቅም ፡ አሉ ።

ወአልቦ ፡ እንከ ፡ ነቢይ ።

ያውስ ፡ ተራ ፡ ነቢይ ፡ ነውን ፡ ሙሴ ፡ የሠራት ፡ (የተቀበላት) ፡ ሕግ ፡ አይደለችምን ፡ ቢሏቸው ፡ ሙሴም ፡ የሚሉት ፡ ነቢይ ፡ አናውቅም ፡ አሉ ።

ወንሕነሂ ፡ ኢንአምር ፡ እንከ ።

አንኪያስ ፡ እኛም ፡ ሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ የሚሉ ፡ አምላክ ፡ አሪያ ፡ የሚሉ ፡ መሥዋዕት ፡ አናውቅም ፡ አሉ ፡ ፀብ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የተጀመረ ፡ ይመስላል ።

፲ ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ እንከ ፡ እግዚኦ ፡ ይጼዕል ፡ ፀራዊ ።

አቤቱ ፡ ፀራዊ ፡ አንጥያኮስ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ይሳደባል ።



2014 04 17

መዘልፈ ፣ ያምዕዩ ፣ ለስምከ ፣ ፀላኢ ።

እስከመቼስ ፣ ለስምህ ፣ የማይገባ ፣ ስም ፣ እየሰጠ ፣ ጣዖት ፣ እያለ ፣ ያሳዝ ነቀል ፣ አንድም ፣ ፀላኢ ፣ አንጥያኮስ ፣ ዘወትር ፣ ስምህን ፣ ያሳዝናል ።

፲፩ ፣ ለምንት ፣ እግዚኦ ፣ ትመይጥ ፣ እዴከ ።

አቤቱ ፣ ሥልጣንህን ፣ ለምን ፣ ትመልሰዋለህ ።

ወየማንከ ፣ ማዕከለ ፣ ሕፅንከ ፣ ለግሙራ ።

ሥልጣንህንስ ፣ በባሕርይህ ፣ ለምን ፣ ፈጽመህ ፣ ትሠውረዋለህ ፣ አንድም ፣ የማንክ ፣ ሥልጣንህንስ ፣ በባሕርይህ ፣ ለምን ፣ ይሠወራል ፣ እንጁን ፣ በልብሱ ፣ ውስጥ ፣ ያደረገ ፣ ሰው ፣ ፈጥኖ ፣ እንዳይረዳ ፣ ለምን ፣ ፈጥነህ ፣ አትረዳኝም ፣ ሲል ፣ ነው ።

፲፪ ፣ እግዚአብሔርሰ ፣ ንጉሥ ፣ ውእቱ ፣ እምቅድመ ፣ ዓለም ።

እግዚአብሔርስ ፣ ፈጥኖም ፣ ባይረዳ ፣ ሥራውን ፣ ያለጊዜው ፣ አይሠራውምና ፣ ታግሦ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ከዕለተ ፣ ረቡዕ ፣ ወዲህ ፣ እንደ ፣ ተገኘ ፣ ሥዕለ ፣ ፀሐይ ፣ አይደለም ፣ ዓለም ፣ ሳይፈጠር ፣ የነበረ ፣ የዘላለም ፣ ንጉሥ ፣ ነው ።

ወገብረ ፣ መድኃኒተ ፣ በማዕከለ ፣ ምድር ፣ ኤር ፣ ፲ ፣ ፲ ።

ይኸውም ፣ ሊታወቅ ፣ በማዕከለ ፣ ምድር ፣ በኢየሩሳሌም ፣ አዳምን ፣ ፈጥሮ ፣ ድኅነትን ፣ አደረገ ።

፲፫ ፣ አንተ ፣ አፅናዕከ ፣ ለባሕር ፣ በኃይልከ ።

አንተ ፣ ውቅያኖስን ፣ ኢትትዓደዊ ፣ እምወሰንኪ ፣ ብለህ ፣ በከሃሊነትህ ፣ አፀናሃት ።

ወአንተ ፣ ሰበርከ ፣ ርእሶ ፣ ከይሲ ፣ በውስተ ፣ ማይ ።

ሌዋታንን ፣ በባሕር ፣ ውስጥ ፣ የወሰንከው ፣ አንተ ፣ ነህ ።

፲፬ ፣ ወአንተ ፣ ቀጥቀጥከ ፣ አርእስቲሁ ፣ ለከይሲ ።

ብሔሞትንም ፣ እራሱን ፣ የመታኸው ፣ አንተ ፣ ነህ ፣ እራሱን ፣ የተመታ ፣ ወደያ ፣ ወዲህ ፣ እንዳይል ፣ በየብስ ፣ የወሰንከው ፣ አንተ ፣ ነህ ።

ወወሀብኮሙ ፣ ሲሳዮሙ ፣ ሕዝበ ፣ ኢትዮጵያ ።

ለኢትዮጵያ ፣ ሰዎችም ፣ ምግባቸውን ፣ የሰጠሃቸው ፣ አንተ ፣ ነህ ፣ በኢትዮጵያ ፣ ሁሉን ፣ መናገር ፣ ነው ።

፲፭ ፣ አንተ ፣ ሰጠቀ ፣ አፍላገ ፣ ወአንቅዕተ ።

አፍላግ ፣ እንደ ፣ ዓባይ ፣ እንደ ፣ በሽሎ ፣ (አንቅዕተ) ፣ እንደ ፣ ቀሐ ፣ እንደ ፣ አንገረብ ፣ ያሉትን ፣ በክፍል ፣ በክፍል ፣ እንዲሔዱ ፣ የምታደርግ ፣ አንተ ፣ ነህ ።

፲፮ ፣ ለከ ፣ ውእቱ ፣ መዓልት ፣ ወዚአከ ፣ ይእቲ ፣ ሌሊት ።

ዓሥራ ፣ ሁለቱ ፣ ሰዓተ ፣ ሌሊት ፣ ዓሥራ ፣ ሁለቱ ፣ ሰዓተ ፣ መዓልት ፣ ያንተ ፣ ገንዘብ ፣ ናቸው ፣ ማለት ፣ የፈጠርካቸው ፣ አንተ ፣ ነህ ። ዘፍ ፣ ፩ ፣ ፩ ።



አንተ ፣ ፈጠርከ ፣ ፀሐየ ፣ ወወርኃ ።

ፀሐይ ፣ ጨረቃን ፣ የፈጠርህ ፣ አንተ ፣ ነህ ። ዘፍ ፣ ፩ ፣ ፲፬-፲፯ ።

፲፯ ፣ ወአንተ ፣ ገበርከ ፣ አድባረ ፣ ወምድረ ፣ ኵሎ ።

አድባረ ፣ ተራራውን ፣ ኮረብታውን ፣ (ወምድረ) ፣ ድልድሉን ፣ ሁሉ ፣ የፈጠርህ ፣ አንተ ፣ ነህ ፣ አንድም ፣ አድባረ ፣ ምድር ፣ በዚህ ፣ ዓለም ፣ ያለ ፣ ተራራውን ፣ ኮረብታውን ፣ የፈጠርህ ፣ አንተ ፣ ነህ ።

ክረምተ ፣ ወሐጋየ ፣ ዘአንተ ፣ ፈጠርከ ።

ዘጠኝ ፣ ወር ፣ በጋን ፣ ሦስት ፣ ወር ፣ ክረምትን ፣ የፈጠርህ ፣ አንተ ፣ ነህ ።

፲፰ ፣ ወተዘከር ፣ ዘንተ ፣ ተግባረከ ።

ይህን ፣ ያደረግኸው ፣ ለፍጥረትህ ፣ ብለህ ፣ ነው ፣ ይህን ፣ ያደረግህለት ፣ ፍጥረትህን ፣ አስብ ፣ አስበህ ፣ አውጣን ፣ አንድም ፣ (ወገብረ) ፣ ግብፃውያንን ፣ አጥፍቶ ፣ እስራኤልን ፣ አድኖ ፣ ድኅነትን ፣ አደረገ ፣ (አንተ ፣ አፅናዕከ) ፣ ኤርትራን ፣ ከሁለት ፣ ከሦስት ፣ ከፍለህ ፣ በከሃሊነትህ ፣ ፀጥ ፣ ያደረግሃት ፣ አንተ ፣ ነህ ፣ (ወአንተ ፣ ሰበርከ) ፣ ፈርዖንን ፣ በኤርትራ ፣ ተሰጥሞ ፣ እንዲቀር ፣ ያደረግኸው ፣ አንተ ፣ ነህ ፣ (ወአንተ ፣ ቀጥቀጥከ) ፣ ሠራዊተ ፣ ፈርዖንን ፣ በኤርትራ ፣ ያሠጠምህ ፣ አንተ ፣ ነህ ፣ (ወወሀብኮሙ) ፣ ለምድያም ፣ ሰዎች ፣ ምግባቸውን ፣ የሰጠኻቸው ፣ አንተ ፣ ነህ ፣ ከተሐዋስያኑ ፣ በቀር ፣ ገንዘቡ ፣ ሁሉ ፣ ሰፍሮላቸው ፣ በመርከብ ፣ ገብተው ፣ ወስደውታልና ፣ (አንተ ፣ ሰጠቀ) ፣ ኤርትራን ፣ ከሁለት ፣ ከሦስት ፣ የከፈልህ ፣ አንተ ፣ ነህ ፣ ወደ ፣ ኤርትራ ፣ የሚገቡ ፣ አንቅዕት ፣ ብዙ ፣ ናቸውና ፣ (ለከ ፣ ውእቱ) ፣ በግብፃውያን ፣ ጨለማ ፣ ሆኖባቸዋል ፣ ለእስራኤል ፣ ግን ፣ ዓሥራ ፣ ሁለቱ ፣ ሰዓተ ፣ ሌሊት ፣ ዓሥራ ፣ ሁለቱ ፣ ሰዓተ ፣ መዓልት ፣ ይፈራረቅላቸው ፣ ነበረና ፣ በግብፅ ፣ የተደረገውን ፣ መናገር ፣ ነው ፣ (አንተ ፣ ፈጠርከ) ፣ ፀሐይ ፣ ጨረቃን ፣ ለኢያሱ ፣ ያቆምኸለት ፣ አንተ ፣ ነህ ፣ ወአቀመ ፣ ፀሐየ ፣ በገባዖን ፣ ወወርኃኒ ፣ በቈላተ ፣ ኢሎም ፣ እንዲል ፣

(ወአንተ ፣ ገበርከ) ፣ አድባረ ፣ ሙሴ ፣ አሮንን ፣ ምድረ ፣ ሰብዓ ፣ ሊቃናትን ፣ ያስነሣህ ፣ አንተ ፣ ነህ ፣ ክረምተ ፣ ሐጋየ ፣ ለኤልያስ ፣ ጊዜ ፣ የተደረገውን ፣ መናገር ፣ ነው ፣ ሦስት ፣ ዓመት ፣ ከመንፈቅ ፣ ድርቅ ፣ ጐድሏና ፣ (ክረምተ) ፣ ከዝያ ፣ አስቀድሞ ፣ ከዝያም ፣ ወዲህ ፣ ያለውን ፣ መናገር ፣ ነው ፣ (ወተዘከር) ፣ ይህን ፣ የደረግህለትን ፣ ፍጥረትህን ፣ አስብ ፣ አስበህ ፣ አውጣን ።

አንድም ፣ (ወገብረ ፣ መድኃኒተ) ፣ ትሩፋንን ፣ ከባቢሎን ፣ አውጥቶ ፣ ድኅነትን ፣ አደረገ ፣ (አንተ ፣ አፅናዕከ) ፣ ባቢሎንን ፣ ለጥፋት ፣ ያፀናኻት ፣ አንተ ፣ ነህ ፣ (ወአንተ ፣ ሰበርከ) ፣ ብልጣ

2014 04 17

ሶርን ፡ በከተማው ፡ ቸብቸበው ፡ ተቈርጦ ፡ እንዲቀር ፡ ያደረግህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወአንተ ፡ ቀጥቀጥከ) ፡ ወራዊት ፡ ብልጣሶርን ፡ ያጠፋህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወወሀብከሙ) ፡ ለትሩፋን ፡ ሞግበቸውን ፡ የሰጠካቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ በምድያም ፡ የተወለዱ ፡ የሙሴ ፡ ልጆች ፡ አብረው ፡ ሔደው ፡ ገንዘቡን ፡ ዘርፈ ዋልና ፤ (አንተ ፡ ሰጠቀ) ፡ ሰባት ፡ ወገን ፡ ተከፍሎላቸው ፡ ሰባት ፡ ወጉር ፡ ወግተው ፡ እንዲወጡ ፡ ያደረ ሀግ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ ወይሠጥቁ ፡ ጿተ ፡ አፍላጋተ ፡ ከመ ፡ ይሑርዎን ፡ በእገሪሆሙ ፡ እንዲል ።

(ለከ ፡ ውእቱ) ፡ እንደ ፡ ሌሊት ፡ የሚከብድ ፡ ጌዋዌ ፡ እንደ ፡ መዓልት ፡ ደስ ፡ የምያሰኝ ፡ ሚጠትን ፡ ያደረግህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (አንተ ፡ ፈጠርከ) ፡ ፀሐየ ፡ ሊቀ ፡ ከሀናቱን ፡ ወርኃ ፡ ንጉሡን ፡ ያስነሣህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወአንተ ፡ ገብርከ) ፡ አድባረ ፡ ልዑላንኑ ፡ ምድረ ፡ ትሑታኑን ፡ የፈጠርህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ ክረምት ፡ ሐጋየ ፡ ተማርከው ፡ ሲወርዱ ፡ ወእሣጡ ፡ ቀሳውስቲሆሙ ፡ ዕርቃናቲሆን ፡ ይላል ፡ የሚጠጡት ፡ አጥተው ፡ ማድጎቻቸውን ፡ እያንኳኩ ፡ ወርደዋል ፤ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ዝናም ፡ እየዘነመላቸው ፡ በየወንዙ ፡ ወሀ ፡ ሞልቶላቸው ፡ እየበሉ ፡ እየጠጡ ፡ መጥተዋልና ፤ (ወተዘከር) ፡ ይህን ፡ ያደረግህለት ፡ ፍጥረትህን ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ።

እንድም ፡ (ወገብረ) ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተሰቅሎ ፡ ነፍሳትን ፡ ከሲኦል ፡ አውጥቶ ፡ ድኅነትን ፡ አደረገ ፤ አንተ ፡ አፅናክ) ፡ ልጅነትን ፡ ጥምቀትን ፡ እንድትሰጥ ፡ ያደረግኻት ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ እንድም ፡ ባሕረ ፡ እሳትን ፡ በከሃሊነትህ ፡ ያፀነኻት ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወአንተ ፡ ሰበርከ) ፡ ዲያብሎስን ፡ በጥምቀት ፡ በመስቀል ፡ ድል ፡ የነሣኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወአንተ ፡ ቀጥቀጥከ) ፡ ሠራዊተ ፡ ዲያብሎስ ፡ አጋንንትንም ፡ ድል ፡ የነሣህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወወሀብከሙ) ፡ ለምእመናን ፡ ሥጋህን ፡ ደምህን ፡ የሰጠኻቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (አንተ ፡ ሰጠቀ) ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በከፍል ፡ በክፍል ፡ እንዲሰጥ ፡ የምታደርገው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ ወበከመ ፡ ይደልዎ ፡ ይበቍዖ ፡ እንዲል ።

ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚሰጥ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ዕናት ፡ እንደ ፡ ምግባሩ ፡ ቅናት ፡ ነውና ፡ (ለከ ፡ ውእቱ) ፡ ከነግህ ፡ እስከ ፡ ቀትር ፡ ብርሃን ፡ ሆኗል ፡ ከቀትር ፡ እስከ ፡ ሰዓት ፡ ጨለማ ፡ ሆኗል ፡ ከሰዓት ፡ እስከ ፡ ሠርክ ፡ ብርሃን ፡ ሁኗልና ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ የተደረገውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (አንተ ፡ ፈጠርከ) ፡ ፀሐይ ፡ ጨለማ ፡ ጨረቃ ፡ ደም ፡ እንዲሆን ፡ ያደረግህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወአንተ ፡ ገበርከ) ፡ ሐዋርያትን ፡ ሰብአ ፡ አርድዕትን ፡ ያስነሣህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ (ክረምተ) ፡ አሪትን ፡ ሐጋየ ፡



ወንጌልን ፡ የሠራህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ በክረምት ፡ ቅጠል ፡ እንጂ ፡ ፍሬ ፡ እንዳይገኝ ፡ በኦሪትም ፡ ተስፋ ፡ እንጂ ፡ ሀብት ፡ ሥርየት ፡ አልተሠጠምና ፡ በበጋ ፡ ፍሬ ፡ እንዲገኝ ፡ በወንጌልም ፡ ሀብት ፡ ሥርየት ፡ ተገኝቷልና ፤ (ወተዘከር) ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያደረግህ ፡ ለፍጥረትህ ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያደረግህለት ፡ ፍጥረትህን ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ።

ፀራዊ ፡ ተዓየረ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እንጥያኮስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተገዳደረው ።

ወሕዝብ ፡ ዓብድ ፡ አምዐየ ፡ ለስሙ ።

ሰነፍ ፡ ዕርዓዊም ፡ የማይገባ ፡ ስም ፡ እየሰጠ ፡ ሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ እያለ ፡ ስሙን ፡ አሳዘነው ።

፲፱ ፡ ኢትመጥዎ ፡ ለአራዊት ፡ ለነፍስ ፡ እንተ ፡ ትገኒ ፡ ለከ ።

ላንት ፡ የምትገዛ ፡ መቃቢስን ፡ ለዕርዓውያን ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጣት ፤ እንድም ፡ ለነፍስ ፡ እንተ ፡ ትገኒ ፡ ለከ ፡ ብለህ ፡ አናብበህ ፡ ላንት ፡ የምትገዛ ፡ የመቃቢስን ፡ ሰውነት ፡ ለዕርዓውያን ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጣት ።

ወኢትርሣዕ ፡ ነፍስ ፡ ነዳያኒከ ፡ ለዝሉፉ ።

የመቃብያንን ፡ ሰውነት ፡ ፈጽመህ ፡ አትዘንጋ ፡ ለጊዜውም ፡ ብትዘነጋት ፡ እንደ ፡ ዘነጋሃት ፡ አትቅር ።

፳ ፡ ወነጽር ፡ ውስተ ፡ ሥርዓትከ ።

የኔስ ፡ የኔ ፡ ነውና ፡ አንተ ፡ የሠራኸው ፡ ሥርዓት ፡ እንዳይፈርስ ፡ እይ ፡ ተመልከት ።

፳፩ ፡ እስመ ፡ በዝኁ ፡ ጽሉማነ ፡ ምድር ፡ አብያተ ፡ ኃጥኣን ።

የኃጥአን ፡ ወገኖች ፡ የሚሆኑ ፡ እፍን ፡ ጭፍን ፡ ያሉ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ደናቁርት ፡ ዕርዓውያን ፡ በዝተዋልና ።

፳፪ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ነዳይ ፡ ተኃፊሮ ።

ይሁዳ ፡ መቃቢስ ፡ አፍሮ ፡ እንዳይገባ ፡ ተዘክር ።

ነዳይ ፡ ወምስኪን ፡ ይሴብሑ ፡ ለስምከ ።

እንዲህ ፡ የሆን ፡ እንደሆን ፡ መቃብያን ፡ ለስምህ ፡ ምሥጋና ፡ ያቀርባሉ ፡ ስምህን ፡ ያመሰግናሉ ።

፳፫ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ወተበቀል ፡ በቀልየ ።

አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሥተህ ፡ ፍረድልኝ ።

ወተዘከር ፡ ዘተዓየሩከ ፡ ዓብዳን ፡ ኵሉ ፡ እሚረ ።

ሰነፎች ፡ ዕርዓውያን ፡ ዘወትር ፡ የተገዳደሩህን ፡ ተገዳሮት ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ።

፳፬ ፡ ወኢትርሣዕ ፡ ቃለ ፡ ለአግብርቲከ ።

የመቃብያንን ፡ ልመና ፡ ቸል ፡ አትበል ፤ እንድም ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቸል ፡ አትበል ።

2014 04 17

ትዝኀርቶሙ ፡ ለጻዳንቅከ ፡ ይዕርግ ፡ ኀቤከ ፡ በ
ኵሉ ፡ ጊዜ ።

ትዝኀርቶሙ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ይዕር
ግ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡
ዕለት ፡ ዕለት ፡ ፡ የሚታበዩት ፡ የጠ
ላቶችህ ፡ የዕርዓውያን ፡ ትዕቢት ፡
ዕለት ፡ ዕለት ፡ ከፊትህ ፡ ይድረስ ።

## መዝሙር ፡ ፹፱ ።

፩ ፡ እንዘ ፡ ለከ ፡ እግዚእ ፡ እንዘ ፡ ለከ ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ ለዕብ
ራውያን ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ ልማድ ፡
ነው ፡ አብርሃም ፡ አብርሃም ፡ አልዓ
ዛር ፡ አልዓዛር ፡ ማርታ ፡ ማርታ ፡ እን
ዲል ። አቤቱ ፡ የምሥጋና ፡ የሃይማ
ኖት ፡ አገዛዝ ፡ እገዛልኻለኊ ፡ እገዛ
ልኻለኊ ።

እንዘ ፡ ለከ ፡ ወእጼውዕ ፡ ስመከ ።

ስገዛልህም ፡ ስምህን ፡ እየጸራኊ ፡
እገዛልሃለኊ ።

ወእነግር ፡ ኵሎ ፡ ስብሐቲከ ።

ጌትነትህን ፡ ተአምራትህንም ፡ ሁሉ ፡
እነግራለኊ ፡ አስተምራለኊ ።

፪ ፡ ሶበ ፡ ረከብኩ ፡ ጊዜሁ ።

ምንጊዜ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ ጊዜ
ውን ፡ ባገኘሁት ፡ ጊዜ ፡ አንድም ፡
ተአምራቱ ፡ በተደረገልኝ ፡ ጊዜ ፡
ነው ።

ወአንሰ ፡ ድጽቀ ፡ እኴንን ፡ ጽሐቀ ፡ ፲፮ ።

ሕዝቅያስ ፡ ሶበ ፡ ረከብኩ ፡ ጊዜሁ ፡
ትላለህ ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ መፍረዱ
ን ፡ አለ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ የሌላ
ውን ፡ አላውቅም ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡
እውነት ፡ የምፈርድ ፡ ይመስለኛል ።

፫ ፡ ተመስወት ፡ ምድር ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡
ይነብሩ ፡ ውስቴታ ።

ኢየሩሳሌም ፡ እንደሰም ፡ ቀለጠች ፡
በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡
ጠፉ ፡ አንድም ፡ ለኪሶን ፡ እንደሰም ፡
ቀለጠች ፡ በለኪሶንም ፡ የሚኖሩ ፡
ሁሉ ፡ ጠፉ ።

ወአነ ፡ አፅናዕኩ ፡ አእማዲሃ ።

ኀያላኒሃ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ኀያላኑን ፡ እየ
ጸለይኊ ፡ በረድኤት ፡ አፀናኋቸው ፡
አንድም ፡ የሰናክሬምን ፡ አርበኞች ፡
በሞት ፡ አፀናኋቸው ።

፬ ፡ ወእቤሎሙ ፡ ለኃጥኣን ፡ ኢየአብሱ ።

እለ ፡ ሰናክሬምን ፡ አይበድሉም ፡
ብዬ ፡ አንድም ፡ ምንም ፡ ባይሰሙት ፡
ነቢይ ፡ ነውና ፡ ይመክራቸዋል ፡ ኢተ
አብሱ ፡ ይላል ፡ እነሰናክሬምን ፡ አት
በድሉ ፡ አልኋቸው ።

ወእለሂ ፡ ይኤብሱ ፡ ኢያንሥኡ ፡ ቀርኖሙ ።

ኢያንሥኡ ፡ ይላል ፡ የሚበድሉ ፡ እለ ፡
ሰናክሬምን ፡ ሥልጣናቸውን ፡ አያነ
ሱም ፡ ብዬ ፡ አንድም ፡ ኢታንሥኡ ፡
ቀርነክሙ ፡ ሥልጣናችሁን ፡ በለሕ
ዝቅያስ ፡ አታንሡ ፡ አልኋቸው ።

፭ ፡ ወኢያንሥኡ ፡ ቀርኖሙ ፡ ውስተ ፡ አርያም ።

ኢያንሥኡ ፡ ይላል ፡ በአርያም ፡ ባለ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ሥልጣናቸውን ፡
አያነሱም ፡ ብዬ ፡ አታንሱ ፡ አልኋ
ቸው ፡ አንድም ፡ ኢታንሥኡ ፡ ቀር
ነክሙ ፡ በአርያም ፡ ባለ ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ሥልጣናችኊን ፡ አንታሡ ፡
አልኋቸው ።

ወኢይንብቡ ፡ ዓመፃ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ።

ኢይነብቡ ፡ ይላል ፡ በእግዚአብሔር ፡
ላይ ፡ ዓመፅን ፡ አይናገሩም ፡ ብዬ ፡
አንድም ፡ ኢትንብቡ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ላይ ፡ ዓመፅን ፡ አትናገሩ ፡ አል
ኋቸው ።

፮ ፡ እስመ ፡ ኢእምጽባሕ ፡ ወኢእምዓረብ ፡ ወ
ኢእምአድባረ ፡ ገዳም ።

እምጽባሕ ፡ ከፋርስ ፡ እምዓረብ ፡ ከግ
ብፅ ፡ እምአድባረ ፡ ገዳም ፡ ከባቢሎን ፡
ተሰብስበው ፡ መጥተዋልና ፡ ምንም ፡
ቢመጡ ፡ ንሥኡ ፡ ትእምርተ ፡ እም
ኣድባረ ፡ ገዳም ፡ እንዲል ።

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኰንን ፡ ውእቱ ።

እግዚአብሔር ፡ ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡
ኰናኒ ፡ በርትዕ ፡ ነውና ፡ መዝ ፡ ፺፱ ፡ ፯ ።





ዘንተ ፡ ያኀሥር ፡ ወዘንተ ፡ ያከብር ።

ሰናክሬምን ፡ ያዋርዳል ፡ ሕዝቅያስን ፡
ያከብራል ፡ ኢሳ ፡ ፺፩ ፡ ፩ ፡ ፯ ።

፯ ፡ እስመ ፡ ጽዋዕ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአብሔር ።

ፅዋዓ ፡ መዓት ፡ በእደ ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ አለና ።

ወይን ፡ ዘኢኮነ ፡ ቱሱሐ ፡ ወምሉእ ፡ ትድሐቱ ።

ማየ ፡ ምሕረት ፡ ያልተቀላቀለው ፡ ወ
ይን ፡ መዓት ፡ የተመላበት ፡ ፅዋዓ ፡
መዓት ፡ በእደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አለ
ና ፡ ተይዟልና ፡ ምሉዕ ፡ ቅድሐቱ ፡ አ
ቀዳዱም ፡ ቸፍ ፡ ብሎ ፡ የመላ ፡ ጌታ ፡
ለልማዱ ፡ መዓቱንና ፡ ምሕረቱን ፡
ያፈራርቀው ፡ ነበር ፡ በነዚህ ፡ ግን ፡
ፍጹም ፡ መዓቱን ፡ አምጥቶባቸዋል
ና ፡ ቱስሐ ፡ ባለው ፡ ፍሡሐ ፡ ይላል ፡
ወይን ፡ ያስተፌሥሕ ፡ ልበ ፡ ሰብእ ፡
እንዳለው ፡ ያለ ፡ ያይደለ ፡ ወይን ፡ መ
ዓት ፡ የተመላበት ፡ ፅዋዐ ፡ መዓት ፡
በእደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተይዟልና ።

ወሦጠ ፡ እምዝንቱ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ።

ከዚህ ፡ ወደዚህ ፡ አጣጣው ፡ አቃዳ
ው ፡ የጋኑን ፡ በማድጋ ፡ የማድጋው
ን ፡ በገንቦ ፡ እንደማድረግ ፡ ማለት ፡
ፈጣን ፡ አሳሳፊ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡
አቁሞ ፡ ከሠራዊቱ ፡ እስከ ፡ ንጉሡ ፡
ድረስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አጠጣው ፡ አን
ድም ፡ ከለኪሶን ፡ እስከ ፡ ነነዌ ፡ ድረስ ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ አጠጣው ።

2014 04 17

ወባሕቱ ፣ ጣሕሉኒ ፣ ኢይትከዐው ።

ነገር ፣ ግን ፣ አተላውም ፣ እንድም ፣ አተላው ፣ ስንኳ ፣ አይፈስስም ።

ወይሰትይዎ ፣ ሆሎሙ ፣ ኃጥኣነ ፣ ምድር ።

ኄቶች ፣ ጉሉ ፣ ይጠጡታል ፣ እንጂ ፣ እሊህ ፣ እለ ፣ ሰናክሬም ፣ ናቸው ፣ የን ጉሥ ፣ ሞት ፣ ሳይቀር ፣ ነገሥታቱ ፣ ይቀበሉታል ፤ ከፅሩው ፣ አተላው ፣ እ ንዲከብድ ፣ ከሠራዊቱም ፣ ሞት ፣ የን ጉሥ ፣ ሞት ፣ ይከብዳልና ፤ ከጽሩው ፣ አተላው ፣ ወደ ፣ ኋላ ፣ እንዲሆን ፣ ከሠ ራዊቱም ፣ ሞት ፣ የንጉሡ ፣ ሞት ፣ ወደ ኋላ ፣ ይሆናልና ፤ የሠራዊቱን ፣ ሞት ፣ በጥሩ ፣ የንጉሡን ፣ ሞት ፣ በተላ ፣ መ ስሎ ፣ ተናገረ ፤ እንድም ፣ የነፍሱ ፣ መከራ ፣ ሳይቀር ፣ ነገሥታቱ ፣ ይቀበ ሉታልና ፤ ከፅሩው ፣ አተላው ፣ እንዲ ከብድ ፤ ከሥጋውም ፣ መከራ ፣ የነፍ ሱ ፣ ይከብዳልና ፣ ከፅሩው ፣ አተላው ፣ ወደ ፣ ኋላ ፣ እንዲሆን ፣ ከሥጋውም ፣ መከራ ፣ የነፍሱ ፣ መከራ ፣ ወደ ፣ ኋላ ፣ ይሆናልና ፣ የሥጋውን ፣ መከራ ፣ በ ጥሩ ፤ የነፍሱን ፣ በተላ ፣ መስሎ ፣ ተና ገረ ፣ ኤር ፣ ፵፱ ፣ ፲፪ ።

፱፤ ወአንሰ ፣ እትፈሣሕ ፣ ለዓለም ።

እኔ ፣ ግን ፣ ለዘላለሙ ፣ ደስ ፣ ይለኛል ፣

ወእዜምር ፣ ለአምላከ ፣ ያዕቆብ ።

ለያዕቆብ ፣ ፈጣሪም ፣ ምስጋና ፣ አቀ ርባለሁ ፤ እሱን ፣ አመሰግናለሁ ።

፲፤ ወእሰብር ፣ አርእስተ ፣ ኃጥኣን ።

የነሰናክሬምን ፣ ሥልጣን ፣ አጠፋለ ሁ ፤ እንድም ፣ ይሰበር ፣ ይጠፋል ፣ እንድም ፣ (ወይሰብር ፣ እግዚአብሔ ር) ፣ ሥልጣናቸውን ፣ ያጠፋል ።

ወይትሌዓል ፣ አቅርንተ ፣ ጻድቃን ።

የሕዝቅያስ ፣ ሥልጣን ፣ ግን ፣ ከፍ ፣ ከፍ ፣ ይላል ፣ እንድም ፣ አሌዕል ፣ ከፍ ፣ ከፍ ፣ አደርጋለሁ ፣ እንድም ፣ ያሌዕል ፣ እግዚአብሔር ፣ ሥልጣናቸውን ፣ ከፍ ከፍ ፣ ያደርጋል ፤ ፩ሳሙ ፣ ፪-፲ ።

## መዝሙር ፣ ፸፭ ።

፩፤ ተዐውቀ ፣ እግዚአብሔር ፣ በይሁዳ ።

ስለሕዝቅያስ ፣ ተናግሮታል ፤ እግዚ አብሔር ፣ በሁለቱ ፣ ነገድ ፣ በመታ መን ፣ ታወቀ ፣ ተረዳ ።

ወዐቢየ ፣ ስሙ ፣ በእስራኤል ።

ስሙም ፣ በእስራኤል ፣ ዘሥጋ ፣ የከ በረ ፣ የገነነ ፣ ሆነ ።

፪፤ ወነበረ ፣ በሰላም ፣ ብሔሮ ።

ሕዝቅያስ ፣ ከሀገሩ ፣ በአንድነት ፣ በፍ ቅር ፣ ኖረ ፤ እንድም ፣ ብሔሩ ፣ ይላል ፣ አገሪቱ ፣ በፍቅር ፣ ኖረች ፣ ወማኅደ ሩሂ ፣ ውስተ ፣ ጽዮን ፣ ማደሪውም ፣ በጽዮን ፣ በኢየሩሳሌም ፣ ነው ፤ እን ድም ፣ ወማኅደሪሂ ፣ ረሰየ ፣ ይላል ፣



ማደሪውን ፣ በኢየሩሳሌም ፣ አደረገ ፤ እንድም ፣ (ተዐውቀ) ፣ እግዚአብሔር ፣ ከነገደ ፣ ይሁዳ ፣ ከተወለዱ ፣ ነገድ ፣ በነሣው ፣ ሥጋ ፣ ታወቀ ፣ ተረዳ ፤ (ወ ዐቢየ) ፤ ስሙም ፣ በእስራኤል ፣ ዘነ ፍስ ፣ የከበረ ፣ የገነነ ፣ ሆነ ፤ (ወነበረ) ፣ ሥጋ ፣ የባሕርይ ፣ አምላክ ፣ ሆኖ ፣ በ መንበረ ፣ ስብሐት ፣ ኖረ ፤ ነሥአ ፣ ደ መና ፣ ወሠወሮ ፤ ወነበረ ፣ በሰላም ፣ ብሔሮ ፣ እንዳለ ፣ ደራሲ ፤ (ወማኅደ ሩሂ) ፣ ማደሪው ፣ እመቤታችን ፣ ናት ፤ እንድም ፣ ማደሪውን ፣ እመቤታችን ን ፣ አደረገ ።

፫፤ ወበህየ ፣ ሰበረ ፣ ኀይለ ፣ ቀስት ።

የቀስቱን ፣ ኃይል ፣ ሰበረ ፣ ማለት ፣ ግብ ሩን ፣ አጠፋ ።

ወልታ ፣ ወኵናተ ፣ ወፀባኢተ ።

በጋሻው ፣ እንዳይመከቱበት ፣ በጦሩ ፣ እንዳይወጉበት ፣ አደረገ ፤ የሚዳ ፣ ፀ ብቱንም ፣ አጠፋ ።

ወበህየ ፣ ሰበረ ፣ አቅርንተ ።

ነጋሪቱን ፣ ሰበረ ፤ እግዚአብሔርማ ፣ ነጋሪት ፣ ሲሰበር ፣ ይውላልን ፣ ግብሩን ፣ አጠፋ ፤ እንድም ፣ ነገሥታቱን ፣ መኳ ንንቱን ፣ ሠራዊቱን ፣ አጠፋ ፤ እን ድም ፣ ሊቃነ ፣ አጋንንትን ፣ ሠራዊተ ፣ አጋንንትን ፣ ድል ፣ ነሣ ።

፬፤ አንተ ፣ ታበርህ ፣ መንክረ ፣ እምአድባር ፣ ዘለዓለም ።

አንተ ፣ ከፀሐይ ፣ ከጨረቃ ፣ ዝምሮ ፣ ብርሃን ፣ ረድኤትህን ፣ ታበራለህ ፤ እን ድም ፣ ከሙሴ ፣ ከአሮን ፣ ይልቅ ፣ ብር ሃን ፣ ረድኤትህን ፣ ታበራለህ ፤ እንድም ፣ ከአብርሃም ፣ ከይስሐቅ ፣ ከያዕቆብ ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣ የተነሣ ፣ ብርሃን ፣ ተአ ምራትህን ፣ ታበራለህ ።

፭፤ ደንገጹ ፣ ኵሎሙ ፣ አብዳን ፣ ልብ ።

የልቡና ፣ ደናቁርት ፣ እለ ፣ ሰናክሬም ፣ የሞት ፣ ድንጋጤ ፣ ደነገፁ ።

ሐለሙ ፣ ሕልመ ፣ ወኢረከቡ ፣ ዘረከቡ ።

ሕልም ፣ አለሙ ፣ ያገኙት ፣ ማግኘት ፣ የለም ፤ ነገ ፣ ይህን ፣ ጊዜ ፣ የምንገድ ለውን ፣ እንገድላለን ፣ የምናድነውን ፣ እናድናለን ፣ ብለው ፣ ነበር ፣ ይህ ፣ ቀር ቶባቸዋልና ፤ እንድም ፣ እነ ፣ ሕዝቅ ያስ ፣ ሕልም ፣ አለሙ ፣ ነገ ፣ ይህን ፣ ጊዜ ፣ የምንሞተው ፣ እንሞታለን ፣ የ ምንማረከው ፣ እንማረካለን ፣ ብለው ፣ ነበር ፤ (ወኢረከቡ ፣ ዘረከቡ) ፣ ምንም ፣ ያገኛቸው ፣ የለም ፤ ይህ ፣ ቀርቶባቸ ዋልና ።

ኵሎ ፣ ሰብእ ፣ ለብዕለ ፣ እደዊሆሙ ።

ሰው ፣ ሁሉ ፣ በጅ ፣ ለተያዘ ፣ ገንዘብ ፣ ባለቤት ፣ ይሸናል ፣ የሚወስድበት ፣ የለም ፣ ብሎ ፣ ነበር ፤ እንድም ፣ (ለብ ዕለ ፣ እደዊሁ) ፣ እየእጅ ፣ እየእጁ ፣ ይዝረፍ ፣ ብሎ ፣ ነበር ፤ እንድም ፣ የሰናክሬምን ፣ ገንዘብ ፣ ይዝረፍ ፣ ኢሳ ፣ ፴፱ ፣ ፰ ።

፮፤ እምተግሣጽከ ፡ አምላከ ፡ ያዕቆብ ።

አቤቱ ፡ የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ከመፍረ
ድህ ፡ የተነሣ ።

ደቀሱ ፡ ዘጸዓነ ፡ አፍራስ ፡ ኅበ ፡ ዝዕ ፡ (ደቀቁ ፡ ዘጽዑኖሙ ፡ አፍራስ ፡ ...)

በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡ ተቀምጠው ፡ የ
መጡ ፡ እለ ፡ ሰናክሬም ፡ በሞት ፡ እን
ቅልፍ ፡ አንቀላፉ ።

፯፤ አንተሰ ፡ ግሩም ፡ አንተ ።

አንተ ፡ ግን ፡ ግሩም ፡ ነህ ።

ወመኑ ፡ ይትቃወሞ ፡ ለመዓትከ ።

መዓትህንም ፡ መመለስ ፡ የሚቻለው ፡
የለም ፡ ሰናክሬም ፡ ስንኳ ፡ ያን ፡ ያ
ህል ፡ ሠራዊት ፡ ይዞ ፡ መመለስ ፡ አል
ተቻለውም ።

፰፤ እምሰማይ ፡ ታሰምዕ ፡ ፍትሐ ።

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ከሰማይ ፡ ሁነህ ፡
ፍርድን ፡ ታሰማለህ ፡ ቢገሥሥም ፡
ቢፈርድም ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ፡ እንድም ፡
የሰውን ፡ ጸሎት ፡ ትቀበላለህ ፡ የምያ
ስፈርድለት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ፍትህ ፡ አ
ለው ።

ምድርኒ ፡ ፈርሀት ፡ ወአርመመት ።

ለኪሰን ፡ ፈራች ፡ ፤ ቻ ፡ ቻ ፡ ትል ፡ የነ
በረ ፡ ጫ ፡ አለች ።

፱፤ ሶበ ፡ ተንሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኰንኖ ።

እግዚአብሔር ፡ ለነሕዝቅያስ ፡ ሊፈ
ርድላቸው ፡ በነሰናክሬም ፡ ሊፈርድ
ባቸው ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ።

ከመ ፡ ያድኅኖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ የዋሃን ፡ ልብ ።

ቅን ፡ ልቡና ፡ ትሑት ፡ ሰብእና ፡ ያላ
ቸውን ፡ እነሕዝቅያስን ፡ ጉሉ ፡ ያድ
ናቸው ፡ ዘንድ ።

፲፤ እስመ ፡ ሕምሬቶሙ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይገኒ ፡ ለከ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሥር ፡ አንድ ፡ ሰጥቶ ፡
ያመሰግንሃል ።

እመኒ ፡ ወልደየ ፡ እንዲል ።

ይህስ ፡ የግድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከፈቃድ ፡
ገንዘቡ ፡ ከዘጠኝ ፡ አንድ ፡ ሰጥቶ ፡
ያመሰግንሃል ።

ወእምተረፈ ፡ ሕሊናሆሙ ፡ ይገብሩ ፡ በዓለከ ።

በልተውለት ፡ ጠጥተውለት ፡ ከተረፈ ፡
ገንዘባቸው ፡ ሰጥተው ፡ በዓልህን ፡
ያከብራሉ ፡ የልደቱ ፡ ለጥምቀት ፡ የ
ትንሣኤው ፡ ለማዕዶት ፡ እንዲተርፍ ።

፲፩፤ ብፅዑ ፡ ወሀቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ለፈጣሪያችን ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ሰጡ ፡
(ይሰጣሉ) ።

ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ዓውዶ ፡ ያበውዑ ፡ አምኃ ።

ለሕዝቅያስም ፡ በዙርያው ፡ ያሉ ፡
እጅ ፡ መንሻ ፡ ያቀርባሉ ፡ ወፈነወ ፡
መሮዳህ ፡ መጻሕፍተ ፡ ወመኅና ፡ ዘ
ምስለ ፡ ብዙኅ ፡ አምኃ ፡ ለሕዝቅያስ ፡
ንጉሠ ፡ ይሁዳ ፡ እንዲል ፡ አንድም ፡
ለጌታ ፡ በዙርያው ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡
ሁሉ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ግብር ፡ ያቀር
ባሉ ።





፲፪፤ ለገሬም ፡ ዘያወፅእ ፡ ነፍሶሙ ፡ ለመላእ
ክት ።

ያለቆቹን ፡ ነፍሳቸውን ፡ ከሥጋቸው ፡
ለሚለይ ፡ ለጌታ ።

ወይገርም ፡ እምነገሥተ ፡ ምድር ።

በራቱ ፡ መዓዘን ፡ ካሉ ፡ ነገሥታት ፡
ግሩም ፡ ለሚሆን ፡ ለጌታ ፡ ምንው ፡
የገበሩማ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ እይደለምን ፡
ቢሉ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ መገበራቸው ፡
የጌታ ፡ ፈቃድ ፡ ነውና ፡ የሕዝቅያስን ፡
ለጌታ ፡ ሰጥቶ ፡ ተናገረ ፡ አንድም ፡
ከሚጠት ፡ በኋላ ፡ እሕዛብ ፡ ለቤተ ፡
እግዚአብሐር ፡ ገብረዋል ፡ ወይከ
ድና ፡ አናቅጸኪ ፡ አግማለ ፡ ምድያም ፡
እንዲል ።

## መዝሙር ፡ ፸፮ ።

፩፤ ቃልየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸራኅኩ ፡
መዝ ፡ ፻፵፩ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ በቃሌ ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሼ ፡ ለመ
ንኁ ፡ አንድም ፡ ልመናዬን ፡ ወደ ፡
እግዚአሔር ፡ አቀረብኁ ።

ቃልየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አፅምአኒ ።

አብጻሕኩ ፡ ይላል ፡ ወደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ መልሼ ፡ የለመንኁትን ፡ ልመ
ናዬን ፡ ሰማኝ ።

፪፤ በዕለተ ፡ ምንዳቤየ ፡ ኀሠሥክዎ ፡ ለእግዚአ
ብሔር ።

በመከራዬ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔርን ፡
በሕግ ፡ በአምልከ ፡ ሻኁት ፡ ኢሳ ፡
፶፰ ፡ ፱ ።

ዕድውየ ፡ ሌሊተ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወኢኮነኒ ።

ጠላቶቼ ፡ በሱ ፡ ፈቃድ ፡ ተገናኙኝ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ እጅ ፡ አላደረጉኝም ፡ አ
ላጠበቁኝም ፡ አንድም ፡ እንዘ ፡ በቅ
ድሚየ ፡ ይላል ፡ ጠላቶቼ ፡ በፊቴ ፡
እያሉ ፡ አላጠቁኝም ፡ አንድም ፡ እደ
ውየ ፡ እጆቼን ፡ ዘርግቼ ፡ በሌሊት ፡
ለመንኁት ።

ቀብፀት ፡ ነፍስየ ፡ ትፍሥሕተ ።

ሰውነቴ ፡ ተስፋ ፡ ቈረጠችብኝ ።

፫፤ ተዘከርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወተፈገሥኩ ።

እግዚአብሐርን ፡ በሕግ ፡ በአምልክ ፡
አሰብኁት ፡ በዚያውም ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡
ዛሬ ፡ በመከራ ፡ ቢጥለኝ ፡ ያሳልፍልኝ ፡
የለምን ፡ ብዬ ።

ተዛዋዕኩኒ ፡ ወአንበዘት ፡ ነፍስየ ።

መከራውን ፡ ተጫዋወትኁት ፡ ሰው
ነቴም ፡ ተቅበዘበዘችብኝ ፡ ኢሳ ፡ ፳፮ ፡
፲፯ ።

፬፤ ተራከብክዎን ፡ ለሰዓታተ ፡ ዘሎሙ ፡ ጸላእ
ትየ ።

ጠላቶቼ ፡ ሁሉ ፡ የነገሡብቸውን ፡ ዘ
መናት ፡ በሐልዮ ፡ ተገናኘኋቸው ።

፮ ፡ እምተግዕዞ ፡ እምላከ ፡ ያዕቆብ ።

አቤቱ ፡ የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ከመፍረ ድህ ፡ የተነሣ ።

ደቀቁ ፡ ሾሎሙ ፡ እለ ፡ ይፄንኑ ፡ አፍራስ ።

በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡ ተቀምጠው ፡ የ መጡ ፡ እለ ፡ ሰናክሬም ፡ በሞት ፡ እን ቅልፍ ፡ እንቀላፉ ።

፯ ፡ አንተሰ ፡ ግሩም ፡ አንተ ።

አንተ ፡ ግን ፡ ግሩም ፡ ነህ ።

ወመኑ ፡ ይትቃወሞ ፡ ለመዓትከ ።

መዓትህንም ፡ መመለስ ፡ የሚቻለው ፡ የለም ፡ ሰናክሬም ፡ ስንኳ ፡ ያን ፡ ያ ህል ፡ ሠራዊት ፡ ይዞ ፡ መመለስ ፡ አል ተቻለውም ።

፰ ፡ እምሰማይ ፡ ታጸምዕ ፡ ፍትሐ ።

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ከሰማይ ፡ ሁነህ ፡ ፍርድን ፡ ታሰማለህ ፡ ቢገሥሥም ፡ ቢፈርድም ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ፡ አንድም ፡ የሰውን ፡ ጸሎት ፡ ትቀበላለህ ፡ የምያ ስፈርድለት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ፍትህ ፡ አ ለው ።

ምድርኒ ፡ ፈርሀት ፡ ወአርመመት ።

ለኪሰን ፡ ፈራች ፤ ፡ ቻ ፡ ቻ ፡ ትል ፡ የነ በረ ፡ ጫ ፡ አለች ።

፱ ፡ ሶበ ፡ ተንሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኵነኔ ።

እግዚአብሔር ፡ ለነሕዝቅያስ ፡ ሊፈ ርድላቸው ፡ በነሰናክሬም ፡ ሊፈርድ ባቸው ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ።

ከመ ፡ ያድኅኖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ የዋሃን ፡ ልብ ።

ቅን ፡ ልቡና ፡ ትሑት ፡ ሰብእና ፡ ያላ ቸውን ፡ እነሕዝቅያስን ፡ ኁሉ ፡ ያድ ናቸው ፡ ዘንድ ።

፲ ፡ እስመ ፡ እምፈቃዱ ፡ የአምንከ ፡ ሰብእ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሥር ፡ አንድ ፡ ሰጥቶ ፡ ያመሰግንሃል ።

አመኖ ፡ ወልድየ ፡ እንዲል ።

ይህስ ፡ የግድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከፈቃድ ፡ ገንዘቡ ፡ ከዘጠኝ ፡ አንድ ፡ ሰጥቶ ፡ ያመሰግንሃል ።

ወእምተረፈ ፡ ሕሊናሆሙ ፡ ይገብሩ ፡ በዓለከ ።

በልተውለት ፡ ጠጥተውለት ፡ ከተረፈ ፡ ገንዘባቸው ፡ ሰጥተው ፡ በዓልህን ፡ ያከብራሉ ፤ የልደቱ ፡ ለጥምቀት ፡ የ ትንሣኤው ፡ ለማዕዶት ፡ እንዲተርፍ ።

፲፩ ፡ ብፅዑ ፡ ወሀቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ለፈጣሪያችን ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ስጡ ፤ (ይሰጣሉ) ።

ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ዓውዱ ፡ ያበውኡ ፡ አምኃ ።

ለሕዝቅያስም ፡ በዙርያው ፡ ያሉ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ያቀርባሉ ፤ ወፈነወ ፡ ዘ መሮዳህ ፡ መጸሕፍተ ፡ ወመኀና ፡ ዘ ምስለ ፡ ብዙኅ ፡ አምኃ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ ንጉሥ ፡ ይሁዳ ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ ለጌታ ፡ በዙርያው ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ግብር ፡ ያቀር ባሉ ።



፲፪ ፡ ለግሩም ፡ ዘያወፅእ ፡ ነፍሶሙ ፡ ለመላእ ክት ።

ያለቆቹን ፡ ነፍሳቸውን ፡ ከሥጋቸው ፡ ለሚለይ ፡ ለጌታ ።

ወይጌርም ፡ እምነገሥተ ፡ ምድር ።

በራቱ ፡ መዓዘን ፡ ካሉ ፡ ነገሥታት ፡ ግሩም ፡ ለሚሆን ፡ ለጌታ ፡ ምንጠ ፡ የገበሩማ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ መግበራቸው ፡ የጌታ ፡ ፈቃድ ፡ ነውና ፡ የሕዝቅያስን ፡ ለጌታ ፡ ሰጥቶ ፡ ተናገረ ፤ አንድም ፡ ከሚጠት ፡ በኋላ ፡ አሕዛብ ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብረዋል ፤ ወይከ ድና ፡ አናቅጸኪ ፡ አግማለ ፡ ምድያም ፡ እንዲል ።

## መዝሙር ፡ ፸፯ ።

፩ ፡ ቃልየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸራኅኩ ፡ መዝ ፡ ፲፵፩ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ በቃሌ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሼ ፡ ለመ ንኁ ፤ አንድም ፡ ልመናዬን ፡ ወደ ፡ እግዚአሔር ፡ አቀረብኍ ።

ቃልየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዕምአኒ ።

አብጻሕኩ ፡ ይላል ፡ ወደ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ መልሼ ፡ የለመንኍትን ፡ ልመ ናዬን ፡ ሰማኝ ።

፪ ፡ በዕለተ ፡ ምንዳቤየ ፡ ኀሠሥክዎ ፡ ለእግዚአ ብሔር ።

በመከራዬ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ ሻኁት ፡ ኢሳ ፡ ፶፰ ፡ ፪ ።

ዕድውየ ፡ ሌሊተ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወኢክሑዱኒ ።

ጠላቶቼ ፡ በሱ ፡ ፈቃድ ፡ ተገናኙኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እጅ ፡ አላደረጉኝም ፡ አ ላጠበቁኝም ፤ አንድም ፡ እንዘ ፡ በቅ ድሜየ ፡ ይላል ፡ ጠላቶቼ ፡ በፊቴ ፡ እያሉ ፡ አላጠቁኝም ፤ አንድም ፡ እደ ውየ ፡ እጆቼን ፡ ዘርግቼ ፡ በሌሊት ፡ ለመንኍት ።

ቀብፀት ፡ ነፍስየ ፡ ትፍሥሕተ ።

ሰውነቴ ፡ ተስፋ ፡ ቈረጠችብኝ ።

፫ ፡ ተዘከርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወተፈግሥኩ ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ አሰብኍት ፡ በዚያውም ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ ዛሬ ፡ በመከራ ፡ ቢጥለኝ ፡ ያሳልፍልኝ ፡ የለምን ፡ ብዬ ።

ተዛዋዕኩሂ ፡ ወአንበዘት ፡ ነፍስየ ።

መከራውን ፡ ተጨዋወትኍት ፡ ሰው ነቴም ፡ ተቅበዘበዘችብኝ ፤ ኢሳ ፡ ፳፮ ፡ ፲፯ ።

፬ ፡ ተራከብክዎን ፡ ለዕቃታተ ፡ ሾሎሙ ፡ ለዓላ ትየ ።

ጠላቶቼ ፡ ሁሉ ፡ የነገሡባቸውን ፡ ዘ መናት ፡ በሐልዮ ፡ ተገናኘኋቸው ።

2014 04 17

ደንገጽኩ ፡ ወኢነበብኩ ፡ ኢዮ ፡ ፳፱ ፡ ፯ ።

እንዲህ ፡ በሰብኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ደነገ ፅኩ ፡ አልተናገርኩም ፡ ድንጋጤ ፡ አ ያናግርምና ፡ ኢሳ ፡ ፳፩ ፡ ፫-፬ ።

፭ ፡ ወሐለይኩ ፡ መዋዕለ ፡ ትካት ።

የቀደመውን ፡ ዘመን ፡ አሰብኩ ።

ተዘከርኩ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ወአንበብኩ ።

መዋዕለ ፡ ትክትና ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የቀደመውን ፡ አሰ ብኩ ፡ በኢ.ግሎም ፡ በዘስርስትኤም ፡ ያን ፡ ያህል ፡ መከራ ፡ ተቀበሉኙ ፡ አለፈላቸው ፡ እኔም ፡ ያልፍልኛል ፡ ብዬ ።

፮ ፡ ሌሊተ ፡ ተዛዋዕኩ ፡ ምስለ ፡ ልብየ ፡ ወአን ቃሕኩዋ ፡ ለነፍስየ ።

በሌሊተ ፡ መከራዬ ፡ ጊዜ ፡ ከልቡ ናዬ ፡ ጋራ ፡ ተጫዋወትኩ ፡ ሰውነቴ ንም ፡ በተስፋው ፡ አነቃቃኋት ፡ መ ከራ ፡ እንጂ ፡ ያልፋል ፡ ብዬ ፤ አን ድም ፡ ሌሊት ፡ ልቡናዬን ፡ አንቅቼ ፡ ከሰውነቴ ፡ ጋራ ፡ ተጫዋወትኩ ፡ ኢሳ ፡ ፳፯ ፡ ፱ ።

፯ ፡ ዐኑ ፡ ለዓለም ፡ ይገድፍ ፡ እግዚአብሔር ።

በውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጊዜው ፡ ቢጥል ፡ ለዘላለም ፡ እንደጣለ ፡ ይቀ ራልን ፡ እያልኩ ።

ወኢይደግምኑ ፡ እንከ ፡ ተግህሎ ።

ቀድሞ ፡ ለአበው ፡ ያደረገውን ፡ ቸር ነቱን ፡ ሁለተኛ ፡ ለውሉድ ፡ አያደር ገውምን ፡ እያልኩ ።

፰ ፡ ወዐኑ ፡ ለግሙራ ፡ ይመትር ፡ ምሕረቶ ፡ ለ ትውልደ ፡ ትውልድ ።

በውኑ ፡ ቸርነቱን ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ፍ ርጃ ፡ አድርጎ ፡ ያስቀረዋልን ።

፱ ፡ ወይረስዖኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተሣህሎ ።

እግዚአብሔር ፡ ቸርነቱን ፡ ይዘነጋዋ ልን ፡ ሰውን ፡ ቀድሞ ፡ የሚያውቀው ፡ ሥራ ፡ በርኅቀተ ፡ ዘመን ፡ እንዲረ ሳው ፡ ይረሳዋልን ።

ወይደፍንኑ ፡ ምረሕቶ ፡ በመዓቱ ።

እንደ ፡ ዓባይ ፡ ያለ ፡ ምሕረቱን ፡ እን ደ ፡ ምንጭ ፡ ባለ ፡ መዓቱ ፡ ይሠውረ ዋልን ፤ አንድም ፡ (ወይደፈንኑ ፡ ምሕ ረቱ ፡ በመዓቱ) ፡ እንደ ፡ ዓባይ ፡ ያለ ፡ ምሕረቱ ፡ እንደ ፡ ምንጭ ፡ ባለ ፡ መዓ ቱ ፡ ይሠወራልን ።

፲ ፡ ወእቤ ፡ እምይእዜ ፡ ወጠንኩ ።

እቤ ፡ ወጠንኩ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ነገር ፡ ዠመ ርኩ ፡ አልኩ ።

ከመ ፡ ዘያስተባልእ ፡ የማኖ ፡ ልዑል ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥልጣኑን ፡ አንድም ፡ (የማኖ ፡ ልዑል) ፡ ልዑል ፡ ሥልጣኑን ፡ እንዲያፈራርቀው ።

፲፩ ፡ ወተዘከርኩ ፡ ግብሮ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ሥራውን ፡ አሰብኩ ፤

እስመ ፡ እዜከር ፡ ዘትካት ፡ ምሕረተከ ። ኢሳ ፡ ፳፫ ፡ ፯ ።

አስፈ.ችው ፡ ወደፊት ፡ ነው ፡ የቀደ



መች ፡ ቸርነትህን ፡ አስቤአለሁና ።

፲፪ ፡ ወአነብብ ፡ በኵሉ ፡ ምግባሪከ ።

ሥራህን ፡ ኁሉ ፡ እናገራለኁ ፡ አስተ ምለሁና ።

ወእዛዋዕ ፡ በግብርከ ።

ሥራህን ፡ ተግባር ፡ አድርጌ ፡ እኖራ ለኁና ።

፲፫ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ መቅደስ ፡ ፍኖትከ ።

አቤቱ ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ትሩፋ ንን ፡ ይዘህ ፡ ጉዞህ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅ ደስ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ሕግህ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይነገራል ።

መኑ ፡ አምላክ ፡ ዐቢይ ፡ ከመ ፡ አምላክነ ።

እንደ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ያለ ፡ ገናና ፡ አም ላክ ፡ ማነው ፡ ማዳን ፡ መታደግ ፡ የሚ ቻለው ።

፲፬ ፡ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሕቲትከ ፡ ዘትገ ብር ፡ መንክረ ። ኤር ፡ ፴፪ ፡ ፰ ።

ድንቅ ፡ ተአምራት ፡ የምታደርግ ፡ ገ ናና ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ ፤ አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ተአምራት ፡ የምታደርግ ፡ ነህ ።

አርኣይኮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ ኀይለከ ።

ለወገኖችህ ፡ ለትሩፋን ፡ ከሃሊነትህን ፡ ገለጽህላቸው ።

፲፭ ፡ ወአድኃንኮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ በመዝራዕትከ ።

ወገኖችህ ፡ ትሩፋንን ፡ በሥልጣንህ ፡ አዳንኻቸው ።

ለደቂቀ ፡ ያዕቆብ ፡ ወዮሴፍ ።

ሕዝብክ ፡ ያለውን ፡ ደቂቀ ፡ ያዕቆብ ፡ ወዮሴፍ ፡ ብሎ ፡ አመጣው ፤ ለዮሴፍ ፡ ለያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ለትሩፋን ፤ ምነው ፤ የዮሴፍማ ፡ ወንድማቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አባታቸው ፡ ነውን ፡ እንዲህን ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ እንደ ፡ አባት ፡ ሆኖ ፡ ልብስ ፡ ቀለብ ፡ እየሰጠ ፡ የሚያኖራቸው ፡ እሱ ፡ ነበርና ፤ አንድም ፡ ለደቂቀ ፡ ያዕቆብ ፡ ወለደቂቀ ፡ ዮሴፍ ፡ ይላል ፡ ለዮሴፍና ፡ ለያዕቆብ ፡ ልጆች ።

፲፮ ፡ ርእዩከ ፡ ማያት ፡ እግዚኦ ።

ማያተ ፡ ኤርትራ ፡ ዓዩህ ።

ርእዩከ ፡ ማያት ፡ ወፈርሁ ።

ፈርሁ ፡ ለማለት ፡ ደገመው ።

ዓይተውህም ፡ ፈሩ ። ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፩ ።

፲፯ ፡ ደንገጹ ፡ ቀላያተ ፡ ማያት ፡ ወደምፀ ፡ ማያ ቲሆሙ ።

ውሀነት ፡ ያላቸው ፡ ወንዞች ፡ ደነገጹ ፡ ውሀነታቸው ፡ ጠፋ ።

ቃለ ፡ ወሀቡ ፡ ደመናት ፡ እሕጸከ ፡ ይወፅኡ ።

እሕፃ ፡ መዓትህ ፡ ሲደረጉ ፡ ደመናት ፡ ቃልን ፡ ሰጡ ፡ ማለት ፡ እሳት ፡ በረድ ፡ አዘነሙ ።

፲፰ ፡ ቃለ ፡ ነጐድጓድከ ፡ በሠረገላት ።

እሳት ፡ በረድ ፡ ማዝነማቸው ፡ በግብ ፃውያን ፡ ነው ፡ አንድም ፡ (ቃለ ፡ ወ ሀቡ) ፡ እሕፃ ፡ መዓትህ ፡ ሲደረጉ ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ በረድ ፡ ይዝነም ፡ እሳ

ደነገፅኩ፡ ወኢነበብኩ፡ ኢዮ፡ ፳፩፡ ፯።

እንዲህ፡ በሰብኣቸው፡ ጊዜ፡ ደነገ ጥኩ፡ አልተናገርኩም፡ ድንጋፄ፡ አ ያናግርምና፡ ኢዮ፡ ፳፩፡ ፫-፱።

፭፡ ወሐለይኩ፡ መዋዕለ፡ ትካት።

የቀደመውን፡ ዘመን፡ አሰብኩ።

ተዘከርኩ፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ ወአንበብኩ።

መዋዕለ፡ ትክትና፡ ዓመተ፡ ዓለም፡ አንድ፡ ወገን፡ የቀደመውን፡ አሰ ብኩ፡ በኢዮብም፡ በሕዝቅያስም፡ ያን፡ ያህል፡ መከራ፡ ተቀበሉ፡ አለፈላቸው፡ እኔም፡ ያልፍልኛል፡ ብዬ።

፮፡ ሌሊተ፡ ተዘከርኩ፡ ምስለ፡ ልብየ፡ ወአን ቃዕኩ፡ ለነፍስየ።

በሌሊት፡ መከራዬ፡ ጊዜ፡ ከልቡ ናዬ፡ ጋራ፡ ተጫዋወትኩ፡ ሰውነቴ ንም፡ በተከፋው፡ እነቃቃኋት፡ መ ከራ፡ እንጂ፡ ያልፋል፡ ብዬ፡ አን ድም፡ ሌሊት፡ ልቡናዬን፡ አንቅቼ፡ ከሰውነቴ፡ ጋራ፡ ተጫዋወትኩ፡ ኢሳ፡ ፳፮፡ ፱።

፯፡ ቦኑ፡ ለዓለም፡ ይገድፍ፡ እግዚአብሔር።

በውኑ፡ እግዚአብሔር፡ ለጊዜው፡ ቢጥል፡ ለዘላለም፡ እንደጣለ፡ ይቀ ራልን፡ እያልኩ።

ወኢይደግም፡ እንከ፡ ተግሂሦ።

ቀድሞ፡ ለአበው፡ ያደረገውን፡ ቸር ነቱን፡ ሁለተኛ፡ ለውሉድ፡ አያደር ገውምን፡ እያልኩ።

፰፡ ወቦኑ፡ ለግሙራ፡ ይመትር፡ ምሕረቶ፡ ለ ትውልደ፡ ትውልድ።

በውኑ፡ ቸርነቱን፡ ለልጅ፡ ልጅ፡ ቍ ርጥ፡ አድርጎ፡ ያስቀረዋልን።

፱፡ ወይረስዕኑ፡ እግዚአብሔር፡ተሣህሎ።

እግዚአብሔር፡ ቸርነቱን፡ ይዘነጋዋ ልን፡ ሰውን፡ቀድሞ፡የሚያውቀው፡ ሥራ፡ በርኅቀት፡ ዘመን፡ እንዲረ ሣው፡ ይረሣዋልን።

ወይደፍንኑ፡ ምረሕቶ፡ በመዓቱ።

እንደ፡ ዓባይ፡ ያለ፡ ምሕረቱን፡ እን ደ፡ ምንጭ፡ ባለ፡ መዓቱ፡ ይሠውረ ዋልን፡ አንድም፡ (ወይደፈንኑ፡ ምሕ ረቱ፡ በመዓቱ)፡ እንደ፡ ዓባይ፡ ያለ፡ ምሕረቱ፡ እንደ፡ ምንጭ፡ ባለ፡ መዓ ቱ፡ ይሠወራልን።

፲፡ ወእቤ፡ እምይእዜ፡ ወጠንኩ።

አቤ፡ ወጠንኩ፡ አንድ፡ ወገን፡ ከዛሬ፡ ጀምሮ፡ እንዲህ፡ ብዬ፡ ነገር፡ ጀመ ርኩ፡ አልኩ።

ከመ፡ ዘያስተባልዕ፡ የማኖ፡ ልዑል።

ልዑል፡ እግዚአብሔር፡ ሥልጣኑን፡ አንድም፡ (የማኖ፡ ልዑል)፡ ልዑል፡ ሥልጣኑ፡ እንዲያፈራርቀው።

፲፩፡ ወተዘከርኩ፡ ግብሮ፡ ለእግዚአብሔር።

የእግዚአብሔር፡ ሥራውን፡ አሰብኩ፡

እስመ፡ እዜከር፡ ዘትካት፡ ምሕረትከ። ኢሳ፡ ፳፫፡ ፯።

አስፈችው፡ ወደፊት፡ ነው፡ የቀደ



መች፡ ቸርነትህን፡ አስቤአለሁና።

፲፪፡ ወአነብብ፡ በኵሉ፡ ምግባሪከ።

ሥራህን፡ ጕሉ፡ እነግራለሁ፡ አስተ ምራለሁና።

ወእዜየድ፡ በግብርከ።

ሥራህን፡ ተግባር፡ አድርጌ፡ እኖራ ለሁና።

፲፫፡ እግዚኦ፡ ውስተ፡ መቅደስ፡ ፍኖትከ።

አቤቱ፡ ከሰባ፡ ዘመን፡ በኋላ፡ ትሩፋ ንን፡ ይዘህ፡ ጉዞህ፡ ወደ፡ ቤተ፡ መቅ ደስ፡ ነው፡ አንድም፡ ሕግህ፡ በቤተ፡ መቅደስ፡ ይነገራል።

መኑ፡ አምላክ፡ ዓቢይ፡ ከመ፡ አምላክነ።

እንደ፡ ፈጣሪያችን፡ ያለ፡ ገናና፡ አም ላክ፡ ማነው፡ ማዳን፡ መታደግ፡ የሚ ቻለው።

፲፬፡ አንተ፡ እግዚአብሔር፡ ባሕቲትከ፡ ዘትገ ብር፡ መንክረ። ኤር፡ ፴፪፡ ፳።

ድንቅ፡ ተአምራት፡ የምታደርግ፡ ገ ናና፡ እግዚአብሔር፡ አንተ፡ ብቻ፡ ነህ፡ አንድም፡ እግዚአብሔር፡ አንተ፡ ብቻ፡ ተአምራት፡ የምታደርግ፡ ነህ።

አርአይኮሙ፡ ለሕዝብከ፡ ኃይለከ።

ለወገኖችህ፡ ለትሩፋን፡ ከሃሊነትህን፡ ገለጽህላቸው።

፲፭፡ ወአድኃንኮሙ፡ ለሕዝብከ፡ በመዝራዕትከ።

ወገኖችህ፡ ትሩፋንን፡ በሥልጣንህ፡ አዳንኻቸው።

ለደቂቀ፡ ያዕቆብ፡ ወዮሴፍ።

ሕዝብከ፡ ያለውን፡ ደቂቀ፡ ያዕቆብ፡ ወዮሴፍ፡ ብሎ፡ አመጣው፡ ለዮሴፍ፡ ለያዕቆብ፡ ልጆች፡ ለትሩፋን፡ ምነው፡ ዮሴፍም፡ ወንድማቸው፡ ነው፡ እንጂ፡ አባታቸው፡ ነውን፡ እንዲህን፡ ካለ፡ ቢሉ፡ እንደ፡ አባት፡ ሆኖ፡ ልብስ፡ ቀለብ፡ እየሰጠ፡ የሚያኖራቸው፡ እሱ፡ ነበርና፡ አንድም፡ ለደቂቀ፡ ያዕቆብ፡ ወለደቂቀ፡ ዮሴፍ፡ ይላል፡ ለዮሴፍና፡ ለያዕቆብ፡ ልጆች።

፲፮፡ ርእዩከ፡ ማያት፡ እግዚኦ።

ማያተ፡ ኤርትራ፡ ዓዩህ።

ርእዩከ፡ ማያት፡ ወፈርሁ።

ፈርሁ፡ ለማለት፡ ደገመው።

ዓይተውህም፡ ፈሩ። ኢሳ፡ ፶፤፡ ፭።

፲፯፡ ደንገፁ፡ ቀላያተ፡ ማያት፡ ወደምፀ፡ ማያ ቲሆሙ።

ውህነት፡ ያላቸው፡ ወንዞች፡ ደነገጡ፡ ውህነታቸው፡ ጠፋ።

ቃለ፡ ወሀቡ፡ ደመናት፡ እሕፃከ፡ ይወፅኡ።

እሕፃ፡ መዓትህ፡ ሲደረጉ፡ ደመናት፡ ቃልን፡ ሰጡ፡ ማለት፡ እሳት፡ በረድ፡ አዘነሙ።

፲፰፡ ቃለ፡ ነጐድጓድከ፡ በመንኰራኵር።

እሳት፡ በረድ፡ ማዝነማቸው፡ በግብፃውያን፡ ነው፡ አንድም፡ (ቃለ፡ ወሀቡ)፡ እሕፃ፡ መዓትህ፡ ሲደረጉ፡ ሙሴ፡ አሮን፡ በረድ፡ ይዝነም፡ እሳ

ቅ ፡ ይውረድ ፡ ብለው ፡ አመለከቱ ፡ (ቃለ፡ነጐድጓድከ)፡እሳት፡ይውረድ፡ በረድ ፡ ይዝነም ፡ ብለው ፡ መጸለያ ቸው ፡ በግብፃውያን ፡ ነው ፡ ሠረገላ ፡ ግደኛ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግብፃውያንም ፡ ቢያምኑበት ፡ ያድርባቸው ፡ ነበርና ፡ ሠረገላ ፡ አላቸው ።

አፅርዕየ ፡ መብረቅከ ፡ ለዓለም ።

መብረቅተ ፡ መዓቱ ፡ ለእስራኤል ፡ አጋዥ ፡ ጠበቃ ፡ በመሆን ፡ ተገለጠ ፡ እስመ ፡ ዓለም ፡ መርድእ ፡ ለጻድቃን ፡ እንዲል ።

ርእየት ፡ ወአድለቅለቀት ፡ ምድር ።

ግብፅ ፡ ፈጽማ ፡ ተናወፀች ፡ ማለት ፡ ጓጉንቸር ፡ ተስቦ ፡ አስገኘች ፡ እን ድም ፡ ትሑታኑ ፡ ጠፉ ።

እንድም ፡ ቃለ ፡ ወሀቡ ፡ እስራኤል ፡ ኤርትራን ፡ ሲሻገሩ ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ ንሴብሖ ፡ ብለው ፡ አመሰገኑ ፡ እን ድም ፡ ዕቦሴቶቹ ፡ እስራኤል ፡ ሲሻ ገሩ ፡ ዕቦሴቶቹ ፡ እስራኤል ፡ ንሴብሖ ፡ ብለው ፡ አመሰገኑ ፡ ቃለ ፡ ነጐድጓ ድከ ፡ የሙሴ ፡ የአሮን ፡ የእስራኤ ልን ፡ ንሴብሖ ፡ ብሎ ፡ ማመስገን ፡ በግብፃውያን ፡ ስጥመት ፡ ነው ፡ (እስ ተርአየ)፡ የግብፃውያን ፡ ስጥመት ፡ ለ እስራኤል ፡ አጋዥ ፡ ጠበቃ ፡ በመሆን ፡ ተገለጸ ፡ ወመጽአት ፡ መቅሠፍት ፡ እንተ ፡ ኢተሐፅፅ ፡ እመብርቅት ፡ እን ዲል ፡ (ርእደት)፡ ኤርትራ ፡ ከሁለት ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለች ፡ እንድም ፡ ለእ ስራኤል ፡ እንደ ፡ ምድር ፡ ፀንታ ፡ የነ በረች ፡ ኤርትራ ፡ በግብፃውያን ፡ ፈረ ሰች ፡ እንድም ፡ ርእዩከ ፡ ማያት ፡ ማ ያት ፡ ዮርዳኖስ ፡ ዓዩህ ፡ ርእዩከ ፡ አይ ተውህም ፡ ፈሩ ፡ ደነገጹ ፡ ውህነት ፡ ያላቸው ፡ ወንዞች ፡ ደነገጹ ፡ ውህነታ ቸውም ፡ ጠፋ ፡ ነድ ፡ ለማየ ፡ ባሕር ፡ ከበበ ፡ ማይ ፡ ኅበ ፡ የሐውር ፡ ፀበበ ፡ ወጕየ ፡ ፃበእመት ፡ ወፈልሐ ፡ ከመ ፡ ዘእርሰንዎ ፡ በእሳት ፡ እንዲል ፡ ከባ ሕረ ፡ ዔው ፡ ኢላቃርም ፡ ድረስ ፡ ተገ ልጸ ፡ ታይቷል ፡ (ቃለ ፡ ወሀቡ)፡ እሒ ፃ ፡ ስሙዓትህ ፡ ሲነገሩ ፡ ይመናት ፡ ቃልን ፡ ሰጡ ፡ አብ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ብሎ ፡ ሲመሰክር ፡ ተሰም ቷል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ ወርዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ሲቀመ ጥ ፡ ታይቷልና ፡ (ቃለ፡ነጐድጓድከ)፡ አብ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ያለ ው ፡ ቃል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ መቀመጥ ፡ በሐ ዋርያት ፡ ቃል ፡ ተሰበከ ፡ (አስተርአየ)፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ብሎ ፡ አብ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ መቀ መጥ ፡ ለሐዋርያት ፡ ለሰብዓ ፡ አርድዕት ፡ አጋዥ ፡ ጠበቃ ፡ በመሆን ፡ ተገለጸ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ ያልተረታ ፡ መናፍቅ ፡ የለምና ፡ (ርእደት)፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ልበ ፡ መናፍ ቃን ፡ አይሁድ ፡ አጋንንት ፡ ጠፉ ።



፲፱ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ፍኖትከ ።

ጐዳናህ ፡ በኤርትራ ፡ ተገለጸ ፡ እን ድም ፡ ሕግህ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተነ ገረ ፡ (ዘጠኙ ፡ ሕጋጋት ፡ በዚህ ፡ ዓለ ም ፡ ተነገረ) ።

ወሣህርከኒ ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡ ብዙኅ ።

ፍለጋህ ፡ በኤርትራ ፡ ተገለጸ ፡ እን ድም ፡ ኢታምልክ ፡ እንድም ፡ ወን ጌል ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተነገረ ፡ ኢሳ ፡ ፵፫-፲፮ ።

ወኢይትዓወቅ ፡ ዓሠርከ ።

ዓሠረ ፡ ተአምራትህ ፡ ግን ፡ አይመ ረመርም ፡ ኖኅን ፡ በመርከብ ፡ አድኖ ፡ እስራኤልን ፡ በእግር ፡ ባያሻግር ፡ በመ ርከብ ፡ ማዳን ፡ እንጂ ፡ በእግር ፡ ማሻ ገር ፡ አይሆንለትም ፡ ባሉ ፡ ነበርና ፡ እስራኤልን ፡ በእግር ፡ አሻግሮ ፡ ኖኅ ን ፡ በመርከብ ፡ ባያድን ፡ በእግር ፡ ማሻገር ፡ እንጂ ፡ በመርከብ ፡ ማዳን ፡ አይሆንለትም ፡ ባሉ ፡ ነበርና ፡ ኖኅን ፡ በመርከብ ፡ አዳነህ ፡ እስራኤልን ፡ በእ ግር ፡ አሻገርህ ፡ በኪ.ንዒ ፡ ወዘእንበለ ፡ ኪ.ን ፡ ዓዲ ፡ አድኃንከ ፡ ሕዝበከ ፡ እስመ ፡ ኢትፈቅድ ፡ ዕሩዓ ፡ ትኩን ፡ በምግባሪከ ፡ እንዲል ።

እንድም ፡ ዓሠረ ፡ ባሕርይህ ፡ አይመ ረመርም ፡ ይወልደዋል ፡ አይቀድመ ውም ፡ ማለት ፡ ረቂቅ ፡ ነውና ።

፳ ፡ ወመራህኮሙ ፡ ከመ ፡ አባግዕ ፡ ለሕዝብከ ።

ወገኖችህ ፡ እስራኤልን ፡ እንደ ፡ አገ ር ፡ መንጋ ፡ ከባቢሎን ፡ መርተህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አወጣኻቸው ፡ እንድም ፡ ምዕመናንን ፡ ከሲኦል ፡ መርተህ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አወጣኻቸው ።

በእደ ፡ ሙሴ ፡ ወአሮን ።

በሙሴ ፡ በአሮን ፡ ምግብና ፡ ባልደ ረብነት ፡ ሥልጣን ፡ ቃል ፡ ሀሉኑ ፡ እዴሁ ፡ ለኢዮአብ ፡ እንዲል ።

## መዝሙር ፡ ፸፯ ።

፩ ፡ አፅምዑ ፡ ሕዝብየ ፡ ሕግየ ።

ተግሣፅ ፡ ለኵሉ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ምዕዳን ፡ ይባላል ፡ ወገኖቼ ፡ ምክሬን ፡ ትምርቴን ፡ ስሙ ፡ ይላል ፡ ዳዊት ፡ እንድም ፡ ጌታ ፡ በቊሙ ፡ ሕጌን ፡ ስሙ ፡ ይላል ።

ወዕልዉ ፡ እዝነክሙ ፡ ኀበ ፡ ቃለ ፡ አፉየ ።

በቃሌ ፡ ወደ ፡ ምነግራችኁም ፡ ነገ[illegible]ድ ፡ የነ[illegible]ግ ፡ ታ[illegible]ና ዕዝን ፡ ልቦናችሁን ፡ መልሳችኁ ፡ ስ ሙኝ ፡ ኢሳ ፡ ፳፰ ፡ ፳ ፡ ፫ ፡ ኢዩ ፡ ፭ ፡ ፩ ።

፪ ፡ እከሥት ፡ በምሳሌ ፡ አፉየ ።

ነገሬን ፡ በምሳሌ ፡ እገልጻለኁ ፡ እን ድም ፡ ወንጌልን ፡ በምሳሌ ፡ አስተ ምራለኁ ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፫ ፡ ፴፭ ።

ወእነግር ፡ እምላለ ፡ ዘእምትካት ።

ት ፡ ይውረድ ፡ ብለው ፡ አመለከቱ ፡ (ቃለ ፡ ነጐድጓድከ) ፡ እሳት ፡ ይውረድ ፡ በረድ ፡ ይዝነም ፡ ብለው ፡ መጸለያቸው ፡ በግብፃውያን ፡ ነው ፡ ሠረገላ ፡ ማደሪ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግብፃውያንም ፡ ቢያምኑበት ፡ ያድርባቸው ፡ ነበርና ፡ ሠረገላ ፡ አሏቸው ።

አስተርአየ ፡ መባርቅቲሁ ፡ ለዓለም ።

መብርቅተ ፡ መዓት ፡ ለእስራኤል ፡ አጋዥ ፡ ጠበቃ ፡ በመሆን ፡ ተገለጠ ፡ እስመ ፡ ዓለም ፡ መርድእ ፡ ለጻድቃን ፡ እንዲል ።

ርእደት ፡ ወአድለቅለቀት ፡ ምድር ።

ግብፅ ፡ ፈጽማ ፡ ተናወፀች ፡ ማለት ፡ ኋጉንቸር ፡ ተሰበ ፡ አስገኘች ፡ አንድም ፡ ትሑታኑ ፡ ጠፉ ።

አንድም ፡ ቃለ ፡ ወሀቡ ፡ እስራኤል ፡ ኤርትራን ፡ ሲሻገሩ ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ ንሴብሖ ፡ ብለው ፡ አመሰገኑ ፡ አንድም ፡ ዕነሴቶቹ ፡ እስራኤል ፡ ሲሻገሩ ፡ ዕዘሴቶቹ ፡ እስራኤል ፡ ንሴብሖ ፡ ብለው ፡ አመሰገኑ ፤ ቃለ ፡ ነጐድጓድከ ፡ የሙሴ ፡ የአሮን ፡ የእስራኤልን ፡ ንሴብሖ ፡ ብሎ ፡ ማመስገን ፡ በግብፃውያን ፡ ስጥመት ፡ ነው ፡ (አስተርአየ) ፡ የግብፃውያን ፡ ስጥመት ፡ ለእስራኤል ፡ አጋዥ ፡ ጠበቃ ፡ በመሆን ፡ ተገለጸ ፡ ወመጽአት ፡ መቅሠፍት ፡ እንተ ፡ ኢተሐፅዕ ፡ እመብርቅት ፡ እንዲል ፡ (ርእደት) ፡ ኤርትራ ፡ ከሁለት ፡

ከሦስት ፡ ተከፈለች ፡ አንድም ፡ ለእስራኤል ፡ እንደ ፡ ምድር ፡ ፀንታ ፡ የነበረች ፡ ኤርትራ ፡ በግብፃውያን ፡ ፈረሰች ፡ አንድም ፡ ርእዩከ ፡ ማያት ፡ ፈሪያት ፡ ዮርዳኖስ ፡ ዓዩህ ፡ ርእዩከ ፡ እይ ፡ ማተውህም ፡ ፈሩ ፡ ደነገጹ ፡ ውሀነት ፡ ያላቸው ፡ ወንዞች ፡ ደነገጹ ፡ ውሀነታቸውም ፡ ጠፋ ፡ ነድ ፡ ለማየ ፡ ባሕር ፡ ከበበ ፡ ማይ ፡ ኀበ ፡ የሐውር ፡ ዐበበ ፡ ወጕየ ፡ ፃበእመት ፡ ወፈለሐ ፡ ከመ ፡ ዘእርሰንም ፡ በእሳት ፡ እንዲል ፡ ከባሕረ ፡ ፄው ፡ ኢላታርም ፡ ድረስ ፡ ተገልጾ ፡ ታይቷል ፡ (ቃለ ፡ ወሀቡ) ፡ እሐፃ ፡ ስሙዓትህ ፡ ሲነገሩ ፡ ደመናት ፡ ቃልን ፡ ሰጡ ፡ አብ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ብሎ ፡ ሲመሰክር ፡ ተሰምቷል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ ወርዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥ ፡ ታይቷልና ፡ (ቃለ ፡ ነጐድጓድከ) ፡ አብ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ መቀመጥ ፡ በሐዋርያት ፡ ቃል ፡ ተሰበከ ፡ (አስተርአየ) ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ብሎ ፡ አብ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ መቀመጥ ፡ ለሐዋርያት ፡ ለሰብዓ ፡ አርድዕት ፡ አጋዥ ፡ ጠበቃ ፡ በመሆን ፡ ተገለጸ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ በለው ፡ ቃል ፡ ያልተረታ ፡ መናፍቅ ፡ የለምና ፡ (ርእደት) ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ልበ ፡ መናፍቃን ፡ አይሁድ ፡ አጋንንት ፡ ጠፉ ።



፲፱ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ፍኖትከ ።

ጐዳናህ ፡ በኤርትራ ፡ ተገለጸ ፡ አንድም ፡ ሕግህ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተነገረ ፡ (ዘጠኙ ፡ ሕገጋት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተነገረ) ።

ወሣዕርከኒ ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡ ብዙኅ ።

ፍለጋህ ፡ በኤርትራ ፡ ተገለጸ ፡ አንድም ፡ ኢታምልክ ፡ አንድም ፡ ወንጌል ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተነገረ ፡ ኢሳ ፡ ፃ፫-፲፯ ።

ወኢይትዓወቅ ፡ ዓሠርከ ።

ዓሠረ ፡ ተአምራትህ ፡ ግን ፡ አይመረመርም ፡ ኖኅን ፡ በመርከብ ፡ አድኖ ፡ እስራኤልን ፡ በእግር ፡ ባያሻግር ፡ በመርከብ ፡ ማዳን ፡ እንጂ ፡ በእግር ፡ ማሻገር ፡ አይሆንለትም ፡ ባሉ ፡ ነበርና ፡ እስራኤልን ፡ በእግር ፡ አሻግሮ ፡ ኖኅን ፡ በመርከብ ፡ ባያድን ፡ በእግር ፡ ማሻገር ፡ እንጂ ፡ በመርከብ ፡ ማዳን ፡

አይሆንለትም ፡ ባሉ ፡ ነበርና ፡ ኖኅን ፡ በመርከብ ፡ አዳንህ ፡ እስራኤልን ፡ በእግር ፡ አሻገርህ ፡ በኪንህ ፡ ወዘእንበለ ፡ ኪን ፡ ዓዲ ፡ አድኀንከ ፡ ሕዝበከ ፡ እስመ ፡ ኢትፈቅድ ፡ ዕሩዓ ፡ ትኩን ፡ በምግባሪከ ፡ እንዲል ።

አንድም ፡ ዓሠረ ፡ ባሕርይህ ፡ አይመረመርም ፡ ይወልደዋል ፡ አይቀድመውም ፡ ማለት ፡ ረቂቅ ፡ ነውና ።

፳ ፡ ወመራሕኮሙ ፡ ከመ ፡ አባግዕ ፡ ለሕዝብከ ።

ወገኖችህ ፡ እስራኤልን ፡ እንደ ፡ አገር ፡ መንጋ ፡ ከባቢሎን ፡ መርተህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አወጣኻቸው ፡ አንድም ፡ ምዕመናንን ፡ ከሲኦል ፡ መርተህ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አወጣኻቸው ።

በእደ ፡ ሙሴ ፡ ወአሮን ።

በሙሴ ፡ በአሮን ፡ ምግብና ፡ ባልደረብነት ፡ ሥልጣን ፡ ቃል ፡ ሀሎኑ ፡ እዴሁ ፡ ለኢዮአብ ፡ እንዲል ።

## መዝሙር ፡ ፸፰ ።

፩ ፡ አፅምዑ ፡ ሕዝብየ ፡ ሕግየ ።

ተግሣፅ ፡ ለኵሉ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ምዕዳን ፡ ይባላል ፡ ወገኖቼ ፡ ምክሬን ፡ ትምርቴን ፡ ስሙ ፡ ይላል ፡ ዳዊት ፡ አንድም ፡ ጌታ ፡ በቁሙ ፡ ሕጌን ፡ ስሙ ፡ ይላል ።

ወዕልዉ ፡ እዝነክሙ ፡ ኀበ ፡ ቃለ ፡ አፉየ ።

በቃሌ ፡ ወደ ፡ ምነግራችኁም ፡ ነገር ፡

ዕዝን ፡ ልቡናችሁን ፡ መልሳችኁ ፡ ስሙኝ ፤ ኢሳ ፡ ፳፰ ፡ ፳ ፡ ፫ ፡ ኢዩ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

፪ ፡ እከሥት ፡ በምሳሌ ፡ አፉየ ።

ነገሬን ፡ በምሳሌ ፡ እገልጸለኊ ፡ አንድም ፡ ወንጌልን ፡ በምሳሌ ፡ አስተምራለኊ ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፫ ፡ ፴፭ ።

ወእነግር ፡ አምሳለ ፡ ዘእምትካት ።

ከቀድሞ ፡ የነበረ ፡ ወግ ፡ ታሪክ ፡ እና

2014 04 17

ገራለት ፡ እንድም ፡ አስቀድሞ ፡ የተ
ሠራች ፡ ወንጌልን ፡ አስተምራለት
ና ፡ በመልክ ፡ ጺዲቅ ፡ ጊዜ ፡ ታይታ ፡
ጠፍታለችና ።

፫ ፡ ኵሎ ፡ ዘሰማዕነ ፡ ወዘርኢነ ፡ ኢሳ ፡ ፶ ፡ ፲ ።

የሚቀድመው ፡ አለ ።

ወዘነገሩነ ፡ አበዊነ ፡ ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ።

አስቀድሞ ፡ አባቶቻችን ፡ የነገሩንን ፡
እኛም ፡ በጆሮቻችን ፡ የሰማነውን ፡ ባይ
ናችን ፡ ያየነውን ፡ እናገራለኍና ።

፬ ፡ ወኢኀብኡ ፡ እምደቂቆሙ ፡ ለካልእ ፡ ትው
ልድ ።

ለሌላ ፡ ትውልድ ፡ ይኸን ፡ ዘንድ ፡
ከልጆቻቸው ፡ ያልሠወሩትን ፡ እን
ድም ፡ ለሳቸው ፡ ሁለተኛ ፡ ትውልድ ፡
ከሚሆኑ ፡ ከልጆቻቸው ፡ ያልሠወሩ
ትን ።

ወነገሩ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ጌትነቱን ፡ ነገሩ ፡
እንድም ፡ ዘነገሩ ፡ ያስተማሩት ፡ ጌት
ነቱን ፡ ተአምራቱን ፡ እነግራለኍና ።

ኃይሎሂ ፡ ወመንክረ ፡ ዘገብረ ።

ያደረገውን ፡ ከሃሊነቱን ፡ ተአምራ
ቱን ፡ እነግራለሁና ፡ ዘኁ ፡ ፳ ፡ ፳—፳ ፡
ምዕ ፡ ፲፱ ፡ ፲፰ ።

፭ ፡ ዘአቀመ ፡ ስምዐ ፡ ለያዕቆብ ።

ለሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ኢታምልክን ፡ ያፀ
ናላቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ያፀ
ናላቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘገብረ ፡

ያፀናላቸው ፡ ኢታምልክን ፡ እነግራ
ለኍና ።

ወመርሐ ፡ ሕገ ፡ ለእስራኤል ።

ላሥሩም ፡ ነገድ ፡ ዘጠኙን ፡ ሕገጋት ፡
የሠራላቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡
እንድም ፡ የሠራላቸው ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ዘገብረ ፡ እንድም ፡ የሠራላቸ
ው ፡ ዘጠኙን ፡ ሕገጋት ፡ እነግራኍና ።

ዘአዘዞሙ ፡ ለአበዊነ ።

ላባቶቻችን ፡ ያዘዛቸው ፡ ትእዛዙን ፡
እንድም ፡ ያዘዛቸው ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘገብረ ፡ እንድም ፡ ያዘዛቸውን ፡ ትእ
ዛዝ ፡ እነግራለኍና ።

ከመ ፡ ይንግሩ ፡ ለደቂቆሙ ።

ለልጆቻቸው ፡ ይነግሩ ፡ ዘንድ ።

፮ ፡ ወከመ ፡ ያእምር ፡ ካልእ ፡ ትውልድ ።

ሁለተኛ ፡ የሚነሳ ፡ ትውልድ ፡ ያውቅ ፡
ዘንድ ።

ደቂቅ ፡ እለ ፡ ይትወለዱ ፡ ወይትነሥኡ ።

ተወልደው ፡ ፪ኛ ፡ የሚነሱ ፡ ልጆች ።

ወይዜንውዎሙ ፡ ለደቂቆሙ ።

የገነፈለ ፡ ወ ፡ ነው ፡ ለልጆቻቸው ፡
ይነግሩ ፡ ዘንድ ፡ እሳቸው ፡ ለልጆቻ
ው ፡ ለልጆቻቸው ፡ ልጆቻቸው ፡ ለል
ጆ ፡ ልጆቻቸው ፡ ይነግሩ ፡ ያስተምሩ ፡
ዘንድ ፡ ዘዐ ፡ ፲ ፡ ፪ ፡ ኢያ ፡ ፬ ፡ ፫ ።

፯ ፡ ከመ ፡ ይረስዩ ፡ ትውክልቶሙ ፡ ላዕለ ፡ እግ
ዚአብሔር ።

እምነታታቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡
ላይ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ማለት ፡ ሁለ
ቱ ፡ ነገድ ፡ ኢታምልክን ፡ ይጠብቁ ፡
ዘንድ ።

ወከመ ፡ ኢይርስዕዎ ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔርንም ፡ ሥራ ፡ እንዳይ
ዘነጉ ፡ ማለት ፡ ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ ዘጠ
ኙን ፡ ሕጋጋት ፡ እንዳይዘነጉ ።

ወይኅሥሡ ፡ ትእዛዞ ።

ወነበበ ፡ ያለውን ፡ ቃሉን ፡ ይሹ ፡
ዘንድ ።

፰ ፡ ከመ ፡ ኢይኩኑ ፡ ከመ ፡ አበዊሆሙ ።

እሳቸውም ፡ እንዳባቶቻቸው ፡ እን
ዳይሆኑ ።

ትውልድ ፡ ዐሳቲ ፡ ወመራሪ ።

ከዳተኛ ፡ ሰውን ፡ እግዚአብሔርን ፡
የምታሳዝን ፡ ትውልድ ።

ትውልድ ፡ እንተ ፡ ኢያርትዐት ፡ ልባ ።

ልቡናዋን ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ያላቀናች ፡ ኢሳ ፡ ፴ ፡ ፲ ።

ወኢተአመነት ፡ መንፈሳ ፡ በእግዚአብሔር ።

ልቡናዋ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያላመነ
ች ፡ እንድም ፡ (ኢያአመነት) ፡ ይላል ፡
ልቡናዋን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያላሳ
መነች ።

፱ ፡ ደቂቀ ፡ ኤፍሬም ፡ ይሰድቁ ፡ ወይነድፉ ።

መላው ፡ እስራኤል ፡ ቀስታቸውን ፡
እየቀፈሩ ፡ እየነደፉ ፡ ይጥሉ ፡ ነበር ፡
ማለት ፡ ኃይላቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡
እንድም ፡ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ቀስ
ታቸውን ፡ እየቀፈሩ ፡ እየወጉ ፡ ይጥ
ሉ ፡ ነበር ።

ወተገፍትኡ ፡ አመ ፡ ዕለተ ፡ ቀትል ።

ነገር ፡ ግን ፡ አልተጠቀሙም ፡ በሰል
ፍ ፡ ቀን ፡ ድል ፡ ተነሡ ፡ ማለት ፡ ኃይ
ላቸው ፡ አላዳናቸውም ።

፲ ፡ እስመ ፡ ኢዐቀቡ ፡ ሕገ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ሕጉን ፡ አልጠበቁምና ።

ወአበዩ ፡ ሖሪረ ፡ በሕጉ ፡ ኤር ፡ ፴፪ ፡ ፳፫ ።

በሕጉም ፡ ፀንተው ፡ አልኖሩምና ፡
እንድም ፡ በደመናው ፡ ፀንተው ፡ አ
ልኖሩምና ፡ ወግዕዙ ፡ እስራኤል ፡
በሕገ ፡ ደመና ፡ እንዲል ፡ ታሪክ ፡
ሙሴ ፡ ከሥሩ ፡ ነገድ ፡ አሥር ፡ ሰው ፡
መርጦ ፡ ኢያሱና ፡ ካሌብን ፡ አለቃ ፡
አድርጎ ፡ ምድረ ፡ ርስትን ፡ ሰልላችኍ ፡
ኍ ፡ ብሎ ፡ ሰደዳቸው ፡ ደጋውን ፡ ቈ
ላውን ፡ ሰልለው ፡ ከወይኑ ፡ ዘለላ ፡
ከሥንዴው ፡ ዛላ ፡ በባጢ ፡ ቆር ፡
ይዘው ፡ መጡ ፡ ከመንገድ ፡ አሥሩ ፡
እንገባም ፡ ብለዋል ፡ ኢያሱና ፡ ካ
ሌብ ፡ እንገባለን ፡ ብለዋል ፡ ኋላ ፡
ሙሴ ፡ ከለበት ፡ ደረሱ ፡ እንደምን ፡
ሁናችኍ ፡ መጣችኍ ፡ ሀገሪቱስ ፡ እን
ደምን ፡ ያለች ፡ ናት ፡ ብለው ፡ ጠየቋ
ቸው ፡ ሀገርሰ ፡ ሀገር ፡ ይእቲ ፡ ሀገሪ
ቱም ፡ ሀገር ፡ አትመስል ፡ የወይኑ ፡
ዘለላ ፡ ጋን ፡ ይመላ ፡ የሥንዴው ፡

ገራለት ፡ እንድም ፡ አስቀድማ ፡ የተ
ወራች ፡ ወንጌልን ፡ አስተምራለት
ና ፡ በመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ጊዜ ፡ ታይታ ፡
ጠፍታለችና ።

፫ ፡ ኵሎ ፡ ዘሰማዕነ ፡ ወዘርኢነ ፡ ኤሬ ፡ ፯ ፡ ፱ ።

የሚቀድመው ፡ አለ ።

ወዘነገሩነ ፡ አበዊነ ፡ ቈላ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ።

አስቀድሞ ፡ አባቶቻችን ፡ የነገሩንን ፡
እኛም ፡ በጆሮቻችን ፡ የሰማነውን ፡ በይ
ናችን ፡ ያየነውን ፡ እናገራለትና ።

፬ ፡ ወኢኀብኡ ፡ እምደቂቆሙ ፡ ለካልዕ ፡ ትውልድ ።

ለሌላ ፡ ትውልድ ፡ ይኸን ፡ ዘንድ ፡
ከልጆቻቸው ፡ ያልሠወሩትን ፤ እን
ድም ፡ ለሳቸው ፡ ሁለተኛ ፡ ትውልድ ፡
ከሚሆኑ ፡ ከልጆቻቸው ፡ ያልሠወሩ
ትን ።

ወነገሩ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ጌትነቱን ፡ ነገሩ ፤
እንድም ፡ ዘነገሩ ፡ ያስተማሩት ፡ ጌት
ነቱን ፡ ተአምራቱን ፡ እንነግራለትና ።

ኃይሎሂ ፡ ወመንክሮሂ ፡ ዘገብረ ።

ያደረገውን ፡ ከሃሊነቱን ፡ ተአምራ
ቱን ፡ እነግራለሁና ፡ ዘፋ ፡ ፯ ፡ ፯—፰ ፡
ምሳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፰ ።

፭ ፡ ዘአቀመ ፡ ስምዐ ፡ ለያዕቆብ ።

ለሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ኢታምልከን ፡ ያፀ
ናላቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ያፀ
ናላቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘገብረ ፡
ያፀናላቸው ፡ ኢታምልከን ፡ እነግረ
ለጉና ።

ወሠርዐ ፡ ሕገ ፡ ለእስራኤል ።

ላሥሩም ፡ ነገድ ፡ ዘጠኙን ፡ ሕጋጋት ፡
የሠራላቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡
እንድም ፡ የሠራላቸው ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ዘገብረ ፡ እንድም ፡ የሠራላቸ
ው ፡ ዘጠኙን ፡ ሕጋጋት ፡ እነግራጉና ።

ዘአዘዞሙ ፡ ለአበዊነ ።

ላባቶቻችን ፡ ያዘዛቸው ፡ ትእዛዙን ፡
እንድም ፡ ያዘዛቸው ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘገብረ ፡ እንድም ፡ ያዘዛቸውን ፡ ትእ
ዛዝ ፡ እነግራለጉና ።

ከመ ፡ ይንግሩ ፡ ለደቂቆሙ ።

ለልጆቻቸው ፡ ይነግሩ ፡ ዘንድ ።

፮ ፡ ወከመ ፡ ያእምር ፡ ካልዕ ፡ ትውልድ ።

ሁለተኛ ፡ የሚነሳ ፡ ትውልድ ፡ ያውቅ ፡
ዘንድ ።

ደቂቅ ፡ እለ ፡ ይትወለዱ ፡ ወይትነሥኡ ።

ተወልደው ፡ ፪ኛ ፡ የሚነሱ ፡ ልጆች ።

ወይዜንዉ ፡ ለቂቆሙ ።

የገነፈለ ፡ ወ ፡ ነው ፡ ለልጆቻቸው ፡
ይነግሩ ፡ ዘንድ ፡ እሳቸው ፡ ለልጆቻ
ው ፡ ለልጆቻቸው ፡ ልጆቻቸው ፡ ለል
ጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ይነግሩ ፡ ያስተምሩ ፡
ዘንድ ፡ ዘዐ ፡ ፲ ፡ ፪ ፡ ኢዮ ፡ ፩ ፡ ፫ ።

፯ ፡ ከመ ፡ ይረስዩ ፡ ትውክልቶሙ ፡ ላዕለ ፡ እግ
ዚአብሔር ።

እምነታታቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡



ላይ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ማለት ፡ ሁለ
ቱ ፡ ነገድ ፡ ኢታምልከን ፡ ይጠብቁ ፡
ዘንድ ።

ወኢይረስዑ ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔርንም ፡ ሥራ ፡ እንዳይ
ዘነጉ ፡ ማለት ፡ ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ ዘጠ
ኙን ፡ ሕጋጋት ፡ እንዳይዘነጉ ።

ወይሕሥሡ ፡ ትእዛዞ ።

ወነበበ ፡ ያለውን ፡ ቃሉን ፡ ይሹ ፡
ዘንድ ።

፰ ፡ ከመ ፡ ኢይኩኑ ፡ ከመ ፡ አበዊሆሙ ።

እሳቸውም ፡ እንዳባቶቻቸው ፡ እን
ዳይሆኑ ።

ትውልድ ፡ ዕሉት ፡ ወመሪር ።

ከዳተኛ ፡ ሰውን ፡ እግዚአብሔርን ፡
የምታሳዝን ፡ ትውልድ ።

ትውልድ ፡ እንተ ፡ ኢያርትዓት ፡ ልባ ።

ልቡናዋን ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ያላቀናች ፡ ኢሳ ፡ ፴ ፡ ፱ ።

ወኢተአመነት ፡ መንፈሳ ፡ በእግዚአሔር ።

ልቡናዋ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያላመነ
ች ፡ እንድም ፡ (ኢያእመነት) ፡ ይላል ፡
ልቡናዋን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያላሳ
መነች ።

፱ ፡ ደቂቀ ፡ ኤፍሬም ፡ ይወስቁ ፡ ወይነድፉ ።

መላው ፡ እስራኤል ፡ ቀስታቸውን ፡
እየቀፈሩ ፡ እየነደፉ ፡ ይጥሉ ፡ ነበር ፡
ማለት ፡ ኃይላቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡
እንድም ፡ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ቀስ
ታቸውን ፡ እየቀፈሩ ፡ እየወጉ ፡ ይጥ
ሉ ፡ ነበር ።

ወተገፍትዑ ፡ አመ ፡ ዕለተ ፡ ቀትል ።

ነገር ፡ ግን ፡ አልተጠቀሙም ፡ በሰል
ፍ ፡ ቀን ፡ ድል ፡ ተነሡ ፡ ማለት ፡ ኃይ
ላቸው ፡ አላዳናቸውም ።

፲ ፡ እስመ ፡ ኢዐቀቡ ፡ ሕጎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ሕጉን ፡ አልጠበቁምና ።

ወአበዩ ፡ ሐዊረ ፡ በሕጉ ፡ ኤር ፡ ፵፬ ፡ ፳፫ ።

በሕጉም ፡ ፀንተው ፡ አልኖሩምና ፤
እንድም ፡ በደመናው ፡ ፀንተው ፡ አ
ልኖሩምና ፤ ወግዕዙ ፡ እስራኤል ፡
በሕገ ፡ ደመና ፡ እንዲል ፡ ታሪክ ፡
ሙሴ ፡ ከሥሩ ፡ ነገድ ፡ አሥር ፡ ሰው ፡
መርጦ ፡ ኢያሱና ፡ ከሌብን ፡ አለቃ ፡
አድርጎ ፡ ምድረ ፡ ርስትን ፡ ሰልላችሁ ፡
ኑ ፡ ብሎ ፡ ሰደዳቸው ፡ ደጋውን ፡ ቈ
ላውን ፡ ሰልለው ፡ ከወይኑ ፡ ዘለላ ፡
ከሥንዴው ፡ ዛላ ፡ በባጢ ፡ ቀፎ ፡
ይዘው ፡ መጡ ፡ ከመንገድ ፡ አሥሩ ፡
እንገባም ፡ ብለዋል ፤ ኢያሱና ፡ ከ
ሌብ ፡ እንገባለን ፡ ብለዋል ፤ ኋላ ፡
ሙሴ ፡ ከለበት ፡ ደረሱ ፤ እንደምን ፡
ሁናችሁ ፡ መጣችሁ ፡ ሀገሪቱስ ፡ እን
ደምን ፡ ያለች ፡ ናት ፡ ብለው ፡ ጠየቋ
ቸው ፡ ሀገርስ ፡ ሀገር ፡ ይእቲ ፡ ሀገሬ
ቱም ፡ ሀገር ፡ አትመስል ፡ የወይኑ ፡
ዘለ[illegible] ፡ [illegible] ፡ ይ[illegible] ፡ [illegible]ሥንዴው

2014 04 17

ዛላ ፡ እፍኝ ፡ ይመላ ፡ ባሕቱ ፡ ርዒን
ትውልዶ ፡ ለዒናቅ ፡ ኑሆሙ ፡ ከመ ፡
ዘግባ ፡ ወዕንዖሙ ፡ ከመ ፡ አውልዕ ፡
ምድርኒ ፡ ትረድእሙ ፡ ወተአቅበሙ ፡
ሰዎቹም ፡ ኀያላን ፡ ናቸው ፡ ሀገሪቱም ፡
አታስደፍራቸውም ፡ ብለው ፡ ዓሥሩ ፡
አስፈርተው ፡ አስገርመው ፡ ተናገሩ ፡
ኢያሱና ፡ ካሌብ ፡ ግን ፡ በፈቃደ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንገባለን ፡ ብለዋል ፡
ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ ያሥሩን ፡ ሰምተው ፡
አንገባም ፡ አሉ ፡ ሙሴ ፡ ሰምቶ ፡ እንገ
ባለን ፡ አለ ፡ እንገባለንስ ፡ ካላችኁ ፡
ሙሴ ፡ ይነሣ ፡ ታቦቱ ፡ ጽዮንም ፡ ት
ነሣ ፡ አሉ ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ ኢያ
ሱና ፡ ካሌብም ፡ ቢሉ ፡ ጊዜውም ፡
አይደለ ፡ ብለው ፡ ወድቀው ፡ ማለዱ
ቸው ፡ አይሆንም ፡ ብለው ፡ ተጋፍ
ተው ፡ ሔዱ ፡ በዳር ፡ በዳር ፡ ያሉ ፡
ሰዎች ፡ ገጠሟቸው ፡ ድል ፡ አድር
ገው ፡ ሰድደዋቸዋል ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡
ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከገደል ፡ ወድቀው ፡
ከባሕር ፡ ጠልቀው ፡ አልቀዋል ፡ ወ
ዲያውም ፡ ሙሴ ፡ ኢታመክሮ ፡ ለእ
ግዚአብሔ ፡ አምላክክ ፡ ብሎ ፡ በአ
ሪት ፡ ጽፎታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

፲፰፡ ወረሥሙ ፡ ረድኤቶ ።

የተደረገላቸውን ፡ እንድም ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ያደረገላቸውን ፡ ረድኤ
ቱን ፡ ዘንግተዋልና ፡ ታሪክ ፡ ዮፍ
ታሔ ፡ ትውልዱ ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡
ካልገቡት ፡ ከመንፈቀ ፡ ነገድ ፡ ምናሴ ፡
ነው ፡ ወንድሞቹ ፡ የዘማ ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡
ከኛ ፡ ጋራ ፡ ርስት ፡ መውረስ ፡ አይገ
ባህም ፡ ብለው ፡ አባርረው ፡ ሰደዱት ፡
የናቱ ፡ አገር ፡ ግፍ ፡ ትባላለች ፡ ከዚ
ያች ፡ ሔዶ ፡ ኀያል ፡ ነውና ፡ ሰባ ፡ ያህል ፡
በለድ ፡ አስከትሎ ፡ ይኖራል ፡ ንጉሠ ፡
ሞዓብ ፡ ምድሬን ፡ መልሱልኝ ፡ ብሎ ፡
ወደ ፡ እስራኤል ፡ ላከባቸው ፡ ይህ ፡
ኁሉ ፡ መሆኑ ፡ መስፍን ፡ ባይኖረን ፡
ንቆን ፡ አጥቅቶን ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ቢስ ፡
የቢስ ፡ ቀን ፡ ክፉ ፡ የክፉ ፡ ቀን ፡ እን
ዲሉ ፡ ዮፍታሔን ፡ መስፍናውን ፡
እንሰጥሃለን ፡ ብላችኁ ፡ ሔዳችኁ ፡
ይዛችኁት ፡ ኑ ፡ ብለው ፡ ሰዎች ፡ ላኩ ፡
ቀድሞ ፡ ጠልታችኁ ፡ አባረራችኁኝ ፡
አሁን ፡ ለምን ፡ መጣችሁብኝ ፡ ወግዱ
ልኝ ፡ አላቸው ፡ ይልቁንስ ፡ የምንነግ
ርህን ፡ ስማን ፡ አሉት ፡ ምስፍናውን ፡
ልትሰጡኝ ፡ ማሉልኝ ፡ አላቸው ፡
እኛስ ፡ ለምን ፡ መጥተናል ፡ አሉት ፡
ተነሥቶ ፡ ሔዶ ፡ እሥራኤል ፡ ከግ
ብፅ ፡ ከወጡ ፡ ዓሪት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡
ሁኗል ፡ ባሪት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ም
ድር ፡ ተገኝቶ ፡ ምድሬን ፡ መልሱ
ልኝ ፡ ትላለህ ፡ እንደ ፡ ሌላ ፡ የተበ
ደልከው ፡ በደል ፡ እንዳለ ፡ ንገረን ፡
አሉት ፡ አባታችኁ ፡ ሰባቱ ፡ ወስዷል ፡
አላቸው ፡ የኛ ፡ አባት ፡ ከንተ ፡ አባት ፡
አልወሰደም ፡ ከንተ ፡ አባት ፡ ንጉሠ ፡
አሞሬዎን ፡ ወስዷል ፡ ከንጉሠ ፡ አሞ
ሬዎን ፡ የኛ ፡ አባት ፡ ወስዷል ፡ አሉት ፡
አይሆንም ፡ መልሱልኝ ፡ አላቸው ፡



እንኪያስ ፡ አምላክህ ፡ ከሞስ ፡ ያወ
ረሰህን ፡ ትወርሳለህ ፡ እኛም ፡ አምላ
ካችን ፡ ያወረሰንን ፡ እንወርሳለን ፡
ብሎ ፡ ዘመተ ፡ ድል ፡ አድርጌ ፡ የተ
መለስኁ ፡ እንደሆነ ፡ መጀመርያ ፡ የ
ተቀበለኝን ፡ እሠዋልሃለኁ ፡ ብሎ ፡
ተሣለ ፡ እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ዮፍታሔ ፡
መጣ ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ ሊቀበለው ፡
የሚሔድ ፡ ለማዳ ፡ በግ ፡ ነበረው ፡
ያን ፡ እሠዋልሃለኁ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ድል ፡
አድርጎ ፡ ሲመለስ ፡ ደቂቀ ፡ ኤፍሬም ፡
ከመንገድ ፡ ቈይተው ፡ ምነው ፡ ዘም
ተህ ፡ ጠላቶችህን ፡ ስታጠፋ ፡ ሳትነ
ግረን ፡ አሉት ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ ከተት ፡
ሠራዊት ፡ ምታ ፡ ነጋሪት ፡ ብዬ ፡ አ
ዋጅ ፡ ነግሬ ፡ ዘመትኁ ፡ አላቸው ፡
አንተ ፡ ግዳይ ፡ ትወዳለህና ፡ ነው ፡ እ
ንጂ ፡ አለመንገርህ ፡ መቼስ ፡ ምን ፡
እናደርገለን ፡ ማርካችኁ ፡ ያመጣች
ሁትን ፡ ገንዘብ ፡ አካፍሉን ፡ አሏቸው ፡
እኛ ፡ እግራችንን ፡ ለጠጠር ፡ ደረታ
ችንን ፡ ለጦር ፡ ሰጥተን ፡ ያመጣነ
ውን ፡ ልናካፍላችኁ ፡ አይሆንም ፡
አሉ ፡ ገጠሙ ፡ ድል ፡ አርጓቸዋል ፡
ሁሉም ፡ እስራኤል ፡ ናቸውና ፡ የማ
ይለዩ ፡ ኸኑ ፡ ደቂቀ ፡ ኤፍሬም ፡ የጸ ፡
ጻያፍ ፡ ነበረባቸው ፡ በሉ ፡ መምሕጻን ፡
ይላቸዋል ፡ ለባብ ፡ ለገደል ፡ ይስጠን ፡
ማለት ፡ ነው ፡ በሉ ፡ መምሕሳን ፡ ይላሉ ፡
በሉ ፡ ሽሆሊት ፡ ይላቸዋል ፡ ወዐበዩ ፡
ብሂለ ፡ ሽሆሊት ፡ ይላል ፡ ሽሆሊት ፡
ማለት ፡ ተሳናቸው ፡ በዚህ ፡ ምክን
ያት ፡ ለይቶ ፡ አጥፍቷቸዋል ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንዲት ፡ ድንግል ፡
መልክ ፡ መልካም ፡ ልጅ ፡ ነበረችው ፡
አባትሽ ፡ እንጂ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡
መጣ ፡ አሏት ፡ ባልንጀሮቿን ፡ ሰብ
ስባ ፡ አታሞ ፡ እየመታች ፡ ተቀበለ
ችው ፡ ከፈረስ ፡ ከሠረገላ ፡ ወርዶ ፡
ልብሱን ፡ ቀድዶ ፡ ለምንት ፡ ከመዝ ፡
አዕቀዕክኒ ፡ ወለትየ ፡ ልጄ ፡ ምነው ፡
እንዲህ ፡ አሰነካከልሽኝ ፡ አላት ፡ ም
ነው ፡ አለችው ፡ ስዘምት ፡ መጀመ
ሪያ ፡ የሚቀበለኝን ፡ እሠዋልኻለሁ ፡
ብዬ ፡ ተስፋዬ ፡ ነበረ ፡ እንዳልሰዋሽ ፡
ልጄ ፡ ነሽ ፡ እሳዘንሽኝ ፡ እንዳልተው
ሽም ፡ መሐላ ፡ የሚፋረስብኝ ፡ ኾነ ፡
አላት ፡ ስንኳን ፡ የሔድኽበት ፡ የቀ
ናህ ፡ እንጂ ፡ ይኸስ ፡ አይጎዳም ፡ የተ
ሳልከውን ፡ አድርግ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለ
ድንግልናዬ ፡ የማለቅስበት ፡ ቀን ፡ ስ
ጠኝ ፡ አለችው ፡ ለሁት ፡ ወር ፡ ሰጣት ፡
ቀን ፡ ባልንጀሮቿን ፡ ሰብስባ ፡ ከተ
ራራ ፡ ላይ ፡ ወጥታ ፡ ስታለቅስ ፡ ትው
ላለች ፡ ሲመሽ ፡ ከቤቷ ፡ ገብታ ፡ ታ
ድራለች ፡ ከሁለት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ሠው
ቷታል ፡ ጌታም ፡ እንደተቀበለለት ፡
ለማጠየቅ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወረዶ ፡
በልቶለታል ፡ መሳ ፡ ፲፩ ፡ ፩-፱ ።
ወመንክሮሂ ፡ ዘአርአዮሙ ።
ያደረገላቸውን ፡ ተአምራትንም ፡ ዘን
ግተዋል ።

2014 04 17

፲፪፡ ዘገብረ፡ መንክረ፡ በቅድመ፡ አበዊሆሙ።

በገቶቻቸው፡ ፊት፡ ያደረገውን፡ ተአምራቱን፡ ዘንግተዋልና።

በምድረ፡ ግብፅ፡ ወበሐቅለ፡ ጣኔዎስ።

በግብፅ፡ አገር፡ ጣኔዎስ፡ በሚባል፡ በረኀ፤ አንድም፡ በጣኔዎስ፡ ፈርዖን፡ አገር።

፲፫፡ ሰጠቀ፡ ባሕረ፡ ወአኅለፎሙ።

ዘገብረ፡ ተአምረ፡ በግብፅ፡ ብሎ፡ እስኪያመጣው፡ ድረስ፡ ሌላ፡ አገባብ፡ ባሕር፡ ከፍሎ፡ አሻገራቸው።

ወአቀመ፡ ማየ፡ ከመ፡ ዝቅ።

ወሀውንም፡ እንደ፡ ራዋት፡ ወሀ፡ ወሰነላቸው።

፲፬፡ መርሆሙ፡ መዓልተ፡ በደመና።

የዳዊት፡ እኩሌታ፡ ከዚህ፡ ነው፤ በመዓልት፡ በደመና፡ መርቶ፡ አወጣቸው፤ ሰባት፡ ደመና፡ ታዝዞላቸው፡ ነበር፤ አንዱ፡ ደመና፡ ከላይ፡ ዋዕየ፡ ፀሐይ፡ እንዳያገኛቸው፡ ይጋርድላቸዋል፤ አንዱ፡ ከታች፡ እሾህ፡ እንቅፋት፡ እንዳያገኛቸው፡ እንደሸማ፡ ይጐዘጐዝላቸዋል፤ አንዱ፡ በቀኝ፡ አንዱ፡ በግራ፤ አንዱ፡ በፊት፡ አንዱ፡ በኋላ፡ ይጋረድላቸዋል፤ አንዱ፡ የሁለት፡ የሦስት፡ ቀን፡ ጎዳና፡ እየሔደ፡ መንገድ፡ ይጠርግላቸዋል፤ ማታም፡ ከደብተራ፡ አሪት፡ ሁኖ፡ ሲያበራላቸው፡ ያድር፡ ነበር።

ወኵሎ፡ ሌሊተ፡ በብርሃነ፡ እሳት።

በሌሊትም፡ በብርሃን፡ እሳት፡ ይመራቸው፡ ነበር፤ ዘፀ፡ ፲፫፡ ፳፩-፳፪፤

፲፭፡ አንቅዐ፡ ኰኵሐ፡ በበድው።

በበረኃ፡ ሳሉ፡ ወሀ፡ ከጭንጫ፡ አፈለቀላቸው፤

ወአስተዮሙ፡ ከመ፡ ዘእምቀላይ፡ ብዙኅ።

ሥፉሕ፡ ሲል፡ ነው፤ እንደ፡ ጣና፡ እንደ፡ ምጽዋ፡ አብዝቶ፡ አጠጣቸው። ኢሳ፡ ፵፰፡ ፳፩።

፲፮፡ ወአውኀዘ፡ ማየ፡ ከመ፡ ዘእምአፍላግ፤

እንደ፡ ዐባይ፡ እንደ፡ በሽሎ፡ አድርጎ፡ አፈሰሰላቸው።

ወአውፅአ፡ ማየ፡ እምእብን።

ወሀ፡ ከጭንጫ፡ አፈለቀላቸው።

፲፯፡ ደገሙ፡ ኣበሱ፡ አብሶ፡ ሎቱ።

ይኸውም፡ ይህ፡ ነው፤ ከዚህ፡ ጋራ፡ እሱን፡ መበደልን፡ ደገሙ፤ አንድም፡ ደገሙ፡ ዓዲ፡ ዳግመኛ፡ በደሉ።

ወአበሱ፡ ሎቱ፤

እሱንም፡ በደሉት።

ወአምረርዎ፡ ለልዑል፡ በበድው፤

ልዑል፡ እግዚአብሔርንም፡ በበረኃ፡ ሳሉ፡ አሳዘኑት።

፲፰፡ ወአመከርዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ በልቦሙ።

እግዚአብሔርን፡ በልባቸው፡ አስበው፡ በቃላቸው፡ ተፈታተኑት።



ከመ፡ ይስአሉ፡ መብልዐ፡ ለነፍሶሙ።

ለሰውነታቸው፡ ምግብን፡ መለመን፡ ሲያሻቸው፡ ገና፡ ሳይለምኑት፤ ኢሳ፡ ፳፱፡ ፲።

፲፱፡ ሐመይዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወይቤሉ።

እግዚአብሔርን፡ እንዲህ፡ ብለው፡ አሙት፤ ምን፡ አሉት።

ይክልኑ፡ እግዚአብሔር፡ ሠሪዐ፡ ማዕድ፡ በገዳም።

ሠሪዓ፡ ማዕደም፤ ይላል፡ ከዚህ፡ ከደጋ፡ ሰማይ፡ ዝቅ፤ ምድር፡ ብቅ፡ ቢል፡ ውርጭ፡ አይታጣምና፡ ያን፡ እያረጋ፡ መና፡ ከደመና፡ አወረድኰላችኍ፡ ይለናል፡ እንጂ፡ በበረኃማ፡ ሲሆን፡ ማዕድ፡ ሠርቶ፡ መስጠት፡ ይቻለዋልን፡ አሉት።

፳፡ ይዘብጥ፡ ኰኵሐ፡ ወያውሕዝ፡ ማየ።

ከደጋ፡ ምንጭ፤ ከወንዝ፡ ደንገያ፡ አይታጣምና፡ ወሀ፡ ከጭንጫ፡ አፈለቅኍላችኍ፡ ይለናል፡ እንጂ፤ ከበረኃማ፡ ቢሆን፡ ወሀ፡ አፍልቶ፡ መመገብ፡ ይቻለዋልን፡ አሉ።

ወይክልኑ፡ ውሂበ፡ ኅብስት።

ኅብስት፡ መስጠት፡ ይቻለዋልን፡ አሉ።

ወይሥራዕ፡ ማዕደ፡ ለሕዝቡ።

ለወገኖቹ፡ ማዕድ፡ ሠርቶ፡ መስጠት፡ ይቻለዋልን፡ አሉት።

፳፩፡ ወሰምዐ፡ ዘንተ፡ እግዚአብሔር፡ ወአናሕሰየ።

እግዚአብሔርም፡ ይህን፡ ሰምቶ፡ ናቃቸው፡ አቀለላቸው፤ ለወርቅ፡ ዝርግፍ፡ ያሉት፡ እንጉት፡ ላሽከት፡ እንዲሉ፤ ለክህነት፡ ለመንግሥት፡ እንኳቸው፡ እስራኤል፡ እንዲህን፡ ኾኑ፡ ብሎ፤ አንድም፡ (እንኳ፡ ሰየ)፡ ይላል፤ ጸብን፡ አበዛ።

ወነደ፡ እሳት፡ ላዕለ፡ ያዕቆብ።

በያዕቆብ፡ ላይ፡ እሳት፡ ነደደ፡ ማለት፡ መቅሠፍት፡ ታዘዘ፤ ሉቃ፡ ፱፡ ፶፬-፶፮።

ወመጽአ፡ መቅሠፍት፡ ላዕለ፡ እስራኤል፤

ነደ፡ ያለውን፡ መጽአ፡ እሳት፡ ያለውን፡ መቅሠፍት፡ ያዕቆብ፡ ያለውን፡ እስራኤል፡ ብሎ፡ ገለጸው፤ አንድም፡ በቁሙ፡ ወበልዐ፡ ፩፡ ኅብረ፡ ይላል፤ ከበረኃ፡ እሳት፡ ተነሥቶ፡ በየነገዳቸው፡ ተሰልፈው፡ ሲሔዱ፡ አንዱን፡ ኅብር፡ አስቀርቶታልና፡ እንዲህ፡ አለ፤ በእስራኤል፡ መቅሠፍት፡ ታዘዘባቸው፤ ዘኍ፡ ፲፩፡ ፩።

፳፪፡ እስመ፡ ኢተአምንዎ፡ ለእግዚአብሔር።

እግዚአብሔርን፡ አላመኑትምና።

ወኢተወከሉ፡ በአድኅኖቱ።

በትድግናውም፡ አላኑምና።

፳፫፡ ወአዘዘ፡ ደመና፡ በላዕሉ።

ከምድር፡ በላይ፡ ያለ፡ ደመናን፡ አዘዘ፤ እርኃው፡ የሚል፡ ነውና።

ወአርኀወ፡ ኆኃተ፡ ሰማይ።

የሰማ... ከፈተ፡ አዘ...

2014 04 17

ማይ ፣ መክፈት ፣ መዘጋት ፣ ኑሮበት ፣ አይደለም ፤ አዝነመ ፣ ብሎ ፣ የሚያ መጣ ፣ ነውና ።

፳፬ ፤ ወአዝነመ ፣ ሎሙ ፣ መና ፣ ይብልዑ ።

አዝነመ ፣ መና ፣ ይብልዑ ፣ መና ፣ ብለህ ፣ ግጠም ፤ መና ፣ ይበልዑ ፣ ዘንድ ፣ መናውን ፣ አዘነመላቸው ፤ ዘፀ ፣ ፲፮ ፣ ፲፫-፲፬ ።

ወወሀቦሙ ፣ ኅብስተ ፣ ሰማይ ።

ከሰማይ ፣ የወረደውን ፣ ኅብስት ፣ ሰጣቸው ፣ አሁን ፣ በሰማይ ፣ አበዛ ፤ እንጀራ ፣ ኑሮ ፣ አይደለም ፣ ከወደ ፤ ላይ ፤ ስለወረደ ፤ ወእንዘ ፣ የኀድግ ፤ ሀበ ፤ ይላል ፣ የውርጭ ፣ ገበታ ፤ ይዘረጋላቸዋል ፣ አመድ ፣ ትብያ ፣ ይዞ ፤ እንዳይነግ ፤ ነው ፤ ወርዕየቱ ፣ ከመ ፣ ተቅዳ ፣ ይላል ፤ መልኩ ፣ በረድ ፣ መስሎ ፤ አክሉ ፣ ድንብላል ፤ አህሎ ፣ ይዘንምላቸው ፣ ነበር ፤ ከሥጋ ፣ በቀር ፤ ያሉትን ፤ ሁሉ ፣ ይሆንላቸዋል ፤ ይፈጩታል ፤ ይቂሉታል ፤ መንከከ ፤ ያደርጉታል ። ዮሐ ፣ ፯ ፣ ፴፫ ።

፳፭ ፤ ወኅብስተ ፣ መላእክቲሁ ፣ በልዑ ፣ እጓለ ፣ እመሕው ።

በመላእክት ፣ እጅ ፤ የወረደውን ፤ እንጀራ ፤ አንድም ፣ ያለቆቹ ፤ የሙሴ ፤ የአሮን ፤ ምግብ ፤ መላው ፤ እስራኤል ፣ በሉ ፣ መናኛና ፣ ማለፊያ ፤ የለውምና ፤ እንደ ፣ ከፉ ፣ ቀን ፤ እህል ፤ አንድም ፣ የመላእክትን ፣ ምስጋና ፣ አመሰገኑ ።

ፈነወ ፣ ሎሙ ፣ ስንቆሙ ፣ ዘየዐክሎሙ ።

የሚበቃቸውን ፤ ምግባቸውን ፣ ሰጣቸው ፤ አሁን ፤ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ሰጣቸው ፣ ማለት ፣ አይደለም ፣ ሳርባ ፣ ዘመን ፣ የሚበቃቸው ፤ አንድ ፣ ቀን ፣ መታዘዙን ፣ ሲያይ ፣ እንዲህ ፣ አለ ።

፳፮ ፤ ወአንሥአ ፣ ዓዜበ ፣ እምሰማይ ።

ዓዜባዊ ፣ ነፋስንም ፤ በግራ ፣ አስነሣ ።

ወአምጽአ ፣ መስዐ ፣ በኃይሉ ።

መስዓዊ ፤ ነፋስን ፤ በቀኝ ፤ በኃይል ፣ አመጣ ።

፳፯ ፤ ወአዝነመ ፣ ላዕሌሆሙ ፣ ሥጋ ፣ ከመ ፣ መሬት ።

ዘወትር ፤ መና ፤ ፀባ ፣ መና ፤ ኒጋ ፤ መና ፤ መናውን ፤ መብላት ፤ ሰለቸን ፤ መኑ ፣ እምአብልዐነ ፣ ሥጋ ፤ ሥጋ ፣ ማን ፤ ባበላን ፤ ብለዋል ፤ በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ፍንንጓል ፤ ፍንንጓል ፤ አምር ፤ ያህል ፤ ሥጋ ፣ አንድም ፣ አብዝቶ ፤ አዘነመላቸው ።

ወከመ ፣ ኆፃ ፣ ባሕር ፣ አዕዋፍ ፣ ዘይሠርር ።

ሥጋ ፤ መገብኳችኍ ፣ ይለናል ፣ እንጂ ፣ የፈረስ ፤ የበቅሎ ፤ ሥጋ ፤ ይሁን ፤ አናውቅም ፣ እኛ ፣ አላረደነው ፣ ብለዋል ፣ በዚህ ፣ ጊዜ ፣ በክንፋቸው ፣ እንደሚሔዱ ፣ አዕዋፍ ፣ ቆቅ ፣ ጅግራ ፣ በገዞ ፤ ዘነመላቸው ፤ አንድም ፣ አዕዋፈ ፣ ይላል ፤ በክንፋቸው ፣ የሚበሩ ፣ ቆቅ ፣ ጅግራን ፤ እንደ ፣ ባሕር ፣ አሸዋ ፣ አብዝቶ ፤ አዘነመላቸው ።



፳፰ ፤ ወወድቀ ፣ ማእከለ ፣ ተዓይኒሆሙ ።

በከተማቸው ፣ መካከል ፣ ዱብ ፣ ዱብ ፣ ብሎ ፣ ወደቀላቸው ።

ወዐውደ ፣ ደባትሪሆሙ ።

በየድንኳናቸው ፣ አደባባይ ፣ ወደቀላቸው ፤ መጠነ ፣ ቆመ ፣ ብእሲ ፣ ይላል ፣ እንዳይጣሉ ፣ በየድንኳናቸው ፣ እንዳይርቃቸው ፣ በሰው ፣ ቁመት ፣ ልክ ፣ እንዳስቄራጭ ፣ እያወራረደ ፣ ትንሽ ፣ ትልቁን ፣ አወረደላቸው ፤ እየቈለመሙ ፣ እየጠመዘዙ ፣ ከየድንኳናቸው ፣ አግብተው ፣ ተመግበዋቸዋል ።

፳፱ ፤ በልዑ ፣ ወጸግቡ ፣ ጥቀ ።

በልተው ፣ ፈጽመው ፣ ጠገቡ ፣ ጥጋቡ ፣ ምንድነው ፤ ሰለቹት ፤ በል ።

ወወሀቦሙ ፣ ለፍትወቶሙ ።

ፈቃዳቸውን ፣ ለመፈጸም ፤ የሚሹትን ፤ ሁሉ ፣ ሰጣቸው ፤ ዘኁ ፣ ፲፩ ፣ ፬-፴፭ ።

፴ ፤ ወኢያኅጥኦሙ ፣ እምዘ ፣ ፈተዉ ።

ከሚሹት ፣ ነገር ፣ ሁሉ ፣ ምንም ፣ አላሳጣቸውም ፤ ሥጋ ፣ ቢሉ ፣ ሥጋ ፣ መና ፣ ቢሉ ፣ መና ፤ ሰጣቸው ።

ወእንዘ ፣ ዓዲ ፣ መብልዖሙ ፣ ውስተ ፣ አፉሆሙ ።

ምግባቸው ፤ ባፋቸው ፣ ሳለ ፣ ገና ፣ አላምጠው ፣ ሳይውጡት ።

፴፩ ፤ መጽአ ፣ መቅሠፍተ ፣ እግዚአብሔር ፣ ላዕሌሆሙ ።

ከእግዚአብሔር ፣ የታዘዘ ፣ መቅሠፍት ፣ መጣባቸው ፣ ማለት ፣ ሕማመ ፣ ወጊዕ ፣ ሁኖባቸዋል ።

ወቀተሎሙ ፣ መብዝኀቶሙ ።

ብዙኆቹንም ፣ ሲል ፣ ነው ፣ ከእስራኤል ፣ የሚበዙትን ፣ አጠፋቸው ፣ በሺህ ፣ አበው ፣ በመቶ ፣ ውሉድ ፣ ይበዛሉና ።

ወአዕቀፆሙ ፣ ለኅሩያኒ ፣ እስራኤል ።

ለክህነት ፣ ለመንግሥት ፣ የተመረጡ ፣ እስራኤልን ፣ በሞት ፣ አሰነካከላቸው ፣ ዘኍ ፣ ፲፭ ፣ ፱-፴፫ ።

፴፪ ፤ ወምስለ ፣ ዝኒ ፣ ዓዲ ፣ አበሱ ፣ ሎቱ ።

ይህም ፣ ይህ ፣ ነው ፣ ከዚህ ፣ ጋራ ፣ ሁለተኛ ፣ በደሉ ።

ወኢተአመንዎ ፣ በተአምራቲሁ ።

ባደረገላቸው ፣ ተአምራት ፣ አንድም ፣ በደመናው ፣ አላመኑበትም ።

፴፫ ፤ ወኀልቀ ፣ በከንቱ ፣ መዋዕሊሆሙ ።

ዘመናቸው ፣ በከንቱ ፣ የተፈጸመ ፣ ከንግ ፣ ከሠልስት ፣ እንገባለን ፣ በማለት ።

ወኀለፈ ፣ በጕጕዓ ፣ ዓመቲሆሙ ።

ዘመናቸውም ፣ በመቸኰል ፣ አለፈ ፣ ጫን ፣ ተብትብ ፣ ዕሠር ፣ ፍታ ፣ በማለት ።

፴፬ ፤ አመ ፣ ይቀትሎሙ ፣ ውእተ ፣ አሚረ ፣ የኀሥሥዎ ።

ባጠፋቸውም ፣ ጊዜ ፣ ያንጊዜውኑ ፣ በሕግ ፣ በአምልኮ ፣ ይሹታል ።

2014 04 17

ይትመየጡ ፡ ወይኀሥሥዎ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

መከራ ፡ ቢያመጣባቸው ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ከገቢረ ፡ ኀጢአት ፡ ወደ ፡ ገ ቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ይመለሳሉ ፡ ሕጉን ፡ አምልኮቱን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ይገሠግሣሉ ፡ ይማልዳሉ ።

፴፭፡ ወተዘከሩ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ረዳኢሆሙ ።

ረዳታቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቀው ፡ ይገይሡ ፡ ይትመ የጡ ፡ በል ።

ወእግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ መድኀኒሆሙ ።

ድኅነታቸውን ፡ የሚያደርግላቸው ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደሆነ ፡ አውቀው ፡ ኢሳ ፡ ፲ ፡ ፳-፳፩ ።

፴፮፡ ወአፍቀርዎ ፡ በአፉሆሙ ።

በፋቸው ፡ እንወድድኀለን ፡ ይሉታል ።

ወሐሰውዎ ፡ በልሳኖሙ ።

በልቡናቸው ፡ ግን ፡ ይክዱታል ፡ እሉ ፡ ሕዝብ ፡ በአፉሆሙ ፡ ያፈቅሩኒ ፡ ወበ ልቦሙሰ ፡ ነዋኀ ፡ ይርኅቁ ፡ እምኔየ ፡ እንዲል ።

፴፯፡ ወኢኮነ ፡ ርቱዕ ፡ ልቦሙ ፡ በላዕሌሆሙ ።

በሰውነታቸው ፡ ያለ ፡ ልቡናቸው ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቀና ፡ አይደለም ።

ወኢተአመንዎ ፡ በኪዳኑ ።

ወኢተአመኑም ፡ ይላል ፡ በሕጉ ፤ አ ንድም ፡ አወርሰክሙ ፡ ባለው ፡ ቃሉ ፡ አላመኑምና ።

፴፰፡ ውእቱሰ ፡ መሐሪ ፡ ውእቱ ።

እሱ ፡ ግን ፡ መሐሪ ፡ ነውና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነውና ።

ወይሠሪ ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ወኢያጠፍኦሙ ።

ኀጢአታቸውን ፡ ኍሉ ፡ ይቅር ፡ ይላቸዋል ፡ ይቅር ፡ ይላቸዋል ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ አያጠፋቸውም ።

ወያበዝኅ ፡ መዪጠ ፡ መዓቱ ።

መዓቱን ፡ መመለሱን ፡ ያበዛል ፡ ማለት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይቅር ፡ ይላቸው ፡ ነበር ።

ወኢያነድድ ፡ በኵሉ ፡ መቅሠፍቱ ።

በመቅሠፍቱ ፡ ኍሉ ፡ አያጠፋቸውም ፡ ለሕይወት ፡ ካላለው ፡ የበሉት ፡ አንቆ ፡ የጠጡት ፡ እንገዘ ፡ ይገድላልና ፡ አ ንድም ፡ ወኢያነድድ ፡ ኵሎ ፡ በመ ቅሠፍቱ ፡ ኍሉን ፡ በመቅሰፍቱ ፡ አ ያጠፋም ፡ ኢሳ ፡ ፶፰ ፡ ፱ ።

፴፱፡ ወተዘከረ ፡ ከመ ፡ ሥጋ ፡ እሙንቱ ።

ሥጋውያን ፡ ደማውያን ፡ እንደሆኑ ፡ አውቆ ፡ ኢያነድድ ፡ ላለው ።

መንፈስ ፡ እምከመ ፡ ወፅአ ፡ ኢይገ ብዕ ፡ ነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ ከተለየች ፡ በ ኋላ ፡ አትመለስምና ፡ እንዲህ ፡ ይ ቅር ፡ አላቸው ፡ እንጂ ፡ ይቅር ፡ ባይ ላቸውማ ።

፵፡ ሚመጠነ ፡ አምዕዕዎ ፡ በገዳም ።

በበረሓ ፡ ሳሉ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ማሳዘን ፡ አሳዘኑት ፡ (አሳዝነውት ፡ ነበር) ።

ወወሀክዎ ፡ በበድው ።

በበረሓ ፡ ሳሉ ፡ ቀሰቀሱት ፡ አነሣሡት ፡ ቅሠፈን ፡ ቅሠፈን ፡ አሉት ።

፵፩፡ ተመይጡ ፡ ወአመከርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ከአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ከገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ኀጢአት ፡ ተመልሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተፈታተኑት ።

ወወሀክዎ ፡ ለቅዱስ ፡ እስራኤል ።

ዕኑዐ ፡ እስራኤል ፡ ክቡረ ፡ እስራኤል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቀሰቀሱት ፡ አነሣ ሡት ።

፵፪፡ ወኢተዘከሩ ፡ እዴሁ ።

ሥልጣኑን ፡ አላሰቡም ።

ዘአድኀኖሙ ፡ እምእደ ፡ ፀሮሙ ።

ከጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ያዳናቸውን ።

፵፫፡ ዘገብረ ፡ ተአምረ ፡ በግብፅ ።

ሠጠቀ ፡ ባሕረ ፡ ወአኅለፎሙ ፡ ብሎ ፡ ሌላ ፡ አግብቶበት ፡ ነበርና ፡ አመጣው ፡ በግብፅ ፡ ዘጠኙን ፡ ተአምራት ፡ ያደ ረገ ፡ ሥልጣኑን ፡ አንድም ፡ ዘጠኙን ፡ ተአምራት ፡ ያደረገ ፡ ሥልጣኑ ፡ ነው ።

ወመንክረ ፡ በሐቅለ ፡ ጣኔዎስ ።

በጣኔዎስ ፡ ፈርዖን ፡ አገር ፡ አንድም ፡ ጣኔዎስ ፡ በሚባል ፡ በረኃ ፡ ያደረገ ውን ፡ ድንቅ ፡ ተአምራት ፡ አንድም ፡ ያደረገ ፡ ሥልጣኑ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ ሥልጣኑን ፡ አላሰቡም ፡ ዘፀ ፡ ፱ ፡ ፩-፵፩ ።

፵፬፡ ወረሰየ ፡ ደመ ፡ አፍላጊሆሙ ።

አፍላጋቱንም ፡ ደም ፡ ያደረገ ፡ ሥል ጣኑ ፡ ነው ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ወሀው ፡ ደም ፡ ሁኗልና ፡ ሙሴን ፡ እየታፈን ሀ ፡ እርጨጠው ፡ አለው ፡ ቢረጨጠው ፡ ደም ፡ ሁኗል ፡ በእስራኤል ፡ ግን ፡ የጠ ሀው ፡ ጽርየት ፡ አልተለወጠባቸውም ።

ወለአንቅዕቲሆሙኒ ፡ ከመ ፡ ኢይስትይዎ ።

ምንጮቻቸውንም ፡ እንዳይጠጡት ፡ ደም ፡ ያደረገ ፡ ሥልጣኑ ፡ ነው ፡ ዘፀ ፡ ፯ ፡ ፲፯-፳፭ ።

፵፭፡ ፈነወ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ አኮተ ፡ ወበልዖሙ ።

በሳቸው ፡ ተርብ ፡ ሳንጃ ፡ ተቈናጣጭ ፡ ዝንብ ፡ አመጣ ፡ ነከሳቸው ፡ በቀሚ ሳቸው ፡ ውስጥ ፡ እየገባ ፡ ቢቆነጥጣ ቸው ፡ ዝሰ ፡ አዕባዕተ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ብለዋል ።

ወቈርነናዓተ ፡ ወአርኰሶሙ ።

ቀንዳማ ፡ ትል ፡ ጓጉንቸር ፡ ዛጕል ፡ ልብሱ ፡ ተሳበ ፡ አመጣባቸው ፡ በሞ ት ፡ አሳደፋቸው ፡ አንድም ፡ (ወቈር ነናዓት ፡ አርኰሶሙ) ፡ ይላል ፡ ቈርነ ናዓት ፡ በሞት ፡ አሳደፋቸው ፡ አንድ



2014 04 17

ም ፡ ከሚበሉት ፡ ከሚጠጡት ፡ እየ
ገባ ፡ አረከሳቸው ፡ ዘፀ ፡ ፰ ፡ ፩-፴፪ ።

፵፯ ፡ ወቀተለ ፡ በአስሐትያ ፡ ፍሬሆሙ ።

እህላቸውን ፡ ለኩብኩባ ፡ ሰጠባቸው ።

ወተገብሮሙኒ ፡ ለአንበጣ ።

መከራቸውንም ፡ ለአንበጣ ፡ ሰጠባ
ቸው ፡ አንበጣ ፡ የሚለው ፡ በራሪው ፡
አናኵዕ ፡ የሚለው ፡ ኩብኩባ ፡ ነው ።

፵፰ ፡ ወቀተለ ፡ ወይኖሙ ፡ በበረድ ።

ወይናቸውንም ፡ በበረድ ፡ ጨፈጨ
ፈው ።

ወበለሶሙኒ ፡ በአስሐትያ ።

በለሳቸውንም ፡ በውርጭ ፡ አደረቀ
ው ።

፵፱ ፡ ወወሀበ ፡ ለበረድ ፡ እንስሳሆሙ ።

ከብቶቻቸውንም ፡ ለበረድ ፡ አሳልፎ ፡
ሰጠባቸው ።

ወንዋዮሙኒ ፡ ለእሳት ።

ገንዘባቸውንም ፡ ለእሳት ፡ ሰጠባቸ
ው ፤ በግብፅ ፡ ዝናም ፡ አይዘንምም ፡
ያንጊዜም ፡ ጊዜ ፡ ገጥሞት ፡ ቢዘጋም ፡
እሳትና ፡ በረድ ፡ እንደ ፡ ሰምና ፡ እንደ
ፈትል ፡ ተጠምቶ ፡ ወርዷል ፡ ከብቱ
ም ፡ ላዩ ፡ ደህና ፡ ይመስላል ፡ ውስ
ጡን ፡ ግን ፡ ጠብተው ፡ ያዩት ፡ እንደ
ሆነ ፡ ሥጋውን ፡ ጨርሶ ፡ አጥንቱን ፡
አክስሎት ፡ ይገኝ ፡ ነበረ ፡ ዘፀ ፡ ፱ ፡
፳፪ ፡ ፴፭ ።

፶ ፡ ፈነወ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መቅሠፍተ ፡ መዓቱ ።

ፍጹም ፡ መዓቱን ፤ አንድም ፡ ፈርዶ ፡
ያመጣው ፡ መዓቱን ፡ ላከባቸው ።

መቅሠፍተ ፡ ወመንሱተ ፡ ወሕማመ ።

አንድ ፡ ወገን ፡ ፍጹም ፡ መዓቱን ፡
አመጣባቸው ፡ አንድም ፡ (መቅሠፍ
ተ) ፡ ዘጠኙን ፡ (መንሱተ) ፡ ዓሥሩን ፡
(ሕማመ) ፡ ሞተ ፡ በኵርን ፡ አንድም ፡
(ሕማመ) ፡ አሥራ ፡ አንደኛ ፡ ሥጥ
መትን ፡ አመጣባቸው ።

ፈነወ ፡ ምስለ ፡ መላእክት ፡ ዕኩያን ።

ይህን ፡ ጉሉ ፡ ክፋት ፡ ከሚስማማቱ
ው ፡ መላእክት ፡ ጋራ ፡ አመጣባቸው ፤
ወበእንተ ፡ መዓቶሙ ፡ ተሰምዩ ፡ ሌጌ
ዎን ፡ እንዲል ፡ ለመዓት ፡ እንጂ ፡ ለም
ሕረት ፡ የማይታዘዙ ፡ ነገደ ፡ ቅዱስ ፡
ሚካኤል ፡ አሉና ፡ ቀናዕያን ፡ ለእም
ላክሙ ፡ ይላቸዋል ።

፶፩ ፡ ወጺሐ ፡ ፍኖተ ፡ ለመዓቱ ።

ለመዓቱ ፡ ጽርጊያ ፡ ጎዳና ፡ አደረጋ
ቸው ።

ወኢምሕክ ፡ እሞት ፡ ለነፍሶሙ ።

ሰውነታቸውን ፡ ከሞት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡
አላላትም ፡ አላዘነላትም ።

ወዓፀወ ፡ ውስተ ፡ ሞት ፡ እንስሳሆሙ ።

ከብቶቻቸውንም ፡ በሞት ፡ በር ፡ ዘግ
ቶ ፡ ተዋቸው ።



፶፪ ፡ ወቀተለ ፡ ኵሎ ፡ በኵሮሙ ፡ በምድረ ፡
ግብፅ ።

በግብፅ ፡ የግብፃውያንን ፡ በኵር ፡
ጉሉ ፡ አጠፋባቸው ፡ እምበኵረ ፡
ንጉሥ ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡
መንግሥት ፡ እስከ ፡ በኵረ ፡ ዓመት ፡
ዘይውዕል ፡ ታሕተ ፡ እግረ ፡ ማሕረፅ ፡
እንዲል ፡ ፂውውትም ፡ ይላል ።

ወቀዳሜ ፡ ኵሉ ፡ ተግባሮሙ ፡ በውስተ ፡ አብያ
ቲሆሙ ።

አስቀድሞ ፡ የደረሰ ፡ በቤታቸው ፡
ያለ ፡ መከራቸውን ፡ ጉሉ ፡ አጠፋብ
ቸው ፡ እንደ ፡ ጠበል ፡ ፌሾ ፡ ያለው
ን ፡ አስቀድሞ ፡ የደረሰውን ፡ መከር ፡
ወቅተው ፡ በጎታ ፡ በጎተራ ፡ በጉሽ
ጉሻ ፡ ያደርጉታል ፡ የአፍአውን ፡
በልቶ ፡ ጨርሶ ፡ ከደጃቸው ፡ ይሰፍ
ራል ፡ ዙሪያውን ፡ ከብቦ ፡ የማያስገባ ፡
የማያስወጣቸው ፡ ኸነ ፡ ከቤታቸው ፡
ውስጥ ፡ ያለውን ፡ አውጥተው ፡ ሰጥ
ተውት ፡ የታዘዘ ፡ ነውና ፡ ተመግቦ ፡
ሔዷልና ፤ አንድም ፡ ግብፃውያን ፡
ከነገር ፡ ቀደም ፡ ባሪያ ፡ አህያ ፡ መግ
ዛት ፡ ይወድዱ ፡ ነበርና ፡ ያንንም ፡
ሁሉ ፡ አ[illegible]ፋባቸው ።

፶፫ ፡ ወአውፈሮሙ ፡ ከመ ፡ አባግዕ ፡ ለሕዝቡ ።

ወገኖቹ ፡ እስራኤልን ፡ ግን ፡ እንደ ፡
አባግዕ ፡ አሠማራቸው ።

ወአውዕዖሙ ፡ ገዳመ ፡ ከመ ፡ መርዔት ።

እንዳገር ፡ መንጋ ፡ ወደ ፡ ገዳመ ፡ ኢ
ያሱን ፡ አወጣቸው ፡ ሆሴ ፡ ፱ ፡ ፲፮ ።

፶፬ ፡ ወመርሆሙ ፡ በተስፋው ፡ ወኢፈርሁ ።

አወርስከሙ ፡ ባለው ፡ ቃሉ ፡ መርቶ ፡
አወጣቸው ፡ በዚህም ፡ አላፈሩም ።

ወደፈኖሙ ፡ ባሕር ፡ ለፀሮሙ ፡ ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፳፰ ።

ጠላቶቻቸው ፡ ግብፃውያንን ፡ ግን ፡
ባሕር ፡ አሠጠማቸው ።

፶፭ ፡ ወወሰዶሙ ፡ ደብረ ፡ መቅደሱ ።

መመስገኛው ፡ ወደ ፡ ምትሆን ፡ ወደ ፡
ሲና ፡ ወሰዳቸው ።

ደብር ፡ ዘፈጠረት ፡ የማኑ ፡ ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ።

ደብረ ፡ መቅደሱም ፡ ያልኋት ፡ ሥል
ጣኑ ፡ በእህል ፡ በተክል ፡ ያፀናቻት ፡
ደብረ ፡ ሲና ፡ ናት ።

፶፮ ፡ ሰደደ ፡ አሕዛበ ፡ እምቅድመ ፡ ገጾሙ ።

አሕዛብን ፡ ግን ፡ ከፊታቸው ፡ አስወ
ጥቶ ፡ ሰደደላቸው ፡ አንድም ፡ እም
ቅድመ ፡ ገጹ ፤ ገጸ ፡ መዓቱ ፡ ከመገ
ለጽ ፡ የተነሣ ፡ በሞት ፡ አንድም ፡ በበ
ታ ፡ አስወጥቶ ፡ ሰደደላቸው ።

ወአውረሶሙ ፡ በሐብለ ፡ ርስቱ ።

ምድረ ፡ ርስትን ፡ የረዘመውን ፡ በጠ
ፍር ፡ ያጠረውን ፡ በድግር ፡ አወረሳ
ቸው ፤ አንድም ፡ በሀብል ፡ ርስቶ ፡
በኢያሱ ፡ አድሮ ፡ ርስቱ ፡ ኢየሩሳሌ
ምን ፡ አወረሳቸው ፡ አንድም ፡ በር
ስተ ፡ ሀብሉ ፡ በአብርሃም ፡ በይስሐ
ቅ ፡ በያዕቆብ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አወረሳ
ቸው ፡

ም ፣ ከሚበሉት ፣ ከሚጠጡት ፣ እየገባ ፣ አረከሳቸው ፣ ዘፀ ፡ ፰ ፡ ፳-፴፪ ።

፵፯ ፣ ወወሀበ ፡ ለአናኵዕ ፡ ፍሬሆሙ ።

እህላቸውን ፣ ለኩብኩብ ፣ ሰጠባቸው ።

ወተግባሮሙኒ ፡ ለአንበጣ ።

መከራቸውንም ፣ ለአንበጣ ፣ ሰጠባቸው ፣ አንበጣ ፣ የሚለው ፣ በራሪው ፣ አናኵዕ ፣ የሚለው ፣ ኩብኩብ ፣ ነው ።

፵፰ ፣ ወቀተለ ፡ ወይኖሙ ፡ በበረድ ።

ወይናቸውንም ፣ በበረድ ፣ ጨፈጨፈው ።

ወበለሶሙኒ ፡ በአስሐትያ ።

በለሳቸውንም ፣ በውርጭ ፣ አደረቀው ።

፵፱ ፣ ወወሀበ ፡ ለበረድ ፡ እንስሳሆሙ ።

ከብቶቻቸውንም ፣ ለበረድ ፣ አሳልፎ ፣ ሰጠባቸው ።

ወንዋዮሙኒ ፡ ለእሳት ።

ገንዘባቸውንም ፣ ለእሳት ፣ ሰጠባቸው ፤ በግብፅ ፣ ዝናም ፣ አይዘንምም ፣ ያንጊዜም ፣ ጊዜ ፣ ገጥሞት ፣ ቢዘጋም ፣ እሳትና ፤ በረድ ፣ እንደ ፣ ሰምና ፣ እንደ ፈትል ፣ ተጠምቶ ፣ ወርዷል ፣ ከብቱም ፣ ላዩ ፣ ደህና ፣ ይመስላል ፣ ውስጡን ፣ ግን ፣ ጠብተው ፣ ያዩት ፣ እንደ ሆነ ፣ ሥጋውን ፣ ጨርሶ ፣ አጥንቱን ፣ አክስሎት ፣ ይገኝ ፣ ነበረ ፣ ዘፀ ፡ ፱ ፡ ፳፪ ፡ ፴፭ ።

፶ ፣ ፈነወ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መቅሠፍተ ፡ መዓቱ ።

ፍጹም ፣ መዓቱን ፤ አንድም ፣ ፈርዖ ፣ ያመጣው ፣ መዓቱን ፣ ላከባቸው ።

መቅሠፍተ ፡ ወመንሱተ ፡ ወሕማመ ።

አንድ ፣ ወገን ፣ ፍጹም ፣ መዓቱን ፣ አመጣባቸው ፣ አንድም ፣ (መቅሠፍት) ፣ ዘጠኙን ፣ (መንሱት) ፣ ዓሥሩን ፣ (ሕማመ) ፣ ሞተ ፣ በኵርን ፤ አንድም ፣ (ሕማመ) ፣ አሥራ ፣ አንደኛ ፣ ሥጥመትን ፣ አመጣባቸው ።

ፈነወ ፡ ምስለ ፡ መላእክት ፡ ዕኩያን ።

ይህን ፣ ጉሉ ፣ ከፋት ፣ ከሚስማማቸው ፣ መላእክት ፣ ጋራ ፣ አመጣባቸው ፤ ወበእንተ ፣ መዓቶሙ ፣ ተሰምዩ ፣ ሌጌዎን ፣ እንዲል ፣ ለመዓት ፣ እንጂ ፣ ለምሕረት ፣ የማይታዘዙ ፣ ነገደ ፣ ቅዱስ ፣ ሚካኤል ፣ አሉና ፣ ቀናዕያን ፣ ለአምላከሙ ፣ ይላቸዋል ።

፶፩ ፣ ወጼሐ ፡ ፍኖተ ፡ ለመዓቱ ።

ለመዓቱ ፣ ጽርጊያ ፣ ጎዳና ፣ አደረጋቸው ።

ወኢምሕካ ፡ እሞት ፡ ለነፍሶሙ ።

ሰውነታቸውን ፣ ከሞት ፣ ወደ ፣ ኋላ ፣ አላላትም ፣ አላዘነላትም ።

ወዓፀወ ፡ ውስተ ፡ ሞት ፡ እንስሳሆሙ ።

ከብቶቻቸውንም ፣ በሞት ፣ በር ፣ ዘግቶ ፣ ተዋቸው ።



፶፩ ፣ ወቀተለ ፡ ኵሎ ፡ በኵሮሙ ፡ በምድረ ፡ ግብፅ ።

በግብፅ ፣ የግብፃውያንን ፣ በኵር ፣ ጉሉ ፣ አጠፋባቸው ፤ እምበኵረ ፣ ንጉሥ ፣ ዘይነብር ፡ ዲበ ፣ መንበረ ፣ መንግሥት ፡ እስከ ፣ በኵረ ፣ ዓመት ፣ ዘይውዕል ፣ ታሕተ ፣ እግረ ፡ ማሕረፅ ፣ እንዲል ፡ ጊውውትም ፣ ይላል ።

ወቀዳሜ ፣ ኵሉ ፣ ተግባሮሙ ፣ በውስተ ፣ አብያቲሆሙ ።

አስቀድሞ ፣ የደረሰ ፡ በቤታቸው ፣ ያለ ፣ መከራቸውን ፡ ጉሉ ፡ አጠፋባቸው ፣ እንደ ፣ ጠበል ፡ ፌሽ ፣ ያለውን ፡ አስቀድሞ ፡ የደረሰውን ፣ መከር ፡ ወቅተው ፣ በጎታ ፣ በጎተራ ፡ በጉሽጉሽ ፡ ያደርጉታል ፡ የአፍአውን ፣ በልቶ ፣ ጨርሶ ፡ ከደጃቸው ፣ ይሰፍራል ፣ ዙሪያውን ፣ ከብቦ ፡ የማያስገባ ፣ የማያስወጣቸው ፡ ኸነ ፡ ከቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፣ አውጥተው ፣ ሰጥተውት ፣ የታዘዘ ፡ ነውና ፡ ተመግቦ ፣ ሔዷልና ፤ አንድም ፡ ግብፃውያን ፣ ከነገር ፣ ቀደም ፣ ባሪያ ፣ አህያ ፣ መግዛት ፡ ይወድዱ ፣ ነበርና ፡ ያንንም ፡ ሁሉ ፡ አ(ጠ)ፋባቸው ።

፶፪ ፣ ወአውፈሮሙ ፣ ከመ ፣ አባግዕ ፣ ለሕዝቡ ።

ወገኖቹ ፡ እስራኤልን ፡ ግን ፣ እንደ ፣ አባግዕ ፡ አሠማራቸው ።

ወአውዐሞ ፣ ገዳመ ፣ ከመ ፣ መርዔት ።

እንዳገር ፡ መንጋ ፣ ወደ ፡ ገዳመ ፣ ኢያሶን ፡ አወጣቸው ፣ ሆዕ ፣ ፱ ፣ ፲፯ ።

፶፫ ፣ ወመርሆሙ ፣ በተስፋው ፣ ወኢፈርሁ ።

አወርሰከሙ ፣ ባለው ፣ ቃሉ ፣ መርቶ ፣ አወጣቸው ፣ በዚህም ፣ አላፈሩም ።

ወደፈኖሙ ፣ ባሕር ፣ ለፀሮሙ ፣ ዘፀ ፣ ፲፬ ፣ ፳፯ ።

ጠላቶቻቸው ፣ ግብፃውያንን ፣ ግን ፣ ባሕር ፣ አሠጠማቸው ።

፶፬ ፣ ወወሰዶሙ ፣ ደብረ ፣ መቅደሱ ።

መመስገኛው ፣ ወደ ፣ ምትሆን ፣ ወደ ፣ ሲና ፣ ወሰዳቸው ።

ደብር ፣ ዘፈጠረት ፣ የማኑ ፣ ዘፀ ፣ ፲፭ ፣ ፲፯ ።

ደብረ ፣ መቅደሱም ፣ ያልኋት ፣ ሥልጣኑ ፣ በእህል ፣ በተክል ፣ ያፀናቻት ፣ ደብረ ፣ ሲና ፣ ናት ።

፶፭ ፣ ሰደደ ፣ አሕዛበ ፣ እምቅድመ ፣ ገጾሙ ።

አሕዛብን ፣ ግን ፣ ከፊታቸው ፣ አስወጥቶ ፣ ሰደደላቸው ፤ አንድም ፣ እምቅድመ ፣ ገጹ ፤ ገጽ ፣ መዓቱ ፣ ከመገለጹ ፣ የተነሣ ፣ በሞት ፣ አንድም ፣ በበታ ፣ አስወጥቶ ፣ ሰደደላቸው ።

ወአውረሶሙ ፣ በሐብለ ፣ ርስቱ ።

ምድረ ፣ ርስትን ፣ የረዘመውን ፣ በጠፍር ፣ ያጠረውን ፣ በድግር ፣ አወረሳቸው ፤ አንድም ፣ በሀብል ፣ ርስቶ ፣ በኢያሱ ፣ አድሮ ፣ ርስቱ ፣ ኢየሩሳሌምን ፣ አወረሳቸው ፣ አንድም ፣ በርስተ ፣ ሀብሉ ፣ በአብርሃም ፣ በይስሐቅ ፣ በያዕቆብ ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣ አወረሳቸው ።

2014 04 17

ወአንበረ ፡ ውስተ ፡ አብያቲሆሙ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ።

ሕዝበ ፡ እስራኤልን ፡ ግን ፡ በከነዓን ፡ ሰዎች ፡ በታነፀ ፡ ግምባቻቸው ፡ በደረሰ ፡ መከራቸው ፡ አኖራቸው ፤ አንድም ፡ አብያቲሆሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ነው ፤ እስራኤልን ፡ በቤታቸው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አኖራቸው ።

፶፮ ፡ አመከርዎ ፡ ወአምዕዕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየተፈታተኑ ፡ አሳዘኑት ።

ወኢዐቀቡ ፡ ስምዖ ።

አምልኮቱን ፡ አልጠበቁምና ።

፶፯ ፡ ተመይጡ ፡ ወዓለዉ ፡ ከመ ፡ አበዊሆሙ ።

ከአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ ጣዖት ፤ ከገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ተመልሰው ፡ እንደ ፡ አባቶቻቸው ፡ ከዱ ።

ወኮኑ ፡ ከመ ፡ ቀስት ፡ ጠዋይ ።

እንዲህ ፡ ተመልሰው ፡ እንደ ፡ ጠማማ ፡ ነፍጥ ፡ ሆኑ ፤ አንድም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ቀስት ፡ ሆኑ ፡ ያ ፡ አላዋቂ ፡ ሰው ፡ የሰደደው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተመልሶ ፡ ግንባር ፡ ይመታል ፤ አንድም ፡ ጠዋእያን ፡ አዕምሮ ፡ ኾኑ ። ሆሴ ፡ ፯፥፲፮ ።

፶፰ ፡ ወአምዕዕዎ ፡ በአውግሪሆሙ ።

በየግምባቻቸው ፡ በየቅጽራቸው ፡ ጣዖት ፡ አምልከው ፡ አሳዘኑት ፡ ወያማስን ፡ አውግረ ፡ ዛውዕ ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ በየተራራው ፡ ጣዖት ፡ አቁመው ፡ አሳዘኑት ፤ ይሁዳ ፡ ይሁዳ ፡ በጉልቄ ፡ አህጉሪከ ፡ አማልክቲከ ፡ ከማሁ ፡ ብዙኅ ፡ አጋንንቲከ ፡ እንዲል ።

ወአቅንዕዎ ፡ በግልፎሆሙ ።

በግልፎሆሙ ፡ ይላል ፤ በተቀረጸ ፡ በተነፈ ፡ ጣዖታቸው ፡ አስቀኑት ፡ አሳዘኑት ።

፶፱ ፡ ወሰምዐ ፡ ዘንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአናኆሶሙ ።

እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ናቃቸው ፡ አቃለላቸው ፡ ቁ ፡ ፳፭ ።

ወመነኖሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ፈድፋደ ።

እስራኤልን ፡ ፈጽሞ ፡ ናቃቸው ፤ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ማየት ፡ አይደለም ፡ በረድኤት ፡ ተለያቸው ፡ ሲል ፡ ነው ።

፷ ፡ ወኀደጋ ፡ ለደብተራ ፡ ሴሎም ።

ደብተራ ፡ ሴሎምን ፡ በረድኤት ፡ ተለያት ።

ደብተራሁ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ኀደረ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ።

ደብተራም ፡ ያልኋት ፡ ከሙሴ ፡ ከአሮን ፡ ጋራ ፡ በረድኤት ፡ አድሮባት ፡ ይኖርባት ፡ የነበረ ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ ናት ።

፷፩ ፡ ወወሀበ ፡ ኀይሎሙ ፡ ለተፄውዎ ።

ገንዘባቸውን ፡ ኃይለ ፡ ደማስቆ ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ ወገናቸውን ፡ ለምርኮ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠባቸው ።



ወሥነሙኒ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ፀሮሙ ።

ጌጣቸውን ፤ አንድም ፡ ካህናቱን ፡ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አድርጎ ፡ አሳያቸው ፤ ወነሣእኩ ፡ ፪ ፡ አብትረ ፡ ለአሐቲ ፡ ሰመይክዋ ፡ ሥነ ፡ ወለካልዕታ ፡ ሐብለ ፡ እንዲል ።

፷፪ ፡ ወዐፀዎሙ ፡ ውስተ ፡ ኲናት ፡ ለሕዝቡ ።

ወገኖቹንም ፡ በሞት ፡ በረት ፡ ዘግቶ ፡ ተዋቸው ።

ወተሀየዮሙ ፡ ለርስቱ ።

ርስቱ ፡ ጉልቱ ፤ የሚሆኑ ፡ እስራኤልን ፡ ቻል ፡ አላቸው ።

፷፫ ፡ ወበልዓቶሙ ፡ እሳት ፡ ለወራዙቶሙ ።

ጎበዛዝቱንም ፡ ጦር ፡ አጠፋቸው ።

ወኢላሐዋ ፡ ደናግሊሆሙ ።

ቈንጃጅቱ ፡ ደናግሉ ፡ በጎበዛዝቱ ፡ ሞት ፡ አላዘኑም ፡ ጥንቱን ፡ ለልማዱ ፡ በጎበዛዝቱ ፡ ሞት ፡ ማዘን ፡ ማልቀስ ፡ ይገባቸው ፡ ነበር ፤ ማን ፡ ያጫውተናል ፤ ማን ፡ ይጠይቀናል ፡ ብለው ፡ ሞት ፡ በየደጁ ፡ ሁኗልና ፤ ማን ፡ ይዘን ፡ ማን ፡ ያልቅስ ፡ ኢሳ ፡ ፫፥፲፮ ፤ ኤር ፡ ፩ ፡ ፲፱ ።

፷፬ ፡ ወካህናቲሆሙኒ ፡ ወድቁ ፡ በኲናት ።

ካህናቱም ፡ በጦር ፡ ተነባብረው ፡ ወደቁ ፡ ጥንቱን ፡ ለልማዱ ፡ የካህናት ፡ ሞት ፡ በፍልጠት ፡ በቁርጠት ፡ ነበር ፡ አፍኒና ፡ ፊንሐስን ፡ ያያል ።

ወኢበከያ ፡ ዕቤራቲሆሙ ።

ባልቴቶቹ ፡ በካህናቱ ፡ ሞት ፡ አላለቀሱም ፡ ጥንቱን ፡ ለልማዱ ፡ ማን ፡ ይምክረን ፤ ማን ፡ ይጠይቀን ፡ ብለው ፡ ማልቀስ ፡ ይገባቸው ፡ ነበረ ፤ ሞት ፡ በየደጁ ፡ ሁኗልና ፡ ማን ፡ ያልቅስ ፤ ኢዮ ፡ ፳፯ ፡ ፲፱-፲፭ ።

፷፭ ፡ ወተንሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ዘንቃሕ ፡ እምንዋም ።

የተኛ ፡ ሰው ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲነሣ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ፈጥኖ ፡ በረድኤት ፡ ተነሣ ።

ወከመ ፡ ኃያል ፡ ወኅዳገ ፡ ወይን ።

ከመ ፡ ዘኃደጎ ፡ ሥካረ ፡ ወይን ፡ ይላል ፡ የወይን ፡ ስካር ፡ እንዳለፈለት ፡ ሰው ፤ አንድም ፡ ከመ ፡ ኅዱግ ፡ ወይን ፡ ይላል ፤ አበርትቶ ፡ እንደ ፡ ተጣለ ፡ ወይን ፡ ባገራቸው ፡ ዕኑ ፡ መጠጥ ፡ አለ ፡ ሰው ፡ የጠጣው ፡ እንደሆነ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ወድቆ ፡ ይሰነብታል ፤ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ጥዒና ፡ አግኝቶ ፡ ኃይል ፡ ተሰምቶት ፡ ይነሣል ፤ አንድም ፡ ወይን ፡ በተተከለ ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ዳስ ፡ ጥለውለት ፡ ያፈራል ፤ አንድም ፡ ወይን ፡ በክረምት ፡ ወድቆ ፡ ይከርማል ፡ በበጋ ፡ ዳስ ፡ ጥለው ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ያደርጉታል ፤ ይለመልማል ፤ ያብባል ፤ ያራፈል ፤ ጌታም ፡ ትሩፋንን ፡ ይዞ ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥቷልና ።

፷፮ ፡ ወቀተለ ፡ ፀሮ ፡ በድኅሬሁ ።

በእስራኤል ፡ ከፈረደ ፡ በኋላ ፡ በአሕዛብ ፡ ፈረደባቸው ፤ አንድም ፡ እስራኤልን ፡ ተከትለው ፡ የመጡ ፡ ግብ

2014 04 17

ወአንሥኡ ፡ መዐተ ፡ አብያቲሆሙ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ።

ሕዝበ ፡ እስራኤልን ፡ ግን ፡ በከነዓን ፡ ሰዎች ፡ በታነፀ ፡ ግምባቸው ፡ በደረሰ ፡ መከራቸው ፡ አኖራቸው ፡ አንድም ፡ አብያቲሆሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ነው ፡ እስራኤልን ፡ በቤታቸው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አኖራቸው ።

፶፮ ፡ አመከርዎ ፡ ወአምዕዕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየተፈታተኑ ፡ አሳዘኑት ።

ወኢዓቀቡ ፡ ስምዖ ።

ምስክሩን ፡ አልጠበቁምና ።

፶፯ ፡ ተመይጡ ፡ ወዓለዉ ፡ ከመ ፡ አበዊሆሙ ።

ከእምልክተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ እምልክተ ፡ ጣዖት ፡ ከገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ተመለሰው ፡ እንደ ፡ አባቶቻቸው ፡ ከዱ ።

ወኮኑ ፡ ከመ ፡ ቀስት ፡ ጠዋይ ።

እንዲህ ፡ ተመለሰው ፡ እንደ ፡ ጠማማ ፡ ነፍጥ ፡ ሆኑ ፤ አንድም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ቀስት ፡ ሆኑ ፡ ያ ፡ አላዋቂ ፡ ሰው ፡ የሰደደው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተመልሶ ፡ ግንባር ፡ ይመታል ፤ አንድም ፡ ጠዋእያን ፡ አዕምሮ ፡ ኾኑ ። ሆሴ ፡ ፯፡፲፮ ።

፶፰ ፡ ወአምዕዕዎ ፡ በአውግሪሆሙ ።

በየግምባቸው ፡ በየቅጽራቸው ፡ ጣዖት ፡ አምልከው ፡ አሳዘኑት ፡ ወያማስን ፡ አውግረ ፡ ዛውዕ ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ በየተራራው ፡ ጣዖት ፡ አቁመው ፡ አሳዘኑት ፤ ይሁዳ ፡ ይሁዳ ፡ በኍልቈ ፡ አህጉሪከ ፡ አማልክቲከ ፡ ከማሁ ፡ ብዙኃ ፡ አጋንንቲከ ፡ እንዲል ።

ወአቅንዕዎ ፡ በግልፎሆሙ ።

በግልፎሆሙ ፡ ይላል ፤ በተቀረጸ ፡ በተነፈ ፡ ጣዖታቸው ፡ አስቀኑት ፡ አሳዘኑት ።

፶፱ ፡ ወሰምዐ ፡ ዘንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአኅሰረ ።

እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ናቃቸው ፡ አቃለላቸው ፡ ቈ ፡ ፳፰ ።

ወመነኖሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ፈድፋደ ።

እስራኤልን ፡ ፈጽሞ ፡ ናቃቸው ፤ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ማየት ፡ አይደለም ፡ በረድኤት ፡ ተለያቸው ፡ ሲል ፡ ነው ።

፷ ፡ ወኃደጋ ፡ ለደብተራ ፡ ሴሎም ።

ደብተራ ፡ ሴሎምን ፡ በረድኤት ፡ ተለያት ።

ደብተራሁ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ኃደረ ፡ ምስለ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

ደብተራም ፡ ያሏት ፡ ከሙሴ ፡ ከአሮን ፡ ጋራ ፡ በረድኤት ፡ አድሮባት ፡ ይኖርባት ፡ የነበረ ፡ ደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ናት ።

፷፩ ፡ ወወሀበ ፡ ኃይሎሙ ፡ ለተፄውዎ ።

ገንዘባቸውን ፡ ኃይለ ፡ ደማስቆ ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ ወገናቸውን ፡ ለምርኮ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠባቸው ።



ወሥነሙኒ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ፀሮሙ ።

ጌጣቸውን ፤ አንድም ፡ ክህናቱን ፡ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አድርጎ ፡ አሳያቸው ፤ ወነሥአኩ ፡ ፪ ፡ አብትረ ፡ ለአሐቲ ፡ ሰመይክዋ ፡ ሥነ ፡ ወለካልዕታ ፡ ሐብለ ፡ እንዲል ።

፷፪ ፡ ወዐፀዎሙ ፡ ውስተ ፡ ኲናት ፡ ለሕዝቡ ።

ወገኖቹንም ፡ በሞት ፡ በረት ፡ ዘጋቶ ፡ ተዋቸው ።

ወተሀየየሙ ፡ ለርስቱ ።

ርስቱ ፡ ጉልቱ ፡ የሚሆኑ ፡ እስራኤልን ፡ ቻል ፡ አላቻቸው ።

፷፫ ፡ ወበልዖሙ ፡ እሳት ፡ ለወራዙቶሙ ።

ጎበዛዝቱንም ፡ ጦር ፡ አጠፋቸው ።

ወኢለሐዋ ፡ ደናግሊሆሙ ።

ቈንጃጅቱ ፡ ደናግሉ ፡ በጎበዛዝቱ ፡ ሞት ፡ አላዘኑም ፡ ጥንቱን ፡ ለልማዱ ፡ በጎበዛዝቱ ፡ ሞት ፡ ማዘን ፡ ማልቀስ ፡ ይገባቸው ፡ ነበር ፤ ማን ፡ ያጫውተናል ፤ ማን ፡ ይጠይቀናል ፡ ብለው ፡ ሞት ፡ በየደጁ ፡ ሁኗልና ፤ ማን ፡ ይዘን ፡ ማን ፡ ያልቅስ ፡ ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ፡ ኤር ፡ ፩ ፡ ፲፱ ።

፷፬ ፡ ወካህናቲሆሙኒ ፡ ወድቁ ፡ በኲናት ።

ካህናቱም ፡ በጦር ፡ ተነባብረው ፡ ወደቁ ፡ ጥንቱን ፡ ለልማዱ ፡ የካህናት ፡ ሞት ፡ በፍልጠት ፡ በቁርጠት ፡ ነበር ፡ አፍኒና ፡ ፊንሐስን ፡ ያያል ።

ወኢበክያ ፡ ዕቤራቲሆሙ ።

ባልቴቶቹ ፡ በካህናቱ ፡ ሞት ፡ አላለቀሱም ፡ ጥንቱን ፡ ለልማዱ ፡ ማን ፡ ይምከረን ፡ ማን ፡ ይጠይቀን ፡ ብለው ፡ ማልቀስ ፡ ይገባቸው ፡ ነበረ ፤ ሞት ፡ በየደጁ ፡ ሁኗልና ፡ ማን ፡ ያልቅስ ፤ ኢዮ ፡ ፳፯ ፡ ፲፱ - ፲፩ ።

፷፭ ወተንሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ዘንቃሕ ፡ እምንዋም ።

የተኛ ፡ ሰው ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲነሣ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ፈጥኖ ፡ በረድኤት ፡ ተነሣ ።

ወከመ ፡ ኃያል ፡ ወኅዳገ ፡ ወይን ።

ከመ ፡ ዘኅደጎ ፡ ሥካረ ፡ ወይን ፡ ይላል ፡ የወይን ፡ ስካር ፡ እንዳለፈለት ፡ ሰው ፤ አንድም ፡ ከመ ፡ ኅዱግ ፡ ወይን ፡ ይላል ፤ አበርትቶ ፡ እንደ ፡ ተጣለ ፡ ወይን ፡ ባገራቸው ፡ ዕኑ ፡ መጠጥ ፡ አለ ፡ ሰው ፡ የጠጣው ፡ እንደሆነ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ወድቆ ፡ ይሰነብታል ፤ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ጥዒና ፡ አግኝቶ ፡ ኃይል ፡ ተሰምቶት ፡ ይነሣል ፤ አንድም ፡ ወይን ፡ በተተከለ ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ዳስ ፡ ጥለውለት ፡ ያፈራል ፤ አንድም ፡ ወይን ፡ በክረምት ፡ ወድቆ ፡ ይከርማል ፡ በበጋ ፡ ዳስ ፡ ጥለው ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ያደርጉታል ፤ ይለመልማል ፡ ያብባል ፡ ያራፈል ፤ ጌታም ፡ ትሩፋንን ፡ ይዞ ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥቷልና ።

፷፮ ወቀተለ ፡ ፀሮ ፡ በድኅሬሁ ።

በእስራኤል ፡ ከፈረደ ፡ በኋላ ፡ በአሕዛብ ፡ ፈረደባቸው ፤ አንድም ፡ እስራኤልን ፡ ተከትለው ፡ የመጡ ፡ ግብፃ

2014 04 17

ወአንበረ፡ውስተ፡አብያቲሆሙ፡ሕዝበ፡እስ
ራኤል።

ሕዝበ፡እስራኤልን፡ግን፡በከነዓን፡ሰዎች፡በታነፀ፡ግምባቸው፡በደረሰ፡መከራቸው፡አኖራቸው፡እንድም፡አብያቲሆሙ፡ለእስራኤል፡ነው፤እስራኤልን፡በቤታቸው፡በኢየሩሳሌም፡አኖራቸው።

፶፮፡ አመረርዎ፡ወአምዕዕዎ፡ለእግዚአብሔር።

ልዑል፡እግዚአብሔርን፡እየተፈታተኑ፡አሳዘኑት።

ወኢዐቀቡ፡ስምዖ።

እምልክቱን፡አልጠበቁምና።

፶፯፡ ተመይጡ፡ወዓለዉ፡ከመ፡አበዊሆሙ።

ከእምልክተ፡እግዚአብሔር፡ወደ፡እምልክተ፡ጣዖት፤ከገቢረ፡ጽድቅ፡ወደ፡ገቢረ፡ኃጢአት፡ተመለሰው፡እንደ፡አባቶቻቸው፡ከዱ።

ወኮኑ፡ከመ፡ቀስት፡ወግዱ።

እንዲህ፡ተመልሰው፡እንደ፡ጠማማ፡ነፍጥ፡ሆኑ፤እንድም፡እንደ፡ባሕር፡ቀስት፡ሆኑ፡ያ፡አላዋቂ፡ሰው፡የሰደደው፡እንደ፡ሆነ፡ተመልሶ፡ግንባር፡ይመታል፤እንድም፡ጠዋኢያን፡አዕምሮ፡ኽኑ።ሆሴ፡፯፡፲፮።

፶፰፡ ወአምዕዕዎ፡በአውግሪሆሙ።

በየግምባቸው፡በየቅጽራቸው፡ጣዖት፡እምልከው፡አሳዘኑት፡ወያምግሰ

ን፡አውግረ፡ዛውዕ፡እንዲል፤እንድም፡በየተራራው፡ጣዖት፡አቁመው፡አሳዘኑት፤ይሁዳ፡ይሁዳ፡በጕልቄ፡አህጉሪከ፡አማልክቲከ፡ከማሁ፡ብዙኅ፡አጋንንቲከ፡እንዲል።

ወአቅንዕዎ፡በግልፎሙ።

በግልፎሙ፡ይላል፤በተቀረጸ፡በተኀነፈ፡ጣዖታቸው፡አስቆኑት፡አሳዘኑት።

፶፱፡ ወሰምዐ፡ዘንተ፡እግዚአብሔር፡ወአስተሐቀሮ።

እግዚአብሔር፡ይህን፡ሰምቶ፡ናቃቸው፤አቃለላቸው፤ቈ፡፴፩።

ወመንነሙ፡ለእስራኤል፡ፈድፋደ።

እስራኤልን፡ፈጽሞ፡ናቃቸው፤ከፍና፡ዝቅ፡አድርጎ፡ማየት፡አይደለም፤በረድኤት፡ተለያቸው፡ሲል፡ነው።

፷፡ ወኀደጋ፡ለደብተራ፡ሴሎም።

ደብተራ፡ሴሎምን፡በረድኤት፡ተለያት።

ደብተራሁ፡እንተ፡ባቲ፡ኀደረ፡ምስለ፡ሰብእ።

ደብተራም፡ያልኋት፡ከሙሴ፡ከአሮን፡ጋራ፡በረድኤት፡አድሮባት፡ይኖርባት፡የነበረ፡ደብተራ፡ኦሪት፡ናት።

፷፩፡ ወመጠወ፡ኀይሎሙ፡ለተፄውዎ።

ገንዘባቸውን፡ኃይል፡ይማርኩ፡እንዲል፤እንድም፡ወገናቸውን፡ለምርኮ፡አሳልፎ፡ሰጠባቸው።



ወሥምረቶሙ፡ውስተ፡እደ፡ፀርሙ።

ጌጣቸውን፤እንድም፡ካህናቱን፡በጠላቶቻቸው፡እጅ፡አድርጎ፡አሳያቸው፤ወንግሥኩ፡፪፡አብትረ፡ለእሐቲ፡ሰመይክዋ፡ሥን፡ወለካልዕታ፡ሐብል፡እንዲል።

፷፪፡ ወዐፀዎሙ፡ውስተ፡ኲናት፡ለሕዝቡ።

ወገኖቹንም፡በሞት፡በረት፡ዘግቶ፡ተዋቸው።

ወተሀየየሙ፡ለርስቱ።

ርስቱ፡ጉልቱ፡የሚሆኑ፡እስራኤልን፡ቸል፡አላቸው።

፷፫፡ ወበልዖሙ፡እሳት፡ለወራዙቶሙ።

ጎበዛዝቱንም፡ጦር፡አጠፋቸው።

ወኢለቀሳ፡ደናግሊሆሙ።

ቈንጃጅቱ፡ደናግሉ፡በጎበዛዝቱ፡ሞት፡አላዘኑም፡ጥንቱን፡ለልማዱ፡በጎበዛዝቱ፡ሞት፡ማዘን፡ማልቀስ፡ይገባቸው፡ነበር፤ግን፡ያሚውተና፤ግን፡ይጠይቀናል፡ብለው፡ሞት፡በየደጁ፡ሁኗልና፤ግን፡ይዘን፡ግን፡ያልቅስ፡ኢሳ፡፲፫፡፲፯፡ኤር፡፭፡፲፬።

፷፬፡ ወካህናቲሆሙ፡ወድቁ፡በኲናት።

ካህናቱም፡በጦር፡ተነዋብረው፡ወደቁ፡ጥንቱን፡ለልማዱ፡የካህናት፡ሞት፡በፍልጠት፡በቁርጠት፡ነበር፡አፍኒና፡ፊንሐስን፡ያያል።

ወኢበከያ፡ዕቤራቲሆሙ።

ባልቴቶቹ፡በካህናቱ፡ሞት፡አላለቀሱም፡ጥንቱን፡ለልማዱ፡ማን፡ይምከረን፡ማን፡ይጠይቀን፡ብለው፡ማልቀስ፡ይገባቸው፡ነበረ፤ሞት፡በየደጁ፡ሁኗልና፡ማን፡ያልቅስ፤ኢዮ፡፳፯፡፲፬፡፲፭።

፷፭ ወተንሥአ፡እግዚአብሔር፡ከመ፡ዘንቃህ፡እምንዋም።

የተኛ፡ሰው፡ፈጥኖ፡እንዲነሣ፡እግዚአብሔርም፡ከሰባ፡ዘመን፡በኋላ፡ፈጥኖ፡በረድኤት፡ተነሣ።

ወከመ፡ኃያል፡ወኅዳገ፡ወይን።

ከመ፡ዘኃይሉ፡ምክረ፡ወይን፡ይላል፡የወይን፡ስካር፡እንዳለፈለት፡ሰው፤እንድም፡ከመ፡ኅዱግ፡ወይን፡ይላል፤አበርትቶ፡እንደ፡ተጣለ፡ወይን፡ባገራቸው፡ፅኑ፡መጠጥ፡አለ፡ሰው፡የጠጣው፡እንደሆነ፡ሦስት፡ቀን፡ወድቆ፡ይሰነብታል፤በሦስተኛው፡ቀን፡ጥኂና፡አግኝቶ፡ኃይል፡ተሰምቶት፡ይነሣል፤እንድም፡ወይን፡በተተከለ፡በሦስት፡ዓመት፡ዳስ፡ጥለውለት፡ያፈራል፤እንድም፡ወይን፡በክረምት፡ወድቆ፡ይከርማል፡በበጋ፡ዳስ፡ጥለው፡በዚያ፡ላይ፡ያደርጉታል፤ይለመልማል፤ያብባል፤ያፈራል፤ጌታም፡ትሩፋንን፡ይዞ፡ከባቢሎን፡ወጥቷልና።

፷፮ ወቀተለ፡ፀሮ፡በድኅሬሁ።

በእስራኤል፡ከፈረደ፡በኋላ፡በእስራ
ኤል፡ፈረደባቸው፤እንድም፡እስራ
ኤልን፡[illegible]

ሙትን ፡ እመጠመ ፡ እንድም ፡ በዘድ ኅሬሁ ፡ ይላል ፤ ወደ ፡ ኋላው ፡ በተ መለሰ ፡ ወሀ ፡ ግብፃውያንን ፡ አጠፋ ። እንድም ፡ (ወተንሥአ) ፡ ሦስት ፡ መዓ ልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃ ብር ፡ አድሮ ፡ ተነሣ ፡ (ወከመ) ፡ የወ ይን ፡ ሥክር ፡ እንዳለፈለት ፡ ሰው ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲነሣ ፡ ጌታም ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ተነሣ ፡ እንድም ፡ ከመ ፡ ኀዳግ ፡ አበርትቶ ፡ እንደ ፡ ተ ጣለ ፡ ወይን ፡ ያን ፡ ጠጥቶ ፡ ወድቆ ፡ ይሰነብታል ፤ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ፈ ጥኖ ፡ ይነሣል ፤ ጌታም ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ፈጥኖ ፡ ተነስቷልና ፤ (ወቀተለ) ፡ በአ ጻምና ፡ በሔዋን ፡ ከፈረደላቸው ፡ በ ኋላ ፡ በአጋንንት ፡ ፈረደባቸው ፡ እን ድም ፡ (በዘድኅሬሁ) ፡ በኋላው ፡ በተ ተከለ ፡ መስቀል ፡ ዲያብሎስን ፡ ድል ፡ ነሣው ፤ እንድም ፡ ተከታይ ፡ ጠላት ፡ ዲያብሎስን ፤ እንድም ፡ ታናሽ ፡ ጠ ላት ፡ ዲያብሎስን ፡ ድል ፡ ነሣው ፡ ገ መስ ፡ ደኅሪት ፡ እንዲል ።

ወወፀፆሙ ፡ ኃሣረ ፡ ዘለዓለም ።

ለዘለዓለም ፡ የሚሆን ፡ ሥጥመትን ፡ በግብፃውያን ፤ አመጣባቸው ፤ እን ድም ፡ በአጋንንት ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚ ሆን ፡ ድል ፡ መንሣትን ፡ አመጣብ ቸው ።

፷፯ ፡ ወገደጋ ፡ ለደብተራ ፡ ዮሴፍ ።

ደብተራ ፡ ዮሴፍን ፡ በረድኤት ፡ ተለ ያት ፡ እንድም ፡ እሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ነ ገድ ፡ በረድኤት ፡ ተለያቸው ፡ ምነው ፡ ዮሴፍ ፡ ወንድማቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አባታቸው ፡ ነውና ፡ እንዲህን ፡ አለ ፡ ቢሉ ፤ እንዘ ፡ ይሰፍር ፡ ሲሳየ ፡ ለአኅ ዊሁ ፡ እንዲል ፡ እንዳባት ፡ ሁኖ ፡ ልብ ስ ፡ ቀለብ ፡ እያሰጠ ፡ ያኖራቸው ፡ ነበ ርና ፤ እንድም ፡ ብሕርየ ፡ ዮሴፍን ፡ ከመዋሃድ ፡ ተለያት ።

ወኢኀረየ ፡ ለሕዝበ ፡ ኤፍሬም ።

ነገደ ፡ ኤፍሬምን ፡ ለምስፍና ፡ እንጂ ፡ ለመንግሥት ፡ አልመረጠውም ፡ እን ድም ፡ ብሕርየ ፡ ኤፍሬምን ፡ ለመዋ ሃድ ፡ አልመረጠውም ።

፷፰ ፡ ወኀረየ ፡ ለሕዝበ ፡ ይሁዳ ።

ነገደ ፡ ይሁዳን ፡ ለመንግሥት ፡ መር ጠው ፤ እንድም ፡ ብሕርየ ፡ ይሁዳን ፡ ለመዋሃድ ፡ መረጠው ፡ እንጂ ።

ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ዘአፍቀረ ።

ደብረ ፡ ጽዮንን ፡ የወደደ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ እንድም ፡ እመቤታችንን ፡ የወደደ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ እንድም ፡ የወደደ ፡ እሱ ፡ ኀረዮ ።

፷፱ ፡ ሐነፀ ፡ መቅደሶ ፡ በአርያም ።

መመስገኛው ፡ የምትሆን ፡ ቤተ ፡ መ ቅደስን ፡ በልዕልና ፡ ሠራት ፡ እንድም ፡ ማደሪያው ፡ የምትሆን ፡ እመቤታች ንን ፡ በልዕልና ፡ ፈጠራት ።

ወሣረራ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ዘለዓለም ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለዘለዓለም ፡ አፅንቶ ፡ ሠራት ፡ እንድም ፡ እመቤታችንን ፡ በንጽሕና ፡ በቅድስና ፡ ፈጠራት ።

፸ ፡ ወኀረየ ፡ ለዳዊት ፡ ገብሩ ።

አገልጋዩ ፡ ባለሟሉ ፡ ዳዊትን ፡ ለመ ንግሥት ፡ መረጠው ።

ወነሥኦ ፡ እመርዔተ ፡ አባግዒሁ ።

የበጎች ፡ መንጋ ፡ ከሚጠብቅበት ፡ ቦታ ፡ መረጠው ።

፸፩ ፡ ወተመጠዎ ፡ እምድኅረ ፡ ሐራሳት ።

አባግዕን ፡ ከሚጠብቅበት ፡ ቦታ ፡ መ ረጠው ፡ እንድም ፡ እምድኅረ ፡ ሐራ ሳት ፡ የበጎች ፡ አራሶች ፡ ከሚጠብቅ በት ፡ ቦታ ፡ እንድም ፡ እምድኅረ ፡ ሐራ ሳት) ፡ ወይፋፍኖን) ፡ ከምያስጠምዱ በት ፡ ቦታ ፡ እንድም ፡ ድኅረ ፡ ወፍረ ፡ ሐረስት ፡ ዘመን ፡ መሳፍንት ፡ ሲፈጸም ፡ ዘመን ፡ ነገሥት ፡ ሲደርስ ፡ መረጠው ፡ እንድም ፡ ከመሳፍንት ፡ በኋላ ፡ መረ ጠው ፡ ሐራሲ ፡ ዘፍጥረት ፡ ዲበ ፡ ወ ፍረ ፡ ሐረስት ፡ እንዲል ።

ከመ ፡ ይርአዮ ፡ ለያዕቆብ ፡ ገብሩ ።

ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ዘ ንድ ።

ወለእስራኤል ፡ ርስቶ ።

ርስቱ ፡ ጉልቱ ፡ የሚሆኑ ፡ ዓሥሩን ፡ ነገድም ፡ ይጠብቃቸው ፡ ዘንድ ።

፸፪ ፡ ወርዐዮሙ ፡ በየዋሃተ ፡ ልቡ ።

የዋሃትን ፡ በያዘ ፡ ልቡናው ፡ ይጠብ ቃቸው ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ ጌታ ፡ በቅ ንነቱ ፡ በኀዳጌ ፡ በቀልነቱ ፡ ይጠብቃ ቸው ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ ጠበቃቸው ።

ወመርሆሙ ፡ በጥበበ ፡ እደዊሁ ።

ዳዊት ፡ በፈሊጥ ፡ ቃሉ ፡ እንድም ፡ ጌታ ፡ አወረስከሙ ፡ ባለው ፡ ቃሉ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ ጠ በቃቸው ፡ ኤር ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።

## መዝሙር ፡ ፸፰ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ ቦኡ ፡ አሕዛብ ፡ ውስተ ፡ ርስትከ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ፡ የመ ቃብያን ፡ ዘሞዓብ ፡ የመቃብያን ፡ ዘብ ንያሚ ፡ ልጆችም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ አቤቱ ፡ እለ ፡ አንጥያኮስ ፡ ወደ ፡ ርስ ትህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገቡ ።

ወአርኰሱ ፡ ጽርሐ ፡ መቅደስከ ።

መመስገኛህ ፡ የምትሆን ፡ ኢየሩሳ ሌምንም ፡ አሳደፉ ፡ ሥዕለ ፡ ፀሐይ ፡ አቁመው ፡ መስዋዕተ ፡ እሪያ ፡ ሠው ተው ፡ ነው ፡ ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፰ ፡ ፳፩ ።

ወረሰይዋ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ከመ ፡ ልገተ ፡ ዓቃቤ ፡ ቀምሕ ።

ኢየሩሳሌምን ፡ እንደ ፡ ተክል ፡ ጠባቂ ፡ ጎጆ ፡ አደረጓት ፡ ፍሬዋን ፡ ከነሣ ፡ በ ኋላ ፡ እቃጥሏት ፡ ይሔዳል ፡ እነር ሱም ፡ ገንዘቧን ፡ ዘርፈው ፡ ሰውን ፡ ማር ከው ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ አቃጥለው ፡

2014 04 17

ሔደዋልና ፡ ይህስ ፡ አይደለም ፡ እ
ነሱ ፡ አላቃጠሉም ፡ ብሎ ፡ ተክል ፡
ጠባቂ ፡ ፍሬዋን ፡ ከነግ ፡ በኋላ ፡ ባዶ
ዋን ፡ ጥሏት ፡ ይሔዳል ፡ እነሱም ፡ ገን
ዘቧን ፡ ዘርፈው ፡ ሰውን ፡ ማርከው ፡
ሔደዋልና ፡ እንድም ፡ (እግዚአ ፡
ቦኡ) ፡ አለ ፡ መኰንን ፡ ሞዓብ ፡ ወደ ፡
ርስትህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገቡ ፡
ወአርኰሱ) ፡ መመስገኛህ ፡ የምትሆ
ን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ አሳደፉ ፡ (ወረሰ
ይዋ) ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ እንደ ፡ ተክል ፡
ጠባቂ ፡ ጎጆ ፡ አደረጓት ፡ ታሪክ ፡ ይ
ህስ ፡ እንደምነው ፡ ቢሉ ፡ መኰንን ፡
ሞዓብ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡
ወሎ ፡ ቃልቻ ፡ ድምፅ ፡ አሰምቶ ፡
ሰውን ፡ ማርኮ ፡ ገንዘቡን ፡ ዘርፎ ፡ ሲ
ሔድ ፡ መልአክም ፡ ቢሉ ፡ ያልታ
ወቀ ፡ ነቢይም ፡ ቢሉ ፡ ነቢየ ፡ ሬማ
ትም ፡ ቢሉ ፡ ተፈማህ ፡ በብርሃን ፡ አ
ሐቲ ፡ ሰዓት ፡ ወድኅረ ፡ ሀሎ ፡ ይትቤ
ቀለክ ፡ አምላክ ፡ እስራኤል ፡ አለው ፡
ምን ፡ ላድርግ ፡ አለው ፡ ተመልሰህ ፡
በእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እመን ፡ አለው ፡
እምኖ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ለሕፃናቱ ፡
ሕፃን ፡ ለሽማግሌው ፡ ሽማግሌ ፡ መ
ምር ፡ ይዞ ፡ ሔዶ ፡ በኢየሩሳሌም ፡
ልክ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አሠርቶ ፡ ኢየ
ሩሳሌም ፡ ዘሞአብ ፡ አሰኝቷታል ፡ በ
ሚሞትበትም ፡ ጊዜ ፡ ሲላስ ፡ አብያ
ፎቲኖስ ፡ የሚባሉ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡
ነበሩት ፡ አስጠርቶ ፡ ልጆቼ ፡ ፈጣሪ
ያችሁን ፡ ክዱ ፡ ለጣዖት ፡ ስገዱ ፡

የሚል ፡ ቢመጣ ፡ ፈጣሪችሁን ፡ እ
ትክዱት ፡ በሃይማኖታችሁ ፡ ሙቱ
በት ፡ ከእሥራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ በቀር ፡
ሌላ ፡ ፈጣሪ ፡ የለም ፡ ብሏቸዋልና ፡
እንዲህ ፡ አለ ። እንድም ፡ እግዚአ ፡
ቦኡ) ፡ አለ ፡ ጺሩጻይዳን ፡ ወደ ፡ ኢየ
ሩሳሌም ፡ ገቡ ፡ ወአርኰሱ ፡ ኢየሩ
ሳሌምን ፡ አሳደፏት ፡ ታሪክ ፡ ይህስ ፡
እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ሃምሳ ፡ በአ
ምሳለ ፡ አደው ፡ ሐያ ፡ በአምሳለ ፡ አ
ንስት ፡ ጣዖት ፡ አስከትሎ ፡ መጣ ፡
ወዓርገ ፡ ውስተ ፡ እዙዝ ፡ ደብር ፡
ይላል ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ ወጥተው ፡ እንደ ፡
እንበሳ ፡ ተገርመው ፡ ተቀመጡ ፡ በከ
ተማ ፡ ያሉት ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ መከራ ፡
አፅኑባቸው ፡ ስታመጡ ፡ እነሱን ፡ አ
ምጡ ፡ እያሉ ፡ ሔደው ፡ ውጡልን ፡
አሏቸው ፡ ወአርዓዩ ፡ ገጸሙ ፡ መን
ገለ ፡ ምሥራቅ ፡ ይላል ፡ ፊታቸውን ፡
ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ አዙረው ፡ ጸለዩ ፡
ሁለት ፡ መላእክት ፡ ሁነው ፡ ሲወርዱ ፡
እንዱ ፡ እንዱን ፡ በሰይፍ ፡ ሲመታ
ው ፡ ለዝያ ፡ የብርሃን ፡ አክሊል ፡ ሲወ
ርድለት ፡ አይተዋል ፡ ወዲያው ፡ እን
ትሙ ፡ ሲላስ ፡ ወአብያ ፡ ወፎጢኖስ ፡
ሀለወክሙ ፡ ከመዝ ፡ ትትኰነኑ ፡ ብሏ
ቸዋል ፡ በሰማዕትነት ፡ ሙቱ ፡ እንጂ ፡
ሲለን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ከድመት ፡ ጠጉ
ር ፡ ልመው ፡ ወርደዋል ፡ እርሱም ፡
ተቀብሎ ፡ በበትረ ፡ መሐፒል ፡ አስ
መትቶ ፡ በማኅቶተ ፡ ቁድ ፡ አቃጥሎ ፡
ለለማዳ ፡ እንበሳ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷቸ



ዋል ፡ እንበሳውም ፡ ለሰማዕታት ፡
ሰገዶ ፡ ከሱ ፡ ወገን ፡ ሰማንያ ፡ ሰው ፡
አጠፋ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዘመዶቻቸው ፡
እንፍታችሁ ፡ አልዋቸው ፡ ለሰማዕ
ትነት ፡ ሳንደርስን ፡ አይሆንም ፡ አሏ
ቸው ፡ እሱም ፡ በኑ ፡ ዘተኈረውክሙ ፡
ይላል ፡ የተመለሳችሁት ፡ መመለስ ፡
አለን ፡ አላቸው ፡ ዕንቢክ ፡ እንመለስ
ም ፡ አሉት ፡ በሰይፍ ፡ አስመትቶ ፡
ቀን ፡ ለአዕዋፍ ፡ ሌት ፡ ለአራዊት ፡
ይብሏቸው ፡ ብሎ ፡ ዓሥራ ፡ አራት ፡
ቀን ፡ አስጥሏቸዋል ፡ የማይበሏቸው ፡
ሆን ፡ ከባሕር ፡ አስጥሏቸዋል ፡ የማ
ያዘቅጣቸው ፡ ሆን ፡ አሉ ፡ ዕደው ፡
አብከዩኒ ፡ በሞቶሙ ፡ እምሕይወቶ
ሙ ፡ ብሏል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰይፍ ፡
ሰይፋቸውን ፡ መዝዘው ፡ ታዩት ።
ወጐየ ፡ ንጉሥ ፡ እማዕዘን ፡ እስከ ፡
ማዕዘን ፡ ይላል ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ አላ
ቸው ፡ ከክፋትህ ፡ ትመለስ ፡ እንደ
ሆን ፡ ተመለስ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡
እንልሃለን ፡ አሉት ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች ፡
አስገድያለሁ ፡ ቅበሩ ፡ ብሎ ፡ እዘዘ ፡
መላእክት ፡ ሠውረዋቸዋል ፡ እንድ
ም ፡ የመቃቢስ ፡ ዘብንያሚን ፡ ልጆች ፡
ለጣዖት ፡ ስገዱ ፡ ፈጣሪያችሁን ፡ ክዱ ፡
አላቸው ፡ አይሆንም ፡ አሉት ፡ በበ
ትረ ፡ መሐፒል ፡ አስመትቶ ፡ በማኅ
ቶተ ፡ ቁድ ፡ አቃጥሎ ፡ በሰይፍ ፡ አስ
መትቶ ፡ ቀን ፡ ለአዕዋፍ ፡ ሌት ፡ ለአ
ራዊት ፡ ይብሏቸው ፡ ብሎ ፡ ዓሥራ ፡
አራት ፡ ቀን ፡ አስጥሏቸዋል ፡ የማይ

በሏቸው ፡ ሆን ፡ ከባሕር ፡ አስጥሏቸ
ዋል ፡ የማያዘቅጣቸው ፡ ሆን ፡ እሉ ፡
ዕደው ፡ አብከዩኒ ፡ እምሕይወቶሙ ፡
በሞቶሙ ፡ ብሏል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡
ሰይፍ ፡ ሰይፋቸውን ፡ መዝዘው ፡ ታ
ዩት ፡ ወጐየ ፡ ንጉሥ ፡ እመዓዝን ፡
እስከ ፡ መዓዝን ፡ ይላል ፡ ምን ፡ ላድ
ርግ ፡ አላቸው ፡ ከክፋትህ ፡ ትመለስ ፡
እንደሆን ፡ ተመለስ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡
ምን ፡ እንልሃለን ፡ አሉት ፡ ደጋግ ፡
ሰዎች ፡ አስገድያለሁ ፡ ቅበሩ ፡ ብሎ ፡
አስቀብሯቸዋል ፡ ወረሰይዋ ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፡ ዘመኰንን ፡ ሞዓብን ፡ እንደ
ተክል ፡ ጠባቂ ፡ ጎጆ ፡ አደረጓት ፡ አለ ፡
የተመቸ ።

፪ ፡ ወረሰዩ ፡ አብድንቲሆሙ ፡ ለአግብርቲከ ፡
መብልዓ ፡ ለአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወሥጋሆሙኒ ፡
ለጻድቃኒከ ፡ ለአራዊተ ፡ ገዳም ።

ወረሰዩ ፡ አብድንቲሆሙ ፡ ወሥጋሆ
ሙኒ ፡ ለአግብርቲከ ፡ ወለጻድቃኒከ ፡
መብልዓ ፡ ለአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወለአ
ራዊተ ፡ ገዳም ፡ ብለህ ፡ አቅና ፡ የባለ
ሟሎችህ ፡ የወዳጆችህ ፡ የመቃብያን ፡
አስከሬናቸውን ፡ ሥጋቸውን ፡ ቀን ፡
ለአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ሌሊት ፡ ለአራዊ
ት ፡ ምግብ ፡ አድርገው ፡ እንድም ፡
ይብሏቸው ፡ ብለው ፡ ሰጡ ፡ ኤር ፡ ፯ ፡
፴ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ፡ ፬ ።

፫ ፡ ወክዐዉ ፡ ደሞሙ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ዓውዳ ፡
ለኢየሩሳሌም ።

በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ እንደኀ

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

2014 04 17

ወንሕነ ፡ ሕዝብከ ፡ ወአባግዐ ፡

ለዘላለሙ ፡ ለስምህ ፡ እንገዛልሃለን ።

መርዔትከ ፡ ንገኒ ፡ ለከ ፡ ለዓለም ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡

ጌትነትህንም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ እንነግ ሩለን ፡ እንድም ፡ ወደፊትም ፡ ለዘላ ለሙ ፡ የምንገዛልህ ፡ ጌትነትህንም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ስንነግር ፡ የምንኖር ፡ የጥንት ፡ ተገዥዎችህ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ወገ ኖችህ ፡ ነን ።

## መዝሙር ፡ ፸፱ ።

፩ ፡ ኖላዊሆሙ ፡ ለእስራኤል ፡ አፅምዕ ፡

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ፡ ያባ ቶቻቸው ፡ የትሩፋትንም ፡ ያዘክራል ፡ የጌታም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ የእስራኤል ፡ ዘሥጋ ፡ ጠባቂ ፡ የምትኾን ፡ አቤቱ ፡ ስማ ፡ አዕምዕ ፡ ያለውን ፡ ይገልጠው ።

ዘይርእዮሙ ፡ ከመ ፡ አባግዐ ፡ ዮሴፍ ፡

ዘትርእዮሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የዮሴፍ ፡ በጎች ፡ በግብፅ ፡ ይጠበቁ ፡ እንደነበረ ፡ የእስራኤል ፡ ዘሥጋ ፡ ጠባቂ ፡ ስማ ።

ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ ኪሩቤል ፡ አስተርእየ ።

ኖላዊሆሙ ፡ ለእስራኤል ፡ አፅምዕ ፡ ቢሉት ፡ በኪሩቤል ፡ አድሮ ፡ የሚኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ መጣኍ ፡ ደረስኍል ህ ፡ እንደማለት ፡ በረድኤት ፡ ተገለጸ ።

፪ ፡ በቅድመ ፡ ኤፍሬም ፡ ወብንያም ፡ ወምናሴ ።

በኤፍሬም ፡ በብንያም ፡ በምናሴ ፡ ፊት ፡ እንድም ፡ ከገነደ ፡ ኤፍሬም ፡ በተወ ለደ ፡ በኢያሱ ፡ ከነገደ ፡ ብንያም ፡ በተ ወለደ ፡ በናዖድ ፡ ከነገደ ፡ ምናሴ ፡ በተ ወለደ ፡ በጌዴዎን ፡ ምስፍና ፡ ኢያ ፡ ፵ ፡ ፲፩ ፡ አር ፡ ፴፭ ፡ ፲ ፡ ሕዝ ፡ ፴፮ ፡ ፳፱ ።

ለሙ ፡ የምንገዛልህ ፡ ጌትነትህንም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ስንነግር ፡ የምንኖር ፡ የጥንት ፡ ተገዥዎችህ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ወገ ኖችህ ፡ ነን ።

እንድም ፡ (ኖላዊሆሙ ፡) ፡ የእስራኤል ፡ ዘነፍስ ፡ ጠባቂ ፡ ስማ ፡ ዘይርእዮሙ ፡ የዮሴፍ ፡ በጎች ፡ ይጠበቁ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የእስራኤል ፡ ዘነፍስ ፡ ጠባቂያ ቸው ፡ ስማ ፡ ዘይነብር ፡ ኖላዊሆሙ ፡ ቢሉት ፡ በየማን ፡ አብ ፡ በዘባነ ፡ ኪሩ ብ ፡ የሚኖር ፡ ጌታ ፡ እነ ፡ ውእቱ ፡ ኖ ላዊ ፡ ኄር ፡ ሲል ፡ በሥጋ ፡ እንድም ፡ በመምርነት ፡ ተገለጸ ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ፡ (በቅድመ ፡ ኤፍሬም ፡) ፡ ከነገደ ፡ ኤፍ ሬም ፡ ከነገደ ፡ ብንያም ፡ ከነገደ ፡ ም ናሴ ፡ በነማው ፡ ሥጋ ፡ ተገለጸ ። እን ድም ፡ ከነገደ ፡ ብንያም ፡ ከነገደ ፡ ኤፍ ሬም ፡ ከነገደ ፡ ምናሴ ፡ በተወለዱ ፡ ሐዋርያት ፡ ፊት ፡ በመምርነት ፡ ተገ ለጠ ።

አንሥእ ፡ ኃይለከ ፡ ወነዓ ፡ አድኅነነ ።

ሥልጣንህን ፡ ረድኤትህን ፡ ገልጸህ ፡ አድነን ፡ እንድም ፡ አብ ፡ ቢሉ ፡ ወል ድን ፡ በሥጋ ፡ ገልጸህ ፡ ወልድ ፡ ቢሉ ፡ ኃይልህን ፡ በሥጋ ፡ ገልጸህ ፡ ሰው ፡ ሁነህ ፡ አድነን ።



፫ ፡ እምላክ ፡ ኃያላን ፡ ሚጠነ ።

የኃያላኑ ፡ ባለቤት ፡ አቤቱ ፡ ከባቢ ሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንድም ፡ ከሲኦል ፡ ከገሃነም ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መልሰን ።

አብርህ ፡ ገጸከ ፡ ላዕሌነ ፡ ወንድኀን ።

ገጽ ፡ ረድኤት ፡ ገጽ ፡ ምሕረትህን ፡ ገል ጸህ ፡ እንድም ፡ ሰው ፡ ሁነህ ፡ አድነን ።

፬ ፡ እግዚኦ ፡ እምላክ ፡ ኃያላን ።

አቤቱ ፡ የኃያላኑ ፡ ባለቤት ።

እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ትትመዓዕ ፡ ላዕለ ፡ ጸሎተ ፡ ገብ ርከ ።

ባሪህ ፡ ትሩፋ ፡ የጸለየውን ፡ ጸሎት ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ትጸየፈዋለህ ፡ ቸል ፡ ትለዋለህ ፡ ትነጥበዋለህ ።

፭ ፡ ወትሴስየነ ፡ ዕክለ ፡ አንብዕነ ።

ትሴስየነ ፡ ከልኁ ፡ ብሎ ፡ ዕክለ ፡ ብ ሏል ፡ እንጀ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ታሳዝነናለህ ፡ እንድም ፡ ዕንባችንን ፡ እስከ ፡ መች ፡ ትመግበናለህ ፡ እን ድም ፡ ዕንባችን ፡ የወደቀበትን ፡ እህ ል ፡ እስከ ፡ መች ፡ ትመግበናለህ ።

ወታሰትየነ ፡ አንብዓነ ፡ በመሥፈርት ።

በመሥፈርት ፡ ኃጢአታችን ፡ እስከ ፡ መች ፡ ድረስ ፡ ዕንባችንን ፡ ታጠጣና ለህ ፡ የሚበሉትን ፡ የሚጠጡትን ፡ ሲሰጧቸው ፡ እየሰደቡ ፡ እየመቱ ፡ ይሰጧቸዋል ፡ ሆድ ፡ ብሷቸው ፡ ያለቅ ሳሉ ፡ ከሚበሉት ፡ ከሚጠጡት ፡ ይወ ድቃል ፡ አብረው ፡ ይመገቡታልና ፡ እንድም ፡ እስከ ፡ መች ፡ ታሳዝነናለህ ፡ ኢሳ ፡ ፶ ፡ ፳ ፡ ሕዝ ፡ ፬ ፡ ፲፫ ።

፮ ፡ ወረሰይከነ ፡ ነገረ ፡ ለጎሮ ።

የጐረቤቶቻችን ፡ ተረት ፡ (መተረቻ) ፡ አደረግኸን ።

ወተሣለቁ ፡ ላዕሌነ ፡ ጸላዕትነ ።

ጠላቶቻችን ፡ ዘበቱብን ።

፯ ፡ እግዚኦ ፡ እምላክ ፡ ኃያላን ፡ ሚጠነ ።

አቤቱ ፡ የኃያላኑ ፡ ባለቤት ፡ ከባቢ ሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መልሰን ።

አብርህ ፡ ገጸከ ፡ ላዕሌነ ፡ ወንድኀን ። ዕቀብ ፡ ፳፯ ፡ ቁ ፡ ፲፱ ።

ገጽ ፡ ረድኤትህን ፡ አብራልን ፡ እኛም ፡ ከመከራው ፡ እንዳን ።

፰ ፡ ዓፀደ ፡ ወይን ፡ አፍለስከ ፡ እምግብጽ ።

እስራኤልን ፡ ከግብፅ ፡ አወጣህ ፡ በለ ስ ፡ ዘይቤ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ እሙ ንቱ ፡ እንዲል ።

ሰደድከ ፡ አሕዛበ ፡ ወተከልከ ፡ ኪያሃ ።

አሕዛብን ፡ ከሀገራቸው ፡ አስወጣኸ ቸው ፡ አባቶቻችንን ፡ በደረሰ ፡ መከ ራቸው ፡ በታነፀ ፡ ግምባቸው ፡ አወ ረስሃቸው ፡ ኢያ ፡ ፭ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ማቴ ፡ ፳፩ ፡ ፴፫ ፡ ማር ፡ ፲፪ ፡ ፩ ፡ ሉቃ ፳፬ ።

፱ ፡ ወጺሕከ ፡ ፍኖተ ፡ ቅድሜሃ ።

በፊቷ ፡ መንገዷን ፡ ጠርገህላት ፡ ማለት ፡

አሕዛብን ፡ እየወጉ ፡ መጥተዋልና ።

ተክልከ ፡ ሥረዊሃ ፡ ወመልአት ፡ ምድረ ።

ሥርወ ፡ አባትነቷን ፡ ተክለህ ፡ ልጆቿ

ም ፡ ምድርን ፡ ሞሉ ፡ (ልጆቻቸው) ።

፲፡ ወከደነ ፡ አድባረ ፡ ጽላሎታ ።

ሥልጣኗ ፡ ከአሕዛብ ፡ በላይ ፡ ኾኖ ፡

እንድም ፡ (ዓፀደ ፡ ወይን) ፡ ምእመና

ን ፡ ከሲኦል ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አወጣህ ፤

ወሰመያ ፡ ለሲኦል ፡ ግብጸ ፡ እንዲል ፡

(ሰደድከ) ፡ አጋንንትን ፡ ከሰው ፡ ልቡ

ና ፡ አስወጥተህ ፡ ሰደድኻቸው ። ምእ

መናን ፡ በገነት ፡ በመንግሥት ፡ ሰማ

ያት ፡ ሠራኻቸው ፡ (ወጼሕከ) ፡ በየ

ጕዳናው ፡ እየሆኑ ፡ የሚያስቱ ፡ አጋ

ንንትን ፡ አጠፋኻቸው ፤ (ተከልከ) ፡ ሐ

ዋርያትን ፡ በመምርነት ፡ ተክልኻቸ

ው ፡ ምእመናን ፡ እየተማሩ ፡ ምድ

ርን ፡ መሉ ፡ (ወከደኑ) ፡ ሥልጣናቸው ፡

ከአሕዛብ ፡ ከአጋንንት ፡ በላይ ፡ ኾነ ፡፡

ወአዕፀ ፡ ቄድሩ ፡ ዘመ ፡ ኀርዎ ፡ እግዚአብሔር ።

ልጆቿም ፡ የግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡

እንደ ፡ ሆኑ ፡ እንደ ፡ አብርሃም ፡ እንደ ፡

ይስሐቅ ፡ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ ናቸው ።

፲፩፡ ወሰፍሐ ፡ አዕፁቂሃ ፡ እስከ ፡ ባሕር ።

አዕፁቂሃና ፡ አዕፁቂሃ ፡ አንድ ፡ ወገ

ን ፡ ልጆቿም ፡ ከጤግሮስ ፡ እስከ ፡ ኤፍ

ራጥስ ፡ ደረሱ ።

ወእስከ ፡ አፍላግ ፡ ሠርፃ ።

ከዳን ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤህ ፡ ደረሱ ፤

ኢ.ሳ ፡ ፳፱ ፡ ፲፯ ።

፲፪፡ ለምንት ፡ ትንሥት ፡ ፀቈና ።

እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነበር ፡ አጥሯን ፡

ለምን ፡ ታፈርሰዋለህ ፡ እንድም ፡ ረድ

ኤቷን ፡ ለምን ፡ ትነሣታለህ ።

ወይበልዓ ፡ ኵሉ ፡ ኃላፊ ፡ ፍኖት ።

ጠጭ ፡ ወራጅ ፡ አሕዛብ ፡ ለምን ፡ ይማ

ርኳታል ፡ አሕዛብ ፡ እስራኤልን ፡ ከማ

ረኩ ፡ በኋላ ፡ እንዋል ፡ እንደር ፡ እያ

ሉ ፡ ምና ፡ ኃላፊ ፡ ፍኖት ፡ አላቸው ፡

እንድም ፡ ፈርዖን ፡ ኒካው ፡ እግረ ፡ መን

ገዱን ፡ ማርኳቸዋልና ፡ እንድም ፡ (ወ

አዕፁቂሃኒ) ፡ የምእመን ፡ መንገዶቿ ፡

እግዚአብሔር ፡ መርጦ ፡ እንደ ፡ ሾማ

ቸው ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ ናቸው ፡

(ወሰፍሐ) ፡ ከውቅያኖስ ፡ እስከ ፡ ውቅ

ያኖስ ፡ ደረሱ ፡ (ወእስከ ፡ አፍላግ) ፡

ከአድማስ ፡ እስከ ፡ አድማስ ፡ ደረሱ ፡

ሰው ፡ ያለበትን ፡ ያያል ፡ (ለምንት) ፡

ልጅነቷን ፡ ሰጥተህ ፡ ለምን ፡ ትነሣ

ለህ ፡ (ወይበልዓ) ፡ መናፍቅ ፡ ለምን ፡

ያስታታል ።

፲፫፡ ወአርኰሳ ፡ ሐሬውያ ፡ ሐቅል ።

የበረኃ ፡ እሪያ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ይማ

ርኳታል ፡ እንድም ፡ መናፍቅ ፡ ለም

ን ፡ ያስታታል ።

ወተርእያ ፡ እንስሳ ፡ ገዳም ፡ ሆሴ ፡ ፪ ፡ ፲፱ ።

የበረኃ ፡ እንስሳ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ይማ

ርኳታል ፡ እንድም ፡ መናፍቅ ፡ ያስ

ታታል ፡ ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፭-፯ ፡ ፳፯ ፡ ፲ ።



፲፬፡ አምላከ ፡ ኃያላን ፡ ተመየጥ ።

የኃያላን ፡ ባለቤት ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡

ምሕረት ፡ ተመለስ ፡ ተመለሳ ፡ እን

ድም ፡ ተመየጥን ፡ ተመለስልን ።

ሐውጽ ፡ እምሰማይ ፡ ወርኢ ።

ከሰማይ ፡ ሁነህ ፡ በዓይን ፡ ምሕረት ፡

እይ ፡ ተመልከት ፡ እንዲህ ፡ አይተህ ፡

ተመልክተህ ፡ በረድኤት ፡ ጎብኘ ።

ወተሣሃላ ፡ ለዛ ፡ ዓፀደ ፡ ወይን ።

ይህችን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡

የምትኾን ፡ ቤተ ፡ እስራኤልን ፡ ከሰባ ፡

ዘመን ፡ በኋላ ፡ ይቅር ፡ በላት ፡ እን

ድም ፡ የክርስቶስ ፡ ማደሪያ ፡ የምት

ሆን ፡ ምዕመን ፡ ከምስት ፡ ሺህ ፡ አም

ስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡

ሁነህ ፡ ይቅር ፡ በላት ።

፲፭፡ አስተናሥኣ ፡ ወአፅንዓ ፡ ዘተከለት ፡ የማንከ ።

ሥልጣንህ ፡ የፈጠረቻት ፡ ቤተ ፡ እስ

ራኤልን ፡ በረድኤት ፡ ምእመንን ፡

በልጅነት ፡ አፅንተህ ፡ አነሣሣት ።

በወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘአፅናዕከ ፡ ለከ ።

በኢያሱ ፡ አድረህ ፡ ያፀናሃት ፡ እስ

ራኤልን ፡ እንድም ፡ በልጅህ ፡ ህል

ው ፡ ሁነህ ፡ ያፀናኻት ፡ ምእመን ፤

ዮሐ ፲፭ ፡ ፩-፥ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ።

፲፮፡ ለውዒት ፡ በእሳት ፡ ወምልሕት ።

ነቅለው ፡ በእሳት ፡ ያቃጠሏት ፡ ወይ

ን ፡ ሲተክል ፡ በእሳት ፡ ለብልበ ፡

ነውና ፡ እንድም ፡ ምልሕት ፡ ይቀድ

ማል ፡ ከገሯ ፡ አስወጥተው ፡ የሰደዱ

ዋት ፡ ለውዒት ፡ በእሳት ፡ መከራ ፡

ያቃጠሏት ፡ ቤተ ፡ እስራኤልን ፡ በረ

ድኤት ፡ አፅናት ፡ እንድም ፡ እለ ፡

መልሕዋ ፡ ወእለ ፡ አውዓይዋ ፡ ቤተ ፡

እስራኤልን ፡ ከገሯ ፡ አስወጥተው ፡

የሰደዱዋት ፡ በእሳት ፡ መከራ ፡ ያቃ

ጠሏት ፡ ሰዎች ።

እምተግሣፀ ፡ ገጽከ ፡ ይትኀጐሉ ።

ገጽ ፡ መዓትህ ፡ ከመገለጽ ፡ የተነሣ ፡

ይጠፋሉ ፡ ይጥፉ ፡ እንድም ፡ (ለው

ዒት) ፡ ከገነት ፡ አስወጥተው ፡ የሰደ

ዱዋት ፡ በእሳተ ፡ ገሃነም ፡ ያቃጠሏት ፡

ምእመንን ፡ በልጅህ ፡ አፅናት ፡ እን

ድም ፡ (እለ ፡ መልሕዋ) ፡ ምእመንን ፡

ከገነት ፡ አስወጥተው ፡ የሰደዱዋት ፡

በእሳተ ፡ ሲኦል ፡ ያቃጠሏት ፡ አጋን

ንት ፡ (እምተግሣፀ ፡ ገጽከ) ፡ ሰው ፡

ከመሆንህ ፡ የተነሣ ፡ ይጠፋሉ ፡ ይጥፉ ።

፲፯፡ ለይኩን ፡ ዕዴከ ፡ ላዕለ ፡ ብእሲ ፡ የማንከ ።

ኀይልህ ፡ በዘሩባቤል ፡ እንድም ፡ ል

ጅህ ፡ በሥጋ ፡ ይደር ፡ ብእሲ ፡ በው

ስተ ፡ ብእሲ ፡ እንዲል ።

በወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘአፅናዕከ ፡ ለከ ።

አንድ ፡ ወገን ፡ እንዳስለፈው ፡ ቁ ፡ ፲፭ ።

፲፰፡ ወኢንርኀቅ ፡ እምኔከ ።

ከንተ ፡ በረድኤት ፡ አንራቅ ።

አሕይወነ ፡ ወንጸውዕ ፡ ስመከ ።

ስምህን ፡ እንጸራ ፡ ዘንድ ፡ አድነን ፡

እንድም ፡ አድነንና ፡ ስምህን ፡ እን

ጽራ ፡ እንድም ፡ (አሕየወነ) ፡ ከመከ

2014 04 17

ራው ፡ አድነን ፡ (ወንዒውዕ) ፡ እን ዲህ ፡ የሆን ፡ እንደሆን ፡ እኛም ፡ ስም ህን ፡ እንጠራለን ።

፲፱ ፡ እግዚኦ ፡ አምላክነ ፡ ኃያል ፡ ሚጦነ ።

አቤቱ ፡ የኃያላኑ ፡ ባለቤት ፡ ከባቢ ሎን ፡ አውጣን ።

አብርህ ፡ ገጸከ ፡ ላዕሌነ ፡ ወንድኅን ።

ገጼ ፡ ምሕረትህን ፡ አብርተህ ፡ ከመ ከራው ፡ አድነን ፡ እስራኤል ፡ የወጡ ፣ በዘሩባቤል ፡ በኤርምያስ ፡ በክልዕ ፡ ስገሬ ፡ ነውና ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላ ልሶ ፡ ተናገረው ፡ ቁ ፡ ፫ ፡ ፯ ።

## መዝሙር ፡ ፹ ።

፩ ፡ ተፈሥሑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘረድአነ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ በረዳን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምናችኍ ፡ ደስ ፡ ይበላችኍ ፡ ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፯ ።

ወየብቡ ፡ ለአምላከ ፡ ያዕቆብ ።

ለያዕቆብም ፡ ፈጣሪ ፡ ምሥጋና ፡ አቅ ርቡ ።

፪ ፡ ንሥኡ ፡ መዝሙረ ፡ ወሀቡ ፡ ከበሮ ።

በገናውን ፡ ያዙ ፡ ቀንደውንም ፡ ለም ያውቁ ፡ ለሚመቱ ፡ ስጡ ።

መዝሙር ፡ ሐዋዝ ፡ ዘምስለ ፡ መሰንቆ ።

በገና ፡ ከመሰንቆ ፡ ጋራ ፡ ስምስጋና ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነውና ።

፫ ፡ ንፍሑ ፡ ቀርነ ፡ በሠቀ ፡ ሠርቅ ።

በሠርቀ ፡ ወርኅ ፡ ነጋሪት ፡ ምቱ ።

በእምርት ፡ ዕለት ፡ በዓልነ ።

የተረዳች ፡ በምትሆን ፡ በዓላችን ፡ እን ድም ፡ (ተፈሥሑ) ፡ ከሁለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሁኖ ፡ በረዳን ፡ በእ ግዚአብሔር ፡ እምነን ፡ በተሠራል ን ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ይበለን ፡ መጽአ ፡ ወረደአሙ ፡ ለዕለ ፡ ይትዔገሉሙ ፡ ሰይጣን ፡ እስመ ፡ በዘ ፡ አመከርዎ ፡ አሕመምዎ ፡ ከህለ ፡ እንከ ፡ ረድኤ ቶሙ ፡ ለሕሙማን ፡ ወረድአኒ ፡ ዘ ከመ ፡ ምክረ ፡ ፈቃዱ ፡ እንዲል ፡ ወየ ብቡ) ፡ ለያዕቆብም ፡ ፈጣሪ ፡ ምሥ ጋና ፡ አቅርቡ ፡ ንሥኡ ፡ ወንጌልን ፡ ያዙ ፡ ወሀቡ) ፡ አሪትን ፡ ለአሪታው ያን ፡ ተውላቸው ፡ መዝሙር) ፡ ወን ጌል ፡ ከአሪት ፡ ጋራ ፡ የተስማማ ፡ ሕግ ፡ ነውና ፡ ንፍሑ) ፡ በዕለተ ፡ ሆሣእና ፡ በእለተ ፡ ትንሣኤ ፡ ነጋሪት ፡ ምቱ ፡ በእምርት) ፡ የተረዳች ፡ በምትሆን ፡ በዓላችን ፡ ኤር ፡ ፬ ፡ ፳ ።

፬ ፡ እስመ ፡ ሥርዓቱ ፡ ለእስራኤል ፡ ውእቱ ።

የእስራኤል ፡ ዘሥጋ ፡ ሥርዓቱ ፡ እን ድም ፡ የእስራኤል ፡ ዘነፍስ ፡ ሥር ዓቱ ፡ ይህ ፡ ነውና ።



ወፍትሑ ፡ ለአምላከ ፡ ያዕቆብ ።

የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ፈርዖ ፡ የሠራው ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነውና ፡ ኢሳ ፡ ፵፰ ፡ ፰ ።

፭ ፡ ዘአቀመ ፡ ስምዐ ፡ ለዮሴፍ ።

ለዮሴፍ ፡ የሠራለት ፡ ትምህርቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እንድም ፡ ለዮሴፍ ፡ እም ልክነቱን ፡ የሠራለት ፡ የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ፈርዖ ፡ የሠራው ፡ ሕግ ፡ ነውና ።

አመ ፡ የሐውር ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ።

ወደ ፡ ግብፅ ፡ በሔደ ፡ ጊዜ ፡ የሠራለት ።

ወሰምዐ ፡ ልሳነ ፡ ዘኢየአምር ።

የማያውቀውን ፡ ቋንቋ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ።

፮ ፡ ወሜጠ ፡ ዘባኖ ፡ እምሕራማቲሆሙ ።

ዘባለ ፡ ልቡናውን ፡ ከመስጊዳቸው ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ።

ወተቀንያ ፡ እደዊሁ ውስተ ፡ አክፋር ።

በጅሮንድነት ፡ ምስለኔነት ፡ ተሹሞ ፡ እህል ፡ አሠፋሪ ፡ ኾነ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ መኳንንቱ ፡ ዮሴፍን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ እንሒድ ፡ ያሉት ፡ እንደሆነ ፡ መቼ ፡ ያደርሰኛል ፡ እያለ ፡ እንቅብ ፡ ቅርጫት ፡ ሲያነሣ ፡ ሲጥል ፡ ይውል ፡ ነበርና ።

፯ ፡ በምንዳቤከ ፡ ጸዋዕከኒ ፡ ወአድኀንኩከ ።

በመከራህ ፡ ቀን ፡ ለመንከኝ ፡ እኔም ፡ ከመከራህ ፡ አዳንኹህ ።

ወተሠጠውኩከ ፡ በኅውሎ ፡ ኅቡዕ ።

በረቂቅ ፡ እንድም ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ተነጋገርኹህ ።

ወአመከርኩከ ፡ በኀበ ፡ ማየ ፡ ቅሥት ።

ፀብ ፡ ክርክር ፡ ባለበት ፡ ወሀ ፡ ተፈታ ተንኹህ ።

፰ ፡ ስምዐኒ ፡ ሕዝብየ ፡ ወእንግርከ ፡ እስራኤል ፡ እስምዕ ፡ ለከ ።

ስምአኒ ፡ ሕዝብየ ፡ እስራኤል ፡ እን ግርከ ፡ ወእሰምዕ ፡ ለከ ፡ ብለህ ፡ እ ቅና ፡ ወገኔ ፡ እስራል ፡ እነግርሃለኍ ፡ እስተምርኻለኍና ፡ ምክሬን ፡ ትምር ቱን ፡ ስማኝ ፡ እንድም ፡ (ስምዓኒ) ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡ ስማኝ ፡ ባትሰማኝ ፡ ግን ፡ እገኝብሃለኍ ፡ (እሰምዕ ፡ ብከ) ።

፱ ፡ እመሰ ፡ ሰማዕከኒ ፡ ኢይከውነከ ፡ አምላክ ፡ ግብት ።

እሰምዕ ፡ ብከ ፡ ማለቱ ፡ ባትሰማኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሰማኻኝ ፡ የድንገት ፡ አምላክ ፡ ጣዖት ፡ አልኾንብህም ፡ ጣዖት ፡ የተገኘ ፡ ከሲሩህ ፡ ወዲህ ፡ ነውና ፡ አምላክ ፡ ግብት ፡ አለው ፡ እንድም ፡ ጢት ፡ ሠርተው ፡ ለማታ ፡ መስገድ ፡ ያደርሱታልና ።

ወኢትስግድ ፡ ለአምላክ ፡ ነኪር ።

ልዩ ፡ ለሚሆን ፡ ለጣዖት ፡ አትስገድ ።

፲ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አም ላክከ ።

ፈጣሪህ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝና ።

ዘአውፃእኩከ ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ።

ከግብፅ ፡ ያወጣኹህ ።

2014 04 17

አርኅብ ፡ አፉከ ፡ ወእመልኦ ፡ ለከ ፡ ዘዘ ፡ ፳ ፡ ፪ ፡ ።

ለምንኛና ፡ የለመንኸኝን ፡ ሁሉ ፡ እሰ ጥሃለሁ ፡ አደርግልሃለሁ ።

፲፩ ፡ ወኢሰምዑኒ ፡ ሕዝብየ ፡ ቃልየ ፡ ወእስራ ኤልኒ ፡ ኢያፅምዑኒ ።

ሕዝብየ ፡ እስራኤል ፡ ኢሰምዑኝ ፡ ወኢያዕምዑኝ ፡ ቃልየ ፡ ብለህ ፡ አቅና ፡ ወገኖቼ ፡ እስራኤል ፡ ምክሬን ፡ ትምርቴን ፡ ፈጽመው ፡ አልተቀበሉኝም ፡ ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፳፱ ፡ ኤር ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።

፲፪ ፡ ወፈነውኩ ፡ ሎሙ ፡ በከመ ፡ ምግባሮሙ ።

የሚቀድመው ፡ አለ ።

ወሖሩ ፡ በሕሊናየ ፡ ልቦሙ ።

በልባቸው ፡ ሐሳብ ፡ በሠሩት ፡ ጣዖት ፡ ኃጢአት ፡ ፀንተው ፡ ኖሩ ፡ እኔም ፡ እንኪያስ ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ መከራውን ፡ እንድም ፡ ፍዳውን ፡ አመ ጣሁባቸው ፡ ኤር ፡ ፯ ፡ ፳፬ ፡ ፲፩ ፡ ፰ ። ግብ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯ ፡ ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ።

፲፫ ፡ ሶበሰ ፡ ሰምዑኒ ፡ ሕዝብየ ፡ ቃልየ ።

ወገኖቼ ፡ ትምርቴን ፡ ተቀብለውኝ ፡ ቢሆን ።

ወእስራኤልኒ ፡ ሶበ ፡ ሖሩ ፡ በፍኖትየ ።

ሕዝብየ ፡ እስራኤል ፡ ወገኖቼ ፡ እስራኤል ፡ በሕጌ ፡ ፀንተው ፡ ምክሬን ፡ ትምርቴን ፡ ተቀብለውኝ ፡ ቢሆን ።

፲፬ ፡ እምአኅሠርክዎሙ ፡ ለዘ ፡ ሎሙ ፡ ጸላእቶሙ ።

ጠላቶቻቸውን ፡ ሁሉ ፡ ተሰቅዩ ፡ በጠ ፋሁላቸው ፡ ነበር ።

ወእምወደይኩ ፡ እዴየ ፡ ዲበ ፡ እለ ፡ ይሣቅይዎሙ ።

ሥቃይ ፡ በሚያፀኑባቸው ፡ ላይ ፡ እጄ ፡ መዓቱን ፡ በመጣሁባቸው ፡ ነበር ።

፲፭ ፡ ጸላእቱሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሐሰውዎ ።

የእግዚአብሔርስ ፡ ጠላቶቹ ፡ ሲያድኑ ፡ አያድኑም ፡ ሲታደግ ፡ አይታደ ግም ፡ አሉት ።

ወይከውን ፡ ጊዜሆሙ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

ሰውን ፡ የሚያጠፉበት ፡ ጊዜያቸው ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ሰውን ፡ አጥፍተው ፡ ወደኋላ ፡ የሚቀሩ ፡ ስለ ሆነ ፡ እንድም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ሲገ ድሉ ፡ ይኖራሉና ፡ እንድም ፡ እራሳ ቸው ፡ የሚጠፉበት ፡ ጊዜ ፡ ለዘላለም ፡ ነው ፡ ማለት ፡ እንደነሱ ፡ ያለ ፡ ሳይ ሞት ፡ ሳይተክ ፡ አይውልም ፡ አያድር ምና ፡ እንድም ፡ ፍዳቸው ፡ ለዘላለም ፡ ነው ።

፲፮ ፡ ወሴሰዮሙ ፡ ሥብሐ ፡ ሥርናይ ።

ያፈራውን ፡ የተፈተገውን ፡ ልጸ ፡ ጉ ርዶ ፡ የወጣለትን ፡ ስንዴ ፡ መገባቸው ።

ወእፅገቦሙ ፡ መዓረ ፡ እምኰኵሕ ።

ከዋሻ ፡ እንድም ፡ ከማገኝ ፡ የተገኘው ን ፡ ማር ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ፡ እን ድም ፡ ዕናቱን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እን ድም ፡ ብዕለ ፡ አሕዛብን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ።

እንድም ፡ ወሴሰዮሙ ፡ ሥብሐ ፡ ሥር ናይን ፡ ሥጋውን ፡ መገባቸው ፡ (ወእ ፅገቦሙ ፡ መዓረ ፡ እምኰኵሕ) ፡ ደሙ ንም ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ፡ ወ ኰኵሕሰ ፡ ክርስቶስ ፡ ውእቱ ፡ እን ዲል ።



ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለአብና ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዘላለሙ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸ ዋል ። አሜን ።

## መዝሙር ፡ ፹፩ ።

፩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቆመ ፡ ውስተ ፡ ማኅበረ ፡ አማልክት ።

ዘለፋ ፡ ካህናት ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ በካህናት ፡ ጉባዔ ፡ ተገልጾ ፡ ተቀመጠ ፡ በበጎዎች ፡ ካህናት ፡ አድሮ ፡ ክፎዎች ፡ ካህናትን ፡ ለመዝለፍ ፡ የሚያረዳ ፡ ሰው ፡ በይባባይ ፡ ቆሞ ፡ እንዲያረዳ ፡ በዚያ ፡ መስሎ ፡ ተናገረ ፡ ኢሳ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።

ወይኴንን ፡ በማዕከለ ፡ አማልክት ።

ተገልጾም ፡ በበጎዎች ፡ ካህናት ፡ አድ ሮ ፡ ክፉዎች ፡ ካህናትን ፡ ይዘልፋል ፡ በክፉዎች ፡ ካህናት ፡ ይፈርዳል ።

፪ ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ትኴንኑ ፡ ዓመፃ ።

እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ በሐሰት ፡ ትፈርዳ ላችኁ ፡ ማማለጃ ፡ ትበላላችኁ ፡ እያለ ።

ወታደልዉ ፡ ለገጸ ፡ ኃጥኣን ።

ከብቱ ፡ ለበዛ ፡ ፈቱ ፡ ለወዛ ፡ ለባለፀጋ ፡ ታደላላችኁ ፡ እያለ ፡ እምትሁብ ፡ ለኃ ጥእ ፡ ሀብ ፡ ለጻድቅ ፡ እንዲል ።

እንድም ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ሐሰት ፡ ትፈርዳላችኁ ፡ ማማለጃ ፡ ትበላላች ኁ ፡ (ወታደልዉ ፡) ፈቱ ፡ ለወዛ ፡ ከ ብቱ ፡ ለበዛ ፡ ለባለጠጋ ፡ ታደላላችኁ ፡ ብለህ ፡ ከዚህ ፡ እሥር ፡ ኤር ፡ ፭ ፡ ፳፰ ።

፫ ፡ ፍትሑ ፡ ለንዴይ ፡ ወለዕጓለ ፡ ማውታ ።

ይህንስ ፡ ትታችኁ ፡ ለደኃ ፡ እናት ፡ አባቱ ፡ ለሞቱበት ፡ ልጅ ፡ ፍረዱ ።

ወአጽድቁ ፡ ግፉዓ ፡ ወምስኪነ ፡ ዘዘ ፡ ፳፫ ፡ ፩-፫ ። ዘሌ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ ።

ለጦም ፡ አዳሪ ፡ ለተበደለው ፡ እውነ ት ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ ፍረዱ ፡ ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ።

፬ ፡ ወአድኅኑ ፡ ባሕታዌ ፡ ወነዳየ ።

ለችጋረኛው ፡ ለብቸኛው ፡ እውነት ፡ ፈርዳችኁ ፡ አድኑ ።

ወእንግፍዎሙ ፡ እምእደ ፡ ኃጥኣን ።

ከባለፀጎች ፡ እጅ ፡ አድኗቸው ።

2014 04 17

፭ ፡ ኢያእመሩ ፡ ወኢለበዉ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ የሐውሩ ።

ቢመክሯቸው ፡ ቢያስተምሯቸው ፡ አላወቁም ፡ ልብ ፡ አላደረጉም ፡ (ወውስተ ፡ ጽልመት) ፡ በድንቁርና ፡ ይኖራሉ ፡ እንድም ፡ (ከመ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት) ፡ ይላል ፡ ቢመክሯቸው ፡ ቢያስተምሯቸው ፡ እናውቅ ፡ ልብ ፡ እናደርግ ፡ ብለው ፡ በገሃነም ፡ እንዲኖሩ ፡ አያውቁም ፡ ልብ ፡ አያደርጉም ፡ እንድም ፡ (እንዘ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት) ፡ ይላል ፡ በድንቁርና ፡ እየኖሩ ፡ አላወቁም ፡ ልብ ፡ አላደረጉም ፡ እንድም ፡ (ኢይአሚሮሙ ፡ ወኢለቢዎሙ) ፡ የሐውሩ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት) ፡ ቢመክሯቸው ፡ ቢያስተምሯቸው ፡ እናውቅ ፡ ልብ ፡ እናደርግ ፡ ብለው ፡ በገሃነም ፡ ይኖራሉ ።

ወያንቀለቅሉ ፡ ኵሉ ፡ መሠረታተ ፡ አድባር ።

የንጉሥታቱ ፡ መሠረት ፡ የሚሆኑ ፡ ካህናት ፡ ሁሉ ፡ ጠፉ ።

፮ ፡ አንሰ ፡ እቤ ፡ አማልክት ፡ አንትሙ ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፴፬ ።

እኔስ ፡ አማልክት ፡ ዘበፀጋ ፡ ብያችኍ ፡ ነበር ።

ወደቂቀ ፡ ልዑል ፡ ኵልክሙ ። ዘፀ ፡ ፯ ፡ ፩ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፬ ።

መላችኍ ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ብያችኍ ፡ ነበር ።

፯ ፡ አንትሙሰ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ትመውቱ ።

ለካ ፡ እላንተስ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ትሞታላችኍ ።

ወከመ ፡ ፩ ፡ እመላእክት ፡ ትወድቁ ።

ከለቆች ፡ ተለይቶ ፡ እንደ ፡ ተጎዳ ፡ እንደ ፡ ፩ ፡ ትጐዳላችኍ ።

እንድም ፡ እቤ ፡ እኔስ ፡ አማልክት ፡ ዘበፀጋ ፡ ብያችኍ ፡ ነበር ፡ (ወደቂቀ ፡ ልዑል) ፡ መላችኍንም ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ብያችኍ ፡ ነበር ፡ (አንትሙሰ) ፡ ለካ ! እላንተስ ፡ እንደ ፡ ረአይት ፡ ትሞታላችኍ ፡ ወከመ ፡ ፩) ፡ ከለቆቹ ፡ ተለይቶ ፡ እንደ ፡ ተጎዳ ፡ እንደ ፡ ስማግያስ ፡ ትጐዳላችኍ ፡ ታሪክ ፡ ይህስ ፡ እንደምንድ ነው ፡ ቢሉ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ንጽሐ ፡ ጠብቀው ፡ ከሴት ፡ ርቀው ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እያሉ ፡ እያመሰገኑ ፡ ምስጋናቸው ፡ ምግብ ፡ ኍኗቸው ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ ይኖራሉ ፡ ደቂቀ ፡ ቃየልም ፡ ብዙ ፡ ኀብረ ፡ ኃጢአት ፡ እየሠሩ ፡ በምድረ ፡ ፋይድ ፡ ይኖራሉ ፡ ዝሙትን ፡ እንደ ፡ እንስሳት ፡ በደባባይ ፡ ይሠሩት ፡ ነበር ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ ካሉ ፡ ከደቂቀ ፡ ሴት ፡ እንዱ ፡ ለመፍቅደ ፡ ደብር ፡ ደቂቀ ፡ ቃየል ፡ ካሉበት ፡ ሔዶ ፡ እንደ ፡ እንስሳት ፡ እስበሳቸው ፡ ሲንጠለጠሉ ፡ ዓይቶ ፡ ይልቁንም ፡ አለቃይቱ ፡ ኑኄም ፡ ትባላለች ፡ ከበሮ ፡ ይዛ ፡ እንደ ፡ ዋነተኛ ፡ መኻል ፡ ለመሐል ፡ እስክስክ

ስታ ፡ ስትወርድ ፡ ዓይቶ ፡ በሐፀ ፡ ገዝሙት ፡ ተነደፈ ፡ ሔዶ ፡ ወንድሞቹን ፡ የኛማ ፡ ኑሮ ፡ ምን ፡ ኑሮ ፡ ይባላል ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ከምስጋና ፡ በቀር ፡ ያገኘነው ፡ ያለ ፡ ሥጋችን ፡ ከጥንቷ ችን ፡ ተጣብቆ ፡ ተጣግቶ ፡ ኑሮን ፡ ደቂቀ ፡ ቃየል ፡ ይኖሩታል ፡ እንጂ ፡ አላቸው ፡ ከዝያው ፡ ሁነው ፡ አቈል ቍለው ፡ ቢመለከቱ ፡ እንደ ፡ እንስሳት ፡ እሰበሳቸው ፡ ሲንጠለጠሉ ፡ ዓይተው ፡ ንዑ ፡ ንረድ ፡ ወንርዓይ ፡ አሐተ ፡ አሐተ ፡ ወንስድ ፡ አሐተ ፡ አሐተ ፡ አሉ ፡ አለቃቸው ፡ ስማግዝያስ ፡ ይባላል ፡ ተው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ላታደርጉት ፡ ለምን ፡ ትዋሻላችኍ ፡ አላቸው ፡ እንተ ፡ ብትተወው ፡ እኛ ፡ እንተወውም ፡ አሉት ፡ እንግድያስ ፡ አታደርጉትም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የምታደርጉትስ ፡ ከሆነ ፡ እኔ ፡ ፈጻዬሃ ፡ ለዛቲ ፡ አበሳ ፡ በዚህ ፡ የመጣውን ፡ ፍዳ ፡ እኔ ፡ እቀበለዋለሁ ፡ አላቸው ፡ እንድ ፡ ሁነው ፡ ወረዱ ፡ በኃጢአቱ ፡ እሱ ፡ ፀንተውበታል ፡ ከነዚህም ፡ የሚወለድ ፡ ረጅሙ ፡ በፀሐይ ፡ አብስሎ ፡ የሚመገብ ፡ አጭሩ ፡ በሽብሬ ፡ ጥላ ፡ የሚውል ፡ ሁኗል ፡ ከነዚህም ፡ እንዱ ፡ ረአይት ፡ ይባላል ፡ ከፀሐይ ፡ ጋሬ ፡ ሲሮጥ ፡ ውሎ ፡ ቀድሟት ፡ መስኮቷን ፡ ያዘባት ፡ ስትገባ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ብታቃጥለው ፡ ለቀቀላት ፡ ገባች ፡ በሱም ፡ ሐሩር ፡ ፀናበት ፡ እንድም ፡ መልእኩ ፡ ድኝ ፡ አቅምሶታል ፡ ቢያቃጥለው ፡ ከውቅያኖስ ፡ ወህ ፡ ጠጥቶ ፡ ስንዝር ፡ እንጐሎታል ፡ ቅትት ፡ አድርጎ ፡ ነፍቶ ፡ የገያስኼደው ፡ ሆን ፡ መልአኩ ፡ በሰይፍ ፡ በጣለት ፡ ከሆዱ ፡ የወጣ ፡ ወህ ፡ ሰባ ፡ ሰማንያ ፡ ሰው ፡ አጥፍቷል ፡ ከውቅያኖስም ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ መልቷልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

እንድም ፡ (አንሰ ፡ እቤ) ፡ እኔስ ፡ አማልክት ፡ ዘበፀጋ ፡ አዕይንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብያችኍ ፡ ነበር ፡ ወደቂቀ) ፡ መላችኍንም ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ብያችኍ ፡ ነበር ፡ እንትሙስ ፡ ለካ) ፡ እላንተስ ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ ትሞታላችኍ ፡ (ትጠፋላችኍ) ፡ ወከመ ፡ ፩) ፡ ከሐዋርያት ፡ ተለይቶ ፡ እንደ ፡ ተጎዳ ፡ እንደ ፡ ይሁዳም ፡ ትጎዳላችኍ ።

እንድም ፡ (አንትሙ) ፡ ለካ ፡ እላንተስ ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ ትሞታላችኍ ፡ (ወከመ ፡ ፩) ፡ ከመላእክትም ፡ ተለይቶ ፡ እንደ ፡ ተጎዳ ፡ እንደ ፡ ዲያብሎስ ፡ ትጐዳላችኍ ።

፰ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ወኰንና ፡ ለምድር ።

አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሣ ፡ ከህናት ፡ በድለዋልና ፡ ምድርን ፡ ፍረድባት ፡ ማለት ፡ የዘሩባትን ፡ እንዳትበቅል ፡ የተከሉባትን ፡ እንዳታጸድቅ ፡ አድርጋት ።

እስመ ፡ አንተ ፡ ትወርስ ፡ በኵሉ ፡ አሕዛብ ።

ትንግሥ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በሬቱ ፡ መዓዝን ፡ ባሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሠ



2014 04 17

ልጥነህ ፡ ትኖራለህና ፡ እንድም ፡ ትወ
ርስ ፡ ዠሎ ፡ አሕዛበ ፡ አሕዛብን ፡

ሁሉ ፡ ትገዛለህና ፡ ወያወርስ ፡ በዠሉ ፡
እንዲል ።

## መዝሙር ፡ ፹፪ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ መኑ ፡ ይማስለከ ፡ መዝ ፡ ፹፰ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናገሮታል ፡ አ
ቤቱ ፡ እንዳንት ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፡
ማዳን ፡ መታደግ ፡ የሚቻለው ።

ኢታርምም ፡ ወኢትጸመም ፡ እግዚኦ ፡ መዝ ፡
ገ፫ ፡ ፬ ፡ ማቴ ፡ ጸ፱ ፡ ጸ፪ ።

ቢሆንም ፡ ዝም ፡ አትበል ፡ አትዘግይ ፡
ቸለል ፡ አትበል ፡ እንድም ፡ ዝም ፡
አትበል ፡ አትዘግይ ፡ ቸለል ፡ አትበል ፡
እንጂ ፡ ሉቃ ፡ ፲፰ ፡ ፊል ፡ ፮ ፡ ፲ ።

፪ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ወውዑ ፡ ፀርከ ።

እነሆ ፡ ጠላቶችህ ፡ ዕርዓውያን ፡ አግ
ርረዋል ፡ ደንፍተዋልና ።

ወእንሥኡ ፡ ርእሶሙ ፡ ጸላዕትከ ።

ጠላቶችህ ፡ ረሳቸውን ፡ ነቅንቀዋልና ።

፫ ፡ ወተጓሕለውዎሙ ፡ ምክረ ፡ ለሕዝብከ ።

ወገኖችህ ፡ መቃብያንን ፡ ምክርን ፡
ከድተዋቸዋልና ፡ እንድም ፡ በምክ
ር ፡ ተተንኩለዋቸዋልና ፡ ከድተዋቸ
ዋልና ።

ወተማከሩ ፡ ዲበ ፡ ቅዱሳኒከ ።

ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ በሚሆኑ ፡ በመ
ቃብያን ፡ ተማክረዋልና ።

፬ ፡ ወይቤሉ ፡ ንዑ ፡ ንሥርዎሙ ፡ እምኢሕ
ዛብ ።

ከሰው ፡ ለይተን ፡ እንድም ፡ አሕዛ
ብን ፡ ሰሚ ፡ አድርግ ፡ አሕዛብ ፡ ኑ ፡
እስራኤልን ፡ እናጥፋቸው ፡ ብለዋ
ልና ።

ወኢይዝከሩ ፡ እንከ ፡ ስመ ፡ እስራኤል ።

እስራኤል ፡ ኢይዝክሩ ፡ ስመ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እስራኤል ፡ የእ
ግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እንዳይጠሩ ፡
እንድም ፡ እንዳለ ፡ አሕዛብ ፡ የእስራ
ኤልን ፡ ስም ፡ እንዳይጠሩ ፡ እንድም ፡
ስመ ፡ እስራኤልናሆሙ ።

እስራኤል ፡ የእስራኤልነታቸውን ፡
ስም ፡ እንዳይጠሩ ።

፭ ፡ እስመ ፡ ተማከሩ ፡ ኅቡረ ፡ ወኅረዩ ።

አንድ ፡ ሁነው ፡ በንድነት ፡ ተከክለ
ው ፡ ተማክረዋልና ።

ላዕሌከ ፡ ተሰካተዩ ፡ ወተካየዱ ።

በንተ ፡ ላይ ፡ ተማምለዋል ፡ ሴራ ፡
ቈርጠዋልና ፡ ሐተታ ፡ በመቃብያን ፡
መክረዋል ፡ እንጂ ፡ በጌታ ፡ መክረ
ዋልና ፡ እንዲህን ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ በዓ
ሉን ፡ የሚያከብሩ ፡ መቃብያን ፡ ናቸ



ው ፡ በመቃብያን ፡ መምከር ፡ በጌታ ፡
መምከር ፡ ነውና ።

፮ ፡ ተዓይኒሆሙ ፡ ለኤዶምያስ ፡ ወለእስማኤ
ላውያን ፡ ዘፍ ፡ ፴፯ ፡ ፰ ።

እንዲህ ፡ የሚያደርጉ ፡ እለ ፡ ማን ፡
ናቸው ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ መቼስ ፡
ሌላ ፡ ማን ፡ አለ ፡ የኤዶምያስ ፡ የእስ
ማኤል ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ ኤዶምያስ ፡
የኤሳው ፡ የፈቲው ፡ ስሙ ፡ ነው ፡
ፈታዊሃ ፡ ለመብልዕ ፡ እንዲል ። ዘፍ ፡
፳፭ ፡ ፴ ።

ታሪክ ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅን ፡ ይስ
ሐቅ ፡ ያዕቆብንና ፡ ኤሳውን ፡ ይወል
ዳል ፡ ያዕቆብ ፡ ዓሥራ ፡ ሁለቱን ፡
ነገድ ፡ ዓሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ መቃ
ብያንን ፡ ይወልዳሉ ፡ ኤሳውም ፡ ለብ
ቻው ፡ ዓሥራ ፡ ሁለት ፡ ነገድ ፡ ይወል
ዳል ፡ የእስማኤል ፡ አብርሃም ፡ ከሳራ ፡
ይስሐቅን ፡ ይወልዳል ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕ
ቆብን ፡ ያዕቆብ ፡ ዓሥራ ፡ ሁለቱን ፡
ነገድ ፡ ዓሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ መቃ
ብያንን ፡ ይወልዳሉ ።

ሞዓብ ፡ ወአጋራውያን ።

ሞዓብን ፡ አቂየው ፡ እስማኤላውያ
ንና ፡ አጋራውያን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡
አብርሃም ፡ ከአጋር ፡ እስማኤልን ፡
ይወልዳል ፡ እስማኤል ፡ ስድስት ፡
ሕፃናት ፡ ይወዳል ፡ እሊህ ፡ ወንድሞ
ቻችን ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ማን ፡
አለ ፤ ዘፍ ፡ ፲፯ ፡ ፲፩ ።

፯ ፡ ጌባል ፡ ወአሞን ፡ ወአማሌቅ ።

ጌባል ፡ ትውልዱ ፡ ከእስራኤልም ፡
ከአሕዛብም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አልታወ
ቀም ፡ እንድም ፡ ታውቋል ፡ ከእስራ
ኤል ፡ ነው ፡ በመኻከል ፡ በለድ ፡ ሁኖ ፡
ኖሯል ። ታሪክ ፡ ታራ ፡ አብርሃምንና ፡
አራንን ፡ ይወልዳል ፡ አብርሃም ፡ ይስ
ሐቅን ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብን ፡ ያዕቆ
ብ ፡ ዓሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ዓሥራ ፡
ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ መቃብያንን ፡ ይወል
ዳሉ ፡ አራን ፡ ሎጥን ፡ ሎጥ ፡ ሞዓብ
ንና ፡ አሞንን ፡ ይወልዳል ፡ የሞዓብ
ና ፡ የአሞን ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ ማን ፡ አለ ፡ አማሌቅ ፡ አብርሃ
ም ፡ ይስሐቅን ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብን ፡
ያዕቆብ ፡ ዓሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡
ዓሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ መቃብያንን ፡
ይወልዳሉ ፤ አብርሃም ፡ ይስሐቅን ፡
ይስሐቅ ፡ ኤሳውን ፡ ኤሳው ፡ ዓሥራ ፡
ሁለት ፡ ነገድ ፡ ይወለዳል ፡ ከሥራ ፡
ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ አንዱ ፡ አርፋስክድ ፡
ነው ፡ አርፋስክድ ፡ አማሌቅን ፡ ይወ
ልዳል ፡ ቴምና ፡ ለአማሌቅ ፡ ሁለት ፡
ልጆች ፡ ትወልድለታለች ፤ ወቴምና
ስ ፡ ዕቅብቱ ፡ ወለደት ፡ ሎቱ ፡ ፪ኤ ፡
ደቂቀ ፡ እንዲል ፤ እሊህ ፡ ወንድሞ
ቻችን ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ማን ፡
አለ ።

ወኢሎፍሊ ፡ ምስለ ፡ ዕብእ ፡ ጢሮስ ።

ኢሎፍሊ ፡ ትውልድ ፡ ከሕዝብ ፡ ከአ

2014 04 17

ሕዛብ ፡ ነው ፡ ሰብአ ፡ ጢርስ ፡ ከሰብ
አ ፡ ኢሉፍሊ ፡ ሰብአ ፡ ኢሉፍሊ ፡
ከሰብአ ፡ ጢርስ ፡ ጋራ ፡ ናቸው ፡ እን
ጂ ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ አለ ፡ በምስጥርያም ፡
ጢሮሳውያን ፡ ተብለዋል ።

፰ ፡ አምርሂ ፡ ንብረ ፡ ምክሕሆሙ ።

አምር ፡ ስንኳ ፡ ዘመዴ ፡ አንድም ፡
ዕቁ ፡ ድኅ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አንድም ፡
አሦርም ፡ ኃያል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ከሳ
ቸው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆነ ፡ ወእምይ
እቲ ፡ ምድር ፡ ወፅአ ፡ አሦር ፡ ንጉሥ ፡
ወነደቃ ፡ ለነነዌ ፡ እንዲል ።

ወኮነምሙ ፡ ረድኤተ ፡ ለደቂቀ ፡ ሎጥ ።

እነሆ ፡ ሁሉ ፡ ለሎጥ ፡ ልጆች ፡ ረዳት ፡
ኾኗቸው ፡ ለነሱ ፡ ባይሆንላቸው ፡
ጌሻ ፡ ሁነው ፡ እኛ ፡ ለናንተ ፡ እንገዛ
ለን ፡ እናንተ ፡ እነሱን ፡ አስገዙን ፡
እያሉ ፡ እየመሩ ፡ ይዘዋቸው ፡ ይመ
ጡ ፡ ነበርና ፡ ወይመርሕሙ ፡ እንስ
ርት ፡ ወአውስት ፡ እንዲል ።

፱ ፡ ረሰዮሙ ፡ ከመ ፡ ምድያም ፡ ወሲሳራ ።

እንደ ፡ ምድያም ፡ እንደ ፡ ሲሳራ ፡ አድ
ርጋቸው ፡ ሲሳራ ፡ ቢቶደዱ ፡ ነው ፡
ምድያምን ፡ እቂየው ።

ወኮመ ፡ ኢያቢስ ፡ በፈለገ ፡ ቂሶን ።

ቂሦን ፡ በሚባል ፡ ወንዝ ፡ ወድቆ ፡
እንደ ፡ ቀረ ፡ እንደ ፡ ኢያቢስ ፡ አድር
ጋቸው ፡፡ ታሪክ ፡ ኢያቢስ ፡ ንጉሡ ፡
ነው ፡ ይህስ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡

ባርቅ ፡ ትውልዱ ፡ ከነገደ ፡ ንፍታሌ
ም ፡ ነው ፡ በሱ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ኢያ
ቢስ ፡ ቢቶደዱ ፡ ሲሳራ ፡ ይባላል ፡
ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ የብረት ፡ ሠረገላ ፡ አለ
ው ፡ ዲቦራ ፡ የምትባል ፡ ነቢይት ፡
ነበረች ፡ (አለች) ፡ ባርቅን ፡ ወጥተህ ፡
ግጠመው ፡ ድል ፡ ታደርገዋለህ ፡ አለ
ችው ፡ መሐዱንስ ፡ እሔድ ፡ ነበር ፡
ነገር ፡ ግን ፡ አንቺ ፡ ካልመጣሽ ፡ የም
ረዳበትን ፡ ሰዓት ፡ በምን ፡ አውቀዋ
ለሁ ፡ አላት ፡ እኔማ ፡ የመጣሁ ፡ እን
ደሆነ ፡ ድሉ ፡ የሴት ፡ ይባልብሃል ፡
አለችው ፡ ድል ፡ ማድረጉ ፡ ይገኝ ፡
እንጂ ፡ ይህስ ፡ አይጉዳም ፡ አላት ፡
ሔዶች ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ ተማለፉ ፡
በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግጠመው ፡ አለችው ፡
ገጠመው ፡ ውጋ ፡ ውጋ ፡ የሚል ፡ ነጋ
ሪት ፡ አስምቶለት ፡ ድል ፡ አድርጓል ፡
ኢያቢስ ፡ ከዝያው ፡ ሙቷል ፡ ሲሳራ ፡
ወእምስጠ ፡ በረዋጊ ፡ ፈረስ ፡ ይለዋ
ል ፡ በበላ ፡ ፈረሱ ፡ አምልጦ ፡ ሲሔድ ፡
ከእስራኤልና ፡ ከአሕዛብ ፡ መለያ ፡
ደረሰ ፡ ኢያኤል ፡ ብእሲተ ፡ ከቤር ፡
ቂንያዊ ፡ ይላታል ፡ ለእስራኤልም ፡
ለአሕዛብ ፡ እየገበሩ ፡ በመኻከል ፡
ይኖራሉ ፡ ገሐሥ ፡ እግዚእየ ፡ ጌታዬ ፡
ከቤት ፡ ግባ ፡ አለችው ፡ ገብቶ ፡ ወሀ ፡
ጠምቶኛል ፡ አጠጭኝ ፡ አላት ፡ ወእ
ስተየቶ ፡ ፅጸ ፡ አይገነ ፡ ይላል ፡ እን
ድ ፡ መንቀል ፡ ወገሚት ፡ አቀረበች
ለት ፡ ጠጥቶ ፡ ብርድ ፡ ብርድ ፡ ብሎ
ኛልና ፡ ደራርበሽ ፡ አልብሺኝ ፡ አላት ፡



ደራርባ ፡ አለበሰችው ፡ ሰጠው ፡ መጥቶ ፡
የጠየቀሽ ፡ እንደሆነ ፡ የለም ፡ በዪ ፡
ብሏት ፡ ተኛ ፡ እንቅልፍ ፡ ሲወስደው ፡
የብረት ፡ ካስማ ፡ በቀኝ ፡ እጇዋ ፡ እን
ስታ ፡ ወነሢአ ፡ መትከለ ፡ ደብተረ ፡
ጸቀወቶ ፡ ደመቀቶ ፡ ይላል ፡ ከቅል
ጡና ፡ ከቅልጡ ፡ መታችው ፡ በጎበ ፡
ተራገጸ ፡ ሲማራ ፡ ወበሆየ ፡ ኃሥረ ፡
ይላል ፡ ሬሳ ፡ ሽሽ ፡ ጥሎ ፡ ጉሰቁሎ ፡
ተበላሽቶ ፡ ሙቷል ፡ ባርቅ ፡ እያሳደ
ደ ፡ ደርሶ ፡ ሚሳራን ፡ አላየሽውምን ፡
አላት ፡ ሚሳራን ፡ ይሁን ፡ ጠላቶችህ ፡
ብላ ፡ ግዳይ ፡ ጥላለታለችና ፡ እንዲህ ፡
አለ ፤ መሳ ፡ ፬-፳፬ ።

፲ ፡ ወይመረዉ ፡ ከመ ፡ እለ ፡ እንዶር ።

እንደ ፡ እንዶራውያን ፡ ይጥፉ ፡ ወው
ረወ ፡ እንዶራውያነ ፡ እንዶራውያንን ፡
አጥፍቷቸልና ።

ወይኩኑ ፡ ከመ ፡ መሬተ ፡ ምድር ።

እንደ ፡ ምድር ፡ ትብያ ፡ ይሁኑ ።

፲፩ ፡ ረሰዮሙ ፡ ለመላእክቲሆሙ ፡ ከመ ፡ ሄሬብ ፡
ወዜብ ።

መኳንንቱን ፡ እንደ ፡ ሄሬብ ፡ እንደ ፡
ዜብ ፡ አድርጋቸው ።

ወዘብሄል ፡ ወስልማና ፡ ወኵሎሙ ፡ መላእክቲ
ሆሙ ።

እንደ ፡ ዘብሄል ፡ እንደ ፡ ስልማና ፡ እ
ንደ ፡ መኳንንቱም ፡ ሁሉ ፡ ይሁኑ ፡
አንድም ፡ እንደ ፡ ነገሥታቱ ፡ እንደ ፡
ነገሥታቱ ፡ መኳንንቱ ፡ እንደ ፡ መኳ
ንንቱ ፡ ይሁኑ ።

፲፪ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ንወርስ ፡ ምሥዋዐ ፡ እ
ግዚአብሔር ።

የግዚአብሔር ፡ ምሥዋዓ ፡ ብርቱን ፡
እንወርሳለን ፡ እንደሚሉ ፡ (ታሪክ) ፡
በጌዴዎን ፡ ጊዜ ፡ የምድያም ፡ ሰዎች ፡
እስራኤልን ፡ ያጠቋቸው ፡ ነበር ፡ በዘ
ር ፡ ጊዜ ፡ መጥተው ፡ ያደገውን ፡ ለወ
ገን ፡ አብልተውባቸው ፡ ያላደገውን ፡
ወገን ፡ አስጠቅጥቀውባቸው ፡ ይሔ
ዱ ፡ ነበር ፡ በመከርም ፡ ጊዜ ፡ መጥ
ተው ፡ አጭደው ፡ በልተው ፡ ለወገን ፡
አብልተው ፡ የተረፈውን ፡ በእሳት ፡
አቃጥለውባቸው ፡ ይሔዳሉ ፡ የምድ
ያም ፡ ሰዎች ፡ መጡ ፡ መጡ ፡ ሲባል ፡
ወእንዘ ፡ ይዘብጥ ፡ ወልዱ ፡ ጌዴዎን ፡
ከመ ፡ ያምሥጥ ፡ ይላል ፡ ስንዴውን ፡
ሊያሸሽ ፡ ሲወቃ ፡ መልአኩ ፡ መጥቶ ፡
አፅኑዓ ፡ ኃይል ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስ
ሌከ ፡ አለው ፡ ባባቶቻችን ፡ ጊዜ ፡ ይሉ
ናል ፡ እንጂ ፡ በኛስ ፡ አላደረብንም ፡
እግዚአብሔርማ ፡ ከደረብኝ ፡ የምድ
ያም ፡ ሰዎች ፡ ለምን ፡ ያጠቁኛል ፡
አለው ፡ ሑር ፡ አንተ ፡ ታድኅናሙ ፡
በኃይልከ ፡ አለው ።

አፅላፍየኒ ፡ ውሁድ ፡ ወገኔም ፡ ጥቂት ፡
ነው ፡ እንደምን ፡ ይሆንልኛል ፡ አለ
ው ፡ ባንተ ፡ አድሬ ፡ አድናቸዋለሁ ፡
ብሏል ፡ ሒድ ፡ አለው ፡ እንኪያስ ፡
ቂየኝ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠውቼ ፡ ልምጣ ፡
ብሎት ፡ ሔደ ፡ መሥዕት ፡ ሠውቶ ፡
ሥጋውን ፡ በቅርጫት ፡ ደሙን ፡ በብ

2014 04 17

ርት ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡ ቀረበ ፡ ደንግያውን ፡ ጸፍጽፎ ፡ እንጨቱን ፡ ረብርቦ ፡ ከዚዩ ፡ ላይ ፡ አድርጎታል ፡ መልአኩ ፡ በዘንግ ፡ ቢነካው ፡ ተቃጥሏል ፡ ምሳሌ ፡ ሥጋው ፡ የእሕዛብ ፡ እሳት ፡ የመቅሠፍት ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁለት ፡ የኩናት ፡ ጌዴዎን ፡ መልአኩ ፡ የጌዴዎን ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፡ ፀምር ፡ ልዘርጋ ፡ ጠል ፡ ከፀምር ፡ ይውረድ ፡ ዳርና ፡ ዳሩ ፡ ይቡስ ፡ ይሁን ፡ አለው ፡ ይሁንልህ ፡ አለው ፡ ሦስተኛ ፡ ፀምር ፡ ልዘርጋ ፡ ጠል ፡ በዳርና ፡ በዳሩ ፡ ይውረድ ፡ ፀምር ፡ ይቡስ ፡ ይሁን ፡ አለው ፡ ይሁንልህ ፡ አለው ፡ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ ለጊዜው ፡ ፀምር ፡ የእስራኤል ፡ ጠል ፡ የረድኤት ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠል ፡ ከፀምር ፡ መውረዱ ፡ እስራኤልን ፡ የማዳኑ ፡ (የመርዳቱ) ፡ በዳርና ፡ በዳር ፡ አለመውረዱ ፡ አሕዛብን ፡ ያለመርዳቱ ፡ ምሳሌ ፡ እንድም ፡ ፀምር ፡ አይለወጥም ፡ የእስራኤል ፡ ጠል ፡ የመቅሠፍት ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠል ፡ ከፀምር ፡ አለመውረዱ ፡ እስራኤልን ፡ ያለማጥፋቱ ፡ በዳርና ፡ በዳር ፡ መውረዱ ፡ አሕዛብን ፡ የማጥፋቱ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። ፍጻሜው ፡ ግን ፡ ፀምር ፡ የእመቤታችን ፡ ጠል ፡ የጌታ ፡ ጠል ፡ ከፀምር ፡ መውረዱ ፡ ጌታ ፡ ከመቤታችን ፡ የመወለዱ ፡ በዳርና ፡ በዳር ፡ አለመውረዱ ፡ ጌታ ፡ በሌሎች ፡ ሴቶች ፡ ያለማደሩ ፡ ምሳሌ ፡ እንድም ፡ ጠል ፡ የዘር ፡ ምሳሌ ፡ ፀምር ፡ ይቡስ ፡ መሆኑ ፡ እመቤታችን ፡ እንበለ ፡ ዘርዕ ፡ ፀንሳ ፡ እንበለ ፡ ዘርዕ ፡ የመውለዷ ፡ በዳርና ፡ በዳር ፡ መውረዱ ፡ ሌሎች ፡ ሴቶች ፡ በዘር ፡ በሩካቤ ፡ የመውለዳቸው ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰውን ፡ ሰብስቦ ፡ ጉዞ ፡ ጀመረ ፡ ይህማ ፡ በሠራዊታችን ፡ ብዛት ፡ በኀይላችን ፡ ፅናት ፡ ልትሉኝ ፡ አይደለምን ፡ ፈሪ ፡ ተለይ ፡ ብለህ ፡ አዋጅ ፡ ንገር ፡ አለው ፡ ፈሪ ፡ ተለይ ፡ ብሎ ፡ አዋጅ ፡ ነገረ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ተመለሰ ፡ አሁንም ፡ በዝታችኋልና ፡ ከወንዝ ፡ ይዘኻቸው ፡ ውረድ ፡ መሣሪያውን ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ አጣምሮ ፡ ይዞ ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ እንደውሻ ፡ እየጠለፈ ፡ የሚጠጣውን ፡ ይዘህ ፡ ሒድ ፡ መሣሪያውን ፡ አኑሮ ፡ እንደላም ፡ ተጎንብሶ ፡ የሚጠጣውን ፡ የነዚህን ፡ መሣሪያ ፡ ለኒያ ፡ ሰጥተህ ፡ እንያን ፡ አሰናብተህ ፡ እሊህን ፡ አስከትለህ ፡ ሒድ ፡ አለው ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ ሁነው ፡ የተገኙ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ናቸው ፡ እኒህን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ጊዜ ፡ ከፋፍ ፡ ላይ ፡ ሠፈሩ ፡ አሕዛብ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፡ ከሜዳ ፡ ላይ ፡ ሰፍረዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወርደህ ፡ ሰልል ፡ አንተም ፡ ትፈራ ፡ እንደሆነ ፡ አንተ ፡ ጠፋራን ፡ ቀልዔክ ፡ ከብላቴናህ ፡ ጋራ ፡ ውረድ ፡ አለው ፡ ብላቴናውን ፡ አስከትሎ ፡ ሒዶ ፡ ያምሳ ፡ አለቃው ፡ በለ



በት ፡ በኩል ፡ ሲሰልል ፡ እንዱ ፡ ላንዱ ፡ ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ ሕልም ፡ ዓይቼ ፡ የገብስ ፡ ጥረኝ ፡ የምታህል ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወርዳ ፡ ከሠፈራችን ፡ ገብታ ፡ ከተማችንን ፡ ስትገለባብጠው ፡ አየሁ ፡ አለው ፡ ምን ፡ ብለህ ፡ ፈታኸው ፡ አለው ፡ ገብስ ፡ የሚበቅልበት ፡ ሀገሩ ፡ ደጋ ፡ ነው ፡ ገብስ ፡ የተናቀ ፡ ምግብ ፡ ነው ፡ የዮአስ ፡ ልጅ ፡ ጌዴዎን ፡ ሰውነቱ ፡ የተናቀ ፡ ነው ፡ ጦር ፡ ይሰበስባል ፡ እሱ ፡ ያሳፍረኝ ፡ ይመስለኛል ፡ ብሎ ፡ ሲነግረው ፡ ሰምቶ ፡ ተመልሶ ፡ መቶውን ፡ በቀኝ ፡ መቶውን ፡ በግራ ፡ መቶውን ፡ በመከከል ፡ ያሰልፋቸዋል ፡ እሱም ፡ በመኻከል ፡ ሁኖ ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ ፋኖስ ፡ በግራ ፡ እጃቸው ፡ መለከት ፡ እሲዝ ፡ እኔ ፡ የምሠራውን ፡ እይታችሁ ፡ ሥሩ ፡ አላቸው ። ከሠፈሩ ፡ አጠገብ ፡ ሲደርስ ፡ የጌዴዎን ፡ ጦር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ድል ፡ መጣብህ ፡ ብሎ ፡ ፋኖሱን ፡ ሠበረው ፡ መለከቱን ፡ ነፋ ፡ እነሱም ፡ ፋኖሳቸውን ፡ ሠብረው ፡ መለከታቸውን ፡ ነፉ ፡ የፋኖው ፡ የመለከቱ ፡ ብዛት ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ የሰው ፡ ብዛት ፡ እንዴት ፡ ይሆን ፡ ብለው ፡ ሲሸሹ ፡ እስ ፡ በሳቸው ፡ ተላልቀዋል ። ከከተማው ፡ ገብቶ ፡ ገብሩልኝ ፡ አላቸው ፡ ፍርድ ፡ ያልብስህ ፡ አንተ ፡ መስፍን ፡ ነህ ፡ እነሱ ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ፡ ላንተ ፡ ገብረን ፡ ስንገኝ ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ እንገታችንን ፡ ዝቅ ፡ ብለው ፡ በታችኑን ፡ ይቀጡን ፡ የለምን ፡ አሉት ፡ እውነታችሁ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ የነዚያንስ ፡ መደረሻ ፡ ላላሳያችሁ ፡ የዕለት ፡ እራት ፡ የጣት ፡ ቀለበት ፡ ልትሉኝ ፡ አይገባችሁም ፡ ብሎ ፡ ገስግሶ ፡ ሒዶ ፡ ነገሥታቱን ፡ ከገወቻ ፡ አገኛቸው ፡ መኳንንቱንም ፡ ደቂቀ ፡ ኤፍሬም ፡ ሲሸሹ ፡ አግኝተው ፡ ማርከው ፡ ወስደው ፡ ግዳይ ፡ ጣሉለት ፡ መኳንንቱንም ፡ ነገሥታቱንም ፡ እንድ ፡ አድርጎ ፡ ባደባባይ ፡ አሰቅሏቸዋል ፡ ኋላ ፡ ደቂቀ ፡ ኤፍሬም ፡ ምነው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ሥራ ፡ ስትሠራ ፡ ሳትነግረን ፡ ቀረህ ፡ አሉት ፡ አሁንስ ፡ ቢሆን ፡ እላንተ ፡ የሠራችሁትን ፡ ሥራ ፡ ማን ፡ ሠርቶታል ፡ ብሏቸዋል ።

፲፫ ፤ አምላኪየ ፡ ረሲዮሙ ፡ ከመ ፡ መንኰራኵር ።

ፈጣሪዬ ፡ እንደሠረገላ ፡ አድርጋቸው ፡ ማለት ፡ ሠረገላ ፡ ገልበጥ ፡ ገልበጥ ፡ እንዲል ፡ በመዓትህ ፡ አገለባበጣቸው ፡ አንድም ፡ ሠረገላ ፡ ከርኅቀተ ፡ ዘመን ፡ የተነሣ ፡ እየተነደለ ፡ እየተጎረደ ፡ ይወድቃል ፡ እነሱንም ፡ በመዓትህ ፡ ጣላቸው ፡ አንድም ፡ ሠረገላ ፡ እንደሔደበት ፡ መሬት ፡ አድርጋቸው ፡ ያ ፡ እንዲዳስ ፡ በመዓትህ ፡ ዳሳቸው ።

ወከመ ፡ ሣዕር ፡ ዘቅድመ ፡ ገጸ ፡ እሳት ።

በእሳት ፡ ፊት ፡ በእሳት ፡ እንፃር ፡ እንዳለ ፡ ሣር ፡ አድርጋቸው ።

2014 04 17

፲፬፡ ወከመ፡ እሳት፡ ዘያውኢ፡ ገዳመ ።

በረሃውን ፡ እደሚያቃጥል ፡ እሳት ፡ አድርጋቸው ፡ ያ ፡ ጢ ፡ ጢ ፡ ብሎ ፡ እንዲጠፋ ፡ እንደዚያ ፡ ይጥፉ ፡ እን ድም ፡ እሳት ፡ በረሃውን ፡ እንደሚያ ቃጥል ፡ እንድም ፡ እሳት ፡ እንደማ ያቃጥለው ፡ እሳት ፡ እድርጋቸው ።

ወከመ ፡ ነበልባል ፡ ዘያንድድ ፡ አድባረ ።

ነበልባል ፡ እንደምታቃጥለው ፡ ተ ራራ ፡ እድርጋቸው ፡ እንድም ፡ እሳት ፡ ተራራውን ፡ እንደሚያቃጥል ፡ በእ ሳት ፡ መዓትህ ፡ እጥፋቸው ።

፲፭፡ ከማሁ ፡ ስድዶሙ ፡ በአውሎከ ።

በፅኑ ፡ ሥልጣንህ ፡ እንድም ፡ ፈጥ ነህ ፡ እጥፋቸው ።

ወሁኮሙ ፡ በመቅሠፍትከ ።

ዓውሎክ ፡ የለውን ፡ መቅሠፍትከ ፡ ብሎ ፡ ገለጸው ፡ በመቅሰፍትህ ፡ እው ከቻቸው ።

፲፮፡ ምላእ ፡ ውስተ ፡ ገጾሙ ፡ ኃሣረ ።

በፊታቸው ፡ ድል ፡ መነሣትን ፡ ተዋ ርዶን ፡ እምጣባቸው ።

ወእያምሩ ፡ ስመከ ፡ እግዚኦ ፡ ቍ ፡ ፲፰ ።

እንዲህ ፡ የተደረገባቸው ፡ እንደሆን ፡ ስምህን ፡ (የእምሩ) ፡ ያውቃሉ ፡ እን ድም ፡ ይህ ፡ ተደርጎባቸው ፡ ስምህን ፡ ያእምሩ ፡ ይወቁ ።

፲፯፡ ይትኃፈሩ ፡ ወይትሀወኩ ፡ ለዓለም ።

ይፍሩ ፡ ይዋረዱ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ይታ ወኩ ፡ እንድም ፡ እጥብቀህ ፡ ያፍ ራሉ ፡ ይዋረዳሉ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ይታ ወከሉ ።

ይህሥሩ ፡ ወይትኃጉሉ ።

ይዋረዱ ፡ ይጥፉ ፡ እንድም ፡ የኀሥሩ ፡ ይዋረዳሉ ፡ ይጠፋሉ

፲፰፡ ወያእምሩ ፡ ስመከ ፡ እግዚኦ ፡ ቍ ፡ ፲፮ ።

ይህ ፡ የተደረገባቸው ፡ እንደሆን ፡ ስ ምህን ፡ ያውቃሉ ፡ ይወቁ ።

ከመ ፡ አንተ ፡ ባሕቲትከ ፡ ልዑል ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ።

እስመ ፡ ቢልም ፡ ከመ ፡ ብለህ ፡ ተር ጉም ፡ በራቱ ፡ መዓዘን ፡ ሁሉ ፡ ልዑል ፡ ገናና ፡ እምላክ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ እን ደሆንህ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ።

## መዝሙር ፡ ፹፫ ።

፩፡ ጥቀ ፡ ፍቁር ፡ አብያቲከ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚአ ፡ ኃያላን ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ የምዕ መናንም ፡ ነገር ፡ እለበት ፡ እቤቱ ፡ የ ኃያላኑ ፡ ባለቤት ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ እጅግ ፡ ወደድጉ ፡ ናፈቅጉ ፡ እምስ ቱን ፡ ስድስቱን ፡ ቆመ ፡ ብዕሲ ፡ ሲ ያይ ፡ እብያት ፡ ብሎ ፡ እበዛ ፡ እን ድም ፡ ኅብስተ ፡ ገጽ ፡ የሚያቀርቡ በት ፡ ጕርጅ ፡ ጕርጅ ፡ እለና ፡ እን ድም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ እጅግ ፡ ወደድጉ ፡ ናፈቅጉ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ትወረሳለችና ፡ እብያት ፡ ብሎ ፡ እ በዛ ፡ እስመ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እቡየ ፡ ብዙህ ፡ ማኅደር ፡ ወምዕራፍ ፡ ቦቱ ፡ እንዲል ።



፪፡ ተፈሥሐት ፡ ነፍስየ ፡ በአፍቅሮ ፡ አዕጻዲከ ፡ እግዚኦ ።

እቤቱ ፡ ሰውነቴ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በ መውደድ ፡ ነፍሴ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማ ያትን ፡ በመውደድ ፡ ደስ ፡ አላት ።

ልብየኒ ፡ ወሥጋየኒ ፡ ተፈግሐ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕያው ።

ነፍሴም ፡ ሥጋዬም ፡ ሕያው ፡ ባሕ ርይ ፡ በሚሆን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እ ምነው ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

፫፡ ዖፍኒ ፡ ረከበት ፡ ላቲ ፡ ቤተ ።
ሆሴ ፡ ፲፩ ፡ ፲ ፡ ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ፡ ሉቃ ፡ ፲፱ ፡ ፯ ።

ዖፍ ፡ ስንኳ ፡ ቤትን ፡ እገኘች ፡ ኢል ሳቤጥኒ ፡ ይእቲኒ ፡ ሳሬ ፡ እንዲል ።

ወማዕነቅኒ ፡ ኀበ ፡ ታንብር ፡ እጕሊሃ ።

ዋኖስም ፡ ገላግልቷን ፡ የምታኖርበት ፡ ቦታ ፡ እገኘች ።

ምሥዋዒከ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚአ ፡ ኃያላን ።

ምሥዋዒከስ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እቤቱ ፡ የኃያላኑ ፡ ባለቤት ፡ ማደሪያህ ፡ የሚ ሆኑ ፡ ትሩፋን ፡ ግን ፡ ማደሪያ ፡ እጥ ተው ፡ ባቢሎን ፡ ለባቢሎን ፡ ይንከ ራተታሉ ።

እንድም ፡ (ዖፍኒ) ፡ ነቢያት ፡ ትንቢታ ቸውን ፡ የሚቀበሏቸው ፡ ሕዝቡን ፡ እገኙ ፡ (ወማዕነቅኒ) ፡ ካህናትም ፡ ትም ህርታቸውን ፡ የሚቀበሏቸው ፡ ሕዝ ቡን ፡ እገኙ ፡ ልጅ ፡ ካባቱ ፡ ባሕርይ ፡ (አብራክ) ፡ እንዲገኝ ፡ ምሥጢርም ፡ ከባሕርያቸው ፡ ይገኛልና ፡ (ምሥዋ ዒከ) ፡ ቤተ ፡ ኀበ ፡ ታንብር ፡ ያልሁት ፡ እዝነ ፡ ሰማዕያንን ፡ ልበ ፡ ሰማዕያንን ፡ ነው ።

እንድም ፡ (ዖፍኒ) ፡ ዖፍ ፡ ስንኳ ፡ ቤት ን ፡ እገኘች ፡ (ወማዕነቅኒ) ፡ ዋኖስም ፡ ገላግልቷን ፡ የምታኖርበት ፡ እገኘች ፡ (ምሥዋዒከስ) ፡ ማደሪያህ ፡ የምት ሆን ፡ እመቤታችን ፡ ግን ፡ ማደሪያ ፡ እጥታ ፡ ግብፅ ፡ ለግብፅ ፡ ትንከራተ ታለች ፡ እንድም ፡ (ዖፍኒ) ፡ እመቤ ታችን ፡ ቤትን ፡ እገኘች ፡ (ወማዕነ ቅኒ) ፡ እመቤታችን ፡ ዮሴፍን ፡ ሰሎ ሜን ፡ የምታኖርበት ፡ ቦታ ፡ እገኘች ፡ (ምሥዋዒከ) ፡ ቤተ ፡ ኀበ ፡ ታንብርም ፡ ያልሁት ፡ ደብረ ፡ ቍስቋምን ፡ ነው ።

ንጉሥየኒ ፡ ወአምላኪየ ።

ንጉሤም ፡ ፈጣሪዬም ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እንድም ፡ ንጉሥ ፡ ሠራዊቱን ፡ ፈጣ ሪ ፡ ፍጥረቱን ፡ እንዲረዳ ፡ ፈጥነህ ፡ እርዳኝ ።

፬፡ ብፁዓን ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ቤትከ ።

እቤቱ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎ ች ፡ ሁሉ ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

2014 04 17

ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ይሴብሑከ ፡

ለዘላለሙም ፡ የሚያመሰግኑህ ፡ ንዑ-
ዳን ፡ ከቡራን ፡ ናቸው ፡ እንድም ፡
ለዘላለሙ ፡ የሚያመሰግኑህ ፡ እንድ
ም ፡ ብፁዓን ፡ በቤትህ ፡ በመንግሥት ፡
ሰማያት ፡ የሚኖሩ ፡ ንዑዳን ፡ ከቡ
ራን ፡ ናቸው ፡ (ወለዓለመ ፡ ዓለም) ፡
ለዘላለሙ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡
እያመሰገኑህ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ንዑ
ዳን ፡ ከቡራን ፡ ናቸው ፡ እንድም ፡
በኢየሩሳሌም ፡ እንድም ፡ በመንግ
ሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚኖሩ ፡ ንዑዳን ፡
ከቡራን ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ለዘላለ
ሙ ፡ ያመሰግኑሃል ፡፡

፭ ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘእምኀቤከ ፡ ረድኤቱ ፡
እግዚኦ ፡

አቤቱ ፡ ረድኤተ ፡ ሥጋው ፡ ከንተ ፡
ዘንድ ፡ የሚደረግለት ፡ ትሩፍ ፡ እን
ድም ፡ ረድኤተ ፡ ነፍሱ ፡ ከንተ ፡ ዘን
ድ ፡ የሚደረግለት ፡ የሚታዘዝለት ፡
ምዕመን ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡፡

፮ ፡ ወዘይሔሊ ፡ በልቡ ፡ ዘበዓለሙ ፡ ውስተ ፡
ቈላተ ፡ ብካይ ፡ ብሔር ፡ ኀበ ፡ መሐልክሙ ፡

ሰባ ፡ ዘመን ፡ ይኖሩበት ፡ ዘንድ ፡ አል
ቅሱበት ፡ ብለህ ፡ በወሰንህላቸው ፡
በባቢሎን ፡ ሁኖ ፡ በኢየሩሳሌም ፡
የሚደረገውን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ የሚ
ያስብ ፡ እንድም ፡ መከነ ፡ ብካይ ፡ በሚ
ሆን ፡ በቀላውትምኖስ ፡ ሁኖ ፡ በደ
ብረ ፡ ሲና ፡ የተሠራውን ፡ ሕግ ፡ የሚ
ያስብ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡
ይበልዑ ፡ ወይሰትዩ ፡ ታሕተ ፡ ወይ
ኖሙ ፡ ወይነብሩ ፡ ተአሚኖሙ ፡
ይላል ፡ እስራኤል ፡ ከግብፅ ፡ ከወጡ ፡
በኋላ ፡ በቀላውትምኖስ ፡ ዳስ ፡ ጥለ
ው ፡ ድንኳን ፡ ተክለው ፡ የሠባ ፡ አር
ዴው ፡ የፀሬ ፡ አውርደው ፡ በልተው ፡
ጠጥተው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አድርገ
ዋል ፡ መልእክ ፡ መጥቶ ፡ ስምዑኒ ፡
ሕዝብየ ፡ እስራኤል ፡ እግዚብብሔር ፡
ይሰማዕክሙ ፡ ወገኖቼ ፡ እስራኤል ፡
ምክሬን ፡ ትምርቴን ፡ ስሙ ፡ ሁለተ
ኛ ፡ ኃጢአት ፡ የሠራችሁ ፡ እንደሆነ ፡
በግብፅ ፡ ከተቀበላችሁት ፡ የበለጠ ፡
መከራ ፡ ይመጣባችኋል ፡ አላቸው ፡
ሁለተኛ ፡ ኃጢአት ፡ የሠራን ፡ እንደ
ሆነ ፡ በግብፅ ፡ ከተቀበልነው ፡ መከራ ፡
የበለጠ ፡ መከራ ፡ ሊያገኘን ፡ አሉት ፡
አዎን ፡ አላቸው ፡ እንገት ፡ ላንገት ፡
ተያይዘው ፡ አልቅሰዋል ፡ ቀላውት
ምኖስ ፡ ብለውታል ፡ መከነ ፡ ብካይ ፡
ማለት ፡ ነው ፡ እንድም ፡ በወሰንኸላ
ቸው ፡ ብሔረ ፡ ብካይ ፡ በሚሆን ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሁኖ ፡ በመንግሥተ ፡
ሰማያት ፡ የሚደረገውን ፡ ተድላ ፡ ደ
ስታ ፡ የሚያስብ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡
ክቡር ፡ ነው ፡፡

እስመ ፡ መምሕረ ፡ ሕግ ፡ ይሁብ ፡ በረከተ ፡

ጠምሕረ ፡ ሕግ ፡ ዘሩባቤል ፡ በረከተ ፡
ሥጋን ፡ ይሰጣልና ፡ እንድም ፡ ሕግ
ን ፡ የሠራ ፡ የወሰነ ፡ ያስተማረ ፡ ጌታ ፡
በረከተ ፡ ሥጋን ፡ በረከተ ፡ ነፍስን ፡
ይሰጣልና ፡፡



፯ ፡ ወየሐውር ፡ እምኃይል ፡ ውስተ ፡ ኃይል ፡

ከኃይል ፡ ወደ ፡ ኃይል ፡ ይሔዳል ፡
ማለት ፡ ድል ፡ ከማድረግ ፡ ድል ፡ ወደ ፡
ማድረግ ፡ እንድም ፡ ጌታ ፡ ተአምራ
ት ፡ ከማድረግ ፡ ተአምራት ፡ ወደ ፡
ማድረግ ፡ ይሔዳል ፡፡

ወያስተርኢ ፡ አምላከ ፡ አማልክት ፡ በጽዮን ፡

ይህን ፡ ለማድረግ ፡ ጣዖታትን ፡ ቀጥ
ቅጦ ፡ የሚያጠፋ ፡ እንድም ፡ ከህና
ትን ፡ የፈጠረ ፡ ጌታ ፡ በኢየሩሳሌም ፡
በረድኤት ፡ እንድም ፡ ከመቢታችን ፡
በነሣው ፡ ሥጋ ፡ ተገለጠ ፡፡

፰ ፡ እግዚኦ ፡ አምላከ ፡ ኃያላን ፡ ስምዓኒ ፡
ጸሎትየ ፡

አቤቱ ፡ የኃያላኑ ፡ ባለቤት ፡ ልመና
ዬን ፡ ስማኝ ፡፡

ወአፅምዓኒ ፡ አምላኩ ፡ ለያዕቆብ ፡

የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ አቤቱ ፡ ስማኝ ፡

፱ ፡ ወርዕየኒ ፡ እግዚኦ ፡ ተአምኖትየ ፡

አቤቱ ፡ እምነቴን ፡ እወቅልኝ ፡፡

ወንጽር ፡ ኀበ ፡ ገጸ ፡ መሢሕከ ፡

የኔስ ፡ የኔ ፡ ነውና ፡ ቀብተህ ፡ ወዳን
ገሥኸው ፡ ወደ ፡ ዘሩባቤል ፡ ዕይ ፡
ተመልከት ፡፡

፲ ፡ እስመ ፡ ትኄይስ ፡ አሐቲ ፡ ዕለት ፡ ውስተ ፡
አዕጻዲከ ፡ እምአዕላፍ ፡

በባቢሎን ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከመኖር ፡
ከባቢሎን ፡ ወጥቶ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ገብቶ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አድሮ ፡ መሞ
ት ፡ ይሻላልና ፡፡

አብደርኩ ፡ እትገደፍ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡

የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ በምትኸ
ን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አ
ድሮ ፡ መሞትን ፡ ወደድኩ ፡፡

እምአንብር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ኃጥኣን ፡

በባቢሎን ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከመኖር ፡
እንድም ፡ (አብደርኩ ፡ እምእንበር) ፡
በባቢሎን ፡ ከብሬ ፡ ገንኜ ፡ ከኖር ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼ ፡ ተዋርጄ ፡ ዘግቼ ፡
መኖር ፡ ይሻለኛል ፡፡

፲፩ ፡ እስመ ፡ ጽድቀ ፡ ወምጽዋተ ፡ ያፈቅር ፡
እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔር ፡ እውነትን ፡ ምፅዋት
ን ፡ ይወዳልና ፡ እንድም ፡ እውነትን ፡
ምጽዋትን ፡ የያዘ ፡ ሰውን ፡ ይወዳል
ና ፡ እንድም ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖትን ፡
ይወዳልና ፡ እንድም ፡ ምግባር ፡ ሃይ
ማኖት ፡ የያዘ ፡ ሰውን ፡ ይወዳልና ፡፡

እግዚአብሔር ፡ ይሁብ ፡ ክብረ ፡ ወሞገሰ ፡

እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ላደረጉ ፡ ሰዎ
ች ፡ ክብረ ፡ ሥጋ ፡ ክብረ ፡ ነፍስን ፡
ሞገስ ፡ ሥጋ ፡ ሞገስ ፡ ነፍስን ፡ ይሰ
ጣል ፡፡

እግዚአብሔር ፡ ኢያስተሐጕሎሙ ፡ እምበረከቱ ፡
ለእለ ፡ የሐውሩ ፡ በየዋሀት ፡

እግዚአብሔር ፡ በየዋሀነት ፡ ሕግ ፡
በመጠበቅ ፡ በንጽሕ ፡ የሚኖሩትን ፡

2014 04 17

ከበረከተ፡ሥጋ፡ ከበረከተ፡ነፍስ፡ወገ ን ፡ ነስቶ ፡ እንዲቸገሩ ፡ አያደርግም።

፲፪ ፡ እግዚእ ፡ አምላክ ፡ ኃያላን ።

አቤቱ ፡ የኃያላኑ ፡ በለቤት ።

ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘተወከለ ፡ ኪያከ ።

አንተን ፡ ያመነ ፡ ትሩፍ ፡ እንድም ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

## መዝሙር ፡ ፹፱ ።

፩ ፡ ተማኅፀልከ ፡ እግዚእ ፡ ምድረከ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ የምዕ ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ የምዕ መናንም ፡ ነገር ፡ አሰበት ፡ አቤቱ ፡ ምድር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከሰባ ፡ ዘመ ን ፡ በኋላ ፡ ይቅር ፡ አልሃት ፡ ማለት ፡ የዘሩባትን ፡ እንድታበቅል ፡ የተከሉ ባትን ፡ እንድታጸድቅ ፡ አደረግኻት ፡ እንድም ፡ ምድር ፡ ምዕመንን ፡ ከም ስት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ይቅር ፡ አልሃት ፡ ማለት ፡ ም ግባር ፡ ሃይማኖት ፡ እንድትሠራ ፡ አደ ረግኻት ፡ እንድም ፡ ምድር ፡ ትሩፋን ፡ ይቅር ፡ አልሃት ፡ ማለት ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡ እንድትሠራ ፡ አደረግኻ ት ፡ ከምዕመን ፡ ትሩፍ ፡ ይቀድማል ፡ ተሳስቶ ፡ ነው ።

ወሜጥከ ፡ ፄዋው ፡ ለያዕቆብ ።

የያዕቆብ ፡ ዘሥጋን ፡ እንድም ፡ የያ ዕቆብ ፡ ዘነፍስን ፡ ምርኮውን ፡ መለ ስህ ።

፪ ፡ ወኃደገ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ለሕዝብከ ።

የወገኖችህን ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ይቅ ር ፡ አልህ ፡ ይቅር ፡ ብለህ ፡ ሜጥከ ።

ወከደንከ ፡ ኵሎ ፡ አበሳሆሙ ።

ኃጢአታቸውን ፡ ሁሉ ፡ ሠወርህ ፡ ማለት ፡ ይቅር ፡ አልህ ፡ ይቅር ፡ ብለህ ፡ መለስህ ።

፫ ፡ ወኃደገ ፡ ኵሎ ፡ መዓተከ ።

ፍጹም ፡ መዓትህን ፡ ይቅር ፡ አልህ ፡ እንድም ፡ ይቅር ፡ ብለህ ፡ ሜጥከ ፡

ወሜጥከ ፡ መቅሠፍተ ፡ መዓትከ ።

ፍጹም ፡ መዓትህን ፡ እንድም ፡ ፈር ደህ ፡ ያመጣኸው ፡ መዓትህን ፡ መለ ስህ ፡ መልሰህ ፡ ይቅር ፡ አልህ ።

፬ ፡ ሚጠነ ፡ አምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኤር ፡ ፳፱ ፡ ፲፱ ።

ድኅነታችንን ፡ የምታደርግልን ፡ ፈጣ ሪያችን ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳ ሌም ፡ መልሰን ፡ የትንቢት ፡ ነገር ፡ ከዝያ ፡ ሜጥከ ፡ አለ ፡ ከዚህ ፡ ሚጠነ ፡ አለ ፡ እንድም ፡ ከዝያ ፡ ምንም ፡ ጊዜ ው ፡ ባይደርስ ፡ አይቀርምና ፡ ጊዜው ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ሁኖ ፡ ተገልጾለት ፡ ሜጥከ ፡ አለ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜው ፡ ገና ፡ ነውና ፡ ሚጠነ ፡ አሎ ፡ እንድም ፡ ትሩ ፋን ፡ የወጡ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡



በዘሩባቤል ፡ በኤርምያስ ፡ በካልዕ ፡ ዕዝራ ፡ የወጡት ፡ ሜጥከ ፡ ያልወጡ ት ፡ ሚጠነ ፡ ይላሉ ፡ እንድም ፡ ከገ ሃነም ፡ ከሲኦል ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መልሰን ፡ የተመቸ ፡ በየጊዜው ፡ ሲደረግ ፡ ይና ራልና ።

ወሚጥ ፡ መዓተከ ፡ እምኔነ ።

መዓትህን ፡ ከኛ ፡ አርቀው ።

፭ ፡ ወለዓለም ፡ ኢትትመዓዓነ ።

ለጊዜውም ፡ ብትፈርድብን ፡ ለዘለላ ሙ ፡ (ፈጽመህ) ፡ አትፍረድብን ።

ወኢታንሀ ፡ መዓተከ ፡ ዓለመ ፡ ትውልደ ፡ ትውልድ።

ለልጅ ፡ ልጅ ፡ መዓትህን ፡ አብዝተ ህ ፡ አታምጣብን ፡ ኢሳ ፡ ፷፬ ፡ ፱ ።

፮ ፡ አንተ ፡ አምላክነ ፡ ተመየጠነ ፡ ወአሕይወነ።

ፈጣሪያችን ፡ አንተ ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ከቀጣ ፡ ወደ ፡ ትዕግሥት ፡ ተመለሰልን ፡ ተመለሰልን ፡ እንጂ ፡ ኢታንህ ።

ወሕዝብከኒ ፡ ይትፌሥሑ ፡ ብከ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ወገኖችህ ፡ ትሩ ፋን ፡ (ምዕመናን) ፡ ባንተ ፡ እምነው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፯ ፡ አርእየነ ፡ እግዚኦ ፡ ሣህለከ ።

አቤቱ ፡ ይቅርታህን ፡ አድርግልን ፡ ግለጽልን ።

ወሀበነ ፡ አምላክነ ፡ አድኅኖተከ ።

ፈጣሪያችን ፡ ትድግናህን ፡ ስጠን ።

፰ ፡ እሰምዕ ፡ ዘይነብበኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ አም ላኪየ ።

ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚናገረ ኝን ፡ እሰማለሁ ።

እስመ ፡ ይነብብ ፡ ሰላመ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝቡ ።

ለወገኖቹ ፡ እንድነትን ፡ ፍቅርን ፡ ይና ገራልና ።

ላዕለ ፡ ጻድቃኑ ፡ ወላዕለ ፡ እለ ፡ ይመይጡ ፡ ልበ ሙ ፡ ኀቤሁ ።

ለነቢያት ፡ ለካህናትም ፡ ልቡናቸው ንም ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚመ ለሱ ፡ ለሕዝቡ ፡ እንድነትን ፡ ፍቅርን ፡ ይናገራልና ፡ እንድም ፡ (ላዕለ ፡ ሕዝ ቡ) ፡ ለነቢያት ፡ ለካህናት ፡ (ወላዕለ ፡ ጻድቃኑ) ፡ ለወገኖቹ ፡ እንድነትን ፡ ፍቅርን ፡ ይናገራልና ፡ ይህስ ፡ አይደ ለም ፡ ሕዝቡ ፡ ያላቸው ፡ በቁሙ ፡ ሕዝቡን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ (እስመ ፡ ይነ ብብ ፡ ሰላመ ፡ ላዕለ ፡ ጻድቃኑ ፡ ወላ ዕለ ፡ እለ ፡ ይመይጡ ፡ ልበሙ ፡ ኀቤሁ) ፡ ልቡናቸው ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ለሚመለሱ ፡ ለወገኖቹ ፡ በነ ቢያት ፡ በካህናት ፡ አድሮ ፡ ሰላመ ፡ ዓቀብከ ፡ እሪትከ ፡ ትበልዕ ፡ ከራሚ ፡ ከራሚከ ፡ ብሎ ፡ እንድነትን ፡ ፍቅ ርን ፡ ይናገራልና ፡ ፈጣሪዬ ፡ እግዚ አብሔር ፡ የሚናገረኝን ፡ እሰማለሁ ።

2014 04 17

፱ ፡ ወባሕቱ ፡ ቅሩብ ፡ አድኅኖቱ ፡ ለእለ ፡ ይፈርህዎ ።

ባሕቱ ፡ ዋዌ ፡ ነው ፡ በሕግ ፡ በአም ልኮ ፡ ለሚፈሩት ፡ ለሚያመልኩት ፡ ትድግናው ፡ ቅርብ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይደረግላቸዋል ።

ከመ ፡ ይኅድር ፡ ስብሐቲሁ ፡ ውስተ ፡ ምድርነ ።

ተአምራቱ ፡ ጌትነቱ ፡ ይቅርታው ፡ በቤታችን ፡ ይነገር ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ በሰውነታችን ፡ ይመሰገን ፡ ዘንድ ።

፲ ፡ ሣህል ፡ ወርትዕ ፡ ተራከባ ።

ይቅርታ ፡ ዓቂበ ፡ ሕግ ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡ ተገናኙ ።

ጽድቅ ፡ ወሰላም ፡ ተሰዓማ ።

እውነት ፡ አንድነት ፡ ፍቅር ፡ ተገናኙ ።

፲፩ ፡ ርትዕሰ ፡ እምድር ፡ ሠረፀት ።

ዓቂበ ፡ ሕግ ፡ ከሰው ፡ ተገኘች ።

ወጽድቅኒ ፡ እምሰማይ ፡ ሐወፀ ።

ቸርነትም ፡ ከጌታ ፡ ተገኘ ።

፲፪ ፡ ወእግዚአብሔርኒ ፡ ይሁብ ፡ ምሕረቶ ።

ሕጉን ፡ ቢጠብቁ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ቸርነቱን ፡ ይሰጣል ።

ምድርኒ ፡ ትሁብ ፡ ፍሬሃ ፡ ዘካ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ።

ምድር ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ የዘሩባትን ፡ ታበቅላለች ፤ የተከሉባትን ፡ ታጸድ ቃለች ፤ ኢሳ ፡ ፵፩ ፡ ፩ ።

፲፫ ፡ ጽድቅ ፡ የሐውር ፡ ቅድሜሁ ።

ቸርነት ፡ በባሕርዩ ፡ አለ ።

ወየኃድግ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ ዓሠሮ ።

ዓሠረ ፡ ተአምራቱን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይተዋል ፤ አለ ፤ በየጎዳናው ፡ ተአም ራት ፡ አድርጎ ፡ አውጥቷቸዋልና ። አንድም ፡ (ሣህል ፡ ወርትዕ ፤ ጽድቅ ፡ ወሰላም) ፡ ሣህልና ፡ ጽድቅ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ርትዕና ፡ ሰላም ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ንጉሡ ፡ በክብረ ፡ ክህ ነትና ፡ በግብረ ፡ መንግሥት ፡ ተገናኙ ፤ (ርትዕሰ) ፡ ንጉሡ ፡ በግብር ፡ ምድራዊ ፡ ነው ፡ ምድራዊ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ማለት ፡ ይፈርዳል ፤ ይተቻል ፤ (ወጽ ድቅኒ) ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ግን ፡ በግብር ፡ ሰማያዊ ፡ ነው ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምርት ፡ ያስምራል ፤ (እግዚአብሔርኒ) ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ በግብረ ፡ ክህነት ፡ ንጉሡ ፡ በግብረ ፡ መንግሥት ፡ አንድ ፡ ቢሆኑ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሚጠትን ፡ ይሰጣ ል ፤ (ምድርኒ) ፡ ትሩፋም ፡ አምልኮን ፡ ሕግን ፡ ይዛ ፡ ትገኛለች ።

(ጽድቅ ፡ የሐውር) ፡ በዘሩባቤል ፡ ፊት ፡ ሳንቲ ፡ ዘጉፍ ፡ መለከት ፡ ይሔዳል ፤ (ወየኃድግ) በቁሙ ፡ ፍለጋውን ፡ በ ዚህ ፡ ዓለም ፡ ይተዋል ፡ ማለት ፡ በዚ ህ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ዋለ ፡ ከዚህ ፡ አደረ ፡ ይባላል ።

አንድም ፡ (ሣህል ፡ ወርትዕ ፡ ጽድቅ ፡ ወሰላም) ፡ አንዳንድ ፡ ወገን ፡ ሣህል ፡ ጽድቅ ፡ ጌታ ፡ በተጠማቂነት ፡ (ርትዕ ፡ ሰላም) ፡ ዮሐንስ ፡ በጥምቀት ፡ በጽ ንፈ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ተገናኙ ፤ (ርትዕሰ) ፡ ዮሐንስ ፡ ምድራዊ ፡ ነው ፡ ምድራዊ ፡ ልደቱን ፡ ይናገራል ፡ ዘካርያስ ፡ አባቱ ፡ ኤልሣቤጥ ፡ እናቱ ፡ ይሁዳ ፡ ርስቱ ፡ እያለ ፡ (ወጽድቅኒ) ፡ ጌታ ፡ ግን ፡ ሰማ ያዊ ፡ ነው ፡ ሰማያዊ ፡ ትምርትን ፡ ያስ ተምራል ፡ አቡየ ፡ ፈነወኒ ፡ ወአነ ፡ ተፈኖኩ ፡ ብሎ ፤ (እግዚአብሔርኒ) ፡ ጌታ ፡ በተጠማቂነት ፡ ዮሐንስ ፡ በጥ ማቂነት ፡ በጽንፈ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ቢገና ኙ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ልጅነትን ፡ ይሰ ጣል ፤ ጌታ ፡ በሠላሳ ፡ ዘመን ፡ የተጠ መቀው ፡ ጥምቀት ፡ እኛ ፡ በርባ ፡ ቀን ፡ ለምንጠመቀው ፡ ጥምቀት ፡ ዓረቦን ፡ ነውና ፤ (ምድርኒ) ፡ ምዕመንም ፡ ምግ ባር ፡ ሃይማኖትን ፡ ይዛ ፡ ትገኛለች ፤ (ጽድቅ) ፡ ዮሐንስ ፡ በፊቱ ፡ ይሔዳል ፤ መንፈቅ ፡ በዕንስ ፡ መንፈቅ ፡ በማስተ ማር ፡ ይቀድመዋልና ፤ (ወየኃድግ) ፡ ዓሠረ ፡ ተአምራቱን ፤ ዓሠረ ፡ ትም ርቱን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይተዋል ፤ ዓ ሠረ ፡ ተአምራቱን ፤ ቀዋ ፡ በግዑ ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ዘያኀትት ፡ ኀጢአተ ፡ ዓለም ፡ ብሎ ፡ ዓሠረ ፡ ትምርቱን ፡ እን ቲአየሰ ፡ ኃልቀት ፡ ብሎ ፡ ይሰጠዋል ፤ እንድም ፡ (ሣህል ፡ ወርትዕ ፡ ጽድቅ ፡ ወሰላም) ፡ አንዳንድ ፡ ወገን ፡ መለክ ትና ፡ ትስብዕት ፡ በማኅፀነ ፡ ማርያም ፡ ተገናኙ ፤ እንድም ፡ ሣህል ፡ ጽድቅ ፡ ርትዕ ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ጽድቅ ፡ ሰላም ፡ እመቤታችን ፡ በቤተ ፡ ዘካርያስ ፡ ተገ ናኙ ፡፡ ምንትኑ ፡ አነ ፡ ከመ ፡ ትምጽኢ ፡ ኀቤየ ፡ እሙ ፡ ለእግዚእየ ፡ እንዲል ፤ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፵፫ ።

እመቤታችንን ፡ ሰላም ፡ አላት ፡ ብኪ ፡ ድኅነ ፡ ዓለም ፡ ወበወልድኪ ፡ ኮነ ፡ ሰላም ፡ ይላታልና ፤ (ርትዕሰ) ፡ ትስብ ዕት ፡ ከመቤታችን ፡ ተከፈለ ፤ (ወጽ ድቅኒ) ፡ ቃል ፡ ከአብ ፡ ተገኘ ፤ (እግዚ አብሔርኒ) ፡ ትስብዕት ፡ መለኮት ፡ በ ኅፀነ ፡ ማርያም ፡ ቢገናኙ ፤ እግዚአብ ሔርም ፡ ልጁን ፡ ለኩነት ፡ ይሰጣል ። (ምድርኒ) ፡ እመቤታችንም ፡ ሥጋዋን ፡ ነፍሷን ፡ በቅድስና ፡ በንጽሕና ፡ አፅ ንታ ፡ ለተዋህዶ ፡ በቅታ ፡ ትገኛለች ፤ (ጽድቅ) ፡ በዘመኑ ፡ ወንጌል ፡ ትነገራ ለች ፤ (ወየኃድግ) ፡ ዘእንበረ ፡ መስቀለ ፡ ሞትየ ፡ ኢይክል ፡ ይፀመደኒ ፡ ብሎ ፡ ጠንከሩን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይተዋል ።

መዝሙር ፡ ፻፴፫ ።

፩ ፡ አፅምዕ ፡ እግዚኦ ፡ እዝንከ ፡ ኀቤየ ፡ ወስምዓኒ ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ አቤቱ ፡ ዕዝነ ፡ ፈቃድህን ፤ ዕዝነ ፡ ምሕረትህን ፡ ወደኔ ፡ መልሰህ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

እስመ ፡ ነዳይ ፡ ወምስኪን ፡ አነ ።

እኔ ፡ ፍጹም ፡ ድኃ ፡ ነኝና ።

፪ ፡ ዕቀባ ፡ ለነፍስየ ፡ እስመ ፡ የዋህ ፡ አነ ።

እኔ ፡ የዋህ ፡ ዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ ነኝና ፡ ሰው



2014 04 17

ነቴን ፡ ከመከራው ፡ ጠብቃት ።

አድኅኖ ፡ ለገብርከ ፡ እምኅዚየ ፡ ዘተወከለ ፡ ኪያከ ።

ራሱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ያቀርባል ፡ እ
ንድ ፡ ጊዜ ፡ ያርቃል ፡ አቤቱ ፡ ፈጣ
ሪዬ ፡ ባንተ ፡ ያመነ ፡ ባሪህ ፡ ሕዝቅያ
ስን ፡ አድነው ።

፫፡ ተሣሀለኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ኀቤከ ፡ እጸርሕ ፡ ኵሎ ፡ እሚረ ።

አቤቱ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ወዳንተ ፡ መ
ልሼ ፡ እለምናለሁና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

፬፡ ወአስተፍሥሐ ፡ ለነፍሰ ፡ ገብርከ ።

የባርያህ ፡ የሕዝቅያስን ፡ ሰውነት ፡
ከደዌ ፡ አድነህ ፡ ደስ ፡ አሰኛት ።

እስመ ፡ ኀቤከ ፡ አንቃእዶኩ ፡ ነፍስየ ፡ መዝ ፡ ፵፪ ።

በአንቃድዎ ፡ ልቡና ፡ በሰቂለ ፡ ሕሊና ፡
ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ እለምናለሁና ።

፭፡ እስመ ፡ መሐሪ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ወመስተ ሣህል ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ቸር ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነህና ።

ወብዙኅ ፡ ሣህልከ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይጼውዑከ ።

ለሚለምኑህ ፡ ሁሉ ፡ ይቅርታህ ፡ ብዙ ፡
ነውና ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ እንድም ፡ ለሚለም
ኑህ ፡ ኁሉ ፡ ይቅርታህ ፡ ብዙ ፡ ነውና ።

፮፡ አፅምዕ ፡ እግዚኦ ፡ ጸሎትየ ።

አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወነጽር ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ።

ነገረ ፡ ስዕለትየ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የልመናዬ
ን ፡ ነገር ፡ ተቀበል ፡ ወነጸረ ፡ ላዕለ ፡ አቤ
ል ፡ ወላዕለ ፡ መሥዋዕቱ ፡ እንዲል ።

፯፡ በዕለተ ፡ ምንዳቤየ ፡ ጸራህኩ ፡ ኀቤከ ፡ እስመ ፡ ሰማእከኒ ፡ ዮና ፡ ፪ ፡ ፫ ።

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ በሰናክሬም ፡
ጊዜ ፡ ልመናዬን ፡ ሰምተኸኛልና ፡
አሁንም ፡ በመከራዬ ፡ ቀን ፡ ወዳንተ ፡
መልሼ ፡ ለመንሁ ።

፰፡ አልቦ ፡ ዘይመስለከ ፡ እምነ ፡ አማልክት ፡ እግዚኦ ፡ ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፲፩ ።

አቤቱ ፡ በስመ ፡ አማልክት ፡ ከሚጸሩ ፡
አማልክት ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፡ ወገን ፡ እ
ንተን ፡ የሚመስልህ ፡ የለም ።

ወአልቦ ፡ ዘከመ ፡ ምግባሪከ ።

አንተም ፡ እንደምትሠራው ፡ ሥራ ፡
ያለ ፡ የሚሠራ ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ሰማ
ዩን ፡ ብትፈጥር ፡ ምድሩን ፡ መፍጠር ፡
የተቻለው ፡ የለም ፡ ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፮ ።

፱፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ ገበርከ ፡ ይምጽኡ ።

እንዲህም ፡ ከኸኝ ፡ የፈጠርኻቸው ፡
አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ መጥተው ፡ ባንተ ፡
ይመኑ ።

ወይስግዱ ፡ ቅድሜከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ከፊትህ ፡ ይስገዱ ፡ ማለት ፡
ባንተ ፡ ይመኑ ፡ (ላንተ ፡ ይገዙ) ።

ወይሰብሑ ፡ ለስምከ ፡ ኢሳ ፡ ፷፮ ፡ ፲፫ ።

ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ ያቅርቡ ፡ ስም
ህን ፡ ያመስግኑ ።

፲፡ እስመ ፡ ዓቢይ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ዘትገብር ፡ መንክረ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራት ፡
የምታደርግ ፡ ገናና ፡ አምላክ ፡ ነህና ።



አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሕቲትከ ፡ ዓቢይ ።

አንተ ፡ ብሕቲትከ ፡ ገናና ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህና ፡ ፊል ፡ ፲፭ ፡ ፬ ።

፲፩፡ ምርሐኒ ፡ እግዚኦ ፡ ፍኖተከ ።

መሐረኒ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ አቤቱ ፡ ሕግ
ህን ፡ ግለጽልኝ ፡ አስተምረኝ ፡ መዝ ፡
፳፮ ፡ ፲፩ ፡ ፻፲፰ ፡ ፰ ።

ወአሖር ፡ በጽድቅከ ።

በቸርነትህ ፡ አንድም ፡ በሕግሕ ፡ ፀ
ንቼ ፡ እኖር ፡ ዘንድ ።

ይትፌሥሐኒ ፡ ልብየ ፡ ለፈሪሃ ፡ ስምከ ።

ስምህን ፡ በማምለክ ፡ በመፍራት ፡ እን
ድም ፡ ስምህን ፡ ለማምለክ ፡ ለመፍ
ራት ፡ ልቡናዬ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

፲፪፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ በኵሉ ፡ ልብየ ።

እግዚአ ፡ አምላኪየ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ በ
ኵሉ ፡ ልብየ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡
እገዛልሃለሁ ።

ወእሴብሖ ፡ ለስምከ ፡ ለዓለም ።

ለዘላለሙ ፡ ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ አቀ
ርባለሁ ፡ ስምህን ፡ አመሰግናለሁ ።

፲፫፡ እስመ ፡ ዓብየት ፡ ምሕረትከ ፡ ላዕሌየ ።

ቸርነትህ ፡ ለኔ ፡ በዝታ ፡ ተደርጋልኛ
ለችና ።

ወአድኃንካ ፡ ለነፍስየ ፡ እምሲኦል ፡ ታሕቲት ።

ሰውነቴን ፡ ሙቶ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡
ከመውረድ ፡ አንድም ፡ ነፍሴን ፡ ወደ ፡
ሲኦል ፡ ከመውረድ ፡ አድነኃታልና ፡
አንድም ፡ አዳንኃት ።

፲፬፡ እምላኪየ ፡ ዓማፅያን ፡ ቆሙ ፡ ላዕሌየ ።

ፈጣሪዬ ፡ እለ ፡ ስናክሬም ፡ በጸላት
ነት ፡ ተነሡብኝ ።

ወማኅበረ ፡ እኩያን ፡ ኀሠሥዋ ፡ ለነፍስየ ።

የእኩያን ፡ የነሰናክሬም ፡ ወገኖች ፡
ሰውነቴን ፡ ለሞት ፡ ለጥፋት ፡ ሿት ።

ወኢረሰዩከ ፡ ቅድሜሆሙ ።

ምነው ፡ እኔሳ ፡ ወደኋት ፡ ሔጄ ፡ ት
ለኝ ፡ እንደሆን ፡ አንተንስ ፡ በፊታ
ቸው ፡ አላደረጉህም ፡ ማለት ፡ ያይብ
ናል ፡ ይሰማብናል ፡ ይፈርድብናል ፡
አላሉህም ።

፲፭፡ አንተሰ ፡ እግዚኦ ፡ ሐመፊ ፡ ወመስተሣህል ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ቸር ፡ ይቅር ፡
ባይ ፡ ነህ ፡ እንድም ፡ ነህና ።

ርኁቀ ፡ መዓት ፡ ወብዙኅ ፡ ምሕረት ፡ ወጻድቅ ።

መዓትህ ፡ የራቀ ፡ ቸርነትህ ፡ የቀረበ ፡
አንድም ፡ መዓትህ ፡ ያነሠ ፡ ቸርነትህ ፡
የበዛ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነህ ፡ ዘፀ ፡
፴፬ ፡ ፮-፯ ፡ ኢዮ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ፡ መዝ ፡ ፻፫ ፡ ፰ ፡ ፻፩ ፡
፭ ፡ ፲፭ ።

፲፮፡ ነጽር ፡ ላዕሌየ ፡ ወተሣሀለኒ ።

ኪያየ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እኔን ፡ በዓይኑ ፡
ምሕረት ፡ ዓይተህ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

2014 04 17

፱፱ ፡ ኃይለ ፡ ለገብርከ ።

ለባርያህ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ ኃይልን ፡ ስጠው ፡ በደዌ ፡ ያለ ፡ ነውና ፡ ሀበ ፡ አለ ።

ወአድኅኖ ፡ ለወልደ ፡ አመትከ ።

የባርያህ ፡ ልጅ ፡ ሕዝቅያስን ፡ አንድም ፡ የጥንት ፡ ተገዥችህ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ ሕዝቅያስን ፡ ከደዌ ፡ አድነው ።

፲፯ ፡ ግበር ፡ ምስሌየ ፡ ትእምርተ ፡ ለሠናይ ።

ለን ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ለኛ ፡ የተአምራት ፡ ምልክት ፡ የሚሆን ፡ ሚጠተ ፡ ፀሐይን ፡ ድኅነተ ፡ ደዌን ፡ አድርግልን ።

ይርአዩ ፡ ጸላእትየ ፡ ወይትኀፈሩ ።

ፀላቶቻችን ፡ እለ ፡ ሰናክሬም ፡ የሕዝቅያስን ፡ ድኅነት ፡ ዓይተው ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ፡ አንድም ፡ ያፍሩ ፡ ይዋረዱ ፡ ዘንድ ፡ ይርአዩ ።

ከመ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ረዳእከኒ ፡ ወአስተፈሥሐከኒ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ረድተህ ፡ ደስ ፡ እንዳሰኘኸን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ አንድም ፡ አንተ ፡ ረድተህ ፡ ደስ ፡ እንዳሰኘኸን ፡ አይተው ፡ ጠላቶቻችን ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ።

## መዝሙር ፡ ፹፮ ።

፩ ፡ መሠረታቲሃ ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡ ቅዱሳን ።

ስለሕዝቅያስ ፡ ተናግሯታል ፡ የትሩፋን ፡ የመቤታችን ፡ የምእመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ መሰናቷ ፡ በኪዳን ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብ ፡ ነው ።

፪ ፡ ያፈቅሮን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአናቅጸ ፡ ጽዮን ፡ እምኵሉ ፡ ተዓይኒሁ ፡ ለያዕቆብ ።

እግዚአብሔርም ፡ ከከተማው ፡ ይልቅ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ይወዳል ፡ ጉባዔ ፡ ይነገርበታልና ፡ ስሙ ፡ ይጠራበታል ፡ ይመሰገንበታልና ።

፫ ፡ ነኪር ፡ ነገሩ ፡ በእንቲአኪ ፡ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ።

ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ የተደረገው ፡ ነገር ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ጠላቷ ፡ ሰናክሬም ፡ ጠፍቶላታልና ።

አንድም ፡ (መሠረታቲሃ) ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ መሰናቷ ፡ ባምስቱ ፡ በስድስቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ ነው ፡ (ያፈቅሮን ፡ እምነቱ) ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከገጠሩ ፡ ይልቅ ፡ ከተማውን ፡ ይወዳል ፡ (ነኪር) ፡ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ስላንቺ ፡ የተደረገው ፡ ነገር ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ጠላቷ ፡ ብልጣሶር ፡ ጠፍቶላታልና ፡ ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፳፯ ።



፬ ፡ ዕዜክሮን ፡ ለረዓብ ፡ ወለባቢሎን ፡ እለ ፡ የአምራኒ ፡ ኢሳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱ ።

አስቀድሞ ፡ የሚያውቁኝ ፡ የማውቃቸው ፡ ረዓብን ፡ ባቢሎንን ፡ አስባቸዋለሁ ፡ ረዓብ ፡ ዘማ ፡ ከሌብና ፡ ኢያሱን ፡ ሰውራ ፡ ሰድዳለችና ።

ባቢሎን ፡ መሮዳህ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ ገብሯልና ።

ወናሁ ፡ ኢሎፍሊ ፡ ወጢሮስ ፡ ወሕዝበ ፡ ኢትዮጵያ ።

እነሆ ፡ ኢሎፍሊን ፡ ጢሮስን ፡ ኢትዮጵያን ፡ አስባቸዋለሁ ፡ ኢሎፍሊ ፡ ሴት ፡ ጌትያዊ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ራሱን ፡ ሁኖ ፡ ለዳዊት ፡ አድሮለታልና ፡ ጢሮስ ፡ ሰሎሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ ወአርድኦ ፡ በዕፀወ ፡ ጳውቂና ፡ ወቂድሮስ ፡ ይላል ፡ ኪራም ፡ እንጨት ፡ ጠርቦ ፡ ደንግያ ፡ አለዝቦ ፡ ረድቶታልና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያገራችን ፡ ንግሥት ፡ ማክዳ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ተንከራ ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ይላል ፡ ሉል ፡ ገበሮ ፡ ለሰሎሞን ፡ ገብራለታለችና ።

እሉ ፡ ተወልዱ ፡ በህየ ።

በዚህ ፡ የተወለዱ ።

፭ ፡ እምን ፡ ጽዮን ፡ ይብል ፡ ሰብእ ።

ሰዎቹም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እናታችን ፡ እግዚአብሔር ፡ አባታችን ፡ ይላሉ ።

ወሰብእ ፡ ተወልደ ፡ በውስቴታ ።

ተወልዶ ፡ በውስቴታ ፡ ይነግሥ ፡ በጠቢታ ፡ በል ፡ ሕዝቅያስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተወልዶ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይነግሥ ፡ ዘንድ ፡ አንድም ፡ ዘሩባቤል ፡ በባቢሎን ፡ ተወልዶ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይነግሥ ፡ ዘንድ ።

ወውእቱ ፡ ልዑል ፡ ሣረራ ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በረድኤት ፡ አፀናት ።

፮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነግሮሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ በመጽሐፍ ።

መጽሐፉ ፡ ሲል ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ ለወገኖቹ ፡ መጽሐፍን ፡ ይነግራቸዋል ፡ አንድም ፡ እንዳለ ፡ በአሪት ፡ ለእመ ፡ ዓቀብከ ፡ ኦሪተከ ፡ ትበልዕ ፡ ከራሜ ፡ ከራሜከ ፡ ወይሠፍፍ ፡ ማኅበብተ ፡ ወይንከ ፡ ወትሬኢ ፡ ውሉደ ፡ ውሉድከ ፡ እስከ ፡ ሣልስ ፡ ወራብዕ ፡ ትውልድ ፡ ብሎ ፡ ይነግራቸዋል ።

ወለመላእክቲሆሙ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ በውስቴታ ።

በኢየሩሳሌም ፡ ለተወለዱ ፡ ላለቆቹ ፡ መጽሐፉን ፡ ይነግራቸዋል ፡ አንድም ፡ ለእመ ፡ ዓቀብከ ፡ ብሎ ፡ በኦሪት ፡ ይነግራቸዋል ።

ከመ ፡ ፍሡሓን ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴትኪ ።

በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ እንዲኖሩ ፡ ይነግራቸዋል ።

አንድም ፡ (መሠረታቲሃ) ፡ የእመቤ

2014 04 17

ታችን ፡ መገኛቷ ፡ ሥርወ ፡ ልደቷ ፡
ከቤተ ፡ ክህነት ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡
ነው ፡ (ያበድሮን ፡ እምነሰ) ፡ ከሴሶ
ቹ ፡ ይናገል ፡ ይልቅ ፡ የመቤታችንን ፡
ሕዋሳት ፡ ለተዋህዶ ፡ ይወዳዋል ፡
(ነኪር) ፡ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እመ
ቤታችን ፡ ስላንቺ ፡ የተደረገ ፡ ነገር ፡
ድንቅ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ያለ ፡ ዘር ፡ ያለ ፡
ሩካቤ ፡ መፅነሷን ፡ መውለዷን ፡ መና
ገር ፡ ነው ፡ እንድም ፡ (መሠረታቲሃ) ፡
የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሰናቷ ፡ በኪ
ዳን ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ወያዕቆብ ፡
ነው ፡ (ያበድሮን ፡ እምነሰ) ፡ በወርቅ ፡
በዕንቍ ፡ ከተሠራው ፡ ከነገሥታቱ ፡
ቤት ፡ ይልቅ ፡ በጭቃ ፡ በጨፈቃ ፡
የተሠራውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡
ይወድዳልና ፡ እንድም ፡ ከሳመኑ ፡
አሕዛብ ፡ ይልቅ ፡ ያመኑ ፡ ምእመና
ንን ፡ ይወድዳል ፡ (ነኪር) ፡ ሀገረ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ስላንቺ ፡ የተደረገው ፡
ነገር ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ለቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ የሰጡ ፡ እንደሆነ ፡ ኅብ
ስቱ ፡ ተለውጦ ፡ ሥጋ ፡ መለኮት ፡
ወይኑ ፡ ተለውጦ ፡ ደመ ፡ መለኮት ፡
ይሆንበታልና ፡ ለምእመን ፡ የሰጡ ፡
እንደሆነ ፡ ሥጋውን ፡ ቈርሶ ፡ ደሙ
ን ፡ አፍስሶ ፡ ሰጥቷታልና ፡ (ዕዜከሮን) ፡
አስቀድሞ ፡ የሚያውቁኝ ፡ ምእመ
ናን ፡ አሕዛብን ፡ አውቃቸዋለሁ ፡ ወ
ናሁ ፡ ምእመናን ፡ አሕዛብን ፡ አስባ
ቸዋለሁ ፡ (እሉ ፡ ተወልዱ) ፡ በመቤ
ታችን ፡ ያ ፡ ኑ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
የተወለዱትን ፡ (እምን ፡ ጽዮን) ፡ እመ
ቤታችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እናታ
ችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ አባ
ታችን ፡ ይላል ፡ (ወብእሲ) ፡ ጌታ ፡ ከመ
ቤታችን ፡ በሥጋ ፡ ተወለደ ፡ ብእሲ ፡
በውስተ ፡ ብእሲ ፡ እንዲል ።

እንድም ፡ ምዕመናን ፡ ከቤተ ፡ ክርስ
ያን ፡ መንፈሳዊ ፡ ልደትን ፡ ተወለዱ ፡
(ወውእቱ ፡ ልዑል) ፡ እግዚአብሔር ፡
ን… ጌታችንን ፡ በንጽሕና ፡ አፀናት ፡
እንድም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በረድ
ኤት ፡ አፀናት ፡ (እግዚአብሔር ፡ ይነ
ግሮሙ) ፡ እግዚአብሔር ፡ ለወገኖቹ ፡
ለምእመናን ፡ እሚሄ ፡ ይበርሁ ፡ ጻድ
ቃን ፡ ምስብዒተ ፡ እደ ፡ እምብርሃን ፡
በሐይ ፡ በመንግሥተ ፡ አቡሆሙ ፡ ዘበ
ሰማያት ፡ ብሎ ፡ በወንጌል ፡ ይነግራቸ
ዋል ።

(ወለመላእክቲሆሙ) ፡ በዚ ፡ ላመኑ ፡
ላለቆቹ ፡ እንድም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ በልጅነት ፡ ለተወለዱ ፡ ለሊቃ ፡
ጳጳሳት ፡ ለጳጳሳት ፡ ይነግራቸዋል ።
(ከመ ፡ ፍሡሓን) ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
በልጅነት ፡ ተወልደው ፡ የሚኖሩ ፡
ሁሉ ፡ እንድም ፡ በመቤታችን ፡ ያመ
ኑ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ እንዲኖሩ ፡
ይነግራቸዋል ፡ ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፮ ፡ ፳፮ ፡ ፲ ።


ወተንሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ዘንቃህ ፡ እምንዋም ፡ መዝሙር ፡ ፸፯ ።


ወአንበሩኒ ፡ ውስተ ፡ ዐዘቅት ፡ ታሕተ ፡ መዝሙር ፡ ፹፯ ።

2014 04 17







## መዝሙር ፡ ፹፯ ።

፩፤ እግዚአብሔር ፡ አምላኪ ፡ መድኃኒትየ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ታናግሮታል ፤ እግዚ አብሔር ፡ ድኅነቴን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነው ፤ ፈጣሪዬ ፡ እግዚ.አብ ሔር ፡ ድኅነቴን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ ነው ፤ እንድም ፡ ሰሚ ፡ አድርገህ ፡ ድ ኅነቴን ፡ የምታደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እግዚ.አብሔር ፤ ኢሳ ፡ ፲፱ ።

ዕለትየ ፡ ጸራህኩ ፡ ኀቤከ ፡ ወሌሊትየኒ ፡ ቅድሜከ ።

ለኔ ፡ ብለህ ፡ በፈጠርህልኝ ፡ ሌሊትና ፡ መዓልት ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለመ ንኁ ፤ መዓልትና ፡ ሌሊት ፡ መፈጠሩ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፤ ወበእንቲአከሙ ፡ ፈ ጠርክዋ ፡ ለዕለት ፡ እንዲል ፤ እንድም ፡ ለምኖለኁና ፤ ኢሳ ፡ ፷፯ ፡ ፱ ።

፪፤ ለትባዕ ፡ ጸሎትየ ፡ ቅድሜከ ።

ልመናዬ ፡ ከፊትህ ፡ ትድረስ ።

አፅምዕ ፡ እዝነከ ፡ ኀበ ፡ ስዕለትየ ።

ዕዝነ ፡ ምሕረትህን ፤ ዕዝነ ፡ ፈቃድህን ፡ ወደ ፡ ልመናዬን ፡ መልስህ ፡ ስማኝ ።

፫፤ እስመ ፡ ፀግበት ፡ ነፍስየ ፡ ሕማመ ።

ሰውነቴ ፡ መከራውን ፡ ሰልችታለችና ፤

ወሕልጸቀት ፡ ለሞት ፡ ሕይወትየ ።

ሰውነቴ ፡ ለሞት ፡ ደርሳለችና ።

፬፤ ወተኈለቁ ፡ ከመ ፡ እለ ፡ ይወርዱ ፡ ውስተ ፡ ዓዘቅት ።

ሙቶው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ከወረዱ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተቈጠርኁ ፤ እንድም ፡ ሙቶው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ እንደ ፡ ወረዱ ፡ ሰዎች ፡ ሆንሁ ፡ ሐዲስ ፡ እን ዳለፈው ።

ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘአልቦ ፡ ረዳኢ ።

ረዳት ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ ሰው ፡ ሆንኁ ፤ እንድም ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አደረጉኝ ።

፭፤ ግዑዝ ፡ ውስተ ፡ ምውታን ።

ጉዞዬንም ፡ ወደ ፡ ምውታን ፡ አቃና ኁ ፤ አደረግኁ ፤ እንድም ፡ (ግዑዝ) ፡ ጉዞዬ ፡ ከሙታን ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ ኸኸ ፤ እንድም ፡ (እንዘ ፡ ግዑዝ) ፡ በመለኮቱ ፡ ከሕማም ፡ ከሞት ፡ ግዑዝ ፡ ስሆን ፡ ከሙታን ፡ ጋራ ፡ ተቈጠርኁ ፤ እን ድም ፡ ከሙታን ፡ ጋራ ፡ ከተቈጠርኁ ፡ በኋላ ፡ በትንሣኤ ፡ ግዑዝ ፡ ነኝ ።

ከመ ፡ ቅቱላን ፡ ወግዱፋን ፡ እለ ፡ ይሰክቡ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ።

ሙቶው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ እንደ ፡ ተጣሉ ፡ ሰዎች ፡ ሆንሁ ፤ እንድም ፡ ሙቶው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ከወረዱ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተቈጠርኁ ፤ ኢዮ ፡ ፲፯ ፡ ፲፫ ።

እለ ፡ ኢዘከርኮሙ ፡ ለግሙራ ።

ፈጽመህ ፡ ልብስ ፡ ምግብ ፡ ዝናብ ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ እንዳላልሃቸ ው ፡ ሰዎች ።

እስመ ፡ እሙንቱኒ ፡ ርኁቁ ፡ እምዕዴከ ። ኢሳ ፡ ፲ ፡ ፱ ።

እነዚ.ህም ፡ ከዕደ ፡ ምሕረትህ ፡ ፈጽ መው ፡ ርቀዋልና ።

2014 04 17

፮፡ ወአንበሩኒ፡ ውስተ፡ ዐዘቅት፡ ታሕት።

ማርከው፡ ዕኑ፡ መከራ፡ ወዳለበት፡ ወደ፡ ቁላት፡ ጉዞር፡ አውርደው፡ ጣሉኝ፤ እኖሩኝ፤ በዕታ፡ እርቀዋቸዋል፡ ዘመን፡ አብዝተው፡ በኛዋልና፤ እንድም፡ የሐልዮ፡ ኃጢአት፡ ፍዳ፡ ባለበት፡ በሲኦል፡ አኖሩኝ፡ ውስተ፡ ጽልመት፡ ወጽላሎተ፡ ሞት ።

ጽልመት፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ያሉበት፡ ባቢሎን፡ ጽላሎተ፡ ሞት፡ ዓሥሩ፡ ነገድ፡ ያሉበት፡ ቁላተ፡ ጉዞር፡ ነው፤ በዚህ፡ እኖሩኝ፤ እንድም፡ የሐልዮ፤ የነቢብ፡ የገቢር፡ ፍዳ፡ ባለበት፡ በሲኦል፡ በገሃነም፡ እኖሩኝ ።

፯፡ ላዕሌየ፡ ፀንዐ፡ መዓትከ።

በኔ፡ እደ፡ መዓትህ፡ ፀናብኝ ።

ወኵሉ፡ መቅሠፍትከ፡ አምጻእከ፡ ላዕሌየ ።

ፍጹም፡ መቅሠፍትህን፡ በኔ፡ ፈርደህ፡ አመጣህብኝ ።

፰፡ አርኃቀ፡ እምኔየ፡ አእ፡ የአምሮሂ።

የሚያውቁኝ፡ ወዳጆቼን፡ በግብር፡ በዕታ፡ ከኔ፡ አራቅኃቸው ።

ወረሰይኒ፡ ርኩሰ፡ በኀቤሆሙ ።

በሳቸው፡ ዘንድ፡ የማስጠይፍ፡ አደረግኸኝ ።

ወአኃዙኒ፡ አልብየ፡ መፃእ ።

ባቢሎናውያን፡ ያዙኝ፤ ከባቢሎን፡ ተዋግቼ፡ የምወጣበት፡ ኃይል፡ የለኝም ።

፱፡ አዕይንትየ፡ ደከማ፡ በተፅናስ ።

ዐይኖቼም፡ በቀጠና፡ በስልት፡ ደከሙ፤

ወጸራኅኩ፡ ኀቤከ፡ እግዚኦ ።

እኔም፡ ከዚህ፡ መከራ፡ የሚያድን፡ ከንተ፡ በቀር፡ እንደሌለ፡ አውቄ፡ ወዳንተ፡ መልሼ፡ ለመንኁ ።

ወኵሎ፡ ዕለተ፡ አንሥእኩ፡ እደዊየ፡ ኀቤከ ።

ዕለት፡ ዕለት፡ እጄ፡ ቃሌን፡ ለጸሎት፤ እጄ፡ ሥጋዬን፡ ለመሥዋዕት፡ እጄ፡ ልቡናዬን፡ ለአንክሮ፡ አንሣለኁ ።

፲፡ ቦኑ፡ለሙታን፡ ትገብር፡ መንክረከ ።

አወጣህ፡ የለምን፡ ምን፡ ያስቸግልሃል፡ ቢለው፡ በውኑ፡ ለሞቱ፡ ሰዎች፡ ድንቅ፡ ተአምራትህን፡ ታደርገዋለህን፤ እንድም፡ በውኑ፡ ተአምራትህን፡ የምታደርገው፡ ለሞቱ፡ ሰዎች፡ ነውን ።

ወዓቀብተ፡ ሥራይኒ፡ ያንሥኡ፡ ኢ፡፲፩፡ ፲፱።

አንተስ፡ የገደልኸውን፡ ባለመድኃኒቶች፡ ያነሣሉን፤ እንድም፡ (ዓቀብተ፡ ሥራይኒ)፡ ባለመድኃኒቶች፡ አያነሡም ። ኢ፡ ፲፱፡ ፲፱ ።

፲፩፡ ወይነግሩኑ፡ እለ፡ ውስተ፡ መቃብር፡ ሣህለከ ።

በመቃብር፡ ውስጥስ፡ ያሉ፡ ይቅርታህን፡ ቸርነትህን፡ ይነግራሉን፡ እንድም፡ (ኢይነግሩ)፡ አይነግሩም ።

ወጽድቀከኒ፡ ውስተ፡ ሞትኒ ።

ድኅረ፡ ሞትኑ፡ ሲል፡ ነው፤ ከሞት፡ በኋላ፡ ቸርነትህን፡ ይነግራሉን፡ እንድም፡ (ውስተ፡ ሞትኒ)፡ ከሞት፡ በኋላ፡ ቸርነትህን፡ አይነግሩም፡ እንድም፡ (ወጽድቀከኒ)፡ ቸርነትህስ፡ ከሞቱ፡ በኋላ፡ ይታወቃልን፡ እንድም፡ አይታወቅም ።

፲፪፡ ይትዐወቅኑ፡ ውስተ፡ ጽልመት፡ መንክርከ ።

በመቃብርስ፡ ቸርነትህ፡ ይታወቃልን፡ እንድም፡ (ኢይትዐወቅኒ)፡ አይታወቅም ።

ወርትዕከኒ፡ በምድር፡ ተረስዐ ።

ቀንተህ፡ እንድም፡ በቅንነት፡ የምታደርገው፡ ቸርነትህ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ተዘነጋን ።

፲፫፡ ወአነኒ፡ እግዚኦ፡ ኀቤከ፡ ጸራኅኩ ።

አቤቱ፡ እኔም፡ ወዳንተ፡ መልሼ፡ አለምንኃለኁ፡ እንድም፡ እለምንሃለኁና ።

ወጽባሕ፡ ትብጻሕከ፡ ጸሎትዬ ።

ልመናዬ፡ ዕለት፡ ዕለት፡ እንድም፡ ፈጥና፡ ከፊትህ፡ ትድረስ ።

፲፬፡ ለምንት፡ እግዚኦ፡ ትገድፍ፡ ጸሎትየ ።

አቤቱ፡ ልመናዬን፡ ለምን፡ ቸል፡ ትላለህ ።

ወትመይጥ፡ ገጸከ፡ እምኔየ፡ ኢዮ፡ ፲፫፡ ፳፬ ።

ገጽ፡ ምሕረት፡ ገጽ፡ ረድኤትህንስ፡ ከኔ፡ ለምን፡ ታርቀዋለህ ።

፲፭፡ ነዳይ፡ አነ፡ ወሥቁይ፡ እምንእስየ ።

ድኃ፡ የምሆን፡ እኔ፡ ከሕፃንነቴ፡ ጀምሬ፡ መከራ፡ ተቀበልኁ ።

ተልዒልየ፡ ተትሕትኩ፡ ወተመንደብኩ ።

ከብሬ፡ ተዋረድኁ፡ ማለት፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ተብዬ፡ ገብሮ፡ ገዶ፡ ዓመቶ፡ ወለቶ፡ ተባልኁ ።

፲፮፡ ላዕሌየ፡ ኃለፈ፡ መቅሠፍትከ ።

መዓትህ፡ ስባ፡ ዘመን፡ ተመላለሰብኝ ።

ወግረማከ፡ አደንገፀኒ ።

በአሕዛብ፡ አድረኽ፡ ተግረክ፡ ተግረክ፡ ባልኸኝ፡ ጊዜ፡ ፄዋዌህ፡ አስደነገጠኝ፡ ኢዮ፡ ፲፫፡ ፳፭፡ ኢሳ፡ ፳፭፡ ፱ ።

፲፯፡ ዐገቱኒ፡ ዘከሙ፡ ማይ፡ ኵሎ፡ ሚዕ ።

ወሀውን፡ ላሞች፡ ከብበው፡ እንዲመገቡት፡ እኔንም፡ አሕዛብ፡ ከበቡኝ፡ እንድም፡ ወሀ፡ ደሴትን፡ እንዲከብ፡ ከበቡኝ፡ እንድም፡ የተጠማ፡ ሰው፡ ወሀውን፡ ከብቦ፡ እንዲጠጣ፡ ከበቡኝ ።

ወአኃዙኒ፡ ኅቡረ፡ ኢሳ፡ ፲፩፡ ፲፱-፲፫ ።

እንድ፡ ሁነው፡ ባንድነት፡ ያዙኝ ።

፲፰፡ አርኃቁ፡ እምኔየ፡ አዕርክትየ፡ ወቢጽየ ።

ባልንጀሮቼ፡ ወንድሞቼ፡ የሚሆኑ፡ ዓሥሩን፡ ነገድ፡ ከኔ፡ አራቅሃቸው፡ ይላሉ፡ ሁለቱ፡ ነገድ ።

ወአዝማደየ ፡ እምተድኅኖየ ።

በችግሬ ፡ ጊዜ ፡ ከመቸገሬ ፡ የተነሣ ፡ ብሔድ ባቸው ፡ ይህ ፡ ለክፉ ፡ ከማን ፡ ጋራ ፡ ሙሉ ፡ ነበር ፡ ሊያስገኝ ፡ እን ዲሉ ፡ አድርገህ ፡ ዘመዶቼን ፡ ከኔ ፡ አራቅሃቸው ።

## መዝሙር ፡ ፹፰ ።

፩፤ ምሕረትከ ፡ እሴብሕ ፡ እግዚኦ ፡ ለዓለም ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ አቤቱ ፡ ቸርነትህን ፡ ፡ ለዘላለሙ ፡ አመሰግና ለኍ ፡ እንድም ፡ ባደረግህልኝ ፡ ትር ነት ፡ እንድም ፡ ቸርነትን ፡ ታደርግል ኛለህ ፡ ብዬ ፡ አመሰግንሃለኍ ።

ወዕበኒ ፡ ጽድቀከ ፡ በእሰተየ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ።

ቸርነትህንም ፡ ባንደበቴ ፡ ለልጅ ፡ ል ጅህ ፡ እነግራለሁ ፡ አስተምራለሁ ።

፪፤ እስመ ፡ ትቤ ፡ ለዓለም ፡ እሐንጽ ፡ ምሕረተ ።

እንገብር ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ቸርነትን ፡ ለዘ ላለም ፡ አደርጋለኍ ፡ አፀናለኍ ፡ ብለ ሃልና ።

በሰማያት ፡ ጽንዕ ፡ ጽድቅከ ፡ ኢሳ ፡ ፳ ፡ ፲፭ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ፡ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።

ቸርነትህ ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ፀንቶ ፡ ይኖ ራል ።

፫፤ ኪዳነ ፡ ተካየድኩ ፡ ምስለ ፡ ኅሩያንየ ።

ላባትነት ፡ ከመረጥኋቸው ፡ ከአብር ሃም ፡ ከይስሐቅ ፡ ከያዕቆብ ፡ ጋራ ፡ ምህላን ፡ ተማማልኍ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወመሐልኩ ፡ ለዳዊት ፡ ገብርየ ።

እገልጋዬ ፡ ለሚሆን ፡ ለዳዊትም ፡ ማ ልኍ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፬፤ ለዓለም ፡ እስተደሉ ፡ ዘርዓከ ።

የልጅ ፡ ልጅህን ፡ ለዘለዓለም ፡ መንግ ሥት ፡ አዘጋጅቻለኍ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወእሐንፅ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ መንበረከ ።

አፀንዕ ፡ እገብር ፡ ሲል ፡ ነው ፡ መን በረ ፡ መንግሥትህን ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ አደርጋለኍ ፡ አፀናለኍ ፡ ብለህ ፡ ነበር ፡ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፯ ፡ ፲፪-፲፫ ፡ ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፮ ፡ ፯ ፡ ፺፯ ፡ ፲፭ ፡ ገብ ፡ ፪ ፡ ፴ ።

፭፤ ይገንዩ ፡ ሰማያት ፡ ለስብሐቲከ ፡ እግዚኦ ።

ውእተ ፡ እሚረ ፡ ብሎ ፡ እስኪያመ ጣው ፡ ድረስ ፡ ሴላ ፡ አገባበት ፡ አ ቤቱ ፡ ሰማያት ፡ ለጌትነትህ ፡ ይገዛሉ ፡ አሁን ፡ ለነሱ ፡ ግዕዛን ፡ ኑሯቸው ፡ አ ይደለም ፡ ተዘርግተው ፡ እየታዩ ፡ የሚ ያስመሰግኑት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰማይኒ ፡ ይነግር ፡ በአስተርዕዮቱ ፡ እንዲል ፡ እንድም ፡ መላእክት ፡ ለጌትነትህ ፡ ይ ገዛሉ ።



ወጽድቀከኒ ፡ በማኅበረ ፡ ቅዱሳን ።

ቸርነትህም ፡ በመላእክት ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ጉ ባዔ ፡ ይነገራል ፡ ይመሰገናል ።

፮፤ መኑ ፡ ይትዔረዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በደ መናት ።

እግዚአብሔርን ፡ ደመናትን ፡ በመ ፍጠር ፡ እንድም ፡ በልዕልና ፡ እን ድም ፡ ሥጋን ፡ ነፍስን ፡ ፈጥሮ ፡ በማ ዋሀድ ፡ የሚመስለው ፡ (የሚተካከ ለው ፡ ማን ፡ ነው ኢሳ ፡ ፵፯ ፡ ፭ ።

ወመኑ ፡ ይመስሎ ፡ እምደቂቀ ፡ አማልክት ።

በስመ ፡ አማልክት ፡ ከሚጠሩ ፡ አማ ልክት ፡ ነን ፡ ከሚሉስ ፡ ወገን ፡ የሚ መስለው ፡ ማን ፡ ነው ።

፯፤ እግዚአብሔር ፡ ስቡሕ ፡ በምክረ ፡ ቅዱሳን ።

እግዚአብሔር ፡ በመላእክት ፡ ቃል ፡ እንድም ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ቃል ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ።

ዐቢይ ፡ ወግሩም ፡ ዲበ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ዓውዱ ።

በመንበረ ፡ መንግሥቱ ፡ ዙርያ ፡ ባሉ ፡ በሱራፌል ፡ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ እን ድም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ዙርያ ፡ ባሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ግሩም ፡ ነው ፡ ገናና ፡ አምላክ ፡ ነው ።

፰፤ እግዚኦ ፡ አምላከ ፡ ኃያላን ፡ መኑ ፡ ከማከ ።

አቤቱ ፡ የኃያላኑ ፡ ባለቤት ፡ ማዳን ፡ መታደግ ፡ የሚቻለው ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ።

ኃያል ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ወጽድቅ ፡ የዐውደከ ።

አቤቱ ፡ ኃያል ፡ ነህ ፡ ላጥፋ ፡ ብትል ፡ ይቻልሃል ፡ ጻሩ ፡ ግን ፡ ቸርነትህ ፡ ይገ ላግልሃል ።

፱፤ አንተ ፡ ትኴንን ፡ ኃይለ ፡ ባሕር ።

ውቅያኖስን ፡ የምትገዛ ፡ አንተ ፡ ነህ ።

ወአንተ ፡ ታረምሞ ፡ ለድምፀ ፡ ማዕበሉ ።

እስከ ፡ ዝየ ፡ ብጽሒ ፡ ብለህ ፡ የውቅ ያኖስን ፡ ማዕበል ፡ ሞገዱን ፡ ፀጥ ፡ የ ምታደርገው ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፲፤ አንተ ፡ አኅሠርኮ ፡ ለዕቡይ ፡ ከመ ፡ ቅቱል ፤ ፶፯ ፡ ፶፩ ፡ ፱ ፡ ፲ ።

ሴጥታንን ፡ እንደሞተ ፡ ያዋረድከው ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ማለት ፡ በባሕር ፡ ተወ ስኖ ፡ እንዲኖር ፡ ያደረግኸው ።

ወበመዝራዕተ ፡ ኃይልከ ፡ ዘረውኮሙ ፡ ለፀርከ ።

ኃይል ፡ ባለው ፡ ሥልጣንህም ፡ አጋ ንንትን ፡ በየቦታቸው ፡ ወሰንሃቸው ፤ በአየር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በእንጦርጦስ ፡ እንድም ፡ ግሩማን ፡ አራዊትን ፡ በየቦ ታቸው ፡ ወሰንሃቸው ።

እንድም ፡ (አንተ ፡ ትኴንን) ፡ ኤርት ራን ፡ የምትገዛ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወአን ተ) ፡ የኤርትራን ፡ ማዕበል ፡ ሞገዱን ፡ ከሁለት ፡ ከሦስት ፡ ከፍለህ ፡ ፀጥ ፡ ያደ ረግኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (አንተ ፡ አኅ ሠርኮ) ፡ ፈርዖንን ፡ በኤርትራ ፡ ሙጥ ሞ ፡ እንዲቀር ፡ ያደረግኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወበመዝራዕት) ፡ ሠራዊት ፡ ፈር

2014 04 17

ያንንም ፡ ከሥልጣንህ ፡ በተገኘ ፡ ኃይልህ ፡ ያጠፋሃቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ። እንድም ፡ አንተ ፡ (ትኤንን) ፡ ባቢሎንን ፡ የምትገዛ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወአንተ ፡ ታረምም) ፡ የባቢሎንን ፡ የመከራዋን ፡ ፅናት ፡ ፀጥ ፡ ያደረግኸው ፡ ያጠፋኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ። (አንተ ፡ አኅሠርከ) ፡ ብልጣሶርን ፡ በከተማው ፡ ቸብቸበው ፡ ተቈርጦ ፡ እንዲቀር ፡ ያደረግኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወበመዝራዕተ ፡ ኃይልከ) ፡ ከሥልጣንህ ፡ በተገኘ ፡ ኃይልህ ፡ ሠራዊቱ ፡ ብልጣሶርን ፡ አጠፋኻቸው ። እንድም ፡ (አንተ ፡ ትኤንን) ፡ ገሃነምን ፡ የምትገዛ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወንንተ ፡ ታረምም) ፡ የገሃነምን ፡ የመከራዋን ፡ ፅናት ፡ ፀጥ ፡ ያደረግኸው ፡ ያጠፋኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (አንተ ፡ አኅሠርከ) ፡ ዲያብሎስን ፡ በጥምቀት ፡ በመስቀል ፡ ድል ፡ የነሳኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወበመዝራዕተ ፡ ኃይልከ) ፡ ሠራዊቱ ፡ ዲያብሎስን ፡ አጋንንትን ፡ አጠፋሃቸው ።

፲፩ ፤ ዚአከ ፡ ውእቱ ፡ ሰማያት ፡ ወእንቲአከ ፡ ይእቲ ፡ ምድር ፤

ሰማዮች ፡ ያንተ ፡ ገንዘቦች ፡ ናቸው ፤ ምድርም ፡ ያንተ ፡ ገንዘብ ፡ ናት ።

ዓለመኒ ፡ በምልኡ ፡ አንተ ፡ ሣረርከ ፤

ዓለምንም ፡ በሙሉ ፡ በጥቅልሉ ፡ አንተ ፡ ፈጠርህ ፤ እንድም ፡ የፈጠርህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ መዝ ፹፫ ፩-፪ ።

፲፪ ፤ ባሕረ ፡ ወመስዕ ፡ ዘአንተ ፡ ፈጠርከ ።

ባሕሩን ፡ የብሱን ፡ የፈጠርህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ እንድም ፡ ንፁሳን ፡ መዓዝን ፡ የመዓዝን ፡ መዓዝን ፡ አሉና ፤ እንያን ፡ የፈጠርህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ ባርክ ፡ ምሥራቅ ፡ ወምዕራብ ፤ ሰሜን ፡ ወደቡብ ፤ መሥዓ ፡ ወዓዜብ ፤ ሊብ ፡ ወባሕረ ፡ እንዲል ።

ታቦር ፡ ወአርሞንኤም ፡ በስመ ፡ ዚአከ ፡ ይትፌሥሑ ፤

ታቦርና ፡ አርሞንኤም ፡ በስምህ ፡ እምነው ፡ በተደረገላቸው ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ ባገራቱ ፡ ሰዎቹን ፡ መናገር ፡ ነው ፤ ባርቅ ፡ ሲሣራን ፡ ድል ፡ አድርጎበታልና ፤ ምነው ፡ ይህማ ፡ የተደረገው ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ አይደለምን ፤ አርሞንኤምን ፡ እንኳ ፡ ቢሉ ፤ አባራሪው ፡ እስከ ፡ አርሞንኤም ፡ ደርሷልና ።

ወይሴብሑ ፡ ለስምከ ፡

ስምህን ፡ ያመሰግናሉ ፤ ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ ያቀርባሉ ።

፲፫ ፤ መዝራዕትከ ፡ ምስለ ፡ ኃይል ።

ሥልጣንህ ፡ ከኃይል ፡ ጋራ ፡ ተደረገላቸው ፤ እንድም ፡ (ታቦር ፡ ወአርሞንኤም) ፡ ሐዋርያት ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ በአርሞንኤም ፡ ብርሃን ፡ መለኮትህን ፡ ዓይተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ ምነው ፡ ይህማ ፡ የተደረገው ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ አይደለምን ፡ አርሞንኤምን ፡ እንኳ ፡ ቢሉ ፡ ብርሃኑ ፡ እስከ ፡ አርሞንኤም ፡ ደርሷልና ፤ (ወይሴብሑ) ፡ ስምህን ፤ ያመሰግናሉ ፤ ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ ያቀርባሉ ፤ (መዝራዕትከ) ፡ መንፈስ ፡ ቅዱሱ ፡ ከወልድ ፡ ጋራ ፡ ተገልጾላቸዋል ።

ወትትዓቀብ ፡ እዴከ ፡ ወተለዓለት ፡ የማንከ ፤

እጅ ፡ የማንክ ፡ ፀንዓት ፡ ወተለዓለት ፤ ብለህ ፡ ግጠም ፤ ፅሬና ፡ ያለው ፡ ሥልጣንህ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ከበረ ፡ ፀና ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ።

፲፬ ፤ ፍትሕ ፡ ወርትዕ ፡ ተድላ ፡ መንበርከ ፤

እናበህ ፡ ፍትሕ ፡ ርትዕ ፡ የጌትንትህ ፡ ጌጥ ፡ ናቸው ፤ የንግሥታት ፡ የዙፋና ቸው ፤ ጌጽ ፡ የወርቅ ፡ የዕንቍ ፡ ፈርዕ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንድም ፡ ሳይናበብ ፡ ፍትሕ ፡ ርትዕ ፡ ምቹ ፡ ዙፋንህ ፡ ናቸው ።

ሣህል ፡ ወጽድቅ ፡ የሐውር ፡ ቅድመ ፡ ገጽከ ፤

ይቅርታ ፡ ቸርነት ፡ ሰይፍ ፡ ገፃሬህ ፡ ነው ፤ እንድም ፡ በባሕርይህ ፡ አለ ።

፲፭ ፤ ብፁዕ ፡ ሕዝብ ፡ ዘየአምር ፡ የብቦ ።

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ የሚደግም ፡ ሰው ፤ እንድም ፡ ምሥጢሩን ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

እግዚኦ ፡ በብርሃን ፡ ገጽከ ፡ የሐውሩ ።

አቤቱ ፡ ከባሕርይህ ፡ በተገኘ ፡ ረድኤት ፡ ተጠብቀው ፡ ፀንተው ፡ ይኖራሉ ።

፲፮ ፤ ወበስምከ ፡ ይትፌሥሑ ፡ ኵሉ ፡ አሚረ ።

በስምህ ፡ እምነው ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።



ወበጽድቅከ ፡ ይትሌዓሉ ።

በቸርነትህ ፡ ከብረው ፡ ገንነው ፡ ይኖራሉ ።

፲፯ ፤ እስመ ፡ ምክሐ ፡ ኃይሎሙ ፡ አንተ ።

የምታስመካቸው ፡ ኃይላቸው ፡ አንተ ፡ ነህና ፤ ምክሕ ፡ ኃይሎሙ ፡ ብለህ ፡ ነው ፤ እንድም ፡ እንዳለ ፡ የሰራዊታቸው ፡ መመኪያ ፡ አንተ ፡ ነህና ።

ወበሣህልከ ፡ ይትሌዓል ፡ ቀርንነ ።

በይቅርታህ ፡ በቸርነትህ ፡ ሥልጣናችን ፤ እንድም ፡ ንጉሣችን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

፲፰ ፤ እስመ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ረድኤትነ ።

እምእግዚአብሔር ፡ ሲል ፡ ነው ። ረድኤት ፡ ሥጋችን ፡ እንድም ፡ ረድኤት ፡ ነፍሳችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይታዘዛል ፡ (ይደረጋልና) ፡

ወቅዱስ ፡ እስራኤል ፡ ንጉሥነ ።

ፅኑእ ፡ እስራኤል ፡ ክቡረ ፡ እስራኤልም ፡ ንጉሣችን ፡ ነውና ።

፲፱ ፤ ውእተ ፡ አሚረ ፡ ተናገርኮሙ ፡ በራእይ ፡ ለደቂቅከ ።

ይገንያ ፡ ሰማያት ፡ ለስብሐቲከ ፡ ብሎ ፡ አግብቶበት ፡ ነበርና ፡ እመጣው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በነቢይ ፡ አድረህ ፡ ለልጆችህ ፡ ትነግራቸው ፡ ነበር ፡ እንድም ፡ ለነቢያት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተያይተህ ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ ትነጋገራቸው ፡ ነበር ።

2014 04 17

ወትቤ ፡ እሬሲ ፡ ረድኤተ ፡ በላዕለ ፡ ኃይል ።

ረድኤትን ፡ በኃይል ፡ ላይ ፡ አደር ጋለሁ ፡ ማለት ፡ በሠራዊቱ ፡ ኃይ ልን ፡ አደርጋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወአልዓልኩ ፡ ኅሩይየ ፡ እምሕዝብየ ።

አልዓልኩ ፡ እምሕዝብየ ፡ ኅሩይየ ፡ እምሕዝብየ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ለመ ንግሥት ፡ የመረጥሁት ፡ ዳዊትን ፡ በመንግሥት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርገ ዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ፡ እንድም ፡ ዳዊትን ፡ ከወገኖቹ ፡ ለይቼ ፡ በመ ንግሥት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርገዋ ለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳ ፤ ወረከብክዎ ፡ ለዳዊት ፡ ገብርየ ።

አገልጋዬ ፡ ባለሟሌ ፡ ዳዊትን ፡ ለመንግሥት ፡ የበቃ ፡ ሁኖ ፡ አገ ኘሁት ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወቀባዕክዎ ፡ ቅብዓ ፡ ቅዱስ ።

ልዩ፡ ቅብዕን ፡ ቀብቼ ፡ እነገሥሁት፡ ብለህ ፡ ነበር ፡ ክብሩን ፡ ሲያይ ፡ ነው፡ እንጂ ፡ ቅብዑስ፡ አንድ፡ ነው ።

፳፩ ፤ እስመ ፡ እዴየ ፡ ትረድኦ ።

ኃይሌ ፡ ትረዳዋለች ፡ ብለህ ፡ ነበር።

ወመዝራዕትየ ፡ ታፀንዖ ፡ ኢሳ፵፩ ፡ ፲ ።

ሥልጣኔ ፡ ታፀናዋለች ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፪ ፤ ወኢይበቍዖ ፡ ፀላዒ ፡ በላዕሌሁ ።

ጠላት ፡ በሱ ፡ አይሰለጥንበትም ፡ እንድም ፡ በሱ ፡ የሚነሣ ፡ ጠላት ፡ አይረባም ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወውሉደ ፡ ዓመፃ ፡ ኢይደግሙ ፡ አሕምሞቶ ።

የዓመፅ ፡ ልጅ ፡ ባቢሎናዊ ፡ በሱ ፡ መከራ ፡ ማምጣትን ፡ አይደግምም፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ቢነሣበት ፡ እንደ ፡ ተነሣበት ፡ አይቀርም ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፫ ፤ ወእመትሮሙ ፡ ለፀሩ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ።

በቅድመ ፡ ገጹ ፡ ይላል ፡ ጠላቶ ቹን ፡ ከፊቱ ፡ እንድም ፡ በፊቱ ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወእኅሥሮሙ ፡ ለጸላእቱ ።

ጠላቶቹን ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ። ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፲፩ ።

፳፬ ፤ ወሣህልየሰ ፡ወጽድቅየ ፡ ምስሌሁ ።

ሎቱስ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ለሱ ፡ ግን ፡ ይቅርታዬን ፡ ቸርነቴን ፡ አደር ግለታለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወበስምየ ፡ ይትሌዓል ፡ ቀርኑ ።

በስሜ ፡ እምኖ ፡ ሥልጣኑ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፭ ፤ ወእሠይም ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ እዴሁ።

ግዛቱን ፡ ከጤግሮስ ፡ እስከ ፡ ኤፍ ራጥስ ፡ አደርገዋለሁ ፡ ይገዛል ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወውስተ ፡ አፍላግ ፡ የማኖ ።

ሥልጣኑንም ፡ ከዳን ፡ እስከ ፡ ቤር ሳቤህ ፡ አደርገዋለሁ ፡ ይገዛል ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፮ ፤ ወውእቱ ፡ ይብለኒ ፡ አቡየ ፡ አንተ ።

ዳዊት ፡ በጸጋ ፡ አባቴ ፡ ነው ፡ ይለ ኛል ፡ እኔም ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ እለዋ ለሁ ፡ እንድም ፡ ክርስቶስ ፡ በባሕ ርይ ፡ አባቴ ፡ ነው ፡ ይለኛል ፡ እ ኔም ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ እለዋለሁ ፡ ብ ለህ ፡ ነበር ፡ መዝ፡፪፡፯፡፪ነገ፡፯፡፲፬።

እምላኪየ ፡ ወረዳእየ ፡ ወመድኃንየ ፡ ዕብ ፡ ፩ ፡ ፭ ።

ድኅነቴን ፡ የምታደርግልኝ ፡ ረዳ ቴ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነህ ፡ ይለኛል ፡ ብ ለህ ፡ ነበር ።

፳፯ ፤ ወአንሰ ፡ በኵርየ ፡ እሬስዮ ።

እኔም ፡ በኵረ ፡ ምዕመናን ፡ በኵረ ፡ ነገሥታት ፡ አደርገዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወልዑል ፡ ውእቱ ፡ እምነገሥተ ፡ ምድር ።

በእሬስዮ ፡ የሣብህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልዑለ ፡ በውእቱ ፡ የሣብህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልዑል ፡ በል ፡ በእራቱ ፡ መ ዓዝን ፡ ከነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ ይል ቅ ፡ ልዑል ፡ ንጉሥ ፡ አደርገዋ ለሁ ፡ እንድም ፡ ልዑል ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፰ ፤ ወለዓለም ፡ እዓቅብ ፡ ሎቱ ፡ ሣህልየ ።

ለሱ ፡ ለዘላለም ፡ ይቅርታዬን ፡ መሐላዬን ፡ አፀናለታለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወምዕመን ፡ ውእቱ ፡ ለኪዳንየ ።

ሕጌን ፡ ለመጠበቅ ፡ የታመነ ፡ ነው ፡ ሊምሉለት ፡ ይገባል ፡ ብለህ፡ ነበር ።

፳፱ ፤ ወእሬሲ ፡ ዘርዖ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ልጆቹን ፡ ለዘላለም ፡ በመንግሥት፡ የተዘጋጁ ፡ አደርጋቸዋለሁ ፡ ብለህ፡ ነበር ።

ወመንበሩኒ ፡ ከመ ፡ መዋዕለ ፡ ሰማይ ።

መንበረ ፡ መንግሥቱም ፡ ሰማይ ፡ ሳያልፍ ፡ እያልፍም ፡ ብለህ ፡ ነበር። ፪ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፮ ፡ ፩ጢሞ፪ ፡ ፰ ።

፴ ፤ እመሰ ፡ ኀደጉ ፡ ደቂቁ ፡ ሕግየ ።

ልጆቹ ፡ ግን ፡ ሕጌን ፡ ቢያፈርሱ ፡

ወኢሖሩ ፡ በኵነኔየ ።

በሕጌም ፡ ፀንተው ፡ ባይኖሩ ፡

፴፩ ፤ ወእመኒ ፡ አርኰሱ ፡ ሥርዓትየ ።

ሕጌንም ፡ ቢያፈርሱ ፡

ወኢዓቀቡ ፡ ትእዛዝየ ።

ሕጌንም ፡ ባይጠብቁ ፡

፴፪ ፤ እቀሥፎ ፡ በበትር ፡ ለኃጢአቶሙ ።

በታናሽ ፡ መቅሠፍት ፡ እገሥጻቸ ዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር።

ወበመቅሠፍት ፡ ለአበሳሆሙ ።

ልጅ ፡ ቢያጠፋ ፡ በጨንገር ፡ ይሠሩ ታል ፡ ይቀጡታል ፡ እንጂ ፡ በሰ ይፍ ፡ እንዳይመቱት ፡ በጦር ፡ እን



2014 04 17

ዳያወጉት ፡ እንደዚህ ፡ ሁሉ ፡ እኔ ስም ፡ ታላቅ ፡ ታናሽ ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠሩ ፡ በታናሽ መቅሠፍት ፡ ገሥጬ ፡ እመልሳቸዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፴፫ ፡ ምሕረትየሰ ፡ ኢይከልእ ፡ እምኔሆሙ ።

ይቅርታዬን ፡ ግን ፡ ከሳቸው ፡ አላ ርቅም ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወኢይሔስዎ ፡ በጽድቅየ ።

እውነተኛውን ፡ መሐላዬን ፡ አላ ፈርስም ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፴፬ ፡ ወኢያረኵስ ፡ ኪዳንየ ።

መሐላዬን ፡ አላፈርስም ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወኢይፌልሶ ፡ ዘወፅአ ፡ እምአፉየ ፡

ካንደበቴ ፡ የወጣውን ፡ ሐሰት ፡ አልናገርም ፡ ማለት ፡ ምዬ ፡ አል ከዳም ፡ የተናገርሁትን ፡ አላስቀር ም ፡ ብለህ ፡ ነበር ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፴፩-፴፯ ።

፴፭ ፡ ምዕረ ፡ መሐልኩ ፡ በቅዱስየ ፡ ከመ ፡ ለዳዊት ፡ ኢይሔስዎ ።

ዳዊትን፡ እንዳልከዳው፡ በዕኑ፡ መሐ ላዬ ፡ ማልሁ ፡ ማለት ፡ ሕያውዩ ፡ እማንየ ፡ ሕያው ፡ እኔ ፡ በርእስየ ፡ ብዬ ፡ ማልሁ ፡ ይህን ፡ መሐላዬን ፡ አላፈርስም ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፴፮ ፡ ወዘርዑ ፡ ለዓለም ፡ ይሄሉ ።

ልጁ ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ ለዘላለም ፡ በመንግሥቱ ፡ ፀንቶ ፡ ይኖራል ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወመንበሩኒ ፡ ከመ ፡ ፀሐይ ፡ በቅድሜየ ።

መንበረ ፡ መንግሥቱ ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ፀሐ ይ ፡ ሳያልፍ ፡ አያልፍም ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፴፯ ፡ ወምሩቅ ፡ ከመ ፡ ወርኅ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡

ህልው ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ጨረ ቃ ፡ ህልው ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ፡ ማ ለት ፡ ጨረቃ ፡ ሳያልፍ፡ አያልፍም፡ ብለህ ፡ ነበር ፡ አንድም ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ሙቆ ፡ እንደ ፡ ጨረቃ ፡ ደምቆ ፡ ይኖራል ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወስምዑ ፡ ምዕመን ፡ በሰማይ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ።

የዚህ ፡ ምስክሩ ፡ በሰማይ ፡ ያለ ፡ መልአክ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ ያ ፡ ባለማለፍ ፡ ፀንቶ ፡ ይኖራል ፡ እን ድም ፡ የዚህ ፡ እውነተኛ ፡ ምስ ክሩ ፡ ሰማይ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ ም ዕመን ፡ ሰማይ ፡ ይላል ፡ ምዕመን ፡ ሰማይ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፴፰ ፡ አንተሰ ፡ መነንኮ ፡ ወገደፍኮ ።

ይሕዜሰ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ናቅኸው ፡ አቀለልከው ፡ በመከ ራውም ፡ ጣልከው ፡ አንድም ፡ ቀድሞ ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ታደ ርግልን ፡ ነበር ፡ አልኸኝ ፡ ዛሬሳ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ ዛሬስ ፡ ናቅኸ



ው ፡ አቃለልኸው ፡ በመከራው ፡ ጣልኸው ።

ወአናኅሦይኮ ፡ ለመሲሕከ ።

ቀብተህ ፡ ያነገሥኸው ፡ ዳዊትን ፡ ናቅኸው ፡ አቃለልከው ፡ በረድ ኤት ፡ ተለየኸው ።

፴፱ ፡ ወሜጥከ ፡ ሥርዓቶ ፡ ለገብርከ ።

የባሪያህን ሥርዓቱን ፡ ለወጥህ ፡ ማለት ፡ ድል ፡ ያደርግ ፡ የነበረ ውን ፡ ድል ፡ እንዲነሣ ፡ አደረግ ኸው ።

ወአርኰስከ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ መቅደሶ ።

ቤተ ፡ መቅደሱን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አሳደፍህ ፡ ማለት ፡ ኢኮንያን ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ፃህል ፡ ዕዋ ፡ መ ብል ፡ መጠጥ ፡ አድርጎበታልና ።

፵ ፡ ወነሠትከ ፡ ኵሎ ፡ ጥቅሞ ።

ግንቡን ፡ ሁሉ ፡ አፈረስህበት ።

ወረሰይከ ፡ እጽዋኒሁ ፡ መፍርሃ ።

እምባውን ፡ ከተማውን ፡ የሚያስ ፈራ ፡ አደረግኸው ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ በባቢሎን ፡ ኑረው ፡ ቢመጡ ፡ አራዊት ፡ ሠልጥነውበት ፡ አግ ኝተውታልና ፡ አንድም ፡ ምፍራሃ ፡ ይላል ፡ የ ማያድን ፡ አደረግኸው ፡ ማለት ፡ የሌባ ፡ መሸሻ ፡ የወን በዴ ፡ ዋሻ ፡ አደረግኸው ።

፵፩ ፡ ወተማሰጥዎ ፡ ኵሉ ፡ ሐላፌ ፡ ፍኖት ።

ወጭ ፡ ወራጅ ፡ ሁሉ ፡ ይማርከ ዋል ፡ አሕዛብ ፡ እስራኤልን ፡ ከማ ረኩ ፡ በኋላ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አይ ውሉም ፡ አያድሩም ፡ አንድ ፡ ፈር ያን ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ ኒካው ፡ ማርኳቸዋልና ።

ወኮነ ፡ ዕፅለተ ፡ ለጎሩ ።

ለጎረ ፡ ቤቱ ፡ መሰዳደቢያ ፡ ሆነ ፡

፵፪ ፡ ወአልዓልከ ፡ የማነ ፡ ፀሩ ።

የጠላቶቹን ፡ ሥልጣን ፡ ከፍ ፡ ከፍ፡ አደረግህበት ።

ወአስተፍሣሕኮ ፡ ኵሉ ፡ ጸላዕቶ ።

ጠላቶቹን ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አሰኘህ በት

፵፫ ፡ ወሜጥከ ፡ ረድኤተ ፡ ኲናቱ ።

የጦሩን ፡ ረድኤት ፡ መለስህበት ፡ ማለት ፡ ድል ፡ ያደርግ ፡ የነበረ ፡ ድል ፡ እንዲሆን ፡ አደረግኸው ።

ወኢተወከፍኮ ፡ በውስተ ፡ ቀብዕ ።

በሰልፍ ፡ ጊዜ ፡ በረድኤት ፡ አልተ ቀበልኸውም ።

ወሠዓርኮ ፡ እምንጽሑ ።

ከክብሩ ፡ ለየኸው ፡ ከመንግሥቱ ፡ ሻርኸው ።

፵፬ ፡ ወነጻሕከ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ መንበሮ ።

መንግሥቱን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አዋ ረድህ ፡ አንድም ፡ መንበሩን ፡ በም ድር ፡ ጣልኸው ፡ እንዱ ፡ ድስት ፡ ሙሉ ፡ ወርቅ ፡ አገኘ ፡ እነዚያም ፡

2014 04 17

እንደሱ ፡ እናገኛለን ፡ መስሏቸው ፡ ዙፋኑን ፡ እየገለበጡ ፡ ጥለውታልና ፡ እንድም ፡ የዳዊት ፡ የሰሎሞን ፡ ዙፋን ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡ የተሠራ ፡ ነው ፡ ወርቁን ፡ ብሩን ፡ እንወስዳለን ፡ ሲሉ ፡ ከምድር ፡ ጥለውታልና ።

፵፭ ፤ ወአውኃድከ ፡ መዋዕለ ፡ መንበሩ ።

የመንግሥቱን ፡ ዘመን ፡ አሳነሥኸው ፡ የዳዊት ፡ የሰሎሞን ፡ መንግሥት ፡ ዓርባ ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ ነበር ፡ የዮአክስ ፡ የኢኮንያን ፡ መንሥት ፡ ሦስት፡ ሦስት፡ ወር፡ ነውና ።

ወሦጥከ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሐፍረተ ።

ሐፍረትን ፡ ጨመርህበት ፡ ማለት ፡ ድል ፡ መነሣትን ፡ አመጣህበት ።

፵፮ ፤ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ እግዚኦ ፡ ትመይጥ ፡ ለግሙራ ።

አቤቱ ፡ ገጸ ፡ ምሕረት ፡ ገጸ ፡ ረድኤትህን ፡ ከኔ ፡ ወደዚያ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ፈጽመህ ፡ ትመልሰዋለህ ፡ አንድም ፡ ከዚያ ፡ ወደኔ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ፈጽመህ ፡ ትመልሰዋለህ ፡ አንድም ፡ ትትመየጥ ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ፈጽመህ ፡ አትመለስም ።

ወይነድድ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ መዓትከ ።

መዓትህ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ በለዝያ ፡ አይነድባቸውም ፡ አንድም ፡ በኛ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ይነድብናል ።

፵፯ ፤ ተዘከር ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ኃይልየ ።

ኃይሌ ፡ አንድም ፡ ወገኔ ፡ ደካማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕወቅ ።

ቦኑ ፡ ለከንቱ ፡ ፈጠርኮ ፡ ለኵሉ ፡ ዕጓለ ፡ እመ ሕያው ።

ትሩፋን ፡ በባቢሎን ፡ ለመቅረት ፡ ነው ፡ የፈጠርከውን ፡ አንድም ፡ ለሁሉ ፡ አድርጎ ፡ ተናግሮታል ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠርከው፡ በመቃብር ፡ ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ ለመቅረት ፡ ነውን ።

፵፰ ፤ መኑ ፡ ሰብእ ፡ ዘየሐዩ ፡ ወኢይሬእያ ፡ ለሞት ።

አወጣህ ፡ የለምን ፡ ምን ፡ ያስቸኩልሃል ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሕያው ፡ ሁኖ ፡ የሚኖር ፡ ሞትንስ ፡ የማያይ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፡ አንድም ፡ አስነሣህ ፡ የለምን ፡ ቢለው፡ ጥንቱን ፡ የማይሞት ፡ ሞትንስ ፡ የማያይ ፡ ሰው ፡ ማነው ።

ወመኑ ፡ ዘያድኅና ፡ ለነፍሱ ፡ እምእደ ፡ ሲኦል ።

ሰውነቱን ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ከመውረድ ፡ የሚያድናት ፡ አንድም ፡ ነፍሱን ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ከመውረድ ፡ የሚያድናት ፡ ማነው ። ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፳፮ ።

፵፱ ፤ አይቴ ፡ ውእቱ ፡ ዘትካት ፡ ሣህልከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ የቀደመው ፡ ቸርነትህ ፡ ወዴት ፡ አለ ።



ዘመሐልከ ፡ ለዳዊት ፡ ገብርከ ፡ በጽድቅ ።

ላገልጋይህ ፡ ለዳዊት ፡ በውነት ፡ የማልከው ፡ መሐላ ፡ ወዴት ፡ አለ ።

፶ ፤ ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ዘፀዓልዎሙ ፡ ለአግብርቲከ ።

አቤቱ ፡ ባሮችህ ፡ ትሩፋንን ፡ የሰደቡአቸውን ፡ ስድብ ፡ አንድም ፡ የሚሳደቡ ፡ አሕዛብን ፡ አስብ ፡ አስበሕ ፡ አውጣን ።

ዘተወከፍኩ ፡ በሕፅንየ ፡ ብዙኃ ፡ አሕዛበ ።

በክንዴ ፡ የተሸከምኋቸው ፡ ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ፡ የተሸከምኋቸውን ፡ መሸከም ፡ አለ ፡ ድንኳ፡ ወንትዐዮ፡ ብኪ፡ እያሉ ፡ ኮር ፡ ይወጡባቸዋል ፡ ፈረፈር ፡ ይሻገሩባቸዋል ፡ የመሸታ ፡ ጠላ ፡ ይቀዱባቸዋልና ።

፶፩ ፤ ዘፀዓሉ ፡ ጸላዕትከ ፡ እግዚኦ ።

ጠላቶችህ ፡ ባቢሎናውያን ፡ የሚሳደቡትን ፡ ስድብ ፡ አስብ ፡ አንድም ፡ ጸላዕተከ ፡ የሚሳደቡ ፡ ጠላቶችህ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ።

ወፀዓሉ ፡ ዕቤራተ ፡ መሲሕከ ።

ቀብተህ ፡ ያነገሥሀቸው ፡ የነገሥታቱን ፡ እናት ፡ የሚሳደቡ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ አስብ ፡ ማርከው ፡ ወስደው ፡ ሞግዚት ፡ ደንገ ፡ ጡር ፡ ገረድ ፡ አበዛ ፡ ጋጋሪ ፡ ያደርጓቸዋል ፡ ያለመዱት ፡ ነውና ፡ አይሆንላቸውም ፡ ስለዚህ ፡ ሴትነታቸው ፡ ነውን ፡ ይሏቸዋልና ፡ አንድም ፡ ያለ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ይደርሱባቸዋል ፡ ስለዚህ ፡ ሴትነታቸው ፡ ምን ፡ ያጓድዳቸዋል ፡ ብለው ፡ ይሰድቧቸዋልና ፡ አንድም ፡ ዕብሬተ ፡ መሲሕከ ፡ ነገሥታቱ ፡ የነገሡባቸውን ፡ ዘመናት ፡ የሚሳደቡ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ አስብ ፡ የዮአክስ ፡ የኢኮንያን ፡ መንግሥት ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ መንግሥት ፡ ከመንግሥት ፡ ሊቈጠር ፡ ነውን ፡ እያሉ ።

፶፪ ፤ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለም ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን ።

እግዚአብሔር ፡ ለዘላለሙ ፡ ይክበር፡ ይመስገን ፡ ይኸውም ፡ ይደረግ ፡ ይደረግ ፡ መከራውን ፡ ተናግሮ ፡ ይትባረክ ፡ አለ ፡ ይሙት ፡ በቃ ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ እንዲሄድ ፡ እስከዚህ ፡ በሦስት ፡ ለይኩን ፡ ከፍሎ ፡ ተናግሮታል ።

## መዝሙር ፡ ፹፱ ።

፩ ፤ እግዚኦ ፡ ፀወነ ፡ ኮንከነ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ አቤቱ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ እምባ ፡ መፀግያ ፡ ሆንኸን ።

2014 04 17

፪ ፡ ዘእንበለ ፡ ይቁም ፡ አድባር ፡ ወይትፈ ጠር ፡ ዓለም ፡ ወምድር ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡ አንተ ፡ ክመ ።

እግዚአ ፡ ዘእንበለ ፡ ይቁም ፡ በል ፡ ተራራ ፡ ሳይፀና ፡ ሰማይ ፡ ምድር ፡ ሳይፈጠር ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበርህ ፡ ዓለምን ፡ አሣልፈህ ፡ መቼም ፡ መች ፡ የምትኖር ፡ አቤቱ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ እምባ ፡ መፀግያ ፡ ሆንኸን ፡ እንድም ፡ አቤቱ ፡ ተራራ ፡ ሳይፀና ፡ ሰማይ ፡ ምድር ፡ ሳይፈ ጠር ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበ ርህ ፡ ዓለምንም ፡ አሳልፈህ ፡ መ ቼም ፡ መች ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ እ ምባ ፡ መፀጊያ ፡ ሁነህ ፡ ትኖራለህ ፡ ኢዮ፲፩ ፡ ፮ ።

፫ ፡ ኢትሚጦ ፡ ለሰብእ ፡ ለኃሣር ።

ኃሣርን ፡ ለሰው ፡ ሰውን ፡ ለኃ ሣር ፡ (ለመከራ) ፡ አሳልፈህ ፡ አት ሰጠው ።

ወትቤ ፡ ተመየጡ ፡ ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕ ያው ።

አንተ ፡ ወትቤ ፡ ተመየጡ ፡ ከገ ቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመ ለሱ ፡ እኔም ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ም ሕረት ፡ እመለስላችኋለሁ ፡ ብለ ሃልና ፡ እኛም ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ተመልሰናልና ፡ አንተም ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ተመ ልሰህ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

፬ ፡ እስመ ፡ እሠርቱ ፡ ምዕት ፡ ዓመት ፡ በቅ ድሜከ ፡ ከመ ፡ ዕለት ፡ እንተ ፡ ትማልም ፡ ኃለፈት ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፰ ።

በሰው ፡ ዘንድ ፡ ሺህ ፡ ዘመን ፡ ባን ተ ፡ ዘንድ ፡ ትናንት ፡ እንዳለፈች ፡ እንደ ፡ አንዲት ፡ ዕለት ፡ ናትና ።

፭ ፡ ወሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ምንኑ ፡ ዓመታት ፡ በቅድሜከ ።

በሰው ፡ ዘንድ ፡ ሺህ ፡ ሰዓት ፡ ሌሊ ትና ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተናቀች ፡ እንደ ፡ አንዲት ፡ ሰዓት ፡ ናትና ፡ እንዳንተ ፡ አቈጣ ጠር ፡ ሳይሆን ፡ እንደኛ ፡ አቈጣጠር ፡ አይተህ ፡ አውጣኝ ።

፮ ፡ በጽባሕ ፡ ይሠርፅ ፡ ወየኃልፍ ።

ጢት ፡ ፈጥኖ ፡ በቅሎ ፡ ማታ ፡ እን ደሚጠፋ ፡ ሣር ፡ ነውና ።

ወሠርከሰ ፡ ይወድቅ ፡ የቢስ ፡ ወእንጸም ።

በሠርክ ፡ ግን ፡ ኳ ፡ ኩርኳ ፡ ብሎ ፡ ደርቆ ፡ ይወድቃል ፡ እንድም ፡ እ ንደሚወድቅ ፡ እንደ ፡ ዕፀ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ሰውም ፡ እንደዚያ ፡ ይጠ ፋልና ፡ ጽባሕ ፤ ሐምሌ ፡ ነሐሴ ፡ ሠርክ ፤ ኅዳር ፡ ታኅሣሥ ፡ ነው ። ኢዮ ፡ ፲፱ ፡ ፩—፪ ። ሲራ ፡ ፲፰ ፡ ፰፮ ። ኢሳ ፡ ፵፮ ፡ ፰ ። ማቴ ፡ ፮ ፡ ፴ ።



፯ ፡ እስመ ፡ ኃለቅነ ፡ በመዓትከ ።

በመዓትህ ፡ ተፈጽመናልና ፡ ይወ ድቅ ፡ እንድም ፡ እንዲህ ፡ ነውና ።

ወደንገፅነ ፡ በመቅሠፍትከ ።

በመቅሠፍትህ ፡ ደነገጥን ።

፰ ፡ ወሤምከ ፡ ኃጢአተነ ፡ ቅድሜከ ።

ኃጢአታችንን ፡ በፊትህ ፡ አኖርህ ፡ ማለት ፡ ታውቀዋለህ ፡ እንድም ፡ ታውቀዋለህና ፡ ።

ወዓለምነኒ ፡ ውስተ ፡ ብርሃነ ፡ ገጽከ ።

ደስ ፡ ብሎን ፡ የሠራነውን ፡ ኃጢ አታችንን ፡ ታውቀዋለህ ፡ እንድ ም ፡ ትሩፍ ፡ ዓለመኛ ፡ ነህና ፡ መ ከራ ፡ አይንካኝ ፡ ትል ፡ እንጂ ፡ ይሆናል ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኛስ ፡ ተድላችን ፡ የፊትህ ፡ ብር ሃን ፡ ተሥሎበት ፡ በተወለደ ፡ በ ሙሴ ፡ ጊዜ ፡ ቀርቷል ።

፱ ፡ እስመ ፡ ኀልቀ ፡ ኵሉን ፡ መዋዕሊነ ።

ዘመናችን ፡ በመከራው ፡ ተፈጽ ሟልና ፡ ወዓለምነኒ ። እንድም ፡ እ ንዲህ ፡ በመከራው ፡ ተፈጽሟልና ።

ወኀለቅነ ፡ በመቅሠፍትከ ።

በመቅሠፍትህ ፡ ተፈጸምን ።

፲ ፡ ወዓመቲነኒ ፡ ከመ ፡ ሣሬት ፡ ይከውና ።

ዘመኖቻችንም ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ይሆናሉ ፡ ማለት ፡ ሸረሪት ፡ ከእ ሳት ፡ የገባች ፡ እንደሆነ ፡ እጥንት ፡ ጉልጥምት ፡ የላትም ፡ ቀልጣ ፡ ትጠ ፋለች ፡ ሰውም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ደረሰ ፡ አይባልምና ።

ወመዋዕለ ፡ ዓመቲነ ፡ ፸ ፡ ክራማት ።

ትሩፋን ፡ በባቢሎን ፡ የሚኖሩት ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ነው ።

ወእመሰ ፡ በዙኅ ፡ ሰማንያ ፡ ዓም ። ኤር ፳፭ ፡ ፱-፲ ።

ከዚያም ፡ ዕልፍ ፡ ቢል ፡ ሰማንያ ፡ ዘ መን ፡ ነው ።

ወፈድፋዶንስ ፡ እምዕላ ፡ የማ ፡ ወሕማም ።

ከዚህ ፡ ከሰማንያ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በባቢሎናውያን ፡ ዘንድ ፡ ጻር ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ አትር ፈን ፡ እንገዛቸዋለን ፡ ማለታቸው ። እንድም ፡ በትሩፋን ፡ ዘንድ ፡ ጻዕ ር ፡ ገዓር ፡ ነው ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ሲፈ ጸም ፡ እወጣችኋለሁ ፡ ብሏቸዋል ፡ ይህ ፡ ከቀረ ፡ መቅረቱ ፡ ነውና ። እንድም ፡ (ወመዋዕለ ፡ ዓመቲነ) ፡ ለሁሉ ፡ አድርጎ ፡ ተናግሮታል ፡ ብሎ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖረው ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ነው ። (ወእመሰ ፡ በዝኃ) ፡ ዕልፍም ፡ ቢል ፡ ሰማንያ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ (ወፈድፋ ዶንስ) ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ጻዕር ፡ ገዓር ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ዓይን ፡ ይፈዛል ፡ ጆሮ ፡ ይደነግ ዛል ፡ አፍንጫ ፡ ያነዝዛል ፡ ወገብ ፡

2014 04 17

ይያዛልና ። አንድም ፡ ሰው ፡ ከዚ
ህ ፡ ዓለም ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡
ከሚኖረው ፡ ይልቅ ፡ በመከራ ፡
የሚኖረው ፡ ይበዛልና ።

አንድም፡ (ወመዋዕለ ፡ ዓመቲነ) ፡
ይህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖረው ፡ ሰባት ፡
ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ (ወእመሰ) ፡
ከሰባት ፡ ሺሕም ፡ እልፍ ፡ ቢል ፡
ስምንት ፡ ሺሕ፡ ነው ፡ (ወፈድፋ
ዶንሰ) ፡ ከስምንት ፡ ሺሕ ፡ በ
ኋላ ፡ ግን ፡ በጻድቃን ፡ ዘንድ ፡
ጸር ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ከስምንት ፡
ሺሕ ፡ በኋላ ፡ መጥቼ ፡ ይህን ፡ ዓ
ለም ፡ እሳልፌ ፡ ዋጋችሁን ፡ እሰ
ጣችኋለሁ ፡ ብሏቸዋል ፡ ይህ ፡
የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መቅረት ፡
ነውና ። አንድም ፡ በኃጥአን ፡ ዘ
ድ ፡ ጸዕር ፡ ገዓር ፡ ነው ፡ ማለት ፡
ከገሃነም ፡ መከራ ፡ የሲኦል ፡ መ
ከራ ፡ ይቀላል ፡ ይባላልና ።

እስመ ፡ ኀለፈት ፡ የዋሃት ፡ እምኔነ ፡ ወተገሠፅነ

ሕግ ፡ መጠበቅ ፡ አንድም ፡ ቅን
ነት ፡ ከኛ ፡ ጠፍቷልና ፡ በመከ
ራውም ፡ ተገሥፀናልና ፡ ወፈድፋ
ዶንሰ ፡ ሳለው ፡ አንድም ፡ ሕግ ፡
መጠበቅ ፡ ከኛ ፡ ጠፍቷልና ፡ በመ
ከራው ፡ ተገሠፅን ።

፲፩ ፡ መኑ ፡ የአምር ፡ ኀይለ ፡ መቅሠፍትከ ።

መከራ ፡ ባታመጣብን ፡ መቅሠ
ፍትህን ፡ የምታመጣበት ፡ ኃይል
ህን ፡ ማን ፡ ባወቀው ፡ ነበር ።

እምግርማ ፡ መዓትከ ፡ ኈልቆ ።

ከመዓትህ ፡ መፍራት ፡ የተነሣ ፡
ማለት ፡ መዓትህን ፡ ከመግለፅህ ፡
የተነሣ ፡ ተፈጸሙ ።

፲፪ ፡ ከመዝ ፡ አርኢ ፡ የማንከ ።

ኃልቁ ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ተናገርሁ ፡
ሥልጣንህን ፡ ግለጽ ።

ለምሁራን ፡ ልብ ፡ በጥበብ ።

ጥበብን ፡ አንድም ፡ ሕግን ፡ ለም
ናውቅ ፡ ለኛ ።

፲፫ ፡ ተመየጥ ፡ እግዚኦ ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ።

አቤቱ ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕ
ረት ፡ ተመለስ ፡ እንጂ ፡ የማትመ
ለስ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ።

ወተናበብ ፡ በእንተ ፡ አግብርቲከ ።

ስለ ፡ ባሮችህ ፡ ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተና
ገር ፡ ስጠኝ ፡ ፍጅታ ፡ ማለት ፡
አይደለም ፡ የግብር ፡ ሙግት ፡ ነው፡
ፍረድ ፡ ሲል ፡ ነው ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ፀገብነ ፡ በጽባሕ ፡ ምሕረተከ ።

በሰባ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ንጋት ፡ ደስ፡
የሚያሰኝ ፡ ቸርነትህን ፡ አግኝተና
ልና ፡ ደስ ፡ አለን ።

ተፈሣሕነ ፡ ወተሐሠይነ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕሊነ ።

ባለ ፡ ዘመናችን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡
ደስ ፡ አለን ።

፲፭ ፡ ወተፈሣሕነ ፡ ህየንተ ፡ መዋዕል ፡ ዘአሕ
መምከነ ።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ ተቀ
በልነ ፡ (ዘመን) ፡ ፈንታ ።



ታቦር ፡ ወአርሞንኤም ፡ በስመ ፡ ዚአከ ፡ ይትፌሥሑ ፤ መዝሙር ፡ ፹፰ ።



አንተ፡እግዚኦ፡አቅደምከ፡ግርሮታ፡ለምድር፤ ወግብረ፡እደዊከ፡እማንቱ፡ሰማያት፤ መዝሙር ፡ ፻፩ ።

2014 04 17







ወህየንተ፡ዓመት፡እንተ፡ርኢናሃ፡ለእኪት።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ የመከራዋን ፡ ዕናት ፡ ስለ ፡ አየነ ፡ (ዘመን) ፈንታ

፲፮። ርኢ፡ ላዕለ፡ አግብርቲከ፡ ወላዕለ፡ ተግባርከ፡ እግዚእ ።

እቤቱ ፡ ፍጥረቶችህ ፡ አገልጋዮችህ ፡ የሚሆኑ ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብን ፡ እይ ፡ ተመልከት ፡ ተግባርንና ፡ አግብርትን ፡ ላዕለንና ፡ ላዕለን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ አድርገህ ።

ወምርሆሙ ፡ ለደቂቆሙ ።

እንዲህ ፡ ዓይተህ ፡ ተመልከተህ ፡ ልጆቻቸው ፡ ትሩፋንን ፡ ከባቢሎን ፡ መርተህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም፡ አውጣቸው ።

፲፯፡ ለይኩን ፡ ብርሃኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ላዕሌነ ።

የእግዚአብሔር ፡ ረድኤቱ ፡ ይደረግልን ።

ወይሠርኅ፡ለነ፡ተግባረ፡እደዊነ ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእጃችን ፡ ሥራ ፡ የቀና ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ የተከልነው ፡ ይጸድቃል ፡ የዘራነው ፡ ይበቅላል ፡ እንድም ፡ የፈጣሪያችን ፡ ሚጠቱ ፡ ይደረግልን ፡ (ወይሠርኅ) ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቀኝ ፡ እጃችን ፡ መወርወር ፡ በግራ ፡ እጃችን ፡ መመከት ፡ ይሆንልናል ።

እንድም ፡ (እስመ ፡ ጸገብነ) ፡ ባምስት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ንጋት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ካንተ ፡ የሚገኝ ፡ ልጅነት ፡ አግኝተን ፡ ደስ ፡ ብሎናልና ፡ (ተፈግሕነ፡ ወተሐሠይነ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕሊነ) ፡ ባለ ፡ ዘመናችን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ አለን ፡ (ወተፈግሕነ ፡ ህየንተ ፡ መዋዕል ፡ ዘአሕመምከነ) አምስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ ስለ ፡ ተቀበልነ ፡ ፈንታ ፡ ደስ ፡ አለን ፡ ወህየንተ ፡ ዓመት ፡ እንተ ፡ ርኢናሃ ፡ ለእኪት) ፡ የመከራ ፡ ነፍስ ፡ ዕናቷን ፡ ስለ ፡ አየንበት፡ ዘመን ፡ ፋንታ ፡ ደስ ፡ አለን ፡ (ርኢ ፡ ላዕለ ፡ አግብርቲከ ፡ ወላዕለ ፡ ተግባርከ ፡ እግዚእ) ፡ ተግባር ፡ ከፍጥረቶችህ ፡ የሚሆኑ አዳምና ፡ ሔዋንን ፡ አግብርቲከ ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ እይ ፡ ተመልከት ፤ (ወምርሆሙ ፡ ለደቂቆሙ) ፡ እንዲህ ፡ አይተህ ፡ ተመልከተህ ፡ ልጆቻቸው ፡ ምዕመናንን ፡ ከሲኦል ፡ መርተህ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አውጣቸው ፤ (ለይኩን ፡ ብርሃኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ላዕሌነ) ፡ የፈጣሪያችን ፡ የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ብርሃኑ ፡ ወልድ ፡ በሥጋ ፡ ይሁን ፡ (ወይሠርኅ ፡ ለነ ፡ ተግባረ ፡ እደዊነ) ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡

2014 04 17

ሆኑ ፡ ትንቢተ ፡ ቃልን) ፡ የተናገር
ነው ፡ ትንቢት ፡ ያስተማርነው ፡
ትምህርት ፡ እውነት ፡ ይሆናል ፡
እንድም ፡ (ለይኩን ፡ ብርሃኑ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ላዕሌነ) ፡
የፈጣሪያችን ፡ የእግዚአብሔር ፡
ብርሃኑ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኛ ፡
ይደር ፡ (ወይሠርኅ ፡ ለነ ፡ ተግባረ ፡
እደዊነ) ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ፡
ጸሎተ ፡ ቃልን ፡ መሥዋዕት ፡ እደ
ዊን ፡ የጸለይነው ፡ ጸሎት ፡ የሠዋ
ነው ፡ መሥዋዕት ፡ ያርጋል ።

## መዝሙር ፡ ፺ ።

፩ ፤ ዘየኀድር ፡ በረድኤተ ፡ ልዑል ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ የ
ምዕመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ በል
ዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፡
ተጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ሕዝቅያስ ፡
እንድም ፡ ባሕታዊ ፡

ወይነብር ፡ ውስተ ፡ ጽላሎቱ ፡ ለአምላከ ፡ ሰማይ ።

ሰማይን ፡ በፈጠረ ፡ በእግዚአብሔ
ር ፡ ጽላሎተ ፡ ረድኤት ፡ ተጠብቆ ፡
የሚኖር ፡ ሕዝቅያስ ፡ እንድም ፡
ተጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ባሕታዊ ።

፪ ፤ ይብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስካይየ ፡ አንተ ።

እግዚአብሔርን ፡ አምባ ፡ መጸጊያዬ ፡
አንተ ፡ ነህ ፡ ይለዋል ።

አምላኪየ ፡ ወረዳእየ ፡ ወእትዌከል ፡ ቦቱ ።

ፈጣሪዬ ፡ ነው ፡ ረዳቴ ፡ ነው ፡ እ
ኔም ፡ ይረዳኛል ፡ ብዬ ፡ እምንበታ
ለሁ ።

፫ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይባልሐኒ ፡ እመሥገርት ፡
ነዓዊት ።

እሱ ፡ ከከባቢ ፡ ወዕመድ ፡ ያድነኛ
ልና ፡ እንድም ፡ ከሚከብቡኝ ፡ ከነ
ሰናከሬም ፡ እንድም ፡ ከመከራው ፡
እንድም ፡ ከፀብዓ ፡ ሰይጣን ፡ ያድ
ነኛልና ።

ወእምነገር ፡ መደንግጽ ።

ከሚያስደነግፅ ፡ ከሰናከሬም ፡ ነ
ገር ፡ እንድም ፡ ከሰይጣን ፡ ጦር ፡
ያድነኛልና ፡ መደንግፅ ፡ ቃል ፡
የሆውከ ፡ ልበ ፡ ብእሲ ፡ እንዲህ ፡
ምሳ ፡ ፲፪ ፡ ፳፭ ።

፬ ፤ ይጼልለከ ፡ በገበዋቲሁ ።

ሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ አመንህ ፡ አበጀህ ፡
በጽላሎተ ፡ ረድኤቱ ፡ ከመከራ
ው ፡ ይሠውርሃል ።

ወትትዌከል ፡ በታሕተ ፡ ክንፊሁ ።

በክንፈ ፡ ረድኤቱ ፡ ተጠብቀህ ፡
ትኖራለህ ።

ጽድቅ ፡ በወልታ ፡ የዓውደከ ።

ቸርነት ፡ እንደ ፡ ጋሻ ፡ ሁኖ ፡ ይጠ
ብቅሃል ።



፭ ፤ ወኢትፈርህ ፡ እምግርማ ፡ ሌሊት ።

ኢትፍራህም ፡ ይላል ፡ ከሌሊት ፡
መፈራት ፡ ማለት ፡ ከሰይጣን ፡
እንድም ፡ ከፀብዓ ፡ አጋንንት ፡ የተ
ነሣ ፡ አትፈራም ፡ አትፍራ ።

እምሐፅ ፡ ዘይሠርር ፡ በመዓልት ።

በመዓልት ፡ ከሚወረወር ፡ ጦር ፡
ማለት ፡ ከቀን ፡ ወራሪ ፡ ከፀብዓ ፡
አጋንንት ፡ አትፈራም ፡ አትፍራህ።

፮ ፤ እምግብር ፡ ዘየሐውር ፡ በጽልመት ።

በጨለማ ፡ ከሚሄድ ፡ ማለት ፡ ከሌ
ሊት ፡ ሰባሪ ፡ እንድም ፡ ከፀብዓ ፡
አጋንንት ፡ አትፈራም ፡ አትፍራ ።

እምድድቅ ፡ ወእምጋኔነ ፡ ቀትር ።

ከአደጋ ፡ ነገር ፡ ከሰናከሬም ፡ የተ
ነሣ ፡ አትፈራም ፡ አትፍራ ።

ሐተታ ፡ ሰናከሬም ፡ ከለኪሶን ፡ የስ
ፈረ ፡ በቀትር ፡ ነውና ፡ ጋኔን ፡ ቀ
ትር ፡ አለው ፡ እንድም ፡ ከፀብአ ፡
አጋንንት ፡ ከዲያብሎስ ፡ አትፈራ
ም ፡ ሰው ፡ ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡
ውሎ ፡ ቀትር ፡ ሲሆን ፡ ፀሐይ ፡ ና
ላውን ፡ ባቃጠለው ፡ ጊዜ ፡ አእም
ሮው ፡ ይፈዛል ፡ አጋንንት ፡ ድል ፡
ይነሡታልና ፡ እንድም ፡ ዲያብሎ
ስ ፡ አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ ድል ፡ የ
ነሣው ፡ (ያሳተው)፡ በቀትር፡ነውና።

፯ ፤ ይወድቁ ፡ በገቦከ ፡ ፲፻ ።

በግራህ ፡ በወረወርህ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፡
ሰዎች ፡ ይወድቃሉ ።

እዕላፍ ፡ በየማንከ ፡ ወኀቤከሰ ፡ ኢይቀርቡ ።

በቀኝህ ፡ በወረወርህ ፡ ጊዜ ፡ እ
ልፍ ፡ ሰዎች ፡ ይወድቃሉ ፡ ወዳን
ተ ፡ ግን ፡ አይቀርቡም ። እንድም ፡
(ይወድቁ ፡ በገቦከ ፡ ፲፻) ፡ በግራህ ፡
ባማተብህ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፡ አጋንንት ፡
ድል ፡ ይነሣሉ ፡ (እዕላፍ ፡ በየማ
ንከ) ፡ በቀኝህም ፡ ባማተብህ ፡ ጊዜ ፡
እልፍ ፡ አጋንንት ፡ ድል ፡ ይነሣሉ ፡
(ውኀቤከሰ) ፡ ወዳንተ ፡ ግን ፡ አይቀር
ቡም ።

፰ ፤ ወባሕቱ ፡ ትሬኢ ፡ በአዕይንቲከ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሲጠፉ ፡ ባይንህ ፡ ታያ
ለህ ፡ እንጂ ፡ አይቀርቡም ።

ወትሬኢ ፡ ፍዳሆሙ ፡ ለኃጥአን ።

እለሰናከሬም ፡ እንድም፡ አጋንንት ፡
ፍዳቸውን ፡ ሲቀበሉ ፡ ታያለህ ።

፱ ፤ እስመ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ተስፋየ ፡
መዝሙር ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ አለኝታዬ ፡ ነህና ፡
እዎን ፡ ይደረግልኛል ።

ልዑል ፡ ረሰይከ ፡ ፀወንከ ።

እንዲህ ፡ አልህ ፡ ሕዝቅያስ ፡ እን
ድም ፡ ባሕታዊ ፡ አበጀህ ፡ ልዑል ፡
እግዚአብሔርን ፡ አምባ ፡ መፀግያ ፡
አደረግህ ።

፲ ፤ ወኢይቀርብ ፡ እኩይ ፡ ኀቤከ ።

ሰናከሬም ፡ እንድም ፡ ዲያብሎስ ፡
ወደ ፡ አንተ ፡ አይቀርብም ።

2014 04 17

ወኢይበውዕ ፡ መቅሠፍት ፡ ቤተከ ።

መቅሠፍት ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ አይገባም ፡ እንድም ፡ በወገኖችህ ፡ አይታዘዝም ፡ እንድም ፡ ሰናክሬም ፡ እንድም ፡ ፀብዓ ፡ አጋንንት ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ አይገባም ።

፲፩ ፡ እስመ ፡ ለመላእክቲሁ ፡ ይኤዝዞሙ ፡ በእንቲአከ ።

ስለ ፡ አንተ ፡ መላእክትን ፡ ያዝዛቸዋልና ፡

ከመ ፡ ይዕቀቡከ ፡ በኵሉ ፡ ፍናዊከ ፡ ዘፀሸሮ ፡ ፭ ።

በሥራህ ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቁህ ፡ ዘንድ ፡ ማቴ ፡ ፬ ፡ ፮ ።

፲፪ ፡ ወበእደዊሆሙ ፡ ያነሥኡከ ።

ያንሥኡክም ፡ ይላል ፡ በእጃቸው ፡ ያነሡሃል ፡ እንድም ፡ ያነሡህ ፡ ዘንድ ፡

ከመ ፡ ኢትትዓቀፍ ፡ በዕብን ፡ እግርከ ።

ኢይትዓቀፍ ፡ በዕብን ፡ እግርከ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እግርህ ፡ በደንጊያ ፡ እንዳይመታ ፡ እንድም ፡ (ከመ ፡ ኢትትዓቀፍ ፡ በዕብን ፡ እግረከ) ፡ እግርህን ፡ በደንግያ ፡ እንዳትመታ ፤ ቅዱሳን ፡ ሲበቁ ፡ ባንበሳ ፡ በዘንዶ ፡ ይቀመጣሉና ። ሉቃ ፡ ፲ ።

፲፫ ፡ ላዕለ ፡ ተዝትላ ፡ ወከይሲ ፡ ትኬዕን ።

ላዕለ ፡ ተዝትላ ፡ በሰናክሬም ፡ ላይ ፡ ወከይሲ ፡ በመሮዳህ ፡ ላይ ፡ ትሠለጥናለህ ።

ወትከይድ ፡ አንበሳ ፡ ወከይሴ ፡ ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ።

ተዝትላ ፡ ያለውን ፡ አንበሳ ፡ ከይሲ ፡ ያለውን ፡ ከይሲ ፡ ብሎ ፡ ደገመው ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ብየ ፡ ተወከለ ፡ አድኅኖ ።

በኔ ፡ አምኗልና ፡ አድነዋለሁ ።

ወእከድኖ ፡ እስመ ፡ አዕመረ ፡ ስምየ ።

ስሜን ፡ መጥራት ፡ ወዷልና ፡ ከመከራው ፡ እሰውረዋለሁ ።

፲፭ ፡ ይጼውዓኒ ፡ ወእሰጠዎ ።

ይለምነኛል ፡ እኔም ፡ ልመናውን ፡ እቀበለዋለሁ ፡ የለመነኝን ፡ አደርግለታለሁ ።

ሀሎኩ ፡ ምስሌሁ ፡ አመ ፡ ምንዳቤሁ ። ኤር ፡ ፴ ፡ ፲፭ ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ነበርሁ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ (እሄሉ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ በመከራው ፡ ጊዜ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ እኖራለሁ ።

አድኅኖ ፡ ወእሴብሖ ።

ከመከራው ፡ አድኜ ፡ አከብረዋለሁ ፡ እንድም ፡ (አድኅኖ) ፡ ከመከራው ፡ አድነዋለሁ ፡ (ወእሴብሖ ፡ ቦቱ) ፡ ይላል ፡ እመሰገንበታለሁ ፡ እንድም ፡ እሱን ፡ አድኜ ፡ ክብሬን ፡ እገልጽበታለሁ ።

፲፮ ፡ ለኑኃ ፡ መዋዕል ፡ አጸግቦ ።

ኑኃ ፡ መዋዕለ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ረጅም ፡ ወራት ፡ ሰፊ ፡ ዘመናት ፡ ሰጥቼ ፡ ደስ ፡ አሰኘዋለሁ ።



ወአርእዮ ፡ አድኅኖትየ ።

ትድግናዬን ፡ እገልጽለታለሁ ፡ መዝ ፡ ፹፱ ፡ ፲፬ ፡ ፹፯ ፡ ኢሳ ፡ ፴፰ ፡ ፩ ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለአብና ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ክብርና ፡ ምስጋና ፡ ይግባቸው ። ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምፅአት ፡ ድረስ ፡ ከምፅአትም ፡ በኋላ ፡ ለዘላለሙ ፤

አሜን ።

በእውነት ፡ እንበል ፡ ሐሰት ።

## መዝሙር ፡ ፺፩ ።

፩ ፡ ይኄይስ ፡ ተአምኖ ፡ በእግዚአብሔር ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ እንደ ፡ ሰናክሬም ፡ በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡ ከመታመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መታመን ፡ (ማመን) ፡ ይበልጣል ፡ (ይሻላል) ።

ወዘምሮ ፡ ለስምከ ፡ ልዑል ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ስምህን ፡ ማመስገን ፡ ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብ ፡ ይበልጣል ፡ (ይሻላል) ።

እንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ስምህን ፡ ማመስገን ፡ ይበልጣል ፡ (ይሻላል) ።

፪ ፡ ወነጊር ፡ በጽባሕ ፡ ምሕረተከ ።

ቸርነትህንም ፡ በቀን ፡ መናገር ፡ ይበልጣል ።

ወጽድቀከኒ ፡ በሌሊት ።

ምሕረትከ ፡ ወጽድቀከ ፡ ቸርነትህንም ፡ በመዓልት ፡ በሌሊት ፡ መናገር ፡ ይበልጣል ።

፫ ፡ በዘእሠርቱ ፡ አውታሪሁ ፡ መዝሙረ ፡ ማኅሌት ፡ ወመሰንቆ ።

ዐሥር ፡ አውታር ፡ ያለው ፡ የምስጋና ፡ በገና ፡ እየደረደሩ ፡ መሰንቆ ፡ እየመቱ ፡ እንድም ፡ ዐሥር ፡ ሕዋሳት ፡ ባለው ፡ ሰውነት ፡ በሃይማኖት ፡ ፀንቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መገዛት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማመስገን ፡ ይበልጣል ።

፬ ፡ እስመ ፡ አስተፍሣሕከኒ ፡ እግዚኦ ፡ በግብረከ ።

አቤቱ ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ ማለት ፡ ሰናክሬምን ፡ ገድለህ ፡ ደስ ፡ አሰኝተኸኛልና ፡ ይኄይስ ፡ እንድም ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፡

ወእትሐሠይ ፡ በግብረ ፡ እደዊከ ።

ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ በእጅህ ፡ በቃልህ ፡ በምትሠራልኝ ፡ ሥራ ፡ ማለት ፡ ድህነተ ፡ ደዌን ፡ አድርገህ ፡ ደስ ፡ ታሰኘኛለህ ።

2014 04 17

፭ ፡ ጥቀ ፡ ዐቢይ ፡ ግብርከ ፡ እግዚኦ ፡ ፈ... ።

አቤቱ ፡ ሥራህ ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ ረቂቅ ፡ ነው ።

ወፈድፋደ ፡ ዕሙቅ ፡ ሕሊናከ ።

ባሕርይህ ፡ እንድም ፡ ፍርድህ ፡ ፈጽሞ ፡ ጥልቅ ፡ ነው ።

፮ ፡ ብእሲ ፡ ዓብድ ፡ ኢያአምር ።

ሰነፍ ፡ ሰናክሬም ፡ እንድም ፡ ማናቸውም ፡ ሰነፍ ፡ ሥራህ ፡ ረቂቅ ፡ ባሕርይህ ፡ ፍርድህ ፡ ጥልቅ ፡ መሆኑን ፡ አያውቅም ።

ወዘአልቦ ፡ ልብ ፡ ኢይሌብዎ ፡ ለዝንቱ ።

ወዘአልቦ ፡ ልብ ፡ ለማለት ፡ ደገመው ፡ ልብ ፡ የሌለው ፡ ሰናክሬም ፡ እንድም ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ አያስተውለውም ።

፯ ፡ ሶበ ፡ ይበቊሉ ፡ ኃጥኣን ፡ ከመ ፡ ሣዕር ።

እለ ፡ ሰናክሬም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ በዝተው ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡

ወይሠርፁ ፡ ኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።

ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ እነሰናክሬም ፡ በዝተው ፡ ቢነሡ ፡

ከመ ፡ ይሠረዉ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

እንዲህ ፡ በዝተው ፡ ሊቀሩ ፡ አይደለም ፡ ለዘላለም ፡ ተንቃቅለው ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡

፰ ፡ አንተሰ ፡ ልዑል ፡ ለዓለም ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ለዘላለም ፡ የምትኖር ፡ ልዑል ፡ ነህ ፡ አጥፊ ፡ ለጥፋት ፡ የሚልህ ፡ የለም ።

፱ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ጸላእትከ ፡ ይትኀጐሉ ።

እነሆ ፡ ጠላቶችህ ፡ እለሰናክሬም ፡ ይጠፋሉና ፡ አንተሰ ፡ ልዑል ፡

ወይዘረዉ ፡ ኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።

ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋሉና ።

፲ ፡ ወይትሌዓል ፡ ቀርንየ ፡ ከመ ፡ ዘሐርኰ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ከብሬ ፡ ገንኜ ፡ እኖራለሁ ፡ እንድም ፡ የኔ ፡ ግን ፡ ሥልጣኔ ፡ ቀንዱ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ርኤም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላልና ፡ ልዑል ፡ ላለው ።

ወይጠልል ፡ በቅብዕ ፡ ሲበትየ ።

በዘይት ፡ ይለመልማል ፡ ማለት ፡ የምበላውን ፡ የምጠጣውን ፡ ሳላጣ ፡ ከልጅነት ፡ እስከ ፡ ሺበት ፡ እደርሳለሁ ፡ አረጃለሁ ።

፲፩ ፡ ወርእየት ፡ ዓይንየ ፡ በጸላእትየ ። መዝ ፡ ፶፫ ፡ ፯ ።

ዓይኔ ፡ ሠራዊቱ ፡ ጠፍተው ፡ አየች ፡ እንድም ፡ ዘከኑ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ዓይኔ ፡ በሠራዊቱ ፡ የተደረገውን ፡ አየች ።

ወሰምዓት ፡ ዕዝንየ ፡ ዲበ ፡ ሆሙ ፡ ለዕኩያን ፡ እለ ፡ ቆሙ ፡ ላዕሌየ ።

በጸላትነት ፡ በተነሡብኝ ፡ በክፉ ዎች ፡ ነገሥታቱ ፡ ላይ ፡ የተደረገ



ውንም ፡ ጆሮዬ ፡ ሰማች ፡ ቁም ፡ ላዕሌየ ፡ ወቅትለኒ ፡ እንዲል ፡

፲፪ ፡ ጻድቅሰ ፡ ከመ ፡ በቀልት ፡ ይፈሪ ። ኢዮ ፡ ፰ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ።

ጻድቅ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ግን ፡ እንድም ፡ ማናቸውም ፡ ጻድቅ ፡ እንደ ፡ ዘንባባ ፡ ያፈራል ፡ ማለት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ያገኛል ፡

ወይበዝኅ ፡ ከመ ፡ ዘግባ ፡ ዘሊባኖስ ።

በጸጋ ፡ እንደ ፡ ተተከለ ፡ ዘግባ ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ፆ ፡ ከፍሬ ፡ እንዲደርስ ፡ ብዙ ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ያገኛል ።

፲፫ ፡ ትኩላን ፡ እሙንቱ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ።

እነዚህም ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተተከሉ ፡ ናቸው ፡ እንድም ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተተከሉ ፡ እንደ ፡ ዘግባ ፡ እንደ ፡ ዘንባባ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ እንዲያፈራ ፡ እነሱም ፡ ብዙ ፡ ፀጋ ፡ ክብር ፡ ያገኛሉ ።

ወይበቊሉ ፡ ውስተ ፡ ዓጸዱ ፡ ለአምላክነ ።

በፈጣሪያችን ፡ ቦታ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንደ ፡ በቀሉ ፡ እንደ ፡ ዘግባ ፡ እንደ ፡ ዘንባባ ፡ ናቸው ።

፲፬ ፡ ውእተ ፡ አሚረ ፡ ይበዝኁ ፡ በርሥኣን ፡ ጥሉል ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ በሳ ፡ ንጉሥ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ ሕፃን ፡ አረጋዊ ፡ በበሳ ፡ ዕርግና ፡ ያረጃሉ ፡ ማለት ፡ ሕፃኑ ፡ ወተት ፡ ፍትፍት ፡ ሳያጣ ፡ አረጋዊው ፡ መውጣት ፡ መውረድ ፡ ሳይኖርበት ፡ ይኖራል ።

ወይከውኑ ፡ ዕሩፋነ ።

ከመከራው ፡ ያርፋሉ ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ይኖራሉ ።

፲፭ ፡ ወይነግሩ ፡ ከመ ፡ ጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይነግራሉ ፡ ያስተምራሉ ፡ እንድም ፡ (ይንግሩ) ፡ ያስተምሩ ።

ወአልቦ ፡ ዐመፃ ፡ በኀቤሁ ።

በሱም ፡ ዘንድ ፡ ሐሰት ፡ እንደ ፡ ሌለበት ፡ ይነግራሉ ፡ ያስተምራሉ ፡ እንድም ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ ሐሰት ፡ የለበትም ።

መዝሙር ፡ ፺፪ ።

፩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነግሠ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለብሰ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ እግዚአብሔር ፡ ነግሦ ፡ (የመንግሥቱን ፡ የጌትነቱን ፡ ልብስ ፡ ለበሰ) ፡ ማለት ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሠራ ።

2014 04 17

ለብሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይሎ ፡ ወተቀንተ ።

ስብሐቲሁ ፡ ለብሰ ፡ ወኃይሎ ፡ ቀንተ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ እግዚእ አብሔር ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፡ ኃይልንም ፡ እንደ ፡ ዝናር ፡ ታጠቀ ፡ ማለት ፡ በኃይላቸው ፡ የሚመኩ ፡ ኃያላንን ፡ አጠፋ ።

ወአጽንዓ ፡ ለዓለም ፡ ከመ ፡ ኢትትሀወክ ።

ይህችን ፡ ዓለም ፡ እንድም ፡ ኢያሩ ሳሌምን ፡ እንዳትናወጥ ፡ በረድ ኤት ፡ አፀናት ፡ ማለት ፡ ሀገራቱ ፡ እንዳትፈታ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እን ዳትፈርስ ፡ አደረጋት ።

፪፡ ድልው ፡ መንበርከ ፡ እግዚኦ ።

ንበርር ፡ ሲል ፡ ነው ፡ አቤቱ ፡ ጌት ነትህ ፡ ለዘላለም ፡ ፀንቶ ፡ ይኖራል ፡ (የኖረ ፡ ነው) ።

እምትካት ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡ አንተ ፡ ክመ ።

ትጌሉ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ቅድመ ፡ ዓ ለም ፡ የነበርህ ፡ ዓለምን ፡ አሳል ፈህ ፡ መቼም ፡ መች ፡ ትኖራለህ ፡ የምትኖር ፡ ነህ ። እንድም ፡ ነገሥ ፡ ብዬም ፡ ብናገር ፡ ሥራው ፡ ሐዲስ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ገናስ ፡ ነግሥ ፡ እንዳልልህ ፡ ጌት ነትህ ፡ ለዘላለም ፡ ፀንቶ ፡ የሚኖር ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበርህ ፡ ዓለምን ፡ አሳልፈህ ፡ መቼም ፡ መች ፡ የምት ኖር ፡ ንጉሥ ፡ ነህ ።

፫፡ አልዓሉ ፡ አፍላግ ፡ እግዚኦ ፡ አልዓሉ ፡ አፍላግ ፡ ቃላቲሆሙ ።

አቤቱ ፡ አፍላግ ፡ ቃላቸውን ፡ ፈጽ መው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ። [illegible]

እምቃለ ፡ ማያት ፡ ብዙኅ ።

ብዙ ፡ ውኆች ፡ ከመንባታቸው ፡ የተነሣ ።

፬፡ መንክር ፡ ተላዐፆ ፡ ለባሕር ።

የባሕር ፡ ጨዋታዋ ፡ ድንቅ ፡ ነው፡ ኃይለኛ ፡ ነፋስ ፡ የገሠጻት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ ተራራ ፡ ያህል ፡ ሆኖ ፡ ሲነሣ ፡ ያስደነግ ጣል ፡ መጠነኛ ፡ ነፋስ ፡ ሲነካት ፡ ግን ፡ ወለል ፡ ወለል ፡ እያለች ፡ ስትሄድ ፡ ደስ ፡ ታሰኛለችና ፡ እን ድም ፡ እንደ ፡ ፈረሰኛ ፡ ሁና ፡ ሲ ነሣ ፡ ደስ ፡ ያሰኛልና ።

መንክር ፡ እግዚአብሔር ፡ በአርያም ።

ድንቅስ ፡ በለኝ ፡ እስከ ፡ ዝየ ፡ ብጽ ሒ ፡ ብሎ ፡ የወሰነ ፡ በአርያም ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ።

እንድም ፡ (አልዓሉ ፡ አፍላግ) ፡ (አለዓሉ ፡ ቃላቲሆሙ) ፡ አቤቱ ፡ እስራኤል ፡ ቃላቸውን ፡ ለምስጋና፡ ፈጽመው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ፡ (እምቃለ ፡ ማያት) ፡ ከነቢያት ፡ ትንቢት ፡ ከካህናት ፡ ትምህርት ፡ የተነሣ ፡ (መንክር) ፡ የቤተ ፡ እስ ራኤል ፡ ሥርዓቷ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ (መንክርስ) ፡ ድንቅስ ፡ በለኝ ፡



ወስብሃ ፡ ዓም ፡ ሐሲቶ ፡ ብሎ ፡ የወሰነ ፡ በልዕልና ፡ ያለ ፡ እግዚእ ብሔር ።

እንድም ፡ (አልዓሉ ፡ አፍላግ ፡ ቃላቲሆሙ) ፡ ምዕመናን ፡ ቃላቸ ውን ፡ ለምስጋና ፡ ፈጽመው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ፡ (እምቃለ ፡ ማ ያት) ፡ ከሐዋርያት ፡ ትምርት ፡ የተነሣ ፡ (መንክር) ፡ የተምቀት ፡ ሥርዓቷ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ ያርባ ፡ የሰማንያ ፡ ቀን ፡ ያርባ ፡ የሰማንያ ፡ ዘመን ፡ ይጠመቃልና ፡ (መንክርስ) ፡ ድንቅስ ፡ በለኝ ፡ በነገሥ ፡ ዕለት ፡ አትወለድ ፡ እምወለትከ ፡ ብሎ ፡ ተምቀትን ፡ የሠራ ፡ በልዕልና ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ።

፭፡ ስምዓ ፡ [illegible] ።

እምልኮትህ ፡ ፈጽሞ ፡ የታመነ ፡ እውነተኛ ፡ ነው ።

ለቤትከ ፡ ይደሉ ፡ ስብሐት ፡ እግዚኦ ፡ ለነዋኀ ፡ መዋዕል ።

አቤቱ ፡ ለፊ ፡ ዘመናት ፡ ረጅም ፡ ወራት ፡ ለወገኖችህ ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ፡ እንድም ፡ አንተን ፡ ማመስገን ፡ ይገባቸዋል ፡ እንድ ም ፡ በወገኖችህ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ መመስገን ፡ ይገባሃል ፡ እን ድም ፡ ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ መመስ ስገን ፡ ይገባታል ፡ እንድም ፡ ለቤ ተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንድም ፡ ለም ዕመን ፡ መመስገን ፡ ይገባታል ።

## መዝሙር ፡ ፺፫ ።

፩፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ መስተበቅል ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናገርታል ፡ በምልዓት ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነት ፡ ፈራጅ ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ መስተበቅል ፡ ገሃደ ።

እግዚአብሔር ፡ ሲፈርድም ፡ ተገልጾ ፡ ይፈርዳል ፡ እንድም ፡ ገሃደ ፡ ለማ ለት ፡ ይገመው ፡ በለ ።

፪፡ ተለዐል ፡ ዘትኴንና ፡ ለምድር ።

በባቢሎን ፡ የሚፈርድባት ፡ እግዚእ ብሔር ፡ እስራኤልን ፡ አድና ፡ አሕዛ ብን ፡ አጥፍቶ ፡ ልዕልናውን ፡ ገለጸ ።

ፍድዮሙ ፡ ፍዳሆሙ ፡ ለዕቡያን ።

በባቢሎናውያን ፡ ፍዳቸውን ፡ አም ጣባቸው ።

፫፡ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ኃጥኣን ፡ እግዚኦ ።

ኃጥአን ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ይታ በያሉ ፡ እፍዘዙታል ፡ ይገለጠው ።

እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ይትሜክሑ ፡ ኃጥኣን ።

ኃጥአን ፡ ባቢሎናውያን ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ይታበያሉ ።

፬፡ ይትናገሩ ፡ ወይነቡ ፡ ዓመፃ ።

ዓመፃን ፡ እየተናገሩ ፡ ይከራከራሉ ፡

2014 04 17

ወይነሥኡ ፡ ዘሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ፡ ዳን ፡ ፲፩ ፡ ፳፯ ።

ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ ባቢሎናውያን ፡ ሁሉ ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ አትርፈን ፡ እንገዛለን ፡ እያሉ ፡ ዓመፅን ፡ ይናገራሉ ።

፭ ፡ ወአኅሠሩ ፡ ሕዝበከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ወገኖችህን ፡ ፲ን ፡ ነገድ ፡ አዋረዱ ።

ወሣቀዩ ፡ ርስተከ ።

ርስትህ ፡ ጉልትህ ፡ በሚሆኑ ፡ በሁለቱ ፡ ነገድም ፡ ሥቃይ ፡ አፀኑባቸው ።

፮ ፡ ወቀተሉ ፡ ዕቤረ ፡ ወዕጓለ ፡ ማውታ ።

ባልቴቱን ፡ እናት ፡ አባቱ ፡ የሞቱበት ፡ የድኃውንም ፡ ልጅ ፡ ገደሉ ።

ወቀተሉ ፡ ፈላሴ ።

ድኃ ፡ ገደል ፡ ናቸው ። ዘፀ ፡ ፳፪ ፡ ፳፩ ፡ ፳፬ ።

፯ ፡ ወይቤሉ ፡ ኢይሬኢ ፡ እግዚአብሔር ። ወኢየአምር ፡ አምላከ ፡ ያዕቆብ ።

ኢይሬእ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢየአምር ፡ አምላከ ፡ ያዕቆብ ፡ ብለህ ፡ አትና ፡ እረ ፡ ተዉ ፡ የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያይባችኋል ፡ ያውቅባችኋል ፡ ቢሏቸው ፡ የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያያልን ፡ ያውቃልን ፡ እሱስ ፡ አያይም ፡ አያውቅም ፡ አውቆም ፡ አይፈርድም ፡ አሉ ። ኢሳ ፡ ፳፱ ፡ ፲፭ ፡ ሕዝ ፡ ፰ ፡ ፲፪ ።

፰ ፡ ለብዉ ፡ አብዳን ፡ ሕዝብ ።

እላንት ፡ ሰነፎች ፡ ወገኖች ፡ የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲያይ ፡ እንዲያውቅ ፡ አውቆም ፡ እንዲፈርድ ፡ እወቁ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።

አብዳንኬ ፡ ማዕዜ ፡ ይጠበቡ ።

እኔ ፡ ቢቸግረኝ ፡ ለብዉ ፡ አብዳን ፡ ሕዝብ ፡ እያልሁ ፡ እነግራለሁ ፡ አስተምራለሁ ፡ እንጂ ፡ እሊህ ፡ አላዋቆች ፡ ባቢሎናውያን ፡ መቼ ፡ ያውቃሉ ፡ እንድም ፡ እላንት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አያውቅም ፡ አላችሁት ፡ እንጂ ፡ የማያውቅ ፡ መቼ ፡ ነው ።

፱ ፡ ዘተከለሁ ፡ ለዕዝን ፡ ኢይሰምዕኑ ። መዝ ፡ ፹፯ ፡ ፪ ።

ሌላው ፡ ሊሰማበት ፡ ጆሮን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እሱ ፡ ለራሱ ፡ አይሰማምን ፡ ኢየአምር ፡ ላለው ።

ወዘፈጠራሁ ፡ ለዓይን ፡ ኢይሬኢኑ ። ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፫ ።

ሌላው ፡ ሊያይበት ፡ ዓይንን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እሱ ፡ ለራሱ ፡ ዓያይምን ፡ ኢይሬኢ ፡ ላለው ፡ ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፳፪ ። ሉቃ ፡ ፲፰ ፡ ፯ ። ራዕ ፡ ፮ ፡ ፲ ።

፲ ፡ ዘይጌሥፆሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ኢይዛለፍኑ ።

በአሕዛብ ፡ የፈረደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በላንት ፡ አይፈርድምን ።



ዘይሜሕሮሙ ፡ ለሰብእ ፡ ጥበብ ።

ለሰው ፡ ጥበብን ፡ የሚገልጽ ፡ ሕግን ፡ የሚያስተምር ፡ አያውቅም ፡ አይፈርድምን ፡ ኢየአምር ፡ ላለው ።

፲፩ ፡ እግዚአብሔር ፡ የአምር ፡ ሕሊናሆሙ ፡ ለጠቢባን ፡ ከመ ፡ ከንቱ ፡ ውእቱ ።

እንኳን ፡ እሱን ፡ አያውቅም ፡ ልትሉት ፡ እናውቃለን ፡ የሚሉ ፡ የፈላስፎች ፡ ዕውቀት ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፡ (ታሪክ)፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ ፈላስፎች ፡ አንዱ ፡ ፈላስፋ ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ ፈርቶ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ የሞትሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አትቅበሩኝ ፡ ዕውቀት ፡ ይከፈልባችኋል ፡ ሥጋዬን ፡ ብትበሉት ፡ ግን ፡ ጥበብ ፡ ይገለጽላችኋል ፡ አላቸው ፡ ይሞታል ፡ ብለው ፡ ቢያዩት ፡ የማይሞት ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ እንጠብቀዋለን ፡ ብለው ፡ አርደው ፡ ሥጋውን ፡ ተቀራምተው ፡ በልተውታል ፡ በልዑ ፡ ዝግና ፡ ወሰትዩ ፡ መረቆ ፡ እንዲል ። አንዱ ፡ ሞትን ፡ የሚፈራ ፡ ነው ፡ በፍልስናው ፡ ዕፀ ፡ ሕይወትን ፡ አግኝቶ ፡ ባዲስ ፡ ሸክላ ፡ ዘፍዝፎ ፡ ከመንደር ፡ አጠገብ ፡ ያደረግሁት ፡ እንደሆን ፡ ለሰው ፡ ይተርፋል ፡ ብሎ ፡ ተመቅኝቶ ፡ ሰው ፡ ከማይደርስበት ፡ እታጠባለሁ ፡ ብሎ ፡ ተሸክሞ ፡ ለመታጠብ ፡ ሲሄድ ፡ ጌታ

ምቀኝነት ፡ አይወድምና ፡ በላዩ ፡ እንዳለ ፡ መልአኩ ፡ ሰበረበት ፡ በእኩሌታው ፡ አካሉ ፡ ፈሰሰበት ፡ እኩሌታው ፡ አካሉ ፡ ሕያው ፡ እኩሌታው ፡ አካሉ ፡ ምውት ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ ሁኗልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፳፪ ።

፲፪ ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘአንተ ፡ ገሠጽኮ ፡ እግዚኦ ።

እስከዚያውም ፡ ድረስ ፡ አቤቱ ፡ አንተ ፡ በመከራ ፡ የሠራኸው ፡ የቀጣኸው ፡ ትሩፋ ፡ እንድም ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። እዮ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ።

ወዘመሐርኮ ፡ ሕገከ ።

ሕግን ፡ የገለጽህለት ፡ ያስተማርከው ።

፲፫ ፡ ከመ ፡ ይትገሐሥ ፡ እመዋዕለ ፡ ዕኩያት ።

መቅሠፍት ፡ ከታዘዘባቸው ፡ ዘመናት ፡ እንድም ፡ እመዋዕለ ፡ እኩያን ፡ እኩያን ፡ ነገሥታት ፡ ከነገሡባቸው ፡ ዘመናት ፡ እንድም ፡ እመዋዕለ ፡ እኩያት ፡ ከክፉዎች ፡ ዘመናት ፡ ይርቅ ፡ ዘንድ ።

እስከ ፡ ይትከረይ ፡ ግብ ፡ ለኃጥእ ።

በባቢሎናውያን ፡ እስኪፈረድባቸው ፡ ድረስ ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ኢይገድፎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ።

እግዚአብሔር ፡ ዐሥሩን ፡ ነገድ ፡ መከራው ፡ አይጥላቸውምና ።

2014 04 17

ወኢየኃድጎሙ ፡ ለርስቱ ።

ርስቱ ፡ ጉልቱ ፡ የሚሆኑ ፡ ሁለቱ ንም ፡ ነገድ ፡ በመከራው ፡ አይ ጥላቸውምና ።

፲፫ ፡ እስከ ፡ ይትመየጥ ፡ ፍትሕ ፡ ለዘይጸድቅ ።

እውነተኛ ፡ ለሚሆን ፡ ለትሩፍ ፡ እስኪፈረድለት ፡ ድረስ ፡

ወዘሎሙ ፡ ርቱዓን ፡ ልብ ፡ እለ ፡ ኪያሃ ፡ በሙ ።

ይእቲ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ወሰምዓት ፡ ዮዲት ፡ በኪያሆን ፡ መዋዕል ፡ ወበ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ዕለት ፡ ወኪያሃ ፡ ሰዓት ፡ አልቦ ፡ ዘየአምራ ፡ እንዲል ፤ ቅን ፡ ልቡና ፡ ትሑት ፡ ሰብእና ፡ ሕግ ፡ መጠበቅ ፡ ላለባቸው ፡ ሁሉ ፡ እስኪፈረድ ።

፲፮ ፡ መኑ ፡ ይትቃወሞሙ ፡ በእንተ ፡ ዕኩያት ።

በባቢሎናውያን ፡ ፍዳ ፡ ይገባቸ ዋል ፡ ብዬ ፡ ብፈርድባቸው ፡ አይ ገባቸውም ፡ ብሎ ፡ የሚከራከረኝ ፡ ማን ፡ ነው ፡ እንድም ፡ ይትናሥ ዓኒ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ ባጠፋቸው ፡ ተው ፡ አታጥፋቸው ፡ ብሎ ፡ በጠላ ትነት ፡ የሚነሣብኝ ፡ ማን ፡ ነው ፤ (መኑ ፡ ይትቃወሞሙ) ፡ በኢጋንንት ፡ ፍዳ ፡ ይገባቸዋል ፡ ብዬ ፡ ብፈርድ ባቸው ፡ አይገባቸውም ፡ ብሎ ፡ የሚከራከረኝ ፡ ማን ፡ ነው ፤ (ይት ናሥዓኒ) ፡ አጋንንትን ፡ ባጠፋቸው፡ ተው ፡ አታጥፋቸው ፡ ብሎ ፡ በጠ ላትነት ፡ የሚነሣብኝ ፡ ማን ፡ ነው ።

ኢዮ ፡ ፱ ፡ ፫ ።

ወመኑ ፡ ይትቃወመኒ ፡ በእንተ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ። ኢዮ ፡ ፱ ፡ ፰ ።

ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ ባቢሎናውያ ንን ፡ እንድም ፡ አጋንንትን ፡ አጠ ፋቸዋለሁ ፡ ብል ፡ ተው ፡ አታጥ ፋቸው ፡ ብሎ ፡ የሚከራከረኝ ፡ ማን ፡ ነው ።

፲፯ ፡ ሶበ ፡ አኮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘረድአኒ ።

እግዚአብሔር ፡ የረዳኝ ፡ ባይሆን ፡ እንድም ፡ የረዳኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባይሆን ፡ እንድም ፡ ከሁለት ፡ ባሕ ርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ከሁለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ሁኖ ፡ የረ ዳኝ ፡ ባይሆን ።

ሕቀ ፡ ከመ ፡ ዘእምኀደረት ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ሲኦል ።

ሰውነቴ ፡ በባቢሎን ፡ ልትቀር ፤ እንድም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ልት ወርድ ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ቀርቷት ፡ ነበር ፤ እንድም ፡ ነፍሴ ፡ በሲኦል ፡ ልትኖር ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ቀርቷት ፡ ነበር ።

፲፰ ፡ ወሶበ ፡ እቤ ፡ ድሕፀ ፡ እገርየ ።

ልቡናዬም ፡ በገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ በአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ተሰነካከለ ፡ ባልሁ ፡ ጊዜ ፡



ምሕረትከ ፡ እግዚኦ ፡ ረድአኒ ።

አቤቱ ፡ ቸርነትህ ፡ ረዳኝ ፡ እን ድም ፡ የረዳኝ ፡ ቸርነትህ ፡ ነው ፤ (ዘረድአኒ) ፡ ብለህ ፡ ነው ፤ እንድም፤ ወልድ ፡ ከሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ፡ ባሕርይ ፡ ከሁለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ሆኖ ፡ ረዳኝ ፤ እንድም ፡ (ዘረድአኒ) ፡ የረዳኝ ፡ ወልድ ፡ ነው ፡

፲፱ ፡ እግዚኦ ፡ በከመ ፡ ብዝኆ ፡ ሕማማ ፡ ለልብየ ።

አቤቱ ፡ እንደ ፡ ልቡናዬ ፡ ኀዘን ፡ ብዛት ፡ መጠን ፤

ናዝዞትከ ፡ አስተፍሥሐ ፡ ለልብየ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ኃሊቆ ፡ ብለህ ፡ የተናገርኸው ፡ ነገር ፡ ሰውነቴን ፡ ደስ ፡ አሰኛት ። ኢር ፡ ፳፱ ፡ ፲ ፡ ፭ ፡ ፲ ፡ ቶሮ ፡ ፩ ፡ ፩ ።

፳ ፡ ወኢይትቃወመከ ፡ መንበረ ፡ ዓመፃ ።

እኔን ፡ ከፋርስ ፡ ከባቢሎን ፡ ላው ጣ ፡ ባልህ ፡ ጊዜ ፡ የዓመፅ ፡ ዙፋን ፡ ብልጣሶር ፡ አይቃወምህም ።

ዘይፈጥር ፡ ፃማ ፡ ዲበ ፡ ትእዛዝ ።

ኢታምልክ ፡ ባዕደ ፡ አምላከ ፡ ዘእ ንበሌየ ፡ ብለህ ፡ በተናገርከው ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ጣዖት ፡ አምልኩ ፡ ብሎ ፡ የሚናገር ።

፳፩ ፡ ወይነዐዉ ፡ ለነፍሰ ፡ ጻድቅ ።

የጻድቅ ፡ ትሩፍን ፡ ሰውነት ፡ ለጥ ፋት ፡ የሚያድን ፡

ወይኴንኑ ፡ ደመ ፡ ንጹሐ ።

ንጹሕ ፡ የሚሆን ፡ የትሩፍን ፡ ደ ም ፡ የሚያፈስ ፡ እንድም ፡ (እግ ዚኦ ፡ በከመ ፡ ብዝኆ ፡ ሕማማ ፡ ለልብየ) ፡ አቤቱ ፡ እንደ ፡ ልቡ ናዬ ፡ ኀዘን ፡ ብዛት ፡ መጠን ፤ (ናዝ ዞትከ) ፡ በጉሙስ ፡ ዕለት ፡ ብለህ ፡ የተናገርከው ፡ ቃል ፡ ነፍሴን ፡ ደስ፡ አሰኛት ፤ (ወኢይትቃወመከ) ፡ እኔን ፡ ከሲኦል ፡ ከገሃነም ፡ ላውጣ ፡ ባልህ ፡ ጊዜ ፡ የዓመፅ ፡ ዙፋን ፡ ዲያ ብሎስ ፡ አይቃወምህም ፡ (ዘይፈ ጥር) ፡ ጻድቅ ፡ ኢትቅትል ፡ ብለህ ፡ በተናገርከው ፡ ላይ ፡ ነፍስ ፡ ግደሉ ፡ ብሎ ፡ የሚያስተምር ፡ (ወይነዕዋ)፡ የአዳምን ፡ ነፍስ ፡ ለቍራኛነት ፡ የሚያድን ፡ (ወይኴንን) ፡ ደመ ፡ በለስን ፡ የሚያስፈስስ ፡ እንድም ፡ (ዘይፈጥር) ፡ ለእመ ፡ በላዕከሙ ፡ በለስ ፡ ሞተ ፡ ትመውቱ ፡ ብለህ ፡ በተናገርከው ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ለእመ በላዕከሙ ፡ በለስ ፡ ትከውኑ ፡ አማ ልክተ ፡ ብሎ ፡ የሚያስተምር ፡ (የ ሚናገር) ፡ (ወይነዕዋ) ፡ የጌታን ፡ ነፍስ ፡ እቈራኛለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚ ቃጣ ፡ (ወይኴንን) ፡ የጌታን ፡ ደም ፡ የሚያፈስስ ።

፳፪ ፡ ወኮነኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀወንየ ።

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አምባ ፡ መጸ ግያ ፡ ሆነኝ ፤

አምላኪየ ፡ ወረድኤተ ፡ ተስፋየ ።

አለኝታዬን ፡ የሚያደርግልኝ ።

2014 04 17

ፈጣሪዬ ፡ ነው እንድም ፡ ፈጣሪዬ ፡ አለኝታዬን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ ነው ።

፳፫ ፤ ወይፈድዮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ ዕከዮሙ ።

እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ቸው ፡ መጠን ፡ ፍዳቸውን ፡ ያመ ጣባቸዋል ።

ወያጠፍዖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጠ ፋቸዋል ።

መዝሙር ፡ ፺፭ ።

፩ ፤ ንዑ ፡ ንትፈሣሕ ፡ በእግዚአብሔር ።

ስለ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ ይህ ንም ፡ በዕረፍት ፡ ሳለ ፡ ተናግሮ ታል ፤ በእግዚአብሔር ፡ እምነን ፡ ደስ ፡ ይበለን ፤ እንድም ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡

ወንየብብ ፡ ለአምላክነ ፡ ወመድኀኒነ ።

ድኅነታችንን ፡ ለሚያደርግልን ፡ ፈጣሪያችን ፡ ምስጋና ፡ እናቅርብ ፤ እንድም ፡ እናቀርብ ፡ ዘንድ ።

፪ ፤ ወንብጻሕ ፡ ቅድመ ፡ ገጹ ፡ በአሚን ።

በሃይማኖት ፡ ፀንተን ፡ ከፊቱ ፡ እን ቅረብ ፤ እንድም ፡ በሃይማኖት ፡ ፀንተን ፡ ከፊቱ ፡ እንቀርብ፡ ዘንድ፤

ወበመዝሙር ፡ ንየብብ ፡ ሎቱ ።

በገናውን ፡ እየደረደርን ፡ ለሱ ፡ ም ስጋና ፡ እናቅርብ ፤ እንድም ፡ ለሱ ፡ ምስጋና ፡ እናቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ።

፫ ፤ እስመ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ገናና፡ ነውና ።

ወንጉሥ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አማልክት ።

አማልክት ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ ነውና።

እስመ ፡ ኢይገድፎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ።

እግዚአብሔር ፡ ወገኖቹን ፡ ትሩፋን ን ፡ በመከራው ፡ አይጥላቸውምና ፡ ንዑ ፡ ንትፈሣሕ ።

፬ ፤ እስመ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ኵሉ ፡ አጽና ፈ ፡ ምድር ። ሲራ ፡ ፲ ፡ ፬ ።

እስመ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ብለህ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ውረድ ፡ አኃዜ ፡ ዓለ ም ፡ በእራሁ ፡ እንዲለው ፡ ጽንፈ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ በመኻል ፡ እጁ ፡ ተይዟልና ።

አድባር ፡ ነዋኃት ፡ ዚአሁ ፡ ውእቱ ።

ረጃጅሙም ፡ ተራሮች ፡ የሱ ፡ ገን ዘቦች ፡ ናቸው ፤ ኢሳ ፡ ፵፬ ፡ ፲፭ ።

፭ ፤ እስመ ፡ እንቲአሁ ፡ ይእቲ ፡ ባሕር ፡ ወ ውእቱ ፡ ፈጠራ ።

ባሕር ፡ የሱ ፡ ገንዘብ ፡ ናትና ፡ እሱ ም ፡ ፈጥሯታልና ።



ወለየብስኒ ፡ እደዊሁ ፡ ገብራ ።

የብስንም ፡ ሥልጣኑ ፡ ፈጥሯታልና።

፮ ፤ ንዑ ፡ ንስግድ ፡ ወንግነይ ፡ ሎቱ ።

እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፡ ኑ ፡ እን ስገድለት ፡ እንገዛለት ፡ እንድም ፡ እንስግድለት ፡ እንገዛለት ፡ ዘንድ ፡ ኑ ።

ወንብኪ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘውእቱ ፡ ፈጠረነ ።

በፈጠረን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኑ ፡ እናልቅስ ፡ እንድም ፡ እናለቅስ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፡ ማልቀስ ፡ በወለደው ፡ በፈጠረው ፡ ነውና ። ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፮ ።

፯ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ አምላክነ ።

እሱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ነውና ።

ንሕነሰ ፡ ሕዝቡ ፡ አባግዐ ፡ መርዔቱ ።

የጥንተ ፡ ተገኘሮች ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ወገኖቹ ፡ ነን ።

፰ ፤ ዮም ፡ እመ ፡ ሰማዕክሙ ፡ ቃሎ ።

ምድረ ፡ ርስት ፡ ትገባላችሁ ፡ የሚ ል ፡ በሰማችሁ ፡ ጊዜ ።

ኢታጽንዑ ፡ ልበክሙ ።

አይችልም ፡ አያገባንም ፡ በማለት ፡ ልቡናችሁን ፡ አታፅኑ ፡ እንድም ፡ (ዮም) ፡ ትንሣኤ ፡ ዕርገት ፡ በአት ፡ ዕረፍት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንዳለ ፡ ቢነግሯችሁ ፡ (ኢታጽንዑ) የለም ፡ በማለት ፡ ልቡናችሁን ፡ አታፅኑት ።

ከመ ፡ አመ ፡ አምረርዎ ፡ በገዳም ።

በገዳም ፡ ባሳዘኑት ፡ ጊዜ ፡ እንዳሳ ዘኑት ፡ ኢታጽንዑ ፡ ልበክሙ ። እ ንድም ፡ በገዳም ፡ ባሳዘኑት ፡ ጊዜ ፡ እንዳሳዘናቸው ፡ አሳዝናችሁት ፡ እ ንዳያሳዝናችሁ ፡ ልቡናችሁን ፡ አታ ፅኑ ።

ወከመ ፡ አመ ፡ አመከርዎ ።

አምረርዎ ፡ በገዳም ፡ አመከርዎ ፡ በገዳም ፡ ነው ፤ በገዳም ፡ በተፈታተ ኑት ፡ ቀን ፡ ባሳዘኑት ፡ ጊዜ ፡ እንዳ ሳዘናቸው ፡ እንዳያሳዝናችሁ ፡ እን ዳሳዘኑት ፡ እንዳታሳዝኑት ፡ እንዳ ፀኑ ፡ አታፅኑ ።

፱ ፤ ዘአመከሩኒ ፡ አበዊክሙ ።

የፈተኑኝ ፡ አባቶቻችሁ ፡ ናቸው ። ፈተኑኒ ፡ ማንሻ ፡ እንድም ፡ የፈ ተኑኝ ፡ አባቶቻችሁ ።

ፈተኑኒ ፡ ወርአዩ ፡ ምግባርየ ።

ፈተኑኝ ፤ ፈተኑኝና ፡ ሥራዬን ፡ አወቁ ። ዘፀ ፡ ፲፮ ፡ ፮ ፡ ኢሳ ፡ ፷፫ ፡ ፲ ።

፲ ፤ አርብዓ ፡ ዓመተ ፡ ተቈጣዕክዎሙ ፡ ለ ይእቲ ፡ ትውልድ ።

ተቈጣዕክዎሙ ፡ ካለ ፡ ለእሙንቱ ፡ ለይእቲ ፡ ካለ ፡ ተቈጣዕክዋ ፡ ቢል ፡ በቀና ፡ ነበር ፤ ልማደ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ያርባውን ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ያርባ ፡ ዘመን ፡ መንገድ ፡ ይሁን ባቸው ፡ ብዬ ፡ ፈረድሁባቸው ፡

2014 04 17

አሕቲ ፡ ዕለት ፡ ትኩንክሙ ፡ ዓመ ፡ እንዲል ፡ እንደ ፡ ፍርታ ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ተከዜ ፡ ይመልሳቸው ፡ ነበርና ።

ወእቤ ፡ ዘልፈ ፡ ይስሕት ፡ ልቦሙ ።

ዘወትር ፡ ስሑታን ፡ ልብ ፡ ናቸው ፡ አልሁ ።

እሙንቱሰ ፡ ኢያእመሩ ፡ ፍናዊየ ።

እሊህ ፡ ግን ፡ ሥራዬን ፡ አላወቁም ፡ እንድም ፡ አባቶቻቸው ፡ እስራኤል ፡ ሥራዬን ፡ አላወቁም ፡ ልጆቻቸው ፡ አይሁድም ፡ ሥራዬን ፡ አላወቁም ።

፲፩ ፡ በከመ ፡ መሐልኩ ፡ በመዓትየ ።

ፈርጁ ፡ (ተቈጥቼ) ፡ ሕያው ፡ እኔ ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ማልሁ ።

ከመ ፡ ኢይበውኡ ፡ ውስተ ፡ ዕረፍትየ ። ዕብ ፫ ፡ ፯ ፡ ፲፩ ።

ወደ፡ምድረ፡ ርስት፡ እንድም፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንዳይገቡ ።

## መዝሙር ፡ ፺፮ ።

፩ ፡ ስብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስብሐተ ፡ ሐዲሰ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንግዳ ፡ ምስጋና ፡ አመስግኑት ።

ስብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵላ ፡ ምድር ።

እግዚአብሔርን ፡ በምድር ፡ መልታችሁ ፡ ያላችሁ ፡ ሁላችሁ ፡ አመስግኑት ።

፪ ፡ ስብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወባርኩ ፡ ለስሙ ።

እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ ስሙንም ፡ አመስግኑ ፡ ለስሙ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ ማለት ፡ ስሙን ፡ እየጸራችሁ፡አመስግኑት ። ሲራ ፡ ፴፱ ፡ ፴፭ ።

ወተዘያነዉ ፡ እምዕለት ፡ ዕለተ ፡ አድኅኖቶ ።

ዕለተ ፡ አድኅኖቱ ፡ ይላል ፡ ከዕለተ፡ ዲዋዌ ፡ ለይታችሁ ፡ ትድግናውን ፡ ያደረገባትን ፡ ዕለተ ፡ ሚጠትን ፡ እንድም ፡ እምዕለት ፡ ዕለተ ፡ አድኅኖቶ ፡ ብለህ ፡ ከቀን ፡ በቀን ፡ እያላችሁ ፡ ትድግናውን ፡ ተጨዋወቱ፡ ኢሳ ፡ ፶፪ ፡ ፯ ፡ ፶፰ ፡ ፪ ።

፫ ፡ ወንገርዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ስብሐቲሁ ።

ጌትነቱን ፡ ለአሕዛብ ፡ ንገሯቸው ።

ወለኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ተአምራቲሁ ።

ተአምራቱንም ፡ ለአሕዛብ ፡ ንገሯቸው ።

፬ ፡ እስመ ፡ ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወብዙኅ ፡ አኰቴቱ ። መዝ ፡ ፵፰ ፡ ፩ ።

እግዚአብሔር ፡ ገናና ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ ምስጋናውም ፡ ፍጹም ፡ ነውና ።



ወግሩም ፡ውእቱ ፡ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አማልክት ።

አማልክት ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፡ ሁሉ ፡ በላይም ፡ ግሩም ፡ ነውና ፤

፭ ፡ እስመ፡አማልክተ፡አሕዛብ፡አጋንንት ።

የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ግን ፡ አጋንንት ፡ ናቸውና ፤ የፈጠሩት ፡ የለም ፤

እግዚአብሔርሰ ፡ ሰማያተ ፡ ገብረ ።

እግዚአብሔርሳ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ትለኝ፡ እንደ፡ ሆነ፡ እግዚአብሔርስ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ ሰባቱን ፡ ሰማያት ፡ ፈጠረ ።

፮ ፡ አሚን ፡ ወሠናይት ፡ ቅድሜሁ ።

ሃይማኖት ፡ ምግባር ፡ በፊቱ ፡ ነው፡ ማለት ፡ ሃይማኖት ፡ ምግባርን ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ይወዳል ።

ቅድሳት ፡ ወዕበየ ፡ ስብሐት ፡ ውስተ ፡ መቅደሱ ።

አሚን ፡ ወሠናይት ፡ ያለውን ፡ ደገመው ፡ እንድም ፡ (ቅድሳት) ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡ መመስገን ፤ (ዕበየ ፡ ስብሐት) ፡ ዓቢይ፡ ስብሐት ፡ መባል፡ ገንዘቡ ፡ ነው ።

፯ ፡ አምጽኡ፡ለእግዚአብሔር፡በሐውርተ፡ አሕዛብ ።

አንጋደ ፡ አሕዛብ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የአሕዛብ ፡ ወገኖች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ፡ አምጽኡ ፡ ያለውን ፡ ያምጣው ።

አምጽኡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብረ ፡ ወስብሐተ ። መዝ ፡ ፳፰ ፡ ፩ ።

አመጣጡ፡ ክብርን ፡ ምስጋናን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ፡ አሁን ፡ ክብር ፡ ስብሐት ፡ እንደ ፡ ላም ፡ ተነድቶ ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ተጎትቶ ፡ የሚመጣ ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ፡ ክቡር ፡ ስቡሕ ፡ እያላችሁ ፡ አመስግኑት ፡ ሲል ፡ ነው ።

፰ ፡ አምጽኡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስብሐተ ፡ ለስሙ ።

ለእግዚአብሔር ፡ ለስሙ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፤

ንሥኡ ፡ መሥዋዕተ ፡ ወባኡ ፡ ውስተ ፡ አፅዋዲሁ ።

መሥዋዕቱን ፡ ይዛችሁ ፡ ወደ ፡ቤተ፡ እግዚአብሔር ፡ ግቡ ። ኤር ፡ ፴፫ ፡ ፲፩ ።

፱ ፡ ስግዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በዓፀደ ፡ መቅደሱ ።

ለእግዚአብሔር ፡ በቅጽረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እጅ ፡ ንሡ ።

ታድለቀልቅ ፡ እምቅድሜሁ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵላ ፡ ምድር ።

የእግዚአብሔር ፡ ገጸ ፡ መዓት ፡ ከመገለጽ ፡ የተነሣ ፡ ባቢሎን ፡ መላዋ ፡ ትጠፋለች ።

፲ ፡ በልዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነግሠ ።

እግዚአብሔር ፡ እስታውቆ ፡ እን

2014 04 17

ደ ፡ ነገሥ ፡ ለእሕዛብ ፡ ንገሯቸው ፡

ወዓፀንእ ፡ ለዓለም ፡ ከመ ፡ ኢታንቀልቅል ፡

ኢየሩሳሌም ፡ እንዳትናወጽ ፡ በረ ድኤት ፡ አፅናት ።

ወይኴንኖሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ በርትዕ ።

አሕዛብን ፡ በውነት ፡ ፈርዶ ፡ ያጠ ፋቸዋል ።

፲፩ ። ይትፌሣሕ ፡ ሰማያት ፡ ወትትሐሠይ ፡ ምድር ።

ሰማይና ፡ ምድር ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ ማለት ፡ ሰማይ ፡ ዝና ም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ ይሰ ጣል ፡ ምድርም ፡ የተከሉባትን ፡ ታጸድቃለች ፡ የዘሩባትን ፡ ታበቅ ላለች ፤ እንድም ፡ ሰማያት ፡ መ ላእክት ፡ ልዑላን ፡ (ምድር) ፡ ደ ቂቀ ፡ አዳም ፡ ትሑታን ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ ልዑላን ፡ ትሑ ታን ፡ በሁሉ ፡ እሉ ።

ወትትከወስ ፡ ባሕር ፡ በምልዓ ።

ባቢሎን ፡ ግን ፡ መላዋ ፡ ትደረጻ ለች ፡ ኢሳ ፡ ፲፬ ፡ ፯ ።

፲፪ ። ትትሐሠይ ፡ ገዳም ፡ ወኵሉ ፡ ዘውስ ቴታ ።

ይህቺ ፡ ዓለም ፡ በውስጧም ፡ የሚ ኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ እን ድም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በውስጧም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ፈት ፡ ሁናለችና ፡ ገዳም ፡ አላት ፡ ኢየሩሳሌምን ።

ውእተ ፡ አሚረ ፡ ይትፌሣሑ ፡ ኵሉ ፡ ዕፀወ ፡ ገዳም ።

ጌታ ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመ ከር ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፡ በበረኃ ፡ ያሉ ፡ ዕፀዋት ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ይለመልማሉ ፡ ያብባሉ ፡ ያፈራሉ ፡ እንድም ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጥተው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖ ሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል።

እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ይመጽእ ። ኢሳ ፡ ፴፭ ፡ ፩ ፡ ፶፱ ፡ ፲፫ ።

የእግዚአብሔር ፡ ገጽ ፡ ምሕረት ፡ ከመገለጹ ፡ የተነሣ ፡ ይመጽእ ፡ ይመጣልና ።

፲፫ ። ይመጽእ ፡ ወይኴንና ፡ ለምድር ።

መጥቶስ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለምድር ፡ ይፈርድላ ታል ፡ በምድር ፡ ይፈርድባታል ፤ ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተናገረ ፡ ለሁለ ቱም ፡ ያመጣል ።

ወይኴንና ፡ ለዓለም ፡ በጽድቅ ።

ለኢየሩሳሌም ፡ በውነት ፡ ይፈርድ ላታልና ፡ ይፈርድላታል ፡ ላለው ፡

ወለአሕዛብኒ ፡ በርትዕ ።

በባቢሎንም ፡ በውነት ፡ ይፈርድባታ ልና ፡ ይፈርድባታል ፡ ላለው ፤ እን ድም ፡ ከአካል ፡ ጣለው ፤ ለሕዝቡ ፡ ይፈርድላቸዋልና ፡ በአሕዛብ ፡ ግን ፡ ይፈርድባቸዋልና ።





፩ ። እግዚአብሔር ፡ ነግሠ ፡ ትትሐሠይ ፡ ምድር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ እግዚ አብሔር ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ደስ ፡ ይላ ታል ፡ ማለት ፡ የዘሩባትን ፡ ታበ ቅላለች ፡ የተከሉባትን ፡ ታጸድ ቃለች ። እንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሠርቷልና ፡ ትሩፍ ፡ ደስ ፡ ብሏት ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትወጣለች ።

ወይትሐሠያ ፡ ደሰያት ፡ ብዙኃት ።

ብዙ ፡ ደሴቶች ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ ማለት ፡ በደሴት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። ወንግር ምሙ ፡ ሠናይቶ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ደሴት ፡ እንዲል። እንድም ፡ ደሴት ፡ በወሀ ፡ እንዲከበብ ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ በመከራ ፡ የተከበቡ ፡ ትሩፋን ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ መከራው ፡ ርቆላቸው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፪ ። ደመና ፡ ወቆባር ፡ ዐውዱ ።

ደመና ፡ ጽጋግ ፡ በዙሪያው ፡ አለ ፡ ማለት ፡ በባሕርዩ ፡ ፅኑ ፡ መቅሠፍ ት ፡ አለ ።

ፍትሕ ፡ ወርትዕ ፡ ተድላ ፡ መንበሩ ።

ፍትሕ ፡ ርትዕ ፡ ምቹ ፡ ዙፋኑ ፡ ናቸ ው ። ኢሳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፫ ።

፫ ። እሳት ፡ የሐውር ፡ ቅድሜሁ ።

እሳት ፡ በፊቱ ፡ ይሄዳል ፡ ማለት ፡ መቅሠፍት ፡ በባሕርዩ ፡ አለ ።

ወነድ ፡ የዓገተሙ ፡ ለጸላእቱ ።

ጠላቶቹን ፡ እሳት ፡ ይከብባቸዋል ፡ ማለት ፡ መቅሠፍት ፡ ያጠፋቸዋል ።

፬ ። አስተርአየ ፡ መባርቅቲሁ ፡ ለዓለም ።

መባርቅት ፡ መዓቱ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ እንድም ፡ ለትሩፋን ፡ (ረጅ) ፡ ረዳት ጠበቃ ፡ በመሆን ፡ ተገለጸ ።

ርዕየት ፡ ወአድለቅለቀት ፡ ምድር ።

በዟዋዌ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በሚ ጠት ፡ ጊዜ ፡ ባቢሎን ፡ ጠፋች ። ኢሳ ፡ ፳፮ ፡ ፲፩ ።

፭ ። አድባርኒ ፡ ተመስጡ ፡ ከመ ፡ መዓር ።

ነገሥታቱ ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ ቀልጠው ፡ ጠፉ ። ኢሳ ፡ ፳፱ ፡ ፮ ።

እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ገጽ ፡ መዓቱ ፡ ከመገለጹ ፡ የተነሣ ።

እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵላ ፡ ምድር ።

የእግዚአብሔር ፡ ገጽ ፡ መዓቱ ፡ ከመ ገለጹ ፡ የተነሣ ፡ ባቢሎን ፡ መላዋ ፡ ትጠፋለች ። ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ፡ መዝ ፡ ፲፲ ፫ ፡ ፮ ።

2014 04 17

፮ ፡ ይነግራ ፡ ሰማያት ፡ ጽድቀ ፡ ዚአሁ ።

ሰማያት ፡ እንድም ፡ መላእክት ፡ ቸርነቱን ፡ ይነግራሉ ፡ ያስተምራሉ ።

ወርእዩ ፡ አሕዛብ ፡ ርእዩ ፡ ስብሐቲሁ ።

አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ጌትነቱን ፡ አዩ ፡ አወቁ ።

፯ ፡ ይትኃፈሩ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይሰግዱ ፡ ለግልፎ ።

ለተቀረጸ ፡ ለተጎነፈ ፡ ጣዖት ፡ የሚሰግዱ ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ፤ እንድም ፡ እጥብቀህ ፡ ያፍራሉ ፡ ይዋረዳሉ ።

ወእለ ፡ ይትሜክሁ ፡ በአማልክቲሆሙ ።

ቤል ፡ ዳጎን ፡ ያድነናል ፡ እያሉ ፡ በጣዖቶቻቸው ፡ የሚመኩ ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ፡ ያፍራሉ ፡ ይዋረዳሉ ።

ወይሰግዱ ፡ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክቲሁ ።

እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ ሁሉ ፡ ለራሳቸው ፡ ይባላቸው ፡ እንጂ ፡ ለሱስ ፡ መላእክት ፡ ሁሉ ፡ ይሰግዱለታል ፤ ይገዙለታል ። ኢሳ ፡ ፵፪ ፡ ፲፯ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፮ ።

፰ ፡ ሰምዓት ፡ ወተፈሥሐት ፡ ጽዮን ።

ልዑላኑ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወተሐሠያ ፡ አዋልደ ፡ ይሁዳ ።

የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ትሑታኑ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

በእንተ ፡ ፍትሕከ ፡ እግዚእ ።

አቤቱ፡አንተ ፡ ስለ ፡ ፈረድህላቸው ፤

፱ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ።
ቴትከ ፡ ልዑል ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ።

እግዚአብሔር ፡ በ፱ቱ ፡ መዓዝን ፡ ያለህ ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህና ፡ መዝ ፡ ፹፩ ።

ፈድፋደ ፡ ተለዓልከ ፡ እምኵሉ ፡ አማልክት ።

በስመ ፡ አምላክነት ፡ ከሚጠሩ ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመህ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አልህ። ኢሳ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።

፲ ፡ እለ ፡ ታፈቅርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጽልእዋ ፡ ለእኪት ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የምትወዱት ፡ ኃጢአትን ፡ ጣዖትን ፡ ጥሏት ፡ ተዋት ።

የዓቅብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነፍሰ ፡ ጻድቃኑ ።

እግዚአብሔር ፡ የትሩፋንን ፡ ሰውነት ፡ ከመከራ ፡ ይጠብቃልና ።

ወያድኅኖሙ ፡ እምእደ ፡ ኃጥአን ። ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፱ ፡ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፭ ።

ከባለጸጎችም ፡ እጅ ፡ ያድናቸዋልና፡ እንድም፡ ይጠብቃል፡ ያድናቸዋል ፡ ብለህ ፡ እሠር ።

፲፩ ፡ ብርሃ ፡ ሠረቀ ፡ ለጻድቃን ።

ለትሩፋን ፡ ሚጠት ፡ ተደረገላቸው፡ እንድም ፡ ለጻድቃን ፡ ጌታ ፡ ተወለደላቸው ።



ወለርቱዓነ ፡ ልብ ፡ ትፍሥሕት ።

ፈጽመው ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ትሑት ፡ ሰብዕና ፡ ላላቸው ፡ ለትሩፋን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ለጻድቃን ፡ ልጅነት ፡ ተሰጣቸው ።

፲፪ ፡ ይትፌሥሑ፡ጻድቃን፡በእግዚአብሔር።

ትሩፋን ፡ እንድም ፡ በቁሙ ፡ ጻድቃን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምነው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወይገንዩ ፡ ለዝክረ ፡ ቅድሳቱ ። መዝ ፡ ፳፱ ።

ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡ ለሚመሰገን ፡ ለስሙ ፡ መታሰቢያም ፡ ይገዛሉ ።

## መዝሙር ፡ ፺፯ ።

፩ ፡ ሰብሑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስብሐተ ፡ ሐዲሰ ። መዝ ፡ ፺፭ ፡ ፩ ፡ ፻፵፱ ፡ ፩ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንግዳ ፡ ምስጋና ፡ አመስግኑት ።

እስመ ፡ መንክር ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ድንቅ ፡ ነውና ።

ወአድኀኖቶ ፡ የማኑ ።

በሥልጣኑ ፡ የሚያደርገው ፡ ትድግናውም ፡ ድንቅ ፡ ነውና ።

ወመዝራዕቱ ፡ ቅዱስ ።

ሥልጣኑም ፡ ዕፁ ፡ ልዩ ፡ ነውና ።

፪ ፡ አርአየ ፡ እግዚአብሔር ፡ አድኅኖቶ ።

እግዚአብሔር ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡ ትድግናውን ፡ ገለጸ ፡ እንድም ፡ ባምስት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ወልድን ፡ በሥጋ ፡ ገለጸ ።

ወበቅድመ ፡ አሕዛብ ፡ ከሠተ ፡ ጽድቆ ።

በአሕዛብም ፡ ፊት ፡ ወ[illegible]

ሐሊቆን ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ኪዳኑን ፡ እንድም ፡ በእጋንንት ፡ ፊት ፡ በኅሙስ ፡ ዕለት ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ኪዳኑን ፡ ገለጸ ።

፫ ፡ ወተዘከረ ፡ ሣህሎ ፡ ለያዕቆብ ።

ለሁሉቱ ፡ ነገድ ፡ ይቅርታውን ፡ አሰቦ ፡ እንድም ፡ ለያዕቆብ ፡ ዘነፍስ ፡ ይቅርታውን ፡ አሰቦ ።

ወጽድቆሂ ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል ።

ቸርነቱንም ፡ ሏሥሩ ፡ ነገድ ፡ እንድም ፡ ለእስራኤል ፡ ዘነፍስ ፡ አሰቦ፡

ርእዩ ፡ ኵልክሙ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ፡ አድኅኖቶ ፡ ለአምላክነ ።

የምድር ፡ ዳርቻ ፡ በምትሆን ፡ በቁላት ፡ ጎዘን ፡ ያላችሁ ፡ ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ እንድም ፡ በነቢብ ፡ በገቢር ፡ ፍዳ ፡ የተያዛችሁ ፡ መላችሁ ፡ የፈጣሪያችንን ፡ ትድግናውን ፡ እወቁ ።

፬ ፡ የብቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ ምድር ።

ባራቱ ፡ መዓዘን ፡ ያላችሁ ፡ ትሩፋን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡

2014 04 17

አቅርቡ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመ
ስግኑ ። መዝ ፡ ፷፭ ፡ ፩ ፡ ፺፱ ፡ ፩ ።

ሰብሑ ፡ ተፈሥሑ ፡ ወዘምሩ ።

ሰብሑ ፡ ወዘምሩ ፡ ወተፈሥሑ ፡
ነው ፡ ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ አመስግኑ ፡
ለሱ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ አንድም ፡
እግዚአብሔርን ፡ በማመስገናችሁ ፡
ደስ ፡ ይበላችሁ ።

፭ ፤ ዘምሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመሰንቆ ።

መሰንቆውን ፡ እየመታችሁ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።

በመሰንቆ ፡ ወበቃለ ፡ መዝሙር ።

መሰንቆና ፡ መሰንቆ ፡ አንድ ፡ ወገ
ን፡ መሰንቆውን፡ እየመታችሁ፡ በበ
ገና ፡ ዕቃ ፡ (ቃል) ፡ ምስጋና ፡ አቅ
ርቡ ።

፮ ፤ በቀርነ ፡ ዝብጦ ፡ ወበቃለ ፡ ቀርን ።

ስንተል ፡ ነጋሪትም ፡ እየመታችሁ፡
አንድም፡ተመትቶ፡የተሠራ፡ነጋሪት፡
እየመታችሁ ፡ አንድም ፡ ዝብጡ ፡
ቀርነ ፡ ነጋሪት ፡ ምቱ ፤ አንድም ፡
ተራ ፡ ነጋሪትም ፡ እየመታችሁ ፡

ወየብቡ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሥ ።

በቤተ ፡ መቅደስ ፡ እግዚአብሔርን ፡
አመስግኑት ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ሁሉ ፡ (ቅድመ) ፡ ፊቱ ፡ ሲሆን ፡
ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ቅድሙ ፡ ይለዋ
ልና ፡

፯ ፤ ወትትከወስ ፡ ባሕር ፡ በምልዓ ።

የላንትን ፡ ምስጋና ፡ ሰምታ ፡ ባቢ
ሎን ፡ በመላዋ ፡ ትደረጸለች ።

ዓለምኒ ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ።

ዓለም ፡ በቁሙ ፡ በዚህም ፡ ዓለ
ም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ። ኢሳ ፡ ፵፪ ፡ ፲፩ ።

፰ ፤ አፍላግኒ ፡ ይጠፍሑ ፡ እደ ፡ ኅቡረ ።

ነገሥት ፡ እስራኤል ፡ ደስ ፡ ይላቸ
ዋል ።

ወአድባርኒ፡ ይትሐሠዩ፡ እስመ፡በሀየ፡ይኴንና፡
ለምድር ።

በልቡና ፡ በነገር ፡ ለምድር ፡ ይፈ
ርድላታል ፡ በምድር ፡ ይፈርድባ
ታልና ፡ እስራኤልም ፡ ሁለቱ ፡ ነገ
ድ ፡ ካሥሩ ፡ ነገድ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡
ብሏቸው ፡ ባንድነት ፡ ያመሰግናሉ።

፱ ፤ ወይኴንና ፡ ለዓለም ፡ በጽድቅ ።

ለኢየሩሳሌም ፡ አንድም ፡ ለትሩ
ፍ ፡ በውነት ፡ ይፈርድላታልና ፤
ይፈርድላታል ፡ ላለው ፡ ስጥ ።

ወለአሕዛብኒ ፡ በርትዕ ።

በባቢሎን ፡ አንድም ፡ በአሕዛብ ፡
በውነት ፡ ይፈርድባታልና ፤ ይፈር
ባታል ፡ ላለው ፡ ስጥ ።

## መዝሙር ፡ ፺፱ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር፡ ነግሠ ፡ ይትገዘፉ፡አሕዛብ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡
ሠራ ፡ አሕዛብም ፡ ጠፉ ።



ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ ኪሩቤል ፡ አድለቅለቃ ፡
ለምድር ።

በኪሩቤል ፡ አድሮ ፡ የሚኖር ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ በዟዋዌ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሩ
ሳሌምን ፡ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ ባቢሎ
ንን ፡ አጠፋት ።

፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ ዐቢይ ፡ በጽዮን ፡

በጽዮን ፡ ሰማያዊት ፡ በጽዮን ፡ ምድ
ራዊት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ገናና ፡ ነው ።

ወልዑል ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አሕዛብ ።

ከአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ገናና ፡
አምላክ ፡ ነውና ።

፫ ፤ ኵሉ ፡ ይገኒ ፡ ለስምከ ፡ ዐቢይ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ ገናና ፡ ለሚሆን ፡
ስምህ ፡ ይገዛል ።

እስመ ፡ ግሩም ፡ ወቅዱስ ፡ ውእቱ ።

ዕፁዕ ፡ ከሐሊ ፡ ገናና ፡ ነውና ።

፬ ፤ ክቡር ፡ ንጉሥ ፡ ፍትሐ ፡ ያፈቅር ።

ክቡር ፡ ዘሩባቤል ፡ አንድም ፡ ጌታ ፡
እውነት ፡ መፍረድን ፡ ይወዳል ።

አንተ ፡ አፅናዕከ ፡ ለጽድቅ ፡ በኀይልከ ።

አንተ ፡ ወልድ ፡ ዓም ፡ ሐሊቆን ፡
ብለህ ፡ ዕለተ ፡ ሚጠትን ፡ በከሀ
ሊነትህ ፡ አፀናኸት ፡ ማለት ፡ እን
ድትፈጸም ፡ አደረግኸት ፡ ፈጸም
ምኸት ።

ፍትሐ ፡ ወጽድቀ ፡ ለያዕቆብ ፡ አንተ ፡ ገበርከ ።

ፍትሐ ፡ ወጽድቀ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡
ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡ ሚጠትን ፡ አደ
ረግህለት ፡ ሚክ ፡ ፯ ፡ ፰ ።

፭ ፤ ተለዐሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራ
ኤልን ፡ አሕዛብን ፡ አጥፍቶ ፡ ልዕ
ልናውን ፡ ገለጸ ።

ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ መከየደ ፡ እገሪሁ ።

ከእግሩ ፡ መመላለሻ ፡ በታች ፡ ለ
ሱ ፡ ይሰግዱለታል ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ።

፮ ፤ እስመ ፡ ቅዱሳን ፡ እሙንቱ ፡ ሙሴ ፡ ወ
አሮን ፡ በክሀነቶሙ ።

ቅዱሳን፡ በክህነቶሙ ፡ ሙሴ ፡ ወአ
ወአሮን ፡ ሙሴ ፡ አሮንም ፡ በክህ
ነታቸው ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸ
ውና ፡ ይሰግዱለታል ። ዘሌ ፡ ፲፰ ፡ ፩ ።

ወሳሙኤልኒ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ይጼውዑ ፡ ስሞ ።

ሳሙኤልም ፡ ስሙን ፡ ከሚጠሩ ፡
ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ይሰግድለታል ፤ እን
ድም ፡ ሳሙኤል ፡ ወእለ ፡ ይጼውዑ፡
ስሞ ፡ ሳሙኤልና ፡ ስሙን ፡ የሚ
ጠሩ ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ይሰግዱለታል።

ይጼውዕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውእቱኒ ፡ ይሰ
ጠዎሙ ።

እግዚአብሔርን ፡ ይለምኑታል ፡
እሱም ፡ ልመናቸውን ፡ ይሰማቸ
ዋል ፡ ማለት ፡ የለመኑትን ፡ ያደር
ግላቸዋል ። [illegible]

፯ ፤ ወይትናገሮሙ ፡ በዓምደ ፡ ደመና ።

በረቂቅ ፡ እንድም ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ይነግራቸው ፡ ነበረ ፡ ሳሙኤልን ፡ ወደ:ት ፡ ተናግሮት ፡ ነበር ፡ ቢሉ ፡ እስራኤል ፡ አባ ፡ ጸሊ ፡ በእንቲአነ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ የመብረቅ ፡ የነጐድ ጓድ ፡ ድምፅ ፡ አሰምቷልና ።

ወየዐቅቡ ፡ ስምዖ ።

ኢታምልክን ፡ ይጠብቃሉ ።

ወትእዛዞ ፡ ዘወሀቦሙ ።

የሠራቸው ፡ ፲ቱን ፡ ሕጊጋትም ፡ ይጠብቃሉ ።

፰ ፤ እግዚኦ፡አምላክነ ፡ አንተ ፡ ሰማዕኮሙ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ አንተ ፡ ልመ ናቸውን ፡ ሰምተኻቸዋልና ።

እግዚኦ ፡ አንተ ፡ ተሣሃልኮሙ ።

አቤቱ፡አንተ፡ይቅር፡ብለኻቸዋልና ።

ወትትቤቀል ፡ በኵሉ ፡ ምግባሮሙ ።

በሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ ትፈርድላቸዋ ለህና ፡ ተበቀል ፡ ሊ.ተ ፡ እምዕድ ውየ ፡ እንዲል ።

፱ ፤ ተለዐሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራ ኤልን ፡ አድኖ ፡ አሕዛብን ፡ አጥ ፍቶ ፡ ልዕልናውን ፡ ገለጸ ።

ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ መቅደሱ።

መመስገኛው ፡ በምትሆን ፡ ደብረ ፡ መቅደስ ፡ በተሠራችባት ፡ በኢየሩ ሳሌም ፡ ይሰግዱለታል ።

እስመ ፡ ቅዱስ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አ ምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕኑዕ፡ ከሐሊ ፡ ነውና ።

## መዝሙር ፡ ፺፱ ።

፩ ፤ የብቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ ምድር። መዝ ፡ ፷፭ ፡ ፩ ። ፺፯ ፡ ፬ ።

በእራቱ ፡ መዓዝን ፡ በምልዓት ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፤ ለሱ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ አንድም፡ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ መልታችሁ ፡ ያላችሁ ፡ እናንተ ፡ እግዚአብሔ ርን ፡ አመስግኑ ።

፪ ፤ ተቀነዩ፡ለእግዚአብሔር፡በትፍሥሕት።

ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ ። መዝ ፡ ፲፪ ፡ ፲፩ ።

ወባኡ ፡ ቅድሜሁ ፡ በሐሤት ።

ደስ ፡ እያላችሁ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅ ደስ ፡ ግቡ ።

፫ ፤ አእምሩ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ው እቱ ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እን ደሆነ ፡ እወቁ ።

ወውእቱ ፡ ፈጠረነ ፡ ወአኮ ፡ ንሕነ ።

እሱ ፡ እንደ ፡ ፈጠረን ፡ እኛ ፡ ፍጠ ረን ፡ እንዳላልነው ፡ አንድም ፡ እር



ስ ፡ በርሳችን ፡ እንዳልተፈጠርን ፡ አንድም ፡ እኛ ፡ እሱን ፡ እንዳልፈ ጠርነው ፡ እሱ ፡ እኛን ፡ እንደ ፡ ፈጠረን ፡ እወቁ ።

ንሕነስ ፡ ሕዝቡ ፡ ወአባግዐ ፡ መርዔቱ ።

እኛ ፡ ግን ፡ ወገኖቹ ፡ ነን ፡ ከዚያ ውም ፡ ዘንድ ፡ የጥንተ ፡ ተገገሮቹ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ ልጆች ፡ ተገገሮቹ ፡ ነን ። ኢሳ ፡ ፵፩ ፡ ፩ ።

፬ ፤ ባኡ ፡ ውስተ ፡ አናቅጺሁ ፡ በተጋንዮ ።

ተግታችሁ ፡ በማመስገን ፡ አንድም፡ በተጋንዮ ፡ ተግታችሁ ፡ ለማመስ ገን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግቡ ።

ወውስተ ፡ አዕጻዲሁ ፡ በስብሐት ፡ እመንዎ ።

ከቤተ ፡ መቅደስም ፡ ገብታችሁ ፡ በጥንተ ፡ ምስጋናው ፡ አመስግኑት ፡ አመኑ፡ወልድዮ፡እንዲል ። ኤር ፡ ፮ ፡ ፲፮ ።

፭ ፤ ወሰብሑ ፡ ለስሙ ፡ እስመ ፡ ኄር ፡ እግ ዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ቸር ፡ ነውና ፡ ለስሙ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ ስሙ ፡ ልዩ ፡ እሱ ፡ ልዩ ፡ ሆኖ ፡ አይ ደለም ፡ ስሙን ፡ እየጠራችሁ ፡ አመ ስግኑት ፡ ማለት ፡ ነው ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

ወለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ጽድቁ ።

ቸርነቱ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

## መዝሙር ፡ ፻ ።

፩ ፤ ምሕረተ ፡ ወፍትሐ ፡ እኀሊ ፡ ለከ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል። ምሕ ረትን ፡ ፍትሕን ፡ ታደርግልኛለህ ፡ ብዬ ፡ (እሴብሕ) ፡ አመስግናለሁ ።

እዜምር ፡ ወእሌቡ ፡ ፍኖተ ፡ ንጹሐ ።

ምሕረትን ፡ ፍትሕን ፡ እንድታደር ርግልኝ ፡ አውቄ ፡ አመሰግንሃለሁ ፡ ንጹሕ ፡ ሕግህንም ፡ እጠብቃለሁ ።

፪ ፤ ማዕዜ ፡ ትመጽእ ፡ ኀቤየ ።

ምሕረተ ፡ ወፍትሐ ፡ እኀሊ ፡ ለከ ፡ እዜምር፡ ወእሌቡ ፡ ፍኖተ፡ ንጹሐ ፡ ብ

ትላለህ ፡ እንጂ ፡ በኔ ፡ መቼ ፡ ታም ናለህ ፡ እለው ፡ ጌታ ፡ ትሩፋን ።

ወአሐውር ፡ በየውሀተ ፡ ልብየ ፡ ማዕከለ ፡ ቤትየ ።

እኔስ ፡ ጎዳኔ ፡ በቀል ፡ ሁኜ ፡ በወ ገኖቼ ፡ በእስራኤል ፡ መኻል፡ መቼ፡ እኖራለሁ ።

፫ ፤ ወኢረሰይኩ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንትየ ፡ ግ ብረ ፡ ዕከየ ።

ካይኖቼ ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ አላ ደረግሁም ፡ ማለት ፡ ላጥፋህ ፡ አላ

2014 04 17

ጸላእኩ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።

ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኢኮንያንን ፡ ጠላሁ ፡ እንድም ፡ ጠላሁ ፡ እንጂ ፡ ኢረሰይኩ ፡

፬ ፡ ወኢተለወ፤ ልብ ፡ ጠዋይ ።

ጠማማ ፡ አእምሮ ፡ ያለበት ፡ እኔን ፡ አይመስልም ። እንድም ፡ (ልበ ፡ ጠዋይ) ፡ የጠማማ ፡ የኢኮንያን ፡ የሴዴቅያስ ፡ እንድም ፡ የባቢሎናዊ ፡ ልብ ፡ እኔን ፡ አይመስልም ።

ሶበ ፡ ተግኅሠ ፡ ዕኩይ ፡ እምኔየ ፡ ኢያእመርኩ ። ዘዘ ፡ ፩፻ ፡ ፩ ፡ ፫ ።

ኢኮንያን ፡ ሴዴቅያስ ፡ እንድም ፡ ባቢሎናዊ ፡ ጣዖት ፡ ባመለከ ፡ ጊዜ፡ ሳጠፋው ፡ አልወደድሁም ።

፭ ፡ ዘየሐሚ ፡ ቢጾ ፡ በጽሚት ፡ ኪያሁ ፡ ሰደድኩ ።

ወንድሙን ፡ በቀስታ ፡ የሚያማ ፡ ኢኮንያን ፡ ሴዴቅያስን ፡ ከሕይወት ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ከተድላ ፡ ወደ ፡ መከራ ፡ አስወጥቼ ፡ ሰደድሁ ፡ ሰደድሁ ፡ እንጂ ።

ዕቡየ ፡ ዓይን ፡ ወስሱዓ ፡ ልብ ፡ ኢይትሀወል ፡ ምስሌየ ።

ባይኑ ፡ ብቅና ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ የሚመለከት ፡ ልቡ ፡ ለምግብ ፡ ጣዖት ፡ ለማምለኪ ፡ የሚሳሳ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ በረድኤት ፡ አንድ ፡ አይሆንም ፡

፮ ፡ አዕይንትየሰ ፡ ኅበ ፡ መሃይምናነ ፡ ምድር ።

የኔስ ፡ አይኖቼ ፡ በምድር ፡ የታመኑ ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ ይመለከታሉ ።

ከመ ፡ አንብሮሙ ፡ ምስሌየ ።

በረድኤት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ እኖራቸው ፡ ዘንድ ፡

ዘየሐውር ፡ በፍኖት ፡ ንጹሕ ፡ ውእቱ ፡ ይትለዓከኒ ።

በንጹሕ ፡ ግብር ፡ ፀንቶ ፡ የሚኖር ፡ ካህን ፡ ጽድቁ ፡ ነቢይ ፡ ጽድቁ ፡ ያስተምርልኛል ።

፯ ፡ ወኢይነብር ፡ ማዕከለ ፡ ቤትየ ፡ ዘይገብር ፡ ትዕቢተ ።

ትዕቢተኛ ፡ ኢኮንያን ፡ ሴዴቅያስ ፡ እንድም ፡ ባቢሎናዊ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ በረድኤት ፡ አይኖርም ።

ወኢያረትዕ ፡ ቅድሜየ ፡ ዘይነብብ ፡ ዓመፃ ።

ዓመፅን ፡የሚናገር፡ ኢኮንያን፡ ሴዴቅያስ ፡ ነገረ ፡ መንግሥቱን ፡ አያቀናም ።

፰ ፡ በጽባሕ ፡ እቀትሎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ኃጥአኒ ፡ ምድር ።

የዚህ ፡ ዓለም ፡ ኃጥአን ፡ ኢኮንያንን ሴዴቅያስን ፡ ሁሉ ፡ ፈርጄ ፡ አጠፋቸዋለሁ ።

ከመ ፡ እሥርዎሙ ፡ እምሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ለኵሎሙ ፡ ገብርተ ፡ ዓመፃ ።

የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ከም



ትሆን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ፡ እንድም ፡ (ምሕረተ ፡ ወፍትሐ ፡ እኀሊ ፡ ለከ) ፡ ምሕረትን ፡ ፍትሕን ፡ አደርግልሃለሁ ፡ ይላል ፡ ጌታ ፡ ትሩፍን ፡ (እዜምር ፡ ወእሌቡ ፡ፍኖተ ፡ ንጹሐ) ፡ እኔም ፡ እንጂ ፡ እንድታደርግልኝ ፡ አውቄ ፡ አመሰግንሃለሁ፡ ይላል ፡ ትሩፍ ፡ ጌታችንን። (ማዕዜ ፡ ትመጽእ ፡ ኀቤየ) ፡ ምሕረተ ፡ ወፍትሐ ፡ እኀሊ ፡ ለከ ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ በረድኤት ፡ ወደኔ ፡ መቼ ፡ ትመጣለህ ። (ወእሐውር ፡ በየውሀተ፡ ልብየ ፡ ማእከለ፡ ቤትየ)፡ እኔስ ፡ ጠላት ፡ ጠፍቶልኝ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጥቼ ፡ በዕረፍት ፡ መቼ፡ እኖራለሁ። (ወኢረሰይኩ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንትየ ፡ ግብረ ፡ እኩየ) ፡ ጣዖትን ፡ አላመለክሁም ። (ጸላእኩ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ) ፡ ዓመፅን ፡ የሚሠሩ፡ ባቢሎናውያንን ፡ጠላሁ ፡እንጂ፡ ኢረሰይኩ ። (ወኢተለወ፤ ልብ ፡ ጠዋይ፡የኢኮንያንን፡የሴዴቅያስን ፡ ልብ፡ ጠላሁ ፡ እንጂ ፡ ኢረሰይኩ ፡ (ሶበ ፡ ተግሕሠ ፡ ዕኩይ ፡ እምኔየ ፡ ኢያእመርኩ) ፡ ነቢየ ፡ ሐሰት ፡ ካህን ፡ ጣዖት ፡ ከኔ ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ ጣዖት ፡ አላመለክሁም ። (ዘየሐሚ ፡ ቢጾ ፡ በጽሚት ፡ ኪያሁ ፡ ሰደድኩ) ፡ ወንድሙን ፡ በቀስታ ፡ የሚያማ ፡ ኢኮንያን ፡ ሴዴቅያስን ፡ ከሕይወት ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ አስወጥቼ ፡ ሰደድሁ ፡ እንጂ ፡ ኢያእመርኩ ። (ዕቡየ ፡ ዓይን ፡ ወስሱዓ ፡ ልብ ፡ ኢይትሀወል ፡ ምስሌየ) ፡ ባይኑ ፡ ብቅና ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ የሚመለከት ፡ ልቡ፡ ጣዖት ፡ ለማምለክ ፡ የሚሳሳ ፡ በኔ ፡ ነግሦ ፡ አይኖርም ፡ (አዕይንትየሰ ፡ ኀበ ፡ መሃይምናነ ፡ ምድር) ፡ የኔስ ፡ ዓይኖቼ ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ ይመለከታሉ ፡ (ከመ ፡ አንብሮሙ ፡ ምስሌየ) ፡ በመምርነት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ እኖራቸው ፡ ዘንድ ፡ (ዘየሐውር ፡ በፍኖት ፡ ንጹሕ ፡ ውእቱ ፡ ይትለዓከኒ) ፡ በንጹሕ ፡ ግብር ፡ ፀንቶ ፡ የሚኖር ፡ ካህን ፡ ጽዱቁ ፡ ነቢየ ፡ ጽድቁ ፡ ያስተምርልኛል ።(ወኢይነብር ፡ ማዕከለ ፡ ቤትየ ፡ ዘይገብር ፡ ትዕቢተ) ፡ ትቢተኛ ፡ ኢኮንያን ፡ ሴዴቅያስ ፡ በወገኖቼ ፡ ነግሦ ፡ አይኖርም ፡ (ወኢያረትዕ፡ ቅድሜየ፡ ዘይነብብ ፡ ዓመፃ) ፡ ዓመፅን ፡ የሚናገር ፡ ኢኮንያን ፡ ሴዴቅያስ ፡ ነገሩን ፡ መንግሥቱን ፡ አያቀናም ፡ (በጽባሕ ፡ እቀትሎሙ ፡ ለኵሎሙ፡ ኃጥአኒ ፡ ምድር) ፡ በቀኖና ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እየጸለይሁ ፡ አጠፋቸዋለሁ፡ (ከመ፡ እሥርዎሙ፡እምሀገረ፡ እግዚአብሔር፡ ለኵሎሙ፡ገበርተ፡ዓመፃ)፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ከምት

2014 04 17

ሆን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ዓመፅን ፡ የሚሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡

፲፱ ፤ ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለ ዓመ ፡ ዓለም ። አሜን ።

## መዝሙር ፡ ፻፩

ጸሎት ፡ ባሕታዊ ፡ ሶበ ፡ ይቴክዝ ፡ ወይክዑ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስዕለቶ ።

ጸሎት ባሕታዊ ፡ ዘጸለየ ፡ ባሕታዊ ፡ ይላል ፤ ትሩፍ ፡ አንድም ፡ ማናቸ ውም ፡ ባሕታዊ ፡ ባዘነ ፡ በተከዘ ፡ ጊዜ ፡ ልመናውንም ፡ ወደ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የጸለየው ፡ ጸሎት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ የተ ናገረው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ወጸለየ ፡ ጦቢት ፡ ጸሎተ ፡ ትፍሥሕት ፡ ጸሎ ት ፡ ብሂል ፡ ተናገሮ ፡ ምስለ ፡ እግዚ አብሔር ፡ እንዲል ።

፩ ፤ ስምዐኒ ፡ እግዚኦ ፡ ጸሎትየ ።

ስለ፡ትሩፋን፡ ተናግሮታል፡ አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወይብጻሕ ፡ ቅድሜከ ፡ ገዓርየ ።

ጩኸቴም ፡ ከፊትህ ፡ ይድረስ ።

፪ ፤ ወኢትሚጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔየ ።

ገጸ ፡ ምሕረትህን ፡ ገጸ ፡ ረድኤት ህን ፡ ከኔ ፡ ወደዚያ ፡ አትመልሰው ።

በዕለተ ፡ ምንዳቤየ ፡ አፅምዕ፡ ዕዝነከ ፡ ኀቤየ ።

በመከራዬ ፡ ቀን ፡ ዕዝነ ፡ ፈቃድ ህን ፡ ወደኔ ፡ መልሰህ ፡ ስማኝ ፤ ስ ማኝ ፡ እንጂ ፡ ኢትሚጥ ።

እመ ፡ ዕለተ ፡ እጼውዓከ ፡ ፍጡነ ፡ ስምዐኒ ፡ መዝ ፡ ፻፴፯ ፡ ፫ ።

በለመንኩህ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥነህ ፡ ልመ ናዬን ፡ ስማኝ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ኀልቀ ፡ ከመ ፡ ጢስ ፡ መዋዕልየ ።

ዘመኔ ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ ማለት ፡ ጢስ፡ በንኖ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ዘመኔም ፡ በ መከራው ፡ ተፈጽምዋልና ።

ወነቅፃ ፡ ከመ ፡ ሣዕር ፡ አዕፅምትየ ።

ሰውነቴም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ደርቋ ልና ።

፬ ፤ ተቀሠፍኩ ፡ ወየብሰ ፡ ከመ ፡ ሣዕር ፡ ልብየ ።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ በሠውጠ ፡ መከራ ፡ የተገረፍሁ ፡ ሆንሁ ፡ ልቡናዬም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ደረቀ ፡ ማለት ፡ አእ ምሮዬ ፡ ተለየኝ ።



እስመ ፡ ተረሥዓኒ ፡ በሊዓ ፡ ዕክል ።

ብተው ፡ ብተው ፡ እህል ፡ መብላት፡ ተዘንግቶኛልና ፡ አግኝቶ ፡ አይደ ለም ፡ ማጣቱን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፭ ፤ እምቃለ ፡ ገዓርየ ፡ ጠግዓ ፡ ሥጋየ ፡ ዲበ ፡ አዕፅምትየ ።

ከመከራዬ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሰው ነቴ ፡ ደረቀ ፡ አንድም ፡ ሥጋዬ ፡ ካጥንቴ፡ ጋራ ፡ ተጣጋ ። ኢዮ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።

፮ ፤ ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ ዓድግ ፡ መረብ ፡ ዘገዳም ፡ ኤር ፡ ፲፪ ፡ ፳፯ ።

በበረኃ ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ በዳ ፡ አ ህያ ፡ ሆንሁ ፡ ይህ ፡ የበዳ ፡ አህያ ፡ ቆርበተ ፡ ስስ ፡ ነው ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ ይጣሉታል ፡ ቀን ፡ ከቦታው ፡ አይወጣም ፡ ሌሊት ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ነፋስ፡ መልሶ ፡ አፉን ፡ ከፍት ፡ ከድን ፡ ከፍት ፡ ከድን ፡ ያደርገዋል ፡ ሐለ ስትዮታት ፡ ይቀውሙ ፡ ማዕከለ ፡ አድባር ፡ ወያበቅዉ ፡ አንፎሙ ፡ መንገለ ፡ ነፋስ ፡ እንዲል ።

መልአኩ ፡ የሣር ፡ የወሀ መዓዛ ፡ አምጥቶ ፡ ያሸተዋል ፡ የሦስት ፡ ቀን፡ መንገድ፡ ሂዶ፡ ሣሩን፡ በልቶ ፡ ወሀውን ፡ ጠጥቶ ፡ ተሐዋስያን ፡ ከቦታቸው ፡ ሳይወጡ ፡ ዕለቱን ፡ ከቦታው ፡ ገብቶ ፡ ያድራል ።

ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ ጉጋ ፡ ውስተ ፡ ሌሊተ ።

ውስተ ፡ ቤት ፡ ሌሊተ ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ ሌሊት ፡ ይላል ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዳለች ፡ ቁንጫ ፡ ሆ ንሁ ፡ እፂ ፡ አትተኛ ፡ ሰውን ፡ አታስተኛ ፡ በመከራ ፡ ታሳድራ ለች ፤ አንድም ፡ ከመ ፡ ጋጋኖ ፡ ይላል ፡ እንደ ፡ ጋጋኖ ፡ ሆንሁ ፡ ያ ፡ እየጮኸ ፡ እንዲያድር ፡ ባለመከራ፡ ሆንሁ ፡ አንድም ፡ ከመ ፡ ጉጋ ፡ እ ንደ ፡ ጉጉት ፡ ሆንሁ ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ አትወጣም ፡ ከዖፌ ፡ ንስር ፡ እስከ ፡ ዖፌ ፡ ድንቢጥ ፡ ያሉ ፡ አእዋፍ ፡ ሁሉ ፡ ይሠለጥኑበታል ፡ እንዲህ ፡ ሆንሁ ፡ አንድም ፡ ቤቷን ፡ በሰገ ነት ፡ እንደምትሠራ፡ ዖፍ ፡ ሆንሁ ፡ ቀን ፡ ስትሠራ ፡ ውላ ፡ ማታ ፡ ይጠ ፉታል ፡ አንድም ፡ ይፈርስባታል ፡ የት ፡ ውዬ ፡ የት ፡ ልደር ፡ እያለ ች ፡ እንድትኖር ።

፯ ፤ ተጋሕኩ ፡ ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ ዖፍ ፡ ባሕ ታዊ ፡ ውስተ ፡ ናኅስ ።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ ለመከራው ፡ የተጋሁ፡ በሰገነት ፡ እንደምትኖር ፡ ወፍም ፡ ሆንሁ ፡ የጭቃ ፡ ቤት ፡ ሠርታ ፡ የ ምትኖር ፡ ወፍ ፡ አለችና ፡ አንድ ም ፡ እንደ ፡ ጉጉት ፡ ሆንሁ ።

፰ ፤ ወትሎ ፡ አሚረ ፡ ይዔዕሉኒ ፡ ጸላእትየ ።

ጠላቶቼ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይሰድቡ ኛል ።

ወእለሰ ፡ ይሴቡኒ ፡ ይሰከትቶ ፡ ላዕሌየ ።

ስለ[illegible] ፡ ከሀገሬ ፡ አስወጥተው ፡ የሚ[illegible] ፡ (ይ[illegible]) ፡ ማ[illegible]

2014 04 17

ው ፡ የሚወስዱኝ ፡ በኔ ፡ ይማማሉ ፡ ብኛል ፡ ሴራ ፡ ይቆርጡብኛል ፡ ወዳንት ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ እስረህ ፡ ስደድልኝ ፡ ወደኔ ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ እስሬ ፡ እሰድድ ልሃለሁ እየተባባሉ ።

፱ ፡ እስመ ፡ሐመደ ፡ ከመ ፡ እክል ፡ ቀማሕኩ ።

አመዱን ፡ እንደ ፡ እህል ፡ ተመገብሁት ፡ ማለት ፡ ተዋርዷቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እንድም ፡ ግዳይ ፡ ብለው ፡ ይጥሏቸዋል ፡ ሲነሱ ፡ አመዱን ፡ በግንባራቸው ፡ በከንፈራቸው ፡ ይዘውት ፡ ይነሣሉና ፡ እንድም ፡ እሸር ፡ ባሸሩን ፡ ጓያውን ፡ ባቄላውን ፡ ይሰጧቸዋልና ፡

ወስቴየኒ ፡ ምስለ ፡ አንብዕየ ፡ ሰተይኩ ።

መጠጤንም ፡ ከዕንባ ፡ ጋራ ፡ ጠጣሁ ፡ ኢሳ ፡ ፴ ፡ ፳ ።

፲ ፡ እምገጸ ፡ መቅሠፍተ ፡ መዓትከ ።

ይህም ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ያገኘኝ ፡ ገጸ ፡ መዓትህ ፡ ከመገለጹ ፡ የተነሣ ፡ ነው ።

እስመ ፡ አንሣእከኒ ፡ ወነፃህከኒ ።

አንስተህ ፡ ጥለኸኛልና ፡ እንሥተው ፡ የጣሉት ፡ እንዲጎዳ ፡ ጎድተኸኛልና ፡ እንድም ፡ አክብረህ ፡ አዋርደኸኛልና ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ አድርገህ ፡ ቋሚ ፡ ለጓሚ ፡ አድርገኸኛልና ፡ ገብሮ ፡ ገዶ ፡ ዓመቶ ፡ ወለቶ ፡ ተብዬ ፡ እንድሰደብ ፡ አድርገኸኛልና ።

፲፩ ፡ ወመዋዕልየኒ ፡ ከመ ፡ ጽላሎት ፡ ኀለፈ ።

ዘመኔም ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ተፈጸመ ።

ወአንሂ ፡ ከመ ፡ ሣዕር ፡ የበስኩ ።

እኔም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ደረቅሁ ፡ ማለት ፡ ወዝ ፡ ልምላሜ ፡ እንዳይገኝበት ፡ አእምሮ ፡ ተለየኝ ።

፲፪ ፡ አንተሰ ፡ እግዚኦ ፡ ለዓለም ፡ ትነብር ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ለዘላለም ፡ ትኖራለኅ ።

ወዝክርከኒ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ።

ስም ፡ አጠራርህም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ይኖራል ፡ ሰቆ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ።

፲፫ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ወተሣሃላ ፡ ለጽዮን ።

አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሥተህ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ይቅር ፡ በላት ፡ ማለት ፡ አገሪቱ ፡ እንድትቀና፡ቤተ፡ መቅደስ ፡ እንድትሠራ ፡ አድርግ ።

እስመ ፡ ጊዜሃ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ትሠሃላ ።

ይቅር ፡ ትላት ፡ ዘንድ ፡ ጊዜዋ ፡ ደርሷልና ።

ወበጽሐ ፡ ዕድሜሃ ።

የይቅርታዋም ፡ ዘመን ፡ ደርሷልና ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ሠምሩ ፡ አግብርቲከ ፡ ዕበኒሃ ።

ባሮችህ ፡ ትሩፋን ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ድንጊያዋን ፡ ወድደዋልና ።



ወአክበርዎ ፡ ለመሬታ ።

መሬቷንም ፡ ወደዋልና ፡ ጨው ፡ ከብሮ ፡ ዋለ ፡ እንዲሉ ፡ እንድም ፡ የናፍቆት ፡ ድንጋያዋን ፡ ተንተርሰ ነው ፡ መሬቷን ፡ ልሰነው ፡ ስላሉ ፡ የባቢሎን ፡ ድንጋያዋ ፡ ሻፎ ፡ መሬቷ ፡ ቀይ ፡ ነው ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ግን ፡ ድንግዖዋ ፡ መዓዝን ፡ መሬቷ ፡ መረሬ ፡ ነውና ፡ እንድም ፡ (ዕበኒሃ)፡ ኢታምልክን፡ (መሬታ) ፡ ዘጠኙን ፡ ሕገጋት ፡ እንድም ፡ (ዕበኒሃ) ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላትን ፡ (መሬታ) ፡ ወነበቦ ፡ ወነበቦ ፡ ያለውንም ፡ ቃል ፡ ጠበቅን ፡ ብለዋልና ።

እንድም ፡ (እስመ ፡ ሠምሩ)፡ባሮችህ፡ እለ ፡ ንዕማን ፡ የወልደ ፡ አዴር ፡ ቢቶደድ ፡ ነው ፡ ከሰልፍ ፡ ላይ ፡ ሲዋጋ ፡ ተመትቶ ፡ በደም ፡ አማቂት ፡ አካሉ ፡ በለምፅ ፡ ነዶ ፡ ይኖር፡ ነበር ፡ ሚስቱ ፡ ሲወጣ ፡ ሲገባ ፡ አካሉን ፡ እያየች ፡ ስታዝን ፡ ትኖር ፡ ነበር ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ የምትሆን ፡ እንዷት ፡ ሴት ፡ ማርኮ ፡ ወስዶ ፡ ደንገጥር ፡ ትሁንሽ ፡ ብሎ ፡ ለሚስቱ ፡ ሰጥቷት ፡ ነበርና ፡ ምነው ፡ ታዝኛለሽ ፡ አለቻት ፡ ምነው ፡ አላዝን ፡ የባለቤቴ ፡ አካሉ ፡ በለምፅ ፡ ነዶ ፡ አለቻት ፡ መፍትው ፡ ይሑር፡ ኀበ ፡ ነቢየ ፡ እግዚአብሔር፡ ከኔ ፡ አገር ፡ ቢሄድ ፡ ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያድነው ፡ ነበር ፡ አለችው ፡ ቤት ፡ ከጌታው ፡ ቤት ፡ ውሎ ፡ ማታ ፡ ሲገባ ፡ ይህን ፡ ነገረችው ፡ እሱም ፡ ለጌታው ፡ ነገረው ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ በሁለት ፡ በቅሎ ፡ አስጭኖ ፡ አፈውሶ ፡ ለንዕማን ፡ ቍልኤየ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰደደ ፡ ርዕዩ፡ ዘከመ ፡ የኃሥሥ፡ ምክንያተ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ይላል ።

ፀብ ፡ የሻ ፡ ዳኛ ፡ አምጡ ፡ ይላል ፡ የዶሮ ፡ ሻኛ ፡ እንዲሉ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ልጣለው ፡ ሲል ፡ እያችሁን ፡ ቦኑ ፡ እነ ፡ እክል ፡ ቀቲለ ፡ ወአሕይዎ ፡ እኔ ፡ ማዳን ፡ መግደል፡ የሚቻለኝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ነኝ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ልጣላው ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እለ ፡ ካጠገቡ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሀገርህ ፡ እንዳለ ፡ ታውቅ ፡ የለምን ፡ ወደዚያ ፡ አትሰደውምን ፡ አሉት ፡ እንድም ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ (ኤልሣዕ) ፡ ከዚያው ፡ ነበርና ፡ እራሱን ፡ እርቆ ፡ እንዲህ ፡ ይለዋል ፡ እንድም ፡ ከዚያ ፡ ሳይኖር ፡ በፀጋ ፡ ዐውቆ ፡ የመጣ ፡ ወደኔ ፡ ነውና ፡ ወደኔ ፡ ላከው ፡ አለው፡ እሱም ፡ (ኤልሣዕም) ፡ እስራኤል ፡ ለምፅ ፡ ይጸየፋሉና ፡ በዚያው ፡ ዮርዳኖስ ፡ ሄደህ ፡ ተጠመቅ ፡ ብሎ ፡ ይልክበታል ፡ እኔ ፡ ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢሉ ፡ [illegible] ፡ አይቶ ፡ [illegible]

2014 04 17

ቃሉ ፡ ተናግሮ ፡ በእጁ ፡ ዳስሦ ፡ ያድ ነኛል ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ የወሀ ፡ የወሀ ፡ ምናለኝ ፡ ቀሐ ፡ እንዲሉ ፡ የ ወሀ ፡ የወሀማ ፡ ምንተ ፡ ይቤሉኒ ፡ ማያተ ፡ ብሔርየ ፡ ባብና ፡ ወፋርፋ ፡ ኢይሄይሱኑ ፡ ማያተ ፡ ብሔርየ ፡ እማያተ ፡ ብሔርሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ከዚህ ፡ ከቀዝቃዛ ፡ ከደጋ ፡ ወሀማ ፡ ሙቀት ፡ ያለው ፡ ያገሬ ፡ ወሀ ፡ አይ ሻልምን ፡ ብሎ ፡ ተቈጥቶ ፡ ተመለ ሰ ፡ ከኤልሣዕ ፡ ዘንድ ፡ ተልከው ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡ ግድ ፡ የለህም ፡ ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገ ረው ፡ ነገር ፡ አይቀርም ፡ ሂደህ ፡ ተጠመቅ ፡ ብለውት ፡ አንድም ፡ የሱው ፡ አሽከሮች ፡ ለኛም ፡ ለፀብ ፡ ይመችናል ፡ ሂደህ ፡ ተጠመቅ ፡ ብለ ውት ፡ ነው ፡ ወርዶ ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ ፡ ቢጠመቅ ፡ ከለምጹ ፡ ነጽቷል ። ከዚያ ፡ ተመ ልሶ ፡ ሂዶ ፡ ወርቁን ፡ ብሩን ፡ ከፊ ቱ ፡ አፍስሶለታል ፡ እሣየጦኑ ፡ ለ ፀጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀጋ ፡ እግዚ አብሔርን ፡ ለወርቅ ፡ እሸጠዋለ ሁን ፡ ብሎ ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ታል ፡ እንክያ ፡ ምን ፡ ላድርግልህ ፡ አለው ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እመን ፡ አለው ፡ ይህማ ፡ እንዳይ ሆን ፡ ጌታዬ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ሲሄድ ፡ እኔን ፡ አስከትሎ ፡ ነው ፡ ለጣዖት ፡ ሲሰግድ ፡ ቅሉ ፡ የኔን ፡ ትከሻ ፡ ይዞ ፡ ነው ፡ እንደምን ፡ አድርጎ ፡ ይሆንልኛል ፡ አለው ፡ ይህንማ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ዐውቃለሁ ፡ አለው ፡ እንዲህስ ፡ ባደርግ ፡ አለው፡ እንዴት ፡ አለው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አፈር ፡ ድንጊያ ፡ ጭኜ ፡ ሂጄ ፡ ከ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ አጠገብ ፡ መድብ ፡ አሠርቼ ፡ እሱ ፡ ለጣዖት ፡ ሲሰግድ ፡ እኔ ፡ ለመሬቱ ፡ ብሰግድስ ፡ አለው ፡ መልካም ፡ ነው ፡ አለው ፡ ወሐረ ፡ በኪዳኑ ፡ ምድር ፡ ይላል ፡ መሬቱ ን ፡ በሁለት ፡ በቅሎ ፡ አስጭኖ ፡ ሂዶ ፡ ጌታው ፡ ለጣዖት ፡ ሲሰግድ ፡ እሱ ፡ ለመሬቱ ፡ የሚሰግድ ፡ ሁ ኗል ፡ ይኸውም ፡ ሃይማኖት ፡ ሁ ኖት ፡ ተጠቅሞበታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ፪ ፡ ነገ ፡ ፭ ፡ ፩—፲፱ ።

፲፩ ፤ ወይፍርሁ ፡ አሕዛብ ፡ ስመከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ሠራዊቱ ፡ ያምላክነትህን ፡ ስም ፡ ይፍሩ ፡ ማለት ፡ ፈርተው ፡ ያምልኩ ።

ወነገሥት ፡ ንጉሥት ፡ ለስብሐቲከ ።

ነገሥታቱም ፡ ሁሉ ፡ ለጌትነ ትህ ፡ ይገዙ ፤ አንድም ፡ (ወይፍር ሁ ፡ አሕዛብ) ፡ ቂሮስ ፡ ዳርዮስ ፡ ስምህን ፡ ፈርተው ፡ ያመስግኑ ፡ (ወነገሥት ፡ ንጉሥት ፡ ዮሴፅ ፡ ዘሩ ባቤልም ፡ ለጌትነትህ ፡ ይገዛሉ ፡ ይገዙ ።

፲፮ ፤ እስመ ፡ የሐንፃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጽ ዮን ።

እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ እንድትሠራ ፡ ያደርጋልና ።



ወያስተርኢ ፡ በስብሐቲሁ ።

በጌትነቱም ፡ ይገለጿልና ።

፲፯ ፤ ወነጸረ ፡ ላዕለ ፡ ጸሎተ ፡ ነዳይ ።

ትሩፋ ፡ ያቀረበውን ፡ ልመናም ፡ ተቀብሏልና ፤ ወነጸረ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ላዕለ ፡ አቤል ፡ ወላዕለ ፡ መ ሥዋዕቱ ፡ እንዲል ።

ወኢተቈጥዐ ፡ ስእለቶሙ ። መዝ ፡ ፳፩ ፡ ፳፬ ።

የትሩፋንን ፡ ልመናቸውን ፡ ቸል ፡ አላለም ፡ አላነጠበምና ።

፲፰ ፤ ወተጽሕፈት ፡ ዛቲ ፡ ለካልእ ፡ ትው ልድ ።

ይህቺ ፡ ዕለተ ፡ ሚጠት ፡ ለሌላ ፡ ትውልድ ፡ ተሰጠች ፤ ማለት ፡ በእ ስራኤል ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ በኢ ኮንያን ፡ ተማርከዋል ፡ በሰላትያል ፡ ተገዝተዋል ፡ በዘሩባቤል ፡ ወጥተ ዋል ። በአሕዛብ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ በስልምናሶር ፡ ተማርከዋል ፡ በዮ ልማሮዴቅ ፡ ተገዝተዋል ፡ በብ ልጣሶር ፡ ወጥተዋልና ። አንድም ፡ በካልዕ ፡ ትውልድ ፡ በሌላ ፡ ትው ልድ ፡ ተደረገች ፡ ማለት ፡ በቂ ሮስ ፡ በዳርዮስ ፡ አንድም ፡ አበው ፡ አልቀው ፡ ውሉድ ፡ ወጥተዋልና ፡ ለካልዕ ፡ ትውልድ ፡ አለ ።

ሕዝብ ፡ ዘይትፈጠር ፡ ይሴብሖ ፡ ለእግዚአብ ሔር ።

ሁለተኛ ፡ የሚነጣ ፡ ሕዝብ ፡ ከዚ ዜው ፡ ደርሶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግነዋል ። መዝ ፡ ፳፩ ፡ ፳፩ ፡ ኢሳ ፶፫ ፡ ፳፩ ።

፲፱ ፤ እስመ ፡ ሐወጸ ፡ እምሰማይ ፡ መቅደሶ ።

እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ ሁኖ ፡ መመስገኛው ፡ የምትሆን ፡ ኢየሩሳ ሌምን ፡ በረድኤት ፡ ጎብኝቷልና ።

እግዚአብሔር ፡ ሐወጸ ፡ እምሰማይ ፡ ዲበ ፡ ም ድር ።

ዲበ ፡ ምድር ፡ ለማለት ፡ ደግሞታል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ ሁኖ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለከተ ።

፳ ፤ ከመ ፡ ይስማዕ ፡ ገዐሮሙ ፡ ለሙቁሓን ።

የትሩፋንን ፡ ልመና ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ያሕይዎሙ ፡ ለደቂቀ ፡ ቅቱላን ። ኢሳ ፶፩ ፡ ፲፬ ።

የሙታንን ፡ ልጆች ፡ ትሩፋንንም ፡ ከመከራው ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡

፳፩ ፤ ከመ ፡ ይንግሩ ፡ በጽዮን ፡ ስመ ፡ እግዚ አብሔር ። ወስብሐቲሁኒ ፡ በኢየሩሳሌም ።

ከመ ፡ ይንግሩ ፡ በጽዮን ፡ ወበ ኢየሩሳሌም ፡ ስመ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ወስብሐቲሁኒ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ (በጽዮን) ፡ በከተማ ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ ጌትነቱንም ፡ (በኢየሩ ሳሌም) ፡ በገጸር ፡ ይነግሩ ፡ ያስ ተምሩ ፡ ዘንድ ።

፳፪ ፤ ሶበ ፡ ተጋብኡ ፡ አሕዛብ ፡ ኅቡረ ።

ሠራዊቱ ፡ በሃይማኖት ፡ ባንድ ነት ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡

2014 04 17

ወነገሥትኒ፡ከመ፡ይትቀነዩ፡ለእግዚአብሔር። ነገሥታቱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ ቂሮስ ፡ ዳርዮስ ፡ በሃይማኖት ፡ አንድነት ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ (ወነገሥትኒ) ፡ ዮሴፍ፡ዘሩባቤልም፡ለእግዚአብሔር፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ።

፳፪ ፡ ወተሠጠዎ ፡ በፍኖተ ፡ ኀይሉ ። ኃይልን ፡ አድርጎ ፡ ባስማረካቸው ፡ ትዳና ፡ አወጣቸው ፤ እንድም ፡ በየ ትዳናው ፡ ኃይልን ፡ አድርጎ ፡ ማለት ፡ በተአምራት ፡ አወጣቸው።

ንግረኒ ፡ ውኅዶን ፡ ለመዋዕልየ ። በባቢሎን ፡ የምኖረውን ፡ የዘመ ኔን ፡ ልክ ፡ ንገረኝ ።

፳፫ ፡ ኢትስደኒ ፡ በመንፈቀ ፡ ዓመትየ ። ሰባ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ቢለው ፡ እን ኪያስ ፡ ይህ ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ሳይ ፈጸም ፡ በመከራው ፡ አታጥፋኝ ፤ እንድም ፡ ለሁሉ ፡ አድርጎ ፡ ተና ግሮታል ፡ ብለህ ፡ (ንገረኒ) ፡ በዚ ህ ፡ ዓለም ፡ የምኖረውን ፡ የዘመ ኔን ፡ ልክ ፡ ንገረኝ ፡ ሰባ ፡ ሰማ ንያም ፡ እንደሆነ ፡ ወእመ ፡ ፈጠሮ፡ ይእቲ ፡ አሚረ ፡ ይኤዝዞ ፡ እን ዲል ፤ ሲፈጥረው ፡ የዘመኑን ፡ ልክ ፡ አውቆ ፡ ነውና ፡ የሚፈጥ ረው ። (ኢትስደኒ) ፡ ይህ ፡ አንተ ፡ የሰጠኸኝ ፡ ዘመን ፡ ሳይፈጸም ፡ በእኩሌታው ፡ አታጥፋኝ ።

ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ዓመቲከ ። ዘመንህ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ አይፈ ጸምምና ።

፳፬ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ አቅደምከ ፡ ሣርር ታ ፡ ለምድር ። አቤቱ ፡ አንተ ፡ ምድርን ፡ አስቀ ድመህ ፡ ፈጠርህ ፡ (ሐተታ) ፡ አቅ ደምከ ፡ አለ ፡ ከማን ፡ ቢሉ ፡ ከሰ ማይ ፡ ምነው ፡ የሰማይና ፡ የም ድርማ ፡ ተፈጥሯቸው ፡ በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ በመ ታየት ፡ አቅደምከ ፡ አለ ፡ ዛሬ ፡ ቅሉ ፡ ሰማይ ፡ አይታይምና ። አን ድም ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ለምድር ፡ ሰጥተህ ፡ ከመታየቷ ፡ መፈጠሯን ፡ ብቻ ፡ አስቀደምህ ፡ ከዚህ ፡ እስከ፡ ብሩህ ፡ ሰማይ ፡ ወህ ፡ መልቶ ፡ ነ በርና ።

ወግብረ ፡ እደዊከ ፡ እማንቱ ፡ ሰማያት ። ሰማያትም ፡ የእጅህ ፡ የቃልህ ፡ ፍጥረት ፡ ናቸው ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፲ ።

፳፭ ፡ እማንቱስ ፡ ይትኀጐላ ፡ ወአንተሰ ፡ ትሄሉ ። ሰማይ ፡ ምድር ፡ ያልፋሉ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ አታልፍም ።

ወዙሉ ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ ይበሊ ። ሁሉ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያልቃል ፤ ዕድሜና ፡ ጠርቅ ፡ ሲበጣጠል ፡



ያልቃል ፡ እንዲሉ ፡ ለሁሉ ፡ ው ራጅ ፡ አለው ፡ ለልብስ ፡ ግን ፡ ውራጅ ፡ የለውምና ። ኢዮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፱ ፡ ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፮ ።

ወከመ ፡ ሞጣሕት ፡ ትዌልጦሙ ፡ ወይትዌ ለጡ ። እንደ ፡ ሌታ ፡ ቀን ፡ ግምጃ ፡ ትለ ዋውጣቸዋለህ ፡ ይለዋወጣሉ ፡ ማለት ፡ በሕፃንነት ፡ በእርጅና ፡ በሕይወት ፡ በሞት ፡ በሰብእ ፡ ትካት ፡ በሰብእ ፡ ሰዶም ፡ በሰ ብእ ፡ ገሞራ ፡ ትለዋውጣቸዋለህ ፡ ይለዋወጣሉ ።

እንድም ፡ (አንተ ፡ እግዚእ) ፡ ሥጋን ፡ ከነፍስ ፡ አስቀድመህ ፡ ፈጠርህ ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአር ያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ እንዲል ፡ (ሐተታ) ፡ ተፈጥሯቸው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ የነ ፍስ ፡ ተፈጥሮ ፡ እምነበ ፡ እልቦ ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ የተመቸ፡ ምንም ፡ ሥጋ ፡ የተገኘ ፡ (የተፈ ጠረ) ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ ቢሆን ፡ የሥጋ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆኑ ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ የተፈጠሩ ፡ እሑድ ፡ ነውና ፡ ግብር ፡ እምግ ብር ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ለነ ገር ፡ ከነገር ፡ አካል ፡ ይቀድማ ልና ፡ (ወግብረ ፡ እደዊከ) ፡ ነፍ ሳት ፡ የእጅህ ፡ የቃልህ ፡ ፍጥረ ት ፡ ናቸው ፡ (እማንቱስ) ፡ ነፍ ሳት ፡ ይጠፋሉ ፡ አባ ፡ ለትጹን ፡

እንዳስጠፍት ፡ ነፍስ ፡ በነፍስስ ፡ ጥፋት ፡ የለባትም ፡ ብሎ ፡ ከኃ ማርም ፡ ከክብርም ፡ አልደረሰ ችም ፡ ይህስ ፡ መቼ ፡ ይሆናል ፡ ከኃማር ፡ ከወጡ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መግባት ፡ ከክብርም ፡ ከወጡ ፡ ገሃነም ፡ መውረድ ፡ ነው ፡ ምስት ፡ ቦታ ፡ የለ ፡ ወእዘከረ ፡ መጽሐፍ ፡ አምላካዊ ፡ ፫ተ ፡ መ ካናተ ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ በኃጢ አት ፡ መለወጧን ፡ ሲያይ ፡ አን ድም ፡ መለያየት ፡ የጋራ ፡ ከሆነ ፡ ብሎ ፡ (ወአንተሰ ፡ ትሄሉ) ፡ አን ተ ፡ ግን ፡ አታልፍም ፡ (ወዙሉ) ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያልፋል ፡ ወከመ ፡ ሞጣሕት ፡ ትጠው ሞሙ ፡ ወይጠወሙ ፡ ይላል ፤ እንደ ፡ ሻግሌ ፡ ግምጃ ፡ መጋ ረጃ ፡ ትጠቀልላቸዋለህ ፡ ይጠቀ ለላሉ ፤ ያን ፡ እንዱን ፡ ከሁለት ፡ ሁለቱን ፡ ካራት ፡ አራቱን ፡ ከስ ምንት ፡ አጥፈው ፡ በማጥን ፡ ያና ፋታል ፡ እሱም ፡ ሰዓቱን ፡ በዕለት ፡ ዕለቱን ፡ በወር ፡ ወሩን ፡ ባመት ፡ ዓመቱን ፡ በሺህ ፡ ሺሁን ፡ በሁ ለት ፡ ሺህ ፡ ሁለቱን ፡ ሺህ ፡ ባራት፡ ሺህ ፡ አራቱን ፡ ሺህ ፡ በስምንት ፡ ሺህ ፡ አጥፎ ፡ በኅልፈት ፡ ማጥን ፡ ይከትተዋልና ። ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፮ ፡ ዕብ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።

፳፮ ፡ አንተሰ ፡ አንተ ፡ ከመ ፡ ዳግ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ። አንተ ፡ ግን ፡ መቼም ፡ መች ፡ አንተ ፡ ነህ ።

ወጎሥቲከኒ ፡ ዘኢየሐልቅ ፡
ዘመንህም ፡ አይፈጸምም ።
፳፰ ፡ ደቂቀ ፡ አግብርቲከ ፡ ይነብርዋ ።
ተንሥእ ፡ እግዚእ ፡ ወተሠሃላ ፡
ለጸዮን ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።
የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡
ልጆች ፡ ወርስዋት ፡ ይኖራሉ ።
ወዘርዖሙ ፡ ለዓለም ፡ ይፀንዕ ።
ልጆቻቸውም ፡ ለዘላለም ፡ ጸን
ተው ፡ ወርሰዋት ፡ ይኖራሉ ፤ ይኸ
ውም ፡ ሊታወቅ ፡ ከሚጠት ፡
በኋላ ፡ ደቂቀ ፡ እስሙናይን ፡ ወር
ሰዋት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ኢሳ ፡ ፶፱ ፡
፱ ፡ ስብ ፡ ፩ ፡ ፲-፲፪ ፡ ራዕ ፡ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ።

## መዝሙር ፡ ፳፪ ።

፩ ፡ ትባርኪ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ቍ ፡ ፳፪ ፡ መዝ ፡ ፻፫ ፡ ፩ ፡ ፴፭ ።
ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ ሰው
ነቱ ፡ እንድም ፡ ልቡናዬ ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ ታመሰግነዋለች ።
ወኵሉ ፡ አዕፅምትየ ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ።
ስሞ ፡ ቅዱስም ፡ ይላል ፡ ሕዋ
ሳቱ ፡ ሁሉ ፡ ዕኑዕ ፡ ከሀሊ ፡ የሚ
ሆን ፡ ስሙን ፡ ያመሰግናሉ ፤ እን
ድም ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ፡ ብለህ ፡
ዕኑዕ ፡ ከሀሊ ፡ ለሚሆን ፡ ስሙ ፡
ምስጋና ፡ ያቀርባሉ ።
፪ ፡ ትባርኪ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ደገመው ።
ወኢትርሳዕ ፡ ኵሉ ፡ ስብሐቲሁ ።
ትሩፍ ፡ ትባርኪ ፡ ነፍስየ ፡ አልኸ ፡
አበጀሀ ፡ ጌትነቱን ፡ ሁሉ ፡ አትር
ሣ ፡ አትዘንጋ ።
፫ ፡ ዘይሠሪ ፡ ለከ ፡ ኵሉ ፡ ኃጢአተከ ።
ኃጢአትህን ፡ ሁሉ ፡ የሚያስተሠ
ርይልህ ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ ኃጢ
አትህን ፡ ሁሉ ፡ የሚያስተሠርይ
ልህ ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አት
ርሣ ።
ዘይፌውሰከ ፡ እምኵሉ ፡ ደዌከ ።
ከደዌህ ፡ ሁሉ ፡ የሚያድንህ ፡ ጌት
ነቱ ፡ ነው ፡ የሚያድንህ ፡ ጌት
ነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ።
፬ ፡ ዘያድኅና ፡ እሙስና ፡ ለሕይወትከ ።
ሰውነትህን ፡ ከጥፋት ፡ የሚያድ
ናት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ የሚያድ
ናት ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አት
ርሣ ።
ዘይኬልለከ ፡ በሣህሉ ፡ ወበምሕረቱ ።
በይቅርታው ፡ በቸርነቱ ፡ ከመከ
ራው ፡ ሁሉ ፡ የሚሠውርህ ፡ ጌት
ነቱ ፡ ነው ፤ የሚሠውርህ ፡ ጌት
ነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ።
፭ ፡ ዘያፀግብ ፡ እምበረከቱ ፡ ለፍትወትከ ።
ሰውነትህን ፡ ከበረከቱ ፡ ሰጥቶ ፡



ዶስ ፡ የሚያስኛት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡
ዶስ ፡ የሚያስኛት ፡ ጌትነቱን ፡ አት
ዘንጋ ፡ አትርሣ ። ፴፭ ፡ ፩ ።
ዘይሔድሳ ፡ ከመ ፡ ንስር ፡ ለውርዙትከ ።
ሰውነትህን ፡ እንደ ፡ ዖፌ ፡ ፌን
ክስ ፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱ ፡
ነው ፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱን ፡
አትዘንጋ ፡ አትርሣ ። (ታሪክ) ፡
ዖፌ ፡ ፌንክስ ፡ ብልየት ፡ ያገኘው ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ከቈላ ፡ ወርዶ ፡ ከሁ
ለት ፡ ከሶስት ፡ ላይ ፡ ዕንጨት ፡
ይሰበስባል ፡ እንድም ፡ ባለወ
ጎች ፡ ይሰበስቡለታል ፡ ተራራ ፡
ተራራ ፡ ያህል ፡ ሲሆን ፡ ከውቅ
ያኖስ ፡ አብዮ ፡ የሚባል ፡ ድኝ
ነት ፡ ያለው ፡ ጭቃ ፡ አለ ፡ ከዚያ ፡
ሂዶ ፡ ተቀብቶ ፡ መጥቶ ፡ ከተቆ
ለለው ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡
ሁለት ፡ ክንፉን ፡ ያማታዋል ፡
ወይወጽእ ፡ እሳት ፡ እማዕከለ ፡
ክንፊሁ ፡ ይላል ፡ እሳት ፡ ከክ
ንፉ ፡ ወጥቶ ፡ ያቃጥለዋል ፡ በዚያ ፡
አገር ፡ ዝናም ፡ አይዘንምም ፡ ባም
ስት ፡ መቶ ፡ ባምስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፡ ለተሐድሶተ ፡ ንስር ፡
ካፈያ ፡ ያካፋል ፡ በነጋው ፡ ትል ፡
ያህል ፡ ሁኖ ፡ ተፈጥሮ ፡ ያድራል ፡
በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ዖፌ ፡ ድንቢ
ጥ ፡ ያህላል ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡
ቡላል ፡ ያህል ፡ ሆኖ ፡ ያድራል ፡
ባራተኛው ፡ ቀን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡
አድርሶ ፡ ይሄዳል ። እንድም ፡ ሰው
ነትህን ፡ እንደ ፡ እርኩም ፡ የሚያ
ድሳት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ እርኩም ፡
አርባ ፡ ቀን ፡ ከመብል ፡ ተከል
ክሎ ፡ አፉን ፡ ከደንግያ ፡ ላይ ፡
ያጠራጠሰው ፡ እንደሆነ ፡ እንደ ፡
ዋንጫ ፡ ውልቅ ፡ ብሎ ፡ ይወድ
ቅለታል ፡ ይታደሳል ። እንድም ፡
እንደ ፡ እባብ ፡ ሰውነትህን ፡ የሚ
ያድሳት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ። (ታሪክ) ፡
እባብ ፡ ብልየት ፡ ያገኘው ፡ እንደ
ሆነ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ከምግብ ፡ ተከ
ልክሎ ፡ በሥቁረተ ፡ ዕፅም ፡ በሥ
ቁረተ ፡ ዕብንም ፡ ቢሉ ፡ ሲያልፍ፡
ተገፍፎ፡ይወድቅለታል፡ ይታደሳል፡
ነገር ፡ ግን ፡ ንስርን፡ እባብ፡ የሚል፡
ንባብ ፡ አልተገኘም ፡ እንድም ፡
ሰውነትህን ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጉ
ባኤ ፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው፡
የሚያድሳት ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘ
ንጋ ፡ አትርሣ ።
፮ ፡ ገባሬ ፡ ሣህል ፡ እግዚአብሔር ።
ይቅርታን ፡ የሚያደርግ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡
ይቅርታን ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ።
ወይፈትሕ ፡ ለኵሉ ፡ ግፉዓን ፡ ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፬ ።
ለተበደሉ ፡ ሁሉ ፡ ይፈርድላቸ
ዋል ፡ እንድም ፡ ለተበደሉ ፡ ለት
ሩፋን፡ይፈርድላቸዋል፡ ዘፀ፡ ፳፬ ፡ ፩ ፡ ፫ ።
፯ ፡ አርአየ ፡ ፍናዊሁ ፡ ለሙሴ ።
ለሙሴ ፡ ኢታምልክን ፡ ገለጸለት ።

2014 04 17

ወዓመቲከኒ ፡ ዘኢያሐልቅ ፡

ዘመንህም ፡ አይፈጸምም ።

፳፰፤ ደቂቀ ፡ አግብርቲከ ፡ ይነብርዋ ።

ተንሥእ ፡ እግዚእ ፡ ወተሠሃላ ፡ ለጽዮን ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።
የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ወርሰዋት ፡ ይኖራሉ ።

ወዘርዖሙኒ ፡ ለዓለም ፡ ይሴሰዩ ።

ልጆቻቸውም ፡ ለዘላለም ፡ ጸን ተው ፡ ወርሰዋት ፡ ይኖራሉ ፤ ይኸ ውም ፡ ሊታወቅ ፡ ከሚጠት ፡ ዘኋላ ፡ ደቂቀ ፡ እስሙናይን ፡ ወር ሰዋት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ኢሳ ፡ ፵፱ ፡ ፳ ፡ ስብ ፡ ፩ ፡ ፲-፲፱ ፡ ራዕ ፡ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ።

## መዝሙር ፡ ፺፯ ።

፩፤ ትባርኮ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ። ቍ ፡ ፳፱ ፡ መዝ ፡ ፻፫ ፡ ፩ ፡ ፴፭ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ ሰው ነቱ ፡ እንድም ፡ ልቡናዬ ፡ እግዚ አብሔርን ፡ ታመሰግነዋለች ።

ወኵሉ ፡ አዕፅምትየ ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ።

ስሞ ፡ ቅዱስም ፡ ይላል ፡ ሕዋ ሳቴ ፡ ሁሉ ፡ ፅኑዕ ፡ ከሀሊ ፡ የሚ ሆን ፡ ስሙን ፡ ያመሰግናሉ ፤ እን ድም ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ፡ ብለህ ፡ ፅኑዕ ፡ ከሀሊ ፡ ለሚሆን ፡ ስሙ ፡ ምስጋና ፡ ያቀርባሉ ።

፪፤ ትባርኮ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ደገመው ።

ወኢትርሣዕ ፡ ኵሉ ፡ ስብሐቲሁ ።

ትሩፍ ፡ ትባርኮ ፡ ነፍስየ ፡ አልኸ ፡ አበጀህ ፡ ጌትነቱን ፡ ሁሉ ፡ አትር ሣ ፡ አትዘንጋ ።

፫፤ ዘይሠሪ ፡ ለከ ፡ ኵሉ ፡ ኃጢአተከ ።

ኃጢአትህን ፡ ሁሉ ፡ የሚያስተሠ ርይልህ ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ ኃጢ አትህን ፡ ሁሉ ፡ የሚያስተሠርይ ልህ ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አት ርሣ ።

ዘይፌውስከ ፡ እምኵሉ ፡ ደዌከ ።

ከደዌህ ፡ ሁሉ ፡ የሚያድንህ ፡ ጌት ነቱ ፡ ነው ፡ የሚያድንህ ፡ ጌት ነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ።

፬፤ ዘያድኅና ፡ እሙስና ፡ ለሕይወትከ ።

ሰውነትህን ፡ ከጥፋት ፡ የሚያድ ናት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ የሚያድ ናት ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አት ርሣ ።

ዘይኬልለከ ፡ በሣህሉ ፡ ወበምሕረቱ ።

በይቅርታው ፡ በቸርነቱ ፡ ከመከ ራው ፡ ሁሉ ፡ የሚሠውርህ ፡ ጌት ነቱ ፡ ነው ፤ የሚሠውርህ ፡ ጌት ነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ።

፭፤ ዘያጸግባ ፡ እምበረከቱ ፡ ለፍትወትከ ።

ሰውነትህን ፡ ከበረከቱ ፡ ሰጥቶ ፡



ደስ ፡ የሚያሰኛት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛት ፡ ጌትነቱን ፡ አት ዘንጋ ፡ አትርሣ ። ፴፭ ፡ ፩ ።

ዘያሔድሳ ፡ ከመ ፡ ንስር ፡ ለውርዙትከ ።

ሰውነትህን ፡ እንደ ፡ ዖፈ ፡ ፊን ክስ ፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘንጋ ፡ አትርሣ ። (ታሪክ) ፡ ዖፈ ፡ ፊንክስ ፡ ብልየት ፡ ያገኘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከቈላ ፡ ወርዶ ፡ ከሁ ለት ፡ ከሶስት ፡ ላይ ፡ ዕንጨት ፡ ይሰበስባል ፡ እንድም ፡ ባለወ ጎች ፡ ይሰበስቡለታል ፡ ተራራ ፡ ተራራ ፡ ያህል ፡ ሲሆን ፡ ከውቅ ያኖስ ፡ አብዮ ፡ የሚባል ፡ ድኝ ነት ፡ ያለው ፡ ጭቃ ፡ አለ ፡ ከዚያ ፡ ሂዶ ፡ ተቀብቶ ፡ መጥቶ ፡ ከተቆ ለለው ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ሁለት ፡ ክንፉን ፡ ያማታዋል ፡ ወይወጽእ ፡ እሳት ፡ እማዕከለ ፡ ክነፊሁ ፡ ይላል ፡ እሳት ፡ ከክ ንፉ ፡ ወጥቶ ፡ ያቃጥለዋል ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ዝናም ፡ አይዘንምም ፡ ባም ስት ፡ መቶ ፡ ባምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ለተሐድሶተ ፡ ንስር ፡ ካፊያ ፡ ያካፋል ፡ በነጋው ፡ ትል ፡ ያህል ፡ ሁኖ ፡ ተፈጥሮ ፡ ያድራል ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ዖፈ ፡ ድንቢ ጥ ፡ ያህላል ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ቡላል ፡ ያህል ፡ ሆኖ ፡ ያድራል ፡ ባራተኛው ፡ ቀን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ አድርሶ ፡ ይሄዳል ። እንድም ፡ ሰው ነትህን ፡ እንደ ፡ እርኩም ፡ የሚያ ድሳት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ፡ እርኩም ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ከመብል ፡ ተከል ክሎ ፡ አፉን ፡ ከደንግያ ፡ ላይ ፡ ያጠራጠሰው ፡ እንደሆነ ፡ እንደ ፡ ዋንጫ ፡ ውልቅ ፡ ብሎ ፡ ይወድ ቅለታል ፡ ይታደሳል ። እንድም ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ሰውነትህን ፡ የሚ ያድሳት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው ። (ታሪክ) ፡ እባብ ፡ ብልየት ፡ ያገኘው ፡ እንደ ሆነ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ከምግብ ፡ ተከ ልክሎ ፡ በሥቁረተ ፡ ዕፅም ፡ በሥ ቁረተ ፡ ዕብንም ፡ ቢሉ ፡ ሲያልፍ፡ ተገፍፎ፡ይወድቅለታል፡ ይታደሳል፡ ነገር ፡ ግን ፡ ንስርን፡ እባብ፡ የሚል፡ ንባብ ፡ አልተገኘም ፡ እንድም ፡ ሰውነትህን ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጉ ባኤ ፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱ ፡ ነው፡ የሚያድሳት ፡ ጌትነቱን ፡ አትዘ ንጋ ፡ አትርሣ ።

፮፤ ገባሬ ፡ ሣህል ፡ እግዚአብሔር ።

ይቅርታን ፡ የሚያደርግ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅርታን ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ።

ወይፈትሕ ፡ ለኵሉ ፡ ግፉዓን ፡ ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፬ ።

ለተበደሉ ፡ ሁሉ ፡ ይፈርድላቸ ዋል ፡ እንድም ፡ ለተበደሉ ፡ ለት ሩፋን፡ይፈርድላቸዋል፡ ዘፀ ፳፱ ፡ ፩ ፡ ፫ ።

፯፤ አርአየ ፡ ፍናዊሁ ፡ ለሙሴ ።

ለሙሴ ፡ ኢታምልክን ፡ ገለጸለት ።

2014 04 17

ወለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ሥምረቶ ።

ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ዘጠኙ
ን ፡ ሕጊጋት ፡ የገለጸላቸው ፡ እሱ ፡
ነው ፡ እድሎ ፡ መስጠት ፡ አይ
ደለም ፡ ሁሉም ፡ በሁሉ ፡ እሱ ፡
በእግዚእን ፡ አቡነ እንዳለ ፡

፰ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ኢዮ ፡ ፩ ፡ ፰፭ ፡ ፰፪ ።

እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነው ።
ይቅር ፡ ባይም ፡ ነው ፡ መዝ፡፻፵፬፡፰።
ርኁቀ ፡ መዓት ፡ ወብዙኃ ፡ ምሕረት ፡ ወጻ
ድቅ ። ዘፀ ፡ ፴፬ ፡ ፯ ፡ ፮ ።

መዓቱ ፡ የራቀ ፡ ቸርነቱ ፡ የቀረበ ፡
ነው ፡ እንድም ፡ መዓቱ ፡ ያነሰ ፡
ቸርነቱ ፡ የበዛ ፡ ነው ፡ (ጻድቅ) ፡
የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ኢዮ ፡ ፱ ፡
፲፫ ፡ መዝ ፡ ፲፫ ፡ ፭ ፡ ፲፭ ። ያዕ ፡ ፭ ፡ ፲፭ ፡ ፱ ።

፱ ፡ ኢይቀሥፍ ፡ ወትረ ፡ ወኢይትመዓዕ ፡
ዘልፈ ።

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ሰው ፡ በበ
ደለው ፡ ቍጥር ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡
ፈርጄ ፡ ላጥፋ ፡ አይልም ። ኢሳ ፡ ፶፯ ፡
፲፯ ።

፲ ፡ አኮ ፡ በከመ ፡ ኃጢአትነ ፡ ዘገብረ ፡ ለነ ።

ብነ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በኃጢአታችን ፡
ልክ ፡ መከራ ፡ ያመጣብን ፡ አይ
ደለም ።

ወኢፈደየነ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ።

በታላቁ ፡ ኃጢአታችንም ፡ ልክ ፡
ፍዳ ፡ ያመጣብን ፡ አይደለም ።

፲፩ ፡ ወበከመ ፡ ልዑል ፡ ሰማይ ፡ እምድር ።

ከምድር ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ሰማይ ፡
ፀንቶ ፡ እንዲኖር ።

አፅንዐ ፡ ምሕረቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡
እለ ፡ ይፈርህዎ ።

እግዚአብሔር ፡ ለሚፈሩት ፡ ለሚ
ያመልኩት ፡ ቸርነቱን ፡ አብዝቶ ፡
አደረገላቸው ። ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፱ ።

፲፪ ፡ ወበከመ ፡ ይርኅቅ ፡ ሠርቅ ፡ እምዓ
ረብ ።

ከምዕራብ ፡ ምሥራቅ ፡ እንዲርቅ ፡
አርኀቀ ፡ እምኔነ ፡ ኃጢአተነ ።

ኃጢአታችንን ፡ ከኛ ፡ አራቀልን ።

፲፫ ፡ ወበከመ ፡ ይምሕር ፡ አብ ፡ ውሉዶ ።

አባት ፡ ለልጆቹ ፡ እንዲያዝን ፡
እንዲራራ ።

ከማሁ ፡ ይምሕሮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእለ ፡
ይፈርህዎ ።

እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ለሚፈሩት ፡ ለሚያመል
ኩት ፡ ይራራላቸዋል ። ሚል ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።
ሉቃ ፡ ፲፭ ፡ ፳ ። ያዕ ፡ ፱ ፡ ፳ ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ የአምር ፡ ፍጥረተነ ።

እሱ ፡ ባሕርያችን ፡ ደካማ ፡ እንደ
ሆነ ፡ ያውቃልና ። ተዘከር ፡ ማ
ንሻ ፤ እንድም ፡ ባሕርያችን ፡ ደ
ካማ ፡ እንደሆነ ፡ ታውቃለህና ፡

ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ከመ ፡ መሬት ፡ ንሕነ ።

አቤቱ ፡ እኛ ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡
እንደሆን ፡ አስብ ።



፲፭ ፡ ሰብእሰ ፡ ከመ ፡ ሣዕር ፡ መዋዕሊሁ ።

መዋዕሊሁ ፡ ለሰብእ ፡ ነው ፡ ሰው
ስ ፡ ዘመኑ ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ነው ፤
ያ ፡ ፈጥኖ ፡ ደርቆ ፡ እንዲጠፋ ፡
ፈጥኖ ፡ ይጠፋል ።

ወከመ ፡ ጽጌ ፡ ገዳም ፡ ከማሁ ፡ ይፈሪ ።

ይትነገፍ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንደ ፡
በረኃ ፡ አበባ ፡ ይረግፋል ፡ ማ
ለት ፡ ያልፋል ፡ ለምልሞ ፡ አብቦ ፡
አፍርቶ ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲጠፋ ፡ እን
ደዝያ ፡ ነው ፡ እንድም ፡ እንደ ፡ ዕፅ ፡
ከንቱ ፡ ነው ፡ ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፮ ፡ ፰ ።

፲፮ ፡ እስመ ፡ መንፈስ ፡ ይወፅዕ ፡ እምኔሁ
ወኢይሄሉ ፡ እንከ ።

ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ ይለያልና ፡ ከተ
የለም ፡ በኋላ ፡ አይመለስምና ።

ወኢየአምር ፡ እንከ ፡ መካኖ ።

ቦታውንም ፡ አያውቀውም ፡ ማ
ለት ፡ ዕትብቱ ፡ የተቆረጠበትን ፡
መካን ፡ ድማሁን ፡ መካን ፡ መን
ግሥቱ ፡ ሰማይን ፡ መካን ፡ ገሃን
ምን ፡ አያውቅምና ። ኢዮ ፡ ፲፬ ፡ ፲ ።

፲፯ ፡ ሣህሉሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምዓለ
ም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።

የእግዚአብሔርስ ፡ ይቅርታው ፡
ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ፡
ምጽአት ፡ ድረስ ፡ ሲደረግ ፡ ይኖ
ራል ።

ላዕለ ፡ እለ ፡ ይፈርህዎ ።

ይኸውም ፡ ለማናቸውም ፡ አይደ
ለም ፡ ለሚፈሩት ፡ ለሚያመልኩ
በት ፡ ነው ።

ወጽድቁኒ ፡ ላዕለ ፡ ትውልደ ፡ ትውልድ ።

ቸርነቱም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ።
ዘፀ ፡ ፴፬ ፡ ፯ ፡ ፯ ፡ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፶ ።

፲፰ ፡ ለእለ ፡ የዐቅቡ ፡ ሕጎ ።

መጽሐፍ ፡ ጭብጡን ፡ አይለቅ
ቅም ፡ ያውም ፡ ሕጉን ፡ ለሚጠ
ብቁ ፡ ነው ።

ወይዜከሩ ፡ ትእዛዞ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ።

አስቦ ፡ መቅረት ፡ አለና ፡ ከመ ፡
ይግበሩ ፡ አለ ፡ ይሠሩት ፡ ዘንድ ፡
ሕጉን፡ለሚያስቡ፡ነው። ሲራ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ።

፲፱ ፡ እግዚአብሔር፡አስተዳለወ፡መንበሮ፡
በሰማያት ።

እግዚአብሔር ፡ በሰማይ ፡ ዙፋ
ኑን ፡ አዘጋጀ ፤ በግሥ ፡ ተናገረው ፡
ንጉሥ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ እን
ዲፈርድ ፡ ይፈርዳል ፡ ሲል ፡
ነው ።

ወኵሉ ፡ ይኬንን ፡ በመንግሥቱ ።

እንደ ፡ ጌትነቱ ፡ ሁሉን ፡ ይገዛል ፡
በሁሉ ፡ ይፈርዳል ።

፳ ፡ ባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵልክሙ ፡
መላእክቲሁ ።

የሰው ፡ አለቆች ፡ መላችሁ ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ አመስግኑት ።

ፅኑዓን ፡ ወኃያላን ፡ እለ ፡ ትገብሩ ፡ ቃሎ ።

ሕጉን ፡ የምትጠብቁ ፡ ፅኑ ፡ ኃያላ

2014 04 17

ንም ፡ የምትሆኑ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ አመስግኑት ።

ወእለ ፡ ትሰምዑ ፡ ቃለ ፡ ነገሩ ። ኢሳ ፡ ፳፮ ፡ ፭ ።

ከምስዓል ፡ ከአዕናቍ ፡ የነገሩን ፡ ምሥጢር ፡ የምታውቁ ።

፳፩ ፤ ይባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵሉ ፡ ኃይሉ ።

ይኸውም ፡ እላንት ፡ ብቻ ፡ አይደላችሁም ፡ ከሀሊነቱን ፡ የሚገልጽባቸው ፡ ሠራዊተ ፡ መላእክትም ፡ ያመስግኑታል ።

ላዕኩ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ ፈቃዶ ።

ላዕካኒሁ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ሕጉን ፡ አምልኮቱን ፡ የሚጠብቁ ፡ ሊቃነ ፡ መላእክትም ፡ ያመስግኑታል ።

፳፪ ፤ ይባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵሉ ፡ ተግባሩ ።

ነማግለትና ፡ ፍጥረቶቹ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግኑታል ።

ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርት ፡ መለኮቱ ።

በሐውርተ ፡ መለኮቱ ፡ ያለ ፡ እንደ ሆነ ፡ ጌትነቱ ፡ መልቶበት ፡ ባለ ፡ ሀገር ፡ ያሉ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፤ በሐውርት ፡ መለኮቱ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ጌትነቱ ፡ ባሬቱ ፡ መዓዝን ፡ ምሉዕ ፡ ነው ።

ትባርኮ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የኔም ፡ ልቡናዬ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታመስግነዋለች ። ባንዳንድ ፡ መሥመር ፡ እያገባ ፡ ተናግሮት ፡ ነበር ፡ የኋላ ፡ መምህራን ፡ ይበዛል ፡ ይቻካል ፡ ብለው ፡ በመጀመሪያና ፡ በመጨረሻ ፡ አድርገውታል ። ቍ፩ ፡ ፪መዝ ፡ ፻፫ ፡ ፩ ፡ ፴፭ ።

## መዝሙር ፡ ፻፫ ።

፩ ፤ ትባርኮ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ። ቍ፡ ፴፭ ፡ መዝ ፡ ፻፭ ፡ ፩ ፡ ፪—፳፪ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ የሥነ ፡ ፍጥረትም ፡ ነገር ፡ አለበት ፤ ሰውነቴ ፡ እንድም ፡ ልቡናዬ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታመሰግነዋለች ።

እግዚአ ፡ አምላኪየ ፡ ጥቀ ፡ ዐበይከ ፡ ፈድፋደ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ ፈጽመህ ፡ ከበርህ ።

አሚነ ፡ ወዕበየ ፡ ስብሐት ፡ ለበስከ ።

ሃይማኖትን ፡ ምግባርን ፡ ወደድህ ፡ እንድም ፡ (አሚነ) ፡ መታመንን ፡ (ወዕበየ ፡ ስብሐት) ፡ ዓቢየ ፡ ስብሐት ፡ መባልን ፡ ገንዘብ ፡ አደረግህ ፤ (ወደድህ) ።

፪ ፤ ወለበስከ ፡ ብርሃነ ፡ ከመ ፡ ልብስ ።

ብርሃንን ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ ተጐናጸፍኸ ፡ ማለት ፡ የባሕርይ ፡ ክብርን ፡ ገንዘብ ፡ አደረግህ ።



ወረበብኮ ፡ ለሰማይ ፡ ከመ ፡ ሠቅ ፤ ኤር ፡ ፵ ፡ ፲ ፡ ኢሳ ፡ ፶ ፡ ፫ ።

ሰማይን ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ድንኳን ፡ እንድም ፡ እንደ ፡ ገበታ ፡ የዘረጋኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ኤር ፡ ፲ ፡ ፲፪ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩ ።

፫ ፤ ዘይጠፍር ፡ በማይ ፡ ጽርሖ ።

ዘጠፈረ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ወሀን ፡ አዳራሹን ፡ ያደረገ ፡ አንተ ፡ ነህ ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፮ ፡ ፰ ።

ወረሰየ ፡ ደመና ፡ መከየዶ ።

መመላለሻውን ፡ ደመናን ፡ ያደረገ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ማለት ፡ ምልዓቱን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ዘሐውር ፡ በክንፈ ፡ ነፋስ ።

በነፋስ ፡ ክንፍ ፡ የሚሄድ ፡ አለ ፡ ፍጥነቱን ፡ ሲያይ ። እንድም ፡ የቅጽል ፡ ቅጽል ፡ አድርገህ ፡ በነፋስ ፡ ክንፍ ፡ የሚሄድ ፡ ደመናን ፡ መሄጃውን ፡ ያደረገ ፡ ወሀን ፡ አዳራሹን ፡ ያደረገ ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፬ ፤ ዘይሬስዮሙ ፡ ለመላእክቲሁ ፡ መንፈሰ ።

መላእክትን ፡ በርቀት ፡ የፈጠራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወለእለ ፡ ይትለአክዎ ፡ ነደ ፡ እሳት ።

ዘይሬስዮሙ ፡ ለመላእክቲሁ ፡ እለ ፡ ይትለአክዎ ፡ መንፈሰ ፡ ወነደ ፡ እሳት ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ የሚያገለግሉት ፡ መላእክትን ፡ ከእሳት ፡ ከነፋስ ፡ የፈጠራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ሐተታ) ፡ የመላእክት ፡ ተፈጥሯቸው ፡ ከእሳት ፡ ከነፋስ ፡ ነውና ፡ ይህስ ፡ አይደለም ፡ ሰበሰ ፡ ተፈጥሩ ፡ እምነፋስ ፡ ወእሳት ፡ እሞቱ ፡ ወእማስኑ ፡ ከማነ ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ ተፈጥሯቸው ፡ እምኀበ ፡ አልቦ ፡ ነው ፡ ተፈጥሮቶሙስ ፡ ለመላእክት ፡ እምብርሃን ፡ እምላካዊ ፡ እንዲል ።

ግብራቸውን ፡ ሲያይ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እሳት ፡ ነፋስ ፡ ኃያላን ፡ ረቂቃን ፡ ፈጣኖች ፡ ፈጻምያን ፡ ፈቃድ ፡ ናቸው ፡ መላእክትም ፡ ኃያላን ፡ ረቂቃን ፡ ናቸውና ፡ ለተልዕኮ ፡ ይፋጠናሉና ፡ የፈጣሪያቸውን ፡ ፈቃድ ፡ ይፈጽማሉና ።

፭ ፤ ሣረራ ፡ ለምድር ፡ ወአፅንዓ ።

ምድርን ፡ አፅንቶ ፡ ፈጠራት ።

ከመ ፡ ኢታንቀልቅል ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለሙ ፡ እንዳትናወፅ ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ፲ ።

፮ ፤ ወቀላይኒ ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ አፅፋ ።

ወሀ ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ መጐናጸፍያዋ ፡ ነው ፡ እንድም ፡ ቀላዩኒ ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ አፅፋ ፡ ይላል ። ወሀን ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ አጐናፀፋት ፡ ወማይ ፡ የዓውዳ ፡ ለምድር ፡ እምጉድሉ ፡ ገጸ ፡ ቲሃ ፡ ከመ ፡ ብያዳተ ፡ አንቀቅሆ ፡ የዓውድ ፡ እልመሂሃ ፡ እንዲል ።

ውስተ ፡ አድባር ፡ ይቀውሙ ፡ ማያት ።

ውሆች ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ፀንተው ፡ ይኖራሉ ፡ ማለት ፡ የሥነ ፡ ፍጥረቱን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ እስከ ፡ ብሩህ ፡ ሰማይ ፡ ድረስ ፡ ወሀ ፡ መልቶ ፡ ነበርና ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

፯ ፡ እምተግሣፅከ ፡ ይጐዩ ።

ለይትጋባዕ ፡ ከማለትህ ፡ የተነሣ ፡ ይሸሻሉ ፡ ማለት ፡ ይከፈላሉ ።

ወእምድምፀ ፡ ነጐድጓድከ ፡ ይደነግፁ ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፱ ።

እምተግሣፅከ ፡ ወእምድምፀ ፡ ነጐድጓድከ ፡ ይጐዩ ፡ ወይደነግጹ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ኪቃልህ ፡ መሰማት ፡ የተነሣ ፡ ይደነግጻሉ ።

፰ ፡ የዓርጉ ፡ አድባረ ፡ ወይወርዱ ፡ ገዳመ ።

ወደ ፡ ተራራ ፡ ይወጣሉ ፡ ወደ ፡ በረኃ ፡ ይወርዳሉ ፡ ይጐዩ ፡ ወይደነግጹ ፡ ያለውን ፡ ደገመው ፤ ውስተ ፡ ብሔር ፡ ኀበ ፡ ሣረርኮሙ ፡ ወሠራዕኮሙ ፡ ወደ ፡ ሠራህላቸው ፡ ወደ ፡ ወሰንህላቸው ፡ ቦታ ። ኢሳ ፡ ፵፱ ፡ ፲፰ ።

፱ ፡ ወሰኖሙ ፡ እምኀበ ፡ ኢየኀልፉ ።

ወሰናቸውም ፡ ከማይተላለፉበት ፡ ነው ፤ እንድም ፡ (አጥብቀህ ፡ አንቀጽ ፡ አድርገህ) ፡ ከማይተላለፍበት ፡ ወሰናቸው ፡ ብለህ ፡ ዕሠር ። ኢዮ ፡ ፲፬ ፡ ፭ ።

ከመ ፡ ኢይትመየጡ ፡ ወኢይክድንዋ ፡ ለምድር ።

ተመልሰው ፡ ይህቺን ፡ ዓለም ፡ እንዳያለብሷት ፡ እንድም ፡ ውስተ ፡ (አድባር ፡ ይቀውሙ ፡ ማያት) ፡ አንቀዕት ፡ በዲጋ ፡ ይጀምራሉ ። (እምተግሣፅከ ፡ ወእምድምፀ ፡ ነጐድጓድከ ፡ ይጐዩ ፡ ወይደነግፁ ፡ የዐርጉ ፡ አድባረ ፡ ወይወርዱ ፡ ገዳመ) ፡ ከመፍረድህ ፡ የተነሣ ፡ ከዲጋ ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ ይወርዳሉ ፡ (ውስተ ፡ ብሔር ፡ ኀበ ፡ ሣረርኮሙ ፡ ወሠራዕኮሙ) ፡ ወደ ፡ ሠራህላቸው ፡ ወደ ፡ ወሰንህላቸው ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ (ወሰኖሙ ፡ ከመ ፡ ኢይትመየጡ) ፡ እንዳሰፈው ። እንድም ፡ (ውስተ ፡ አድባር) ፡ ዝናማት ፡ መዝነም ፡ ከዲጋ ፡ ይጀምራሉ ፡ (እምተግሣፅከ) ፡ ከመፍረድህ ፡ የተነሣ ፡ እየዘነሙ ፡ ከዲጋ ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ ይወርዳሉ ፡ (ውስተ ፡ ብሔር) ፡ ወደ ፡ ሠራህላቸው ፡ ወደ ፡ ወሰንህላቸው ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ ይወርዳሉ ፤ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ወሀ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ይወርዳል ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አይወጣምና ፡ (ወሰኖሙ ፡ ከመ ፡ ኢይትመየጡ ፡ እንዳሰፈው ።

እንድም ፡ (ውስተ ፡ አድባር) ፡ በሐምሌ ፡ በነሐሴ ፡ ተራራ ፡ ተራራ ፡ ያህል ፡ እየሆነ ፡ ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ ይነሣል ። እምተግሣፅከ) ፡ ከመፍረድህ ፡ የተነሣ ፡ ይሸሻሉ ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ ይወርዳሉ ፡ ማለት ፤ በኅዳር ፡ በታኅሣሥ ፡ ይጐድላሉ ፡ (ውስተ ፡ ብሔር) ፡ ወሰኖሙ ፡ እንዳሰፈው ። (ከመ ፡ ኢይትመየጡ) ፡ ተመልሰው ፡ ይህችን ፡ ዓለም ፡ እንዳያለብሷት ፡ ማለት ፤ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ወሀ ፡ ኪቃሊሙ ፡ አያልፍምና ።



እንድም ፡ (ውስተ ፡ አድባር) ፡ ትሩፋን ፡ በባቢሎናውያን ፡ እጅ ፡ ተማርከው ፡ ባቢሎን ፡ ወርደው ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ይኖራሉ ፡ (እምተግሣፅከ) ፡ ወእምድምፀ ፡ ነጐድጓድከ) ፡ አንተ ፡ ከመፍረድህ ፡ የተነሣ ፡ ተማርከው ፡ ባቢሎን ፡ ይወርዳሉ ፡ (የዓርጉ) ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ይሆናሉ ። (ወይወርዱ) ፡ ቋሚ ፡ ለጓሚ ፡ ይሆናሉ ፡ (ውስተ ፡ ብሔር) ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ይኖሩባት ፡ ዘንድ ፡ በወሰንህላቸው ፡ በባቢሎን ፡ (ወሰኖሙ) ፡ ከማይተላለፉበት ፡ ከባቢሎን ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ወሰናቸው ። (ከመ ፡ ኢይትመየጡ) ፡ ሰብዓ ፡ ዘመን ፡ ሳይፈጸም ፡ ተመልሰው ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ እንዳይወርሷት ።

፲ ፡ ዘይፌኑ ፡ አንቅዕተ ፡ ውስተ ፡ ቈላት ።

እንዱን ፡ ይዞ ፡ ይሄዳል ፡ ምንጩን ፡ ከዲጋ ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ እንዲሄድ ፡ የሚያደርገው ፡ እሱ ፡ ነው ፡ እንድም ፡ ትሩፋንን ፡ ተማርከው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ እንዲወርዱ ፡ የሚያደርግ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ማዕከለ ፡ አድባር ፡ የኀልፉ ፡ ማያት ።

ውሆች ፡ በወሀና ፡ በወሀ ፡ መካከል ፡ እንድም ፡ በተራራና ፡ በተራራ ፡ መካከል ፡ ይሄዳሉ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ወሀ ፡ ዙሮ ፡ ይሄዳል ፡ እንጂ ፡ ተራራውን ፡ ሠንጥቆ ፡ ልሂድ ፡ አይልምና ። እንድም ፡ ትሩፋን ፡ በኃያላኑ ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ይወርዳሉ ።

፲፩ ፡ ወያሰትዩ ፡ ለኵሉ ፡ አርዌ ፡ ገዳም ።

ውሀኑታቸውን ፡ በበረሀ ፡ ላሉ ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ ያጠጣሉ ። እንድም ፡ ትሩፋን ፡ ገንዘባቸውን ፡ ለአሕዛብ ፡ ይሰጣሉ ።

ወይትዌከፉ ፡ ሐለስትዮታት ፡ ለጽምእሙ ።

ሐለስትዮ ፡ ያለ ፡ እንዶ ፡ ሆነ ፡ የበዳ ፡ አህያ ፡ ሐልስትዮ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ጠጣ ፡ ነው ፡ ጥማቸውን ፡ ለማራቅ ፡ ወሀውን ፡ ይጠጣሉ ፤ በሐለስትዮታት ፡ ሁሉን ፡ መናገር ፡ ነው ። እንድም ፡ በልተው ፡ ጠጥተው ፡ ንዴታቸውን ፡ ለማራቅ ፡ አሕዛብ ፡ የትሩፋንን ፡ ገንዘብ ፡ ይቀበላሉ ።

፲፪ ፡ ወያጸሉ ፡ ህየ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ።

የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ከወሀው ፡ ዳር ፡ ያርፋሉ ፡ እንድም ፡ ትሩፋን ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ይኖራሉ ።

ወያነቅዉ ፡ በማእከለ ፡ ጾላዕት ።

በዋሻው ፡ መካከል ፡ ተቀምጠው፡

ይፈሙኝሉ ፡ ከወሀ ፡ ጻር ፡ ዛፍ ፡
ዝያል፡ አይታጣምና፡ ከዚያ፡ ተቀም
ጠው ፡ ጭው ፡ ጭው ፡ ይላሉ ።
እንድም ፡ ትሩፋን ፡ በባቢሎን ፡
መከራ ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ሲያለቅ
ሱ ፡ ይኖራሉ ። [illegible]

[illegible]

ተራሮችን ፡ ውስጥ ፡ ውስጣቸውን ፡
የሚያጠጣቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ባያ
ጠጣቸው ፡ እንደ ፡ ጕተራ ፡ በፈረ
ሱ ፡ ነበርና ፡ ይኸውም ፡ ሊታወቅ፡
ድርቅ ፡ በሆነ ፡ ዘመን ፡ ተራራው ፡
ሊናድ ፡ ይታያል ፤ እንድም ፡ ነገ
ሥታቱን ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡
አድሮ ፡ የሚያስተምራቸው ፡ እሱ ፡
ነው ።

[illegible]

ተግባር ፡ ይመናፍሬ ፡ ዝናም ፡ ነው ፤
ትፅግብ ፡ ምድር ፡ ፍሬ ፡ እምተግባ
ርከ ፡ ይላል ፤ ምድር ፡ ከደመና ፡
የተገኘውን ፡ ዝናም ፡ ትረካለች ።

[illegible]

ለእንስሳ ፡ ምግብ ፡ ሊሆን ፡ ሣርን ፡
የሚያበቅል ፡ ዝናም ፡ ነው ፤ እን
ድም ፡ ጌታ ፡ ነው ።

[illegible]

ለሰው ፡ ለሚገዛ ፡ ለእንስሳ ፡ ልም
ላሜ ፡ ያለውን ፡ የሚያበቅል ፡
ዝናም ፡ ነው ፤ እንድም ፡ ጌታ ፡
ነው ። እንድም ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ለሚገዛ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ እህሉን ፡
ተክሉን ፡ የሚያበቅል ፡ ዝናም ፡
ነው ፤ እንድም ፡ ጌታ ፡ ነው ። እን
ድም ፡ እህልን ፡ ተክልን ፡ የሚ
ያበቅል ፡ ጌታ ፡ ነው ፤ (ለቅኔ ፡
ዕጓለ ፡ እመሕያው) ፡ ሰው ፡ ያን ፡
እየበላ ፡ ለመገዛት ።

[illegible]

እምፍሬ ፡ ተግባርከ ፡ ትፅግብ ፡
ምድር ፡ ብሎ ፡ ነበርና ። ቍ ፡ ፲፫ ።
ከምድር ፡ ሁሉን ፡ ያበቅል ፡ ዘንድ ፡
ነው ። [illegible]

[illegible]

ወይን ፡ የሰውን ፡ ልቡና ፡ ደስ ፡
ያሰኛል ፤ እንድም ፡ ወይን ፡ መፈ
ጠሩ ፡ ለከንቱ ፡ አይደለም ፡ የሰ
ውን ፡ ልቡና ፡ ደስ ፡ ሊያሰኝ ፡
ነው ፡ እንጂ ።

[illegible]

ዘይትም ፡ የሰውን ፡ መልክ ፡ ብ
ሩሀ ፡ መልአክ ፡ ያስመስላል ፡
እንድም ፡ ዘይት ፡ መፈጠሩ ፡ ለከ
ንቱ ፡ አይደለም ፡ የሰውን ፡ መል
ክ ፡ ብሩሀ ፡ መልአክ ፡ ሊያስመ
ስል ፡ ነው ፡ እንጂ ።

[illegible]

እህል ፡ የሰውን ፡ ኃይል ፡ ያፀናል ።
እንድም ፡ እህል ፡ መፈጠሩ ፡ ለከ
ንቱ ፡ አይደለም ፡ የሰውን ፡ ኃይ
ል ፡ ለማፅናት ፡ ነው ፡ እንጂ ።
እንድም ፡ (ወይን ፡ ያስተፌሥሖ ፡
ልበ ፡ ሰብእ) ፡ ደሙ ፡ ልበ ፡ ነፍ
ስን ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። እንድም ፡
ደሙ ፡ መሰጠቱ ፡ ለከንቱ ፡ አይ
ደለም ፡ ልበ ፡ ነፍስን ፡ ደስ ፡ ሊያ
ሰኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ። (ወቅብዕ ፡
ለአብርሆ ፡ ገጽ )፡ መንፈስ ፡ ቅዱ
ስ ፡ ሰውን ፡ ብሩህ ፡ መልአክ ፡ ያ
ስመስላል ። እንድም ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ መሰጠቱ ፡ ለከንቱ ፡ አይ
ደለም ፤ ብሩህ ፡ መልአክ ፡ ሊያስ
መስል ፡ ነው ፡ እንጂ ። (ዕክል ፡
ያፀንዕ ፡ ኃይለ ፡ ሰብእ) ፡ ሥጋው ፡
ኃይለ ፡ ነፍስን ፡ ያፀናል ፡ እን
ድም ፡ ሥጋው ፡ መሰጠቱ ፡ ለከ
ንቱ ፡ አይደለም ፡ ኃይለ ፡ ነፍ
ስን ፡ ሊያፀና ፡ ነው ፡ እንጂ ።

[illegible]

በበረኃ ፡ የሚኖሩ ፡ ዕፀዋት ፡ ሁሉ ፡
ዝናሙን ፡ ለምላሜውን ፡ ይረካ
ሉ ፡ እንድም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እህሉን ፡
ተክሉን ፡ በልተው ፡ ደስ ፡ ይላ
ቸዋል ። እንድም ፡ ምዕመናን ፡
ሁሉ ፡ ልጅነትን ፡ አግኝተው ፡
ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ተቀብለው ፡
ደስ ፡ ይላቸዋል ።

[illegible]

የደጋውን ፡ ዛፍ ፡ የፈጠርህ ፡
አንተ ፡ ነህ ፡ እንድም ፡ የደጋ
ውን ፡ ዛፍ ፡ የፈጠርህ ፡ ለከንቱ ፡
አይደለም ፡ የአዕዋፍ ፡ ማደሪያ ፡
ሊሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ። እንድም ፡
አብርሃምን ፡ የፈጠርኸ ፡ አንተ ፡
ነህ ፤ አብርሃምን ፡ የፈጠርኸ ፡
ለከንቱ ፡ አይደለም ፡ የሁሉ ፡
አባት ፡ ሊሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ።

[illegible]

በዛፉ ፡ ላይ ፡ አዕዋፍ ፡ ይፈለፍላሉ ፡
እንድም ፡ ከአብርሃም ፡ [illegible]
[illegible]

[illegible]

[illegible]

ኤል ፡ አባት ፡ ሊሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡

ወዖፃዕት ፡ ምጕያዮን ፡ ለግሔ ። ኢዮ ፡ ፴፯ ፡ ፳ ።

ዋሻው ፡ መፈጠፉ ፡ ለግሔያት ፡ (ለአሽኮኮዎች) ፡ መኖሪያ ፡ መሸሸ ፡ ሊሆን ፡ ነው ። እንድም ፡ ለከንቱ ፡ አይደለም ፡ ለግሔያት ፡ መኖሪያ ፡ መሸሻ ፡ ሊሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፲፱ ፡ ወገብርከ ፡ ወርኀ ፡ በዕድሜሁ ።

ጨረቃን ፡ በምልዓት ፡ ፈጠርህ ።

ፀሐይኒ ፡ አእመረ ፡ ምዕራቢሁ ።

ፀሐይም ፡ መግቢያውን ፡ ዐወቀ ። በምዕራብ ፡ ተፈጥሯልና ፡ እንድም ፡ በምሥራቅ ፡ ስድስት ፡ በምዕራብ ፡ ስድስት ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ መሳከው ፡ አሉት ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡ ከሆነ ፡ ብሎ ፡ ያለ ፡ ጊዜው ፡ ልሒድበት ፡ አይልምና ፡ እንድም ፡ ደክሞ ፡ ከመንገድ ፡ ልደር ፡ አይልምና ።

፳ ፡ ታመጽእ ፡ ጽልመተ ፡ ወይከውን ፡ ሌሊተ ።

ጭለማን ፡ ታመጣለህ ፡ ሌሊት ፡ ይሆናል ። እንድም ፡ ጼዋዌን ፡ ታገዛለህ ፡ ይደረጋል ።

ወይወፅኡ ፡ ቦቱ ፡ ኵሉ ፡ አራዊተ ፡ ገዳም ።

በበረኃ ፡ የሚኖሩ ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ ይሠማራሉ ።

፳፩ ፡ ዕጓለ ፡ አናብስት ፡ ይጥሕሩ ፡ ወይመሥጡ ።

ያንበሳ ፡ ገላግልት ፡ እየጮኹ ፡ ምግባቸውን ፡ ይንጥቃሉ ። እንድም ፡ አሕዛብ ፡ እየፎከሩ ፡ ይማርካሉ ።

ወይስእሉ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲሳዮሙ ።

ምግባቸውንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይለምናሉ ፡ ማለት ፡ እንዲያገኙ ፡ አውቆ ፡ መስጠቱን ፡ መናገር ፡ ነው ። እንድም ፡ እሱ ፡ ባወቀ ፡ ይለምኑታልና ። እንድም ፡ አሕዛብ፡ይለምኑታል፡ይሰጣቸዋል ።

፳፪ ፡ ወእምከመ ፡ ሠረቀ ፡ ፀሐይ ፡ የአትዉ ።

ፀሐይ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ አራዊት ፡ ወደ ፡ በዓታቸው ፡ ይገባሉ ። እንድም ፡ ሚጠት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ይጠፋሉ ።

ወይውዕሉ ፡ ውስተ ፡ ግበቢሆሙ ።

በየፍርኩታቸው ፡ በየዋሻቸው ፡ ገብተው ፡ ይውላሉ ፡ እንዘ ፡ ይቈርሩ ፡ ይላል ፡ ኢዮብ ፡ ሲፈሩ ፡ ሲንቀጠቀጡ ፡ ይውላሉ ። እንድም ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ይወርዳሉ ።

፳፫ ፡ ወይወፅእ ፡ ሰብእ ፡ ውስተ ፡ ተግባሩ ።

ፀሐይ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ይሠማራል ።



ይውዕል ፡ ወይትቀነይ ፡ እስከ ፡ ይመሲ ።

ሰው ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ይሠማራል ፡ (ይውዕል) ፡ እስኪመሽ ፡ ሲሠራ ፡ ይውላል ።

፳፬ ፡ ጥቀ ፡ ዐቢይ ፡ ግብርከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ሥራህ ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡ ነው ። መዝ ፡ ፺፯ ፡ ፭ ። ሲራ ፡ ፲፮ ፡ ፴ ።

ወኵሎ ፡ በጥበብ ፡ ገበርከ ።

ሰውን ፡ በመዓልት ፡ እንጂ ፡ በሌሊት ፡ እንዳይሠማራ ፡ አራዊትን ፡ በሌሊት ፡ እንጂ ፡ በመዓልት ፡ እንዳይሠማሩ ፡ ወሰንህ ፡ እንድም ፡ የወሰንህ ፡ አንተ ፡ ነህ ። ከሰው ፡ በቀር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ያፈረሰ ፡ የለም ፡ ሁሉም ፡ እሱ ፡ በወሰናቸው ፡ ይኖራሉ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ጨለማ ፡ ለብሶ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ ይሄዳልና ። እንድም ፡ ሰውን ፡ አቅንቶ ፡ መፍጠሩ ፡ ትንሣኤ ፡ አላችሁ ፡ አራዊትን ፡ አስጎንብሶ ፡ መፍጠሩ ፡ ትንሣኤ ፡ የላችሁም ፡ ሲል ፡ ነውና ።

መልአ ፡ ምድረ ፡ ዘፈጠርከ ፡

የፈጠርኸው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ምድርን ፡ መላ ፡ ምልዓ ፡ ምድር ፡ ሆን ። ኢሳ ፡ ፷፰ ፡ ፷፩-፷፱ ።

፳፭ ፡ ዛቲ ፡ ባሕር ፡ ዐባይ ፡ ወረኀብ ።

ይህቺ ፡ ባሕር ፡ ውቅያኖስ ፡ የወርድ ፡ የቁመት ፡ ስፊ ፡ ናት ።

ህየ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቍ ።

በውቅያኖስ ፡ ያለ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የለውም ።

እንስሳ ፡ ዐበይት ፡ ምስለ ፡ ደቂቅ ።

ታላላቁ ፡ ከታናናሹ ፡ ጋራ ፡ ማለት ፡ ዓሣ ፡ ዓንበሪ ፡ አዞ ፡ ጉማሬ ፡ ሁሉ ።

፳፮ ፡ ህየ ፡ የሐውራ ፡ አሕማር ።

በባሕር ፡ ላይ ፡ መርከቦች ፡ ይሄዳሉ ። ወፈቀዳ ፡ ይሠጠማ ፡ አሕማር ፡ እንዲል ።

ከይሲ ፡ ዘፈጠርከ ፡ ይሣለቅ ፡ ላዕሌሆሙ ።

የፈጠርኸው ፡ ዘንዶ ፡ በሳቸው ፡ ይዘብትባቸዋል ። ስፈዶ ፡ የሚባል ፡ መልኩ ፡ ባሕር ፡ የሚመስል ፡ ዘንዶ ፡ አለ ፡ ነጋድያን ፡ በመርከብ ፡ ተጭነው ፡ ሲሄዱ ፡ ማዕበሉን ፡ መስሎ ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ መጥቶ ፡ መርከባቸውን ፡ ይበሳዋል ፡ ይሰጥማሉ ፡ ከዚያ ፡ ሆኖ ፡ ይመገባቸዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እንድም ፡ (ዛቲ ፡ ባሕር) ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የቁመት ፡ የወርድ ፡ በፊ ፡ ናት ። (ህየ ፡ ዘይትሐወስ) ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ እስራኤል ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የላቸውም ፡ (እንስሳ) ፡ ታላላቁ ፡ ከታናናሹ ፡ ጋራ ፡ የዕድሜ ፡ የማዕርግ ፡ ነው ፡ (ህየ ፡ የሐውራ) ፡ አሕዛብ ፡ ይዘምቱበታል ። አሌሎን ፡ ለአሕማር ፡ አለ ፡

ቦን ፡ ክንፍ ፡ እንዲል ፡ ኢሳ ፡ (ከይሲ ፡ ዘፈጠርከ) ፡ ናቡከደነፆር ፡ ይማርካቸዋል ።

እንድም ፡ (ዛቲ ፡ ባሕር) ፡ ይህቺ ፡ ዓለም ፡ የቁመት ፡ የወርድ ፡ ስፋ ፡ ናት ፡ (ህየ ፡ ዘይትሐወስ) ፡ በዚች ፡ ዓለም ፡ የሚኖር ፡ ፍጥረት ፡ ፆ ፍር ፡ ቍጥር ፡ የለውም ፡ (እን ስሳ) ፡ ታላላቁ ፡ ከታናናሹ ፡ ጋራ ፡ (ህየ) ፡ ነቢያት ፡ ይመግቧቸዋል ። (ከይሲ) ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የፈጠር ኸው ፡ ዲያብሎስ ፡ እቈራኛቸ ዋለሁ ፡ ይላል ።

እንድም ፡ (ዛቲ ፡ ባሕር) ፡ ጥም ቀት ፡ ስፋ ፡ ናት ፡ ማለት ፡ ጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ መድረሷን ፡ መና ገር ፡ ነው ። (ህየ) ፡ በጥምቀት ፡ ያመኑ ፡ ምዕመናን ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። (እንስሳ)፡ ታላላቁ፡ ከታናናሹ፡ ጋራ፡ የሰድሚ ፡ የማዕርግ ፡ ትንሹም ፡ ትልቁም ፡ ያርባ ፡ የሰማንያ ፡ ቀን ፡ ያርባ ፡ የሰማንያ ፡ ዘመን ፡ ይጠመቃልና ። (ህየ) ፡ ሐዋርያት ፡ ይመግቧታል ፡ (ከይሲ) ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዲያብሎስ ፡ እቈራኛቸዋ ለሁ ፡ ይላል ፡ አይሆንለትም ፡ እንጂ ፡ ኢሳ ፡ ፳፯ ፡ ፩ ።

፳፯ ፡ ወኵሉ ፡ ይሴፎ ፡ ብነቢከ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ አንተን ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል ።

ተሀቦሙ ፡ሲሳዮሙ ፡ በጊዜሁ ።

ምግባቸውን ፡ በየጊዜው ፡ ትሰጣ ቸው ፡ ዘንድ ፡ ማለት ፡ በዘር ፡ ጊዜ ፡ ዘሩን ፡ በመከር ፡ ጊዜ ፡ መከ ሩን ።

፳፰ ፡ ወእምከመ ፡ ወሀብኮሙ ፡ ያስተጋ ብኡ ።

ከሰጠኻቸውም ፡ በኋላ ፡ በረቅ ፡ በጎታ ፡ በጎተራ ፡ ይሰበስባሉ ፡ እን ድም ፡ ለሰው ፡ አይሰጡም ፡ ጭ ብጥ ፡ አድርገው ፡ ይይዛሉ ።

ወፈቲሖከ ፡ እዴከ ፡ ታወምብ ፡ ለኵሉ ፡ እም ሕረትከ ።

አንተ ፡ ግን ፡ እጅ ፡ ሰፊ ፡ ነህና ፡ እጅህን ፡ ዘርግተህ ፡ ከቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ምግባቸውን ፡ ሰጥተህ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ታሰኘለህ ፡ መዝ ፡ ፻፵፬ ፡ ፲፮ ። ማቴ ፡ ፮ ፡ ፳፭ ። ፊል ፡ ፬ ፡ ፮ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

፳፱ ፡ እመሰ ፡ሜጥከ ፡ ገጸከ ፡ ይደነግጹ ።

ለጊዜው ፡ ገጽ ፡ መዓትህን ፡ ብት መልሰው ፡ ግን ፡ በመከራው ፡ በረኃቡ ፡ ይደነግጣሉ ።

ትወጽእ ፡ መንፈሶሙ ፡ ወየሐልቁ ።

ነፍሳቸው ፡ ከሥጋቸው ፡ በረኃ ቡ ፡ እለየዋለሁ ፡ ትላለች ፡ (ወየ ሐልቁ) ፡ እለቅን ፡ እለቅን ፡ ይላሉ ።

ወይገብኡ ፡ ውስተ ፡ መሬቶሙ ፡ ኢዮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።

ወደ ፡ መሬታቸው ፡ (መሬትነ ታቸው) ፡ ይመለሳሉ ። ሲራ ፡ ፲፯ ፡ ፴ ።



፴ ፡ ትፌኑ ፡ መንፈስከ ፡ ወይትፈጠሩ ።

ኋላ ፡ ግን ፡ ዝናም ፡ የቋጠረ ፡ ደመናን ፡ የያዘ ፡ ነፋስን ፡ ታመ ጣለህ ፡ በዝናም ፡ የበቀለውን ፡ እህሉን ፡ ተክሉን ፡ በልተው ፡ ይታደሳሉ ።

ወትሔድስ ፡ ገጸ ፡ ለምድር ።

ምድርን ፡ በልምላሜ ፡ ታድሳታ ለህ ፡ ለሰስ ፡ ያለ ፡ ዝናም ፡ የወ ረደ ፡ እንደሆነ ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኗ ፡ ብላ ፡ ትበ ቅላለችና ። እንድም ፡ ትሩፍን ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በሚጠት ፡ ደስ ፡ ታሰኛታለህ ።

እንድም ፡ (ታወፅእ ፡ መንፈሶ ሙ) ፡ ነፍሳቸውን ፡ ከሥጋቸው ፡ በሞት ፡ ትለያታለህ ። (የሐልቁ) ፡ ይፈጸማሉ ። (ወይገብኡ) ፡ ወደ ፡ መሬትነታቸው ፡ ይመለሳሉ ። መ ሬት ፡ አንተ ፡ ወትገብዕ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ እንዲል ፡ (ትፌኑ) ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ታሳድርባቸዋለህ ፡ ታድሰው ፡ ይነ ሣሉ ። (ወትሔድስ) ፡ ምዕመናን ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ታድሳታ ለህ ።

፴፩ ፡ ለይኩን ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዓለም ።

የእግዚአብሔር ፡ ጌትነቱ ፡ ለዘ ላለሙ ፡ ሲመሰገን ፡ ይኑር ፡ (ይኖ ራል) ።

ይትፌሣሕ ፡ እግዚአብሔር ፡ በተግባሩ ።

እግዚአብሔር ፡ በፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ ደስ ፡ የማያሰኝ ፡ ፍጥረት ፡ አልፈጠረምና ፡ በእንቢ ተኛነቱ ፡ ይቀርበታል ፡ እንጂ ።

፴፪ ፡ ዘይኔጽሮ ፡ ለምድር ፡ ወይሬስያ ፡ ከመ ፡ ትርዓድ ።

በዔዋዌ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ ባቢሎንን ፡ ትፈታ ፡ ዘንድ ፡ በዓይኑ ፡ መዓት ፡ የሚያያት ፡ እሱ ፡ ነው ። እንድ ም ፡ ታልፍ ፡ ዘንድ ፡ ይህቺን ፡ ዓለም ፡ በዓይኑ ፡ መዓት ፡ የሚያ ያት ፡ እሱ ፡ ነው ።

ዘይገሥሦሙ ፡ ለአድባር ፡ ወይጠይሱ ።

ነገሥታቱን ፡ በኵርናዓ ፡ መዓቱ ፡ የሚዳስሳቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ይ ጠይሱ) ፡ ይጠፋሉ ፤ ይጤሱ ፡ ይ ጠፉ ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ ተራሮች ን ፡ በእደ ፡ ኀልፈት ፡ የሚዳስሳ ቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። ያልፋሉ ፤ ያልፉ ፡ ዘንድ ።

፴፫ ፡ እሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር፡በሕይወትየ።

እግዚአብሔርን ፡ ባለ ፡ ዘመኔ ፡ ሁሉ ፡ አመሰግነዋለሁ ፡ መዝ፡፻፵፭፡፪።

ወእዜምር ፡ ለአምላኪየ ፡ በአምጣነ ፡ ሀሎኩ።

ለፈጣሪዬ ፡ በዕድሜዬ ፡ ልክ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

፴፬ ፡ ወአሥምሮ ፡ በቃልየ ።

ቃልየም ፡ ቢል ፡ በ ፡ ብለህ ፡ ተር

ጉም ፤ በቃሌም ፡ ደስ ፡ እሰኘዋ ለሁ ።

ወአንስ ፡ እትፌሣሕ ፡ በእግዚአብሔር ። ዕን ፡ ፪ ፡ ፲፰ ።

እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እ ምኜ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

ፀሐ ፡ ወዮንለቁ ፡ ኃጥአን ፡ እምድር ።

ኃጥአን ፡ ግን ፡ እንድም ፡ ባቢሎ ናውያን ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ ተለይ ተው ፡ እንድም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ይጠፋሉ ፡ ይጥፉ ።

ወዐማፅያንሂ ፡ ኢይሄልዉ ፡ እንከ ።

ዐመፀኞችም ፡ ቢኖሩ ፡ ቢኖሩ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከዚህ ፡ ቀድ ሞ ፡ የኖሩትን ፡ ያህል ፡ አይኖሩም ።

ትባርኪ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቁ ፡ ፩ ።

ሰውነቴ ፡ እንድም ፡ ልቡናዬ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታመስግንዋለች ።

## መዝሙር ፡ ፻፭ ።

ሃሌ ፡ ሉያ ።

ትድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ ዓለምን ፡ አሳልፎ ፡ የሚኖር ፡ እንድም ፡ ያህ ፡ ይላል ፡ በዓረብ ፡ ስብሐት ፡ ለእግ ዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፩፤ ግነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወጸውዑ ፡ ስሞ ።

ስሙን ፡ እየጠራችሁ ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ የምስጋና ፡ የሃይማ ኖት ፡ አገዛዝ ፡ ተገዙ ።

ወንገርዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ምግባሮ ።

ከሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ጀምሮ ፡ ያደረ ገውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥ ራውን ፡ ለአሕዛብ ፡ ንገሯቸው ፡ አስተምሯቸው ።

፪፤ ሰብሐ ፡ ወዘምሩ ፡ ሎቱ ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአ ምልኮት ፡ እሱን ፡ አመስግኑት ፡ ለስሙም ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።

ወንግሩ ፡ ኵሎ ፡ መንክሮ ። ኢሳ ፡ ፲፪ ፡ ፬፡ ፳፮ ፲፫ ።

ድንቅ ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ንገሩ ፡ አስተምሩ ።

፫፤ ወትከብሩ ፡ በስሙ ፡ ቅዱስ ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ የሚሆን ፡ ስሙ ን ፡ በማመስገን ፡ (ለስሙ) ፡ ለማ መስገን ፡ ትከበራላችሁ ።

ለይትፌሣሕ ፡ ልብ ፡ ዘየኀሥሥ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአም ልኮ ፡ የሚሻው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ደስ ፡ ይበለው ።

፬፤ ኅሥሥዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወትጸንዑ ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአም



ልኮት ፡ በጸሎት ፡ ሹት ፤ እን ዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ እሱን ፡ በማመን ፡ በማምለክ ፡ ፀንታችሁ ፡ ትኖራላችሁ ።

ወኅሡ ፡ ገጾ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ገጹ ፡ ምሕረት ፡ ገጹ ፡ ረድኤቱንም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሹ ። ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፮ ።

፭፤ ወተዘከሩ ፡ መንክሮ ፡ ዘገብረ ።

ያደረገውን ፡ ተአምራቱን ፡ አስ ቡ፡ ቡ ፡

ተአምሪሁ ፡ ወኵነኔ ፡ አፉሁ ።

ተአምራቱን ፡ ባንደበቱ ፡ የሠራ ውን ፡ ሕጉን ፡ አስቡ ፡

፮፤ ዘርዐ ፡ አብርሃም ፡ አግብርቲሁ ።

ማን ፡ ማን ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ እገሌ ፡ እገሌ ፡ ምን ፡ አስኝቶኝ ፡ ባለሚሉ ፡ የአብርሃም ፡ ልጆች ፡ መላችሁ ።

፯፤ ወደቂቀ ፡ ያዕቆብ ፡ ኅሩያኒሁ ።

ለክህነት ፡ ለመንግሥት ፡ የተመ ረጣችሁ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ መላችሁ ።

ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐ ዋቂ ፡ ነውና ።

ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡ ኵነኔሁ ። መዝ ፡ ፻፱ ፡ ፳፪ ።

ግዛቱ ፡ ባሪቱ ፡ መጓዝን ፡ ምሉዕ ፡ ነው ።

፰፤ ወተዘከረ ፡ ሥርዓቶ ፡ ዘለዓለም ።

ተዘከረ ፡ ዘለዓለም ፡ ሥርዓቶ ፡ ዘለ ዓለም ፡ ይላል ፤ ለዘላለም ፡ የሚ ኖር ሥርዓቱን ፡ ሕጉን ፡ አሰበ ፡ ፈጸመ ።

ቃሎ ፡ ዘአዘዘ ፡ ለ፲፻ቱ ፡ ፻ት ፡ ትውልድ ።

ሥርዓቶ ፡ ያለውን ፡ ቃሎ ፡ ብሎ ፡ ገለጸው ፤ ለሺሕ ፡ ትውልድ ፡ የሠራውን ፡ ሕጉን ፡ አሰቦ ፡ ሺሕ ፡ ትውልድ ፡ ኑሮ ፡ አይደለም ፡ በፍ ጹም ፡ ተናገረው ። እስመ ፡ አነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ዘእ ገብር ፡ ምሕረተ ፡ ለእለ ፡ ያፈቅ ሩኒ ፡ እስከ ፡ ፲ቱ ፡ ፻ት ፡ ትውል ልድ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ አምላክ ፡ ቀናዒ ፡ ዘእፈዲ ፡ ኃጢአተ ፡ አ በው ፡ ላዕለ ፡ ውሉድ ፡ እስከ ፡ ሣልስ ፡ ወራብዕ ፡ ትውልድ ፡ ለእለ ፡ ይጸልዑኒ ፡ እንዲል ፡ ዘፍ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ፡ ዘፀ ፡ ፳፭ ።

፱፤ ዘሠርዐ ፡ ለአብርሃም ።

ለአብርሃም ፡ የሠራለት ፡ ሥርዓቱ ን ፤ እንድም ፡ ለአብርሃም ፡ ሥር ዓቱን ፡ የሠራለት ፡ እግዚአብሔር ፡ አሰበ ። እንድም ፡ ያዘዘለት ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ፳፮ ፡ ፩ ። ፪ ፡ ፬ ።

ወመሐለ ፡ ለይስሐቅ ።

ለይስሐቅ ፡ የማለውን ፡ መሐላ ፡ አሰበ ። እንድም ፡ ለይስሐቅ ፡ የማለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሰበ ።

2014 04 17

እንድም ፡ የማለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

፲ ፡ ወአቀሙ ፡ ስምዐ ፡ ለያዕቆብ ።

ለያዕቆብ ፡ ያፀናለት ፡ እምልኮ ቱን ፡ አሰበ ። እንድም ፡ ለያዕቆብ ፡ እምልኮቱን ፡ ያፀናለት ፡ እግዚ አብሔር ፡ አሰበ ። ለያዕቆብ ፡ እም ልኮቱን ፡ ያፀናለት ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ነው ።

ወለእስራኤልኒ ፡ ኪዳና ፡ ዘለዓለም ።

ያዕቆብ ፡ ያለውን ፡ እስራኤል ፡ ብሎ ፡ ደገመው ፡ ለእስራኤልም ፡ የማለውን፡ለዘላለም፡ፀንቶ፡የሚኖር ፡ መሐላውን ፡ አሰበ ፡ ዘፍ ፡ ፴፭ ፡ ፱ ፡ ፲፪ ።

፲፩ ፡ ወይቤሎ ፡ ለከ ፡ እሁበከ ፡ ምድረ ፡ ከነ ዓን ።

ምድረ ፡ ከነዓንን ፡ ወርዷን ፡ ቁመ ቷን ፡ ለከ ፡ ወለዘርዕከ ፡ እሁብ ከሃ ፡ ብሎ ፡ የማለውን ፡ መሐላ ውን ፡ አሰበ ፡ እንድም ፡ እሰጥ ሃለሁ ፡ አለው ፡ ብለህ ፡ እሥር ።

ትክፍልተ ፡ ሐብለ ፡ ርስትክሙ ።

ርስተ ፡ ሐብልክሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የረዘመውን ፡ በጠፍር ፡ ያጠረውን ፡ በድግር ፡ ትካፈሉ ፡ ዘንድ ፡ ር ስት ፡ ልትሆናችሁ ። ዘፍ ፡ ፲፪ ፡ ፩ ፡ ፮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ።

፲፪ ፡ እንዘ ፡ ውኁዳን ፡ ጥቀ ፡ እሙንቱ ።

እሊህ ፡ ፈጽመው ፡ ጥቂት ፡ ሳሉ ፡ ይህን ፡ ተስፋውን ፡ ነገራቸው ።

ወፈላስያን ፡ ውስቴታ ።

ለከነዓን ፡ ነው ፡ በከነዓንም ፡ ስደ ተኞች፡ መፃተኞች ፡ ሁነው ፡ ሳሉ ።

፲፫ ፡ ወኃለፉ ፡ እምሕዝብ ፡ ውስተ ፡ ሕዝብ ።

ከንዱ፡ ነገድ ፡ ወደ ፡ እንዱ፡ ነገድ ፡ ሄዱ ።

፲፬ ፡ ወእምንግሥት ፡ ውስተ ፡ ካልዕ ፡ ሕዝብ ።

ካንዱም ፡ ንጉሥ ፡ ወዳንዱ ፡ ን ጉሥ ፡ ሄዱ ። እንድም ፡ ውስተ ፡ ነገሥተ ፡ ካልዕ ፡ ሕዝብ ፡ ይላል ፡ ካንዱ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ወዳ ንዱ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ሄዱ ።

ወኢኃደገ ፡ ይምሐጠሙ ፡ ሰብእ ።

ሰው ፡ ይጣላቸው ፡ ዘንድ ፡ ፀበ ን ፡ አልተወባቸውም ። እንድም ፡ ኢኃደገ ፡ ሰብእ ፡ ይምሐጠሙ ፡ ይጣሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ሰዎችን ፡ አላሠለጠነባቸውም ።

ወገሠፀ ፡ ነገሥተ ፡ በእንቲአሆሙ ።

በሳቸው ፡ ምክንያት ፡ ስለሳቸው ፡ ነገሥታቱን ፡ ገሠፀላቸው ፡ እን ጂ ፡ ኢኃደገ ፡ ሰብእ ።

፲፭ ፡ ወኢትግሥሥዎሙ ፡ መሲሐንየ ።

ቅቡዓንየ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ቀብቼ ፡ ያነገሥኋቸው ፡ ነገሥታቱን ፡ አት ንኳቸው ፡ መቼ ፡ ተቀባና ፡ እን ዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ቅቡዓኑን ፡ ስለ ፡ ወለደ ፡ ብሎ ። እንድም ፡ ቅብር ፡



በድንከ ፡ ኀበ ፡ ዘፈቀድከ ፡ እስመ ፡ ከመ ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ እምታ ታሕተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለ ውታልና ። ዘፍ ፡ ፳ ፡ ፲፭ ፡ ፳፫ ፡ ፮ ።

ወኢታእኩይዎሙ ፡ ዲበ ፡ ነቢያትየ ።

በነቢያትም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አታ ምጡባቸው ፡ ብሎ ፡ ገሠፀላቸው ፡ እንጂ ፡ ኢኃደገ ፤ መቼ ፡ ነቢይ ፡ ተባለና ፡ ነቢያትየ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ነቢያትን ፡ ስለ ፡ ወለደ ፡ እንድም ፡ ፀውዕዎ ፡ ለእግዚእየ ፡ ይጸሊ ፡ ሎቱ ፡ እስመ ፡ ከመ ፡ ነቢይ ፡ ው እቱ ፡ ብላዋለችና ። ዘፍ ፡ ፳ ፡ ፯ ። (ታ ሪክ) ፡ አብርሃም ፡ በዘመኑ ፡ ረኀብ ፡ ሆኖ ፡ ይልቁንም ፡ በከነዓን ፡ ፀንቶ ል ፡ ሚስቱን ፡ ሣራን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ተሰደደ ፡ ምድረ ፡ ግብ ፅ ፡ ሲደርሱ ፡ አእምር ፡ ከመ ፡ ሠናይተ ፡ ላህይ ፡ አንቲ ፡ ወእ ምከመ ፡ ርዕዩኪ ፡ ሰብእ ፡ ግብፅ ፡ ኪያየ ፡ ይቀትሉ ፡ ወኪያኪ ፡ ያሐ ይዉ ፡ ግበሪ ፡ ምሕረተ ፡ ምስ ሌየ ፡ ከመ ፡ እሕየው ፡ በዕብሬ ትኪ ፡ በሊዮሙ ፡ እኅቱ ፡ አነ ፡ ይላል ፡ እኔ ፡ እስካሁን ፡ ወጥቼ ፡ ወርጄ ፡ አገለገልኋችሁ ፡ እንግ ዲህ ፡ ወዲህ ፡ አላንተ ፡ ፈንታች ሁን ፡ እኔን ፡ አገልግሉኝ ፡ አን ቺን ፡ ሲሉ ፡ እንዳይጣሉኝ ፡ ም ንሽ ፡ ነው ፡ ያሉሽ ፡ እንደሆነ ፡ እሱም ፡ ወንድሜ ፡ እኔም ፡ እኅቱ ፡ ነኝ ፡ በዬ ፡ አላት ፡ ከዚያ ፡ ሲወ ርዱ ፡ ሸማ ፡ አጣቦች ፡ አገኟ ቸው ፡ ያም ፡ ለኔ ፡ ትገባለች ፡ ያም ፡ ለኔ ፡ ትገባለች ፡ ብለው ፡ ተሻምተዋታል ፡ አንድ ፡ ሕፅ ው ፡ ነበረ ፡ ይህችስ ፡ ለሁላችሁ ም ፡ አትገባም ፡ ለንጉሡ ፡ ትገ ባለች ፡ ብሎ ፡ ወስዶ ፡ ለፈርዖን ፡ ሰጠው ፡ ምንህ ፡ ናት ፡ አለው ፡ እኅቴ ፡ ናት ፡ አለው ። እሷንም ፡ ምንሽ ፡ ነው ፡ አላት ፡ ወንድሜ ፡ ነው ፡ አለችው ፡ ከሱ ፡ ተቀብሎ ፡ ምግባቸውን ፡ መግቦ ፡ እሱን ፡ ከእንግዳ ፡ ቤት ፡ አሳደሩት ፡ እለ ፡ እሷን ፡ ከእልፍኝ ፡ አግብቶ ፡ ልድረስብሽ ፡ ቢል ፡ ንዑስ ፡ መሌ ሊቱ ፡ መከዳ ፡ ያህል ፡ አበጠ ፡ እጁ ፡ ሰለለ ፡ ነገሩ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ገልጸሽ ፡ ንገሪኝ ፡ አላት ፡ ብንፈራህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዮ ፡ ሰው ፡ እኮን ፡ ባሌ ፡ ነው ፡ አለ ችው ፡ ምን ፡ ይበጀኛል ፡ አላት ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ይጸልይልህ ፡ አለ ችው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አስጠርቶ ፡ ምነው ፡ እኅቴ ፡ ናት ፡ አላልከ ኝምን ፡ አለው ፡ አሕዛብ ፡ ዕኑዓን ፡ ናችሁና ፡ ብፈራህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሚስቴ ፡ ናት ፡ አለው ፡ ብትነግ ረኝ ፡ የጉልማሳ ፡ ሚስት ፡ እነካ ፡ ነበርን ፡ አለው ፡ እሱም ፡ ወዲ ያው ፡ ጸልዮ ፡ አድኖታል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለሱ ፡ ንዑስ ፡ መሌሊቱ ፡

2014 04 17

መከዳ ፡ ያህል ፡ እንዳበጠ ፡ እጁ ፡ እንደ ፡ ሰለለ ፡ እስመስሎ ፡ ወርቅ ፡ እመርቶ ፡ ስጥቶታል ። እሷም ፡ እድለውኩ ፡ ለገጽኪ ፡ ፊትሽን ፡ ስላየሁ ፡ ብሎ ፡ በሥር ፡ ምዝምዝ ፡ ወርቅ ፡ ለእጆቹ ፡ ለእግሯ ፡ እን ባር ፡ ስጥቷታል ፡ ከአቢሜሌክም ፡ ቢጃፉ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ተደርጓል ፡ ለሱም ፡ እንዲህ ፡ አድርጎለታል ፡ ለዚም ፡ ገረድ ፡ ደንገጥር ፡ ይሁ ኑሽ ፡ ብሎ ፡ አጋርንና ፡ ኬጡራን ፡ ስጥቶ ፡ ሰድዷታል ። ዘፍ ፡ ፲፫ ፡ ፲ ፡ ፳ ፡ ፳ ፡ ፳—፲፰ ።

፲፮ ፡ ወአምጽአ ፡ ረኀበ ፡ ለብሔር ።

ለሀገር ፡ ረኀብን ፡ አመጣ ፡ ይጠ ቅም ፡ ይመስል ፡ ለብሔር ፡ አለ ። እንድም ፡ እስቀድመው ፡ ተጠን ቅቀው ፡ የቈዩ ፡ ብዙ ፡ የተጠቀ ሙ ፡ አሉና ፡ እንድም ፡ በብሔር ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በሀገር ፡ ረኀብን ፡ አመጣ ፡ ኩን ፡ ጠቢብ ፡ ለዕድ ሜከ ፡ እንዲል ፡ ማቴ ።

ወአጥፍአ ፡ ኵሎ ፡ ኃይለ ፡ ዕክል ።

ዘመደ ፡ ዕክል ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የህ ልን ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ ፡ እን ድም ፡ በቁሙ ፡ የህሉን ፡ ኃይል ፡ አጠፋ ፡ ቢበሉትም ፡ ስልት ፡ ቀ ጠና ፡ ሁኖ ፡ አጥፍቷቸዋልና ፡ ወነፋኅከሞሙ ፡ እንዲል ።

፲፯ ፡ ፈነወ ፡ ብእሴ ፡ ቅድሜሆሙ ።

ከሳቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ዮሴፍን ፡ ላከ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ወረደ ፡ ብሎ ፡ የሚያመጣ ፡ ነውና ።

ተሠይጠ ፡ ዮሴፍ ፡ ወኮነ ፡ ገብረ ።

ፈነወ ፡ ያለውን ፡ ተሠይጠ ፡ ብ እሴ ፡ ያለውን ፡ ዮሴፍ ፡ ብሎ ፡ አመጣው ፡ ዮሴፍ ፡ ተሸጠ ፡ በግ ብፅ ፡ ተገዢ ፡ ሁኖ ፡ ኖረ ።

፲፰ ፡ ወሐመ ፡ እገሪሁ ፡ በመዋቅሕት ።

እግሩ ፡ በእግር ፡ ብረት ፡ ታሥሮ ፡ ሠሰሰለ ።

ወአምሠጠት ፡ ነፍሱ ፡ እምሐጺን ።

ሰውነቱ ፡ ከመታሠር ፡ አመለጠች።

፲፱ ፡ ዘእንበለ ፡ ይብጻሕ ፡ ቃሉ ።

አዘክረኒ ፡ በቅድመ ፡ ፈርዖን ፡ እግዚእከ ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ ሳይ ደርስ ።

ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምከሮ ።

አመከሮ ፡ ይላል ፡ ቃለ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ተፈታተነው ፡ ማለት ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ እንዲታሠር ፡ አደረገው ፡ እንድም ፡ (ዘእንበለ ፡ ይብጻሕ ፡ ቃሉ) ፡ አዘክረኒ ፡ በቅ ድመ ፡ ፈርዖን ፡ እግዚእከ ፡ ያ ለው ፡ ቃሉ ፡ ከፈርዖን ፡ ሳይደርስ ፡ (ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምከሮ) ፡ የሁለቱን ፡ መኳንንት ፡ ሕልም ፡ እንዲፈታ ፡ አደረገው ፡ እንድም ፡ አዘክረኒ ፡ በቅድመ ፡ ፈርዖን ፡ እግዚእከ ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ ከፈር



ዖን ፡ ሳይደርስ ፡ የንጉሡን ፡ ሕ ልም ፡ እንዲፈታ ፡ አደረገው ። ምነው ፡ የንጉሡንማ ፡ ሕልም ፡ የፈታው ፡ ኋላ ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ፡የሁለቱን፡መኳንንት፡ሕልም፡በ መፍታቱ ፡ ታውቋልና ። እንድም ፡ ፈርዖን ፡ ሕልሜን ፡ የሚፈታ ፡ አምጡልኝ ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ ከዮ ሴፍ ፡ ሳይደርስ ፡ ንጉሡን ፡ ሕ ልም ፡ እንዲያይ ፡ አደረገው ። እንድም ፡ ፈትታችሁ ፡ አምጡ ልኝ ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ ከዮሴፍ ፡ ሳይደርስ ፡ ሕልሜን ፡ የሚፈታ ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ። ለያዕቆብ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፡ ዐሥራ ፡ አንዱ ፡ በዮሴፍ ፡ ቀን ተውበት ፡ ለግብፃውያን ፡ ሸጡ ት ፡ እንያስ ፡ ለእስማኤላውያን ፡ ነው ፡ የሸጡት ፡ እስማኤላውያን ፡ ለግብፃውያን ፡ ስለ ፡ ሸጡት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ በምን ፡ ምክንያት ፡ ቢሉ ፡ ያዕቆብ ፡ ራሔልን ፡ ይወ ዳታል ፡ ከሷ ፡ ዮሴፍን ፡ ብንያ ምን ፡ ይወልዳል ፤ በዚህ ፡ ም ክንያት ፡ ይወደዋል ፤ ከመውደ ዱም ፡ የተነሣ ፡ ዐራት ፡ ኅብር ፡ አምስተኛ ፡ በወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ግምጃ ፡ አልብሶት ፡ ይኖራል ፤ በ ዚህ ፡ ምክንያት ፡ ይቀኑበታል ፤ ኋላም ፡ እሱ ፡ ለያዘው ፡ ነዶ ፡ ወ ንድሞቹ ፡ የያዙት ፡ ነዶ ፡ ሲሰ ግድ ፡ አይቶ ፡ ላባቱ ፡ ነገረው ፡ ወንድሞችህ ፡ በረኀብ ፡ ምክን ያት ፡ ይገዙልህ ፡ ይሆናል ፡ አለ ው ፡ ሁለተኛ ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ከዋክብት ፡ ላ ንድ ፡ ኮከብ ፡ ሲሰግዱ ፡ አይቶ ፡ ነገረው ፡ ፀሐይ ፡ የተባልሁ ፡ እኔ ፡ አባትህ ፡ ነኝ ፡ ጨረቃ ፡ የተባ ለች ፡ እናትህ ፡ ናት ፡ እናቱስ ፡ ከመንገድ ፡ ሙታ ፡ ቀርታለች ፡ ብሎ ፡ ካራቱ ፡ ዕቁባቱ ፡ እንዱቱ ፡ ዘለፋ ፡ አብረው ፡ ወርዳ ፡ ነበ ርና ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ከዋክብት ፡ የተባሉ ፡ ወንድሞችህ ፡ ናቸው ፡ በረኀብ ፡ ምክንያት ፡ ይገዙልህ ፡ ይሆናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለወንድ ሞችህ ፡ አትንገራቸው ፡ ይጣሉ ሃል ፡ አለው ፡ ከብቶቻቸውን ፡ ይዘው ፡ የሚኖሩ ፡ ግር ፡ ወሀ ፡ ካለበት ፡ ነውና ፡ ስንቃቸውን ፡ አሲዞ ፡ ይህን ፡ ስጥተህ ፡ ወን ድሞችህ ፡ ያሉበትን ፡ ጠይቀህ ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ፡ ሲፈልጋ ቸው ፡ ሰንብቶ ፡ አጣቸው ፡ መል አኩ ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ ተገ ልጾ ፡ ታየው ፤ አይቴ ፡ ይርእዩ ፡ አኃውየ ፡ አለው ፡ ቴምናስራህ ፡ ነበሩ ፡ ወደ ፡ ዶታዩን ፡ እንሂ ዳለን ፡ ሲሉ ፡ ሰምቻቸው ፡ ነበር ፡ አለው ፤ ሄዶ ፡ ከሩቅ ፡ አይተው ፡ በወቂት ፡ መጽአ ፡ ዝኩ ፡ እትኑ ፡ ሐላሚ ፡ ሕልም ፡ ንዑ ፡ ንቅትሎ ፡ ወንደዮ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡ ወንር

2014 04 17

ዓይ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ እሕላሚሁ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ይነግሥብን ፡ እንደሆን ፡ እናያለን ፡ እሱ ፡ ያመጣላቸውን ፡ ስንቅ ፡ ተቀብለው ፡ ከብበው ፡ እየተቀባበሉ ፡ ይመቱት ፡ ዝሙሩ ፡ የሴፍ ፡ የጊታ ፡ ምሳሌ ፡ ተቀብለው ፡ ከብበው ፡ እንደ ፡ መቱት ፡ ቤተ ፡ እይሁድም ፡ የጊታን ፡ ትምርቱን ፡ ይጠላሉ ፡ ተእምራቱን ፡ ይወዳሉና ፡ በእንተ ፡ ሠናይሰ ፡ ግብርከ ፡ ኢንዌግረከ ፡ እላ ፡ በእንተ ፡ ጽርፈትከ ፡ እንዲል ፡ ተሉ ፡ ርቤል ፡ ያጥንታችንን ፡ ፍላጭ ፡ የሥጋችንን ፡ ቁራጭ ፡ ተዉ ፡ ብሉ ፡ እስጥዲችቀል ፡ ታላቅ ፡ ወንድም ፡ ስለ ፡ አባት ፡ ነውና ፡ እንድም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ በባላ ፡ ምክንያት ፡ ካባቱ ፡ ከያዕቆብ ፡ ተጣልቶ ፡ ነበርና ፡ መታረቅያ ፡ ይሆነኛል ፡ ብሎ ፡ ፴፯ ፡ ፵፩ ፡ ፳፱ ፡ ዓዘቅት ፡ ሐዲስ ፡ ይላታል ፡ ወሀ ፡ ያልወጣላት ፡ ጉድጓድ ፡ እለች ፡ እሱን ፡ ከዚያ ፡ አግብተው ፡ ይመገቡ ፡ ዝሙር ፡ ከብት ፡ የሚመልሱ ፡ በተራ ፡ ነው ፡ የርቤል ፡ ተራ ፡ ደርሶት ፡ ሊመልስ ፡ ሄዶ ፡ እስማኤላውያን ፡ መጡ ፡ ይሁዳ ፡ የይሁዳ ፡ ፈታውራሪ ፡ ነውና ፡ ወንድማችንን ፡ ገድለን ፡ ብንቀብረው ፡ ምን ፡ ይረባናል ፡ ይጠቅመናል ፡ እንሽጠው ፡ አላቸው ፡ ወሚጥዎ ፡ ለሾ፡ ዲናር ፡ ያላል ፡ ለኻያ ፡ ወቄት ፡ ሸጠውታል ፡ በግብፅ ፡ ሠላሳ ፡ ያላልላ ፡ ቢሉ ፡ የሚያን ፡ ያግኑት ፡ ነው ፡ በከነዓን ፡ ኻያው ፡ በግብፅ ፡ ሠላሳ ፡ ይሆናል ፡ እንድም ፡ ጲጥፋራ ፡ በሠላሳ ፡ ወቄት ፡ ገዝቶታል ፡ ኻያውን ፡ ሰጥቶ ፡ በሥሩን ፡ ከሹመ ፡ ተቀበሉ ፡ ብዒቸው ፡ ኼሙ ፡ አስቀርቶባቸዋል ፡ ርቤል ፡ መጥቶ ፡ ምነው ፡ እንዲህ ፡ አደረጋችሁ ፡ ያጥንታችንን ፡ ፍላጭ ፡ የሥጋችንን ፡ ቁራጭ ፡ ወንድማችንን ፡ አላቸው ፡ ጠቦት ፡ አርደው ፡ ልብሱን ፡ በደም ፡ ጠምተው ፡ ርኢ ፡ ለእመ ፡ ከዳኑ ፡ ውእቱ ፡ ለወልድከ ፡ ያን ፡ ብላቴና ፡ ወደኛ ፡ ሰደኸው ፡ ኑሯልን ፡ አውሬም ፡ በልቶት ፡ እንደሆነ ፡ ልብሱን ፡ እንዲህ ፡ ሁኖ ፡ አገኘነው ፡ ብለው ፡ ላኩበት ፡ እያለቀሰ ፡ ዓይኑ ፡ ጠፍቷል ፡ ፴፯ ፡ ፶፬ ፡ ፩ ፡ ፳፱ ። የሴፍ ፡ የመለኮት ፡ ልብስ ፡ የትስብዕት ፡ ደም ፡ ከልብሱ ፡ እንጂ ፡ ከዮሴፍ ፡ እንዳልደረሰ ፡ ሕማም ፡ ሞትም ፡ ከትስብዕት ፡ እንጂ ፡ ከመለኮት ፡ ላለመድረሱ ፡ ምሳሌ ። ጲጥፋራ ፡ በዮሴፍ ፡ ምክንያት ፡ ከበረ ፡ አበጻራ ፡ በታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ከበረ ፡ ጲጥፋራ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ከመጣ ፡ ገንዘቤ ፡ በዛ ፡ ብሎ ፡ የሚያ ፡ ንብረቱን ፡ የቤት ፡ ጉስጉሱን ፡ ሰጥቼሃለሁ ፡



አለው ፡ ወወደየት ፡ እስያንገቲሃ ፡ ብእሲተ ፡ እግዚኡ ፡ እንዲል ፡ ሲወጣ ፡ ሲገባ ፡ እያየች ፡ ዓይኗን ፡ ጣለችበት ፡ ከዕለታት ፡ ባንዳቸው ፡ ነዓ ፡ ስከብ ፡ ምስሌየ ፡ ብላ ፡ ገልጣ ፡ ነገረችው ፡ ጊታዬ ፡ በገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ ሲያሠለጥነኝ ፡ ባንቺ ፡ ብቻ ፡ አላሠለጠነኝም ፡ አላት ። ከዕለታት ፡ ባንዱ ፡ ባዒ ፡ ሊተገባሩ ፡ ወጥቶ ፡ ላለ ፡ ከዕቃ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ገምጂ ፡ ሲያናፍስ ፡ ዕቃ ፡ ሲቆጥር ፡ አንተ ፡ ባሪያ ፡ ዛሬ ፡ ገና ፡ አለቀቅሁኸም ፡ ብላ ፡ ተራምዳ ፡ ያዘችው ፡ ነጥቄ ፡ እሄዳለሁ ፡ ቢል ፡ ቀሚሱ ፡ ከወደ ፡ ኋላው ፡ ተቀደደበት ፡ ጨሌንካውን ፡ ላንቃ ፡ ሰበረበት ፡ ብታፍር ፡ ቀሚዷን ፡ ከወደ ፡ ፊቷ ፡ ቀደደች ፡ ሙሽች ፡ መጥተው ፡ ምን ፡ ሆንሽ ፡ አሏት ፡ ሰው ፡ ባሪያ ፡ ሲገዛ ፡ እፍንጫ ፡ ጉራዳ ፡ ፊተ ፡ ጨምዳዳ ፡ ራሰ ፡ ቆርዳዳ ፡ ይገዛል ፡ ቢሉት ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ባሪያ ፡ ገዝቶ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ አይሆንም ፡ ብለው ፡ ቀሚሷን ፡ ቀድዶት ፡ ሄዶ ፡ አለቻቸው ፡ አሕዛብ ፡ ፍርድ ፡ ጠንቃቆች ፡ ናቸውና ፡ ፈታድስ ፡ ያንቺ ፡ ይመስላል ፡ ያጣ ፡ ቢሆን ፡ የሱ ፡ በፊቱ ፡ ያንቺ ፡ በኋላሽ ፡ ባልተቀደደም ፡ ነበርን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይስ ፡ ይበልሽ ፡ ብለው ፡ እስሩት ፡ ባዒ ፡ መጣ ፡ ለቅናት ፡ የለው ፡ ፅናት ፡ እንዲሉ ፡ አያደርገም ፡ አላለም ፡ ከፈርዖን ፡ እስረኞች ፡ ወስዶ ፡ ያረበው ፡ ኸሙ ፡ እስረኞች ፡ እንተ ፡ ባልነቸው ፡ ይውጡ ፡ ይግቡ ፡ ብሎታል ፡ ያለኸመት ፡ እላይረም ፡ ወእጎጸረ ፡ ዉጉበሉ ፡ ሚመት ፡ ወእርሰየ ፡ ገዞ ፡ እንዲል ፡ ፴፱ ፡ ፵፩ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ፡ የፈርዖን ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊ ፡ ሥጋ ፡ መልካሚ ፡ ታሥረው ፡ ነበረ ፡ ሕልም ፡ አይተው ፡ የሚተረጉምላቸው ፡ አጥተው ፡ አዝነው ፡ ሳሉ ፡ ፀሐይ ፡ ሲሞቅ ፡ ቆይቶ ፡ ገብቶ ፡ ምነው ፡ አዝናችኋል ፡ አላቸው ፡ በሠሩ ፡ ለልብ ፡ ብሩህ ፡ ገጽ ፡ ወእምኩመ ፡ ይቱከዝ ፡ ልብ ፡ ይደምን ፡ ገጽ ፡ እንዲል ፡ ሕልም ፡ አይተን ፡ የሚተረጉምልን ፡ አጥተን ፡ አሉት ፡ ሕልምን ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጸለት ፡ ሰው ፡ ይተረጉመዋል ፡ ንገሩኝ ፡ ብሎ ፡ በነገሩ ፡ ሃይማኖቱን ፡ አመለከታቸው ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊው ፡ ሦስት ፡ የወይን ፡ ዘለላ ፡ በጊታዬ ፡ ፅዋ ፡ አፅርቼ ፡ ለጊታዬ ፡ ስሰጠው ፡ አየሁ ፡ አለው ፡ ሦስት ፡ የወይን ፡ ዘለላ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ምሳሌ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ከሹመትህ ፡ ትመለሳለህ ፡ አለው ፡ ለገዛ ፡ ሲተረጉምለት ፡ ሰምቶ ፡ ሥጋ ፡ መልከኛውም ፡ በሦስት ፡ እንቅብ ፡ (መሶብ) ፡ እያረርቢ ፡ ይዤ ፡

ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ስገባ ፡ አዕዋፍ ፡ ከላዩ ፡ ገልብጠው ፡ ሲመገቡት ፡ አየሁ ፡ አለው ፡ ሦ ስት ፡ እንቅብ ፡ ሦስት ፡ (መሶብ) ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ምሳሌ ፡ እንቅብ ፡ መሥፈሪያ ፡ እንደሆነ ፡ ዕለትም ፡ የዕድሜ ፡ መሥፈሪያ ፡ ነው ።

እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ፈርዖን ፡ ይሰቅልሃል ፡ ንጉሥ ፡ የሰቀለውን ፡ አንበሳ ፡ የሰበረውን ፡ የሚነካው ፡ የለምና ፡ አዕዋፍ ፡ ይበሉሃል ፡ ብሎ ፡ ተረጐመበት ፡ ለገዢ ፡ ለተ ረጐመለት ፡ ለጸጅ ፡ አሳላፊው ፡ ቀድሞም ፡ በግፍዕ ፡ ተሸሜለሁ ፡ ዛሬም ፡ በግፍ ፡ ታሥሬያለሁና ፡ አዘክረኒ ፡ ቅድመ ፡ እግዚእከ ፡ ፈርዖን ፡ አለው ፡ ይህም ፡ ለዮ ሴፍ ፡ ዕዳ ፡ ሆኖበት ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ እንዲታሠር ፡ አድርጎ ታል ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ፈር ዖን ፡ በዓል ፡ አደረገ ፡ አሕዛብ ፡ የተወለዱበትን ፡ ቀን ፡ ያከብራሉ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ተወልደን ፡ ከዚህ ፡ ማዕርግ ፡ የደረስንበት ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ከጠባብ ፡ ወደ ፡ ሰፊ ፡ የወጣንበት ፡ ሲሉ ፡ መኳ ንንቱ ፡ ሁሉን ፡ አክብረው ፡ እጅ ፡ ሊነሱ ፡ ከፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ገቡ ፡ እንደምን ፡ ሁናችሁ ፡ ሮላ ችሁ ፡ አላቸው ፡ መልካም ፡ ውሰ ናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የቀድሞውን ፡ ጸጅ ፡ አሳላፊ ፡ የዛሬውን ፡ ሥጋ ፡ መልከኛ ፡ ለሹመት ፡ የቀድሞውን ፡ ሥጋ ፡ መልከኛ ፡ የዛሬውን ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊ ፡ ለቅጣት ፡ ብለናል ፡ እሉት ፡ ያንን ፡ ወደሹመት ፡ መለሰው ፡ ያም ፡ ተቀጣ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ይዘነጋዋል ፡ ዘፍ ፡ ፵ ፡ ፩-፳፫ ፡ በሁለ ተኛው ፡ ዓመት ፡ ፈርዖን ፡ ሕል ም ፡ አየ ፤ ከባሕር ፡ ዳር ፡ ያለሁ ፡ ይመስለዋል ፡ ሰባት ፡ የወፈሩ ፡ የሰቡ ፡ ላሞች ፡ ወጥተው ፡ ሲሰ ማሩ ፡ ሰባት ፡ የከሱ ፡ ላሞች ፡ ወጥተው ፡ ውጠዋቸው ፡ ያልቀ መሱ ፡ ሲመስሉ ፡ ሁለተኛ ፡ ሰባ ት ፡ ያፈሩ ፡ የለመለሙ ፡ እሸቶች ፡ ሲወጡ ፡ ሰባት ፡ የደረቁ ፡ የሰ ለቱ ፡ እሸቶች ፡ ወጥተው ፡ ውጠ ዋቸው ፡ ያልቀመሱ ፡ ሲመስሉ ፡ አየ ፤ ወእእመረ ፡ ፈርዖን ፡ ከመ ፡ ሕልም ፡ ውእቱ ፡ ይላል ፤ ሕልም ፡ እንደሆነ ፡ ዐወቀ ፤ ሕልምማ ፡ እንግዲያ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ምሳሌ ፡ ያለው ፡ ደግ ፡ ሕልም ፡ እንደሆነ ፡ ዐወቀ ፡ ወአ ስተጋብአሙ ፡ ለጠበብቱ ፡ ጠበ ብቱን ፡ ጠርቶ ፡ ተርጉሙልኝ ፡ አላቸው ፡ ወስዕኑ ፡ ፈከሮቶ ፡ መተ ርጐም ፡ ተሳናቸው ፤ ጠጅ ፡ አሳ ላፊው ፡ እዜከራ ፡ ለዘቀደመት ፡ ኃጢአትየ ፡ ዝንጋዔየ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እኔና ፡ ባልንጀራዬ ፡ ታሥ



ረን ፡ ሳለን ፡ ሁለታችንም ፡ ሕል ም ፡ አየን ፡ ለኔ ፡ ተረጐመልኝ ፡ ሆነልኝ ፡ በሱም ፡ ተረጐመበት ፡ ሆነበት ፤ አሁንም ፡ ከጴጥፋራ ፡ ባሪያ ፡ በቀር ፡ ሕልምህን ፡ የሚ ተረጉምልህ ፡ የለም ፡ አለው ። ዘፍ ፡ ፵፩ ፡ ፩-፲፫ ፡

፳ ፡ ፈነወ ፡ ንጉሥ ፡ ወፈትሖ ።

ንጉሡ ፡ ብላቴና ፡ ልኮ ፡ ፈታው ፡ ማለት ፡ ራሱን ፡ ላጭታችሁ ፡ ገላውን ፡ አጥባችሁ ፡ ጌጠኛ ፡ ልብስ ፡ አልብሳችሁ ፡ አምጡ ልኝ ፡ አለ ፤ አመጡት ፡ ሄዶ ፡ እጅ ፡ ነሣ ፡ ሕልም ፡ አይቼ ፡ የሚተረጉምልኝ ፡ አጥቼ ፡ መተ ርጐመ ፡ ሕልም ፡ ነህ ፡ ቢሉኝ ፡ ትተረጉምልኝ ፡ ብዬ ፡ አለው ፤ ሕልምን ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጸለት ፡ ይተረጉመዋል ፡ ንገ ረኝ ፡ ልተርጉምልህ ፡ ብሎ ፡ ሃይ ማኖቱን ፡ በነገሩ ፡ ያመለክተዋል ፤ ነገረው ፤ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ሕልሙ ፡ ለእግዚእየ ፡ ሕልሙ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ መደጋገሙ ፡ ምሳሌ ፡ ያለ ው ፡ ደግ ፡ ሕልም ፡ ነው ፡ ለማ ለት ፡ ሰባት ፡ የሰቡ ፡ አልሕምት ፡ የለመለሙ ፡ ያፈሩ ፡ ሰዊት ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የሰባቱ ፡ ዘመን ፡ ጥጋብ ፡ ምሳሌ ፡ ሰባት ፡ የከሱ ፡ ላሞች ፡ ሰባት ፡ የደረቁ ፡ የሰለቱ ፡ እሸቶች ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የሰባቱ ፡ ዘመን ፡ ረኀብ ፡ ምሳሌ ፡ ውጠዋቸው ፡ ያልቀመሱ ፡ ሲመስሉ ፡ ማየትህ ፡ የሰባቱን ፡ ዓመት ፡ ጥጋብ ፡ የሚያ ዘነጋ ፡ የሰባት ፡ ዓመት ፡ ረኀብ ፡ ይሆናል ፤ የጥጋቡንም ፡ የረኀቡ ንም ፡ ማየትህ ፡ ጥጋቡም ፡ ረኀ ቡም ፡ የሚሆን ፡ ባንተ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ከወህ ፡ ዳር ፡ መሆኑ ፡ ዝናም ፡ አይዘንምላቸውም ፡ ኑሯ ቸው ፡ በመስኖ ፡ ነውና ፡ አን ድም ፡ ጥጋብም ፡ ረኀብም ፡ በመ ስኖ ፡ ነውና ። ቢገኝ ፡ ጥጋብ ፡ ቢታጣ ፡ ረኀብ ፡ ለዚህ ፡ ምን ፡ ይበጀኛል ፡ አለው ፡ ሚም ፡ ማእ ምሪ ፡ ወለባዊ ፡ ብልህ ፡ ሰው ፡ ሹም ፡ አለው ፤ ሹመት ፡ ተካሠሰ ፡ ወእልቦ ፡ ዘይጠበብ ፡ እምኔከ ፡ ተሠየም ፡ ሊቀ ፡ ካንተ ፡ ወዲያ ፡ ዐዋቂ ፡ ማንን ፡ አገኘለሁ ፡ ተሾ ምልኝ ፡ አለው ።

ወሤሞ ፡ መልአከ ፡ አሕዛብ ።

ለአሕዛብ ፡ ገዢ ፡ አደረገው ፡ ማለት ፡ ብላቴን ፡ ጌትነትን ፡ ሾመው ። ዘፍ ፡ ፵፩ ፡ ፲፬—፵፫ ።

፳፩ ፡ ወረሰዮ ፡ እግዚአ ፡ ለቤቱ ።

በቤቱ ፡ ሁሉ ፡ አዛዥነት ፡ ሾመው፤ ኢል ፡ አብሬኤል ፡ ዐዋጅ ፡ አብ ሬል ፡ ገብር ፡ ኮነ ፡ እግዚአ ፡ ማ ለት ፡ ነው ፡ ሐቲም ፡ ቀለበቱን ፡ አድርጎ ፡ ኩፋሩን ፡ አልብሶ ፡ መያቡት ፡ በምትባል ፡ በቅሎ ፡

2014 04 17

አስቀምጦ ፡ ግብፅን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ተመርቷት ፡ ውኃል ፡ ወስመ ዮ ፡ እስፍንቶፎኒህ ፡ ከሚቴ ፡ ምሥ ጢር ፡ መዝገበ ፡ ጥበብ ፡ ሊቀ ፡ ጠቢባን ፡ ማለት ፡ ነው ። ዘፍ፡ ፵፮፡ ፵፱ ፡ ፵፰ ። ወዲያው ፡ የወርቅ ፡ የ ብር ፡ የንፍጥ ፡ ግብሩ ፡ እህል ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ፀዋጅ ፡ ነገረ ፡ የሚነቅዘውን ፡ እያስወቀጠ ፡ እ ያስፈጨ ፡ እንደ ፡ ጠብ ፡ እያሠራ፡ የማይነቅዘውን ፡ እያስወቃ ፡ እ ንደ ፡ እናርያ ፡ በንታ ፡ በንተራ ፡ በሬቅ ፡ ሰበሰበው ፡ በሰባት ፡ ዓመ ት ፡ ጥጋብ ፡ ለሰባት ፡ ዓመት ፡ ረኀብ ፡ አዘጋጀ ፡ ያዕቆብ ፡ ልጆቹ ፡ በግብፅ ፡ እህል ፡ አለ ፡ ሲሉ ፡ ሰምቻለሁና ፡ ሸምታችሁ ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ አሲዞ ፡ ሰደዳቸው ፡ ሄደው ፡ ካደ ባባይ ፡ ተቀመጡ ፡ ዮሴፍ ፡ አይ ቶ ፡ በወቃቸው ፡ ነገር ፡ ሲሰማ ፡ ሁዳድ ፡ ሲያስሆድድም ፡ ቢሉ ፡ ምንድር ፡ ናችሁ ፡ ብላችሁ ፡ ጠይቋቸው ፡ አለ ፡ ምንድር ፡ ናችሁ ፡ አሏቸው ፡ ሸማቾች ፡ ነን ፡ አሉ ፡ ሐሰታችሁ ፡ ነው ፡ ሰላ ዮች ፡ ናችሁ ፡ የከተማውን ፡ መፅ ናት ፡ አለመፅናት ፡ የሰውን ፡ መብ ዛት ፡ አለመብዛት ፡ ልትሰልሉ ፡ ነው ፡ የመጣችሁ ፡ አላቸው ። ስላይ ፡ ካንዱ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ካንዱ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ተወፃዕቶ ፡

ይመጣል ፡ እንጂ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ልጆች ፡ አንድ ፡ ሁነን ፡ እንመጣ ለንን ፡ አሉት ። አንድ ፡ ሰው ፡ ዐሥር ፡ ልጆች ፡ ይወልዳልን ፡ አላቸው ፡ አሬ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት፡ ነበርን ፡ አሉት ፡ ሁለቱ ፡ ሄት ፡ ሄደዋል ፡ አላቸው ፡ አንዱ ፡ ሕ ፃን ፡ ሁኖ ፡ ከቤት ፡ ቀርቷል ፡ አንዱን ፡ አውሬ ፡ በላው ፡ ብለው ፡ አረዱት ። ፴ ፡ ፩ - ፳፬ ፡ ፴፩ ፡ ፳፫ - ፳፮ ። ከቤት ፡ ያለውን ፡ ወንድማችሁን ፡ ያመጣችሁ ፡ እንደሆነ ፡ እየወጣ ችሁ ፡ እየገባችሁ ፡ ትሸምታላ ችሁ ፡ ያለዚያ ፡ ግን ፡ አይሆን ላችሁም ፡ ብሎ ፡ ስምዖንን ፡ መያ ዣ ፡ አድርጎ ፡ አስቀረው ፡ እስመ ፡ ፀንዓ ፡ ቦቱ ፡ በቀዳሚ ፡ ተውይ ይጠቱ ፡ ይላል ፡ የማይገባ ፡ ነገር ፡ ተናግሮት ፡ ነበርና ፡ መለየቱን ፡ ይቅመሰው ፡ ብሎ ፡ ለዮሴፍስ ፡ ይህ ፡ ቂም ፡ ነገሩ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ሰውነቱ ፡ ተጎድቶ ፡ ነበ ርና ፡ መውጣት ፡ መውረዱን ፡ ይረፈው ፡ ብሎ ። ሹሙ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ወርቅ ፡ ይዘው ፡ መጥተ ዋል ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፡ አትንካ ፡ እህሉን ፡ በየአይበታቸው ፡ እየመ ላህ ፡ ወርቁን ፡ በየአይበታቸው ፡ እያደረግህ ፡ ስጣቸው ፡ አለው ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ፡ ገፈራ ፡ የሚያበሉ ፡ ካንድ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ገፈራ ፡ ለማብላት ፡ አንዱ ፡



አይበቱን ፡ ቢፈታ ፡ ወርቁን ፡ አገ ኘ ፡ ሊተስ ፡ ገብአተኒ ፡ ወርቅየ ፡ አለ ፡ ሁሉም ፡ በየቤታቸው ፡ ሲ ገቡ ፡ አገኙት ። ስምዖንስ ፡ አላ ቸው ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ መያዣ ፡ አድርጎ ፡ አስቀረው ፡ አሉት ፡ በልተው ፡ ሲጨርሱ ፡ ብንያምን ፡ ካላመጣችሁ ፡ አይሆንላችሁም ፡ ብሎናልና ፡ ብንያምን ፡ ስጠን ፡ ሸምተን ፡ እናምጣ ፡ አሉት ። ዮሴፍ ፡ ኢሀሎ ፡ ስምዖን ፡ ኢሀሎ ፡ ዮሴፍን ፡ አውሬ ፡ በላው ፡ አላች ሁኝ ፡ ስምዖንን ፡ መያዣ ፡ አድር ጎ ፡ አስቀረው ፡ አላችሁኝ ፡ በማ ናችውም ፡ ምክንያት ፡ ሙቶ ፡ ቢ ቀር ፡ ወታወርድዎ ፡ ለርስዓንየ ፡ በኀዘን ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ እን ጻዘንሁ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ልታወ ርዱኝ ፡ ነው ፡ አላቸው ። ዘፍ ፡ ፵፪ ፡ ፩ - ፴፰ ። ሮቤል ፡ እኔ ፡ ይህና ፡ ባልመልሰው ፡ የኔን ፡ ልጆች ፡ ግደል ፡ አለው ፡ ያላዋቂ ፡ እነጋ ገር ፡ ይሁዳ ፡ እኔ ፡ ይህና ፡ ባልመ ልሰው ፡ ዕዳው ፡ በኔ ፡ ይሁን ፡ አለው ፡ የሱን ፡ ተቀብሎታል ፡ እመቤታችን ፡ ጌታችን ፡ በጉል በቱ ፡ ያሉ ፡ ነውና ። ከዚህም ፡ ቢሆን ፡ ረኀቡ ፡ ይገድለዋል ፡ ይዛችሁት ፡ ሂዱ ፡ ብሏቸዋል ፡ ከግብፅ ፡ መልሰው ፡ ያመጡትን ፡ ወርቅ ፡ ሌላም ፡ ያንን ፡ ያህል ፡ ወርቅ ፡ በግብፅ ፡ የሌለ ፡ በከን

ዓን ፡ ያለ ፡ ሽቱ ፡ ማር ፡ ገጹ ፡ በረ ከት ፡ አሲዞ ፡ ሰደዳቸው ፡ ሄደው ፡ ከጥንት ፡ ቦታቸው ፡ ተቀመጡ ፡ ዝኑ ፡ ውእቱ ፡ እኁክሙ ፡ ዘትብሉ፡ ናመጽአ ፡ እናመጣዋለን ፡ ያላ ችሁት ፡ ወንድማችሁ ፡ ይህ ፡ ነውን ፡ አላቸው ፡ አዎን ፡ አሉት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሀሉ ፡ ምስሌከ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ አይ ለይህ ፡ ከኔህ ፡ ከክፉዎች ፡ ጋራ ፡ የምትኖር ፡ አለው ። ድኅንኑ ፡ ዝስኩ ፡ አረጋዊ ፡ አቡክሙ ፡ አላ ቸው ፡ እወ ፡ ዳኅን ፡ አዎን ፡ ደኅና ፡ ነው ፡ አሉ ፡ ወዓዲ ፡ ሕያው ፡ ገና ፡ ከጉልበት ፡ ነውን ፡ አላቸው ፡ አዎን ፡ አሉ ፡ ቡሩክ ፡ ብእሲሁ ፡ አላቸው ፡ አባታችንን ፡ አመሰ ገነልን ፡ ብለው ፡ እጅ ፡ ነሡ ። ሹ ሙን ፡ ከፈርዖን ፡ ደርሼ ፡ እስ ክመለስ ፡ ከወንድማቸው ፡ አገና ኛቸው ፡ አለው ፡ ቀድሞ ፡ ወስ ደነው ፡ በነበረ ፡ ወርቅ ፡ ሊያግ ዙን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቀድሞ ፡ የወሰድነውን ፡ ወርቅ ፡ አምጥ ተናል ፡ ሌላም ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ይዘን ፡ መጥተናል ፡ አሉት ፡ ሠሚርየ ፡ ነሣእክዎ ፡ ጠብሼ ፡ ለዕዳ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቼዋለሁ ፡ እምላክ ፡ አቡክሙ ፡ ወሀበክሙ ፡ መድፍነ ፡ ያባታችሁ ፡ እምላክ ፡ ያልታወቀ ፡ ሸሸጎ ፡ ሰጥቷችሁ ፡ እንደሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።

2014 04 17

ገጹ ፡ በረከቱን ፡ አዘጋጁ ፡ ዮሴፍ ፡
ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ደርሶ ፡
ሲመለስ ፡ ገጹ ፡ በረከቱን ፡ አበ
ረከቱ ፡ ሦስት ፡ ማዕድ ፡ አሠራ ፡
አንዱ ፡ ለቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ አንዱ ፡
ለግብጻውያን ፡ አንዱ ፡ ለወን
ድሞቹ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ የምት
ችል ፡ ሌማት ፡ አሠርቶ ፡ እንደ ፡
ትውልዳችሁ ፡ ተቀመጡ ፡ አላ
ቸው ፡ ሮቤል ፡ በቀኙ ፡ ብንያም ፡
በግራው ፡ ተቀመጡ ፡ ወእዕበየ ፡
ክፍሎ ፡ ለብንያም ፡ ኀምስ ፡ እዴ ፡
ይላል ፡ ይራርቦ ፡ ጣለለት ፡ እንያ ፡
ሁልተኛቸው ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ግን ፡
እንግዳ ፡ ነውና ። ዘፍ ፡ ፵፫ ፡ ፩—፴፬ ።
በሌተው ፡ ጠጥተው ፡ ስድስቱ ፡
አንድ ፡ ወገን ፡ ሁለቱ ፡ አንድ ፡ ወ
ገን ፡ ሁለቱ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሁነው ፡
ይጫወታሉ ፡ ብንያም ፡ ዝም ፡
አለ ፡ ምነው ፡ አትጫወትምን ፡
ብለህ ፡ ጠይቀው ፡ አለው ፡ እኒህ ፡
ስድስቱ ፡ ያንዲት ፡ ሁለቱ ፡ ያን
ዲት ፡ ሁለቱ ፡ ያንዲት ፡ ልጆች ፡ ና
ቸው ፡ እኔም ፡ ወንድም ፡ ነበረኝ ፡ አ
ውሬ ፡ በላው ፡ አለው ። ካንድ ፡ ላይ ፡
ኮሬይ ፡ ዘብሩር ፡ ካንድ ፡ ላይ ፡ ገይብ ፡
ብሩር ፡ ይላታል ፡ በቀለበቱ ፡ ሲመታ
ት ፡ ትሰማለች ፡ ሮቤል ፡ ትላለች ፡ ሮ
ቤል ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ አለን ፡ ይላቸ
ዋል ፡ ስምዖን ፡ ትላለች ፡ ስምዖን ፡
የሚባል ፡ ሰው ፡ አለን ፡ ይላቸዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሹሙ ፡ ቀድሞ ፡
የወሰዱትን ፡ ወርቅ ፡ ሌላም ፡ ያን ፡
ያህል ፡ ጨምረው ፡ አምጥተዋል ፡
ይለዋል ፡ አትንካ ፡ እህሉን ፡ በየ
አይበታቸው ፡ እየመላህ ፡ ወር
ቁን ፡ በየአይበታቸው ፡ እያደረ
ግህ ፡ ስደዳቸው ፡ ከታናሹ ፡ ልጅ ፡
አይበት ፡ የኔን ፡ ፅዋ ፡ አግብተ
ህ ፡ እንደ ፡ ጥበብህ ፡ መልሰህ ፡
አምጣልኝ ፡ አለው ። ጥቂት ፡
እልፍ ፡ እንዳሉ ፡ ተከትሎ ፡ ለ
ምንት ፡ ሰረቀው ፡ ገይብ ፡ ዘያ
ቀሪ ፡ ቦቱ ፡ እግዚእየ ፡ የበቅንት ፡
ወረታ ፡ ክፋት ፡ ነውን ፡ ጌታዬ ፡
የሚጠጣበትን ፡ ፅዋ ፡ ለምን ፡
ሰረቃችሁ ፡ አላቸው ፡ እኛስ ፡
አልወሰድንም ፡ ከነዓን ፡ እንኳ ፡
ይዘን ፡ ሄደን ፡ የነበረውን ፡ መል
ሰን ፡ አምጥተናል ፡ አሉ ፡ የተ
ኘገበት ፡ ይሙት ፡ አሉ ፡ ሞትማ ፡
ለምን ፡ ይሞታል ፡ ባሪያ ፡ ሁኖ ፡
ይገዛ ፡ እንጂ ፡ አላቸው ፡ በሮቤል ፡
ይገርምራል ፡ ሰው ፡ ጠላቱን ፡
ሲያውቅ ፡ በወዳጁ ፡ እንዲጀም
ር ፡ ከብንያም ፡ ተገኘ ፡ ቀድሞ ፡
እናቱ ፡ ከመንገድ ፡ ሙታ ፡ የቀ
ረች ፡ ከሷ ፡ የተወለደ ፡ ይህ ፡ እን
ዲህ ፡ አደረገን ፡ አሉ ፡ ዘፍ ፡ ፵፬ ፡ ፩ ።
ሮቤል ፡ እኔ ፡ ስለሱ ፡ ልገዛ ፡
እሱን ፡ አስናብትልኝ ፡ አለው ፡
የተገኘበትን ፡ ትቼ ፡ ያልተገኘ
በትን ፡ አለው ፡ ዮሴፍ ፡ እንዲህ ፡



ማድረጉ ፡ በቀደመ ፡ ከፋታቸው ፡
ያሉ ፡ እንደሆን ፡ ጥለውት ፡ ይሄ
ዱሉ ፡ ብሎ ፡ ሊሰልላቸው ፡ ነው ፡
የተገኘበትን ፡ አምጣ ፡ ብልህ ፡
እሊህን ፡ ለምን ፡ አመጣኻቸው ፡
አለው ። ይሁዳ ፡ አባቴን ፡ እን
ዲህ ፡ ሲል ፡ ስምቼዋለሁ ፡ አባቴ ፡
ሲሞት ፡ አላይም ፡ እኔ ፡ ስለሱ ፡
ልገዛ ፡ እሱን ፡ አስናብትልኝ ፡
አለው ፡ የተገኘበትን ፡ ትቼ ፡
ያልተገኘበትን ፡ አልሻም ፡ አለ
ው ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የወንድማችን ፡
ግፍዕ ፡ አይደለምን ፡ ያጥንታች
ነን ፡ ፍላጭ ፡ የሥጋችነን ፡ ቍ
ራጭ ፡ ወንድማችነን ፡ ሸጠነ
ው ፡ ይባባሉ ፡ ዠመሩ ፡ መተር
ጉም ፡ እንዳለ ፡ ባያውቁ ፡ እን
ድም ፡ መተርጉም ፡ ዮሴፍ ፡ እን
ዳለ ፡ ባያውቁ ፡ ዘፍ ፡ ፵፬ ፡ ፩ ፡ ፴፬ ።
ከቤት ፡ ይዟቸው ፡ ገብቶ ፡ እኔ ፡
ውእቱ ፡ ዮሴፍ ፡ እኁክሙ ፡ ዘሜ
ጥክሙኒ ፡ አላቸው ፡ ደነገጡ ፡
አይዟችሁ ፡ አትደንግጡ ፡ እና
ንተ ፡ ለክፋት ፡ አድርጋችሁት ፡
ነበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡
ለበጎ ፡ ነው ፡ ያደረገው ፡ በዘመነ ፡
ረኃብ ፡ ልመግባችሁ ፡ እኔ ፡ ባል
ኖር ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከሄት ፡ በተ
ገኘ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ለወንድሞቹ ፡
ሁለት ፡ ሁለት ፡ ልብስ ፡ ለብን
ያም ፡ አምስት ፡ ልብስ ፡ ሦስት ፡
መቶ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ላባቱም ፡

ይህን ፡ ያህል ፡ የሚመጣበትን ፡
ባሥር ፡ ወቄት ፡ የተገዛ ፡ ሥረ
ገላ ፡ ፲ቱ ፡ እብትለ ፡ ወ፲ቱ ፡ አሕ
ዱግ ፡ የጓዝ ፡ መጫኛ ፡ ዐሥር ፡
በቅሎ ፡ ዐሥር ፡ አህያ ፡ ልኮለታ
ል ፡ ከብርየ ፡ በብሔረ ፡ ባዕድ ፡
በባዕድ ፡ አገር ፡ ያገኘሁትን ፡
ክብሬን ፡ ላባቴ ፡ ንገሩት ። አመ
ላልሼ ፡ እንዳልመግብህ ፡ ከሰ
ባቱ ፡ ዓመት ፡ ረኀብ ፡ ሁለት ፡
ዓመት ፡ ተነሥቶለታል ፡ አም
ስት ፡ ዓመት ፡ ቀርቶለታል ፡ ብላ
ችሁ ፡ ይዛችሁልኝ ፡ ኑ ፡ አንተ ፡
ሸጠኸው ፡ አንተ ፡ ሸጠኸው ፡ እያ
ላችሁ ፡ አትጣሉ ፡ እላንት ፡ ለክ
ፋት ፡ ብታደርጉት ፡ እግዚአብሔር ፡
ለበጎ ፡ ነው ፡ ያደረገው ፡ በዘመነ ፡
ረኃብ ፡ ልመግባችሁ ፡ እኔ ፡ ባል
ኖር ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ወይፈት ፡ ይገኝ ፡
ነበር ፡ ብሏቸዋል ።

ወአኮነኒ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ጥሪቱ ።

በገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ አሠለጠነው ፡
በጅሮንድነት ፡ ሾመው ፡ ወእ
ንሰስወ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ይወስ ፡
ግብፅ ፡ ይላል ፡ ግብፅን ፡ ዞሮ ፡
ተመርቷታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

፳፪ ፡ ከመ ፡ ይገሥፆሙ ፡ ለመላእክቲሁ ፡
ከማሁ ።

እለቆቹን ፡ ይሠራቸው ፡ ይቀጻ
ቸው ፡ ዘንድ ፡ (ከማሁ) ፡ እሱ ፡
የተቀጸ ፡ የተሠራ ፡ እንደሆን ፡

2014 04 17

እንድም ፡ እንደ ፡ ንጉሡ ፡ እንደ ፡ ፈርዖን ፡ ሁና ።

ወከመ ፡ ያየብቡመ ፡ ለሊ ፡ ታውንቲሆሙ ፡ ከማሁ ።

ሥዩማኑን ፡ ያራቅቃቸው ፡ ዘን ድ ፡ (ከማሁ) ፡ እሱ ፡ የተራቀቀ ፡ እንደሆን ፡ እንድም ፡ እንደ ፡ ፈር ዖን ፡ ሁና ።

፹፫ ፡ ወቦአ ፡ እስራኤል ፡ ብሔረ ፡ ግብፅ ።

እስራኤል ፡ ግብፅ ፡ ገባ ።

ወያዕቆብኒ ፡ ኀደረ ፡ ምድረ ፡ ካም ።

እስራኤል ፡ ያለውን ፡ ያዕቆብ ፡ ቦአ ፡ ያለውን ፡ ኃደረ ፡ ብሔረ ፡ ግብፅ ፡ ያለውን ፡ ምድረ ፡ ካም ፡ ብሎ ፡ ደገመው ፡ ያዕቆብም ፡ በ ካም ፡ ሰፈ ፡ አደረ ። ዘፍ ፡ ፵፯ ፡ ፩ ፡ ፮ ።

፹፬ ፡ ወአብዝኆሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ ፈድፋደ ።

ወገኖቹ ፡ እስራኤልን ፡ ፈጽሞ ፡ አበዛቸው ፡ አከበራቸው ።

ወአጽንዖሙ ፡ እምፀሮሙ ።

ከጠላቶቻቸው ፡ ከግብፃውያን ፡ ይልቅ ፡ እሳቸውን ፡ አጸናቸው ።

፹፭ ፡ ወሜጠ ፡ ልቦሙ ፡ ከመ ፡ ይጽልእ ፡ ሕዝቦ ።

ልቡሙ ፡ ለግብፅ ፡ ነው ፡ ወገኖቹ ፡ እስራኤልን ፡ ይጠሉ ፡ ዘንድ ፡ የግ ብፃውያንን ፡ ልቡና ፡ መለሰ ፡ በመ ጀመሪያ ፡ ፈርዖን ፡ ፍቅር ፡ ጸንቷ ል ። ዘፍ ፡ ፵፩ ፡ ፵፱ ፡ ፵፮ ።

በሁለተኛው ፡ ፈርዖን ፡ ፍቅር ፡ ተከፍሏል ። ዘፀ ፡ ፩ ፡ ፰፱ ፡ በሦስተ ኛው ፡ ፈርዖን ፡ ፀብ ፡ ፀንቷልና ። ዘፀ ፡ ፩ ፡ ፲-፲፱ ፡ እንድም ፡ ልቡሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ነው ፡ ግብፃውያ ንን ፡ ይጠሉ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤ ልን ፡ ልባቸውን ፡ መለሰ ፡ ሕ ዝቡ ፡ እሳቸው ፡ ግብፃውያን ፡ በተፈጥሮ ፡ ወገኖቹ ፡ ናቸውና ፡ ወእንግዕዶሙ ፡ ግብፃውያን ፡ ለዕብራውያን ፡ ወአዕሐብዎሙ ፡ ይላል ፡ ውጡልን ፡ ውጡልን ፡ ብለዋቸዋል ።

ወከመ ፡ የሀብልይዎሙ ፡ ለአግብርቲሁ ።

እስራኤልን ፡ ይዘርፏቸው ፡ ዘን ድ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ገንዘባቸውን ፡ ይወስዱባቸው ፡ ነበርና ፡ እንድም ፡ እስራኤል ፡ ግብፃውያንን ፡ ይዘርፏቸው ፡ ዘ ንድ ፡ በልብስ ፡ ጎስት ፡ ምክን ንያት ፡ ዘርፈዋቸዋልና ፡ እግብ ርቲሁ ፡ በተፈጥሮ ።

፹፮ ፡ ፈነወ ፡ ሙሴሃ ፡ ገብሮ ።

አገልጋዩ ፡ ባለሟሉ ፡ ሙሴን ፡ ከምድያም ፡ ላከ ።

ወአሮንሃ ፡ ኅሩዮ ።

የመረጠው ፡ ባለሟሉ ፡ አሮንንም ፡ ከሚኒኬም ፡ ላከ ።

፹፯ ፡ ወሜሙ ፡ ቃለ ፡ ትእምርት ፡ ላዕሌሆሙ ።

ለሳቸው ፡ የምልክት ፡ ቃል ፡ ገለ



ዘሠርዐ ፡ ለአብርሃም ፡ ወመሐለ ፡ ለይስሐቅ ፤



ወአቀመ ፡ ስምዐ ፡ ለያዕቆብ ፤ መዝሙር ፡ ፸፮ ።

2014 04 17





ጸላቸው ፡ ሰጣቸው ። ዘፀ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፴፬ ፡
ሙሴ ፡ ከምድያም ፡ አሮን ፡ ከሴኬም ፡
ሲመጡ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ከመንገድ ፡ ተገናኝተዋል ፡ ጌታ ፡
ሙሴን ፡ ፈንዎሙ ፡ ለሕዝ
ብየ ፡ እስራኤል ፡ ከመ ፡ ይፀመ
ዱኒ ፡ በሐቅል ፡ ብለህ ፡ ለፈር
ዖን ፡ ንገረው ፡ አለው ፡ ጎሥሥ ፡
ባዕደ ፡ ዘትልዕክ ፡ እስመ ፡ አነ ፡
ላዕላዓ ፡ ልሳን ፡ የምትልከው ፡
ሌላ ፡ ፈልግ ፡ እኔ ፡ ድዳ ፡ ጸያፍ ፡
ነኝ ፡ ከሰው ፡ ፊት ፡ አከናውኖ ፡
መናገር ፡ አይሆንልኝም ፡ አለው ።
ጸያፍ ፡ እእ ፡ የሚል ፡ ነው ፡ ዲዳ ፡
ረን ፡ ለ ፡ የሚል ፡ ነው ፡ ለሰው ፡
የሚያይበትን ፡ ዓይን ፡ የሚናገር
በትን ፡ አንደበት ፡ የሚሰማበ
ትን ፡ ገሮ ፡ የፈጠረ ፡ ማን ፡ ይመ
ስልሃል ፡ እኔ ፡ አይደለሁምን ፡
ሂድ ፡ አለው ፡ አይሆንም ፡ አ
ለው ። ወአሮን ፡ እኁከ ፡ ይኩ
ንከ ፡ አፈ ፡ እኔ ፡ ላንተ ፡ እነግር
ሃለሁ ፡ አንተ ፡ ለአሮን ፡ ንገረ
ው ፡ አሮን ፡ ለሕዝቡ ፡ ይንገር
ልህ ፡ አለው ። ማን ፡ ላከኝ ፡ ል
በል ፡ አለው ፡ አኸያ ፡ ሸራኸያ ፡
አልሻዳ ፡ ላከኝ ፡ በል ፡ አለው ፡
አኸያ ፡ ዘሀሎ ፡ ሸራኸያ ፡ ወይ
ሄሉ ፡ አልሻዳይ ፡ አምላክ ፡ ተስ
ፋ ፡ ማለት ፡ ነው ። ምን ፡ ምል
ክት ፡ ላሳየው ፡ አለው ፡ ምን ፡
ይዘሃል ፡ አለው ፡ ምንው ፡

በትር ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ያውቅ ፡
የለምን ፡ ቢሉ ፡ ማናገር ፡ ቢሻ
ው ፡ ምንተ ፡ ትሬዒ ፡ አሞፅ ፡
ምንተ ፡ ትሬዒ ፡ ኤርምያስ ፡
እንዳለው ፡ ያለ ፡ ነው ። በትር ፡
ይገርለሁ ፡ አለው ፡ ከምድር ፡
ጣላት ፡ አለው ፡ ወገደፎ ፡ ጣለው ፡
ወኮነ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ወፈርሀ ፡
ሙሴ ፡ ወጕየ ፡ ከምድር ፡ ቢጥ
ለው ፡ እባብ ፡ ሆነ ፡ ሙሴ ፡ ፈ
ርቶ ፡ ሸሸ ። ወአንሥእ ፡ በዘነቡ ፡
ኽርራቱን ፡ ይዘህ ፡ አንሣው ፡ አለ
ው ፡ ቢያነሣው ፡ ደኅና ፡ ሆነ ፡
ሁለተኛ ፡ እጅህን ፡ ከብብትህ ፡
አግብተህ ፡ አውጣው ፡ አለው ፡
አግብቶ ፡ ቢያወጣው ፡ ለምፅ ፡
ሆነ ፡ ሁለተኛ ፡ አግብተህ ፡ አው
ጣው ፡ አለው ፡ አግብቶ ፡ ቢያ
ወጣው ፡ ደኅና ፡ ሆነ ። ዘፀ ፡ ፬ ፡
፩ ፡ ፲፱ ፡ ይህን ፡ ሁለቱን ፡ አድርገህ ፡
አሳይተህ ፡ ቢሰጥ ፡ ሰጠ ፡ ያልሰ
ሰጠህ ፡ እንደሆነ ፡ ዘጠኝ ፡ መቅ
ሠፍት ፡ ዐሥረኛ ፡ ሞተ ፡ በኵር ፡
ዐሥራ ፡ አንደኛ ፡ ሥጥመት ፡
አምጣበት ፡ አለው ። ፯ ፡ ፱-፲፫ ። ሄዶ ፡
ፈንዎሙ ፡ ለሕዝብየአ ፡ እስራ
ኤል ፡ ከመ ፡ ይፀመዱኒ ፡ በሐ
ቅል ፡ ብሎሃል ፡ አለው ፡ ማን ፡
ነው ፡ አለው ፡ አኸያ ፡ ሸራኸያ ፡
አልሻዳይ ፡ አለው ፡ ምን ፡ ምል
ክት ፡ አለህ ፡ አለው ፡ በትሩን ፡
ከምድር ፡ ጣለው ፡ እባብ ፡ ሆነ ፡

ኸራቱን ፡ ይዞ ፡ ቢያነሣው ፡ ደኅና ፡ ሆነ ፤ ሁለተኛ ፡ እጁን ፡ ከብብቱ ፡ አግብቶ ፡ ቢያወጣው ፡ ለምፅ ፡ ሆነ ፡ ሁለተኛ ፡ አግብቶ ፡ ቢያወጣው ፡ ደኅና ፡ ሆነ ፡ ይህንስ ፡ የኔም ፡ ካህናት ፡ ያደርጉታል ፡ ብሎ ፡ ኢያኔስ ፡ ኢያንበሬስ ፡ የሚባሉ ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ካህናተ ፡ ጣኦት ፡ ነበሩት ፡ አስጠርቶ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ፡ ብትራቸውን ፡ ቢጥሉት ፡ እባብ ፡ ሆነ ፡ መልሰው ፡ ቢያነሡት ፡ አልሆነላቸውም ፤ እጃቸውን ፡ ከብብታቸው ፡ አግብተው ፡ ቢያወጡት ፡ ለምፅ ፡ ሆነ ፡ መልሰው ፡ አግብተው ፡ ቢያወጡት ፡ ደኅና ፡ የማይሆንላቸው ፡ ሆነ ፤ ሙሴ ፡ በትሩን ፡ ቢጥላት ፡ እባብ ፡ ሆነች ፡ የነሱን ፡ በትር ፡ ውጣ ፡ እያባረረች ፡ ሰድዳቸዋለች ፤ ወጉዩ ፡ በሥላቅ ፡ ይላል ፡ የሙሴ ፡ በትር ፡ ልትነድፈን ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ እየዘበቱ ፡ ሸሽተዋል ፤ ንጉሡንም ፡ ልትነድፈው ፡ ሄደች ። ለጊዜው ፡ አሰድዳችኋለሁ ፡ አድኑኝ ፡ አላቸው ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔርኒ ፡ ኢየአምር ፡ ወለእስራኤልኒ ፡ ኢይፌንዎ ፡ አለ ፤ ዐሥር ፡ መቅሠፍት ፡ ዐሥራ ፡ አንደኛ ፡ ሥጥመት ፡ እመጣባቸው ።

ወመንክርኒ ፡ በምድረ ፡ ካም ።

በካም ፡ ዕፃ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራቱን ፡ አደረገባቸው ።

፳፰ ፤ ፈነወ ፡ ጽልመተ ፡ ወአጽለሞሙ ።

ጨለማ ፡ አምጥቶ ፡ አጨለማቸው ፡ ማለት ፤ ጨለማ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡ ሆነ ፡ በግብፃውያን ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ጨለማ ፡ ሁኖባቸዋል ፤ ለእስራኤል ፡ ግን ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ይፈራረቅላቸው ፡ ነበር ።

ወአምረርዎ ፡ ለቃሉ ።

ፈንዎሙእ ፡ ያለውን ፡ ቃሉን ፡ አሳዘኑት ፡ ማለት ፡ አንቀበልም ፡ አሉ ። ዘፀ ፡ ፲ ፡ ፳፩ ።

፳፱ ፤ ወረሰየ ፡ ማየሙ ፡ ደመ ።

ወሀውን ፡ ደም ፡ አደረገው ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ደም ፡ ሁኗል ፤ በእስራኤል ፡ ግን ፡ የወሀው ፡ ጽርየት ፡ አልተለወጠባቸውም ።

ወቀተለ ፡ ዓሣቲሆሙ ።

ዓሦቻቸውንም ፡ ገደለባቸው ፡ በዕምዕ ፡ እንድም ፡ ምግብ ፡ ቢለውጥባቸው ። ዘፀ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ፡ ፳፭ ።

፴ ፤ ወአውፅአት ፡ ምድሮሙ ፡ ቈርነናዓተ ።

ምድራቸው ፡ ዛጉል ፡ ልብሱ ፡ ተሳቦ ፡ ጓጉንቸር ፡ አስገኘች ።

ውስተ ፡ አብያተ ፡ ነገሥቶሙ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ በንጉሥታቱ ፡ ቤት ፡ ተደረገ ፡ አንድም ፡ በንጉሥታቱ ፡ ቤት ። ዘፀ ፡ ፰ ፡ ፭ ፡ ፲፭ ።



፴፩ ፤ ይቤ ፡ ወመጽአ ፡ አኮት ።

ሳንጃ ፡ ተርብ ፡ ተቈናጣጭ ፡ ዝን ብ ፡ ይምጣ ፡ አለ ፡ መጣ ።

ወትንንያ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድሮሙ ።

ትንኙም ፡ በምድራቸው ፡ ሁሉ ፡ ይምጣ ፡ አለ ፡ መጣ ፤ ሴቶቹም ፡ ልባልግ ፡ ወንዶቹም ፡ ሱሪ ፡ ቢያደርጉ ፡ ቀሚስ ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ ቢያጠልቁ ፡ አላዳናቸውም ፡ ን ውስ ፡ መሌሊታቸውን ፡ እየመጠመጠ ፡ ፈጅቷቸዋል ፡ ዝሰ ፡ አፅባዕተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለ ዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ዘፍ ፡ ፰ ፡ ፲፮ ፡ ፴፯ ።

፴፪ ፤ ወረሰየ ፡ ዝናሞሙ ፡ በረደ ።

ዝናማቸውንም ፡ በረድ ፡ አደረገባቸው ።

ወነደ ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ ምድሮሙ ።

በምድራቸው ፡ እሳት ፡ ዘነመ ፤ (ነደደ) ፡ በግብፅ ፡ ዝናም ፡ አይዘንምም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጊዜ ፡ ገጥሞት ፡ እሳትና ፡ በረድ ፡ እንደ ፡ ሰምና ፡ እንደ ፡ ፈትል ፡ ተጣምቶ ፡ ወርዷል ። ዘፍ ፡ ፱ ፡ ፳፪ ፡ ፴፭ ።

፴፫ ፤ ወቀተለ ፡ ወይኖሙ ፡ ወበለሶሙ ።

ወይናቸውንም ፡ በለሳቸውንም ፡ አደረቀባቸው ፡ ከላይ ፡ በረድ ፡ ያረግፋል ፡ ከታች ፡ እሳት ፡ ያቃጥላልና ።

ወቀጥቀጠ ፡ ኵሉ ፡ ዕፀወ ፡ ብሔሮሙ ።

ያገራቸውን ፡ ዕንጨት ፡ ሁሉ ፡ ጨፈጨፈው ፤ አንድም ፡ ኵሉ ፡ ብለህ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ያገራቸውን ፡ ዕንጨት ፡ ጨፈጨፈው ።

፴፬ ፤ ይቤ ፡ ወመጽአ ፡ አንበጣ ።

ጌታ ፡ አንበጣ ፡ ይምጣ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፤ መጣ ። አንድም ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ አንበጣ ፡ ይምጣ ፡ ብለው ፡ ጸለዩ ፤ መጣ ። አንበጣ ፡ የሚለው ፡ በራሪው ፡ ነው ።

ወደጎብያ ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቍ ።

ጌታ ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ኩብኩባ ፡ ይምጣ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፤ መጣ ። አንድም ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ ኩብኩባ ፡ ይምጣ ፡ ብለው ፡ ጸለዩ ፤ መጣ ። ዘፍ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭ ፡ ፳ ።

፴፭ ፤ ወበልዐ ፡ ኵሎ ፡ ፍሬ ፡ ምድሮሙ ።

የምድራቸውን ፡ አዝመራ ፡ ሁሉ ፡ በላ ፡ አንድም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የምድራቸውን ፡ አዝመራ ፡ በላ ።

ወቀዳሚ ፡ ኵሉ ፡ ተግባሮሙ ።

አስቀድሞ ፡ የደረሰ ፡ መከራቸውን ፡ በላባቸው ፡ እንደ ፡ ጠበል ፡ እንደ ፡ ፌሾ ፡ ያለውን ።

፴፮ ፤ ወቀተለ ፡ ኵሎ ፡ በኵረ ፡ ብሔሮሙ ።

ያገራቸውን ፡ በኵር ፡ ሁሉ ፡ ገደለባቸው ፡ እምበኵረ ፡ ንጉሥ ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ መን

ግሥት ፡ እስከ ፡ በዘረ ፡ እመት ፡
ዘንውዕል ፡ ታሕተ ፡ እግረ ፡ ማሕ
ረዕ ፡ እንዲል ፡፡ ዘፍ ፡ ፵፱ ፡ ፲፫ ፡፡

፵፮ ፡ ወአውፅኦሙ ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ፡፡

ወርቅ ፡ ብር ፡ ሰጥቶ ፡ አወጣቸ
ው ፡ እንድም ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡
አስጊጦ ፡ ሰደዳቸው ፡፡ ጌታ ፡ ሙ
ሴን ፡ እሑቴ ፡ ተርፈተኒ ፡ ሞተ ፡
በዘር ፡ የማመጣ ፡ ነኝና ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ሠውታችሁ ፡ ደሙን ፡
መቃን ፡ መድረኩን ፡ እርጩት ፡
ያን ፡ እያየ ፡ ሞተ ፡ በዘር ፡ እን
ዲመለስ ፡ አለው ፡ እስራኤልም ፡
ያዘዛቸውን ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አደ
ረጉ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በግብፃውያን ፡
ሞተ ፡ በዘር ፡ አመጣባቸው ፡ የግ
ብፃውያንን ፡ በዘር ፡ እያጠፋ ፡
ከእስራኤል ፡ ከተማ ፡ ደረሰ ፡
ደሙ ፡ በግዕን ፡ አይቶ ፡ ፈራ ፡
ወሰበ ፡ ርዕየ ፡ ደመ ፡ በግዕ ፡
ፈርሃ ፡ ሞተ ፡ በዘር ፡ አእመረ ፡
ወለበወ ፡ ሞተ ፡ እግዚእነ ፡ ይላ
ል ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ድል ፡
ይነሳኝ ፡ ይሆን ፡ ብሎ ፡ ተመ
ልሶ ፡ የግብፃውያንን ፡ በዘር ፡
ይፈጽም ፡ ዠመረ ፡፡ የግብዕ ፡ ሰ
ዎች ፡ ሄደው ፡ አንተ ፡ በዘር ፡
ሚስትህ ፡ ልጅህ ፡ በዘር ፡ አላ
ንት ፡ ካለቃችሁ ፡ መንግሥቱ ፡
ሬማን ፡ ይሆናል ፡ አትሰድዷቸ
ውምን ፡ ብለዋቸዋል ፡ ልጆቻ

ችሁን ፡ ትታችሁ ፡ ሂዱ ፡ አሏ
ቸው ፡ መሥዋዕት ፡ መሠዋት ፡
ከቀረ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሁኗል ፡
ልጆቻችንማ ፡ ከቀሩ ፡ በኋላ ፡ ።
መን ፡ ማንን ፡ አብነት ፡ አድር
ገው ፡ ይሠዋሉ ፡ ከብቶቻችሁን ፡
ትታችሁ ፡ ሂዱ ፡ አሏቸው ፡ ፈጣ
ሪያችን ፡ ፈረስ ፡ በቅሎ ፡ አህያ ፡
ላም ፡ በሬ ፡ በግ ፡ ፍየል ፡ ሠዉ ፡
ይለን ፡ እንደሆነ ፡ እናውቅ ፡
አሉ ፡ ውሰዱ ፡ አሏቸው ፡ በዚህም ፡
ላይ ፡ መክፈልት ፡ ሲሹ ፡ መቅ
ሠፍት ፡ እንዲሉ ፡ መሥዋዕት ፡
ስትሠዉ ፡ ንጹሕ ፡ ልብስ ፡ ለብ
ሳችሁ ፡ ሠዉ ፡ ይለናል ፡ እንዴት ፡
እናድርግ ፡ አሉት ፡ ለይትወሀስ ፡
ገብር ፡ እምእግዚኡ ፡ ወእመት ፡
እምእግዝእታ ፡ ወኃዳሪት ፡ እም
ኃደርታ ፡ ወንድ ፡ ባሪያ ፡ ከጌ
ታው ፡ ሴት ፡ ባሪያ ፡ ከመቤቷ ፡
ይዋሱ ፡ ብሎ ፡ ዐዋጅ ፡ ነገረላ
ቸው ፡ በስንት ፡ ቀን ፡ ትመለሳ
ላችሁ ፡ አላቸው ፡ ምሕዋረ ፡
ሠሉስ ፡ ዕለት ፡ ሰጊደነ ፡ ንገብዕ ፡
ኀቤክሙ ፡ አሉት ፡ በልብሰ ፡
ሕስት ፡ ምክንያት ፡ ገንዘባቸው
ን ፡ ዘርፈዋቸው ፡ ወጥተዋልና ፡
እንዲህ ፡ አለ ፡፡ ዘፍ ፡ ፲ ፡ ፳፮ ፡ ፳፱ ፡፡

ወአልቦ ፡ ደዌ ፡ ውስተ ፡ሕዝቦሙ ፡፡

በወገኖቻቸው ፡ በእስራኤል ፡ ግን ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ደዌ ፡ የለባቸውም ፡፡



፵፰ ፡ ወተፈሥሑ ፡ ግብፅ ፡ በፀዐቶሙ ፡፡

በእስራኤል ፡ መውጣት ፡ ግብፃ
ውያን ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡፡

እስመ ፡ ፈርሀምሙ ፡፡

ግብፃውያን ፡ በመቅሠፍት ፡ እንዳ
ያጠፏቸው ፡ እስራኤልን ፡ ፈርተ
ዋቸው ፡ ነበርና ፡ እንድም ፡ እስ
ራኤል ፡ ከግብፅ ፡ በመውጣታቸው ፡
ደስ ፡ አላቸው ፡፡ እስመ ፡ ፈ.ሆሆሙ ፡
ግብፃውያንን ፡ ፈርተዋቸው ፡ ነበ
ርና ፡፡

፵፱ ፡ አንጦለለ ፡ ደመና ፡ ወሠወሮሙ ፡፡

ደመና ፡ ጋርዶ ፡ ሠወራቸው ፡፡
እንድም ፡ ደመና ፡ ጋረዳቸው ፡፡
ሠወራቸውም ፡፡

እሳትኒ ፡ ከመ ፡ ያብርህ ፡ሎሙ ፡ በሌሊት ፡፡

እሳተኒ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እሳትንም ፡
በሌሊት ፡ ያበራላቸው ፡ ዘንድ ፡
አዘዘላቸው ፡፡ እንድም ፡ እሳትኒ ፡
እሳትም ፡ በሌሊት ፡ ያበራላቸው ፡
ዘንድ ፡ ታዘዘላቸው ፡፡ ከግብፅ ፡
ወጥተው ፡ በበረኃ ፡ ሳሉ ፡ ስባት ፡
ደመና ፡ ታዝዞላቸዋል ፡ አንዱ ፡
ከላይ ፡ ዋዕየ ፡ ፀሐይ ፡ እንዳያገ
ኛቸው ፡ ይጋርድላቸዋል ፡ አንዱ ፡
ከታች ፡ እሾህ ፡ እንቅፋት ፡ እን
ዳያገኛቸው ፡ ይጎዘጉዝላቸዋል ፡
አንዱ ፡ በፊት ፡ አንዱ ፡ በኋላ ፡
አንድ ፡ በቀኝ ፡ አንድ ፡ በግራ ፡
ይሆንላቸዋል ፡ ሰባተኛው ፡ የሁ

ለት ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ጐዳና ፡ ሲጠ
ርግላቸው ፡ ውሎ ፡ ማታ ፡ እንደ ፡
ዐምደ ፡ ብርሃን ፡ ሁኖ ፡ በደ
ብተራ ፡ አራት ፡ ላይ ፡ ሲያበ
ራላቸው ፡ ያድራል ፡፡ ፈርዖን ፡
በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከሰገነት ፡
ወጥቶ ፡ ቢመለከት ፡ ከተማይቱ ፡
ጫ ፡ ብላ ፡ አይቶ ፡ ወይኔ ፡ ወይ ፡
ከገንዘቤ ፡ ወይ ፡ ከባሮቼ ፡ ሳል
ሆን ፡ ቀረሁ ፡ ብሎ ፡ ጫን ፡ ታጠቅ ፡
አለ ፡፡ ሠራዊቱን ፡ አስከትቶ
ገሥግሶ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ የተጓዙ
ትን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ደረሰባቸው ፡፡
ወሰሰለ ፡ ደመና ፡ እምቅድሜሆ
ሙ ፡ ወኃለፈ ፡ እንተ ፡ ድኅሬ
ሆሙ ፡ ይላል ፡ መንገድ ፡ ጠ
ራጊ ፡ ደመና ፡ ሂዶ ፡ ተጋርዶላ
ቸው ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ እየተሰ
ማሙ ፡ ባንድ ፡ ችካል ፡ ከብታቸ
ውን ፡ እያሠሩ ፡ ሳይገናኙ ፡ ተጉ
ዘዋል ፡፡ ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ፡፡

፶ ፡ ሰአሉ ፡ ወመጽአ ፡ ፍርፍርት ፡፡

ሥጋ ፡ ለመኑ ፡ ድርጭት ፡ የባ
ሕር ፡ ዶሮ ፡ መልኳ ፡ ከሻዋ ፡
ውስጢ ፡ ሥብ ፡ ነው ፡ መጣላ
ቸው ፡ (ታዘዘላቸው) ፡፡

ወአጽገቦሙ ፡ ኅብስተ ፡ ሰማይ ፡፡

ከሰማይ ፡ የወረደውን ፡ የተገኘ
ውን ፡ ኅብስት ፡ አብልቶ ፡ አጠ
ገባቸው ፡፡ ዘፀ ፡ ፲፮ ፡ ፲፫ ፡፡

2014 04 17

፵፩ ፤ አንቅዐ ፡ ኰኵሐ ፡ ወአሐውዘ ፡ ማየ ።

ወሀ ፡ ከጭንጫ ፡ አፈለቀላቸው ።

ወሖሩ ፡ ውስተ ፡ አፍላገ ፡ በድው ።

ወንዝ ፡ ለወንዝ ፡ ወደ ፡ በረኃ ፡ ሄዱ ፤ አንድም ፡ እምአፍላግ ፡ በድወ ፡ ወንዙን ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ በረኃ ፡ ሄዱ ፤ አንድም ፡ ውስተ ፡ አፍላግ ፡ በድወ ፡ በወንዙ ፡ ወደ ፡ በረኃ ፡ ሄዱ ።

፵፪ ፤ እስመ ፡ ተዘከረ ፡ ቃሎ ፡ ቅዱስ ፡ ዘነበበ ፡ አብርሃም ፡ ገብሩ ።

ዘምስለ ፡ አብርሃም ፡ ሲል ፡ ነው ። ከባለሟሉ ፡ ከገልጋዩ ፡ ከአብርሃም ፡ ጋራ ፡ የተማማለውን ፡ ፅኑ ፡ መሐላውን ፡ አስቦአልና ፤ አሁን ፡ ዘንግቶት ፡ ኑሮ ፡ አሰበው ፡ ማለት ፡ አይደለም ፤ አደረገው ፡ ፈጸመው ፡ ሲል ፡ ነው ። ዘፀ፪፡፳፬ ።

፵፫ ፤ ወአውጽኦሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ በትፍሥሕት ።

ወገኖቹ ፡ እስራኤልን ፡ ደስ ፡ እሰኝቶ ፡ ከግብፅ ፡ አወጣቸው ።

ወለኅሩያኒሁ ፡ በሐሤት ።

ለክህነት ፡ ለመንግሥት ፡ የመረጣቸው ፡ እስራኤልን ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ አወጣቸው ።

፵፬ ፤ ወወሀቦሙ ፡ በሐውርተ ፡ አሕዛብ ።

የአሕዛብን ፡ አገር ፡ ሰጣቸው ።

ወወረሱ ፡ ፃማ ፡ ባዕድ ።

ከእምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሌዩ ፡ የሆኑ ፡ አሕዛብ ፡ የደከሙበትን ፡ ወረሱ ፡ ማለት ፤ የታነፀ ፡ ግምባቸውን ፡ የደረሰ ፡ መከራቸውን ፡ አወረሳቸው ። ዳን ፡ ፲፩፡፳፭ ።

፵፭ ፤ ከመ ፡ ይዕቀቡ ፡ ሕጎ ።

እንዲህም ፡ ማድረጉ ፡ ዘጠኙን ፡ ሕገጋት ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ወይኅሥሡ ፡ ሥርዓቶ ።

ይኅሥሡም ፡ ይላል ፤ ሕጉን ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፡ ማለት ፡ ኢታምልክን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ሕዝ ፡ ፲፩ ፡ ፳ ።

## መዝሙር ፡ ፻፮ ።

ሃሌ ፡ ሉያ ።

ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ ዓለም ፡ እሳልፎ ፡ የሚኖር ።

፩ ፤ ግነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ኄር ። ዕዝ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ ፤ ቸር ፡ ነውና ፡ ቸር ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ። መዝ ፡ ፻፭ ፡ ፩ ። ፻፲፯ ፡ ፩ ። ፻፴፭ ፡ ፩ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፡ ስለሆነ ፤ አንድም ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ፡ ስለሆነ ።



፪ ፤ መኑ ፡ ይነግር ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ።

ይገብር ፡ ይቀድማል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕጉን ፡ ለራሱ ፡ የሚሠራ ።

ወይገብር ፡ ከመ ፡ ይስማዕ ፡ ኵሎ ፡ ስብሐቲሁ ።

ይነግር ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ለሌላው ፡ የሚያስተምር ፡ ማን ፡ ነው ፤ (ከመ ፡ ይስማዕ) ፡ ንዑ ፡ ኀቤየ ፡ ያለውን ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፤ አንድም ፡ ኃይልና ፡ ስብሐት ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ተአምራቱን ፡ የሚያስተምር ፡ ማን ፡ ነው ፡ (ከመ ፡ ይስማዕ) ፡ የሚያስተምረው ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ እንዲሰማ ፡ አድርጎ ፡ የሚያስተምር ፡ ማን ፡ ነው ።

፫ ፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ የዓቅቡ ፡ ፍትሐ ።

ፍርድ ፡ የሚጠነቅቁ ፡ ሕግ ፡ የሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

ወይገብሩ ፡ ጽድቀ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ሁል ፡ ጊዜ ፡ እውነተኛውን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ማለት ፡ ቸርነትን ፡ ለሰው ፡ የሚያደርጉ ።

፬ ፤ ተዘከረነ ፡ እግዚኦ ፡ በሣህልከ ፡ ሕዝብከ ።

ተዘከረነ ፡ ካለ ፡ ለሕዝብከ ፡ ሕዝብከ ፡ ካለ ፡ ተዘከር ፡ ባለ ፡ በቀና ፡ ነበር ፡ ልማደ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤ አቤቱ ፡ እኛን ፡ ወገኖችህን ፡ በቸርነትህ ፡ አስበን ።

ወተሣሃለነ ፡ በአድኅኖትከ ።

በትድግናህ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

፭ ፤ ከመ ፡ ንርአይ ፡ ሠናይቶሙ ፡ ለኅሩያኒከ ።

የነቢያት ፡ የካህናትን ፡ ተድላ ፡ ደስታቸውን ፡ እናይ ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ንትፈሣሕ ፡ በፍሥሓ ፡ ሕዝብከ ።

በወገኖችህ ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ንክበር ፡ ምስለ ፡ ርስትከ ።

ርስትህ ፡ ጕልትህ ፡ ከሚሆኑ ፡ ከነቢያት ፡ ከካህናት ፡ ጋራ ፡ እንከብር ፡ ዘንድ ፡ አንድም ፡ (ከመ ፡ ንርአይ) ፡ የሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እናይ ፡ ዘንድ ። (ወከመ ፡ ንትፈሣሕ) ፡ በሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡ (ወከመ ፡ ንክበር) ፡ ርስትህ ፡ ጕልትህ ፡ ከሚሆኑ ፡ ከሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ከብረን ፡ ገንነን ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ ይላሉ ፡ ዐሥሩ ፡ ነገድ ።

፮ ፤ አበስነ ፡ ምስለ ፡ አበዊነ ።

ትሩፍ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ የመጣብህ ፡ ብትበድል ፡ አይደለምን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ ብንበድልም ፡ ከአባቶቻችን ፡ ጋራ ፡ እንዳባቶቻችን ፡ በደልን፡ ኢሳ ፡ ፷፫ ፡ ፷፮ ፡ ኤር ፡ ፲፬ ፡ ፳ ።

2014 04 17

ዓመፅነ ፡ ወጌገይነ ።

ፈጽመን ፡ በደልን ።

፯ ፡ ወአበዊነ ፡ በብሔረ ፡ ግብፅ ፡ ኢያእመሩ ፡ መንክረከ ።

አባቶቻችንም ፡ በግብፅ ፡ ሳሉ ፡ ያደረግህላቸውን ፡ ተአምራት ፡ አላወቁም ፡ ነበር ፤ በኛ ፡ ብርቱ ፡ ድንቁ ፡ ምንድን ፡ ነው ። አሁን ፡ ያባቶቻቸውን ፡ ኃጢአት ፡ ማዘከር ፡ አይደለም ፡ እልያ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡ ቢመለሱ ፡ ይቅር ፡ እል ሃቸው ፡ እኛም ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተን ፡ ከተመለስን ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡

ወኢተዘከሩ ፡ ብዝኃ ፡ ምሕረትከ ።

ብዙኃ ፡ ምሕረተከም ፡ ይላል ፡ የቸርነትህን ፡ ብዛት ፡ እንድም ፡ ብዙ ፡ የሚሆን ፡ ቸርነትህን ፡ አላወቁም ፡ ነበረ ።

ወአምረሩከ ፡ እመ ፡ የዓርጉ ፡ ባሕረ ፡ ኤርትራ ።

ኤርትራንም ፡ በተሻገሩ ፡ ጊዜ ፡ አሳዝነውህ ፡ ነበረ ።

፰ ፡ ወአድኀኖሙ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ።

ስምየኒ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ስላለ ፡ አዳናቸው ፡ እንጂ ፡ ማለ ት ፡ አዳንኳቸው ፡ እንጂ ፡ ሲል ፡ ነው ።

ከመ ፡ ያርእዮሙ ፡ ኃይሎ ።

ከሃሊነቱን ፡ ይገልጽላቸው ፡ ዘንድ ።

፱ ፡ ወገሠፆ ፡ ለባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ወየብሰ ።

ኤርትራን ፡ አርምሚ ፡ ተፈፀሚ ፡ ብሎ ፡ ገሠጻት ፡ (ወየብሰት) ፡ ከሦ ስት ፡ ካራት ፡ ተከፈለች ።

ወመርሖሙ ፡ በቀላይ ፡ ከመ ፡ ዘበገዳም ።

በወንዙ ፡ በየብስ ፡ እንደሚሄድ ፡ ሰው ፡ መርቶ ፡ አወጣቸው ። ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ፡ ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፲፮ ።

፲ ፡ ወአድኀኖሙ ፡ እምእደ ፡ ጸላእቶሙ ።

ከጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አዳናቸው ።

ወአንገፎሙ ፡ እምእደ ፡ ፀሮሙ ፡ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፸፩ ።

እምእደ ፡ ጸላእቶሙና ፡ እምእደ ፡ ፀሮሙ ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ከጠላ ቶቻቸው ፡ ከግብፃውያን ፡ እጅ ፡ አስለቀቃቸው ።

፲፩ ፡ ወደፈኖሙ ፡ ማይ ፡ ለእለ ፡ ሮድዎሙ ።

የተከተሏቸው ፡ የከበቧቸው ፡ ግብ ፃውያንን ፡ ግን ፡ ባሕር ፡ ቀበራ ቸው ።

ወኢተርፈ ፡ አሐዱ ፡ እምውስቴቶሙ ።

ከእስራኤል ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ አልቀረም ፡ ሁሉም ፡ ተሻገሩ ፡ እንጂ ። እንድም ፡ ከግብፃውያን ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ አልቀረም ፡ ሁ ሉም ፡ ሠጠሙ ፡ እንጂ ። ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፳፰ ፡ ፴፩ ።

፲፪ ፡ ወተአመኑ ፡ በቃሉ ።

ለጊዜው ፡ አመርሰከሙ ፡ ባለው ፡ ቃሉ ፡ አመኑ ።



ወሰብሕዎ ፡ በስብሐቲሁ ።

በጥንተ ፡ ምስጋናው ፡ አመሰገ ኑት ። ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፴፩ ።

፲፫ ፡ ወአፍጠኑ ፡ ረሲዓ ፡ ምግባሩ ።

ረሢዓ ፡ ምግባሮም ፡ ይላል ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ፈጥነው ፡ ሥራውን ፡ ዘነጉ ፤ እንድም ፡ ሥራውን ፡ መዘንጋት ፡ አፈጠኑ ።

ወኢተዓገሡ ፡ በምክሩ ።

አወጣችኋለሁ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ (ነገር) ፡ አልፀኑም ፤ በሕጉ ፡ አል ኖሩም ፡ ዘፀ ፡ ፲፮ ፡ ፳፩ ፡ ፲፯ ፡ ፪ ።

፲፬ ፡ ወፈተዉ ፡ ፍትወተ ፡ በገዳም ።

በበረኃ ፡ ሳሉ ፡ የማይገባ ፡ ተም ኔት ፡ ተመኙ ። የግብፃውያን ፡ ወንድ ፡ ወንዱ ፡ አልቆ ፡ ሴት ፡ ሴቱ ፡ ቀርቷል ፡ እንዳንዷቱን ፡ አግብተን ፡ እንኑር ፡ ብለዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ወአምረርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በበድው ።

እግዚአብሔርን ፡ በበረኃ ፡ ሳሉ ፡ አሳዘኑት ።

፲፭ ፡ ወወሀቦሙ ፡ ዘሰአሉ ።

እሱ ፡ ግን ፡ የለመኑትን ፡ ሁሉ ፡ ሰጣቸው ፡ ወሀ ፡ ቢሉ ፡ ወሀ ፡ መና ፡ ቢሉ ፡ መና ።

ፈነወ ፡ ጽጋበ ፡ ለነፍሶሙ ።

ለሰውነታቸው ፡ የሚያሻቸውን ፡ ምግብ ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ።

፲፮ ፡ ወአምዕዕዎ ፡ ለሙሴ ፡ በትዕይንት ።

ሙሴን ፡ በከተማቸው ፡ አሳዘኑት ።

ወለአሮን ፡ ቅዱሰ ፡ እግዚአብሔር ።

ፅኑዓ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክቡረ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሮንንም ፡ አሳ ዘኑት ።

፲፯ ፡ አብቀወት ፡ ምድር ፡ ወውሕጠቶ ፡ ለዳታን ።

ዳታንን ፡ ምድር ፡ ተከፍታ ፡ አሠ ጠመችው ።

ወደፈነቶሙ ፡ ለተዓይነ ፡ አቤሮን ።

አቤሮንንም ፡ ከነከተማው ፡ ከነ ሠራዊቱ ፡ አሠጠመችው ።

፲፰ ፡ ወነደ ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ ተዓይኒሆሙ ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፯ ፡ ፳፮ ፡ ፲፩ ።

በሰፈራቸው ፡ በከተማቸው ፡ እ ሳት ፡ ነደደ ፤ እንድም ፡ መቅሠ ፍት ፡ ታዘዘ ።

ወአውዐዮሙ ፡ ነበልባል ፡ ለኃጥአን ።

ኃጥአን ፡ ዳታንና ፡ አቤሮንንም ፡ የእሳት ፡ ላንቃ ፡ አቃጠላቸው ። (ታ) ፡ ደቂቀ ፡ ቆሬ ፡ ነገደ ፡ ሌዊ ፡ ዳ ታንና ፡ አቤሮን ፡ ነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ናቸው ።

ደቂቀ ፡ ቆሬ ፡ በአሮን ፡ ዳታንና ፡ አቤሮን ፡ በሙሴ ፡ እሱና ፡ ወን ድሙ ፡ መንግሥትን ፡ ክህነት ፡ እንድ ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡ ሌዊ ፡

2014 04 17

አይወልደንም ፡ እኛስ ፡ ከበዙሩ ፡ ከሮቤል ፡ ተወልደን ፡ የለምን ፡ ብለው ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡባቸው ፤ ካህናት ፡ ፈሊጥ ፡ አዋቆች ፡ ናቸውና ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የተነሣን ፡ እንደሆነ ፡ ሕዝቡ ፡ የምቀኝነት ፡ እንደሆነ ፡ ያውቁብናልና ፡ እኛ ፡ አስቀድመን ፡ ክህነታችነን ፡ በሙሴ ፡ ዳኝነት ፡ እጅ ፡ እናድርግ ፡ እላንተም ፡ በኛ ፡ ዳኝነት ፡ ምስፍናችሁን ፡ እጅ ፡ ታደርጋላችሁ ፡ ብለው ፡ ተሰብስበው ፡ ሄደው ፡ ሙሴን ፡ ሥጋ ፡ በገበታ ፡ (ነገር) ፡ በተርታ ፡ እንዲሉ ፡ ሹመት ፡ ፈንታችነን ፡ ስጠን ፡ እንሾም ፡ አሉት ፤ እሱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አግኝቶ ፡ ተሹሞታል ፡ እላንተም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አግኝታችሁ ፡ ተሾሙት ፡ አላቸው ፤ ይህማ ፡ የማድላት ፡ አማርኛ ፡ አይደለምን ፡ ዛሬስ ፡ በገዛ ፡ ሹመታችን ፡ ሱባዔ ፡ ግቡበት ፡ ይለናል ፡ ሆነ ፤ ብለው ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ የሚበዙ ፡ ካህናት ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰው ፡ ማዕጠንት ፡ አበጅተው ፡ ይዘው ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ ከደብተራ ፡ አሪት ፡ በር ፡ ቁመው ፡ ነበረ ፤ (ወሮድዎሙ ፡ ይላል) ፡ ገር ምመዋቸው ፡ ገብተው ፡ ቢያጥኑ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኗቸውን ፡ ሳይነካ ፡ እንደ ፡ ተለበለበ ፡ ግንድ ፡ አድርጓቸዋል ፤ እንደምን ፡ ላድርጋቸው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢያመለክት ፡ እሳቸውን ፡ በመጐናጸፍያቸው ፡ እያወጣህ ፡ አፍስሳቸው ፡ ዕቃው ፡ ግን ፡ ከቡር ፡ ዕቃ ፡ ነውና ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕቃ ፡ አሰራው ፡ ብሎታል ፡ ወተቀደሰ ፡ ማዕጠንታቲሆሙ ፡ በነፍሳቲሆሙ ፡ እንዲል ፡ ያዘዘውን ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፤ ዳታንና ፡ አቤሮንንም ፡ መሬት ፡ ተከፍታ ፡ አሥጥማቸዋለች ፤ ቆሬም ፡ ነገር ፡ ለማፅናት ፡ ሂዶ ፡ ነበር ፡ አብሮ ፡ ሠጥሟል ። ዘኍ ፡ ፲፮ ፡ ፩—፵ ።

፲፱ ፤ ወገብሩ ፡ ላሕመ ፡ በኮሬብ ።

በኮሬብ ፡ ስብኮ ፡ ላሕም ፡ አቆሙ ።

ወሰገዱ ፡ ለግልፎ ። ዘፀ ፡ ፴፪ ፡ ፩—፴፭ ፡ ሕዝ ፡ ፳ ፡ ፲ ።

ለተቀረጸ ፡ ለተገነፈ ፡ ጣዖት ፡ ሰገዱ ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፭ ።

፳ ፤ ወወለጡ ፡ ክብሮሙ ።

ክብራቸውን ፡ ለወጡ ።

በአምሳለ ፡ ላህም ፡ ዘይትረዐይ ፡ ሣዕረ ።

ወደ ፡ ሣር ፡ በሚሠማራ ፡ ሣርን ፡ በሚበላ ፡ ላም ፡ አምሳል ፡ ወርቅ ፡ ብራቸውን ፡ ለወጡ ። እንድም ፡ ወሊጠሙ ፡ ይላል ፤ ክብራቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለውጠው ፡ ሣርን ፡ በሚበላ ፡ ላሕም ፡ አምሳል ፡

የተሠራ ፡ ጣዖትን ፡ አመለኩ ። ኤር ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

፳፩ ፤ ወረሥዕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘአድኅኖሙ ።

ያዳናቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዘንግተው ፡ ጣዖት ፡ አመለኩ ።

ዘገብረ ፡ ዐቢያተ ፡ በግብጽ ።

በግብፅ ፡ ታላላቅ ፡ ተአምራት ፡ ያደረገ ፡ ማለት ፡ ዘጠኙን ፡ መቅሠፍት ፡ ያመጣ ፡ እሱን ፡ ረሥዕዎ ፡ ዘነጉት ። እንድም ፡ ያመጣ ፡ እሱ ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፲፫ ።

፳፪ ፤ ወመንክረ ፡ በምድረ ፡ካም ።

በካም ፡ ዕፃ ፡ ሞተ ፡ በኵርን ፡ ያደረገ ፡ እሱን ፡ ዘነጉት ። እንድም ፡ ሞተ ፡ በኵርን ፡ ያደረገ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወግሩመ ፡ በባሕረ ፡ ኤርትራ ።

በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ግሩም ፡ የሚሆን ፡ ሥጥመትን ፡ ያደረገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዘነጉት ። እንድም ፡ ግሩም ፡ የሚሆን ፡ ሥጥመትን ፡ ያደረገ ፡ እሱ ፡ ነው ።

፳፫ ፤ ወይቤ ፡ ከመ ፡ ይሥርዎሙ ።

ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡

ሶበ ፡ አኮ ፡ ሙሴ ፡ ኅሩዩ ።

እማላጁ ፡ ሙሴ ፡ ባይሆን ፡ ቆመ ፡ ማንኛ ፡ እንድም ፡ ባለሟሉ ፡ ሙሴ ፡ ባማላጅነት ፡ ከፊቱ ፡ ባይቆም ።

ቆመ ፡ ቅድሜሁ ፡ አመ ፡ ብድብድ ።

ባለሟሉ ፡ ሙሴ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ቸነትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ ዓባር ፡ ቸነፈር ፡ በታዘዘበት ፡ ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ባማላጅነት ፡ ቆመ ።

ከመ ፡ ይሚጥ ፡ መቅሠፍተ ፡ መዐቱ ።

ፈርዶ ፡ ያመጣውን ፡ መቅሠፍት ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ኢይሥርዎሙ ።

ፈጽሞ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዳያጠፋቸው ።

፳፬ ፤ ወመነኑ ፡ ምድረ ፡ መፍትወ ።

ለከ ፡ ወለዘርዕከ ፡ እሁበካ ፡ ለይእቲ ፡ ምድር ፡ ብሎ ፡ ትንቢት ፡ ያናገረላቸውን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ንቀዋል ፡ አቃልለዋልና ።

ወኢተአመኑ ፡ በቃሉ ።

ወኢተአመንዎ ፡ ለቃሉ ፡ ይላል ፤ አወርስከሙ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ አላመኑም ።

፳፭ ፤ ወአንጐርጐሩ ፡ በውስተ ፡ ተዐይኒሆሙ ።

በለስ ፡ ወይን ፡ ከዚህ ፡ ወዴት ፡ አለ ፡ ብለው ፡ በከተማቸው ፡ ውስጥ ፡ አዘኑ ።



2014 04 17

ወእስምዐ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ አል ሰሙም ፡ ማለት ፡ አልጠበቁም ።

፷፬ ፡ ወአንስት ፡ እደው ፡ ላዕሌሆሙ ።

እሱም ፡ እንኪያስ ፡ ብሎ ፡ እደ ፡ መዓቱን ፡ እነግባቸው ፡ (አመጣ ባቸው) ።

ኩሙ ፡ ደንገፁሙ ፡ በዓዳም ።

በበረኃ ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ማ ለት ፡ እንደ ፡ ሻሽ ፡ ተነጥፈው ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ረግፈው ፡ እንደ፡ ግንድ ፡ ተረብርበው ፡ ይቀሩ ፡ ዘንድ ።

፷፭ ፡ ወከሙ ፡ ደንገፁ ፡ ዘርዖሙ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ።

የልጅ ፡ ልጆቻቸውንም ፡ በአሕ ዛብ ፡ አገር ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ።

ወከሙ ፡ ይዘርዎሙ ፡ ውስተ ፡ በሐውርት ።

ፋርስ ፡ ባቢሎን ፡ ዕርዕ ፡ ሚዶን ፡ ይበትናቸው ፡ ዘንድ ።

፷፮ ፡ ወተፈልጡ ፡ በብዔል ፡ ፌጎር ።

የብዔል ፡ ፌጎር ፡ ነን ፡ በማለት ፡ ተከተሉ ፡ (ሐ) ፡ በሐሳዊ ፡ መሲ ሕ ፡ ጊዜ ፡ ዘመርምያዋእስ ፡ ተብለ ው ፡ እንዲከተሉ ። እንድም ፡ ፌጎር ፡ ካህን ፡ ጣዖት ፡ ነው ፤ ፌጎር ፡ የሚ ባል ፡ ካህን ፡ ጣዖት ፡ ሳቆመው ፡ ጣዖት ፡ የፈሰሰውን ፡ ደም ፡ ተ ቀቡ ። በግዐ ፡ ፍጹሚ ፡ እንዲል ፡ በግዐ ፡ ቅብዓት ፡ ሲል ። እንድም ፡ ፌጎር ፡ የሚባል ፡ ጋኔን ፡ ላደረ በት ፡ ጣዖት ፡ ሰገዱ ፤ መስገድ ፡ እንጂ ፡ በፊት ፡ ነው ። እንድም ፡ ፌጎር ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ የቆመ ፡ ጣዖትን ፡ በማምለክ ፡ ተፈጸሙ ፡ አለቁ ።

ወበልዑ ፡ መሥዋዕተ ፡ ምውተ ።

ምውት ፡ መሥዋዕትን ፡ በሉ ፡ ሕያው ፡ መሥዋዕት ፡ አለና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ የማያድን ፡ ሲል ፡ ነው ። እንድም ፡ መሥዋ ዕተ ፡ ምውት ፡ ይላል ፡ ለምውት ፡ ጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ በሉ ።

፷፯ ፡ ወወሀክዎ ፡ በምግባሪሆሙ ።

እግዚአብሔርን ፡ በሥራቸው ፡ እነማሡት ፡ ማለት ፤ ቅሠፈን ፡ ቅሠፈን ፡ አሉት ።

ወበዝኃ ፡ ብድብድ ፡ ላዕሌሆሙ ።

አባር ፡ ቸነፈር ፡ በዛባቸው ፡ ማ ለት ፤ ፀናባቸው ።

፷፰ ፡ ተንሥአ ፡ ፊንሐስ ፡ ወአድኀኖሙ ።

ፊንሐስ ፡ በሥራ ፡ ተነሥቶ ፡ አዳ ናቸው ።

፷፱ ፡ ኀደገ ፡ ብድብድ ፡ ወተኈለቈ ፡ ጽድቀ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

አባር ፡ ቸነፈር ፡ ፀጥ ፡ አለ ፡ እ ስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ (ተኈለቈ ፡ ጽድቀ) ጽድቅ ፡ ሁኖ ፡ ተሰጠው ፡ ከጽድቅ ፡ ተቈ ጠረለት ፡ (ታ) ፡ በለዓም ፡ የሚ ባል ፡ ሀብተ ፡ መርገም ፡ የተ ሰጠው ፡ ነበረ ፡ ባላቅ ፡ ወልዶ ፡ ሶፎር ፡ ግብፃውያንን ፡ በባሕር ፡ ያሠጠመ ፡ ዓግ ፡ ሲዖንን ፡ ንጉሠ ፡ አራዶን ፡ ያጠፋ ፡ ጦር ፡ የማይመ ልሰው ፡ ኃይለኛ ፡ ጠላት ፡ መጥ ቶብኛልና ፡ መጥተህ ፡ ረግመህ ፡ አጥፋልኝ ፡ ቤትህን ፡ በወርቅ ፡ በዕንቍ ፡ እንዕልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ፤ እደሩ ፡ ፈጣሪዬን ፡ ልጠ ይቀው ፡ አላቸው ፡ እደሩ ፡ ፀውዓኒ ፡ ባላቅ ፡ ወልዶ ፡ ሶፎር ፡ እመስጴ ጦምያ ፡ ዘሶርያ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ርግሞ ፡ ሊተ ፡ ለያዕቆብ ፡ ወፀ ዓሎ ፡ ሊተ ፡ ለእስራኤል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፤ አትሂድ ፡ አለው ፡ አል ሆነላችሁም ፡ ሂዱ ፡ አላቸው ፡ ሄዱ ፡ ገንዘብ ፡ ቢያንሰው ፡ መላ ክተኞቹ ፡ ተራ ፡ ቢሆኑበት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አሲዞ ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች ፡ አድርጎ ፡ ላከ ፤ እደሩ ፡ ፈጣሪዬን ፡ ልጠይቅ ፡ አላቸው ፡ ጠየቀው ፡ ሂድ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አትርገም ፡ አለው ። ነገሩ ፡ ቀዋሚ ፡ እይደለምሳ ፡ መላላሽ ፡ ነውሳ ፡ ከሄድሁስ ፡ እኔ ፡ አውቃ ለሁ ፡ ብሎ ፡ መርገሙን ፡ እያሰ ላሰለ ፡ ሲሄድ ፡ መልአኩ ፡ ሰይ ፉን ፡ መዝዞ ፡ ላህያው ፡ ታያት ፤ ፈርታ ፡ ቆመች ፤ ሂጂ ፡ እያለ ፡ ይመታት ፡ ገመረ ፡ መልአኩ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ቆመ ፤ እልፍ ፡ ብላ ፡ ቆመች ፤ ሂጂ ፡ እያለ ፡ ይመ ታት ፡ ገመረ ፡ በሦስተኛው ፡ ከቅ ጽርና ፡ ከቅጽር ፡ መሐል ፡ ይዛው ፡ ገባች ። ወመለጠቶ ፡ እገሪሁ ፤ እግሩን ፡ ላጠችው ። አርጌ ፡ ነቢ ይ ፡ ብለሽ ፡ ነው ፡ ብያ ፡ እንዲህ ፡ የምትጫወችብኝ ፡ ጦር ፡ በና ረኝ ፡ በወጋሁሽ ፡ ሰይፍ ፡ ቢኖ ረኝ ፡ በመታሁሽ ፡ ነበር ፡ አላት ፤ አኮኑ ፡ ዕድግትከ ፡ ዘትጼዓነኒ ፡ እምንዕስከ ፡ ከሕፃንነትህ ፡ ጀ ምሮ ፡ የምትቀመጥብኝ ፡ አህያህ ፡ እይደለሁምን ፡ ዳገቱን ፡ ውጭ ፡ ሜዳውን ፡ ሩጭ ፡ ብትለኝ ፡ ምን ፡ ቀን ፡ እንቢ ፡ ብዩህ ፡ አውቃለሁ ፡ ካንተ ፡ የሚበልጥ ፡ መልአኩን ፡ አይቼ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አለችው ፤ ለሱም ፡ ተገልጾለት ፡ ፈርቶ ፡ ወርዶ ፡ ልመለስን ፡ አለው ፡ መ ሆኑን ፡ ሂድ ፤ ባሕቱ ፡ ዘወደየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃለ ፡ ውስተ ፡ አፉከ ፡ ኪያሁ ፡ ተዓቀብ ፡ ለነቢብ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጸልህን ፡ እ ንጂ ፡ ሌላ ፡ አትናገር ፡ አለው ፤ ሄደ ፤ ባላቅ ፡ ወልደ ፡ ሶፎር ፡ ደስ ፡ አለው ፤ ስለ ፡ መጣሁ ፡ ደስ ፡ አይበልህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገ ለጸልኝን ፡ ነው ፡ የምናገር ፡ አለው ። ዘኍ ፡ ፳፪ ፡ ፩—፶፩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡



2014 04 17

መሥዋዕት ፡ ሠውቶ ፡ ከመሥዋ
ዕትህ ፡ ቁም ፡ አለው ፡ እያሟረ
ተ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሂዶ ፡ ም
ንተ ፡ አረገም ፡ ዘእግዚአብሔር ፡
አረገመ ፡ ወምንተ ፡ እጼዕል ፡ ዘእ
ግዚአብሔር ፡ ኢጸዐለ ፡ አለ ፤ እር
ግምልኝ ፡ ብለህ ፡ ትመርቃቸዋ
ለህን ፡ አለው ፤ ቀድሞስ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ የገለፀልኝን ፡ ነው ፡ የም
ናገር ፡ ብሎ ፡ ነግሬህ ፡ የለምን ፡
አለው ፤ መሥዋዕት ፡ ቢያንስ
ብት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሰባት ፡ ላም ፡
ሰባት ፡ በግ ፡ ሰባት ፡ ፍየል ፤ ሠ
ውቶ ፡ እርገምልኝ ፡ አለው ፤ እን
ደ ፡ ልማዱ ፡ እያሟረተ ፡ ወደ ፡
ምሥራቅ ፡ ሂዶ ፡ ናሁ ፡ እምእር
እስተ ፡ አድባር ፡ እሬእዮ ፡ ወእም
አርእስተ ፡ አውግር ፡ እሌብዎ ፡
ዘእግዚአብሔር ፡ እምላኩ ፡ ምስ
ሌሁ ፡ ሕዝብ ፡ ዘባሕቲቱ ፡ የኃ
ድር ፡ አለ ፤ ይህ ፡ ሁለተኛህ ፡ ነው ፡
እርገምልኝ ፡ ብለህ ፡ ትመርቃቸ
ዋለህን ፡ አለው ፤ ቀድሞስ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ የገለጸልኝን ፡ ነው ፡
የምናገር ፡ ብዬ ፡ ነግሬህ ፡ የለ
ምን ፡ አለው ፤ ሰው ፡ ቢበዛበት ፡
ዓይን ፡ ቢፈራ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እን
ድ ፡ ነገድ ፡ ከሌለበት ፡ ወስዶ ፡
እርገምልኝ ፡ አለው ፡ ሚ ፡ ይሜኒ ፡
ተዓይኒከ ፡ ያዕቆብ ፡ ወሕድ ፡ እብ
ያቲከ ፡ እስራኤል ፤ ኮከብ ፡ ይሠ
ርቅ ፡ እምያዕቆብ ፡ ወያዓትት ፡
ኃጢአተ ፡ እምእስራኤል ፡ አለው ፤
ደገኛው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ሦስ
ተኛህ ፡ ነው ፡ እርገምልኝ ፡ ብለህ ፡
ትመርቃቸዋለህን ፡ አለው ።

ቀድሞስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለ
ጸልኝን ፡ ነው ፡ የምናገር ፡ ብዬ ፡
ነግሬህ ፡ የለምን ፡ አለው ፤ ለኔ
ማ ፡ ምን ፡ ዕዳዬ ፡ ላንተ ፡ ቀ
ረብህ ፡ ቤትህን ፡ በወርቅ ፡ በዕ
ንቍ ፡ እንጽልሃለሁ ፡ ብዬ ፡ ነበረ ፡
ቀረብህ ፡ እንጂ ፡ አለው ፤ ከብተ ፡
ነቢ ፡ እንዲሉ ፡ መቼስ ፡ አንተ ፡
የምትሻው ፡ ጥፋታቸውን ፡ አይ
ደለምን ፡ አለው ፤ ሌላ ፡ ምን ፡
እሻለሁ ፡ አለው ፡ እንኪያስ ፡
ቁሜ ፡ ረግሜ ፡ ባላጠፋ ፡ ተቀ
ምጩ ፡ ረግሜ ፡ (መክሬ) ፡ አጠ
ፋልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡
በመና ፡ የተናደደ ፡ እስራኤል ፡
ሴት ፡ ሲያይ ፡ አያስችለውምና ፡
ሕፃናቱን ፡ ሴቶች ፡ ጣዖቱን ፡
አሳዝለህ ፡ ስደዳቸው ፡ እንድረ
ሰባችሁ ፡ ያዳቸዋል ፤ ለዚህ ፡
ስገዱ ፡ ይህን ፡ ብሉ ፡ ይበዱቸው ፡
ይሰግዳሉ ፡ ይበላሉ ፤ ፈጣሪያቸው ፡
ለአምልኮቱ ፡ ቀናዒ ፡ ነውና ፡
ያጠፋልሃል ፡ አለው ፤ እንደ ፡ ነገ
ረው ፡ አድርጎ ፡ ሰደዳቸው ፤ እን
ዳለውም ፡ ተሻምተው ፡ እንድረሰ
ባችሁ ፡ እዷቸው ፤ ለዚህ ፡ ስገዱ ፡
ይህን ፡ ብሉ ፡ እዷቸው ፡ ሰገዱ ፡



በሉ ፡ ቸነፈር ፡ ይፈጃቸው ፡ ጀ
መረ ፡ የይሁዳ ፡ የቤት ፡ አለቃ ፡
ዘምሬ ፡ ይባላል ፡ የእሕዛብ ፡ የቤ
ት ፡ አለቃ ፡ ልጅ ፡ ከስቢ ፡ ትባላ
ለች ፡ ተጠቃቅሰው ፡ ከአልፍኝ ፡
እንድም ፡ ከጕድጓዳ ፡ መሬት ፡
ሲገቡ ፡ ብላቴና ፡ አይቶ ፡ ለፊን
ሐስ ፡ ነገረው ፡ ለመባዕ ፡ የመጣ ፡
ዘገር ፡ ነበረ ፡ ያንን ፡ ይዞ ፡ ሂዶ ፡
ሥራቸውን ፡ ከሚሠሩበት ፡ እን
ድ ፡ አድርጎ ፡ ወጋቸው ፤ ፊንሐስ ፡
ወልደ ፡ አሮን ፡ ወልደ ፡ አልዓዛር ፡
እስተንፈስካ ፡ ለልብየ ፡ ብሎታል ፤
ቸነፈሩም ፡ ትቷቸዋል ፡ በዚህም ፡
ምክንያት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ መዋ
ዕለ ፡ ክህነት ፡ ተሰጥቶታልና ፡
እንዲህ ፡ አለ ። ዘኍ ፡ ፳፫ ፡ ፩-[illegible] ፤ ፩
፳፭ ። ፩ ፡ ፩-፲፰ ።

፴፪ ፤ ወአምዕዕዎ ፡ በኀበ ፡ ማየ ፡ ቅሰት ።

ጸብ ፡ ክርክር ፡ ባለበት ፡ ውሃ ፡
አሳዘኑት ፤ ጌታና ፡ሙሴ ፡ ሙሴና ፡
እስራኤል ፡ ተከራከረውበታልና ፤
እንዲህ ፡ አለ ።

ወሐመ ፡ ሙሴ ፡ በእንቲአሆሙ ። ዘፀ ፡ ፲፯ ፡
፩-፯ ።

ሙሴ ፡ በላቸው ፡ ምክንያት ፡ ባለ
መከራ ፡ ሆነ ።

፴፫ ፤ እስመ ፡ አምረርዋ ፡ ለነፍሱ ።

ሰውነቱን ፡ አሳዝነዋታልና ።

ወአዘዘ ፡ በከናፍሪሁ ።

ባንደበቱ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፤
ከዕለታት ፡ ባንዳቸው ፡ እስራ
ኤል ፡ ሙሴን ፡ ሙሴ ፡ ውሃ ፡
ሙሴ ፡ ውሃ ፡ እያሉ ፡ ዘበዘቡት ።
የወለደች ፡ እናት ፡ ያሳደገች ፡ ሞግ
ዚት ፡ ይመስል ፡ ምን ፡ ይዘበዝ
ቡኛል ፡ ብሎ ፡ ንሴብሖን ፡ ሳይ
ደግም ፡ ሰጣቸው ። ከዚያ ፡ አስ
ቀድሞ ፡ ንሴብሖን ፡ ደግሞ ፡ እን
ከሙ ፡ ስትዩ ፡ ዘወሀበክሙ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ኪያሁ ፡ ሰብሑ ፡ ብሎ ፡
ነበር ፡ የሚሰጣቸው ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡
ግን ፡ ደክሞት ፡ ነበርና ፡ እንዲህ ፡
ሳይል ፡ ሰጣቸው ፤ እነሱም ፡ ሳያ
መሰግኑት ፡ ጠጥተውታል ። ጌታ ፡
ሙሴን ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ኢትበውእ ፡
ለኢየሩሳሌም ፡ በእንተ ፡ ዘኢቀ
ደስከኒ ፡ ብሎታል ። በዚህ ፡ ምክ
ንያት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አልገባም ፤
ምድረ ፡ ናባው ፡ ወድቆ ፡ ቀርቷል ።

፴፬ ፤ ወኢሠረዉ ፡ አሕዛበ ፡ ዘይቤሎሙ ፡
እግዚአብሔር ።

ሠርጠው ፡ ያለበት ፡ ነው ፤ እግዚ
አብሔር ፡ አጥፉ ፡ ያላቸውን ፡ አሕ
ዛብን ፡ አላጠፉምና ። ፩ ፡ ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳፬ ።

፴፭ ፤ ወተደመሩ ፡ ምስለ ፡ አሕዛብ ።

ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ በሥራ ፡ አንድ ፡
ሆኑ ።

ወተምህሩ ፡ ምግባሮሙ ።

የአሕዛብን ፡ ሥራ ፡ ተማሩ ፡ ግለ
ት ፡ ሠሩ ።

፵፫ ፣ ወተቀንየ ፡ ለግብፅሆሙ ።

ለግብፅሙም ፡ ይላል ፤ ለተቀረጸ ፤ ለተጐነፈ ፡ ጣዖታቸውም ፡ ተገዙ ።
ኢሳ ፡ ፲ ፡ ፲ ።

ወገሮሙ ፡ ጊዜ ።

ይኸውም ፡ ዕዳ ፡ ሆነባቸው ።

፵፬ ፣ ዘበሉ ፡ ደቂቆሙ ፡ ወእዋልዲሆሙ ፡ ለአጋንንት ።

ወንድ ፡ ሴት ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለአጋንንት ፡ ሠዉ ። ዘሌ ፡ ፲፰ ፡ ፯ ። ዘዳ ፡ ፴፪ ፡ ፲፯ ። ኤር ፡ ፴፪ ፡ ፴፭ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፳ ። ራእ ፡ ፱ ፡ ፳ ።

፵፭ ፣ ወከዐዉ ፡ ደመ ፡ ንጹሐ ።

ንጹሕ ፡ ደምን ፡ አፈሰሱ ።

ደመ ፡ ደቂቆሙ ፡ ወእዋልዲሆሙ ።

ንጹሕም ፡ ያልሁት ፡ የወንድ ፡ የሴት ፡ ልጆቻቸው ፡ ደም ፡ ነው ።
ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፩ ።

ወሦዑ ፡ ለግልፎ ፡ ከነዓን ።

ከነዓን ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ለሚያመልከው ፡ ጣዖት ፡ ሠዉ ። እንድም ፡ ከነዓን ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ለቆመ ፡ ጣዖት ፡ ሠዉ ።

ወተቀትለት ፡ ምድር ፡ በደም ።

ተሜረየት ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ምድር ፡ በደም ፡ ታለለች ። እንድም ፡ ተቀብፀት ፡ ደምን ፡ ተቀባች ፤ ተመስሐት ፡ ይላል ፡ በዐረቡ ፡ ተሜረየት ፡ ሲል ፤

፶፰ ፣ ወረሰዮሙ ፡ ምድር ፡ በምግባሬሆሙ ።
ኢሳ ፡ ፳፬ ፡ ፭ ።

ምድር ፡ በሥራቸው ፡ ጠፋች ።

ወዘመዉ ፡ በጣዖቶሙ ።

በጣዖታቸው ፡ ሰሰኑ ። መሰሰን ፡ ብቻ ፡ የወንድና ፡ የሴት ፡ አይደለም ፤ ጣዖትም ፡ ማምለክ ፡ ሴሰኝነት ፡ ነውና ።

፶፱ ፣ ወተምዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ መዓተ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝቡ ።

እግዚአብሔር ፡ በሕዝቡ ፡ ፈጽሞ ፡ ፈረደባቸው ።

ወአስቈረሮሙ ፡ ለርስቱ ።

ርስቱ ፡ ጉልቱ ፡ የሚሆኑ ፡ እስራኤልንም ፡ ተጸየፋቸው ፡ ማለት ፤ በረድኤት ፡ ተለያቸው ።

፷፩ ፣ ወአግብአሙ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ፀሮሙ ።

በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አስማረካቸው ፤

ወቀነይዎሙ ፡ ጸላእቶሙ ።

ጠላቶቻቸው ፡ ግብጻውያን ፡ አስጨንቀው ፡ አስጠብበው ፡ ገዟቸው ።

፷፪ ፣ ወአሕመምዎሙ ፡ ፀሮሙ ።

ጠላቶቻቸው ፡ መከራ ፡ አጸኑባቸው ።

ወኀሥሩ ፡ በታሕተ ፡ እደዊሆሙ ።

በእጃቸው ፡ ጭብጥ ፡ በእግራቸው ፤



ወሜጦ ፡ መልአከ ፡ አሕዛብ ፤ መዝሙር ፡ ፸፰ ።



ወገሠጾ ፡ ለባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ወየብሰት ፤ ወመርሖሙ ፡ በቀላይ ፡ ከመ ፡ ዘበገዳም ፤ መዝሙር ፡ ፻፭ ።





አርግተ ፡ ብለው ፡ በመገዛታቸው ፡ ተዋረዱ ፡ ጕስቁሉ ።

፵፫ ፡ ወዘልፈ ፡ ያድኅኖሙ ።

እሱ ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ ያድናቸው ፡ ነበረ ።

አመንቀስ ፡ አምዕዕዎ ፡ በምክሮሙ ።

እሳቸው ፡ ግን ፡ በሥራቸው ፡ አሳ ዘኑት ።

ወሐሙ ፡ በኀጢአቶሙ ።

ወደው ፡ በሠሩት ፡ ኀጢአት ፡ ባ ለመከራ ፡ ሆኑ ።

፵፬ ፡ ወርእዮሙ ፡ ከመ ፡ ተመንደቡ ።

መከራው ፡ እንደ ፡ ጸናባቸው ፡ አየ ፡ አይቶ ፡ አየና ።

ወሰምዖሙ ፡ ጸሎቶሙ ።

ልመናቸውን ፡ ሰማቸው ።

፵፭ ፡ ወተዘከረ ፡ ኪዳኖ ።

መሐላውን ፡ አደረገ ፡ ፈጸመ ፡

ወነስሐ ፡ በከመ ፡ ብዙኅ ፡ ምሕረቱ ።

እንደ ፡ ቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ተመ ለሰ ።

፵፮ ፡ ወወሀቦሙ ፡ ግዕዛ ፡ በቅድመ ፡ ኵሎሙ ፡ ፡ እለ ፡ ፄወውዎሙ ።

ይገዷቸው ፡ ይቀሙቸው ፡ ብሎ ፡ በማረካቸው ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ይቅርታውን ፡ አደረገላቸው ።

፵፯ ፡ አድኅነነ ፡ እግዚኦ ፡ አምላክነ ።

እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ያባቶቻቸውን ፡ ሲናገር ፡ መጥቶ ፡ ነበር ፡ እን ግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የነሱን ፡ ይናገ ራል ፡ አቤቱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ከጠ ላቶቻችን ፡ እጅ ፡ አድነን ።

ወአስተጋብአነ ፡ እምአሕዛብ ፡

ከፋርስ ፡ ከባቢሎን ፡ ከጽርእ ፡ ከሚዶን ፡ ሰብስበን ፡

ከመ ፡ ንግነይ ፡ ለስምከ ፡ ቅዱስ ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብተን ፡ ጽኑዕ ፡ ከሃሊ ፡ ለሚሆን ፡ ስምህ ፡ እን ገዛ ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ንትመካሕ ፡ በስብሐቲከ ።

ጌትነትህን ፡ በማመስገን ፡ ከብ ረን ፡ ገነን ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ። እ ምከመ ፡ አድማዕነ ፡ መንግሥተ ፡ ንትሜካህ ፡ እንዲል ።

፵፰ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ እስራኤል ።

እስራኤልን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።

ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ ከምጽአትም ፡ በኋላ ፡ የሚኖር ።

ለይበል ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን ። ራእ ፡ ፲፱ ፡ ፲፬ ። ፩ ፡ ፩ ።

ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ይደረግ ፡ ይደረግ ፡ ይ

በአ ፡ እስከዚም ድረስ ብሏት ልዩ ኩን ብምስት ለይበሉ ተናግሯታል።

## መዝሙር ፡ ፻፯ ።

፩፡ ግነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ኄር ።
ለዩ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ተገዙ፡ ቸር፡ ነውና።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፡ ለሰው ፡
ለዘ ፡ ሆነ ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ፡
ለዘ ፡ ሆነ ።
፪፡ ለይበሉ ፡ እለ ፡ አድኀኖሙ ፡ እግዚአብ
ሔር ።
እግዚአብሔር ፡ ከመከራ ፡ ያዳ
ናቸው ፡ ሁሉ ፡ ግንዩ ።
እለ ፡ አድኀኖሙ ፡ እምእደ ፡ ጸላኢ ።
ከጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ያዳናቸው ፡
ሁሉ ።
፫፡ ወአስተጋብአሙ ፡ እምበሓውርት ።
ከሩቁ ፡ መሕዘን ፡ ሰበሰባቸው ፡
[illegible]
[illegible]
በሐውርት ፡ ያለውን ፡ ይደርሰራልና፤
እምጽባሕ ፡ ከፋርስ ፡ እምዐረብ ፡
ከግብጽ ፡ መስዕ ፡ ከባቢሎን ፡ ባ
ሕር ፡ ከሀገድ ፡ የሰበሰባቸው ፡ ትሩ
ፋን ፡ ግንዩ ፡ ለይበሉ ። ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።
፬፡ [illegible]
ውኃ ፡ በሌለበት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
ተቅበዘበዙ ፡ ጠኑ ።
[illegible]
ፍኖተ ፡ ሀገሮሙ ፡ ይላል ፡ ያገራ
ቸውን ፡ መንገድ ፡ አላገኙምና ፡
(ሐ) ፡ ወደ ፡ ጉንደር ፡ የሚወስ
ዱትን ፡ በአገው ፡ አዙረው ፡ እን
ዲወስዱት ፡ እንስሙ ፡ ፈት ፡ ለፈ
ት ፡ የወሰድናቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
እየጉበሉ ፡ ይሄዱብናል ፡ ብለው ፡
አዙረው ፡ ወሰደዋቸዋል ፡ የሀገራ
ችንን ፡ መንገድ ፡ አገኘን ፡ እያሉ ፡
በየጉዳናው ፡ ወድቀው ፡ ወድቀ
ው ፡ ቀርተዋል ።
፭፡ ርኁባን ፡ ወጽሙኣን ፡ ወነፍሶሙ ፡
[illegible]
ተራቡ ፡ ተጸሙ ፡ ተዋሕዳቸው ፡
ያለች ፡ ነፍሳቸው ፡ ከሥጋቸው ፡
አለይ ፡ አለይ ፡ አለች ።
፮፡ ወጸርሑ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሶበ ፡
ተመንደቡ ።
እንዲህ ፡ መከራ ፡ ባገኘቸው ፡
ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መል
ሰው ፡ ለመኑ ።
ወአድኀኖሙ ፡ እምንዳቤሆሙ ።
እግዚአብሔርም ፡ ከገኘቸው ፡ መ
ከራ ፡ አዳናቸው ።
፯፡ ወመርሖሙ ፡ ፍኖተ ፡ ርትዕ ።
የቀናውን ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ መን
ገድ ፡ መርቶ ፡ አወጣቸው ።



ከመ ፡ ይሑሩ ፡ ፍኖተ ፡ ሀገሮሙ ።
በሀገራቸው ፡ መንገድ ፡ ይሄዱ ፡
ዘንድ ። ሁለት ፡ ዓመት ፡ የሄዱ
ትን ፡ ጉዳና ፡ ሥርዋ ፡ መንገድ ፡
አገኙተው ፡ (ተገለጸላቸው) ፡ በአ
ርባ ፡ ቀን ፡ ደርሰዋል ።
፰፡ ንግሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሕረቶ ፡ ወ
መንክሮ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።
ንገሩ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ምሕ
ረቱ ፡ ወመንክር ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ብለሀ ፡ ግጠም ። ይህን ፡
እንዲህ ፡ ያደረገ ፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ ቸርነቱን ፡ ተአምራቱን ፡
ለሰው ፡ ንገሩ ፤ አስተምሩ ።
፱፡ እስመ ፡ አጽገበ ፡ ነፍሰ ፡ ርኅብተ ።
ሰባ ፡ ዘመን ፡ የተራበች ፡ የትሩ
ፋን ፡ ሰውነት ፡ ምግበ ፡ ሥጋን ፡
ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ አሰኝቷልና ።
[illegible]
ወመልአ ፡ ለነፍስ ፡ ዕራቅ ፡ በረከተ ።
የሰውን ፡ ዕራቍትነት ፡ በረከተ ፡
ሥጋን ፡ መልቷታልና ። እንድም ፡
ለዕርቅት ፡ ነፍስ ፡ ይላል ፤ ሰባ ፡
ዘመን ፡ ከበረከተ ፡ ሥጋ ፡ የተራ
ቈተች ፡ የትሩፋን ፡ ሰውነት ፡
በረከተ ፡ ሥጋን ፡ መልቷልና ።
እንድም ፡ (እስመ ፡ አጽገበ) ፡
አምስት ፡ ሺሕ ፡ ከምስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፡ ረኀበ ፡ ነፍስ ፡ የተራበች ፡
የምእመናን ፡ ነፍስ ፡ በረከተ ፡ ነፍ
ስን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ አሰኝቷልና ።
አምስት ፡ ሺሕ ፡ ከምስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፡ ከበረከተ ፡ ነፍስ ፡ የተ
ራቈተች ፡ የምእመናንም ፡ ሰው
ነት ፡ በረከተ ፡ ነፍስን ፡ መልቷ
ታልና ። [illegible]
፲፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡
ወጽላሎተ ፡ ሞት ።
በባቢሎን ፡ በቈላተ ፡ ንዦር ፡ ለሚ
ኖሩ ፤ እንድም ፡ በኀልዮ ፡ በነ
ቢብ ፡ በገቢር ፡ ፍዳ ፡ ለተያዙ ።
ሙቁሓን ፡ በንዴት ፡ ወበኀጺን ።
በመከራ ፡ በንዴት ፡ በእግር ፡
ብረት ፡ የታሰሩትን ፤ እንድም ፡
በፍዳ ፡ በቍራኝነት ፡ የተያዙ
ትን ፡ ኢሳ ፡ [illegible] ።
፲፩፡ እስመ ፡ አምረሩ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።
ኢታምልክ ፡ ያለ ፡ እንድም ፡ ኢት
ብልዑ ፡ ያለ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ አሳዝነዋልና ፡ ማለት ፤
እንቀበልም ፡ ብለዋልና ።
ወአምዐዑ ፡ ምክረ ፡ ልዑል ።
መክር ፡ የሠራቸው ፡ ዘጠኙን ፡
ሕገጋትም ፡ እንቀበልም ፡ ብለ
ዋልና ።
፲፪፡ ወሰርሐ ፡ በሕማም ፡ ልቦሙ ።
ልበ ፡ ሥጋቸው ፡ በመከራ ፡ ሥጋ ፡
ልበ ፡ ነፍሳቸው ፡ በመከራ ፡ ነፍ
ስ ፡ ደከመ ።
ደወዩ ፡ ወነትኑ ፡ [illegible] ።
ደወዩ ፡ የሞት ፡ ደዌ ፡ ታመሙ ፤

አጥቦ ፡ ገንዞ ፡ የሚቀብራቸው ፡ አጡ ። እንድም ፡ በኀጢአት ፡ ደዌ ፡ ታመመ ፡ የሚያጠምቃቸው ፡ አጡ ። አውቀረ ፡ ዓቲ ፡ ጥምቀተ ፡ መቃብረ ፡ ነፍስ ፡ ውኑተማ ፡ በአባን ፡ ሠላስ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ የሚያስጠይፍ ፡ ሆኑ ፡ በድን ፡ ርኩስ ፡ እንዲል ።

፲፫ ፡ ወጸርኁ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሶበ ፡ ተመንደቡ ።

እንዲህ ፡ መከራ ፡ ባገኛቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሰው ፡ ለመኑ ።

ወአድኀኖሙ ፡ እምንዳቤሆሙ ።

እሱም ፡ ካገኛቸው ፡ መከራ ፡ አዳናቸው ።

፲፬ ፡ ወአውፅኦሙ ፡ እምጽልመት ፡ ወጽላሎተ ፡ ሞት ።

ሁሉቱን ፡ ነገድ ፡ ከባቢሎን ፡ ሰሎሩን ፡ ነገድ ፡ ከቈላተ ፡ ጎዞር ፡ አወጣቸው ። እንድም ፡ ምእመናንን ፡ የኀልዮ ፡ የነቢብ ፡ የገቢር ፡ ፍዳ ፡ ካለበት ፡ ከሲኦል ፡ ከገሃነም ፡ አወጣቸው ።

ወሰበረ ፡ መዋቅሕቲሆሙ ።

እግር ፡ ብረታቸውን ፡ ሰብሮ ፡ እንድም ፡ ቍራኝነታቸውን ፡ አጥፍቶ ።

፲፭ ፡ ንገሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሕረቶ ፡ ወመንክራቲሁ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።

የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነቱን ፡ ተአምራቱን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ንገሩ ፡ አስተምሩ ።

፲፮ ፡ እስመ ፡ ሰበረ ፡ ኆኀተ ፡ ብርት ።

ኀያላኑን ፡ አጥፍቷልና ። እንድም ፡ መርገመ ፡ ሥጋ ፡ መርገመ ፡ ነፍስን ፡ ሰራዊተ ፡ አጋንንትን ፡ አጥፍቷልና ። ማር ፡ ፩ ፡ ፳፬ ።

ወቀጥቀጠ ፡ መናሥግተ ፡ ዘኀጺን ።

ንጉሥታቱን ፡ መኳንንቱን ፡ ኀያላኑን ፡ እንድም ፡ መርገመ ፡ ሥጋ ፡ መርገመ ፡ ነፍስን ፡ ሊቃነ ፡ አጋንንትን ፡ አጥፍቷልና ። ኢሳ ፡ ፵፭ ፡ ፪ ።

፲፯ ፡ ወተወከፎሙ ፡ እምፍኖተ ፡ ኃጢአቶሙ ።

በድለው ፡ ከሄዱበት ፡ አገር ፡ ከባቢሎን ፡ በረድኤት ፡ እንድም ፡ ከመከራ ፡ በንስሓ ፡ ተቀበላቸው ። እንድም ፡ ኀጢአት ፡ ሠርተው ፡ ከሄዱበት ፡ አገር ፡ ከሲኦል ፡ በልጅነት ፡ ከመከራ ፡ በንስሓ ፡ ተቀበላቸው ።

እስመ ፡ ሐመሙ ፡ በኀጢአቶሙ ።

ወደው ፡ በሠሩት ፡ ኀጢአት ፡ ባለመከራ ፡ ሁነዋልና ።

፲፰ ፡ መነነት ፡ ኵሎ ፡ መብልዐ ፡ አስቈረረት ፡ ነፍሶሙ ።

ሰውነታቸው ፡ መብሉን ፡ ሁሉ ፡ ተጸየፈችው ፡ ማለት ፡ አግኝታው ፡ አይደለም ፡ አጥታው ፡ ነው ፡ እንጂ ። እንድም ፡ መሥዋዕቱን ፡



ተጸየፈችው ፡ የሚያስጸይፍ ፡ መሥዋዕት ፡ አለን ፡ ቢሉ ፡ አለማዳኑን ፡ መናገር ፡ ነው ። ወዝኵልነ ፡ ከነ ፡ ኀሱራነ ፡ ወከነ ፡ ጽድቅነ ፡ ከመ ፡ ጸርቀ ፡ ትክቶ ፡ ፈወስናሃ ፡ ለባቢሎን ፡ ወኢ ተፈወሰት ፡ እንዲል ። እንድም ፡ ሰውነታቸው ፡ በሞት ፡ አስጸየፈች ፡ በድን ፡ ርኩስ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ ነፍሳቸው ፡ ምግቡን ፡ ተጸየፈችው ፡ በነፍስ ፡ ምግብ ፡ ኑሮ ፡ አይደለም ፡ የክብሩን ፡ መቅረት ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወቀርቡ ፡ ኀበ ፡ አናቅጸ ፡ ሞት ።

ሞት ፡ ገድሎ ፡ ገድሎ ፡ ወደሚያወርድበት ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ሊወርዱ ፡ ቀረቡ ፡ አናቅጽ ፡ ብሎ ፡ አበዛ ፡ በሀገራቸው ፡ መቃብር ፡ ሲቈፍሩ ፡ ዐፈር ፡ አይመልሱም ፡ አልፍኝ ፡ ካዳራሽ ፡ አድርገው ፡ ያንጹሉ ፡ የኖረውን ፡ እፊት ፡ በአልፍኝ ፡ ትኩሱን ፡ ባዳራሽ ፡ ያደርጉታል ፡ ሽቱ ፡ ለመቅባት ፡ እንዲመቻቸው ፡ ነው ። እንድም ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ሊወርዱ ፡ ቀረቡ ።

፲፱ ፡ ወዐውየዉ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሶበ ፡ ተመንደቡ ።

መከራ ፡ ባገኛቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሰው ፡ ለመኑ ።

ወአድኀኖሙ ፡ እምንዳቤሆሙ ።

እሱም ፡ ከመከራቸው ፡ አዳናቸው ። ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፲፫ ።

፳ ፡ ፈነወ ፡ ቃሎ ፡ ወፈወሶሙ ።

ረድኤቱን ፡ ሰዶ ፡ አዳናቸው ፡ እንድም ፡ ልጁን ፡ በሥጋ ፡ ሰዶ ፡ አዳናቸው ።

ወአድኀኖሙ ፡ እሞቶሙ ።

ከሞተ ፡ ሥጋቸው ፡ እንድም ፡ ከሞተ ፡ ነፍሳቸው ፡ አዳናቸው ። ኢሳ ፡ ፲፱ ፡ ፩ ።

፳፩ ፡ ንገሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሕረቶ ፡ ወመንክራቲሁ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።

የእግዚአብሔርን ፡ ጌትነቱን ፡ ተአምራቱን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ንገሩ ፡ አስተምሩ ።

፳፪ ፡ ወይሡዑ ፡ ሎቱ ፡ መሥዋዕተ ፡ ስብሐት ።

ሡዑ ፡ ካልሁ ፡ ብሎ ፡ መሥዋዕት ፡ ብሒል ፡ እንጂ ፡ የጌትነት ፡ ምስጋና ፡ ያመስግኑት ፡ ሲል ፡ ነው ።

ወይንግሩ ፡ ግብሮ ፡ በትፍሥሕት ።

ሥራውን ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ይንገሩ ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ።

፳፫ ፡ እለ ፡ ይወርዱ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ በአሕማር ።

በመርከብ ፡ ተጭነው ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ የሚሄዱ ፡ ሰዎች ።

ወይትገበሩ ፡ ተግባሮሙ ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡ ብዙኅ ።

ስቶሕ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በስፊ ፡ ውሃ ፡ ላይ ፡ ሁነው ፡ ሥራቸውን ፡

2014 04 17

ይሠራሉ ፤ ሐር ፡ ይጕንጕናሉ ፤ ምንጣፍ ፡ ይታታሉ ፤ ቀለም ፡ ያገባሉ ፤ ነፍጥ ፡ ይጠርጋሉ ፤ ጋሻ ፡ ይሰጕዳሉ ።

፳፬ ፤ እሙንቱስ ፡ የአምሩ ፡ ግብረ ፡ እግዚ አብሔር ።

በየብስ ፡ ካሉ ፡ ይልቅ ፡ በባሕር ፡ ያሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ያውቃሉ ፡ ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ ተ ራራ ፡ ተራራ ፡ ያኽል ፡ ሁኖ ፡ ሲ ነሣ ፡ እያዩ ።

ወመንክርኒ ፡ በውስተ ፡ ልጐት ።

ድንቅ ፡ ሥራውንም ፡ በጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ያውቃሉ ።

፳፭ ፤ ይቤ ፡ ወመጽአ ፡ መንፈስ ፡ ዐውሎ ።

ይብል ፡ ይላል ፤ ጌታ ፡ ጥቅል ፡ ነፋስ ፡ ይምጣ ፡ ብሎ ፡ ያዛል ፤ ይመጣል ።

ወተለዐለ ፡ ማዕበል ።

ወይትሌዐል ፡ በል ፤ ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፤ (ወ ደ ፡ ላይ ፡ ይወጣል) ።

፳፮ ፤ የዐርጉ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ።

ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይዟቸው ፡ ይወ ጣል ።

ወይወርዱ ፡ ውስተ ፡ ቀላይ ።

ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ያወርዳ ቸዋል ።

ወተመሰወት ፡ ነፍሶሙ ፡ በሕማም ።

ትትመሰው ፡ በል ፡ በመከራው ፡ ነፍሳቸው ፡ ከሥጋቸው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ትላለች ፤ ሰውነታቸው ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ ትቀልጣለች ።

፳፯ ፤ ደንገፁ ፡ ወተሀውኩ ፡ ከመ ፡ ስኩር ።

ይደነግፁ ፡ ወይትሀወኩ ፡ በል ፤ እንደ ፡ ሰከረ ፡ ሰው ፡ ደንግጠው ፡ አእምሯቸው ፡ ይለያቸዋል ።

ወተሰጥመ ፡ ኵሉ ፡ ጥበቦሙ ።

ወይሰጠም ፡ ይላል ፤ ጥበባቸው ፡ ሁሉ ፡ ይሰወራቸዋል ፡ ማለት ፤ መልሕቅ ፡ መጣል ፡ ዐሳማ ፡ መት ከል ፡ ይሳናቸዋል ።

፳፰ ፤ ወዐውየዉ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሶበ ፡ ተመንደቡ ። ወአድኀኖሙ ፡ እምንዳቤሆሙ ።

የዐወይዉ ፡ ወያድኅኖሙ ፡ በል ፤ እንዲህ ፡ መከራ ፡ ባገኛቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መል ሰው ፡ ይለምናሉ ፤ እሱም ፡ ካገ ኛቸው ፡ መከራ ፡ ያድናቸዋል ።

፳፱ ፤ አጥፍአ ፡ ለዐውሎ ፡ ወአርመመ ፡ ባ ሕር ።

ያጠፍአ ፡ ወያረምም ፡ ነው ፤ ጥቅ ሉን ፡ ነፋስ ፡ ያጠፋዋል ፤ ባሕሩ ፡ ጸጥ ፡ ይላል ።

ወአርመመ ፡ ማዕበል ።

ወያረምም ፤ ማዕበሉም ፡ ጸጥ ፡ ይላል ።



፴ ፤ ወተፈሥሑ ፡ እስመ ፡ አዕረፉ ።

ወይትፌሥሑ ፡ ከመከራው ፡ ያ ርፉሉ ፤ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወመርሖሙ ፡ ውስተ ፡ መርስ ፡ ኀበ ፡ ፈቀዱ ።

ይመርሖሙ ፡ ነው ፤ ሊሄዱበት ፡ ወደሚወዱት ፡ ወደብ ፡ መርቶ ፡ ያወጣቸዋል ።

እንድም ፡ (እለ ፡ ይወርዱ) ፡ በመ ርከብ ፡ ተጭነው ፡ ወደ ፡ ደሴት ፡ የሚሄዱ ፡ ሰዎች ፡ (ይትጌበሩ) ፡ በደሴት ፡ ሁነው ፡ ሥራቸውን ፡ ይሠራሉ ፤ ተክል ፡ ተክለው ፡ ነው። (እሙንቱስ) ፡ በየብስ ፡ ካሉ ፡ ይልቅ ፡ በደሴት ፡ ያሉ ፡ የእግዚ አብሔርን ፡ ሥራ ፡ ያውቃሉ ፤ ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ ተራራ ፡ ተራራ ፡ ያኽል ፡ ሁኖ ፡ ሲነሣ ፡ እያዩ ። (ወመንክሮሂ) ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ውንም ፡ በደሴት ። (ይቤ) ፡ ጌታ ፡ መከራ ፡ ይምጣ ፡ አለ ፤ መጣ ። (ወተለዐለ) ፡ መከራው ፡ ጸና ። (የዐርጉ) ፡ ለኤልያስ ፡ ለኢ ያሱ ፡ የተለመነህ ፡ አምላክ ፡ ተለመነን ፡ ይላሉ ። (ወይወርዱ ፡ ለሙሴ) ፡ የተለመነህ ፡ አምላክ ፡ ተለመነን ፡ ይላሉ ። (ወተመሰወ ት) ፡ ነፍሳቸው ፡ ከሥጋቸው ፡ በመ ከራው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ እለች። (ደንገፁ) ፡ ደነገፁ ፡ እንደ ፡ ሰከ ረ ፡ ሰው ፡ አእምሯቸው ፡ ተለያ ቸው ፡ (ወተሰጥመ) ፡ የነቢያት ፡ ትንቢታቸው ፡ የካህናት ፡ ትም ርታቸው ፡ ጠፋባቸው ። (ወዐ ውየዉ) ፡ መከራ ፡ በጸናባቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መል ሰው ፡ ለመኑ ። (ወአድኀኖሙ) ፡ እሱም ፡ ልመናቸውን ፡ ሰማቸው ። (አጥፍአ) ፡ ብልጣሶርን ፡ አጠ ፋው ፡ መከራው ፡ ጸጥ ፡ አለ ። (ወአርመመ) ፡ የመከራው ፡ ጽናት ፡ ጸጥ ፡ አለ ። (ወተፈሥሑ) ፡ ከመ ከራ ፡ ሥጋ ፡ ዐርፈዋልና ፡ ደስ ፡ አላቸው ። (ወመርሖሙ) ፡ ሊሄዱ በት ፡ ወደ ፡ ወደዱት ፡ ወደ ፡ ኢየ ሩሳሌም ፡ መርቶ ፡ አወጣቸው ። እንድም ፡ (እለ፡ ይወርዱ)፡ በጎ ያላኑ ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ የሚሄዱ ፡ ትሩፋን ፡ (ይትጌበሩ) ፡ ሥራቸውን ፡ ይሠ ራሉ ። የቆመውን ፡ ይቈርጣሉ ፡ የ ተጋደመውን ፡ ይፈልጣሉ ፤ (እሙ ንቱስ) ፡ በአፍአ ፡ ካሉ ፡ ከለዕን ባቆም ፡ ይልቅ ፡ በከተማ ፡ ያሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ያው ቃሉ ። (ወመንክሮሂ) ፡ ድንቅ ፡ ሥራውንም ፡ በከተማ ፡ ያውቃሉ ። (ይቤ) ፡ ጌታ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ይምጣ አለ ፡ መጣ ። (ወተለዐለ) ፡ ጦሩ ፡ ጸና ። (የዐርጉ) ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥት ፡ ይሆናሉ ። (ወይወርዱ) ፡ ቋሚ ፡ ለጓሚ ፡ ይሆናሉ ። ገብሮ ፡ ገዶ ፡ እመቶ ፡ ወለቶ ፡ ተብለው ፡ ይሰ ይባሉ ። (ወተመስወት) ፡ ሰውነ

ታቸው ፡ በመከራው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ትላለች ። (ደንገፁ) ፡ እንደ ፡ ሰከረ ፡ ሰው ፡ እእምሯቸው ፡ ተለያቸው ። (ወተሰጥመ) ፡ በግራ ፡ እጃቸው ፡ መመከት ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ መወርወር ፡ ይሳናቸዋል ። (ወዐውየዉ) ፡ መከራ ፡ በጸናባቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሰው ፡ ይለምናሉ ። (ወአድኅኖሙ) ፡ እሱም ፡ ካገኛቸው ፡ መከራ ፡ ያድናቸዋል ። (አጥፍአ) ፡ ናቡከደነጾርን ፡ አጠፋው ። (ወአርመመ) ፡ ባሕር ፡ ማዕበል ፡ እንድ ፡ ወገን ፤ መከራው ፡ ጸጥ ፡ አለ ። (ወተፈሥሑ) ፡ ከመከራው ፡ ዐርፈዋልና ፡ ደስ ፡ አላቸው ። (ወመርሖሙ) ፡ ይሄዱበት ፡ ወደ ፡ ወደዱት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መርቶ ፡ አወጣቸው ።

እንድም ፡ (እለ ፡ ይወርዱ) ፡ በጎንያኑ ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ እቶን ፡ እሳት ፡ የሚሄዱ ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ አሉሉን ፡ ለእሕግር ፡ እንዲል ። (ይትጌበሩ) ፡ በእቶን ፡ እሳት ፡ ሁነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግናሉ ። (እሙንቱስ) ፡ ከእቶን ፡ እሳት ፡ በአፍአ ፡ ካሉ ፡ ከነዳንኤል ፡ ይልቅ ፡ በእቶን ፡ እሳት ፡ ያሉ ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ፡የእግዚአብሔርን ፡ ሥራውን ፡ ያውቃሉ ። ተእምራት ፡ ተደርጎላቸው ፡ (ወመንክሮሂ) ፡ ድንቅ ፡ ሥራውንም ፡ በእቶን ፡ እሳት ፡ (ይቤ) ፡ ናቡከደነጾር ፡ ምስል ፡ ይቁም ፡ ብሎ ፡ እዘዘ፤ ቁመቱ ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፡ ደረቱ ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ ጣዖት ፡ በሐቅለ ፡ እዱራን ፡ ቆመ ። (ወተለዐለ) ፡ እሳቱ ፡ እርባ ፡ ዘጠኝ ፡ ክንድ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ተመዞ ፡ ወጣ ። (የዐርጉ) ፡ ይባርክዎ ፡ ሰማያት ፡ ብለው ፡ (ወይወርዱ) ፡ ይባርክዎ ፡ ቀላያት ፡ ብለው ፡ ያመሰግናሉ ። (ወተመስወት) ፡ ሰውነታቸው ፡ በመከራው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ እለች ፤ ለነሱ ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ። (ደንገፁ) ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፤ (ወተሰጥመ) ፡ የባቢሎናውያን ፡ ጥበባቸው ፡ ሁሉ ፡ ተሰወረቻቸው ። ወውስተ ፡ እሳቱስ ፡ ይወድቁ ፡ ፒሳ ፡ እንዲል ። (ወዐውየዉ) ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ መከራ ፡ በጸናባቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሰው ፡ ለመኑ ። (ወአድኅኖሙ) ፡ እሱም ፡ ካገኛቸው ፡ መከራ፡ አዳናቸው ፤ (አጥፍአ) ፡ ዮልማሮዱትን ፡ አጠፋው ፤ (ወአርመመ) ፡ ባሕር ፡ ማዕበል ፡ አንድ፡ ወገን ፡ የመከራው ፡ ጽናት ፡ ጠፋ። (ወተፈሥሑ) ፡ ከመከራው ፡ ዐርፈዋልና ፡ ስላረፉ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤ (ወመርሖሙ) ፡ ይሄዱበት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ወደዱት ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መርቶ ፡



አወጣቸው ። አንትሙ ፡ ሲድራቅ ፡ ወሚሳቅ ፡ ወዐብደናጎ ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንዑ ፡ ፃኡ ፡ ብሏቸዋል ። እንድም ፡ (እለ ፡ ይወርዱ) ፡ በቃለ ፡ መጻሕፍት ፡ ተገሥጸው ፡ ከመምህራን ፡ ቃል ፡ ሰምተው ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ የሚሄዱ ፡ ባሕታውያን ፡ (ይትጌበሩ) ፡ በገዳም ፡ ሁነው ፡ የገዳሙን ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ፡ ተክል ፡ ተክለው ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ይዘው ፡ ራሳቸውን ፡ ረድተው ፡ ይኖራሉ ። (እሙንቱስ) ፡ ካልመነኑት ፡ ይልቅ ፡ የመነኑት፡ የእግዚአብሔርን፡ ሥራ፡ ያውቃሉ ፡ ግርማ ፡ እራዊትን ፡ ጸብአ ፡ አጋንንትን ፡ ዕጸበ ፡ ገዳምን ፡ አያዩ ። (ወመንክሮሂ) ፡ በገዳም ፡ ድንቅ ፡ ሥራውን ፡ ያውቃሉ ። (ይቤ) ፡ ጌታ ፡ ሰይጣን ፡ ለፈተና ፡ ይምጣ ፡ ብሎ ፡ ያዛል ፡ ይመጣል ። (ወይትሌዐል) ፡ ጸብአ ፡ አጋንንት ፡ ይጸናል ፤ (የዐርጉ) ፡ ከፍ ፡ ጺምነት ፡ ይደርሳሉ ። (ወይወርዱ) ፡ ወደ ፡ ወጣኒነት ፡ ይመለሳሉ ። (ወትትመሰው) ፡ ሰውነታቸው ፡ በመከራው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ትላለች ። (ደደንገፁ) ፡ እእምሯቸው ፡ ይለያቸዋል ። (ወይሰጠም) ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ማግተብ ፡ ስመ ፡ ሥላሴ ፡ መጥራት ፡ ይጠፋባቸዋል ። (ወዐውየዉ) ፡ ጸብአ ፡ አጋንንት ፡ በጸናባቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሰው ፡ ለመኑ ። (ወአድኅኖሙ) ፡ እሱም ፡ ከጸብአ ፡ አጋንንት ፡ አዳናቸው ። (አጥፍአ) ፡ ጸብአ ፡ አጋንንትን ፡ አጠፋ ፤ (ወአርመመ) ፡ ባሕር ፡ ማዕበል ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ጸብአ ፡ አጋንንት ፡ ፈጽሞ ፡ ጠፋ ። (ወተፈሥሑ) ፡ ከጸብአ ፡ አጋንንት ፡ ዐርፈዋልና ፡ ስላረፉ ፡ ደስ ፡ አላቸው ። (ወመርሖሙ) ፡ ይሄዱበት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ወደዱት ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መርቶ ፡ አወጣቸው ።

፴፩ ፤ ንገሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሕረቶ ፡ ወመንክሮሂ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።

የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነቱን ፡ ተእምራቱን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ንገሩ ፡ አስተምሩ ።

፴፪ ፤ ወያዑብዩዎ ፡ በማኅበረ ፡ አሕዛብ ።

በአሕዛብ ፡ እንድም ፡ በእስራኤል ፡ ጉባኤ ፡ ያከብሩታል ።

ወይሴብሕዎ ፡ በመንበረ ፡ ሊቃውንት ።

በሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ እንድም ፡ በሐዋርያት ፡ በስብከት ፡ አርድእት ፡ ጉባኤ ፡ ያመሰግኑታል ።

፴፫ ፤ ወረሰዮሙ ፡ ለአፍላግ ፡ በድወ ።

በዬዋዌ ፡ ጊዜ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ወንዞች ፡ የብስ ፡ ያደረጋቸው ፡ እንድም ፡ የልጅነት ፡ መገኛ ፡

2014 04 17

የነበረች ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ልጅ
ነት ፡ እንዳይገኝባት ፡ ያደረገ ፡

ወረሰየ ፡ ምጽማእ ፡ መልበ ፡ ግዳ ።

የውሃ ፡ መገኛ ፡ የነበረች ፡ ኢየሩሳ
ሌምን ፡ በዒዋዌ ፡ ጊዜ ፡ የውሃ ፡
መጽምያ ፡ ያደረገው ፡ ማለት ፡
ውሃ ፡ እንዳይገኝበት ፡ አደረገው ።
እንድም ፡ ልጅነት ፡ ይገኝበት ፡
ትምርት ፡ ይነገርበት ፡ የነበረ ፡
ኢየሩሳሌምን ፡ ልጅነት ፡ እንዳይገ
ኝበት ፡ ትምርት ፡ እንዳይነገር
በት ፡ አደረገ ። ኢሳ ፡ ፲፭ ፡ ፩ ።

፵፬ ፡ ወረሰየ ፡ ለምድር ፡ ጼው ፡ እንተ ፡ ትፈ
ሪ ። ሚክ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።

ኢየሩሳሌምን ፡ ጨው ፡ የምታ
ፈራ ፡ አደረጋት ፡ እንድም ፡ ለም
ድር ፡ እንተ ፡ ትፈሪ ፡ ረስያ ፡ ጼወ ፡
እኽል ፡ ተክል ፡ የምታፈራ ፡ ኢየ
ሩሳሌምን ፡ ጨው ፡ አደረጋት ፡
ማለት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የማታፈራ ፡
አደረጋት ፡ እንድም ፡ የልጅነት ፡
መገኛ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የማይገኝ
ባት ፡ አደረጋት ።
ኤር ፡ ፲፱ ፡ ፩ ።

በእከዮሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብርዋ ።

ወርሰዋት ፡ በሚኖሩ ፡ በእስራ
ኤል ፡ ክፋት ፡ እንድም ፡ በአይ
ሁድ ፡ ክፋት ።

፵፭ ፡ ወረሰየ ፡ ለበድው ፡ ሙሐዘ ፡ ማይ ።

የአሕዛብ ፡ አገር ፡ ባቢሎንን ፡

በዒዋዌ ፡ ጊዜ ፡ የውሃ ፡ መፍሰሻ ፡
አደረገው ፡ ይህስ ፡ አይደለም ፡
ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ ውሃ ፡ አል
ነበረበትም ፡ ማለት ፡ ይሆናል ፡
ብሎ ፡ በዒዋዌ ፡ ጊዜ ፡ የባስ ፡
የነበረች ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በሚ
ጠት ፡ ጊዜ ፡ የውሃ ፡ መፍሰሻ ፡
አደረጋት ። እንድም ፡ የልጅነት ፡
የትምርት ፡ መገኛ ፡ አደረጋት ።

ወለምድረ ፡ በድው ፡ ቀላያተ ፡ ማያት ።

ምድረ ፡ በዳ ፡ ሁኖ ፡ የነበረ ፡
ኢየሩሳሌምን ፡ የውሃ ፡ መገኛ ፡
አደረገው ፡ እንድም ፡ ልጅነት ፡
ትምርት ፡ ታጥቶበት ፡ የነበረ ፡
ኢየሩሳሌምን ፡ የልጅነት ፡ የት
ምርት ፡ መገኛ ፡ አደረገው ።
ኢሳ ፡ ፵፩ ፡ ፲ ፡ ፶፩ ፡ ፲፰ ።

፵፮ ፡ አንበረ ፡ ሀየ ፡ ርኁባነ ።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ ተይዘው ፡ የነበሩ ፡
ትሩፋንን ፡ ከዚያ ፡ አኖራቸው ።
እንድም ፡ (ርኁባን) ፡ ሐዋርያትን ፡
በመምርነት ፡ ከዚያ ፡ አኖራቸው ።

ሐነጹ ፡ አህጉረ ፡ ኅበ ፡ ይነብሩ ።

ቤት ፡ ሠሩ ፡ አገር ፡ አቀኑ ፡ እን
ድም ፡ ለዘላለም ፡ የሚኖሩባት ፡
መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በወን
ጌል ፡ አዘጋጁ ።

፵፯ ፡ ተከሉ ፡ ወይነ ፡ ወዘርኡ ፡ ገራውህ ።
ኤር ፡ ፵፩ ፡ ፭ ።

ወይንን ፡ ተከሉ ፡ ዘርንም ፡ በእ



ርሻቸው ፡ ላይ ፡ ዘሩ ። እንድም ፡
ሐዋርያት ፡ አስተማሩ ፡ አሳመኑ ፡
አጠመቁ ።

ወገብሩ ፡ ማእረረ ፡ እክለ ።

መከር ፡ አበጁ ፡ እንድም ፡ ከፍ
ጹምነት ፡ አደረሱ ።

፵፰ ፡ ባረኮሙ ፡ ወበዝኁ ፡ ፈድፋደ ።

አከበራቸው ፡ አበዛቸው ፡ ፈጽ
መው ፡ በዙ ።

ወእያውኅደ ፡ ሎሙ ፡ እንስሳሆሙ ።

ከብቶቻቸውን ፡ እንድም ፡ መም
ሮቻቸውን ፡ አላሳነሰባቸውም ።
ወእደ ፡ አልቦ ፡ አልሕምት ፡ ምዕ
ንጋዕ ፡ ንጹሕ ፡ ወእደ ፡ ብዙኅ ፡
እከል ፡ ይትበወቅ ፡ እምኀይለ ፡
ላሕሙ ፡ እንዲል ።

፵፱ ፡ ደወዩ ፡ ወውኅዱ ።

ብሉዩን ፡ ይዞ ፡ ይሄዳል ፡ የሞት ፡
ደዌ ፡ ታመሙ ፡ አንስንስ ፡ አሉ ።

በሕማም ፡ እኩይ ፡ ወበጻዕር ፡ ኢሳ ፡ ፶፬ ፡ ፭ ።

በዒዋዌ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤል ፡ በሚ
ጠት ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ጠፉ ።

፶ ፡ ወተክዕወ ፡ ኅሳር ፡ ዲበ ፡ መላእክት ።

ባለቆቹ ፡ መቅሠፍት ፡ በዝቶ ፡
ታዘዘባቸው ።

ወአስሐቶሙ ፡ ውስተ ፡ በድው ፡ ዘእኮነ ፡
ፍኖት ።

መንገድ ፡ ባይደለ ፡ በምድረ ፡

በዳ ፡ አቅበዘበዛቸው ። እንድም ፡
(ወአሥነቶሙ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡
ዘእኮነ ፡ በድወ) ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
ባይደለ ፡ መንገድ ፡ አሳረፋቸው ።
ኢሳ ፡ ፴፫ ፡ ፮ ፡ ፰ ።

፶፩ ፡ ወረድአ ፡ ለነዳይ ፡ በተጽናሱ ።

በተጽናሱ ፡ ዘሩባቤልን ፡ በችጋሩ ፡
ጊዜ ፡ አሳረፈው ።

ወረሰየ ፡ ከመ ፡ አባግዐ ፡ ብሔር ።

እንደ ፡ አገር ፡ በጎች ፡ ያደረገው ፡
እሱ ፡ ነው ። እንድም ፡ እንዳገር ፡
መንጋ ፡ አደረገው ። ያ ፡ ሲወጣ ፡
ደስ ፡ እንዲያሰኝ ፡ ደስ ፡ አሰኘው ።

፶፪ ፡ ይርአዩ ፡ ራትዓን ፡ ወይትፌሥሑ ።

ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ይህን ፡ አይ
ተው ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ። እንድም ፡
ደስ ፡ ይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡
ይዩ ።

ወትትፈፀም ፡ አፋተ ፡ ዙሉ ፡ ዐመፃ ።

ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ እንገዛቸ
ዋለን ፡ የሚሉ ፡ የባቢሎናውያን ፡
አንደበት ፡ ምላሽ ፡ ታጣለች ።

፶፫ ፡ መኑ ፡ ጠቢብ ፡ ዘየዐቅቦ ፡ ለዝ ።

ይህን ፡ የሚያስተውለው ፡ ብልኅ ፡
ዐዋቂ ፡ ማነው ፡ እያለ ፡ የሰውን ፡
ልቡና ፡ ያነቃቃል ።

ወየአምር ፡ ከመ ፡ መሐሪ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ቸር ፡
እንደሆነ ፡ የሚያውቅ ፡ ማነው ፡
እያለ ። ሆሴ ፡ ፲፬ ፡ ፱ ።

2014 04 17

## መዝሙር ፡ ፻፯ ።

፩ ፡ ጥቡዕ ፡ ልብየ ፡ እግዚኦ ፡ ጥቡዕ ፡ ልብየ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናገሮታል ፡ አቤቱ ፡ ልቡናዬ ፡ ትጉህ ፡ ነው ።

ጥቡዕ ፡ ልብየ ፡ እሴብሕ ፡ ወእዜምር ።

ልቡናዬ ፡ ትጉህ ፡ ነው ፡ እኔም ፡ ፈጽሜ ፡ አመሰግናለሁ ።

ወይትነሣእ ፡ ክብርየ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ክብሬ ፡ ይመለስልኛል ።

፪ ፡ ወእትነሣእ ፡ በመዝሙር ፡ ወበመሰንቆ ።

በገናዬን ፡ መሰንቆዬን ፡ ይዤ ፡ እነሣለሁ ።

ወእትነሣእ ፡ በጽባሕ ።

ፈጥኜ ፡ እነሣለሁ ።

፫ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ በውስተ ፡ አሕዛብ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ በአሕዛብ ፡ ጉባኤ ፡ እገዛልሃለሁ ።

ወእዜምር ፡ ለከ ፡ በውስተ ፡ ሕዝብ ።

በሕዝቡም ፡ ጉባኤ ፡ ምስጋና ፡ አቀርብልሃለሁ ።

፬ ፡ እስመ ፡ ዐብየት ፡ እስከ ፡ ሰማያት ፡ ምሕረትከ ።

ቸርነትህ ፡ በዝታ ፡ ተደርጋለችና ።

ወእስከ ፡ ደመናት ፡ ጽድቅከ ።

ይቅርታህም ፡ እስከ ፡ ደመና ፡ ደርሳለችና ።

፭ ፡ ተለዐል ፡ እግዚአብሔር ፡ መልዕልተ ፡ ሰማያት ።

እግዚአብሔር ፡ አሕዛብን ፡ አጥፍቶ ፡ እስራኤልን ፡ ታድጎ ፡ ልዕልናውን ፡ ገለጸ ።

ወበኵሉ ፡ ምድር ፡ ስብሐቲሁ ።

ጌትነቱም ፡ ባራቱ ፡ መእዝን ፡ ተነገረ ።

፮ ፡ ከመ ፡ ይድኀኑ ፡ ፍቁራኒከ ።

ወዳጆችህ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ።

አድኅን ፡ በየማንከ ፡ ወስምዐኒ ።

ልመናዬን ፡ ሰምተህ ፡ በሥልጣንህ ፡ አድነኝ ።

፯ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነበበ ፡ በመቅደሱ ።

እግዚአብሔር ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ አድሮ ፡ ተናገረ ።

እትሐሠይ ፡ ወእትካፈል ፡ ሰቂማ ።

ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ምርኮውን ፡ እካፈላለሁ ፡ ምህርካ ፡ ያለውን ፡ ሰቂማ ፡ አለው ።

ወእሳፈር ፡ አዕጻዳተ ፡ ቈላት ።

የአሕዛብን ፡ አውራጃ ፡ እሰፍር ባታለሁ ።



፰ ፡ ዚአየ ፡ ውእቱ ፡ ገለዓድ ፡ ወዚአየ ፡ ምናሴ ።

ነገደ ፡ ገለዓድ ፡ ነገደ ፡ ምናሴ ፡ የኔ ፡ ወገን ፡ ነው ።

ወኤፍሬም ፡ ሰዋቀ ፡ ርእስየ ።

ምስማክ ፡ ርእስየ ፡ ያለውን ፡ ሰዋቀ ፡ ርእስየ ፡ አለው ። ነገደ ፡ ኤፍሬም ፡ መጠጊያዬ ፡ ነው ።

ወይሁዳ ፡ ንጉሥየ ።

ነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ንጉሤ ፡ ነበር ።

፱ ፡ ወሞአብ ፡ ካህን ፡ ተስፋየ ።

ካህን ፡ ሞአብም ፡ አገልጋዬ ፡ ነበር ።

ዲበ ፡ ኤዶምያስ ፡ እሰፍሕ ፡ መከየድየ ።

እግሬን ፡ በኤዶምያስ ፡ ላይ ፡ እዘረጋ ፡ ነበር ።

ሊተ ፡ ይገንዩ ፡ ኢሎፍሊ ።

ኢሎፍላውያን ፡ ለኔ ፡ ይገዙ ፡ ነበር ።

፲ ፡ መኑ ፡ ይወስደኒ ፡ ሀገረ ፡ ጥቅም ።

ወደ ፡ ጥቅመ ፡ እያሪኮ ፡ ማን ፡ በወሰደኝ ።

ወመኑ ፡ ይመርሐኒ ፡ እስከ ፡ ኤዶምያስ ።

እስከ ፡ ኤዶምያስ ፡ መርቶ ፡ ማን ፡ ባወጣኝ ።

፲፩ ፡ አኮኑ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ዘገደፍከነ ።

አቤቱ ፡ በመከራ ፡ የጣልከን ፡ አንተ ፡ አይደለህምን ።

ወኢትወፅእ ፡ እግዚኦ ፡ ምስለ ፡ ኀይልነ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ከኀይላችን ፡ ከሰራዊታችን ፡ ጋራ ፡ የማትመጣ ፡ ሆንክ ።

፲፪ ፡ ሀበነ ፡ ረድኤተ ፡ ለምንዳቤነ ።

ለመከራችን ፡ ረዳት ፡ ስጠን ።

ወከንቱ ፡ ተአምኖ ፡ በሰብእ ።

በሰው ፡ ማመን ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

፲፫ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ንገብር ፡ ኀይለ ።

በእግዚአብሔር ፡ አምነን ፡ ኀይል ፡ እናደርጋለን ፡ እንጂ ።

ወውእቱ ፡ ያኀስሮሙ ፡ ለእለ ፡ ይሣቅዩነ ።

መከራ ፡ የሚያጸኑብንን ፡ ሁሉ ፡ እሱ ፡ ያጠፋቸዋል ።

## መዝሙር ፡ ፻፰ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ ኢትጸመመኒ ፡ ስብሐትየ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናገሮታል ።

፪ ፡ እስመ ፡ አፈ ፡ ዐማፂ ፡ ወአፈ ፡ ኃጥእ ፡ አብቀዉ ፡ ላዕሌየ ።

ተበቅዉ ፡ ቢል ፡ ይቀናል ፡ የኃጥአን ፡ የዐማፅያን ፡ የባቢሎናውያን ፡ ነገር ፡ በዝቶብኛልና ። አንድም ፡ ኃጥአን ፡ ዐማፅያን ፡ የሚሆኑ ፡ ባቢሎናውያን ፡ ነገራቸውን ፡ አብዝተውብኛልና ።

ወነበቡ ፡ ላዕሌየ ፡ በልሳነ ፡ ዐመፃ ።

በኔ ፡ በመዕን ፡ በሚናገር ፡ አንደ
በት ፡ ይናገራሉ ።

፫ ፡ ወገቱኒ ፡ በጽልእ ።

በጸብ ፡ ከበቡኝ ፤ በፍቅር ፡ መከ
በብ ፡ አለና ።

ወጸብኡኒ ፡ በከንቱ ።

በግፍ ፡ ተጸሉኝ ።

፬ ፡ ዘእምአፍቀሩኒ ፡ አስተዋደዩኒ ።

ከወደዱኝ ፡ ይልቅ ፡ እንደ ፡ መው
ደድ ፡ ሁሉ ፡ መውደድን ፡ ይመ
ስል ፡ እንድም ፡ ከመውደድ ፡ ወጥ
ተው ፡ አማሉኝ ፡ አዋቀሡኝ ፤
አካሰሱኝ ።

ወአንሰ ፡ እጼሊ ።

ሎሙ ፡ ያለበት ፡ ነው ፤ እኔ ፡
ግን ፡ እጸልይላቸዋለሁ ፤ ሊቀ ፡
ካህናት ፡ ናውና ።

፭ ፡ ፈደዩኒ ፡ እኪተ ፡ ህየንተ ፡ ሠናይት ።

በጎስ ፡ ስላደረግሁላቸው ፡ የከ
ፋት ፡ ብድራት ፡ ከፈሉኝ ።

ወጸልኡኒ ፡ ህየንተ ፡ ዘአፍቀርኩክምሙ ።

ስለ ፡ ወደድኋቸው ፡ ፈንታ ፡ ጸሉኝ ፤
አሁን ፡ እኔ ፡ ምን ፡ አላለሁ ።

፮ ፡ ሢም ፡ ላዕሌሁ ፡ ኃጥአ ።

ባዕድ ፡ ንጉሥ ፡ እንግሥባቸው ።
እንድም ፡ በይሁዳ ፡ ዕፃ ፡ ባዕድ ፡
ማትያስን ፡ ሹምበት ። በኃጥእ ፡
ስፍራ ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ ኃጥእ ፡
አለው ።

ወሰይጣን ፡ ይቁም ፡ በየማኑ ።

በአንጥያኮስ ፡ ጽኑ ፡ ባለጋራ ፡ ይ
ቁም፡ይነሣበት።ወእቀመ ፡ አጼርሃ ፡
ሰይጣነ ፡ ላዕለ ፡ ሰሎሞን ፡ እን
ዲል ። እንድም ፡ በይሁዳ ፡ ሰይጣ
ን ፡ ይደርበት ።

፯ ፡ ወሶበሂ ፡ ይትዋቀሥ ፡ ይፃእ ፡ ተመዊኦ ።

በተጸላ ፡ በተከራከረ ፡ ጊዜ ፡
ተረትቶ ፡ ተመትቶ ፡ ይመለስ ።

ወጸሎቱሂ ፡ ትኩኖ ፡ ጌጋየ ።

ልመናው ፡ ዕዳ ፡ በደል ፡ ትሁን
በት ።

፰ ፡ ወይኩና ፡ መዋዕሊሁ ፡ ኅዳጠ ።

ዘመኑም ፡ ይነስ ፤ ኃጥእ ፡ ዘመ
ኑን ፡ አይፈጽምምና ።

ወሢመቶሂ ፡ ይንሣእ ፡ ባዕድ ።

መንግሥቱንም ፡ ባዕድ ፡ ንጉሥ ፡
ይውሰድበት ። እንድም ፡ የይሁ
ዳን ፡ ሀገረ ፡ ስብከቱን ፡ ባዕድ ፡
ማትያስ ፡ ይውሰድበት ። ግብ ፡
፩ ፡ ፳ ።

፱ ፡ ወይኩኑ ፡ ደቂቁ ፡ ዕጓለ ፡ ማውታ ።

ያንጥያኮስ ፡ ልጆቹ ፡ የይሁዳ ፡
ወገኖቹ ፡ ድኻች ፡ (ድኻ ፡ አደግ) ፡
ይሁኑ ።



ወብእሲቱሂ ፡ ትኩን ፡ መበለተ ።

ያንጥያኮስ ፡ ሚስቱ ፡ የይሁዳ ፡
ወገኑ ፡ ድኻ ፡ አደግ ፡ ትሁን ።

፲ ፡ ይትሀወኩ ፡ ደቂቁ ፡ ይፍልሱ ፡ ወያስተ
ፍእሙ ።

ያንጥያኮስ ፡ ልጆቹ ፡ የይሁዳ ፡
ወገኖቹ ፡ ይታወኩ ፤ ከሀገራቸው ፡
ወጥተው ፡ አፍ ፡ ሙሉ ፡ ቍራሽ ፡
ለመቀላወጥ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ አገር ፡
ተሰደው ፡ ይሂዱ ። እንድም ፡
የሚያቀላውጣቸው ፡ አጥተው ፡
ይሙቱ ።

ወይስድድዎሙ ፡ እምአብያቲሆሙ ።

እንቀላውጣለን ፡ ብለው ፡ ከሄ
ዱበት ፡ ቤታቸው ፡ አስወጥተው ፡
ይስደዷቸው ። እንድም ፡ ከራሳ
ቸው ፡ ቤት ፡ አስወጥተው ፡ ይስ
ደዷቸው ። እንድም ፡ ሥላሴ ፡
አይሁድን ፡ ከሀገራቸው ፡ ከኢ
የሩሳሌም ፡ አስወጥተው ፡ ይስ
ደዷቸው ። እንድም ፡ ከገነት ፡
ከመንግሥት ፡ ሰማያት ፡ አስወጥ
ተው ፡ ይስደዷቸው ። ኤር ፡ ፲፰ ፡ ፳፯ ።

፲፩ ፡ ወይበረብሮ ፡ በዓለ ፡ ዕዳ ፡ ኵሎ ፡ ን
ዋዮ ።

ባለጋራ ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ይዝ
ረፈው ። እንድም ፡ ይሁዳን ፡
ባለጋራው ፡ ማትያስ ፡ ይዝረፈ
ው ፡ ማለት ፤ ሀገረ ፡ ስብከቱን ፡
ይውሰድበት ፤

ወየሐብልዮ ፡ ነኪር ፡ ኵሎ ፡ ተግባሮ ።

የአፍአውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ባ
ዕድ ፡ ይውሰድበት ። እንድም ፡
ማትያስ ፡ ክብሩን ፡ ይውሰድበት ።

፲፪ ፡ ወኢይርከቦ ፡ ዘይረድኦ ።

በከብት ፡ በጕልበት ፡ የሚረዳው ፡
አይኑር ፤ አያግኝ ።

ወኢይምሐርዎሙ ፡ ለዕጓለ ፡ ማውታሁ ።

ያንጥያኮስን ፡ ልጆቹን ፡ የይሁዳን ፡
ወገኖቹን ፡ አይዘኑላቸው ፡ አይራሩ
ላቸው ፡ ሥላሴ ፡ ይቅር ፡ አይበ
ሏቸው ።

፲፫ ፡ ወይሠረዉ ፡ ደቂቁ ።

ያንጥያኮስ ፡ ልጆቹ ፡ የይሁዳ ፡
ወገኖቹ ፡ ይጥፉ ።

በአሐቲ ፡ ትውልድ ፡ ትደምሰስ ፡ ስሙ ።

ያንጥያኮስ ፡ ስሙ ፡ ባንዲት ፡
ትውልድ ፡ ትጥፋ ፤ ምነው ፡
ልጅ ፡ ወልዶ ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡
ልጁ ፡ ልጅ ፡ ስላልወለደ ፤ የይሁዳ ፡
የተመቸ ።

፲፬ ፡ ወትዘከር ፡ ኃጢአተ ፡ አቡሁ ፡ በቅድ
መ ፡ እግዚአብሔር ።

ያባቱ ፡ ኃጢአት ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ ትታሰብ ።

ወኢይደምስስ ፡ ጌጋያ ፡ ለእሙ ።

የናቱም ፡ ኃጢአት ፡ አይሰረይ
ላት ። እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ስለ፡ምን ፡

2014 04 17

ቢሉ ፡ እነሱም ፡ እሱን ፡ መስለ
ው ፡ ከሥሩ ፡ ብሎ ።

፲፭ ፡ ወየሀሉ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘልፈ ፡ ጊዜ ።

ሁል ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ይታሰብ ፡ ይታሰብ ፡ እን
ጂ ፡ አይደምሰስ ።

ወይትሐጐል ፡ እምድር ፡ ዝክሩ ።

ስም ፡ አጠራሩ ፡ ከሰው ፡ ተለ
ይቶ ፡ እንድም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡
ይጥፋ ። ኢዮ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ። ምሳ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ።

፲፮ ፡ እስመ ፡ ኢተዘከረ ፡ ይግበር ፡ ምጽዋተ ።

እንጥያኮስ ፡ ምጽዋትን ፡ ይመ
ጸውት ፡ ዘንድ ፡ አላሰበምና ።
እኮ ፡ ዘያጽሕቆ ፡ ምሕረ ፡ ነዳ
ያን ፡ አባ ፡ እስመ ፡ ሰራቂ ፡ ው
እቱ ፡ የዐቅብ ፡ አስከሬን ፡ እን
ዲል ።

ሰደደ ፡ ብእሴ ፡ ነዳየ ፡ ወምስኪነ ።

ነዳይ ፡ ምስኪን ፡ የሚሆን ፡ መቅ
ቢስን ፡ አስወጥቶ ፡ ሰደደና ።
እንድም ፡ ይሁዳ ፡ አይሁድ ፡ ነ
ዳይ ፡ ምስኪን ፡ የሚሉት ፡ ጌታ
ን ፡ በሞት ፡ አስወጥቶ ፡ ሰደ
ልና ።

ቀተሎ ፡ ልበ ፡ ለቀቲል ።

ያንጥያኮስ ፡ ልቡናው ፡ ለመግ
ደል ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ እንድም ፡ የይ
ሁዳ ፡ ልቡናው ፡ ጽኑ ፡ ነው ።
ኢዮ ፡ ፩፻ ፡ ፮ ። ኤር ፡ ፶፰ ፡ ፲፱ ።

፲፯ ፡ ዘአብደራ ፡ ለመርገም ፡ ወትምጽኦ ።

መርገምን ፡ የመረጣት ፡ የወደ
ዳት ፡ እሱ ፡ ነው ፡ እንዲህም ፡
ከሆነ ፡ ትምጻበት ። እንድም ፡
ዘአብደራ ፡ መርገም ፡ ለትምጽ
እ ፡ የመረጣት ፡ የወደዳት ፡ መር
ገም ፡ ትምጣበት ።

ዘአበያ ፡ ለበረከት ፡ ወትርሐቅ ፡ እምኔሁ ።

በረከትን ፡ አልቀበልም ፡ ያላት ፡
እሱ ፡ ነው ፡ እንዲህም ፡ ከሆነ ፡
ትለየው ። እንድም ፡ ዘአበያ ፡
በረከት ፡ ለትርሐቅ ፡ እምኔሁ ፡
አልቀበልም ፡ ያላት ፡ በረከት ፡
ትለየው ።

፲፰ ፡ ወለብሳ ፡ ለመርገም ፡ ከመ ፡ ልብስ ።

ይልበሳ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ መርገ
ምን ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ ይጐናጸፋት ።

ወቦአ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ውስተ ፡ አማዑቱ ።

ይባእ ፡ በል ፡ ውሃ ፡ ከሰውነት ፡
ገብቶ ፡ እንዲስማማ ፡ መር
ገምም ፡ ከሰውነቱ ፡ ይስማማ ።

ወከመ ፡ ቅብዕ ፡ ውስተ ፡ አዕፅምቲሁ ።

ዘይት ፡ ቅቤ ፡ ከሰውነት ፡ እንዲ
ስማማ ፡ መርገም ፡ ይስማማው ።

፲፱ ፡ ለትኩኖ ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ ዘይትዐጸፍ ።

እንደሚጐናጸፉት ፡ ሸማ ፡ ትሁ
ንበት ፡ ማለት ፡ ያ ፡ ከአካል ፡
እንዳይለይ ፡ አትለየው ።



ወከመ ፡ ቅናት ፡ ዘይቀንት ፡ ዘልፈ ።

ዘወትር ፡ አዙረው ፡ አዙረው ፡
እንደሚታጠቁት ፡ ድግ ፡ ትሁ
ንበት ፡ ያን ፡ መልሰው ፡ መል
ሰው ፡ እንደ ፡ ታጠቁት ፡ ሁል ፡
ጊዜ ፡ አትለየው ።

፳ ፡ ዝ ፡ ግብር ፡ ለእለ ፡ ያስተዋድዩኒ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

ዝ ፡ መርገም ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ይህ ፡
መርገም ፡ እኔን ፡ ከእግዚአብ
ሔር ፡ ጋራ ፡ በሚያጣሉኝ ፡ በሚ
ያሳጡኝ ፡ በጠላቶቼ ፡ ይሁንባ
ቸው ።

ወለእለ ፡ ይነቡ ፡ እኩየ ፡ ላዕለ ፡ ነፍስየ ።

በሰውነቴ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ በሚ
ናገሩብኝ ፡ ሁሉ ፡ ይሁንባቸው ።

፳፩ ፡ አንተሰ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚኦየ ፡ ግበር ፡ ምሕረከ ፡ ላዕሌየ ፡ በእንተ ፡ ስምከ ።

ሊቀስ ፡ በል ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡
ለኔ ፡ ግን ፡ ስምየኒ ፡ መሐሬ ፡
ወመስተሣህል ፡ ስላልህ ፡ ቸር
ነትህን ፡ አድርግልኝ ።

እስመ ፡ ሠናይ ፡ ምሕረትከ ።

ቸርነትህ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡
ነውና ።

፳፪ ፡ አድኅነኒ ፡ እስመ ፡ ነዳይ ፡ ወምስኪን ፡ አነ ።

እኔ ፡ ነዳይ ፡ ምስኪን ፡ ነኝና ፡
አድነኝ ።

ልብየኒ ፡ ደንገፀኒ ፡ በውስቴትየ ።

ልብየ ፡ በውስጥየ ፡ በሰውነቴ ፡
ያለ ፡ ልቡናዬ ፡ ደነገፀብኝ ፡
ማለት ፡ አእምሮዬ ፡ ተለየኝ ።

፳፫ ፡ ወኀለቁ ፡ ከመ ፡ ጽላሎት ፡ በኀልፈ ።

እንዳለፈ ፡ ጥላ ፡ ሆንሁ ፡ ያ ፡
ታይቶ ፡ እንዲጠፋ ፡ በመከራው ፡
ተፈጸምሁ ።

ወተነገፍኩ ፡ ከመ ፡ አንበጣ ።

ውርጭ ፡ እንዳደረበት ፡ አንበጣ ፡
በመከራ ፡ ረገፍሁ ። አንበጣ ፡
ከቦታው ፡ ከወጣ ፡ አይመለስ
ም ፡ በየበረሓው ፡ ረግፎ ፡ ይቀ
ራል ። እኔም ፡ እንደዚያ ፡ ባለ
መከራ ፡ ሆንሁ ።

፳፬ ፡ ወደከመ ፡ ብረክየ ፡ በጾም ።

ብርክ ፡ ሥጋዬ ፡ በቀጠና ፡ ደከመ ።

ወስሕከ ፡ ሥጋየ ፡ በኀጢአ ፡ ቅብዕ ።

ሰውነቴ ፡ ዘይት ፡ ባለመብላት ፡
ቅቤ ፡ ባለመጠጣት ፡ ሻከረ ፡ ማ
ለት ፡ ጐሰቈለ ። ኢሳ ፡ ፳፬ ፡ ፲፯ ።

፳፭ ፡ ወአንሰ ፡ ተጽዕልኩ ፡ በኀቤሆሙ ።

እኔ ፡ ግን ፡ በሳቸው ፡ ዘንድ ፡
የተሰደብሁኝ ፡ ሆንሁ ።

ሶበ ፡ ይሬእዩኒ ፡ የሐውሱ ፡ ርእሶሙ ።

ባዩኝ ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸውን ፡ ይነ
ቀንቁብኛል ።



2014 04 17

፳፮ ፡ ርድአኒ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ።

እቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ርዳኝ ።

ወአድኅነኒ ፡ በእንተ ፡ ምሕረትከ ።

ስዶ ፡ ቸርነትህም ፡ አድነኝ ።

፳፯ ፡ ወያእምሩ ፡ ከመ ፡ እዴከ ፡ ይእቲ ፡ ዛቲ ።

ይህቺ ፡ ሥልጣንህ ፡ በኔ ፡ መከራ ፡ እንዳመጣችብኝ ፡ በሳቸውም ፡ መከራ ፡ እምጥታባቸው ፡ በፍዳ ፡ ይወቋት ። እንድም ፡ ያስማረከችኝ ፡ ይህቺ ፡ ሥልጣንህ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ እነሱም ፡ ይወቁ ።

አንተሰ ፡ እግዚኦ ፡ ገበርከ ።

እቤቱ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ አትራገሙ ፡ አትሳደቡ ፡ ብለህ ፡ ሥራት ፡ ሠርተህ ፡ ነበር ።

፳፰ ፡ እሙንቱሰ ፡ ይረግሙ ፡ ወአንተ ፡ ባርከ ።

እሳቸው ፡ ይሳደባሉ ፡ ይረግማሉ ፡ (ወአንተ) ፡ አንተ ፡ ግን ፡ አከብር ፡ አብዛ ።

ይትኀፈሩ ፡ እለ ፡ ይትነሥኡ ፡ ላዕሌየ ።

በጸላትነት ፡ የሚነሡብኝ ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ ፤ ይዋረዱ ። እንድም ፡ ያፍራሉ ፤ ይዋረዳሉ ።

ወተፈርከሰ ፡ ይትፌሣሕ ።

ባሪያህ ፡ መቃቢስ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ደስ ፡ ይበለው ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ።

፳፱ ፡ ወይልበሱ ፡ ኀፍረተ ፡ ወኀሣረ ፡ እለ ፡ ያስተዋድዩኒ ።

እኔን ፡ የሚያጸሉኝ ፡ ግን ፡ ኀፍረትን ፡ ተዋርዶን ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ ይጐናጸፉ ።

ወይትዐጸፍዋ ፡ ከመ ፡ ዐጽፍ ፡ ለኀጢአቶሙ ።

ኀጢአታቸውን ፡ እንደ ፡ ዐጽፍ ፡ ይጐናጸፏት ። እንድም ፡ በፍዳ ፡ ይቅመሷት ።

፴ ፡ እገኒ ፡ በአፉየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፈድፋደ ።

ለእግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ባንደበቴ ፡ ፈጽሜ ፡ እመሰግናለሁ ።

ወእሴብሖ ፡ በማእከለ ፡ ብዙኀ ።

በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ መኻል ፡ አመሰግነዋለሁ ።

፴፩ ፡ እስመ ፡ ቆመ ፡ በየማነ ፡ ነዳይ ።

በይሁዳ ፡ መቃቢስ ፡ በስተቀኝ ፡ በረድኤት ፡ ተገለጸ ።

ከመ ፡ ያድኅና ፡ ለነፍስየ ፡ እምእለ ፡ ሮድዋ ።

ሰውነቴን ፡ ከከበቧት ፡ ከጽርአውያን ፡ ያድናት ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ (እስመ ፡ ቆመ) ፡ ጌታ ፡ በፈያታዊ ፡ ዘፀጋም ፡ ቀኝ ፡ በፈያታዊ ፡ ዘየማን ፡ ግራ ፡ ተሰቀለ ። (ከመ ፡ ያድኅና) ፡ ነፍሴን ፡ ከከበቧት ፡ አጋንንት ፡ ያድናት ፡ ዘንድ ።



መዝሙር ፡ ፳፱ ።

፩ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ለእግዚእየ ፡ ንበር ፡ በየማንየ ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ዳረቅ ፡ ሐዲስ ፡ ይባላል ። ጌታዬ ፡ አብ ፡ ጌታዬ ፡ ወልድን ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ። እሁን ፡ በሥላሴ ፡ ቀኝ ፡ ግራ ፡ ኑሮባቸው ፡ አይደለም ፤ ዕሪናቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ። ንበር ፡ ማለቱ ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ እንግድነት ።

እስከ ፡ እትብእሙ ፡ ለጸላእትከ ፡ ታሕተ ፡ መከየደ ፡ እገሪከ ።

ጠላቶችህን ፡ በግርህ ፡ ርግጥ ፡ በእጅህ ፡ ጭብጥ ፡ አድርጌ ፡ እስካስገዛልህ ፡ ድረስ ፡ ንበር ፡ አለው ፡ (ሐ) ፡ መከየደ ፡ እግር ፡ እንድ ፡ ወገን ፡ ሥልጣን ፡ ምእመናን ፡ መላእክት ፤ ጸላእት ፡ አይሁድ ፡ መናፍቃን ፤ አጋንንት ፡ ግዳይ ፡ ይጥሏቸዋልና ። ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፵፬ ። ማር ፡ ፲፪ ፡ ፴፮ ። ሉቃ ፡ ፳ ፡ ፵፪ ። ግብ ፡ ፪ ፡ ፴፰ ።

፪ ፡ በትረ ፡ ኀይል ፡ ይፌኑ ፡ ለከ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምጽዮን ።

እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ኀይል ፡ ያለው ፡ ሥልጣንን ፡ ከጽዮን ፡ ሰማያት ፡ ይልክልኻል ፡ ማለት ፤ ገንዘብ ፡ ያደርግልኻል ። እንድም ፡ በማሕፀነ ፡ ማርያም ፡ በተዋሕዶ ፡ አምላክነትን ፡ ይሰጥኻል ፤ ይፈኑ ፡ አለ ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ እንግድነት ። እንድም ፡ በትረ ፡ ኀይል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ይልክልኻል ፡ ማለት ፤ ለምስክርነት ። አሚሃ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ዘበአማን ፡ ወወልድ ፡ ዘበአማን ፡ እንዲል ።

ወትኴንን ፡ በማእከለ ፡ ጸላእትከ ።

በጸላቶችኽ ፡ በአይሁድ ፡ በመናፍቃን ፡ በአጋንንት ፡ ትፈርድ ፡ ዘንድ ። መዝ ፡ ፪ ፡ ፮ ። ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፩ ። ዳን ፡ ፮ ፡ ፲ ። ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፶፱ ። ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፳፪ ። ራእ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።

፫ ፡ ምስሌከ ፡ ቀዳማዊ ፡ በዕለተ ፡ ኀይል ።

ቀዳማዊ ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ በዕለተ ፡ ፍጥረት ፡ ነበረ ። ይህስ ፡ አይደለም ፤ ስሚው ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ፍጥረት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበር ። እንድም ፡ ወልድ ፡ ቀዳማዊ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ፍጥረት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበር ። ይህን ፡ ዓለም ፡ እምኀበ ፡ አልቦ ፡ ኀበ ፡ ቦ ፡ አምጥቶ ፡ ፈጥሮበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ።

2014 04 17

በብርሃናሙ ፡ ለቅዱሳን ።

በቅዱሳሆሙ ፡ ለመላእክት ፡ ሲል፡ ነው ፡ መላእክት ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ብለው ፡ ባመስገኑበት ፡ ቀን ። ወዝንቱ ፡ ብርሃን ፡ ኮኖሙ ፡ ጥበበ ፡ ወአእምሮ ፡ እንዲል ።

ወለድኩከ ፡ እምከርሥ ፡ እምቅድመ ፡ ኮከብ ፡ ጽባሕ ።

ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ አስቀድሞ ፡ ባሕርይ ፡ ዘእምባሕርይ ፡ አካል ፡ ዘእምአካል ፡ ወለድኩኽ ። እንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ፅንስ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ እንበለ ፡ ዘርዕ ፡ ተፀንሶበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃናሙ) ፡ በትንቢቶሙ ፡ ለነቢያት ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የነቢያት ፡ ትንቢት ፡ በተፈጸመበት ፡ ቀን ። (ወለድኩከ) ፡ ከዲያብሎስ ፡ መፈጠር ፡ አስቀድሞ ፡ ወለድኩኽ ። እኖ ፡ ወድቀ ፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ፡ እንዲል ።

እንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ልደት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ በጎቱም ፡ ድንግልና ፡ ተወልዶበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃናሙ) ፡ በቅዳሴሆሙ ፡ ለመላእክት ፡ በጎል ፡ ተጥሎ ፡ በጨርቅ ፡ ተጠቅልሎ ፡ አይተውት ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ወሰላም ፡ በምድር ፡ ሥምረቱ ፡ ለሰብእ ፡ ብለው ፡ ባመሰገኑበት ፡ ቀን ፡ (ወለድኩከ) ፡ ከዖር ፡ ጨቅጨት ፡ በኋላ ፡ ካጽቢያ ፡ ኮከብ ፡ አስቀድሞ ፡ ከማሕፀን ፡ ማርያም ፡

እንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ስባ ከት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ ተአምራት ፡ አድርጎበታል ፡ ድውይ ፡ ፈውሶበታል ፡ ሙት ፡ አንሥቶበታል ፡ ጋኔን ፡ አውጥቶበታል ፡ ኀብስት ፡ አበርክቶበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃናሙ) ፡ ለሐዋርያት ፡ ዕውቀት ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ። እንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ ሰባት ፡ ተአምራት ፡ ተደርጎበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃናሙ) ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብት ፡ ብርሃናቸውን ፡ ባጡበት ፡ ቀን ። ወርኢኩ ፡ ረሲዓነ ፡ እንዘ ፡ ይወርዱ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ቅዱስ ፡ እንዲል ።

እንድም ፡ ነፍሳት ፡ ብርሃንን ፡ ባገኙበት ፡ ቀን ። እለ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ፃኡ ፡ ወእለ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ተከሥቱ ፡ ወርእዩ ፡ ብርሃነ ፡ ዐቢየ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ በዕለተ ፡ ትንሣኤ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበር ፡ ምስት



መዓልት ፡ ምስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ተነሥቶበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃናሙ) ፡ ለሐዋርያት ፡ ዕውቀት ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ወከኑ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ይሳል ፡ እንደ ፡ ተደመፀ ፡ ብሩና ፡ ሁነዋልና ። (ወለድኩከ) ፡ ካጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ አስቀድሞ ፡ ከዖሮ ፡ ጨቅጨት ፡ በኋላ ፡ በትንሣኤ ፡ ወለድኩኽ ።

እንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በስብከተ ፡ ሐዋርያት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበር ፡ ተአምራት ፡ ተደርጎበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃናሙ) ፡ ለምእመናን ፡ ዕውቀት ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ።

እንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ በዕለተ ፡ ዕርገት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበር ፡ በይባቤ ፡ መላእክት ፡ አርጎበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃናሙ) ፡ በቅዳሴሆሙ ፡ ለመላእክት ፡ መላእክት ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እያሉ ፡ ባመሰገኑበት ፡ ቀን ።

እንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ በህልውና ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ይመጣል ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ እምኀበ ፡ ቦ ፡ ኀበ ፡ አልቦ ፡ ያሳልፍበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃናሙ) ፡ በዕሴቶሙ ፡ ለጻድቃን ፡ ጻድቃን ፡ ዋጋቸውን ፡ በሚያገኙበት ፡ ቀን ።

፬ ፡ መሐለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢይኔስሕ ።

እግዚአብሔር ፡ ማለ ፡ ከማለም ፡ መሐላውን ፡ አያፈርስም ፡ በመሐላው ፡ አይጸጸትም ። እንድም ፡ መሐላውን ፡ የማያፈርስ ፡ በመሐላው ፡ የማይጸጸት ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለ ። ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቀን ፡ ጥሎኝ ፡ ጠጅ ፡ አስከሮኝ ፡ ሰው ፡ አገብሮኝ ፡ ልማልን ፡ ብሎ ፡ ይጸጸታል ፡ እሱ ፡ ግን ፡ አያደርገውን ፡ አይናገር ፡ የተናገረውን ፡ አያስቀርምና ።

አንተ ፡ ካህኑ ፡ ለዓለም ፡ በከመ ፡ ሢመቱ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ።

እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ያለ ፡ ሹመት ፡ ተሹመኸ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ እንድም ፡ በቁሙ ፡ የዓለም ፡ እኀልጋይ ፡ አንተ ፡ ነኽ ። መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ጌታን ፡ በምን ፡ ይመስለዋል ፡ ቢሉ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅን ፡ ዘእልቦ ፡ አብ ፡ ወእም ፡ ይለዋል ፡ ምነው ፡ በስንክሳር ፡ ተጽፎ ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ በሌዋውያን ፡ ከታብ ፡ ስለ ፡ ሌለ ፡ ጌታም ፡ ለቀዳማዊ ፡ ልደቱ ፡ እናት ፡ ለደኃራዊ ፡ ልደቱ ፡ አባት ፡ የለውምና ። እንድም ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡

በስንዴ ፡ በወይን ፡ ያስታኀሡት ፡
ነበር ፤ ጌታም ፡ ሥጋውን ፡ በስ
ንዴ ፡ ደሙን ፡ በወይን ፡ አድር
ጎ ፡ ሰጥቶናልና ። እንድም ፡ መ
ልከ ፡ ጼዴቅ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተገ
ኘ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አለፈ ፡ አይባል
ም ፤ ጌታም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተገኘ ፡
በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያልፋል ፡ አይባል
ምና ። አልቦ ፡ ጥንት ፡ ለዘመኑ ፡
ወአልቦ ፡ ተፍጻሜት ፡ ለመዋዕ
ሊሁ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ መ
ልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ዘእምነገዱ ፡ ለካ
ም ፡ ይለዋል ፡ ከቤተ ፡ ሌዊ ፡
ሳይወለድ ፡ ከካም ፡ ተወልዶ ፡
ክህነትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል ፤
ጌታም ፡ ከቤተ ፡ ሌዊ ፡ ሳይወ
ለድ ፡ ከቤተ ፡ ይሁዳ ፡ ተወልዶ ፡
ክህነትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓልና ።
ዘፍ ፡ ፲፬ ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፴፩ ፡ ፲፩ ። ዳን ፡ ፮ ፡
፲፩ ። ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፴፱ ። ዕብ ፡ ፭ ፡ ፮ ፡ ፯ ፡
፳፩ ።

፭፤ እግዚአብሔር ፡ በየማንከ ።

እግዚአብሔር ፡ በዕሪናህ ፡ አለ ።

ይቀጠቅጦሙ ፡ ለነገሥት ፡ በዕለተ ፡ መዓቱ ።

በዕሪናህ ፡ ሁኖ ፡ መዓቱን ፡ በሚ
ፈጽምበት ፡ (በሚያመጣበት) ፡
በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ነገሥታቱን ፡
ቀጥቅጦ ፡ ያጠፋቸዋል ።

፮፤ ይኴንኖሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ወያበዝኆ ፡ አ
ብድንተ ።

በአሕዛብ ፡ ይፈርድባቸዋል ፡ አስ
ከሬኑን ፡ ያበዛል ፡ ማለት ፡ እን
ዱን ፡ ከሁለት ፡ ከሦስት ፡ ይከፍ
ለዋል ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ የሚ
ፈርድባቸው ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡
ስለ ፡ ሆኑ ። እንድም ፡ የኃጥአንን ፡
ብዛት ፡ የጻድቃንን ፡ ማነስ ፡
መናገር ፡ ነው ።

ወይሰብር ፡ አርእስተ ፡ ብዙኃን ፡ በዲበ ፡ ም
ድር ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡
ቸብቸቦ ፡ ይቈርጣል ፡ ማለት ፡
የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ሥልጣን ፡ ያጠ
ፋል ፡ ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፳፰ ።

፯፤ እምውኂዝ ፡ ስትዩ ፡ ማየ ፡ በፍኖት ።

ትሩፋን ፡ በጕዳና ፡ ውሃ ፡ ጠጡ ።
እንድም ፡ ምእመናን ፡ ከቀኝ ፡
ጐኑ ፡ በፈሰሰ ፡ ማየ ፡ ገቦ ፡ ተጠ
መቁ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከመንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ልጅነትን ፡ አገኙ ።

ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ይትሌዐል ፡ ርእሱ ።

ስለዚህ ፡ ዘሩባቤል ፡ ይነግሣል ፤
ጌታ ፡ ይሰቀላል ። ንሕነ ፡ እባል ፡
ወውእቱ ፡ ርእስ ፡ እንዲል ። እን
ድም ፡ ለምእመናን ፡ ልጅነትን ፡
ስለ ፡ መስጠት ፡ ርእስ ፡ ጌታ ፡
ይሰቀላል ፤ እስመ ፡ ዓዲሁ ፡ እወ
ረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእንተ ፡
ዘኢ.ተሰብሐ ፡ ወልድ ፡ ዕጓለ ፡
እመሕያው ፡ እንዲል ፡ ዮሐ ፡



## መዝሙር ፡ ፻፲ ።

፩፤ እነኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ ጠሮሎ ፡ ልብየ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ አቤ
ቱ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ እገዛ
ልኻለሁ ።

፪፤ በምክረ ፡ ራትዓን ፡ በማኅበር ፡ ዐቢይ ።

በምክረ ፡ ራትዓን ፡ ግብረ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ በማኅበር ፡ ዐቢይ ፤
የእግዚአብሔር ፡ ፍጥረት ፡ በሚ
ሆኑ ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ትም
ርት ፡ ጸንቼ ፡ በብዙ ፡ ጉባኤ ፡ እገ
ዛልኻለሁ ።

ወትትኀሠሥ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ፈቃዱ ።

ቅጽል ፡ አድርገህ ፡ ፈቃዱ ፡ አ
ሚን ፡ በል ።

፫፤ አሚን ፡ ወዕበየ ፡ ስብሐት ፡ ምግባሩ ።

በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ትሻለች ፤ ጌታ ፡
ሰው ፡ ሊያምን ፡ ምግባር ፡ ሊሠ
ሠራ ፡ ይወዳልና ። እንድም ፡
አሚን ፡ ትትኀሠሥ ፡ ውስተ ፡
ኵሉ ፡ ፈቃዱ ፤ ሃይማኖት ፡ ወዶ ፡
በፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡
ትሻለች ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሂል ፡
እያጣ ፡ ይቀርበታል ፡ እንጂ ፡ ሊ
ያምን ፡ ምግባር ፡ ሊሠራ ፡ ይወ
ዳልና ። (ወዕበየ ፡ ስብሐት ፡ ም
ግባሩ) ፡ ዐቢየ ፡ ስብሐት ፡ መባ
ልም ፡ ለጌታ ፡ ገንዘቡ ፡ ነው ።

ወጽድቁ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ።

ቸርነቱም ፡ ለዘላለም ፡ ሲደረግ ፡
ይኖራል ።

፬፤ ተዝካረ ፡ ገብረ ፡ ለስብሐቲሁ ።

ቸርነቱን ፡ ለጌትነቱ ፡ መታሰ
ቢያ ፡ አደረገ ።

መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነው ፤ ይ
ቅር ፡ ባይም ፡ ነው ።

፭፤ ወወሀቦሙ ፡ሲሳዮሙ ፡ ለእለ ፡ ይፈ
ርሁዎ ።

ለሚፈሩት ፡ ለሚያመልኩት ፡ ለት
ሩፋንም ፡ ምግባቸውን ፡ ሰጣ
ቸው ።

ወተዘከረ ፡ ኪዳኖ ፡ ዘለዓለም ።

ተዘከረ ፡ ዘለዓለም ፡ ኪዳኖ ፡ ዘለ
ዓለም ፤ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚ
ኖር ፡ መሐላውን ፡ አሰበ ። እን
ድም ፡ አሰቦ ፤

፮፤ ወአርአዮሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ ኀይለ ፡ ምግባሩ ።

ለወገኖቹም ፡ በሥልጣኑ ፡ የሚ
ሠራውን ፡ ሥራ ፡ ገለጸላቸው ።

ከመ ፡ የሀቦሙ ፡ ርስተ ፡ ለአሕዛብ ።

ለሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ርስታቸ
ው ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ይሰጣቸው ፡
ዘንድ ። እንድም ፡ ርስተ ፡ ዘአሕ

2014 04 17

ዛብ ፡ የአሕዛብን ፡ ርስት ፡ ለእ
ስራኤል ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ።

፯፡ ግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ጽድቅ ፡ ወርትዕ ።

የእጁ ፡ የቃሉ ፡ ሥራ ፡ የሚሆኑ ፡
ጽድቅ ፡ ኢታምልክ ፡ ርትዕ ፡
ዘጠኙ ፡ ሕግጋት ። እንድም ፡ ጽ
ድቅ ፡ ወንጌል ፡ ርትዕ ፡ ኦሪት ፡
ናቸው ።

ወእሙን ፡ ኵሉ ፡ ትእዛዙ ።

ወንበቦ ፡ ወንበቦ ፡ ያለውም ፡ የታመ
ነ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ዳን ፡ ፱-፴፯ ።

፰፡ ወጽኑዕ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለሙ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

ግቡር ፡ በጽድቅ ፡ ወበርትዕ ።

በሚገባ ፡ በውነት ፡ የተሠራ ፡
ነው ።

፱፡ መድኀኒተ ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለሕዝቡ ።

እግዚአብሔር ፡ ለወገኖቹ ፡ ሚ
ጠትን ፡ አደረገላቸው ። እንድም ፡
ጌታን ፡ በሥጋ ፡ ሰደደላቸው ።

ወአዘዘ ፡ ሥርዐቶ ፡ ዘለዓለም ።

ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ሕ
ጉን ፤ እንድም ፡ ኦሪትን ፡ ሠራላ
ቸው ።

ቅዱስ ፡ ወግሩም ፡ ስሙ ፡ ዚአሁ ።

ስሙ ፡ የሚያስፈራ ፡ የሚያስገ
ርም ፡ ጽንዕ ፡ ከሃሊ ፡ ነው ።

፲፡ ቀዳሚሃ ፡ ለጥበብ ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ።

የጥበብ ፡ መጀመሪያ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ መፍራት ፡ ነው ። እንድ
ም ፡ የዘጠኙ ፡ እበጋዝ ፡ ኢታም
ምልክ ፡ ናት ።

ምክር ፡ ሠናይት ፡ ለኵሉ ፡ ዘይገብራ ።

ዘጠኙም ፡ ለሚሠራት ፡ በጎ ፡ ትም
ርት ፡ ናት ።

ወስብሐቲሁኒ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ።

ጌትነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ሲነገር ፡ ይኖ
ራል ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓ
ለመ ፡ ዓለም ። አሜን ።

## መዝሙር ፡ ፻፲፩ ።

፩፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘይፈርሆ ፡ ለእግዚአ
ብሔር ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ሕ
ዝቅያስ ፡ ንኡድ ፡ ክቡር ፡
ነው ።



ወዘይፈቅድ ፡ ትእዛዞ ፡ ፈድፋደ ።

ትእዛዙንም ፡ የሚጠብቅ ፤ እንድም ፡
ዘጠኙንም ፡ ፈጽሞ ፡ የሚጠብቅ ፡
ሰው ፤ እንድም ፡ ሕዝቅያስ ፡ ንኡድ ፡
ክቡር ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ፪ ፡ ፶፮ ፡ ፩—፪ ።

፪፡ ወይከውን ፡ ጽኑዐ ፡ ዘርዑ ፡ ውስተ ፡
ምድር ። ሚራ ፡ ፴፩ ፡ ፲፯ ።

ልጁ ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ክብሮ ፡ ገኖ ፡ ይኖራል ፤ (የጸና ፡
ይሆናል) ።

ትውልደ ፡ ጻድቃን ፡ ይትባረኩ ።

የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆ
ብ ፡ ልጆች ፡ እለ ፡ ኢሳይያስ ፡
እለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ከብረው ፡ ገነው ፡
ይኖራሉ ።

፫፡ ክብር ፡ ወብዕል ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ።

ክብረ ፡ ሥጋ ፡ ክብረ ፡ ነፍስ ፡
ብዕለ ፡ ሥጋ ፡ ብዕለ ፡ ነፍስ ፡
በቤቱ ፡ እንድም ፡ በወገኖቹ ፡
ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

ወጽድቁኒ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ።

ሞተ ፡ ሰናክሬም ፡ ሚጠተ ፡ ፀሓ
ይ ፡ ሲነገርለት ፡ ይኖራል ።

፬፡ ሠረቀ ፡ ብርሃን ፡ ለራትዓን ፡ በውስተ ፡
ጽልመት ።

ለኢሳይያስ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ በመ
ከራቸው ፡ ጊዜ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡
ተደረገላቸው ።

መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነው ፡ ይቅር ፡
ባይም ፡ ነው ።

ወጻድቅ ፡ አምላክነ ።

ወጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላ
ክነ ፡ ይላል ፤ ፈጣሪያችን ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡
የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

፭፡ ብእሲ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ወኄር ።

ሕዝቅያስም ፡ እንዳቅሙ ፡ ለሰ
ው ፡ የሚያዝን ፡ የሚራራ ፡ ነው ፤
ይቅር ፡ ባይም ፡ ቸርም ፡ ነው ።

ወይሬኢ ፡ ቃሎ ፡ በውስተ ፡ ፍትሕ ።

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ በፍርድ ፡
ጊዜ ፡ ቍርጥ ፡ አድርጎ ፡ ይፈርዳል ።
እንደ ፡ ሰው ፡ ውዝፍ ፡ አድርጎ ፡
አይተውም ፤ ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ይዋል ፡ ይደር ፡ ይላል ፤ እሱ ፡
ግን ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ መጡ ፡
ፈርዶ ፡ ያሰናብታልና ። ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፬ ።

፮፡ ወኢይትሀወክ ፡ ለዓለም ።

ለዘላለም ፡ መከራ ፡ መጥቶበት ፡
በመከራ ፡ አይታወክም ።

ዝክረ ፡ ጻድቅ ፡ ለዓለም ፡ ይሄሉ ።

የጻድቅ ፡ የሕዝቅያስ ፡ እንድም ፡
የጻድቅ ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ለዘላለም ፡
ሲነገር ፡ ይኖራል ።

፯፡ ወኢይፈርህ ፡ እምነገር ፡ እኩይ ።

ክፉ ፡ ነገር ፡ የተነገ ፡ አይፈ

2014 04 17

ራም ። እንድም ፡ እምነገረ ፡ እ
ኩይ ፡ ይላል ፡ ከረፋስቴስ ፡ እነ
ጋገር ፡ የተነገ ፡ አይፈራም ።

[illegible]

በእግዚአብሔር ፡ ለማመን ፡ የሕ
ዝቅያስ ፡ ልቡናው ፡ ትጉህ ፡ ነው ።

[illegible]

ልቡናው ፡ ጽኑዕ ፡ ነው ፡ ለዘላ
ለም ፡ መከራ ፡ አግኝቶት ፡ በመ
ከራ ፡ አይታወክም ።

[illegible]

ጠላቶቹ ፡ ጠፍተው ፡ እስኪያይ ፡
ድረስ ፡ ጽኑዕ ፡ ልቡ ። ዘረወ ፡ ማ
ንኛ ፡ እንድም ፡ ጠላቶቹ ፡ ጠፍ
ተው ፡ እስኪያይ ፡ ድረስ ፡

[illegible]

ገንዘቡን ፡ ለነዳይ ፡ በተን ፡ ማለት ፡
መጽወተ ፡ ሰጠ ።

[illegible]

ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ይላል ።

ሚጠት ፡ ፀሓይ ፡ ሞት ፡ ሰንከ
ራም ፡ ሲነገርለት ፡ ይኖራል ።

[illegible]

ሥልጣኑ ፡ ከብሮ ፡ ገኖ ፡ ይኖራል ።

[illegible]

ኃጥእ ፡ ስናከሬም ፡ የኔን ፡ መፈ
ወስ ፡ የሱን ፡ መሞት ፡ ያያል ፤
አይቶ ፡ ይበሳጫል ፤ ተበሳጭቶ ፡
እሱን ፡ የሚጐዳው ፡ ሆኖ ፡ አይ
ደለም ፤ ብስጩ ፡ ለልማዱ ፡ ባል
ጋው ፡ በመከዳው ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡
እንዲሉ ።

[illegible]

ጥርሱን ፡ እያፋጨ ፡ እንደ ፡
ሠም ፡ ቀልጦ ፡ ይጠፋል ።

[illegible]

የኃስናከሬም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እን
ዲሁ ፡ እያሉ ፡ ትፈጽማለች ።

## መዝሙር ፡ ፻፲፪ ።

[illegible]

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ።
የእግዚአብሔር ፡ ባሮች ፡ ትሩፋን ፡
እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

[illegible]

ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ምስጋና ፡

አቅርቡ ፡ ስሙን ፡ አመስግኑ ።

[illegible]

[illegible]

የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ይክበር ፡
ይመስገን ።



[illegible]

ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡
ድረስ ። [illegible]

[illegible]

ከፀሓይ ፡ መውጫ ፡ እስከ ፡ ፀሓይ ፡
መግቢያ ፡ ድረስ ።

[illegible]

አላሉተሀ ፡ ይከበር ፡ ይመስገን ፤
አተብቀሀ ፡ ይከብራል ፡ ይመስ
ገናል ።

[illegible]

እግዚአብሔር ፡ ከአሕዛብ ፡ በ
ላይ ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡ ነው ።

[illegible]

ጌትነቱም ፡ በሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ ሲነ
ገር ፡ ይኖራል ። እንድም ፡ በመላእ
ክት ፡ ዘንድ ፡ ሲመሰገን ፡ ይኖራል ።

[illegible]

እንደ ፡ ፈጣሪያችን ፡ እንደ ፡
እግዚአብሔር ፡ ማደን ፡ መታ
ደግ ፡ የሚቻለው ፡ ማነው ።

[illegible]

በአርያም ፡ ሁኖ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
እንድም ፡ በበርባኖስ ፡ የሚያረ
ገውን ፡ ነገር ፡ የሚያውቅ ፡ ማነው ።

[illegible]

ይነብር ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡
ብሎ ፡ ነበርና ፡ በሰማይ ፡ ብቻ ፡
ነውን ፡ ቢለው ፡ በሰማይም ፡
በምድርም ፡ የሚያረገውን ፡ በው
ቀ ፡ የሚሠራ ፡ እንድም ፡ በሰማ
ይም ፡ በምድርም ፡ ምሉእ ፡ ነው ።

[illegible]

ድኻውን ፡ ከትቢያነቱ ፡ የሚያ
ነሣው ፡ እሱ ፡ ነው ።

[illegible]

ለምስኪን ፡ እመራት ፡ ለማለት ፡ ደግ
መው ። [illegible]

[illegible]

ካለቆቹ ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ።

[illegible]

ከሕዝቡ ፡ አለቆችም ፡ ጋራ ፡ ያኖ
ረው ፡ ዘንድ ። [illegible]

[illegible]

መካን ፡ የምትኖር ፡ የእስራኤልን ፡
ቤት ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በቤቱ ፡
በኢየሩሳሌም ፡ የሚያኖራት ፡ እሱ ፡
ነው ። ነቢያት ፡ የሚጠትን ፡ ነ
ገር ፡ ሲናገሩ ፡ ስምታ ፡ ሚጠት ፡
ሲያረግ ፡ ልጅ ፡ ረጅ ፡ የለኝ ፡
ማን ፡ ያወጣኛል ፡ ስትል ፡ ዘሩ
ባቤልን ፡ አንግሦ ፡ አውጥቷታልና ።

ወያስተፌሥሓ ፡ ለእመ ፡ ውሉድ ።

የልጆች ፡ እናት ፡ የምትሆን ፡ የእስራኤልን ፡ ሴት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛት ፡ እሱ ፡ ነው ። ሚጠትስ ፡ ቢደረግ ፡ በጀርባዬ ፡ ልጅ ፡ በራሴ ፡ ትብትብ ፡ ምንጣፍ ፡ ተሸክሜ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ይሆንል ኛል ፡ ስትል ፡ ዘሩባቤልን ፡ አን ግሦ ፡ አውጥቷታልና ። እንድም ፡ (ዘያነሥእ) ፡ ቋሚ ፡ ለጓሚ ፡ የነ በረ ፡ ዘሩባቤልን ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥ ት ፡ የሚያደርገው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወያሌዕሎ) ፡ ደገመው ። (ከመ ፡ ያን ንብሮ) ፡ ካለቆቹ ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ፡ (ወምስለ ፡ መላእክት) ፡ ከ ሕዝቡ ፡ አለቆች ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ፡ (ዘያነብራ) ፡ ነቢያትን ፡ በሕዝቡ ፡ መኻል ፡ የሚያኖራ ቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። ሰባ ፡ ዘመን ፡ ከትንቢት ፡ ተከልክለዋልና ፡ መ ካን ፡ አላቸው ።

(ወያስተፌሥሓ) ፡ ካህናትንም ፡ በ ሕዝቡ ፡ መኻል ፡ ደስ ፡ የሚያሰ ኛቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። ልጅ ፡ ከና ናቴ ፡ ባሕርይ ፡ እንዲገኝ ፡ ትም ርትም ፡ የሚገኝ ፡ ከባሕርያቸው ፡ ነውና ። እንድም ፡ (ዘያነሥእ) ፡ አዳምን ፡ ከመሬት ፡ የፈጠረ ፡ እሱ ፡ ነው ። ጠነሥእ ፡ መሬት ፡ እግእከለ ፡ ምድር ፡ ወገብሮ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እንዲል ፡ እንድም ፡ ሥጋን ፡ ከመታብር ፡ ያነሣው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወያሌዕሎ) ፡ ለምስኪን ፡ ለማለት ፡ ደገመው ። (ከመ ፡ ያንብሮ) ፡ ከመ ላእክት ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ፡ (ወምስለ ፡ መላእክት) ፡ ከመላ እክት ፡ አለቆች ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ። (ዘያነብራ) ፡ ወንጌልን ፡ እንድትነገር ፡ የሚያደርግ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ መካን ፡ አላት ፡ በመልክ ፡ ጼዴቅ ፡ ጊዜ ፡ ታይታ ፡ ጠፍታለችና ። እንድም ፡ (ዘያነብራ) ፡ ምእመናንን ፡ በገነት ፡ በመንግ ሥት ፡ ሰማያት ፡ የሚያኖራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፡ መካን ፡ አላቸው ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ልጅነት ፡ አጥተዋልና ። (ወያስተፌሥሓ) ፡ አሪትን ፡ እን ድትነገር ፡ አድርጎ ፡ ሕዝቡን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፡ እመ ፡ ውሉድ ፡ አላት ፡ ከሙሴ ፡ ከአሮን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሐና ፡ እስከ ፡ ቀያፋ ፡ ድረስ ፡ ሥራቷን ፡ የሚያስተምሩ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ አላጠፋባትምና ። እንድም ፡ ምእ መናንን ፡ ከሲኦል ፡ አውጥቶ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። ኢዮ ፡ ፴ ፡ ፬ ፡ ፮ ።



## መዝሙር ፡ ፻፲፫ ።

፩፡ እመ ፡ ይወፅእ ፡ እስራኤል ፡ እምግብጽ ፡ እስራኤል ፡ ተዋረሲ ፡ እንዲል ፡

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ የምእመናንንም ፡ ነገር ፡ አለበት ። እመ ፡ ወዕአ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እመ ፡ ይትባሀሎ ፡ ለሰይጣን ፡ እንዲል ። ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ ከግብጽ ፡ በወ ጡ ፡ ጊዜ ፡

ወቤተ ፡ ያዕቆብ ፡ እምሕዝብ ፡ ፀር ።

ሁለቱም ፡ ነገድ ፡ ፀርነት ፡ ካላ ቸው ፡ ከግብጻውያን ፡ ተለይተ ው ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡

፪፡ ወኮነ ፡ ይሁዳ ፡ መቅደሶ ።

ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ማደሪያው ፡ ሆነ ።

ወእስራኤልኒ ፡ ምኵናኖ ።

እስራኤል ፡ ዘሥጋ ፡ ዐሥሩ ፡ ነገ ድም ፡ ርስቱ ፡ ጕልቱ ፡ ሆኑ ። እን ድም ፡ (እመ ፡ ይወፅእ) ፡ እስራ ኤል ፡ ዘነፍስ ፡ ከሲኦል ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ወሰመያ ፡ ለሲኦል ፡ ግብጸ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ በወጡበት ፡ ወራት ። (ወቤተ ፡ ያዕቆብ) ፡ ያዕ ቆብ ፡ ዘነፍስም ፡ ፀርነት ፡ ካላ ቸው ፡ ከአጋንንት ፡ ተለይተው ፡ በወጡበት ፡ ወራት ፡ (ወኮነ ፡ ይ ሁዳ ፡ መቅደሶ) ፡ ይሁዳ ፡ ሥ ጋን ፡ ተዋሐደ ። (ወእስራኤልኒ) ፡ እስራኤል ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፡ ነበ ፡ ያዕቆብ ፡ ኅድሪ ፡ ወቤተ ፡

፫፡ ባሕርኒ ፡ ርእየት ፡ ወጕየት ።

ኤርትራ ፡ በሙሴ ፡ በአሮን ፡ አድ ሮ ፡ ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡ አይታ ፡ ሸሸች ።

ወዮርዳኖስኒ ፡ ገብአ ፡ ድኅሬሁ ።

ፈላሹም ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተ መለሰ ።

፬፡ አድባር ፡ አንፈርዐጹ ፡ ከመ ፡ ሐራጊት ።

ሙሴ ፡ አሮን ፡ እንደ ፡ ጊደር ፡ ዘለሉ ።

ወአውግርኒ ፡ ከመ ፡ መሐስዐ ፡ አባግዕ ።

ሰብዓ ፡ ሊቃናትም ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ጠቦት ፡ ዘለሉ ። ኢሳ ፡ ፲፭ ፡ ፩ ። ፶፩ ፡ ፲፰ ።

እንድም ፡ (ባሕርኒ) ፡ ዮርዳኖስ ፡ ጌታን ፡ አይታ ፡ ሸሸች ፡ (ወዮር ዳኖስኒ) ፡ ፈላሹም ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመለሰ ። (አድባር) ፡ ሐዋርያት ፡ እንደ ፡ ጊደር ፡ ዘለሉ ። (ወአውግርኒ) ፡ ሰብዓ ፡ አርድ እትም ፡ እንደ ፡ ጠቦት ፡ ዘለሉ ።

፭፡ ምንት ፡ ኮንኪ ፡ ባሕር ፡ ዘጐየይኪ ።

ኤርትራ ፡ እንድም ፡ ዮርዳኖስ ፡ አረ ፡ የሸሸሽ ፡ ምን ፡ ሁነሻል ።

ወአንተኒ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ዘገባእከ ፡ ድኅሬከ ።

አንተስ ፡ ፈላሹ ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ ኋላህ ፡ የተመለስህ፡ ምን፡ ሁነሃል ።

2014 04 17

፮፤ [illegible]

ተራሮች ፡ እንደምን ፡ መሬ ፡ እር
ገ ፡ እንደም ፡ ሊዋርዱት ፡ እን
ደ ፡ ጌደር ፡ የበለፃቸው ፡ ምን ፡
ሁናቸጋል ።

[illegible]

ለፀን ፡ ሊቃናት ፡ እንደም ፡
ለፀን ፡ እርድኤት ፡ እንደ ፡ ፀጋ ፡
ልዑት ፡ የበለፃቸው ፡ ምን ፡ ሁና
ቸጋል ።

፯፤ [illegible]

የእግዚአብሔር ፡ ገጹ ፡ ምሕረት ፡
ገጹ ፡ ረድኤት ፡ ከመገለጹ ፡ የተ
ነሣ ፡ ባሕር ፡ ተከፍሎላቸው ፡
ወላት ፡ ወፍቶላቸው ፡ ይገባቸጋል ፤
ይኸውም ፡ ሊያገለቸው ፡ ነው ።
እንደም ፡ እሳት ፡ ባትገነባኝ ፡
እኔ ፡ እንገራችጋለሁ ፤ እግዚአብ
ሔር ፡ ሰው ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡
ወላቶቻቸው ፡ እያሉድ ፡ መናፍ
ቃን ፡ አጋንንት ፡ ወፍተውላቸ
ው ፤ ይገባቸጋል ፤ ይኸውም ፡
ሊያገለቸው ፡ ነው ።

[illegible]

የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ገጹ ፡ ምሕረቱ ፡
ከመገለጹ ፡ የተነሣ ።

፰፤ [illegible]

ዘርዐያ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ይዘችን ፡

ዓለም ፡ በሥጋ ፡ ፍጥረት ፡ የውኃ ፡
መፍሰሻ ፡ ያደረጋት ፡ እሱ ፡ ነው ።
እንደም ፡ እብን ፡ መሬን ፡ የው
ሃ ፡ መፍሰሻ ፡ ያደረጋት ፡ እሱ ፡
ነው ። እንደም ፡ እያሩሳሌምን ፡
በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ የውኃ ፡ መፍ
ሰሻ ፡ ያደረጋት ፡ እሱ ፡ ነው ።

[illegible]

እብን ፡ መሬን ፡ የውኃ ፡ መነሻ ፡
ያደረጋት ፡ እሱ ፡ ነው ። እብን ፡
ብሉይት ፡ ያላታል ።

፱፤ [illegible]

አቤቱ ፡ ይህ ፡ ለኛ ፡ የሚገባን ፡
አይደለም ፤ ለኛ ፤ አይደለም ።

[illegible]

ለስምህ ፡ እንዲመሰገን ፡ አድርግ ፡
እንደም ፡ ነፀብ ፡ ከብሉይ ፡ ለም
ሀን ፡ እንድናመሰግን ፡ ይሁን ፡
እንጂ ፡ እናያ ፡ አቀጭቶ ፡ ሥራ ፡
ለማውራት ፡ አሉ ፡ ተሉት ፡ ነዚ
ደበት ፡ ሀገር ፡ አከብረው ፡ ያሉ
ቀበሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጌታውን ፡
ያገኙን ፡ ለም ፡ ጠርቼ ፡ ብዬድ ፡
እዋርደው ፡ ሰይጹኝ ፡ እኔማ ፡
ምን ፡ ሰሃቱ ፡ እንደ ፡ ጊዜ ፡ ተደ
ርጎብኝ ፡ የለምን ፡ ያገኙ ፡ ለም ፡
መዋረዱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚቈ
ጨኝ ፡ ይለዋል ፤ እናያ ፡ ሥራ ፡
ለማውራት ።

[illegible]

በይቅርታህ ፡ በቸርነትህም ።

፲፤ [illegible]

ትሩፋን ፡ ፈጣሪ ፡ እልን ፡ ያለሉ ፡
እንጂ ፡ ፈጣሪ ፡ ካላቸው ፡ ለመሄ ፡
ይህናቸዋል ፡ እያድናቸውምን ፡ እ
ንዲያሉን ፡ እሕዛብ ።

፲፩፤ [illegible]

እላቸው ፡ ባያውቁ ፡ እንዲህ ፡
ያለሉ ፡ እንጂ ፡ የኛስ ፡ ፈጣሪያ
ችን ፡ ከሰብቱ ፡ በማያት ፡ በላይ ፡
ባለ ፡ በጽርሐ ፡ አርያም ፡ አለ ።

[illegible]

በሰማይም ፡ አለ ፤ በሰማይ ፡ ብቻ ፡
ነውን ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በም
ድርም ፡ አለ ። ሄዱ ፡ በፈቃዱ ፡
ማገኛ ፤ እንደም ፡ በሰማይም ፡ በም
ድርም ፡

[illegible]

እግዚአብሔር ፡ የወደደውን ፡ ሁ
ሉ ፡ ፈጠረ ፡ [illegible]

፲፪፤ [illegible]

የአሕዛብ ፡ እግልኦት ፡ ግን
እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የወደ
ዱትን ፡ እንዳደረጉ ፡ የወርቅ ፡
የብር ፡ ናቸው ። እንደም ፡ የወ
ርቅ ፡ የብር ፡ የሚሆኑ ፡ እሌህ ፡

[illegible]

የሰው ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ።

[illegible]

፲፫፤ [illegible]

ለው ፡ ሠራሽ ፡ የሚሆኑ ፡ እሌህ ፡
አፍ ፡ አላቸው ፡ አይናገሩም ።
እንደም ፡ አፍ ፡ ሳላቸው ፡ አይ
ናገሩም ።

[illegible]

ዐይን ፡ አላቸው ፡ አያዩም ፡ እን
ደም ፡ ዐይን ፡ ሳላቸው ፡ አያዩም ።

፲፬፤ [illegible]

ጆሮ ፡ አላቸው ፡ አይሰሙም ።
እንደም ፡ ጆሮ ፡ ሳላቸው ፡ አይ
ሰሙም ።

[illegible]

አፍንጫ ፡ አላቸው ፡ አያሸቱም ።
እንደም ፡ አፍንጫ ፡ ሳላቸው ፡
አያሸቱም ። [illegible]

፲፭፤ [illegible]

እጅ ፡ አላቸው ፡ አይዳስሱም ።
እንደም ፡ እጅ ፡ ሳላቸው ፡ አይ
ዳስሱም ።

[illegible]

እግር ፡ አላቸው ፡ አይሄዱም ።
እንደም ፡ እግር ፡ ሳላቸው ፡ አይ
ሄዱም ።

2014 04 17

ወኢይነቡ ፡ በጕረዒቶሙ ።

ባንደበታቸው ፡ አይናገሩም ።

ወአልቦ ፡ መንፈስ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ።

ባንደበታቸው ፡ ቃል ፡ እስትን ፋስ ፡ የለም ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ይቀር ባቸዋል ።

፲፮ ፡ ከማሆሙ ፡ ለይኩኑ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ገብርዎሙ ።

እሳቸውማ ፡ ምን ፡ ባይ ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ አይደሉምን ፡ ብሎ ፡ የሠ ሯቸው ፡ ሁሉ ፡ እንደሳቸው ፡ ይ ሁኑ ፡ ማለት ፡ አፍ ፡ ሳላቸው ፡ የማይናገሩ ፡ ዐይን ፡ ሳላቸው ፡ የማያዩ ፡ ጆሮ ፡ ሳላቸው ፡ የማይ ሰሙ ፡ አፍንጫ ፡ ሳላቸው ፡ የማያ ሸቱ ፡ እጅ ፡ ሳላቸው ፡ የማይዳ ስሱ ፡ እግር ፡ ሳላቸው ፡ የማይ ሄዱ ፡ ይሁኑ ።

ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይትዌከሉ ፡ ቦሙ ።

እለ ፡ ይትዌከልምሙም ፡ ይላል ፡ ስንኳን ፡ የሠሯቸው ፡ ያድኑናል ፡ ብለው ፡ የሚያምኑባቸው ፡ ሁሉ ፡ እንደሳቸው ፡ ይሁኑ ፡ ኢሳ ፡ ፬ ፡ ፰።

፲፯ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ተወከሉ ፡ በእግዚአ ብሔር።

የእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ ጭዎች ፡ ይህ ፡ እንዳያገኛችሁ ፡ በእግዚ አብሔር ፡ እመኑ ።

ረዳኢሆሙ ፡ ውእቱ ፡ ወምእመኖሙ ።

ረዳኢከሙ ፡ ወምእመንከሙ ፡ ይ ላል ፡ የታመነ ፡ ረዳታችሁ ፡ የታ መነ ፡ ወዳጃችሁ ፡ ነውና ።

፲፰ ፡ ቤተ ፡ አሮን ፡ ተወከሉ ፡ በእግዚአ ሔር ።

የአሮን ፡ ወገኖች ፡ ካህናት ፡ በእግዚአብሔር ፡ እመኑ ።

ረዳኢሆሙ ፡ ውእቱ ፡ ወምእመኖሙ ።

ረዳኢከሙ ፡ ውእቱ ፡ ወምእመንከ ሙ ፡ የታመነ ፡ ወዳጃችሁ ፡ ነውና ።

፲፱ ፡ እለ ፡ ትፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተወከሉ ፡ በእግዚአብሔር ።

ነሚማለትና ፡ እግዚአብሔርን ፡ በ ሕግ ፡ በእምልኮ ፡ የምትፈሩት ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ አንድም ፡ መላችሁ ፡ እስራኤል ፡ በእግዚአ ብሔር ፡ እመኑ ።

ረዳኢሆሙ ፡ ውእቱ ፡ ወምእመኖሙ ።

ረዳኢከሙ ፡ ወምእመንከሙ ፡ የታ መነ ፡ ረዳታችሁ ፡ የታመነ ፡ ወዳ ጃችሁ ፡ ነውና ።

፳ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተዘከረነ ፡ ወባረከነ ።

እግዚአብሔር ፡ አንሰናልና ፡ አብ ዛን ፡ ተዋርደናልና ፡ አከብረን ። አንድም ፡ ተዘከረነ ፡ ወባረከነ ፡ ተዋርደን ፡ ነበርና ፡ አከብረን ፡ አንሰን ፡ ነበረና ፡ አብዛን ።

ባረከ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ።

የእስራኤልን ፡ ወገኖች ፡ ጭዎ ችን ፡ አከብር ፡ አብዛ ።



ወባረከ ፡ ቤተ ፡ አሮን ።

የአሮን ፡ ወገኖች ፡ ካህናትን ፡ አከብር ፡ አብዛ ።

፳፩ ፡ ባረኮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ነሚማለትና ፡ እግዚአብሔርን ፡ በ ሕግ ፡ በእምልኮ ፡ የሚፈሩትን ፡ ሁሉ ፡ አከብራቸው ፡ አብዛቸው ።

ለንኡሶሙ ፡ ወለዐቢዮሙ ።

ታላቁንም ፡ ታናሹንም ፡ አከብ ራቸው ፡ አብዛቸው ። አንድም ፡ ለንኡስከሙ ፡ ወለዐቢይከሙ ፡ ይላል ፡ ከላንተ ፡ ዘንድ ፡ ያሉትን ፡ ታናናሾቻችሁን ፡ ታላላቆቻችሁን፡ ያከብር ፡ ያብዛ ። ንኡስ ፡ ዐቢይ ፡ የዕድሜ ፡ የመዓርግ ፡ ነው ።

፳፪ ፡ ይዌስክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌክሙ ።

እግዚአብሔር ፡ በላንት ፡ ላይ ፡ ልጆችን ፡ ይጨምር ።

ላዕሌክሙ ፡ ወላዕለ ፡ ውሉድክሙ ።

በላንት ፡ ላይ ፡ ልጆችን ፡ በልጆቻች ሁ ፡ ላይ ፡ የልጅ ፡ ልጆችን ፡ ይጨምር ።

፳፫ ፡ ቡሩካን ፡ አንትሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘገብረ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ።

ሰማይን ፡ ምድርን ፡ የፈጠረ ፡ የእግዚ አብሔር ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ፍጥ ረት ፡ ናችሁ ።

፳፬ ፡ ሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ለግዚአብሔር ።

ሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ ማደሪያ ፡ ናቸው ።

ምድረሰ ፡ ወሀበ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።

ምድርን ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ማደ ሪያ ፡ ሊሆን ፡ ፈጥሮ ፡ ሰጠ ፡ ማ ለት ፡ እርሶ ፡ ቈፍሮ ፡ ሊመገብ ። አንድም ፡ (ሰማየ ፡ ሰማያት) ፡ ልዕልና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገን ዘብ ፡ ነው ። (ምድረሰ) ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ ግን ፡ ትሕትና ፡ ነው ፡ ትሕትና ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

፳፭ ፡ ዘአኮ ፡ ሙታን ፡ ይሴብሑከ ፡ እግ ዚአ።

አቤቱ ፡ የሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ ስጠን ፡ ብለው ፡ አያመሰግኑህምና ።

ወኢኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይወርዱ ፡ ውስተ ፡ ሲ ኦል ።

ሙተው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ የወ ረዱ ፡ ሁሉ ፡ ልብስ ፡ ቀለብ ፡ ስጠን ፡ ብለው ፡ አያመሰግኑህምና ።

፳፮ ፡ ንሕነ ፡ ሕያዋን ፡ ንባርኮ ፡ ለእግዚአብ ሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ እኛ ፡ ሕያዋን ፡ እናመሰግነዋለን ፡ እንጂ ። አን ድም ፡ እንዲህ ፡ የሚልህ ፡ የለ ምና ፡ እኛ ፡ ሕያዋን ፡ ኑረን ፡ እናመስግንህ ፡ ዘንድ ፡ መኖሩን ፡ ስጠን ።

እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።

ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ።



2014 04 17

## መዝሙር ፡ ፹፯ ፡

፩ ፡ እግዚኦ ፡ አምላከ ፡ መድኃኒትየ ፡ ቅድሜከ ፡ ጸራኅኩ ፡

ሰለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መጥራት ፡ ወድጃለሁና ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ ስማኝ ፡ እንድም ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ ስምቶኛልና ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መጥራት ፡ ወደድሁ ፡

፪ ፡ ወአድምዐ ፡ እዝኖ ፡ ኀቤየ ፡

እዝን ፡ ፈቃዱን ፡ ወደኔ ፡ መልሶ ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ ሰምቷልና ፡

ወጸዋዕክዎ ፡ በመዋዕልየ ፡

ባለ ፡ ዘመኔ ፡ ለምኜዋለሁና ፡ አፍዝዞታል ፡ ይገለጸው ፡

፫ ፡ አኀዙኒ ፡ ጻዕረ ፡ ሞት ፡

ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ መከራ ፡ አገኝቶኛልና ፡

ወረከቡኒ ፡ ሕማመ ፡ ሲኦል ፡

ለመቃብር ፡ የሚያበቃ ፡ መከራ ፡ አገኝቶኛልና ፡

ረከባኒ ፡ ቢል ፡ ያቀናል ፡ ጻዋትወ ፡ መከራ ፡ አገኙተውኛልና ፡

፬ ፡ ጸዋዕኩ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡

እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በምስጋና ፡ ጸራሁ ፡ ገለጸው ፡

እግዚኦ ፡ ባልሓ ፡ ለነፍስየ ፡

ወውእቱ ፡ ባልሓ ፡ ይላል ፡ እሱም ፡ ሰውነቴን ፡ ካገኘት ፡ መከራ ፡ አዳናት ፡ እንድም ፡ አቤቱ ፡ ሰውነቴን ፡ ካገኘት ፡ መከራ ፡ አድናት ፡

፭ ፡ መሓሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጻድቅ ፡ ወአምላክነ ፡ መስተሣህል ፡

መሓሪ ፡ ወጻድቅ ፡ ወመስተሣህል ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክን ፡ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነው ፡ ቸር ፡ ነው ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡

፮ ፡ የዐቅብ ፡ ሕፃናተ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔር ፡ ሕፃናትን ፡ በና ታቸው ፡ ማሕፀን ፡ ሳሉ ፡ ይጠብቃል ፡ የበላችው ፡ ተጭኖ ፡ የጠጣችው ፡ እንዝዞ ፡ እንዳይገድላቸው ፡ እንድም ፡ ሕፃናት ፡ ሥጋን ፡ ይጠብቃል ፡ ከገደል ፡ እንዳይወድቁ ፡ ከባሕር ፡ እንዳይጠልቁ ፡ እንድም ፡ ሕፃናት ፡ ነፍስን ፡ ይጠብቃል ፡

ተመንደብኩ ፡ ወአድኀነኒ ፡

መከራ ፡ አገኘኝ ፡ ካገኘኝ ፡ መከራ ፡ አዳነኝ ፡

፯ ፡ ግብኢ ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ ዕረፍትኪ ፡

ሰውነቴ ፡ ወደ ፡ ተድላ ፡ ደስታሽ ፡ ተመለሽ ፡



እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረድአኒ ፡

ረድኢኪ ፡ ቢል ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ረድቶሻልና ፡

፰ ፡ እስመ ፡ አድኀና ፡ ለነፍስየ ፡ እሞት ፡

ሰውነቴን ፡ ከሞተ ፡ ሥጋ ፡ አድኗታልና ፡

ወለአዕይንትየኒ ፡ እምአንብዕ ፡

አዕይንተ ፡ ሥጋዬንም ፡ ከእንብዐ ፡ ሥጋ ፡ አድኗቸዋልና ፡

ወለእገርየኒ ፡ እምዳኅፅ ፡

እእጋረ ፡ ሥጋዬንም ፡ ከዳኅፀ ፡ ሥጋ ፡ አድኗቸዋልና ፡

፱ ፡ ከመ ፡ አሥምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በብሔረ ፡ሕያዋን ፡

እግዚአብሔርን ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ሀገር ፡ በም ትሆን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ደስ ፡ አሰኘው ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ (ግብኢ) ፡ ነፍሴ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ተመለሽ ፡ (እስመ ፡ እግዚአብሔር) ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሁለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሁኖ ፡ ረድቶሻልና ፡ እንድም ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረዳት ፡ ሆኖኛልና ፡ (እስመ ፡ አድኀና) ፡ ነፍሴን ፡ ከሞተ ፡ ነፍስ ፡ አድኗታልና ፡ (ወለአዕይንትየኒ ፡ እምአንብዕ) ፡ አዕይንተ ፡ ነፍሴን ፡ ከእንብዐ ፡ ነፍስ ፡ አድኗታልና ፡ እሁን ፡ በነፍስ ፡ ልቅሶ ፡ ኑሮ ፡ አይደለም ፡ የመከራውን ፡ ጽናት ፡ መናገር ፡ ነው ፡ (ወለእገርየኒ) ፡ እእጋረ ፡ ነፍሴንም ፡ ከዳኅፀ ፡ ነፍስ ፡ አድኗቸዋልና ፡ (ከመ ፡ አሥምሮ) ፡ እግዚአብሔርን ፡ በጻድቃን ፡ በሰማዕታት ፡ በመላእክት ፡ ሀገር ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ደስ ፡ አሰኘው ፡ ዘንድ ፡

## መዝሙር ፡ ፹፰ ፡

፩ ፡ አመንኩ ፡ በዘነበብኩ ፡

ሰለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ ሕዝቅያስ ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ወልድ ፡ የተባልህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ በቀኝ ፡ እጅህ ፡ ሳትወረውር ፡ በግራ ፡ እጅህ ፡ ሳትመክት ፡ ጠላት ፡ የጠፋልህ ፡ ድንግል ፡ የተባለች ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ናት ፡ የእሕዛብ ፡ እለንጋ ፡ ያልሞኘባት ፡ እንግዳ ፡ ፈረስ ፡ ያልረገጣት ፡ እሆን ፡ ይሆናል ፡ እሆን ፡ እሆና ለሁ ፡ ብትል ፡ አይደለም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ የመጣብህ ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆን ፡ እምን ፡ ይህ ፡ መከራ ፡ ያገኘኝ ፡ ይህን ፡ በተናገርሁ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ በውቅሁ ፡ በተናገርሁት ፡ ነገር ፡ አመንሁ ፡

ወአነሰ ፡ ብዙኀ ፡ ሐመምኩ ።

እኔስ ፡ ዋዌ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ በተናገርሁት ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ አገኘኝ ። እንድም ፡ ፈድፋዴ ፡ ባለመከራ ፡ ሆንሁ ። ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፲ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፫ ።

፪ ፡ አነሰ ፡ እቤ ፡ እምገዕዝየ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ሐሳዊ ፡ ውእቱ ።

እኔ ፡ ከራሴ ፡ ጀምሮ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፡ አልሁ ፡ በዚህም ፡ ሐዊ ፡ አመስግኖታል ፡ እንሰ ፡ እቤ ፡ በተድላየ ፡ ኢይትሀወክ ፡ ለዓለም ፡ ባለው ፡ ግን ፡ ነቅፎታል ። ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፴፫ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፬ ።

፫ ፡ ምንተ ፡ እዐስዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘገብረ ፡ ሊተ ።

ይህን ፡ ስላደረገልኝ ፡ ፈንታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ወረታ ፡ እከፍለዋለሁ ።

፬ ፡ ጽዋዐ ፡ ሕይወት ፡ እትሜጦ ።

ድኅነትን ፡ አገኝቻለሁ ፡ (ትች) ፡ እንድም ፡ ድኅነትን ፡ አገኛለሁ ፡ እንጂ ፡ ምንተኑ ፡ እዐስዮ ።

ወስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጼውዕ ።

የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ እጠራለሁ ፡ እንጂ ፡ ምንተኑ ፡ እዐስዮ ።

፭ ፡ ክቡር ፡ ሞቱ ፡ ለጻድቅ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ባወቀው ፡ ነገር ፡ በእግዚአብሔር ፡ በክብርት ፡ የጻድቅ ፡ ሰው ፡ ሞት ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ ሐተታ ፡ እንዳለፈው ።

፮ ፡ እግዚኦ ፡ አነ ፡ ገብርከ ።

አቤቱ ፡ እኔ ፡ አገልጋይህ ፡ ተገዥህ ፡ ነኝ ።

ገብርከ ፡ ወልደ ፡ አመትከ ።

ያውም ፡ የቤት ፡ ባሪያህ ፡ ልጅ ፡ የምሆን ፡ ባሪያህ ፡ ነኝ ፡ ከወንድ ፡ ባሪያ ፡ ልጅ ፡ የቤት ፡ ባሪያ ፡ ልጅ ፡ ይታመናልና ። የወንድ ፡ ባሪያ ፡ ልጅ ፡ ይጠረጠራል ፡ እሁን ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ የአገሌ ፡ ልጅ ፡ ሁኖ ፡ ነውን ፡ እንዲያው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተብሎ ። ሴት ፡ ግን ፡ ባደባባይ ፡ ትወልደዋለች ፡ ታሳድገዋለችና ፡ አይጠረጠርም ። እኔም ፡ በገቢረ ፡ ኀጢአት ፡ በአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ የማይጠረጠሩ ፡ የጥንተ ፡ ተገዦችህ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ ተገዥህ ፡ ነኝ ።

፯ ፡ ወሰበርከ ፡ መቀሕትየ ።

እስራቴን ፡ እንድም ፡ መከራዬን ፡ አጠፋኽልኝ ።

ለከ ፡ እሠውዕ ፡ መሥዋዕተ ፡ ስብሐት ።

እሠውዕ ፡ ካልሁ ፡ ብሎ ፡ መሥዋዕት ፡ ብሏል ፡ እንጂ ፡ ለጌትነትህ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ፡ ጌትነትህን ፡ አመሰግናለሁ ።



፰ ፡ ወእሁብ ፡ ብፅዐትየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝቡ ።

ይህን ፡ ብታደርግልኝ ፡ ይህን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብዬ ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ የተሳልሁትን ፡ ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ስለቴን ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እሰጣለሁ ፤ በሰው ፡ ፊት ፡ መሳል ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ መስጠት ፡ ይገባልና ።

፱ ፡ በዐጸደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ በምትሆን ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ።

ወበማእከሌኪ ፡ ኢየሩሳሌም ።

በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ።

## መዝሙር ፡ ፻፲፮ ።

፩ ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵልክሙ ፡ አሕዛብ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ የምእመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ። ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ መላችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

ወይሴብሕዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ።

ይኸውም ፡ እላንት ፡ ብቻ ፡ አይደላችሁም ፤ ሁለቱ ፡ ነገድም ፡ ያመሰግኑታል ። ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፲፩ ።

፪ ፡ እስመ ፡ ጸንዐት ፡ ምሕረቱ ፡ ላዕሌነ ።

ለኔ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ሚጠቱ ፡ ለኛ ፡ ጸንታ ፡ ተደርጋልናለችና ።

ወጽድቁሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሄሉ ፡ ለዓለም ።

ወጽድቁኒ ፡ ይላል ፤ ቸርነቱም ፡ ለዘላለም ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራልና ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፳፪ ። ግብ ፡ ፲፪ ፡ ፳፮ ።

እንድም ፡ ይህን ፡ ሲቁ ፡ በሥርዐተ ፡ ቅዳሴ ፡ ሐዲስ ፡ አድርጎ ፡ ወስዶታል ።

(ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵልክሙ ፡ አሕዛብ) ፡ ምእመናን ፡ አሕዛብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

(ወይሴብሕዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ) ። ምእመናን ፡ እስራኤል ፡ ያመስግኑታልና ።

(እስመ ፡ ጸንዐት ፡ ምሕረቱ ፡ ላዕሌነ) ። ልጅነት ፡ ለኛ ፡ ጸንታ ፡ ተደርጋልናለችና ። (ወጽድቁሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሄሉ ፡ ለዓለም) ። የእግዚአብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራልና ። እንድም ፡ ልጅነት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ።

2014 04 17

## መዝሙር ፻፲፯ ።

፩ ፡ ግንዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ኄር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ ቸር ነውና ፡ ቸር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፪ ፡ ንግሩ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ከመ ፡ ኄር ።

የእስራኤል ፡ ወገን ፡ የምትሆኑ ፡ ጭፆች ፡ ቸር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንገሩ ፤ አስተምሩ ።

ከመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንገሩ ።

፫ ፡ ንግሩ ፡ ቤተ ፡ አሮን ፡ ከመ ፡ ኄር ።

የአሮን ፡ ወገን ፡ ካህናት ፡ ቸር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንገሩ ፤ አስተምሩ ።

ከመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዘላለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

፬ ፡ ንግሩ ፡ ዙሉከሙ ፡ እለ ፡ ትፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኄር ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የምትፈሩት ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፤ እንድም ፡ መላችሁ ፡ እስራኤል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንገሩ ፤ አስተምሩ ።

ከመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዘላለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

፭ ፡ ሶበ ፡ ተመንደብኩ ፡ ጸዋዕክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ትሩፋ ፡ እንዲህ ፡ የምትል ፡ ምን ፡ አድርጎልኻል ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መከራ ፡ ባገኘኝ ፡ ጊዜ ፡ ለመንሁት ።

ሰምዐኒ ፡ ወአርሐበ ፡ ሊተ ።

ልመናዬን ፡ ሰምቶ ፡ ተድላ ፡ ደስታዬን ፡ አበዛልኝ ፤ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ አለ ።

፮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረድአኒ ፡ ኢይፈርህ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ምንተ ፡ ይሬስየኒ ።

እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛል ፤ አልፈራም ፤ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ። እንድም ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፡ ብዬ ፡ አልፈራም ። ዘኍ ፡ ፲፬ ፡ ፱ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴፩ ።

፯ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረድአኒ ፤ ወአነ ፡ እሬኢ ፡ ለጸላእትየ ።

እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛል ፤ እኔም ፡ ጠላቶቼን ፡ ንቄ ፡ አጥቅቼ ፡ አያቸዋለሁ ።



፰ ፡ ይኄይስ ፡ ተአምኖ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምተአምኖ ፡ በዕጓለ ፡ እመሕያው ።

በሰራዊቱ ፡ [illegible] ን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማመን ፡ ይበልጣል ።

፱ ፡ ይኄይስ ፡ ተሰፍዎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምተሰፍዎ ፡ በመላእክት ።

በንሰጎል ፡ ንጉሡ ፡ ግብጽ ፡ ከማመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማመን ፡ ይበልጣል ። እንድም ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ በተሠራ ፡ ጣዖት ፡ ከማመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማመን ፡ ይበልጣል ። (ይኄይስ) ፡ በአጋንንት ፡ ከማመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማመን ፡ ይበልጣል ። ኢሳ ፡ ፳ ፡ ፮ ።

፲ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ዐገቱኒ ።

አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ከበቡኝ ።

ወበስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሞኦክዎሙ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርቼ ፡ ድል ፡ ነሣኋቸው ።

፲፩ ፡ ዐጊተሰ ፡ ዐገቱኒ ።

መከበብን ፡ ከበቡኝ ።

፲፪ ፡ ዐገቱኒ ፡ ከመ ፡ ንህብ ፡ መዓረ ።

ሲከቡኝም ፡ ንህብ ፡ መዓርን ፡ እንደሚከበው ፡ ከበቡኝ ።

ወነደ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ አሥዋክ ።

እሳት ፡ ሥብ ፡ ነው ፤ ሥብ ፡ በእሳት ፡ እንዲቀልጥ ፡ ጠፉ ፤ ዐረብ ፡ እሳት ፡ ሲል ፡ ሥብ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ ከመ ፡ አሥዋክ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ እሾኽ ፡ በእሳት ፡ ጢ ፡ ጢ ፡ ብሎ ፡ እንዲያልቅ ፡ አለቁ ።

ወበስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሞኦክዎሙ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርቼ ፡ ድል ፡ ነሣኋቸው ። ኢሳ ፡ ፴፫ ፡ ፲፪ ። ዘዳ ፡ ፩ ፡ ፬ ።

፲፫ ፡ ተንተንኩ ፡ ለወዲቅ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ አንሥአኒ ።

በመከራው ፡ ልያዝ ፡ ቀረበሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከመከራው ፡ አዳነኝ ።

፲፬ ፡ ኀይልየኒ ፡ ወዝማሬየኒ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ብዋጋ ፡ ኃይሌ ፡ ስም ፡ አጸራሬ ፡ ነው ።

ወኮኖ ፡ ሊተ ፡ መድኃኒተ ።

እሱም ፡ ድኅነት ፡ ሆነኝ ። ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፪ ። ኢሳ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ።

፲፭ ፡ ቃለ ፡ ትፍሥሕት ፡ ወሰላም ፡ በአብያተ ፡ ጻድቃን ።

በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ጉባኤ ፡ ሚጠት ፡ ይደረጋል ፡ የሚል ፡ የደስታ ፡ ቃል ፡ ተሰማ ። እንድም ፡ በጻድቃን ፡ አገር ፡ በገነት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ የምስጋና ፡ ቃል ፡ ተሰማ ።

የማነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብረት ፡ ኀይለ ።

ሥልጣን ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይ ... አደረገች ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፶፩ ።

2014 04 17

[illegible]

ሥልጣን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገችኝ ።

[illegible]

ሥልጣን ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀይ ልን ፡ አደረገች ። [illegible] ፡ መሆን ፡ [illegible] ፡ ቃሉ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ ምሳሌ ። [illegible]

[illegible]

እደናለሁ ፡ እንጂ ፡ አልሞትም ።

[illegible]

የእግዚአብሔርንም ፡ ሥራውን ፡ እነግራለሁ ፡ እስተምራለሁ ።

[illegible]

እግዚአብሔር ፡ መገሠጽን ፡ ገሠ ጸኝ ።

[illegible]

ነገር ፡ ግን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ አልሰጠኝም ። [illegible]

[illegible]

የቤተ ፡ መቅደስን ፡ በር ፡ ክፈ ቱልኝ ።

[illegible]

ከዚያ ፡ ገብቼ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እገዛ ፡ እገልግል ፡ ዘንድ ።

[illegible]

ይህች ፡ ኢያሩሳሌም ፡ እንደም ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ በር ፡ እግዚ አብሔር ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡ ለትሩ ፋን ፡ [illegible] ፡ ናት ።

[illegible]

ትሩፋን ፡ ይገቡባታል ። እንደም ፡ (ከርኅወ ፡ ሊተ ፡ አናቅጸ ፡ ጽድ ቅ) ፡ የኀንትን ፡ በር ፡ ክፈቱልኝ ። ወእግቢኦ ፡ ለሰራሌ ፡ በውስቴ ፡ እጼሁ ፡ ሰይፈ ፡ እሳት ፡ እንዲል ። (አባል) ፡ ከዚያ ፡ ገብቼ ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ እገዛ ፡ ዘንድ ። (ዛ ፡ አን ቀጸ) ፡ ይህች ፡ ኀንት ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ለጻድቃን ፡ በደሙ ፡ ፀል ሶ ፡ ጉልቶ ፡ የሠራት ፡ ናት ። (ጻድቃን) ፡ በቅሙ ፡ ጻድቃን ፡ ይገቡባታል ።

[illegible]

አበቱ ፡ ሊመናቹን ፡ ሰምተኸኛል ና ፡ አገለግልሃለሁ ።

[illegible]

ድኅነትም ፡ ሆንኸኛልና ።

[illegible]

አናጠች ፡ የናቁት ፡ እብን ፡ መሠ [illegible]

[illegible]

አስተጋባኢተ ፡ ሕንጻ ፡ ሆንች ። [illegible] ፡ እንቅፅት ፡ አዕይንትም ፡ ይላል ፡ ሀሥራ ፡ ሁለት ፡ ምንጭ ፡ እሳት ፡ ሀሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ ሀየ



ነገዶቹው ፡ ይጠጣሉ ። ይህችም ፡ ጠላት ፡ የተነሣባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ረግረግ ፡ ውና ፡ ታስጥምናቸዋለች ፡ ተበትኖ ፡ ሄዱለች ፡ ዘሩባቤል ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ መቃን ፡ በያደረጋት ፡ አጠረች ፡ ጉበን ፡ በያደረጋት ፡ ረዘመች ፡ ወድቃ ፡ ትገኝራለች ። ሕንጻው ፡ ተፈጸሞ ፡ እንደ ፡ መእዝን ፡ መግ ጠሚያ ፡ ሲቀር ፡ በፈቃደ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ በገዛ ፡ እጁዋ ፡ ገጥ ማ ፡ ተገኝታለችና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። [illegible]

[illegible]

የመእዝን ፡ መሰብሰቢያ ፡ መሆኗ ፡ መናቋም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈ ቃድ ፡ ነው ።

[illegible]

ይህችውም ፡ ላይነ ፡ ሥጋችን ፡ ድንቅ ፡ ናት ። እንድም ፡ (አብን) ፡ አሕዛብ ፡ የናቁት ፡ ዘሩባቤል ፡ (ወይሊቴ) ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆነ ። (እምኀበ ፡ እግዚአብሔር) ፡ መናቂም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሆ ኑም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነው ። (ወንካር) ፡ ይኸውም ፡ ላይነ ፡ ሥጋችን ፡ ድንቅ ፡ ነው ። እንደ ም ፡ (አብን) ፡ እይሁድ ፡ [illegible] ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ [illegible]

[illegible] ፡ በዐረ ፡ [illegible] ፡ እግዚአብሔርን ፡ [illegible] ፡ በዐረ ፡ [illegible] ፡ እግዚአብሔር ፡ [illegible] ፡ ነፍሳችን ፡ [illegible]

[illegible]

[illegible]

ይህች ፡ [illegible] ፡ እግዚአብሔር ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ ሁሉ ፡ [illegible] ፡ ናት ፡ እንደም ፡ ይህች ፡ [illegible] ፡ እግዚአብሔር ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ ናት ።

[illegible]

[illegible]

[illegible]

አቤቱ ፡ አድኅን ፡ እንደም ፡ አድ ነን ፡ አቤቱ ፡ አድኅን ።

[illegible]

አቤቱ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ እቅናልና ።

[illegible]

[illegible]

2014 04 18

ክቡር ፡ ነው ። እንድም ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ባወጣለት ፡ ስም ፡ በስ
ምዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ መስክሮለት ፡ የመጣ ፡
ጌታ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

ባረክናክሙ ፡ እምቤተ ፡ እግዚአብሔር ።

ከቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተወፃዕ
ተን ፡ አከበርናችሁ ፡ ይላሉ ፡ ነ
ቢያት ፡ ካህናት ፤ እንድም ፡ ሐዋር
ያት ፡ ማቴ ፡ ፳፩ ፡ ፱ ። ማር ፡ ፲፩ ፡ ፲ ።

፳፯ ፡ እግዚአብሔር ፡ እግዚእ ፡ አስተርአየ ፡ ለነ ።

በምልአት ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡
በረድኤት ፡ ተገለጸ ፤ እንድም ፡
በሥጋ ፡ ተገለጸ ።

ግበሩ ፡ በዓለ ፡ በትፍሥሕት ፡ በኅበ ፡ እለ ፡ ያ
ስተሐምምዎ ።

እምነበ ፡ እለ ፡ ያስተምሙ ፡ ሎቱ ፡
ይላል ፤ ለሱ ፡ ከሚያስተነትኑ ፡
በሱ ፡ ስም ፡ ከሚያስተምሩ ፡ ከነ
ቢያት ፡ ከካህናት ፡ አብነት ፡
ነሥታችሁ ፡ የብሉዩን ፡ በዓል ፡
አክብሩ ። እንድም ፡ በሱ ፡ ስም ፡
ከሚያስተምሩ ፡ ከሐዋርያት ፡ አብ
ነት ፡ ነሥታችሁ ፡ የሐዲሱን ፡
በዓል ፡ አክብሩ ፤ እንድም ፡ ከሰ
ማዕታት ፡ አብነት ፡ ነሥታችሁ ፡
መከራ ፡ ተቀበሉ ። እንድም ፡
ምግባር ፡ ሠርታችሁ ፡ ዕረፍት ፡
ነፍስ ፡ አግኙ ። በዓሎሙ ፡ ለአ
እጹግ ፡ ገዳም ፡ እንዲል ።

እስከ ፡ አቅርንቲሁ ፡ ለምሥዋዕ ።

አቅርንተ ፡ ምሥዋዑን ፡ ሥብ ፡
እስከ ፡ መምላት ፡ ደርሳችሁ ።
እንድም ፡ አቅርንተ ፡ ምሥዋ
ውን ፡ እስከ ፡ መያዝ ፡ ደርሳችሁ ።
እንድም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡
እስከ ፡ መምላት ፡ ደርሳችሁ ፡
እንድም ፡ መስቀል ፡ ቀኖት ፡
እስከ ፡ መቀበል ፡ ደርሳችሁ ።

፳፰ ፡ አምላኪየ ፡ አንተ ፡ እገኒ ፡ ለከ ።

ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ ነኸና ፡ እገዛ
ልኻለሁ ።

አምላኪየ ፡ አንተ ፡ ወእሌዕለከ ።

ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ ነኸና ፡ ልዑል ፡
እያልሁ ፡ አመሰግንኻለሁ ።

እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚእ ፡ እስመ ፡ ሰማዕከኒ ።

ልመናዬን ፡ ሰምተኸኛልና ፡ እገ
ዛልኻለሁ ።

ወኮንከኒ ፡ መድኀኒየ ።

ድኅነትም ፡ ሁነኸኛልና ።

፳፱ ፡ ግነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ኄር ።

ቸር ፡ ነውና ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ተገዙ ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፤ ስለ ፡
ሆነ ።





ክፍል ፡ ፩ ፡ አሌፍ ፡ ብፁዓን ፡ እሉ ፡ እግዚአ
ብሔር ።

አሌፍ ፡ ማለት ፡ ፩ዱ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህንም ፡ አሌ
ፋት ፡ አዳም ፡ በገነት ፡ ሳለ ፡ ሰባ
ት ፡ ዓመት ፡ ሲጸልየው ፡ ኑሯል ።
ኋላ ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ በላ ፡ ሳተ ፤ ተሰ
ውሮታል ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የተነ
ሡ ፡ አበው ፡ ደመ ፡ አቤል ፡ ያስጥ
መን ፡ እያሉ ፡ የሚያምኑ ፡ ሁነዋ
ል ። ጌታ ፡ በዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ደም ፡
እይማሉ ፡ ብሎ ፡ ለሔኖክ ፡ በጸፍጸ
ፈ ፡ ሰማይ ፡ ጽፎ ፡ አሳየው ፤ በብ
ርት ፡ ቀርጾ ፡ አኑሮታል ፤ ከዚያ ፡
በኋላ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የ
ሚምሉ ፡ ሁነዋል ። ነቢያትም ፡
በየመጻፋቸው ፡ እየወሰዱ ፡ ጽፈ
ውታል ። ኤርምያስም ፡ አራት ፡
ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ ተናግሮታል ፤
ዳዊትም ፡ ባሥረኛው ፡ አርእ
ስት ፡ ተናግሮታል ። ይኸውም ፡
ዐሥሩ ፡ ቃላት ፡ ናቸው ። ዘጠ
ኙን ፡ ትእዛዘከ ፡ ፍኖተከ ፡ ኩነ
ኔከ ፤ ኢታምልክን ፡ ሰምዐከ ፡
እያላቸው ፡ ይሄዳል ። ስምዕከ ፡
እለ ፡ መስክሮ ፡ ሠርቶታልና ።
ቃልከ ፡ እለ ፡ ተናግሮ ፡ ሠርቶ
ታልና ። ፍናዊከ ፡ እለ ፡ በመንገ
ድ ፡ እንዲሄዱበት ፡ ሰውም ፡ በሕጉ ፡
ጸንቶ ፡ ይኖራልና ። ኩነኔከ ፡
እለ ፡ ይፈርድበታልና ፤ ትእዛ
ዝከ ፡ እለ ፡ እዝዞ ፡ ሠርቶታልና ።
እንድም ፡ ይህንኑ ፡ ቅሉ ፡ የሚ
ያዘዋውረው ፡ እለ ።

፩ ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ንጹሓን ፡ በፍኖቶሙ ።

በሃይማኖት ፡ ከክሕደት ፡ ንጹ
ሓን ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ንኡዳን ፡
ክቡራን ፡ ናቸው ።

ወእለ ፡ የሐውሩ ፡ በሕገ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ በሠራቸው ፡ በዘ
ጠኙ ፡ ሕገጋት ፡ ጸንተው ፡ የሚ
ኖሩ ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።
እንድም ፡ በምግባር ፡ ከኀጢአት ፡
ንጹሓን ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡
ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።
(ወእለ ፡ የሐውሩ) ፡ በማናቸውም ፡
ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸንተው ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ንኡዳን ፡ ክቡ
ራን ፡ ናቸው ።

፪ ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ የኀሥሡ ፡ ስምዖ ።

እምልኮቱን ፡ የሚሹ ፡ ማለት ፡
በኢታምልክ ፡ ጸንተው ፡ የሚ
ኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡
ናቸው ።

ወበኵሉ ፡ ልቦሙ ፡ የኀሥሥዎ ።

በፍጹም ፡ ልቡናቸው ፡ የሚሹት ፡
ሰዎች ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ና
ቸው ።

2014 04 18

፫ ፡ እለሰ ፡ ይገብሩ ፡ ዐመፃ ፡ ፍኖቶ ፡ ዘእው ፡ ኢሖሩ ።

በአመራረድ ፡ ተረጉመው ፡ የሚቀድመው ፡ አለ ።

፬ ፡ አንተ ፡ አዘዝከ ፡ ይዕቀቡ ፡ ትእዛዝከ ፡ ፈድፋደ ።

አንተ ፡ ትእዛዝህን ፡ ሕግህን ፡ ፈጽመው ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ፡ ብለህ ፡ አዝዘህ ፡ ነበር ። ዐመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ በሕግህ ፡ በትእዛዝህ ፡ ጸንተው ፡ አልኖሩም ። እንድም ፡ እሱ ፡ ሕጉን ፡ ትእዛዙን ፡ ፈጽመው ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ፡ ብሎ ፡ ሥራት ፡ ሠርቶ ፡ ነበር ፤ ዐመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ እሊሉ ፡ ግን ፡ ሕጉን ፡ ትእዛዙን ፡ አልጠበቁም ፤ በሕጉ ፡ በትእዛዙ ፡ ጸንተው ፡ አልኖሩም ።

፭ ፡ ይረትዕስ ፡ ይርታዕ ፡ ፍኖትየ ።

እንዲህስ ፡ የሚቀና ፡ ከሆነ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ መንገዴ ፡ ይቅናልኝ ።

ከመ ፡ እዕቀብ ፡ ሥንእከ ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼ ፡ ሕግህን ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ።

፮ ፡ ወእቱ ፡ ጊዜ ፡ ኢይትኀፈር ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼ ፡ ሕጉን ፡ በጠበቅሁ ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ መከራ ፡ መጥቶብኝ ፡ መከራውን ፡ አላፍርም ።

በርእየ ፡ ዘኵሉ ፡ ትእዛዝከ ።

ሕግህን ፡ በመስማት ፡ በመጠበቅ ።

፯ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ በልብ ፡ ርቱዕ ።

አቤቱ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ እገዛልኻለሁ ።

ሶበ ፡ ተመሀርኩ ፡ ኵነኔ ፡ ጽድቅከ ።

ምን ፡ ጊዜ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደ ሆነ ፡ እውነተኛውን ፡ ሕግህን ፡ በተማርሁ ፡ ጊዜ ።

፰ ፡ ወእዐቅብ ፡ ኵነኔከ ።

ሕግህን ፡ እጠብቃለሁ ።

ወኢትግድፈኒ ፡ ለዝሉፉ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ፈጽመህ ፡ በመከራው ፡ አትጣለኝ ።

ክፍል ፡ ፪ ፡ ቤት ፡ ብሂል ፡ ባዕል ፡ እግዚአብሔር ።

ቤት ፡ ማለት ፡ ባዕል ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ። ቢገናኝ ፡ አ ፡ አብ ።

፱ ፡ በምንት ፡ ያረትዕ ፡ ወሬዛ ፡ ፍኖቶ ።

ወሬዛ ፡ ትሩፍ ፡ ግብሩን ፡ ጐዳናውን ፡ በምን ፡ ያቀናል ፡ ብትል ፡

በዐቂበ ፡ ነቢብከ ።

ሕግህን ፡ በመጠበቅ ፡ ነዋ ። እንድም ፡ እንዲህ ፡ ቢሉ ፡ ሕግህን ፡ በመጠበቅ ፡ አይደለምን ።



፲ ፡ ወበኵሉ ፡ ልብየ ፡ ኀሠሥኩከ ።

በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ ሻሁህ ።

ኢታርሕቀኒ ፡ እምትእዛዝከ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ከሕግህ ፡ አታውጣኝ ፡ አትለየኝ ።

፲፩ ፡ ውስተ ፡ ልብየ ፡ ኀባእኩ ፡ ነቢብከ ።

ሃይማኖትህን ፡ በልቡናዬ ፡ ሰወርሁ ።

ከመ ፡ ኢየአብስ ፡ ለከ ።

ኪያክ ፡ አንተን ፡ እንዳልከድ ፡ አንተን ፡ ሕግህን ፡ በልቡናዬ ፡ ሰወርሁ ፡ አንተን ፡ እንዳልበድል ።

፲፪ ፡ ቡሩክ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነኽ ፡ ክቡር ፡ ምስጉንም ፡ ነኽ ።

ወምህረኒ ፡ ኵነኔከ ።

መህረኝ ፡ ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፡ አስተምረኝ ።

፲፫ ፡ በከናፍርየ ፡ ነገርኩ ፡ ኵሎ ፡ ኵነኔ ፡ አፉከ ።

ባንደበትህ ፡ የሠራኸውን ፡ ሕግህን ፡ ባንደበቴ ፡ ነገርሁ ፡ አስተማርሁ ።

፲፬ ፡ በፍኖተ ፡ ስምዕከ ፡ ተፈገፍኩ ።

በእምልኮትህ ፡ ጐዳና ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ ማለት ፡ እምልኮትህን ፡ በመጠበቅ ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

ከመ ፡ ዘበዝኀ ፡ ብዕል ።

ፍጹም ፡ ብዕል ፡ እንዳገኘ ፡ ሰው ። ወርቅ ፡ ብር ፡ አግኝቶ ፡ ፈረስ ፡ በቅሎ ፡ ያጣ ፡ እንደሆነ ፡ ያዝናል ፤ ፈረስ ፡ በቅሎም ፡ አግኝቶ ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ ያጣም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያዝናል ። ሁሉንም ፡ ያገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይለዋልና ።

፲፭ ፡ ወእዛዋዕ ፡ በትእዛዝከ ።

ሕግህን ፡ ተግባር ፡ አድርጌ ፡ እኖራለሁ ።

ወእኀሥሥ ፡ ፍኖቶከ ።

ሕግህን ፡ ለራሴ ፡ እሻለሁ ።

፲፮ ፡ ወእነብብ ፡ ትእዛዛቲከ ።

አዝዘህ ፡ የሠራኸውን ፡ ሕግህንም ፡ ለሌላው ፡ እነግራለሁ ፤ አስተምራለሁ ።

ወኢይረስዕ ፡ ቃለከ ።

ተናግረህ ፡ የሠራኸውን ፡ ሕግህንም ፡ አልዘነጋም ።

ክፍል ፡ ፫ ፡ ጋሜል ፡ ብሂል ፡ ግሩም ፡ እግዚአብሔር ።

ጋሜል ፡ ማለት ፡ ግሩም ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲፯ ፡ ዕስዮ ፡ ለገብርከ ።

ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡ ሚጠትን ፡ ሐሤት ፡ ንስሓን ፡ ስጠው ።

ከመ ፡ እሕየው ፡ ወእዕቀብ ፡ ነቢብከ ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼ ፡ ከመከራ ፡

2014 04 18

[illegible]

ው ፡ በርና ፡ [illegible] ፡ ሕግሙም ፡
በመጠበቅ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ።

[illegible]

በደናቸን ፡ አብራችው ፡ እንድ
ም ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
ምክራር ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
ልዑን ።

[illegible]

ሕግሙን ፡ ከመጠበቁ ፡ የተገኘ ፡
መድምም ፡ [illegible] ፡ ተደረገ
ብኝ ። እንደም ፡ ሕግሙን ፡ ከመ
ጠበቁ ፡ የተገኘ ፡ ግሩም ፡ ድንቅ ፡
የሚሆን ፡ [illegible] ፡ ይደረግል
ኛል ።

[illegible]

እኔ ፡ በባዕዳን ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
ናኝ ።

[illegible]

ሕግሙን ፡ [illegible] ፡ እትሰውረው ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ ምክራር ፡ [illegible] ።

[illegible]

በውነቴ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ።

[illegible]

[illegible] ፡ [illegible] ፡ ሕግሙን ።

[illegible]

ትዕዛዛቶቹ ፡ ባዕዳንወንያን ፡ ሥ
ራችችው ፡ ቀደችችው ፡ እንደም ፡
[illegible] ፡ [illegible] ።

[illegible]

ትዕዛዛቶቹ ፡ ርኅማን ፡ የሚሆኑ ፡
ከሕግህ ፡ የወጡ ፡ ባዕዳንወንያን ፡
እንደም ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
ሥራችችው ፡ ቀደችችው ።

[illegible]

[illegible] ፡ ተቀርዶውን ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ።

[illegible]

ሕግሙን ፡ [illegible] ።

[illegible]

የባዕዳንወንያን ፡ እስቶች ፡ [illegible]
[illegible] ፡ ተቀምጠው ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ።

[illegible]

እኔ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ ነገር ፡ ነው ፡ [illegible] ፡ ሕግ
ሆን ፡ ተግባር ፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ።

[illegible]

ሕግህ ፡ [illegible] ፡ ትምርቴ ፡ ነ
ውና ።

[illegible]

[illegible] ፡ ሕጎንት ፡ ትምርቴ ፡
ናቸው ።



[illegible]

[illegible] ፡ [illegible] ፡ ጽድው ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ ነው ፡ [illegible] ፡
[illegible] ።

[illegible]

በውነቴ ፡ በባዕዳን ፡ ተቀረደች ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ እያሉ ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ እንደም ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ።

[illegible]

[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡ እንደም ፡ ሕግሙን ፡
በመጠበቁ ፡ እደናኝ ።

[illegible]

[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡ እስተማርው ።

[illegible]

ሕግሙን ፡ [illegible] ፡ [illegible]

[illegible]

[illegible] ፡ ሕግሙን ፡ [illegible]
[illegible] ።

[illegible]

ድንቅ ፡ የሚሆን ፡ [illegible] ፡
ተግባር ፡ እድርጌ ፡ [illegible] ።

[illegible]

[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ።

[illegible]

[illegible] ፡ እንደም ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
ናኝ ።

[illegible]

[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ።
እንደም ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ የባዕዳንወንያን ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ።

[illegible]

ሕግሙን ፡ በመጠበቁ ፡ [illegible] ፡
[illegible] ።

[illegible]

[illegible] ፡ ሕግሙን ፡ [illegible]
[illegible] ።

[illegible]

ሕግሙም ፡ [illegible] ።

[illegible]

[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ።

እንዲሁም ፡ ከሆነ ፡ አንተም ፡ በመከራው ፡ አታሳፍረኝ ። እንድም ፡ በመከራው ፡ እንዳታሳፍረኝ ፡ ባንተ ፡ አመንሁ ። እንድም ፡ አቤቱ ፡ ባንተ ፡ እምኛለሁና ፡ በመከራው ፡ አታሳፍረኝ ።

፴፪፡ ፍኖተ ፡ ትእዛዝከ ፡ ሮጽኩ ።

አዝዘህ ፡ በሠራኻቸው ፡ በዘጠኙ ፡ ሕጋጋትም ፡ ጸናሁ ። እንዲም ፡ ጸንቼ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወረድሁ ።

ሶበ ፡ አርሐብኮ ፡ ለልብየ ።

ልቡናዬን ፡ በዕውቀት ፡ ባሰፋኸው ፡ ጊዜ ።

ክፍል ፡ ፭፡ ሄ ፡ ብሂል ፡ ሀልው ፡ እግዚአብሔር ።

ሄ ፡ ማለት ፡ ህልው ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፴፫፡ ምሀረኒ ፡ እግዚእ ፡ ፍኖተ ፡ ጽድቅከ ።

አቤቱ ፡ እውነተኛውን ፡ ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፡ አስተምረኝ ።

ወእኅሥሥ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ሁል ፡ ጊዜ ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ።

፴፬፡ አለብወኒ ፡ ወእኅሥሥ ፡ ሕገከ ።

ሕግህን ፡ እሻ ፡ ዘንድ ፡ ዕውቀት ፡ ግለጽልኝ ።

ወእዕቀቦ ፡ በኵሉ ፡ ልብየ ።

በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ ልጠብቀው ።

፴፭፡ ምርሐኒ ፡ ፍኖተ ፡ ትእዛዝከ ።

አዝዘህ ፡ የሠራኸው ፡ ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፡ አስተምረኝ ።

እስመ ፡ ኪያሃ ፡ ፈቀድኩ ።

ሕግህን ፡ ሽቻለሁና ።

፴፮፡ ሚጥ ፡ ልብየ ፡ ውስተ ፡ ስምዕከ ።

ልቡናዬን ፡ ወደ ፡ እምልኮትህ ፡ መልሰው ።

ወአኮ ፡ ውስተ ፡ ትዕግልት ።

ወደ ፡ ጣዖት ፡ ያይደለ ፡ ወይስትዩ ፡ ወይኑ ፡ ትዕግልት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አምላኮሙ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ (ሚጥ) ፡ ልቡናዬን ፡ ወደ ፡ ሕግህ ፡ መልስ ። (ወአኮ) ፡ ወደ ፡ ቅሚያ ፡ ያይደለ ።

፴፯፡ ሚጦን ፡ ለአዕይንትየ ፡ ከመ ፡ ኢይርአያ ፡ ከንቶ ።

ከንቱ ፡ ነገርን ፡ እንዳያዩ ፡ ዐይኖቼን ፡ መልሳቸው ፡ ማለት ፡ ከንቱ ፡ ጣዖትን ፡ እንዳያመልኩ ፡ ሰውነቶቼን ፡ ወደ ፡ አምልኮትህ ፡ መልሳቸው ።

ወአሕይወኒ ፡ በፍኖትከ ።

ሕግህን ፡ በመጠበቁ ፡ አድነኝ ።

፴፰፡ አቅም ፡ ለገብርከ ፡ ዘነበብከ ፡ ውስተ ፡ ነቢብከ ።

አቅም ፡ ለገብርከ ፡ ዘነበብከ ፡ ለገብርከ ፡ ይላል ፡ እውነት ፡ በሚናገር ፡ ቃልህ ፡ ወስብዓ ፡ ዓም ፡ ኀሊቆን ፡ ብለህ ፡ የተናገርኸውን ፡ ቃል ፡ ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡ አድርግለት ። እንብብ ፡ በውስተ ፡ ወንጌሉ ፡ ዘሠርዐ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲል ።



፴፱፡ አእትት ፡ ሕምኔየ ፡ ጽዕለተ ፡ ዘተሐዘብኩ ።

የተጠራጠርሁትን ፡ ስድቡን ፡ ከኔ ፡ አርቀው ። ባሮቻችን ፡ ናችሁ ፡ አትወጡም ፡ እያሉ ፡ ይሰድቧቸዋል ፡ እውነት ፡ ባቢሎን ፡ ተማርኮ ፡ ለመቅረት ፡ ነው ፡ የፈጠርከን ፡ እያሉ ፡ ያዝናሉና ።

እስመ ፡ ሠናይ ፡ ኵነኔከ ።

ሕግህ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነውና ።

፵፡ ናሁ ፡ ፈተውኩ ፡ ትእዛዘከ ።

እነሆ ፡ ሕግህን ፡ ወድጃለሁና ።

ወአሕይወኒ ፡ በጽድቅከ ።

በቸርነትህ ፡ አድነኝ ።

ክፍል ፡ ፮፡ ዋው ፡ ብሂል ፡ ዋሕድ ፡ እግዚአብሔር ።

ዋው ፡ ማለት ፡ ዋሕድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢገናኝ ፡ ሐው ። እምብዝኀ ፡ ትንታት ፡ ለሐው ፡ ይበዝኀ ፡ ፍሕሙ ፡ እንዲል ። ሢራ ፡ ፲፩ ፡ ፴፪

፵፩፡ ይምጻእ ፡ ላዕሌየ ፡ ምሕረትከ ፡ እግዚእ ።

ሊቱ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ አቤቱ ፡ ቸርነትህ ፡ ይደረግልኝ ።

እግዚእ ፡ አድኅኖትከ ፡ በከመ ፡ ነቢብከ ።

አቤቱ ፡ ወስብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡ በተናገርኸው ፡ እንድም ፡ ሕግህን ፡ በመጠበቁ ፡ ትድግናህን ፡ አድርግልኝ ።

፵፪፡ አውሥኦሙ ፡ ቃለ ፡ ለእለ ፡ ይጼእሉኒ ።

እኔስ ፡ አልችልልህምና ፡ ለሚሰድቡኝ ፡ ለባቢሎናውያን ፡ ቃል ፡ መልስላቸው ። ስጠኝ ፡ ፍጆታ ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ የግብር ፡ ሙግት ፡ ነው ።

እስመ ፡ ተወከልኩ ፡ ቢቃልከ ።

በሕግህ ፡ እምኛለሁና ።

፵፫፡ ኢታእትት ፡ ቃለ ፡ ጽድቅ ፡ እምአፉየ ፡ ለግሙራ ።

እውነተኛውን ፡ ሕግህን ፡ ካንደበቴ ፡ ፈጽመህ ፡ አታርቀው ።

እስመ ፡ ተወከልኩ ፡ በኵነኔከ ።

በሕግህ ፡ ጸንቻለሁ ፡ እምኛለሁና ።

፵፬፡ ወእዐቅብ ፡ ሕገከ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሕግህን ፡ እጠብቃለሁ ።

ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለሙ ።

፵፭፡ ወአሐውር ፡ ስፉሐ ።

ስፉሐ ፡ አእምሮ ፡ ሁኜ ፡ እኖራለሁ ።

2014 04 18

እስመ ፡ ትእዛዝከ ፡ ገሥሥኩ ።

ሕግህን ፡ ሽቻለሁና ።

፺፮ ፡ ወእንግር ፡ ስምዐከ ፡ በቅድመ ፡ ነገሥት ፡ ወኢይትኀፈር ።

በንገሥታቱ ፡ ፊት ፡ ሕግህን ፡ እምልክህን ፡ እናገራለሁ ፡ ስና ገርም ፡ አላፍርም ፡ እንዷህ ፡ የ ሚሉ ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ ናቸው ።
ጉባ ፡ ፲፫ ፡ ፲፮ ፡ ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ፡ ፳፭ ።

፺፯ ፡ ወአነብብ ፡ ትእዛዘከ ፡ ዘአፍቀርኩ ፡ ጥቀ ።

ፈጽሜ ፡ የወደድሁትን ፡ ሕግህን ፡ እነግራለሁ ፡ እስተምራለሁ ።

፺፰ ፡ ወአንሣእ ፡ እደውየ ፡ ኀበ ፡ ትእዛዝከ ፡ ዘአፍቀርኩ ።

እደ ፡ ቃሌን ፡ ለጸሎት ፡ እደ ፡ ሥጋ ዬን ፡ ለመሥዋዕት ፡ እደ ፡ ልቡ ናዬን ፡ ለአንክሮ ፡ ለተዘክሮ ፡ ወደ፡ ወደድሁት ፡ ሕግህ ፡ እነሣለሁ ።

ወአኀሥሥ ፡ በትእዛዝከ ።

ሕግህን ፡ ግብር ፡ አድርጌ ፡ እኖ ራለሁ ።

ክፍል ፡ ፯ ፡ ዛይ ፡ ብሂል ፡ ዝኩር ፡ እግዚአብሔር ።

ዛይ ፡ ማለት ፡ ዝኩር ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፺፱ ፡ ተዘከር ፡ ቃለከ ፡ ዘአስፈወከኒ ፡ ለገብርከ ።

ለባሪያህ ፡ ለኤርምያስ ፡ ተስፋ ፡ ያደረግህለትን ፡ ሚጠትን ፡ አስ ብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ።

፻ ፡ ወይእቲ ፡ አስተፍሥሐተኒ ፡ በሕማምየ ።

ይህችውም ፡ ሚጠት ፡ በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አሰኘችኝ ።

እስመ ፡ ቃልከ ፡ አሕየወኒ ።

በተናገርኸው ፡ ጊዜ ፡ እንድም ፡ ተናግረህ ፡ የሠራኸው ፡ ሕግህ ፡ አድ ኖኛልና ።

፻፩ ፡ ዕቡያን ፡ ዐመፁ ፡ ፈድፋደ ።

ዕቡያን ፡ ባቢሎናውያን ፡ እንድም ፡ ኤኮንያን ፡ ሴዴቅያስ ፡ ፈጽመው ፡ በደሉ ።

ወእምሕግከሰ ፡ ኢተግሕሥኩ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ከሕግህ ፡ አልወጣሁም ።

፻፪ ፡ ተዘከርኩ ፡ ፍትሐከ ፡ ዘእምዓለም ።

ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ ሲነ ገር ፡ የሚኖር ፡ ፈርደህ ፡ የሠራኸ ውን ፡ ሕግህን ፡ አሰብሁ ።

ወተፈሣሕኩ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ደስ ፡ አለኝ ። ኢሳ ፡ ፶፮ ፡ ፱ ።

፻፫ ፡ ሐዘን ፡ አኀዘኒ ፡ እምኃጥአን ፡ እለ ፡ ኀደጉ ፡ ሕገከ ።

ሕግህን ፡ ካፈረሱ ፡ ከኃጥአን ፡ ከባ ቢሎናውያን ፡ የተነሣ ፡ እንድም ፡ ከባቢሎናውያን፡ የመጣ ፡ መከራ ፡ አገኘኝ ።



፻፬ ፡ መዝሙረ ፡ ኮነኒ ፡ ሥርዐትከ ።

ሕግህ ፡ መጫወቻ ፡ ኾነኝ ።

በብሔር ፡ በኀበ ፡ ፈለስኩ ።

ተሰድጄ ፡ በሄድኹበት ፡ ሀገር ፡ በባ ቢሎን ።

፻፭ ፡ ተዘከርኩ ፡ በሌሊት ፡ ስመከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ በቁሙ ፡ በሌሊት ፡ እንድ ም ፡ በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ የአምላክነ ትህን ፡ ስም ፡ አሰብሁ ።

ወዐቀብኩ ፡ ሕገከ ።

ሕግህንም ፡ ጠበቅሁ ።

፻፮ ፡ ወይእቲ ፡ ኮነተኒ ።

ይህችውም ፡ ረባችኝ ፡ ጠቀመ ችኝ ።

እስመ ፡ ኵነኔከ ፡ ኀሠሥኩ ።

ሕግህን ፡ ሽቻለሁና ።

ክፍል ፡ ፰ ፡ ሔት ፡ ብሂል ፡ ሕያው ፡ እግዚ አብሔር ።

ሔት ፡ ማለት ፡ ሕያው ፡ እግዚ አብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢገ ናኝ ፡ ዛህን ።

፻፯ ፡ ክፍልየ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ዕድል ፡ ፈንታዬ ፡ ፅዋ ፡ ተርታዬ ፡ ነው ።

ወእቤ ፡ ይዕቀቡ ፡ ሕገከ ።

ሕግህን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ጠ ብቁ ፡ ብዬ ፡ አዘዝሁ ።

፻፰ ፡ ስእልኩ ፡ ገጸከ ፡ እግዚኦ ፡ በኵሉ ፡ ል ብየ ።

አቤቱ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ ገጼ ፡ ምሕረትህን ፡ ገጼ ፡ ረድኤ ትህን ፡ ሻሁ ።

ተሣሀለኒ ፡ በከመ ፡ ነቢብከ ።

ቃሰብኅ ፡ ዓም ፡ ኃሊቆን ፡ ብለህ ፡ በተናገርኸው ፡ እንድም ፡ ሕግ ህን ፡ በመጠበቁ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

፻፱ ፡ ወኀለይኩ ፡ በእንተ ፡ ፍናዊከ ።

የሕግህን ፡ ነገር ፡ አሰብሁ ፡ ማ ለት ፡ ሕግህን ፡ ጠበቅሁ ።

ሜጥኩ ፡ እግርየ ፡ ውስተ ፡ ስምዐከ ።

እግረ ፡ ኅሊናዬን ፡ ወደ ፡ እምል ኮትህ ፡ መለስሁ ።

፻፲ ፡ አጥባዕኩ ፡ ወኢናፈቅ ፡ ለዐቂበ ፡ ትእዛ ዝከ ።

ሕግህን ፡ ለመጠበቅ ፡ ጨከንሁ ፡ ያድነኝን ፡ ይሆን ፡ አያድነኝ ፡ ብዬ ፡ አልተጠራጠርሁም ።

፻፲፩ ፡ አሕባለ ፡ ኃጥአን ፡ ተገፈፉ ፡ ላዕሌየ ።

ኃጥእን ፡ ባቢሎናውያን ፡ ገመድ ፡ ዘረጉብኝ ፡ ማለት ፡ ምክር ፡ መከ ሩብኝ ፡ ጦር ፡ ሸመቁብኝ ።

ወሕገከሰ ፡ ኢረሳዕኩ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሕግህን ፡ አልዘነጋ ሁም ።

፻፲፪ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ እትነሣእ ።

በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ እንድም ፡

2014 04 18

ለሀ ፡ እንደ ፡ ተናገርከው ፡ እንድም ፡ ሕግህን ፡ እንደ ፡ መጠበቄ ፡ ይደ ረግልኝ ።

፸፯ ፡ ይምጽኡኒ ፡ ሣህልከ ፡ ወእሕየው ።

ቸርነትህ ፡ ይደረግልኝ ፡ ወእሕየ ው ፤ እኔም ፡ ከመከራው ፡ ልዳን ።

እስመ ፡ ተምሃርየ ፡ ውእቱ ፡ ሕግከ ።

ሕግህ ፡ መማሬ ፡ ትምርቴ ፡ ነውና ። እንድም ፡ መማሬ ፡ ትምርቴ ፡ ሕ ግህ ፡ ነውና ።

፸፰ ፡ ይትኀፈሩ ፡ ዕቡያን ፡ እስመ ፡ ዐመ ፃ ፡ መከሩ ፡ ላዕሌየ ።

ባቢሎናውያን ፡ በኔ ፡ ዐመፃን ፡ መ ክረዋልና ፤ ይፈሩ ። እንድም ፡ እለ ፡ ዐመፃ ፡ መከሩ ፡ በኔ ፡ ዐመፅን ፡ የ መከሩ ፡ ባቢሎናውያን ፤ እንድም ፡ ኤኮንያን ፡ ሴዴቅያስ ፡ ይፈሩ ፤ ይዋ ረዱ ።

ወአንሰ ፡ እዛዋዕ ፡ በትእዛዝከ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ቢመክር ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ብዬ ፡ ሕግህን ፡ ተግ ግባር ፡ አድርጌ ፡ እኖራለሁ ።

፸፱ ፡ ይግብኡኒ ፡ እለ ፡ ይፈርሁከ ።

የኔስ ፡ የኔ ፡ ነውና ፤ የሚፈሩህ ፡ የሚ ያመልኩህ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ከባ ቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይመለ ሱልኝ ። የኃጥኡ ፡ ዳፋ ፡ ጻድቁን ፡ ያዳፋ ፡ እንዲሉ ፡ የኔ ፡ ዳፋ ፡ ተርፏ ቸው ፡ በባቢሎን ፡ አይቅሩ ።

ወእለ ፡ የአምሩ ፡ ስመከ ።

ስምህን ፡ ዐውቀው ፡ የሚወዱ ።

፹ ፡ ለይኩን ፡ ልብየ ፡ ንጹሐ ፡ በኵነኔከ ፡ ከመ ፡ ኢይትኀፈር ።

በመከራው ፡ እንዳላፍር ፡ ልቡናዬ ፡ በሕግህ ፡ ከኀጢአት ፡ በሃይማኖት ፡ ከክሕደት ፡ ንጹሕ ፡ ይሁን ።

ክፍል ፡ ፲፩ ፤ ካፍ ፡ ብሂል ፡ ከሃሊ ፡ እግዚአ ብሔር ።

ካፍ ፡ ማለት ፡ ከሃሊ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፹፩ ፤ ኀለፈት ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ አድኅኖ ትከ ።

ሰውነቴ ፡ ትድግናህን ፡ ናፈቀች ፤ ወደደች ።

ወተወከልኩ ፡ በቃልከ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡ በተናገርከ ው ፤ እንድም ፡ በሕግህ ፡ አመንሁ ።

፹፪ ፤ ደከማ ፡ አዕይንትየ ፡ ለመድኀኒትከ ።

ዐይኖቼ ፡ ትድግናህን ፡ በመሻት ፤ እንድም ፡ በመመልከት ፡ ደከሙ ። እንደ ፡ ባለቀጠሮ ፡ ካሁን ፡ ካሁን ፡ ይመጣል ፡ እያለ ፡ መንገድ ፡ መን ገዱን ፡ እንዲመለከት ።

እንዘ ፡ ይብላ ፡ ማእዜ ፡ ታስተፈሥሐኒ ።

ታስተፈሥሐኒ ፡ ቢል ፡ ይቀናል ፤ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አ ውጥተህ ፡ መቼ ፡ ደስ ፡ ታሰኘን ፡ ይሆን ፡ እያሉ ።



፹፫ ፤ እስመ ፡ ኮንኩ ፡ ከመ ፡ ዝቅ ፡ ውስ ተ ፡ አስሐትያ ።

ከውርጭ ፡ እንዳደረ ፡ ራዋት ፡ ሁኛ ለሁና ፡ ማለት ፤ ተዋርዶ ፡ ደቂቀውን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወዘኮነኔከሰ ፡ ኢረሳዕኩ ።

እኔ ፡ ግን ፡ መከራ ፡ ጸናብኝ ፡ ብዬ ፡ ከሕግህ ፡ አልወጣሁም ።

፹፬ ፤ ሚመጠን ፡ እማንቱ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለገብርከ ።

ባሪያህ ፡ ትሩፍ ፡ በባቢሎን ፡ የሚ ኖረው ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ብዬህ ፡ የለ ምን ፡ ቢለው ።

ማእዜ ፡ ትፈትሕ ፡ ሊተ ፡ እምእለ ፡ ይሰዱኒ ።

ማርከው ፡ ከሚወስዱኝ ፡ ከባቢሎና ውያን ፡ መቼ ፡ ትፈርድልኛለህ ፡ ይላል ።

፹፭ ፤ ነገሩኒ ፡ ኃጥአን ፡ ዛውዐ ።

ኃጥአን ፡ ባቢሎናውያን ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ነገሩኝ ፡ ማለት ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ አትርፈን ፡ እንገዛችኋለን ፡ አሉ ።

ወአኮሰ ፡ ከመ ፡ ሕግከ ፡ እግዚኦ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡ እንደ ፡ ተና ገርከው ፡ ያይደለ ። እንድም ፡ (ነገ ሩኒ) ፡ ጣዖት ፡ አምልክ ፡ አሉኝ ። ወያማስን ፡ አውግረ ፡ ዛውዕ ፡ እን ዲል ። (ወአኮሰ) ፡ ኢታምልክ ፡ ባዕ ድ ፡ አምላከ ፡ ዘእንበሌየ ፡ ብለህ ፡ እንደ ፡ ተናገርከው ፡ ያይደለ ።

፹፮ ፤ ኵሉ ፡ ትእዛዛቲከ ፡ ጽድቅ ።

ሕግህ ፡ ሁሉ ፡ እውነተኛ ፡ ነው ።

በዐመፃ ፡ ሰደዱኒ ፡ ርድአኒ ።

በግፍ ፡ ከሀገሬ ፡ አስወጥተው ፡ ሰደ ዱኛልና ፡ ርዳኝ ፡ አድነኝ ።

፹፯ ፤ ሕቀ ፡ ከመ ፡ ዘምድርምሰሉኒ ፡ ውስ ተ ፡ ምድር ።

ከባቢሎን ፡ ሊያጠፉኝ ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ቀርቶኝ ፡ ነበረ ። እንድም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ሊያወርዱኝ ፡ ጥ ቂት ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ቀርቶኝ ፡ ነበረ ።

ወአንሰ ፡ ኢኀደጉ ፡ ትእዛዘከ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሕግህን ፡ አልተውሁም ፤ ማለት ፤ አላፈረስሁም ።

፹፰ ፤ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አሕይወኒ ።

እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ከመከራው ፡ አድነኝ ።

ወእዕቀብ ፡ ስምዐ ፡ አፉከ ።

ባንደበትህ ፡ የሠራኸው ፡ አምልኮ ትህን ፡ ልጠብቅ ።

ክፍል ፡ ፲፪ ፤ ላሜድ ፡ ብሂል ፡ ልዑል ፡ እግ ዚአብሔር ።

ላሜድ ፡ ማለት ፡ ልዑል ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢገኝ ፡ ዙሉ ።

2014 04 18

፹፱ ፤ እግዚኦ ፡ ለዓለም ፡ ይነብር ፡ ቃልከ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ።

አቤቱ ፡ ለይኩን ፡ ብለህ ፡ የፈጠር ከው ፡ ብርሃን ፤ እንድም ፡ ሕግህ ፡ ባለማለፍ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

፺ ፤ ወለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ጽድቅከ ።

ቸርነትህም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ሲነ ገር ፡ ይኖራል ።

ሣረርካ ፡ ለምድር ፡ ወትነብር ።

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ምድርን ፡ ፈጠርኻት ፤ ለዘላለም ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ።

፺፩ ፤ ወበትእዛዝከ ፡ ይቀውም ፡ ዕለት ።

የፈጠርኸው ፡ ፀሐይ ፡ ባንተ ፡ ትእ ዛዝ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ። ስማ ፡ ለአ ሐቲ ፡ ዕለት ፡ እንዲል ።

እስመ ፡ ኵሉ ፡ ቀንይከ ።

ሁሉን ፡ ፈጥረኻልና ። እ ፡ እብ ፡ ኵሎ ፡ ቀንይከ ፡ እንዲል ።

፺፪ ፤ ሶበ ፡ እኮ ፡ ሕግከ ፡ ተምሃርየ ፡ ውእቱ ።

ሕግህ ፡ መምሬ ፡ ትምርቴ ፡ ባይሆን ፡

ትካት ፡ እምተሀጕልኩ ፡ በኀሳርየ ።

በኀጢአት ፡ ሳለሁ ፡ እንድም ፡ በመ ከራዬ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ በጠፋሁ ፡ ነበር ።

፺፫ ፤ ለዓለም ፡ ኢይረስዕ ፡ ኵነኔከ ።

ሕግህን ፡ ለዘላለም ፡ አልዘነጋም ።

እስመ ፡ ቦቱ ፡ አሕየውከኒ ።

ሕግህን ፡ በመጠበቅ ፡ ከመከራ ፡ አድነኸኛልና ።

፺፬ ፤ ዘዚአከ ፡ አነ ፡ አድኅነኒ ።

እኔ ፡ ያንተ ፡ ገንዘብ ፡ ነኝና ፡ አድ ነኝ ።

እስመ ፡ ኵነኔከ ፡ ኀሠሥኩ ።

ሕግህን ፡ ሻቻለሁና ።

፺፭ ፤ ኪያየ ፡ ይጸንሑ ፡ ኃጥአን ፡ ይቅትሉኒ ።

ባቢሎናውያን ፡ ይገሉኝ ፡ ዘንድ ፡ ያደፍጡብኛል ፤ ይሸምቁብኛል ።

እስመ ፡ ስምዐከ ፡ ለበውኩ ።

እምልኮትህን ፡ ይገርለሁ ፤ ሕግህን ፡ ጠብቄ ፡ አለሁና ።

፺፮ ፤ ለኵሉ ፡ ግብር ፡ ርኢኩ ፡ ማኅለቅቶ ።

የሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ዐወ ቅሁ ፤ ቢገዙ ፡ ቢነዱ ፡ ያልፋል ።

ወትእዛዝከሰ ፡ ርሒብ ፡ ፈድፋደ ።

ሕግህ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ ሰፊ ፡ ነው ፤ አያልፍም ።

ክፍል ፡ ፲፫ ፤ ሜም ፡ ብሂል ፡ ምዑዝ ፡ እግ ዚአብሔር ።

ሜም ፡ ማለት ፡ ምዑዝ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፺፯ ፤ ጥቀ ፡ አፍቀርኩ ፡ ሕገከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ፡ሕግህን፡ ፈጽሜ፡ ወደድሁ ፤ ናፈቅሁ ።



ወኵሎ ፡ እሚረ ፡ ተምሃርየ ፡ ውእቱ ።

ዕለት፡ ዕለት፡ ሕግህ፡ መምሬ፡ ትም ርቴ ፡ ነውና ።

፺፰ ፤ ወእምጸላእትየ ፡ አጥበብከኒ ።

ከጠላቶቼ ፡ ይልቅ ፡ ሕግህ ፡ አራቀ ቀኝ ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ሊተ ፡ ውእቱ ።

ለዘላለም፡ መምሬ፡ትምርቴ፡ ነውና።

፺፱ ፤ ወእምኵሎሙ ፡ እለ ፡ መሀሩኒ ፡ ጠበ ብኩ ።

ከሚያስተምሩኝ ፡ ይልቅ ፡ ሕግህ ፡ አራቀቀኝ ።

እስመ ፡ ተምሃርየ ፡ ውእቱ ፡ ትእዛዝከ ።

ሕግህ ፡ መምሬ፡ ትምርቴ ፡ ነውና ።

፻ ፤ ወእምአእሩግኒ ፡ ጠበብኩ ።

ከሽማግሎች ፡ ይልቅ ፡ ዐዋቂ ፡ ሆን ሁ ፤ ይህ ፡ ዳንኤል ፡ ነው ። አብዳ ንኑ ፡ አንትሙ ፡ ዘትኴንኑ ፡ ወለተ ፡ እስራኤል ፡ ዘእንበለ ፡ ትሕትቱ ፡ ወ ትጠይቁ ፡ ብሏቸዋል ።

እስመ ፡ ትእዛዘከ ፡ ኀሠሥኩ ።

ሕግህን ፡ ሻቻለሁና ።

፻፩ ፤ እምኵሉ ፡ ፍኖተ ፡ ዐመፃ ፡ ከላእኩ ፡ እግርየ ።

ከዐመፅ ፡ ሥራ፡ ሁሉ ፡ እግሬ ፡ ልቡ ናዬን ፡ ለየሁ ። እንድም ፡ ፍኖተ ፡ ዐማፅያን ፡ ከባቢሎናውያን ፤ እን ድም ፡ ከኤኮንያን ፡ ከሲዶቅያስ ፡ ግብር ፡ እግሬ ፡ ልቡናዬን ፡ ከለከ ልሁ ።

ከመ ፡ እዕቀብ ፡ ነቢበከ ።

ተናግረህ ፡ የሠራኸውን ፡ ሕግህን ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ።

፻፪ ፤ ወኢተግሕሥኩ ፡ እምኵነኔከ ።

ከሕግህም ፡ አልወጣሁም ።

እስመ ፡ አንተ ፡ ምህርከኒ ።

አንተ ፡ ገልጸኸልኛል ፡ አስተምረ ኸኛልና ።

፻፫ ፤ ጥዑም ፡ ለጕርዔየ ፡ ነቢብከ ።

ሕግህ ፡ ለሰውነቴ ፡ የተስማማ ፡ ነው ።

እመዓር ፡ ወሶከር ፡ ጥዑምኒ ፡ ለአፉየ ።

ከመዓር ፡ ከሸንኩር ፡ ይልቅ ፡ ላንደ በቴ ፡ የጣፈጠ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ የተ ስማማ ፡ ነው ።

፻፬ ፤ ወእምትእዛዝከ ፡ ለበውኩ ።

ሕግህን፡ ከመጠበቄ፡ የተነሣ፡ ቢጠ ብቁት ፡ እንዲያድን ፡ ባይጠብቁት ፡ እንዲያጠፋ ፡ ዐወቅሁ ።

በእንተ ፡ ዝ ፡ ኵሉ ፡ ፍኖተ ፡ ዐመፃ ፡ ጸላእኩ ።

ስለዚህ ፡ የዐመፅን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ጸላሁ ። እንድም ፡ ፍኖተ ፡ ዐማፅ ያን ፡ የባቢሎናውያንን ፤ እንድም ፡ የኤኮንያንን፡ የሲዴቅያስን ፡ ግብር ፡ ተውሁ ፤ ጸላሁ ።

ክፍል ፡ ፲፬ ፡ ኖን ፡ ብሂል ፡ ንጉሥ ፡ እግዚ አብሔር ።

ኖን ፡ ማለት ፡ ንጉሥ ፡ እግዚአብ ሔር፡ ማለት፡ ነው፤ ቢገናኝ ፡ መና ።

፻፭ ፡ ማኅቶት ፡ ለእገርየ ፡ ሕግከ ።

ለእገርየም ፡ ይላል ፤ ሕግህ ፡ ለሰው ነቴ ፡ ፋና ፡ ነው ።

ብርሃን ፡ ለፍናትየ ።

ኢታምልከም ፡ ለሥራዬ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ። ከፋና ፡ ብርሃን፡ የፀሐይ ፡ ብር ሃን ፡ እንዲበልጥ ፡ ከዘጠኙም፡ ኢታ ምልክ ፡ ትበልጣለችና ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፮ ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ።

፻፮ ፡ መሐልኩ ፡ ወአቀምኩ ፡ ከመ ፡ እዕ ቀብ ፡ ዘንተ ፡ ኵነኔ ፡ ጽድቅከ ።

እውነተኛውን ፡ ሕግህን ፡ እጠብቅ፡ ዘንድ ፡ ጨክኜ ፡ ማልሁ ።

፻፯ ፡ ወሐመምኩ ፡ ፈድፋደ ።

ፈጽሜ ፡ ባለመከራ ፡ ሁኛለሁና ።

እግዚኦ ፡ አሕይወኒ ፡ በከመ ፡ ነቢብከ ።

አቤቱ ፡ በሕግህ ፤ እንደም ፡ ወሰ ብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡ በተናገርከው ፡ አድነኝ ።

፻፰ ፡ ሥምር ፡ እግዚኦ ፡ ቃለ ፡ አፉየ ።

አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ወደህ ፡ ተቀ በል ።

ወምሀረኒ ፡ ኵነኔከ ።

ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፤ አስተምረኝ ።

፻፱ ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ እደዊከ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቴን ፡ ባንተ ፡ እጅ ፡ ሥልጣን ፡ አስጠብቃለሁ ።

ወኢረሳዕኩ ፡ ሕገከ ።

ሕግህንም ፡ አልዘነጋሁም ።

፻፲ ፡ ሠርው ፡ ሊተ ፡ ኃጥኣን ፡ መሥገርተ ።

ባቢሎናውያን ፡ ምክር ፡ መከሩብኝ፤ ጦር ፡ ሸመቁብኝ ።

ወኢስሕትኩ ፡ እምትእዛዝከ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ቢመክር ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ከሕግህ ፡ አልወጣሁም ።

፻፲፩ ፡ ወወረስክዎ ፡ ስምዐከ ፡ ለዓለም ።

እምልኮትህን ፡ ለዘላለም ፡ ገንዘብ ፡ አደረግሁ ፤ አደረግሁ ፡ እንጂ ፤ ኢረ ሳዕኩ ።

እስመ ፡ ሐሤቱ ፡ ለልብየ ፡ ውእቱ ።

እምልኮትህ ፡ ለልቡናዬ፡ ተስፋው ፡ ነውና ። ኤር ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ።

፻፲፪ ፡ ሜጥኩ፡ልብየ፡ከመ፡እግበር፡ትእዛዘከ ።

ሕግህን ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ልቡ ናዬን ፡ ወደ ፡ እምልኮትህ ፡ መለ ስሁ ።

ለዓለም ፡ ዘእንበለ ፡ ሒስ ።

እግበር ፡ ዘእንበለ ፡ ሒስ ፡ ሜጥኩ ፡ ዘእንበለ ፡ ሒስ ፡ በል ፡ ለዘላለሙ ፡ ያለነውር ፡ ያለነቀፋ ።



ክፍል ፡ ፲፭ ፡ ሳምኬት ፡ ብሂል ፡ ሰፋኒ ፡ እግዚ አብሔር ።

ሳምኬት ፡ ማለት ፡ ሰፋኒ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፻፲፫ ፡ ዐማፅያን ፡ ጸላእኩ ።

ባቢሎናውያንን ፤ እንደም ፡ ኤኮን ያንን ፡ ሴዴቅያስን ፡ ጸላሁ ።

ሕገከሰ ፡ አፍቀርኩ ።

ኪያከስ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አንተን ፡ ግን ወደድሁ ። እንደም ፡ የባቢሎናው ያንን ፤ እንደም ፡ የኤኮንያንን ፡ የ ሴዴቅያስን ፡ ሥራ ፡ ጸላሁ ፤ ሕግ ህን ፡ ግን ፡ ወደድሁ ።

፻፲፬ ፡ ረዳእየ ፡ ወምስካይየ ፡ አንተ ።

ረዳቴ ፡ አንባ ፡ መፀጊያዬ ፡ አንተ ፡ ነህና ።

ወበቃልከ ፡ ተወከልኩ ።

በሕግህ ፤ እንደም ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ባልከው ፡ አመንሁ ።

፻፲፭ ፡ ተገሐሡ ፡ እምኔየ ፡ ዐማፅያን ።

ሰሚ ፡ አድርገህ ፤ ባቢሎናውያን ፡ ከኔ ፡ ራቁልኝ ።

ወእኀሥሥ ፡ ትእዛዘ ፡ ለአምላኪየ ።

የፈጣሪዬን ፡ ሕጉን ፡ እንድጠብቅ ፡ ልሁን ፤ ልጠብቅ ። እንደም ፡ አር ቀህ ፤ ባቢሎናውያን ፡ ከኔ ፡ ይራቁል ኝ ፡ የፈጣሪዬን ፡ ሕጉን ፡ እጠብቅ፡ ዘንድ ።

፻፲፮ ፡ ተወከፈኒ ፡ በከመ ፡ ነቢብከ ፡ ወእሕየው ።

ሕግህን ፡ በመጠበቄ ፤ እንደም ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡ በተናገር ከው ፡ ረድኤት ፡ ተቀበለኝ ። ወእሕ የው ፡ ወእሕዮም ፡ ይላል ፤ እኔም ከመከራው ፡ ልዳን ።

ኢታስተኀፍረኒ ፡ እምተስፋየ ።

ካለኝታዬ ፡ ለይተህ ፡ አታሳፍረኝ ።

፻፲፯ ፡ ርድአኒ ፡ ወአድኅነኒ ።

ረድተህ ፡ አድነኝ ፤ እንደም ፡ ረድ ተህ፡አድነኝ ፡ እንጂ ፤ ኢታስተኀፍ ረኒ ።

ወአነብብ ፡ ዘንተ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሕግህን ፡ እነግራለሁ ፤ አስተምራለሁ ።

፻፲፰ ፡ አኅሠርኮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይርሕቁ ፡ እምትእዛዝከ ።

ከሕግህ ፡ የወጡ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ እንደም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኤኮንያንን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋኻቸው ።

እስመ ፡ ዐመፃ ፡ ፍትወቶሙ ።

ፈቃዳቸው ፡ ዐመፅ ፡ ነውና ። እን ድም ፡ ዐመፅ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ነውና ።

፻፲፱ ፡ ዐላውያን ፡ እሙንቱ ፡ ኵሎሙ ፡ ኃጥ ኣን ፡ ምድር ።

ባቢሎናውያን ፡ ሁሉ ፡ ዐላውያን ፡ ናቸው ።

በእንተ ፡ ዝ ፡ አፍቀርኩ ፡ ስምዐከ ።

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ማለት ፡ ዐላዊ ፡ እን

2014 04 18

ዳልሆን ፡ አምልኮትህን ፡ ሕግህን ፡ ወደድሁ ።

፻፲፱ ፡ አውድድ ፡ ውስተ ፡ ሥጋየ ፡ ፈሪሆተከ ።

ቅኑ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አምልኮትህን ፡ ሕግህን ፡ በሰውነቴ ፡ እስማማ ።

እስመ ፡ ፈራህኩ ፡ እምገሃነእከ ።

ከሕግህ ፡ የተነሣ ፡ ፈርቻለሁና ።

ክፍል ፡ ፲፮ ፤ ዔ ፡ ብሂል ፡ ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ።

ዔ ፡ ማለት ፡ ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቢገናኝ ፡ እ ፡ እብ ፡ ኰሉ ፡ ሰዓታት ፡ ጋዳ ፡ ለከ ።

፻፳፩ ፡ ገበርከ ፡ ፍትሐ ፡ ወጽድቀ ።

ፍትሕንና ፡ ጽድቅን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ አድርገህ ፡ ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡ ሚጠትን ፡ አደረግህለት ።

ኢትመጥወኒ ፡ ለእለ ፡ ይገፍዑኒ ።

ሥቃይ ፡ ለሚያጸኑብኝ ፡ ለባቢሎናውያን ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጠኝ ።

፻፳፪ ፡ ጽንሖ ፡ ለገብርከ ፡ ውስተ ፡ ሠናይ ።

ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡ በበጎ ፡ ወረታ ፡ በበጎ ፡ ረድኤት ፡ በበጎ ፡ ሚጠት ፡ ቈየው ።

ወኢይትዐገሉኒ ፡ ዕቡያን ።

ባቢሎናውያን ፡ እንዳይቀሙኝ ፡ ለጊዜውማ ፡ ቀምተውት ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ቀሙኝ ፡ እንዳይቀሩ ።

፻፳፫ ፡ ጸከማ ፡ አዕይንትየ ፡ ለአድኅኖትከ ።

ዐይኖቼ ፡ ትድግናህን ፡ በመጠበቅ ፡ ደከሙ ።

ወለቃለ ፡ ጽድቅከ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ኀሊቆን ፡ ያልከውንም ፡ በመሻት ።

፻፳፬ ፡ ግበር ፡ ለገብርከ ፡ በከመ ፡ ነቢብከ ።

ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ሚጠትን ፡ አድርግለት ።

ወምህረኒ ፡ ኰነኔከ ።

ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፤ አስተምረኝ ።

፻፳፭ ፡ ገብርከ ፡ ነ ፡ አለብወኒ ።

እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ነኝና ፡ ዕውቀትን ፡ ግለጽልኝ ።

ወአእምር ፡ ስምዐከ ።

አምልኮትህን ፡ ሕግህን ፡ ልወቅ ፡ ልጠብቅ ።

፻፳፮ ፡ ጊዜ ፡ ገቢር ፡ ለእግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ የሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ አለው ። አንድም ፡ ለገቢር ፡ ለእግዚአብሔር ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ ለገቢር ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ።

ወዐለዉ ። ሕገከ ።

ባቢሎናውያን ፡ ግን ፡ ሕግህን ፡ አፈረሱ ።

፻፳፯ ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ አፍቀርኩ ፡ ትእዛዘከ ።

እነሱ ፡ እንዳፈረሱ ፡ እኔም ፡ እንዳላፈርስ ፡ ሕግህን ፡ ወደድሁ ።



እምወርቅ ፡ ወሕምጳዝዮን ።

ከወርቅ ፡ ከዕንቍ ፡ ይልቅ ፡ ሕግህን ፡ ወደድሁ ። ኢዮ ፡ ፳፫ ፡ ፲፪ ።

፻፳፰ ፤ በእንተ ፡ ዝ ፡ እርታዕኩ ፡ ኀበ ፡ ኵሉ ፡ ትእዛዝከ ።

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ማለት ፤ ዐላዋቂ ፡ እንዳልባል ፡ እግረ ፡ ኀሊናዬን ፡ ወደ ፡ ሕግህ ፡ አቀናለሁ ።

ኵሉ ፡ ፍኖተ ፡ ዐመፃ ፡ ጸላእኩ ።

የዐመፅን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፤ አንድም ፡ ፍኖተ ፡ ዐማፅያን ፤ የባቢሎናውያንን ፤ አንድም ፡ የኤኮንያንን ፡ የሴዴቅያስን ፡ ግብር ፡ ጸላሁ ።

ክፍል ፡ ፲፯ ፤ ፌ ፤ ብሂል ፡ ፍቁር ፡ እግዚአብሔር ።

ፌ ፡ ማለት ፡ ፍቁር ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፻፳፱ ፤ መንክር ፡ ስምዕከ ።

አምልኮትህ ፡ ሕግህ ፡ ድንቅ ፡ ነው ።

በእንተ ፡ ዝ ፡ ኀሠሠቶ ፡ ነፍስየ ።

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሰውነቴ ፡ ናፈቀችው ፤ ወደደችው ።

፻፴ ፤ ነገረ ፡ ቃልከ ፡ ያበርህ ፡ ወያጠብብ ፡ ሕፃናተ ።

ለይኩን ፡ ብለህ ፡ የፈጠርኸው ፡ ፀሓይ ፡ ሕፃናት ፡ ሥጋን ፡ ፈጽሞ ፡ ያራቅቃል ። አንድም ፡ ተናግረህ ፡ የሠራኸው ፡ ሕግህ ፡ ሕፃናት ፡ ነፍስን ፡ ያራቅቃል ።

፻፴፩ ፤ አፉየ ፡ ከሠትኩ ፡ ወነፍስየ ፡ አናኅኩ ።

አፌን ፡ ከፈትሁ ፡ ልቡናዬንም ፡ አሰፋሁ ፤ የወደዱትን ፡ ምግብ ፡ አፍን ፡ ከፍተው ፡ ሆድን ፡ አስፍተው ፡ እንዲመገቡት ፡ ባፌም ፡ በልቤም ፡ ወድጄ ፡ ተቀበልሁ ።

እስመ ፡ ትእዛዘከ ፡ አፍቀርኩ ።

ሕግህን ፡ ሽቻለሁና ።

፻፴፪ ፤ ነጽር ፡ ላዕሌየ ፡ ወተሣሀለኒ ።

ኪያየ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እኔን ፡ በዐይነ ፡ ምሕረት ፡ እየኝ ፡ ተመልከተኝ ፤ እንዲህ ፡ አይተህ ፡ ተመልክተህ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

በከመ ፡ ፍትሖሙ ፡ ለእለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ስመከ ።

ስምህን ፡ ለሚወዱ ፡ ለነቢያት ፡ ለካህናት ፡ እንድትፈርድላቸው ፡ መጠን ።

፻፴፫ ፤ አርትዕ ፡ ፍኖትየ ፡ ወሐረትየ ፡ በከመ ፡ ነቢብከ ።

ሕግህን ፡ እንደ ፡ መጠበቄ ፤ አንድም ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ኀሊቆን ፡ ብለህ ፡ እንደ ፡ ተናገርህ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ መንገዴን ፡ አቅናልኝ ፡

ወኢይማእኒ ፡ ኵሉ ፡ ኀጢአት ።

ባቢሎናዊ ፤ አንድም ፡ በቁሙ ፡ ኀጢአት ፡ ድል ፡ እንዳይነሣኝ ።

ዘፍ ፡ ፬ ፡ ፯ ። ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ።

፻፴፬ ፤ አድኅነኒ ፡ እምትዕግልተ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

ከሰው ፡ ቅሚያ ፡ አድነኝ ። አን

2014 04 18

ድም ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ ሰው ፡ የሠ ራውን ፡ ጣዖት ፡ ከማምለክ ፡ አድ ነኝ ። ወይሰትዩ ፡ ወይነ ፡ ትዕግ ልት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አምላኮሙ ፡ እንዲል ፡

ወእዕቀብ ፡ ትእዛዘከ ።

ሕግህን ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ።

፻፴፭ ፡ እብርሀ ፡ ገጽከ ፡ ላዕለ ፡ ገብርከ ።

ለገብርከ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ለባሪያህ ፡ ለትሩፋ ፡ ብርሃን ፡ ረድኤትህን ፡ አብራለት ። እንድም ፡ አብርተህ ፡ ደስ ፡ አሰኘው ።

ወምሀረኒ ፡ ኵነኔከ ።

መሀረኒ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ሕግህንም ፡ ግለጽልኝ ፤ አስተምረኝ ።

፻፴፮ ፡ ሙሓዘ ፡ ማይ ፡ ወረደ ፡ እምአዕይንትየ ።

የእንባ ፡ ጐርፍ ፡ ካይኔ ፡ በዝቶ ፡ ፈ ሰሰ ፤ የብጽብጽ ፡ ነው ።

ወእመ ፡ አኮሰ ፡ እምእ.ዐቀብኩ ፡ ሕገከ ።

እምዐቀብኩ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የብጽ ብጽስ ፡ ባይሆን ፡ ሕግህን ፡ በጠበ ቅሁ ፡ ነበር ። እንድም ፡ (እምእ.ዐ ቀብኩ ፡ መከራስ ፡ ባታመጣብኝ ፡ ሕግህን ፡ ባልጠበቅሁም ፡ ነበር ፡ መከራ ፡ ብታመጣብኝ ፡ ጠበቅሁ ፡ እንጂ ። እንድም ፡ (ሙሓዘ ፡ ማይ) ፡ የእንባ ፡ ጐርፍ ፡ ካይኔ ፡ በዝቶ ፡ ፈ ሰሰ ፡ ማለት ፤ የንስሓ ፡ ነው ። (ወእ መ ፡ አኮሰ) ፡ የንስሓ ፡ ባይሆን ፡ ሕግ ህን ፡ ባልጠበቅሁም ፡ ነበር ፤ የን ስሓ ፡ ቢሆን ፡ ጠበቅሁት ፡ እንጂ ። እንድም ፡ መከራ ፡ እየተቀበልሁ ፡ እኔን ፡ አለማዳንህ ፡ ሕግህን ፡ ባል ጠብቅ ፡ ነዋ ፡ እንዲህ ፡ ማለት ፤ ንስሓዬ ፡ እውነተኛ ፡ ባይሆን ፡ ነዋ ።

ክፍል ፡ ፲፰ ፤ ጻዴ ፡ ብሂል ፡ ጽድቅ ፡ እግዚአ ብሔር ።

ጻዴ ፡ ማለት ፡ ጻድቅ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቢገናኝ ፡ ፋጻ። ከመ ፡ ፋጻ ፡ ቀጢን ፡ ወከመ ፡ መሰ ንቆ ፡ ሐዋዝ ፡ ያስተፌሥሐኒ ፡ በሰ ሚዖቱ ፡ እንዲል ።

፻፴፯ ፡ ጻድቅ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ወርቱዕ ፡ ኵሉ ፡ ፍናዊከ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ የባሕርይ ፡ አም ላክ ፡ ነህ ፤ ሕግህም ፡ የቀና ፡ ነው ።

፻፴፰ ፡ ወአዘዝከ ፡ ስምዐከ ፡ በጽድቅ ።

አምልኮትህን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ፡ ብለህ ፡ አዘዝህ ።

ወርቱዕ ፡ ፈድፋደ ።

ይኸውም ፡ ፈጽሞ ፡ የቀና ፡ ነው ።

፻፴፱ ፡ መሰወኒ ፡ ቅንአተ ፡ ቤትከ ።

ለቤተ ፡ መቅደስህ ፡ እንድም ፡ ለሕ ግህ ፡ የቀናሁት ፡ መቅናት ፡ እንደ ሳት ፡ አቃጥሎኛልና ።

እስመ ፡ ረስዑ ፡ ትእዛዘከ ፡ ጸላእትየ ።

ባቢሎናውያን ፡ ሕግህን ፡ ስለ ፡ ዘ ነጉ ፡ ኢሳ ፡ ፷፰ ፡ ፯ ።



፻፵ ፡ ርሱን ፡ ቃልከ ፡ ፈድፋደ ።

ሕግህ ፡ ፈጽሞ ፡ የጋለ ፡ የፈላ ፡ ነው ።

ወገብርከሰ ፡ አፍቀሮ ።

ሕግህ ፡ እንዲህ ፡ የጋለ ፡ የፈላ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ባሪያህም ፡ እጠብቀዋ ለሁ ።

፻፵፩ ፡ ወሬዛ ፡ አነ ፡ ወትሑት ።

እኔ ፡ ትሑት ፡ ወሬዛ ፡ ነኝ ፤ የጐል ማሳ ፡ ልቡ ፡ ከደረቱ ፡ እንዳለው ፡ ያለሁ ፡ አይደለሁም ።

ሕገከሰ ፡ ኢረሳዕኩ ።

ሕግህን ፡ አልዘነጋሁም ።

፻፵፪ ፡ ጽድቅከሰ ፡ ጽድቅ ፡ ዘለዓለም ።

ሕግህ ፡ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ እውነተኛ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

ወቃልከኒ ፡ እሙን ፡ ውእቱ ።

ኢታምልክም ፤ እንድም ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ያልከው ፡ ቃልህ ፡ የታመነ ፡ ነው ።

፻፵፫ ፡ ሕምም ፡ ወምንዳቤ ፡ ረከቡኒ ።

መከራ ፡ ጸዋትወ ፡ መከራ ፡ አገኘኝ።

ወትእዛዝከሰ ፡ ተምሃርየ ፡ ውእቱ ።

ሕግህ ፡ ግን ፡ መምሬ ፡ ትምርቴ ፡ ነው ።

፻፵፬ ፡ ጽድቅ ፡ ውእቱ ፡ ስምዕከ ፡ ለዓለም ።

አምልኮትህ ፡ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፤ እውነተኛ ፡ ነው ።

አለብወኒ ፡ ወአሕይወኒ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ሕግህን ፡ ግለጽ ልኝ ፤ ከመከራ ፡ አድነኝ ።

ክፍል ፡ ፲፱ ፤ ቆፍ ፡ ብሂል ፡ ቅሩብ ፡ እግዚአ ብሔር ።

ቆፍ ፡ ማለት ፡ ቅሩብ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፻፵፭ ፡ ጸራሕኩ ፡ በኵሉ ፡ ልብየ ፡ ስምዐኒ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ ለም ኜለሁና ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወኀሠሥኩ ፡ ኵነኔከ ።

ሕግህን ፡ ሻሁ ።

፻፵፮ ፡ ጸራሕኩ ፡ ኀቤከ ፡ ስምዐኒ ፡ ወአድ ኅነኒ ።

ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለምኜለሁና ፡ ልመናዬን ፡ ሰምተህ ፡ አድነኝ ።

ወእዕቀብ ፡ ስምዐከ ።

አምልኮትህን ፡ ልጠብቅ ።

፻፵፯ ፡ በጽሕኩ ፡ ማእከለ ፡ አድባር ፡ ወከ ላሕኩ ።

በተራሮቹ ፡ መኻል ፡ ደርሼ ፡ ጮ ህኩ ፡ ማለት ፤ ምነው ፡ ጊዜው ፡ ደርሷል ፡ አታወጡኝምን ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ ነቢያት ፡ ወደ ፡ ካህናት ፡ መ ልሼ ፡ ለመንሁ ።

እስመ ፡ ቃለከ ፡ ተሰፈውኩ ።

ሕግህን ፡ ተስፋ ፡ አድርጌአለሁና ።

2014 04 18

፻፵፰ ፤ በጽሒ ፡ አዕይንትየ ፡ ለገይስ ።

ዐይኖቼ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመ ገሥገሥ ፡ ደረሱ ፤ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ሁኖ ፡ ታይቶት ፡ እንዲህ ፡ አለ ። አንድም ፡ በተስፋ ው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንዳለ ፡ ሁኖ ፡ በጽሒ ፡ አለ ።

ከመ ፡ እንብብ ፡ ቃለከ ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼ ፡ ሕግህን ፡ እን ግር ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ።

፻፵፱ ፤ ስማዕ ፡ እግዚኦ ፡ ቃልየ ፡ በከመ ፡ ሣህልከ ።

አቤቱ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወአሕይወኒ ፡ በከመ ፡ ፍትሕከ ።

ፈርደህ ፡ አድነኝ ። አንድም ፡ ፍር ድህን ፡ እንደ ፡ መጠበቄ ፡ አድነኝ ።

፻፶ ፤ ቀርቡ ፡ እለ ፡ ሮዱኒ ፡ በዐመፃ ።

በግፍ ፡ የሚጠሉኝ ፡ የከበቡኝ ፡ ጠላ ቶቼ ፡ ባቢሎናውያን ፡ እኔን ፡ ለማ ጥፋት ፡ ወደኔ ፡ ቀረቡ ።

ወእምሕግከ ፡ ርሕቁ ።

ቀርቡም ፡ ማለቱ ፡ እኔን ፡ ለማጥ ፋት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሕግህ ፡ ግን ፡ ራቁ ። አንድም ፡ ኢርሕቁ ፡ እንዚያ ፡ ቢርቁ ፡ እኔ ፡ አልራቅሁም ።

፻፶፩ ፤ ቅሩብ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ቅሩብ ፡ ነህ ።

ወርቱዕ ፡ ኵሉ ፡ ፍናዊከ ።

ሕግህ ፡ ሁሉ ፡ የቀና ፡ ነው ።

፻፶፪ ፤ እምትካት ፡ አእመርኩ ፡ ስምዐከ ።

ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ እምልኮትህን ፡ ዐወቅሁ ።

ከመ ፡ ለዓለም ፡ ሣረርኮ ።

ለዘላለም ፡ አጽንተህ ፡ እንደ ፡ ሠራ ኻቸው ።

ክፍል ፡ ፳ ፤ ሬስ ፡ ብሂል ፡ ርእስ ፡ እግዚአ ብሔር ።

ሬስ ፡ ማለት ፡ ርእስ ፡ እግዚአብ ብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቢገናኝ ፡ ኋራ ፡ ፀሐይ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አብ ፡ ኋራ ፡ ወልድ ፡ ኋራ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኋራ ፡ እንዲል ፡ እገው ፤ አብ ፡ ፀሐይ ፡ ወልድ ፡ ፀሐይ ፡ መ ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፀሐይ ፡ ሲል ።

፻፶፫ ፤ ርኢ ፡ ሕማምየ ፡ ወአድኅንኒ ።

መከራዬን ፡ እይተህ ፡ አድነኝ ።

እስመ ፡ ኢረሳዕኩ ፡ ሕገከ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ያልከውን ፤ አንድ ም ፡ ሕግህን ፡ አልዘነጋሁምና ።

፻፶፬ ፤ ፍታሕ ፡ ፍትሕየ ፡ ወባልሐኒ ።

ፈርደህ ፡ ከመከራ ፡ አድነኝ ።

ወበእንተ ፡ ቃልከ ፡ አሕይወኒ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡ ስለ ፡ ተናገ ርህ ፤ አንድም ፡ ሕግህን ፡ ስለ ፡ ጠበ ቅሁ ፡ አድነኝ ።



፻፶፭ ፤ ርሑቅ ፡ ሕይወትየ ፡ እምኃጥአን ።

አናዋሬ ፡ ከባቢሎናውያን ፡ የራቀ ፡ ነው ። አንድም ፡ ርሑቅ ፡ ሕይወት ፡ እምኃጥአን ፡ ይላል ፤ እግዚአብ ሔር ፡ ከባቢሎናውያን ፡ የራቀ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ አድሮባቸው ፡ አይ ኖርም ።

እስመ ፡ ኢኀሠሡ ፡ ኵነኔከ ።

ሕግህን ፡ አልሹምና ።

፻፶፮ ፤ ብዙኅ ፡ ሣህልከ ፡ እግዚኦ ፡ ፈድፋደ ።

አቤቱ ፡ ይቅርታህ ፡ ፈጽሞ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

ወአሕይወኒ ፡ በከመ ፡ ፍትሕከ ።

ፈርደህ ፤ አንድም ፡ ሕግህን ፡ እንደ ፡ መጠበቄ ፡ አድነኝ ።

፻፶፯ ፤ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ሮዱኒ ፡ ወአመንደቡኒ ።

የከበቡኝ ፡ መከራ ፡ ያጸኑብኝ ፡ ጠላ ቶቼ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

ወኢተግሕሥኩ ፡ እምስምዕከ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ቢበዛ ፡ ምን ፡ ያደ ርገኛል ፡ ብዬ ፡ ከሕግህ ፡ አልራቅ ሁም ።

፻፶፰ ፤ ርኢኩ ፡ አብዳነ ፡ ወተከዝኩ ።

ባቢሎናውያን ፡ ሕግህን ፡ ሲያፈ ርሱ ፡ አይቼ ፡ አዘንሁ ፡ እንጂ ፤ ኢተግሕሥኩ ።

እስመ ፡ ኢዐቀቡ ፡ ቃለከ ።

ሕግህን ፡ አልጠበቁምና ። ሕዝ ፡ ፱ ፡ ፬ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፰ ።

፻፶፱ ፤ ርኢ ፡ ከመ ፡ አፍቀርኩ ፡ ትእዛዘከ ።

ሕግህን ፡ እንደ ፡ ጠበቅሁ ፡ ዕወቅ ።

እግዚኦ ፡ አሕይወኒ ፡ በሣህልከ ።

አቤቱ ፡ እንደ ፡ ይቅርታህ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ አድ ነኝ ።

፻፷ ፤ ቀዳሚ ፡ ቃልከ ፡ ጽድቅ ፡ ውእቱ ።

የዘጠኙን ፡ አቢጋዝ ፡ ኢታምልክ ፡ ናት ።

ወለዓለም ፡ ኵሉ ፡ ኵነኔከ ፡ ጽድቅ ።

እውነተኛ ፡ የሚሆኑ ፡ ዘጠኙ ፡ ሕገ ጋትም ፡ ለዘላለም ፡ ጸንተው ፡ ይኖ ራሉ ። አንድም ፡ ለዘላለም ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ዘጠኙ ፡ ሕገጋት ፡ ናቸው ።

ክፍል ፡ ፳፩ ፤ ሳን ፡ ብሂል ፡ ሰፋኒ ፡ እግዚ አብሔር ።

ሳን ፡ ማለት ፡ ሰፋኒ ፡ እግዚአብሔ ር ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህን ፡ ስቡሕ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ያን ፡ ሰፋኒ ፡ ይህ ን ፡ ሰፋኒ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ያን ፡ ስቡሕ ።

፻፷፩ ፤ መላእክት ፡ ሰደዱኒ ፡ በከንቱ ።

መላእክት ፡ ከሀገሬ ፡ አስወጥተው ፡ ሰደዱኝ ፡ ማለት ፤ ባኡ ፡ ከለዳው ያን ፡ ወዄውውዎሙ ፡ ለዕብራው ያን ፡ ብለው ፡ በር ፡ ከፍተው ፡ ቴዎ ቴዎቸውን ፡ አብርተው ፡ አስማረ ኩኝ ። አንድም ፡ ኀጢአት ፡ ሳል ሠራ ፡ ጣዖት ፡ ሳላመልክ ፡ ኢኮን



2014 04 18

ፆን ፡ ሊፈትንበ ፡ ኀጢአት ፡ ሞር ተው ፡ ጣዖት ፡ አምልኮው ፡ እስ ማርኩኝ ። እንድም ፡ እል ፡ ናቡከደ ነጸር ፡ በማፍዕ ፡ ማረኩኝ ።

[illegible]

ወነቢያት ፡ በካህናት ፡ እድረሀ ፡ ፪፻፪ ፡ ይደረጋል ፡ ከማለትህ ፡ የተ ነግ ፡ ልቡናዬ ፡ ደነገፀብኝ ። እን ድም ፡ በእሕዛብ ፡ እድረሀ ፡ ተማ ረክ ፡ ተማረክ ፡ ከማለትህ ፡ የተ ነግ ፡ ልቡናዬ ፡ ተሸበረብኝ ።

፻፷፪ ፡ [illegible]

ኋላ ፡ ግን ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡ በተናገርከው ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

[illegible]

ብዙ ፡ ምርኮ ፡ እንዳገኘ ፡ ሰው ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

፻፷፫ ፡ [illegible]

የዐመፃን ፡ ሥራ ፡ ማለት ፡ ጣዖትን፡ ኀጢአትን ፡ ጸላው ፡ ተጸየፍሁ ።

[illegible]

ሕግህን ፡ ግን ፡ ወደድሁ ።

፻፷፬ ፡ [illegible]

ለኔ ፡ ብለህ ፡ በፈጠርህልኝ ፡ ቀን ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ አመሰግንሃለሁ ። እን ድም ፡ ስብዓ ፡ ያሏል ፡ ሳታንሣ ፡ ለኔ ፡ ብለህ ፡ በፈጠርህልኝ ፡ ቀን ፡ ሰባት ፡ ጊዜያን ፡ አመሰግንሃለሁ ።

[illegible]

እውነተኛው ፡ ሕግህ ፡ ተገዘ፡ ብሎ፡ ስላ[illegible] ።

፻፷፭ ፡ [illegible]

ስምህን ፡ መጽራት ፡ ለሚወዱ ፡ ለነቢያት ፡ ለካህናት ፡ እንድም ፡ ለሁሉ ፡ ብዙ ፡ እንድነት ፡ ፍቅር ፡ አላቸው ። እንድም ፡ ይደረግላቸ ዋል ፡ ይደረግላቸው ።

[illegible]

መከራ ፡ ዕቅፍት ፡ ሥጋ ፡ ዕቅፍት ፡ ነፍስ፡ የለባቸውም፡ አይኑርባቸው ።

፻፷፮ ፡ [illegible]

አቤቱ ፡ ትድግናህን ፡ ተስፋ ፡ አደ ረግሁ ።

[illegible]

ሕግህንም ፡ ጠበቅሁ ።

፻፷፯ ፡ [illegible]

ሰውነቴ ፡ እንድም ፡ ልቡናዬ ፡ እ ምልኮትህን ፡ ጠበቀች ።

[illegible]

ፈጽማ ፡ ወደደችው ።

፻፷፰ ፡ [illegible]

ዘጠኙን ፡ ቃላት ፡ ኢታምልክንም ፡ ጠበቅሁ ።

[illegible]

ሥራዬም ፡ ሁሉ ፡ ከፊትህ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ወነበቦ ፡ ወነበቦ ፡ ያለው ም ፡ ሕግህ ፡ ሁሉ ፡ በፊቴ ፡ ነው ፤ እጠብቀዋለሁ ።

ክፍል ፡ ፳፪ ፡ ታው ፡ [illegible]

ታው ፡ ማለት ፡ ትጉህ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቢገናኝ ፡ ሰታ ው ፡ እግዚእ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ሴቴ ፡ ማረማ ፡ እንዲል ፡ ዐረብ ፡ እግዝእ ት ፡ ሲል ።

፻፷፱ ፡ [illegible]

አቤቱ ፡ ልመናዬ ፡ ከፊትህ ፡ ትድ ረስ ።

[illegible]

ወሰብዓ ፡ ዓም፡ ብለህ፡ እንደ፡ ተናገ ርህ ፤ እንድም ፡ ሕግህን ፡ እንደ ፡ መጠበቄ ፡ ዕውቀት ፡ ግለጽልኝ ።

፻፸ ፡ [illegible]

አቤቱ ፡ ልመናዬ ፡ ከፊትህ ፡ ትድ ረስ ።

[illegible]

ወሰብዓ፡ ዓም፡ ብለህ፡ እንደ ፡ ተናገ ርህ ፤ እንድም ፡ ሕግህን ፡ እንደ ፡ መጠበቄ ፡ እድነኝ ።

፻፸፩ ፡ [illegible]

እንደበቴ ፡ ሕግህን ፤ እንድም ፡ ጌት ነትህን ፡ ተናገረ ።

[illegible]

ሕግህን ፡ ገልጸህልኛል ፡ እስተም ረኸኛልና ።



፻፸፪ ፡ [illegible]

እንደበቴ ፡ ሕግህን ፡ ተናገረ ።

[illegible]

ሕግህ ፡ ሁሉ ፡ እውነተኛ ፡ ነውና ።

፻፸፫ ፡ [illegible]

ሥልጣንህ ፡ ያድነኝ ፡ ዘንድ ፡ የሚ ያድነኝ ፡ ይሁን ።

[illegible]

ሕግህን ፡ ወድጄለሁና ።

፻፸፬ ፡ [illegible]

አቤቱ ፡ ትድግናህን ፡ ወደድሁ ።

[illegible]

ሕግህም፡ መምሪ ፡ ትምርቴ ፡ ነው ።

፻፸፭ ፡ [illegible]

ሰውነቴ ፡ ከመከራ ፡ ትዳንልኝ ፤ እ ኔም ፡ ከመከራ ፡ ያዳነኝ ፡ ብዬ ፡ እመሰግንሃለሁ ።

[illegible]

ሕግህም ፡ በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ ይር ዳኝ ።

፻፸፮ ፡ [illegible]

እንደ ፡ ጠፋ ፡ በግ ፡ ተዘንጋሁ ፤ የ ሰው ፡ ልጅ ፡ ከተመረረ ፡ በግ ፡ ከ በረረ ፡ እንዲሉ ። እንድም ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ በግ ፡ ኮንሁ ፡ ማለት ፤ ከማ ኀበረ ፡ መላእክት ፡ ተለየሁ ።

2014 04 18

ጐሥዐ ፡ ለንብብከ ፡ እስመ ፡ ትእዛዘከ ፡ ኢረሳ ዕኩ ።

ሕግህን ፡ አልዘነጋሁምና ፡ እኔን ፡ ባሪያህን ፡ ፈልገኝ ፡ ማለት ፤ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አውጣኝ ። እንድም ፡ ቃልህን ፡ አልዘነጋሁምና ፡ ከሲኦል ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አውጣኝ ፡ ይላል ፡ አዳም ።

## መዝሙር ፡ ፻፲፱ ።

፩ ፤ ጎበከ ፡ እግዚኦ ፡ ጸራሕኩ ፡ ሶበ ፡ ተመንደብኩ ፡ ወሰማዕከኒ ።

በሳኦል ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግሮታል ፤ እግዚኦ ፡ ጎቤከ ፡ ጸራሕኩ ፡ ሲል ፡ ነው ። አቤቱ ፡ ከዚህ፡ አስቀድሞ ፡ በጎልያድ ፡ ጊዜ ፡ ልመናዬን ፡ ሰምተኸኛልና ፡ አሁንም ፡ መከራ ፡ ባገኘኝ ፡ ጊዜ ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለመንሁ ።

፪ ፤ እግዚኦ ፡ አድኅና ፡ ለነፍስየ ፡ እምከናፍረ ፡ ዐመፃ ።

አቤቱ ፡ በከዳተኛ ፡ እንደበት ፡ ከሚናገሩ ፡ ከሰራዊቱ ፡ አድነኝ ።

ወእምልሳን ፡ ጽልሑት ።

በአንደበቱ ፡ ክዳትን ፡ ተንኰልን ፡ ከሚናገር ፡ ከሳኦልም ፡ አድነን ።

፫ ፤ ምንተ ፡ ይሁቡከ ፡ ወምንተ ፡ ይዌስኩከ ፡ በእንተ ፡ ከናፍረ ፡ ጕሕሉት ።

ሳኦል ፡ በከዳተኛ ፡ አንደበት ፡ ስለ ፡ ተናገርህ ፡ ፍትሑ ፡ ርትዑ ፡ ምላሴ ፡ ምን ፡ ይሰጡሃል ፤ መንግሥቱን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሰጥተውሃል ።

፬ ፤ አሕጻሁ ፡ ለኀያል ፡ ስሑል ፡

አሕጻ ፡ ካለ ፡ ስሑላን፤ ስሑል፡ ካለ ፡ ሐጽ ፡ ቢል ፡ ይቀናል፤ ልማደ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። የኀያል ፡ ወልድ ፡ አሕጻ ፡ መዓቱ ፡ የጋሉ ፡ የተቡ ፡ ናቸው ።

ከመ ፡ አፍሓመ ፡ ሐቅል ።

እንደ ፡ በረሓ ፡ ቋያ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የቀረኝ ፡ በዚህ ፡ ይጥፋበት ።

፭ ፤ ሰይ ፡ ልየ ፡ ዘርሕቀ ፡ ማኅደርየ ።

ማደሪያዬ ፡ ስራቀ ፡ ለኔ ፡ ወዮልኝ ። እንድም ፡ ለዘርሕቁ ፡ እማኅደርየ ፡ ይላል ፤ ከማደሪያዬ ፡ ለራቅሁ ፡ ለኔ ፡ ወዮልኝ ፡ ወዮታ ፡ አለብኝ ፤ ወዮ ፡ ሊሉልኝ ፡ ይገባል ።

ወኀደርኩ ፡ ውስተ ፡ አዕጻዳተ ፡ እለ ፡ ቄዳር ።

በዘላን ፡ ቤት ፡ ላደርሁ ፤ እንድም ፡ ውስተ ፡ አዕጻዳት ፡ ይላል ፤ እንደ ፡ ዘላን ፡ ለሆንሁ ፡ ለኔ ፡ ወዮልኝ ። ዘላን ፡ ነቀል ፡ ተከል ፡ ነው ፤ ካደረበት ፡ አይውልም ፡ ከዋለበት ፡



አያድርም ፤ እሱም ፡ እንደዚያ ፡ ሁኗልና ። እንድም ፡ እንደ ፡ ወታደር ፡ ቤቱን ፡ አፍርሶ ፡ ሲሠራ ፡ ሠርቶ ፡ ሲያፈርስ ፡ ይኖራል ። እንድም ፡ ሠርቶ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አድሮ፡ ጥሎት ፡ ይሄዳል ፤ እሱም ፡ ሲሸሽ ፡ ውሎ ፡ ማታ ፡ ያድርበታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

፮ ፤ ብዙኀ ፡ ተዐገሠት ፡ ነፍስየ ፡ ።

ሰውነቴ ፡ ብዙውን ፡ መከራ ፡ ታግሣ ፡ ተቀበለች ።

ምስለ ፡ እለ ፡ ይጸልኡ ፡ ሰላመ ።

አንድነትን ፡ ፍቅርን ፡ ከሚጸሉ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡

፯ ፤ እንዘ ፡ ሰላማዊ ፡ አነ ።

እኔ ፡ አንድነትን ፡ ፍቅርን ፡ የያዝሁ ፡ ስሆን ፡ አንድነትን ፡ ፍቅርን፡ የሚጠሉትን ፡ ሰዎች ፡ ጸላሁ ።

ሶበ ፡ እትናገሮሙ ፡ ማንሻ ። እንድም ፡ እኔ ፡ አንድነትን ፡ ፍቅርን ፡ የያዝሁ ፡ ስሆን ፡ አንድነትን ፡ ፍቅርን ፡ ከሚጸሉ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ እንደሚጠሉ ፡ ሰዎች ።

ሶበ ፡ እትናገሮሙ ፡ ይጸብኡኒ ፡ በከንቱ ።

በተናገርኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ሳልጸላቸው፡ በግፍዕ ፡ ይጸሉኛልና ። ናባል ፡ የሚባል ፡ ባለጸጋ ፡ ነበረ ፤ ብዙ ፡ የከብት ፡ የፍየል ፡ የበግ ፡ መንጋ ፡ ነበረው ፤ ከብቶቹ ፡ በደጋ ፡ እሱ፡ በቈላ፡ ይኖራሉ ፤ ዳዊት ፡ በሽፍትነት ፡ ሳለ ፡ በቈላ ፡ ያሉ ፡ ከብቶቹን ፡ ሌሊት ፡ እንደ ፡ ግድግዳ ፡ እንደ ፡ ተራዳ ፡ ሁኖ ፡ ይጠብቅለታል ፤ እንዲት ፡ ጠቦት ፡ እንኳ ፡ ሳይነካ ፡ ነው ። በሀገራቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ሲላጩ ፡ በግ ፡ ሲያሸልቱ ፡ ብዙ ፡ ድግስ ፡ ተደግሶ ፡ ነው ፤ በዚያ ፡ ልማድ ፡ ብዙ ፡ ድግስ ፡ አስደግሶ ፡ በግ ፡ በሚያሸልትበት ፡ ቀን ፡ ይህን ፡ ያየ ፡ የዳዊት ፡ ብላቴና ፡ ሄዶ ፡ ነገረው ፤ አይሆንም ፡ ያለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እጣላውና ፡ ይጣላኛል ፡ አለው ፤ መቼስ ፡ ላንተ ፡ ብሎ ፡ አልደገሰው ፡ ለፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡ አለው ፤ እንኪያስ ፡ አንተ ፡ ሚስትህ ፡ ልጆችህ ፡ ቤተ ፡ ሰብህ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ናችሁ ፡ አለህ ፡ ብላችሁ ፡ ንገሩት ፡ አላቸው ፤ ሰው ፡ እንደ ፡ ነገሩት ፡ በቅሎ ፡ እንዲህማ ፡ ሩት ፡ ነውና ፡ ሄዶ ፡ ላሸከሮቹ ፡ ምሳ ፡ ላክልኝ ፡ ብሎሃል ፡ ብሎ ፡ አሽከር ፡ ነገረው ፤ ማነው ፡ አለው ፤ ዳዊት ፡ ነው ፡ አለው ፤ ዳዊት፡ ዳዊት ፡ የማነው ፡ ዳዊት ፡ አለው ፤ የእሴይ ፡ ልጅ ፡ አለው ፤ እሴይ ፡ እሴይ ፤ አብዳንኑ ፡ እሱ ፡ እግብርት ፡ ዘተኀጥኡ ፡ እምገጸ ፡ እግዚእሙ ፤ ዛሬስ ፡ እኒህ ፡ ከጌታቸው ፡ ባለሚልንት ፡ ወጥተው ፡ የሸፈቱ ፡ ባሮች ፡ አእምሯቸውን ፡ አጥተው፡ ገና ፡ እንግሣለሁ ፡ እያለ ፡ ያወራ

2014 04 18

ልና ፡ በመሬ ፡ መንግሥት ፡ ልጊብርለት ፡ ነውን ፡ የንገሥ ፡ ጊዜ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ላሽከሮቹ ፡ ምሳ ፡ የደገስሁትን ፡ ለሱ ፡ አሽከሮች ፡ ልልክ፡ ነውን፡ አይሆንም ፡ አለው ፡ አፈሴ ፡ ብላቴና ፡ እንኳንስ ፡ የነ ገሩትን ፡ ያልነገሩትን ፡ ጨምሮ ፡ መናገር ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ ማሩን ፡ አምርሮ ፡ ወተቱን ፡ አጥቍሮ ፡ ይና ገራል ። ሄዶ ፡ ነገረው ፡ እኔማ ፡ እል ነገርኋችሁምን ፡ ቅንቱ ፡ አስይፍ ቲከሙ ፡ ስይፋችሁን ፡ ታጠቁ ፡ ኢያተርፍ ፡ ሰብእ ፡ ዛሬ ፡ ከናባል ፡ ቤት ፡ ስንኳን ፡ ሰው ፡ ውሻ ፡ ድ መት ፡ አይተርፈኝም ፡ ተነሡ ፡ እንሂድ ፡ ብሎ ፡ መንገድ ፡ ጀመረ ። ይህን ፡ የሰማ ፡ የናባል ፡ ብላቴና ፡ ላም ፡ ራሱም ፡ ይለዋል ፡ ሂዶ ፡ አቢግያን ፡ ባልሽን ፡ የምታድኚ በት ፡ ግብር ፡ ፈልጊ ፡ ዳዊት ፡ ላሽ ከሮቹ ፡ ምሳ ፡ ላክልኝ ፡ ብሎ ፡ ቢል ክበት ፡ ክፉ ፡ ቃል ፡ ሲመልስለት ፡ ሰምቻለሁ ፡ ዳዊት ፡ ተኳር ፡ ነው ፡ ሊጣላው ፡ ይመጣል ፡ ሲሆን ፡ መስ ጠት ፡ ባይሆንም ፡ ደግ ፡ ቃል ፡ መ መለስ፡ ይገባ ፡ ነበረ፡ ይህን ፡ ያኸል ዘመን ፡ ከብታችንን ፡ እየጠበቀ ፡ አላት። ኀምስተ ፡ አባግዐ፡ ግቡራተ ፡ ይላል ፡ አምስት ፡ በግ ፡ አሳርዳ ፡ አሥርታ ፡ አምስቱን ፡ አስነድታ ፡ የበለስ ፡ ቋንጣ ፡ አምስት ፡ የወይን ፡ ፈቀን ፡ አሲዛ ፡ እምስት ፡ መቶ ፡ እንጀራ ፡ ያ፲፮ ፡ አህያ ፡ ጭነት ፡ ዶቄት ፡ አሲዛ ፡ ሄደች ። እሱ ፡ ሚዳውን ፡ ጨርሶ ፡ ዐቀበቱን ፡ ሲይዝ ፡ እሷ ም ፡ ቍልቍለቱን ፡ ጨርሳ ፡ ሚዳ ውን ፡ ስትይዝ ፡ ተገናኙ ። መጻሕ ኪኑ ፡ ከመ ፡ ታድኅኒዮ ፡ ለገዛኩ ፡ ናባል ፡ ጊጉይ ፡ አላት ። ጌታዬ ፡ ይህ ንግ ፡ ማን ፡ ይከለክልሃል ፡ ይል ቅስ ፡ ስንኳን ፡ ላንተ ፡ ምሳ ፡ ላሽ ከሮችህ ፡ ምሳ ፡ የማይበቃ ፡ ምሳ ፡ ይገር ፡ መጥቻለሁና ፡ ተቀበለኝ ፡ አለችው ። በዚያውስ ፡ ላይ ፡ በነገ ዘቡ ፡ ብትጣላው ፡ እግዚአብሔር ፡ አይፈርድብህምና ፡ አለችው። አድ ለውኩ ፡ ለገጽኪ ፡ ስላንች ፡ ምሬ ዋለሁ ፡ ብሎ ፡ በፍቅር ፡ ተገናኝ ተው ፡ ተጫዋውተው ፡ ተለያዩ ተዋል ። ናባል ፡ ማታ ፡ ፀልቶ ፡ ጠጥቶ ፡ ሰክሮ ፡ አየችው ፡ አሁን ፡ ብነግረው ፡ አያውቀውም ፡ ብላ ፡ አንተ ፡ ትላንት ፡ እንጂ ፡ ዳዊት ፡ ሊገድልኽ ፡ መጥቶ ፡ ነበረ ፡ አለች ው። ዳዊት ፡ ብሎ ፡ ደንግጦ ፡ እንደ፡ ደነገጠ ፡ ሰንብቶ ፡ ባሥረኛው ፡ ቀን ፡ መልአኩ ፡ ቀሠፈው ፡ ስለ ምን ፡ ቢሉ ፡ ደግን ፡ ሰው ፡ ማዋ ረድ ፡ አይገባም ፡ ብሎ ። እንድም ፡ ጌታ ፡ እመቤታችን ፡ በአብራኩ ፡ ያሉ ፡ ናቸውና ። ፩ ፡ ነገ ፡ ፳፭ ።



## መዝሙር ፡ ፻፳ ።

፩፤ እንሣእኩ ፡ አዕይንትየ ፡ መንገለ ፡ አድባር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ ዐይኖ ቼን ፡ በተስፋው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳ ሳሌም ፡ አቀናሁ ። አንድም ፡ ም ነው ፡ ጊዜው ፡ ደርሷል ፡ አታወጡ ኝምን ፡ እያልሁ ፡ ወደ ፡ ነቢያት ፡ ወደ ፡ ካህናት ፡ ዐይኔን ፡ አቀናሁ ።

እምአይቴ ፡ ይምጽእ ፡ ረድኤትየ ።

ረዳቴ ፡ ከየትም ፡ ከየት ፡ ይደረግ ልኝ ፡ ይታዘዝልኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብዬ ።

፪፤ ረድኤትየሰ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

እንዲህስ ፡ እንዳልል ፡ የኔ ፡ ረድ ኤት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይደረግልኛል ፡ ይታዘዝልኛል ።

ዘገብረ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ።

ሰማይን ፡ ምድርን ፡ ከፈጠረ ።

፫፤ ወኢይሁቦን ፡ ሁከተ ፡ ለእገሪከ ።

ትሩፍ ፡ እንዲህ ፡ እልህ ፡ አበጀህ ፤ በወገኖችህ፤ አንድም ፡ በሕዋሳትህ ፡ መከራ ፡ አያመጣባቸውም ።

ወኢይዴቅስ ፡ ዘየዐቅበከ ።

የሚጠብቅህ፡ እግዚአብሔር ፡ እያን ቀላፋም ፤ እግዚአብሔርማ ፡ ሲተኛ፡ ሲነሣ ፡ ይኖራልን ፡ መራዳቱን ፡ በመነሣት ፡ አለመራዳቱን ፡ በመ ኛት ፡ መስሎ ፡ ተናገረ ።

፬፤ ናሁ ፡ ኢይዴቅስ ፡ ወኢይነውም ፡ ዘየዐቅቦ ፡ ለእስራኤል ።

ለእስራኤል ፡ ለማለት ፡ ደገመው ፤ እስራኤልን ፡ የሚጠብቀው ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ፈጽሞ ፡ እያንቀላፋም ። ፩ ፡ ፳፮ ።

፭፤ እግዚአብሔር ፡ ይዕቀብከ ፡ ወእግዚአ ብሔር ፡ ይከድንከ ፡ በየማነ ፡ እዴሁ ።

እግዚአብሔር ፡ በሥልጣኑ ፡ ሰው ሮ ፡ ከመከራው ፡ ይጠብቅህ ።

፮፤ መዓልተ ፡ ፀሐይ ፡ ኢያውዒከ ።

በመዓልት ፡ ፀሐይ ፡ እያቃጥልህ ።

ወኢወርኅ ፡ በሌሊት ።

በሌሊት ፡ ጨረቃ ፡ እያቀዝቅዝህ ፡ ማለት ፤ የቀን ፡ ወራሪ ፡ የሌሊት ፡ ሰባሪ፡ እያግኝህ። ፴፭ ፡ ፲፬ ።

፯፤ እግዚአብሔር ፡ ይዕቀብከ ፡ እምኵሉ ፡ እኩይ ።

እግዚአብሔር ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ እን ድም ፡ ከመከራው ፡ ሁሉ ፡ ይጠብ ቅህ ።

ወይትማሐፀና ፡ ለነፍስከ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ሰማይ ፡ ሩቅ ፡ እደ ራ ፡ ጥብቅ ፡ እንዲሉ ፡ ሰውነትህን ፡ አጽንቶ ፡ ይጠብቃት ።

፰፤ እግዚአብሔር ፡ ይዕቀብከ ፡ በንግደ ትከ ፡ ወበእትወትከ ።

እግዚአብሔር ፡ በንግደትከ ፡ ከኢ

2014 04 18

የሩሳሌም ፡ በወጣህ ፡ ጊዜ ፡ በእት
ወትከ ፡ ባቢሎን፡ በገባህበት ፡ ጊዜ።
እንድም ፡ (በንግደትከ) ፡ ከባቢሎ
ን ፡ በወጣህበት ፡ ጊዜ ። (ወበእት
ወትከ) ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በገባህበ
ት ፡ ጊዜ ። እንድም ፡ በወጣህበት ፡
ጊዜ ፡ ከመከራው ፡ ይጠብቅህ ።

እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።

ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡
ድረስ ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓ
ለመ ፡ ዓለም ። አሜን ።

## መዝሙር ፡ ፻፳፩ ።

፩ ፤ ተፈሣሕኩ ፡ እስመ ፡ ይቤሉኒ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነሐውር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ ነቢ
ያት ፡ ካህናት ፡ የእግዚአብሔር ፡
ማደሪያ ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ኢየ
ሩሳሌም ፡ እንሄዳለን ፡ ብለውኛልና፡
ደስ ፡ አለኝ ።

፪ ፤ ወቆማ ፡ እገሪነ ፡ ውስተ ፡ አዕጻድኪ ፡ ኢየሩሳሌም ።

ኢየሩሳሌም ፡ እግሮቻችን ፡ ባደባ
ባይሽ ፡ ቁመዋልና ፡ ደስ ፡ ደስ ፡ አ
ለኝ ፤ ሳይደረግ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡
ሁኖ ፡ እየታየው ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
እንድም ፡ ነሐውር ፡ ወይቀውማ ፡
ይላል ፡ እብነት ፤ ካህናት ፡ ወደ ፡
ኢየሩሳሌም ፡ እንሄዳለን ፡ እግሮ
ቻችንም፡ በኢየሩሳሌም፡ አደባባይ፡
ይቆማሉ ፡ ብለውኛልና ፡ ደስ ፡ አ
ለኝ ።

፫ ፤ ኢየሩሳሌምስ ፡ ሕንጽት ፡ ከመ ፡ ሀገር ።

ኢየሩሳሌምኒ ፡ ይላል ፤ ኢየሩሳሌ
ምም ፡ ከመ ፡ ሀገርናሃ ፡ እንደ ፡ ቀደ
መ ፡ አገርነቷ ፡ በዘር ፡ በተክል ፡
የታነጸች ፡ ናት ።

እለ ፡ ከማሃ ፡ ወኅቡረ ፡ ምስሌሃ ።

ወእለ ፡ ከማሃ ፡ ኅቡረ ፡ ምስሌሃ ፡
ይላል ፤ እንደሷም ፡ ያሉ ፡ አህጉር ፡
ከሷ ፡ ጋራ ፡ እንደሷ ፡ ባንድነት ፡
በዘር ፡ በተክል ፡ ሕንጻን ፡ የታነጹ ፡
ናቸው ። እንድም ፡ (ኢየሩሳሌም) ፡
ቢለው፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ትላለህ ፤ ኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡
ምን ፡ ያለች ፡ ናት ፡ ትለኝ ፡ እንደ
ሆነ፤ (ኢየሩሳሌምስ) ፡ ኢየሩሳሌም
ስ ፤ እንደሷ ፡ ካሉ ፡ አህጉር ፡ ጋራ ፡
በዘር ፡ በተክል ፡ የታነጸች ፡ ናት ።

ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ፡ ፳፮ ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ፫ ።



፬ ፤ እስመ ፡ ህየ ፡ ዐርጉ ፡ አሕዛብ ።

እስራኤል ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ወጥተዋልና ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስምዐ ፡ እስራኤል ።

አሕዛብም ፡ ያልኋቸው ፡ የእስራ
ኤል ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑ ፡ የእግዚ
አብሔር ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ። እን
ድም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወገኖች ፡
ለመሆናቸው ፡ ስምዕ ፡ እስራኤል ፡
እስራኤልነታቸው ፡ ምስክራቸው ፡
ነው ፤ እስራኤል ፡ ማለት ፡ ነጻሪ ፡
ከሃሊ ፡ ከመ ፡ አምላኩ ፡ ኀሊና ፡
ዘርእዮ ፡ ቅሩበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ማለት ፡ ነውና ።

ከመ ፡ ይግነዩ ፡ ለስምከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ለስምህ ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ።

ዘዳ ፡ ፲፪ ፡ ፭ ። ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፳ ።

፭ ፤ እስመ ፡ ህየ ፡ አንበሩ ፡ መናብርቲሆሙ ፡ ለኩነኔ ።

ለመፍረድ ፡ ለመተቸት ፡ ዙፋናቸ
ውን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አኑረዋልና ፤
ተፈሣሕኩ ።

መናብርተ ፡ ቤተ ፡ ዳዊት ።

መናብርትም ፡ ያልሁት ፡ የዳዊት ፡
ቤት ፡ ዙፋን ፡ ነው ፤ መናብርት ፡
ብሎ ፡ አበዛ ፡ የሊቀ ፡ ካህናቱን ፡
ደርቦ ። እንድም ፡ መንግሥት ፡ ያለ
ክህነት ፡ አይጸናምና ፤ እንድም ፡
ክህነት ፡ ለመንግሥት ፡ ጌጹ ፡
ነውና ። ወትርሲተ ፡ ቤቱ ፡ ለዳ
ዊት ፡ ወመንግሥተ ፡ ዶቂቀ ፡ ው
ሉዱ ፡ ዘበሕጉ ፡ እንዲል። ማቴ ፡ ፲ ፡ ፱ ፡
፳፰ ። ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፴ ።

፮ ፤ ወተገሠፃነዉ ፡ ዳኅናሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ።

የኢየሩሳሌምን ፡ ድኅነቷን ፡ ተናግ
ረዋልና ፤ ተፈሣሕኩ ።

ወፍሥሐሆሙ ፡ ለእለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ስመከ ።

ስምህን ፡ መጽራት ፡ የሚወዱ ፡ የነ
ቢያት ፡ የካህናት ፡ ተድላ ፡ ደስታቸ
ውን ፡ ሰምቻለሁና ፤ ተፈሣሕኩ ።

፯ ፤ ይኩን ፡ ሰላም ፡ በኀይልከ ።

በኀይልህ ፡ እንድም ፡ በዕውቀትህ ፡
አንድነት፡ ፍቅር ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ።

ወትፍሥሕት ፡ ውስተ ፡ ማኅፈደ ፡ ክበዲከ ።

ብዙ ፡ ረድኤት ፡ በሚገኝበት ፡ በሚ
ደረግበት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተድላ ፡
ደስታ ፡ ይደረጋልና ።

፰ ፤ በእንተ ፡ አኀውየ ፡ ወቢጽየ ።

አኀውየ ፡ ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፤ ቢ
ጽየ ፡ ስላሥሩ ፡ ነገድ ።

ይትናገሩ ፡ ሰላመ ፡ በእንቲአኪ ።

ያንቺን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ይናገራ
ሉና ።

፱ ፤ ወበእንተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኪየ ፡ ኀሠሥኩ ፡ ሠናይተኪ ።

የፈጣሪዬ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደ
ሪያም ፡ ስለሆንሽ ፡ ተድላ ፡ ደስ
ታሽን ፡ ሻሁ ።

2014 04 18

## መዝሙር ፡ [illegible] ።

[illegible]

ሰለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናገርታል ፡ እግ [illegible]

[illegible]

ይቅር ፡ እስኪለን ፡ ድረስ ።

[illegible]

አሌፍ ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ ይቅር ፡ በለን ።

[illegible]

በደለን ፡ [illegible] ፡ በሉችተናልና ።

[illegible]

## መዝሙር ፡ [illegible] ።

[illegible]

ሰለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናገርታል ፡ እግ [illegible]

እምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በጎለ ፡ ከኛ ። [illegible]



[illegible]

በልጆችዋ [illegible] ፡ በጸሎትንት ፡ በተነ ሥብን ፡ ጊዜ ፡ እንደም ፡ እጋን ንት ፡ በመስጠንብን ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ እሳቸው ፡ በማያረጋቸው ።

[illegible]

እለን ፡ እለን ፡ በገል ፡ እንደ ፡ ጥል ሎ ፡ ውጠው ፡ እንደ ፡ እንቀት ፡ በማተው ፡ እስቀሩን ፡ ብዙ ፡ በተ ጠራጠርው ፡ ነበር ።

[illegible]

በኛ ፡ ቀጥና ፡ መናታቸውን ፡ እን ዳነውብን ፡ መጠን ።

[illegible]

በመከራ ፡ ሥጋ ፡ እንደም ፡ በወሩ ፡ ውጠው ፡ እስቀሩን ፡ ብዙ ፡ በተጠ ራጠርው ፡ ነበር ። እንደም ፡ እሕ ዛብ ፡ ያላሉ ፡ እብነት ፡ እንደም ፡ በዩዳ ፡ በለስ ፡ በዲዋዊ ፡ ነፍስ ፡ እንደ ፡ ተያዘን ፡ እስቀሩን ፡ ብዙ ፡ በተጠራጠርው ፡ ነበር ።

[illegible]

ሰውነታችን ፡ ከመከራ ፡ ሥጋ ፡ እንደም ፡ ነፍሳችን ፡ ከመከራ ፡ ነፍስ ፡ ዳነች ።

[illegible]

ሰውነታችን ፡ ከመከራ ፡ ሥጋ ፡ እንደም ፡ ነፍሳችን ፡ ከመከራ ፡ ነፍስ ፡ ዳነች ።

[illegible]

[illegible] ፡ እንደም ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ እንደ ፡ [illegible] ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ።

[illegible]

ያዩ ፡ የፈለስሉትን ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ ድና ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ ሰውነታችን ፡ [illegible] ፡ ሥጋ ፡ እንደም ፡ ነፍሳችን ፡ [illegible] ፡ በለስ ፡ [illegible] ፡ ነፍስ ፡ ዳነች ።

[illegible]

መከራ ፡ ሥጋ ፡ ጠፋች ፡ እኛ ፡ ግን ፡ ዳነን ፡ እንደም ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ ጠፋች ፡ እኛ ፡ ግን ፡ ዳነን ።

[illegible]

ረድኤትነ ፡ ሊል ፡ ነው ፡ የኛም ፡ ረድኤታችን ፡ ደኅንነታችን ፡ በማ ይን ፡ ምድርን ፡ በፈጠረ ፡ [illegible] እግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እምነን ፡ ይደረግ ልናል ፡ ተደረገልን ።

2014 04 18

## መዝሙር ፡ ፻፳፬ ።

፩ ፤ እለ ፡ ተወከሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናገሮታል ፤ በእግዚአብሔር ፡ ያመኑ ፡ ትሩፋን ፡ በጽዮን ፡ እጠገብ ፡ እንዳሉ ፡ እንደ ፡ እራራት ፡ እንደ ፡ ቀርጹ ፡ ናቸው ፡ እራራት ቀርጹ ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ እኒህም ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ። እንድም ፡ ከመ ፡ ዘደብረ ፡ ጽዮን ፡ ይላል ፤ በእግዚአብሔር ፡ ያመኑ ፡ ሕዝቡ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንዳሉ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ናቸው ፤ እሊያ ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠብቀው ፡ እንዲኖሩ ፡ እሊህም ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠብቀው ፡ ይኖራሉ ።

ወኢይትሀወክ ፡ ለዓለም ፡ ዘየኀድር ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ።

በኢየሩሳሌም ፡ አድሮ ፡ የሚኖር ፡ ትሩፍ ፡ መከራ ፡ መጥቶበት ፡ ለዘላለም ፡ በመከራው ፡ አይታወክም ።

፪ ፤ አድባር ፡ የዐውዳ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ይዐግቶ ፡ ሕዝቦ ።

ቁሮስ ፡ ዳርዮስ ፡ ሕዝቡን ፡ ከበው ፡ ይኖራሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ በቂሮስ ፡ በዳርዮስ ፡ አድሮ ፡ ሕዝቡን ፡ ይጠብቃል ።

እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።

ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ።

፫ ፤ እስመ ፡ ኢየኀድግ ፡ እግዚአብሔር ፡ በትረ ፡ ኃጥአን ፡ ላዕለ ፡ መክፈልተ ፡ ጻድቃን ፡ ከመ ፡ ኢያንሥኡ ፡ እደዊሆሙ ፡ ጻድቃን ፡ በዐመፃ ።

ትሩፋን ፡ እደ ፡ ቃላቸውን ፡ ለጸሎት ፡ እደ ፡ ሥጋቸውን ፡ ለመሥዋዕት ፡ እደ ፡ ልቡናቸውን ፡ ለአንክሮ ፡ ለተዘክሮ ፡ ወደ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ ኀጢአት ፡ እንዳያነሡ ፡ እግዚአብሔር ፡ በአብርሃም ፡ በይስሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ በትሩፋን ፡ የባቢሎናውያንን ፡ ሥልጣን ፡ አይተውምና ፡ አድባር ፡ የዐውዳ ።

አሡኒ ፡ ማንኛ ፤ አንድም ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነውና ።

አሡኒ ፡ እግዚኦ ፡ ለኄራን ፡ ወለርቱዓነ ፡ ልብ ።

አቤቱ ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ላላቸው ፡ ለትሩፋን ፡ ሚጠቱን ፡ አዘጋጅላቸው ፤ አከናውንላቸው ።

፬ ፤ ወእለሰ ፡ ይትመየጡ ፡ ውስተ ፡ ዕሎ ፡

ወደ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ ኀጢአት ፡ የሚሄዱትን ፡ ከፎችን ፡ ግን ፡

ይወስዶሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ገበርተ ፡ ዐመፃ ።

እግዚአብሔር ፡ ዐመፅን ፡ ከሚሠሩ ፡ ከባቢሎናውያን ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ባቢሎናውያን ፡ ወደ ፡ መከራ ፡ ይወስዳቸዋል ፡ ያጠፋቸዋል ።

ሰላም ፡ ላዕለ ፡ እስራኤል ።

ለበጎቹ ፡ እስራኤል ፡ ግን ፡ እንድንት ፡ ፍቅር ፡ ይደረግላቸዋል ፤ ይደረግላቸው ። ገላ ፡ ፮ ፡ ፲፮ ።

## መዝሙር ፡ ፻፳፭ ።

፩ ፤ አመ ፡ ሜጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፄዋ ፡ ጽዮን ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናገሮታል ፤ የምእመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ። እግዚአብሔር ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ምርኮ ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፡

ወኮነ ፡ ፍሡሓነ ።

ደስ ፡ ያለን ፡ ሆንን ። አንድም ፡ የገነትን ፡ ምርኮ ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ደስ፡ አለን ። አንድም ፡ ደስ ፡ ያለን ፡ በሆንን ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ ደስ ፡ ባለን ፡ ጊዜ ።

፪ ፤ አሚሃ ፡ መልአ ፡ ፍሥሓ ፡ አፉነ ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ አፋችንን ፡ ደስታ ፡ መላው ፡ ማለት ፤ ደስ ፡ አለው ። አፋችንን ፡ መልተን ፡ አመሰገን ፤ ባመሰገንን ፡ ጊዜ ።

ወተሐሥየ ፡ ልሳንነ ።

አንደበታችንን ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ አመሰገንን ፤ ባመሰገንን ፡ ጊዜ ። ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፰ ፡ ፲ ።

፫ ፤ አሚሃ ፡ ይብሉ ፡ አሕዛብ ።

ያን፡ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ እንዲህ፡ አሉ።

አዐበየ ፡ ገቢረ ፡ ሎሙ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ለትሩፋን ፡ ተአምራቱን ፡ አብዝቶ ፡ አደረገላቸው ፡ አሉ ፤ ሰባት ፡ አህጉር ፡ ወግተው ፡ ወጥተዋልና ። አንድም ፡ ለምእመናን፡ ትምርቱን፡ ተአምራቱን ፡ አብዝቶ ፡ አደረገላቸው ፡ አሉ ፡ ማለት ፤ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ሰጣቸው ።

ወኮነ ፡ ፍሡሓነ ።

ደስ ፡ አለን ። ኢሳ ፡ ፻ ፡ ፫ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፵፱ ።

፬ ፤ ሚጥ ፡ እግዚኦ ፡ ፄዋነ ።

አቤቱ ፡ ምርኳችንን ፡ ከባቢሎን ፡ መልስ ።

ከመ ፡ ውሒዝ ፡ ውስተ ፡ አዜብ ።

ውሃ ፡ ከደጋ ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ እንዲፈስ ፡ ወደ ፡ ጥንተ ፡ ቦታው ፡ ወደ ፡ ውቅያኖስ ፡ እንዲመለስ ። ወእምከመ ፡ ፈነውከኒ ፡ ብሔረ ፡ አዜብ ፡ ሀበን ፡ ቢፃ ፡ እንዳለች ፡ እስካ ፡ ወለተ ፡ ካሌብ ። አንድም ፡ በረድ ፡ በፀሐይ ፡ ቀልጦ ፡ ወደ ፡ ጥንተ ፡ ውሀነቱ ፡ እንዲመለስ ። ወይትመየጥ ፡ አዜብ ፡ በታሕተ ፡ መስዕ ፡ እንዲል ። እኛንም ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡

2014 04 18

ኢየሩሳሌም ፡ መልሰን ። ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፲፱ ።

፩ ፡ እለ ፡ ይዘርዑ ፡ በአንብዕ ፡ ወበሐሤት ፡ የአርሩ ።

እያለቀሱ ፡ የሚዘሩ ፡ ሰዎች ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ መከራቸውን ፡ ይሰበስ ባሉ ። ኢሳ ፡ ፷፩ ፡ ፲፱ ፡ ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፱ ።

፪ ፡ ሶበ ፡ የሐውሩ ፡ ወፈሩ ፡ እንዘ ፡ ይበ ክዩ ።

እንደ ፡ ሐምሌ ፡ እንደ ፡ ነሐሴ ፡ ከቤ ታቸው ፡ ሲወጡ ፡ እያለቀሱ ፡ ከቤ ታቸው ፡ ይወጣሉ ፡ ላዩ ፡ ውሃ ፡ ታቹ ፡ ውሃ ፡ ሁኖባቸው ፡ ነውና ።

ወጾሩ ፡ ዘርዖሙ ።

ምሬር ፡ ቀንበር ፡ ዘር ፡ ተሸክመው ፡ ላም ፡ በሬ ፡ ነድተው ፡ ጭቃው ፡ እስከ ፡ ጉልበታቸው ፡ ውጧቸው ፡ ሲሄዱ ።

ወሶቦ ፡ የአትዉ ፡ መጽኡ ፡ እንዘ ፡ ይትፌሥሑ ።

ወደ ፡ ቦታቸው ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ይመጣሉ ፡ ማታ ፡ ዘሩ ፡ በቅቷቸው ፡ ትልሙ ፡ ተከናውኖላ ቸው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋልና ። እንድም ፡ በኅዳር ፡ በታኅሣሥ ፡ መከሩን ፡ አይ ተው ፡ እኸሉን ፡ በሬቅ ፡ በጐታ ፡ በ ጐተራ ፡ ከተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወጾሩ ፡ ከላስስቲሆሙ ።

ተረፈ ፡ ዘሩን ፡ ተሸክመው ፡ ከላ ስስት ፡ አለው ፡ በኋላ ፡ ግብሩ ። እን ድም ፡ በመከር ፡ ጊዜ ፡ ነዶውን ፡ ተሸክመው ፡ ሲገቡ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። እንድም ፡ (እለ ፡ ይዘርዑ) ፡ በባ ቢሎን ፡ ጊዜ ፡ ተማርከው ፡ ከኢየሩሳ ሌም ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የሚሄዱ ፡ ትሩፋን ፡ (በሐሤት) ፡ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ይመለሳሉ ። (ሶበሰ) ፡ ተማርከው ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ሲወርዱ ፡ እያዘኑ ፡ እያለቀሱ ፡ ይሄዳሉ ። (ወጾሩ) ፡ ንዝ፡ ትብትብ ፡ ምንጣፍ ፡ ተሸክመው ፡ ሲሄዱ ። እንድም፡ ተስፋውን ፡ ሰም ተው ፡ ሲሄዱ ፡ ወዘይበዝኁ ፡ ሕዝበ ፡ አውረድከ ፡ በተስፋ ፡ እንዲል ፤ ተ ስፋውን ፡ ሰምተው ፡ የወረዱ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ። (ወሶበ ፡ የአትዉ) ፡ በሚ ጠት ፡ ጊዜ ፡ ሲመለሱ ፡ ደስ ፡ እያ ላቸው ፡ ይመለሳሉ ። (ወጾሩ) ፡ የአ ሕዛብን ፡ ገንዘብ ፡ ተሸክመው ። እንድም ፡ ተስፋውን ፡ ሰምተው ፡ ሲሄዱ ። እንድም ፡ (እለ ፡ ይዘርዑ) ፡ ፂዋዌ ፡ ነፍስ ፡ አግኝቷቸው ፡ በአ ጋንንት ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ የሚሄዱ ፡ ነፍሳት ፡ በሥርከ ፡ ዐርብ ፡ ሚጠተ ፡ ነፍስን ፡ አግኝተው ፡ ደስ ፡ ይላቸ ዋል ። (ሶበሰ) ፡ ከገነት ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ሲሄዱ ፡ እያለቀሱ ፡ ይሄዳሉ ። (ወጾሩ) ፡ ፍዳ ፡ ተቀብ ለው ፡ እንድም ፡ በኅሙስ ፡ ዕለት ፡ የሚል ፡ ተስፋ ፡ መስቀልን ፡ ሰም ተው ፡ (ወሶበ ፡ የአትዉ) ፡ ከሲ ኦል ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ በሚገቡበት ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ እያላ



ቸው ፡ መጡ ። (ወጾሩ) ፡ ልጅነት ፡ አግኝተው ፡ እንድም ፡ ተስፋው ፡ ተፈጽሞላቸው ፤ እንድም ፡ ሥጋ ውን ፡ ደሙን ፡ ተቀብለው ፡ ደስ ፡ እያላቸው ።

እንድም ፡ (እለ ፡ ይዘርዑ) ፡ እያዘኑ ፡ ዘር ፡ ገድልን ፡ የሚዘሩ ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ (ሶበሰ) ፡ ሰማዕታት ፡ እሳቱን ፡ ስለቱን ፡ ጻድቃን ፡ ግርማ ሌሊቱን ፡ ድምፀ ፡ አራዊቱን ፡ ጸ ብእ ፡ አጋንንቱን ፡ እያሰቡ ፡ እያዘኑ ፡ ይሄዳሉ ፡ ማለት ፤ ያለማችዋልና ። (ወጾሩ) ፡ ሰማዕታት ፡ የሚታሰሩበ ትን ፡ ገመድ ፡ የሚሰቀሉበትን ፡ ግንድ ፡ ጻድቃን ፡ እስኬማቸውን ፡ ይዘው ፡ (ወሶበ ፡ የአትዉ) ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። (ወጾሩ)፡ ክብራቸውን ፡ አግኝተው ። ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፮ ፡ ፯ ፡ ፷፩ ፡ ፯ ፡ ፴፮ ፡ ፲ ፡ ፷፭ ፡ ፲፬ ፡ ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፩ ፡ ራእ ፡ ፳፩ ፡ ፬ ፡ ፲፬ ።

## መዝሙር ፡ ፻፳፮ ።

፩ ፡ እመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢሐነጸ ፡ ቤተ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ የም እመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ። (ታ) ፡ ከባቢሎን ፡ ሳሉ ፡ ባባቶቻችን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ የመጣባቸው ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ባይሠሩ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ እኛ ፡ ሚጠቱ ፡ የተደረገልን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቤት ፡ ሳንሠራ ፡ ዘር ፡ ሳንዘራ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ እን ሠራለን ፡ ብለው ፡ ብፅዐት ፡ ገቡ ። በዘሩባቤል ፡ መንግሥት ፡ በቅ ዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አማላጅነት ፡ በእግ ዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ሚጠቱ ፡ ተደረገላቸው ፡ ዘሩባቤል ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ እንሥራ ፡ አላቸው ፡ አስቀድሞ ፡ የመቀመጫዬ ፡ ይባስ ፡ እንዲሉ ፡ ዘንድሮማ ፡ ከምን ፡ ተቀምጠን ፡ እንሠራለን ፡ አሉት ፡ ፈቅዶላቸው ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ እን ዳንድ ፡ ቤት ፡ ሠሩ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ እንሥራ ፡ አላቸው ፡ እንድ ፡ ቤት ፡ ለሰው ፡ ይሆን ፡ ለከብት ፡ ለእንግዳን ፡ ይሆን ፡ ለባለቤት ፡ አ ሉት ፡ እኔማ ፡ ምን ፡ ዕዳዬ ፡ ብፅ ዐት ፡ እንደ ፡ ፈረሰባችሁ ፡ ዕወቁ ፡ አላቸው ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ መሥራት ፡ ጀምረዋል ፡ ረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተለይቷቸዋልና ፡ ቀን ፡ ሲሠሩ ፡ ይውላሉ ፡ ሌት ፡ ፈርሶ ፡ ያድራል ። እንድም ፡ እነእ ጀም ፡ ኮንታ ፡ አልራቁም ፡ ነበርና ፡ እያፈረሱባቸው ፡ ይሄዳሉና ፡ እመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢሐነጸ ፡ ቤተ ፡ አለ ። በዚህም ፡ መጽሐፍት ፡ ተባ ብረውብታል ፤ ኢሳይያስ ፡ እዴየ ፡ ማረረት ፡ ለምድር ፡ ወየማንየ ፡

2014 04 18

አጽንዖቱ፥ ለሰማይ፥ ዝንቱስ፥ግብረ፥ አደውየ ፡ አየኑ ፡ ተሐንጸ ፡ ቤተ ፡ ለመካነ ፡ ምዕራፍየ ፡ ብሎ ፡ ሐጌ ፡ ዘካርያስም ፡ እሉ ፡ ሕዝብ ፡ ይቤሉ ፡ ኢኮነ ፡ ጊዜሁ ፡ ለሐኒጸ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ብሎ ፡ ከዚህም ፡ ዳዊት ፡ እን ዲህ ፡ ብሏል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ን ፡ ካልሠራ ፡ ማለት ፡ ካልረዳ ፡

ከንቶ ፡ ይጻምዉ ፡ እለ ፡ የሐንጹ ።

ቤት ፡ እንሠራለን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች፥ በከንቱ ፡ ይደክማሉ ፡ ድካማቸው ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

እመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢዐቀበ ፡ ሀገረ ።

እግዚአብሔር ፡ ሀገርን ፡ ካልጠ በቀ ፡

ከንቶ ፡ ይትጋሁ ፡ እለ ፡ ይጌልዉ ።

ሀገርን ፡ የሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ሀገ ርን ፡ እንጠብቃለን ፡ ማለታቸው ፡ ከንቱ፥ ነው። እንድም ፡ (እመ ፡ እግ ዚአብሔር) ፡ እግዚአብሔር ፡ ምግ ባር ፡ ካላሠራ ፡ ማለት ፡ ካልረዳ ፡ (ከንቶ) ፡ ምግባር ፡ እንሠራለን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ በከንቱ ፡ ይደከ ማሉ። (እመ ፡ እግዚአብሔር) ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ሰውነትን ፡ ካልጠበቀ፥ (ከንቶ) ፡ ሰውነታችንን ፡ እንጠብ ቃለን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ማለት ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቀን ፡ ከሴት ፡ ርቀን ፡ እንኖራለን ፡ ማለታቸው ፡ ከንቱ ፡ ነው ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፩ ።

፪፡ ወከንቱ ፡ ገይሥትክሙ ።

ቤት ፡ እንሠራለን ፡ ሀገር ፡ እንጠ ብቃለን፥ ማለታችሁ ፡ ከንቱ ፡ ነው። እንድም ፡ ምግባር ፡ እንሠራለን ፡ ሰውነታችንን ፡ እንጠብቃለን ፡ ማለ ታችሁ፥ ከንቱ ፡ ነው ። እንድም ፡ ከንቶ ፡ ይላል ፡ በከንቱ ፡ ነው ።

ተንሥኡ ፡ እምድኅረ ፡ ነበርክሙ ።

ድኅረ ፡ አዕረፍክሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ዓመት ፡ ካረፋችሁ ፡ በኋላ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ለመሥራት ፡ ተነሡ ።

እለ ፡ ትሴሰዩ ፡ እክለ ፡ ሕማም ።

እንቢ ፡ ብላችሁ ፡ መከራ ፡ የምት ቀበሉ ፤ እንድም ፡ እክለ ፡ ሕማምን፥ የምትመገቡ ፡ ሰዎች ፡ ተንሥኡ። ወነፍኅክምሙ ፡ ይላል ፡ በቀጠና ፡ ጊዜ ፡ እኽል ፡ ደዌ ፡ ይሆናልና ።

ሶበ ፡ ይሁቦሙ ፡ ንዋመ ፡ ለፍቁራኒሁ ።

ለወዳጆቹ ፡ ለትሩፋን ፡ ዕረፍትን ፡ በሰጣቸው ፡ ጊዜ ፡ እንቢ ፡ ብላ ችሁ ፡ መከራ ፡ የምትቀበሉ ፡ ትሩ ፋን ፡ ለመማረክ ፡ ተነሡ ። ናሁ ፡ ማንሻ ። ኢሳ ፡ ፴ ፡ ፳ ።

፫ ፡ ናሁ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውሉድ ።

ለወዳጆቹ ፡ ለትሩፋን ፡ ዕረፍትን ፡ በሰጣቸው ፡ ጊዜ ፡ የተገኘ ፡ የእግ ዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ የሚሆን ፡ ውሉድ ፡ ዘሩባቤል ፡ ነው ።



ዕሴተ ፡ ፍሬሃ ፡ ለከርሥ ።

የናት ፡ የማሕፀኗ ፡ ዋጋ ፡ የሚሆን ፡ ውሉድ ፡ ዘሩባቤል ፡ ነው ።

፬፡ ከመ ፡ አሕጻ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ኃያል ።

ባርበኛ ፡ እጅ ፡ የተያዙ ፡ ፍላጾች ፡ እንዲያስፈሩ ።

ከማሁ ፡ ደቂቆሙ ፡ ለንጉፋን ።

የሙታን ፡ ልጆች ፡ ትሩፋንም ፡ እን ዲህ ፡ የሚያስፈሩ ፡ ናቸው። እንድ ፡ ጊዜ ፡ ኃያልነታቸውን ፡ እንድ ፡ ጊዜ ፡ ደካምነታቸውን ፡ ይናገራል።

፭፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘይፈጽም ፡ ፍትወቶ ፡ እምኔሆሙ ።

ባንዱም ፡ ባንዱም ፡ በያንዳንዱ ፡ ፈቃዱን ፡ የሚፈጽም ፡ ዘሩባቤል ፡ ንኡድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

ወኢይትኀፈር ፡ ሶበ ፡ ይትናገርሙ ፡ ለጸላ እቱ ፡ በአናቅጽ ።

ጠላቶቹን ፡ ባደባባይ ፡ ገብሩ ፡ ቀ ቅሉ ፡ ሲል ፡ የማያፍር ፡ ዘሩባቤል ፡ ንኡድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፤ እንድም ፡ አያፍርም ። ማቴ ፡ ፩ ፡ ፮ ።

## መዝሙር ፡ ፻፳፯ ።

፩፡ ብፁዓን ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ እግ ዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የሚፈሩት ፤ እንድም ፡ በማናቸው ም ፡ ሕጉ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩት ፡ ሰዎች ፤ እንድም ፡ ትሩፋን ፡ ንኡ ዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

ወእለ ፡ የሐውሩ ፡ በፍናዊሁ ።

በማናቸውም ፡ ሕጉ ፤ እንድም ፡ በዘጠኙ ፡ ሕጋጋት ፡ ጸንተው ፡ የሚ ኖሩ ፡ ሰዎች ፤ እንድም ፡ ትሩፋን ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

፪፡ ፍሬ ፡ ጻማከ ፡ ተሴሰይ ።

እንዲህ ፡ እልሀ ፡ ትሩፍ ፡ እበጅህ ፤ ጽረህ ፡ ግረህ ፡ ብላ ።

ብፁዕ ፡ አንተ ፡ ወሠናይ ፡ ለከ ።

እንዲህ ፡ ያደረግህ ፡ እንደ ፡ ሆን፥ ንኡድ ፡ ክቡር ፡ ነህ ፤ ክብር ፡ ይሰ ጥሃል ።

፫፡ ብእሲትከ ፡ ከመ ፡ ወይን ፡ ስሙር ፡ ውስተ ፡ ጽርሐ ፡ ቤትከ ።

በቤትህ ፡ አድራ ፡ ያለች፥ ሚስትህ ፡ እንዳማረ ፡ እንደ ፡ ተወደደ ፡ እንደ ፡ ዕፀ ፡ ወይን ፡ ናት ።

ወውሉድከ ፡ ከመ ፡ ተክለ ፡ ዘይት ፡ ሐዲስ ፡ ዐውደ ፡ ማእድከ ።

ማእድህን ፡ ከበው ፡ የሚኖሩ ፡ ልጆችህም ፡ በመታደስ ፡ ጸንቶ ፡ እንደሚኖር ፡ እንደ ፡ ተክለ ፡ ዘይት፥ ናቸው ።

2014 04 18

፬ ፡ ናሁ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ይትባረክ ፡ ብእሲ ፡ ዘይፈርሆ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ዘሩባ ቤል ፡ እንሆ ፡ እንዲህ ፡ ከብሮ ፡ ገኖ፡ ይኖራል ። ኢዮ ፡ ፩ ፡ ፩ ።

፭ ፡ ይባርከ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምጽዮን ።

በጽዮን ፡ ምድራዊት ፡ በጽዮን ፡ ሰማያዊት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ያከብርሃል ፡ ያበዛሃል ፡ ያከብርህ ፡ ያብዛህ ።

ወትሬኢ ፡ ሠናይታ ፡ ለኢየሩሳሌም ።

አንተም ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ታያለህ ።

በኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወትከ ።

ባለ ፡ ዘመንህ ፡ ሁሉ ።

፮ ፡ ወትሬኢ ፡ ውሉደ ፡ ውሉድከ ።

የልጅ ፡ ልጆችህን ፡ ታያለህ ። ይህ ም፡ሊታወቅ ፡ የዘሩባቤል ፡ ዘመኑ ፡ አርባ ፡ ነው ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ አይቶ ፡ ሙቷልና ።

ሰላም ፡ ላዕለ ፡ እስራኤል ።

ለእስራኤልም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ይደረግላቸዋል ።

## መዝሙር ፡ ፻፳፱ ።

፩ ፡ ዘልፈ ፡ ይጸብኡኒ ፡ እምንእስየ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ ከሕ ፃንነቴ ፡ ጀምሮ ፡ እምንእስየ ፡ ከጥ ቂትነቴ ፡ ጀምሮ ፡ ዘወትር ፡ ይጣ ሉኛል ።

ይብል ፡ እስራኤል ፡ ዘልፈ ፡ ይጸብኡኒ ፡ እም ንእስየ ።

ይብል ፡ እስራኤል ፡ ለማለት ፡ ደገ መው ።

፪ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢይክሉኒ ።

ነገር ፡ ግን ፡ አልቻሉኝም ፡ የማታ ፡ ማታ ፡ ድሉ ፡ በኔ ፡ አደረ ።

፫ ፡ ዲበ ፡ ዘባንየ ፡ ዘበጡ ፡ ኃጥአን ።

ባቢሎናውያን ፡ ትብትብ ፡ ምን ጣፍ ፡ አሸክመው ፡ ጀርባ ፡ ጀርባ ባዬን ፡ አሉኝ ። እንድም ፡ በቁሙ ፡ ነጋሪት ፡ መቱብኝ ፡ እንደ ፡ ገጸር ፡ ሰሞነኛ ፡ የጥምቀት ፡ ዕለት ፡ ጥና ውን ፡ ባንድ ፡ እጁ ፡ ይዞ ፡ ነጋሪቱን፡ ላንዱ ፡ አሸክሞ ፡ ድም ፡ እያደረገ ፡ እንዲሄድ ። እንድም ፡ መላእክት ፡ ባሉ ፡ ከለዳውያን ፡ ወዬውውምሙ ፡ ለዕብራውያን ፡ ብለው ፡ ነጋሪት ፡ መትተው ፡ በር ፡ ከፍተው ፡ ቴሃ ፡ አብርተው ፡ አስማርከዋቸዋልና ፡ ኃጥአን ፡ አላቸው ፡ መላእክትን ፡ ለኃጥአን ፡ ስለ ፡ ረዱ ።

ወአስተርሐቅዋ ፡ ለኀጢአቶሙ ።

ኀጢአታቸውን ፡ አብዝተው ፡ ሠ



ሯት ። እንድም ፡ ሠርተው ፡ አልሠ ራንም ፡ አሉ ።

፬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ ሰበረ ፡ አሕዳ ፊሆሙ ፡ ለኃጥአን ።

ጻድቁ ፡ ባሕርይ ፡ እግዚአብሔር ፡ በባቢሎናውያን ፡ የጦር ፡ ምክር ፡ አጠፋባቸው ፡ በሕዳፈ ፡ ይከውን ፡ ጸብእ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ ሰበረ ፡ ከማድን ፡ አመጣባቸው ። ኢሳ ፡ ፲፱ ፡ ፩ ።

፭ ፡ ይትኀፈሩ ፡ ወይግብኡ ፡ ድኅሬሆሙ ።

ይፈሩ፡ ይዋረዱ፤ ድል፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ይቅሩ ።

ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይጸልእዋ ፡ ለጽዮን ።

ማን ፡ ማን ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እ ገሌ ፡ እገሌ ፡ ምን ፡ አሰኝቶኝ ፡ ጽዮ ንን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የሚጠሏት ፡ ሁሉ ።

፮ ፡ ወይኩኑ ፡ ከመ ፡ ሣዕረ ፡ እንሕስት ።

በሰገነት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ በቀለ ፡ ሣር ፡ ይሁኑ ።

ዘይየብስ ፡ ዘእንበለ ፡ ይምሐውዎ ።

ሳያጭዱት ፡ እንደሚደርቅ ።

፯ ፡ ወኢይመልእ ፡ እዴሁ ፡ ለዘየዐጽዶ ።

ለሚያጭደው ፡ በችቦው ፡ እንደማ ይመላ ።

ወእሕፅኖ ፡ ለዘያስተጋብእ ፡ ከላስስቲሁ ።

ነዶውን ፡ ለሚሰበስበው ፡ በእቅፉ ፡ እንደማይመላ ። ኢሳ ፡ ፴፯ ፡ ፳ ።

፰ ፡ ወኢይበሉ ፡ እለ ፡ የኀልፉ ፡ በረከተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌነ ።

ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የሚመላለሱ ፡ ትሩፋን ፡ እግዚአ ብሔር ፡ አድሮብናል ፡ አይበሉ ። (ታ) ፡ ለኤርምያስ ፡ ባሮክ ፡ አቤሜ ሌክ ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ ደቀ ፡ መዛ ሙርት ፡ ነበሩት ። የዚዋዌን ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ ሰምተው ፡ ኢታር እየነ ፡ ሙስናሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ እያሉ ፡ ሲጸልዩ ፡ ይኖራሉ ፤ ኤርም ያስም ፡ ይጸልዩላቸዋል ። ይልቁ ንም ፡ ለአቤሜሌክ ፡ ይጸልይለታ ል ፤ አርኅየኒ ፡ ዘእገብሮ ላዕለ ፡ አቤሜሌክ ፡ ገብርከ ፡ ኢትዮጵ ያዊ ፡ ዘየዐቅቦሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ወሊተኒ ፡ ለገብርከ ፤ እስራኤልን ፡ ለሚጠብቃቸው ፡ እኔንም ፡ ባሪያ ህን ፡ ለሚጠብቀኝ ፡ ለአቤሜሌክ ፡ የማደርገውን ፡ ግለጽልኝ ፡ እያለ ፤ ሊ፡ተኒ ፡ ማለቱ ፡ ከዐዘቅት ፡ ኰስሕ ፡ ጥለውት ፡ ሳለ ፡ ጸልዮ ፡ አድኖት ፡ ነበርና ፤ ዜዋዌ ፡ ቢደርስ ፡ ኤርም ያስን ፡ ባሮክን ፡ ዐፅመ ፡ አበውን ፡ አስጠብቀው ፡ አቤሜሌክን ፡ ለሕ ሙም ፡ የምንቀባው ፡ ዐጽቀ ፡ በ ለስ ፡ ቈርጠህ ፡ አምጣ ፡ ብለህ ፡ አዘዘው ፡ እኔ ፡ ባወቅሁ ፡ እጠብቃ ቸዋለሁ ፡ አለው ። እሱም ፡ ያዘዘ ውን ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤል ፡ ተማርከው ፡ ባቢ ሎን ፡ ወረዱ ፤ አቤሜሌክ ፡ ቈጽለ ፡ በለስ ፡ ቈርጦ ፡ በመሶበ ፡ ወርቅ ፡

እድርጎ ፡ ሲመለስ ፡ ጊዜው ፡ ቀትር፡
ነበረና ፡ ዋዕየ ፡ ፀሓይ ፡ ተስምቶት ፡
ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ሄዶ ፡ ተኛ ፡ ስድሳ ፡
ስድስት ፡ ዘመን ፡ ተኝቶ ፡ ቢነቃ ፡
ጊዜ ፡ ገጥሞት ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡
እልፍ ፡ ብሎ ፡ መሶበ ፡ ወርቁን ፡
ከፍቶ ፡ ቢያይ ፡ ቅጠሉ ፡ ሳይጠ
ወልግ ፡ ደሙ ፡ ሲንጠበጠብ ፡ አገ
ኘው ፡ እሄዳለሁ ፡ ብሎ ፡ መንገድ ፡
ጀመረ ፡ አላስኬደው ፡ አለ ፤ ካሁን፡
አሁን ፡ አእምሮዩ ፡ ተለየኝን ፡ ወ
ይስ ፡ እንቅልፉ ፡ ባይለቀኝ ፡ ነው ፡
እያለ፡ሲያወጣ፡ ሲያወርድ ፡ አንድ ፡
አረጋዊ ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ ታየው ፡
አንዳንድ ፡ ሰው ፡ አይታጣምና ፤
አገርስ ፡ በጠፋ ፡ በስድሳ ፡ ስድስት ፡
ዘመን ፡ ሰው ፡ የለም ፡ ተርፈትሯል ፡
ብሎ ፡ መልአኩ ፡ በአምሳለ ፡ አረ
ጋዊ ፡ ታየው ። ከሱ ፡ ሄዶ ፡ አይቱ ፡
ሀለዉ ፡ ኤርምያስ ፡ ወአኀውየ ፤
መምሬ ፡ ኤርምያስ ፡ ወንድሞቼ ፡
እስራኤል ፡ ወዴት ፡ አሉ ፡ አለው ።
አንተኑ ፡ ነግዳ ፡ ለኢየሩሳሌም ፤
ኢየሩሳሌም ፡ ከጠፋች ፡ እስራኤል ፡
ከተማረኩ፡ ስድሳ፡ ስድስት፡ ዓመት፡
ሁኗል ፡ የኢየሩሳሌም ፡ እንግዳ ፡
አንተ ፡ ነህን ፡ አለው ። አራት ፡ አከ
ብር ፡ ገጸ ፡ አረጋዊ ፡ ትላለች ፡ እ
ንጂ ፡ ባትል ፡ ጅጁ ፡ ጀውጃዋ ፡
አእምሮውን ፡ ያጣ ፡ ሽማግሌ ፡
ብዬ ፡ በሰደብኩህ ፡ ነበር ። ዘሎ፡፲፱፡
፩፪። ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ የላከህ ፡ እ

ለው ፤ በዘር ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ መከር፡
ሆንብህሳ ፤ በመከር ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤
ወርኀ ፡ ዘርዕ ፡ ሆንብህሳ ፤ በዘር ፡
የላኩት ፡ በዝርዝር ፡ የተባልህ ፡
አንተ ፡ ነህን ። አንተስ ፡ ወልድየ ፡
ምሕረተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሀሎ ፡
ምስሌከ ፤ ልጄ ፡ እግዚአብሔር ፡
በቸርነቱ ፡ በይቅርታው ፡ ከመከ
ራው ፡ ቢሰውርህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
እስራኤል ፡ ከተማረኩ ፡ ኢየሩሳ
ሌም ፡ ከጠፋች ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡
ዘመን ፡ ሁኗል ። መኑ ፡ ተዘከሮ ፡
ለኤርምያስ ፤ ኤርምያስ ፡ ያለ ፡
በዙረት ፡ በባቢሎን ፡ ይልቅ ፡ ና ፡
ከወንድምህ ፡ ላገናኝህ ፡ ብሎ ፡ ወ
ስዶ ፡ ገጠመው ። አንድ ፡ ሰዓት ፡
አንገት ፡ ላንገት ፡ ተያይዘው ፡
ተላቅሰዋል ። አባታችን፡ ኤርምያስ፡
ሚጠት ፡ ይደረጋል ፡ እያለ ፡ ሲና
ገር ፡ ሰምተነው ፡ ነበር ፤ ጊዜው ፡
እንዲገለጽልን ፡ ወደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ እናመልክት ፡ ብለው፡ ቢያመ
ለክቱ ፡ ለሚጠት ፡ አራት ፡ ዓመት ፡
እንደ ፡ ቀረው ፡ ተገልጦላቸው ፡
ከአሕዛብ ፡ የተጋባችሁ ፡ ተፋቱ ፡
ያልተጋባችሁ ፡ አትጋቡ ፡ ለሚ
ጠት ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ቀርቶታል ፡
ብለው ፡ ጽፈው ፡ ማን ፡ በወሰደልን፡
እያሉ ፡ ሲጨነቁ ፡ ወዲያው ፡ የታ
ዘዘ ፡ ንስር ፡ መጣ ፤ ይመስጋገናሉ ፤
ሰላም ፡ ለከ ፡ አ ፡ ንስር ፡ ዘእሙር ፡
በብርሃን ፡ አዕይንቲከ ፤ ወልድየ ፡



ኢትትመሰሎ ፡ ለቋዕ ፡ እላ ፡ ተመ
ሰላ ፡ ለርግብ ፡ አንተ ፡ ሥልሰ ፡ አብ
ጽሐት ፡ ቃላ ፡ ኀበ ፡ ኖኅ ፤ ባይ
ንህ ፡ ጽርየት ፡ የታወቅህ ፡ ንስር ፡
አንድነት ፡ ፍቅር ፡ ይገባሃል ፡ የኖ
ኅን ፡ መልክት ፡ ያስቀረ ፡ ቋዕን ፡
አትመሰለው ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላ
ልሳ ፡ ያደረሰች ፡ ርግብን ፡ ምሰላት ፡
እንጂ ፡ አለው ። ዘፍ፡፰፡፮፡፲፪።እሱም፡
ፈንታውን ፡ ያመሰግነዋል ፤ ሰላም ፡
ለከ ፡ አ፡ባሮክ ፡ መጋቤ ፡ ሃይማኖት፤
የሃይማኖት፡ አደግኸኝዋ ፡ ባለቤቷ ፡
ባሮክ ፡ እንደ ፡ ምንህ ፡ አለው ፡ ኢት
ትገሐሥ ፡ ኢለየማን ፡ ወኢለፀጋም፡
እላ ፡ ኩን ፡ ከመ ፡ ሐጽ ፡ ዘተውህበ፡
ለሰራር ፤ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡
አትበል፤ እንደ ፡ ተወረወረ ፡ ቀስት ፡
ሁንህ ፡ ሂድ ። ወለእመ ፡ ረከቡከ ፡
ዕድዋኒሃ ፡ ለሃይማኖት ፡ ብድሮሙ ፡
ብቃለ፡ እግዚአብሔር፤ የሃይማኖት ፡
ጠላቶች ፡ አጋንንት ፡ ቢያገኙህ ፡
ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርተህ ፡
ድል ፡ ንሣቸው ፡ አለው ። ጠማሩን፡
ቈጽለ ፡ በለሱን፡ ባንገቱ ፡ አስረው ፡
ሰደዱት ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኤርምያ
ስ ፡ ዘመዱ ፡ የሆን ፡ ሙቶበት ፡ ከነ
ገሥታቱ ፡ ተካሶ ፡ ሊያስቀብር ፡
ከፈረስ ፡ ማንብ ፡ አሳርፎ ፡ ሳለ ፤
ኤርምያስ ፡ ኤርምያስ ፡ ብሎ ፡
ብቃል ፡ ሱብአዊ ፡ ጠርቶ ፡ ጠማሩን ፡
ቈጽለ ፡ በለሱን ፡ ጣለለት ። እን
ድም ፡ ወከዶ ፡ በእግሩ ፡ ለምውት ፡

ይላል ፤ ረቦ ፡ መጥቶ ፡ ከምውቱ ፡
ላይ ፡ ዐረፈ ፤ ተነሥቶ ፡ ከወረቀቱ ፡
ላይ፡ ያለውን፡ መስከሮ ፡ ተመልሶ ፡
ዐርፏል ፤ ወረቀቱም ፡ ለሚጠት ፡
አራት ፡ ዓመት ፡ ቀርቶታል ፤ ከአ
ሕዛብ ፡ የተጋባችሁ ፡ ተፋቱ ፡ ያል
ተጋባችሁ ፡ ተጠበቁ ፡ የሚል ፡
ነው ። ኤርምያስም ፡ ያንኑ ፡ ሲያስ
ተምር ፡ ኖረ ፤ ደጋጎቹ ፡ የተጋቡ ፡
ተፋቱ ፤ ያልተጋቡ ፡ ተጠበቁ ፤
ከፎቹ ፡ ማን ፡ ሚጠቱ ፡ ይገኝ ፡ እ
ንጂ ፡ ሚስቶቻችንንስ ፡ ማን ፡ አፋ
ቶን ፡ ሀገራችንንስ ፡ ማን ፡ ነሥ
ቶን ፡ ብለው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡
ሲኖሩ ፡ ጊዜው ፡ ቢደርስ ፡ ደጋጉን ፡
ይዞ ፡ ጉዞ ፡ ጀመረ ፤ እሊያም ፡ ተከ
ተሉት ፤ አትከተሉኝ ፡ አትምጡ
ብኝ ፡ ቀድሞ ፡ እንዲህ ፡ ብላችሁ ፡
አይሆንም ፡ ብላችኋል ፡ አላቸው ፤
አሕዛብም ፡ እንዲህ ፡ ሲጠሏችሁ ፡
ከዚሁ ፡ አትኖሩምን ፡ የሚስት ፡
የልጅ ፡ አገርስ ፡ አገር ፡ አይደለ
ምን ፡ አሏቸው ፤ አይሆንም ፡ ሳንገ
ባ ፡አንቀርም ፡ ብለው ፡ ተከተሉት ፤
ፈለገ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ሲደርሱ ፡ ባሮ
ክና ፡ አሜቤሌክ ፡ ሊቀበሉት ፡
ሄዱ ፤ የአሕዛብን ፡ ሴቶች ፡ አይ
ተው ፡ ምነው ፡ ወረቀት ፡ ልከን
ብህ ፡ነበር፡ አልደረሰህምን ፡አሉት ፤
ደርሶልኝ፡ ነበረ፡ አይሆንም፡ ብለው፡
መጡ ፡ እንጂ ፡ አላቸው ፤ እነሱን ፡
አስረድቶ ፡ ገጠማቸው ፡ ድል ፡

2014 04 18

አድርጎ ፣ ስለ ዳኞቻቸው ፤ ተመልሰው ፣ ወደ ፣ ነበሩበት ፣ ሄዱ ፤ እንግዲህ ፣ ወዲህስ ፣ እትምጣብን ፣ እትሂዱ ፣ ስንላቸው ፣ አይሰሙም ፣ ብላችሁ ፣ ሄዳችሁል ፣ የወደዱትን ፣ ቢያጡ ፣ የጠሉትን ፣ ይቀባጠሙ ፣ ብለው ፣ ለዳኞቻቸው ፣ እግራቸው ፣ እንዳይረስ ፣ ሄደው ፣ አገር ፣ እቅንተው ፣ ኦሪዋል ፣ ሥመርናያ ፣ ብለዋታል ፣ በዚህ ፣ ሰማርያ ፣ ተብላለች ። እንድም ፣ (ወኢይቤሉ) ፣ ማስተማሪቻውን ፣ ትተው ፣ አገር ፣ ላገር ፣ የሚዞሩ ፣ መምራን ፣ ረድኤተ ፣ እግዚአብሔር ፣ እድርብናል ፣ አይሉሉ ። እንድም ፣ በእታቸውን ፣ ትተው ፣ ከተማ ፣ ለከተማ ፣ የሚዞሩ ፣ መነኮሳት ፣ ረድኤተ ፣ እግዚአብሔር ፣ እድርብናል ፣ አይሉሉ ።

ባረክናክሙ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ።

ነቢያት ፣ ካህናት ፤ እንድም ፣ ምእመናን ፤ እንድም ፣ መነኮሳት ፣ በስመ እግዚአብሔር ፣ ጠርተን ፣ አከበር ናችሁ ፣ አይሉአችሁ ።

መዝሙር ፡ ፻፳፱ ።

፩ ፡ እምዕምቅ ፡ ጸዋዕኩከ ፡ እግዚኦ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናገርታል ፤ አቤቱ ፣ በባቢሎን ፣ በቂላቱ ፣ ሐዘን ፣ ሁኜ ፣ ለመንኩህ ። እንድም ፣ መጽሐፈ ፣ መነኮሳት ፣ እምርርርሮ ፣ ልብየ ፣ ብሎ ፣ ወስፈታል ፣ ብለህ ፣ በጥልቅ ፣ ልቡና ፣ በጹሕቀ ፣ ልቡና ፣ ሁኜ ፣ ለመንኩህ ።

፪ ፡ እግዚኦ ፡ ስምዐኒ ፡ ቃልየ ።

አቤቱ ፣ ልመናዬን ፣ ስማኝ ።

ወይኩን ፡ እዝንከ ፡ ዘያጸምዕ ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ።

እዝን ፣ ፈቃድህ ፣ እዝን ፣ ምሕረትህም ፣ የልመናዬን ፣ ቃል ፣ የሚሰማኝ ፣ ይሁን ።

፫ ፡ እመሰ ፡ ኃጢአተኑ ፡ ትትዓቀብ ።

የኛንማ ፣ ኃጢአት ፣ የምትጠባበቅ ፣ የምትቈጣጠር ፣ ከሆን ።

እግዚኦ ፡ እግዚኦ ፡ መኑ ፡ ይቀውም ።

አቤቱ ፣ ካንተ ፣ ፊት ፣ ጻድቅ ፣ ንጹሕ ፣ ሆኖ ፣ የሚገኝ ፣ ማነው ። ዘፀ ፡ ፴፬ ፡ ፯ ። ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፲፩ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ገላ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ።

፬ ፡ እስመ ፡ እምኀቤከ ፡ ውእቱ ፡ ሣህል ።

የኛ ፣ ይቅርታ ፣ ካንተ ፣ ዘንድ ፣ ይታዘዛል ፣ ይደረጋልና ፤ ይቅር ፣ በለን ፣ እንጂ ፣ የኛንማ ፣ ኃጢአት ፣ የምትጠባበቅ ፣ የምትቈጣጠር ፣ ከሆን ፣ ካንተ ፣ ፊት ፣ ጻድቅ ፣ ንጹሕ ፣ ሆኖ ፣ የሚገኝ ፣ ማነው ።



ወአንተ ፡ ሰምዐከ ፡ ተሰፈውኩከ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፣ ስምየ ፣ መሐሪ ፣ ወመስተ ማህል ፣ ስላልህ ፣ እኔም ፣ እንተን ፣ ተስፋ ፣ አደረግሁ ።

፭ ፡ ተወከለት ፡ ነፍስየ ፡ በሕግከ ።

ሰውነቴ ፣ በሕግህ ፣ ጸናች ። እንድም ፣ በሕግህ ፣ ጸንታ ፣ መከራውን ፣ ታግሣ ፣ ተቀበለች ።

ተወከለት ፡ ነፍስየ ፡ በእግዚአብሔር ።

ሰውነቴ ፣ በእግዚአብሔር ፣ አመነች ።

፮ ፡ እምሰዓተ ፡ ጽባሕ ፡ እስከ ፡ ሌሊት ።

ከጧት ፣ እስከ ፣ ማታ ፣ ድረስ ። እንድም ፣ ከዕለተ ፣ ልደት ፣ እስከ ፣ ዕለተ ፣ ሞት ፣ ድረስ ።

እምሰዓተ ፡ ጽባሕ ፡ ተወከለ ፡ እስራኤል ፡ በእግዚአብሔር ።

እስራኤል ፣ ለማለት ፣ ያገመው ፤ እስራኤል ፣ በእግዚአብሔር ፣ አመነ ።

፯ ፡ እስመ ፡ እምኀቤሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሣህል ።

ይቅርታ ፣ ከእግዚአብሔር ፣ ዘንድ ፣ ይታዘዛል ፣ ይደረጋልና ።

ወብዙኅ ፡ አድኅኖ ፡ በኀቤሁ ።

ከሱ ፣ ዘንድ ፣ ብዙ ፣ ትድግና ፣ ይደረጋልና ።

፰ ፡ ወውእቱ ፡ ያድኅኖ ፡ ለእስራኤል ፡ እምኵሉ ፡ ኃጢአቱ ።

እኔ ፣ እቸገራለሁ ፣ እንጂ ፣ እስራኤልንስ ፣ ኃጢአት ፣ ወርቆ ፣ ካገኘው ፣ መከራ ፣ ሁሉ ፣ እሱ ፣ ያድነዋል ።

መዝሙር ፡ ፻፴ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ ኢያትዐበየ ፡ ልብየ ።

ስለ ፣ ትሩፋን ፣ ተናግሮታል ፤ አቤቱ ፣ ልቡናዬ ፣ አይኩራብኝም ።

ወኢያልዐላ ፡ አዕይንትየ ።

ዐይኖቼም ፣ አይመቀኙብኝም ።

ወኢሖርኩ ፡ ምስለ ፡ ዐቢያት ።

ከመኳንንቱ ፣ ከመምለክያን ፣ ጣያት ፣ ጋራ ፣ ወደ ፣ ቤተ ፣ ጣዖት ፣ አልሄድሁም ።

ወእምስለ ፡ እለ ፡ ይከብሩ ፡ እምኔየ ።

ከኔ ፣ ይልቅ ፣ ከሚከብሩ ፣ ከካህናት ፣ ጣያት ፣ ጋራ ፣ አልሄድሁም ።

፪ ፡ ወሶበሰ ፡ ኢተሐትኩ ፡ ርእስየ ።

ራሴን ፣ አዋረድሁ ፣ እንጂ ።

ወአልዐልኩ ፡ ቃልየ ።

በቃሌ ፣ ወጳንተ ፣ መልኧ ፣ ለመንሁ ፣ እንጂ ።

ከመ ፡ ዘእጎጽግዋ ፡ ኅፃን ፡ እሙ ።

የናቱን ፣ ጡት ፣ እንዳስጣሉት ፣ ብላቴና

ከመ ፡ ትፈድያ ፡ ለነፍስየ ።

ለሰውነቴ ፣ ዕሴት ፣ ንስሓን ፣ ሚጠትንም ፣ ትሰጣት ፣ ታደርግላት ፣ ዘንድ ።

2014 04 18

፫ ፡ ተመከል ፡ እስራኤል ፡ በእግዚአብሔር ።
እስራኤል ፡ በእግዚአብሔር ፡ እመን ።
እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ። ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ። አሜን ።

## መዝሙር ፡ ፻፴፩ ።

፩ ፡ ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ለዳዊት ፡ ወለኵሉ ፡ የውሀቱ ።
ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ የጌታም ፡ ነገር ፡ አለበት ። አቤቱ ፡ ዳዊትን ፡ አስብ ፡ ሕግ ፡ መጠበቁን ፡ ቅንነቱንም ፡ ሁሉ ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ ከባቢሉን ፡ አውጣን ።

፪ ፡ ዘከመ ፡ መሐለ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበፅዐ ፡ ለአምላከ ፡ ያዕቆብ ።
ዘከመ ፡ መሐለ ፡ ወበፅዐ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ያዕቆብ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ለያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ማለ ፡ እንደ ፡ ተሳለ ።

፫ ፡ ከመ ፡ ኢይበውእ ፡ ውስተ ፡ ጽላሎተ ፡ ቤትየ ።
ወደ ፡ ማርፍበት ፡ ቤቴ ፡ አልገባም ፡ እንዳለ ። እንድም ፡ እንዳልገባ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ማለ ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ።

ወኢየዐርግ ፡ ውስተ ፡ ዐራት ፡ ምስካብየ ።
ወደምተኛበት ፡ ወደ ፡ አልጋዬ ፡ ወደ ፡ ዙፋኔ ፡ አልወጣም ፡ እንዳለ ፡ እንዳልወጣ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ማለ ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ።

፬ ፡ ወከመ ፡ ኢይሁቦን ፡ ንዋመ ፡ ለአዕይንትየ ።
ላይኖቼ ፡ ጽኑ ፡ እንቅልፍን ፡ አልሰጣቸውም ፡ እንዳለ ፡ እንዳልሰጣቸው ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ማለ ።

ወኢድቃሰ ፡ ለቀራንብትየ ።
ለሽፋሽፍቶቼም ፡ ሽልብታን ፡ አልሰጣቸውም ፡ እንዳለ ፡ እንዳልሰጣቸው ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ማለ ።

ወእዕረፍተ ፡ ለመላትሕየ ።
ለፊቶቼም ፡ ዕረፍትን ፡ አልሰጣቸውም ፡ እንዳለ ፡ ማረፍ ፡ በፊት ፡ ነውና ። እንድም ፡ መጠጊያ ፡ እንድም ፡ ከተጸፍዖ ፡ አላሳርፋቸውም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ማለ ።



፭ ፡ እስከ ፡ እረክብ ፡ መካነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወማኅደረ ፡ ለአምላከ ፡ ያዕቆብ ።
እስከ ፡ እረክብ ፡ መካና ፡ ወማኅደሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ያዕቆብ ፡ የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማደሪያ ፡ ፈጽሜ ፡ እስካገኝ ፡ ድረስ ፡ ለግራ ፡ ለቀኝ ፡ ፊቶቼ ፡ ዕረፍትን ፡ አልሰጣቸውም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ማለ ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ። ዳዊት ፡ እነዐግን ፡ እነሴምንን ፡ ንጉሥ ፡ አራድን ፡ ወግቶ ፡ ደብረ ፡ ጽዮንን ፡ አቅንቶ ፡ በጽድ ፡ በዘግባ ፡ በተሠራ ፡ ቤት ፡ ይኖራል ፡ ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ በድንኳን ፡ ትኖራለች ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሲያዝን ፡ ይኖራል ። ነቢዩ ፡ ናታን ፡ ይባሱን ፡ ሊጠይቀው ፡ ሄዶ ፡ ንጉሥ ፡ ምነው ፡ አዝነኻል ፡ አለው ፡ እኔ ፡ ያላዘንሁ ፡ ማን ፡ ይዘን ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ እንደምታዩኝ ፡ በጽድ ፡ በዘግባ ፡ በተሠራ ፡ ቤት ፡ እኖራለሁ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ በድንኳን ፡ ትኖራለች ፡ አለው ። እውነትህ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ጠላትህን ፡ ላጠፋልህ ፡ መንግሥትህን ፡ ላሰፋልህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ወረታ ፡ ትከፍለዋለህ ፡ እነጽ ፡ አለው ፡ ያውስ ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳናመለክት ፡ ይሆናልን ፡ ብሎ ፡ ተያይዘው ፡ ቀን ፡ ዋዕየ ፡ ፀሐይ ፡ እንደ ፡ ዝናም ፡ ከሚዘንብበት ፡ ሌሊት ፡ ቊር ፡ እንደ ፡ በረድ ፡ ከሚፈላበት ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ሄደው ፡ ቀናና ፡ ገቡ ፡ ለዳዊት ፡ አልተገለጸለትም ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ቢሉ ፡ ደም ፡ አፍሳሽ ፡ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ ነበርና ። ይህስ ፡ አይደለም ፡ ዕርቅ ፡ ይም ፡ ያደርቅ ፡ እንዲሉ ፡ በንስሓ ፡ ታርቆታል ፡ ብሎ ፡ በእንተ ፡ አጽባእት ፡ ዘዐውዱ ፡ ያላል ፡ በዳዊት ፡ ጊዜ ፡ ጠላት ፡ አልጠፋም ፡ ነበርና ፡ አዝኖለት ፡ ነው ። ለናታን ፡ ግን ፡ ተገልጾለት ፡ አኮ ፡ አንተ ፡ ዘትነድቅ ፡ ሊተ ፡ ቤተ ፡ ለስምየ ፡ዳእሙ ፡ ወልድከ ፡ ዘወፅአ ፡ እምሐቌከ ፡ ውእቱ ፡ ይነድቅ ፡ ሊተ ፡ ይላል ። ከአብራክህ ፡ የተከፈለ ፡ ልጅህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ማደሪያዬን ፡ የሚሠራልኝ ፡ አንተ ፡ አይደለህም ፡ አንተስ ፡ ጠላት ፡ አጥፋ ፡ ድንበር ፡ አስፋ ፡ ብሎኻል ፡ በለው ፡ አለው ። እንድም ፡ ለዳዊት ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የሥጋዌ ፡ ነገር ፡ ተገልጾለታል ፡ ለጌታም ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡ ቢለምኑት ፡ የበለጠ ፡ ነገር ፡ መግለጽ ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ ሱቱኤል ፡ ዕዝራ ፡ ሚጠተ ፡ እስራኤልን ፡ እንኛለሁ ፡ ብሎ ፡ ግብር ፡ ቢገባ ፡ የበለጠ ፡ የሥጋዌ ፡ ነገር ፡ ተገልጾለት ፡ እንበሳ ፡ ወፅአ ፡ እምገዳም ፡ ውእቱኬ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ እንዳለ ። የመንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ነገር ፡ ተገልጾለት ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ዝንቱ ፡ ዐቢይ ፡ እንዳለ ። ዳንኤልም ፡ ሚ

2014 04 18

ጠተ ፡ እስራኤልን ፡ አገኛለሁ ፡
ብሎ ፡ ግብር ፡ ቢገባ ፡ የበለጠ ፡
የሥጋዌ ፡ ነገር ፡ ተገልጾለት ፡ መቅ
ደስ ፡ ትትሐነጽ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ፡
ንጉሥ ፡ ወእምዝ ፡ ትትመዘበር ፡
እንዳለ ፡ ከዚህም ፡ ዳዊት ፡ እንዲህ፡
አለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከማናቸውም፡
ርስቱ ፡ ከማናቸው ፡ ነገዶ ፡ ይሆን ፡
ብሎ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ግብር ፡ ገባ ፡ ር
ስቱ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ነገዱ ፡ ይሁዳ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ተገልጾለታል ። ፩ ፡ ነገ ፡
፲ ፡ ፩ ። ግብ ፡ ፲ ፡ ፵፮ ።

፮ ፡ ናሁ ፡ ሰማዕናሁ ፡ በኤፍራታ ።

በኤፍራታ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ትሠ
ራለች ፡ ሲል፡ ሰማነው፡ ሰማዕናሁ ፡
ማለት ፡ ራሱን ፡ ከናታን ፡ አግብቶ ፡
ምንም ፡ ባይገለጽለት ፡ አብሮ ፡ ገብ
ቶ ፡ ነበርና ።

ወረከብናሁ ፡ ውስተ ፡ ገዳመ ፡ ገዳም ።

ገዳመ ፡ ገዳም ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ዛፍ ፡
ባለበት ፡ አገር ፡ (በረሓ) ፡ ማለት ፡
ኋላ ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ በተፈታች ፡
በኢየሩሳሌም ፡ ተሠርቶ ፡ አገኘ
ነው ። ሚክ ፡ ፭ ፡ ፩ ። ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፵፪ ።

፯ ፡ ንበውእ ፡ እንከሰ ፡ ውስተ ፡ አብያቲሁ ፡
ለእግዚአብሔር ።

እንግዲህስ ፡ ወዲህ ፡ ግዱን ፡ ከሰባ ፡
ዘመን ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ማደሪያ፡ ወደምትሆን፡ ወደ ፡ ቤተ ፡
መቅደስ ፡ እንገባለን ፡ አለ ፡ ወሰብ
ዓ ፡ ዓም ፡ ያለው ፡ አይቀርምና ።

ወንሰግድ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡ ቆሙ ፡
እግረ ፡ እግዚእነ ።

የጌታችን ፡ እግር ፡ ከቆመበት ፡
ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብተን ፡ እንሰ
ግዳለን ። ዳዊት ፡ ኢዮአብን ፡ አኢ
ላፈ ፡ እስራኤልን ፡ ቍጠራቸው ፡
አለው ፡ ጌታዬ ፡ አሁን ፡ ሰው ፡ ገን
ዘቡን ፡ ቢቈጥሩበት ፡ ይወዳልን ፡
እስራኤል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገን
ዘቦች ፡ ናቸው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይሆ
ናል ፡ አለው ፡ ቍጠር ፡ ብልህ ፡ አለ
ው ፡ በከተማ፡ ያሉ፡ ነገዶ፡ ይሁዳን ፡
ቈጥሮ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ሳይሻገር ፡
ክረምት ፡ ገባበት ፡ ምን ፡ ያኽል ፡
ሆኑ ፡ አለው ፡ ሰማኒያ ፡ ስምንት ፡
እልፍ፡ ሆኑ፡ አለው ፡ ሽምገለናልሳ ፡
ለዋስ ፡ በቅተናል፡ አለው ። ጌታ ፡ ለ
ናታን ፡ ይነግረዋል ፡ ሦስት ፡ ዓመ
ት ፡ ረኃብ ፡ ከማመጣብህ ፡ ሦስት ፡
ወር ፡ በጠላትህ ፡ እጅ ፡ ከምጥልህ ፡
ሦስት ፡ ቀን ፡ መከራ ፡ ከማመጣብ
ህ ፡ ከኒህ ፡ ከሦስቱ ፡ እንዱን ፡ ምረ
ጥ ፡ ብሎሃል ፡ በለው ፡ አለው ፡
ሄዶ ፡ ነገረው ። ዐጸበኒ ፡ እምኵለ
ሄ ፡ ሁሉም ፡ አስጨነቀኝ ፡ ይኄይ
ሰኒ ፡ እደቅ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እምእደቅ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡
ሰብእ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመዓቱ ፡
ቸርነቱ ፡ ይበዛል ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡
መከራ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ይሁንለ
ት ፡ ብለህ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
አመልክትልኝ ፡ አለው ፡ ባንድ ፡



ሰዓት ፡ ከነግህ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
ሠለስት ፡ ሦስት ፡ እልፍ ፡ ሰራዊት ፡
ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ መኳንንት ፡ አለቁ
በት ። ምንተ ፡ ገብሩ ፡ እሉ ፡ አባ
ግዕ ፡ እንዘ ፡ አነ ፡ ሀሎኩ ፡ ደዬ ፡
እዴከ ፡ ላዕሌየ ፡ ወላዕለ ፡ ቤተ ፡
አቡየ ፡ ብሏል ። በዐውደ ፡ ኦርና ፡
መልአከ ፡ መድምስስ ፡ ሲቀሥፍ ፡
ታይቶታል ፡ ገሥግሦ ፡ ሄዶ ፡ ጌታዬ
ምን ፡ ልታደርግ ፡ መጣህ ፡ አለው ፡
መሥዋዕት ፡ ልሠዋ ፡ ነው ፡ አለው ፡
እነሆ ፡ በጉ ፡ ፍየሉ ፡ ላሙ ፡ የወይ
ድ፡ከውን ፡ ሠዋ ፡ አለው ፡ በገንዘብ ፡
ገዝቶ ፡ ሠውቷል ፡ ከዚያው ፡ ቤተ ፡
መቅደስ ፡ ሠርቷልና ፡ እንዲህ ፡
አለ ። ይህማ ፡ መልአክ ፡ አይደለም
ን ፡ እግዚአብሔር ፡ አለ ፡ ምነው ፡
ቢሉ ፡ አለቃው ፡ ካለበት ፡ ጭፍራ
ው ፡ ጭፍራው ፡ ካለበት ፡ አለቃው፡
እንዳይለይ ፡ መልአክ ፡ ካለበት ፡
ጌታ ፡ ጌታ ፡ ካለበት ፡ መልአክ ፡
አይለይምና ። እንድም ፡ ናሁ ፡ ሰማ
ዕናሁ) ፡ በነቢያት ፡ አድሮ ፡ እወር
ዳለሁ ፡ እወለዳለሁ ፡ ሲል፡ሰማነው፡
(ወረከብናሁ) ፡ የሕዝብን ፡ የአሕ
ዛብን፡ ሥጋ ፡ ተውሕዶ፡ አገኘነው ።
እንድም ፡ (ናሁ) ፡ በኤፍራታ ፡ ተወ
ልዶ ፡ በግዕዘ ፡ ሕፃናት ፡ ሲያለቅስ ፡
ሰማነው ፡ በጎለ ፡ እንስሳ ፡ ተወ
ድቶ ፡ እምኀ ፡ ንግሥ ፡ ተወረየ ፡
ወከመ ፡ ሕፃናት ፡ በከየ ፡ እንዘ ፡
ይሰሕል ፡ እምእጥባተ ፡ እሙ ፡
ሲላቸ ፡ እንዲል ። (ወረከብናሁ) ፡
በጎል ፡ ተጥሎ ፡ በጨርቅ ፡ ተጠ
ቅሎ ፡ አገኘነው ። (ንበውእ) ፡ እን
ግዲህስ ፡ ግዱን ፡ ካምስት ፡ ሺሕ ፡
አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡
ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እን
ገባለን ፡ ግዱን ፡ አለ ፡ በኅሙስ ፡
ዕለት ፡ ያለው ፡ አይቀርምና ።

ወንሰግድ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡ ቆሙ ፡ እግ
ረ ፡ እግዚእነ ።

የጌታችን ፡ እግር ፡ ወደ ፡ ቆመበት ፡
ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እን
ሰግዳለን። እንድም ፡ (ናሁ ፡ ሰማዕና
ሁ) ፡ ናሁ ፡ ነዐርግ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወ
ይትኄየጥዎ ፡ ለወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመ
ሕያው ፡ ወይሰቅልዎ ፡ ወይትንሣ
እ ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡ ሲል ፡ ሰማ
ነው ። (ወረከብናሁ) ፡ በቀራንዮ ፡
በተተከለ ፡ መስቀል ፡ ተሰቅሎ ፡
አገኘነው ። (ንበውእ) ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ወደምትሆን ፡
ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንገባ
ለን ፡ እሴኒ ፡ ጌታ ፡ ተአምራት ፡
ባደረገበት ፡ ሁሉ ፡ ቤተ ፡ መ
ቅደስ ፡ እሠርታበታለችና ። (ወን
ሰግድ) ፡ የጌታችን ፡ እግር ፡ በቆመ
በት ፡ እንሰግዳለን ፡ ማለት ፡ ይሆኛ ፡
ቀራንዮ ፡ ናት ፡ መላእክት ፡ በዕ
ለተ ፡ ዐርብ ፡ ከጌታ ፡ ጐን ፡ የፈስ
ሰውን ፡ ደሙን ፡ በጽዋዐ ፡ ብርሃን ፡

2014 04 18

ተቀብለው ፡ ረጭተውታል ፤ ደሙ ፡
በፈሰሰበት ፡ ሁሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ተሠርቶበታልና ፡ እንዲህ ፡
አለ ።

፰ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ ዕረፍ
ትከ ።

አቤቱ ፡ ትሩፋንን ፡ ወደምታሳርፍ
በት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትሩፋ
ንን ፡ ይዘህ ፡ ተነሣ ። እንድም ፡ ምእ
መናንን ፡ ወደምታሳርፍበት ፡ ወደ ፡
መንግሥተ፡ ሰማያት፡ ምእመናንን ፡
ይዘህ ፡ ተነሣ ።

አንተ ፡ ወታቦተ ፡ መቅደስከ ።

አንተ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮንን ፡ ይዘህ ፤
እንድም ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡
ይዘህ ፡ ተነሣ ። እንድም ፡ እመቤታ
ችንን ፤ እንድም ፡ ምእመናንን ፡ ይዘ
ህ ፡ ተነሣ ።

፱ ፡ ካህናቲከ ፡ ይለብሱ ፡ ጽድቀ ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካህና
ቱ ፡ ጽድቅን ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ይለ
ብሳሉ ፡ ማለት ፤ እውነተኞች ፡ ይባ
ላሉ ። እንድም ፡ ምእመናን ፡ ልጅ
ነትን ፡ ያገኛሉ ።

ወጻድቃኒከ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ይትፌሥሑ ።

ትሩፋንም ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይላቸ
ዋል ። እንድም ፡ በቁሙ ፡ ጻድቃን፡
መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብለው ፡
ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፲ ፡ በእንተ ፡ ዳዊት ፡ ገብርከ ።

አገልጋይህ፡ ባለሟልህ፡ ስለሚሆን ፡
ስለ ፡ ዳዊት ፡ ብለህ ።

ወኢትሚጥ ፡ ገጸከ ፡ እመሲሕከ ።

ቀብተህ ፡ ካነገሥከው ፡ ከዘሩባ
ቤል ፡ ገጽ ፡ ረድኤት ፡ ገጽ ፡ ምሕረት
ህን ፡ አትመልሰው ።

፲፩ ፡ መሐለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊት ፡
በጽድቅ ፤ ወኢይኔስሖ ።

እግዚአብሔር ፡ ለዳዊት ፡ በውነት ፡
ማለ ፤ ከማለም ፡ መሐላውን ፡ አያ
ፈርስም ፡ በመሐላው፡ አይጸጸትም ።

እስመ ፡ እምፍሬ ፡ ከርሥከ ፡ እነብር ፡ዲበ ፡
መንበርከ ።

ከባሕርይህ ፡ የተከፈለ ፡ ልጅህ ፡
ክርስቶስን ፡ በዙፋንህ ፡ አስቀምጥ
ልሃለሁ ፡ ብሎ ። እንድም ፡ እንዳስ
ቀምጥልህ ፡ አማንየ ፡ ሕያውየ ፡
ብሎ ፡ ማለ ፤ ምነው ፡ ይህማ ፡ የተ
ነገረ ፡ ለሰሎሞን ፡ አይደለምን ፡
ቢሉ ፡ ለጊዜው፡ ለሰሎሞን ፡ ቢሆን፡
ፍጻሜው ፡ ለጌታ ፡ ነውና ፤ ፍጻሜ
ው ፡ ለጌታ ፡ ያልሆነ ፡ ትንቢት ፡
የለም ። ለጊዜው ፡ ለሰሎሞን ፡ ፍጻ
ሜው ፡ ለጌታ ፡ መሆኑ፡ እንደ፡ምን ፡
ነው ፡ ቢሉ ፡ ሰሎሞን ፡ በጸጋ ፡ በ
ሥጋ ፡ በግድ ፡ የገዛቸውን ፡ ሁሉ ፡
ጌታ ፡ በባሕርይ ፡ በነፍስ ፡ በፈቃድ፡
ገዝቷቸዋልና። ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ሙሴ፡
ነቢየ ፡ ያነሥእ ፡ ለክሙ ፡ እግዚአ



ብሔር ፡ እምአኀዊክሙ ፡ ዘከማየ ፡
ወሎቱ ፡ ስምዕዎ ፡ ብሎ ፡ የተናገ
ረው ፡ ለጊዜው ፡ ለኢያሱ ፡ ቢሆን ፡
ፍጻሜው ፡ ለጌታ፡ እንደ ፡ ሆነ ። እን
ድም ፡ የጌታ ፡ መንግሥት ፡ መታ
ወቂ ፡ ነቢዩ ፡ መንበርከ ፡ እግዚእ ፡
ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ብሎ ፡ በተናገረ
ለት ፡ ነውና ። እንድም ፡ ስምዒ ፡
ወለትየ ፡ ወርእዪ ፡ ወአጽምዒ ፡ እዝ
ነኪ ፡ ብሎ ፡ የትንቢት ፡ ዙፋን ፡
አድርጎ ፡ በተናገረላት ፡ በምእመን፡
ላይ ፡ ነውና ። እንድም ፡ በሥጋ ፡
እነግሥሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ዲበ ፡ መን
በረ ፡ ዳዊት ፡ ትጸንዕ ፡ መንግሥቱ ፡
ለክርስቶስ ፡ እንዲል ። ወዲያውስ ፡
መንግሥት ፡ ከዚህን ፡ ያምራል ፤
ከዳዊት ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡
አብ ፡ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
የሚያድን ፡ የሚገድል ፡ ሁኗልና ።

፲፪ ፡ ለእመ ፡ ዐቀቡ ፡ ደቂቅከ ፡ ሕግየ ።

ልጆችህ ፡ ሕጌን ፡ ቢጠብቁ ።

ወሰምዑኒ ፡ ዘንተ ፡ ዘእሜህሮሙ ።

ይህን ፡ የማስተምራቸውን ፡ ቢቀበ
ሉኝ ።

ወደቂቆሙኒ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ይነብሩ ፡
ዲበ ፡ መንበርከ ።

እርሳቸው፡ ልጆቻቸውም፡ለዘላለም፡
በዙፋንህ ፡ ተቀምጠው ፡ ይኖራሉ።

፲፫ ፡ እስመ፡ኀረያ፡እግዚአብሔር፡ለጽዮን።

እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከ
ሁሉ፡ አገር፡ ለይቶ ፡ መርጧታልና።
እንድም ፡ እመቤታችንን ፡ ለእናት
ነት ፡ መርጧታልና ።

ወአብሃራ ፡ ከመ ፡ ትኩኖ ፡ ማኅደረ ።

ማደሪያው ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ መር
ጧታልና ። እንድም ፡ እመቤታች
ንም ፡ እናቱ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ መር
ጧታልና ። ጣ ፡ ፮ ፡ ፲፯ ።

፲፬ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ምዕራፍየ ፡ ለዓለም ።

ይህቺ ፡ ጽዮን ፤ እንድም ፡ ይህቺ ፡
ማርያም ፡ ለዘላለም ፡ ማደሪያዬ ፡
ናት ፤ ለዘላለም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ፡
ስትባል ፡ የምትኖር ፡ ስለ ፡ ሆነ ።
እንድም ፡ ከሷ ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡
ለዘላለም ፡ የሚኖር ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

ዝየ ፡ አኀድር ፡ እስመ ፡ ኀረይክዋ ።

መርጫታለሁና ፡ እድሪባት ፡ እኖ
ራለሁ ። ኢሳ ፡ ፷፰ ፡ ፲፪ ።

፲፭ ፡ ለዕቤራቲሃ ፡ ባርኮ ፡ እባርኮን ።

ባልቴቶቹን ፡ ፈጽሜ ፡ አከብራቸ
ዋለሁ ፤ አበዛቸዋለሁ ። እንድም ፡
ምእመናንን ፡ ፈጽሜ ፡ አከብራቸ
ዋለሁ ።

ወለነዳያኒሃ ፡ አጸግቦሙ ፡ እክለ ።

በውስጧ ፡ ያሉ ፡ ነዳያንን፡ እኽል ፡
ሰጥቼ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸዋለሁ ። እን
ድም ፡ ነዳያን ፡ ነፍስን ፡ እክለ ፡
ጸጋ ፡ ብዕለ፡ ጸጋ፡ ሰጥቼ ፤ እንድም ፡
ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ልጅነትን ፡
ሰጥቼ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸዋለሁ ።

2014 04 18

፲፮ ፡ ወለካህናቲሃ ፡ አለብሶሙ ፡ ሕይወተ ።

ካህናቱንም ፡ ሕይወትን ፡ እጐናጸፋቸዋለሁ ፡ ማለት ፡ በሕይወት ፡ እንዲኖሩ ፡ አደርጋቸዋለሁ ።

ወጻድቃኒሃ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ይትፌሥሑ ።

ትሩፋን ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። እንድም ፡ ጻድቃን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብለው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፲፯ ፡ ወበህየ ፡ አበቍል ፡ ቀርነ ፡ ለዳዊት ።

ለዳዊት ፡ ዘሩባቤልን ፡ እስነሣለታለሁ ። እንድም ፡ ለዘሩባቤል ፡ ሥልጣንን ፡ እሰጠዋለሁ ።

ወአስተዳሉ ፡ ማኅቶተ ፡ ለመሲሕየ ።

ቀብቼ ፡ ላነገሥሁት ፡ ለዘሩባቤል ፡ መንግሥትን ፡ አዘጋጅለታለሁ ። እንድም ፡ ለዳዊት ፡ ክርስቶስን ፡ እስነሣለታለሁ ። እንድም ፡ ለክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ ሥልጣንን፡ እሰጠዋለሁ ። (ወአስተዳሉ) ፡ ለክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ መንግሥትን ፡ አዘጋጅለታለሁ ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ እንግድነት ። እንድም ፡ ማኅቶት ፡ ዮሐንስን ፡ እስነሣለታለሁ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ማኅቶት ፡ ዘየኀቱ ፡ እንዲል ። ዮሐ ።

ወአለብሶሙ ፡ ኀፍረተ ፡ ለጸላእቱ ።

በባቢሎናውያን ፡ እንድም ፡ በአይሁድ ፡ በመናፍቃን ፡ በኢጋንንት ፡ ግን ፡ ድል ፡ መንሣትን ፡ አመጣባቸዋለሁ ።

ወቦቱ ፡ ይፈሪ ፡ ቅድሳትየ ።

በሱ ፡ ክብሬ፡ ይገለጻል ። እንድም ፡ በሱ ፡ ሚጠት ፡ ይደረጋል ። እንድም እንድነት ፡ ሦስትነት ፡ ይገለጻል ። እንድም ፡ በሱ ፡ የምከበረው ፡ ክብሬ ፡ ሰውን፡ ያፈራልኛል ። ኢሳ፡፶፱፡፫።

መዝሙር ፡ ፻፴፪ ።

፩ ፡ ናሁ ፡ ሠናይ ፡ ወናሁ ፡ አዳም ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ የምእመናንም ፡ ነገር፡ አለበት ። እንሆ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ መልካም ፡ ነው ።

ሶበ ፡ ይሄልዉ ፡ አኀው ፡ ኅቡረ ።

ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ ከፋርስ ፡ ከባቢሎን፡ ወጥተው ፡ ከሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቢኖሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ መልካም ፡ ነው ።

፪ ፡ ከመ ፡ ዕፍረት ፡ ዘይውሕዝ ፡ እምርእሱ ፡ እስከ ፡ ጽሕሙ ።

ከራስ ፡ ጸጕር ፡ ጀምሮ፡ እስከ ፡ ጽሕሙ ፡ ድረስ ፡ የወረደ ፡ ሽቱ ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝ ፡ ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ ከሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ጋራ ፡ እንድነት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቢኖሩ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።

ጽሕሙ ፡ ለአሮን ፡ ዘይወርድ ፡ ዲበ ፡ ኅባኤ ፡ መልበሱ ።

እፍዝዞት ፡ ነበርና ፡ ገለጸው ፡ ጽሕሙ ፡ ያልሁት ፡ ከሽንጕበቱ ፡ እስከ ፡ ተባት ፡ ቍልፍ ፡ ነው፡ከራስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጽሕም ፡ የሚፈስ ፡ የሚወርድ ፡ ሽቱ ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።



፫ ፡ ወከመ ፡ ጠለ ፡ አርሞንኤም ፡ ዘይወርድ ፡ ዲበ ፡ አድባረ ፡ ጽዮን ።

የሰማዩ ፡ ለደጋ ፡ የደጋው ፡ ለቈላ ፡ እንዲተርፍ ፡ የሁለቱም ፡ ነገድ ፡ ትንቢት ፡ ላሥሩ ፡ ነገድ ፡ ተርፏቸው ፡ ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ ከሁለቱ ፡ ነገድ፡ጋራ፡ባንድነት፡በኢየሩሳሌም፡ ቢኖሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ መልካም፡ ነው ። በነፍኒፎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ይትጋባእ ፡ ያዕቆብ ፡ እምጽንሓሖሙ ፡ ለተረፈ ፡ እስራኤል ፡ እንዲል ።

እስመ ፡ ህየ ፡ አዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረከቶ ።

እግዚአብሔር ፡ በረከት ፡ ሥጋን ፡ ከዚያ ፡ አዟልና ።

ወሕይወተ ፡ እምይእዜ ፡ ወስከ ፡ ለዓለም ።

ሕይወትንም ፡ አዟልና ። እንድም ፡ ሕይወት ፡ ይላል ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ፡ምጽአት፡ሲደረግ፡ይኖራልና ። እንድም ፡ (ናሁ ፡ ሠናይ) ፡ እንሆ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ መልካም ፡ ነው ። (ሶበ ፡ ይሄልዉ) ፡ ምእመናንና ፡ አሕዛብ ፡ ከምእመናን ፡ እስራኤል ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ በገነት ፡ ቢኖሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ መልካም ፡ ነው ። (ከመ ፡ ዕፍረት) ፡ ከራስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጽሕም ፡ ድረስ ፡ የወረደ ፡ ሽቱ ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝ ፡ ምእመናን፡ አሕዛብም ፡ ከምእመናን ፡ እስራኤል ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ በገነት ፡ ቢኖሩ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡ (ጽሕሙ ፡ ለአሮን) ፡ ጽሕምም ፡ ያልሁት ፡ ከሽንጕበቱ ፡ እስከ ፡ ተባት ፡ ቍልፍ ፡ ድረስ ፡ የሚወርድ ፡ የአሮን ፡ ጽሕም ፡ ነው ፡ ከራስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጽሕም ፡ ድረስ ፡ የሚወርድ ፡ ሽቱ ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝ ፡ ያም ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።

(ወከመ ፡ ጠለ ፡ አርሞንኤም) ፡ የሰማዩ ፡ ለደጋ ፡ የደጋው ፡ ለቈላ ፡ እንዲተርፍ ፡ የምእመናን ፡ እስራኤልም ፡ ተስፋ ፡ ለምእመናን ፡ አሕዛብ ፡ ተርፏቸው ፡ ምእመናን ፡ አሕዛብ ፡ ከምእመናን ፡ እስራኤል ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ በገነት ፡ ቢኖሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ መልካም ፡ ነው ። (እስመ ፡ ህየ) ፡ እግዚአብሔር ፡ በረከት ፡ ነፍስን ፡ አዟልና ።

ወሕይወተ ፡ እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።

እንዳለፈው ።

2014 04 18

## መዝሙር ፡ ፻፴፫ ።

፩ ፡ ናው ፡ ይባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ ማሕሌት ፡ ዘበበ ፡ መዓርጊሁ ፡ ይላል ። ሌዋዊ ፡ እሱ ፡ ሳይቀምስ ፡ ስንኳን ፡ እሱ ፡ ጠባቂውም ፡ ሳይቀምስ ፤ ለከ፡ ወለዘርዕከ ፡ እሁበከሃ ፡ ለይእቲ ፡ ምድር ፡ ብሎ ፡ ላባቴ ፡ ለአብርሃም ፡ ከሰጠው ፡ ምድር ፡ ያገኙሁት ፡ ፍሬ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወስዶ ፡ ለሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ይሰጠዋል ፤ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ ከብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ኅቤከንና ፡ እንግአኩን ፡ ተፈግሕኩን ፡ መላውን ፤ ከተዘከሮ ፡ ሦስቱን ፡ ዐሥራ ፡ አምስቱን ፡ መዝሙር ፡ ደግሞ ፡ ለሱ ፡ የሚገባውን ፡ አስቀርቶ ፡ ይሰጠዋል ፤ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ እቡን ፡ ዘበሰማያት ፡ ገብቶበታል ፤ ዛሬም ፡ ለቀሳውስት ፡ የሚገባቸውን ፡ ዓሥራቱን ፡ በኩራቱን ፡ ይዞ ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ደግመው ፡ ያስናብቱታል ። እግዚአብሔርን ፡ እንሆ ፡ ያመሰግኑታል ።

ኵሎሙ ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ባለሟሎች ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ሁሉ ።

እለ ፡ ይቀውሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ።

ቤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማገልገል ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ።

ውስተ ፡ ዐጸደ ፡ ቤተ ፡ አምላክነ ።

የፈጣሪያችን ፡ ማደሪያ ፡ የሚሆን ፡ ቅድስቱን ፡ ቅኔ ፡ ማሕሌቱን ፡ በማገልገል ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ።

፪ ፡ በሌሊት ፡ አንሥኡ ፡ እደዊክሙ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ።

በቁሙ ፡ በሌሊት ፤ እንድም ፡ በመከራችሁ ፡ ጊዜ ፡ እደ ፡ ሥጋችሁን ፡ ለመሥዋዕት ፡ እደ ፡ ቃላችሁን ፡ ለጸሎት ፡ እደ ፡ ልቡናችሁን ፡ ለአንክሮ ፡ ለተዘክሮ ፡ አንሡ ።

ወባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

፫ ፡ ይባርከ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምጽዮን ፡

በጽዮን ፡ ሰማያዊት ፡ በጽዮን ፡ ምድራዊት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያክብር ፡ ያብዛ ። እንድም ፡ አጥብቀህ ፡ ያከብራል ፡ ያበዛል ።

ዘገብረ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ።

ሰማይ ፡ ምድርን ፡ የፈጠረ ።

## መዝሙር ፡ ፻፴፬ ።

፩ ፡ ሰብሑ ፡ ለስመ ፡ እግዚአብሔር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ አመስግኑ ፤ ለስሙ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።



ሰብሕዎ ፡ አግብርቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ባለሟሎች ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

፪ ፡ እለ ፡ ይቀውሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ።

እለ ፡ ትቀውሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ቤተ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማገልገል ፡ ጸንታችሁ ፡ የምትኖሩ ።

ውስተ ፡ ዐጸደ ፡ ቤተ ፡ አምላክነ ።

የፈጣሪያችን ፡ ማደሪያ ፡ የሚሆን ፡ ቅድስቱን ፡ ቅኔ ፡ ማሕሌቱን ፡ በማገልገል ፡ ጸንታችሁ ፡ የምትኖሩ ።

፫ ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ኄር ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ቸር ፡ ነውና ፡ አመስግኑት ።

ወዘምሩ ፡ ለስሙ ፡ እስመ ፡ ሠናይ ።

ለስሙ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፤ ስሙ ፡ የተወደደ ፡ ያማረ ፡ ነውና ። እንድም ፡ ስሙን ፡ ማመስገን ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነውና ።

፬ ፡ እስመ ፡ ለያዕቆብ ፡ ኀረዮ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ መርጧቸዋልና ።

ወለእስራኤልኒ ፡ ሎቱ ፡ ለርስቱ ።

ርስቱ ፡ ጉልቱ ፡ የሚሆኑ ፡ ዐሥሩንም፡ ነገድ ፡ መርጧቸዋልና ። እንድም ፡ ርስቱን፡ ኢየሩሳሌምን፡ ለመውረስ፡ መርጧቸዋልና። ኢሳ፡፲፬፡፩።

፭ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ አእመርኩ ፡ ከመ ፡ ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር፡ ገናና ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዐውቂያለሁና ።

ወአምላክነኒ ፡ እምኵሉ ፡ አማልክት ።

ፈጣሪያችንም ፡ በስመ ፡ አማልክት፡ ከሚጠሩ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ነውና ።

ዘፀ ፡ ፲፰ ፡ ፲፩ ። ኤር ፡ ፲ ፡ ፲ ።

፮ ፡ ኵሉ ፡ ዘፈቀደ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ።

እስመ ፡ ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ እምኵሉ ፡ አማልክት ፡ አእመርኩ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ዘፈቀደ ፡ ገብረ ፡ ብለኸ ፡ ግጠም ፤ በስመ ፡ አማልክት ፡ ከሚጠሩ ፡ ሁሉ ፡ አማልክት ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፡ ሁሉ ፡ ገናና፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዐውቂያለሁና ፤ የወደደውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጠረ ። ይህስ ፡ አይደለም ፤ እሱ ፡ ባያውቅለት ፡ ፈጣሪነቱ ፡ ይቀርበታልን ፡ ብሎ ፡ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር፡ ገናና ፡ ነውና ፡ የወደደውን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ፈጠረ ፡ ዐውቃለሁ ።

በሰማይኒ ፡ ወበምድርኒ ።

በሰማይም ፡ በምድርም ፡ በምልአት፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር። እንድም፡ ሰማይን ፡ ምድርን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ።

2014 04 18

በባሕርኒ ፡ ወበኵሉ ፡ ቀላያት ።

በባሕርም ፡ በቀላያትም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ፡ እንድም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ።

፮ ፣ ያፀናት ፡ ደመናተ ፡ እምአጽናፈ ፡ ምድር ።

ደመናትን ፡ ከጽንፈ ፡ ምድር ፡ የፈጠረ ፡ እሱ ፡ ነው ። እንድም ፡ ደመናትን ፡ ፈጠረ ። የደመናትን ፡ ተፈጥሮ ፡ ከዚህ ፡ ይናገራሉ ፡ ከዚህ ፡ እስከ ፡ ብሩህ ፡ ሰማይ ፡ ውሃ ፡ መልቶ ፡ ነበርና ፡ ለይትጋባእ ፡ ማይ ፡ ውስተ ፡ ምእላዲሁ ፡ ብሎ ፡ ከሦስት ፡ ከፍሎታል ፡ ምድርም ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ሠረበው ፡ ጉበት ፡ ሁና ፡ ታየች ፤ ዐሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ነፋሳት ፡ አውጥቶ ፡ አስመታት ፤ ጸጥ ፡ አለች ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከይቡስ ፡ ምድር ፡ ይቡስ ፡ ጢስ ፡ ከርጡብ ፡ ባሕር ፡ ርጡብ ፡ ጢስ ፡ ወጥቶ ፡ አንድ ፡ ደመና ፡ ሁኗል ፤ ወይመውቁ ፡ በፀሓይ ፡ ወይከውኑ ፡ ክልኤሆሙ ፡ አሐደ ፡ ደመና ፡ እንዲል ።

ወገብረ ፡ መብረቀ ፡ ለጊዜ ፡ ዝናም ።

መብረቅን ፡ ለዝናም ፡ ምልክት ፡ አደረገ ። እንድም ፡ ለዝናም ፡ ምልክት ፡ የሚሆን ፡ መብረቅን ፡ ፈጠረ ። የመብረቅ ፡ ተፈጥሮ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ውሃው ፡ በደመና ፡ አይበት ፡ ተቋጥሮ ፡ በነፋስ ፡ ወደሌጋዝ ፡ ተጭኖ ፡ ሲመጣ ፡ ደመናና ፡ ደመና ፡ በተጋጨ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ዐረቂ ፡ ከውሃ ፡ ይወጣል ፡ ወተት ፡ ሲገፋ ፡ ቅቤ ፡ እንዲወጣው ።

ዘያወፅኦሙ ፡ ለነፋሳት ፡ እመዛግብቲሆሙ ።

ነፋሳትን ፡ ከየግምጃቸው ፡ የሚያወጣቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ዓሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነፋሳት ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ መሳክው ፡ አሏቸው ፤ በምሥራቅ ፡ ስድስት ፡ በምዕራብ ፡ ስድስት ፤ ከዚህ ፡ እየመጠነ ፡ የሚያወጣቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። እንድ ፡ ጊዜ ፡ የወጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዓለምን ፡ የሚያሳልፉ ፡ ናቸውና ። ኢዮ ፡ ፴፯ ፡ ፱ ። ኤር ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፰ ።

፰ ፣ ዘቀተለ ፡ ኵሉ ፡ በኵሮሙ ፡ ለግብጽ ።

የግብጻውያንን ፡ በኵር ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ።

እምሰብእ ፡ ወእስከ ፡ እንስሳ ።

እምበኵረ ፡ ሰብእ ፡ እስከ ፡ በኵረ ፡ እንስሳ ፡ በል ፤ ከሰው ፡ በኵር ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ በኵር ፡ ድረስ ።

፱ ፣ ፈነወ ፡ ተአምረ ፡ ወመንክረ ፡ ማእከሌኪ ፡ ግብጽ ።

ግብጽ ፡ ዐሥር ፡ መቅሠፍት ፡ ዐሥራ ፡ እንደኛ ፡ ስጥመት ፡ አመጣብሽ ።

ላዕለ ፡ ፈርዖን ፡ ወላዕለ ፡ አግብርቲሁ ።

በፈርዖን ፡ በሰራዊቱ ፡ ላይ ።



፲ ፣ ዘቀተለ ፡ አሕዛበ ፡ ብዙኃነ ።

ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ ያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ አንድ ፡ አርእስት ።

ወቀተለ ፡ ነገሥተ ፡ ጽኑዓነ ።

ጽኑዓን ፡ የሚሆኑ ፡ ነገሥታቱንም ፡ ያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ሁለት ፡ አርእስት ፤ ለሁለቱም ፡ ያመጣል ።

፲፩ ፣ ለሴዎን ፡ ንጉሠ ፡ አሞሬዎን ።

የአሞሬዎንን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዎንን ፡ ያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ወዐራቱ ፡ ዘኑጺን ፡ ተስዐቱ ፡ በእመት ፡ ይለዋል ፤ ዘጠኝ ፡ ክንድ ፡ የብረት ፡ አልጋ ፡ ነበረው ፤ ጽኑዓን ፡ ላለው ።

ወለዐግ ፡ ንጉሠ ፡ ባሳን ።

የባሳን ፡ ንጉሥ ፡ ዐግንም ፡ ያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ብዙኃን ፡ ላለው ።

ወለኵሎሙ ፡ ነገሥተ ፡ ከነዓን ።

የከነዓን ፡ ነገሥታትንም ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ አሕዛብ ፡ ላለው ።

፲፪ ፣ ወወሀበ ፡ ምድሮሙ ፡ ርስተ ።

ለእስራኤል ፡ ምድራቸውን ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ሰጣቸው ።

ርስተ ፡ እስራኤል ፡ ገብሩ ።

ርስትም ፡ ያልሁት ፡ ያገልጋዩ ፡ የባለሟሉ ፡ የእስራኤል ፡ ርስት ፡ ነው ። ይህችም ፡ ርስት ፡ የሴም ፡ ርስት ፡ ናትና ፤ እለዚህም ፡ የሴም ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ። እንድም ፡ ወወሀቦሙ ፡ ይላል ፡ የኻያ ፡ ዘጠኙ ፡ ነገሥት ፡ ከነዓንን ፡ ርስት ፡ ሰጣቸው ፡ እስራኤልም ፡ ገብሩ ፡ ርስተ ፤ ርስት ፡ አድርገው ፡ ኖሩ ። ኢያ ፡ ፲፭ ፡ ፰፫ ። ፲፫ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ። ኤር ፡ ፴፪ ፡ ፰፪ ። ሚራ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ።

፲፫ ፣ ስምከ ፡ እግዚኦ ፡ ለዓለም ፡ ዓለም ።

አቤቱ ፡ ስምህ ፡ ለዘላለም ፡ ሲመሰገን ፡ ይኖራል ።

ወዝክርከኒ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ።

ስም ፡ አጸራርህም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ሲነገር ፡ ይኖራል ።

፲፬ ፣ እስመ ፡ ይኴንን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቦ ።

እግዚአብሔር ፡ ለወገኖቹ ፡ ይፈርድላቸዋልና ፤ ስጠኝ ፡ ፍጆታ ፡ ብሎ ፡ ዘንግ ፡ መምዘዝ ፡ ማቅናት ፡ አይደለም ፡ የግብር ፡ ሙግት ፡ ነው ።

ወይትናበብ ፡ በእንተ ፡ አግብርቲሁ ።

ለባለሟሎቹ ፡ ለሕዝቡ ፡ ይፈርድላቸዋልና ። ዘዳ ፡ ፴፪ ፡ ፴፯ ።

፲፭ ፣ አማልክቲሆሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ዘወርቅ ፡ ወዘብሩር ።

የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለወገኖቻቸው ፡ እንዳይፈርዱ ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ ሥራ ፡ ናቸው ። እንድም ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ ሥራ ፡ የሚሆኑ ፡ የአሕዛብ ፡ አማልክትስ ፡

ግብረ ፡ እደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

የሰው ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ።

፲፮፤ አፍ፡ቦሙ፡ወኢይነቡ።

የሰው ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ የሚሆኑ ፡ እሊህ ፡ አፍ ፡ አላቸው ፤ አይናገሩም ።

ዐይነ፡ቦሙ፡ወኢይሬእዩ።

ዐይን ፡ ሳላቸው ፡ አያዩም ።

፲፯፤ እዝነ፡ቦሙ፡ወኢይሰምዑ።

ጆሮ ፡ ሳላቸው ፡ አይሰሙም ።

አንፈ፡ቦሙ፡ወኢያጼንዉ።

አፍንጫ ፡ ሳላቸው ፡ አያሸቱም ።

እደ፡ቦሙ፡ወኢይገሱ።

እጅ ፡ አላቸው ፤ አይዳስሱም ።

እግረ፡ቦሙ፡ወኢየሐውሩ።

እግር ፡ ሳላቸው ፡ አይሄዱም ።

ወኢይነቡ፡በጕረዒቶሙ።

በቃላቸው ፡ አይናገሩም ።

ወአልቦ፡መንፈስ፡ውስተ፡አፉሆሙ።

ባንደበታቸው ፡ ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ የለም ።

፲፰፤ ከማሆሙ ፡ ለይኩኑ ፡ ዘገብርዎሙ ፡ እለ፡ገብርዎሙ።

እሳቸውማ ፡ ምን ፡ ባይ ፡ የሠሯቸው ሁሉ ፡ እንደሳቸው ፡ ይሁኑ ።

ወኵሎሙ፡እለ፡ይትአመኑ፡ቦሙ።

ስንኳን ፡ የሠሯቸው ፡ ያመኑባቸው፡ ሁሉ ፡ እንደሳቸው ፡ ይሁኑ ።

፲፱፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ ሐራ ፡ እላንት ፡ ግን ፡ ይህ ፡ እንዲያገኛችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

ቤተ ፡ አሮን ፡ ባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የአሮን ፡ ወገኖች ፡ ካህናት ፡ እግዚ አብሔርን ፡ አመስግኑት ፤ እሊህ ፡ ጻድቃ ፡ እስቴዋ ፡ ናቸው ።

፳፤ ቤተ ፡ ሌዊ ፡ ባርክዎ ፡ ለእግዚአብ ሔር ።

የሌዊ ፡ ወገኖች ፡ መላችሁ ፡ ካህ ናት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግ ኑት ።

እለ ፡ ትፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩት ፡ የምታመልኩት ፡ ነቢያት ፤ ካህ ናት ፤ እንድም ፡ መላችሁ ፡ እስራ ኤል ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግ ኑት ።

፳፩፤ ቡሩክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ ዘየኀድር ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ።

በጽዮን ፡ ሰማያዊት ፡ በጽዮን ፡ ምድ ራዊት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ እግዚአብ ሔር ፤ እንድም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በረድኤት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ እግዚ አብሔር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።



፩፤ ግነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ኄር ። እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ ቸር ፡ ነውና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እብ ፡ ተ ገዙ ፤ እሱን ፡ አመስግኑ ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ሆነ፤ ለዘላለም ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፪፤ ግነዩ ፡ ለአምላከ ፡ አማልክት ።

አማልክትን ፡ ለፈጠረ ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ ወልድ ፡ ተገዙ ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ።

፫፤ ግነዩ ፡ ለእግዚአ ፡ አጋዕዝት ።

የአጋዕዝት ፡ ባለቤት ፡ ለሚሆን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገዙ ፡ ለእጠይቆ ፡ ፫ቱ ፡ እካላት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ግነዩ ፡ ግነዩ ፡ ግነዩ ፡ ብሎ ፡ መላልሶ ፡ ተናገረው ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ።

፬፤ ዘገብረ ፡ ዐቢየ ፡ መንክረ ፡ ባሕቲቱ ።

ብቻውን ፡ ታላቅ ፡ ፍጹም ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ እሱ ፡ ነው ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፭፤ ዘገብረ ፡ ሰማያተ ፡ በጥበቡ ።

ከባሕርዩ ፡ በተገኘ ፡ ዕውቀት ፡ ይህ ፡ ይበቃል ፡ ብሎ ፡ ሰማያትን ፡ በማያት ፡ የፈጠረ ፡ እሱ ፡ ነው ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ።

፮፤ ዘአጽንዓ ፡ ለምድር ፡ ላዕለ ፡ ማይ ።

ምድርን ፡ በውኃ ፡ ላይ ፡ አጽንቶ ፡ የፈጠረ ፡ እሱ ፡ ነው ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፯፤ ዘገብረ ፡ ብርሃናተ ፡ ዐቢያተ ፡ ባሕ ቲቱ ።

ለይኩን ፡ ብሎ ፡ ፍጹም ፡ የሆኑን ፡ ደጋጉን ፡ ብርሃን ፡ የፈጠረ ፡ እሱ ፡ ነው ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ።

፰፤ ፀሐየ ፡ ዘይኤዝዝ ፡ መዓልተ ።

ፀሐይ ፡ በመዓልት ፡ እንዲመግብ ፡ ያደረገ ፡ እሱ ፡ ነው ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፱፤ ወወርኀ ፡ ወከዋክብተ ፡ ዘይኤዝዙ ፡ ሌሊተ ።

ጨረቃና ፡ ከዋክብት ፡ በሌሊት ፡ እንዲመግቡ ፡ ያደረገ ፡ እሱ ፡ ነው ።

2014 04 18

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ።

፲ ፡ [illegible]
ግብጻውያንን ፡ ከበኵሮቻቸው ፡ ጋራ ፡ ያጠፋቸው ፡ እሱ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፲፩ ፡ ወአውፅኦሙ ፡ ለእስራኤል ፡ እማእከሎሙ ።
እንተ ፡ ማእከሎሙም ፡ ይላል ፡ እስራኤልን ፡ ግን ፡ ከመካከላቸው ፡ ያወጣቸው ፡ እሱ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፲፪ ፡ በእድ ፡ ጽንዕት ፡ ወበመዝራዕት ፡ ልዑላት ።
በጸናች ፡ መቅሠፍት ፡ ዓሥረኛ ፡ ሞተ ፡ በኵር ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ።

፲፫ ፡ ዘነፈቃ ፡ ለባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ወከፈላ ።
ኤርትራን ፡ ከመሐት ፡ ከምድት ፡ ከፍሎ ፡ ጸጥ ፡ ያደረጋት ፡ እሱ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፲፬ ፡ ወአውፅኦሙ ፡ ለእስራኤል ፡ እንተ ፡ ማእከላ ።
እማእከላም ፡ ይላል ፡ እስራኤልን ፡ ግን ፡ በመካከሏ ፡ ያወጣቸው ፡ እሱ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ።

፲፭ ፡ [illegible] ፡ ለፈርዖን ፡ [illegible] ፡ ውስተ ፡ ባሕረ ፡ ኤርትራ ።
ፈርዖንን ፡ ከሰራዊቱ ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ያሰጠመው ፡ እሱ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፲፮ ፡ [illegible] ፡ ለሕዝቡ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ።
ወገኖቹ ፡ እስራኤልን ፡ ወደ ፡ ገዳመ ፡ ሲና ፡ ያወጣቸው ፡ እሱ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ።

፲፯ ፡ [illegible] ፡ ነገሥት ፡ [illegible] ።
ወገን ፡ ከሆኑ ፡ [illegible] ፡ ያፈለሰ ፡ እሱ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፲፰ ፡ [illegible] ፡ ነገሥተ ፡ [illegible] ።
ኃያ ፡ ዝነኞችን ፡ ነገሥታት ፡ ያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ።



እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፲፱ ፡ [illegible] ፡ ነገሥተ ፡ ጽኑዓነ ።
ጽኑዓን ፡ ነገሥታትን ፡ ያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፳ ፡ ለሴዎን ፡ ንጉሠ ፡ አሞሬዎን ።
የአሞሬዎን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዎንን ፡ ያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ።

፳፩ ፡ ወለዐግ ፡ ንጉሠ ፡ ባሳን ።
የባሳን ፡ ንጉሥ ፡ ዐግንም ፡ ያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፳፪ ፡ ወወሀበ ፡ ምድሮሙ ፡ ርስተ ።
ወወሀቦሙ ፡ ይላል ፡ ምድራቸውን ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ሰጣቸው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ።

፳፫ ፡ ርስተ ፡ ለእስራኤል ፡ ገብሩ ።
እስራኤልም ፡ ርስት ፡ አድርገው ፡ ኖሩ ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ም [illegible] ነው ፡ በቸርነቱ ፡ [illegible] እንጂ ፡ [illegible] ፡ እሱ ፡ [illegible] ነውና ።

፳፬ ፡ እስመ ፡ [illegible] ፡ እግዚአብሔር ፡ [illegible] ።
እግዚአብሔር ፡ በመከራችን ፡ ጊዜ ፡ በቸርነቱ ፡ አሰበን ፡ ማለቱ ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ።

፳፭ ፡ [illegible] ።
ከጠላቶቻችንም ፡ እጅ ፡ አድኖ ናልና ፡ ማለቱ ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፳፮ ፡ [illegible] ።
ለሥጋዊ ፡ ለደማዊ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ምግብን ፡ የሚሰጥ ፡ እሱ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ።

፳፯ ፡ [illegible] ።
ሰማይን ፡ ለፈጠረ ፡ አምላክ ፡ ተገዙ ።
እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።
ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቸርነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ [illegible]

2014 04 18

ን ፡ ቢቋጥሩት ፡ ኀይ ፡ ሰባት ፡ ይሆ
ናል ፡ ሦስቱ ፡ የተመሰገኘ ፡ ኀይ ፡
አራቱ ፡ ያመሰገኘ ፡ ወለዘሰሎሙ ፡
ነገሥት ፡ ከነዓንን ፡ የጨመረ ፡ እን
ደሆን ፡ ኀይ ፡ ስምንት ፡ ይሆናል ፡
አራቱ ፡ ያራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ ኀይ ፡
አራቱ ፡ የኀይ ፡ አራቱ ፡ ካህናት ፡
ሰማይ ፡ ምሳሌ ።

## መዝሙር ፡ ፻፴፯ ።

፩ ፡ ውስተ ፡ አፍላገ ፡ ባቢሎን ፡ ሀየ ፡ ነበ
ርነ ፡ ወበከይነ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ ትሩ
ፋን ፡ ተማርከው ፡ ባቢሎን ፡ ሲወ
ርዱ ፡ ዘመድ ፡ ከዘመዱ ፡ ወንድ ፡
ልጅ ፡ ካባቱ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ከናቷ ፡
ሳይለያዩ ፡ ባንድነት ፡ ወርደዋል ፡
ከባቢሎን ፡ ወንዝ ፡ ሲደርሱ ፡ በሚ
ለያዩበት ፡ ጊዜ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡
ለባሪያ ፡ መስንቆ ፡ ምን ፡ ነው ፡
የቆመውን ፡ መቍረጥ ፡ የተኛውን ፡
መፍለጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብለው ፡
በገናቸውን ፡ ከአኻያ ፡ ላይ ፡ ሰቅ
ለው ፡ ተሊቃቅሰው ፡ ተለያይተ
ዋል ፡ ያገራችን ፡ ነገሥታት ፡ ዘም
ተው ፡ ሲመለሱ ፡ ካገራቸው ፡ ወ
ንዝ ፡ ሲደርሱ ፡ የመባ ፡ አርደው ፡
የጸሪ ፡ አውርደው ፡ በልተው ፡
ጠጥተው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አድር
ገው ፡ ከከተማቸው ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡
መሳፍንቱ ፡ መኳንንቱ ፡ ጎያላኑ ፡
የማረኳቸውን ፡ እየነጠሉ ፡ ይዘው ፡
ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሲሄዱ ፡ አልቅሰው ፡
እንዲለያዩ ፡ በባቢሎን ፡ ወንዝ ፡ ተቀ
ምጠን ፡ አለቀስን ። እንድም ፡ በሲ
እል ፡ ወንዝ ፡ ተቀምጠን ፡ አለቀስን ።

ሶበ ፡ ተዘከርናየ ፡ ለጽዮን ።

ኢየሩሳሌምን ፡ እንድም ፡ ገነትን ፡
ባሰብናት ፡ ጊዜ ።

፪ ፡ ውስተ ፡ ኲሓቲሃ ፡ ሰቀልነ ፡ እንዚራ
ቲነ ።

እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለባሪያ ፡ በገና ፡
ምን ፡ ነው ፡ የቆመውን ፡ መቍረጥ ፡
የተኛውን ፡ መፍለጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ብለን ፡ በገናችንን ፡ ከአኻያ ፡ ሰቀ
ልን ። እንድም ፡ ተድላ ፡ ነፍሳችንን ፡
በኢየሩሳሌም ፡ እንድም ፡ በዕፀ ፡
በለስ ፡ ምክንያት ፡ ልጅነታችንን ፡
ተውን ። እንድም ፡ ተድላ ፡ ነፍሳች
ንን ፡ በገነት ፡ ተውን ።

፫ ፡ እስመ ፡ በሀየ ፡ ተስእሉነ ፡ እለ ፡ ፄወ
ዉነ ፡ ነገረ ፡ ማሕሌት ።

የማረኩን ፡ ሰዎች ፡ በባቢሎን ፡ የም
ስጋና ፡ ነገር ፡ ጠይቀውናልና ፡ ጋላን ፡
ሻንቅላን ፡ ማርከው ፡ ወስደው ፡
የሀገርክን ፡ ዘፈን ፡ እየዘፈንህ ፡
አጫውተን ፡ እንዲሉት ። እንድም ፡
ድል ፡ የነሡን ፡ አጋንንት ፡ በሲኦል ፡
የምስጋና ፡ ቃል ፡ ጠይቀውናልና ።



ወእለሂ ፡ ይወስዱነ ፡ ይቤሉነ ፡ ሕልዩ ፡
ለነ ፡ እምሓልዩ ፡ ለጽዮን ።

ማርከው ፡ ባቢሎን ፡ የሚወስዱን ፡
ሰዎች ፡ አስቀድሞ ፡ በኢየሩሳሌም ፡
ታመሰግኑት ፡ የነበረውን ፡ ምስጋና ፡
ስውረው ፡ አመስግኑ ፡ ብለውናልና ፤
ሰው ፡ ሊሰርቅ ፡ ሊቀማ ፡ ሲሄድ ፡
ወንድሜ ፡ መንገድ ፡ አስቢያለሁ
ና ፡ አትርሳኝ ፡ ብሎ ፡ እንዲሄድ ።
እንድም ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ ወደ ፡
ገሃነም ፡ የሚያወርዱን ፡ አጋንንት ፡
በገነት ፡ የምታመሰግኑትን ፡ ምስ
ጋና ፡ አመስግኑ ፡ ብለውናልና ፡
ሰቀልነ ። እሁን ፡ ለአጋንንት ፡ ምስ
ጋና ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ የሚረ
ባቸው ፡ የሚጠቅማቸው ፡ ሁኖ ፡
አይደለም ፤ ሰው ፡ ሊሰርቅ ፡ ሊቀማ ፡
ሲሄድ ፡ ከመነኰሲ ፡ ሄዶ ፡ አባቴ ፡
አትርሳኝ ፡ ብሎ ፡ እቡን ፡ ዘበስማ
ያት ፡ ተቀብሎ ፡ እንዲሄድ ።

፬ ፡ እፎ ፡ ነሐሊ ፡ ማሕሌተ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ በምድር ፡ ነኪር ።

ከአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዩ ፡
በሚሆን ፡ በባቢሎን ፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ ምስጋና ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እናመ
ስግናለን ፡ ብለን ፡ ሰቀልነ ። እንድ
ም ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እናመስግናለን ።
እንድም ፡ ልጅነት ፡ በሌለበት ፡
በሲኦል ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እናመስግ
ናለን ፡ አልን ።

፭ ፡ እመሰ ፡ ረሳዕኩኪ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለት
ርስዐኒ ፡ የማንየ ።

ኢየሩሳሌም ፡ እንዲህስ ፡ ዘንግቼሽ ፡
እንደ ፡ ሆን ፡ ሥልጣኔ ፡ ትለየኝ ፡
መለየትማ ፡ ተለይታው ፡ የለምን ፡
እንደ ፡ ተለየችኝ ፡ ትቅር ፡ ሲል ፡
ነው ። እንድም ፡ ገነት ፡ እንዲህስ ፡
ዘንግቼሽ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ልጅነቴ ፡
ትለየኝ ፤ መለየትማ ፡ ተለይታው ፡
የለምን ፡ ቢሉ ፡ እንደ ፡ ተለየችኝ ፡
ትቅር ፡ ሲል ፡ ነው ።

፮ ፡ ወይጥጋዕ ፡ ልሳንየ ፡ በጕርዔየ ፡ ለእመ ፡
ኢተዘከርኩኪ ።

እንዲህስ ፡ ያላሰብሁሽ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡
እንደበቴ ፡ ከጕረሮዬ ፡ ጋራ ፡ ይጣጋ ።
ባንደበቴ ፡ ያለ ፡ ጕረሮዬ ፡ በጽምእ ፡
ይጣጋ ። እንድም ፡ በጽምእ ፡ ነፍስ ፡
ይያዝ ።

ወለእመ ፡ ኢበጻዕኩ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ በቀ
ዳሚ ፡ ትፍሥሕትየ ።

አስቀድሞ ፡ ሳልማርክ ፡ ከኢየሩሳ
ሌም ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ሳለሁ ፡
ይህን ፡ ብታደርግልኝ ፡ ይህን ፡ እሰ
ጣለሁ ፡ ብዬ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ እል
ተሳልሁ ፡ እንደ ፡ ሆን ። እንድም ፡ ስባ
ቱን ፡ ዓመት ፡ በገነት ፡ ሳለሁ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አላቀረብሁ ፡
እንደ ፡ ሆን ፡ ይጥጋዕ ፡ ልሳንየ ።

፯ ፡ ተዘከሮሙ ፡ እግዚኦ ፡ ለደቂቀ ፡ ኤዶ
ም ፡ በዕለተ ፡ ኢየሩሳሌም ።

እቤቱ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በታጣችበት ፡

2014 04 18

ቀን ፡ የኤዶምን ፡ ልጆች ፡ በመዓት
ህ ፡ አስባቸው ። ኤዶም ፡ የኤዶም ፡
የፈቱው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ፈታዊ ፡
ለመብልዕ ፡ እንዲሉ ። እንደም ፡ ነ
ነት ፡ በታማችበት ፡ ቀን ፡ የሏያብ
ሉቡን ፡ ወገኖች ፡ በመዓትህ ፡ አስ
በቸው ።

[illegible]

ወራችን ፡ ከሰልፍኛዋ ፡ ድረስ ፡
ተወራግበት ፡ ተሥማራበት ፡ የሚ
ሉ ፡ እሊህን ፡ እንደም ፡ ሥልጣና
ችን ፡ አፍአዊ ፡ ውሳጣዊ ፡ ትሩፋ
ታን ፡ እስከ ፡ ማስለቀቅ ፡ ድረስ ፡ የ
ሚሉ ፡ እሊህን ፡ አጥፋቸው ።

፱ ፡ ወለተ ፡ ባቢሎን ፡ ጎስቋት ።

ጉስቁላ ፡ የባቢሎን ፡ ልጅ ፡ እንደ
ም ፡ ወራዳ ፡ የገሃነም ፡ ልጅ ።

ብፁዕ ፡ ዘይትፈደየኪ ፡ በቀል ፡ ተበቀልክነ ።

ተበቅሎ ፡ የሚያጠፋሽ ፡ ዘሩባቤል ፡
ንጉድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። እንደም ፡
እንደ ፡ ተበቀልሽን ፡ ተበቅሎ ፡
የሚያጠፋሽ ፡ እንደም ፡ እንቺስ ፡
የሚበቀሽን ፡ ያሽል ፡ ተበቀልሽን ፡
ነበር ፡ ተበቅሎ ፡ የሚያጠፋሽ ፡ ዘሩ
ባቤል ፡ ንጉድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። ተ
በቀልክነ ፡ ተበቀልክኒ ፡ ይላል ።
[illegible]

፲ ፡ ብፁዕ ፡ ዘያጸንዖሙ ፡ ለደቂቅኪ ፡ ወይነፅሮሙ ፡ ውስተ ፡ ኰኵሕ ።

ልጆችሽን ፡ ይዞ ፡ በጭንግጫ ፡ ላይ ፡
የሚፈጫቸው ፡ የሚፈጠርቃቸው ፡
ዘሩባቤል ፡ ንጉድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።
እንደም ፡ ወገኖችሽ ፡ ኢጋንንትን ፡
ይዞ ፡ በመስቀል ፡ በጥምቀት ፡ ድል ፡
የሚነሣቸው ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉድ ፡
ክቡር ፡ ነው ።

## መዝሙር ፡ ፻፴፯ ።

፩ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ በኵሉ ፡ ልብየ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ አቤ
ቱ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ እገዛልኻ
ለሁ ።

እስመ ፡ ሰማዕከ ፡ ዘኵሉ ፡ ቃለ ፡ አፉየ ።

ጥንደበቴ ፡ የለመንኩህን ፡ የሊመና
ዬን ፡ ቃል ፡ ሰምተኸኛልና ።

በቅድመ ፡ መላእክቲከ ፡ እዜምር ፡ ለከ ።

ባለቆቹ ፡ ፊት ፡ ላንተ ፡ ምስጋና ፡
አቀርባለሁ ።

፪ ፡ ወእሰግድ ፡ ውስተ ፡ ጽርሐ ፡ መቅደስከ ።

መመስገኛህ ፡ በምትሆን ፡ በኢየሩ
ሳሌም ፡ እሰግድልሃለሁ ።

ወእገኒ ፡ ለስምከ ።

ለስምህም ፡ እገዛለሁ ።



በምሕረትከ ፡ ወበጽድቅከ ።

በይቅርታህ ፡ በቸርነትህ ።

እስመ ፡ አዕበይከ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ስመከ ፡ ቅዱሰ ።

ጽንዕ ፡ ክሃሊ ፡ የሚሆን ፡ ስምህን ፡
ባሪቱ ፡ መንእሀን ፡ እንዲመሰገን ፡
አድርገሃልና። ኢሳ ፡ ፲፪ ፡ ፩ ።

፫ ፡ እመ ፡ ዕለተ ፡ እጼውዓከ ፡ ፍጡነ ፡ ስምዐኒ ።

በለመንኩህ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥነህ ፡ ልመ
ናዬን ፡ ሰማኸኝ ።

ብዙኀ ፡ አጽናዕካ ፡ ለነፍስየ ፡ በኀይልከ ።

ሰውነቴን ፡ በከሃሊነትህ ፡ ፈጽመህ፡
አጸናኻት ።

፬ ፡ ይገንዩ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ ኵሎሙ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር ።

የማመሰግንህ ፡ የምገዛልህ ፡ እኔ ፡
ብቻ ፡ አይደለሁም ፡ ባሪቱ ፡ መኳ
ንን ፡ ያሉ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ያመ
ሰግኑሃል ።

እስመ ፡ ሰምዑ ፡ ዘኵሉ ፡ ቃለ ፡ አፉከ ።

ጥንደበትህ ፡ የሠራኸውን ፡ ሕግ ፡
ሠርተዋል ፡ ጠብቀዋልና ።

፭ ፡ ወየሐልዩ ፡ በሰብሐተ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ በሚመሰገንበት ፡
በጥንተ ፡ ምስጋና ፡ ያመሰግናሉ ።

እስመ ፡ ዐቢይ ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ (ሥራ) ፡
ፍጹም ፡ ነውና ።

፮ ፡ እስመ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይሬኢ ፡ ለትሑታን ።

በጽርሑ ፡ አርያም ፡ የሚኖር ፡ ል
ዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በአንቀር
ጸስ ፡ የሚያረጋውን ፡ ያያልና ።

ወልዑላነ ፡ እምርሑቅ ፡ የአምር ።

የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እስቀ
ድሞ ፡ ሳይሠራ ፡ ያውቀዋል ።

፯ ፡ እመኒ ፡ ሖርኩ ፡ ማእከለ ፡ ምንዳቤ ፡ አንተ ፡ ታሐይወኒ ።

ጸዋትወ ፡ መከራ ፡ ወጺ ፡ አስበት ፡
ወጺ ፡ ባቢሎን ፡ ምንም ፡ ብወርድ ፡
ከመከራው ፡ አንተ ፡ ታድነኛለህ ።
እንደም ፡ ምክንያተ ፡ መከራ ፡ የሚ
ሆን ፡ ብልጣሶር ፡ ወጸለበት ፡ ወጺ ፡
ባቢሎን ፡ ምንም ፡ ብወርድ ፡ ከብ
ልጣሶር ፡ አንተ ፡ ታድነኛለህ ።

ላዕለ ፡ መዓተ ፡ ጸላእትየ ፡ ሰፋሕከ ፡ እደዊከ ።

ሰፋሕከም ፡ ይላል ፡ በእሕዛብ ፡ በፈ
ረድህባቸው ፡ ጊዜ ፡ እጄን ፡ ዘር
ግቼ ፡ እንድማርካቸው ፡ አደረግኸ
ኝ ። እንደም ፡ በኔ ፡ ፈርደህ ፡ አሕ
ዛብን ፡ ባመጣብኝ ፡ ጊዜ ፡ እጄ
ን ፡ ዘርግቼ ፡ እንድማርካ ፡ አደረግ
ኸኝ ። እንደም ፡ እጄን ፡ ዘርግቼ ፡
የዛሬን ፡ እንኳ ፡ አውሎኝ ፡ አልኋ
ቸው ።

ወአድኀነኒ ፡ የማንከ ።

ኋላ ፡ ግን ፡ ሥልጣንህ ፡ አዳነኝ ።

2014 04 18

፯ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ይትበቀል ፡ ሊተ ።

እኔ ፡ እቸገርላለሁ ፡ እንጂ ፡ እግዚ
አብሔርስ ፡ ይፈርድልኛል ፤ ተበ
ቅሎ ፡ ጠላቴን ፡ ያጠፋልኛል ።

እግዚኦ ፡ ግብአከ ፡ ለዓለም ።

አቤቱ ፡ ይቅርታህ ፡ ለዘላለም ፡ ሲደ
ረግ ፡ ይኖራልና ፤ ይትበቀል ፡ ሊተ ።
አንድም ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፤

እግዚኦ ፡ ተግባረ ፡ እደዊከ ፡ ኢትትሀየይ ።

አቤቱ ፡ የእጅህ ፡ የቃልህ ፡ ፍጥረት ፡
የምንሆን ፡ እኛን ፡ ቸል ፡ አትበለን ።
ኢሳ ፡ ፷፬ ፡ ፰ ።

መዝሙር ፡ ፻፴፰ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ አመከርከኒ ፡ ወአእመርከኒ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናገርታል ፤ የም
እመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ። አቤቱ ፡
ሰባ ፡ ዘመን ፡ በመከራ ፡ ፈተንኸኝ ፡
መረመርከኝ ፤ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡
በሚጠት ፡ ዐወቅኸኝ ። አንድም ፡
አምስት ፡ ሺሕ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፡ በመከራ ፡ ነፍስ ፡ ፈተንኸኝ ፡
መረመርከኝ ፤ ካምስት ፡ ሺሕ ፡ አም
ስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በሚ
ጠተ ፡ ነፍስ ፡ ዐወቅኸኝ ።

፪ ፡ አንተ ፡ ተአምር ፡ ንብረትየ ፡ ወተን
ሥኦትየ ።

ንብረትየ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ መኖሬን ፤
ወተንሥኦትየ ፤ ከኢየሩሳሌም ፡ መነ
ሣቴን ። አንድም ፡ በባቢሎን ፡ መኖ
ሬን ፡ ከባቢሎን ፡ መነሣቴን ። አን
ድም ፡ በኀጢአት ፡ መኖሬን ፡ በን
ስሓ ፡ መመለሴን ፡ ታውቀዋለህ ።
አንድም ፡ በገነት ፡ መኖሬን ፤ ከገ
ነት ፡ መነሣቴን ። አንድም ፡ በሲ
እል ፡ መኖሬን ፤ ከሲእል ፡ መነሣ
ቴን ። አንድም ፡ በኀጢአት ፡ መኖ
ሬን ፤ በንስሓ ፡ መመለሴን ፡ ታው
ቀዋለህ ።

ወአንተ ፡ ተአምር ፡ ኵሎ ፡ ኀሊና ፡ ልብየ ፡
እምርሑቅ ።

የልቡናዬን ፡ ሐሳብ ፡ ሁሉ ፡ ሳይታ
ሰብ ፡ አስቀድሞ ፡ አንተ ፡ ታውቀ
ዋለህ ። ውእቱሰ ፡ የእምር ፡ ኀሊና ፡
ሰብእ ፡ እምቅድመ ፡ ኩነታ ፡ እን
ዲል ። ኢሳ ፡ ፷፮ ፡ ፲፰ ። ማራ ፡ ፺፪ ፡ ፲፰ ፲፱ ።

፫ ፡ ፍናትየ ፡ ወአሠርየ ፡ አንተ ፡ ተኀሥሥ ።

ፍናት ፡ አሠር ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ግብ
ሬን ፡ አስቀድመህ ፡ አንተ ፡ ወሰ
ንህ ።

ወኵሎ ፡ ፍናውየ ፡ አንተ ፡ አቅደምከ ፡ አእ
ምሮ ።

ሥራዬን ፡ ሁሉ ፡ አስቀድመህ ፡
ዐወቅህ ። እምቅድመ ፡ ይፍጥሮ ፡
ለአዳም ፡ ውእቱ ፡ የእምር ፡ ግብሮ ፡
እንዲል ።



፬ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ቃል ፡ ዐመፃ ፡ ውስተ ፡
ልሳንየ ።

ባንደበቴ ፡ የዐመፅ ፡ ቃል ፡ እንደ
ሌለ ፡ ማለት ፤ በእጁ ፡ ነፍስ ፡ መግ
ደል ፡ በቃሉ ፡ መበደል ፡ በልቡናዬ ፡
ቂም ፡ በቀል ፡ እንዳለመኖሩ ፡
መጠን ።

ናሁ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ አእመርከ ፡ ኵሎ ፡
ዘቀዳሚ ፡ ወዘደኃሪ ።

ዘቀዳሚ ፡ በኢየሩሳሌም ፤ ወዘደ
ኃሪ ፡ በባቢሎን ። አንድም ፡ ዘቀ
ዳሚ ፡ በባቢሎን ፤ ወዘደኃሪ ፡ በኢ
የሩሳሌም ። አንድም ፡ ዘቀዳሚ ፡
በኀጢአት ፡ ወዘደኃሪ ፡ በንስሓ ፡
መኖሬን ፡ ታውቀዋለህ ። ኢዮ ፡ ፲ ፡ ፭ ።
አንድም ፡ ዘቀዳሚ ፡ በገነት ፤ ወ
ዘደኃሪ ፡ በሲኦል ፤ ዘቀዳሚ ፡ በሲ
ኦል ፤ ወዘደኃሪ ፡ በገነት ። አንድም ፡
ዘቀዳሚ ፡ በኀጢአት ፤ ወዘደኃሪ ፡
በንስሓ ፡ መመለሴን ፡ ታውቀዋ
ለህ ።

፭ ፡ አንተ ፡ ፈጠርከኒ ፡ ወወደይከ ፡ እዴከ ፡
ላዕሌየ ።

በሥጋ ፡ ፈጥረህ ፡ በነፍስ ፡ አእምሮ ፡
ጠባይዕ ፡ አሳደርህብኝ ። ኢዮ ፡ ፲ ፡ ፰ ።

፮ ፡ ተነክረ ፡ አእምሮትከ ፡ በላዕሌየ ።

በሥጋ ፡ ፈጥረህ ፡ በነፍስ ፡ አእምሮ ፡
ጠባይዕ ፡ ብታሳድርብኝ ። ሀልዎት
ህን ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ ባዕድ ፡
ሆነብኝ ፡ ማለት ፤ የሀኬት ፡ ነው ።

ጸንዐት ፡ ወኢይክል ፡ ምስሌሃ ።

ጽንዐት ፡ ብየ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ሀልዎ
ትህ ፡ ጸናችብኝ ፤ እሷን ፡ መርምሮ ፡
ማወቅ ፡ ተሳነኝ ።

፯ ፡ አይቴ ፡ አሐውር ፡ እመንፈስከ ።

በሥጋ ፡ ፈጥረህ ፡ በነፍስ ፡ አእምሮ ፡
ጠባይዕ ፡ ብታሳድርብኝ ፡ ሀልዎ
ትህን ፡ መርምሬ ፡ አላውቅ ፡ ብዬ ፡
ማለቴ ፡ ከሥልጣንህ ፡ ወዴት ፡
ወዴት ፡ እደርሳለሁ ።

ወአይቴ ፡ እጐይይ ፡ እምቅድመ ፡ ገጽከ ።

ከፊትህ ፡ ወዴት ፡ እደርሳለሁ ።
ኢሳ ፡ ፲ ፡ ፫ ።

፰ ፡ እመሂ ፡ ዐረጉ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡
ህየኒ ፡ አንተ ።

ወደ ፡ ሰማይ ፡ ብወጣ ፡ አንተ ፡ ከዚ
ያም ፡ አለህ ።

ወእመኒ ፡ ወረድኩ ፡ ውስተ ፡ ቀላይ ፡ ህየኒ ፡
ሀሎከ ።

ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ብወርድም ፡
ከዚያም ፡ አለህ ። ኢዮ ፡ ፲፩ ፡ ፰ ።

፱ ፡ ወእመኒ ፡ ነሣእኩ ፡ ክንፈ ፡ ከመ ፡ ንስር ።

ማብቀል ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡
ንስር ፡ ክንፍ ፡ ባበቅል ፡ ቅሉ ፤

ወሰረርኩ ፡ እስከ ፡ ማኅለቅቱ ፡ ባሕር ።

እስከ ፡ አድማስ ፡ ብደርስ ።

፲ ፡ ህየኒ ፡ እዴከ ፡ ትመርሐኒ ፡ ወታነብረኒ ፡
የማንከ ።

እደ ፡ የማንከ ፡ ትመርሐኒ ፡ ወታነብ

ረኒ ፡ የማገኘ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፤ ከዚ
ያ ፡ መርታ ፡ የምታደርሰኝ ፡ ይሀች ፡
ሥልጣንህ ፡ አይደለችምን ።

፲፮ ፡ ወእቤ ፡ ጽልመትኑ ፡ እንጋ ፡ ኬደኒ ።

በሥጋ ፡ ፈጥረህ ፡ በነፍስ ፡ አእም
ሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ብታሳድርብኝ ፡ ሀል
ዎትህን ፡ መርምሬ ፡ አላውቅ ፡ ማ
ለቴ ፡ እንዲሀን ፡ ድንቍርና ፡ ጸንቶ
ብኛልን ። እንድም ፡ (አንተ ፡ ፈጠ
ርከኒ) ፡ በሥጋ ፡ በነፍስ ፡ ፈጥረህ ፡
ሕግ ፡ ሠራኸልኝ ። (ተንከረ) ፡ በሥ
ጋ ፡ በነፍስ ፡ ፈጥረኸ ፡ ሕግ ፡ ብ
ትሠራልኝ ፡ ሕግኸን ፡ መጠበቅ ፡
ባዕድ ፡ ሆነብኝ ፤ የሀኬት ፡ ነው ።
(ጸንዐተኒ) ፡ ሕግኸ ፡ ጸናችብኝ ፤
እፂን ፡ መጠበቅ ፡ ተሳነኝ ። (አይ
ቴኑ) ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ፈጥረህ ፡
ሕግ ፡ ብትሠራልኝ ፡ ሕግህንማ ፡
አልጠብቅ ፡ ብዬ ፡ ከሥልጣንህ ፡
ወጥቼ ፡ ወዴት ፡ እደርሳለሁ ። እ
ንድም ፡ (አንተ ፡ ፈጠርከኒ) ፡ በነ
ፍስ ፡ በሥጋ ፡ ፈጥረህ ፡ ሕግ ፡ ሠራ
ህልኝ ። (ተንከረ) ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡
ፈጥረህ ፡ ሕግ ፡ ብትሠራልኝ ፡ ሕግ
ህን ፡ መጠበቁ ፡ ታወቀልኝ ። (ጸን
ዐተኒ) ፡ ሕግህ ፡ ጸናችልኝ ፤ ከርሷ ፡
ጋራ ፡ ሳለሁ ፡ ባቢሎናዊ ፡ ድል ፡
አይነሣኝም ። (አይቴኑ) ፡ በነፍስ ፡
በሥጋ ፡ ፈጥረህ ፡ ሕግ ፡ ብትሠራ
ልኝ ፡ ሕግህንማ ፡ አልጠብቅ ፡ ብዬ ፡
እል ፡ ዘንድ ፡ ከሥልጣንህ ፡ ወጥ
ቼ ፡ ወዴት ፡ እደርሳለሁ ።

እንድም ፡ (አንተ ፡ ፈጠርከኒ) ፡ በ
ሥጋ ፡ ፈጥረህ ፡ በነፍስ ፡ አእምሮ ፡
ጠባይዕ ፡ አሳደርህብኝ ። (ተንከረ) ፡
በሥጋ ፡ ፈጥረህ ፡ በነፍስ ፡ አእምሮ ፡
ጠባይዕ ፡ ብታሳድርብኝ ፡ ባሕርይ
ህን ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ ባዕድ ፡
ሆነብኝ ፡ ማለት ፤ የስኢን ፡ ነው ።
(ጸንዐተኒ) ፡ ባሕርይህ ፡ ጸናችብኝ ፤
እርሷን ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ ተነ
ሣኝ ። (አይቴኑ) ፡ በሥጋ ፡ ፈጥረህ ፡
በነፍስ ፡ አእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ብታ
ሳድርብኝ ፡ ባሕርይህን ፡ መርምሬ ፡
ዐውቃለሁ ፡ እልማ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
ባሕርይህ ፡ እልፍኝ ፡ ማን ፡ አሳል
ፎኝ ። (ወእይቴ) ፡ እንዳለፈው ፡ (ወ
እቤ ፡ ጽልመትኑ) ፡ በሥጋ ፡ በነ
ፍስ ፡ ፈጥረህ ፡ ሕግ ፡ ብትሠራልኝ ፡
ሕግህን ፡ አላውቅም ፡ እል ፡ ዘንድ ፤
እንድም ፡ አላውቅም ፡ ማለቴ ፡ እን
ዲህን ፡ ድንቍርና ፡ ጸንቶብኛልን ።
እንድም ፡ በሥጋ ፡ ፈጥረህ ፡ በነፍስ ፡
አእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ብታሳድርብኝ ፡
ባሕርይህን ፡ መርምሬ ፡ ዐውቃለሁ ፡
እል ፡ ዘንድ ፡ እንዲህን ፡ ድንቍ
ርና ፡ ጸንቶብኛልን ።

ወሌሊትኒ ፡ ብሩህ ፡ ውስተ ፡ ትፍሥሕትየ ።

ሌሊት ፡ ኀጢአቴ ፡ ባንተ ፡ በደስ
ታዬ ፡ ዘንድ ፡ የበራ ፡ ነው ፤ አንተ ፡
ታውቀዋለህ ፤ አይሰወርህም ፤ ስው
ሮ ፡ ነውና ፡ የሚሠራው ፡ ኀጢአ
ቱን ፡ ሌሊት ፡ አለው ። እንድም ፡



ሌሊት ፡ ጊዋዌ ፡ ባንተ ፡ በደስታዬ ፡
ዘንድ ፡ ብሩህ ፡ ነው ፤ ሳያውቅ ፡
ተደርጎበታልና ፡ ጊዋዌን ፡ ሌሊት ፡
አለው ። እንድም ፡ ሕግ ፡ መጠበቁ ፡
ባንተ ፡ በደስታዬ ፡ ዘንድ ፡ ብሩህ ፡
ነው ፡ ማለት ፤ ታውቀዋለህ ፤ ስው
ሮ ፡ ነውና ፡ የሚሠራው ፡ ሕጉን ፡
ሌሊት ፡ አለው ። እንድም ፡ ሌሊት ፡
ባሕርይህ ፡ ባንተ ፡ በደስታዬ ፡ ዘ
ንድ ፡ ብሩህ ፡ ነው ፡ ታውቀዋለህ ።
ሌሊት ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፤ ብሩህ ፡
በርሱ ፡ ዘንድ ።

፲፪ ፡ እስመ ፡ ጽልመትኒ ፡ ኢይጸልም ፡ በኀ
ቤከ ።

ባንተ ፡ በጌታዬ ፡ ዘንድ ፡ አለማ
ወቅ ፡ የለምና ።

ወሌሊትኒ ፡ ብሩህ ፡ ከመ ፡ መዓልት ።

ከመ ፡ መዓልት ፡ ለማለት ፡ ደገ
መው ።

በአምጣነ ፡ ጽልመታ ፡ ከማሁ ፡ ብርሃና ።

በአምጣነ ፡ ተከብቶታ ፡ ከማሁ ፡
ተከሥቶታ ፤ በኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡
መሰወሯ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ መገለጿ ፡
ነውና ። እንድም ፡ በአምጣነ ፡ ተዔ
ውዎታ ፡ ከማሁ ፡ ተመይጦታ ፤
በኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ መማረኳ ፡
ባንተ ፡ ዘንድ ፡ መመለሷ ፡ ነውና ።
እንድም ፡ በባሕርይ ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡
እንደ ፡ መሰወሯ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡
መገለጿ ፡ ነውና ።

፲፫ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ፈጠርከ ፡ ቍልያትየ ፡
እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ዕውቀትን ፡ ፈጥ
ረህልኛልና ፤ እቤ ፡ ላለው ። እንድ ፡
አንተ ፡ ዕውቀት ፡ ፈጥረህልኛልና ።

ወተወከፍከኒ ፡ ከመ ፡ እአምር ።

ሁሉን ፡ መርምሬ ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡
በረድኤት ፡ ተቀብለኸኛልና ፤ እቤ ፡
ላለው ። እንድም ፡ እንዲህ ፡ ዐውቅ ፡
ዘንድ ፡ በረድኤት ፡ ተቀበልኸኝ ።

፲፬ ፡ እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ግሩመ ፡
ተሰባሕከ ።

አቤቱ ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡
ተመስግነኻልና ፡ እገዛልኻለሁ ።

መንክር ፡ ግብርከ ፡ ወነፍስየ ፡ ትጤይቆ ፡ ጥቀ ።

ሥራህ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፤ ሰውነቴም ፡
ፈጽማ ፡ ትረዳዋለች ።

፲፭ ፡ ወኢይትኀባእ ፡ እምኔከ ፡ አዕፅምትየ ፡
ዘገበርከ ፡ በኅቡእ ።

በሥጋዬ ፡ ሰውረህ ፡ የፈጠርኸው ፡
ዐጥንቴ ፡ ካንተ ፡ አይሰወርም ፤ ታ
ውቀዋለህ ። እንድም ፡ ነፍሴ ፡ ካ
ንተ ፡ አትሰወርም ፤ ታውቃታለህ ።
ዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ኀሥሥ ፡ ፈውስ ፡
ለሥጋከ ፡ ወሥራየ ፡ ለአዕፅምቲከ ፡
እንዲል ።

ወአካልየ ፡ በመትሕተ ፡ ምድር ።

በሥራዬ ፡ ተሰውራ ፡ ያለች ፡ ነፍ
ሴም ፡ እንድም ፡ በመቃብር ፡ ያለች ፡
ሥጋዬ ፡ አትሰወርህም ።.

2014 04 18

፲፩ ፤ ወዐቢ ፡ ገበርኩ ፡ ርእያ ፡ አዕይንቲከ ።
የሠራሁትንም ፡ ኀጢአት ፡ ዐይና
ችኸ ፡ አዩ ፡ ማለት ፤ ታውቀዋለህ ።

ወኵሉ ፡ ይጸሐፍ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፍከ ።
የሠራሁት ፡ ኀጢአት ፡ ሁሉ ፡ በመ
ጽሐፍህ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ። እንድም፡
ፍጥረት ፡ ሁሉ ፤ እንድም ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ የተ
ጻፈ ፡ እንዳይጠፋ ፡ አይጠፋም ።
ወኵሉ ፡ ዘገብረ ፡ ይኀልቁ ፡ እ
ንዲል ፤ ስንኳንስ ፡ እሱ ፡ ሽከላ ፡
ሠሪ ፡ እንኳ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ይህን ፡
ሠራሁ ፡ ብላ ፡ ትናገራለች ።

መዓልተ ፡ ይትፈጠሩ ፡ ወኢይሄሉ ፡ እንከ ፡
አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ።
ኀጣውእ ፡ በሌሊትም ፡ በመዓል
ትም ፡ በዝተው ፡ ይሠራሉ ፤ ከኒህ ፡
ከኀጣውእ ፡ አንዱ ፡ አይሰወርህም ፤
ታውቀዋለህ ። እንድም ፡ ሰዎች ፡
በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ይፈጠ
ራሉ ፤ ከኒህ ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ስንኳ፡
አይሰወርህም ፤ ታውቀዋለህ ። እን
ድም ፡ ሐዋርያት ፡ በሐዲስ ፡ ተፈ
ጥሮ ፡ ይፈጠራሉ ፡ ከርሳቸው ፡ እን
ዱ ፡ ይሁዳ ፡ አይሰወርህም ፤ ትለየ
ዋለህ ። እንድም ፡ መላእክት ፡ በብ
ሉይ ፡ ተፈጥሮ ፡ ይፈጠራሉ ፤ ከር
ሳቸው ፡ አንዱ ፡ ዲያብሎስ ፡ አይ
ሰወርህም ፤ ትለየዋለህ ።

፲፮ ፤ ወበኀቤየሰ ፡ ፈድፋደ ፡ ክቡራን ፡ አዕ
ርክቲከ ፡ እግዚኦ ።
ትሩፍ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ የመ
ጣብህ ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ እንጂ፡
ባታከብር ፡ ነው ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፤ የሌላውን ፡ አላውቅም ፡ እንጂ ፡
በኔስ ፡ ዘንድ ፡ አቤቱ ፡ ባለሟሎችህ፡
ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ፈጽሞ ፡ ንኡዳን፡
ክቡራን ፡ ናቸው ።

ወፈድፋደ ፡ ጸንዑ ፡ እምቀደምቶሙ ።
አስቀድመው ፡ ከነበሩ ፡ አበው ፡ ይ
ልቅ ፡ እኒህ ፡ ፈጽመው ፡ ጸኑ ።

፲፰ ፤ እኋልቆሙ ፡ እምኆጻ ፡ ይበዝኁ ።
እቈጥራቸዋለሁ ፡ ቍጥራቸው ፡ ከባ
ሕር ፡ አሸዋ ፡ ይበዛል ፡ ማለት ፤ ዐበ
ይተ ፡ ነቢያት ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡
ከደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ ከሐ
ዋርያት፡ ሰብዓ፡ አርድእት፡ ከሰብዓ ፡
አርድእት ፡ ሊቃውንት ፡ ከሊቃው
ንት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ የሚ
ነሡ ፡ ምእመናን ፡ ይበዛሉና ።

ተንሣእኩኒ ፡ ወዓዲ ፡ ሀሎኩ ፡ ምስሌከ ።
ከኢየሩሳሌም ፡ ወጥቼ ፡ ወደ ፡ ባቢ
ሎን ፡ ወረድሁ ፤ በባቢሎን ፡ በተስ
ፋው ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ እኖራለሁ ።
እንድም ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥቼ ፡ ወደ ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ተመለስኩ ፤ በኢየሩሳ
ሌም ፡ ፡ ድኤት ፡ ካንተ ፡ ጋራ፡ እኖ
ራለሁ ።

፲፱ ፤ እመሰ፡ ቀተልከሙ፡ ለኃጥኣን፡እግዚኦ ፡
አቤቱ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ ብታጠፋ
ቸው ፡

ዕድው ፡ ደም ፡ ተገሐሡ ፡ እምኔየ ።
የሰውን ፡ ደም ፡ የሚያፈሱ ፡ እለ ፡
አጅም ፡ ኮንታ ፡ ራቁልኝ ።

፳ ፤ እስመ ፡ ይዜኀሩ ፡ በኀሊናሆሙ ።
እለ ፡ አጅም ፡ ኮንታ ፡ በአሕዛብ ፡
ይመካሉና ።

ወይነሥእዎን ፡ ለአህጉሪከ ፡ በከንቱ ።
ኢየሩሳሌምን ፡ ጣዖት ፡ እያመለኩ ፡
ወርሰዋት ፡ ይኖራሉ ። እንድም ፡
(እመሰ ፡ ቀተልከሙ) ፡ አቤቱ ፡ ባቢ
ሎናውያንን ፡ እታጥፋቸው ፡ እንጂ፡
ብታጠፋቸውስ ፡ (ዕድው ፡ ደም) ፡
እነ፡ አጅም፡ ኮንታ፡ ባልራቁልኝም ፡
ነበር ። (እስመ ፡ ይዜኀሩ) ፡ እለ ፡ አ
ጅም ፡ ኮንታ ፡ በአሕዛብ ፡ ይመኩ ፡
ነበርና ። (ወይነሥእዎን) ፡ ሀገርህ ፡
ባቢሎንን፡ ጣዖት ፡ እያመለኩ ፡ ወር
ሰዋት ፡ ይኖራሉና ፡ በተፈጥሮ ፡ ገን
ዘቡ ፡ ናትና ፡ አህጉሪከ ፡ አለ ።

፳፩ ፤ አኮኑ ፡ ጸላእተከ ፡ ጸላእኩ ፡ እግዚኦ ።
አስፈቺውን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ አድርግ።
አቤቱ ፡ ጠላቶችህን ፡ ጠልቻለሁና።

ወተመነስውኩ ፡ በእንተ ፡ ፀርከ ።
በጠላቶችህ፡ ምክንያት፡ ባለመከራ ፡
ሆኛለሁና ።

፳፪ ፤ ፍጹመ ፡ ጽልአ ፡ ጸላእክዎሙ ።
ፈጽሜ ፡ ጠልቻቸዋለሁና ።

ወኮኑኒ ፡ ፀርየ ።
እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፡ ጠላት ፡
ሆኑኝ ። እንድም ፡ ቢጠሉት ፡ እይ
ጠላን ፡ እለ ፡ ብትጠላቸው ፡ እንጂ ፡
ነው፡ ትለኝ፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንዲያው፡
ሳልጠላቸው ፡ በግፍ ፡ ጠላት ፡ ሆ
ኑኝ ።

፳፫ ፤ ፍትነኒ ፡ እግዚኦ ፡ ወአመክር ፡ ልብየ።
በኀቤየሰ ፡ ፈድፋደ ፡ ክቡራን ፡
ብሎ ፡ ነበርና ፡ ትሩፍ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡
መከራ ፡ የመጣብህ ፡ ኀጢአት ፡
ብትሠራ ፡ አይደለም ፡ ትለኝ ፡ እን
ደሆን ፤ ኀጢአት ፡ እሠራ ፡ ጣዖት ፡
አመልክም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኢየሩሳ
ሌም ፡ እውጥተህ ፡ ፍተነኝ ፡ መር
ምረኝ ፡ ሐሰቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

አመክረኒ ፡ ወርኢ ፡ ፍናውየ ።
ፍተነኝ ፤ ሥራዬን ፡ እይ ፤ ተመል
ከት ።

፳፬ ፤ ወርኢ ፡ እመ ፡ ተረክበ ፡ ዐመፃ ፡ በላ
ዕሌየ ።
በኔ ፡ ዐመፃ ፡ ይገኝብኝ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ እይ ፤ ተመልከት ።

ወምርሐኒ ፡ ፍኖተ ፡ ዘለዓለም ።
ለዘላለም ፡ ሲነገር ፡ የሚኖር ፡ የኢ
የሩሳሌምን ፡ መንገድ ፡ መርተህ ፡
አውጣኝ ። እንድም ፡ ሕግህን ፡ አስ
ተምረኝ ።

2014 04 18

## መዝሙር ፡ ፻፴፱ ።

፩ ፡ አድኅነኒ ፡ እግዚኦ ፡ እምብእሲ ፡ እኩይ ።

በሳአል ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተና
ግሮታል ፡ አቤቱ ፡ ከክፉ ፡ ሰው ፡
ከሳኦል ፡ አድነኝ ።

ወእምሰብእ ፡ ዐማፂ ፡ ባልሐኒ ።

ዐመፀኞች ፡ ከሚሆኑ ፡ ከሰራዊ
ቱም ፡ አድነኝ ።

፪ ፡ እለ ፡ ዐመፃ ፡ መከሩ ፡ በልቦሙ ።

በልባቸው ፡ አስበው ፡ ዐመፅን ፡
ከሚመክሩ ።

ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ይሬውፉኒ ፡ ይቅትሉኒ ።

ይገድሉኝ ፡ ዘንድ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡
ይከቡኛል ። አንድም ፡ ይገድሉኝ ፡
ዘንድ ፡ ከሚመክሩብኝ ፡ ከንጉሡ ፡
ከሰራዊቱ ፡ አድነኝ ።

፫ ፡ ወአብልኁ ፡ ልሳኖሙ ፡ ከመ ፡ አርዌ ፡
ምድር ።

እንደበታቸውን ፡ እንደ ፡ እርዌ ፡
ምድር ፡ ከሚያፋጥኑ ።

ሐምዝ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ታሕተ ፡ ከናፍሪ
ሆሙ ።

ካንደበታቸው ፡ በታች ፡ የእባብ ፡
መርዝ ፡ አለ ፡ (ያለ) ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።
ያዕ ፡ ፫ ፡ ፰ ።

፬ ፡ ዕቀበኒ ፡ እግዚኦ ፡ እምእደ ፡ ኃጥእን ።

አቤቱ ፡ ከኃጥአን ፡ ወገኖች ፡ እጅ ፡
ጠብቀኝ ።

ወእምብእሲ ፡ ዐማፂ ፡ አድኅነኒ ።

ዐመፀኛ ፡ ከሚሆን ፡ ከሳኦል ፡ አድ
ነኝ ።

እለ ፡ መከሩ ፡ ያዕቅጹ ፡ መከየድየ ።

መከየዴ ፡ ልቡናዬን ፡ ያሰናክሉኝ ፡
ዘንድ ፡ የመከሩብኝን ። አንድም ፡
ሰውነቴን ፡ አንድም ፡ ወገኖቼን ፡
ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ከመከሩብኝ ፡ አድ
ነኝ ።

፭ ፡ ወኀብኡ ፡ ሊተ ፡ መሥገርተ ፡ ዕቡያን ።

እምዕቡያን ፡ እለ ፡ ኀብኡ ፡ ሊተ ፡
መሥገርተ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ጦር ፡
ከሸመቁብኝ ፡ ምክር ፡ ከመከሩብኝ ።

ወሰተሩ ፡ አሕባለ ፡ መሣግር ፡ ለእገርየ ።

በወገኖቼ ፡ አንድም ፡ በሕዋሳቴ ፡ ም
ክር ፡ መከሩብኝ ፤ ጦር ፡ ሸመቁብኝ ።

ወአንበሩ ፡ ዕቅፍተ ፡ ውስተ ፡ ፍኖትየ ።

በመንገዴ ፡ ዕንቅፋት ፡ አስቀመጡ
ብኝ ፤ ማለት ፡ ጦር ፡ ሸመቁብኝ ፤
ምክር ፡ መከሩብኝ ። አንድም ፡ ዕቅ
ፍት ፡ ትኩኖ ፡ ብለው ፡ ሚልኮልን ፡
ሰጡኝ ፡ እሷን ፡ ብሎ ፡ ሲገባ ፡ ሲ
ወጣ ፡ እንገድለዋለን ፡ ብለው ።

፮ ፡ ወእቤሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላኪየ ፡
አንተ ።

እግዚአብሔርን ፡ ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡
ነህ ፡ አልሁት ።



ወአጽምዐኒ ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ።

እብሎ ፡ አጽምዐኒ ፤ የልመናዬን ፡
ነገር ፡ ስማኝ ፡ አልሁት ፤ እለዋለሁ ።

፯ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚኦ ፡ ኀይለ ፡ መድኀኒ
ትየ ።

የድኅነቴን ፡ ኀይል ፡ የምታደርግል
ኝ ፡ አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ አጽምዐኒ ።
አንድም ፡ የድኅነቴ ፡ ኀይል ፡ የም
ትሆን ፡ አቤቱ ፡

ሰወርከኒ ፡ በዕለተ ፡ ቀትል ፡ መልዕልተ ፡
ርእስየ ።

በሰልፍ ፡ ቀን ፡ በኔ ፡ አድረህ ፡ አዳ
ንኸኝ ። አንድም ፡ እንደ ፡ ድባብ ፡
ሆነህ ፡ አዳንኸኝ ። ያ ፡ ከዋዕየ ፡ ፀ
ሓይ ፡ እንዲያድን ፡ ከተጣለ ፡ ጠጠ
ር ፡ ከተወረወረ ፡ ጦር ፡ አዳንኸኝ ።

፰ ፡ ኢትመጥወኒ ፡ እግዚኦ ፡ እምፍትወ
ትየ ፡ ለኃጥእን ።

አቤቱ ፡ ወድጄ ፡ የሠራሁት ፡ ኀጢ
አት ፡ ከመገለጽ ፡ የተነሣ ፡ ለነሳ
ኦል ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጠኝ ።

ተማከሩ ፡ ላዕሌየ ፡ ወኢትኅድገኒ ፡ ከመ ፡
ኢይዘኀሩ ።

በኔ ፡ መክረውብኛልና ፡ እኔን ፡ ገድ
ለው ፡ እንዳይታበዩ ፡ በመከራው ፡
አትጣለኝ ።

፱ ፡ ርእሰ ፡ ማዕገቶሙ ።

ከበው ፡ እንግደለው ፡ ማለታቸው ።

ወጻማ ፡ ከናፍሪሆሙ ፡ ይድፍኖሙ ።

ባንደበታቸው ፡ እንሰረው ፡ ብለው ፡
መምከራቸው ፡ መቅሠፍት ፡ ታም
ጣባቸው ።

፲ ፡ ወይደቅ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ አፍሓመ ፡ እሳት ።

ትደቅ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በርሳቸው ፡
ጽኑ ፡ መቅሠፍት ፡ ትምጣባቸው ።

ወትነፅቆሙ ፡ ውስተ ፡ ምድር ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይህች ፡ መቅሠፍት ፡
ታጥፋቸው ።

በምንዳቤ ፡ ከመ ፡ ኢይክሀሉ ፡ ቀዊመ ።

መከራ ፡ በሚቀበሉበት ፡ ጊዜ ፡
አግባ ፡ መልስ ፡ ብሎ ፡ መዋጋት ፡
እንዳይቻላቸው ። አንድም ፡ ሐዩወ ፡
ይላል ፤ በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ በሕይ
ወት ፡ መኖር ፡ እንዳይቻላቸው ።

፲፩ ፡ ብእሲ ፡ ነባቢ ፡ ኢያረትዕ ፡ በዲበ ፡
ምድር ።

መቀባጠርን ፡ የሚያበዛ ፡ ሰው ፡ በ
ዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገሩን ፤ አንድም ፡
መንግሥቱን ፡ አያቀናም ።

ወለብእሲ ፡ ዐማፂ ፡ ትንዕዎ ፡ እኪት ፡ ለአማስኖ ።

ዐመፀኛን ፡ ሰው ፡ ለማጥፋት ፡ መቅ
ሠፍት ፡ ታድነዋለች ። ኢዮ ፡ ፲፭ ፡ ፪ ።
፲፰ ፡ ፳፱ ።

፲፪ ፡ አእመርኩ ፡ ከመ ፡ ይገብር ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ኵነኔ ፡ ለነዳያን ፡ ወፍትሐ ፡ ለምስኪናን ።

ኵነኔ ፡ ወፍትሐ ፡ ለነዳያን ፡ ወለም
ስኪናን ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፤ እግዚአ
ብሔር ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ለድኾ

2014 04 18

ች ፡ ለጦም ፡ አዳሮችም ፡ ፍርድን ፡ እንዲፈርድ ፡ በወቅሁ ።

፲፱ ፡ ወባሕቱ ፡ ጻድቃን ፡ ይገንዩ ፡ ለስምከ ።

ነገር ፡ ግን ፡ የኔ ፡ ወገኖች ፡ ለስምህ ፡ ይገዛሉ ።

ወይነብሩ ፡ ራትዓን ፡ ቅድመ ፡ ገጽከ ።

ቅንነትም ፡ ያላቸው ፡ የኔ ፡ ወገኖች ፡ በባለሟልነት ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ።

## መዝሙር ፡ ፶ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ ጸራሕኩ ፡ ኀቤከ ፡ ስምዐኒ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ አቤቱ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ መልሼ ፡ ለመንሁ ፤ አንተም ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ። እንድም ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለምኘለሁና ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወአጽምዕ ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ፡ ዘጸራሕኩ ፡ ኀቤከ ።

ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ የለመንሁትን ፡ የልመናዬን ፡ ነገር ፡ ስማኝ ።

፪ ፡ ተወከፈኒ ፡ ጸሎትየ ፡ ከመ ፡ ዕጣን ፡ በቅድሜከ ።

የአሮንን ፡ መሥዋዕት ፡ የዘካርያስን ፡ ዕጣን ፡ ወደህ ፡ እንደ ፡ ተቀበልክ ፡ የኔንም ፡ ጸሎት ፡ ወደህ ፡ ተቀበለኝ ።

አንሥኦ ፡ እደውየ ፡ መሥዋዕተ ፡ ሠርክ ።

እጄ ፡ ልቡናዬ ፡ ጸሎተ ፡ ሠርክን ፡ ይዟልና ። ሉቃ ፡ ፳ ፡ ፩ ።

፫ ፡ ሢም ፡ እግዚኦ ፡ ዐቃቤ ፡ ለአፉየ ።

አቤቱ ፡ ላንደበቴ ፡ ጠባቂ ፡ ሹምለት ፡ ማለት ፤ አርምሞ ፡ ትዕግሥትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርግለት ።

ወመዓጸ ፡ ዘዐቅም ፡ ለከናፍርየ ።

ያውም ፡ ልክ ፡ መጠን ፡ ያለው ፡ አርምሞ ፡ ትዕግሥት ፡ ነው ፤ እጅግም ፡ ዝምታ ፡ ደንቆሮ ፡ ያሰኛል ። እጅግም ፡ መናገር ፡ ቀባጣሪ ፡ ፍየል ፡ አፍ ፡ ያሰኛልና ። ሢራ ፡ ፳፱ ፡ ፳፮ ።

፬ ፡ ኢትሚጦ ፡ ለልብየ ፡ ውስተ ፡ ነገር ፡ እኩይ ።

ልቡናዬን ፡ ወደ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ኀጢአት ፡ ወደ ፡ ጣዖት ፡ አትመልሰው ።

ለአመክንዮ ፡ ምክንያት ፡ ለኀጢአት ።

ኢትሚጦ ፡ ለአመክንዮ ፡ ኢትሚጦ ፡ ለኀጢአት ፡ ኢትሜጦ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፡ ገበርተ ፡ ዐመፃ ፡ ይላል ፤ ኀጢአት ፡ ለመሥራት ፡ ምክንያት ፡ ለማግኘት ፡ ወደ ፡ ኀጢአት ፡ አትመልሰው ።

ምስለ ፡ ሰብእ ፡ ገበርተ ፡ ዐመፃ ።

ዐመፅን ፡ ከሚሠሩ ፡ ከባቢሎናውያን ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ባቢሎናውያን ።



ወኢይትኀበር ፡ ምስለ ፡ ኅሩያኒሆሙ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ያገኘህ ፡ ጣዖት ፡ ብታመልክ ፡ አይደለምን ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከተመረጡት ፡ ከካህናት ፡ ጣዖቱ ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ የለኝም ፤ አንድ ፡ አልሆንሁም ።

፭ ፡ ገሥጸኒ ፡ በጽድቅ ፡ ወተዛለፈኒ ፡ በምሕረት ።

እንዳችም ፡ የምግባር ፡ ሕጸጽ ፡ ቢኖርብኝ ፡ በቸርነትህ ፡ ዝለፈኝ ፡ ገሥጸኝ ።

ወቅብዐ ፡ ኃጥአንስ ፡ ኢይትቀባዕ ፡ ርእስየ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ያገኘህ ፡ (የመጣብህ) ፡ የአሕዛብን ፡ ገንዘብ ፡ ብትበላ ፡ አይደለምን ፡ ትለኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የአሕዛብን ፡ ገንዘብ ፡ አልበላም ።

እስመ ፡ ዓዲ ፡ ጸሎትየኒ ፡ ከመ ፡ ኢትግበሎሙ ።

እንደ ፡ ገና ፡ የምጸልየው ፡ ጸሎት ፡ ይቅር ፡ እንዳትላቸው ፡ ነውና ። ኤር ፡ ፲ ፡ ፳፭ ።

፮ ፡ ተሰጥሙ ፡ በጥቃ ፡ ኰኵሕ ፡ ጽኑዓኒሆሙ ።

ኀያላኑ ፡ በጽኑ ፡ መቅሠፍት ፡ ጠፉ ። እንድም ፡ አጠገብ ፡ ባለ ፡ ጦር ፡ ጠፉ ። በቂሮስና ፡ በዳርዮስ ፡ ጠፉ ። እንድም ፡ ከመ ፡ ዘበጥቃ ፡ ኰኵሕ ፡ ይላል ፤ ከገደል ፡ ሥር ፡ እንዳለ ፡ ተክል ፡ ጠፉ ። ያን ፡ እየታደሰ ፡ ይዞት ፡ እንዲወርድ ፡ እንደዚያ ፡ ጠፉ ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፲፱ ።

ስምዑኒ ፡ ቃልየ ፡ እስመ ፡ ተከሀለኒ ።

ነገር ፡ አስማምቶ ፡ አስወድዶ ፡ አሻሽሎ ፡ መናገር ፡ ተችሎኛልና ፡ ነገሬን ፡ ተቀበሉኝ ። (ታ) ፡ ለዳርዮስ ፡ ሦስት ፡ ባለሟሎች ፡ ነበሩት ፤ አስማምተን ፡ አስወድደን ፡ ተናግረን ፡ ነገሩ ፡ የተወደደለት ፡ ባለሟል ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ መከረው ፡ አንዱ ፡ ወይን ፡ ይመውእ ፡ አንዱ ፡ ንጉሥ ፡ ይመውእ ፡ አንዱ ፡ ብእሲት ፡ ትመውእ ፡ ወእምኵሉስ ፡ ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብኳል ፤ ይህን ፡ የተናገረ ፡ ዘሩባቤል ፡ ነው ። ይህን ፡ ጽፈው ፡ ከራስጌው ፡ አኑረዋል ፤ ያን ፡ አይቶ ፡ እንዲህ ፡ ያደረገ ፡ ማነው ፡ አለ ። እለ ፡ ዘሩባቤል ፡ ናቸው ፡ አሉት ፤ አስጠርቶ ፡ አንተ ፡ ወይን ፡ ይመውእ ፡ ያልከው ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ አለ ፤ ጌታዬ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ወይን ፡ የጠጣ ፡ ሰው ፡ ደካማው ፡ ብርቱ ፡ ንፉግ ፡ ለጋስ ፡ ይሆናል ፤ ይህን ፡ ያደረገ ፡ አሸናፊ ፡ አይባልምን ፡ አለው ።

አንተስ ፡ ንጉሥ ፡ ይመውእ ፡ ያልከው ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ አለው ፤ ንጉሥ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ ይህን ፡ ዓለም ፡ እርሶ ፡ ቈፍሮ ፡ ውሃውን ፡ ገድቦ ፡ ዓሣውን ፡ አውጥቶ ፡ የሚመገበው ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ሰውን ፡ የሚገዛ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፤ ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ ንጉሥ ፡ አሸናፊ ፡ አይባልምን ፡ አለው ።

2014 04 18

እንተስ ፡ ብእሲት ፡ ትመውእ ፡ ያል ከው ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ አለው ፤ ነገሩ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ አይለወጥም ፡ ንጉሥ ፡ መልክ ፡ መልካም ፡ ሴት ፡ ያገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በገንዘቤ ፡ እዘ ገርበት ፡ ብሎ ፡ ያመለጥናታል ፡ ይኸ ውም ፡ ሊታወቅ ፡ አርጤምስ ፡ ወለ ተ ፡ በጥሪቴ ፡ ትጸፍዕ ፡ ገጽከ ፡ ወትነ ሥእ ፡ አክሊለከ ፡ ወትወድዮ ፡ ውስ ተ ፡ ርእሳ ፡ ፊትህን ፡ ጸፍታ ፡ ዘውድ ህን ፡ አንሥታ ፡ ከራሷ ፡ ላይ ፡ ትደፋ ዋለች ፡ ትቈጣታለህ ፡ ትኵረፋለች ፡ መልሰህ ፡ ታቈላምጣታለህ ፡ እን ዲህ ፡ የምታደርግ ፡ ሴት ፡ አሸናፊ ፡ አትባልምን ፡ አለው ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሏል ፡ ጽድቅ ፡ ይመውእ ፡ ያልከውሳ ፡ አለው ፡ ሰው ፡ በሐሰት ፡ ሲከራከር ፡ ይውላል ፡ የማታ ፡ ማታ ፡ እውነት ፡ የያዘ ፡ ይረታ ፡ እንተም ፡ መንግሥቴን ፡ እጅ ፡ ያደ ረገልኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስራኤልን ፡ አወጣቸዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ፡ መንግሥቱን ፡ እጅ ፡ አድርጎልሃል ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ መንግሥት ፡ የሚገባኝ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ እኔን ፡ አን ግሠህ ፡ እስራኤልን ፡ አታወጣቸው ምን ፡ አለው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ወጥተዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

፯ ፤ ከመ ፡ ግዙፈ ፡ ምድር ፡ ተሠጥቁ ፡ በዲበ ፡ ምድር ።

ከመ ፡ ግዙፍ ፡ ምድር ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ዋልካ ፡ እንደ ፡ ወፍራም ፡ መሬት ፡ ተሠነጣጠቁ ፡ ማለት ፤ ያ ፡ በሚያዝያ ፡ በግንቦት ፡ እንዲሠነጣጠቅ ፡ በሬ ፡ የሚውጥ ፡ እንዲሆን ፡ ጠፉ ።

ወተዘርወ ፡ አዕፅምቲሆሙ ፡ በኀበ ፡ ሲኦል ።

ወገናቸው ፡ አንድም ፡ ሕዋሳታ ቸው ፡ በመቃብር ፡ ጠፋ ፡ አንድም ፡ ነፍሳቸው ፡ በሲኦል ፡ ጠፋች ።

፰ ፤ እስመ ፡ ኀቤከ ፡ እግዚኦ ፡ አዕይንትየ ።

አቤቱ ፡ ዐይኖቼ ፡ ወዳንተ ፡ ይመ ለከታሉ ፡ እንደ ፡ ባለቀጠሮ ፤ ያ ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ይመጣል ፡ እያለ ፡ እንዲመለከት ፡ እኔም ፡ ከዛሬ ፡ ነገ ፡ ከዘንድሮ ፡ ከርሞ ፡ ታወጣኛለህ ፡ በማለት ።

ብከ ፡ ተወከልኩ ፡ ኢታውፅእ ፡ ለነፍስየ ።

ባንተ ፡ አምኛለሁና ፡ ነፍሴን ፡ ከሥ ጋዬ ፡ አትለያት ። አንድም ፡ ሰው ነቴን ፡ ከባቢሎን ፡ ሳታወጣት ፡ እንዳትቀር ፡ ባንተ ፡ አመንሁ ።

፱ ፤ ዕቀበኒ ፡ እመሥገርት ፡ እንተ ፡ ኀብኡ ፡ ሊተ ።

ሰውረው ፡ ከመከሩብኝ ፡ ምክር ፡ ከሸመቁብኝ ፡ ጦር ፡ አድነኝ ።

ወእማዕቀፎሙ ፡ ለገበርተ ፡ ዐመፃ ፤

ወእማዕቅፎሙም ፡ ይላል ፤ ዐመፅን ፡ ከሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ጦር ፡ ምክር ፡ አድነኝ ።

ለይደቁ ፡ ውስተ ፡ መሥገርቶሙ ፡ ኃጥኣን ።

ኃጥኣን ፡ ባቢሎናውያን ፡ በመከ



ሩት ፡ ምክር ፡ በሸመቁት ፡ ጦር ፡ ይጥቁ ።

እስከ ፡ አኀልፍ ፡ አነ ፡ ባሕቲትየ ።

እኔ ፡ ብቻዬን ፡ እስከወጣ ፡ ድረስ ፤ እኔ ፡ ከመጣሁ ፡ በኋላ ፡ ይቅር ፤ በላቸው ፡ ማለት ፡ አይደለም ፤ እኔ ፡ ልዳን ፡ እነሱ ፡ ይጥፉ ፡ ሲል ፡ ነው ። ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመ ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ። አሜን ።

መዝሙር ፡ ፻፵፩ ።

፩ ፤ ቃልየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸራኅኩ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ የም እመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ። ልመ ናዬን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መ ልሼ ፡ ለመንሁ ።

ቃልየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰአልኩ ።

ሰአልኩ ፡ ለማለት ፡ ደገመው ፤ በቃሌ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መ ልሼ ፡ ለመንሁ ።

፪ ፤ ወእክዑ ፡ ቅድሜሁ ፡ ስእለትየ ።

ልመናዬን ፡ ከፊቱ ፡ አቀረብኩ ፤ አክዕዋ ፡ ለነፍስየ ፡ እንዲል ።

ወእነግር ፡ ቅድሜሁ ፡ ሕማምየ ።

መከራዬን ፡ ለርሱ ፡ እነግረዋለሁ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ሁሉ ፡ ፊቱ ፡ ነውና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ኢዮ ፡ ፳ ፡ ፰ ። ፳፫ ፡ ፲ ።

፫ ፤ ሶበ ፡ ተኀልቀ ፡ ነፍስየ ፡ በላዕሌየ ።

በኔ ፡ ያለች ፡ ሰውነቴ ፡ በመከራው ፡ አለይ ፡ አለይ ፡ ባለች ፡ ጊዜ ።

አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ተአምር ፡ ፍኖትየ ።

አቤቱ ፡ የባቢሎን ፡ መንገዴን ፡ አንተ ፡ ታውቀዋለህ ።

በፍኖት ፡ እንተ ፡ ሖርኩ ፡ ኀብኡ ፡ ሊተ ፡ መሥገርተ ።

በዚች ፡ በሄድኩባት ፡ በባቢሎን ፡ መንገድ ፡ ምክር ፡ መከሩብኝ ፤ ጦር ፡ ሸመቁብኝ ።

፬ ፤ ወተመየጥኩ ፡ መንገለ ፡ የማንየ ፡ ወር ኢኩ ።

ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ ተመ ልሼ ፡ ተመለከትሁ ፤ አየሁ ።

ወኀጣእኩ ፡ ዘየአምረኒ ።

እንዲህ ፡ ባይ ፡ ብመለከት ፡ የማው ቀው ፡ አጣሁ ።

ወገበጠኒ ፡ እመሥጥ ፡ እልቦየ ።

ከባቢሎን ፡ ተዋግቼ ፡ የምወጣበት ፡ ኃይል ፡ የለኝም ።

ወአልቦ ፡ ዘይትኃሠሥ ፡ በእንተ ፡ ነፍስየ ።

ስለ ፡ ሰውነቴ ፡ የሚገላግል ፡ የለ

ም ። እሕዛብ ፡ ጽኑዓን ፡ ናቸውና ፡ ምን ፡ አደረገ፡ ምን ፡ አለ ፡ አይሉም፤ ጣለው ፡ በለው ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ። እንድም ፡ (ሶበ ፡ ተኀልቅ) ፡ ሰውነቴ ፡ በመከራው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ባለ፡ፉ ፡ ጊዜ ። (አንተ ፡ እግዚእ ፡ ተአምር ፡ ፍኖትየ) ፡ አቤቱ ፡ አንተ፡ የእቶን ፡ እሳት ፡ መንገዱን ፡ ታውቀዋለህ ። (በዛቲ ፡ ፍኖት) ፡ በዚች ፡ በሄድሁባት ፡ በእቶን ፡ እሳት ፡ መንገድ ፡ ምክር ፡ መከሩብኝ ፡ ጦር ፡ ሸመቁብኝ ። እንድም ፡ ሰይፍ ፡ መዘውባቸዋል ፡ ጦር ፡ ወርውረውባቸዋልና ። (ወተመየጥኩ) ፡ ወደ ፡ ቀኝ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ ተመልሼ ፡ አየሁ ፡ ተመለከትሁ ። (ወኀጣእኩ) ፡ እንዲህ ፡ ባይ ፡ ብመለከት ፡ የማውቀው ፡ አጣሁ ። (ወኀበሂ) ፡ ከእቶን ፡ እሳት ፡ የምወጣበት ፡ ኀይል ፡ የለኝም ። (ወእልቦ ፡ ዘይትኀሠሥ ፡ በእንተ ፡ ነፍስየ) ፡ የሚገላግል፡ የለም ፡ እሕዛብ ፡ ጽኑዓን ፡ ናቸውና ፡ በመከራ ፡ላይ ፡መከራ፡ይጨምራሉ። እንድም፡ (ሶበ ፡ ተኀልቅ) ፡ በቁመ ፡ ነፍሴ ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ በጸናባት ፡ ጊዜ ፡ (አንተ ፡ እግዚእ) ፡ አቤቱ ፡ አንተ ፡ የሲኦል ፡ መንገዱን ፡ ታውቀዋለህ ። (በዛቲ ፡ ፍኖት) ፡ በዚች ፡ በሄድኩባት ፡ በሲኦል ፡ መንገድ ፡ ምክር ፡ መከሩብኝ ፡ ማለት ፡ በየጉዳናው ፡ የሚያስደነግጡትን ፡ አጋንንት ፡ መናገር ፡ ነው ። (ወተመየጥኩ) ፡ ወደ ፡ ግራዩም ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ተመልሼ ፡ አየሁ ፡ ተመለከትኩ ። (ወኀጣእኩ) ፡ እንዲህ ፡ ባይ ፡ ብመለከት ፡ የማውቀው ፡ አጣሁ ፡ ለእለሂ ፡ ይመርሖኒ ፡ ወለእለሂ ፡ ይተልወኒ ፡ ኢኑእምሮሙ ፡ እስመ ፡ ጽሉማን ፡ እሙንቱ ፡ እንዳለ ። (ወኀበሂ) ፡ ከሲኦል ፡ የምወጣበት ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡ የለኝም ። (ወእልቦ ፡ ዘይትኀሠሥ ፡ በእንተ ፡ ነፍስየ) ፡ የሚገላግል ፡ የለም ፡ አጋንንት ፡ ጽኑዓን ፡ ናቸውና ፡ በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ ይጨምራሉ ።

፮ ፡ ገባእኩ ፡ እግዚኦ ፡ ጸራሕኩ ፡ ወእቤለከ ፡ አንተ ፡ ተስፋየ ።

አቤቱ ፡ እንዲህ ፡ መከራ ፡ በጸናብኝ፡ ጊዜ ፡ አለኝታዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ብዬ፡ ወዳንተ ፡ ተመልሼ ፡ ለመንሁ ።

ወአንተ ፡ መክፈልትየ ፡ በምድረ ፡ ሕያዋን ።

የሥስቴ ፡ ሕያዋን ፡ አገር ፡ በምትሆን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዕድል ፡ ተርታዬ፡ ጽዋ፡ ፈንታዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ብዬ ። እንድም ፡ በመላእክት ፡ በጻድቃን ፡ በሰማዕታት ፡ አገር ፡ በገነት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ዕድል ፡ ፈንታዬ ፡ ጽዋ ፡ ተርታዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ብዬ ።

፯ ፡ ነጽር ፡ ስእለትየ ፡ እስመ ፡ ሐመምኩ ፡ ፈድፋደ ።

ፈጽሜ ፡ ባለመከራ ፡ ሆኛለሁና ፡



መከራዬን ፡ ልመናዬን ፡ እይ ፡ ተመልከት ።

አድኀነኒ ፡ እምኀሊ ፡ ሮዳኒ ፡ እስመ ፡ ይኄይሉኒ ።

ይበረቱብኛልና ፡ ከከበቡኝ ፡ ጠላቶቼ ፡ አድነኝ ።

፰ ፡ ወአውፅኣ ፡ እሞቅሕ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ ከእስራት ፡ እንድም ፡ ከእቶን ፡ እሳት ፡ አድናት። እንድም፡ ነፍሴን ፡ ከቍራኝነት ፡ ከፍዳ ፡ ከሲኦል ፡ ከገሃነም ፡ አድናት ።

ከመ ፡ እግነይ ፡ ለስምከ ፡ እግዚእ ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼ ፡ ለስምህ ፡ እገዛ ፡ ስምህን ፡ አመሰግን ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ ከእቶን ፡ እሳት ፡ ድኜ ፡ በገነት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ስምህን ፡ አመሰግን ፡ ዘንድ ።

ኪያየ ፡ ይጸንሑ ፡ ጻድቃን ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ ተዐስየኒ ።

ዕሴተ ፡ ንስሓ ፡ ሚጠትን ፡ እስክትሰጠኝ ፡ ድረስ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ እኔን ፡ ይጠብቃሉ ፡ እሊያ ፡ ካልወጡ ፡ እሊህ ፡ አይወጡምና ። እንድም ፡ ዕሴተ ፡ ሃይማኖትን ፡ ተአምራትን ፡ ንስሓን ፡ እስክትሰጠኝ ፡ ድረስ ፡ በእስራኤል ፡ ያሉ ፡ እሉ ፡ ዳንኤል ፡ እኔን ፡ ይጠብቃሉ ። እንድም ፡ ዕሴተ ፡ ንስሓ ፡ ሚጠትን ፡ እስክትሰጠኝ ፡ ድረስ ፡ ቀደምት ፡ ጻድቃን ፡ ደኀርት ፡ ጻድቃን ፡ እኔን ፡ ይጠብቃሉ ። እንድም ፡ ዕሴተ ፡ ሃይማኖት ፡ ዕሴተ ፡ ምግባር ፡ ገነት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ እስክትሰጠኝ ፡ ድረስ ፡ ቀደምት ፡ ጻድቃን ፡ ደኀርት ፡ ጻድቃን ፡ እኔን ፡ ይጠብቃሉ ፤ ምነው ፡ እሊህማ ፡ ሥርተው ፡ ት ፡ ለየምን ፡ በጊታ ፡ ግፍ ፡ አይፈ ንበትምን ፡ ቢሉ ፡ አወን ፡ አያፈግን በትም ፡ ላንድ ፡ ኸማግሌ ፡ ዐሥር ፡ ልጆች ፡ ይኖሩታል ፡ እምቡቱ ፡ ቁሉ፡ እምቡቱ ፡ ደጋ ፡ ይሰማራሉ ፡ ደጋ ፡ የተሰማሩ ፡ አስቀድመው ፡ ይገባሉ ፡ በዳረጎት ፡ ያቈያቸዋል ፡ እንጂ ፡ እራታቸውን ፡ እንዳያሰጣቸው ፡ ጌታም ፡ ሁሉንም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ያወርሳቸዋል ፡ እንጂ ፡ እኩሌቶቹን ፡ በፊት ፡ እኩሌቶቹን፡በኋላ፡ አያወርሳቸምና ።

## መዝሙር ፡ ፻፲፯ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ ስምዐኒ ፡ ጸሎትየ ።

ሰለ ፡ትሩፋን ፡ተናግሮታል ፡አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወአጽምዐኒ ፡ ስእለትየ ፡ በጽድቅከ ።

በቸርነትህ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

2014 04 18

ወለምዕዴ ፡ በርትዕከ ።

ቀንተህ ፡ በቅንነት ፡ ስማኝ ።

፪ ፡ ወኢትባእ ፡ ውስተ ፡ ቅሥተ ፡ ምስለ ፡ ገብርከ ።

ከባሪያህ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ክርክር ፡ አትግባ ፡ ግለት ፣ የኔን ፡ ኀጢአት ፡ አትመርምር ፡ ጌታና ፡ ሎሌ ፡ ተጣልቶ ፡ ቅልና ፡ ደንጊያ ፡ ተማቶ ፡ አይሆንም ፡ እንዲሉ ።

እስመ ፡ ኢይጸድቅ ፡ ኵሉ ፡ ሕያው ፡ በቅድሜከ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ጻድቅ ፡ ንጹሕ ፡ ሆኖ ፡ አይገኝምና ። ኢዮ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ፡ ፲፭ ፡ ፲፬ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ሮደ ፡ ጸላኢ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ ብልጣሶር ፡ ነፍሴን ፡ ዲያብሎስ ፡ ከዓታልና ።

ወአኅሰረ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ለሕይወትየ ።

ሰውነቴን ፡ በባቢሎን ፡ ነፍሴን ፡ በገሃነም ፡ አዋረዳት ።

ወአንበረኒ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ከመ ፡ ምዉተ ፡ ትካት ።

አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ሰው ፡ በቁላተ ፡ ሐዘን ፡ አኖሩኝ። እንድም፡ የነቢብ ፡ የገቢር ፡ ፍዳ ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ከሲኦል ፡ አኖሩኝ ። ሰቈ ፡ ፫ ፡ ፯ ።

፬ ፡ ወተቀብፀት ፡ ነፍስየ ፡ በላዕሌየ ።

እንዲህ ፡ ባለመከራ ፡ በሆንሁ ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቴ ፡ ተስፋ ፡ ቈረጠችብኝ ።

ወደንገፀኒ ፡ ልብየ ፡ በውስጥየ ።

በሰውነቴ ፡ ያለ ፡ ልቡናዬ ፡ ደንገፀብኝ ።

፭ ፡ ወተዘከርኩ ፡ መዋዕለ ፡ ትካት ።

አግሎም ፡ ዘሳርስትኤም ፡ የነገሡባቸውን ፡ ዘመናት ፡ አሰብሁ ።

ወአነበብኩ ፡ በኵሉ ፡ ግብርከ ።

ሁሉ ፡ ግብረከ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ከዚህ፡ አስቀድሞ ፡ ሥራህን ፡ ሁሉ ፡ ነገርሁ ።

ወአነበብኩ ፡ ግብረ ፡ እደዊከ ።

እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ የእጅህ ፡ የቃልህን ፡ ሥራ ፡ እነግራለሁ ፤ አስተምራለሁ ።

፮ ፡ ወአንቃዕዶኩ ፡ እደውየ ፡ ኀቤከ ።

እጄ ፡ ቃሌን ፡ በጸሎት ፡ ወዳንተ ፡ አነሣለሁ ።

ነፍስየኒ ፡ ከመ ፡ ምድረ ፡ በድው ፡ ጸምአተከ ።

ሰውነቴም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ዝናምን ፡ እንደሚናፍቅ ፡ አንተን ፡ ናፈቀች ፤ ወደደች ።

፯ ፡ ፍጡነ ፡ ስምዐኒ ፡ እግዚኦ ፡ ኀለፈት ፡ ነፍስየ ።

አቤቱ ፡ ሰውነቴ ፡ በመከራው ፡ አለይ ፡ አለይ ፡ ብላለችና፡ ፈጥነህ ፡ ስማኝ ።



ወኢትሚጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔየ ።

ገጽ፡ ምሕረትህን፡ ገጽ፡ ረድኤትህን፡ ከኔ ፡ አትመልሰው ፤ ለጊዜውም ፡ ብትመልሰው ፡ እንደ ፡ መለስከው፡ አትቅር ።

ወኢይኩን ፡ ከመ ፡ እለ ፡ ይወርዱ ፡ ውስተ ፡ ዐዘቅት ።

ተማርከው ፡ ፋርስ ፡ ባቢሎን ፡ እንደሚወርዱ ፡ እንደ ፡ ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ አልሁን ፤ እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ናቸው። እንድም ፡ ሙተው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ እንደ ፡ ወረዱ ፡ ሰዎች ፡ አልሁን ። እንድም ፡ እንዳልሆን ፡ ኢትሚጥ ። ኢዮ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።

፰ ፡ ዘይሰማዕ ፡ ግበር ፡ ሊተ ፡ ምሕረተከ ፡ በጽባሕ ።

ዘይትዐወቅ ፡ ምሕረተከ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ዕለት ፡ ዕለት ፡ የሚታወቅ ፡ ቸርነትህን ፡ አድርግልኝ ፤ ወኢይሰማዕ ፡ በኀቢክሙ ፡ ነጊረ ፡ ጋእዝ ፡ እንዲል ።

እስመ ፡ ኪያከ ፡ ተወከልኩ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ ባንተ ፡ እምኛለሁና ።

ምርሐኒ ፡ እግዚኦ ፡ ፍኖተ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ እሖር ።

አቤቱ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የምሄድበትን ፡ መንገድ ፡ ምራኝ ። እንድም፡ ጸንቼባት፡ የምኖር፡ ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፤ አስተምረኝ ።

እስመ ፡ ኀቤከ ፡ አንቃዕደውኩ ፡ ነፍስየ ።

በአንቃዕድዎ ፡ ልቡና ፡ በተዘክሮ ፡ ኀሊና ፡ ሆኜ ፡ ሰውነቴን ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለምኛለሁ ።

፱ ፡ አድኅነኒ ፡ እግዚኦ ፡ እምፀርየ ።

አቤቱ ፡ ከጠላቴ ፡ ከብልጣሶር ፤ እንድም ፡ ከጠላቴ ፡ ከዲያብሎስ ፡ አድነኝ ።

እስመ ፡ ኀቤከ ፡ ተማኅፀንኩ ።

ሰውነቴን ፡ ባንተ ፡ አስጠብቂአለሁና ።

፲ ፡ ምሀረኒ ፡ እግዚኦ ፡ ከመ ፡ እግበር ፡ ፈቃደከ ።
እስመ ፡ አምላኪየ ፡ አንተ ።

ምርሐኒ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አቤቱ ፡ አንተ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነህና ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼ ፡ አንተ ፡ የምትወደውን፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የኢየሩሳሌምን፡ ጕዳና ፡ መርተህ ፡ አውጣኝ ። እንድም ፡ (መሀረኒ) ፡ አንተ ፡ የምትወደውን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፤ አስተምረኝ ።

ወመንፈስከ ፡ ቅዱስ ፡ ይምርሐኒ ፡ በምድረ ፡ ጽድቅ ።

መንፈስህ ፡ ረድኤትህ ፡ መርቶ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ጽድቅ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያድርሰኝ ። እንድም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መርቶ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ያድርሰኝ ፤ ያደርሰኝ ፡ ዘንድ ፡ ምርሐኒ ።

2014 04 18

፲፩ ፡ በእንተ ፡ ስምከ ፡ እግዚኦ ፡ አሕይወኒ ፡ በጽድቅከ ።

ስምዩኒ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተማህል ፡ ስላልህ ፡ በቸርነትህ ፡ እንድም ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ባልከው ፡ በጽኑ ፡ ቀጠሮህ ፡ አድነኝ ።

ወአውፅኦ ፡ እምንዳቤሃ ፡ ለነፍስየ ።

ሰውነቴን ፡ ከመከራ ፡ ሥጋ ፡ ነፍ ሴን ፡ ከመከራ ፡ ነፍስ ፡ አድናት ።

፲፪ ፡ ወበምሕረትከ ፡ ሠርዎሙ ፡ ለፀርየ ።

ፈርደህ ፡ ጠላቶቼን ፡ አጥፋቸው ።

ወታጠፍኦሙ ፡ ለዘሎሙ ፡ እለ ፡ ያሐምምዋ ፡ ለነፍስየ ።

እኔ ፡ እቸነፋለሁ ፡ እንጂ ፡ በሰውነቴ ፡ መከራ ፡ የሚያጸኑባትን ፡ ጠላቶቼን ፡ ሁሉ ፡ ታጠፋቸዋለህ ።

እስመ ፡ አነ ፡ ገብርከ ።

እኔ ፡ እገልጋይህ ፡ ተገዥህ ፡ ነኝና ።

## መዝሙር ፡ ፻፵፬ ።

፩ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኪየ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ የራሱም ፡ አሰበት ። ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

ዘመሀሮን ፡ ጸብአ ፡ ለእደውየ ።

ለእጆቼ ፡ ሰልፍን ፡ እንድም ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ማማተብን ፡ ያስተማራቸው ።

ወቀትለ ፡ ለአጻብዕየ ።

ለእጆቼ ፡ መግደል ፡ መስለብን ፡ ያስተማራቸው ። እንድም ፡ በቀላውትምናስ ፡ የመብረቅ ፡ የነጐድጓድ ፡ ድምፅ ፡ እስማልሃለሁ ፡ ሂደህ ፡ ገጠማቸው ፡ አለው ፤ ሄዶ ፡ ገጠማቸው ፤ የነጐድጓድ ፡ ድምፅ ፡ አሰምቶለት ፡ ድል ፡ አድርጓልና ።

፪ ፡ መሐሪየ ፡ ወጸወንየ ።

የሚያዝንልኝ ፡ የሚራራልኝ ፡ አምባ ፡ መጸጊያዬ ፡ እርሱ ፡ ነው ።

ምስካይየ ፡ ወመድኀንየ ።

መጸጊያዬ ፡ ድኅነቴን ፡ የሚያደርግልኝ ።

ምእመንየ ፡ ወኪያሁ ፡ ተወከልኩ ።

የታመነ ፡ ወዳጄ ፡ የታመነ ፡ ረዳቴ ፡ ነው ፤ እኔም ፡ በርሱ ፡ አመንሁ ።

ዘያገርር ፡ ሊተ ፡ አሕዛበ ፡ በመትሕቴየ ።

አሕዛብን ፡ በእጄ ፡ ጭብጥ ፡ በእግሬ ፡ ርግጥ ፡ አድርጎ ፡ የሚያስገዛልኝ ፡ እሱ ፡ ነው ። እንድም ፡ አጋንንትን ፡ ድል ፡ እንድነሣ ፡ የሚያደርግልኝ ፡ እሱ ፡ ነው ።

፫ ፡ እግዚኦ ፡ ምንትኑ ፡ ውእቱ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ታስተርኢ ፡ ሎቱ ።

አቤቱ ፡ በረድኤት ፡ ትገለጽለት ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ። እንድም ፡ ሰው ፡ ሆነህ ፡ ሥጋ ፡



ለብሰህ ፡ ትገለጽለት ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ለዚህን ፡ ይበቃል ።

ዕጓለ ፡ እመሕያውሰ ፡ ዘተሐስቦ ።

በረድኤትስ ፡ ትጐበኘው ፡ ዘንድ ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ለዚህን ፡ ይበቃል ።

፬ ፡ ሰብእሰ ፡ ከንቶ ፡ ይመስል ።

እንዲህስ ፡ እንዳልል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ዕፅ ፡ ከንቱን ፡ ይመስላል ፤ ዘወትር ፡ ከዚህ ፡ ያረስ ፡ አይባልም ።

ወመዋዕሊሁኒ ፡ ከመ ፡ ጽላሎት ፡ የኀልፍ ።

ዘመኑም ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ይፈጸማል ።

፭ ፡ እግዚኦ ፡ አጽንን ፡ ሰማያቲከ ፡ ወረድ ።

አቤቱ ፡ በመላእክት ፡ አድረህ ፡ ርዳኝ ። በነያላኑ ፡ በነዮርናዕ ፡ መዓትህ ፡ ውረድባቸው ። እንድም ፡ ባሕርየ ፡ መላእክትን ፡ ባሕርይ ፡ ሳታደርግ ፡ ባሕርየ ፡ አዳምን ፡ ባሕርይ ፡ አድርገህ ፡ አድነኝ ።

ገሥሦሙ ፡ ለአድባር ፡ ወይጠይሱ ።

ነገሥታቱን ፡ በእጁ ፡ መዓትህ ፡ ዳሳቸው ፤ እንዲህም ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይጠይሱ ፤ ይጠፋሉ ፤ ይጤሱ ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ይጥፉ ። እንድም ፡ አጋንንትን ፡ ዳሳቸው ፤ ይጥፉ ። ኢሳ ፡ ፷፬ ፡ ፩ ።

፮ ፡ አብርቅ ፡ መባርቅቲከ ፡ ወዘርዎሙ ።

መባርቅተ ፡ መዓትን ፡ አብዝተህ ፡ አምጣባቸው ፤ (ወዘርዎሙ) ፡ በትናቸው ። እንድም ፡ ሰብዓ ፡ አርድእትን ፡ አብዝተህ ፡ አስነሣቸው ፤ በመምርነት ፡ በትናቸው ።

ፈኑ ፡ እሕጻከ ፡ ወሀውኮሙ ።

አሕጻ ፡ መዓትህን ፡ አምጣባቸው ፤ አውካቸው ፤ አውከባቸው ። እንድም ፡ ሐዋርያትን ፡ በመምርነት ፡ አስነሣቸው ፤ አይሁድን ፡ መናፍቃንን ፡ አጋንንትን ፡ አውካቸው ፤ አውከባቸው ። ኢሳ ፡ ፬ ፡ ፱-፶ ።

፯ ፡ ፈኑ ፡ እዴከ ፡ እምአርያም ።

ረድኤትህን ፡ ከአርያም ፡ ላክ ። እንድም ፡ ልጅህን ፡ በሥጋ ፡ ላክ ።

አድኅነኒ ፡ ወባልሐኒ ፡ እማይ ፡ ብዙኅ ።

በሥልጣንህ ፡ ከብዙ ፡ መከራ ፤ እንድም ፡ ከብዙ ፡ ጦር ፡ አድነኝ ። እንድም ፡ በልጅህ ፡ ከፍትወታት ፡ እኩያት ፡ ከኀጣውእ ፡ ከፍዳ ፡ ከመከራ ፡ ነፍስ ፡ ፈጽመህ ፡ አድነኝ ።

ወእምእደ ፡ ደቂቀ ፡ ነኪር ።

ከለናምሩድ ፡ ከለሳእል ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ አድነኝ ። እንድም ፡ ከዲያብሎስ ፡ ወገኖች ፡ ሥልጣን ፡ አድነኝ ።

፰ ፡ እለ ፡ ከንቶ ፡ ነበበ ፡ አፉሆሙ ።

እንደበታቸው ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ የተናገረ ፡ ማለት ፡ ጣዖትን ፡ አምላኩ ፡ ያለ ። እንድም ፡ ከሰብዓ ፡ ዘመን ፡ አትርፈን ፡ እንገዛለን ፡ ያለ ። እንድም ፡ ለእመ ፡ በላዕክሙ ፡

በለስ ፡ ሞተ ፡ ትመውቴ ፡ ብለህ ፡ በተናገርከው ፡ ላይ ፡ ለእመ ፡ በላ ዕክሙ ፡ በለስ ፡ ትከውኑ ፡ እግል ከተ ፡ ብሎ ፡ የተናገረ ።

ወየማናሙኒ ፡ የማን ፡ በመፃ ።

እጃቸው ፡ ማግለጃን ፡ የተመላ ። እንድም ፡ ሥልጣናቸው ፡ ዐመፅን ፡ የተመላ፤ የዐመፅ፡ ሥልጣን፡ የሆነ ። ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፫።

፱ ፤ እግዚኦ ፡ ስብሐተ ፡ ሐዲስ ፡ እሴብሐከ።

አቤቱ ፡ ብታድነኝ ፡ እንግዳ ፡ ምስ ጋና ፡ አመሰግንሃለሁ ። እንድም ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ፡ እያልሁ ፡ አመሰ ግንሃለሁ ።

ወበመዝሙር ፡ ዘዐሠርቱ ፡ አውታሪሁ ፡ እዜ ምር ፡ ለከ ።

ዐሥር ፡ አውታር ፡ ያለው ፡ በገና ፡ እየደረደርሁ ፤ እንድም ፡ ዐሥር ፡ ሕዋሳት ፡ ባለው ፡ ሰውነት፡ ጸንቼ ፤ እንድም ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላት ፡ በተጻ ፉበት ፡ በአሪት ፡ ሆኜ ፤ እንድም ፡ በምግባር፡ በሃይማኖት ፡ ጸንቼ ፡ አመሰግንሃለሁ ።

፲ ፤ ዘይሁቦሙ ፡ ለነገሥት ፡ መድኀኒተ ።

ለነገሥታቱ ፡ ድኅነትን ፡ የሚሰጣ ቸው ፡ ማለት ፤ የሚያድናቸው ፡ እርሱ ፡ ነው ።

ዘአድኀኖ ፡ ለዳዊት ፡ ገብሩ ፡ እምኲናት ፡ እኪት ።

አገልጋዩ ፡ ባለሟሉ ፡ ዳዊትን ፡ ከሳኦል ፤ እንድም ፡ ጽኑ ፡ ከሚሆን ፡ ከማናቸውም ፡ ጦር ፡ ያዳነው ፡ እር ሱ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ተናግሮ ፡ አንድ፤ አመጣ ፤ ብዙ ፡ ተናግሮ ፡ አንድ ፡ ማምጣት ፡ ልማድ ፡ ነው ፤ ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ተመሰ ልዎሙ ፡ ለእለ ፡ በአሚን ፡ ወበት ዕግሥት ፡ ወረሱ ፡ ተስፋሆሙ ፡ ብሎ ፤ ወለአብርሃምኒ ፡ አመ ፡ አሰ ፈዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳለ ። ያዕቆብም ፡ አርአያሃሰ ፡ አበዊነ ፡ ለትዕግሥተ፡ ተጽናስከሙ፤ ብከሙ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ ተናገሩ ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፤ ናሁ ፡ ናስተበፅ ዖሙ ፡ ለእለ ፡ ተዐገሡ ፡ ብሎ ፤ ወሰ ማዕክሙ ፡ ትዕግሥቶ ፡ ለኢዮብ ፡ እንዳለ ። ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ ወከ ማሁ ፡ ትካትኒ ፡ ቅዱሳት ፡ አንስት ፡ እለ ፡ ይትዌከላ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያሰርግዋ፡ ርእሶን ፡ በተአዝዞ፡ ለአም ታቲሆን፡ ብሎ፡ ከመ፡ ሣራ፡ እንዳለ።

፲፩ ፤ አድኀነኒ ፡ ወባልሐኒ ፡ እምእዴሆሙ ፡ ለደቂቀ ፡ ነኪር ።

ከለናምሩድ ፡ ልጆች ፤ እንድም ፡ ከዲያብሎስ ፡ ወገኖች ፡ ፈጽመህ ፡ አድነኝ ።

እለ ፡ ከንቶ ፡ ነበበ ፡ አፉሆሙ ።

እንደበታቸው ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ከሚናገር ።

ወየማናሙኒ ፡ የማን ፡ ዐመፃ ።

ሥልጣናቸው ፡ የዐመፅ ፡ ሥልጣን ፡ ከሚሆን ።



እለ ፡ ደቂቆሙ ፡ ከመ ፡ ተክለ ፡ ዘይት ፡ ሐዲስ ፡ ጽኑዓን ፡ በውርዙቶሙ ።

ከመ ፡ ተክለ ፡ ዘይት ፡ ለማለት ፡ ደገመው ፤ ኅይላቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወአዋልዲሆሙኒ ፡ ርሱያት ፡ ወስርግዋት ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ጽርሕ ።

ሴቶች ፡ ልጆቻቸውም ፡ እንደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አዳራሽ ፡ ፈጽ መው ፡ የተሸለሙ ፡ ናቸው ። ያ ፡ የወርቅ ፡ የዕንቍ ፡ ፈርጽ ፡ እንዳለ በት ፡ ብዕላቸውን ፡ መናገር ፡ ነው።

፲፫ ፤ ወአብያቲሆሙኒ ፡ ምሉእ ።

ቤታቸውም ፡ ከመሠረት ፡ እስከ ፡ ጠፈር ፡ ድረስ ፡ ብር ፡ ወርቅ ፡ ዕን ቍን ፡ የተመላ ፡ ነው ።

ወይሰወጥ ፡ እምዝ ፡ ውስተ ፡ ዝ ።

ከዚህ ፡ እስከዚያ ፡ የተመላ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ ካባት ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ የሚ ያልፍ ፡ ከሜዳ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ የሚ ል ፡ ከቤት ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ የማይወ ጣ ፡ ነው ።

ወአባግዒሆሙኒ ፡ ብዙኃን ፡ ይትዋለዳ ።

በጎቻቸውም ፡ ብዙውን ፡ ይረባሉ ።

ወይትባዝኃ ፡ በሙፋሪሆን ።

በየተሰማሩበት ፡ በዝተው ፡ ይገባ ሉ ። ሦስት ፡ መቶ ፡ ሆነው ፡ ተ ሰማርተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሆነው ፡ ይገባሉ ። ኢሳ ፡ ፳ ፡ ፲ ፯ ። ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፵፪ ።

፲፬ ፤ ወአልሕምቲሆሙኒ ፡ ሥቡሕ ።

ሥቡሓን ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ላሞቻቸ ውም ፡ የሠቡ ፡ ናቸው ፤ ደንገሉን ፡ እየበሉ ። እንድም ፡ ከለመለመ ፡ ሣር ፡ ከጺራ ፡ ውሃ ፡ ያውሏቸዋልና ።

ወአልቦ ፡ ድቀት ፡ ለቅጽሮሙ ።

ለቅጽራቸውም ፡ መፍረስ ፡ የለ ውም ፤ እነሱ ፡ የሰውን ፡ ሀገር ፡ ቅጽር ፡ ቢያፈርሱ ፡ እንጂ ፡ የነሱን ፡ ሀገር ፡ ቅጽር ፡ የሚያፈርስባቸው ፡ ከሌለ ፡ ዘንድ ።

ወአልቦ ፡ እንተ ፡ ኀበ ፡ ይበውእዎሙ ።

ወደ ፡ ቤታቸው ፡ የሚገባባቸው ፡ የለም ። እነሱ ፡ ከሰው ፡ ቤት ፡ ይገባሉ ፡ እንጂ ፡ ከነሳቸው ፡ ቤት ፡ የሚገባባቸው ፡ ከሌለ ፡ ዘንድ ።

ወአልቦ ፡ በውያት ፡ ውስተ ፡ ሀገሮሙ ።

በሀገራቸው ፡ ጩኸት ፡ የለባቸ ውም ፤ እነርሱ ፡ ሰውን፡ ያስጮኹሉ፡ እንጂ ፡ እነሱን ፡ የሚያስጮኻቸው፡ ከሌለ ፡ ዘንድ ። ኢዮ ፡ ፳፩ ፡ ፮-፲፫ ።

፲፭ ፤ አስተብፅዕዎ ፡ ለዘከመ ፡ ዝ ፡ ሕዝብ ።

እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ለጊዜው ፡ ዕፁብ ፡ ይሉታል ።

ብፁዕ ፡ ሕዝብ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ አምላኩ ።

እዩ ፡ ብፁዕስ ፡ በለኝ ፡ ፈጣሪው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልክ ፡

2014 04 18

ነው ። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪው ፡ የሆነለት ፡ ማለት ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልክ ፡ ሰው ፡ ንጉድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

## መዝሙር ፡ ፻፵፭ ።

፩ ፤ አሐዕለከ ፡ ንጉሥየ ፡ ወአምላኪየ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ ፈጣሪዬ ፡ ንጉሜ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርግሃለሁ ፤ አሁን ፡ ፍጡር ፡ ፈጣሪውን፡ የሚያከብር ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ፤ ልዑል ፡ እያልኩ ፡ አመሰግንሃለሁ ።

ወእባርክ ፡ ለስምከ ።

ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ፤ ስምህን ፡ አመሰግናለሁ ።

ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለሙ ፡ አመሰግንሃለሁ ። ኢሳ ፡ ፷፭ ፡ ፩ ።

፪ ፤ ዘሎ ፡ እሜረ ፡ እባርከከ ።

ዕለት ፡ ዕለት ፡ አመሰግንሃለሁ ።

ወእሴብሕ ፡ ለስምከ ።

ስምህን ፡ አመሰግናለሁ ፤ ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለሙ ።

፫ ፤ ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወብዙኅ ፡ አኰቴቱ ።

እግዚአብሔር ፡ ገናና ፡ ነው ፤ ምስጋናውም ፡ ፍጹም ፡ ነው ።

ወአልቦ ፡ ጽንፍ ፡ ለዕበየ ፡ ዚአሁ ።

ለጌትነቱም ፡ ልክ ፡ መጠን ፡ ወሰን ፡ የለውም ።

፬ ፤ ትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ይንእዱ ፡ ምግባሪከ ።

የልጅ ፡ ልጅ ፡ ሥራህን ፡ ይናገራሉ ፤ ያመሰግናሉ ።

ወይዜንዉ ፡ ኀይለከ ።

ከሃሊነትህን ፡ ይናገራሉ ፤ ያስተምራሉ ።

፭ ፤ ወይነግሩ ፡ ዕበየ ፡ ክብረ ፡ ስብሐተ ፡ ቅድሳቲከ ።

ዕበየ ፡ ክቡር ፡ ስብሐቲከ ፤ ክቡር ፡ የሚሆን ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡ የሚመሰገን ፡ የጌትነትህን ፡ ገናንነትም ፡ ይናገራሉ ።

ወያየድዑ ፡ መንክረከ ።

ሥራህን ፡ ይናገራሉ ።

፮ ፤ ወይብሉ ፡ ግሩም ፡ ኀይልከ ።

ኀይልህ ፡ ግሩም ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤ (ኀይለከ) ፡ ኀይልህን ፡ ግሩም ፡ ነው፡ ይላሉ ።

ወይነግሩ ፡ ኀይለ ፡ ግርማከ ።

የሥልጣንህን ፡ ኀይል ፡ ይነግራሉ ።



ምንተ ፡ ኮንኪ ፡ ባሕር ፡ ዘጕየይኪ ፤ ወአንተኒ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ዘገባእከ ፡ ድኅሬከ ፤ መዝሙር ፡ ፻፲፫ ።



ባሕርኒ ፡ ርእየት ፡ ወጐየት ፤ ወዮርዳኖስኒ ፡ ገብአ ፡ ድኅሬሁ ፤ መዝሙር ፡ ፻፲፫ ።







ወያየድዑ ፡ ጽንዐከ ።

ከሃሊነትህን ፡ ይናገራሉ ።

፯ ፡ ወይጐሥዑ ፡ ተዝካረ ፡ ብዝኀ ፡ ምሕረትከ ።

ብዙ ፡ የሚሆን ፡ የቸርነትህን ፡ መታሰቢያ ፡ ይናገራሉ ። ወትጐሥዖሙ ፡ ባሕር ፡ ለነጋድያን ፡ እንዲል ።

ወይትሐሠዩ ፡ በጽድቅከ ።

በቸርነትህም ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፩—፲፩ ። ፩ ፡ ሕጹ ፡ ፳፱ ፡ ፲፭ ። ራእ ፡ ፩ ፡ ፱—፲፪ ። ፲፭ ፡ ፫ ።

፰ ፡ መሓሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነው ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነው ።

ርሑቀ ፡ መዓት ፡ ወብዙኅ ፡ ምሕረት ፡ ወጻድቅ ።

ቸርነቱ ፡ የቀረበ ፡ መዓቱ ፡ የራቀ ፤ እንድም ፡ ቸርነቱ ፡ የበዛ ፡ መዓቱ ፡ ያነሰ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

፱ ፡ ኄር ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኵሉ ፡ ይትዔገሦም ።

እግዚአብሔር ፡ ለፈተና ፡ መከራ ፡ ባመጣባቸው ፡ ጊዜ ፡ መከራ ፡ እንጂ ፡ ለወዳጆቹ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መከራውን ፡ ታግሠው ፤ እንድም ፡ በሃይማኖት ፡ መከራ ፡ በመጣባቸው ፡ ጊዜ ፡ ታግሠው ፡ መከራ ፡ ለተቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ቸር ፡ ነው ።

ወሣህሉ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ተግባሩ ።

ይቅርታውም ፡ ለፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ይደረጋል ።

፲ ፡ ይገነዩ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ ኵሉ ፡ ተግባርከ ።

አቤቱ ፡ ፍጥረትህ ፡ ሁሉ ፡ ይገዙልሃል ።

ይባርኩከ ፡ ጻድቃኒከ ።

ወገኖችህ ፡ ጻድቃን ፡ ያመሰግኑሃል ።

፲፩ ፡ ስብሐተ ፡ ይብሉ ፡ ለመንግሥትከ ።

ለጌትነትህ ፡ የክብር ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ፡ ይላሉ ፤ ምስጋና ፡ ያቀርባሉ ።

ወይነግሩ ፡ ኀይለከ ።

ከሃሊነትህንም ፡ ይናገራሉ ፤ ያስተምራሉ ።

፲፪ ፡ ከመ ፡ ይንግርዎሙ ፡ ለውሉደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ኀይለከ ።

ለዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ኀይለከ ፡ ለማለት ፡ ይገመው ።

ወዕበየ ፡ ክብረ ፡ ስብሐተ ፡ መንግሥትከ ።

ክቡር ፡ ስብሐቲከ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ክቡር ፡ የሚሆን ፡ የጌትነትህን ፡ ምስጋና ፡ ገናንነቱን ፡ ይናገራሉ ።

፲፫ ፡ መንግሥትከሰ ፡ መንግሥተ ፡ ዘለዓለም ።

መንግሥትከሰ ፤ መንግሥትህም ፡ የዘላለም ፡ መንግሥት ፡ ነው ፡ ማለት ፤ ከዳዊት ፡ ከሰሎሞን ፡ መንግሥት ፡

2014 04 18

ይበልጣል ፤ የነዚያ ፡ ፵ ፡ ፵ ፡ ዘመ
ን ፡ ነው ፤ የርሱ ፡ ግን ፡ የዘላለም ፡
ነውና ።

ወምኵናኒከ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ።

ግዛትህም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ፤
ሲነገር ፡ ይኖራል ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፯ ። ዳን ፡
፬ ፡ ፫ ።

፲፬ ፤ ምእመን ፡ እግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡
ቃሉ ።

እግዚአብሔር ፡ በተናገረው ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ የታመነ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ የተ
ናገረውን ፡ አያስቀርም ።

ወጻድቅ ፡ በኵሉ ፡ ምግባሩ ።

በሥራው ፡ ሁሉ ፡ እውነተኛ ፡ ነው ።

፲፭ ፤ ይሰውቆሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእለ ፡
ተንተኑ ።

እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ መከራ ፡ የቀ
ረቡትን ፡ ሰዎች ፡ ከመከራ ፡ ያድና
ቸዋል ።

ያነሥኦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእለ ፡ ወድቁ ።

እግዚአብሔር ፡ በመከራ ፡ የተያዙ
ትን ፡ ከመከራ ፡ ያድናቸዋል ።

፲፮ ፤ ዐይነ ፡ ኵሉ ፡ ነፍስ ፡ ይሴፎ ፡ ኪያከ ።

የሰው ፡ ሁሉ ፡ ሰውነት ፡ አንተን ፡
ተስፋ ፡ ያደርጋል ፤ በየጊዜው ፡ ምግ
ባቸውን ፡ ትሰጣቸዋለህና ፡ በዘር ፡
ጊዜ ፡ ዘሩን ፡ በመከር ፡ ጊዜ ፡ መከ
ሩን ፡ ትሰጠናለህ ፡ በማለት ።

አንተ ፡ ትሁቦሙ ፡ሲሳዮሙ ፡ በጊዜሁ ።

አንተ ፡ የበልጉን ፡ በበልግ ፡ የመከ
ሩን ፡ በመከር ፡ ትሰጣቸዋለህና ።
ማቴ ፡ ፮ ፡ ፳፭ ። ራእ ፡ ፬ ፡ ፮ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

፲፯ ፤ ትስፍሕ ፡ የማነከ ፡ ወታጸግብ ፡ ለኵሉ ፡
እንስሳ ፡ ዘበሥርዐትከ ።

እጅ ፡ ሰፊ ፡ ነህና ፡ እጅህን ፡ ዘርግ
ተህ ፡ በሥርዐትህ ፡ ጸንተው ፡ ለሚ
ኖሩ ፡ ለእንስሳት ፡ ምግባቸውን ፡
ሰጥተህ ፡ ደስ ፡ ታሰኛቸዋለህ ፤ ከ
ሰው ፡ በቀር ፡ ከሥርዐቱ ፡ የወጣ ፡
የለምና ።

፲፰ ፤ ጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ ፍና
ዊሁ ።

እግዚአብሔር ፡ በተናገረው ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ እውነተኛ ፡ ነው ።

ወኄር ፡ በኵሉ ፡ ምግባሩ ።

በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ቸር ፡ ነው ።

፲፱ ፤ ቅሩብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኵሎሙ ፡
እለ ፡ ይጼውዕዎ ።

እግዚአብሔር ፡ ለሚለምኑት ፡ ሁሉ ፡
ቅርብ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ ልመናቸ
ውን ፡ ፈጥኖ ፡ ይሰማቸዋል ።

ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይጼውዕዎ ፡ በጽድቅ ።

ከዚያውም ፡ ዘንድ ፡ በውነት ፡ ለሚ
ለምኑት ፡ ይሰማቸዋል ፤ በሐሰት ፡
ቢለምኑት ፡ አይሰማምና ፡ በጽድ
ቅ ፡ አለ ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፳ ። ያዕ ፡ ፭ ፡ ፲፮ ።



፳ ፤ ይገብር ፡ ፈቃዶሙ ፡ ለእለ ፡ ይፈርህዎ ።

ለሚፈሩት ፡ ለሚያመልኩት ፡ ፈቃ
ዳቸውን ፡ ያደርግላቸዋል ።

ይሰምዖሙ ፡ ጸሎቶሙ ፡ ወያድኅኖሙ ።

ልመናቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ ከመከራ ፡
ያድናቸዋል ።

፳፩ ፤ የዐቅቦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኵ
ሎሙ ፡ እለ ፡ ይፈርህዎ ።

እግዚአብሔር ፡ የሚፈሩት ፡ የሚያ
መልኩትን ፡ ሁሉ ፡ ከመከራው ፡
ይጠብቃቸዋል ።

ወይሤርዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ኃጥአን ።

ባቢሎናውያንን ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ተበ
ቅሎ ፡ ያጠፋቸዋል ።

፳፪ ፤ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነግር ፡ አፉየ ።

እንደበቴ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስ
ጋና ፡ ጌትነት ፡ ተአምራት ፡ ይና
ገራል ፤ ያስተምራል ።

ወይባርክ ፡ ዘሥጋ ፡ ይባርክ ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ።

ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡
ጽኑዕ ፡ ክሃሊ ፡ ለሚሆን ፡ ስሙ ፡
ምስጋና ፡ ያቀርባል ፤ ስሙን ፡ ያመ
ሰግናል ።

ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለም ።

በ፶ ፡ ፶ ፡ መሥመር ፡ እያገባ ፡ ተና
ግሮት ፡ ነበር ፡ የኋላ ፡ መምህራን ፡
ይበዛል ፡ ብለው ፡ በመጀመሪያና ፡
በመጨረሻ ፡ አድርገውታል ።

## መዝሙር ፡ ፻፵፭ ።

፩ ፤ ተእኵቶ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ ሰው
ነቴ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታመሰግና
ለች ።

፪ ፤ እሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሕይወ
ትየ ።

እግዚአብሔርን ፡ ባለ ፡ ዘመኔ ፡ ሁ
ሉ ፡ አመሰግነዋለሁ ።

ወእዜምር ፡ ለአምላኪየ ፡ በእምጣነ ፡ ሀሎኩ ።

ፈጣሪዬን ፡ የምኖረውን ፡ ያኸል ፡
አመሰግነዋለሁ ፤ ገለጸው ። አንድ
ም ፡ ለፈጣሪዬ ፡ ምስጋና ፡ አቀር
ባለሁ ።

፫ ፤ ኢትትአመኑ ፡ በመላእክት ።

በስኅል ፡ ንጉሠ ፡ ግብጽ ፡ አትመኑ ።

ወኢ.በዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እለ ፡ ኢይክሉ ፡
አድኅኖ ።

ማዳን ፡ በማይቻላቸው ፡ ፈራሽ ፡
በስባሽ ፡ በሚሆኑ ፡ በሰራዊቱም ፡
አትመኑ ። አንድም ፡ (ኢትትአ
መኑ) ፡ በአጋንንት ፡ አትመኑ ፡
(ወኢ.በዕጓለ ፡ እመሕያው) ፡ በሰው ፡

2014 04 18

መራኽ፡ ጣዖት፡ አትመኑ። ኢሳ፡ ፪፡ ፯።

፬፤ ትወፅእ፡ ነፍሶሙ፡ ወይገብኡ፡ ውስተ፡ መሬቶሙ።

ነፍሳቸው፡ ከሥጋቸው፡ ትለያለች፤ ወደ፡ መሬትነታቸው፡ ይመለሳሉ፤ ይገብኡ፡ ማለቱ፡ ጥንቱን፡ ተፈጥሯቸው፡ ከመሬት፡ ነውና።

ውእተ፡ አሚረ፡ ይጠፍእ፡ ኵሉ፡ ምክሮሙ።

ነፍሳቸው፡ ከሥጋቸው፡ በተለየች፡ ጊዜ፡ ምክራቸው፡ ሁሉ፡ ይጠፋል፤ እረ፡ ሳሉም፡ ይደናገራል። ኢዮ፡ ፴፬፡ ፲፬።

፭፤ ብፁዕ፡ ብእሲ፡ ዘአምላኩ፡ ያዕቆብ፡ ረዳኢሁ።

ረዳቱ፡ የያዕቆብ፡ ፈጣሪ፡ የሆነለት፡ ሰው፡ ንኡድ፡ ክቡር፡ ነው።

ወትውክልቱኒ፡ ላዕለ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኩ።

እምነቱንም፡ በእግዚአብሔር፡ በፈጣሪው፡ ያደረገ፡ ሰው፡ ንኡድ፡ ክቡር፡ ነው።

፮፤ ዘገብረ፡ ሰማየ፡ ወምድረ።

ሰማይን፡ ምድርን፡ በፈጠረ።

ወባሕረ፡ ወኵሎ፡ ዘውስቴታ።

ባሕሩን፡ በባሕር፡ ያለውን፡ ሁሉ፡ የፈጠረ።

ዘየዐቅብ፡ ለጽድቅ፡ ዘለዓለም።

ለዘላለም፡ ስትነገር፡ የምትኖር፡ ሚጠትን፡ የሚጠብቃት፡ ማለት፤ የሚያጸናት፡ እሱ፡ ነው።

፯፤ ወይፈትሕ፡ ሎሙ፡ ለግፉዓን።

ለተበደሉ፡ ለትሩፋን፤ እንድም፡ ለተበደሉ፡ ሁሉ፡ የሚፈርድላቸው፡ እሱ፡ ነው።

ዘይሁቦሙ፡ሲሳዮሙ፡ ለርኁባን።

ለትሩፋን፤ እንድም፡ ለተራቡ፡ ሁሉ፡ ምግባቸውን፡ የሚሰጣቸው።

እግዚአብሔር፡ ይፈትሖሙ፡ ለሙቁሓን።

የታሰሩ፡ ትሩፋንን፤ እንድም፡ ማናቸውንም፡ የታሰሩትን፡ ሁሉ፡ የሚፈታ።

፰፤ እግዚአብሔር፡ ያነሥኦሙ፡ ለእለ፡ ወድቁ፤

በመከራ፡ የተያዙ፡ ትሩፋንን፤ እንድም፡ በመከራ፡ የተያዙ፡ ሌሎችንም፡ ከመከራ፡ የሚያድናቸው፡ እሱ፡ ነው።

እግዚአብሔር፡ ያጠብቦሙ፡ ለዕዉራን።

ዕዉራንን፡ የሚያራቅቃቸው፡ እግዚአብሔር፡ ነው። እንድም፡ ትሩፋንን፡ የሚያራቅቃቸው፡ እግዚአብሔር፡ ነው። ወኮኑ፡ ከመ፡ ዕዉራን፡ እንዲል፤ በባቢሎን፡ እንደ፡ ዕዉራን፡ ሆነው፡ ነበርና።

እግዚአብሔር፡ ያፈቅሮሙ፡ ለጻድቃን።

እግዚአብሔር፡ ትሩፋንን፤ እንድም፡ በቁሙ፡ ጻድቃንን፡ ይወዳቸዋል። ኢሳ፡ ፷፭፡ ፩። ሉቃ፡ ፲፰፡ ፵፫። ዮሐ፡ ፲፡ ፳፩።



፱፤ እግዚአብሔር፡የዐቅቦሙ፡ ለፈላስያን።

እግዚአብሔር፡ ትሩፋንን፤ እንድም፡ ስደተኞችን፡ ይጠብቃቸዋል።

ወይትዌከፎሙ፡ ለዕቤራት፡ ወለዕጓለ፡ ማውታ።

የትሩፋን፡ ባልቴቶችን፡ እናት፡ አባቱ፡ የሞቱበት፡ የድኻውን፡ ልጅ፤ እንድም፡ ሌሎቹን፡ ሁሉ፡ በረድኤት፡ የሚቀበላቸው፡ እሱ፡ ነው። እንድም፡ ይቀበላቸዋል።

ወያማስና፡ ፍኖተ፡ ኃጥኣን።

የባቢሎናውያንን፤ እንድም፡ የኃጥኣንን፡ ሁሉ፡ መንገዳቸውን፤ እንድም፡ ሥራቸውን፡ ያጠፋል።

፲፤ ይነግሥ፡ እግዚአብሔር፡ ለዓለም።

እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ እያደረገ፡ ለዘላለም፡ ነግሦ፡ ይኖራል።

አምላክኪ፡ ጽዮን፡ ለትውልደ፡ ትውልድ።

ኢየሩሳሌም፡ ፈጣሪሽ፡ እግዚአብሔር፡ ለዘላለም፡ የመንግሥት፡ ሥራ፡ ሲሠራ፡ ይኖራል። ኢሳ፡ ፶፪፡

## መዝሙር፡ ፻፵፮።

፩፤ ሰብሕዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ እስመ፡ ሠናይ፡ መዝሙር።

ስለ፡ ትሩፋን፡ ተናግሮታል፤ እግዚአብሔርን፡ አመስግኑት፤ እግዚአብሔርን፡ ማመስገን፡ ያማረ፡ የተወደደ፡ ነውና።

ወለአምላክነ፡ ሐዋዝ፡ ስብሐ።

ሐዋዝ፡ ስብሐም፡ ይላል፤ ፈጣሪያችንን፡ በጎ፡ ምስጋና፡ አመስግኑት። ሐዋዝ፡ ስቡሕ፤ ለፈጣሪያችን፡ ምስጋና፡ ማቅረብ፡ ያማረ፡ የተወደደ፡ ነውና። ሉቃ፡ ፩፡ ፳።

፪፤ የሐንጻ፡ እግዚአብሔር፡ ለኢየሩሳሌም።

እግዚአብሔር፡ ኢየሩሳሌምን፡ ከስብዓ፡ ዘመን፡ በኋላ፡ ያንጻታል።

ወያስተጋብእ፡ ዝርዎቶሙ፡ ለእስራኤል።

ዝርዋኒሆሙ፡ ሲል፡ ነው፤ ፋርስ፡ ባቢሎን፡ ጽርእ፡ ሜዶን፡ የተበተኑ፡ እስራኤልንም፡ ይሰበስባቸዋልና። ኢሳ፡ ፩-፹፯፡ ፲፭፡ ፲፱።

፫፤ ዘይፌውሶሙ፡ ለቍሱላነ፡ ልብ።

ቍስላን፡ ልብ፡ ትሩፋንን፤ እንድም፡ ማናቸውንም፡ ሁሉ፡ ከመከራ፡ የሚያድናቸው፡ እሱ፡ ነው።

ወያፀምም፡ ሎሙ፡ ቍስሎሙ።

መከራውንም፡ ያርቅላቸዋል።

፬፤ ዘይኌልቆሙ፡ ለከዋክብት፡ በምልኦሙ።

ከዋክብትን፡ በመላ፡ የሚቈጥራቸው፡ እሱ፡ ነው፤ አንድ፡ ሁለት፡ ሦስት፡ ብሎ።

2014 04 18

ወይፌውሶሙ ፡ ለቍሱላነ ፡ ልብ ፡ ወያስተጋብኦሙ ፡

ሁሉንም ፡ በየስማቸው ፡ የሚጠራ
ቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ዙሐል ፡ መሪህ ፡
አቀድ ፡ አቃርድ ፡ እያለ ፡ አቀድ ፡
ባምስት ፡ መቶ ፡ ባምስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፡ ከፀሐይ ፡ ከጨረቃ ፡ ጋራ ፡
ተራክቦ ፡ ያደርጋል ፤ ያጸልማታል ።
ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፳፮ ።

፭ ፡ ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዐቢይ ፡
ኃይሉ ።

እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ገናና ፡ ነው ፤
ኃይሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድም ፡
ገናና ፡ ነው ፤ ኃይሉ ፡ ስለ ፡ ተገለጸ
በት ፡ በኃይል ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ።

ወአልቦ ፡ ኍልቍ ፡ ለጥበቢሁ ።

ጥበቡ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስም ፡ ሀብቱ ፡ ፍጹም ፡ ነው ፤
ስለ ፡ ሀብቱ ፡ ብዛት ። ኢያ ፡ ፱ ፡ ፲ ።

፮ ፡ ያነሥኦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለየዋሃን ።

እግዚአብሔር ፡ በቁሙ ፡ የዋሃንን ፤
አንድም ፡ ትሑታንን ፡ ከመከራ ፡
ያድናቸዋል ።

ወያኀስሮሙ ፡ ለኃጥኣን ፡ እስከ ፡ ምድር ።

ኃጥአንን ፡ አንድም ፡ ባቢሎናው
ያንን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ እስ
ከ ፡ ማውረድ ፡ ደርሶ ፡ ያጠፋቸዋል ።
ኢሳ ፡ ፳፮ ፡ ፩ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፶፪ ።

፯ ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በአሚን ።

እግዚአብሔርን ፡ በሃይማኖት ፡ ጸን
ታችሁ ፡ አመስግኑት ።

ወዘምሩ ፡ ለአምላክነ ፡ በመሰንቆ ።

ለፈጣሪያችንም ፡ መሰንቆ ፡ እየመ
ታችሁ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።

፰ ፡ ዘይገለብቦ ፡ ለሰማይ ፡ በደመና ።

ሰማዩን ፡ በደመና ፡ የሚሸፍነው ፡
እሱ ፡ ነው ።

ወያስተዴሉ ፡ ክረምተ ፡ ለምድር ።

ዝናምን ፡ ለምድር ፡ ያዘጋጇ ፡ እሱ ፡
ነው ። ዘፍ ፡ ፱ ፡ ፲፬ ። ኤር ፡ ፭ ፡ ፳፬ ። ግብ ፡
፲፬ ፡ ፲፯ ።

፱ ፡ ዘያበቍል ፡ ሣዕረ ፡ ውስተ ፡ አድባር ።

በየተራራው ፡ ሣርን ፡ የሚያበቅል ፡
እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ አንድም ፡
ዝናም ፡ ነው ።

ወሐመልማለ ፡ ለቅኔ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

እኽሉን ፡ ተክሉን ፡ የሚያበቅል ፡
እሱ ፡ ነው ፤ ለቅኔ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ለሚገዛ ፡ ለሰው ፡ ያን ፡ እየ
በላ ፡ ለመገዛት ። አንድም ፡ ለሰው ፡
ለሚገዛ ፡ ለእንስሳ ፡ ልምላሜውን ፡
የሚያበቅል ፡ እሱ ፡ ነው ።

፲ ፡ ዘይሁቦሙ ፡ ሲሳዮሙ ፡ ለእንስሳ ።

ለእንስሶች ፡ ምግባቸውን ፡ የሚሰ
ጣቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ በእንስሳ ፡
ሁሉን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወለዕጕለ ፡ ቋዓት ፡ እለ ፡ ይጼውዕዎ ።

ለሚለምኑት ፡ ለዕጕለ ፡ ቋዓት ፡ ም
ግባቸውን ፡ የሚሰጣቸው ፡ እሱ ፡
ነው ፤ እሱ ፡ ባወቀ ፡ ይለምኑታልና ።



አንድም ፡ እለ ፡ ኢይጼውዕዎ ፡ ይላ
ል ፤ ለማይለምኑት ፡ ለዕጕለ ፡ ቋዓ
ት ፡ ምግባቸውን ፡ የሚሰጣቸው ፡
እሱ ፡ ነው ። ይህስ ፡ እንደ ፡ ምን ፡
ነው ፡ ቢሉ ፤ ቋዕ ፡ ሲወለድ ፡
ፍሕም ፡ መስሎ ፡ ይወለዳል ፤ እ
ናት ፡ አባቱ ፡ ምን ፡ ጕድ ፡ ተወ
ለደብን ፡ ብለው ፡ ትተዉት ፡ ይሄ
ዳሉ ፤ ሲርበው ፡ ጧ ፡ ጧ ፡ እያደረገ ፡
አፉን ፡ ይከፍተዋል ፤ ተሐዋስያን ፡
ርጥበት ፡ ሲሹ ፡ ይገባሉ ፤ ግጥም ፡
አድርጎ ፡ ይዞ ፡ ይመገባቸዋል ፤
አንድም ፡ ተሐዋስያን ፡ ሲያልፉ ፡
በእስትንፋሱ ፡ እየሳበ ፡ እስከ ፡
፵ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ይመገባቸዋል ፤
ከአርባ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ጸጕር ፡ ያበ
ቅላል ፤ በመልክ ፡ ይመስላቸዋል ፤
ተመልሰው ፡ ይረዱታል ። ኢዮ ፡ ፴፰ ፡
፵፩ ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፳፬ ።

፲፩ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ኀይለ ፡ ፈረስ ።

የፈረስ ፡ ኀይል ፡ አይወድም ።

ወኢይሠምር ፡ በአቍያጸ ፡ ብእሲ ።

የሰውን ፡ ጭን ፡ አይወድም ፡ ግል
ት ፤ ፈረስ ፡ በዋዲ ፡ ጭን ፡ አግባቂ ፡
ሰው ፡ አይወድም ፤ በዚህ ፡ ደስ ፡
አይለውም ።

፲፪ ፡ ይሠምር ፡ እግዚአብሔር ፡ በእለ ፡
ይፈርህዎ ።

እግዚአብሔር ፡ የሚፈሩትን ፡ የሚ
ያመልኩትን ፡ ይወዳል ፤ በዚህ ፡
ደስ ፡ ይለዋል ።

ወበእለ ፡ እለ ፡ ይትዌከሉ ፡ በምሕረቱ ።

በቸርነቱ ፡ የሚያምኑትን ፡ ይወዳል ፤
በሚያምኑበት ፡ ያድራል ፡ ደስ ፡
ይለዋል ።

## መዝሙር ፡ ፻፵፯ ።

፩ ፡ ትሴብሖ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለእግዚአብ
ሔር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ እግ
ዚአብሔርን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ገጸር ፡
ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ያመሰግኑታል ።

ወሰብሒዮ ፡ ለአምላክኪ ፡ ጽዮን ።

በከተማ ፡ ያሉ ፡ ሰዎችም ፡ ፈጣሪ
ያችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰ
ግኑታል ። ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፲፩ ፡ ፳፮ ።

፪ ፡ እስመ ፡ አጽንዐ ፡ መናሥግተ ፡ ኆኃትኪ ።

ኀያላንኪ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የኀያላንሽን ፡
ሥልጣን ፡ በረድኤት ፡ አጽንቷልና ።

ወባረኮሙ ፡ ለውሉድኪ ፡ በውስቴትኪ ።

በውስጥሽ ፡ ያሉ ፡ ልጆችሽን ፡ አከ
ብሯቸዋል ፤ አብዝቷቸዋልና ።

፫ ፡ ዘረሰየ ፡ ሰላመ ፡ ለበሓውርትኪ ።

በውስጥሽ ፡ ላሉ ፡ አህጉርም ፡ አን
ድነት ፡ ፍቅርን ፡ አድርጓልና ።

2014 04 18

ወእጽገቢኪ ፡ ቄቅሐ ፡ ሥርናይ ።

የተፈተገውን ፡ ያፈራውን ፡ ስንዴ ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ አሰኝቶሻልና ፡ ሰብሐዮ ። ኢሳ ፡ ፷፪ ፡ ፰ ። ፶፰ ፡ ፲፫ ። ሕዝ ፡ ፲፮ ፡ ፲፫ ።

፲፭ ፡ ዘይፌኑ ፡ ቃሎ ፡ ለምድር ።

ፀሐይን ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያወጣ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወፍጡነ ፡ ይረውጽ ፡ ነቢቡ ።

ፀሐይ ፡ ባሬቱ ፡ ማእዘን ፡ ፈጥኖ ፡ ይደርሳል ፡ ማለት ፡ ደክሞ ፡ ከመንገድ ፡ አያድርም ። አንድም ፡ ብርሃኑ ፡ ፈጥኖ ፡ ይደርሳል ፡ ማለት ፤ ፀሐይ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ይደርሳልና ።

፲፮ ፡ ዘይሁብ ፡ በረደ ፡ ከመ ፡ ፀምር ።

በረድን ፡ እንደ ፡ ፀምር ፡ አድርጎ ፡ የሚሰጥ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወይዘርዎ ፡ ለጊሜ ፡ ከመ ፡ ሐመድ ።

ጉሙን ፡ እንደ ፡ ትቢያ ፡ የሚመል ሰው ፡ እሱ ፡ ነው ።

፲፯ ፡ ወያወርድ ፡ በረደ ፡ ከመ ፡ ፍተታት ።

በረዱን ፡ በክፍል ፡ በክፍል ፡ አድርጎ ፡ የሚያወርድ ፡ እሱ ፡ ነው ። መላእክት ፡ በደመና ፡ አይበት ፡ ቋጥረው ፡ በነፋስ ፡ ወደል ፡ ጋዝ ፡ ጭነው ፡ ሲያመጡት ፡ ቋጥኝ ፡ ቋጥኝ ፡ ያኸላል ፤ ኋላ ፡ በእሳት ፡ ድጅኖ ፡ እየከሰከሱ ፡ እያደቀቁ ፡ በክፍል ፡ በክፍል ፡ ይሰጹታልና ።

ወመኑ ፡ ይትቃወሞ ፡ ለቍሩ ።

ውርጩን ፡ ማን ፡ በተቃወመው ፡ ነበር ። ኢዮ ፡ ፴፯ ፡ ፲ ።

፲፰ ፡ ይፌኑ ፡ ቃሎ ፡ ወይመስዎ ።

እሱ ፡ ፀሐይን ፡ ልኮ ፡ ያቃጥለዋል ፡ እንጂ ፤ ባያቃጥለው ፡ ማን ፡ በተቃወመው ፡ ነበር ።

ይነፍኅ ፡ መንፈሶ ፡ ወያውሕዝ ፡ ማያተ ።

ደመና ፡ የያዘ ፡ ነፋስን ፡ ያመጣል ፤ ደመናውም ፡ ዝናምን ፡ ያዘንማል ። አንድም ፡ (ዘይፌኑ ፡ ቃሎ) ፡ ለትሩፋን ፡ ረድኤቱን ፡ የሚሰጥ ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወፍጡነ) ፡ ሚጠቱ ፡ ፈጥኖ ፡ ይደረጋል ። ፍጡነ ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። (ዘይሁብ) ፡ የዘሩባቤልን ፡ ጦር ፡ እንደ ፡ ፀምር ፡ አድርጎ ፡ የሚያስንሣው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ጦሩን ፡ ሲወለውሉት ፡ ይፈልቃልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። (ወይዘርዎ) ፡ መከራ ፡ ሥጋን ፡ የሚያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወያወርድ) ፡ ጦሩን ፡ አንተ ፡ በዚህ ፡ ውረድ ፡ አንተ ፡ በዚህ ፡ ውጣ ፡ እያለ ፡ በክፍል ፡ የሚሰደው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወመኑ) ፡ ረድኤቱን ፡ ሰዶ ፡ አጠፋው ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ ባያጠፋው ፡ መከራ ፡ ሥጋን ፡ ማን ፡ በተቃወመው ፡ ነበር ። (ይፌኑ ፡ ቃሎ) ፡ ረድኤቱን ፡ ለነቢያት ፡ ለካህናት ፡ ይሰጣል ። (ይነፍኅ) ፡ ነቢያት ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፤ ካህናት ፡ ትምህርት ፡ ያስተምራሉ ። አንድም ፡ (ዘይፌኑ) ፡ ልጁን ፡ ለኩነተ ፡ ሥጋ ፡ የሰጠ ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወፍጡነ) ፡ ወንጌል ፡ ባጭሩ ፡ ማእዘን ፡ ትደርሳለች ፤ ጸልዩ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ይሩጽ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ።

(ዘይሁብ) ፡ ስብከተ ፡ ሐዋርያትን ፡ እንደ ፡ ፀምር ፡ አድርጎ ፡ የሚያስንሣ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ኑፋቄ ፡ የሌለው ፡ ነውና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። (ወይዘርዎ) ፡ የነፍሱን ፡ መከራ ፡ የሚያጠፋ ፡ እሱ ፡ ነው ። (ዘያወርድ) ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የሚሰጥ ፡ እሱ ፡ ነው ። ወበከመ ፡ ይደልዎ ፡ ይበቍዖ ፡ እንዲል ። ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚሰጥ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ጽናት ፡ እንደ ፡ አእምሮ ፡ ስፋት ፡ ነውና ። (ወመኑ) ፡ መከራ ፡ ነፍሱን ፡ ማን ፡ ባጠፋው ፡ ነበር ። (ይፌኑ) ፡ እሱ ፡ ልጁን ፡ በሥጋ ፡ ሰዶ ፡ አጠፋው ፡ እንጂ ፤ እንዲህ ፡ ባያጠፋው ፡ ማን ፡ ባጠፋው ፡ ነበር ። (ይነፍኅ) ፡ ልጅነትን ፡ ለሐዋርያት ፡ ይሰጣል ፤ በሐዋርያት ፡ አድሮ ፡ ያስተምራል ። ልጅነት ፡ ሥጋው ፡ ደሙ ፡ እንዲሰጥ ፡ ትምህርት ፡ እንዲነገር ፡ ይደረጋል ።

፲፱ ፡ ዘነገረ ፡ ቃሎ ፡ ለያዕቆብ ።

ለሁሉቱ ፡ ነገድ ፡ ቃሉን ፡ የሰጠ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ፍትሖ ፡ ወኵነኔሁ ፡ ለእስራኤል ።

ላሥሩም ፡ ነገድ ፡ ዘጠኙን ፡ ሕግጋት ፡ የሰጠ ፡ እሱ ፡ ነው ። አንድም ፡ ወነበቦ ፡ ወነበቦ ፡ ያለውን ፡ ለያዕቆብ ፡ የሰጠ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ኢታምልክንም ፡ ለእስራኤል ፡ የሰጠ ፡ እሱ ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፰ ። ሚል ፡ ፵፩ ፡ ፲፯ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፪ ። ዘዳ ፡ ፬ ፡ ፮-፰ ።

፳ ፡ ወኢገብረ ፡ ከማሁ ፡ ለባዕዳን ፡ አሕዛብ ።

ለሌሎቹ ፡ አሕዛብ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አላደረገም ፤ ኢታምልክን ፡ ዘጠኙን ፡ ሕግጋት ፡ አልገለጸላቸውም ።

## መዝሙር ፡ ፻፵፰ ።

፩ ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምሰማያት ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከሰማይ ፡ አብነት ፡ ነሥታችሁ ፡ አንድም ፡ ሰማያውያን ፡ እላንት ፡ አመስግኑት ። አንድም ፡ በሰማይ ፡ መልቶ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

ይሴብሕዎ ፡ በአርያም ።

የምታመሰግኑትም ፡ እላንት ፡ ብቻ ፡ አይደላችሁም ፤ ከሰማይ ፡ ያሉ ፡ መላእክት ፡ ያመሰግኑታል ።

2014 04 18

፪ ፤ ይሴብሕዎ ፡ ዙሎሙ ፡ መላእክቲሁ ።

ሊቃን ፡ መላእክት ፡ ሁሉ ፡ ያመስ
ግኑታል ።

ይሴብሕዎ ፡ ዙሉ ፡ ኀይሉ ።

ኀይሉን ፡ የሚገልጽባቸው ፡ ሰራ
ዊተ ፡ መላእክት ፡ ሁሉ ፡ ያመስግ
ኑታል ።

፫ ፤ ይሴብሕዎ ፡ ፀሓይ ፡ ወወርኅ ።

ፀሓይ ፡ ጨረቃም ፡ ያመስግኑታል ።

ይሴብሕዎ ፡ ዙሉ ፡ ከዋክብት ፡ ወብርሃን ።

ከዋክብት ፡ ሁሉ ፡ ለይኩን ፡ ብሎ ፡
የፈጠረው ፡ ብርሃንም ፡ ያመስግኑ
ታል ። እንድም ፡ ከዋክብት ፡ ዘብር
ሃን ፡ ይላል ፤ ብርሃን ፡ ያላቸው ፡ ከ
ዋክብት ፡ ያመስግኑታል ። ምነው ፡
ብርሃን ፡ የሌላቸው ፡ ከዋክብት ፡
አሉና ፡ እንዲህን ፡ አለ ፡ ቢሉ ፤
እንደ ፡ ፈርጽ ፡ ሆነው ፡ ብርሃን ፡
ያነሳቸው ፡ ለሰማይ ፡ ጌጥ ፡ ይሁኑ ፡
ብሎ ፡ የፈጠራቸው ፡ በማእከለ ፡
ሰማይ ፡ የሚኖሩ ፡ ልኩአን ፡ ከዋከ
ብት ፡ አሉና ። እንድም ፡ በቁሙ ፡
አቀድ ፡ የሚባል ፡ ብርሃን ፡ የሌ
ለው ፡ ጸሊም ፡ ኮከብ ፡ አለ ፤ ባ
፳፱ ፡ ባ፳፱ ፡ ዘመን ፡ ከፀሓይ ፡
ጋራ ፡ ተራክቦ ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡
ያጸልማታልና ።

፬ ፤ ይሴብሕዎ ፡ ሰማየ ፡ ሰማያት ።

ሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ ያመስግኑታል ።

ማይኒ ፡ ዘመልዕልተ ፡ ሰማያት ።

ከጠፈር ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ሐኖስም ፡
ያመስግነዋል ፤ ምነው ፡ ሰማያት ፡
ብሎ ፡ አበዛ ፡ አንድ ፡ ጠፈር ፡ አይ
ደለምን ፡ ቢሉ ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡
አለውና ።

፭ ፤ ይሴብሑ ፡ ለስመ ፡ እግዚአብሔር ።

እሊህ ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ስም ፡ ምስጋና ፡ ያቀርባሉ ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ወኮኑ ።

እሱ ፡ ይፈጠሩ ፡ ብሏልና ፤ እነሱ
ም ፡ ተፈጥረዋልና ።

ወውእቱ ፡ አዘዘ ፡ ወተፈጥሩ ።

ይቤ ፡ ያለውን ፡ አዘዘ ፡ ኮኑ ፡ ያለ
ውን ፡ ተፈጥሩ ፡ ብሎ ፡ ገለጸው ፤
እሱ ፡ ፈጣሪ ፡ እለሱ ፡ ፍጡራን ፡
ናቸውና ።

፮ ፤ ወአቀሞሙ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡
ዓለም ።

ለዘላለሙ ፡ አጸናቸው ።

ትእዛዘ ፡ ወሀቦሙ ፡ ወኢኀለፉ ።

ሥራት ፡ ሠራላቸው ፤ ወሰን ፡ ወሰኑ
ላቸው ፤ ከሠራላቸው ፡ ሥርዐት ፡
አልወጡም ፤ ከወሰኑላቸው ፡ ወሰን ፡
አላለፉም ።

፯ ፤ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምድር ።

በምድር ፡ መልቶ ፡ ያለ ፡ እግዚአ
ብሔርን ፡ አመስግኑት ። እንድም ፡
ምድራውያን ፡ እናንት ፡ ከምድር ፡
አብንት ፡ ነሥታችሁ ፡ አመስግኑት ።

አኪስትኒ ፡ ወኵሉ ፡ ቀላያት ።

ምንጮች ፡ ናቸው ፤ ኪስ ፡ ይላል ፡
በዐረብ ፡ ምንጭ ፡ ሲል ። አከይስት ፡
ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እባቦች ፤ እባብ ፡
ከውሃ ፡ ምን ፡ ሊያደርግ ፡ ይሄዳል ፡
ቢሉ ፡ ኑሮውን ፡ በውሃ ፡ ያደረገ ፡
አለና ። ታላላቆች ፡ ወንዞችም ፡
ሁሉ ፡ ያመስግኑታል ። ፮፡ቢ ።

፰ ፤ እሳት ፡ ወበረድ ፡ ወአስሐትያ ፡ ወሐ
መዳ ፡ መንፈስ ፡ ዐውሎ ።

በቁሙ ፡ እሳት ፤ በቁሙ ፡ በረድ ፤
አስሐትያ ፡ ውርጭ ፤ ወይትፈለጥ ፡
ከመ ፡ እንተ ፡ ማህው ፡ እንዲል ።
ሐመዳ ፡ ዋግ ፡ ቀቅ ፤ መንፈስ ፡ ዐ
ውሎ ፡ ጥቅል ፡ ነፋስ ፤ እሊህም ፡
ያመስግኑታል ።

ዘይገብር ፡ ነቢቦ ።

ዘገብሮሙ ፡ ነቢቦ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
ተናግሮ ፡ የፈጠራቸው ፡ ሁሉ ፡
ያመስግኑታል ።

፱ ፤ አድባርኒ ፡ ወኵሉ ፡ አውግር ።

ተራራው ፡ ኰረብታው ፡ ሁሉ ።

ዕፀውኒ ፡ ዘይፈሪ ፡ ወኵሉ ፡ አርዝ ።

የሚያፈራውም ፡ የማያፈራውም ፡
ሁሉ ፤ ይህስ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ የሚ
በላው ፡ የማይበላውም ፡ ዕፅ ፡ ሁሉ ።

፲ ፤ አራዊትኒ ፡ ወኵሉ ፡ እንስሳ ።

የማይበሉ ፡ አራዊት ፡ የሚበሉ ፡
እንስሳት ፡ ሁሉ ፤ ይህስ ፡ አይደለም ፤
ፈረስ ፡ በቅሎም ፡ አይበሉምና ፤
አራዊትን ፡ ይበላሉ ፡ ብሎ ፤ አራ
ዊት ፡ የሚላቸው ፡ ብርንዶ ፡ ጕር
ሠው ፤ በጥንት ፡ ከስክሰው ፡ ደም ፡
ጠጥተው ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ፤ እን
ስሳት ፡ የሚባሉ ፡ ግር ፡ ነጭተው ፡
ውሃ ፡ ተጐንጭተው ፡ የሚኖሩ ፡
ናቸው ፡

ዘይትሐወስ ፡ እዕዋፍ ፡ ዘይሰርር ።

በልብ ፡ የሚሳቡ ፡ በክንፍ ፡ የሚ
በሩ ፡ አዕዋፍ ። ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፩ ።

፲፩ ፤ ነገሥተ ፡ ምድርኒ ፡ ወኵሉ ፡ አሕዛብ ።

በምድር ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታትም ፡
አሕዛብም ፡ ሁሉ ። ሰውን ፡ በኋላ ፡
አደረገው ፡ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ገገር ፡
ሰው ፡ ነውና ፡ ጕዳይ ፡ ያለው ፡
ሰው ፡ ምግቡን ፡ መጠጡን ፡ አዘ
ጋጅቶ ፡ እንዲጠራ ።

መላእክትኒ ፡ ወኵሉ ፡ መኳንንተ ፡ ምድር ።

የሰው ፡ አለቆች ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡
መኳንንት ፡ ሁሉ ።

፲፪ ፤ ወራዙትኒ ፡ ወደናግል ።

ወራዙቱም ፡ ደናግልም ፤ ወራዙቱ ፡
ንጽሐ ፡ ጠባይዕ ፡ ያደረባቸው ፡
ደናግል ፡ ያላደረባቸው ።

ሊቃናትኒ ፡ ወመሓዛት ።

ሽማግሎችም ፡ ደጐቦችም ።



2014 04 18

፲፫ ፡ ይሴብሑ ፡ ለስመ ፡ እግዚአብሔር ።

እሊህ ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ያመስግኑት ።

እስመ ፡ ተለዐለ ፡ ስሙ ፡ ለባሕቲቱ ።

ስሙ ፡ ለብቻው ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏል ፡ ከብሯል ፡ ገኗልና ።

ይገንዩ ፡ ሎቱ ፡ በሰማይ ፡ ወበምድር ።

ነግሣለትና ፡ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ መላ እክት ፡ በምድር ፡ ያሉ ፡ ደቂቀ ፡ አዳም ፡ ለሱ ፡ ይገዛሉ ።

፲፬ ፡ ወያሌዕል ፡ ቀርነ ፡ ሕዝቡ ።

የሕዝቡን ፡ ሥልጣን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ።

ወስብሐተ ፡ ኵሉ ፡ ጻድቃኑ ።

የካህናቱንም ፡ ምስጋና ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ።

ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ዘቅሩብ ፡ ሎቱ ።

ሕዝቡም ፡ ጻድቃኑም ፡ ያልኋቸው ፡ ለሱ ፡ አቅራቢያ ፡ ባለሟሎቹ ፡ የሚ ሆኑ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። እንድም ፡ (ወያሌዕል) ፡ የነቢያት ፡ የካህናትን ፡ ሥልጣን ፡ ምስጋና ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፡ (ለደቂቀ) ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ማድረጉም ፡ ባለሟሎቹ ፡ አቅ ራቢያዎቹ ፡ የሚሆኑ ፡ የእስራኤ ልን ፡ ልጆች ፡ ሊያስተምሩ ፡ ነው ።

## መዝሙር ፡ ፻፵፱ ።

፩ ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስብሐተ ፡ ሐዲሰ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ እግዚ አብሔርን ፡ እንግዳ ፡ ምስጋና ፡ አመ ስግኑት ።

ስብሐቲሁ ፡ በማኅበረ ፡ ጻድቃን ።

ይኸውም ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ በመላእክት ፡ ጉባኤ ፡ የሚመሰገ ነው ፡ ምስጋና ፡ ነው ።

፪ ፡ ይትፈሣሕ ፡ እስራኤል ፡ በፈጣሪሁ ።

እስራኤል ፡ በፈጣሪው ፡ አምኖ ፡ በተሠራለት ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

ወደቂቀ ፡ ጽዮን ፡ ይትሐሠዩ ፡ በንጉሦሙ ።

ትሩፋንም ፡ በንጉሣቸው ፡ በዘሩባ ቤል ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። እንድም ፡ በንጉሣቸው ፡ በክርስቶስ ፡ አምነው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። ኢዮ ፡ ፪ ፡ ፳፫ ።

፫ ፡ ወይሴብሑ ፡ ለስሙ ፡ በትፍሥሕት ።

ስሙን ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ያመሰግ ናሉ ።

በከበሮ ፡ ወበመዝሙር ፡ ይዜምሩ ፡ ሎቱ ።

ቀንዳውን ፡ በገናውን ፡ እየመቱ ፡ ለሱ ፡ ምስጋና ፡ ያቀርባሉ ።

፬ ፡ እስመ ፡ ሠምረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሕዝቡ ።

እግዚአብሔር ፡ ወገኖቹን ፡ ይወዳ ልና ። እንድም ፡ በወገኖቹ ፡ አድሮ ፡ መመለክን ፡ ይወዳልና ።



ወያሌዕሎሙ ፡ ለየዋሃን ፡ በአድኅኖቱ ።

የዋሃንንም ፡ በትድግናው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋቸዋልና ።

፭ ፡ ይትሜክሑ ፡ ጻድቃን ፡ በክብሩ ።

ትሩፋን ፡ ከሱ ፡ በቀገኘ ፡ ክብር ፡ ይከብራሉ ። እንድም ፡ ከሱ ፡ በተገ ኘ ፡ ክብር ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። እም ከመ ፡ አድማዕነ ፡ መንግሥተ ፡ ንት ሜክሕ ፡ እንዲል ።

ወይትሐሠዩ ፡ በዲበ ፡ ምስካቢሆሙ ።

በመዓልት ፡ በሌሊት ፡ በመኝታ ቸው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፮ ፡ ወያሌዕልዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በጕራ ዒቶሙ ።

እግዚአብሔርን ፡ በቃላቸው ፡ ያመ ሰግኑታል ።

ሰይፍ ፡ ዘክልኤ ፡ አፉሁ ፡ ውስተ ፡ እደዊሁ ።

ሁለት ፡ ልሳን ፡ ያለው ፡ ሰይፍ ፡ በእጁ ፡ ተይዟል ፡ ማለት ፤ ሁለት ፡ ግብር ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ ባሕ ርዩ ፡ አለ ።

፯ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ በቀለ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ።

ባቢሎናውያንን ፡ ተበቅሎ ፡ ያጠፋ ቸው ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ይዛለፎሙ ፡ ለሕዝብ ።

በሕዝቡም ፡ ይፈርድባቸው ፡ ዘንድ ።

፰ ፡ ወከመ ፡ ይእስሮሙ ፡ ለነገሥቶሙ ፡ በመዋቅሕት ።

ነገሥታቱን ፡ በእግር ፡ ብረት ፡ ያስ ራቸው ፡ ዘንድ ።

ወለክቡራኒሆሙ ፡ በእደ ፡ ሰናስለ ፡ ኀጺን ።

ሥዩማኑን ፡ መኳንንቱን ፡ በሰንሰ ለት ፡ ያስራቸው ፡ ዘንድ ። ናሆ ፡ ፫ ፡ ፲ ።

፱ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ኵነኔ ፡ ዘጽሑፍ ፡ ላዕ ሌሆሙ ።

በርሳቸው ፡ የተጻፈውን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ።

ክብር ፡ ይእቲ ፡ ዛቲ ፡ ለኵሉ ፡ ጻድቃኑ ።

ወስብሐ ፡ ዓም ፡ ኀሊቆ ፡ ብላ ፡ በባቢ ሎናውያን ፡ መቅሠፍትን ፡ የምታ መጣ ፡ ሥልጣኑ ፡ ለትሩፋን ፡ ክብር ፡ ናት ፤ ምነው ፡ ፪ ፡ ተናግሮ ፡ ፩ ፡ አመጣ ፡ ቢሉ ፤ እሊያን ፡ ባጠፋበት ፡ ሥልጣኑ ፡ እሊህን ፡ አድኖበታልና ። እንድም ፡ (ሰይፍ ፡ ዘክልኤ ፡ አፉሁ) ፡ ሁለት ፡ ግብር ፡ ያለው ፡ ሥጋው ፡ ደሙ ፡ በካህናት ፡ እጅ ፡ ይሰጣል ። መንሱትኬ ፡ ውእቱ ፡ ነሚአ ፡ ሥጋ ሁ ፡ በድፍረት ፡ ወተመጥዎ ፡ ደሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ኀፍረት ፡ እንዘ ፡ ቦ ፡ ላዕ ሌሁ ፡ ነውረ ፡ ኀጢአት ፡ ለእመ ፡ ኢያእመረ ፡ ሥጋ ፡ እግዚእነ ፡ በነ ፍሱ ፡ በልዐ ፡ ደይኖ ፡ ወመቅሠ ፍቶ ፡ ለርእሱ ፡ እንዲል ።

(ከመ ፡ ይግበር) ፡ ባልበቁ ፡ ሰዎች ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ። (ወከመ ፡ ይዛለ ፎሙ) ፡ ሳይበቁ ፡ በሚቀበሉ ፡ በሕ ዝቡ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ። (ወከመ ፡ ይእስሮሙ) ፡ ሳይበቁ ፡ በሚቀበሉ ፡ በሚያቀብሉ ፡ በሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡

2014 04 18

ይፈርድ ፡ ዘንድ ። (ወለክቡራኒሆሙ) ፡ ሳይበቁ ፡ በሚቀበሉ ፡ በሚያቀብሉ ፡ በጸጸሳት ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ። (ከመ ፡ ይግበር) ፡ መንስ ትኬ ፡ ውእቱ ፡ ተብሎ ፡ በርሳቸው ፡ የተነገረውን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ። (ክብር ፡ ይእቲ) ፡ ሳይበቁ ፡ በሚቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ፍዳ ፡ የሚያመጣ ፡ ሥጋው ፡ ደሙ ፡ በቅተው ፡ ለሚቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ክብር ፡ ነውና ። እንድም ፡ (ሰይፍ ፡ ዘክልኤ ፡ አፉሁ) ፡ ሁለት ፡ ግብር ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ በባሕርዩ ፡ አለ ። (ከመ ፡ ይግበር) ፡ ያላመኑ ፡ አሕዛብን ፡ ተበቅሎ ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ። (ወከመ ፡ ይዛሥሮሙ) ፡ ያላመኑትን ፡ ይዘልፋቸው ፡ ዘንድ ። (ወከመ ፡ ይእስሮሙ) ፡ ነገሥተ ፡ አሕዛብን ፡ በእግር ፡ ብረት ፡ ያስራቸው ፡ ዘንድ ፡ (ወለክቡራኒሆሙ) ፡ ካህናተ ፡ ጣዖቱንም ፡ በፍንጅ ፡ ያስራቸው ፡ ዘንድ ። (ከመ ፡ ይግበር) ፡ ሐሩ ፡ እምኔየ ፡ ርጉማን ፡ ተብሎ ፡ የተነገረውን ፡ በሳቸው ፡ ያደርስ ፡ ዘንድ ። (ክብር ፡ ይእቲ) ፡ ባላመኑ ፡ ፍዳ ፡ የሚያመጣ ፡ ሥልጣን ፡ ላመኑ ፡ ክብር ፡ ነው ፤ ሐሩ ፡ እምኔየ ፡ በሚልበት ፡ ቃል ፡ ንዑ ፡ ኀቤየ ፡ ይልበታልና ።

## መዝሙር ፡ ፻፶ ።

፩ ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በቅዱሳኑ ።

ሰለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናገሮታል ፤ እግዚአብሔርን ፡ ቅዱሳኑ ፡ እላንት ፡ አመስግኑት ። እንድም ፡ በመዳኛቹ ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ። እንድም ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡ የሚመሰገን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እያላችሁ ፡ አመስግኑት ።

ሰብሕዎ ፡ በጽንዐ ፡ ኀይሉ ።

ጽንዕ ፡ ኀያል ፡ እያላችሁ ፡ አመስግኑት ።

፪ ፡ ሰብሕዎ ፡ በክሂሎቱ ።

ከሃሊ ፡ እያላችሁ ፡ አመስግኑት ።

ሰብሕዎ ፡ በከመ ፡ ብዝኀ ፡ ዕበዩ ።

ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ እያላችሁ ፡ አመስግኑት ።

፫ ፡ ሰብሕዎ ፡ በቃለ ፡ ቀርን ።

ነጋሪት ፡ እየመታችሁ ፡ አመስግኑት ።

ሰብሕዎ ፡ በመዝሙር ፡ ወበመሰንቆ ።

መሰንቆውን ፡ እየመታችሁ ፡ አመስግኑት ።

፬ ፡ ሰብሕዎ ፡ በከበሮ ፡ ወበትፍሥሕት ።

ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ ቀንዳውን ፡ እየመታችሁ ፡ አመስግኑት ።



ሰብሕዎ ፡ በአውታር ፡ ወበእንዚራ ።

አውታር ፡ ጥብሏቃና ፡ ይባላል ፤ ሙቶ ፡ እምሳ ፡ አውታር ፡ ያለው ፡ ነው ፤ በዐፄ ፡ መለከ ፡ ሰገድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሀገራችን ፡ መጥቶ ፡ ነበረ ፤ እንዚራ ፡ ተራ ፡ በገና ፡ ነው ፤ ያን ፡ እየመታችሁ ፡ አመስግኑት ።

፭ ፡ ሰብሕዎ ፡ በጸናጽል ፡ ዘሠናይ ፡ ቃሉ ።

ድምፁ ፡ ያማረ ፡ ናቁስ ፡ ይባላል ፤ እንደ ፡ መረዋት ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ከፊላሻ ፡ ቤት ፡ ይገኛል ፡ ይህን ፡ እየመታችሁ ፡ አመስግኑት ።

ሰብሕዎ ፡ በጸናጽል ፡ ወበይባቤ ።

ተራ ፡ ጸናጽል ፡ እየመታችሁ ፡ በዩዱም ፡ ምስጋና ፡ አመስግኑት ።

፮ ፡ ኵሉ ፡ ነፍስ ፡ ይሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እላንት ፡ ብቻ ፡ አይደላችሁም ፤ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግነዋል ። ይህን ፡ ቢቴጥሩት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ይሆናል ፤ የመቶ ፡ አምሳው ፡ መዝሙር ፡ ምሳሌ ።

## ውዕእ ፡ እምትልቀ ።

፩ ፡ ንኡስ ፡ አነ ፡ እምአኀውየ ።

በኀልያድ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግሮታል ፤ ውዕእ ፡ ምትልቀ ፡ ይለዋል ። ዐሥራ ፡ አንደኛ ፡ አርእስት ፡ ተብሎ ፡ አይቈጠርም ።

ከወንድሞቼ ፡ ይልቅ ፡ ታናሽ ፡ ነበርሁ ።

ወወሬዛ ፡ በቤተ ፡ አቡየ ።

ባባቴ ፡ በእሴይም ፡ ቤት ፡ ደቦል ፡ ሕፃን ፡ ነበርሁ ።

ወእረዒ ፡ አባግዐ ፡ አቡየ ።

ያባቴን ፡ በጎች ፡ እጠብቅ ፡ ነበር ።

፪ ፡ እደውየ ፡ ይገብራ ፡ መሰንቆ ።

እጆቼም ፡ መሰንቆ ፡ ይመቱ ፡ ነበረ ።

ወአጻብዕየ ፡ ያስተዋድዳ ፡ መዝሙረ ።

ጣቶቼም ፡ በገናውን ፡ እያስማሙ ፡ ይደረድሩ ፡ ይመቱ ፡ ነበር ።

፫ ፡ መኑ ፡ ነገሮ ፡ ለእግዚእየ ።

ለጌታዬ ፡ የኔን ፡ ነገር ፡ ማን ፡ ነገረው ።

ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወውእቱ ፡ ሰምዐ ።

እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ፡ እሱ ፡ ሰማኝ ፡ እንጂ ፡ ማን ፡ ነገረው ። ከዚያ ፡ መኑ ፡ ነገሮ ፡ አለ ፤ ከዚህ ፡ ውእቱ ፡ ሰምዐኒ ፡ አለ ፤ እንደምን ፡ ይመቻል ፡ ቢሉ ፤ ለምኖት ፡ ብዙ ፡ የሚያደርግለት ፡ አለና ፡ ውእቱ ፡ ሰምዐኒ ፡ አለ ፤ ሳይለም ፡ ነው ፡ መንግሥትን ፡ ሰጥቶታልና ፡ መኑ ፡ ነገሮ ፡ አለ ።

2014 04 18

ወሴቀ፡ፈነወ፡መልአኮ፡ወአድኀነ ።

እሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልእክ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ ልኮ ፡ እኔን ፡ ከነልያድ ፡ እጆቻኝ ፡ እንደም ፡ ሳሙ ኤልን ፡ ልኮ ፡ ከንደት ፡ አዳነኝ ።

፪፤ ወነሥአኒ፡እምአባግዐ፡አቡየ ።

የአባቴን ፡ በጎች ፡ ከምጠብቅበት ፡ መርጦ ፡ ወሰደ ፡

ወቀብዐኒ፡ቅብዐ፡ቅዱስ ።

ልዩ ፡ ቅብዕ ፡ እንደም ፡ ከቡር ፡ ቅብዕ ፡ ቀባኝ ፡ መንግሥትን ፡ ሲያይ ፡ እንዲህ ፡ እለ ፡ እንጂ ፡ ቅብዑስ ፡ እንድ ፡ ነው ።

፩፤ እኀዊየሰ፡ሠናያን፡ወልሂቃን ።

ወንድሞቼስ ፡ በዋቶች ፡ ያማሩ ፡ የተወደዱ ፡ ነበሩ ፡ የዕድሜ ፡ የመ ዓርግ ።

ወኢሥምረ፡ቦሙ፡እግዚአብሔር ።

ከያሆሙ ፡ ቢል ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እርሳቸውን ፡ ለመንግሥት ፡ አልመረጠም ። እን ድም ፡ በሙ ፡ በእሳቸው ፡ እድር ፡ መመስገንን ፡ አልወደደም ።

፮፤ ወወፃእኩ ፡ ለተቀብሎቱ ፡ ለአሎፍ ፡ ነኪር ።

ከእግዚአብሔር ፡ ወገኖች ፡ ልዩ ፡ ከሚሆን ፡ ከነልያድ ፡ ጋራ ፡ ለመ ጋጠም ፡ ለመቁረቱስ ፡ ወጣሁ ፤ ሕዝብ ፡ ነኪር ፡ እለው ፡ ቁመቱ ፡ ስ ድስት ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር ፡ ያረቱ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር ፤ ወመጸ ሱቱ ፡ ኩናቱ ፡ ሥለስቱ ፡ ምእት ፡ ሰቅሎን ፡ ይላል ፤ ምስት ፡ መቶ ፡ ሚዛን ፡ ያነሣል ። ወዕፀ ፡ ኩናቱ ፡ ከመ ፡ መስቂ ፡ እኑምት ፡ ይላል ፤ የሸሩ ፡ ዛቢያ ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ መ ጠቅለያ ፡ ነው ፤ እንደዚሁ ፡ ባለው ፡ ከመ ፡ ሠርዌ ፡ ተንከተም ፡ ይላል ፡ እብነት ።

ወረገመኒ ፡ በአማልክቲሁ ፡ ርኩሳን ።

ቢል ፡ ዳጎን ፡ ይጣሉህ ፡ ቢል ፡ ዳ ጎን ፡ ይጣሉህ ፡ ብሎ ፡ ረገመኝ ።

፯፤ ወእንዘ፡ንሚለኮ፡በእምላዕሌሁ፡ሰይፎ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሰይፉን ፡ ከወገቡ ፡ መ ዝዤ ፡

መመተርኩ ፡ ርእሶ ።

ቸብቸቦውን ፡ ቈረጥሁት ።

ወአሰሰልኩ ፡ ጽዕለተ ፡ እምደቂቀ ፡ እስራኤል ።

ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተግዳሮቱን ፡ ስድቡን ፡ አራቅሁ ። እንዲህ ፡ ባለ ው ፡ ወእንዘ ፡ ንሥእኩ ፡ እምውስ ተ ፡ ፈለግ ፡ ሠለስተ ፡ እእባነ ፡ ኀምስተም ፡ ይላል ፡ ወወፀፍክዎ ፡ ውስተ ፡ ፍጽሙ ፡ እሚሃ ፡ ወድቀ ፡ በኀይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዓዲ ፡ ነሚልኩ ፡ በእምላዕሌሁ ፡ ሰይፈ ፡ ወመተርኩ ፡ ርእሶ ፡ ለጎልያድ ፡



ናው ፡ ሰማያውያ ፡ በሌሊት ፡ ወረደውያ ፡ ውስተ ፡ ያው ፡ ጎልዕ ፡ መግ ፡ ፻፶፬



ወእንዘ ፡ ንሚለኮ ፡ በእምላዕሌሁ ፡ ሰይፎ ፡ ወመተርኩ ፡ ርእሶ ፡ ለጎልያድ ፤ ገጽ ፡ ፻፶፫ ።

2014 04 18







ወእሰሰልኩ ፡ ጽዕለተ ፡ እምደቂቀ ፡
እስራኤል ፡ ይላል ፡ አብነት ፡፡ እኔ ፡
ግን ፡ ከወንዝ ፡ አምስት ፡ ድንጊያ ፡
ሦስትም ፡ ይላል ፤ አንሥቼ ፡ ግንባ
ሩን ፡ መታሁት ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ወደቀ ፡፡ ዳግ
መኛ ፡ ከወገቡ ፡ ሰይፉን ፡ መዝገር ፡
ቸብቸቦውን ፡ ቈረጥሁት ፤ ከእስራ
ኤልም ፡ ልጆች ፡ ስድቡን ፡ አራ
ቅሁ ፡፡ ይህስ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡
ቢሉ ፤ ኢሎፍላውያን ፡ በእስራኤ
ል ፡ በጸላትነት ፡ ተነሡባቸው ፤ ሳኦ
ልም ፡ ምታ ፡ ነጋሪት ፡ ክተት ፡
ሰራዊት ፡ ብሎ ፡ ዘመተ ፤ የእሴይ
ም ፡ ልጆች ፡ አብረው ፡ ዘመቱ ፤
አፋፍ ፡ ላፋፍ ፡ ሰፈሩ ፡ ዳዊትን ፡
አባቱ ፡ ለወንድሞችህ ፡ ሥንቅ ፡
ይዘህ ፡ ጠይቀህ ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ሰደ
ደው ፤ ቢሄድ ፡ ዘብ ፡ አድረው ፡ አጣ
ቸው ፤ ወንድሞቹ ፡ ወዴት ፡ ሄደ
ዋል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ፤ ዘብ ፡ አድረ
ውልሃል ፡ አሉት ፡፡ የአሕዛብ ፡ አር
በኞቸው ፡ አበጋዛቸው ፡ ጎልያድ ፡
ይባላል ፤ በእስራኤል ፡ ሲገዳደር
ባቸው ፡ ሲሰድባቸው ፡ ሲቀጸጸ
ባቸው ፡ አየ ፡፡ በኛስ ፡ በናንተስ ፡
የቀን ፡ ሐሩር ፡ የሌሊት ፡ ቍር ፡ ለም
ን ፡ ይወርድብናል ፤ ከላንተ ፡ አንድ ፡
ይውረድ ፡ ከኛም ፡ እኔ ፡ እወርዳ
ለሁ ፡ እሱ ፡ እኔን ፡ የገደለ ፡ እንደ ፡
ሆን ፡ እኛ ፡ ለናንተ ፡ እንገዛለን ፡
እኔ ፡ እሱን ፡ የገደልሁት ፡ እንደ ፡
ሆን ፡ እናንተ ፡ ለኛ ፡ ትገዛላችሁ ፡
እያለ ፡ ነው ፡፡ ዳዊትም ፡ ይህን ፡
ለገደለ ፤ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ያደርግለ
ታል ፡ አላቸው ፤ ይህንማ ፡ ለገደለ ፡
ይሁብ ፡ ወለቶ ፡ ወያሬስዮሙ ፡
ለእዝማዲሁ ፡ ግዑዛነ ፤ ይሾመዋል ፡
ይሸልመዋል ፡ ልጁን ፡ ይሰጠዋል ፡
ዘመዶቹንም ፡ ከግብር ፡ ነጻ ፡ ያወ
ጣቸዋል ፡ አሉት ፡፡ ይህንስ ፡ እኔ ፡
በገደልሁት ፡ ነበር ፡ አላቸው ፤
ኤልያብ ፡ ዳዊት ፡ ዙሩ ፡ ነህና ፡
አደርገዋለሁ ፡ ትላለህ ፡ እሊያን ፡
ሁለት ፡ ፍሬ ፡ በጎች ፡ በትነህ ፡
ምን ፡ ትናገራለህ ፡ አለው ፤ የባለ
ጸጋ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡፡ እንዲህ ፡
ማለቱ ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፤ ታላቅ ፡
ወንድም ፡ ያባት ፡ ያኸል ፡ ነውና ፡
ይሞትብኛል ፡ ብሎ ፡ ፈርቶ ፤ አን
ድም ፡ የገደለው ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ከኛ ፡
በላይ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ተመቅ
ኝቶ ፡ ነው ፡፡ አከኑ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፤
በውነት ፡ ያደርገውን ፡ መስለህ ፡
ብሎ ፡ ሄደ ፤ ከዚያም ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡
ቢመለከት ፡ እንዲሁ ፡ ሲሰድባቸው ፡
ሰማው ፤ ይህንስ ፡ እኔ ፡ እገድለዋ
ለሁ ፡ አላቸው ፤ ለንጉሡ ፡ ሄደው ፡
እረ ፡ ጎልያድን ፡ እገድለዋለሁ ፡
የሚል ፡ አንድ ፡ ብላቴና ፡ ተገኘ
ቷል ፡ አሉት ፤ አምጡት ፡ አላ
ቸው ፤ አመጡት ፤ ዳዊትን ፡ አይቶ ፡
አንተኑ ፡ ቀታሊሁ ፡ ለጎልያድ ፤
ጎልያድን ፡ እገድለዋለሁ ፡ የምትል ፡

አንተ፡ነህን፡አለው፤ ስለ፡ምን፡ቢሉ ፡
የጦር ፡ ሰው ፡ ፍድል ፡ እጥር ፡ ያለ ፡
ዐይኑም ፡ ሰሩር ፡ የለበሰ፡ (የጉረሠ)፡
እጢ ፡ ያሜረ ፡ ነው ። እሱ ፡ ግን ፡
ለጋ ፡ ተራ ፡ ብላቴና ፡ ነበርና። ኢይ
ደቅ ፡ ልቡ ፡ ለእግዚእየ ፡ ለእመ ፡
ተንሥአ ፡ ነምር ፡ ወአንበሳ ፡ እሐ
ንቆ ፡ ጕርዔሁ ፡ ወአነግፎ (ሙ) ፡
በበጎቼ ፡ ላይ ፡ ነምርና ፡ አንበሳ ፡
በጸላትነት ፡ የተነሣባቸው ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ነምር ፡ በጡሜ ፡ አንበሳ ፡
በርግሜ ፡ ገድዬ ፡ እስለቅቃለሁ ።
እሱስ ፡ ከለዚያ ፡ ቢያንስ ፡ እንጂ ፡
ይበልጣልን ፡ አለው ። ሚራ፡፵፮፡፫-፮።
ያውስ፡ ቢሆን ፡ ቈጥሮ ፡ የሰጠኝን ፡
አለ ፡ ብሎ ፡ የኔን ፡ መሣሪያ ፡ ስጡ
ት ፡ አለ ፤ ቦርቦርቲውን ፡ ደፋለት ፤
ጋሻ ፡ ጦሩን ፡ ሰጡት ፤ ተፀርሮ ፡
ሄደ ፤ ምዕረ ፡ ሖረ ፡ ወስእነ ፡ ሡጊረ፡
ይላል ፤ አንድ ፡ እርምጃ ፡ እንደ ፡
ሄደ ፡ መገሥገሥ ፡ ተሳነው ፤ ኢለ
መድኩ ፡ በዝንቱ ፡ ግብር ፡ ብሎ ፡
መሣሪያውን ፡ ጥሎ ፡ ምድር ፡ ነገ
ዱን ፡ ቈመጡን ፡ ይዞ ፡ ሄደ ፤ ከወ
ንዝ ፡ አጠገብ ፡ ሲደርስ ፡ አምስ
ትም ፡ ሦስትም ፡ ቢሉ ፡ ደንጊያ ፡
አንሥቶ ፡ ከኪሱ ፡ ያደርጋል ፤ ኀል
ያድ ፡ አይቶ ፡ ከልብኑ ፡ አነ ፡ ከመ ፡
ትምጻእ ፡ ኀቤየ ፡ በበትር ፡ ወበእ
ብን ፤ በትር ፡ ደንጊያ ፡ ይዘህ ፡ ልት
ገድለኝ ፡ የምትመጣው ፡ እኔ ፡ ውሻ፣
ነኝን ፡ ውሻን ፡ ሲርቅ ፡ በደንጊያ ፡
ሲቀርብ ፡ በበትር ፡ እንመታቀለን ፡
ብለው ፡ ይመጣሉ ፡ አለው ፤ አን
ተስ ፡ ተአኪ ፡ እምከልብ ፡ ከልብሰ ፡
የአምር ፡ እግዚኡ ፤ ጌታህን ፡ የማ
ታውቅ ፡ አንተ ፡ ከውሻ ፡ ትብሳለህ፡
ውሻስ ፡ ጌታውን ፡ ያውቃል ፡ አለ
ው ፤ እንኪያስ ፡ አንት ፡ ለካፋ ፡ ና ፡ ና ፡
በዚህ ፡ ጦር ፡ ወግቼ ፡ ቀን ፡ ለአዕ
ዋፍ ፡ ሌሊት ፡ ለአራዊት ፡ ምግብ ፡
አደርግሃለሁ ፡ አለው ፤ አሁን ፡
ያንድ ፡ የዳዊት ፡ ሥጋ ፡ ቀን ፡ ለአ
ዕዋፍ ፡ ሌሊት ፡ ለአራዊት ፡ ምግብ፡
የሚበቃ ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ፤ በዳ
ዊት ፡ መላው ፡ እስራኤልንም ፡ መና
ገር ፡ ነው ። መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡
ሚካኤል ፡ቦርቦርቲውን ፡ አንሥቶ ፡
አስመኝቶ ፡ ሰጠው ፡ በምድር ፡
ነጐድ ፡ ግንባሩን ፡ መታው ፡ ወደቀ፡
ሰይፉን ፡ ከወገቡ ፡ መዞ ፡ ቸብቸ
ቦውን ፡ ቈረጠው ፤ በዚህችም ፡
ቀን ፡ ዳዊት ፡ ገሥግሦ ፡ ሂዶ ፡ እል
ፍ ፡ ሰው ፡ አጥፍቶ ፡ ውኋል ። አን
ድም ፡ ኀልያድ ፡ ገድሎ ፡ ገድሎ ፡
እልፍ ፡ ሊመላው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡
ጐድሎት ፡ ነበር ፤ እሱን ፡ ገድሎ ፡
እልፍ ፡ ገዳይ ፡ ተብሏል ፤ ሳኦልም ፡
ገሥግሦ ፡ ሄዶ ፡ ሺሕ ፡ ገዳይ ፡ ተብ
ሏል ። አንድም ፡ ሳኦል ፡ የገደለው ፡
ሰው ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ሊመላ ፡ አንድ ፡
የጐደለው ፡ ነበር ፤ እሱን ፡ ገድሎ ፡
ሺሕ ፡ ገዳይ ፡ ተብሏል ። ድል ፡